የኢትዮጵያ ታሪክ

ኢጣሊያ በኢትዮጵያ

ከወልወል እስከ ጉንደር

ግንቦት 1927 - ህዳር 1934 ዓ.ም

ከተድላ ዘዮሐንስ ዘውዴ

© መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው።

የመጀመሪያ ዕትም 2004 ዓ.ም

አሳታሚ፦ ማንኩሳ አሳታሚ ኃላ.የተ.የግ.ማኅበር

ማውጫ

ምዕራፍ	አርዕስት	ገፅ
ምስጋና	.....	5
መቅድም	.....	6
መግቢያ	.....	7
ምዕራፍ 1፤	ኢትዮጵያ ከአድዋ እስከ ማይጨው	8
ምዕራፍ 2፤	ኢጣልያ ከውህደት እስከ ማይጨው ዋዜማ	14
ምዕራፍ 3፤	የጎንደር ውዝግብና የወልወል ግጭት የአውሮፓ መንግስታት አመለካከት	20
ምዕራፍ 4፤	ጦርነቱን ለማስቀረት የተደረገ የዲፕሎማቲክ ጥረት	25
ምዕራፍ 5፤	የጦር ዝግጅት	27
ምዕራፍ 6፤	የአድዋና የአክሱም መያዝ	30
ምዕራፍ 7፤	የኢትዮጵያ ሠራዊት የክተት አንቅስቃሴ	32
ምዕራፍ 8፤	የሽሬ ጦር ግንባር	36
ምዕራፍ 9፤	የተንቤን ጦር ግንባር	39
ምዕራፍ10፤	የአምባራዶም ጦር ግንባር	44
ምዕራፍ11፤	የአጋዴን ጦር ግንባር	46
ምዕራፍ 12፤	የቦረና ጦር ግንባር	51
ምዕራፍ 13፤	የማይጨው ጦርነትና የኢትዮጵያ ድል መሆን	57
ምዕራፍ 14፤	ከማይጨው መልስ	61
ምዕራፍ 15፤	የንጉሠ ነገሥቱ ስደትና የኢትዮጵያ ሠራዊት መፍረስ	65
ምዕራፍ 16፤	የኢጣልያን አዲስ አበባ መግባት	68
ምዕራፍ 17፤	ኢትዮጵያ ለምን፣እንደምን ተሸነፈች?	71
ምዕራፍ 18፤	የገጠሩ ሕዝብ ሁኔታና የአርበኝነትአደማመር	75
ምዕራፍ 19፤	የሲዳሞ ተጋድሎ	79
ምዕራፍ 20፤	በሐረርጌ፣ በባሌና በአርሲ የተካሄደ ትግል	87
ምዕራፍ 21፤	በጉራጌ አገር የተካሄደ አርበኝነት	89
ምዕራፍ 22፤	በጋሞ ጎፋ የተካሄደ ትግል	96
ምዕራፍ 23፤	በኢሊባቦርና በከፋ የተካሄደ ትግል	98
ምዕራፍ 24፤	በወለጋ የተካሄደ የአርበኝነት ሥራ	107
ምዕራፍ 25፤	ግንደ በረትና ቦሜጫ የተደረገ ትግል	112
ምዕራፍ 26፤	በመርሃቤቴና በሰላሌ የተካሄደ ትግል	122
ምዕራፍ 27፤	የመገናኛ መሥመርን መቆጣጠር	139
ምዕራፍ 28፤	በቡልጋና ሸንኮራ የተካሄደ ትግል	142
ምዕራፍ 29፤	የአንኮበርና ይፋት ትግል	194
ምዕራፍ 30፤	የመንዝና ተጉለት ተጋድሎ	205
ምዕራፍ 31፤	የጎጃም ጭዝጥዝ	228
ምዕራፍ 32፤	የወሎ ትግል	246
ምዕራፍ 33፤	የትግራይ ተጋድሎ	254
ምዕራፍ 34፤	የጎንደር ተጋድሎ	257
ምዕራፍ 35፤	የአዲስ አበባ የትግል አስተዋጽኦ	294
ምዕራፍ 36፤	የሴቶችና የልጆች ሚና	309
ምዕራፍ 37፤	የውስጥ አርበኞች ተጋድሎ	313

ምዕራፍ 38፤	የስደተኛው ትግል	318
ምዕራፍ 39፤	የአርበኝነት ሥልት	337
ምዕራፍ 40፤	የአርበኞቹ የአርስበርስ ግንኙነት	347
ምዕራፍ 41፤	በአርበኞች ዘንድ የነበረ የፍርድ ሥራ	353
ምዕራፍ 42፤	የጣልያን የግፍ ሥራዎች	360
ምዕራፍ 43፤	የእሥረኞችና የእሥር ቤቶች ሁኔታ	368
ምዕራፍ 44፤	የድርጅት ጥያቄ በአርበኞች ዘንድ	373
ምዕራፍ 45፤	ጤናና ምግብ	380
ምዕራፍ 46፤	ከሐዲዎችና የክህደት ሥራቸው	384
ምዕራፍ 47፤	ግጥምና ቅኔ	394
ምዕራፍ 48፤	የጣልያኖች ፖሊሲ	399
ምዕራፍ 49፤	የኢጣልያን የምሥራቅ አፍሪቃ አስተዳደር	409
ምዕራፍ 50፤	የቅኝ ግዛት ወታደሮች ሚና	419
ምዕራፍ 51፤	የአውሮፓ ሁኔታና የኢትዮጵያ ዲፕሎማቲክ ሥልት	423
ምዕራፍ 52፤	የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የድል ጉዞ	432
ምዕራፍ 53፤	ኢትዮጵያን ነፃ ለማውጣት የተንቀሳቀሰው የእንግሊዝ ጦር	446
ምዕራፍ 54፤	የኢትዮጵያና የጣልያን ጦርነት ፍፃሜ	453
ምዕራፍ 55፤	በጦርነቱ ውስጥ የአምነት ድርጅቶች ሚና	467
ምዕራፍ 56፤	ጦርነቱ በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ላይ ያደረሰው ጉዳት	481
ምዕራፍ 57፤	የጦርነቱ ጠቅላላ ግምጋሜ	491
ምዕራፍ 58፤	የአድዋና የማይጨው ጦርነቶች ንጽጽር	498
ምዕራፍ 59፤	የኢጣልያ ህልምና ውጤቱ	502
ምዕራፍ 60፤	የኢትዮጵያ የጦር ፍርድ ቤት	506
ምዕራፍ 61፤	ከድል በኋላ ትግል	509
ምዕራፍ 62፤	የሰላም ንግግር ከኢጣልያ ጋር	523
ምዕራፍ 63፤	ኢትዮጵያና ነፃነትዋ	527
አባሪ 1፤	የንጉሠ ነገሥት መልአከ ፀሐይ አነጋገስ	535
አባሪ 2፤	የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች ማህበር አመሰራረት	536
አባሪ 3፤	የሙሶሊኒ አጭር የህይወት ታሪክ	538
አባሪ 4፤	የፋሺስት ፓርቲ አነሳስና አወዳደቅ	557
አባሪ ስሌዳ፤	የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦርነት ያስከተለው የኢኮኖሚ ጉዳት	565
	የፀሐፊው አጭር የሕይወት ታሪክና ፎቷቸው	567
	ዋቢ የአማርኛ መጻሕፍት	569
	ዋቢ የእንግሊዝኛ መጻሕፍት	572
	ኢጣልያ በኢትዮጵያ ለሚለው መፀሐፍ የምስክርነት ቃል የሰጡ ሰዎች	573

ምስጋና

ከዚህ የደረስኩት በብዙዎች ዕርዳታና ድጋፍ ሲሆን ጥቂቶቹን ስም በመጥራት፣ ብዙዎችን በጠቅላላው ማመስገን እፈልጋለሁ።

1. በመጀመሪያ ካለመኖር ወደ መኖር አምጥቶ የፈጠረኝን ልዑል እግዚአብሔር፣ በችግሬ ሁሉ የረዳችኝን ቅድስት ድንግል ማርያምን፣ ቸር ጠባቂዬን ቅዱስ ሚካኤልን አመሰግናለሁ።
2. የወለዱኝን፣ ያሳደጉኝን፣ ችግራቸውን ታግሰው የመማር ዕድል የሰጡኝንና ሳይንቁ ቃሌን የሰሙኝን አባቴን አለቃ ዘኦሐንስ ዘውዴ ሀብቴንና እናቴን ወይዘሮ ጸዳለ አባብሰው ተክሌን አመሰግናለሁ።
3. ለአሳደጉኝ አያቴ ለይቶት በሀብትዋ ወልደሥላሴ ወንድሜነህ፣ በችግሬ ለረዱኝ አጐቴ ለፊታውራሪ ወልደ ፃድቅ ዘውዴ፣ ፍሬ ላይተካ በጦርነት ለወደቀው አጐቴ ለአቶ ኃይለሥላሴ ዓለመ ባለውለተኛነቴን እገልፃለሁ።
4. በጦርነቱ ጊዜ በቤተሰብነት የደገፉኝን ወይዘሪት/ወይዘሮ/ እምሪቱ አባብለውን፣ ወይዘሪት/ወይዘሮ/ ሥዕለ ዘኦሐንስን፣ አያ ማሩ አቶ ካሣ ዘኦሐንስን አስባቸዋለሁ።
5. አስተምረው የእውቀት ብርሃን የከፈቱልኝን አለቃ ዘኦሐንስን፣ መምህር ገድሌን፣ መምህር ጌታሁን/ብፁዕ አቡነ ጢሞቴዎስን/፣ ኃይለማርያም ማሞ ትምህርት ቤት ያስገባችንና በኑሮዬ የረደኝን አቶ መኮንን ወልደሚካኤልን፣ በኑሮዬ የረዱኝን አቶ ግዛው ደስታን፣ በአዳሪነት እንድማር የፈቀዱልኝን ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን፣ ደብረ ብረሃን የኃይለማርያም ማሞ ትምህርት ቤትና የአዲስ አበባ መምሕራን ማሠልጠኛ ተቅዋም መምሕራንን፣ እንደዚሁም የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርስቲ የማታውን ክፍል መምህራን አመሰግናቸዋለሁ።
6. ይህንን መጽሐፍ በምጽፍበት ጊዜ ማስረጃ የሰጡኝን፣ በጽሕፈት ሥራ የረዳችኝን ወይዘሪት የወርቅውሃ ጽጌ፣ በሕትመቱ ሥራ የተባበሩኝ የት.መ.ማ.ድርጅት ሹማምንትና ሠራተኞች ባለውለታዎቼ ናቸው።

መቅድም

የዚህ መፅሐፍ ዓላማ በኢትዮጵያና በኢጣልያ መካከል የተካሄደውን ጦርነት በአጠቃላይ ማመልከት ነው። ከወልወል ግጭት እስከ ጎንደር ነጻ መውጣት ለስድስት ዓመት ከስድስት ወር የተካሄደውን ረዥምና መራራ ትግል ይዘክራል። መፅሐፉን የሚያነቡ ሁሉ ከዚህ ቀጥሎ የተመለከቱትን ነጥቦች እንዲያጤኑ ያስፈልጋል።

1. በታሪኩ ሂደት በሀገር ውስጥና በውጭ አገር የተከናወነው ሥራ እንደየጊዜው ቅደም ተከተል ተገልያለል።
2. እውነተኛውን ነገር ፈልፍሎ ለማውጣት ልዩ ጥረት ተደርጎአል።
3. የታሪኩ አጻጻፍ፣
   ሀ. ፍልሚያ በተካሄደባቸው ክፍላተ ሀገር እየተሰየ፣
   ለ. የጊዜው ቅደም ተከተል እየተጠበቀ፣
   ሐ.የመሪዎችና የሠራዊት አገልግሎት እየተመዛዘነ ነው።
4. የታሪኩ ትንታኔ የተመዛዘነና አጠቃላይ ግንዛቤ የሚያስጨብጥ እንዲሆን ጥንቃቄ ተደርጎአል።
5. ዘመንና ቀናት በኢትዮጵያ አቆጣጠር ተመልክተዋል። አስፈላጊ በሆነበት የአውሮፓ ዘመን አቆጣጠር በቅንፍ ተገልጧል።
6. የማዕረግ ሥም የተጠቀሰው ሥራ በተሠራ ጊዜ የነበረው ነው። በኋላ የተገኘው በቅንፍ ውስጥ ተመልክቶአል።
7. የገንዘብ ጉዳይ የታሰበው በኢትዮጵያ ሲሆን አንድ የአሜሪካ ዶላር በሁለት ብር ተኩል፣ አንድ የእንግሊዝ ፓውንድ በአሥር ብር እየተሰላ ነው።
8. የሰውና የስነድ ምንጮች በተገቢው ሥፍራ በቁጥር ከተመለከቱ በኋላ፣ ዝርዝራቸው ለማመሳከሪያነት በየምዕራፉ መጨረሻ ቀርቦአል። አጠቃላይ የሚጣቀሻ መፅሐፍት ዝርዝርና የቃል ምስክርነት የሰጡ ግለሰቦች መግለጫ በመፅሐፉ መጨረሻ ላይ ሰፍሮአል።

መግቢያ

ኢትዮጵያ ለም አፈር፣ ለስላሳ አየር ያለባት፣ ታታሪና አስተዋይ ህዝብ የሠፈረባት ሀገር ናት። ይህም ሆኖ ሕዝቧ በችግር ተቆራምዶ ይኖራል። ይህም ደግሞ ያለምክንያት አይደለም። ሀገሪቱ ዘላቂ ሰላም ባለማግኘቷ፣ ሕዝቧም ስለሁኔታዎች ትክክለኛ ግንዛቤ ካለማግኘቱ የተነሳ ነው። ትክክለኛ ግንዛቤ ማግኘት የሚቻለው ደግሞ ከእውነተኛ ታሪክ ነው።

ኢትዮጵያ ከ3016 ዓመተ ዓለም ጀምሮ፣ ማለትም ክርስቶስ ሊወለድ 2484 ዓመታት ሲቀረው፣ መንግሥት የተመሠረተባት ሀገር ናት። ከሰብታህ እስከ ንግሥት ሳባ፣ ከቀዳማዊ ምኒልክ እስከዛሬ 5000 ዓመት ያህል በመንግሥትነት ጸንታ በነፃነት ኖራለች። በዚህ ረጅም ዘመን ብዙ ውጣ ውረድ አሳዮሞአታል። ታላቅ የታሪክ ሀብትም አድልባለች። ነገር ግን በዚህ የታሪክ ሀብቷ በሚገባ አልተጠቀመችበትም። ለዚህም ብዙ ምክንያቶች አሉ። ብዙው ታሪኳ አልተፃፈም። ከተፃፈው ከጥቂቱም ብዙው ተዛብቶአል፣ ተበላሽቶአል፣ ጠፍቶአል። ይህ ሲሆን የቻለው ደግሞ የተነሳው መሪ ሁሉ ከእሱ በፊት የነበረውን እያስረከሰ፣ የራሱን እያስነገሰ ስለሚያፅፍ የሀገሪቱ ታሪክ የዝቅዝቂት በመሄዱ ነው።

አዲሱ ትውልድ ይህንን መጥፎ ልማድ መዋጋት አለበት። አንድ ታሪክ ጸሐፊ እውነተኛውን ታሪክ ለመፃፍ ካልቻለ ቢተወው ይሻላል። ሐሰት ሰውን እንደሚያጠፋ፣ እውነተኛ ያልሆነ ታሪክ ሀገርን ያጠፋልና!

እኔም በኢትዮጵያና በኢጣልያ መካከል ከህዳር 27 ቀን 1927 ዓ.ም እስከ ህዳር 19 ቀን 1934 ዓ.ም የተካሄደውን ጦርነት ለመፃፍ የተነሳሳሁበት በዚህ መንፈስ ተመርቼ እውነተኛውን ነገር ለኢትዮጵያውያን ወገኖቼ ሰመግለጽ ነው። ታሪክን መመርመር ይጠቅማል። ሲመረመርም አረረ መረረ ሳይሉ እውነተኛውን ነገር ማበጠር ያስፈልጋል። የሀገሩን ታሪክ ያላወቀ ዜጋ ዘጭስማ እንደሚጓዝ ሰው ነው። እርስዎም በታሪክ ብርሃን ለመጓዝ ይሞክሩ።

ይቅናዎ
ተድላ ዘዮሐንስ ዘውዴ
ታህሣሥ 1986 ዓ.ም
አዲስ አበባ።

ምዕራፍ አንድ
ኢትዮጵያ ከአድዋ እስከ ማይጨው

ተደጋግሞ በታሪክ እንደተገለፀው ኢትዮጵያ ዓለምን ረስታ፣ ዓለምም እርስዋን ረስቶአት ወደ ሦስት መቶ ዓመት ኖረች። ከዚህ ረጅም የእንቅልፍ ዘመን በአፄ ቴዎድሮስ (ግ.1847-1860ዓ.ም) ተቀሰቀሰች። ስትነቃም ራስዋን ከአውሮፖ ሀገሮች በጣም ወደ ኋላ ቀርታ አገኘቸው። ይህ ኋላ ቀርነት ለሕልውናዋ አስጊ መሆኑን ተገነዘበች።

በዘመነ መሣፍንት ተከፋፍሎ የነበረውን የግዛት አንድነትዋን እንደገና መልሶ ለመያዝ ሞከረች። የአውሮፖ ሥልጣኔ በፍጥነት ወደ ሀገርዋ ለማስገባት ተጣጣረች። ጉዞዋ የሰመመን ሆነባት። ከዚህም የተነሣ ብዙ መደነቃቀፍ ደረሰባት። አፄ ቴዎድሮስ የኢትዮጵያን አንድነት ለመመሥረት ሞከሩ። ቱርኮችን ከአካባቢያቸው ለማስወጣት፣ ኢየሩሳሌምን ለማስለቀቅ ተመኙ። መድፍና ጀልባ ማሰራት ጀመሩ።[1] በስተኋላም አመለካከታቸው ወደኃይል አዘነበለ። ይህ ደግሞ አውሮፖን አስገነባ። የሃይማኖት ሰባኪያን እያስመሰሉ በላኩአቸው ሰዎች ምክንያት ከእንግሊዞች ጋር ግጭት ተፈጠረ። ለጥፋታቸውም መንስኤ ሆነ።

ንጉሥ ተክለጊዮርጊስ (ግ.1861-1863 ዓ.ም) ከደጃዝማች በዝብዝ ካሣ ከተነሳባቸው ግጭት ፋታ ሳያገኙ ወደቁ። ደጃዝማች በዝብዝ ካሣ ደግሞ አራተኛ ዮሐንስ (ግ.1863-1880ዓ.ም) ተብለው ዘውድ ከተቀዳጁ በኋላ የሀገሪቱን አንድነት ለመገንባት ሞከሩ። ነገር ግን አመለካከታቸው ከሃይማኖት ልዩነት ላይ ስለአተኮረ የእስላሙን ኃይል ቀሰቀሰባቸው። እንግሊዞችም ለጥቃት አጋለጡአቸው። ምፅዋን ለኢጣልያ እጅ አሳውረው ሰጡባቸው። ክርስቲያኖች በመሆናቸው ይረዱኛል ብለው ሲታመኑ፣ የእስላሙን ኃይል አስነሱባቸው። መተማ ወድቀው ቀሩ።[2]

የአውሮፓ ኃያላን መንግሥታት እ.ኤ.አ. በ1885 ዓ.ም በበርሊን ከተማ ተሰበሰቡ። የተሰበሰቡት ምክንያት አፍሪካን እንደምን እንደሚከፋፈሉ ለመቀየስ ነበር። ንግግሩ ያተኮረው "እንደምን" በሚለው ጥያቄ ላይ ብቻ ነበር። "ለምን" የሚለው ጥያቄ ጉዳያቸው አልነበረም። አህጉሪቱን በመላ በቅኝ ገዥነት መያዝ መፈፀም ያለበት እንጂ የሚያከራክር ጉዳይ አልነበረምና።

በዚህ ውሣኔ መሠረት አውሮፓውያን አፍሪካን ተቀራመጡአት። ድርሻቸውም በ1906 ዓ.ም

- የፊረንሣይ ከመቶ 34 እጅ፣
- የእንግሊዝ ከመቶ 32 እጅ፣

- ጀርመን ከመቶ 7 እጅ፣
- ቤልጂግ ከመቶ 7 እጅ፣
- ፖርቹጋል ከመቶ 6 እጅ፣
- ኢጣልያ ከመቶ 5 እጅ፣
- ስፔይን ከመቶ 7 እጅ፣
- ነፃ መንግስታት ከመቶ 2 እጅ ሆነ።

ይህ ሚዛን የኢጣልያን ክብር የሚቀንስ ሆነ። የሊቢያ፣ የሶማልያና ከኤርትራም ምድር አብዛኛው በረሃማ ሆነባት። ስለዚህ ዓይንዋን በኢትዮጵያ ላይ ጣለች።

ዳግማዊ አፄ ምኒልክ ይህንን ሁኔታ ቀደም ብለው ደርሰውበት ነበር። መፍትሔ አድርገው የተከተሉት ዘዴ በግራኝ ወረራ ተከፋፍሎ ተይዞ የነበረውን ደቡባዊውን የአገሪቱን አካባቢዎች መልሰው መያዝ ሆነ። እንደዚሁም አደረጉ። አዲስ አበባንም ቀረቀሩ። ሰሜኑን ደግሞ በመለማመጥና እርስ በርሱ በማስማማት ያዙት። የአሁንዋን ኢትዮጵያ መሠረቱ። ጣልያንን አድዋ(በ1888 ዓ.ም) ላይ ድል በመምታት የሀገራቸውን ነፃነት አረጋገጡ። ነገር ግን ቀደም ብለው በቅኝ ገዥዎች እጅ የወደቁትን የባህር በሮች፣ ማለትም ኤርትራንና ደቡብ ሶማልያን ከኢጣሊያ፣ ሰሜን ሶማልያን ከእንግሊዝ፣ ጅቡቲን ከፈረንሣይ ማስለቀቅ የማይቻላቸው ሆነ። የሕዝቦቹም ስሜት ተከፋፈለባቸው። የቅኝ ገዥዎቹ ኃይል አየለባቸው። የተረፈውን፣ የቀረውን ሕዝቤን ባድን ይሻለኛል አሉ። መተናነቃቸውን ትተው ከአውሮፓ መንግሥታት ጋር ተስማሙ።

በዓለም ፊት ኢትዮጵያ አሸናፊ፣ ኢጣልያ ተሸናፊ ሆነው እንደማይቀሩ ለብልሁ ለአፄ ምኒልክ ግልፅ ነበር። ሌላ ፍልሚያ መካሄድ እንደ አለበት ታውቆአቸዋል። ልዩ ልዩ መሣሪያ አስመጥተው ኮረማሽ አስቀመጡ፣ የጥይት ፋብሪካ አቋቋሙ።[3] በእንግሊዝና በፈረንሣይ ሴራ ቀረባቸው እንጂ፣ ጠመንጃ መስሪያ ፋብሪካ ለማቋቋምም ሞክረው ነበር።[4]

ከአሳቸው በኋላ ጦርነቱ እስኪነሣ ድረስ በነበረው ጊዜ ግን ሀገርን በመከላከል ረገድ አንዳች የረባ ነገር አልተደረገም። ለጥቅምና ለሥልጣን በተደረገ ሽኩቻ ያ ሁሉ ዘመን በከንቱ አለፈ። በዚህ ጉዳይ ያን ጊዜ ባልሥልጣኖች የነበሩ ሁሉ በታሪክ ፊት ተወቃሽ ናቸው። ተወቃሽነታቸውም እንደ ደረጃቸውና እንደቅደም ተከተላቸው ይሆናል። ዋናው አቤቶ ኢያሱ ናቸው። ከአያታቸው ከአፄ ምኒልክ የተሰጣቸውን አልጋ በሥርዓት አለመያዛቸው በአሳቸው በራሳቸው ላይ ጥፋትን፣ በሀገሪቱ ላይ ውድቀትን፣ በሕዝቡ ላይ መንገላታትንና አልቂትን አስከተለ። ዋና ዋና ስህተቶቻቸው፦

1. አፄ ምኒልክን ራሳቸው በሕይወት እያሉ ከአልጋ ለማውረድ መሞከር፣ የሞቱ ዕለት ጉግስ ማጫወት፤[5]
2. የሀገሪቱን ሥርዓት፣ የቤተክርስቲያኒቱን ደንብ አለማክበራቸውና በቅብዐ ቅዱስ ዘውድ አለመቀዳጀት፤
3. በክርስትና ፅንአት በማሳየት ፈንታ ወደ እስልምና ወገን ማዘንበል፤
4. የአፄ ምኒልክን አሽከሮች በሥርዓትና በአክብሮት አለመያዝ፤
5. ሴሰኝነትና ዘራቸውን በየትም መርጨት፤
6. የመንግሥቱን ሥራ በጥሞና በማካሄድ ፈንታ ዙረት ማብዛት፤
7. በአውሮፓ ተቀስቅሶ ከነበረ ጦርነት ጋር በተያያዘ፣ ከማያስፈልግ ንትርክ ውስጥ በመግባት ከቱርክ እና ከጀርመን ጐን መቆም ናቸው።[6]

ቀጥሎ ተጠያቂ የሚሆኑት እቴጌ ጣይቱ ብጡል ይሆናሉ። እቴጌ ጣይቱ ለኢትዮጵያ ታላላቅ ውለታዎች ሰርተዋል። ነገር ግን ሥልጣን በመፈለግ በቤተመንግሥቱ ነገር በመዝራት በዳግማዊ አፄ ምኒልክ ሕመም ላይ ሀዘን መጨመራቸው፣ የአቤቶ ኢያሱን ባህርይ በመጥፎ ነገር በመበከል ማበላሸታቸው የውለታቸውን ያህል በድለዋል።

የዳግማዊ ምኒልክ አሽከሮችም ኃላፊነታቸውን በሚገባ አልተወጡም። ራስ ተሰማ ሥራቸውን በተገቢ መንገድ ባለመፈፀማቸው ከጥፋት ደረሱ። ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ በእነስተኛ ጉዳይ በአቤቶ ኢያሱ በመቀየም መሐላቸውን አፍርሰው የጌታቸውን የምኒልክን ሥርወ መንግሥት ከሚለውጡ ጋር ደባ ውስጥ መግባታቸው የሚነገርላቸውን ያህል አስተዋጽኦ ያደረጉ እንዳልነበሩ ያስረዳል።

በታሪክ ፊት ደጃዝማች ተፈሪ መኮንንም /ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ/ ከተጠያቂነት አይድኑም። የንጉሥ ሚሀለሥላሴ ተወላጅ ይሁኑ፣ ያፍሩአቸው እንጂ አልጋውን በአግባቡ አልወረሱም። በእርግማንና በግዘት አልጋ የተሰጠው ከሚሀለ ሥላሴ ለንጉሥ ኃይለ መለኮት፣ ከአፄ ምኒልክ ደግሞ ለአቤቶ ኢያሱ ነው። እሳቸው ራሳቸውም ቢሆኑ ከልጅ ኢያሱ ጋር የገቡትን ቃል ኪዳን አልጠበቁም። ለዚህም የሰጡት ምክንያት ልጅ ኢያሱ ቃል ኪዳናቸውን አፈረሱ የሚል ነው።[7] ማንኛቸው ቃል ኪዳን እንደ አፈረሱ ለማወቅ አስቸጋሪ ነው። ሐቁ ግን ደጃዝማች ተፈሪ በልጅ ኢያሱ የተቀሰቀሰውን ነገር ለሥልጣን ሲሉ ማባባሳቸው ነው።

በዚህ ጉዳይ የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንም ከተወቃሽነት አትድንም። በወቅቱ ዘውዱን የምትጠብቅ ብሔራዊ ቤተክርስቲያን ናት። የንጉሥ ሚሀለሥላሴንም፣ የዳግማዊ ምኒልክንም ቃል በግዘት ያፀናች እርስዋ ናት። የዘውድ አወራረስ ተፋለስ የሚያስከትል ነገር ሲፈፀም ዝም ማለት አልነበረባትም። ነገር ግን ደጃዝማች ተፈሪ መኮንን

ራስ ተብለው አልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ መሆናቸውን ደገፈች።[8] ምንም እንኳ የልጅ ኢያሱ ከሥልጣን መውረድ የማይቀርና ተገቢ ቢሆን፣ የአልጋ ወራሹ ምርጫ ቢቆይ ይሻል ነበር። ምክንያቱም የአልጋ ወራሽነት ሹመት ከንጉሡ ላልተወለደ የማይሠጥ ሲሆን፣ ከዚህም በስተቀር የባለሙሉ ሥልጣን ማዕረግ ተሰጥቶ አያውቅም ነበርና።

አፄ ምኒልክም ራሳቸው ተሳስተዋል። ስህተታቸውም በልጃቸው ልዕልት ዘውዲቱ ላይ የያታ ልዩነት ማድረግ ነው። ያንን ያህል ደክመው አንድ ያደረጉአትን ሀገር፣ ለኃላፊነቱ አስተማማኝ ላልነበረ ወጣት ለአቤቶ ኢያሱ መጣል አልነበረባቸውም። በውጭ አገር እነ ንግሥት ቪክቶሪያንና ኤልዛቤጥን፣ በኢትዮጵያ እነ ንግሥት ሳባን፣ ማክዳን፣ ሰብለ ወንጌልን፣ አጠገባቸውም እቴጌ ጣይቱን አጢነው ዘውድን ለልጃቸው ለዘውዲቱ በሰጡአቸው በቀለለ ነበር።

ይህ ሁሉ አልሆነም። አልጋው ተነቃነቀ። የተሻለው አማራጭ ልዕልት ዘውዲቱን ማንገሥ፣ ደጃዝማች ተፈሪን ደግሞ ራስ ብሎ አልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ማድረግ ሆነ። ነገር ግን ይህ ትንጅት ሥምረት አጣ። ውዝግብ ፈጠረ።[9] የኢትዮጵያን ሕዝብ አንድነት ተነሰ። ሀገሪቱን ለውጭ ጥቃት አጋለጣት። አፄ ምኒልክ "ነፋስ አይግባባችሁ" ያሉት ምክር አድማጭ አጥቶ የፈሩት ደረሰ።

የኢትዮጵያን ቅጥ ማጣት በትኩረት ይመልከቱ የነበሩት ጠላቶችና ዋና ተቃዋሚዎች ተንቀሳቀሱ። እንግሊዝና ኢጣልያ ሲያውጠነጥኑ የቆዩትን ሤራ አጠናከሩባት። ሮማ ላይ ተነጋገሪው እንግሊዝ በጣና ባሕር ላይ ግድብ ስትገድብ፣ ኢጣልያ ከአሥመራ እስከ ሞቃድሾ በኢትዮጵያ ግዛት ላይ አቋርጣ የባቡር ሀዲድ ልትዘረጋ ተስማሙ። ውሉንም ከዓለም መንግሥታት ማህበር መዝገብ ቤት አገቡ።[10] ከኢትዮጵያ መንግሥት የቀረበውን ተቃውሞ ከቁም ነገር የቆጠረው የለም።

የኢትዮጵያ ሁኔታ በእንዲህ እንደአለ የመጀመሪያው የዓለም ጦርነት ተነሳ። ምንም ውጊያውን ያካሄዱት እንግሊዝ፣ ፈረንሣይና መስኮብ አንድነት ሆነው በጀርመን ላይ ቢሆን፣ በወቅቱ ቱርክ ከጀርመን ጐን፣ የልጅ ኢያሱ ኢትዮጵያ ደግሞ ከቱርክ ጐን ቆመው ነበር። ኢጣልያ መጀመሪያ ከጀርመን ጐን እንደሆነች መስላ ከቆየች በኋላ፣ ሚዛን ሲያደላ አቋሟን ለውጣ ከእንግሊዝና ፈረንሣይ ጐን ቆመች። ጦርነቱ በእንግሊዝና በፈረንሣይ አሸናፊነት ሲደመደም፣ ቀደም ብሎ ተጀምሮ ፊር ሳይዝ የቆየው የዓለም መንግሥታት ጉባኤ በሰኔ ወር 1911 ዓ.ም (ጁን 1919) ተቋቋመ። በዚህ ወቅት በተቀናቃኞቻቸው ላይ የበላይነት የያዙት አልጋ ወራሽ ተፈሪ፣ ኢትዮጵያ የኃያላንን ጥቃት ፅመመከት የምትችለው ከጋራ

ጸጥታ ከለላ ስታገኝ ነው ብለው አመኑ። ኢትዮጵያም የእንግሊዝን ተቃውሞ በሊጣልያ ድጋፍ አክሽፋ በሚያዝያ ወር 1915 ዓ.ም የማሕበሩ ሃያ ስምንተኛ አባል ሆነች።[11]

ከአሥር ዓመታት በኋላ ሊጣልያ የማህበሩን ውል ጥሳ በኢትዮጵያ ላይ የወረራ እንቅስቃሴ አነሣች። በኢትዮጵያ ወገን ስሞታ ከማቅረብ በስተቀር ራስን ለመከላከል እንዳች አልተደረገም። ይሽኛውም የሀገር ተከላካይነቱ ሥራ የነፍጠኛው ሆነ። የያዘው መሣሪያ በአድዋ ጊዜ የማረከው ነው። ከአሱም አብዛኛው ስናድር፣ ናስማር፣ ውጅግራ ነው። በአንድ ጊዜ ከአንድ ጥይት በላይ አይተኩስም፣ ይግላል፣ ቀለሁም ክውስጡ ይጦረዳል፣ ጭሱም ክባድ ነው። ለረጅም ጊዜ በተካሄደው የሥልጣን ሽሚያ ደግሞ ነፍጠኛው ተንገላትቶአል። በልጅ ኢያሱና በንግሥት ዘዉዲቱ ላይ በደረሰው ነገር ቀስሎአል። በአዲሶቹ መሪዎች አልተደሰተም። የማደሪያ መሬቱ እየተነቀለ ለአዳዲሶች ሹማምንት ባለሙዋሎች ተሰጥቶበታል።

በአንፃሩ ደግሞ የአዳዲሶች ባለሥልጣኖች ጦር የውጊያ ብቃት አልነበረውም። የልብ አንድነትም አሳገኘም። በውልድ እና በዝምድና፣ በአምቻ በጋብቻ የተመለመለ እንጂ በመከራ የተፈተነና የጦር ልምድ ያካበተ አልነበረም። አዲሱን የሠልፍ ትምህርት ተምሮ፣ በአንድ አይነት አረማመድና በአንድ ዓይነት ልብስ አምሮ በተመልካች ዘንድ ደስ እንዲያሰኝ የሰለጠነ ነበር። ቁጥሩም እጅግ ጥቂት ነበር።[12] በዚህ ላይ ደግሞ የርስበርስ መናናቅና አንዱ ለአንዱ አልታዘዝም የማለት ሁኔታ ነበር። የኢትዮጵያዊ ዓይነት ቅርፅ አልነበረውም። የእነዚህ ሁኔታዎች ድምር የሀገሪቱን አቅም አሳነሰ። የሕዝቡን አንድነት ቀንሶ አገሪቱን ከጠላት ለተሠነዘረባት አደጋ አጋለጣት።

ማጣቀሻ ፅሑፎች

1. ተክለ ፃድቅ መኩሪያ፣ *አፄ ቴዎድሮስ እና የኢትዮጵያ አንድነት* ፣ገፅ 297።
2. ዝኒ ከማሁ።
3. ጳውሎስ ኞኞ፣ *አጤ ምኒልክ*፣ ገጽ 355።
4. ካፒቴን ሐሪስ
5. ተክለፃድቅ መኩሪያ፣ *አፄ ምኒልክና የኢትዮጵያ አንድነት*፣ገጽ 55።
6. ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፣ *ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ፣ 1ኛ መጽሐፍ*፣ ገጽ 31።
7. ዝኒ ከማሁ፣ገጽ 27-29።
8. ተክለፃድቅ መኩሪያ፣ *የኢትዮጵያ ታሪክ*፣ ገጽ 141።
9. ከበደ ተሰማ፣ የታሪክ ማስታወሻ፣ገጽ 44-73።
10. ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፣ ገጽ 101-105።
11. ክፍለ ጽዮን ማሞ፣ ማለ መጽሔት አንደኛ አመት ቁጥር 2 ጥር 1985 ዓ.ም
12. ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፣ ገጽ 57-58።

ምዕራፍ ሁለት
ኢጣልያ ከውህደት እስከ ማይጨው ዋዜማ

የጣልያንን ሁኔታ ደግሞ በአጭር ማየት አጠቃላይ ግንዛቤ ይሰጣል። እስከ አስራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን ሁለተኛ አጋማሽ ድረስ፤ ኢጣልያ በልዩ ልዩ መሣፍንት የተከፋፈለች ሀገር ነበረች። ክፍፍሉ እስከ ሠላሣ ስምንት ይደርስ እንደነበረ ይነገራል። በዚህ ላይ ደግሞ በዚያን ጊዜ ገናና የነበረው የነምሣ(አስትሪያ) እንዲሁም የፈረንሳይ መንግስት ተፅዕኖ ነበረባት።

የሰርዲኒያው መሥፍን ካርሎ አልቤርቶ ይህንን ክፍፍሉሽ ለማስቀረትና ሀገሪቱን ወደ አንድነት ለመጠትለል ሞከረ። እምብዛም ሳይቀናው ሞተ። ልጁ ዳግማዊ ንጉሥ ኢማኑኤል (ግ.1841-1870 ዓ.ም) ፈሩን ተስትሎ ከዳር አደረሰ። በጀርመንና በነምሣ፣ ቀጥሎም በጀርመንና በፈረንሣይ መንግሥታት መካከል የተካሄደውን ጦርነት በመጠቀም፣ በጳጳሱ ላይ ተፅዕኖ አድርጐ በ1862 ዓ.ም ሮማን መናገሻ ከተማው አደረገ።[1] ኢጣልያም የተዋሃደች ሀገር ሆነች።

ኢጣልያ የውስጥ ጉዳይዋን በዚህ አይነት ከቋጨች በኋላ አውሮፖን ስትመለከት በቅኝ አገዛዝ ረገድ ባዶ እጅዋን ቀርታ አገኘችው። ነገሩ አስደንጋጭ ሆነባት። እንግሊዝ ሰሜን አሜሪካን፣ ከአፍሪካ ደግሞ ከመቶ 32 እጅ፣ መካከለኛውን ምሥራቅ፣ ደቡብ እስያንና ደቡብ ምሥራቅ እስያን፣ አውስትራልያንና ኒውዚላንድን ትገዛለች። ፈረንሣይ ከካናዳ አንዱን ወገን ትቆጣጠራለች፣ ከአፍሪካም ከመቶ 34 እጅ፣ ከመካከለኛው ምሥራቅም ደህና ድርሻ አግኝታለች። ሌሎችም እንደዚሁ የተቻላቸውን ያህል ቆንጥረዋል። በዚህ ሁኔታ ላይ የነበረችው ኢጣልያ ዓይንዋን በኢትዮጵያ ላይ ጣለች። የአውሮፖ መንግሥታትንም አግባባች። እንግሊዞች ለአፄ ዮሐንስ የገቡትን ቃል ኪዳን ጥሰው ከግብፅ የነጠቁአትን ምፅዋን 1877 ዓ.ም መጨረሻ ለገሡአት። አሰብን አስቀድማ በገንዘብ ገዛች። ሶማሊያን ከየባላባቱ በመስማማት ያዘች።

ነገር ግን ይህ ሁሉ በረሃ መሰብሰብ እንጂ የሚያረካት ላይሆን ቀረ። ኢጣልያ ከየአቅጣጫው ጉዞዋን ወደ ማሕል ኢትዮጵያ አቀናች። የያዘቻቸውን ቦታዎች መረማመጃ አደረገች። ለዚህም በኤርትራ በኩል ያሰው ይበልጥ ገር ሆነላት። ወታደሮቿ ከበረሃው ወጥተው ደጋውን ሐማሴንን፣ ሠራዬንና አካለ ጉዛይን ያዙ። ከዚያም ወደ ትግራይ ተሻገሩ። ክተደጋጋሚ ግጭት በኋላ አድዋ ላይ በ1888 ዓ.ም ኢጣልያ ተሸነፈች። የአድዋ ጦርነት ለኢጣልያ የሃፍረት ማቅ አልብሶ ለኢትዮጵያ ነፃነትዋን

አጐናጸፋት። አድዋ፣ በቅኝ ግዛት ለወደቁ ሕዝቦች ሁሉ መልካም ምሳሌ ሆነ።

ከአድዋ ጦርነት በኋላ የኢጣልያ ሁኔታ ችግር የበዛበት ሆነ። ውርደቱ በመግደርደር የሚሸፈን አልነበረም። የጦር ጉዳተኞችን መልሶ ማቋቋም፣ ኢትዮጵያን ተለማምጦ ምርኮኞችን ማስለቀቅ ግድ ነበር። የሊቢያ ጦርነት ፋታ አልሰጠም። የኤርትራና የሶማልያ ቅኝ ግዛቶችም የሚያረካ ጥቅም አላስገኙም።

ይህ በእንዲህ እንደአለ የመጀመሪያው የዓለም ጦርነት ተቀሰቀሰ። ኪያዮች በተባለች አንዲት ትንሽ የቻይና መሬት ምክንያት የተነሳው ጠብ ጃፓንና ጀርመንን አፋጠጠ። ውሎም ሳያድር በጀርመንና በራሽያ መካከል ጦርነት ተነሳ። እንግሊዝና ፈረንሣይ ጥቅምት 25 ቀን 1907 ዓ.ም (ኖቬምበር 1914) ከጦርነቱ ገቡ።

ለኢጣልያ ይህ ሁኔታ አስቸጋሪ ሆነባት። ገለልተኛ መሆን አልቻለችም። መጀመሪያ ወደ ጀርመን አዘነበለች። የማያዋጣት ሲሆን ግንቦት 17 ቀን 1907 ዓ.ም (ሜይ 1915) ከጦርነቱ ገባች። ከእንግሊዝና ከፈረንሣይ ጐን ለመቆም የወሰነችው ከአስትሪያ ጥቂት ቦታ ተበጭቆ እንደሚሰጣት፣ ከቱርክ ግዛትም ድርሻ እንደምታገኝ፣ በአፍሪካ ምድር ቅኝ ግዛት ለማስፋፋት እድል እንደሚኖራት ለንደን ላይ ቀደም ብሎ በተደረገ ንግግር ቃል ስለተገባላት ነበር።[2]

- በአውሮፓ ደግሞ የነበረውን አገዛዝ የሚሸር፣ አዳዲስ አስተዳደር የሚመሠርት ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ተጀመረ። ኮሚኒዝም በራሽያ፣ ናዚዝም በጀርመን፣ ፋሽዝም በኢጣልያ ሥልጣን ያዙ። እነዚህ ንቅናቄዎች ለሕዝቦቻቸው አርነት፣ ለሀገሮቻቸው አክብሮት፣ ለርእዮተ ዓለማቸው ጽንአት የሚያስገኙ ሥራዎች በመሥራት የሕዝብን እምነት ማግኘት ነበረባቸው። ሁሉም በየበኩላቸው እንደዚሁ አደረጉ።

በኢጣልያ የተካሄደው የፋሽስት አብዮት በቢኒቶ ሙሶሎኒ መሪነት በ1915 ዓ.ም (1922) ለሥልጣን በቃ። በ1915 ዓ.ም ገና ከሥልጣን ላይ እርካብ ለወጣው ለሙሶሊኒ ቀደም ብላ ኢጣልያ የገባችበት ስምምነት አላረካውም። በጦርነቱ ፍፃሜ ያገኘችውም ፀጋ በቂ መስሎ አልታየውም። በቬርሳይ ቤተ መንግሥት በተደረገው የሰላም ጉባኤ ላይ ኢጣልያ አክብሮት ሳታገኝ ቀረች። በጀኔቫ የዓለም መንግሥታት ማህበር ሲቋቋም አባል ሆነች። ነገር ግን በክብር አልነበረም፣ በቀዝቃዛ ስሜት እንጂ። የጣልያን ህዝብ ሮማውያን በአካባቢያቸው የነበሩ ሀገሮችን ይገዙበት በነበረ መንፈስ፣ ይህንን ዓይነቱን ስሜት ተቀብሎ በትዕግስት መኖር አቃተው።

በዚያውም ላይ የፋሽስት ደም ጠማሽ አመለካከት ሰፈነበት። ዕለት ዕለት የሚሰማው የሙሶሊኒ ቅዠት ዕረፍት ነሳው።

ማንኛውም ሕዝብ የራሱ የሆነ ባሕርይ፣ ወግና ሥርዐት እንደ አለው ሁሉ፤ የኢጣልያም ሕዝብ የበኩሉ አለው። ጠንካራ ሠራተኛ ነው። በተለይም በምህንድስና ሥራ ጐበዝ ነው። በመንገድና በሕንፃ ሥራ የሚተካከለው ያለ አይመስልም። በሕግ ማስብና የመተዳደርን ሁኔታ ለዓለም ያበረከተ እሱ ነው። ነገር ግን አስተዳደርን እና ፖለቲካን በተመለከተ ገና ብዙ ይቀረዋል። አንዳንድ ባሕርያቱ የአስተዳደር እንዲሁም የፖለቲካ ሥምረት ሊያስገኙለት የሚችሉ አይደሉም። ለምሣሌ ችኩል፣ ቁጡ፣ ለፍላፊ ነው። አብዛኛውን ጊዜ የመንፈስ እርካታ የለውም። የአስተዳደርና የፖለቲካ ሥራ ደግሞ ትዕግስት፣ ዕርጋታ፣ ጭምትነት ይጠይቃል። ባገኘው ለማይረካ፣ ማጣትና ማግኘት ልዩነት የላቸውም።

አዲሱ የፋሽስት መንግሥት ልዩ ልዩ ችግሮች ቀስፈው ያዙት። የፖለቲካ ቡድኖች ብዛት የማይቀንስ፣ የአስተያየታቸው ልዩነት የማይታረቅ ሆነበት። ሥራ አጥነት ጠነከረ። የሕዝቡ የዴሞክራቲክ አስተዳደር ፍላጐት የማያፈናፍነው ሆነ። የኢንዱስትሪ፣ የልማት ሥራዎች የመስፋፋታቸው ጉዳይ ዳተኛ ሆነበት። ብሔራዊ ስሜት እየጐለበተ ሄደ። የጳጳሱና የንጉሡ ተፅዕኖ ከበደው። የዓለም መንግሥታት ንቀት ጣሊያኖችን አናደዳቸው። [3]

በእነዚህ ሁኔታዎች ተቀስፎ የተያዘው ሞሶሎኒ ዓይነ ልቡናውን በኢትዮጵያ ላይ ጣለ። ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛትነት መያዝ ብዙ ጉዳይ የሚተክስለት መስሎ ታየው። የአድዋን ቂም መበቀልና የጣልያንን ክብር ማደስ፣ ሰፊና ለም የቅኝ ግዛት ይዞ የወደቀውን ኢኮኖሚ መገንባት የሚቻለው ኢትዮጵያን በመያዝ መሰለው። በርእዮተ ዓለም ረገድ ለተቅበጠበጠው የኢጣልያ ሕዝብ አዲስ የሰፈራ ቦታና የሥራ እድል መስጠት፣ በዓለም ፊት ሞገስ ማግኘት፣ የሕዝቡን ብሔራዊ ስሜትና አንድነት ማፅናት፣ የእሱን የራሱን ክብር ከፍ ማድረግና የፋሽስት ፓርቲን ርዕዮተ ዓለም መገንባት የሚችለው ኢትዮጵያን በመያዝ መሰለው።

የኢጣልያ ሕዝብ በወቅቱ ነባራዊ ክስተቶች ስሜቶቹ ተቀሰቀሰበት። ወደ ቀድሞ ትልቅነቱ በታሪክ ተመለከተ። በጉ ስሜቱን የሚያጐለብት እና መጥፎ ስሜቱን የሚገታ መሪም፣ መካሪም አላገኘም። ከቤኒቶ ሙሶሊኒ ቅዠት ውስጥ ገባ። ንጉሡም፣ ጳጳሱም አብረውት ገቡ። መኪንንቱ ንጉሡን፣ ካህናቱ ጳጳሱን ከመከተል በስተቀር ሌላ መንገድ አልነበራቸውም። ሙሶሊኒ አዲስ ባቋቋመው የፋሽስት ርዕዮተ ዓለም

ሠላቱን አሰክረው። የእሱን ሐሳብ የሚከተሉትን እየመለመለ ካድሬ አደረጋቸው። በእናት ሀገር ውድቀት ያዘኑ ሰማስመሰል ጥቁር ሸሚዝ አሰበላቸው። ነገር ግን ይህ ጥቁር ልብስ መጥፎ ግብሩን እንደሚያመለክት የተረዳ፣ ከዚያም ለመመለስ የሞከረ አልነበረም። በሐሳቡ ባልተስማሙት ላይ ተፅዕኖ አደረገ። የፖለቲካ መሪዎችንም አሰረ። ኮጥቂቶች በስተቀር የኢጣልያ ሕዝብ ተከተለው። [4]

ሞሶሊኒ ይህንን ዓላማውን በሥራ ለመፈፀም የሚችልበትን መንገድ መቀየስ ጀመረ። አንዱ ተግባሩ የጦር መሣሪያ መሥራት፣ ሊሠራው ያልቻለውን መግዛት፣ ወታደር ማሠልጠንና ወደ ኤርትራና ሶማልያ ማጓጓዝ ሆነ። የጦር መሣሪያ የሚሠሩ ፋብሪካዎች በብዛት ተቋቋመ። በአንድ ጊዜ ስድስት ጥይት የሚጐርሱና በየተራ የሚተኩሱ የምንሸርና የአልቤን ጠመንጃዎች ከነሳንጃና ከነጥይታቸው በብዛት ተሰሩ። ሃያ ጥይት ጐርሶ በአንድ ጊዜ የሚተኩስ መትረየስ፤ እንዲሁም ከምድርና ከአየር የሚተኮስ የውሃ መትረየስ ተሠራ። ከሁሉም በላይ አስተማማኝ የሆነው ታንክ ነበር። ሌላው ዝግጅት በበምብ ረገድ ነበር። በእጅ የሚወረወር፣ ከጠመንጃ አፈሙዝ እየተገጠመ የሚተኮስ፣ ከሰማይ በአይሮፕላን የሚጣል የቦምብ ዓይነቶች ተዘጋጁ። ብዛት ያላቸው አደሮፕላኖች ተሠሩ። ይህም የማይበቃ ሆኖ ከአይሮፕላን የሚረጭ የጋዝና የኬፕሪት መርዝ በፈሳሽ መልክ ተዘጋጀ።

ወታደር ተመለመለ፣ ሰለጠነ። ከኢጣልያ፣ ከኤርትራና ከሶማልያ ብዙ ወታደር ተደራጀ። ብዛት ባይኖረውም ከሲቪያ ተመለመለ። በምድር ጦር፣ በአየር ኃይልና በባሕር ኃይል በኩል ሙሉ ዝግጅት ተደረገ። የዱቼ ሙሶሊኒ ልጅ ቪቶርዮ ሙሶሊኒ ራሱ በአየር ኃይል መኰንንነት ሰለጠነ። ነገር ግን ወደ ኢትዮጵያ የመምጣት ዕድል ሳያገኝ በስፔይን ጦርነት ከአይሮፕላን ጋር ወድቆ ሞተ።

ሞሶሊኒ የማጓጓዣ መኪናዎች አዘጋጀ። ካሚዮን በየአይነቱ አሠራ። ለጦር መኮንኖች እርዳታ አውቶሞቢል፣ ለኢጣልያውያን ሠራተኞች ሞተርሳይክሎች አዘጋጀ። በኢትዮጵያ በረሃማ፣ ደጋማና ተራራማ ቦታዎች ዕቃ የሚያንቡዙ እስከ 50 ሺህ የሚገመቱ አህዮች፣ አጋሰሶችና ግመሎች አዘጋጀ። የኢትዮጵያን የመሬት አቀማመጥ፣ የወንዞችን አፈሳስ፣ የአየር ንብረቱን ፊት ለጦርነት፣ ኋላ ደግሞ ለልማት ሥራ እንደሚበጀው እያስደረገ አስጠና። በዚህ ሁሉ ዓለም ተባበረው፤ የስዊዝ ካናል ክፍት ሆነለት።

ሌላው ትኩረቱ የኢትዮጵያን የውስጥ ሁኔታ በማጥናት መሪዎቹንና ህዝቡን መከፋፈል ሆነ። የመኪንንቱንና የመሣፍንቱን ልቡና

በጥቅምና በሥልጣን እየደለለ የኢትዮጵያን ምስጢር በዘበዘ። ልባቸውን ከፋፈለ። ህዝቡንም በኃይማኖት፣ በጎሣ ማቃቃር ያዙ። ኢትዮጵያ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ በሬዲዮ የምታስተላልፈውን መልእክት እየጠለፈ የሚያደምጥበት መሣሪያ አዘጋጀ። በዚህም ሚሲዮናዉያን፣ የዲፕሎማቲክ ሠራተኞችና ነጋዴዎች ተባበሩት።

ሞሶሎኒ የጦር ትጥቁን ከማዘጋጀት ጋር የኢጣልያን ሕዝብ ሥነ ልቡና ለጦርነቱ ማነሳሳት ያዘ። የጣልያንን ቁጭትና ጥቅም የሚያዳብሩ፣ የኢትዮጵያን ስም የሚያጉድፉ ወሬዎች በሕዝብ መገናኛዎች ነዙ። ዓላማውን ለሕዝብ አስረዱ። የጦርነቱን ግቦች በይፋ አስታወቀ። ከእነሱም ዋና ዋናዎቹ፡

1. ታላቅና ለም የቅኝ ግዛት በመያዝ የጣልያንን ኢኮኖሚ ማዳበር፤
2. ኢትዮጵያን ከኤርትራና ከሶማሊያ ቅኝ ግዛቶች ጋር በመቀላቀል ቦታ የጠበበውን የጣልያንን ሕዝብ አምጥቶ ማስፈር፤
3. ለኢጣልያ ኢንዱስትሪዎች ጥሬ ዕቃና የሰው ኃይል፣ ለምርታቸው ገበያ ማስገኘት፤
4. በአድዋ ጦርነት የተዋረደውን የጣልያንን ክብር በአዲስ ድል ማደስ፤
5. ኢጣልያ በዓለም ጎብረተሰብ ዘንድ አክብሮት እንድታገኝ ማድረግ ነበር።

ከዚህም በተጓዳኝ የዓለምን አመለካከት ወደ እሱ ለመመለስ ልዩ ልዩ ጥረት አደረገ። ምነው ባይ እንዳይኑሳና ዓላማውን እንዳያከሽፍበት፤ በተለይ የአውሮፓ መንግሥታት ተቃውሞ እንዳያነሱበት፤ እንደየጥቅምና ጉዳያቸው እየሸነገለ አስተባበረ። ጥረቱ ሁሉ ሠመረለት። ሙሶሊኒ አስቦ የሚሰራ እንጂ፣ በሰመመን የሚንቀሳቀስ ሰው አልነበረም። የአድዋ ውርደት ተመልሶ እንዳይደገም ተገቢውን ጥንቃቄ አደረገ። ለጦርነቱም መሪዎች የሚሆኑት በጥንቃቄ ተመረጡ። ሰብዓዊ አመለካከት ይታይባቸው የነበሩትን አስወጣ። ለዘብተኛውን ጀነራል ደቦኖን ሽሮ፣ መጀመሪያ ላይ በጨካኝነቱ የተማመነበትን ጀነራል ባዶሊዮን ሾመ። ለጦርነቱም ስልት አወጣለት።

በጠቅላላው የኢጣልያ ዓይን በኢትዮጵያ ላይ፣ የኢትዮጵያ ተሰፋ በዓለም መንግሥታት ማህበር ላይ ሆነ። ሙሶሊኒ በዓላማው ፀና። ጦርነቱን ለመክፈት ጠብ መጫር ያዘ። በጉንደር ቆንሲሉ አማካይነት ያስነሳው ጭቅጭቅ በኢትዮጵያ ጥረት ሲበርድ፣ የወልወልን ግጭት አስነሳ። ይህንንም በሚገባ አናፈሰው፤ ለዓለም ማህበርም ስሞታ አቀረበበት። ይህንን ሁሉ ከአዘጋጀ በኋላ ጦርነቱን በራሱ ሥልጣን ከፈተ።

ሠራዊቱም በአገኘው መሣሪያ ሁሉ፤ በጋዝና በመርዝ ቄምር እንዲዋጋ ትዕዛዝ ሰጠ።

ከሰሜንና ከደቡብ ምሥራቅ በአንድ ጊዜ በምድርና በአየር ተንቀሳቅሶ ኢትዮጵያን በመስቀለኛ ቅስት ወጠራት። የሰሜኑ ጦር ከአሥመራ ተነስቶ በሁለት መንታ መንገድ እንዲንቀሳቀስ አደረገ። አንዱ ቡድን በአዲግራት፣ በመቀሌ፣ በደሴ አድርጉ አዲስ አበባ እንዲገባ። ሁለተኛው ቡድን በአዲጋላ፣ በአክሱም አድርጉ ጐንደር፣ ጉሻምን ከዚያም ወለጋን፣ አፋርና ኢሉባቡርን እንዲይዝ አደረገ። ከሞቃድሾ የሚንቀሳቀሰው ደግሞ እንደዚሁ ከሁለት ተከፍሎ እንዲያጠቃ አሰለፈው። አንዱ ቡድን በፌርፌር፣ በቀብሪ ደሐር፣ በደገሐቡር፣ በጂጂጋ አድርጉ ሐረር እንዲገባና ድሬዳዋን በመያዝ የባቡሩን ሀዲድ እንዲቆጣጠር፣ ከዚያም አዲስ አበባን እንዲያጠቃ። ሌላው ቡድን በደሎ ፣ በነጌሌ፣ በያርጋ ዓለም አድርጉ ደቡቡን እንዲይዝ አደረገ። በአሰብ ለመንቀሳቀስ የሞከረ ቡድንም ነበር። ነገር ግን እምብዛም ውጤት አላስገኘም።

ማጣቀሻ ፅሑፎች

1. Carlton Hayes, *Contemporary Europe*, pp.123-311.
2. Ibid., pp.378-9 and 33-82.
3. Stanley Cooperman, *Benito Mussolini*, pp.147-160.
4. Ibid.,33-82.

ምዕራፍ ሰባት

የጉንደር ውዝግብና የወልወል ግጭት፤ የአውሮፖ መንግሥታት አመለካከት

ኢጣልያ ለጦርነቱ ሙሉ ዝግጅት ከአደረገች በኋላ ጠብ መቈር ጀመረች። ሃይማኖት የሚያስተምሩ መስለው ቀደም ብለው የገቡ ሚሲዮናውያን፣ ነጋዴዎች፣ የዲፕሎማቲክ ሰዎች በዚህ ጉዳይ አገለገሉ። ከተለመደና ቋሚ ከሆነው የስለላና የስብከት ግብራቸው ገቡ።

የኢጣልያ መንግሥት በዚያ አካባቢ የነበሩ ሚሲዮናውያንን ለመርዳት በሚል፤ ጉንደር አንድ ቆንሲል አስቀምጦ ነበር። ይህ ሰው ራፋኤል ዴ ላውሮ የሚባል ሲሆን፣ ወልደ ሩፋኤል ነኝ በሚል ራሱን ሰይሞ አማርኛ በማጥናት አገርና ሕዝቡን ያጠና ሰው ነበር። ከጳጳሱ ከአባ አብርሃም፣ ከካህናቱና ከመኳንንቱ ጋር ወዳጅነት ከመመሥረቱም በላይ፤ በጽህፈት ቤቱ አጠገብ ትምህርት ቤት አቋቁሞ ለተማሪዎች ልብስ እያለበሰ፤ የኢጣልያ ቋንቋና የፋሽስትን ሥርዓት ያስተምር ነበር። ምንም ቁጥጥር ስለማይደረግበት መለከት እያስነፋ መንደር ለመንደር እየዞረ፤ ከፈለገው ሰዉ ጋር ይነጋገርና የወደደውን ያደርግ ነበር። በየድግሱ ቤት እየገባ ይበላና ይጠጣ ነበር። በዚህ ዓይነት የሰበሰበውን ወሬ፣ የራሱን አስተያየት በመጨመር፣ ለኢጣልያ መንግሥት ሪፖርት በመስጠትና ምክር በማቅረብ በጦርነቱ አካሄድ ላይ የበኩሉን ታላቅ አስተዋጽኦ አድርጉአል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ታደሰ ዓለሙ የሚባል የቆንሲሉ ዘበኛና የጉንደር ከተማ ፖሊስ የነበረው በላይ ገብረ እግዚአብሔር፤ አንዲት ብዙነሽ ነጋሽ በምትባል ሴት ምክንያት ጠብ አንስተው ሲታኮሱ፤ ችኮል ታየ የሚባል ሌላ የቆንሲሉ ዘበኛ ሞተ። ራፋኤል ዴ ላውሮ ታላቅ ሪፖርት ስለአቀረበ አዲስ አበባ የነበረው የኢጣልያ ሌጋሲዮን በነገሩ በብርቱ ገባበት። በኢጣልያ መንግሥት ላይ በደል የተፈፀመበት ለማስመሰል ልዩ ጥረት አደረገ። ጠብን ለማብረድ ሲባል የጉንደር ከተማ ከንቲባ የከተማይቱን ዘበኞች አሰልፈው፤ እስከ ቆንሲሉ መሥሪያ ቤት ድረስ ሄደው ይቅርታ ጠየቁ። የደም ዋጋም ለሚቹ ወገኖች ከሚገባቸው በላይ ተከፈለ። በዚህ ዓይነት በጉንደር በኩል የተቀሰቀሰው ጠብ በረደ።[1]

ነገር ግን በጉንደር በኩል አንድ ጠብ ሲበርድ በወልወል በኩል ሌላ ግጭት ተነሳ። ጦርነቱ ከተነሣባቸው ምክንያቶች ዋነኛው እሱ ስለሆነ በዝርዝር መመልከት ይበጃል።

ኢጣልያ ኢትዮጵያን በያዘች ጊዜ ከወዳጅ ጋር የሚያቃቅር ነገር እንዳይኖር በቅድሚያ ተገቢውን ለማድረግ፤ እንግሊዝ በሰሜን ሶማልያና

በኢትዮጵያ መካከል ያለው ወሰን እንዲከለል ጠየቀች። ለወሰኑ ክለላ ሥራ ከእንግሊዝ ወገን ኮሎኔል ክሊፎርድ /ጉዳዩ ጦር ቀመስ ስለሆነ/፤ በኢትዮጵያ በኩል ፊታውራሪ ተሰማ ባንቲ /አፀፋውን ለመመለስ/ ዋና ተካፋዮች ሆኑ። የወሰን መካለሉ ሥራ የሚካሄደው በግንቦት 6 ቀን 1889 ዓ.ም (ሜይ 14 ቀን 1897) በአዜ ምኒልክ እንዲሁም በንግሥት ቪክቶሪያ ወኪል በሆኑት በሠር ጀምስ ሪኔል ሮድ መካከል በተፈረመው ስምምነት[2] መሠረት ሆኖ፤ በወሰኑ ላይ ሕጋዊና ቅዋሚ ምልክቶች በማድረግ ነበር። የወሰን መካለሉ ሥራ ያለ ምንም ችግር ሲካሄድ ቆይቶ የአጋዴን፣ የሰሜን ሶማልያና የደቡብ ሶማልያ ግዛት አስከሚወሰንበት ቦታ ደረሰ። ስምምነቱም በኢትዮጵያ በኩል ከዓለም መንግሥታት ማህበር የገባ ነበር። ቡድኑ ከዚህ ቦታ ሲደርስ ግን ታላቅ ችግር አጋጠመ።

እንግሊዞች የወሰኑ መከለል ሥራ መሬቱ እየተረገጠ፤ ምልክትም እየተደረገበት እንዲሆን ጠየቁ። የኢትዮጵያ ፍላጐት ሕዝቡ በየጐሣው እየተጠየቀ በካርታው ላይ ምልክት እንዲደረግ ነበር። የኢትዮጵያውያኑን ሃሳብ እንግሊዞች ስለአልተቀበሉት፤ መሬት የመቁራት ሥራ ተጀመረ። እስከ ወልወል አካባቢም በሰላም ተካሄደ። የወሰን መከለሉ ሥራ ወደ ወልወል እየተቃረበ ሲሄድ፤ የጉዳዩ አሳሳቢነት እየከበደ ሄደ። መሬት የመቁራት ሥራ እንዲያበቃና በካርታ ላይ ምልክት እንዲደረግ የሚለው የኢትዮጵያ ሃሳብ ጠነከረ። ጉዳዩ አሳሳቢ የሆነበት ምክንያት ጣልያኖች ጠብ ለመጫር ማቆብቆባቸው ስለታወቀ፤ በዚያ ላይ ደግሞ ከወልወል በስተደቡብ ያለው የግጦሽ ቦታ እምብዛም አከራካሪ ባለመሆኑ ነበር። ነገር ግን እንግሊዞች ደጋግመው ጠየቁ። ሀሳባቸው ከኢትዮጵያ ተቆርሶ ለኢጣልያ ይሰጥ የተባለውን ቦታ ለይቶ ለማወቅ ጭምር ነበር። ቡድኑ ሥራውን ለመቀጠል ህዳር 10 ቀን 1927 ዓ.ም ከጂጂጋ ተንቀሳቀሰ። አጃቢና ጠባቂ ኃይል ከኢትዮጵያ ወገን ታዘዘ።

ቡድኑ የወሰን መከለሉን ሥራ ለመቀጠል መንቀሳቀሱ ሲታወቅ ሙሶሊኒ ሙስታሄል እና በዋቢሸበሌ ወንዝ አካባቢ፤ እንደዚሁም የውሃ ጉድጓድ ያለባቸው ወልወል፣ ዋርዴር፣ ገርለጉቤ፣ ቆራሄ፣ ቀብሪደሐርና የፋፈን ወንዝ አካባቢ ያለው ቦታ እንዲያዝ ትዕዛዝ አስተላለፈ። ማንኛውም የኢጣልያ ወታደር የረገጠው መሬት ሁሉ የጣልያን ቅኝ ግዛት መሆን እንደአለበት ገለፀ። በዚህ መመሪያ መሠረት የኢጣልያ ወታደሮች፤ ወሰን ተካዮች ከመድረሳቸው በፊት ወልወልን ለመያዝ ሞከሩ። የኢትዮጵያ ወታደሮች ተከላከሉ። ህዳር 26 ቀን 1927 ዓ.ም ተኩስ ተከፈተ። ኢጣልያ የፈለገችው ግጭት ተፈጠረ። ኢጣልያ አስቀድማ ተዘጋጅታ ስለነበር በታንክ የታገዘ እግረኛ ሠራዊት አሠማራች።

አካባቢውን በአይሮፕላን አስደበደበች። በጀግንነት ሲከላከሉ 94 የኢትዮጵያ ወታደሮች ሞቱ፣ ሌሎች 45 ቆሰሉ። ከኢጣልያ ወገን ደግሞ 217 ባንዳዎች ተገደሉ።

ሙሶሊኒ ኢትዮጵያን ጠብ አጫሪ አስመስሎ በዓለም መንግሥታት ማህበር አቤቱታ አቀረበ። ከዚያም አልፎ፣

1ኛ. የሐረርጌው ገዥ ወልወል ድረስ ሄዶ በዚያ ያሉትን የኢጣልያ የጦር አዛዦች ይቅርታ እንዲጠይቅ፣ ከዚህም በስተቀር አንድ የኢትዮጵያ የክብር ዘብ ተሰልፎ ለኢጣልያ ባንዲራ ሰላምታ እንዲሰጥ፣

2ኛ. የኢትዮጵያ መንግሥት ለፈረሱ ምሽጉች ማሠሪያና ለሞቱ የኢጣልያ ወታደሮች ካሣ 200,000 የማሪያ-ቴሬዛ ብር እንዲከፍል፣

3ኛ. ለግጭቱ መነሻ የሆኑ የኢትዮጵያ ሹማምንቶች ከሥልጣናቸው ወርደው እንዲቀጡ ጠየቀ።[3]

በኢትዮጵያ ወገን ከእነዚህ ጥያቄዎች አንዱን መፈፀም፣ የሀገሪቱን የግዛት አንድነትና ሉዐላዊነት ማስደፈር ሆነ። ኢትዮጵያም በመንግሥታቱ ጉባኤ ውል በአንቀጽ 15 ላይ ተመሥርታ አቤቱታዋን ለማህበሩ አቀረበች። ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ ነገሩን የሚመረምሩ ዳኞች ተሰየሙ። ኢትዮጵያ አንድ ፈረንሣዊና አንድ አሜሪካዊ ስትመርጥ፣ ኢጣልያ ሁለት የራስዋን ዜጐች መደበች።

ነገሩን ለመመርመር ሁለት ቁልፍ ጥያቄዎች መታየት ነበረባቸው። ከእነዚህም አንዱ "ክልሉ የማነው?" የሚል ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ "ግጭቱን ያስነሳው ማን ነው?" የሚሉ ነበሩ። በጉዳዩ መመሪያ ለመቀበል ያለ ሀፍረት ወደ ሮም በመሄድ ሥራው ተጀመረ። ነገር ግን ኢጣልያ "ክልሉ የማነው?" የሚል ጥያቄ እንዳይነሣ፣ የወሰንና ቀደም ብለው የተደረጉ ስምምነቶች እንዳይወሱ ተከላከለች። ስለዚህ የማጣራቱ ሥራ "ጠቡን ማን አስነሣው?" በሚለው በሁለተኛው ጥያቄ ላይ ብቻ አተኮረ። ለኢትዮጵያ የተሻለ የሚሆነው "ክልሉ የማነው?" የሚለው ጥያቄ በመጀመሪያው ደረጃ ቢመረመር ነበር። የማህበሩ ጉባዔ ሐምሌ 27 ቀን 1927 ዓ.ም (አገስት 3 ቀን 1935) ባደረገው ስብሰባ ዳኞች የግዛቱን ጥያቄ እንዳያዩ አዘዘ።

ይኸ በእንዲህ እንዳለ ሂትለር በአንደኛው የዓለም ጦርነት ፍፃሜ ላይ ጀርመን የጦር ኃይል እንዳታቋቁም ተወስኖ የነበረውን ውሣኔ ጥሶ፣ የራይንላንድን ሠራዊት መልሶ ለማደራጀት የወሰደው እርምጃ በአውሮፓ ላይ አዲስ የድንጋጤ መንፈስ ፈጠረ። የማህበሩ አባላት አመለካከት እንደገና ተዘበራረቀ። የወልወል ግጭት ጉዳይ ብዙ ከአወዛገበ በኋላ

ለማህበሩ ጠቅላላ ጉባዔ ቀረበ። ከሚያስገርሙት ሁኔታዎች አንዱ በዚህ ጉባዔ ላይ ኢትዮጵያን ወክሎ የተናገረው ፈረንሣዊው የሕግ አማካሪ ሙሴ ሻሾ መሆኑ ነው። ጉባዔው የኢትዮጵያ ግዛትና ሉአላዊነት አልተነካም የሚሰውን አቅዋም በግልፅ ተቀበለ።[4] የግጭቱን አነሳስ በተመለከተ ደግሞ ኢትዮጵያም፣ ኢጣልያም በወልወል በተደረገው አደጋ ኃላፊ ሊሆኑ አይችሉም ተብሎ ተፈረደ።[5]

የወሰኑን ጉዳይ ባጭሩ መመልከት ደግሞ ሌላ ጠቅላላ ግንዛቤ ይሰጣል። በታህሳስ ወር 1900 ዓ.ም (1907) ክሞቃድሾ በስተ ሰሜን ሦዕራብ 130 ማይል (208 ኪሎ ሜትር) ርቃ በምትገኘው ባይዳዋ በምትባል ቦታ በኢትዮጵያና በኢጣልያ መንግሥታት መካከል ግጭት ደረሰ። በዚህ ግጭት ምክንያት በዳግማዊ ምኒልክና በሣልሣዊ ኢማኑኤል መልእክተኛ በሲኞር ኪሊ ዶ ፊሊዛኖ መካከል አንድ የወሰን ክልል ስምምነት ግንቦት 8 ቀን 1900 ዓ.ም (16 ቀን 1908) ተፈረመ። የስምምነቱ ዓላማ በኢጣልያ ይዞታና በኢትዮጵያ ግዛት መካከል ያለውን ወሰን በማያሻማ ሁኔታ ለመከለል ነበር። ለስምምነቱ መሠረት የሆነው ቀደም ብሎ በ1897 ዓ.ም በሁለቱ መንግሥታት መካከል ተፈርሞ የነበረው ውል ነበር። ምንም በስምምነቱ መሠረት መሬቱ ተረግጦ ወሰኑ ባይቆራም፣ ውሉ ፀንቶ የቆየና በኢትዮጵያ በኩል በ1915 ዓ.ም (1923) ለዓለም መንግሥታት ማህበር ገብቶ የተመዘገበ ነበር።

ወልወል በዚህ ውል ከተከለለው ወሰን 80 ማይል (ወደ 130 ኪሎ ሜትር) የምትርቅ የኢትዮጵያ ግዛት ነች።[6] የኢትዮጵያ ግዛት መሆንዋ አላከራከረም። ግዛቱ የማነው የሚለው ጥያቄ ፊጽሞ እንዳይነሣ ኢጣልያ አጥብቃ የተከላከላቸው በዚህ ምክንያት ነበር። ወልወልና አካባቢዋ በዚያን ጊዜ 359 ጥልቅ የውሃ ጉድጓዶች ነበሩባት። በግጭቱ የፈሰሰው ደም፣ የወደመው ንብረት ቀላል አልነበረም። ነገር ግን ከጥቅማቸው በላይ ምንም ቁም ነገር ማየት ለማይችሉ ልዕለ-ኃያላን እነዚህ ጉዳዮች አንዳች አልነበሩም። ስለዚህ የቅኝ ግዛቶች ሁሉ ፍፃሜ፣ የሁለተኛው የዓለም ጦርነት መንሥዔ የሆነው የወልወል ግጭት ፍቺ ሳያገኝ ቀርቶ ጦርነቱ ቀጠለ።

የኢጣልያ ወረራ እየገፋ ሲሄድ ኢትዮጵያ ለዓለም ማህበር የምታቀርበው ነፍስ አድን የፍርድና የዕርዳታ ጥያቄ ጠነከረ። የአውሮፓ ታላላቅ መንግሥታት የጦርነት ደመና እያንዣበበባቸው ሲመጣ፣ ከማህበሩ ውጭ በሉካርኖ (እ.ኤ.አ 1925) እና እስትሬዛ(እ.ኤ.አ 1935) ላይ ሁለት ስምምነት ቀደም ብለው ተፈራርመው ነበር። ልዕለ-ኃያላኑ የዓለም ማህበርን ውል ወደ ጐን ትተው፣ የኢትዮጵያን ጥያቄ በእነዚህ ሁለት

ስምምነቶች መሠረት ለመፍታት ፈለጉ። ነገር ግን እነዚህ ሁለት ስምምነቶች በአንድ አባል መንግሥት ላይ ጥቃት በደረሰ ጊዜ ስለሚሰጠው ዕርዳታ የተለያየ ድንጋጌ ስለነበራቸው ችግር አጋጠመ። የሉካርኖው ውል እያንዳንዱ ተዋዋይ መንግሥት እንደ ፍላጐትና አቅሙ እንዲረዳ ሲፈቅድ፤ የእስትራሣው ስምምነት ደግሞ ተዋዋዮቹ አገሮች በህብረት ዕርዳታ እንዲሰጡ ይደነግጋል።

የልዕለ-ኃያላኑ መንግሥታት ጭንቅ የእነሱ እንቅስቃሴ ሙሶሊኒን ወደ ሂትለር የሚገፈትር እንዳይሆን ነበር። ስለዚህ ያ ሁኔታ በየትኛውም ምክንያት እንዳይፈጠር መጠንቀቅ ያዙ። ስለ ኢትዮጵያ አቤቱታ ያላቸው አመለካከት ተሰበጣጠረ። ፈረንሣይ በሉካርኖ ውል መሠረት የግል እርዳታ ማቅረብን፤ እንግሊዝ ደግሞ በእስትራሣው ስምምነት መሠረት የህብረት እርዳታ መስጠትን መረጡ። ኢትዮጵያ ግን አንዱንም አልተቀበለችም። ጉዳዩ ከማህበሩ ውጭ ይታይ የሚለው ሀሳብ ደግሞ ከነጭራሹ የክርክር ጭብጥዋን የሚያስለቅቃት ሆነ። አሜሪካን እስታንዳንደርድ ቫኪዩም የተባለው ኩባንያ ኢትዮጵያ ውስጥ ነዳጅ ሊያወጣ ቀደም ብሎ ገብቶበት የነበረውን ውል እንዲሠርዝ አደረገች። ሶቪየት ራሺያ ይህንን ከመሰለ ውዝግብ የመግባት አቅምም ሆነ ፍላጐት አልነበራትም። ሙሶሊኒ አስትሪያን ለእሱ ትቶ በኢትዮጵያ ላይ እንዲያተኩር ማድረግ ለሂትለር ጥቅሙ ሆኖ ታየው። ጃፓን ኢትዮጵያን መደገፉን መረጠች። ነገር ግን ሙከራዋ የዘገየና ፍሬቢስ ሆነባት። ኢትዮጵያ በዚህ የተነሣ ለኢጣልያ ወረራ ተጋለጠች።

<u>ማጣቀሻ ፅሑፎች</u>

1. ተክለፃድቅ መኩሪያ፣ *የኢትዮጵያ ታሪክ፣ ከአፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ*፣ ገጽ 187-190።
2. Pierre Petrides, *Boundary Questions between Ethiopia and Somalia*, pp.21-28
3. ጳውሎስ ኞኞ፣ *የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦርነት*፣ ገጽ 12-19።
4. ጆን ሐዛወይ ስፔንሰር፣ *ጥርስ የገባች ሀገር*፣ ትርጉም በመንግቱ ኃይለማርያም አርአያ መዝገቡ ተክሌ ቢልልኝ፣ ገጽ 62-69።
5. *ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፣ ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ 1ኛ መጽሐፍ*፣ ገጽ 186።
6. Petrides, pp.44-52

ምዕራፍ አራት
ጦርነቱን ለማስቀረት የተደረገ የዲፕሎማቲክ ጥረት

የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የመንግሥታቸው ጠንካራ ጐን የውጭ ግንኙነት ነበር። ጥሩ የውጭ ግንኙነት ፈጠሩ። ኢትዮጵያንም ከዓለም አስተዋውቀው ከመንግስታቱ ማህበር አስገብዋት። እምነታቸውም በዲፕሎማሲ ጥበብ ኢትዮጵያን ከጦርነት ለማዳን ነበር። በመሆኑም በኢትዮጵያ ላይ ኢጣልያ የምትጭረውን ጠብ ለማብረድ ሞከሩ። እንደተገለፀው በጐንደር ከተማ የኢጣልያ ቆንሲል የነበረው ራፋኤል ዲ ላውሮ ያስነሳውን ጠብ አበረዱ።

እንደገና ከእንግሊዞች ጋር በሰሜን ሶማልያና በኢትዮጵያ ወሰን ላይ የመካለል ሥራ በሚካሄድበት ጊዜ፤ የኢጣልያ መንግሥት በ1900 ዓ.ም ከተደረገው የወሰን ክልል ወደ አንድ መቶ ኪሎ ሜትር ያህል ገብቶ በኢትዮጵያ መሬት ላይ ህዳር 26 ቀን 1927 ዓ.ም ግጭት እነሳ።[1] ሞሶሎኒም ጉዳዩን ለዓለም መንግሥታት አቅርቦ፤ የተገላቢጦሽ ኢትዮጵያ ለኢጣልያ ካላ እንድትከፍልና አፊሴላዊ ይቅርታ እንድትጠይቅ ጠየቀ። ከፍ ብሎ እንደተገለጸው

እነዚህን ጥያቄዎች ግን በተመሳሳይ ለመፍታት መሞከር፤ የኢትዮጵያን ክብርና የግዛት አንድነት የሚጐዳ ስለሆነ ተቀባይነት ሳያገኝ ቀረ።[2]

ስለዚህ ንጉሠ ነገሥቱ ስለ ጉዳዩ ለመንግሥታቱ ጉባኤ ሰፊ ሪፖርት አቀረቡ። በኢትዮጵያ ላይ የተፈፀመባትን በደል አስረዱ። ቀደም ሲል እንደተገለፀውም ከብዙ ውዝግብ በኋላ ነገሩን የሚመረምሩ ሽማግሌዎች እንዲመረጡ በዓለም ማህበር ተወሰኖ ሽማግሌዎቹ "ኢትዮጵያም ኢጣልያም በወልወል ለተደረገው አደጋ ኃላፊ ሊሆኑ አይችሉም" ብለው ወሰኑ።[3] ምንም ፍርዱ የፍርሀት ቢሆን፤ ነገሩ በረደ።

ሌላው ችግር፤ እንግሊዞች አስታራቂ በመምሰልና ፈረንሣዮችን በማስከተል የሚያስነሱት ነገር ሆነ። ከዚህም አንደኛው ቀደም ባሉት ጊዜያት አፄ ምኒልክ በታመሙ ጊዜ፤ እንግሊዞች ፈረንሣይንና ኢጣልያንን አስተባብረው ታህሣሥ 13 ቀን 1899 ዓ.ም ለንደን ላይ ተፈራርመውት የነበረው አንድ አስገራሚ ውል ነበር። ውሉም፤

1. የእንግሊዝ መንግሥት በአባይ ውሃ ላይ ልዩ ጥቅም እንዲኖረው፤
2. የፈረንሣይ መንግሥት ለሐዲዱ መፈፀሚያና መመላለሻ መንገድ ሥፍራ እንዲኖረው፤

3. የኢጣልያ መንግሥት የኤርትራና የሞቃዲሾ ቅኝ ግዛቶቹን ለማገናኘት እንዲችል፣ በኢትዮጵያ ላይ አቋርጦ የሚሄድ የባቡር ሐዲድ እንዲዘረጋ የሚል ነበር። የዚህ ስምምነት መገረን እንደገና ከጉዳይ ተቀላቀለ።

ሁለተኛው እንግሊዝ የፈጠረችው ችግር ከፍ ብሎ የተጠቀሰው መዘዘኛ የወሰን ክለላ ጥያቄ ነበር። ይህ ጥያቄ፣ በዚያ ለኢትዮጵያ አስጨናቂ በሆነ ወቅት እንዲነሳ የሚያስገድድ ችግር አልነበረም። ሆኖም ኢትዮጵያ ተስማማችና የክለላው ሥራ ተጀመረ፣ በሰላምም ተካሄደ። ነገር ግን የእንግሊዝ መልእክተኞች ኢጣልያ ግጭት ለመፍጠር መዘጋጀትዋን እያወቁ፣ የግጦሹን ሥፍራ ለሁለቱም ወገን እየዞሩን እንጉብኝ ማለት አመጡ። ከኢትዮጵያ ወገን ሥፍራው በየጐላው እየተጠየቀ በካርታ ላይ እንዲሰፍርና ጉዳዩ በዚሁ እንዲያልቅ የቀረበውን ጥያቄ አንቀበልም፣ ጊዜም አንሰጥም አሉ። በዚህ ዓይነት አስገድደው ኢትዮጵያን ከወልወል ግጭት ውስጥ ጨመሩአት።

ሦስተኛው ችግር የተፈጠረው እንግሊዝ አስታራቂ መስላ ያቀረበችው ሐሳብ ነበር። ይህም በወልወል ግጭት ምክንያት ለተነሳው ጠብ ኢትዮጵያ በአጋዴን በኩል ሀገር ቆርጣ ለኢጣልያ እንድትሰጥ፣ ኢትዮጵያም ከባሕር የምትገናኝበት የዚይላን በር ከእንግሊዝ እንድታገኝ የሚል ነበር። ነገር ግን ሙሶሊኒ ሳይቀበለው ቀረ።

አራተኛው ችግር ደግሞ ኢትዮጵያ በሰሜን በኩል የአክሱምን ቤተክርስቲያን ብቻ ወደ ራስዋ አስቀርታ እስከ ጊቤ ወንዝ ድረስ ያለውን ሀገርዋን ለኢጣልያ እንድትሰጥ፣ ከደቡብም እንደዚሁ ሰፊ ሥፍራ ለኢጣልያ መስፋፊያ እንድትሰጥ የሚል ሆኖ፣ የኢጣልያ መንግሥት የአሰብን የባሕር በርና በጂቡቲ መካከል ያለውን ሥፍራ ለኢትዮጵያ እንዲሰጥ የሚል ማጽናኛ ነበረበት። ይህ ሐሳብ በኢትዮጵያ በኩል ተቀባይነት ሳያገኝ ቀረ።[4] በእነዚህ ሁኔታዎች ምክንያት ችግሩን በዲፕሎማቲክ ዘዴ ለመፍታት የተደረገው ጥረት መክኖ ስለ ቀረ፣ ጦርነቱን የመመከትና የመከላከሉ ሥራ ቀጠለ።

ማጣቀሻ ፅሑፎች

1. ተክለ ፃድቅ መኩሪያ፣ *የኢትዮጵያ ታሪክ ከአፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ*፣ ገፆች 187-96።
2. ጳውሎስ ኞኞ፣ *የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦርነት*፣ ገጽ 16።
3. ቀ.ኃ.ሥላሴ፣ *ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ 1ኛ መጽሐፍ*፣ ገጽ 186።
4. ጳውሎስ ኞኞ፣ ገጽ 9-10። ተክለፃድቅ መኩሪያ፣ ገጽ 223።

ምዕራፍ አምስት
የጦር ዝግጅት

ኢጣልያ የአዘጋጀችው ጦር ከራሷ ተወላጆች፣ ከኤርትራውያን፣ ከሶማሊያና በጥቂቱም ከሊቢያ መሆኑ ቀደም ሲል ተገልፃል።[1] የጦሩ አሰላለፍ ቅደም ተከተል ደግሞ እንደሚከተለው ነበር። ኢጣልያውያኑ ከጎላ ደጀን፣ በሁለተኛ ደረጃ በመካከል ኤርትራውያን /ሕዝብ ሐማሴን የሚሏቸውን/ እና ሶማሌዎች፣ በሦስተኛ ደረጃ በግንባር ደግሞ ከሀገር ውስጥ የተቀጠረው ባንዳ ነበር።

ኢጣልያኖቹ፣ በተለይም የፋሽስት ፓርቲ አባላት የነበሩት የፖለቲካ መሪዎች የጦር አለቆች ሲሆኑ፣ ማንኛውም ነገር የሚወሰነው በእነሱ ነው። የኤርትራና የሶማሊያ ተወላጆች /አስካሪዎች/ የተሰማሩት በተራ ወታደርነትና በአስተርጓሚነት ሥራ ነበር። ሆኖም ኩጣልያኖች በታች ሙሉ ሥልጣን ነበራቸው። ባንዳ እግረኛ ተዋጊ ነው። በስለላ ሥራም ጠላትን ያግዛል። የታዘዘውን ከመሥራት በስተቀር ሌላ ሥልጣን የለውም።

ኢጣልያ በጦርነቱ ከልብ አስባበት ስለነበር በቂ መሣሪያ አዘጋጅታለች። ስለዝግጅቱ የተለያዩ ግምቶች ተሰጥተዋል። እውነት መስሎ የሚታየው ከዚህ የሚከተለው ነው።

ጠመንጃ...	782,390
ሞተረየስ	23,251
መድፍ	2,608
ታንክና መኪና	25,980
ጥይት በያይነቱ	1,281,816,100
የጭነት እንስሳት	162,790
የመድፍ ጥይት	7,600,000
አይሮፕላን	500
መኪናና ሞተር ሳይክል	6,500
የሆስፒታል መርከቦች	8

ትክክለኛ ቁጥሩ ገና ያልታወቀ ቢሆንም፣ በእጅ የሚወረወርና ከአይሮፕላን የሚጣል ቦምብ፣ እንዲሁም ግምቱ ያልታወቀ በአይሮፕላን የሚረጭ የጋዝና የኤፐሪት መርዝ አቅርባለች።

የሰው ኃይልን በተመለከተ የነበረውም ዝግጅት እንደዚሁ ከባድ ነበር።

የጦር መኮንኖች	25,000
እግረኛ ወታደር	509,700
የመንገድ ሠራተኞች	50,000

መምህራን/ለኢጣልያን ልጆች/ . 12,000
ጋዜጠኞች 3,000
ሰላዮች በብዛት አሠማራች::[2]

በ15 እና በ55 ዓመት የዕድሜ ክልል ያሉ ጣልያናውያን ሁሉ በወታደርነት እንዲያገለግሉ አወጀች:: ይህ ለዋናው ጦርነት ያቀረበችው ሲሆን ኢትዮጵያን ከያዘች በኋላ ደግሞ ከሀገር ተወላጅ ባንዳ እየመለመለች የአጫጭር ጊዜ ሥልጠና በመስጠት ጨምራበታለች::

የኢትዮጵያ ጦር ጀሌውንም ጨምሮ 700,000 ይገመታል:: ከዚሁ ውስጥ የጦር ልብስ ለብሶ ደህና የጦር መሣሪያ የጨበጠው ከ25,000 አይበልጥም:: 200 መድፍ 50 ኦርሊኮን/ፀረ አይሮፕላን/፣ 3500 መትረየስ፣ 15 ትንንሽ አይሮፕላኖች እንደነበሩ ይገመታል::[3]

የጦርነቱ አሰመቅረት እየታወቀ ሲሄድ፣ የገነት የጦር ትምህርት ቤት ተቋቋመ:: አንድ መቶ ሃምሳ ያህል ወጣቶች ትምህርት ጀመሩ፣ አስተማሪዎች ሲዊዲኖች ነበሩ:: የስዊድን አልጋ ወራሽ ልዑል ጉስታፍ አዶልፍ ኢትዮጵያን በጉብኙ ጊዜ በተደረገ ንግግር መሠረት የመጡ ነበሩ:: ሥልጠና ከጀመሩት ወጣቶች 105ቱ በጥር ወር 1928 ዓ.ም በመቶ አልቅነት ተመረቁ:: በጦሩ ውስጥ ገብተው እንዲያዋጉ ቢታሰብ እንግሊዝ አዲስ አበባን ይጠብቁ የሚል ሀሳብ አቀረበች:: ወጣቶቹ ከጦር ግንባር እንገባለን አሉ:: ምክር ተደርጉ በሩን እንዲከላከሉ ተወሰነ::[4]

በኢትዮጵያ በኩል የጦር መሣሪያ ለመግዛት መከራ ተደረገ:: ሃያ አምስት ሣጥኖች ከሐምበርግ ከተማ ተጭነው ለንጉሠ ነገሥቱ እንዲደርሱ ተላኩ:: ሰባት ሚሊዮን ጥይት፣ 2,850 ከባድ መሣሪያዎች፣ 1,400 ጠመንጃዎች የያዙ ነበሩ:: ዋጋቸውም የተከፈለባቸው ነበሩ:: ሆኖም ለኢትዮጵያ መንግሥት የጦር መሣሪያ እንዳይገባ በፈረንሣይ መንግሥት ስለተከለከለ፣ ክሺቡቲ ወደብ ከደረሱ በኋላ ታገዱ:: የወደቡ ሠራተኞች "ሠነዱ አልተሟላም" የማለት ሐሳብ ፈጠሩ:: እዚህ ላይ "ጦርነት በተነሣ ጊዜ ኢትዮጵያ ወታደሮችዋንም ሆነ የጦር መሣሪያዋን ያለምንም ዋጋ የባቡሩ ድርጅቱ እንዲያመላልስ ተወስኖአል" የሚለው የአፄ ምኒልክ ስምምነት ከውል አልተቆጠረም::

ለታሪክ ማስታወሻነቱ ጭምር ሳይጠቀስ ሊታለፍ የማይገባው ጉዳይ:- የጣልያን ግልጽ ወረራ ከመጀመሩ ወደ አንድ ዓመት አስቀድሞ በንጉሠ ነገሥቱ በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ትዕዛዝ፣ ሀገሩ ሁሉ ለመከላከሉ ተግባር መዋጮ ታዝዞ ነበር:: የተሰበሰበው ገንዘብ መጠን ባይታወቅም፣ በየባለቤቱ አንድ አንድ ጠገራ ቅማርትሬዛ ብር መዋጣቱ ግን እርግጥ ነው:: ሁኔታው ግን «ሰርገኛ መጣ፣ በርበሬ ቀንጥሱ» ያስባለ ሆኗል::

ኢጣልያ ግን፣ የኢትዮጵያ አቤቱታ እንዳይሰማ የዓለምን ጆሮ ስለደፈነች፣ መሣሪያም እንዳታገኝ የአውሮፖን መንግሥታት ከአስተባበረች በኋላ ጦርነቱን ከፈተች:: ሙሶሊኒም "... ከኢትዮጵያ ጋር ያለኝን ያሁኑንም ሆነ ያለፈውን ቂሜን መበቀል አለብኝ" ብሎ በገሀድ ዛተ:: ይህንንም ብሎ ለላማዊቱን ኢትዮጵያ መስከረም 21 ቀን 1928 ዓ.ም በይፋ ወረረ::

ቀዳማዊ ኃይለሥላሴም በበኩላቸው በማግስቱ መስከረም 22 ቀን የክተት አዋጅ አስነገሩ:: አሥራ አንድ ነጥብ ያለው የጦር መመሪያም ሰጡ::[5]

እዚህ ላይ ለአንባቢያን ላስገነዝብ የምወደው፣ እስከ ሚያዝያ 1937 ዓ.ም ድረስ ዓለምን የለበለበው ሁለተኛው የዓለም ጦርነት በዚሁ ሁኔታ መጀመሩን ነው:: ዓለም ይኸንን ማመን አይወድም:: ነገር ግን ሁለተኛው የዓለም ጦርነት፣ የኢትዮጵያ ድንበር ወልወል ላይ በከንቱ በተደፈረ ጊዜ መከፈቱ የማይታበል የታሪክ ሐቅ ነው::

ማጣቀሻ ፅሑፎች

1. የማስታወቂያ ሚኒስቴር፣ *የኢትዮጵያ የድል መታሰቢያ 23ኛ ዓመት*፣ ገጽ 11::
2. ጳውሎስ ኞኞ፣ *የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦርነት*፣ ገጽ 34-6::
3. ማስታወቂያ ሚኒስቴር፣ ገጽ 62::
4. በኩሎኔል ገብራይ ገብረአግዚአ ለፀሐፊው ተነገረ::
5. *ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፣ ሕይወቱና የኢትዮጵያ አርምጃ ፣1ኛ መጽሐፍ*፣ ገጽ 189-97::

ምዕራፍ ስድስት
የአድዋና የአክሱም መያዝ

በኢትዮጵያና በኢጣልያ መካከል ለተካሄደው ጦርነት፣ አድዋ ታላቅ ሐውልት ነው። ሙሶሊኒ የጣልያኖችን ልቦና ወደ ጦርነቱ ለማስገባት የቻለው፣ ስለ 1888ቱ አድዋ የነበራቸውን ውስጣዊ ስሜት በነገር በመኰርኰር ነበር። ስለዚህ በ1928 ዓ.ም ጦርነት የአድዋ ተመልሶ መያዝ በጣልያኖች ዘንድ ልዩ የታሪክ ክብር ነበረው።[1]

ይህ ስሜት በኢትዮጵያ ዘንድ የታወቀ ስለነበረ፣ የመከላከያ ሥልት ተሠራ። በቀኛዝማች /ደጃዝማች/ ዓባይ ካሣ የሚመራው አንድ የጦር ክፍል ሰንሰለታማ ጉድጓድ /ትረንች/ በመቆፈርና ለጠላት እንዳይታይ ቅጠላ ቅጠል በማልበስ፣ በታንክና በተሽከርካሪ የሚደረገውን ወረራ ለመከላከል ተዘጋጀ። መስከረም 18 ቀን 1928 ዓ.ም ሌሊት ጠላት መንቀሳቀሱ እንደተሰማ ራማ ላይ መንገዱን በመዝጋት አገዱት። የጦሩ መሪ የነበረው ዶክተር ፍራንካ ተይዞ ወደ መጣበት እንዲመለስ ተደረገ። ቀኛዝማች ዓባይ ካሣ የፊታውራሪነት ማዕረግ ተሰጣቸው።

ጣልያኖች ከሽምብቆ እስከ ዛላአንበሳ ያለውን ግንባር በአግረኛ፣ በመድፍና በታንክ በማጥቃትና በአይሮፕላን በማስደብደብ መስከረም 21 ቀን 1928 ዓ.ም ወረራ ከፈቱ። በማግስቱ መስከረም 22 ቀን ኃይላቸውን አጠናክረው ወረራውን አፋፋሙ።[2] በመጀመሪያው እንቅስቃሴያቸው መስከረም 25 ቀን 1928 ዓ.ም አዲግራትን ይዘው፣ ወዲያው መንገድ እየሠሩ ወደ አድዋ አመሩ። ጦሩና ለዚሁ ሥራ የመጡት ባለሙያዎች መንገድ ሲሰሩ፣ የኢጣልያ አይሮፕላኖች አድዋ ከተማ ላይ እያንዣበቡ የስብከት ወረቀት በተኑ። ኢትዮጵያውያንም ፀረ አይሮፕላን ጥይትና መትረየስ በመተኮስ ተከላከሉ። ነገር ግን ውጤት አላገኙም። ሕዝቡ በፍርሃት ከተማዋን ለቅቆ ወጣ።[3]

የኢጣልያን ወታደር የአድዋን ከተማ ለመያዝ ተጠጋ። የኢትዮጵያም ወታደር ተከላከለ። ሠላሣ ጣልያናውያንን ገድሎ ሌሎች 70 አቆሰለ። ሌሎች 33 ጣልያናውያን የደረሱበት ጠፋ። ይሁን እንጂ የ84ኛው ሬጅሜንት 2ኛ ብርጌድ መስከረም 26 ቀን 1928 ዓ.ም የአድዋን ከተማ ያዘ። የዚህች ከተማ መያዝ እንደሌሎች ከተሞች አያያዝ ተራ ነገር አልነበረም። የሦስተኛ አየር ኃይል አዛዥ ጀነራል ራንዛ የአድዋን መያዝ ለደቦኖ በቴሌግራም አስታወቀ። ደቦኖም በተራው ለሙሶሊኒ "..ኢጣልያኖች በኩራት አድዋ ገቡ" ብሎ አስተላለፈ። በሮማ ከተማና በኢጣልያ ወታደሮች ዘንድ ታላቅ ደስታ ሆነ።

ይህ ብቻ አልነበረም። ጣልያኖች ኢትዮጵያን ለመውጋት ሲያስቡ፣ ወታደር ተዘጋጅቶ ሲጓጓዝ ከሮማ ድረስ አብሮ የመጣ፣ በ1888 ዓ.ም በተደረገው የአድዋ ጦርነት ለወደቁት ኢጣልያውያን መታሰቢያ የዕብነ-በረድ ሐውልት፣ በሙሶሊኒ ልዩ ትዕዛዝ በከተማይቱ መካከል ተተክሰ፣ በጀኔራል ደቦኖ በራሱ ተመረቀ።[4]

በጣልያኖች ዘንድ ሌላው አሳሳቢ ቦታ አክሱም ነበር። በእንግሊዝ አቀነባባሪነት ለንጉሠ ነገሥቱ የቀረበው የዕርቅ ሐሳብ ኢትዮጵያ የአክሱምን ቤተክርስቲያን ወደ ራስዋ እንድታደርግ የሚል ነበር። ልክ በውጫሌ ውል አዜ ምኒልክ ደብረ ቢዘንን ወደራሳቸው እንደአደረጉ። የዚህን ቅዱስ ቦታ የኢትዮጵያነት ብዙ መንግሥታት ለዓለም ማህበር ስለአስታወቁና የፊረንሣይ ጋዜጦችም ለሕዝብ በይፋ ስለገለጹ፣ ሙሶሊኒ ለባዶልዮ ማስጠንቀቂያ አስተላለፈ። በምስጢር የጻፈው ቴሌግራም "...ይህ /የአክሱም/ ገዳማዊ ቀበሌ በብርቱ ጥንቃቄ መጠበቅ እንዳለበት እንድታውቀው ነው" የሚል ነበር።

ነገር ግን ባዶልዮ ለዚህ ቴሌግራም በሰጠው መልስ "የአክሱም ገዳም... የኢትዮጵያዊነቱን ክፍል እንደያዘ መቆየት አለበት የተባለውን የውጭ መንግሥታት ሐሳብ ከምንም አልቆጥረውም..." አለ። ሙሶሊኒም "... የአክሱምን ካህናትና መነኩሳት ጠይቀህ ... በኢጣልያን ንጉሣዊ ዙፋን ሥር እንተዳደራለን የሚሉ እንደሆነም.. እያንዳንዳቸውን በጽሑፍ አስፍረህ ቃል የገቡበትን ወደ እኔ እንድትልክልኝ" የሚል ትዕዛዝ አስተላለፈለት።[5] ነገር ግን ምንም ምላሽ ሳያገኝ ቀረ። እዚህ ላይ ሙሶሊኒ የተመለከተው የራሱን ኃይል ብርታት እንጂ፣ የአክሱምን ካህናትና መነኩሳት ልቡና ጥንካሬ ከግምት አላስገባም ነበር።

በዚህ ዓይነት የጣልያን ጦር አክሱም ገባ። የኢትዮጵያም ጦር የቦታውን ቅድስና ለመጠበቅ ሲል አልተከላከለም። በመሆኑም የአክሱም ቤተመቅደስ ጉዳት ሳይደርስበት ቀረ።

ማጣቀሻ ፅሑፎች

1. ተክለፃድቅ መኩሪያ፣ *የኢትዮጵያ ታሪክ አዜ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ*፣ ገጽ 239።
2. ደጃዝማች ዓባይ ካሣ፣ የሕይወት ታሪክ፣ ከደግኖች ማህበር ጽሕፈት ቤት አዲስ አበባ።
3. ጳውሎስ ኞኞ፣ *የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦርነት*፣ ገጽ 70።
4. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 71።
5. ሞገስ ክፍሌ፣ *የሞሶሉኒ ምስጢር* ፣ገጽ 62-63።

ምዕራፍ ሰባት

የኢትዮጵያ ሠራዊት የክተት እንቅስቃሴ

የክተት አዋጅ መስከረም 22፣ 1928 ዓ.ም እንደተሰማ የኢትዮጵያ ሕዝብ ታላቅ ሥጋት ወደቀበት። አብዛኛው የገጠር ሕዝብ መሪዎቹን እያውቅም። በሚያውቃቸው በጥቂቶቹም ላይ እምነት አላደረበትም። ነገር ግን የእናት ሀገር ጥሪ ነውና ተንቀሳቀሰ። አንካሴውን አሾለ፣ ጦሩን፣ ጉራዴውን፣ ሰይፉን ሣለ። የጋሻውን ጥቀርሻ አራገፈ። ጉራዴ፣ ጩቤ፣ ሴንጢ ፣ ዱላና ዘንግ በብዙዎቹ እጅ ይታይ ነበር። ጠመንጃ ያለው የታደለ ነው። ካሉት ጠመንጃዎች የሚበዛው ናስማስር፣ ሰናድር፣ መስኩብና ሹልኪት ሰናድር ነበር። መውዜርና ለበን ብርቅ ናቸው። ከተዘረዘሩት ጠመንጃዎች ደግሞ ከለበን በስተቀር ሌሎች ሁሉ ጭሰማ ናቸው። ይግላሉ ቀለሀቸው በውስጣቸው ይጮረዳል። አንዳንዶቹም ወደኋላቸው ባሩድ ስለሚሸኑና የተካሹን ዓይን ስለሚያጠፋ አያስተማምኑም። አብዛኞች በቂ ጥይትም የላቸውም። ሃያና ሠላሣ ጥይት ያለው ጉበዝ ነው። ከዚህም ውስጥ መሣሪያውን ለመሞከር፣ ዓይኑን ለማጥራት፣ ለዘመቻው ከቤቱ ሲወጣ ቤተሰቡን ለመሰናበት ይተኩስለታል። "ግድ የለም መሣሪያ ከዚያው ይገኛል" ይላል። ከጠላቱ የሚነጥቅበትን መንገድ ያሰላስላል።

ሴቱ ስንቅ ያዘጋጃል። ለቅርብ ጊዜ የሚሆን ጭብጦ፣ ጢብኛ ይጋገራል። ለሩቅ ጊዜ የሚሆን ቆሎ ይቆላል፣ ዳቦቆሎ ይቆርጣል። ከተቻለው ቤት ደግሞ የማር ወይም የቅቤ ጭኮ ይዘጋጃል። ሰሊጥና ኑግ ይለጠለጣል። ለመያዣ ደግሞ ስልቻና ቅል አስፈላጊ ነገሮች ናቸው።

ሌላው ጉዳይ ሰንዞ የሚረዱ እንስሳት ማዘጋጀት ነው። ሰዕቃ መጫኛ ከሁሉም አስተማማኙ ወደል አህያ ነው። ከጠፋ፣ እርጉዝ ከአልሆነች፣ ሌትዋም ትጫናለች። የተቻለው የበቅሎ፣ ካልተገኘም የፈረስ አጋሰስ ያዘጋጃል። የተቻለው የጭን በቅሎና ፈረስ ይኖረዋል። የበቅሎና የፈረስ ዕቃም ይዘጋጃል። ልጓምና እርካብ አስተማማኝነቱ ይረጋገጣል።

በዚህ ዓይነት የተዘጋጀው ሠራዊት ሚስቱን ልጆቹን እየተወ፣ ወላጆቹንና ዘመድ ወዳጆቹን እየተሰናበተ፣ ቤተሰብ የሌለው ጐጆውን እየዘጋ ተነሣ። መንገዱ ሁሉ ቀረርቶ ፉከራ ሆነ። አብዛኛው ወደ ሰሜን ሌላው ደግሞ ወደ አጋዴን ዘመተ። እጅግ የተፈራው የአጋዴን ግንባር ነበር። ወደዚህ ግንባር ለሚዘምተው ሠራዊት የአዳል ጫማ አስፈላጊ ነበር።

ከዚህ ዓይነት ዝግጅት በኋላ ሠራዊቱ ዘመተ። አዲሱ የጦር ሥልት በገጠር ገና አልታወቀም ነበርና፣ የዘመተውም እንደየመሬቱ ደንብ

ነበር። ጥንት የመሬቱ ሥሪት ግንደበል፣ ፋና ወጊ፣ ውሃ ስንቁ፣ ደስታ ተካይ፣ ጠመንጃ ያዥ፣ የቅስና፣ የድቁና፣ የአወዳሽ፣ የገበዝና የመሪጌትነቱ ነበር። የሀገር ጉዳይ ነውና ሁሉም መዝመት አልቀረለትም። ዱማ፣ ሚጥቃሹም፣ ምስለኔ፣ መልከኛ አዝማች ሆነ። ከከተማ የሚንቀሳቀሰው ዘማች ከገጠሩ ዘማች የተሻለ አቅም ነበረው። ቢያምንበትም፣ ባያምንበትም አለቃውን ያውቃል። አብዛኛው የሆነ ዓይነት ጠመንጃና ጥይት አለው። ስለጦርነቱም አንዳንድ ሁኔታዎችን ይረዳል። ሁሉም በየታዘዘበት ጉዳው ቀጠለ።[1] ዘማች ከሄደ በኋላ ሀገር ባዶ ሆነ። ሴት፣ ሽማግሌና ልጅ ብቻ ቀረ። በአብዛኛው የገጠር ቤተሰብ የሚበላው ጥሬ፣ የሚጠጣው ውሃ፣ የሚተኛው ከመሬት ሆነ። ሀዘኑ ከባድ ነበር። ለምሳሌ ቡልጋ አመየት ሀገር በተባለው ቦታ፤ አፀደ ወልደጊዮርጊስ የምትባል ሴት ነበረች። ባልዋ አቶ አበበ ከማይጨው ሲመለስ መቀነትዋ ከወገብዋ ተጣብቆ አልፈታም አሳት። ልጠም አቆሰላት።

አዝማቾች በንጉሠ ነገሥቱ ተሾሙ። ለዋናው የሰሜን ጦር ግንባር ራስ ሙሉጌታ ይገዙ ተሾሙ። ራስ እምሩ ለጐጃም ለጐንደር፣ ራስ ካሣ ለወሎ፣ ራስ ስዩም ለትግራይ ጦር አዛገቦች ሆኑ። ለደቡብ ምሥራቅ ራስ ደስታ ዳምጠው፣ በሐረርጌ በኩል ደግሞ ደጃዝማች ነሲቡ ዘአማኑኤል ተመደቡ።

የንጉሠ ነገሥቱን አመኔታ ያላገኙ በጦርነቱ ውስጥ የመሳተፍ እድል አላገኙም። ራስ ብሩ ወልደገብርኤል ቦታ አልተሰጣቸውም። የወሰው ደጃዝማች በላይ ለመዝመት ቢጠይቁ አልተፈቀደላቸውም። ደጃዝማች አውራሪስ ዱሉ ታስረው እጃቸው ለደጃዝማች ብሩ ተሰጠ።

ሠራዊቱ ወደየጦሩ ግንባር ከመግባቱ በፊት በዋና ዋና ቦታዎች ተሰበሰበ። የትግሬ ጦር እዚያው እደጁ ገጠመ። የጐጃምና የጐንደር በዚያው በኩል ወደሰሜን ዘመተ። የከምባታ ጦር ጥቅምት 1 ቀን 1928 ዓ.ም አዲስ አበባ ገባ። የወለጋ፣ የከፋ፣ የኮንታ፣ የጐሬ ጦር በየአለቃው ኩተተ። ታላቅ ሰልፍ አሳየ። እንደአሸው የሚራመድ እንጂ እንደአውሮፖ ጦር እግሩን አስተባብሮ በህብረት የሚረግጥ አልነበረም። ልብሱም፣ መሣሪያውም፣ አሰላለፉም የተዘበራረቀ ነበር። የጦሩ አዲስ አበባ መሰብሰብ ታላቅ መጨናነቅ ፈጠረ። ሰጠላት ሰላዮችምላያመቻቸው አልቀረም። ሰልፉ ቀርቶ በየአቅጣጫው ቢዘምት በቀለለ ነበር።

ንጉሠ ነገሥቱ ጦሩን ከአሰናበቱና የአጋዴንን ጦር አስከ ጅጅጋ ድረስ በአይሮፕላን ሄደው ከጉበኙ በኋላ፤ ሀዳር 18 ቀን 1928 ዓ.ም ንብላቸውን ወደ ሰሜን ጦር ግንባር ቀጠሉ። ከአዲስ አበባ በአውቶሞቢል ተጉዘው ሀዳር 21 ቀን ደሴ ገቡ።[1] የተጓዙትም የልጅ አያሱን ዕረፍት

በአዲስ አበባ ከተማ ለነበሩት መኪንንትና ወይዛዝርት አርድተው በይፋ ከተሰቀሰ በኋላ በመሆኑ ቀላል አልነበረም።

ወደ ደቡብ ምሥራቅ የዘመተው ጦር ከጋሞጉፋ በአርሲ፣ በሲዳሞ፣ በቦረናና በባሌ በኩል ወደ ደሎ ወረደ። ከሐረርጌ የዘመተው በጅጅጋና በደገሐቡር በኩል አስቀድሞ በመገስገስ፣ በአጋዴን ለነበረው ጦር ድጋፍ ለመስጠት ተዘጋጀ። ይህ ጦር በሌሎች ጉራዎች ከተሰለፉት ጦሮች ሁሉ ጥራትና ብቃት ነበረው።

ንጉሠ ነገሥቱ በደሴ ከተማ እንደአሉ በአንዳንድ ሁኔታዎች ላይ አዳዲስ ገጽታዎች መታዬት ጀመረ። የትግራዩ መሥፍን ደጃዝማች ኃይለሥላሴ ጉግሣ ኢትዮጵያን ከድቶ ከጣልያን ጐን ቆመ። አሱም ከመቀሌ ተነስቶ 1200 የታጠቁ ወታደሮችና መትረየሶች ይዞ አዲግራት ገባ። ከዚያም አሥመራ ደረሰ። በኢትዮጵያ ወገን ለጦርነቱ የተደረገውን ዝግጅት ለጣልያን አስረዳ። ከአዲስ አበባ እስከ ደሴ የተሠራውን መንገድ ጠቆመ።[2] የጉጃም ጦር በደጃዝማች ገሠሠ በለው እና በፊታውራሪ ታምራት አስተባባሪነት ጦርነቱን ወደ ኋላው ትቶ ወደ ቤቱ ተመለሰ። የንጉሠ ነገሥቱ አዋጅ፣ የጳጳሱ ግዝት አላገደውም። በዚህ ላይ የአጋዴኑ ግንባር መላላቱ ተሰማ።

ሁኔታው በዚህ እንዳለ ለመጨረሻ ፍልሚያ የተፋጠጡት ሁለቱ መሪዎች ሹም ሽር አደረጉ። ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የጦር ሚኒስትራቸውን ራስ ሙሉጌታን ሽረው ራስ ካሣን ሾሙ።[3] ሙሶሊኒም በበኩሉ ጄነራል ደቦኖን ሽሮ ጄነራል ባዶሊዮን ሾመ። ይህ የሹመት አሰጣጥ በኢትዮጵያ ሠራዊት ውስጥ ተጨማሪ ድንግርግርን ሲፈጥር፣ በጣልያ ወገን ግን ይበልጥ ቁርጠኛ አልፎ ተርፎም ጨካኝ መሆንን አስገኘ።

የዓለም ቀይ መስቀል የጦሩን አሰላለፍ ተከትሎ ዕርዳታ ለመስጠት በኢትዮጵያ ወገን ገባ። ሥራውን ለማስተባበርና ለመርዳት የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ሐምሌ 1 ቀን 1927 ዓ.ም ተቋቋመ። በሰሜን የጦር ግንባር የእንግሊዝ፣ የኑምሣ /ማለትም የኦስትሪያ/፣ የሆላንድ፣ የፊረንሣይ ቀይ መስቀሎች ገቡ። ከዚህም በስተቀር የግብፅ በጅጅጋ፣ የሰዊድን ደግሞ በቦረና ተሰማሩ።[4]

የኢትዮጵያን ሠራዊት ሥርዓት ለማስያዝና የውጊያ ሥርዓት ለማስለመድ ተሞክረ። የጦር ዕቅድ አውጭዎች የውጭ ሀገር ሰዎች ነበሩ። ንጉሠ ነገሥቱ የሌላ ስው ምክር አልተቀበሉም። ኢትዮጵያውያኑ አዛዦችም ለሚያሰለጥኑት ሠራዊት የሚናገሩት ቃል በፊረንጅ ሥርዓት ነበር። ተሠሰፍ፣ አርገጥ፣ ከመሬት ላይ ተንደባለል፣ ልብስህን ከል ንክር ይሉታል። ነገር ግን ስለስንቱ፣ ስለጤንነቱ የሚያስብለት የለም። ለአራሱ

አስፈላጊውን ማድረግ አለበት። ነገሩ አልጣመውም። ቢሆንም ጉዞውን ተጠበለ።[5]



የኢትዮጵያ ሀዝብ በየአካባቢው ለአይቀሬው ጦርነት ከተት ጀመረ።

ማጣቀሻ ዕሑፎች

1. ተክለፃድቅ መኩሪያ፣ *የኢትዮጵያ ታሪክ ከአፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀ.ኃ.ሥ*፣ ገጽ 215-221።
2. ጳውሎስ ኞኞ፣ *የኢትዮጵያና የጂጣልያ ጦርነት*፣ ገጽ 52-4።
3. Leonard Mosley, *Haile Selassie*, PP.200-8
4. ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፣ *ሕይወቴና የኢትዮጵያ አርዎጃ 1ኛ መጽሐፍ*፣ ገጽ 175።
5. ከአለቃ ወንድም አገኘሁ ለጸሐፊው የተነገረ፡



የኢትዮጵያ ህዝብ በየአካባቢው ለአይቀሬው ጦርነት ክተት ጀመረ፡፡

ምዕራፍ ስምንት
የሽሬ ጦር ግንባር

ሌላው የሰሜን ጦር ግንባር ሽሬ ነበር። በዚህ ግንባር ጦርነቱ ህዳር 1 ቀን 1928 ዓ.ም ተከፈተ። በየቦታው ልዩ ልዩ ጦርነቶች ተካሄዱ።

የኢትዮጵያ ጦር የተሰለፈው በራስ እምሩ ኃይለሥላሴ አዝማችነት ነበር። ጦሩም የጐጃምና የጐንደር ሠራዊት ሲሆን፤ ብዛቱ እስከ ሃያ አምስት ሺህ ተገምቶአል። ከሌላው የኢትዮጵያ ጦር የሚለየው ከቦታው ቅርበት የተነሳ በመንገድ ላይ ብዙ ቅጥቃጤ ያልደረሰበት መሆኑ ነው። እንደተገለፀው በእነ ደጃዝማች ገሠሠ የሚመራው የጐጃም ጦር ቀደም ብሎ ሳይዋጋ ወደ ሀገሩ ተመልሷል፤ ይህ ጦር ግን ልቡ ሳይላላ የሀገር መከላከል ሥራውን እስከ መጨረሻው አካሄደ።

እያንዳንዱ ሽንተረር፣ ተራራ፣ ወንዝና ሸለቆ የጦር አውድማ ሆነ። ሁሉን መዘርዘር ስለሚያስቸግር ዋና ዋናዎቹን እንመለከታለን። ደምበጉና በተባለው ቦታ የነበረውን የጠላት ጦር፤ የኢትዮጵያ ሠራዊት ከብቦ ደጋግሞ በመውጋት አስጨነቀው። ባዶሊዮ በታንክ የተደገፈ አዳዲስ ጦር ቢልክም የኢትዮጵያ ጦር አልተበገረም። ታህሣሥ 7 ቀን 1928 ዓ.ም በተደረገው ውጊያ ከኢጣልያ ወገን ዘጠኝ መኮንኖች፣ 22 ነጭና 370 ጥቁር ወታደሮች ሞቱ። ከዚህም በስተቀር ብዙ ጣልያኖች ከአሥር ታንክና ከሁለት መድፍ ጋር ተማረኩ። ከአልቂትና ከምርኮ፣ ከመቁሰል የተረፈው የጠላት ጦር በአንድ ወገን ከበባውን ሰብሮ አመለጠ። የኢትዮጵያ ጦር እስከ አቢይ አዲ፣ እስከ ሰለክላካ ድረስ አያባረረ ወጋው ::[1]

እንደገና አምባ ደስሬ በተባለው ቦታ በታህሣሥ 13 ቀን 1928 ዓ.ም ውጊያ ተካሄደ። ጠላት የኢትዮጵያን ጦር መቋቋም ስለአቃተው ቦታውን ለቅቆ ወደ አፍጋጋ ሸሸ። በፊት እንዳባተና፣ በኋላ ደግሞ ደስሬ ላይ የደረሰባቸው ሽንፈት ጣልያኖችን አስደነገጣቸው። አድዋ እንዳይደገም ሠጉ። ባዶሊዮ ተሸሮ ግራዚያኒ እንዲተካ ለመሶሊኒ ሐሳብ ቀረበ። በጦር ሚኒስትሩ ብርታት ባዶሊዮ ከመሻር ዳነ። ባዶሊዮ ይህንን እንደሰማ ይበልጥ ጨከነ። አካባቢውን መርዝ አስረጨበት። እንደ እሳት በሚያቃጥለው መርዝ ብዙ ሰው አለቀ፤ ብዙ ሰው ቆሰለ።

ራስ እምሩ ከሞት የተረፈው ሠራዊት ማይላህላ ተዛውሮ እንዲከት አደረጉ። እሳቸውም ጦሩ እስኪሰበሰብ በደፈጣ ቆዩ። ጦሩ ተሰበሰበ፤ ገና ለውጊያ ያልደረሰው ጦር ገባ። ራስ ካሣ ድል ሆነው ወደ ኋላ

መመለሳቸው ተሰማ። ምክር ተደረገ። "ከሚያቃጥልና ከሚገድል ዝናም ጋር ሰው እንደምን ይዋጋል" የሚል ጥያቄ ተነሣ። ጉዳቱን ለመቀነስ የሚያስችል ሥልት ተቀየሰ። ሰማማ፣ ማይላህላ እና ሰለክላካ የመሸገው ሃያ ሺህ ደጀን ጦር እንደገና ተከዜ ላይ እንዲቆይ ተወሰነ። በኢጣልያም በኩል ዝግጅት ተደረገ። በጀነራል ማራሻኛ የሚመራው ሁለተኛው ክፍለ ጦርና በጀነራል ሣቢኒ የሚታዘዘው አራተኛው ክፍለ ጦር በተጠንቀቅ ቆመ።

የካቲት 21 ቀን በጀነራል ማራሻኛ የሚመራው ሃያ ሺህ የጠላት ጦር ከአክሱም ወደ ሰለክላካ ጉዞ ጀመረ። ሰለክላካ ሸለቆ ውስጥ አድፍጦ ይጠባበቅ የነበረው የኢትዮጵያ ጦር የካቲት 21 ቀን፣ ቀትር ላይ ገጠመው። ውጊያው እስከ ሌሊት ድረስ ቆየ። የኢትዮጵያ ጀግና እየተወረወረ በመትረየሱ ላይ ተጠመጠመበት። መሣሪያ የተጫኑትን ካሚዮኖች ለመማረክ ሞከረ። ጣልያኖች ደግሞ ለማዳን በአይሮፕላን ቦምር ተከላከሉ። ታላቅ ጦርነት ተካሄደ። በአካባቢው ያለውን ኮረብታ ለመያዝ ያደረጉትን መከራ ኢትዮጵያውያኑ ተሸቀዳድመው በመያዝ አከሸፉባቸው። ጦርነቱ እስከ የካቲት 26 ቀን ድረስ ቀጠለ። ባዶሊዮ ስምንት ቶን የሚመዝን ቦምብ በአይሮፕላን ቢያወርድበትም የኢትዮጵያ ጦር አልተበገረም።[2]

የኢጣልያ ጦር ብዛት ነበረው። ተተኪ ኃይልም ተሳከለት። በአይሮፕላን ድጋፍ ተሰጠው። እንደ ንጉሠ ነገሥቱ አገላለጽ ከጣልያን ጦር ቆመው በርትተው የሚዋጉት የኤርትራ ወታደሮች ነበሩ እንጂ፣ ጥቁር ሸሚዝ ለባሾች ጣልያኖች ጥቂቶች ነበሩ። ኢጣልያኖች የሚሰለፉት ብጣም ርቀው በስተኋላ ስለነበር እነሱን ለማግኘት ብዙ ችግር ነበር።

በሽም አውሬ የተደረገውም ጦርነት በታሪክ ሊጠቀስ ይገባል። የእኛ ወታደሮች በተሰመደ ፈጣንነታቸው እንደ ነብር እየተወረወሩ በቦርነቱ መካከል ስለገቡ፤ የኢጣልያ ወታደሮች መትረየሳቸውንና ብሠመንጃቸውን ከነጥይቱ፤ እንደዚሁም ቴሌፎናቸውንና የሬዲዮ ማስተላለፊያ መኪናቸውን እየተው እስከ መሸሽ ደረሱ። የተማረከውን ሠሣሪያና ዕቃ ከኢትዮጵያውን የጦር ሠፈር ለማስገባት አራት ሙሉ ቀን ፈጀ።[3]

የኢትዮጵያ ጦር ቦታውን ሳይለቅ ጠንክሮ በመዋጉ፤ ባዶሊዮ መላው የተከዜ አካባቢ በቦምብ እንዲደበደብና መርዝ እንዲረጭበት አደረገ። የተከዜ አካባቢ በሙሉ በራሣ ተሸፈነ። በዛ ቦታ ትግሉ ሊቀጥል አልቻለም። ራስ እምሩም የተረፉአቸውን 300 ያህል ወታደሮች ይዘው ወደ ጉንደር ተመለሱ።

የኢትዮጵያውያኑ ቁርጠኝነት አስገራሚ ነበር። ጣልያኖችን ራሳቸውን አስደንቆአቸዋል። ለማሰረጃ ያህል አንድ ሁኔታ መጥቀስ ይበቃል። በሰሜን ጦር ግንባር በየካቲት 21 እና 26 መካከል በተደረገው ጦርነት ጥቂት የኢትዮጵያ ወታደሮች ተማረኩ። የጦራቸውን ወሬ ቢጠየቁ አንናገርም አሉ። ምክንያቱን ቢጠየቁ ኢትዮጵያውያን እስከ መጨረሻው ሰው ድረስ እንደሚዋጉ፣ እነሱም ቢሰቀቁ ክንዳቸውን እስከሚንተራሱ ጊዜ ድረስ እንደሚፋለሙ አረጋገጡ። ይህም የመላው ኢትዮጵያዊ ሐሳብ መሆኑን ገለጹ።[4]

<u>ማጣቀሻ ፅሑፎች</u>

1. ተክለ ፃድቅ መኩሪያ፣ *የኢትዮጵያ ታሪክ ከአፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀ.ኃ.ሥ.*፣ ገጽ 245-246።
2. ጳውሎስ ኞኞ፣ *የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦርነት*፣ ገጽ 108-111።
3. ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፣ *ሕይወቴና የኢትዮጵያ አርምኛ 1ኛ መጽሐፍ*፣ ገጽ 223-224።
4. ጳውሎስ ኞኞ፣ ገጽ 110።

ምዕራፍ ዘጠኝ
የተንቤን ጦር ግንባር

በኢጣልያ በኩል ዋናው ግንባር የሰሜኑ ነበር። እሱም በመቶ አለቃ ሞርጋንቲኒ የተመራው የኢጣልያ ጦር ዳውሮ ተክሌ በተባለው ቦታ በኢትዮጵያ ጦር ላይ አደጋ በጣለ ጊዜ በይፋ ተከፈተ። ኢጣልያ ከመስከረም 21 ቀን ጀምሮ በአይሮፕላን የአድዋን ከተማና አካባቢውን ስትደበድብ ለንብታ ስለነበር ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴም መስከረም 22 ቀን አሞጅ ስለ አስነገሩ ሁኔታው ግልጽ ሆኖ ነበር።

ተጠንቅቆ ይጠባበቅ የነበረው የኢጣልያ ጦር በየግንባሩ በፍጥነት ተንቀሳቀሰ። መስከረም 25 ቀን አዲግራትን ይዞ ወደ እንቲጮና አድዋ የሚያደርሰውን የመኪና መንገድ መሥራት ጀመረ። በደጃዝማች ገብሬ የሚመራው የኢትዮጵያ ጦር በርትቶ ተከላከለ። ሠላሣ የጠላት ወታደሮች ገድሎ ሌሎች ሰባ አቆሰለ፣ ሌሎች ሠላሣ የደረሱበት ጠፋ። በዚህ ጦርነት ላይ የመጀመሪያውን ወራሪ ኢጣልያዊ መኮንን ገደሉ። ስሙም መቶ አለቃ ሞርጋዜር ነይ ይባል ነበር። ጠላትም በቦምብ መደብደብ ጀመረ። በዚያ የነበሩ የጣልያን ወታደሮች ቦታውን ለቅቀው ስለሸሹ፣ አዛገሮች አዲስ ጦር መተካት ነበረባቸው። ከሁለት ሰዓት ውጊያ በኋላ የኢትዮጵያ ጦር ትዕዛዝ ስለተላለፈለት ዳዕሮ ተክሌን ለቅቆ ወደ ጋሻ ወርቂ አፈገፈገ።

የጣልያን ጦር በአይሮፕላን ወረቀት በመላክ እየተለማመጠና እያስፈራራ፣ አካባቢውንም በቦምብ እየደበደበ ከ40 ዓመት በፊት የሀገሩ ክብር የተዋረደበትን የአድዋን ከተማ መስከረም 26 ቀን 1928 ዓ.ም ከጠዋቱ በአራት ሰዓት ያዘ። ሮም ተዘጋጅቶ የተላከው የዕብነበረድ ሃውልትም በፍጥነት ተተከለ።[1] ከኢትዮጵያውያን ዘንድ ሀዘን፣ በኢጣልያውያን ዘንድ ደስታ ሆነ።

በፀዲያ፣ በሐውዚን፣ በገርዓልታ፣ በኃይሌ የነበረው የኢትዮጵያ ሠራዊት ደግሞ በአቶ /ደጃዝማች/ ገብረሕይወት መሸሻ መሪነት፣ በጥቅምት 1928 ዓ.ም በቅድሚያ በእንዳ ማርያምና በአሸዊት፣ ቀጥሎም በሐመድና በአውገር፣ ከዚያም አፍካሮ በተባሉት ቦታዎች ላይ የሚያስደንቅ ውጊያ አካሄደ። ትግላቸውን በመቀጠል በህዳር ጉንዲ፣ በታህሣሥ ወር በዳዕሮና በደንገሌ፣ በመከፈል፣ በጥር ወር በሐውዜን ቆላ ታላላቅ ውጊያዎች አካሄዱ።

መረራው ተፋፋመ። ከፍ ሲል እንደ ተገለፀው ቅዱስ ቦታ መሆኑ በሁለቱም ወገን የታመነበት አክሱም እምብዛም ጦርነት ላይካሄድበት

ጥቅምት 3 ቀን 1928 ዓ.ም ተያዘ። ቀጣዩ የጣልያን ጦር ዓላማ የመቀሌን ከተማ መያዝ ሆነ። በደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሣና በግብረ አበሮቹ ምክርና ጠቋሚነት የጦርነቱ ሥልት ተቀነባበረ። የኢጣልያ ወጣት መሣፍንትና ምሑራን በልዩ ልዩ ሥራ እየተመደቡ ከሮም መንቀሳቀስ ጀመሩ። በአንፃሩ ደግሞ ብዙ ኤርትራውያን ወታደሮች ከጣልያን እየከዱ ከኢትዮጵያውያን ወንድሞቻቸው መቀላቀል ስለአመጡ፣ በኢጣልያ ዘንድ ሥጋት ተፈጠረ። ከሁኔታው አስደንጋጭነት የተነሣ ጥቁርና ነጭ ተቀላቅሎ እንዲዘምት የሚል አዲስ ትዕዛዝ መጣ።

በዚህ ዓይነት ከተዘጋጀ በኋላ የጣልያን ጦር መቀሌን ለመያዝ ጥቅምት 23 ቀን 1928 ዓ.ም ተንቀሳቀሰ። ጦሩ በሦስት ረድፍ የተከፈለ ነበር። ዕቅዱም ዋናው ጦር ከአዲግራት በመነሣት መሐል ለመሐል በመገዝ ምሽግ እንዲያዘጋጅ፣ ሁለተኛው በስተደቡብ እንዲገዙ፣ ሦስተኛው ደግሞ ከአድዋ ተነስቶ በሐውዜን በኩል አልፎ ሦስቱም ጦሮች መቀሌ እንዲገናኙ ነበር። ቢያስፈልግ ዕርዳታ ለመሰጠት እንዲችል ደግሞ ሌላ አራተኛ ጦር ከምፅዋ ተነስቶ በረሃውን በፍጥነት እንዲያቋርጥ ታዘዘ።[2]

የኢትዮጵያ ሠራዊት በሁሉም በር ተከላከለ። ከምፅዋ ተነስቶ በደንከል በረሃ የሚገዘውን የጠላት ጦር በየቦታው ወግቶ ስምንት ደንጉላ ፈረስና 13 በቅሎዎች ማረከበት። ሦስት መቶ ያህል የኤርትራ ተወላጆች ተገደሉ። ብዙ ኢጣልያውያንም ሞቱ። ጠላትም የአይሮፕላን ድጋፍ በመስጠት ወረራውን ቀጥሎ በደጃዝማች ኃይለሥላሴ ጉግሣ እየተመራ ሀዳር 1 ቀን 1928 ዓ.ም የመቀሌን ከተማ ያዘ።

የጦርነቱ ሂደት ከዚህ ላይ ሲደርስ ጄነራል ባዶሊዮ ማርሻል ተብሎ የአዛዥነቱን ሥልጣን ያዘ። ባዶሊዮ ሹመቱ እንደ ተሰጠው ከሮም ገስግሶ አሥመራ ገባ። የጦርነቱ ሥልት ተለወጠ። የቀድሞው አዛዥ ጄነራል ደቦኖ ጦርነቱን በእግር ጦር ተዋግቶ ማሸነፍ እንደሚቻል ያምን ነበር። በአይሮፕላን በሚጣል ቦምብ መደብደብ አስፈላጊ መስሎ አልታየውም ነበር። የኢጣልያን ስም የሚያጠፋ ሥራ እንዳይሠራ ምክር ይሰጥ ነበር። ከዚህም በስተቀር የኢትዮጵያ ጦር ፈጥኖ የሚያፈገፍገው፣ ከወጥመድ አስገብቶ ለማጥቃት ብሎ ሊሆን እንደሚችል ጠርጥሮ ወደፊት እንዲገፋ የሚደረግለትን ጉትጉታ አልተቀበለም ነበር። የተሻረውም በዚሁ ምክንያት ነበር።[3]

የማርሻል ባዶሊዮ አስተሳሰብ ከዚህ የተለየ ሆነ። ኢጣልያ ዳግማዊ አድዋ ቢደርስባት ሊጠገን የማይችል ውርደት እንደሚሆን ገባው። የጦርነቱ ጊዜ መውሰድ ኢጣልያን በዓለም ማህበር አደባባይ ቁጣ እያበራከተባት መሆኑ ታየው። ስለዚህ ባለው መሣሪያ መዋጋትና ቶሎ

ከነኣሜ ማድረስ ይሻላል ከሚል ድምዳሜ ላይ ደረሰ። ሞሶሎኒ በጦርነቱ ብዙ የደከመውን ደቦኖን ሽሮ እሱን የማርሻልነት ማዕረግ ሰጥቶ የሾመው በፈጨካኝነቱ ተማምኖ ስለነበረ አስተያየቱን ደገፈለት። በእጁ ባለው መሣሪያ ሁሉ እንዲጠቀም፣ ማለትም በቦምብ እንዲደበድብ፣ የጋዝ መርዝና ኢፕሪት በአይሮፕላን እንዲረጭ፣ ሙሉ ሥልጣን ተሰጠው።[4]

ጣልያኖች በተንቤን የጦር ግንባር በኩል ህዳር 27 ቀን 1928 ዓ.ም ውጊያ ከፈቱ። ጦራቸውም ከመቀሌ ተነስቶ ዋሪዮ በር የተባለውን ቦታ ያዘ። ከዚያም በራስ ሙሉጌታ ይመራ የነበረውን የኢትዮጵያን ጦር ለማጥቃት ወደ አምባላጌ ተጠጋ። በስተግራ በኩልም ወደ በለሳ ገፋ። ዙተንቤን ምድር ከባድ ጦርነት ተካሄደ። ከአራት ቀን ውጊያ በኋላ የኢትዮጵያ ሠራዊት አሸነፈ። የጠላት ጦር አፈገፈገ። በጣልያኖች በራሳቸው አመለካከት ጉራው ዳግማዊ አድዋን መሰለ። በራስ ካሣም፣ በራስ ስዩምም የሚመራው የኢትዮጵያ ጦር ታላቅ ጀብዱ ሠራ። ጠላት ከአይሮፕላን በሚጣል ቦምብ ቢደበድበውም፣ የመርዝ ጋዝ ቢረጭበትም አልተበገረም። ጦርነቱ እስከ ጥር ወር ዘለቀ። ከኢጣልያ ወገን 60 የጦር መኰንኖች፣ 605 ነጭ ወታደሮች፣ 417 የቅኝ ግዛት ወታደሮች ተገደሉ። ከኢትዮጵያም ጦር እስከ 8000 የሚገመት ወታደር ሞተ።[5]

ጠላት ባወጣው ዕቅድ መሠረት አንዱ የኢትዮጵያ ጦር ሌላውን እንዳይረዳ መንገዶችና በሮችን አስቀድሞ ዘጋ። ራስ ካሣና ራስ ሥዩም ተንቤን ሲከላከሉ፣ የራስ ሙሉጌታ ጦር እንዳይረዳቸው ደብር ነጋይዳን የተባለውን በር አስያዘ። ራስ እምሩ ከሽሬ እንዳይደርሱላቸው ደግሞ የአዲ ደናግልን መተላለፊያ ያዘ።

በሮችና መተላለፊያዎቹን በዚህ ዓይነት በጦር ካስያዘ በኋላ ጥር 14 ቀን 1928 ዓ.ም ዋሪዮ መልፋ ከተባለው ምሽግ ከጥዋቱ በ3 ሰዓት ወጥቶ ተንቀሳቀሰ። የኢትዮጵያ ሠራዊት ማይ መርታ የሚባለውን ወንዝ ያጠባበቅ ስለነበር፣ ዘጠን ቀርክሀታ ከተባለው ቦታ ላይ ከባድ ውጊያ ተካሄደ። ጦርነቱ ከተኩስ ወደ ጨበጣ ዞረ። ኢትዮጵያውያን በሚያውቁበት ዘዴ በሰይፍና በጉራዴ ጠላታቸውን ጨፈጨፉት። ጦርነቱ ከወላኝነት ደረጃ ላይ ሲደርስ የጣልያን አይሮፕላኖች ደርሰው ከጨበጣው ለመግባት የሚገደረደረውንና ደጀን ሆኖ የሚጠብቀውን የኢትዮጵያ ጦር በቦምብ ደበደቡት። ይህም ሆኖ ኢትዮጵያውያኑ አልተበገሩም። ጦርነቱ 3 መዓልትና 1 ሌሊት ፈጀ። ዓላማቸው ኢትዮጵያውያንን ከመቀሌና ከዙሪያው አስለቅቆ ለመግባት እንዲሁም ከግባ ወንዝ ወዲያ ለማባረር ነበር። አንዳቸውም ሳያሸንፉ ቀሩ። ከኢትዮጵያ ሠራዊት 1000 ሞተ፤

ሌላ 2000 ቆሰሉ። ከኢጣልያ ወገን 1500 ሞተ። ሁለቱም ሰልችተው ወደየሠፈራቸው ተመለሱ።

ከሀዲው ደጃዝማች ኃይለሥላሴ ጉግሣ የመቀሌን ደህንነት አስተማማኝ ለማድረግ የአምባሪዶም መያዝ አስፈላጊ መሆኑን ለባዶሊዮ አበክሮ ምክር አቅርቦ ነበርና፤ በጣልያኖች ወገን ዝግጅት ከተደረገ በኋላ የካቲት 30 ቀን ቀለሚኖ እና ገባ ከሚባሉት ቦታዎች ተንቀሳቀሱ። የኢትዮጵያ ሠራዊት ስለመከተ የካቲት 1 ቀን ታላቅ ጦርነት ተከፈተ። ሳያቋርጥ እስከ የካቲት 7 ቀን ድረስ ቀጠለ። በተለይ የካቲት 4 ቀን 1928 ዓ.ም ሌሊት የኢትዮጵያ ወታደሮች ከጠላት ሠፈር ገብተው የተቃና ሥራ ሠሩ። በዚህ ማታ የጣልያን ጦር አምባራዶም ግርጌ ደርሶ በእግርና በአየር ወረደበት። 40 ቶን በምብ በመጣል ደብድቦ ስለነበርና ብዙ ሠራዊት ስለአለቀ፣ ራስ ሙሉጌታ ወደ ኋላ ለማፈግፈግ ወሰኑ። ከአየሩ ድብደባ ለመሠወር ወደ አዘቦ በረሃ ወረዱ። ለአራት ቀን የኢጣልያ አይሮፕላኖች ሳያገኙአቸው ሰነበቱ። ባገኙአቸውም ጊዜ ድብደባቸውን ቀጠሉ።

በዚህ ጊዜ ከጉዞው ላይ የራስ ሙሉጌታ ልጅ ታጣ። እሳቸውም ልጃቸውን ለማፈላለግ ወደ ኋላ መልእክተኛ ላኩ። መሞቱን ሲሰሙ ደግሞ ደሙን እበቀላለሁ ብለው ወደ ኋላ ተመለሱ። ራስ ሙሉጌታ በጦር ሰልፍ እንደ አሉ ከጦር ሚኒስትርነት በመሻራቸው ልቦናቸው ሳይቆስል አልቀረም። የጦር ሚኒስትርነቱ ሥልጣን ከእሳቸው ተወስዶ ለራስ ካሣ የመሰጠቱ ምክንያት፣ ከዘር በስተቀር የችሎታ ሚዛን የተከተለ አለመሆኑ በሁሉም ዘንድ የታወቀ ስለነበረ፤ ቁስለቱ የመላው ሠራዊት እንጂ የእሳቸው ብቻ እንደአልነበረ መገመት አይዳግትም። ሽረታቸውም ለጠላት ጭምር አስደሳች ነበር። በአዲሱ ሹምሽር የተከዙት ራስ ሙሉጌታ በዚህ ዓይነት ከሠራዊታቸው ሲለዩ ለጠላት ጥቃት ስለተጋለጡ በጥይት ተመትተው ሞቱ። ጣልያኖች በአይሮፕላን ገደልን ይላሉ። በኢትዮጵያ ወገን የሚታመነው ግን በአዘቦ ከሀድያን እጅ እንደተገደሉ ነው።

እዚህ ላይ መጤን የሚገባው ጉዳይ በአንድ ከፍተኛ የጦር አዛዥነት የነበረባቸውን ከባድ ኃላፊነት ዘንግተው የአንድ ሰው ደም ለመበቀል ያደረጉት ሙከራ ስሕተት እንደነበረ ነው።

የኢትዮጵያ ልጆች ግን የአዛዡን ወደኋላ መመለስ ከምንም ሳይቆጥሩ የአምባራዶምን ተራራ መከላከሉን ቀጠሉ። በጦርነቱም ላይ የመጨረሻዎቹ ቆራጥ ጀግኖች ሊያልቁ፣ የካቲት 12 ቀን 1928 ዓ.ም ተፈፀመ። በዚህ ጦርነት ከኢጣልያ ወገን 36 መኰንኖች፣ 621 ነጭና 145 ጥቁር ወታደሮች ሞተዋል። ይህም የሚያሳየው የጥቁሮች ተሳትፎ

መጠነኛ እንደነበረ ነው። ከኢትዮጵያ ወገን የወደቁት እስከ 6000 እንደሚደርስ ተገምቶአል።

በሌላ በኩል ራስ ካሣና ራስ ሥዩም የጋራ ግንባር ፈጥረው በቀጨማ መልፋ የመከላከል ሥራቸውን ቀጠሉ። ጦርነቱም የካቲት 11 ቀን ተጀመረ። አንድ ጊዜ አንዱ፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ሌላው እያሸነፈ የ5 ቀን ውጊያ ተካሄደ። የኢጣልያ አይሮፕላኖች የበምብ ነጮድጓድ አወረዱ፤ የ*ጋዝ መርዝ አዘነመ*። እልቂቱ ከፍተኛ ሆነ። ጦርነቱ ሰው ከማስጨረስ በስተቀር ለኢትዮጵያ አንዳች ፋይዳ መስጠቱ ቀረ። ሁለቱ የጦር መሪዎች ከንጉሠ ነገሥቱ ጦር ጋር ሆነው መዋጋትን በመምረጥ ወደ ኋላ ተመለሱ። ደጃዝማች በየነና መሰሎቻቸው ጠላታችንን ከፊታችን አስቀምጠን ፊታችንን ወደ ኋላ እንመልስም በማለት ጉራዲያቸውን እየመዘዙ ከጠላት መካከል በመግባት ጠላታቸውን እየጨፈጨፉ በጀግንነት ወደቁ።[6] የተንቤን ጦርነት የካቲት 15 ቀን 1928 ዓ.ም እንዲህ ተፈፀመ።

ማጣቀሻ ፅሑፎች

1. ጳውሎስ ኞኞ፣ *የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦርነት*፣ ገጽ 10።
2. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 74።
3. ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፣ *ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ 1ኛ መጽሐፍ*፣ ገጽ 213።
4. ሞገስ ክፍሌ፣ *የምሶሎኒ ምስጢር*፣ ገጽ 79።
5. ጳውሎስ ኞኞ፣ ገጽ 88-89።
6. ተክለሣድቅ መኩሪያ፣ *የኢትዮጵያ ታሪክ*፣ ገጽ 242።

ምዕራፍ አስር
የአምባራዶም ጦር ግንባር

የአምባራዶም ጉራ ጠላትን አስፈራርቶት ነበር። ከዚህም የተነሣ ሞሶሎኒ ለባዶሊዮ ከባድ ማስጠንቀቂያ ሠጠው። ማስጠንቀቂያውም ራስ ሙሉጌታ ከሌሎች የኢትዮጵያ የጦር አዛዦች ሁሉ አስፈሪ መሆናቸውን ገልጾ ጦሩ ምንም ሳይፈራ መዋጋት እንደሚገባው ያስረዳ ነበር።[1] ቀደም ሲል እንደተመለከትነው ደግሞ ደጃዝማች ኃይለሥላሴ ጉግሣ አምባራዶም እስከ አልተያዘ ድረስ በመቀሌ ላይ የኢጣልያኖች ይዞታ አስተማማኝ አለመሆኑን እየገለፀ፣ አምባራዶም በቶሎ እንዲያዝ ይወተውት ነበር።[2]

የጠላት ጦር ራስ ሙሉጌታን ለማጥቃት እና አምባራዶምን ከኢትዮጵያ ሠራዊት አስለቅቆ ለመያዝ የሚችልበትን መንገድ ቀየሰ። ለመጀመሪያው ቀን 1ኛው ክፍለ ጦር ከነበረበት ተንቀሳቅሶ የተቻለውን ያህል እንዲገፋ፣ በሚቀጥለው ቀን ደግሞ 2ኛውና 3ኛው ክፍለ ጦሮች ተንቀሳቅሰው ከአምባራዶም በስተደቡብ እንዲሠፍሩ ባዶሊዮ ትዕዛዝ ሰጠ። ጦርነቱንም እሱ ራሱ እንደሚመራ ቃል ገባ። የጠላትን ጦር መጠጋት በመመልከት የኢትዮጵያ ጦር በበኩሉ ዝግጅት አደረገ። አዲ አማራግ፣ ተግታጋ በተባሉት ቦታዎች ላይ ከየካቲት 1 ቀን ጀምሮ እስከ የካቲት 5 ቀን ድረስ ውጊያ ሲካሄድ ሰነበተ። በተለይ የካቲት 4 ቀን ሌሊት የኢትዮጵያ ወታደሮች ከኢጣልያን ምሽግ ውስጥ ገብተው የተቃና ሥራ ሠሩ።[3]

የአምባራዶም ዋናው ጦርነት የካቲት 5 ቀን 1928 ዓ.ም ጠዋት በ3 ሰዓት ተከፈተ። ጦርነቱ የተጀመረው እንዳግባር በተባለው ቦታ ላይ ሲሆን የኢጣልያን የጦር አዛዦች ጦርነቱን በፅቅድ ለመምራት እስኪቸገሩ ድረስ የኢትዮጵያ ጦር ግራ አጋባቸው። ጥማቸውን የሚያረካ ጠመንጃ አልነበራቸውምና፣ ኢትዮጵያውያኑ በጠመንጃ ከመታኮስ ይልቅ ሰይፍና ጉራዴአቸውን እየመዘዙ በሩጫ ከጠላት መካከል እየገቡ መጨፍጨፍ ቀናቸው።

ጦርነቱ ሙሉ ቀን ዋለ፤ በማግስቱ የካቲት 7 ቀንም ቀጠለ። ራስ ሙሉጌታ በጥሩ ዘዴ ውጊያውን መሩ። ባዶሊዮ ወታደሩን አንድ አቅጣጫ ሲያሲዝ፣ እሳቸው አቅጣቸውን ወዲያው ለውጠው ሌላ አቅጣጫ ፈጥረው ጠላት ያተኮረበትን ቦታ ባዶ ያደርጉብታል፤ ካላሰበና ካልተዘጋጀበት አቅጣጫ ይወጉታል። በዚህ ዓይነት ዘዴ ራስ ሙሉጌታ ባዶሊዮ ራሱን ጭምር ግራ አጋቡት።

የካቲት 7 ቀን የኢጣልያ ጦር አምባራዶምን አስለቅቆ ለመያዝ ከባዶሊዮ ትዕዛዝ ተሰጠ። አይሮፕላኖችም የራስ ሙሉጌታን ሠፈር እንዲደበድቡ ተደረገ። የኢትዮጵያ ጦር በየፊታውራሪዎች እየተመራ በርትቶ

ተዋጋ። ጦርነቱ ሙሉ ቀን ዋለ። አልቂቱ ከመጠን በላይ ስለሆነ ራስ ሙሉጌታ ወደኋላ አፈገፈጉ። ጠላትም የካቲት 7 ቀን ማታ አምባራዶምን ያዘ። ራስ ሙሉጌታ ወደ ኋላ ቢመለሱም ጦርነቱ በቢትወደድ መኮንን ደምሰው መሪነት ቀጠለ። የኢትዮጵያ ጀግኖች እስከ የካቲት 12 ቀን ድረስ ሽንጣቸውን ገትረው እስከ መጨረሻ ተዋጉ።

በጦርነቱ ፍፃሜ ላይ የታየው ሁኔታ አስገራሚ ነበር። ሀላሳ ስድስት ነጭ መኮንኖችና 621 ነጭ ወታደሮች ከ154 ጥቁር ወታደሮች ጋር ሞቱ። የጄኔፍሮች ማነስ በዚህ ጦርነት ላይ በሙሉ ልብ አለመዋጋታቸውን ያመለክታል። በኢትዮጵያ በኩል የሞቱት ከ6000 አላነሱም። በምድር ከተደረገው ውጊያ ሌላ 170 አይሮፕላኖች የቻሉትን ያህል እየተመላለሱ 396 ቶን ከባድ ፈንጂ ጥሰዋል። አንድ አይሮፕላን በኢጣልያን የሕክምና ቡድን ላይ በስሕተት አምስት ቦምብ ጣለች። ከሕክምናው ቡድን በሕይወት የተረፈ አልተገኘም። አንድ መቶ ያህል ሰዎች ሞቱ። በኢትዮጵያውያን በደረሰው ጥቃት ለደረሰው ጉዳት፣ ይህንን ማሰረጃ ማድረግ ይቻላል።

የጣልያን አይሮፕላኖች የራስ ሙሉጌታ ጦር የደረሰበትን ማወቅ አቃታቸው። አካባቢውን ሁሉ እየተዘዋወሩ ዝቅ እያሉ በመብረር መረመሩ። ምልክት እንኳን አላገኙም። ራስ ሙሉጌታ ያፈገፈጉት ቀጥተኛውን መንገድ ይዘው አልነበረም። ወደ አዘቦ ነበር የወረዱት። ራስ ሙሉጌታ በደህና ጉዞ ላይ እንዳሉ ነበር የልጃቸውን ሞት ሰምተው የተመለሱት።

ከሰሜን እየተነሣ ኢትዮጵያን ለሚወጋ ጦር መከላከያ ሆነው ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ የተዘረጉ ብዙ ተራሮችና ሸንተረሮች አሉ። ከእነዚሁ ተራሮች ዋነኛው አምባላጌ የሚባለው ነው። ይህ ተራራ ከሰሜን ለሚያጠቃና ከደቡብ ለሚከላከል ወሳኝነት ያለው የጦር ቦታ ነው። ይህንን የመሰለው የጦር ጉራ አንዳችም ጥንቃቄ ሳይደረግለት ቀርቶ ያለምንም ችግር የኢጣልያን ጦር ወጣበት። ለኢትዮጵያም ጦር ታላቅ ሽንፈት ሆነ። የኢትዮጵያ የጦር መሪዎች ከዚህ ላይ ተሳስተዋል።

ይህ ጦርነት እንደ ንጉሠ ነገሥቱ አገላለጽ የመጨረሻው የታላቁ ጠላታችን ጦርነት ነበር።[4] ከኢትዮጵያ ወገን የወደቀው ከ5000 አላነሰም። ከጠላት ወገን 68 መኮንኖች 332 ነጭ ወታደሮች፣ 873 የቅኝ ግዛት ወታደሮች ሞተዋል። ሰባ አይሮፕላኖች ድብደባ አካሂደው 34 ቶን ቦምብና የጋዝ መርዝ የጣሉ ሲሆን፣ ከእነዚሁ ውስጥ 36 ተመትተው ወድቀዋል።

<u>ማጣቀሻ ፅሑፎች</u>

1. ጳውሎስ ኞኞ፣ *የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦርነት*፣ ገጽ 99።
2. ተክለፃድቅ መኩሪያ፣ *የኢትዮጵያ ታሪክ ከአፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ*፣ ገጽ 242።
3. ዝኒ ከማሁ።
4. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 257።

ምዕራፍ አሥራ አንድ
የኦጋዴን ጦር ግንባር

እንደተገለፀው ዋናው የጦር ግንባር ሶሜን ነው ቢባልም፤ ጦርነቱ የተቀሰቀሰው በኦጋዴን ግዛት ወልወል በተባለው ቦታ ነበር። የታሪኩ ሂደት በአጭሩ ከዚህ እንደሚከተለው ነው። ወልወል ከኢትዮጵያና ከደቡብ ሶማልያ ወሰን ወደ 100 ኪሎ ሜትር የምትርቅ የኢትዮጵያ መሬት ናት። የምትቀርበው ለሶሜን ሶማልያ ነው። በኢጣልያ ጠብ አጫሪነት ግጭት እስከ ተቀሰቀሰበት ጊዜ የይገባኛል የግዛት ጥያቄ ማንም አንስቶባት አያውቅም። በዚያን ጊዜ የእያንዳንዳቸው ጥልቀት እስከ 60 ሜትር የሚደርሱ 359 የውሃ ጉድጓዶች በዛ ነበሩ።

በኢትዮጵያና በሶሜን ሶማልያ መካከል ያለው የግጦሽ መሬት ይከለል የሚል ጥያቄ ከእንግሊዝ ወገን እንደ ተነሳና ጥያቄው ምን ሴራ ጎርሶ እንደተቀሰቀሰ በሌላ ምዕራፍ ተገልያለል። ከዚህ የምንመለከተው ሂደቱን ብቻ ይሆናል።

የኢትዮጵያና የእንግሊዝ ወሰን ተካይ ቡድን ህዳር 14 ቀን 1927 ዓ.ም ወልወል ሲደርስ ጣልያን በምሥጢር ወታደሮች አስገብታ ከጥቂት ጊዜ በፊት ባንዲራዋን አሰቅላ ኖሮአል። ሁለት መቶ ሃምሣ ባንዶች ከዚህ አትለፉ ብለው ወሰን ተካዩን ቡድን አስከለከሉ። በኢትዮጵያ ወታደሮችና በኢጣልያ ባንዶች መካከል ፍጥጫ ተጀመረ። ፍጥጫውን ለማርገብ እንግሊዞች ተጠቂዎቹን፣ ኢትዮጵያኑን ተለማመጡ። አጥቂውን ለማስታገስ በኢትዮጵያዊው ተከላካይ በደጃዝማች ተሰማ ባንቲ፣ በእንግሊዝ ዳኛ በኮሎኔል ክሊፎርድና በአጥቂ የኢጣልያ ጦር አዛዥ በሻምበል ሮበርቶ ችማሩታ መካከል ህዳር 15 ቀን የመልእክት ልውውጥ ቢደረግም፤ ችማሩታ ከነበረበት ቦታ ንቅንቅ የማይል ሆነ። የእንግሊዝ ወሰን ተካዮች ኢጣልያ የዓለምን ሕግ ጥሳ፣ ወሰን አልፋ የኢትዮጵያን ግዛት በኃይል መያዝዋን አስታውቀውና ለኢትዮጵያ መንግሥት በግልባጭ አለምተው ከአደጋ ለመዳን ሀውድ ወደተባለው ቦታ አፈገፈጉ። ከዛም የኢጣልያ አይሮፕላኖች የኢትዮጵያ ጦር ከሠፈረበት በግርለገቡ አካባቢ ማንጎበብና ለማስፈራራት መትረየስ መተኮስ አበዙ።

ነገሩ በዚህ ሁኔታ በመፋዘዝ ሰነበተ። ህዳር 25 ቀን 1927 ዓ.ም ችማሩታ ለደጃዝማች ተሰማ ባንቲ አንድ ደብዳቤ ላከ። ደብዳቤውም የኢትዮጵያ ወታደሮች ለመንቀሳቀስ በመዘጋጀት ላይ ለመሆኑ መረጃ እንደደረሰው ጠቅሶ "ለመወያየት" መቀረጡን የሚገልጽ ማስጠንቀቂያ ነበር። ግጭቱን እንዲፈጥር ከኢጣልያ ባለሥልጣኖች ከተፈቀደለት በኋላ የዛፈው የጠብ መጫሪያ መሆኑ ነው።

ምንም ችግር ሳያጋጥም እንዲሁም የኢትዮጵያ ጦር አንዳች እንቅስቃሴ ሳያደርግ ህዳር 26 ቀን 1927 ዓ.ም ረቡዕ፣ ከቀኑ በ9:00 ሰዓት ባንዳዎች በኢትዮጵያ ወታደሮች ላይ በድንገት ተኩስ ከፈቱ። በምድር ታንኮች፣ በሰማይ አይሮፕላኖች ሥራ ቀጠሉ። ኢትዮጵያውያኑ በጀግንነት ተከላከሉ። ፊታውራሪ ዓለማየሁ ጉሹና ሌሎች 93 ኢትዮጵያውያን በጀግንነት ወደቁ። 127 ባንዳዎች ተገደሉ። ባላምባራስ አሊ ኑር የሠሩትን የጀግነት ሥራ ሠሩ።[1] የወልወል ግጭት ከኢጣልያ መራሪ ጋር፣ እንደዚሁም የባላምባራስ አሊ ኑር ጀግንነት ከወልወል ግጭት ጋር በታሪክ ሲወሳ ይኖራል።

ወሰኑን የመከለሉ ሥራ ቀረና ሌላ ዓይነት የዲፕሎማቲክ ንትርክ ተጀመረ። ኢጣልያም ወልወልን የማትሰቅ ሆነ። የጦርነቱ እሳት በመቀዝቀዝ ፈንታ እየተጋጋመ ሄደ።

በዚህ ጊዜ ወሉል ጂሌ የተባለው ቀንደኛ የሶማሌ ባላባት ተወራሪዋን ኢትዮጵያን ከዶ ከኢጣልያኑ ወራሪ ጐን ቆመ። ግራዝማች አፈወርቅ ወልደ ሰማዕት በግርለገቡ ከጠላት ጋር ፍጥጫቸውን ቀጠሉ። የኢጣልያን ጦር በባዶሊዮ አዛዥነት በትግራይ ማጥቃት ሲጀምር፣ በጀነራል ግራዚያኒ መሪነት በኦጋዴን ላይ ወረራ ተጀመረ። ጦርነቱም በልዩ ልዩ መኪናዎች የተደገፈ፣ በታንክና በአይሮፕላን የሚዋጋ ነበር።

የኢትዮጵያ ሠራዊት በደጃዝማች ነሲቡ ዘአማኑኤል የጦር አበጋዝነት ተሠለፈ። የሐረር፣ የአርሲ፣ የኢሉባቡር፣ የባሌ ጦር በኦጋዴን፣ የሲዳሞ ጦር በቦረና በኩል ለመከላከል ተዘጋጀ። የከፋ ጦር በቦረና ከተሰለፈው የሲዳሞ ጦር ጋር ተቀላቀለ።[2]

በዚህ ግንባር የተሰለፈው ጦር የአደረጃጀት፣ ዩስትራቴጅና የአመራር ችግር ነበረበት። በስትራቴጂው በኩል ሲታይ ቆላው በረሃማ ነው። ጦሩ ለመከላከል ከዚያ ሲገባ ውሃና ምግብ አያገኝም። መገናኛ ስለሌለው ከቀለበት ውስጥ ከገባ ፈልቅቆ በመውጣት መዳን አይችልም። ከበረሃው ወርዶ ካልተዋጋ ደግሞ ሀገሩን ኢጣልያኖች ይይዙታል። ይህም ለኢትዮጵያ ጥቃትና ጉዳት ነው። በአደረጃጀት ሲታይ ደግሞ ፈስበርሳቸው ግንኙነት በሌላቸው ብዙ አዛዦች የሚመራ ነው። በአመራር ረገድ የደጃዝማች ነሲቡ የአበጋዝነት እንጂ የአዛዥነት ሥልጣን የላቸውም። አዛዦ ንጉሠ ነገሥቱ ናቸው። እሳቸውም ከሰሜኑ የጦር ግንባር የሚተርፍ የአመራር ኃይል አልነበራቸውም። የኦጋዴን ጦር ግንባር የሚንቀሳቀሰው በእነዚህ ችግሮች ውስጥ ተተብትቦ እንደታሠረ ነበር። ያም ሆኖ የኢትዮጵያ ጦር ሀገር ከመልቀቅ፣ ከበረሃ ገብቶ ጠላቱን መዋጋትን መረጠ። በቦረና እስከ ዶሎ፣ በባሌ እስከ ኢሚ፣ በጅጅጋ እስከ

ቆራጌ ወረደ። ክንጉሠ ነገሥቱ የተሰጠው ትዕዛዝ የራሱን ግዛት ይዞ ጠላት እስኪጠጋ እንዲጠብቅ ነበር።[3]

የኢጣልያ ጦር በጥቅምት ወር 1928 ዓ.ም ከሞቃድሾ ተነስቶ በሰፊው፣ በሙሉ ኃይሉ ተንቀሳቀሰ። በሦስት ታላላቅ ረድፍ የተከፈለ ነበር። ዋናው ረድፍ በፈርፈር፣ በዛላቦ፣ በቀበሪደሐር፣ በደገሐቡር፣ በጅጅጋ ሐረር ገብቶ ድሬዳዋን የሚይዝ ነበር። ሁለተኛው ደግሞ በኢሚ ወደ ደጋው የባሌ ግዛት የሚወጣ ነበር። ሦስተኛው ደግሞ በደሎ፣ በነገሌ አድርጐ ይርጋ ዓለም ገብቶ ደቡቡን ሀገር የሚይዝ ነበር። ጦሩ በዚህ በተሰጠው ዕቅድ መሠረት ወረራውን ቀጠለ።

የኢትዮጵያ ሠራዊት ወራሪውን ለመመከት የሚቻለውን ሁሉ አድርጐ፣ በፈርፈር በኩል የመጣውን ጦር ቆራጌ ላይ ሲደርስ ጦርነት ገጠመው። ቆራጌ ከሶማሌና ከደቡብ ሁለቱ ወንዞች ያሉበት ሰጥ ያለ ሜዳ በመሆኑ ለጠላት ታንክና አይሮፕላን አመች ቢሆንም የኢትዮጵያ ሠራዊት በጀግንነት ተዋጋ። ቀኝአዝማች አፈወርቅ መራቱን ቆፍረው ነበርና በጋይል ተዋጉት። ጣልያን ሁለት ጊዜም ቢመጣ፣ ሁለት ጊዜም ተሸንፎ ተመለሰ። ጉራውን በእግር ጦርነት ለመስበር እንደአልቻለ በተረዳ ጊዜም የጦሩን ቦታና አሳባቢውን በአይሮፕላን ደበደበ። ጥቅምት 23 ቀን ባካሄደው ድብደባ ጀግናው ግራዝማች አፈወርቅ በቦምብ ፍንጣሪ ቆሰሉ። አሳቸውም አዛዥ ጠይቀው እስኪደርስላቸው ከቦታቸው ቆይተው ወታደሩን አዋጉ። ፊታውራሪ በሌላ ሲተኩላቸው ወደ ደገሐቡር ተመልሰው ከዚያ አረፉ። ስለፊፀሙት አገልግሎት ከዕረፍታቸው በኋላ የደጃዝማችነት ማዕረግ ከንጉሠ ነገሥቱ ተሰጥቷቸዋል። የቆራጌ ጀግና አፈወርቅ ደጃዝማች እየተባሉ ስማቸው በታሪክ በክብር ሲጠራ ይኖራል።

ይህንን ግንባር ንጉሠ ነገሥቱ ከህዳር 9 እስከ 12 ቀን 1928 ዓ.ም ጐበኙ። ጉብኝቱ ለአጭር ጊዜ ቢሆንም ጦሩን ሳያጠናክረው አልቀረም። ነገር ግን የባሌና የቦረናው ግንባሮች ይህንን አላገኙም።

ቀደም ሲል ለዘመቻ በተጠራ ጊዜ የኢሉባቡር ጦር አዲስ አበባ ድረስ መጥቶ በንጉሠ ነገሥቱ ፊት በሰልፍ ከአለፈ በኋላ በባቡር ተጓጉዞ ድሬዳዋ ገባ። ከዚያም ቀርሣ ከተባለው ቦታ ጥቂት ቆይታ ከአደረገ በኋላ ወደ አበከር ሄዶ ከዚያም ለሐረር ከተማ ሰልፉን እያሳየ ውሃ፣ ውሃ በሚል ነጋሪት እየተመራ፣ ተጉዞ ካራማራ ሠፈረ። ቁጥሩ ከ3000 የሚበልጥ ነበር። በዚህ ቦታ ከሁለት ወር በላይ ስለተቀመጠና በውሃ ጥም፣ በረሃብ፣ በበሽታ ስለተዳከመ ወደ ጦር ግንባር ለመግባት በራሱ አነሳሽነት ወሰነ። አለቆችም የጦሩን ጥያቄ መቀበል ግድ ስለሆነባቸው ተስማምተው እንዲዘምት አደረጉ። ደገሐቡር ላይ የጉሩ፣ የጋሙ ጉፋ፣

የአርሲና የኩሎ ጦር ሹማምንት የጋራ ስብስባ አድርገው የጦር እቅድ አወጡ። ዕቅዱም የኢሉባቡር ጦር በደጋሐመዶ፣ የኩሎ ጦር ወደ ጅጅጋ ተመልሶ ደጀን እንዲሆን፣ የሐረርጌ ጦር ቀበሪደሐር ሄዶ ወደጥናን ለተላከው ጦር ደጀን እንዲሆን፣ የአርሲ ጦር ደገሐቡር ቆይቶ ለሐረርጌ ጦር ደጀን /የደጀን ደጀን/ እንዲሆን ነበር። ጦሩ ጀነጋብ እንደደረሰ በአስላስፍ ረገድ ቀኙን እኔ ልያዝ፣ ለእኔ ይሁን በመባባል ስጠብ ተቃረበ። ይህም በውይይት ተፈትቶ ለጦር ተሰለፈ።

የኢጣልያ ጦር በአምስት ጀነራሎች የሚመራ ነበር። ሚያዝያ 7 ቀን፣ በ11 ሰዓት ጥዋት ጦርነት ተከፈተ። ጦርነቱ ጀነጋብ ወንዝ ላይ ነበር። ጠላት በታንክ ቢንቀሳቀስና በአይሮፕላን ቢደበድብም የኢትዮጵያ ጦር አልተበገረም። ከረቡዕ አንስቶ እስከ አሑድ ድረስ አምስት መአልትና አምስት ሌሊት ተዋጋ።[4] አብዛኛው ወታደር በዚሁ ጉራ ላይ ብቻ አለቀ። አለቁ፤ ግን በደህና ተመለሱ።

ፊታውራሪ ጓንጉል ኮላሴ በደጃዝማች አፈወርቅ እግር ከተተኩ በኋላ ጦርነቱ ቀጠለ። ፊታውራሪ ጓንጉል የደረሱት 500 የሠለጠነና በጥሩ ሁኔታ የታጠቀ ጦር ይዘው ነበር። የመጀመሪያውን ግጥሚያ ሀዳር 1 ቀን ነሐሴ በተባለው ቦታ አደረጉ። ይህ ቦታ የፋፈን እና የጀረር ወንዞች የሚገናኙበት ነው። ጠላት በአባባቢው መኖሩ እንደታወቀ፣ ዋናው ጦር ወደ ኋላ እንዲያፈገፍግ አድርገው 40 ወታደር ብቻ ይዘው ነበር ጦርነቱን የጀመሩት። አራት ታንኮች በየተራ ቢመጡባቸው ከአሸዋ ውስጥ እስኪዘፈቁ እየጠበቁ እንዳይነቃነቁ በመትረየስ ጥይት ጠበጠበአቸው። ጣልያኖች መትረየስ ቢተኩሱ፣ የእጅ ቦምብ ቢወረውሩ፣ አሳበቢውን በቤንዚን ቢረጩ አንዳች ማድረግ የማይቻላቸው ሆነ። ከሙሉ ተን ውጊያ በኋላ ጣልያኖች ሸሹ። ኢትዮጵያውያኑ 66 ጠላት ገደሉ። ሰባቱ ኢጣልያውያን ነበሩ። አራቱ ታንኮች ተማረኩ። በኢትዮጵያውያኑ በራሳቸው ላይ የደረሰው ጉዳት ትንሽ ነበር።

ነገር ግን ሌላ ያልታሰበ አደጋ ደረሰ። በእንዴ ታንክ ወስጥ ሰጠኝ የተባለ ወታደር አንድ ዕቃ አግኝቶ አመጣ። ምን እንደሆነ አልታወቀም እንጂ የእጅ ቦምብ ነበር። ምን እንደሆነ ባልታወቀ ዕቃ የተደናገሩት አዛገሮች ወዲያው እንዲጥል አዘዙት። ያ ወታደር እዚያው እመካከላቸው ስለጣለው ቦምቡ ፈነዳ። ሰጠኝና ሌሎች ሰባት ወታደሮች ወዲያው ሲሞቱ፣ ፊታውራሪ ጓንጉል ኮላሴና ወንድማቸው አቶ ኃይለ ማርያም ኮላሴ ቆሰሉ። አቶ ኃይለማርያም ደገሐቡር ሕክምና ጣቢያ ሲሞቱ፣ ጓንጉል ወደ አዲስ አበባ ለሕክምና ተወሰዱ። ጦርነታቸውም የአንድ ቀን ብቻ ሆኖ ቀረ። ወታደሩም ተበተኑ።[5]

በዚህ ዓይነት በሩ ለጠላት ከተከፈተ በኋላ፣ ያለቀው አልቆ፣ የተረፈው የኢትዮጵያ ጦር የተቻለውን ያህል እርስበርሱ በመተባበር፣ እየተከላከለ ወደ ኋላ ተመለሰ። ጠላት መጀመሪያ ቀብሪደሐርን ከዚያም ደገሐቡርን ያዘ። የኢትዮጵያ የጦር አለቆች የንጉሠ ነገሥቱን መሄድ እንደሰሙ በየፊናቸው በበርበራና በጅቡቲ በኩል ከሀገር ወጥተው ነበርና፣ ጠላት ወደ ጅጅጋ በሚያደርገው ግሥጋሴ እምብዛም ችግር አላጋጠመውም።

ማጣቀሻ ፅሑፎች

1. ጳውሎስ ኞኞ፣ *የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦርነት*፣ ገጽ 12-16
2. ተክለፃድቅ መኩሪያ፣ *የኢትዮጵያ ታሪክ ከአፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀ.ኃ.ሥ.* ፣ገጽ 233።
3. ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፣ *ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ 1ኛ መጽሐፍ*፣ ገጽ 198-203።
4. መኮንን እንዳልካቸው፣ *ለልምትክም ብዙ ለልዋሸም*፣ ገጽ 294-302
5. ጳውሎስ ኞኞ፣ ገጽ 142-44።

ምዕራፍ አሥራ ሁለት
የቦረና ጦር ግንባር

በቦረና ግንባር የተሰለፈው አብዛኛው ሠራዊት በራስ ደስታ ዳምጠው የሚመራው የሲዳሞ ጦር ነበር። በደጃዝማች ወልደ ሚካኤል የሚመራውም አብሮት ነበር። በዘመናዊ የጦር ስልት የሠለጠኑ ወጣቶችም ነበሩ። ጦሩ ጥቅምት 5 ቀን 1928 ዓ.ም ከይርጋለም ተንቀሳቀሰ። በጥቅምት 7 ቀን ሀገረ ሰላም ደረሰ። ከዚያም መንገድ እየተመነጠረና ለአግረኛ እንደሚስማማ እየተደለደለ ጉዞ ቀጥሎ መልካ ዳዲ ከተባለው የገናሌ ወንዝ ላይ ጦሩ ሠፈረ። ይህ ቦታ ባሌን እና ሲዳሞን የሚያዋስን ከመሆኑም በላይ ውሃ ያለበት፣ አየሩም ለስላሳ ሆኖ ለጦሩ ምቹ ነበር። ዋሽ ተዘጋጅቶ መሣሪያና ስንቅ ከዚያ ተከተተ።

ጥቅምት 21 ቀን 1928 ዓ.ም ዓርብ መልካ ዳዲ ላይ የነበረው የስዊድን ቀይ መስቀል ሠፈር በቦምብ ተደበደበ። ሌላ የአይሮፕላን ድብደባ ታህሣሥ 7 ቀን አሚኖ በተባለው ቦታ ተካሄደ። በድንገት የደረሰ ድብደባ ስለነበር በለውና በከብት ላይ ጉዳት አስከተሉ። ጦሩም ሀሳቡ ተንጀዋለለበት። እንዋጋ በሚለው የአባቱ ልጅና፣ እናፈግፍግ በሚለው የእናቱ ልጅ መካከል ከባድ ክርክር ተካሄደ። ከክርክሩ መጠን የተነሳ የጦር ዕቅድ ሳይተካከልለት ቀረ። ቢሆንም ትግሉ ቀጠለ። ግራዝማች ገብራይ ኮሎኔል/ ሰባት ራሳቸውን ከጣልያን ከድተው ከኢትዮጵያ ጦር ተቀላቀሉ። ይህም ለኢትዮጵያ ጦር አዲስ የውጊያ ስልት አስገኘ።

ታህሣሥ 21 ቀን 1928 ዓ.ም አሚና በተባለው ቦታ ከጠላት ጋር ጦርነት ተከፈተ። ለመጀመሪያ ጊዜ ድል የኢትዮጵያውን ሆነ። ጠላትም ሸሸ። ታህሣሥ 23 ቀን አንድ ሰላይ አይሮፕላን በመላክ ጠላት አነባቢውን ለለና፣ የኢትዮጵያ ጦር በተደናገረበት ጊዜ ጦር በማቅረብ አዲስ ውጊያ ከፈተ። ጠላት ብዙ የሱማሊያ ወታደርና ታንክ አቀረበ፣ ኢትዮጵያውያን ጠንክረው ተዋጉ። አንድ ታንክ ቆርጠው አስቀሩ። ነገር ግን ጠላት ረዳት ታንክ በመላክ አስጐትቶ ወሰደው። የኢትዮጵያ ጦር ሁኔታውን ከገመገመ በኋላ ከአሚና ወደ መልካ ዳዲ ተመለሰ። ይህም ለጠላት መግቢያ አንድ በር ከፈተ።

ሌላው የጦሩ ሚዳ መልካ ዳዲ ሆነ። የጠላት ጦር እየገፋ ስለመጣ የኢትዮጵያ ጦር ለመመከት ወሰነ። ጦሩ በሦስት ሻምበሎች ተደለደለ። ለሻምበሎችም ረዳቶች ተመደቡላቸው። ሻምበሎቹ ራሳቸው ነገሌ ላይ እንዲጠባበቁ ተደረጉ። ጦር ስውጊያ ተዘጋጀ። ጀነራል /ማርሻል/ ግራዚያኒ ጦሩን እየመራ መጣ። እዚህ ላይ የእኛ ሻምበሎች

በአዋጊነት ወደ ኋላ ሲቀሩ ግራዚያኒ ራሱ ከጦርነቱ መግባቱን ማጤን ይገባል።

በጠላት በኩል የተሰለፈው የኢጣልያ ተወላጅ፣ ሶማሊያዊ እና ከሊቢያ የመጡ ነበሩ። ታንኩን በመሬት፣ አይሮፕላኑን በሰማይ ግንባር ቀደም አድርጉ መጣ። በሦስት ሻምበል የተመደበው የኢትዮጵያ ሠራዊት አርስበርሱ ተቀላቅሎ መከተ። ከባድ ውጊያ ተካሄደ። የጦርነቱ ሚዛን አጠራጣሪ ሲሆን፤ ግራዚያኒ መልካ ዳዲን በአግረኛ ጦር ለመክበብ ሞከረ። ነገር ግን ራስ ደስታ ቁልማዩ የተባለውን ገዥ ቦታ ገስግሰው ያዙበት። የኢትዮጵያ ልጆች "እኛ በዚህ ሥፍራ እንደ ቅጠል ረግፈን፣ እንደ ሻሽ ተነጥፈን ነው እንጂ፤ እንዲያው ጠላት አይገባም።" ብለው ምድር ሰቅስቀው ተዋጉ። ከዋሻው ውስጥ የተቀመጠውን መሣሪያና ስንቅ እያወጡ ተጠቀመበት፤ በተቻላቸው ሁሉ ተከላከሉ። ጠላትን በሩቅ በጥይት፣ በቅርብ በጪቦጣ፣ በሰይፍና በጉራዴ ጨፈጨፉት። መቶ አለቃ በለጠ አንድ ራሱን አንድ መትረየስና ሦስት ሣጥን ጥይት ማረከ። ሌላውም ጀግና የየራሱን አገኘ። ግራዚያኒ የኢትዮጵያ ጦር እንደአልተበገረለት ባየ ጊዜ፤ በከሀዲዎች አማካኝነት እና በግብረ አበሮቹ ጠቋሚነት በመንገሸ ያለውን፣ መሣሪያ የተቀመጠበትን ዋሻ ማወቅ ስለቻለ፤ በባሌ በኩል አዙሮ በመድፍ መደብደብ ያዘ። ዋሻውም ፈርሶ ተደፈነ። በውስጡ የነበረው መሣሪያና ስንቅ ተቀበረ።

ከጥር 4 ቀን ጀምሮ ለሦስት መዓልትና ለሦስት ሌሊት ያለአንዳች ዕረፍት የተካሄደው ውጊያ በጠላት አሸናፊነት ተደመደመ። ድል ወደጠላት የዞረው 1ኛ/ ዋሻው በመናዱና በውስጡ የቀረው ስንቅና ትጥቅ በመቀበሩ፤ 2ኛ/ ብዙዎች ጀግኖችና የጦር መሪዎች በመውደቃቸው፤ 3ኛ/ የጠላት ጦር ከምድር በታንክ፣ በሰማይ በአይሮፕላን በሚጥለው መሣሪያ ብልጫ በማግኘቱ ነበር። እዚህ ላይ ልናስተውሰው የሚገባው ጉዳይ ግራዚያኒ ራሱ በጦርነት ውስጥ ባይኖር ኖሮ የኢትዮጵያ ግምጃ ቤት የነበረውን ዋሻ ለማግኘትና ለማስደብደብ አይችልም ነበር። ዋሻውን ባያስደበድብ ኖሮ ለድል አይበቃም ነበር። በመሆኑም የኢትዮጵያ ሠራዊት ከባድ መሣሪያውን ከገናሌ ወንዝ ውስጥ ጥሎ ተመለሰ።[1]

እዚህ ላይ ጠላት ይህንን ጦርነት እንደምን እንደ አቀነባበረው መመልከት ይገባል። ሞሶሎኒና የጦር አዛዦቹ አስበው የሚሠሩ እንጂ በመላ የሚንቀሳቀሱ አልነበሩም። በተለይም ግራዚያኒ። ግራዚያኒ ቀደም ብሎ ዶሎ በመግባት ጦሩን ማጠናከርና የውጊያ ሥልት መቀየስ ያዘ። ከዛም ጦሩን ከሦስት ከፈለው። በአንድ ጀነራል የሚመራ ጦር በገናሌ የፍያ ሸለቆ እስከ ሣንዶር እንዲገፋ፤ ሁለተኛው ጦር በፊልቱ አድርጉ ወደ

በግልና ማሞ እንዲያልፍ፤ ሶስተኛው ደግሞ ባደዋ ፓርማ በኩል ወደ መልካ ሙሪ እንዲገባ ደለደለ። ጦሩን እንዲህ ከለለለፈ በኋላ አዛዦችን ሰብስቦ "...ኢትዮጵያውያን ለኢጣልያውያን አስደግድጉአቸው" በማለት አዘዛቸው።

ቀጣዩ ጦር ሜዳ፣ ቁልማዩ ሆነ። ይህ ቦታ በአካባቢው ከነበሩት ቦታዎች ሁሉ ለጦርነት ተስማሚ ነበር። ራስ ደስታና ሪዳቶቻቸው ጦሩን በረድፍ፤ በረድፍ ደለደሉት። አዛዦችም ከሠራዊታቸው ጋር ቆሙ። ጣልያን ከ60,000 የማያንስ ወታደር፣ ከ100 የማያንሱ ታንኮች፣ ከ60 የሚበልጡ መድፎች፣ ከ200 የማያንሱ መትረየሶች አቀረበ። በሃምሣ ሁለት አይሮፕላኖች እየተረዳ መጣ። ጦርነቱ መልካ ዳዲ ላይ ጥር 4 ቀን ጠዋት ሲከፈት፤ የቁልማዩው ውጊያ ከቀኑ ልክ 6 ሰዓት ተጀመረ።



በዘመናዊ ስልት የሰለጠኑ ወጣቶችን ያካተተው የደቡቡ ግንባር ለጣልያን ታላቅ ፈተና ነበር።

ከሁለቱም ወገን በሚተኮሰው መሣሪያ ምድር የተገለባበጠች መሰለ። በሁለቱም ወገን የጦርነቱ እቅድ ውጥንቅጡ ወጣ። ራስ ደስታ ዛምጠውና ደጃዝማች በዛብህ ስለሽ ከጦር ውስጥ ገብተው ተዋጉ። የኢትዮጵያ ወታደሮች ከታንኩ ላይ እየወጡ ጠላታቸውን ወደ ውስጥ ሸቀሸቁት። ጦርነቱ እስከ ምሽቱ 3 ሰዓት ቆይቶ ጠላት ተሸንፎ ወደ ኋላው ተመለሰ። እነ ጀነራል በርገዝሊ የቆሰሉትና ሌሎችም ብዙ ኢጣልያውያን የሞቱት ከዚህ ጦርነት ላይ ነው። የኢትዮጵያ ጦር ደስ አሰው። ምርኮው፣ የጦር ጀብዱው ሲሰማ እኾለ ሌሊት ሆነ።



በዘመናዊ ስልት የሰለጠኑ ወጣቶችን ያካተተው የደቡቡ ግንባር ለጣልያን ታላቅ ፈተና ነበር።

ለጥር 5 ቀን አጥቢያ፣ ከሌሊቱ በ11 ሰዓት እንደገና ተኩስ ተከፈተ። ግራዚያኒ ካባሊየር የተባሉ አዲስ የነጭ ወታደሮች አቀረበ። ጦርነቱ ከትናንቱ የበለጠ ሆነ። የልብ ልብ የተሰማው የኢትዮጵያ ጦር ጠላቱን ያለ እንዳች ዕረፍት ለሦስት መዓልትና ለሦስት ሌሊት መውጋቱን ቀጠለ። የቁልማዩ ሜዳ ሬሣ ለበሰ። ጠላት የመልካ ዳዲን ጦርነት ስለአሸነፈ በዚያ የነበረውን ጦር ወደ ቁልማዩ አዞረው። በዛም የኢትዮጵያም ሠራዊት እንደ ቅጠል ረገፈ። ራስ ደስታ በነፍስ አባታቸው በአባ ወልደ ፃድቅ ግዝት ጥቂት የተረፉ ወታደሮቻቸውን ይዘው ወደ ኋላ ተመለሱ። ሦስት መኪናዎች ስለተገኙ የቅርብ የሥራ ጓደኞቻቸውን፣ ታቦቶቹንና ቁስለኞቹን፣ ምርኮኞችና መድፎቻቸውን፣ መትረየሶቻቸውን አስጭነው ወደ ቦረና ነገሌ ተመለሱ።[2]

የቦረና ግንባር አጠቃላይ ሁኔታ ደሴ ለነበሩት ለንጉሠ ነገሥቱ ደረሰ። እሳቸውም የሀገር አስተዳደር ሚኒስትሩ ደጃዝማች ገብረማርያም ወደ ሲዳሞ፣ የገንዘብ ሚኒስትሩ በጅሮንድ ፍቅረ ሥላሴ ከተማ በባሌ በኩል በተጨማሪ ዘምተው ድጋፍ እንዲሰጡ አዘዙ። እንደዚሁም ለሲዳሞና ለባሌ ጦር ሁለት ማጠናከሪያ አዋጆች አወጡ። አዋጆቹም ያፈገፈጉት ጦሮች ተመልሰው ጠላትን እንዲከላከሉ ትዕዛዝ የሚያስተላልፉ ነበሩ። ጥር 19 ቀ ን የተላለፉት እነዚህ ሁለት አዋጆች "እንዴት ሲዳሞን፣ ባሌን ወንድ እንደሌለበት አድርጉ ይግባበት?" የሚል ኃይል ቃል የያዙ ነበሩ።[3]

የመልካ ዳዲን እና የቁልማዩን ጦራ ከሰበረ በኋላ፣ ጠላት ወደ ነጌሌ ገሰገሰ። በኢትዮጵያም በኩል አዲስ ዝግጅት ተደረገ። ይርጋ ዓለም የነበረው ደጀን ተንቀሳቅሶ በአዲስ ገባ። በራስ ደስታ በሚመራው ጦርም ላይ ጠላት የአይሮፕላን ድብደባ አጠነከረበት። በመሆኑም ከነገሌ አፈግፍጉ ዋደራ ላይ ለመመከት ተዘጋጀ። ጥይትና መሣሪያውንም በሰዋራ ጫካና ገደል ውስጥ አኖረ። የማይጠቅመውን ዕቃ ሕዝብ እንዲወስደው አደረገ። ሊያነሳው ያልቻለውን የውጅግራ ጥይትና ሌላም አርጌ መሣሪያ አንድነት ሰብስቦ ለቃጠሎ አዘጋጀው።

በዚህ ወቅት ከኢጣልያ ከድተው ለመርዳት በዳሞ በኩል ጥሰው የመጡ 600 ኤርትራውያን፣ በቀኛዝማች ፀጋዬ መሪነት ጥር 12 ቀን 1928 ዓ.ም ከኢትዮጵያ ጦር ጋር ተቀላቀሉ። ድካም ጸንቶባቸው ክበርና ለዕረፍታቸው ወደ ይርጋ ዓለም ተላኩ። እንዳች ሳይጉድልባቸው በይርጋ ዓለም የ9 ወር ዕረፍት አደረጉ።

ወደ ጦርነቱ ሁኔታ እንመለስ። በዛ ማንኛውም ዝግጅት ከተደረገ በኋላ የጦር ሠፈሩ ከአዶላ ወደ ዋደራ ተዛወረ። ሁለት ጣልያኖች

አካባቢውን ለመሰለል በታንክ ከነገሌ ወደ ዋደራ ሲንቀሳቀሱ በመንገድ ላይ በደፈጣ ተገደሉ። አንደኛው የጦር መኮንን ነበር። እንደዚሁም በሌላ ቀን የኢትዮጵያ ወታደሮች ጠላት የነበረበት ቦታ በድንገት ደርሰው 37 ኢጣልያኖች በመግደልና 7 መትረየስ፣ 115 ጠመንጃ በመማረክ ጀብዱ ሠሩ። ይህ ዓይነት የደፈጣና የአደጋ መጣል ዘዴ ጥሩ ውጤት ስለአስገኘ ቢታታ ከተባለው ቦታ ምሽግ ተሠራ። እርድ ተምሶ ምሽጉ ከተሠራ በኋላ 80 ወታደሮች ከዚያ ውስጥ ገብተው ይጠባበቁ ጀመር።

በየካቲት ወር 1928 ዓ.ም የጠላት ጦር በሰባት መኪና ተሳፍሮ ከነገሌ ወደ ቢታታ መጣ። አመጣጡን ባዩ ጊዜ የኢትዮጵያ ወታደሮች ቦታውን ለቅቀው ከፊትና ከኋላው ተደበቁ። ጠላትም ከቦታው ላይ ምንም ባጣ ጊዜ ከመኪና ወርዶ ምሣ በልቶ መዝናናት ያዘ። ከዋደራ ወገን የተደበቁት 40 የኢትዮጵያ ወታደሮች በድንገት ደርሰው ጨፈጨፉት። ወደ ነገሌ ሲሸሹ ደግሞ ሌሎች 40 ደገሙት። በጠላት ወገን የነበሩት ኢጣልያኖች ብቻ ነበሩ። አንድ መኪና ብቻ ጥቂት ሰዎች ይዞ ሲያመልጥ ሌሎች 63 ኢጣልያኖች ተማረኩ። ወታደሮቹም ተገደሉ። ጦርነቱም ለኢትዮጵያ ጦር በሰላ ቢላዋ ጮማ እንደመቁረጥ ሆነለት። ይህ ጀግንነት የተሠራው ግራዝማች ኃይለ ማርያም ገብረ ሥላሴ በተባሉት የሰላሌ ሰው ነበር።

የደሎ ጉራ ሲፈታ በዚያ ተቆርጦ የቀረው ጦር ታላቅ አበሳ አጋጠመው። በረሃብና በውሃ ጥም አለቀ። የአለቀው አልቆ ከተረፉት ጥቂት ሃያ፣ ሠላሣ ሰዎች ቀን ተጉዘው ሦስት፣ አራት መሣሪያ እየተሸከሙ ዋደራ ገቡ። በተለይ አንድ ቡድን በግራዝማች ሥዩም የሺጥላ መሪነት 45 ቀን ተጉዞ 12 መትረየስና ጥይት ጭኖ ደረሰ። ይህም ለጦርነቱ ድጋፍ ሰጠ። እነዚህ በደሎ በረሃ ተቆርጠው የቀሩ ሰዎች ዋደራ ለመድረስ የበቁት ቀጋና አጋም የተባሉ ዛፎች ፍሬ እየበሉ፣ እንደዚሁም ቀጭኔና ጉሽ እያደኑ፣ የእነሱን ሥጋ እየበሉ ሕይወታቸውን አትርፈው ነው።

ጦርነቱ በዚህ ሁኔታ እንደለለ ከንጉሠ ነገሥቱ ታዝዘው በሰሜን የጦር ግንባር የመጡት የደጃዝማች ገብረ ማርያም፣ ከቆቦ እስከ ደሴ በመኪና፣ ከአዲስ አበባ በአይሮፕላን፣ ከዛም በእግር በአገምጃና በሶዶ አድርገው በመጓጓዝ በመጋቢት ወር 1928 ዓ.ም ከዋደራ ጦር ሠፈር ደረሱ። በጦር ምክር ቤት ተጠንቶ ድኑን የውጊያ ቦታ እንዲሆን ተመረጠ። በደጃዝማች መኮንን ወሰኔ መሪነት የወላይታና ከአዲስ አበባ የዘመተው ጦር ድኑን ላይ እንዲመክት በድምፅ ብልጫ ተወሰነ። ነገር ግን የደጃዝማች ገብረማርያም ከቆቦ ድረሱ መጥቼ እንዴት ዕድል

አይሰጠኝም ስለአሉ ውሣኔው ፈረሰ። ሁለቱ ደጃዝማቾች አብረው እንዲዘምቱ ማድረግ የማይቻል ሆነ። ራስ ደስታ ዳምጠው ራሳቸው እንዳይሄዱ ሠራዊታቸው በደሎ በረሃ ከደረሰበት ጉዳት ገና ስላአላገገመ የማይመች ሆነ። ከብዙ ንትርክ በኋላ የድኑን ጦራ በዕጣ ለደጃዝማች ገብረማርያም ደረሳቸው።

ሻለቃ በቀለ ወያ ደግሞ በሰሜን ጦር ግንባር በአስረክቡት መሣሪያ ልክ ከአዲስ አበባ አራት መድፍ፣ አንድ ሺህ አንድ መቶ ቤልጅግ መውዜር ጠመንጃ ከብዙ ጥይት ጋር ይዘው ሚያዝያ 23 ቀን 1928 ዓ.ም ዋደራ ደረሱ። ይህም ለኢትዮጵያ ጦር የልብ ልብ ሰጠው።[4]

የቦረናው ጦር ግንባር በዚህ ሁኔታ ላይ እንዳለ ንጉሠ ነገሥቱ ሀገር ጥለው ሄዱ። ወሬውም ወዲያው በሬዲዮ ተሰማ። የጦርነቱም ሥልት መሪ ስለአጣ፣ ወደ አርበኝነት ተለወጠ።

ከማይጨው ጦር ግንባር የተመለሰ አንድ ቡድን ንስግሶ ቦረና ገባ። ቀደም ብለው በአካባቢው የነበሩ እንደ አደረጉት፣ ወደ ኬንያ ሳይሰደድ በጋርዱላ አውራጃና በደቡብ ቦረና ትግሉን ቀጠለ። ቡድኑ ትግሉን የቀጠለው ጮማይዴ ላይ በአደረገው ስብሰባ የሃያ አንድ ዓመቱን ወጣት አቶ /ደጃዝማች/ ተስፋዬ ወልዴን መሪ አድርጐ በመምረጥ ነበር። በቡርጂ፣ በአማሮ፣ በገለና፣ በሀገረ ማርያም፣ በባርጐዳ፣ በተልተሌ፣ በያቤሎ፣ በስኮሪ፣ በመርቃ፣ በገለባና በጮራሞ የጦር ሜዳዎች ጠላትን ግንባር ለግንባር እየገጠመ አኩሪ ውጤት አግኝቶአል።[5]

<u>ማጣቀሻ ፅሑፎች</u>

1. ለይፋ አባወሎ፣ *የታሪክ ቅርስ*፣ ገጽ 46-66። ጳውሎስ ኞኞ፣ *የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦርነት*፣ ገጽ 128።
2. ለይፋ አባወሎ፣ ገጽ 66-79።
3. ገብረ ወልድ እንግዳወርቅ፣ *ማይጨው*፣ ገጽ 81-82።
4. ለይፋ አባ ወሎ፣ ገጽ 82-91።
5. የጀግኖች አደራ፣ የጀግኖች ማህበር መጽሔት፣ መጋቢት 28 ቀን 1983 ዓ.ም ገጽ 37-39።

ምዕራፍ አሥራ ሶስት
የማይጨው ጦርነትና የኢትዮጵያ ድል መሆን

ቀደም ባሉት ምዕራፎች ላይ እንደተገለፀው፣ ጦርነቱ ለብዙ ጊዜ በብዙ ቦታ ተካሄዶአል። ከረጅም ትንቅንቅ በኋላ ኢጣልያ የአሸናፊነትን እድል ተቀዳጅታለች። ከታሪክ አኳያ ከሚነሱት ጥያቄዎች አንዱ "ኢትዮጵያ ድል የሆነችው የትና መቼ ነው?" የሚል መሆን ይገባዋል።

በአቢጋዝ የተሰለፈ ጦር ድል መሆን የሀገሪቱን መሸነፍ አያመለክትም። ሀገሪቱ ድል እንደተመታች መቆጠር ያለበት ንጉሠ ነገሥቱ ራሳቸው በቆመባት ጦርነት ላይ ለመጨረሻ ጊዜ የተሸነፈችው ነው። ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ራሳቸው ለመጀመሪያም፣ ለመጨረሻም ጊዜ በዚህ ጦር ሜዳ የቆሙት መጋቢት 22 ቀን 1928 ዓ.ም ማክሰኞ ነው። ኢትዮጵያ ድል የሆነችው በዚህ የጦር ሜዳ ነው። ወደ አምስት ሺህ ዘመን በሚጠጋ ታሪኳ ሰንደቅ ዓላማዋ ወድቆ፣ ንጉሠ ነገሥትዋ ጥሉአት ሄደ፣ ከወራሪ እጅ የወደቀችው በዚህ ቀን፣ በዚህ ቦታ ነው። የጦርነቱ ሂደት ከዚህ እንደሚከተለው ነበር።

በሰሜንም በደቡብም የተሰለፈው የኢትዮጵያ ጦር የተመራው በንጉሠ ነገሥቱ ነበር። የሰሜኑ ጦር ግንባር ዋነኛው እንደ ነበር ተገልፇል። በእሱም የጦር ሚኒስትሩን ጨምሮ አምስት ራሶች፣ ማለትም ራስ እምሩ፣ ራስ ካሣ፣ ራስ ሥዩም፣ ራስ መሉጌታ፣ ራስ ጌታቸው እንደነበሩበትና እነሱም ምን ምን እንደሠሩ አይተናል። ሰበደቡብ ግንባር አንድ ራስ ብቻ፣ ማለትም ራስ ደስታ ዳምጠው ብቻ እንደተሰለፉ አይተናል። በምሥራቅ አንድም ራስ እንደአልነበረ ተረድተናል።

በአመራር ረገድ ለሁሉም አዛዥ ንጉሠ ነገሥቱ ነበሩ። የጦር አበጋዞች የመታዘዝ እንጂ ምክር የመሰጠት መብት አልነበራቸውም። ለስም የተቋቋመውም የአዲስ አበባው ምክር ቤት ስለጦርነቱ አገጣጠም አንድም ጊዜ አልመከረም። ምንም አዋቂና ትጉህ ቢሆኑ፣ በአንድ ሰው አእምሮ፣ በርቀት የተዘረጉ ጦርነቶችን በብቃት መምራት አይቻለም። ከዚህም በተጨማሪ መገናኛ አልነበረም። ጥቂትም ቢኖር፣ ምሥጢር ወደ ጠላት ከማሽጋገር በስተቀር ለኢትዮጵያ የሰጠው ጥቅም እምብዛም ነው።

ሁኔታው እንዲህ ሳለ፣ ንጉሠ ነገሥቱ ከደሴ በመኪናና በበቅሎ ተገዝው መጋቢት 12 ቀን 1928 ዓ.ም ሃያ ከተባለው ቦታ ደረሱ። ራስ ካሣና ራስ ስዩም ከተንቤን ጦርነት የተረፈውን ሠራዊታቸውን ይዘው ቀደም ብለው መጋቢት 10 ቀን ከንጉሠ ነገሥቱ ተገናኝተው ስለነበር ስለ ጦርነቱ ልዩ ልዩ ምክር ተደረገ። ዋና ዋናዎቹ የጦር አማካሪዎች ነጮች

ነበሩ። የንጉሠ ነገሥቱም አመለካከት የሚያዘነብለው ወደ እነሱ ነበር። ንጉሠ ነገሥቱ ምክሩን በትዕግስት ያዙት። እንደምን እንዋጋ ለሚለው ጥያቄ ልዩ ልዩ ሐሳብ ከታሰመ በኋላ ውሣኔ ተደረገ። ክብር ዘበኛ በንጉሠ ነገሥቱ ግንባር እንዲሰለፍ ተመደበ። በግራ ራስ ጌታቸው፣ በመሐል ራስ ካሣ፣ በቀኝ ራስ ሥዩም እንዲሰለፉ ተወሰነ። አቡነ ጴጥሮስና እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ የደብረ ጽጌ ጊዮርጊስን፣ የደብረ መንግሥት ገብርኤልን፣ የደንባሮ /ማንባርዋ/ ማርያምን ይዘው ከንጉሠ ነገሥቱ ፊት እንደሚቆሙ ተወሰነ።

በዚህ መልኩ ጦሩ ከተደለደለ በኋላ መች እንግጠም የሚለው ጥያቄ አስቸገረ። የጦር አለቆች ሠራዊታቸው አልተከተሰንም አያሉ ምክንያት አበዙ። የጦርነቱ ቀን ተጓተተ። ከግንባር የደረሰው ጦር ትዕግሥት አጣ፣ ተቅበጠበጠ። መጋቢት 19 ቀን ባአታዩ ላይ በተደረገ ምክር ጦርነቱ መጋቢት 21 ቀን እንዲሆን ተወሰኖ ከንጉሠ ነገሥቱ መመሪያ ተሰጠ። ጦሩ መጋቢት 21 ቀን ከማታው በ2 ሰዓት እንዲንቀሳቀስ የሚያዝ ነበር። እንዲሁም መመሪያው እርስ በርሱ እንዳይጠራራ፣ እንዳይጮህ፣ እንዳያቅራራ፣ ጠላት የሸሸ መስሎት በማባረር ቀለበት እንዳይገባ ጥንቃቄ እንዲያደርግ፣ ጠላት ድል መሆኑ ሳይረጋገጥ ግዳይ ለመጣል ወደ ኋላ እንዳይመለስ፣ ለዘረፋ እንዳይጣደፍ፣ ረዳት እስኪደርስለት ጠንክሮ እንዲዋጋ፣ ተኩስ ጀምሩ ለማለት አመሻሽ ላይ የርቺት ምልክት እንደሚተኮስ፣ ባለማዕረግ የጠላት ወታደር ምሥጢር ስለሚገኝበት እንዲማረክ እንጂ እንዳይገደል የሚደነግግ ነበር።[1]

ነገር ግን ይህ ውሣኔ ለኢትዮጵያ ሠራዊት ከመድረሱ አስቀድሞ ባዶሊዮ ሁኔታውን አወቀው። ሊያውቀው የቻለው ደግሞ ንጉሠ ነገሥቱ "ቅዳሜ ወይም ሰኞ እንገጥማለን" ብለው ለእቴጌ መነን መጋቢት 19 ቀን ማታ ያስተላለፉትን ቴሌግራም ጠልፎ በማዳመጥ ነበር። ባዶሊዮ ይህንን ምሥጢር እንደ አወቀ ጦሩን ለቅዳሜ ውጊያ አዘጋጅቶ በጥንቃቄ ይጠባበቅ ጀመር።

የኢትዮጵያ ሠራዊት በመመሪያው መሠረት ለእሑድ፣ ለመጋቢት 21 ቀን ሲዘጋጅ ዋለ። ሌሊቱን ከጠላት ተጠግቶ ለውጊያ ቦታ ያዘ። ነገር ግን ከንጉሠ ነገሥቱ ሌላ ትዕዛዝ መጣ። ከሌሊቱ በ11 ሰዓት ጦሩ በየአለበት አንዲውል ተለፈፈ። ጦሩ እንደታዘዘው አደረገ። እሳቸውም በነበሩበት መሐን በተባለው ዋሻ ዋሉ። ጠላት ጦርነቱ ለመጋቢት 21 ቀን መቀጠሩ ቀደም ብሎ ሰምቶ የበኩሉን ዕቅድ አውጥቶ ይጠባበቅ ስለ ነበር፣ ጦርነቱ በአንድ ቀን መዘግየቱ ለጠላት ፋሲካ ሆነለት። ብዛታቸው እስከ አንድ መቶ ሃምሣ የሚደርሱ አይሮፕላኖች ከጉር አይሮፕላን ጣብያው

እየሰነሳ መሉ ቀን በቦምብ ደበደበው፣ መርዝ ረጨበት። የመጋቢት 21 ቀን ውጊያ መተላለፍ ጠላትን በብዙ ጠቀመ። በኢትዮጵያ ሠራዊት ላይ ታላቅ ጉዳት ያደረሰ ስህተት ነበር። ይህ የተደረገበት ምክንያት ገና አልታወቀም።

ጦርነቱ መጋቢት 23 ቀን 1928 ዓ.ም ማክሰኞ ከሌሊቱ በ10 ሰዓት ከ45 ደቂቃ ተከፈተ። የተከፈተውም በድንገት እንጂ፣ አመራር ተሰጥቶበት አልነበረም። አንድ ያልታወቀ የሐማሴን ተወላጅ ሰው ቀደም ብሎ ከጠላት ከድቶ ከኢትዮጵያ ሠራዊት ጋር ተቀላቅሎ ነበር። የግጥሚያው መዘግየት ስለአበሳጨው ሌሊቱን በድብቅ ተመልሶ ወደ ኢጣልያኖች ሠፈር ገባ። ገብቶም በዚያች ሌሊት ኢትዮጵያውያን ጣልያኖችን ሊወሩ መዘጋጀታቸውን ለጀነራል አማሪ ነገረ። የመጨረሻውን መልእክት ርችት በመተኮስ እንደሚያስታውቅ ነግሮ ወደ ኢትዮጵያውያን ሠፈር ተመለሰ። ለእነሱ ደግሞ ጣልያኖች ዛሬ ሌሊት ሳይታሰብ በድንገት ሊገጥሙ ተዘጋጅተዋል በማለት ነግሮ ከአስጠነቀቀ በኋላ ለሁለቱም ወገን ከሚሰማ አማካይ ቦታ ሆኖ ሁለት የሽጉጥ ጥይት ተኮሰ። ጣልያኖች ድምፅ ሲሰሙ፣ መስማታቸውን ለማረጋገጥ በስምምነታቸው መሠረት ቀይ ርችት ተኮሱ። የዚህ ቀይ ርችት ምስጢር ለኢትዮጵያውያኑ አስቀድሞ ተነግሮአቸው ነበርና ተኩሱ ተከፈተ።[2] በዚህ ዓይነት ዋናው ጦርነት ተጀምሮ ቀጠለ።



ንጉሠ ነገሥቱ በጦር አውድ ላይ።

ጦርነቱ በከፍተኛ ደረጃ ተካሄደ። ጠላት ከማይጨው በስተሰሜን ከአለው ተራራ ላይ ስለነበር የኢትዮጵያ ጦር ጠላቱን ለማጥቃት አልተመቸውም። እንዲያውም የኢትዮጵያ ጦር የነበረበት ሥፍራ ወደ



ንጉሠ ነገሥቱ በጦር አውድ ላይ።

ለሜን ማለትም ጣልያን ወደ ነበረበት ተዳፋትነት ስለነበረው ለጥቃት የተጋለጠ ነበር። የኢትዮጵያ ጦር ጠላቱን ለማጥቃት የተቻለውን አደረገ። እስከ ምሽጉ ድረስ እየተጠጋ 5 ያህል ምሽጐች እስከ ማስለቀቅ ደረሱ። ጠላት ከምድር በመድፍ፣ ከሰማይ በአይሮፕላን ድብደባውን አጠናከረ። ንጉሠ ነገሥቱ ራሳቸው የቆሙበት የጦር ሜዳ በመሆኑ ወሣኝነቱ ለሁሉቱም ወገን ግልፅ ነበር።

ንጉሠ ነገሥቱ ከጦርነቱ ሜዳ ገብተው እንደ አንድ ወታደር ተዋጉ። እኩለ ቀን ሲሆን የኢትዮጵያ ጦር መሸሽ ጀመረ። ንጉሠ ነገሥቱም ለንደቅ ዓላማ አስቀመጡ። ነጋሪት እያስመቱ ድል አድርገናል ብላችሁ እልል በሉ ብለው አዘዙ። እንዲሁም ተደረገ። የሸሸው ወታደር እንደገና እየተመለሰ ተዋጋ። መኪንንቱንም ከአዳራሹ ላይ ምን እያልክ ፎከረህልኝ ነበር እያሉ አነቃቁት። ጦርነቱ ከማታው እስከ 5 ሰዓት አልቆመም ነበር። ንጉሠ ነገሥቱ ሲመሽ መጋቢት 21 ቀን አደረውበት ወደ ነበረው መሐን ወደ ተባለው ዋሻ ተመለሱ። ንጉሠ ነገሥቱንም በዚህ ቀን ውሎአቸው ያላመሰገነ አልነበረም። ንጉሠ ነገሥቱ የቆሙበት ሌላ ጦርነት ስለአልተደረገ ይህ የመጨረሻው ሆነ። ኢትዮጵያ ድል የተመታችው በዚሁ በማይጨው ግንባር ነው።

ማጣቀሻ ፅሑፎች

1. ገብረወልድ እንግዳወርቅ፣ *ማይጨው*፣ ገጽ 97-105።
2. ጳውሎስ ኞኞ፣ *የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦርነት*፣ ገጽ 116-117።

ምዕራፍ አሥራ አራት
ከማይጨው መልስ

እንደተገለፀው የኢትዮጵያ መሸነፍ፣ የኢጣልያ ማሸነፍ በማይጨው ጦር ሜዳ መጋቢት 22 ቀን 1928 ዓ.ም ሆነ። ንጉሠ ነገሥቱ ከተዋጉበት ቦታ ወደ ኋላ ተመለሱ። ሐሳባቸው ደግሞ ለመዋጋት እንጂ፣ በዚሁ እንዲያበቃ አልነበረም። ነገር ግን እንደአሰቡት አልሆነም። ጦርነቱ አልተደገመም፤ የመጨረሻው ሆነ። ዝርዝሩን ቀጥሎ እንመለከታለን።

ንጉሠ ነገሥቱ መጋቢት 23 ቀን እና 24 ቀን በዚያው በመሐን ውሉ አደረጉ። ነገር ግን ተመልሰው ከጦር ሜዳው አልገቡም። ሠራዊቱም እንዳይጠጋቸው ተከለከለ።[1] የኢትዮጵያ ጦር ሁለት ቀን ሙሉ ከተዋጋ በኋላ ወደ ኋላው መመለስ ጀመረ። ከጦር መሪዎች አንዱም ወደ ጦርነቱ ሜዳ ስለአልተመለሱ መሪ አልነበረውም። ስለዚህም ሁሉም በየፊናው መንገዱን ወደ ባዕታዩ ቀጠሉ። መሸሽ ጀምሮ የነበረው የጠላት ጦር ለቅቆአቸው የነበረውን ምሽጐች መልሶ ያዘ። ያም ሆኖ ግን "ወደኋላችን እንመለስ" ካሉት "ለጠላታችን ግንባራችንን እንጂ ጀርባችንን አናሳይም" ያሉ ቆራጥ የኢትዮጵያ ጀግኖች ፍልሚያውን ቀጠሉ። እስከ መጋቢት 25 ቀን ዓርብ ድረስ ተኩስ ይሰማ ነበር።

በንጉሠ ነገሥቱ ሠፈር ምክር ተደረገ። መኪንንቱና የጦር አለቆች ሐሳባቸውን ተጠየቁ። ከቀረቡት ሐሳቦች አንደኛው ወደ ባዕታዩ ተመልሰን ጦሩን እንደገና አዘጋጅተን እንዋጋ የሚል በመሆኑ ንጉሠ ነገሥቱ ስጋት አደረባቸው። ሥጋታቸውም ከማይጨው እግር ከነቀልን ዳግመኛ ጦርነት ለመግጠም የማይቻል ይሆናል የሚል ስለነበር "...ያለነው ተዋግተን ብንሞት ይሻላል" አሉ። የንጉሠ ነገሥቱን ሐሳብ መኪንንቱ ስለአልተቀበሉ ክብዙ ንግግር በኋላ፤ መጀመሪያ ራስ ከበደ ወደ ነበሩበት ዋሻ ከዚያም ወደ ባዕታዩ መልስ ሆነ። ንጉሠ ነገሥቱ መጋቢት 24 ቀን ከሌሊቱ በ6 ሰዓት ባዕታዩ ደረሱ።

በባዕታዩ አዲስ የጦር ዕቅድ ተሠራ። ለማጥቃት መሞከር ቀርቶ መከላከል እንደሚሻል ታመነበት። መኪንንቱ ሥራቸውን እየያዙ የሚሰፍሩባቸው አምስት ቦታዎች ተመደቡ። እነሱም፣

1. የባዕታዩ መሐል ሠፈር ለንጉሠ ነገሥቱ ተመደበ።
2. ከቦክራ እና ከመሐል ተራራ መካከል ያለው በር ለደጃዝማች ኃይሉ ከበደ ተሰጠ።
3. ከክሣድ ሃያ እስከ አደባማዙ ያሉት 3 በሮች ለራስ ጌታቸው ተሰጡ።

4. ከክሣድ ሃያ ጀርባ እስከ መሐን ድረስ ያለው ለራስ ክበደ ተመደበ።

5. የሃያ ሚካኤል በር ለግቢ ሚኒስቴር ጭፍራ ተሰጠ።

ለወለላታ መጠባበቂያው በአዲ ወይፈር በር፣ በግሀሌ ቤት በር፣ በሃያ ማርያም በር፣ በገረብ ሃያ በር፣ በመንክሬ በርና እና በቀኛዝማች ኃይለ ሥላሴ ቤት በር፤ በድምሩ በ6 በሮች ጠባቂ ተመደበ። እንደዚሁም በዋግ በኩል ለ5 በሮች፣ በጨርጨር በኩል ለ2 በሮች ወታደር ታዘዘ።

የኢጣልያ ጦር በበኩሉ ንጉሠ ነገሥቱ የነበሩበትን መሐን የተባለውን ቦታ መጋቢት 25 ቀን ያዘ። በዚህ ጊዜ ንጉሠ ነገሥቱ ጦራቸው መታኮሻ ቦታ እንዲይዝ አዘዙ። ራሳቸው እየተዘዋወሩ ቦታ ማከፋፈል ጀመሩ። የጦር ትዕዛዝ ቢሰጡም ያዳመጣቸው የለም። የጦርነቱ መከራ አሰቅቆት ነበርና ወታደሩ ጉዞውን ወደ ኮረም ቀጠለ። መኢንንቱ ይህንን ባዩ ጊዜ ወደ ኋላ ተመልሰን አሸንጌ ላይ እንከላከል የሚል ሐሳብ አቀረቡ። ይህ ሁኔታ ንጉሠ ነገሥቱን እጅግ አበሳጨ። "... የፈቀደ ከእኔ ጋር ይመት። እኔ ግን ወደ ኋላዬ አልመለስም" አሉ። በዚህ ጊዜ የንጉሠ ነገሥቱ ሕይወት አሳሳቢ እየሆነ መጣ።

ከቀኑ በ3 ሰዓት ስብሰባ ተደረገ። ወደ ኋላ ተመልሰን ጦራችንን እያስተባበርን፣ በደፈጣ አደጋ እየጣልን፣ ሊቻልም ፊት ለፊት በመግጠም ብንከላከል ይሻላል የሚል ሐሳብ ቀረበ። ነገር ግን ለንጉሠ ነገሥቱ አልጣማቸውም። ጦሩ ያለው በሁለት ሞት መካከል እንደሆነ አስረዱ። ቆሞ ቢዋጋም፣ ቢሸሽም ሞት እንደማይቀርለት ገልፀው "...የተቻለውን ያህል ሠርተን የኢትዮጵያ ነፃነት በእኛ ደም ይፋቅ" አሉ። 43 ሰዎች በየተራ እየተነሱ ሐሳባቸውን ሰጡ። ከእነሱም 33ቱ ወደ ኋላ ማፈግፈግን መረጡ። በዚሁ እንዲፈፀም ተወሰነ።[2]

የንጉሠ ነገሥቱ ስንበት ጉዳይ ደረሰ። "ከዚህ አግራችንን ከነቀልን ጦርነቱ መደገሙ መቅረቱ ነው" ያሉት በትክክል ተፈፀመ። ከባዕታዩ በኋላ ስለጦርነት ምንም አልተደረገም፣ ሐሳቡ ሁሉ ስለሽሽት ብቻ ሆነ። ጦሩ ተስፋ ቆርጦ የማንንም አመራር ሳይጠብቅ ጉዞውን ወደ መሐል ሀገር ቀጠለ። መጋቢት 27 ቀን 1928 ዓ.ም አሸንጌ ደረሰ። ጣልያንም ከንጉሣችሁ እንጂ ከእናንተ ጠብ የለንም። እንኳችሁም በሰላም መጓዝ ትችላላችሁ የሚል የስብከት ወረቀት ጥሎ ስለነበር፣ የኢትዮጵያ ሠራዊት ሴሊት ለመሸሸ የነበረውን ሐሳብ ትቶ ከአውላላ ሜዳ ላይ ቀን ለቀን መጓዝ ጀመረ። ጠላት ግን ይህንን የሀሰት የስብከት ወረቀት የጣለው ለዘዴው ነበር። ታቹን በአዘቦ በረሃ በእግሩ ዞሮ የሚቆርጥ ጦር አቅርቦ ነበር። እንደልማዱ 150 አይሮፕላን አስነስቶ ድብደባውን ቀጠለ። በመትረየስ ፈጀው። በጠቅላላው 73 ቶን የሚመዝን ቦምብና መርዝ አወረደበት።

የኢትዮጵያ ሠራዊት ድካም ቢሰማውም፣ ድብደባ ቢበዛበትም፣ መከላከሉን አልተወም። በሚቻለው ሁሉ ተዋጋ። በአዘቦ በረሃ በኩል የመጣበትን እግረኛ ጦር አስታገሰ። ከአይሮፕላኖቹም 28 ጣለ። አንግራዝማች እንደሻው ቁንጮ የጀግንነት ሥራ ሠሩ።[3] ይህ ሥራቸው በታሪክ ውስጥ ሊጠቀሰላቸው ይገባል። እነሱ በጀግንነት ባይከላከሉ ኖሮ የአሸንጌ እልቂት ጠላት እንደ አቀደው ሁሉ ፍፁም ይሆንና ምንም ሰው አይተርፍም ነበር።

ከአልቂት የተረፈው የኢትዮጵያ ሠራዊት መጋቢት 27 ቀን ወደ ኮረም ጉዞውን ቀጠለ። ነገር ግን እሱ ከመድረሱ አስቀድሞ በአዘቦ በረሃ የመጣው የጣልያን ጦር በዚሁ ቀን ኮረምን አስቀድሞ መያዙ ተሰማ። ስለዚህ ጦሩ መንገዱን ለውጦ ወደ ላስታ አቀና።

ንጉሠ ነገሥቱ ባላት ጊዮርጊስ፣ በጓሮ ማርያም፣ በመረዋ ሐዶ አድርገው ግራሮች ደረሱ። የአይሮፕላን ድብደባ ስለከበደ እስከዚህ ድረስ ጉዞው በሌሊት ነበር። ከዚህ በኋላ ግን በቀን ሆነ። ከግራሮች ተነስተው በአንጅፋት ማርያም በኩል ውሃ አቦ ገቡ። ከዚያም ጥላስፈሬ ሚያዝያ 3 ቀን ደረሱ። ንጉሠ ነገሥቱ የትንሣኤን በዓል ከጥላስፈሬ ሥላሴ አከበሩ። ሚያዝያ 5 ቀን ከጥላስፈሬ ተነስተው ወደ ላሊበላ በመሄድ የቅዱስ ላሊበላን አብያተ ክርስቲያናት ጐበኙ። ከላሊበላ ተመልሰው ጥላስፈሬ እንደገቡ በሚያዝያ 5 ቀን ተጽፎ የነበረውን አዋጅ አስነገሩ። በአዋጁም የጠላትን አመጣጥ፣ በማይጨው የተሠራውን ሥራ ዘርዝረው "...ታላቁን ጦርነት ለማድረግ ወደ ሸዋ ተጉዘናል። ...ባገርህ ላይ እየተዘዋወርክ...በያለህበት ተዋጋ..." የሚል ነበር።

ከጥላስፈሬ ሚያዝያ 8 ቀን ተነስተው ደላንታ ውስጥ አንጥ ከሚባል ሥፍራ ደረሱ። ከዚያም ሚያዝያ 10 ቀን ወገል ጤና ገቡ። ኅዳሴ ሁኔታ ሰለአልታወቀ ወደ ወረኢሉ ተጓዙ።[4] ይህ ግምት ትክክል ነበር። ምክንያቱም ደሴን አልጋወራሹ አንድም ጥይት ሳይተኩስ ለቀውለት በመሄዳቸው፣ የኢጣልያ ጦር ሚያዝያ 6 ቀን ገብቶበት ነበርና።[5]

ንጉሠ ነገሥቱ አዲስ አበባ ከጣልያኖች ቀድሞ ለመግባት ገሰገሱ። ሚያዝያ 11 ቀን ሰንበሊጥ በር አፋፍን ወርደው አደሩ። ስለጉዞው ባለ5 አንቀጽ መመሪያ አወጡ። ሰውም በየአለቃው እንዲሠፍር፣ ጉዞውንም ከዋናው መንገድና ከገላጣ ቦታ እየወጣ እንዲጓዝ አዘዙ። ሚያዝያ 12 ቀን መቅደላ ሥር አደሩ። በዚሁ ቀን በነዋሪውና በወታደር መካከል ተኩስ ተከፍቶ ብዙ ሰው ሞተ። በማግስቱም አገሩ ዙሪያውን ከብቦ ለጦር ተሰልፎ መጥቶ ነበር። ነገር ግን ንጉሠ ነገሥቱ መኖራቸውን ከተረዳ በኋላ ተመለሰ። አሳቸውም "ከዘመቻ ያለፈቃድ የተመለሰውን እጅን ለእኔ፣ ከብቱን ለአንተ" የሚል አዋጅ አስነገሩ። ይህም ሆኖ መተናኮሱን አልተወም። የመተናኮሉ

ምክንያት የውስልትና ብቻ ሳይሆን፣ በልጅ ኢያሱ አምዋምዋት የተነሳ ሕዝባዊ ስሜትም ነበረበት።



የንጉሰ ነገሥቱ ጉዞ ከማይጨው ወደ አዲስ አበባ።

ጉዞ ተቀጥሶ ሚያዝያ 13 ቀን ተንታ ገቡ። በማግስቱ ደግሞ አበደ ቤት መሮ ከሚባል ቦታ፣ ከዚያም ሚያዝያ 15 ቀን ለጋምቦ ደረሱ። በዚሁ ቀን የጣልያን ጦር ወረኢሉ መግባቱ ተሰማ። ከዚህ በኋላ ደግመን እንዋጋለን የሚለው ሐሳብ አከተመ። በቀጥታ ወደ አዲስ አበባ ጉዞ እንዲደረግ ተወሰነ። የአዲስ አበባው ጉዞ ቀጥሎ በለገሂዳ፣ ጀማ፣ በደብረ ግል አድርገው ዜማ ወንዝን ተሻግረው ሚያዝያ 22 ቀን ፍቼ ከተማ ገቡ። ከፍቼ ከተማ በዚሁ ሌሊት በ7 ሰዓት ተነስተው በአውቶሞቢል በመንዝ ሚያዝያ 21 ቀን ከጥዋቱ በ3 ሰዓት አዲስ አበባ ገቡ።[6]

<u>ማጣቀሻ ዕሑፎች</u>

1. ጳውሎስ ኞኞ፣ *የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦርነት*፣ ገጽ 119።
2. ገብረወልድ እንግዳወርቅ፣ *ማይጨው*፣ ገጽ 108-118።
3. ታደሰ ዘወልዴ፣ *የአባሳሽኝ ዘመን*፣ ገጽ 18።
4. ገብረወልድ እንግዳወርቅ፣ ገጽ 119-125።
5. ጳውሎስ ኞኞ፣ ገጽ 122።
6. ገብረወልድ እንግዳወርቅ፣ ገጽ 126-131።

ምዕራፍ አሥራ አምስት

የንጉሠ ነገሥቱ ስደትና የሠራዊቱ መፍረስ

ከዚህ በኋላ ንጉሠ ነገሥቱ ሁኔታውን የያዙት በትዕግሥትና በዕርጋታ ነበር። ሚያዝያ 23 ቀን ሌሊት አራዳ ቅዱስ ጊዮርጊስ በዓልን አከበሩ። ከቀትር በኋላ ደግሞ በጣርማ በር በኩል ለመጣው የጠላት ጦር ራስ ጌታቸው፣ በጅሩ በኩል ለመጣው ደግሞ ደጃዝማች ፍቅረማርያምን አበጋዝ እድርገው ሾሙ። ሽማግሌና ሴት ከከተማ እንዲወጣ፣ በወጊያ ዕድሜ ላይ ያለ ሁሉ ከሳይ ወጥቶ እንዲሠፍር አዘዙ።[1]

ከዚህ በኋላ ምክር ተደረገ። መኪንንቱና ሊቃውንቱ በንጉሠ ነገሥቱ ሰብሳቢነት በታላቁ ቤተ መንግሥት ተሰብስቦ መከረ። የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደግሞ ሰብቻው ተሰባሰበ። መኪንንቱና ሊቃውንቱ ጉዳዩን የተመለከተው በአገር ባህልና ሥርዓት፣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደግሞ ከፖለቲካ አንፃር ሳይሆን አልቀረም።

የመኪንንቱና የሊቃውንቱ ስብሰባ መጋቢት 24 ቀን ከቀትር በኋላ በ12 ሰዓት ተጀመረ። ልዩ ልዩ ሃሳቦች ቀረቡ። አንደኛው ሐሳብ በማህል ሀገር ስለሚደረግ ውጊያ፣ ሁለተኛው ደግሞ የመንግሥት መቀመጫ ወደ ጐሬ ተሳውሮ ስለመከላከል ነበር። በመሐል ሀገር ለመዋጋት የከጀለው ቡድን ጦር ከሁለት ተከፍሎ አንዱ ቡድን በጣርማ በር ከዚያም አልፎ ቢመጣ በበረሃ እንዲመደብ ሊያሳስብ፣ ሁለተኛው ቡድን በአህያ ፈጅ፣ በጅሁር አፋፍ እንዲዋጋ ነበር። ለዚህ ዕቅድ ማሻሻያ የቀረበው ሐሳብ ደግሞ ጦሩ ከሁለት መክፈሉ ቃርቶ ጥቂት በጥቂት እየተመደበ በሁለቱም በር በሽፍትነት መልክ እንዲከላከል የሚል ነበር። ሌላው ዋና ሐሳብ ደግሞ እንደተጠቀሰው ቤተ መንግሥቱ ወደ ጎሬ ተሳውሮ ጦርነቱ እንዲቀጥል ነበር። ነገር ግን በአንዱም ሳይቆረጥ አደረ።

በማግስቱ ሚያዝያ 25 በዚያው ሰዓት ስብሰባው ሲቀጥል አዲስ ሐሳብ ተረበ። እሱም ንጉሠ ነገሥቱ ወደ ዓለም ማህበር ሄደው ያመልክቱ፣ እስከዚያው ድረስ ጦሩ በየሀገሩ ተሰማርቶ በሽፍትነት እየተከላከለ ፍርድ ይጠበቅ የሚል ነበር።[2] ንጉሠ ነገሥቱ ወደ ውጭ አገር ይሂዱ የሚለው ሐሳብ ተደገፈ። ይህ ሐሳብ በድንገት ሳያልፍ ቀርቶ ውሎ ቢያድር ኖሮ፣ ተቀባይነት የማግኘቱ ጉዳይ ሳያጠራጥር አይቀረም ነበር። ለዚህ ሳይሆን አልቀረም በቶሎ እንዲወሰን የተደረገው። ነገር ግን ቀደም ብሎ መደላድል ተሠርቶለት ስለነበር ሥምረት አገኘ። ቀደም ብሎ የተሠራው መደላደል ከዚህ እንደሚከተለው ነበር።

የእንግሊዝ መንግሥት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሚያዝያ 14 ቀን 1928 ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ፣ የንጉሠ ነገሥቱ ቤተሰብ ኢየሩሳሌም እንዲገባ ተስማምቶ ፈቃድ ሰጠ። የኢትዮጵያ መንግሥት የሚኒስሮች ምክር ቤትም በበኩሉ፣ ንጉሠ ነገሥቱ ወደ ጀኔቫ ሄደው ለዓለም መንግሥታት ማህበር



የንጉሰ ነገሥቱ ጉዞ ከማይጨው ወደ አዲስ አበባ።

ያመልክቱ የሚለውን ሐሳብ 21 ለ3 በሆነ ድምፅ ተቀበለ። ከዚህም በስተቀር ንጉሠ ነገሥቱ ታሳላቆቹን መኳንንት ይዘው ለመሄድ ማሰባቸው ለባለሥልጣኖች የነፍስ ማዳኛ መንገድ ሆኖ ተሠማቸው። በዚህ ሁሉ አቴንይቱ አዲስ አበባ ከነበሩ የታሳላቅ መንግሥታት ኤምባሲዎች ጋር ተነጋግረውበት በተሰጣቸው ምክር መሠረት ባላቸውን ይዘው ለመሄድ ጉትጉታውን አጠነከሩ። የእንግሊዝ መርከብ ጀቡቲ ወደብ ገብቶ ተጠባበቀ። የኢጣልያ ጦር ደብረ ብርሃን ገባ። በዚህ ሁሉ ምክንያት ሐሳቡ ድጋፍ አገኘ።

ንጉሠ ነገሥቱ የመጨረሻዎቹን ትዕዛዞች ሚያዝያ 24 ቀን 1928 ዓ.ም ጠዋት ሰጡ። ትዕዛዞቹም፣

1. መንግሥቱ በአዛዥ ወልደፃድቅ አበጋዝነት ወደ ጎሬ እንዲዛወር።
2. አቶ /ብላታ/ ታከለ ወልደሃዋርያት አዲስ አበባን እንዲጠብቁ።
3. ግብፃዊው ጳጳስ አቡነ ቄርሎስ አዲስ አበባ ቆይተው ሕዝቡን እንዲያረጋጉ የሚሉ ነበሩ።[3]

የንጉሠ ነገሥቱ የአውሮፓ ጉዞ ብዙ ኢትዮጵያውያንን አሰቆጣ። ደጃዝማች ፍቅረማርያም የኢትዮጵያን ክብር የሚያዋርድ ነው በማለት እስከ ግድያ አሰቢቸው። ብላታ ታከለም በበኩላቸው የአርበኝነት ሥራ ለማስጀመር የሚያስችል ሥልጠና ለማካሄድ ሞከሩ። ፊታውራሪ ተክለሃዋርያትም ቅሬታቸውን ገለፁ። ነገር ግን አንዳቸውም ጉዞውን ማገድ አልቻሉም።[4] ግራዚያኒ ይህንን የንጉሠ ነገሥቱን ጉዞ ባወቀ ጊዜ የሚሄዱበትን ባቡር በቦምብ ለመደብደብ አሰበ። ነገር ግን ሙሶሊኒ ራሱ ስለከለከለው ሐሳቡን መፈፀም ሳይቻለው ቀረ።

አላቸው ገብረሕይወትን፣ ራስ ኃይሉንና ሌሎችንም የሚጠራጠሩአቸውን መኳንንት ድሬዳዋ ትተው፣ ቤተሰቦቻቸውንና ባለሟሎቻቸውን ይዘው ጉዞአቸውን ቀጠሉ። ከዚያም ጀቡቲ በሰላም ደርሰው ኢንተርፐራይዝ በሚባል የእንግሊዝ ጦር መርከብ ተሳፍረው ወደ ኢየሩሳሌም ሄዱ። ግንቦት 26 ቀን 1928 ዓ.ም እንግሊዝ ሀገር ገቡ።[5]

የንጉሠ ነገሥቱ ወደ አውሮፓ መሄድ እስከ ዛሬም ድረስ እንደ አከራከረ ነው። ወዳጆቻቸው ይደግፉታል፣ ሌሎች ደግሞ ይቃወሙታል። ደጋፊዎቻቸው የንጉሠ ነገሥቱ ወደ አውሮፓ መሄድ የኢትዮጵያን ጥቃት ለዓለም ኅብረተሰብ ለማሳወቅ እንደረዳ፣ ከዚህም የተሥላ የዓለም ኅብረተሰብ ድጋፍ ተገኝቶ የኢትዮጵያ ነፃነት ሊመለስ እንደቻለ አድርገው ያቀርባሉ። በዚህ ነጥብ የማይስማሙት ግን ሌላ አመለካከት አላቸው። የኢትዮጵያ ነፃነት የተመለሰው በእንግሊዝ እንደሆነ፣ እንግሊዝ ኢጣልያን የወጋቸው፣ ኢጣልያ ከጀርመን ጐን በመቆምዋ እንደሆነ ያስረዳሉ። ለዓለም ማህበር የተነገረው ቃል አንዳች ፍንጭ እንዳላስገኘ በማስረዳ የተደገፈ ክርክራቸውን

ይተነትላሉ። የንጉሠ ነገሥቱ መሰደድ ለኢትዮጵያ ውርደት እንደሆነ አድርገው ይገምታሉ። ነገር ግን ስደቱ ለአሳቸው ለራሳቸው እንደጠቀመ ምንም ጥርጥር የለውም።

የኢትዮጵያ ሠራዊት መፍረስ - የኢትዮጵያ ሠራዊት ከነበረበት የመሣሪያ እጥረት፣ የስንቅ እጦት፣ የአመራር ዝብርቅርቅነትና ከጠላት ሰብስት እየተጋደለ በየጦራው ተዋጋ። በሰሜን ጦር ግንባር በአድዋ፣ በመቀሌ፣ በሽሬ ተጋደለ። በተንቤን ጦር ግንባር በአምባራዶም፣ በአሸንጌ ተጋደለ። በምሥራቅ ከወልወል ጀምሮ በቆራሄ፣ በጀረን ወንዝ፣ በጀመጉታ፣ በሰገግ፣ በደገሐቡር ተከላከለ። በደቡብ ግንባር ደግሞ በዶሎ፣ በመልካ ዳዲ፣ በአሚኖ፣ በቁልማዶ፣ በዋደራ፣ በደገንና በመልካካ በርትቶ ተዋጋ።

ሙሶሊኒ አዳዲስ መሣሪያ የታጠቀና ብዛት ያለው ጦር በታንክ እየተረዳ እንዲዘምትበት አደረገ። በተቀነባበረና በዘመናዊ እቅድ በሚመራ አወጋግ ወጋው። ብዛት ያላቸው አይሮፕላኖችን ከጉርአ እና ከሞቃድሾ አይሮፕላን ማረፊያዎች እያስነሳ በብዙ መቶ ሺህ የሚመዘን ቦምብ ጣለበት፤ መርዝና ጋዝ አዘነበበት። የኤፕሪት ሞስ ረጨበት። ወንዝና ጉድጓዱን እየያዘ፣ ሊይዘው ያልቻለውን መርዝ እየረጨ፣ የሚጠጣው ውሃ አሳጣው። ባላገሩንና ገበሬውን በስብሰት እያታለለ፣ መሣሪያ እያስታጠቀ፣ አርስ በርሱ አፋጀው። ንጉሠ ነገሥቱ ከጦር ሜዳ ላይ ጥለውት እርዳታ ልፈልግ በሚል ምክንያት ተሰደዱ። መኳንንቱና መሣፍንቱ አውላላ ሜዳ ላይ እየጣሉት በባቡር፣ በአውቶሞቢል፣ በካሚዮን እየተሳፈሩ ጥለውት ሄዱ። የቻሉ ከሀገር ወጡ፣ ያልቻሉት ተሸቀዳድመው ከጠላታቸው ጐን ቆሙ።

ሠፊው የኢትዮጵያ የሕዝብ ሠራዊት በየጐጡ ተበተነ። የቻለው ከቤቱ፣ ከወገኑ ገባ። ሌላው ደግሞ በሲዳሞ፣ በጐሬ እያደረገ የማያውቅበትንና ያለመደውን የስደት መንገድ በመከተል ኬንያ ገባ። ወደ በርበራ ሄደ። በምዕራብ የነበረውም ሱዳን ደረሰ። የትም ቢሄድ ግን፣ የዓለመ ገዥ እነሱ ነበሩና ከእንግሊዝ በስተቀር ሌላ አላገኘም። የኢትዮጵያ ሠራዊት ዳግመኛ ይሰበሰባል ተብሎ በማይጠረጠር ዓይነት ተበተነ። በሀገር ላይ ከፍተኛ ውድቀት፣ በሕዝብ ዘንድ ደግሞ መሪር ሐዘን ወደቀ። ምን ማድረግ እንደሚሻል የሚያውቅ ሰው ጠፋ።

ማጣቀሻ ፅሑፎች

1. ገብረወልድ እንግዳወርቅ፣ *ማይጨው*፣ ገጽ 132።
2. ከበደ ተሰማ፣ *የታሪክ ማስታወሻ*፣ ገጽ 164።
3. Angelo Del Boca, *The Ethiopian War: 1935-41*, P.201.
4. Richard Greenfield, *Ethiopia: A New Political History*, pp.220-223.

ምዕራፍ አሥራ ስድስት
የኢጣልያ አዲስ አበባ መግባት

ከሰሜኑም ከምሥራቁም በኩል፣ ጣልያኖች ማይጨው ላይ ድል ከአደረጉ በኋላ አዲስ አበባ ለመግባት በሙሉ ኃይላቸው ተንቀሳቀሱ። የሰሜኑ ጦር እስከ ኮረም ተሰርቶለት የነበረውን የመኪና መንገድ እየተጠቀመ ጉዞውን አፋጠነው። በአዘቦ በረሃ አቋርጦ የአሸንጌን እልቂት ከአካሄደ በኋላ፣ አንዳች ችግር ሳያጋጥመው እርምጃውን ቀጠለ። የመዋጊያ ቦታ እንዲሆኑ ከታሰቡት ቦታዎች አንድዋ ደሴ ነበረች። ነገር ግን እንደታሰበው አልሆነም። አልጋ ወራሹ ልዑል አስፋወሰን ኃይለሥላሴ ለቀውስት ወደ አዲስ አበባ በመምጣታቸው፣ ደሴን አንድ ጥይት እንኳ ሳይተኮስበት ያዘ።[1]

በአድዋ ጦርነት ጊዜ ጣልያኖች በአሰብ በኩል ለመግባት መክራ ማድረጋቸው ይታወሳል።[2] ከዚህ ቀደም ብሎ 1880 ዓ.ም አካባቢ አንድ ኢጣልያዊ ወደ አፍደራ ለጥናትና ምርምር በሚል መጥቶ ደንከሎች ገድለውት ነበር። ታሪክ እየተደጋገመ ይደርሳልና፣ አባቱ በሞተበት በዚህ በአሰብ በር ልጁ ባሮን ፍራንኬት ለመግባት አሰበ። በአይሮፕላን ከርሞ ተነስቶ ካይሮ አረፈ። ከዚያ ተነስቶ ወደ አሥመራ ሲበር አይሮፕላን ስለተሰናከለበት፣ በግንቦት ወር 1927 ዓ.ም በግብፅ በረሃ ተቃጥሎ ሞተ። ከእሱም ጋር የኢጣልያ መንግሥት የሥራ ሚኒስትርና ሌሎችም ሰባት ጣልያኖች አብረው ሞቱ።[3] እንዲህም ሆኖ ጣልያኖች በአሰብ በር ለመግባት የነበራቸውን ዕቅድ አልተዉም ነበርና፣ አንድ ቡድን ጦር ላኩ። ከአሰብ የተንቀሳቀሰው ይህ ጦር በሰርዶ በኩል አድርጐ ወደ ደሴ መጣ። አልጋ ወራሹ ይህንን እንደተገነዘቡ ሁኔታውን ለንጉሠ ነገሥቱ አስታወቁ። የደረሳቸው መልስ "ያሳዝናል" የሚል ሆነ። በዚህ ጊዜ ነበር ከተማውን ለቅቀው ወደ አዲስ አበባ ተመልሰው የመጡት። የጣልያን ጦርም ወደዚያው ገስግሶ ወረኢሉን ያዘ።

ሮቤ ሲደርስ በመጀመሪያዎቹ የሆለታ የጦር ትምህርት ቤት ምሩቆች የሚመራው የኢትዮጵያ ጦር ተከላከለ። የደብረ ሲናን ተራራ አውጣጥና የጣርማ በርን አስተላለፍ ለጠላት አስቸጋሪ አደረጉበት።[4] ለነገሩ የዚህ ጦርነት የውጊያ ስልት ሲታይ፣ ያን ያህል ጠንካራ ገጽታ አይታይበትም። ነገር ግን ጠላት ከንጉሠ ነገሥቱ አስቀድሞ አዲስ አበባ በመግባት ድሉን ለማፋጠን የነበረውን ዕቅድ በማዘግየት ረገድ፣ ንጉሠ ነገሥቱ ቀድመው እንዲገቡና አንዳንድ ውሣኔዎችን ለማድረግ እንዲችሉ ስለአገዘ ሊጠቀስ ይገባል።

ጠላት አዲስ አበባ የሚገባበትን ሥልት ለማቃናት ልዩ ዝግጅት አድርጐ ነበር። ለመኮንኖቹ መቀመጫ 193 ፈረሶች መጥተውለት ነበር። በብዙ መኪናዎችና ሞተር ሳይክሎች ታጅቦ፣ በ12,495 ኢጣልያውያን ወታደሮች እየተመራ፣ ሚያዝያ 27 ቀን 1928 ዓ.ም ከቀትር በኋላ፣ በ11 ሰዓት አካባቢ አዲስ አበባ ዳርቻ ደረሰ። በአዲስ አበባ ላይ ታላቅ ዝናም ይዘንብ ስለነበር መንገዱን ድጥና አስቸጋሪ አደረገበት። ባዶሊዮ ቀበና ወንዝ ሲደርስ ወደ ሰሜን ታጥፎ ከኢጣልያ ኤምባሲ ገባ። አይሮፕላኖችም በአዲስ አበባ ኩተማ በመገለባጥ እያንዣበቡ ደስታቸውን ገለፁ።[5] ማርሻል ባዶሊዮም ለሙሶሊኒ አዲስ አበባ መግባቱንና ኢትዮጵያን መያዙን የሚገልጽ ቴሌግራም አስተላለፈለት።

አዲስ አበባ ከታላቅ ጭንቅ ውስጥ ወደቀች። የሰዉ ሁኔታ ታወከ። ንጉሠ ነገሥቱ ከሄዱበት ከሚያዝያ 24 ቀን ጀምሮ ባዶሊዮ እስከገባበት እስከ ሚያዝያ 27 ቀን 1928 ዓ.ም ድረስ፣ ከተማይቱ መሪም ሆነ አስተዳዳሪ አልነበራትም። ቤተመንግሥቱና አንዳንድ ድርጅቶች፣ በተለይም መሣሪያና ገንዘብ የነበረባቸው ተዘርፈዋል። ንጉሠ ነገሥቱ ጥለውት የሄዱትን ከተማ ክብር ለመጠበቅ ሲባል፣ የሀገሪቱ ምልክት የነበሩት አንበሶች በሀገር ወዳዶች እጅ ተገደሉ። በጠላት ላይ ጥቃት ለማድረስ በተደረጉ አንዳንድ ሙከራዎችና በርስ በርስ ብጥብጥ ጭምርም ከ1,500 የማያንሱ ኢትዮጵያውያን ሞቱ። ብዙዎቹም እግሮቻቸውን እየታሠሩ በኢጣልያ ወታደሮች እየተጐተቱ፣ በየመንገዱ ዳር እየተጣሉ ባዶሊዮ እንዲያያቸው ተደረጉ። እሱም እያያቸው፣ ምንም ሳይናገር አለፈ፣ ይኼም አበጃችሁ ለማለት መሆኑ ነው።

የአዲስ አበባ መያዝ ሮም ሲሰማ፣ የሮማ ከተማ ሕዝብ ተነቅንቆ ወጣ። በየዕለቱ መሶሊኒ ረጃጅም ንግግር ይናገርበትና ታላላቅ ፋክራ ይፎክርበት በነበረው ፒያሳ ቬኒሲያ ቡተባስው አደባባይ ተሰበሰበ። መሶሊኒ ኢጣልያ ብዙ ታሪክ የሠራች ሀገር እንደሆነች ገልፃ፣ ነገር ግን ኢትዮጵያን መያዝዋ ከሁሉም የበለጠ ሥራ እንደሆነ የሚያስረዳ ዲስኩር አደረገ። በዚህ ብቻ አላበቃም። ስለኢትዮጵያ ሕዝብም ተናገረ። "...ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሰላም ሆነለት። በሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ይገዙ የነበሩት ልዩ ልዩ ብሔረሰቦች፣ በኢጣልያ ሰንደቅ ዓላማ ሥር በዐጥታ ሥራቸውን እየሠሩ ሕይወታቸውን ለመምራት ግልፅ ምልክት አሳይተዋል..." አለ። በዚህ ንግግሩ፣ ሊወጣው ከማይችል ማጥ ውስጥ መዘፈቁን አላማወቁን መረዳት ይቻላል።

ከሰሜን የተንቀሳቀሰው የኢጣልያ ጦር ከፍ ሲል የተጠቀሰውን ሲሠራ፣ ከምሥራቅ በሐረርጌ በኩል የመጣው የጠላት ጦር የሐረርን፣

ከዚያም የድሬዳዋን ከተማዎች ሚያዝያ 30 ቀን እና ግንቦት 6 ቀን ያለምንም ችግር ያዙ። ይህም የሆነበት ምክንያት የንጉሠ ነገሥቱን ጥሎ መሄድ ሲሰሙ፣ በዚያ የነበሩት የኢትዮጵያ የጦር አለቆች ሠራዊታቸውን በትነው ጌታቸውን ተከትለው ስለሄዱ ነበር።[6] ግራዝያኒም ወደ አዲስ አበባ በባቡር ዘለቀ።

ማጣቀሻ ፅሑፎች

1. Richard Greenfield, *Ethiopia: A New Political History*, PP. 218.
2. ተክለፃድቅ መኩሪያ፣ *አፄ ምኒልክ እና የኢትዮጵያ አንድነት*፣ ገጽ 345-9።
3. ታደሰ ዘወልዴ፣ *የአባሳሸኝ ዘመን*፣ ገጽ 25-6
4. ከኩሉኔል ገብራይ ገብረ እግዚአብሔር ለጸሐፊው የተነገረ።
5. ጳውሎስ ኞኞ፣ *የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦርነት*፣ ገጽ 146-7።
6. Greenfield, PP.224-9

ምዕራፍ አሥራ ሰባት
ኢትዮጵያ ለምን እንደምን ተሸነፈች

ጦርነቱ ኢጣልያ በአጥቂነትና በወራሪነት፣ ኢትዮጵያ በተከላካይነት የቆመበት ነበር። የማይጨው ጦርነት የተደመደመው በኢጣልያ አሸናፊነት ነበር። እነዚህ ሁኔታዎች አያከራክሩም። የሚያነጋግረው ጉዳይ፦ ኢትዮጵያ ለምን፣ እንደምን በወቅቱ፣ በማይጨው ጦርነት ተሸነፈች? የሚለው ነው።

ይህንን ጠያቂ ቢጥልቅ መመርመር ያስፈልጋል። ኢትዮጵያ ማይጨው ላይ ድል ሆነች፣ ኢጣልያ ድል አደረገች። ባዶሊዮም ጦርነቱን እንደጨረሰ ቆጥሮ ፎከረ። ብዙ ሀገሮችም ጦርነቱ ያለቀ መስሎአቸው ኢጣልያ በኢትዮጵያ ላይ ያላትን ይዞታ አወቁ። ነገር ግን ጦርነቱ ቀጠለ። ጣልያንንም አበሳዋን አሳያት። ኢትዮጵያውያን ጦርነቱን በአርበኝነት መቀጠል ከቻሉ፣ ቀድሞውን ለምን ተሸነፉ? ከተሸነፉስ እንደምን ጦርነቱን መቀጠል ቻሉ? ኢትዮጵያ ለምን፣ እንደምን ተሸነፈች? የሚለውን ጥያቄ እንድንመረምር የምንገደደው በእነዚህ ምክንያቶች ነው።

1ኛ. **የጦር ግንባር ብዛት**፦ በአፄ ምኒልኩ የአድዋ ጦርነት ጊዜ የጦርነቱ ግንባር አንድ ብቻ ነበር። በአሰብ በኩል የነበረው ከቁጥር አይገባም። ስለዚህ ኢትዮጵያ ያለ፣ የሌለ ኃይልዋን አሰባስባ ለመከላከልና ጠላትዋን ድል መትቶ ለመመለስ ቻለች።

በማይጨው ጊዜ ግን እንዲህ አልነበረም። ኢጣልያ በሰሜንና በደቡብ ሶስት የጦር አውዶች ከፈተች። አንዱ ከአሥመራ የሚንቀሳቀሰው የሰሜኑ ጦር ሲሆን፣ እሱም ሁለት አፍት ነበረው። አንደኛው ከአክሱም ተነስቶ በሽሬ፣ በጉንደር፣ በጉጃም አድርጉ ወደ ደቡብ የሚዘልቅ ሲሆን፣ ሌላኛው ደግሞ ከመቀሌ ተነስቶ በአምባላጌ፣ በማይጨው፣ በደሴ አድርጉ አዲስ አበባ የሚገባው ነበር።

ኢጣልያ የከፈተችው ሁለተኛ የጦር ግንባር ከሞቃዲሾ የሚንቀሳቀስ ሆነ። የዚህኛው አንደኛው አፍት በሞያሌ፣ በሽላምቦ፣ በቀብሪደሐር፣ በጅጅጋ፣ በሐረር፣ በድሬዳዋ በኩል አድርጉ አዲስ አበባ የሚገባ ነበር። ሌላኛው የዚህ ጦር አፍት በዶሎ፣ በቦረና ነገሌ፣ በይርጋ ዓለም አድርጉ አዲስ አበባ የሚገባ ነበር። ሶስተኛው ግንባር ደግሞ በአሰብ ገብቶ፣ በሰሜኑ የጦር ግንባር የተሰለፈውን ጦር ሽንጥ ደሴ ላይ እንዲቆርጥ የተሰማራ ነበር። እነዚህ የጦር ግንባሮች እያንዳንዳቸው ከአዲስ አበባ ሲለካ እስከ ሺህ ኪሎ ሜትር ድረስ ከፍተኛ ውጥረት ፈጠሩ። በጦርነቱ ላይ ወሳኝነት ካላቸው ሁኔታዎች አንዱ ይህ ነበር።

2ኛ. **የመሣሪያ እጥረት**፦ በአንድ ጦርነት ላይ ወሳኝነት ከአላቸው ጉዳዮች ዋናው መሣሪያ ነው። ኢጣልያ ለጦርነቱ አስፈላጊ መስለው የታዩአትን መሣሪያዎች ሁሉ በመልክ በመልካቸው ለቁጥር በታከተ ብዛት አዘጋጅታለች። ለአግረኛው ጦርብዙ ጉራሽ ጠመንጃ ከበቂ ጥይት ጋር

ሰርታ አስይዛለች፣ የእጅ ቦምብ አስጨብጣለች። የሚንቀሳቀስበት ታንክና መኪና፣ እንደዚሁም በቂ ስንቅ አቅርባለች። በሰማይ ደግሞ ቦምብ ጣይ አይሮፕላን፣ እንዲሁም የተከለከለ ልዩ መርዝ በገፍ አዘጋጅታ አገልግሎት ላይ እንዲውል አድርጋለች።

በወቅቱ የነበረው የኢትዮጵያ መንግሥት በበኩሉ ጦርነቱ እስከ ተቀሰቀሰበት ጊዜ አንዳች ዝግጅት አላደረገም። እንዲያውም ኢትዮጵያ እንኳን አዲስ መሣሪያ ልትጨምር፣ የነበራትንም በወግ አልያዘችም። ወደፊት እንደምንመለከተው፣ ለምሣሌም የኮረማሽን መሣሪያ ክምችት በአግባቡ አገልግሎት ላይ እንዲውል አላደረገችም።

3ኛ. **የሠራዊት ሥልጠና**፡- ኢጣልያ ጥሩ ሠራዊት አሠልጥናለች። የፋሽስት ካድሬዎችን በአመራር ረገድ አሰልፋለች። ክራስዋ ተወላጆችም በስተቀር የተቻላትን ያህል አስካሪ ወታደሮችን ከሊብያና ከሶማሊያ መልምላለች። ቡተሰይ የኤርትራን ተወላጆች በደንብ አሰልጥና አሰልፋለች።

በኢትዮጵያ በኩል ሁኔታው ከዚህ የተለየ ነበር። ክውጭ የሚጠበቅ አንዳች ድጋፍ አልነበረም። ክራስዋም ሠራዊት የምኒልክ ነፍጠኛ ባዶውን የቀረ፣ የተበላጨ፣ በአሠፋፈሩ የተበታተነ፣ በስሜቱም ያዘነና የተከዘ ነበር። በአዳዲሶቹ ሹማምንት የተቋቋመው ሠራዊት ደግሞ የሙያ ብቃት አላገኘም ነበር።

በወቅቱ ለኢትዮጵያም ሠራዊት ሥልጠና ተሰጥቶ የነበረ ቢሆንም፣ መጀመሪያ ነገር ለጥቂቶች ብቻ እንጂ ለሁሉ አልተዳረሰም፣ ለእነሱም ቢሆን በበቂ ሁኔታ አልተሰጠም፣ ለብለብ ሆነ። ከሥልጠናውም የሚበዛው በሠልፍ ሆኖ ማለፍ እና ግራ ቀኝ እኩል እየረገጡ መራመድ ነበር። የመከላከል እና የማጥቃትን፣ የመሣሪያ መለማመድን፣ እንደ ታንክ የመሣለሱ መሣሪያዎች መጠቀምን አልጨመረም። ስለዚህ የኢትዮጵያ ሠራዊት ታንክ በማረከ ጊዜ የነበረው ዕድል፣ ጠላት መልሶ እንዳይጠቀምበት ማቃጠል እንጂ እሱ ራሱ መጠቀም አልነበረም። አሰልጣኞቹ ፈረንጆች መሆናቸውም ሌላው ችግር የፈጠረ ጉዳይ ነበር።

4ኛ. **ሕዝባዊ ሥነ ልቡና**፡- እንደ መሣሪያ፣ በጦርነት ወቅት ወሣኝነት ከአላቸው ሁኔታዎች አንዱ የሕዝብ ሥነ ልቡና ነው። የኢጣልያ ሕዝብ አንድነቱን አጠናክሮ በአፍላ የለውጥ ሂደት ላይ ነበር። በዚህ ላይ ደግሞ አዲስ የተከሰተው የፋሽስት ፓርቲ የሚበዛውን ወገን ያረካ አመራር አስገኝቶለት ነበር።

በኢትዮጵያ በኩል ግን የነበረው ሁኔታ ከዚህ የራቀ ነበር። አስቀድሞ በልጅ ኢያሱና በንግሥት ዘውዲቱ መካከል በተካሄደው የሥልጣን ሽኩቻ፣ ኋላ ደግሞ ራስ ተፈሪ ከንግሥት ነገሥታት ዘውዲቱ ሥልጣን በወሰዱበት መንገድ ልቡናው የተነካው ይብዛ ነበር። የንግሥት ነገሥታት ዘውዲቱን አሟሟት ሳይረሳ፣ የልጅ ኢያሱ ተጨምሮበት የተከዘው በርክቶ ነበር። በዚህ

ላይ አፄ ምኒልክ ጀምረውት የነበረው የማህበራዊ ውህደት ስለአልቀጠለ በደቡቡና በሰሜኑ ሕዝብ መካከል የልብ አንድነት አልነበረም።

5ኛ. **የጦር አመራር**፡- በጦር አመራር ረገድም በሁለቱ አገሮች፣ ግለትም፡- በኢጣልያና በኢትዮጵያ መካከል፣ ልዩነት ነበር። የኢጣልያን ጦር እንደእነ ደቦኖ፣ ግራዚያኒ የመሰሰሉ አስበው የሚሠሩና (ጨካኝ ቢሆኑም) ቆራጥ የጦር መሪዎች ነበሩት። በፖለቲካውም ረገድ ደግሞ የፋሽስት ፓርቲ አፍላ ሥልጣን ላይ ነበር። በዚያ ሁሉ ላይ ሙሶሊኒ ራሱ በሙሉ ልቡ ጦርነቱን የመራ ሲሆን ንጉሡም፣ ጳጳሱም ተባበሩት።

በኢትዮጵያ በኩል እንደዚህ አልነበረም። በንጉሠ ነገሥቱ ቅሬታ የነበረው ብዙ ነበር። በጦር አመራራቸው ያላመነውም ቀላል አልነበረም። ምክር ቤቱም፣ ሠራዊቱም፣ መኢንንቱም ምክር የመስጠትና የመደመጥ ዕድል አላገኙም። ንጉሠ ነገሥቱ የፈረንጅ እንጂ የወገኖቻቸውን ምክር የማድመጥ ፍላጐት አልነበራቸውም። ከአዲስ አበባ እስከ ሀዩ ድረስ አንዳች ምክር አልተደረገም። ሁሉም ያቆበቆበው ሽሽቶ ነፍሱን ለማዳን ሲሆን፣ አብዛኛው ደግሞ ልቡ ወደጠላት አዘንብሎ ነበር።

6ኛ. **የጦርነት ሥልት**፡- የኢትዮጵያ ሕዝብ የራሱ የሆነ የጦርነት ሥልት አለው። በኢጣልያ ወረራ ጊዜ በዚያ የመጠቀም ዕድል አላገኘም። እንዲዋጋ የተፈለገው በዘመናዊ ሥልት ነው። በእሱ ደግሞ ሥልጠናም፣ መሣሪያም አላገኘም።

በጣልያኖች በኩል ግን በእቅድ የመንቀሳቀስ ሥልት ነበር። የጦር ግንባሮች ሁሉ በአንድ ማዕከላዊ ዘዴ የተቀነባበሩ ነበሩ። እግረኛውና ታንከኛው፣ አየር ኃይሉና ባሕር ኃይሉ በጉበረት ሠሩ።

7ኛ. **መረጃ**፡- ኢጣልያ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዋ ጠንካራ ነበር። ሚሲዮናዊ፣ ዲፕሎማት፣ ነጋዴ፣ ጥናትና ምርምር አድራጊ እያስመሰሉት በሳከቻቸው እና በከፈሉቻቸው ሰዎች አማካኝነት የኢትዮጵያን ሁኔታ አጠናች። ይህም አዲስ ነገር አልነበረም። በአድዋም ጊዜ ተጠቅማበታለች።[1] በዚህ ላይ ደግሞ የኢትዮጵያ የጦር መሪዎች በሬዲዮ ቴሌፎን የሚያስተላልፉትን ምስጢር በሙጥለፍ ተጠቀመች።

በኢትዮጵያ በኩል ግን የጣልያንን የውስጥ ሁኔታ ለማወቅ የተደረገ መከራ አልነበረም። የራስዋን ምስጢር የመጠበቅ ችሎታም እንኳን አልተገኘም። ከዚህ የተነሣ ነው የማይጨው ጦርነት የሚከፈትበት ቀን ምስጢር አስቀድሞ ለጠላት የደረሰው።

8ኛ. **መገናኛ**፡- የኢትዮጵያ ጦር መንገዱን የሚቀይስበት ባሕላዊ ዘዴ አለው። በዘመቻ ጊዜ መንገድ ለሠራዊቱ እንደሚያመች ሆኖ፣ ጠላት በማያውቀው፣ በማይጠረጥርበት መሥመር ይከፈታል። አንዱ ሠራዊት በአንድ መንገድ፣ ሌላው ሠራዊት በሌላ መንገዱ ይጓዛል። ለየብቻው በተራ፣ በተራ ይዋጋል። በማይጨው ጊዜ እንዲህ አልተደረገም። ከንጉሠ ነገሥቱ

አውቶሞቢሎች በስተቀር ሌሎች አንድ መቶ መኪናዎች በሌሉበት በዛን ጊዜ፣ ከአዲስ አበባ እስከ ኮረም የመኪና መንገድ ተሠራ። በየወንዙ ላይ ድልድይ ተጣለ። ነገር ግን ለጠላት መግቢያ እንጂ፣ ለኢትዮጵያ መከላከያ አልጠቀመም። የሕዝብ ጉልበትና ገንዘብ ለራሱ መጠቂያ ሆነ።

በኢጣልያ በኩል ሁኔታው ያለቀ ነበር። እግረኛው ሠራዊት በእግሩ ይጓዛል። በተያዘው አገር የመኪና መንገድ ይሠራል። ወደፊት በተከታታይ ለሚደረገው ጦርነት አዲስ በተዘጋጀው መንገድ በመኪና ይጓዛል።

9ኛ. **ክህደትና ከሀዲዎች**፦ እርስበርሱ በጥቅምና በሥልጣን ቢናቆርም፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ የውጭ ጠላት ሲመጣበት አንድነቱን አጠንክሮ ይመክታል። ይህ ኢትዮጵያውያን የታወቁበትና ሌላው የተደነቀበት ባሕሪያቸው ነው። ነገር ግን በኢጣልያ ወረራ በጦርነቱ ጊዜ የተከሰተው ለየት ባለ ሁኔታ ነበር። ከንጉሠ ነገሥቱ ባለሟሎች አብዛኞች ለጠላት እደሩ። እነቀኛዝማች ተክለ ማርቆስን፣ እነአምባሳደር ወልደማርያምን /ፓሪስ/ ለአብነት መጥቀስ ይቻላል። ሁሉን መዘርዘር ግን ጊዜ ማጥፋት ነው። በአንጻሩ ደግሞ ምንም ጥቅም ያላገኙ፣ ከዚያም አልፎ ቅጣት የደረሰባቸው ለኢትዮጵያ ቆሙ። በዚህ ረገድ ደግሞ አርባ የተገረፉትን ደጃዝማች በየነን፣ በአሥር ላይ የነበሩትን ደጃዝማች አውራሪስ ዱሱን መጥቀስ ይገባል። የዚህ ዓይነቶቹም ሰዎች ቁጥር ብዙ ነው። ከሀዲዎች ምን ምን ሥራ እንደሠሩ፣ ምን ምን ጉዳት እንደአደረሱ ይህንኑ በሚመለከተው ምዕራፍ የተዘረዘረ ስለሆነ ከዚያው መመልከት ነው።

10ኛ. **የጦርነት ጊዜ**፦ ጦርነቱ የተደረገበት ጊዜ ወሣኝነት ነበረው። ዘመቻው ፈጣን፣ ውጊያው አጭር ነበር። በጥቅምት 1923 ዓ.ም ሙሉ ሥልጣን የያዙት ንጉሠ ነገሥቱ ገና አስተዳደራቸው አልጠነከረም ነበርና፣ ለኢትዮጵያ ምቹ ጊዜ አልነበረም። የጦርነቱ ጊዜ የተወሰነው በኢጣልያ ብቻ ነበር። እስዋም የተንቀሳቀሰችው አንድነትዋን ገንብታ፣ የጦር ኃይልዋን አዘጋጅታ፣ የዓለምን ሁኔታ አስተካክላና ገምታ በአመቻት ጊዜ ነበር።

ስለዚህ ኢትዮጵያ የተሸነፈችው በእነዚህና በሌሎችም ብዙ ምክንያቶች ነበር። ሁሉን መዘርዘር አይመችም። ማተኮር የሚገባው ኢትዮጵያ በእነዚህ ሁኔታዎች ከተሸነፈች በኋላ እንደምን ጦርነቱን መቀጠል ቻለች? ከሚለው ጥያቄ ላይ ነው። እሱንም ወደፊት እንመለከታለን።

ማጣቀሻ ፅሑፎች

1. ተክለፃድቅ መኩሪያ፣ *አፄ ምኒልክ እና የኢትዮጵያ አንድነት*፣ ገጽ 161-70።

ምዕራፍ አስራ ስምንት
የገጠሩ ሕዝብ ሁኔታና የአርበኝነት እጀማመር

በኢትዮጵያ የታሪክ ጉዞ ወሳኙ ሕዝብ የገጠሩ ነው። የከተማው አይደለም። ለዚህም እንደ ምክንያት ሊጠቀስ የሚችለው በገጠር የሚኖረው ሕዝብ ከከተማው መብዛቱና በሀገር ጉዳይ የገጠሩ ሕዝብ ልቡና በአመዛኙ የማያወላውል መሆኑ ነው። በዘመቻው ጊዜ ገጠሩ ባዶ ሆነ። ጀግናው ወንዱ ዘመተ። ሴትና ልጅ፣ ሽማግሌ ብቻ ቀረ። የሚታዩት ነገሮች ሁሉ አስፈሪ ሆኑ። ጦርነቱ የገጠሩን ሕዝብ አስገነገነው። ዘማች ከማይጨው ዘጊሳ ሲመለስ የታየው ሁኔታ ደግሞ ይበልጡኑ አስደነገጠው። የንጉሡ አገር ጥሎ ወደ ፈረንጅ አገር መሄድ አስገረመው። ፈረንጅ እዚህ አገር ሲገባ አሳቸው ወደ ፈረንጅ ሀገር የሄዱበት ጥበቡ አልታይህ አለው። የመሣፍንቱ፣ የመኳንንቱ ክህደት አስደነቀው።

ከዘመቻ የተመለሰው ሰው ጥቂት ነው። የሚበዛው በጦርነቱ ላይ ሞቶአል። መርዶው፣ ውሎ የሚደረገው በአያንዳንዱ አካባቢ፣ በየተራ ሆነ። ሁኔታዎች ተዘበራረቁ። ትርምስምሱ ወጣ። እኔ ራሴ በአካባቢዬ ያየሁትን ከመግለፅ በስተቀር ሌላ ማስረጃ መስጠት አልችልም። ስለዚህ በቡልጋ የደረሰውን በአጭር፣ በአጭሩ እመለከታለሁ።

ከማይጨው ጦርነት በኋላ በህይወት የተረፈው የኢትዮጵያ ሠራዊት አመላለስ አሳዛኝ ነበር። አብዛኛው አለ መሣሪያው እና ራቁቱን ነበር። ሌላው የተበጫጨቀ ትንሽ ልብስ ቢኖረው እያፈረ ሌሊት ተደብቆ ከቤቱ የገባም አለ። እኔ ከማውቃቸው ሰዎች መሣሪያቸውን እንደያዙ፣ የጦር ልብስ እንደለበሱ ከትውልድ ሀገራቸው የገቡ አለቃ /ፊታውራሪ/ ወልደፃድቅ ዘውዴና ሶስት አሽከሮቻቸው ብቻ መሆናቸው እስከ ዛሬም ትዝ ይለኛል።

ከዘመቻው መልስ ሕዝቡ እየተሰባሰበ መምከር ያዘ። የመጀመሪያው ጉዳይ መሪ መምረጥ ነበር። እኔን ምረጡኝ የሚል አልነበረም። ሁሉም ፈርቶ እኔ አልችልም፣ አልፈልግም ባይ ሆነ። ከብዙ ምክር በኋላ በየአካባቢው የጉበዝ አለቃዎች ተመረጡ። የጉበዝ አለቆች ደግሞ እየተሰባሰቡ ይማከሩ ጀመር። የአንዱ አገር የጉበዝ አለቃ አንድ፣ የሌላው ሌላ ይላል፣ አይስማሙም፣ ይከፋፈላሉ። ሕዝቡም እነሱን እየተከተለ ይከፋፈላል። ግለሰቦች ሲለሰቻቸው የግላቸውን እርምጃ ይወስዳሉ። ለዛሬው አንባቢ ይህ አግላለፅ ልብወለድ ይመስለዋል። ግን እውነት ነው። አንዳንድ ማስረጃ ለመስጠት እፈልጋለሁ።

ሙገሬ ዛላ፣ ሜጢ በሚባለው ቦታ "ለኢጣልያ እንመን፣ የለም እንሸፍት" በሚል ሐሳብ ሕዝብ እርስ በርሱ ተከፋፍሎ ታሳቅ ክርክር ተካሄደ። "እንሸፍት!" በሚለው ሐሳብ ተስማማ። አቶ ህብተ ኢየሱስ የሚባል ሰው እንቢ ስላለ ሀገር አደመበት። "ከቤቱ ሰው ቢሞት ላያቃብረው፣ አሳት

ላያስጭረው፣ ከንጉሥ መንገድ ውጭ ውሃ ላያስቀዳው ተማማለበት። ከብቱ አንድ ቀን ጫውሶ ዋለበት። ሚስቱ ጥላው ሄደች። ሲጨንቀው ማሩኝ ብሎ ገባ። በዚያች የገጠር አካባቢ የሽፍትነት ሥራ እንዲህ ተጠነሰሰ።

በበረከት ወረዳ ዋጩ ከሚባል ቦታ አቶ በየነ ወልደ ገብርኤል የተባለ ሰው ነበር። ሀገሩ አልሰማማለት ስላለ እሱ ብቻውን ሸፈተ። ጠላትም ወሬውን ሰምቶ ከበበው። በተከበበ ጊዜ አንድ ለበን ጠመንጃ ከአሥር ጥይት ጋር ብቻ ነበረው። ከሁለት ቀን የተኩስ ልውውጥ በኋላ በየነ ሞተ። አሟሟቱም ራሱን በመግደል ነበር። የሞተውም ከአሥሩ ጥይት በስምንቱ ስምንት ሰው ገድሎ፣ ዘጠነኛዋን እሱ ራሱ ጠጥቶ ነበር። አሥረኛዋ መጠባበቂያ ነበረች።

የጠላት ኃይል እያየለ ሲሄድ ጦርነቶች ተቀሰቀሱ። ጦርነቱ ከባድ፣ አስደንጋጭና አስፈሪ ሆነ። ቀስ በቀስ ጀግናው ተንቀሳቀሰ። እርስበርሱ እየተማማለ ሽፍትነቱን ያዘ። ጠላት ሊያውቅና ሊገነዘበው የማይችል አዲስ ሁኔታ ተፈጠረ። በዋናው ጦርነት ጊዜ የታዩት ነገሮች ሁሉ ፍርስ ሆኑ። የጦሩ ግንባር በየተራራው፣ በየሸንተረሩ፣ በየጎጡ ሆነ። አሸንፎኮ ብሎ በድንፋታ የገባው የጠላት ጦር ግራ ገባው። ታንክ የማይደርስበት፣ መድፍ ሊንቀሳቀስ የማይቻልበት፣ በአይሮፕላን በመደብደብ ውጤት የማይገኝበት አዲስ የጦር ሥልት ተከፈተ። ምንም አይነት ሥልጠና ሳያስፈልገው ሽፍታው በዱላ፣ በጦር፣ በጉራዴ የጠላቱን መሣሪያ እየነጠቀ መሣሪያ ጨበጠ። የመሣሪያውንም አጠቃቀም አርስበርሱ ተማማረ። ለየግል ጥቅማቸው ከሚከፋፈሉት ሹማምንት ሲላቀቅ፣ ሥነ ልቡናው አንድ ሆነ። በቀድሞዎቹ መሪዎች ፈንታ አዳዲስና ቆራጥ መሪዎች አገኘ። አዳዲሶቹ መሪዎች ለሹመት፣ ለሽልማት ሳይሆን ለሀገር ነፃነት፣ ለወገን ደህንነት የቆሙ መሆናቸውን አረጋገጡ። ሕዝቡም ተከተላቸው። የጦርነቱ ሥልት ከፈረንጅኛ ዘዴ ተላቅቆ ፍፁም ኢትዮጵያዊ ሆነ። ምሥጢራዊ መረጃ ከሀበሻ ወደ ፈረንጅ መንቆርቆሩ ቀርቶ ከፈረንጅ ወደ ሀበሻ ይፈስስ ጀመር። ጣልያን የሚያስበው ሁሉ ለሽፍቶቹ ከየቦታው በሰው ይደርሳቸው ጀመር። የመገናኛ ችግር የሚያጋጥመው ጠላት ራሱ ሆነ። የሽፍቶቹ ሥራ በየቀዬአቸው መዋጋት ስለሆነ፣ የመጓጓዣ ችግር አልነበረባቸውም። ከሀዲዎች የክህደት ማቃቸውን ለብሰው ከጣልያን ጉያ ተሸጉጡ። ከሕዝብ ስለተነጠሉ አንዳች ማድረግ ተሳናቸው። ጣልያን የጦርነቱን ጊዜ በማፋጠን ያገኘውን ጥቅም፣ ሽፍቶች የጦርነቱን ቦታ በማብዛትና ጊዜውን በማራዘም አጠፉበት። ግራ አጋቡት። ሥራቸውም በሕብረተሰቡ ዘንድ ግንዛቤ እያገኘ ሲሄድ፣ ከሽፍትነት ወደ አርበኝነት ተሸጋገረ።

አርበኞች የፈፀሙትን ሥራ ለመገንዘብ የጦርነት፣ የአርበኝነት፣ የታጋይነት፣ የሽፍትነት ልዩነት ምን ላይ እንደሆነ ለይቶ ማወቅ ይገባል። ሁለት መንግሥታት የሚያካሂዱት ውጊያ ጦርነት ይባላል። አርበኝነት ደግሞ

አንድ ሕዝብ በሌላ አገር ሕዝብ ተወርሮ ነፃነቱን በተገፈፈ ጊዜ መንግሥት በሌለበት ሁኔታ የሚያካሂደው ትግል ነው። ታጋይነት አንድ ግለሰብ ብቻውን ወይም ከጥቂቶች ጋር ስለሀገር የሚያካሂደው ተጋድሎ ነው። ሽፍትነት ግን በግል ጉዳይ በመንግሥት ላይ አመፅ ማካሄድ ነው።

የኢጣልያ ወረራና የኢትዮጵያን የተጋድሎ ስልት ስንመለከት ከእነዚህ ሦስት የውጊያ ስልቶች በሁለቱ፣ ማለትም በጦርነትና በአርበኝነት የተካሄደ ሆኖ እናገኘዋለን። ዝርዝር ሁኔታውንም ከዚህ ቀጥሎ እንመለከታለን።

1ኛ. የወልወል ግጭት ከተከሰተበት ከህዳር 27 ቀን 1927 ዓ.ም እስከ ሚያዝያ 24 ቀን 1928 ዓ.ም ድረስ የተካሄደው ውጊያ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴና ቤኒቶ ሞሶሎኒ በርዕሣነ ብሔርነት የቆሙበት የሁለት መንግሥታት ጦርነት ነበር።

2ኛ. ንጉሠ ነገሥቱ ሀገር ጥለው ከሄዱበት ከሚያዝያ 25 ቀን 1928 ዓ.ም አንስቶ ተመልሰው በአሜድላ በኩል የኢትዮጵያን መሬት እስከረገጡበት እስከ ጥር 16 ቀን 1933 ዓ.ም ድረስ ኢትዮጵያውያን ያካሄዱት ጦርነት ለሀገር የመከላከል የአርበኝነት ተጋድሎ ነው።

3ኛ. ጥር 12 ቀን 1933 ዓ.ም የጉንደር ጦርነት ተፈጽሞ ጀነራል ናዚ እስከተማረከበት እስከ ህዳር 1934 ዓ.ም ድረስ ያለው ደግሞ በኢትዮጵያና በኢጣልያ መንግሥታት መካከል የተካሄደ ጦርነት ነው። የእንግሊዝ ድጋፍ ከኢትዮጵያ ወገን መሆኑ ሁኔታውን አይለውጠውም።

4ኛ. በዚህ ፅሑፍ ውስጥ በእንዳንድ ቦታ ሽፍትነት እንደነበረ ተገልያለል። ይህ አገላለፅ ሰዎች በግላቸው የተጫወቱትን ሚና በዚያን ጊዜ በነበረው አስተሳሰብ ለማሳየት እንጂ፣ ለግል ጥቅማቸው ያካሄዱት ትግል አለመሆኑን አንባቢ እንዲረዳው ያስፈልጋል።

የአዛዥ ሙሉ ሰውን የዕለት ማስታወሻ መነሻ ብናደርግ የአርበኛው ሐሳብ ከጠላት ጋር ተያይዞ ለመሞት፣ ባይሞትም ስቃይ ለማሳየትና ለማየት፣ ለሀገርና ለወገን ለኢትዮጵያ መንግሥት ሠንደቅ ዓላማ ለመሰዋት ነበር። እንደ አለቃ /ፊታውራሪ/ ወልደ ፃድቅ ዘውዴ አባባል ደግሞ ለሃይማኖትና ለሀገር ለመሞት ነበር። የአብዛኛው አርበኛ ሐሳብ ከዚህ አምብዛም የተለየ አልነበረም። እንደ ደጃዝማች መንገሻ ወሰኔ ያሉት ደግሞ ለንጉሠ ነገሥታቸው የቆሙ ነበሩ።

ከዚህ ላይ ሊጠቀስ የሚገባው ነጥብ በዚያን ጊዜ የአርበኝነት ሥራ በዓለም ውስጥ የተለመደ እንዳልነበረ ነው። በዋናው ጦርነት ድል ከሆኑ፣ መሪዎቹ ጥሎአቸው ከሄደ ወይም ከሞተ በኋላ በራሳቸው ኃይል እየተንቀሳቀሱ ከጠላታቸው የታገሉ ሀገሮች እስከዚያን ጊዜ ድረስ አልታዩም። ብዙ ሀገሮች በቀላሉ ለቅኝ ግዛት የተጋለጡት፣ ባዶሊዮም ጦርነቱን ጨረስኩ፣ ሰላም ሆነ ያለው በዚህ ዓይነት የአርበኝነት ተጋድሎ መኖሩን ስለአላወቀ

ነው። ስለዚህ ኢትዮጵያ የአርበኝነት ተጋድሎ መሠረት መሆንዋን መገንዘብ ይገባል።

በዚያን ጊዜ በተካሄደው የአርበኝነት ተጋድሎ የመጀመሪያው ትንቅንቅ ከጣልያን ከራሱ ጋር አልነበረም፤ ከባንዳ ጋር እንጂ። የባንዳው ኃይል ቀላል አልነበረም። ለጥቅም በተገዙ ከሀዲ መኢንንት እየተመራ ለመደበኛው የጠላት ጦር ግንባር ቀደም እየሆነ በብዛት የሚግተለተል የገበሬ የባንዳ ሠራዊት ነበር። በአብዛኛው ከአካባቢው የተመለመለ በመሆኑ መውጫ መግቢያውን ስለሚያውቅ የማጥቃት ኃይል ነበረው። በመሆኑም የመከላከሉ ሥራ ከበደ። በዚሁ ከቀጠለ የአርበኝነት ሥራ ለማካሄድ አይቻልም። በምክርና በተግሣፅ ማስታገስ የተቻለው ጥቂቱን ብቻ ሆነ። ስለዚህ የጠላት መሣሪያ እየሆኑ ምስጢር በሚያቀብሉና ነገር በሚያመላልሱ፣ መሣሪያ ታጥቀው ከጠላት ጐን በቆሙ ባንዶች ላይ የኃይል እርምጃ መውሰድ ግድ ሆነ።

በባንዳ ላይ የኃይል እርምጃ የመውሰድ ጉዳይ አስፈላጊ የመሆኑን ያህል በጥንቃቄ እንዲፈፀም አስፈለገ። እየተገደደ ያለፍላጐቱ አንዳንድ ሥራ የሚሠራውን ሁሉ መግደል ብዙ ሰው መፍጀትና ሀገርን እንደሚጎዳና ወዳጅ፣ ዘመድ መቀየሙ ስለማይቀር ችግሩ ቀላል እንደማይሆን ታወቀ። የአያንዳንዱ ባንዳ ግብር እየተመረመረ በፍርድ ይቀጣ ጀመር።[1] አርበኛ በባንዳ ላይ እንደአሻው እርምጃ መስዶ ቢሆን ኖሮ፣ የሕዝብ ድጋፍና ትብብር አያገኝም ነበር። ስለዚህ በጦር ሜዳ ካልሆነ በስተቀር ባንዳ ያለፍርድ እንዳይገደል ጥንቃቄ ተደረገ። ይህ አሠራር ጥሩ ውጤት ሰጠ።

በዚህ ዓይነት የኢትዮጵያ ሰው ከሦስት ተከፈለ። አንዱ ወገን ለሀገር ለነፃነት ብሎ አርበኝነትን ቀጠለ። ሁለተኛው ወገን ከጠላት ጐን በመቆም የሀገር ጠላትነቱን በግብር ማረጋገጡን ያዘ። ሦስተኛው ወገን ለላማዊ ኑሮውን ተከተለ።

ከዚህ ለታሪክ አወንታ ሊባል መጠቀስ ያለበት ጉዳይ። ለጠላት መሣሪያ እየሆኑ በሀገርና በወገናቸው ላይ ከባድ በደል የፈፀሙ ወንጀለኞች ለፍርድ እንኳን ሳይቀርቡ መቅረታቸው ነው። አሱን ደግሞ በቦታው እንመለከታለን።[2]

ማጣቀሻ ፅሑፎች

1. ሙሉሰው ምትኩ፣ *ክሽዋ አለክ ሱዳን ጠረፍ*፣ ገጽ 9 እና 16።
2. ከድል በኋላ ትግል የሚለውን ምዕራፍ ይመልከቱ።

ምዕራፍ አስራ ዘጠኝ
የሲዳሞ ተጋድሎ

"እንዴት ሲዳሞን ወንድ የሌለበት አድርጉ ጠላት ይግባበት?" ተብሎ ከንጉሠ ነገሥቱ የተላለፈለትን አዋጅ የሲዳሞ ሠራዊት ተቀበለ። ያፈገፈገው ተመልሶ ከጦር ግንባር ገባ። በየአለበት እየተቀረጠ የቀረውም ተመልሶ በአለቆቹ ዙሪያ ቆመ። ነገር ግን ማዕከላዊ አመራር ላያገኝ ቀረ። ድጋፍም የማያገኝ መሆኑን አወቀው።

ድኑን በተባለው ቦታ ዝግጅቱን ቀጠለ፣ አጠናቀቀም። ደጃዝማች ገብረ ማርያም ጦራቸውን ይዘው ግንቦት 25 ቀን 1928 ዓ.ም ከዋደራ ድኑን ገቡ። በደረቅ ሰማይ ዝናም ዘንሞ ውሃ እየጠጡ ተጓዙ። ነገር ግን የጦር አቅዳቸውን በሥራ ላይ ከማዋላቸው በፊት ከሃዲው ፊታውራሪ አደመ ነፍሶ ከአሳቸው ተነጥሎ ከጣልያኖች ጋር ተቀላቀለ። የጦር ሚስጢራቸውንም ለጠላት ሰጠባቸው።

ጠላት የኢትዮጵያን ጦር ምሥጢር ከአደመ ከተረዳ በኋላ ግንቦት 9 ቀን 1928 ዓ.ም ድኑን የተባለውን አካባቢ በአይሮፕላን መደብደብ ጀመረ። በዚህ ጊዜ በአርበኞች ዘንድ ምክር ተደርጉ በፍጥነት የነገሌን ምሽግ ለማጥቃት ተወሰነ። ጠላት በ25 ካሚዮን እግረኛ ጦር አቀረበ፣ እንዲሁም ለካሚዮኖችና ለታንክቹ ደጀን አደረገላቸው። ጠላት ፈጥኖ ተንቀሳቀሰ። ግንቦት 11 ቀን ጦርነቱ ተከፈተ። እነ ሻለቃ /ደጃዝማች/ በቀለ ወያ ኢያነጣጠሩ በመድፍ የጠላትን ወታደር ረፈረፉት። የኢትዮጵያ ጦር ከፊት ለፊት በብርታት ተዋጋ። ጠላት ወደኋላው ለመመለስና ከምሽጉ ለመሸሹጥ ሞከረ። ነገር ግን አስቀድሞ ከኋላ ዙሮ መንገዱን ቆርጦ የነበረው የኢትዮጵያ ጦር ይጠዘጥዘው ጀመር። ወዲያው የጨበጣ ውጊያ ተያዘ። ጥይት ከመተኮስ ይልቅ በጉራዴ መጨፍጨፍ ተሻለ። አይሮፕላኖች በሚያካሂዱት ድብደባ የሚደርሰው ጉዳት የጋራ ሆነ።

ለእርዳታ ከነገሌ ቢታንክና በካሚዮን የመጣው የጠላት ጦር አንዳች ማድረግ አቅቶት ወደ ምሽጉ ተመለሰ። እፁብ ድንቅ የተባለ ውጊያ ተካሄደ። ከጥዋቱ በ4 ሰዓት የተጀመረው ጦርነት ከቀትር በኋላ በ8 ሰዓት በኢትዮጵያውያን አሸናፊነት ተፈፀመ። አንድ መቶ ሃያ ድግን መትረየስ፣ አሥራ ሁለት ባለውሃ መትረየስ፣ አንድ ሺህ አርባ ሰባት አልቤን ጠመንጃ፣ ብዙ ሺህ ጥይት፣ አንድ መቶ ሃምሳ አራት ምንሽር፣ ሦስት ሳንፊል የመገናኛ ሬዲዮ፣ ሦስት መቶ የመድፍ ጥይት፣ ሦስት መቶ ሃምሳ በቅሎ ተማረከ። ሃምሳ ስምንት ኢጣልያኖች፣ ሰባት መቶ ሱማሌዎች ሞቱ። እነ ፊታውራሪ ወልደ ሚካኤል ኃይሉ ነገሌ ከምሽጉ የጣልያኑን መኮንን ማርከው አመጡ። በኪሱም "ልጃችን አደራህን ...ወደፊት አትሂድ፣ እንዳትሞት፣

ኢትዮጵያውያን ጀግኖች ናቸውና" የሚል ወረቀት ተገኘ። ከወላጆቹ የተፃፈለት ነበር።

ጣልያን በዋደራ በኩል ሰብሮ ለመግባት የነበረው ሃሳቡን በአደመ ነፍሶ ምክር ለውጦ፣ በሜጋ በኩል ዞሮ ሲጻሞ ለመግባት አሰበ። ይህንን የሰማው የኢትዮጵያ ጦር ክንዱን ወደ ዋደራ መልሶ ነዋሪ ለመምሰል ቦታ እየተከፋፈለ ቤት መሥራት ያዘ። ቤተክርስቲያንም ሠራ። በአንፃሩ ደግሞ መልካ ጉባ ላይ የነበረውን ድልድይ ሰብሮ የጠላቱን ፅቅድ ለማስናከል ወሰነ።

ለዚሁ ለድልድዩ ሠበራና ለመንገድ ቆረጣ የተመረጡ ወታደሮች ተላኩ። ነገር ግን ከታሰበው ቦታ ሳይደርሱ ቆርቆሮ ከተባለው ቦታ የጠላት ጦር ገጠማቸው። ታላቅ ጦርነት ተደረገ። ውጊያውም ለምንት ቀን ፈጀ። ብዙዎች ሞቱ፣ ብዙዎቹም ቆሰሉ። በዚህ ምክንያት የተላከው የኢትዮጵያ ጦር ዓላማውን መፈፀም አቅቶት ወደ ዋደራ ተመለሰ።

ጣልያን ከነገሌ ወደ ሜጋ ጉዞ ጀመረ። የኢትዮጵያ ልጆች በሩን ይዘው ጠበቁት። ለኔ 19 ቀን ገጠሙት። ከጥዋት ጀምረው ሲዋጉ ውለው አግረኛውን ጦር መለሱት። ነገር ግን በአይሮፕላንና በታንክ እየታገዘ መጥቶ አስለቀቃቸው። ብዙ ቆራጥ ጀግኖች ወደቁ። ራስ ደስታ የዚህን ጉራ መክፈት እንደለሙ የደኃዝማች ባልቻ አባነፍሶን አሽከሮች ጨምረው ጦር ላኩ። ወታደሩም ገላሌ የተባለ መድፍና ሁለት አይሮፕላን ማውረጃ ኦርሊከን፣ ሰባት ድግን መትረየስ በመያዝ ደርሶ ጀባ ሜራ የተባለውን ቦታ ያዘ።

ለኔ 27 ቀን ጠላት በሩን ለመስበር መጣ። የኢትዮጵያ ጦር እንደልማዱ መክቶ በጀግንነት ተዋጋ። ጠላቱንም ድል አድርጐ አባረረው። አሥራ ሰባት ኢጣልያውያንና ብዙ የሶማሌ ወታደር ተገደለ። ሰባት ድግን መትረየስ፣ ሦስት መቶ ጠመንጃ፣ ሁለት ታንክ ተማረከ። ነገር ግን በታንኮቹ ሊጠቀምባቸው አልቻለም።

አልፎ አልፎ ጦርነት ቢያደርግም የኢትዮጵያ ጦር ጀባ ሜራን ሳይለቅ ምሽጉን አጥብቆ እስከ መስከረም ወር 1929 ዓ.ም መጨረሻ ተቀመጠ። ጠላት በበርጉዳ በኩል አዲስ መንገድ እያስመነጠረ መምጣቱ ተሰማ። በኢትዮጵያ በኩል ዝግጅት ተደረገ። አንድ ቡድን ወደ አማሮ ተሻገረና በሀገረ ማርያም ጀርባ በፊንጭ ውሃ በኩል ቦታ ያዘ። የኢትዮጵያ ልጆች መፎካከርና ለሥልጣን መጓጓታቸውን ትተው በአንድ ልብ ቆሙ። በመተባበር አያሌ ጦርነት አካሂደው አያሌ ድል በማግኘት ከዘጠና ቀን ላላነሰ ጊዜ የጀባ ሜራን በር ተከላከሉ።

ይህ ጉራ የማይበገርስት ስለሆነ የጠላት ጦር ከሀገረ ማርያም አንስቶ እስከ ጀባ ሜራ ጋራ ጥማ ሥር ያለውን ቦታ ያዘ። ጉሎልቻ ከተባለው ሥፍራ ላይ ሠፍሮ የጋራውን ጥግ መከታ አድርጐ ተቀመጠ። የኢትዮጵያ ጦርም በሊላ ዳኒሣ በኩል ዞሮ አደጋ በመጣል ኢጣልያኖች ገድሉና ማርከ ተመለሰ። በዚህ ዓይነት በየጊዜውና በየቦታው አደጋ እየጣሉ አደከሙት። የመድፍ

ድብደባውም ሦስት ወር ሙሉ ጦርነቱን ሳያስታግስለት ቀረ። ስለዚህ በተልቅ በርሜል መርዝ አምጥቶ ጣለ።

ይህ በኢትዮጵያ ወታደሮች ሠፈር ላይ የተጣለው አንድ በርሜል መርዝ ስለአልፈነዳ ለጊዜው ጉዳቱ እምብዛም ሆነ። ነገር ግን በርሜሉ ተሰንጥቆ ስለነበር ነፋስ ወደሚነፍስበት ወገን እየተነፈሰ በመዋል፣ በማደር አካባቢውን አቃጠለው። ሰውም፣ እንስሳትም ገደለ። መሬቱ ቀይ ቀለም እንደተነከረ ጨርቅ ወረዛ። የከብት ማሰማሪያ የነበረው የግጦሽ ሣር ተቃጠለ። መራቱም ለብዙ ዘመን አመድ ሆነ።

የኢጣልያ ጦር ጥቅምት 1 ቀን 1929 ዓ.ም በሠላማ አይሮፕላን እየደበደበ ብዙ ታንክ አስቀድሞ በእግር መጣ። የኢትዮጵያም ጦር ተከላከለ። በእጅ ቦምብ ሞምር ከፍ ያለ ጦርነት ተካሄደ። በጀግና ላይ ጀግና ተረባርቦ ወደቀ። ኢላ ዳኒሣ በተባለው በር የተሠለፉ የኢትዮጵያ ልጆችም እንደዚሁ አደረጉ። የጃባ ሜራ ሜዳ በደም ታጠበ፣ በጠላትም፣ በወገንም ሬሣ ተሸፈነ። የኢትዮጵያ ጦር ተሸንፎ በሩ ተከፈተ። ጠላትም እንደተመኘው ጥቅምት 5 ቀን ገባ። መግባቱንም በዚያ ለነበረው ሕዝብ ጥቅምት 6 ቀን ነገረ። በዚህ ጦር ሜዳ ለወደቁ ለእነ ደጃዝማች ደባይ ወልደአማኑኤል በታሪክ ፊት ክብርና ምስጋና ይገባቸዋል።

በወቅቱ በደጃዝማች ጉበረማርያም የሚመራው የኢትዮጵያ ጦር ወደጃባ ሜራ ተጉዞ ነበር። ነገር ግን እሱ ሳይደርስ ጦርነቱ ስለአለቀ ሃሳቡን መፈፀም ሳይችል ቀረ። ስለዚህ በደመርሶ አካባቢ የሚገኙትን ድልድዮች አስፈርሶ፣ ስልኩንም በጣጥሶ፣ አንጥፎ ይጠባበቅ ጀመር። ጠላትም እያንዣራ መጣ። ጥቅምት 9 ቀን 1929 ዓ.ም ወደ አካባቢው ለስለሳ በአራት ካሚዮን መጥተው የነበሩ የጣልያን ወታደሮች ጥይት ሲሰሙ አምልጠው ወደ ኋላቸው ተመለሱ። የኢትዮጵያ ጦር ፍስሐ ገነት ላይ ለመዋጋት ተዘጋጀ።

የፍስሐ ገነት ጦርነት ጥቅምት 11 ቀን 1929 ዓ.ም ጥዋት ለ12 ሰዓት ሩብ ጉዳይ ተከፈተ። ጣልያን በአራት ካሚዮን ሞልቶ ወታደር አመጣ። የኢትዮጵያ መድፈኛ ወደፊት ሦስቱን መኪናዎች አሳልፎ አራተኛውን ካሚዮን ቢመታው መንገዱ ተዘጋ። ከዚያም አከታትሎ ሌሎቹን ሦስት አጠፋቸው። እግረኛውንም የኢትዮጵያ ጦር ከመኪና ሳይወርዱ ተቀባበለው። ዘመኪናዎቹ ውስጥ የነበሩ የኢጣሊያም፣ የሶማሊያም ወታደሮች አለቁ። ሠሣሪያውን ኢትዮጵያውያን ማረኩት። ጠላትም ተዘጋጅቶ ነበርና ወዲያው ሌሎች አራት ታንክና አራት አውቶሞቢሎች ቢያቀርብ የኢትዮጵያ መድፈኛ አራቱንም ታንኮች በፍጥነት አቃጠላቸው። ወዲያው የነጭ እግረኛ ጦር ደረሰ። የኢትዮጵያ ጦር ከየጫካው እየወጣ እንደሠርገኛ ተቀላቀለው። ጣልያን በ9 ሰዓት በተጨማሪ አምስት ታንክና አምስት ካሚዮን ወታደር አመጣ። የኢትዮጵያ መድፈኛ ሦስቱን ታንኮች ወዲያው አወደማቸው። የኢትዮጵያ ጦር የአይሮፕላኑን ድብደባ ከምንጭ ሳይቆጥር ውጊያውን ቀጠለ። ሌላ ደጀን

የጠላት ጦር ከሀገረ ማርያም አመጣ። ከሌሊቱ 5 ሰዓት ሆነ። የጠላት ጦር ተተኪ ሲደርስለት፣ የኢትዮጵያ ጦር ምንም ሪዳት አላገኘም። ጠላትም ጦርነቱን የሚያጣድፈው ይህንን አይቶ ነበር። በዚህ ዓይነት ጠላት የባንዲን ጎራ ሰብሮ፣ የፍስሐ ገነትን ከተማ እጁ አደረገ። በዚህ ጦርነት ላይ የነበሩ ሁሉ፣ በተለይም መድፈኛው ሻለቃ /ደጃዝማች/ በቀለ ወያ ምስጋና ይገባቸዋል።

ከዚህ ጦርነት በኋላ በኢትዮጵያ በኩል እንደገና ምክር ተደረገ። ዋና ዋናዎች ሁኔታዎች፦ የደጃዝማች ገብረማርያም መቁሰል፣ ብዙ የጦር አለቆችና ወታደሮች መውደቅ፣ የተረፈውም መበተኑ ነበር። ጦሩም መክሮ በርትተን ከሌሎች አርበኞች ጋር በመቀላቀል ትግላችንን እንቀጥል በማለት ወሰነ። በዋናው መንገድ ለመጓዝ ስለአልተቻለ፣ በጫካ ውስጥ አዲስ መንገድ እየተመነጠረ ጉዞ ተደረገ። በዚያም ጠላት ተከትሎ መጣ። ተከላክለው በመመለስ ጉዞው ቀጠለ። የተረፉት ሰዎች ሠላሣ ስድስት ብቻ ስለነበሩ አንድ ባለጋሻ መድፍ ይዞ መንቀሳቀስ አስቸገረ። ደጃዝማች ገብረ ማርያም ግን "የምመክና የምኮራበትን መድፌን ትቼ አልሄድም" አሉ። ከመድፋቸው ጋር መሞትን መረጡ። ወታደሮቹ መድፉን እየጐተቱ ከጥቅምት 11 እስከ 13 ቀን ድረስ እህል ሳይቀምሱ ወደ ሀገረ ሰላም ተጓዙ። ከዚያም ጥቅምት 16 ቀን ቡሌ ከሚባለው ቦታ ደርሰው ከሰው ተቀላቀሉ። ከዚያ ደግሞ ጥቅምት 1 ቀን ሀገረ ሰላም ከተማ ገቡ።

ዋደራ በተባለው ቦታ መቀመጥ የማያዋጣ ሆኖ ስለተገኘ፣ ራስ ደስታ ዳምጠው ከ9 ወር ቆይታ በኋላ የጦር ሠፈራቸውን ነቅሰው ወደ አለታ ወንዶ ህዳር 2 ቀን ተነስተው ህዳር 5 ቀን በመድረስ ተፈሪ ኬላ የተባለውን ቦታ ያዙ። ደጃዝማች ገብረ ማርያም ጥቅምት 28 ቀን ከዚሁ ቦታ ደርሰው ስለነበር የሁለቱ ጦር ለመቀላቀል ቻለ።

ጥቅምት 29 ቀን 1929 ዓ.ም አካባቢውን ይደበድቡ ከነበሩ አይሮፕላኖች አንዱ ልኩ ከተባለው ቦታ ተሰናክሎ ወደቀ። በአካባቢው የነበሩ አርበኞች በውስጡ የነበሩትን ሁለት ኢጣልያውያን ቆራርጠው ጣሉአቸው። ሌሎች ጣልያኖች ደግሞ ገሚሱ ይርጋ ዓለም ሚካኤል፣ ሌሎች መናፈሻ ተክለ ሃይማኖት በየዛፉ ላይ ተቆራርጠው ተሰቅለው ተገኙ። በአይሮፕላን ውስጥ ወረቀት ተገኘ። ይህ መኮንን ወደ ሮም ለመሄድ እንዲያስፈቅድለት ለአንድ ወዳጁ ደብዳቤ ፅፎ ያገኘው መልስ ኖሮአል። ደብዳቤው "...ዛሬ የእኛ አገር የሚመኻዋት አይደለችም። እኛም ወደ እናንተ ለመምጣት እናስባለን። በኢትዮጵያ የተነሣ በዚህች በጥቅምት ወር በድፍን አውሮፓ የተሰኮሰው እሳት ምንጊዜም መብረጃ የለውም..." ይል ነበር።

ወደ ዋናው ጉዳያችን ስንመለስ፣ በአርበኞች በኩል ለአዲስ ፍልሚያ ዝግጅት ተደረገ። ከአሥራ ስምንት ዓመት በላይ የሆነ ወንድ ልጅ ሁሉ እንዲከት አዋጅ ታወጀ። ሠራዊቱም አዋጁን አክብሮ፣ ያለውን መሣሪያ ይዞ

ተሰባሰበ። ለሌላው ደግሞ ከጦሩ ግምጃ ቤት ተሰጠው። ይርጋ ዓለም በዕረፍት ላይ የቆዩት 500 ኤርትራውያን መጥተው ተቀላቀሉ። ህዳር 7 ቀን አንድ ቡድን ከጠላት በስተደርባ ዞሮ ስለሳ ከአካሄደ በኋላ የጦርነቱ ዕቅድ በተገኘው መረጃ መሠረት ተሠራ። ወታደሩ የመድፍና የቦምብ አደጋ በማያገኘው ዓይነት ተደለደለ። ከተፈሪ ኬላ ቀኝ ያለው ተራራ ለመድፈኞች፣ በስተግራ ያለው ለአይሮፕላን ተከላካዮች፣ ማለትም፦ ለብለ አርሊኮኖች ተሰጠ። የጦር መሪዎች ሠራዊታቸውን ይዘው ከረባዳው ሥፍራ አደፈጡ። ጠላት ሊያውቀው በማይችል ሁኔታ ተዘጋጁ።

ጠላት ጉዞውን ቀጥሎ ተፈሪ ኬላ ደረሰ። የኢትዮጵያ ሠራዊት መከተ። አንድ ጊዜም ሳያቋርጥ ለ16 ቀን የተካሄደው የጦር ዝግጅት ህዳር 3 ቀን 1929 ዓ.ም ተከፈተ። አይሮፕላኖች ድብደባቸውን ቀጠሉ። ከአዲስ አበባ እየተነሱ ከሚመጡት 17 ጋር ቁጥራቸው ወደ 44 ከፍ ያለ አይሮፕላኖች ድብደባ ቢፈፅሙም የኢትዮጵያ ጦር አልተበገረም። ጠላትም ይህንን ባየ ጊዜ ተጨማሪ ጦር አቀረበ። ኢትዮጵያውያን በስተቀኝ የመጣባቸውን ጦር አበረሩ፣ ነገር ግን በስተግራ የመጣው ጠላት የሚዋጉበትን ቦታ አስለቀቃቸው። ጦርነቱም ስለጠነከረ ጣልያን ምሽግ መሥራት ጀመረ። አይሮፕላኖቹም በአካባቢው የነበሩትን ከተሞች ሙልጭ አድርገው አቃጠሉ።

ኢትዮጵያውያን የጦር ሥልታቸውን ለወጡ። ሲመጣ መከላከል ብቻ ሳይሆን እስከ አለበት ድረስ እየሄዱ አደጋ ይጥሉበት ጀመር። ህዳር 7 ቀን መድፍና አርሊስን ይዘው 300 ሆነው ከበስተደርባው ዞረው ከምሽቱ በ11 ሰዓት አደጋ ጣሉበት። ሠፈሩን አቃጠሉበት። የድንኳኑ ቃጠሎ ሌሊቱን ቀን እስኪያስመስለው ድረስ እሳቱ ተንቀለቀለ። አንድ ጀነራል አንገቱን ተቆርጦ ከብዙ ወታደር ጋር ሞተ። የጦር መጋዘኑ ተቃጠለበት። የኢትዮጵያ አርበኞች አንዳችም ጉዳት አላገኛቸውም።

ህዳር 9 ቀን የኢትዮጵያ አርበኞች ሌላ ጥቃት ለማካሄድ ተንቀሳቀሱ። ሁለት መቶ ወታደሮች፣ ሁለት መድፍ ይዘው ሌሊቱን ሲጓዙ አድረው ሊነጋጋ ከጠላት ጀርባ ዞረው ቦታ ያዙ። ነገር ግን ተኩስ አልከፈቱም፣ አልተንቀሳቀሱም። አድፍጠው ውሰው አይሮፕላኖች ድብደባቸውን ፈፅመው ወደ ሠፈራቸው ሲመለሱ አርበኞች ከቀኑ በአሥር ሰዓት ሥራቸውን ቀጠሉ። ቀላል የመድፍና የጥይት ድብደባ አካሄዱበት። የነበሩትን ታንኮችና ካሚዮኖች አቃጠሉበት።

ህዳር 12 ቀን ደግሞ ሌሊቱን ሲጓዙ አድረው ከንጋቱ በ12 ሰዓት ከፊት ለፊት አደጋ ጣሉበት። ይህ ደግሞ ሌላ ፈሊጥ ሆነበት። አደናግረው ብዙ ጉዳት አደረሱበት። ነገር ግን አይሮፕላኖች በ1 ሰዓት ደርሰው ድብደባ ጀመሩ። እየተፈራረቁ እስከ 12 ሰዓት ዋሉባቸው። ሆኖም የኢትዮጵያ ወታደሮች ምቹ ሥፍራ ይዘው ስለነበር ጉዳት አልደረሰባቸውም። ማታውኑ በደህና ወደ ሠፈራቸው ተመለሱ።

የኢትዮጵያ ጦር አቅሙ እያነሰ፣ ብርካቴውም እየቀነሰ ሄደ። በአግር፣ በአይሮፕላን ቅጥቀጣው በዛበት። ከፍ ያሉ ጀግኖች ተራ በተራ ወደቁ። ብዙ የጦር መሪዎች ቆስለው ከአዛዝነት ወደ ሽክምነት ተዛወሩ። ወታደሩ ችግር በዛበት። ጊዜውም ረዘመበት። ደግሞ ጠላት ከተሞችን በአይሮፕላን ሲያቃጥል፣ አርበኛው ስለ ሚስቱና ስለ ልጆቹ ሁኔታ ማወቅ ግድ ሆነበት። ስለዚህም ቀስ በቀስ ተበተነ። ተዋጊው ኃይል ቢቆጠር አንድ መቶ ሃያ አምስት ብቻ ሆኖ ተገኘ። ከኤርትራዉያኑም የቀሩት ሦስት መቶ ሰባ አምስት ሆኑ። በጠላት በኩል ግን ሁኔታው ከባድ ነበር። ከአዲስ አበባ ሠላሳ ሦስት ካሚዮን ወታደርና አርባ ታንክ ገባ።

እነዚህን ሁኔታዎች በመገምገም የኢትዮጵያ ጦር ምክር አደረገ። አካባቢውን ለቅቆ መሄድና ከሌሎች አርበኞች ጋር ተቀላቅሎ መዋጋት እንደሚሻል ስለታመነበት፣ ጦሩ ተፈሪ ኬላን ሀዳር 19 ቀን 1929 ዓ.ም ለቅቆ ወደ ሀገረ ሰላም ተጓዘ። ጠላትም ይርጋ ዓለም ገባ። ክፍለ ሀገሩም ከኢትዮጵያ አስተዳደር ወደ ጣልያን ቅኝ ግዛት በዚህች ቀን ገባ።

በዛ የነበረው የኢትዮጵያ ጦር ከተፈሪ ኬላ ወደ አርባጉና ዞረ። ከዚያም ጠላቱን እየተከላከለ እስከ ጥር 12 ቀን 1929 ዓ.ም ድረስ ቆየ። በኢጣልያ ወገን ጀነራል ግራዚያኒ የማርሻልነት ማዕረግ ተሰጥቶት አዲስ አበባ ሲገባ፣ የጦር አዛዥ ጀነራል ጀሰዞ ሆነ። እሱም ለራስ ደስታ ዳምጠውና ለደጃዝማች ገብረ ማርያም አንድ ዓይነት ቃል የያዙ ሁለት ደብዳቤዎች ጽፎ ሙሴ ቀስተኛ በተባለ የስዊስ ተወላጅ ነኝ ባይ እጅ ላከ። በደብዳቤዎቹ ሰላምታ ከአቀረበ በኋላ በትግራይ፣ በሐረርጌም የመጣው ጦር አዲስ አበባ መግባቱን ይገልፅና "...እኔ ብቻ እንዳልገባ ብትከለክሉኝ ምን ጥቅም ታገኛላችሁ?" ካለ በኋላ፣ ምህረት እንደተደረገላቸው አረጋግጦ እጃቸውን እንዲሰጡ ይጠይቃል። ሙሴ ቀስተኛም መልዕክቱን ታህሣስ 7 ቀን አርቤጉና ላይ አስረከበ። በቃሉም የተላከበትን ጉዳይ አስረዳ። ግራዚያኒ የላፈላቸውንም ዛቻ የተመሳበት ደብዳቤ አብሮ አስረከበ።

ሁለቱም መሪዎች የሠራዊታቸውን ቁርጠኛ ሐሳብ በማንፀባረቅ ታህሣስ 7 ቀን አንድ ዓይነት ደብዳቤዎች፣ መልስ ሰጡት። የላፈላቸው ደብዳቤ እንደደረሳቸው ገልፀው፣ ስለነፃነታቸው እስከ ሕይወታቸው ፍፃሜ መከራከር እንደሚገባቸው ገለፁለት። ከዚህም አያይዘው ለእሱ ለራሱ ምክር ሰጡት። "...ኢትዮጵያን ይገርስለሁ ካልክ ይልቅ ሰላማዊው ሕዝብ፣ ድኃው በከንቱ እንዳያልቅ... እንዲጠበቁ ሰሹማምንቶችህ ትዕዛዝ ማስተላለፍ ነው..." የሚል ነበር። እሱ ግን ይህንን ምክር ከቁጥር አላገባውም። የኢትዮጵያን ሕዝብ መጨረሱን ቀጠለ። የደብዳቤአቸው ቃል በዚህ ብቻ አላበቃም። የአርበኛውን ቁርጠኛ ሐሳብ የሚገልፅ ነበር። "እኛ ግን" በማለት ይቀጥላል፣ "...እኛ ግን ላንተ ማስረከብ የሚገባን የደማችንን ጠብታ ብቻ እንጂ፣ እንኳንስ

እጃችንን አንዲት ሰባራ ጠመንጃም አንሰጥህም" በማለት ይደመድማል። ጀነራል ጀሰዞም ቁርጡን አውቆ ድብደባውን በአይሮፕላንና በአግር ቀጠለ።

በዚህ ጊዜ በአርበኛው መሃከል ምክር ተደረገ። መጀመሪያ ከጣልያን የተነፃፉት ደብዳቤዎችና ከአርበኞቹ መሪዎች የተሰጠው መልስ ተነበበ። በምክሩም ላይ ልዩ ልዩ ሐሳቦች ቀረቡ። አንዱ ሐሳብ ሲዳሞን ሳንለቅ በዚሁ ክፍለ ሀገር እንዋጋ የሚል ሲሆን፣ ሌላው ደግሞ በአንገት፣ ማለትም፡- ጎንደር ቀርቶ፣ በአማሮ በኩል አድርጉ ወደ ኬንያ ጠረፍ መድረስ የሚል ነበር። ሦስተኛው ሐሳብ በአርሲ በኩል አቋርጦ ጉራጌ አገር ከተደረሰ በኋላ ጎዙን አሩሲ ትቶ የጊቤን ወንዝ ይዞ በጉፋ ድንበር ጠረፍን ተጠግቶ ለመከላከል ነበር። ነገር ግን የሲዳሞው ጦር በዚህ የማይስማማ ሆነ። እዚያው ሲዳሞ ሙዋጋትን መረጠ። በዚሁ መሠረት በሲዳሞ ክፍለ ሀገር የአርበኝነቱን ሥራ ለመቀጠል ተወስኖ ሠራዊቱ ቃለ መሐላ ፈፀመ። ደጃዝማች ገብረ ማርያምም ቀደም ብሎ የተንቀሳቀሰውን ጦራቸውን ወደ አርባ ጉና መለሱ። ከፊሉ እምቢ ብሎ ወደ እገምጃ ጉዞውን ቀጠለ።

ከታህሣሥ 7 እስከ 29 ቀን 1929 ዓ.ም ድረስ ዝግጅት ከተደረገ በኋላ፣ ከጠላት ወገን ከታህሣሥ 30 ጀምሮ አዲስ እንቅስቃሴ ተጀመረ። መጀመሪያ የንጉሠ ነገሥቱን ፎቶግራፍና የስብኩት ቃል የያዘ ወረቀት በአይሮፕላን ተበተነ። ቃሉም በአማርኛ የተፃፈ ሆኖ ንጉሡ ጥለው እንደሄዱ፣ ትንሽ እንኳ ሳያስቡ በሰላም ቦታ ተቀምጠው በሕይወትና በተድላ ጠግበው እንደሚኖሩ ከገለፀ በኋላ፣ "...የሚገርመው በውሸት አምናችሁ ልታልቁና ልትገደሉ ያለልክ ሞኞች መሆናችሁ ነው" የሚል ነበር። ነገር ግን አርበኛው ይህንን ስብከት ከጆሮው አላንጠላጠለውም። ትግሉን ቀጠለ።

ጥር 1 ቀን ሽንቆበር በተባለው ቦታ ጦርነት ተጀመረ። ጦርነቱም በየቦታው፣ በየቀኑ ቀጠለ። እረፍት አልሰጠም። ከጥር 3 ቀን ጀምሮ አይሮፕላኖች በብዛት እየመጡ አካባቢውን በሙሉ ደበደቡት። እንደ እሳተ ገሞራ አቃጠሉት። ከራስ ደስታ ዳምጠው ሳንለይ እንዋጋለን ብለው ምለው የነበሩ፣ አርበኛው ወደሌላ ቦታ ለመዛወር አስቦት የነበረውን ዕቅድ አጨናግፈው ያስቀሩት የሲዳሞ ጦር አባላት፣ ተከቡብን በሚል ምክንያት ነደው እጃቸውን ለጠላት ሰጡ። አንድ ቁምነገር ብቻ ሠሩ። እሱም እኛ እጃችንን ሰጥተናልና እጃችሁን ስጡ የሚል ወረቀት ጽፈው ላኩ። የሚገርመው እጁን አልሰጥም በማለት ከበባውን ሰብረው በወጡት በግራዝማች እቱቢት እጅ መላኩ ነበር። ጠላትም የተማረኩትን ሽማምንት ቀቤና ከተባለው ቦታ ወሰዶ በመትረየስ ፈጃቸው። የፈሩትን ሞት በውርደት ተቀበሉት።

አርበኛው ይዞት የነበረውን ቦታ ለቅቆ ወደ ሌላ ቦታ መዛወርን መረጠ። ምክንያቱም ተማራኪዎቹ የሚያውቁትን ምስጢር ለጠላት መንገራቸው ሳይታለም የተፈታ ነበር። ስለዚህም አርበኞች ከአርቤጉና፣ ቀቤና ወደሚባለው ቦታ ሄዱ። ከዚያም ጉዞ ቀጥለው ሰገታ ከተባለው ቦታ ደረሱ።

ከዚህ ቦታ ጠላት በጠቋሚ ደረሰና አስደናቂ ውጊያ ተደረገ። ከጦር ሜዳው በስተምሥራቅ የነበረውን የጠላት ጦር አርበኛው አመድ አድርጉት ከበባውን ጥሶ አለፈ። ገላግሌ የተባለውን መድፍ ነቅሎ አፈሙዙን ብቻ ይዞ ተንዘ። መከራከሩን ለጌታ ከተባለው ወንዝ አጠገብ ከነበረው ዋሻ ውስጥ ከብዙ ጥይትና ገንዘብ ጋር ደብቆት ሄደ። ነገር ግን ጠላት ከአንድ ከተማረከ ወታደር ምስጢሩን አግኝቶ ወሰደው።

አርበኛው በአርሲ በኩል አልፎ ከሌሎች አርበኞች ጋር ለመቀላቀል በነበረው ሐሳብ መሠረት ጉዞውን ለማፋጠን ሌሊት በመብራት ጭምር ተንዘ። የሲዳሞን አርበኛ፡- ካሕን መሃይምን፣ ሴት ወንድ ሳይል፣ ከሊቅ እስከ ደቂቅ ታቡቱን ይዞ ነዋሪው ተከተሰ። ጥር 11 ቀን ከሌሊቱ በ11 ሰዓት ጠላት ደረሰበት። ጥምቀት ስለነበረ ሠራዊቱ በዚያ ሰዓት ከፀሎትና ከቅዳሴ ላይ እንደሚሆን አምኖ ነበር። አርበኛው ግን ከበባውን ሰብሮ በመውጣት የሁለተኛውን መድፍ መንኮራኩር ከዋሻ ውስጥ ደብቆ አመሰጠ። ለጥር 12 ቀን አጥቢያ ሌሊት ጥሬ ከሚባለው ሲዳሞ፣ ባሌ እና አርሲ ከሚዋሰኑበት ቦታ ደረሰ። ከዚያም ከፍተኛ ውጊያ አደረገ። ጠላት እያየለ፣ አርበኛው አቅሙ እያነሰ፣ ብዛቱም እየቀነሰ ሄደ። ከዶሎ ጀምሮ የደረሰበት ጥቃት እንገፈገፈው። መሪዎቹ አሰቁ። እየቆሰሉ ተማረኩ። ስለዚህ የሲዳሞን ክፍለ ሀገር መልቀቅ ግድ ሆነበት። በዚህ ዓይነት ከዘጠኝ ወር የአርበኝነት ትግል በኋላ ጥር 15 ቀን 1929 ዓ.ም ሲዳሞን ለቀቀ። የጣልያን ሥልጣን በክፍለ ሀገሩ ሰፈነ።

ታላቁ የኢትዮጵያ ሠራዊት ሲዳሞን ከለቀቀም በኋላ የክፍለ ሀገሩ ተጋድሎ አላበቃም። በልጅ /ደጃዝማች/ ተስፋዬ ወልዴ የሚመራው አርበኛ ከቦታ ወደ ቦታ እየተዘዋወረ በቡርጂ፣ በአማሮ፣ በገለና፣ በሀገረ ማርያም፣ በባርጉዳ፣ በቦረና፣ በተልተሌ፣ በያቤሎ፣ በሰብራ፣ በዙርቃ፣ በገለባና በጮራ የጦር ሜዳዎች በእጅጉ ሲፋለም ቆይቷል።[1]

ማጣቀሻ ፅሑፎች

1. "የጀግኖች አደራ"፣ የጀግኖች ማህበር መጽሔት፣ መጋቢት 1983 ገጽ 37-39።

ምዕራፍ ሃያ

በሐረር፣ በባሌና በአርሲ የተካሄደ ትግል

ከአጋዴን የተመለሰው ጦር በየቦታው የተቻለውን ያህል ከተከላከለ በኋላ፣ በምሥራቅ ወገን የነበረው ወደ በርበራ ሲሄድ፣ በምዕራብ ወገን የነበረው ወደ ባሌና አርሲ ገባ። ቡተሰይ በጋራ መሰታ የነበረው ጦር ከሐምሌ 1 ቀን 1928 እስከ ጥቅምት 30 ቀን 1930 ዓ.ም ያደረገው ተጋድሎ የሚጠቀስ ሲሆን፣ ቀደም ብለው በታተሙ መፃሕፍት ተጠቅሷል።

ወደ ባሌ የዘመተው ጦር የሄደው በአርሲ በኩል ነበር። አዝማቹም ደጃዝማች በየነ መርዕድ ነበሩ። ከአቴጌ መነን የማይወለዱት ልዕልት ሮማን ወርቅ ኃይለሥላሴ፣ ከባላቸው ከደጃዝማች በየነ ጋር አብረው ዘምተው ነበር። ከንጉሠ ነገሥቱ ቤተሰብ በጦር ግንባር ቆመው የተማረኩና ታሥረው የሞቱ እሳቸው ብቻ መሆናቸው ነው። በባሌ የዘመተው የኢትዮጵያ ጦር በአጋዴንና በቦረና ግንባር በኩል የመጣውን የጠላት ጦር ከሁለት ፈልቅቆ በመሀሉ በመቆም የሚቻለውን ያህል ተከላከለ። በተሸነፈም ጊዜ በአጋዴን ምዕራባዊ ግዛት የተመለሰውን የኢትዮጵያ ጦር ጨምሮ በአርሲ በኩል ወደ መሀል ሀገር ገባ።

ከሲዳሞ ጦር ውስጥ ሶርፌታ /ዶዶላ አረና/ ከሚባለው አካባቢ የመጣው የሕዝብ ሠራዊት ጥር 5 ቀን 1929 ዓ.ም አርሲ ሲገባ ከባሌ ጦር ጋር ተቀላቅሎ ዳበረ። የዚህ ጦር ሐሳብ አዲስ አበባ ገብቶ የልቡን ሠርቶ ሕይወቱን ማሳለፍ እንዲሆን በምክር ተመርጦም ነበር። ነገር ግን እንደታሰበው አልተፈፀመም። ጠላት ከአዲስ አበባ በስተደቡብ ያለውን ጉራ አጠናከረ። ከዚያም አልፎ በናዝሬት በኩል አልፎ አርሲ ገባ። ቤቱን እያቃጠለና ከብቱን እየዘረፈ በደራ፣ በጡሩታ በኩል ስለመጣ፣ በዚያ የነበረው የኢትዮጵያ ጦር እየተከላከለ ወደ ሶዶና እገምጃ አመራ። ጥቂቱ ደግሞ ወደ ሸንኮራና ቡልጋ ተሻገረ። አዲስ አበባ ለመግባት የነበረው ሐሳብ በዚሁ ተቋርጦ ቀረ። በዚሁ ላይ ደግሞ ከአርበኞች ጋር በነበሩ የኤርትራ ልጆች መካከል የሐሳብ ልዩነት ተፈጠረ። እነሱን የኢትዮጵያ ጦር መግላገል አቃተው። በራሳቸው ውሣኔ መሠረት ተለዩ።

ጦሩ ከዶዶላ ወደ ሂበኖ ቀጠለ። ከዚህ ቦታ ላይ ሲደርስ የኢጣልያን አይሮፕላኖች ስለአገኙት ጥር 19 ቀን 1929 ዓ.ም ከጥዋት እስከ ማታ ታላቅ ድብደባ አካሄዱበት። ከዚያም በማግስቱ የጠላት ጦር የእግረኛ ሠራዊት አቀረበ። ከሲዳሞ በአርሲ ጉና፣ ከአርሲ ደግሞ በኮፈሌ በኩል ከበበ። ኢጣልያ የወረብና የጥቁር እንደዚሁም ከሀገር ውስጥ የተመለመለ የባንዳ ሠራዊት በብዛት አሰለፈ። የኢትዮጵያም ጦር ገድሎ ለመሞት ተዘጋጅቶ ነበርና በብርታት ተዋጋ። የጨበጣ ውጊያ ስለሆነ የጠላት አይሮፕላኖች ወኖቻቸውን ሊረዱ አልቻሉም። ጦርነቱ ከጥዋቱ ረፋድ ጀምሮ ሙሉ ቀን ዋለ።

ውጥንቅጡ ወጣ። ጨለማ ገላገለው። ፊታውራሪ ሽመልስ ሃብቱና ብዙ ጀግኖች ወደቁ።



ከደቡቡ ግንባር የአፋሲና የባሌው ከፍተኛ መስዋእትነት የተከፈለበት ነበር።

ከበባውን ሰብሮ ማለፍ ግዴታ ስለነበር፣ አርበኞች ሌሊቱን ተጉዘው ጥር 21 ቀን ለቂደንበል ደረሱ። በንጋት ለመጓዝ እንዲቻል፣ ሆኖም ግን መድፉ በጠላት እንዳይማረክ በሰዋራ ሥፍራ እስቀምጠውት ሄዱ። ጉዞው በአዳሚቱሉ በኩል ቀጠለ። ጠላትም በአይሮፕላን እየተከታተለ በየቀኑ ድብደባ አካሄደ። የአርሲን ጎብረተሰብ በጀሌነት እያሰለፈ አዋጋው። ጉዞው በዚህ ዓይነት ቀጥሎ የካቲት 9 ቀን 1929 ዓ.ም ታላቅ ጦርነት ተደረገ። የሞተው ሙቶ፣ የተረፈው አርበኛ ጉዞውን ቀጥሎ፣ የካቲት 10 ቀን ከሞጆ ወደ ሻሸመኔ ከሚወስደው መንገድ ላይ ደረሰ። በዛም አድፍጦ ይጠብቅ የነበረውን የጠላት ጦር ደፍጥጦ መንገዱን ለማለፍ ቻለ። የካቲት 11 ቀን መቂ ከተባለው ቦታ እንደደረሱ ጠላት ተከታትሎ ደረሰና ውጊያ ተካሄደ። ሰማንያ ያህል ጣልያኖች ሞቱ። የኢትዮጵያም ጦር በዱግዳ በኩል አድርጉ የካቲት 13 ቀን 1929 ዓ.ም ማረቆ ለመግባት ወደ ጉራጌ አገር ተሻገረ። በዚህ ግንባር የነበረው ትግል በእንዲህ ተፈፀመ።

<u>ማጣቀሻ ፅሑፎች</u>

1. ለይፋ አባ ወሎ፣ *የታሪክ ቅርስ*፣ ገፅ 125-171።

ምዕራፍ ሃያ አንድ
በጉራጌ አገር የተካሄደ አርበኝነት

ከአጋዴንና ከቦረና የጦር ግንባር የተመለሰው ሠራዊት በሐረርጌ፣ በባሌ፣ በሲዳሞና በአርሲ እንደምንም ሲከላከል እንደቆየና ከዚያም ወደ ጉራጌ አገር እንደተሻገረ ተመልክተናል። አሁን ደግሞ በጉራጌ አገር የተካሄደውን ተጋድሎ እናያለን።

ጦሩ ሌሊቱን ተጉዞ ከመቂ ማርቆስ፣ ጉጉቲ ጥዋት ሲነጋ ደረሰ። ከዚያ ደግሞ በአሀዳግን ምክር እየተመራ አዲስ የጠላት ጦር ጠበቀው። የኢትዮጵያ ጦር አዛዦች አስቸኳይ የሐሳብ ልውውጥ አደረጉ። አብዛኞቹ የጦር መሪዎቹ ለሞት ቁርጠኞች ስለነበሩ ከውሣኔ ለመድረስ አልተቸገሩም። በተሰይ ደጃዝማች ገብረ ማርያም ሰውድ ሀገራቸው ለኢትዮጵያ በዚያች ቀን የሞት ጽዋ ለመቀበል ቁርጠኛ መሆናቸውን በሠራዊታቸው ፊት ገለፁ። ከዚህ ፅዋ ለመሳተፍ ያልተዘጋጁ እንዲሄዱ አሰናበቱ። የጠላትን ጦር ብዛትና የአርሳቸውን ሠራዊት መመናመን ተመልክተው "... በቂ ሰው አላገኘንም። ስለሰው አምላኬን ጨምሬአለሁ..." በሚል ቃል የነበሩአቸውን ጥቂት ሰዎች ቦታ አስያዙ። ወጣቱ የጦር መኮንን ሻለቃ /ደጃዝማች/ በቀለ ወያ በዚህ ሐሳብ አልተስማሙም። "...ጠላታችንን የምናጠቃው በመሥራት እንጂ፣ በመሞት ብቻ አይደለምና ለሞት ሳንቸኩል መንገዳችንን ብንቀጥል መልካም ነው..." አሉ። ተቀባይ አላገኙም። ደጃዝማች ለማምለጥ ሲቻላቸው ተዋግቶ መሞትን መረጡ።

የመጣው የጠላት ጦር ከወገን ጦር እጅግ ብዙ ብልጫ ነበረው። ራስ ደስታ ዳምጠው፣ ደጃዝማች ገብረ ማርያም፣ ደጃዝማች መርዕድ በየነና ሻለቃ /ደጃዝማች/ በቀለ ወያ ጥቂት ወታደሮቻቸውን ይዘው የካቲት 13 ቀን ጉጉቲ ከተባለው ቦታ ግንባር ለግንባር ገጠሙት። እያንዳንዳቸው መትረየስ ይዘው ተዋጉ፣ የጠላት ወታደርንም ረፈረፉት። ግን ከብዛቱ የተነሣ መክተው ለመመለስ አልቻሉም። ጦርነቱ ረፋዱ ላይ ተጀምሮ ሙሉ ቀን ቀጠለ።

ውጊያው ከመጠን በላይ ብርቱ ከመሆኑ የተነሣ በትንቅንቁ ሂደት አርበኞቹ ርስ በርሳቸው ተሰያዩ። ሁሉም በየፊናው ሄደ። ከደጃዝማች ገብረ ማርያም ጋር በውሣኔአቸው እንደፀኑ የቆሙት በዚህ ታላቅ የጦር ሜዳ ከብዙ ኢትዮጵያውያን ጋር የደግንነት ሞት ሞቱ። ደጃዝማች በየነ



ከደቡቡ ግንባር የአሩሲና የባሌው ከፍተኛ መስዋእትነት የተከፈለበት ነበር።

መርዕድ መቂ ላይ በተደረገው ጦርነት በኃይል ቢቆስሉም፣ በዚህ ቀን በዋለው ጦርነት ከሜዳ ገብተው የጠላትን ወታደር ሲጠርጉት ዋሉ። ነገር ግን ከቁስላቸው ፅናት የተነሣ ማምለጥ ስለአልቻሉ ከጠላት እጅ ወደቁ። እሱም ቀሉ ከሚባል ቦታ ላይ በመትረየስ ደብድቦ ገደላቸው።

ከራስ ደስታ ዳምጠው ጋር በመሆን ከዚህ ጦርነት የተረፉት ከአሥር ያልበለጡ ወታደሮች ብቻ ነበሩ። ከዚያም ልዕልት ሮማን ወርቅ ኃይሰ ሥላሴን ለፊታውራሪ ታደሰ ገነሜ በአደራ ሰጥተው ጉዞአቸውን ቀጠሉ። ልዕልት ሮማን ወርቅ ለፊታውራሪ ታደሰ የተሰጡት ሊያድኑአቸው እንደሚችሉ ተገምቶ ነበር። ነገር ግን ፊታውራሪ ታደሰ ራሳቸው በገበሬ እጅ ስለተገደሉ፣ ልዕልት ተማረኩ። ከዚያም አዳሜ ቱሉ የተባለው ወረዳ ኃላፊ የነበረው ሰውዬ ከገበሬው ተቀብሎ ለአለቆቹ አስተላለፋቸው። ከዚያም ወደ ጣልያን ሀገር ተወስደው በእሥር ላይ አንዳሉ ሞቱ። እዚህ ላይ ከጦርነቱ ጥቂት ቀደም ብሎም ልዕልት ዘነበ ወርቅ ኃይለሥላሴ፣ ደጃዝማች ኃይለሥላሴ ጉግሣን አግብተው መቀሌ ሲኖሩ ሞተው እንደነበር ይታወቃል። ምንም እንኳን የእኚህኛዋ አሟሟት በሕመም ቢሆንም፣ እነዚህ ሁለት ልዕልቶች በአገር ውስጥ ቆይተው እንደ ማንኛውም ነዋሪ ሕይወታቸውን ለኢትዮጵያ እንደሰጡ ሊታወቅላቸው ይገባል።

ወደ ዋናው ጉዳይ ስንመለስ፣ ራስ ደስታ ዳምጠው የካቲት 15 ቀን በጉዘና በጦርነት ላይ ውለው ለየካቲት 16 ቀን አጥቢያ ሙሽር ከተባለው ቦታ ደረሱ። ከሀገሩ ሰዎች ጋር በተደረገው ንግግር ወደ ግቤ በረዛ መግባት የተሻለ ሆኖ ተገኘ። መንገዱን የሚያውቁ ሁለት ሰዎች ተሰጥተዋቸው ጉዞአቸውን ቀጠሉ። መንገድ ለመሩአቸው ሰባ፣ ሰባ ብር የተከፈላቸው ቢሆንም፣ የተቀጠሩት ባላገሮች ራሳቸው መሐላቸውን አፍርሰው ጠቋሚ በመሆን ለጠላት ነገሩባቸው።

የጠላት ጦርም አገሬውን ጨምሮ በብዛት ሆኖ ቢመጣባቸውም በድፍረት ገጠሙት። ጠላት ሌሊቱን ከአደረገባቸው ከበባ ሰብሮ ለመውጣት ባደረጉት መከራ ከተረፉት አሥር ያህል ሰዎች አራቱ ሞቱ፣ ሁለቱ ቆሰሉ። በዚህ ሁኔታ ራስ ደስታ ዳምጠው ብቻቸውን ቀሩ። ከሞቱትና ከቆሰሉት ወታደሮቻቸው መካከል ሆነው፣ የጦር ልብሳቸውን ለብሰው፣ በቤልጅግ መትረየስ የጠላትን ወታደር እንደረፈረፉት ነጋ። በመሀሉም ጥይት ስለአለቀባቸው ተናደው መትረየሳቸውን ወረወሩት። ከዚያም በአገኙት መሣሪያ ሁሉ ተዋጉ። ያገኙአቸው መሣሪያዎችና የሸጉጣቸው ጥይት አንድ እንኳን ሳይቀር ስለአለቀባቸው እጃቸውን

አሲሳቸው ውስጥ ከትተው በወታደሮቻቸው ራሣ መካከል ይንጐራደዱ ጀመር። ከጥዋቱ በ12 ሰዓት በጣልያኖች እጅ ተያዙ።

እንደተያዙም የሞቱት ወታደሮቻቸው እንዲቀበሩ፣ የቆሰሉትም ተነስተው ሕክምና እንዲደረግላቸው ጠየቁ። በዚሁ ዓይነት ተፈፀመላቸው። ጠላት በበቅሎ አስቀምጦ ከሙሽር እስከ ቡታጅራ ከተማ አመጣቸው። ከዚያም የኢጣልያ መኮንኖች የክብር ሰላምታ ሰጥተው ከድንኳን ውስጥ አስቀመጡአቸው።

ራስ ደስታ መያዛቸውን የሚገልፅ ቴሌግራም ወደ አዲስ አበባ ተላለፈ። በዚያን ሰዓት ለጉዳዩ ውሣኔ የመሥጠቱ ሥልጣን የዋና ጠላታቸው የግራዚያኒ ነበር። እሱም በቶሎ እንዲገደሉ ትዕዛዝ ሰጠ። ውሣኔውን መፈፀም የነበረበት ሻለቃ ቱቺ የተባለው ኢጣልያዊ ለራስ ደስታ መናፈሻ ሊያሳያቸው ማሰቡን ገለፀላቸው። እሳቸው ግን ሞታቸውን አጡቀው ነበርና በጣም ደስ እንደሚላቸው ገለፁለት። ሊፈልጉት የነበረው የድል አክሊልን መቀዳጀት እንደነበረ፣ ስለሀገራቸው ክብር የሚገባቸውን እንደፈፀሙ፣ በጦር አዛዥነታቸው ሙሉ በሙሉ እንደሠሩበት፣ በእሳቸው እዝ የተንቀሳቀሰው የኢትዮጵያ ጦር በእያንዳንዱ ጉራ የፈፀመው ድል እንደ አስደነቃቸው ገለፁ። ንግግራቸውንም "...ያንዲት ደሜ የመጨረሻ ጠብታ...ነፃነትን እንደሚያፈራ አልጠራጠርም" በማለት ደመደሙ። ጠላትም የካቲት 17 ቀን 1929 ዓ.ም ከቀኑ በ7 ሰዓት በዘጠኝ ጥይት ደብድቦ ገደላቸው።



ራስ ደስታ ዳምጠው እጃቸውን በሰጡበት ወቅት።



ራስ ደስታ ዳምጠው እጃቸውን በሰጡበት ወቅት።

በአካባቢው የነበሩ የሦስት ደብር ካህናት በመስቃን መድኃኔ ዓለም ቤተክርስቲያን ፀሎተ ፍትሐት ከአደረሱላቸው በኋላ፣ አስከሬናቸው ወደ ምድረ ከብድ ተገዛ በአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ገዳም የካቲት 18 ቀን 1929 ዓ.ም በክብር ተቀበረ።[1]

እዚህ ላይ በቦረና ጦር ግንባር የተሰለፈውን የኢትዮጵያ ጦር የመሩ፣ በዚያ ግንባር የተሰለፉ ወታደሮች ሁሉ ምስጋና እንደ ሚገባቸው የዚህ መፀሐፍ አዘጋጅ ዕምነት ነው። ከፍ ሲል እንደተገለፀው ጥቂት ከሀድያንና ትንሽ ወላዋዮች ቢኖሩባቸውም፣ አብዛኞቹ የጀግንነትን ሥራ ሠርተዋል። ሽሽተው ማምለጥ ሲችሉ በየነበሩበት ቆመው ጠላትን ግንባር ለግንባር በመጋፈጥ ለሀገራቸው የመጨረሻ ጠብታ ደማቸውን አፍስሰዋል። ጀግናው የኢትዮጵያ ባሕርይ ይህ መሆኑን በግብር አረጋግጠዋል።

ግራዚያኒና ሌሎችም የኢጣልያ ሹማምንት፣ እንዲሁም የጦር መኮንኖች፣ የደቡብ ትግል በእነዚህ የጦር አለቆች የሚፈታ መስሏቸው ነበር። ነገር ግን እንደ አሰቡት አልሆነም። ምክንያቱም ሰው እንጂ የሀገርና የነፃነት ፍቅር አይሞትም። አንዱ ሲሞት ሌላው ይተካልና። የጉራጌ አገር ትግል ከእነራስ ደስታ፣ ደጃዝማች ገብረ ማርያምና ደጃዝማች በየነ አስከሬን ጋር አልተቀበረም። ሌሎች ጀግኖች ተነሱ። በግልፅ እንደታየው ትግሉ ይበልጡኑ ተቀጣጠለ።

ለአርበኞች፣ ከየካቲት 19 ቀን 1929 ዓ.ም ጀምሮ ያለው ጊዜ አስቀድሞ የነፍስ ማዳኛ፣ ከዚያም የመልሶ ማጥቂያ ሆነ። በአካባቢው ያለው የጉራጌና የአማራ ኅብረተሰብ ጠላቱን ለመቋቋም ተደራጀ። ይህንን የውስጥ እንቅስቃሴ ጠላት ተረዳ። አፍራሽ እርምጃ ለመወሰድ የሚረዳውን የልምምጥና የማስፈራራት ሥራውን በጣምራ ቀጠለ። ለዚህ ጉዳይ መማሪያ ያደረገው ሙሴ ቀስተኛን ነበር።

እዚህ ላይ ስለ ሙሴ ቀስተኛ ማንነት አንዳንድ ነጥቦችን እንመልከት። ሙሴ ቀስተኛ ቀደም ብሎ ወደ ኢትዮጵያ በመግባት የአማርኛን ቋንቋ ያጠናና በየመኳንንቱ ቤት እየዞረ ወሬ የሚለቅም፣ የስዊስ ተወላጅ ነኝ ይበል እንጂ በ1888 ዓ.ም በአድዋ ጦርነት ጊዜ የኢጣልያ ወታደር ሆኖ መጥቶ ከተማረከ በኋላ ሳይመለስ እዚሁ የኖረ ሰው ነበር። ከንጉሠ ነገሥቱም መጠነኛ ቅርበት ነበረው። የኢጣልያ መረራ ሲንቀሳቀስ፣ የእነሱ ሰላይ ሆነ። አዲስ አበባ ሲገቡ ደግሞ፣ በአስታራቂነት ስም የአርበኝነት እንቅስቃሴ በሚታይባቸው ቦታዎች እየዞረ ነገር ሚካሄድ አመጣ። ዋና ዋና ሥራዎቹ ሦስት ነበሩ። ከእነዚህም

አንደኛው የአርበኛውን ልብ በስብከት መከፋፈል፣ ሁለተኛው ደግሞ አንዳንዱን ልበ ፍንቅል ወደ ጠላት እንዲገባና ለእነሱ መሣሪያ እንዲሆን ማድረግ ሲሆን፣ ሦስተኛው ደግሞ የአርበኞችን ሁኔታ እያጠና እነሱን ሚዋጓት የሚቻልበትን መንገድ ለጣልያን ምክር መስጠት ነበር። ይህ ሰው ወደ ቡልጋም ሄዶ ነበር። በዚያ ያደረገውን ከቦታው እገልፃለሁ። ቀደም ብሎ ከእነ ራስ ደስታ ጋር አድርጎት የነበረውን በመቀጠል፣ ወደ ጉራጌ አገር ሄደ። በዛ ግን ባላምባራስ /ደጃዝማች/ ገረሱ ዱኪ የሚመሩት የመራና የአመያ አርበኞች በስቅላት ስለቀጡት ጥበቡ ከሸፈ።

ወደ ዋናው ጉዳይ ስንመለስ፣ አርበኛው ጠላቱን በየቦታው ግንባር ለግንባር እየገጠመ ያርበደብደው ቀጠለ። በየካቲት ወር 1930 ዓ.ም ጠላት አዲስ ጦር ላከ። በሻለቃ /ደጃዝማች/ በቀለ ወያ የሚመራው አርበኛ በሶዶ እና በሜጫ ወሰን ላይ ገጥሞ ጥሩ ሥራ ሠራ። ብዙ ጀግኖች ቢሞቱና ሻለቃ በቀለም ጭምር ቢቆስሉም፣ በጦርነቱ በተገኘው ድል የአርበኛው ወኔ በረታ። ጠላት አከታትሎ ሌላ ጦር ላከ። በአይሮፕላን አካባቢውን ደበደበ። ነገር ግን አርበኞቹ እገምጃ ከተባለው ስፍራ ቦታ ይዘው ጠበቁት። በተረበም ጊዜ ጥሩ አድርገው ወጉት። አይሮፕላኖቹ አርበኛውን መጉዳት አልቻሉም። ጦርነቱ እስከ ተከፈተበት ጊዜ ድረስ ጠላት የነበሩበትን አላወቀም ነበር። ጦርነቱ ሲከፈት ደግሞ አርበኛው ፈጥኖ ከጠላት ጋር በመቀላቀል የጨበጣ ውጊያ ስለያዘ፣ ለይቶ መምታት አልቻለም። ከጎህ ቀዳዱ 12 ሰዓት የተከፈተው ጦርነት እስከ ቀኑ 9 ሰዓት ቀጥሎ፣ ጠላት በፍፁም ድል ሆነ። አርበኛው እየተከታተለ ጠላቱን ረፈረፈው። ብዙ የጠላት መኮንኖች በጦር ሜዳው ወድቀው ተገኙ። ብዙ መትረየስ፣ ዘመንጃና ጥይት፣ የመድፍ መጫኛ በቅሎዎች ጭምር ተማረኩ። ታላቅ ደስታ ሆነ። በመሆኑም ብዙ ጀግኖች መሐላቸውን አፀኑ።

በሙሴ ቀስተኛ ላይ የጠቀስኩት ቅጣት በመወሰዱ የተናደደው ጠላት፣ 44 ባታሊዮን ጦር ከጂማ፣ ከሲዳሞ፣ ከሐረርጌ፣ ከአርሲና ከሸዋ በማቅረብ ከበባ አደረገ። አርበኛውም ይህንን የቀረበለትን የጦርነት ማዕድ ለመቋደስ ተዘጋጀ። ወለኒ ዋቤ፣ አምቦ ጉዳ ከሚባለው ተራራ ላይ ግንባር ለግንባር ገጠመው። ጦርነቱ ያለዕረፍት ሦስት መዓልትና ሦስት ሌሊት ቀጠለ። አርበኞች በሚያስደንቅ ብርታትና ቆራጥነት ተዋጉ። የጠላትን ወታደር ጨፈጨፉት፣ ብዙ የጠላት ሹማምንት በጦር ሜዳው ላይ ወደቁ። ነገር ግን የጠላት ጦር ከብዛቱ የተነሳ የማይበገር ሆነ። በርካታ የአርበኛው መሪዎች ከሠራዊታቸው ጋር ወደቁ። ጦርነቱ እየከበደ ስለሄደ፣ በአንድ ወገን ያለው ከባቢ የጠላት ጦር ላይ በድንገት አደጋ በመጣል የጨበጣ ውጊያ በማካሔድ ጥሰውት ወጡ።

ጠላት በጦር ሜዳ ሲሸነፍ "...በሰላም ብረታችሁን አስረክቡ..." የሚል ደብዳቤ ፃፈ። አርበኛውም ብረት አግቡ በማለት የፃፈው ቃል ድፍረት መሆኑን በመግለፅ መልስ ሰጠው። ትግሉ ቀጠለ። መጋቢት 19 ቀን 1930 ዓ.ም ሌላ አዲስ የጠላት ጦር መጣ። ብዛቱም እያሌ ነበር። አርበኛውም በጠራ ሜዳ ላይ ገጥሞ በቀራጥነት ተዋጋ። ነገር ግን ጠላት ስለአየለ ጦርነቱን መቀጠል ወገንን ማስጨረስ ሆነ። ስለዚህ አርበኛው አካባቢውን ለቅቆ ወደ አዳሜ ቱሉ ሄደ። ከዚያም ወደ ቡልጋ ዞረ።

ወደ ቡልጋ ሄደው በዚያ ከነበሩ አርበኞች ጋር ከተመካከሩና የልምድ ልውውጥ ከአደረጉ በኋላ፣ የጉራጌ አገር አርበኞች ወደ ትውልድ አካባቢያቸው ተመልሰው ሥራቸውን ቀጠሉ። ቶሌ በረሌ ላይ ያጋጠማቸውን ጦርነት ከመቅጽበት ድል አድርገው አባረሩት። ብዙ የጠላት ወታደሮችና መኮንኖች በጦር ሜዳው ላይ ወደቁ። ጠላት ኃይሉን እንደገና አጠናክሮ ማጥቃት ቀጠለ። አርበኞችም እጨበር ቆሽት ላይ ቦታ ይዘው በመጠበቅ ገጠሙት። ከባድ ጉዳትም አደረሱበት። ለስምንት ሰዓት በተካሄደው ጦርነት ከጠላት ወገን ብዙ መቶ አለቆችና ሻምበሎች በጦር ሜዳው ወድቀው ተገኙ። ምርኮው ቁጥር አልነበረውም። እርግጥ ከአርበኞችም ወገን ብዙዎች ወድቀዋል።

የ1930 ዓ.ምቱ ትግል በዚህ ዓይነት ተጠናቅቆ የ1931 ዓ.ምቱ ቀጠለ። መስከረም 10 ቀን ባንቱ በተባለው ቦታ በተደረገው ጦርነት ጥሩ ሥራ ተሠራ። ጠላት ከምሽጉ ወጥቶ በጠራ ሜዳ ላይ ስለተጋጠመ፣ በዛ ለነበሩት አርበኞች ተመቻቸው። ለሰባት ሰዓት በተካሄደው ውጊያ ጠላት ተጠርንፎ ወደ ምሽጉ ገባ። አርበኞች ብዙ ግዳይና ምርኮ አገኙ።

የ1931 ዓ.ም ዘመን ለጠላት የሚዛን መጠበቂያ ሲወጣው፣ የአርበኞቹ ኃይል ደግሞ የማይበርድ መሆኑ ታወቀ። በዚህ ላይ የአይሮፕላን ድብደባው የተጠበቀውን ውጤት ማስገኘቱ እየቀነሰ ሄደ። ይህም ሆኖ ጠላት ገና ተስፋ አልቆረጠም ነበርና ማጥቃቱን አልተወም። አርበኞችም ጫካ ደፋሩ በተባለው ቦታ ገጠሙት። ጥሩ ውጊያ ተካሂዶ አርበኞች ድል አገኙ።

ጠላት በዚህ የማጥቃት ሙከራውን አላበቃም። ሚያዝያ 19 ቀን አዋሽ ላይ 5 ሰዓት ሙሉ የፈጀ ጦርነት አካሄደ። ወዲያው ደግሞ ሚያዝያ 23 ቀን ዝቋላ ላይ ሌላ ውጊያ ተካሄደ። እንደዚሁም ሰኔ 13 ረጲ በተባለው ሥፍራ ተደገመ። በተከታታይ ጅሮ በሚባለው ቦታ ውጊያ ተካሄደ። ቀጥሎም ሐምሌ 15 ቀን ጌቶ እሾ ከተባለው ሥፍራ በሁሉም ቦታ ቀኙ ለአርበኞች ሆነ። በጠላት ላይ የሚደርሰው ጉዳት እየበዛ፣ በአርበኞች ላይ የሚደርሰው እየተቀነሰ ሄደ። የጣልያን የጦር መኰንኖች

በየሜዳው ይረፈረፉ ጀመር። የሚማረከውም መሣሪያ ብዛት ከአርበኞቹ ሽክም በላይ ሆነ። ለምሣሌም ያህል በጌቶ እሾ ጦርነት ብቻ 800 ጠመንጃ ከብዙ ጥይት ጋር ተማረከ።

በዚህ መልኩ የድል ወጋገን እየቀደደ ሲመጣ የንጉሠ ነገሥቱ የጦር አንቅስቃሴ ደግሞ እየተሰማ መጣ። ይህም በጠላት ላይ ድንጋጤን፣ በአርበኞች በኩል ብርታትን ፈጠረ። በ1933 ዓ.ም መባቻ አዲስ ምዕራፍ ተከፈተ። ጥቅምት 11 ቀን 1933 ዓ.ም ዝቋላ፣ ወንበራ በተባለው ቦታ ጦርነት ተደርጐ ጥሩ ተግባር ተሠራ። በዚሁ ቀን አቡ ከሚባለው ቀበሌም እንደዚሁ መልካም ተግባር ተሠራ። በሌላ አገላለፅ፣ በልጅ የጨዋታ ፊሊጥ ሥሉስ ዞረ እንደሚባለው ሆነ።

ጥቅምት 13 ቀን 1933 ዓ.ም ሌመን ከሴ በተባለው ቦታ በድንገት ተኩስ ተከፈተ። የበለጠው ምቹ ቦታ በአርበኞች እጅ ስለነበር ቀናቸው። የጣልያን ጦር ደግሞ እንኳን ቆሞ መዋጋት፣ ሸሽቶ ማምለጥ አቃተው። ዋናው የጦር አዛዥ የነበረው ኮሎኔል ከሳበላ፣ ከብዙ የጣልያን መኰንኖች ጋር በጦርነቱ ላይ ወደቀ። አንድ ነጭ መኰንን ተማረከ። አሥራ ሦስት ካሚዮኖች በአርበኞች እጅ ተቃጠሉ። የከሳበላ ሻንጣ ሲከፈት ታላቁ ባለእንበሳ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ተገኘ። ሠራዊቱም በአንድነት ቆሞ፣ የጎሊና ፀሎት አድርሶ፣ ከፍ አድርጐ አውለበለበው። ብዙዎቹም ከደስታ ብዛት አለቀሱ።

ጠላት የሞት ሞቱን ማጥቃት ቀጠለ። መጨረሻ በተባለ ቦታ በተደረገው ጦርነት ሦስት መትረየስ ከብዙ ጠመንጃና ጥይት ጋር በአርበኞች ተማረከ። ጣልያን ከጂማ፣ ከሊዳሞ፣ ከአርሲ፣ ከናዝሬት ከሞጆ፣ ከቢሾፍቱ፣ ከወሊሶ፣ ከአዲስ አበባ ጭምር አዲስ ጦር አመጣ። አርበኞችም በድፍረት ገጠሙት። ጥር 7 ቀን 1933 ዓ.ም ከንጋት እስከ ምሽት በተካሄደው ጦርነት ብዙ የጠላት ወታደሮች ወደቁ። ከአርበኞችም ጥቂት ሞቱ፣ ሌሎች ጥቂት ቆሰሉ። በተከታታይ መቂ እና በዲቂሮ ላይ በተደረጉ ጦርነቶችም አርበኞች ቀናቸው።[2]

ማጣቀሻ ፅሑፎች

1. ለይፋ አባ ወሎ፣ *የታሪክ ማስታወሻ*፣ ገጽ 171-191።
2. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 191-200።

ምዕራፍ ሃያ ሁለት
በጋሞ ጉፋ የተካሄደው ትግል

መጀመሪያ ላይ የጋሞ ጉፋ ጦር የዘመተው ወደ አጋዴን ነበር። የተንዘውም በወላይታ፣ በአላባ ቁሊቶ፣ በሻሸመኔ አድርጉ ባሌ በመግባት ነበር። የባሌ ጦር ከምዕራብ ሐረርጌ፣ ከአርሲና ከሲዳሞ ጦር ጋር ተቀላቅሎ ምን እንደሠራ ቀደም አድርገን አይተናል። ከአልቂት የተረፈው ጦር በወላይታ አድርጉ ወደ ቡልቂ ተመለሰ። የጠላት ጦር የሲዳሞን ከፍለ ሀገር እጅ ከአደረገ በኋላ፣ ይህንን ሠራዊት ተከታተለው። የመጀመሪያው ጦርነት ቡልቂ ላይ ነበር። ምንም እንኳ የኢትዮጵያ ሠራዊት ከክክምትና ከድካም ገና ያላገገመ ቢሆንም፣ በርትቶ ተዋጋ። ነገር ግን ጠላት የአንዱ ጦር ሲደክምበት ሌላ አዲስ እያቀረበ ማጥቃቱን ስለቀጠለ፣ የኢትዮጵያ ሠራዊት ያንን አካባቢ ለቅቆ ወደ ደቡብ ተንዘ።

ጠላት እንደልማዱ እግር በእግር ተከታተለው። ሌላው ጦርነት ደግሞ ባኮ ጋዘር ሆነ። ከዚያም ኢትዮጵያውያን የጀግንነት ተግባር ሠሩ። ጠላት አንዱን ቡድን ሲያባርር፣ ሌላ ቡድን ከኋላው እየደረሰ ብዙ አጠቁት። የኢትዮጵያ ሠራዊት በዚህ ዓይነት እየተከላከለ፣ የሞተው እየሞተ፣ የተረፈው ኬንያ ጠረፍ ደረሰ።

የሲዳሞ ጦር ወደ ባሌ ለመሻገር ቆሽ ከተባለው አካባቢ ሲቃረብ፣ ከጠላት ከድተው ከኢትዮጵያውያን ጐን ቆመው ከነበሩት ሐማሌኖች መካከል አንዱ ቡድን ከራስ ደስታ ጋር ሲቀጥል፣ ሌላው ቡድን ከኢትዮጵያ ጦር ተሰይቶ ወደ ኋላው ተመልሶ እንደነበር ባለፈው ተመልክተናል።

ወደ ኋላው የተመለሰው ቡድን በጉዞ ላይ ሳለ አባላቱ እርስበርሳቸው ሳይስማሙ ቀሩና እንደገና ከሁለት ተከፈሉ። አንደኛው፣ በቀኛዝማች ሰለባ ይመራ የነበረው ቡድን፣ አንድ መቶ አባላት ነበሩበት። ቡድኑ ጉፋ ውስጥ ከገባ በኋላ የጠላት ጦር ስለአጋጠመው 15 ቀን የወሰደ ውጊያ አካሂዶ ግዳጁን ተወጣ። አባላቱ በሙሉ በጦር ሜዳ የክበር ሞት ሞቱ። ምክንያቱም ቢማረኩ የሚጠብቃቸው አበሳ ከባድ ነበር። በቀኛዝማች ገብራይ የሚመራው ሌላኛው ቡድን ግን ምንም ያህል ችግር ሳያጋጥመው ኬንያ ለመግባት ቻለ።[1] በሌላ ወገን ከራስ እምሩ ኃይለሥላሴ ጦር፣ ከጊቤ በክበር ተሰናብተው የመጡት ኤርትራውያን ከደጃዝማች ወልደ ማርያም ጦር ጋር ተቀላቀሉ። ከዚያም ከኢትዮጵያውያን ጋር ሆነው ጠላትን በመከላከል ኬንያ ገቡ።

እዚህ ላይ ከጠላት ከድተው ሱዳን የገቡ ሦስት የኢጣልያ ወታደሮች ለእንግሊዞች በሰጡት ቃል "...በበኩና በኩልም ካሉ

ኢትዮጵያውያን ጋር ተዋጋን።... በባኮ አስከ ቆላ ዘጠኝ ጊዜ ተዋጋን። ሁልቀን ከእኛ አይሞትብንም፣ ከኢጣልያ በኩል ግን እንገድላለን። በከፋም ተዋግተን አንድ ነጭና ብዙ ወታደሮች ገድለናል..." ማለታቸውን መጥቀስ ተገቢ ይሆናል።[2]

ወደ ኬንያ የሄደው ሠራዊት ከኢትዮጵያ ከወጣ በኋላ የቀረው ጦር በጋርዱላ አውራጃ፣ ጉማይዴ ላይ ተዋግቶ ጥሩ ውጤት አገኘ። በዚያም ቡድን የሃያ አንድ ዓመቱን ወጣት ልጅ /ደጃዝማች/ ተስፋዬ ወልዴን መሪ አድርጉ መረጠ። በጋሞ ጉፋና በደቡብ ቦረና እየተዘዋወረ ጠላት በየሠፈረበት ቦታ አደጋ በመጣል ተደጋጋሚ ጉዳት አደረሰበት። በጋርዱላ አውራጃ በጉማይዴ፣ በኃይሎታ፣ በበነያ፣ በማሽሎ፣ በዛርጉላ የጦር ሜዳዎች ከጠላት ጋር ተፋለመ። ዋና ሥልቱ የጠላት ወታደር በውሃ ጥም በሚደክምበት ጊዜ ጠብቆ መምታት፣ እንዲሁም ሥንቅና ትጥቅ ማግኘት ነበር። በ1933 ዓ.ም ደግሞ ቡድኑ ከክፍለ ሀገሩ ዋና ከተማ ሠሠንቻ በመግባት አካባቢውን ከጠላት በማፅዳት የሀገሩን ሰላም አረጋገጠ።[3]

ማጣቀሻ ፅሑፎች

1. ሰይፉ አባ ወሎ፣ *የታሪክ ቅርስ*፣ ገጽ 158።
2. ሕይወት አደሩ፣ *ያቺ ቀን ታሪኳች*፣ ገጽ 71።
3. "የጀግኖች አደራ"፣ የጀግኖች ማህበር መጽሔት፣ መጋቢት 1983 ዓ.ም፣ ገጽ 37-39።

ምዕራፍ ሃያ ሶስት
በኢሊባቡርና በከፋ የተካሄደው ትግል

በራስ እምሩ ኃይለሥላሴ የተመራው የኢትዮጵያ ሠራዊት ከሽሬ ጦርነት በኋላ በጉንደርና በጉጃም አድርጉ ዓባይን በመሻገር በወለጋ በኩል ኢሊባቡር፣ ጉሬ ገባ። ጦሩ ይህንን ያደረገው መንግሥቱ ወደ ጉሬ ተዛውሮ ጦርነቱ በመንግሥት ደረጃ እንዲቀጥል ታቅዶ የነበረውን ሐሳብ በመከተል ነበር። ነገር ግን ንጉሠ ነገሥቱ ባልታሰበ ሁኔታ ትተው ወደ አውሮፓ በመሄዳቸው ይህ ዕቅድ ወደቀ።[1]

በራስ እምሩ የሚመራው ቡድን ከአድካሚ ጉዞ በኋላ ጉሬ ሲገባ፣ ጉስታፍ ርዝን የተባሉት ኢትዮጵያን የሚወዱ የስዊድን መሥፍንም በአደሮፕላን ጎሬ ገቡ። ነገር ግን በአዛዥ ወልደ ፃድቅ መሪነት ወደ ጎሬ ተዛውሮ ጦርነቱ እንዲቀጥል የተሰጠውን ትዕዛዝ ተግባራዊ ማድረግ ስለአልተቻለ፣ ሌላ አዲስ መመሪያ ከንጉሠ ነገሥቱ፣ ከሰንደን ተጠበቀ። የተሳለፈው መመሪያ የተፃፈው ሐምሌ 12 ቀን 1928 ዓ.ም ሲሆን፣ የተላከውም በእነ ልጅ ፈቃደ ሥላሴ ጎሩይና በእነ ብንያም ነበር። እሱውም የእንደራሴ ሥልጣን የሚሠጥ፣ ቢትወደድ ወልደ ፃድቅን ጠቅላይ ሚኒስትር የሚያደርግና 12 ሚኒስትሮች እንዲሾሙ የሚፈቅድ ነበር።[2]

ሁኔታው በዚህ ዓይነት በእንጥልጥል እንደአለ የራስ እምሩን ጎሬ መግባት የሰማው የጥቁር አንበሳ ጦር ንስግሶ በጥቅምት ወር 1929 ዓ.ም ጎሬ ደረሰ። በነባሩ የራስ እምሩ ጦር ላይ ይህ አዲስ የተማሩ ወጣቶችን ያቀፈ ቡድን ሲቀላቀል ጦሩ፣ አዲስ ስሜት አደረበት። አዲስ አበባን ለማጥቃት አሰበ። ጦሩ ከጉሬ ተነስቶ በወለጋ በኩል ወደ አዲስ አበባ አመራ። ራስ እምሩም በጉስታ ቮን ሮዛን አይሮፕላን ወደ ሱዳን ለመሄድ ሲችሉ የሠራዊቱን ጥያቄ ተቀብለው በመሪነት ቆሙ። ምክር ተደርጉ አዲስ የጦር ዕቅድ ተሠራ። እቅዱም፡- 1ኛ/ ራስ እምሩ በነበራቸው ጦር ላይ የጥቁር አንበሳን ሠራዊት ጨምሪው እየመሩ በወለጋ በኩል ወደ አምቦ ሊጓዙ። 2ኛ/ በወቅቱ በጎሬ ከተማ የነበሩት ቢትወደድ ወልደፃድቅ በዚያ የነበረውን ሠራዊት ይዘው በጂማ በኩል እስከ ወሊሶ ድረስ ሊመጡ ሲሆን፤ ዓላማው አዲስ አበባን ከብሶ ጠላትን መድረሻ ማሳጣት ነበር። ሻለቃ በልሁ በስደት ሔደውበት ከነበረው ከካርቱም ተመልሰው በጋምቤላ በኩል በመግባት ከዚህ ጦር ጋር ተሰልፈው ነበር።

ነገር ግን የራስ እምሩን ጦር አመጣጥ የጠላት ጦር አስቀድሞ ሰምቶ ኖሮ፣ ጉዴ ከተባለው ቦታ ጦርነት ገጠማቸው። የኢትዮጵያ ጦር ብልሙ እየተሳበ፣ በጉምብስ እየከበበ ከምሽጉ ከተጠጋ በኋላ፣ በሕብረት ከምሽጉ ዘልሎ በመግባት የጠላትን ወታደር በጠመንጃ፣ በሳንጃ፣ በጩቤ፣ በጉራዴ፣ ባጭሩ

በያገኘው ሁሉ መሣሪያ ወጋው። የአንድ ቀን እረፍት ከተደረገ በኋላም ምክር ተጀመረ። አንዱ ክፍል በቀድሞው ሐሳባችን ፀንተን ወደ አምቦ እንቀጥል ሲል፣ ሌላው ቡድን መንገዳችንን ለውጠን ወደ ጂማ እንሂድ አለ። አዲስ አበባን ለማጥቃትና መልሶ ለመያዝ የታሰበው ሕልም መሆኑ ስለ ታመነበት፣ ወደ ጂማ እንሂድ የሚለው ሀሳብ የድምፅ ብልጫ ስላገኘ ወደ ጂማ ለመሄድ ተወሰነ።

ጦሩ በውሣኔው መሠረት ከወለጋ ወደ ጂማ ተሻግሮ በደሌ ገባ። ከዚያም በጉማይ በኩል አድርጉ አጋሮ ደረሰ። ጦሩ አጋሮ ሲገባ ጠላቱን ለማጥቃት የሚችል፣ ማጥቃት ባይችል ደግሞ ለመከላከል ምቹ ቦታ የሚያገኝ መስሎት ነበር። ነገር ግን እንደዚህ አልሆነም። ሦስት ጣምራ ችግሮች አጋጠሙት። ከእነዚህም አንዱ የጂማ ከተማ በጠላት መያዝ ሲሆን፣ ሁለተኛው በአካባቢው የነበረው የአማራ ሕዝብ ነፍሱን ለማዳን በዙሪያው ተሰብስቦ ሰፈረ። ሦስተኛው ደግሞ ለጠላት አይሮፕላን መጋለጡ ሆነ። እነዚህ ሁኔታዎች ጦሩን እንደምን ለመፈታት እንደአደረሱት ቀጥሎ እንመለከታለን።

የራስ እምሩን አጋሮ መግባት የሰማው የአማራ ሕዝብ ሴት ወንድ፣ ልጅ አዋቂ ሳይል በዙሪያቸው ተሰባሰበ። አሰባሰቡም ነፍሱን ለማዳን ስለነበረ መላቀቅ አልተቻላቸውም። ይህም የሆነበት ምክንያት አባ ጀቢር የተባሉው ባላባት ለአንድ የአማራ ጭንቅላት ሠላሣ ብር እከፍላለሁ የሚል አዋጅ ጠላትን ለማስደሰት አስወጥቶ አማራውን ያስፈጅ ስለነበር ነው። በዚህ ዓይነት ያስቆረጠውን ጭንቅላት ለጣልያን እያቀረበ ገንዘብ ይቀበልበት ስለነበር፣ አንድ ንቅሳት ያለበት የአንድ ሴት ራስ አቅርቦ ጣልያን አዋጁን በሌላ አዋጅ እስከ.ሸርበት ቀን ድረስ የአባ ጀቢር መመሪያ ፀንቶ ተሠርቶበታል። በዚህ አዋጅ መሠረት የስንት አማራ ራስ እንደተቆረጠ ባይታወቅም፣ በጣም ሺህ እንደሚቆጠር ግን አሳጠራጠረም።

ወደ ዋናው ታሪክ ስንመለስ ይህ ሁኔታ ከ3 ሺህ የማይበልጠውን ጦር ከብዙ ጓዝ ጋር እስከ 30 ሺህ አደረሰው። በመሆኑም ቀልጣፋነቱን ቀነሰበት፤ ኃላፊነቱን ደግሞ አከበደበት።

ጉዲ ከተባለው ቦታ ከ10 ሰዓት ጀምሮ ሌሊቱን ጭምር በመጓዝና ቀን ከሥላ ውስጥ በመደበቅ ያሳልፍ የነበረው ጦር፣ አጋሮ ከተማ ሲገባ ስጠላት አይሮፕላን ጥቃት ተጋለጠ። በዚህ ጊዜ የጠላት አይሮፕላን ከትንፋሽ ጋር ገብቶ ሳንባን እያሳበጠ የሚገድል መርዝ እረጨበት። ጦሩም የተገኘውን ጨርቅ በውሃ እየነከረ አፍና አፍንጫውን እንዲይዝ ፈጣን ትዕዛዝ ለሕዝቡ በማስተላለፍ አደጋውን ተከላከለ። ይህ በመደረጉ በሰው ላይ እምብዛም ጉዳት ሳያደርስ ቀረ።

የጂማ በጠላት እጅ መውደቅ በራስ እምሩ ለሚመራው ጦር ታላቅ ጉዳት ነበር። ሁኔታው አዲስ አበቧን ለማስጨነቅ፣ ብሎም ለማስለቀቅ

የነበረውን ዓላማ ሲያፈርስበት፣ የጎሬ ከተማ ከጠላት እጅ መግባት ደግሞ የባሰ ጉዳት አመጣ። የራስ እምሩንም ጦር ወደ አንድ የጠላት ከበባ አቃረበው። ከዚህ ላይ የጎሬን ዕድል ፈንታ መመልከት ያስፈልጋል።

ጎሬ ለመከላከያ ማዕከልነት መመረጥዋ በጠላት ዘንድ የታወቀ ነበር። ስለዚህ ከአዲስ አበባ በወለጋ በኩል ገስግሶ ህዳር 17 ቀን 1929 ዓ.ም ያዛት። የራስ እምሩ ጦር ወደ ወለጋ፣ የቢትወደድ ወልደ ፃድቅ ጦር ወደ ጂማ በመንቀሳቀሱ ከተማይቱ ተከላካይ አልነበራትም። በኮሎኔል ማልታ የሚመራው ጦር ከተማይቱን ለመያዝ ሲቃረብና በዚያ የነበሩ አርበኞች ተከላክለው ማዳን አለመቻላቸውን ሲረዱ፣ ጳጳሱን ይዘው ሚንቤ ወደሚባል ቦታ ሄዱ። ሐላባቸው ከስፋ አርበኞች ጋር ለመቀላቀል ነበር። ነገር ግን ጠላት ፈጥኖ ደረሰባቸው። ጦርነት ተደርጉ ከሁለቱም ወገን ሠላሳ፣ ሠላሳ ያህል ሰው ሞተ። የተረፉት ኢትዮጵያውያን ተማረኩ። የተማረኩትን ጣልያን ወደ ጎሬ እያንገላታ መልሶ ወስዶ የኢትዮጵያውያኑን ጳጳስ አቡነ ሚካኤልን ጭምር በአደባባይ በመትረየስ ረሸናቸው።[3] ዕድል የቀናው፣ ከምርኮ ያመለጠው የኢትዮጵያ ጦር ብቻ ወደ ከፋ ተሻግሮ ትግሉን ቀጠለ።

የጅማና የጎሬ መያዝ በራስ እምሩ የሚመራውን ጦር ሌላ መንገድ እንዲቀይስ ስለአስገደደው፣ ጦሩ ምክር አደርጉ የደኛዝማች ታዬ ጉልላት ግዛት ወደ ነበረው ወደ ከፋ ለመሄድ ወሰነ። ሐሳቡም ነፍሱን በዛ ለማዳንና የተሰበሰበውን ሕዝብ ወደዚያ ወስዶ የተረጋጋ ሁኔታ በመፍጠር አዲስ የጦር እቅድ ለማውጣት ሆነ። ጉዞው አስቸጋሪ ነበር። ከችግሩ አንዱ የጓዙ መብዛት ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ሀገሩ ጥቅጥቅ ባለ ጫካ የተሸፈነ፣ ለብዙ ወራት ዝናባማ፣ መንገዱ ጭቃና ማጥ የበዛበት መሆኑ ነበር። በዚህ ላይ ደግሞ የጠላት እግር በእግር መከተልና የአየር ድብደባውን ማጠናከሩ፣ ጉዳት አበዛ። ቢሆንም ጦሩ ይህንን ሁሉ አበሳ ችሎ ጉዞውን ቀጠለ። ጠላት የጦሩን እንቅስቃሴ በንቃት ይጠባበቅ ነበርና ደን ከሌለበት አውሳላ ሜዳ ላይ ሲደርስ በአይሮፕላን ድብደባውን ያዘ። ነገር ግን ከስድስት የጋማ ከብቶች በስተቀር ወዲያና ወዲህ ይተረማመስ ከነበረው ከዚያ ሁሉ ሰው መግደል ቀርቶ አንድ እንኳን አላቆሰለም። በዚህም ሕዝቡ በወቅቱ እግዚአብሔርን እንደ አመሰገነ የነበሩ ተናግረዋል።

በዚህ ዓይነት ጦሩ ጥቅጥቅ ባለ ጫካ ውስጥ ተጉዞ ከአንድ ገላጣ ቦታ ደረሰ። ሕዝቡ በጉዞው ርዝመትና በረሃብ ተጐድቶ ነበር። ጥቂት ጠንቃቃ ሰዎች ከያዙት ዳቦ ቆሎ፣ ቋንጣ፣ ድርቆሽ አቃመሱት። ከሰው ድካም የተነሳ በአካባቢው የነበሩትን ከብቶች እርዶ መብላት እንኳን አልተቻለም። ነገ አርደን እንበላለን በማለት በተስፋ ተኛ። ነገር ግን በማግስቱ ጥዋት ፊጽሞ ያልተጠበቀ ጦርነት አጋጠመ። እግር በእግር ይከተል የነበረው የጠላት ጦር ጌራ ላይ ደረሰበት። ምንም ድካም ቢበዛበት የኢትዮጵያ ጦር ከመጋጠም በስተቀር ሌላ ምርጫ አልነበረውም። የመጣው የጠላት ጦር ከወለጋ፣ ከጂማና

ከጐሬ የተጠራቀመ ነበር። የኢትዮጵያም ጦር ጓዝ ይብዛበት እንጂ በኢትዮጵያ የውጊያ ስልት የዳበረ ልምድ ያለው ዋኛው የራስ እምሩ ሠራዊት ሲሆን፣ ሌላው ክፍል ደግሞ በዘመናዊ የጦር ትምህርት የሠለጠነው የጥቁር አንበሳ ጦር ነበር። ይህ ስመ ጥር ጦር ሠራዊት የራስ እምሩ አመራር ጥንካሬ ሰጠው። ጠላቱን ግንባር ለግንባር ገጠመው። የኢትዮጵያ ጦር በመሬት ላይ ተኝቶ፣ በየቅርንጫፉ ላይ ተንጠልጥሎ፣ በየግንዱ ላይ ተጣብቆ በጥይት ይቆላው ጀመር። የተራበ አንጀቱን አስሮ፣ ሆዱ በጥጋብ የተቀበተተውን ጠላቱን ረፈረፈው። ውጊያው ከንጋት ጀምሮ እስከ 9 ሰዓት ቆየ። ወንዙ በኢትዮጵያውያን እጅ ገባ። የኢትዮጵያ ጦር ተግባሩን የውሃ ጥማቱን አበረደ። በአንፃሩ የጠላት የውሃ መትረየሶች ውሃ በማጣት ሥራቸውን አቆሙ። አርበኞች እንደ ሥርዓታቸው ከጠላት ጋር ተቀላቅለው የጨበጣ ውጊያ አካሄዱ። የኢትዮጵያ ጦር ይህን ከሠራ በኋላ የሚደርስበትን ጉዳት ለመቀነስ ወደ እርዱ ተመለሰ። ሕዝቡ እልል በማለት ወታደሩን አጽናና።

ጦርነቱ እንደ ጠላት አመጣጥ የከፋ ሊሆን ይችል ነበር። የጥቁር አንበሳ ታሪክ ዘጋቢ አቶ ታደሰ ሜጫ እሳቸው በዋሱበት ጉራ ከጠላት ወገን ሁለት መቶ ወታደር ሞቶ ብዙ እንደቆሰለ፣ ከአርበኞቹ ወገን የሞተውም፣ የቆሰለውም ከአንድ መቶ እንደአልበለጠ ገልጸዋል። ብዙ ሰላማዊ ሰው እንደሞተና እንደቆሰለ አስረድተዋል። በሌሎች ሁለት ጉራዎች የነበረው ሁኔታም ከዚህ እምብዛም እንደማይለይ ገምተዋል። ዋናው ነገር በዚያ ውጊያ ድሉ በማያወላውል ሁኔታ የኢትዮጵያ መሆኑ ነው።

ሠራዊቱ ከጌራ ተነስቶ ጉዞውን ቀጠለ። ቀደም ብዬ እንደገለጽሁት ጦሬ ጓዝ ከብዶበታል። አሁን ደግሞ በጦርነቱ የቆሰለውና ራሱን የማይችለውን ሰው መሸከም ተጨመረበት። ጥቂት እንደተጓዘ ለሰውም፣ ለከብትም አስቸጋሪ ከሆነ ማጥ ውስጥ ገባ። በቃሬዛ ተይዘው ይጓዙ ለነበሩ ጀግኖች የአካልና የኅሊና ቁስል ሆነባቸው። በዚህም የተነሳ ከቁስለኞች አንዱ፣ ሻምበል ሰማ አባየሬ "...ተራችሁ እስኪደርስ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሁን..." በማለት በጥቁር አንበሳ ሠራዊት ደንብ፣ ስምንተኛ ቁጥር መሠረት የተሰጠውን የመትረየስ ሽጉጥ ነቅሎ ሕይወቱን አሳለፈ።

ሠራዊቱ ወደ ጐጀብ ወንዝ ጉዞውን ቀጠለ። በጠላት የተገዙ ባላገሮች በየጫካው እየተሸጐጡ ብዙ ሌትና ሽማግሌ፣ ልጅ ገደሉ። አንዳንዶችም ስለ ወንድ ልጅ ጨርሱን እያሉ ከሰቃያቸው ለማረፍ ይሰምኑ ነበር። ከደጃዝማች ታዬ ጋር ተቀላቅሎ ከረሃብ ለመዳንና ትግሉንም በተጠናከረ ሁኔታ ለመቀጠል ተሰፋ አድርጐ የነበረው ይህ ሠራዊት፣ ቀደም ብሎ እንዲሠፍር ምልክት ተደርጉበት ከነበረበት አንዲት ቦታ ደረሰ። አንዳንድ ጐጀምችና የዘይት ጣላምች፣ ቀዳዳ የምግብ ዕቃ መያዣ ቆርቆሮዎች ወድቀው ይታዩ ነበር። ማለትም በዚያች ቦታ የጠላት ወታደር ሳያልፍ እንዳልቀረ የማያጠራጥር ሁኔታ ተስተዋለ።

ጠላት የጐጀብን ወንዝ ተሻግሮ፣ መድፍና መትረየሱን ጠምጥሞ ይጠብቅ ኖሮአል። ጦሩ ያስተናግደናል ብሎ ተስፋ የጣለባቸው ደጃዝማች ታዬ ለጠላት ገብተው ኖሯል። ሴሊቱን ወደ ሣጃ ከተማ የሚሄደውን የኢትዮጵያ ሠራዊት ጠላት ከሚካ ውስጥ እያወጣ መሣሪያውን በመቀበል ወደ ማረፊያ ቤት ሲያስገባ ስለአደረ፣ የሠራዊቱ ኃይል ተቀንሶ ኖሯል። ነገር ግን እነዚህ ሁኔታዎች በጦሩ ዘንድ አልታወቁም። ጥዋት ሲነጋ የተደራጀ የጠላት ጦር በወንዙ ማዶ እንደሚጠብቀው ሲረዳ አርበኛው አዘነ። ጦርነትና ረዛብ የመተረውን፣ የቀንና የሌሊት ጉዞ ያንገላታውን ወታደር እንደገና መልሰህ ተዋጋ ማለት ለጦር መሪዎች ከባድ ነገር ሆነባቸው። መራር ሐዘንም ተሰማቸው።

ሠራዊቱ ከድንጋጤው ሳይነቃ ሁለት የጣልያን መኮንኖች ሙሉ የጦር ልብስ እንደለበሱ በቀኛዝማች መጅድ አቡድ መሪነት ከሠፈሩ ደረሱ። ወደ ራስ እምሩም ገብተው ተነጋገሩ። ራስ እምሩ በዶክተር ዓመሰወርቅ በየነ ኃላፊነት ሦስት ኢትዮጵያውያን መኮንኖች ወደ ጣልያኖቹ ሠፈር በመላክ እንዲነጋገሩ አደረጉ። ጣልያኖቹ እጅ ከመስጠት በስተቀር አንዳች ነገር አንቀበልም አሉ። ራስ እምሩ ይህንን ሲሰሙ ከጦር ሹማምንቶቻቸው ተመካክረው የተከተላቸውን ሰላማዊ ሕዝብ ሳይቀበላቸው ከጣልያን ጦር መሪ ጋር እንደማይነጋገሩ አስታወቁ። የጣልያን የጦር መሪ ጥያቄአቸውን በመቀበል ሰላማዊዉን ሕዝብ ወሰደ። ተከትሎአቸው የነበረውን ሰላማዊ ሕዝብ ከአስረከቡ በኋላ ራስ እምሩ እጅ አልሰጥም አሉ።



ጀግናው ራስ እምሩ ኃይለሥላሴ

ሁኔታው በእንዲህ እንደአለ ለጣልያኑ የጦር አዛዥ በእጅ የገቡትን ሰላማውያን ሕዝብ እንዲጨርስና የራስ እምሩን ጦር በጋዝ መርዝ እንዲያጠፋ ከግራዚያኒ ትዕዛዝ በቴሌግራም ደረሰው። የጦር አዛዡ የደረሰውን ትዕዛዝ ገልጦ የማስጠንቀቂያ ቃል ሰጠ። ቃሉም "... ሰላማዊውን ሕዝብ መረከባችን

እናንተን ስንፈልግ እንጂ፣ ሽክማችሁን በገዛ እጃችን አቃልለን እንደገና በሙሉ ጉልበት እንድታጠቁን አይደለም። ... እምቢ ብትሉ ግን የተረከብነውን ይህንን እጅግ የበዛ ሕዝብ ...ያሰርህራቴ መፍጀታችን ... አሁኑኑ እወቁት..." የሚል ነበር። አያደርጉትም ተብሎ አልተጠረጠረም። ምክንያቱም ጣልያኖች ሜካኒኤቸውን ቀደም ብለው በግብር አሳይተው ነበርና።

በኢትዮጵያውያን ዘንድ ምክር ተደረገ። ጠላት ጦሩ በ24 ሰዓት እጅ እንዲሰጥ ስለአዘዙ፦

1ኛ. ለሕዝቡ ሕይወት ሲባል ጦሩ እጅ እንዲሰጥ፣

2ኛ. ከጣሊያን ከድተው ከኢትዮጵያውያን ጐን ከቆሙት፣ ከሞት የተረፉት ኤርትራውያን ከጎሬ ግምጃ ቤት የተወሰደው ገንዘብና ጥሩ ጥሩ መሣሪያ ተሰጥቶአቸው እጃቸውን በፍጥነት እንዲያወጡ ተወሰነ።

ውሣኔው ለሠራዊቱ በተገለፀለት ጊዜ ከባድ ሐዘን ሆነ። ኤርትራውያኑ እንደተወሰነው ተደርጐላቸው በሸኘ እጃቸውን አወጡ። የኢትዮጵያም ሠራዊት ሌሊቱን በእጁ የሚገኘውን ጥሩ ጥሩ መሣሪያ ከጐጀብ ወንዝ ውስጥ ሰቀቀው።

ይህ ሁሉ ከተደረገ በኋላ ራስ እምሩ ሠራዊታቸውን አስከትለው ወደ ምርኮው ሠፈር አመሩ። ሽጉጣቸውን እንደታጠቁ በበቅሎአቸው ላይ እንደተቀመጡ ነበሩ። ቀኛዝማች ደጀኔ የተባሉት የጦር መሪ ከጣልያን የጦር መኮንን የተማረከ የደንብ ልብስ ከእነ ማዕረጉ ለብሰው በሌላ በቅሎ ተቀምጠው ጌታቸውን ተከተሉ። ሠራዊቱ በክብር ከጠላት ሠፈር ገባ። ጣልያኖቹም የወገናቸውን የክብር ልብስ የለበሰ ኢትዮጵያዊ ባዩ ጊዜ ተብሳጩ።

ጦሩ እጅ ከሰጠ በኋላ የጠላና የፈራውን ውርደት ተቀበለ። ኢጣልያኖች አንድ በአንድ መሣሪያውን ገፈፉት። ቀኛዝማች ደጀኔ ያንን የኢጣልያዊ መኮንን የክብር የጦር ልብስ ከየት እንደ አመጡት ጠየቃቸው። እሳቸውም በሞታቸው ቆርጠው በግድ የለሽነት በታላቁ የሰሜን ጦርነት ላይ እንደማረኩት ነገሩት። እሱም ሰውየውን ወዴት እንደአደረሱት መልሶ ጠየቃቸው። አጥብቆ ጠያቂ እናቱን ይረዳል እንዲሉ "...እሱን ገድዬ መሣሪያውን ገፈፍኩት። ልብሱንም ይኸው እንደምታየው ለበስኩት..." አሉት። በማናቸውም ጊዜ ቢሆን ሀገራቸውን በሚመለከት ጉዳይ ሁሉ መሥዋዕት ለመሆን ዝግጁ ነበሩና። እሱም ለጊዜው ምንም አላደረጋቸውም።

የኢትዮጵያ ጦር ከተማረከበት ከጐጀብ ወደ ቦንጋ ከተማ በትካዜና በሐዘን ጉዞውን ቀጠለ። ጀሌውን ስለነበረ፣ ከግል ዕቃው በስተቀር ሌላ ሸክም አልነበረበትም። ነገር ግን ሁኔታው ከድንጋይ የሚከብድ እንደ ነበር በሕይወት የተረፉ መሥክረዋል። አንዳንድ የጠላት ወታደሮች ወንድሞቻችንን የፈጁብን



ጀግናው ራስ እምሩ ኃይለሥላሴ

እነዚህ ናቸው እያሱ በሰደፍና በአለንጋ ይመቱታል። ምርኮኛው በዚህ ዓይነት የመከራ ጉዞውን ቀጥሎ በሁለተኛው ቀን ቦንጋ ገባ።

በዛ ራስ እምሩ ከጦራቸው ተለይተው በጥንቃቄ ከሚጠበቁበት ቦታ ተቀመጡ። ጦራቸው የግዙት ቦታ ተመራና የጦር መሪውን ድንኳን ከብቦ ሠፈረ። ሠፈሩን ጠላት በመትረየስና በመድፍ ዙሪያውን አጠረው። ራስ እምሩን ወደ አዲስ አበባ የሚያወጣ አይሮፕላን የሚያርፍበት ሜዳ ዝግጅት ተካሄደ። ጣልያን አገሬውን እያስገደደ ደኑን ያስመነጥር፣ አባጣ ጉባጣውን ያስደለድል ነበር።

ሜዳው ተደልድሎ ሲያልቅ የጣልያን አይሮፕላኖች መጥተው አረፉ። በአንዲት ትንሽ ከተማ እየኖሩ እርስበርሳቸው እንዳይገናኙ ተከልክለው የቆዩት ራስ እምሩና የደጃዝማች ታየ ጉልላቴ ተገናኙ። በጣልያኖች ዘንድ ሁለቱም የቅኝ ግዛት ዜጐች ነበሩ። ልዩነታቸው አንዱ በጦር ሜዳ የተማረከ፣ ሌላው ወድዶ የገባ መሆናቸው ብቻ ነበር። ራስ እምሩንና ደጃዝማች ታዬ ጉልላቴን የያዙት አይሮፕላኖች አከብክበው በመነሳት ወደ አዲስ አበባ በረሩ። የኢትዮጵያ ጦርም ወደ ኋላ ተመልሶ ሪጅም የምርኮኝነት ጉዞውን ወደ ጂማ፣ ከዚያም ወደ አዲስ አበባ ቀጠለ።[4]

በራስ እምሩ የሚመራው ጦር ቢማረክም፣ ጦርነቱ ግን አልቆመም። በፊታውራሪ ደበበ የሚመራ ሌላ የአርበኛ ቡድን ሦስት መዓልትና ሦስት ሌሊት ከተዋጋ በኋላ ሽዋ ጊሚራን በከፊል በቁጥጥሩ ሥር አደረገ። በየካቲት 1931 ዓ.ም የተላለፈ አንድ ሌላ ሪፖርት ደግሞ በጂማና በከፋ ብዙ መሣሪያ የታጠቁና በጣም የደረጁ አርበኞች እንደነበሩ ያስረዳል። ብዙ ነጭ ጣልያኖውያን ወታደሮችም እንደሚዋጉአቸው ይገልፃል። ምርከኞቹ ከቦታው ከመነሳታቸው በፊት እንኩዋን ሦስት ጣልያኖውያን ከጂማ ከተማ ወጥተው ከአርበኞቹ ጋር መቀላቀላቸውንና ያልታደሉ ሦስት ሌሎች ደግሞ ከአርበኞቹ ጋር ከመቀላቀላቸው በፊት መያዛቸውን ያረጋግጣል።[5]

በዛ አካባቢ ሰኒዜው ድል የቀናው የጣልያን ጦር ወደ ከፋ ሲሻገር የጉራጌ አገርና የጂባት አርበኛ ኖኖ በተር በተባለው ቦታ ቀደም ብሎ በተደረገው ስምምነት መሠረት ተባብሮ እየተከተለ ወጋው። በሽዋና በከፋ ድንበር ላይ የምትገኘውን የአበልቲን ምሽግ አስለቀቀው። ከሞት የተረፉትን 17 ጣልያኖውያን ከአርባ መትረየስና ከብዙ ጠመንጃ ጋር ማረካቸው። በአረንገግ ምሽግ የነበረውን የጠላት ጦር በመዓልትና በሌሊት ለሁለት ቀን ወግቶ ወደ ጢሮ አባረረው። ተከታትሎ ጢሮ በመድረስ ኩበቦ ለሁለት ቀን እንደተዋጋ ንጉሠ ነገሥቱ አዲስ አበባ መግባታቸው ተሰማ። ወዲያውም ንጉሠ ነገሥቱ ኖኖ ግሼ ድረስ ሄደው ስለጉብኙት አርበኛው ኃይል ተሰምቶት የሚሸሸውን የጣልያን ጦር ጠልጋ ኖኖ፣ ለሙ ሲቃና ለሙ ካሣ በተባሉ ቦታዎች ላይ ታላላቅ ውጊያዎች በማድረግ ደምስሶ ጂማ ደረሰ።

ጂማ፣ የኦሮሞ-ሲዳማ ክፍለ ሀገር ዋና ከተማ ስለነበረች፣ ከፍተኛ የጠላት ክምችት አዛ ነበር። በዚህ ላይ ከጉጃም በጉሐ ጽዮን፣ በገዳ በኩል ሠብሮ የገባው ጦር ብዙ ስለነበር፣ ከተማይቱ የምትያዝበትን መንገድ በልዩ ዘዴ መቀየስ አስፈለገ። መጀመሪያ ከተማይቱ ከተከበበች በኋላ ምክር ተደርጉ ከፊታውራሪ ገረሱ ዱኪና ከልጅ ጃገማ ኬሎ የተውጣጣ ቡድን ቀደም ብለው ከተማረኩት ጣልያናውያን መካከል የተወሰኑ ሰዎችን ይዞ ንግግር እንዲያደርግ ተወሰነ። ቡድኑም በስምምነቱ መሠረት ተመርጦ ጂማ ከተማ ገባ። የጂማ ሕዝብ ጣልያኖች በጦርነቱ አመካኝተው ሕዝብ ለማስጨረስ እንደ አሰቡ አውቆ ነበርና ሴት፣ ወንድ፣ ሕፃን፣ ሽማግሌ ሳይል ወጥቶ ከቡድኑ ጋር ተደባልቆ ጣልያኖች ያለአንዳች ደም መፋሰስ እጃቸውን እንዲሰጡ ጠየቀ። ጣልያኖችም እንደ ተከበቡና ሕዝብም እንደ ተነሳባቸው ስለተረዱ እና በተካሄደው የጦር ትርእይትም ስለተደናገጡ፣ እጅ ለመስጠት ተስማሙ። እንግሊዞችም ተከታትሰው ስለደረሱ በምክሩ እነሱም ገብተውበት ጣልያኖችን በሙሉ ለኮለኔል ፎክስ፣ መሣሪያውን ፊታውራሪ ገረሱ ዱኪ እንዲረከቡት ስምምነት ተደረገ። በስምምነቱ መሠረት ሰኔ 12 ቀን 1933 ዓ.ም 8000 ጣልያኖች እጅ ሰጡ። ሃምሣ መኪና መድኃኒት እንደዚሁም በርካታ የወርቅ ቡችላና የብር ነዶ ከብዙ መሣሪያ ጋር ተማረከ። ነገር ግን እንግሊዞች ቃላቸውን ባለማክበር ከምርኮው የሚበዛውን ወስዱት። አጋሮ፣ ጌራና ጉማ የነበሩ ጣልያኖውያንም ተማረኩ።[6]

ንጉሠ ነገሥቱ አዲስ አበባ ከገቡ በኋላ፣ ወደ ምዕራብ ኢትዮጵያ የሸሸውን የጠላት ጦር የሚከታተል ሠራዊት ተላከ። ለዚህም ሻለቃ /ራስ/ መሥፍን ስለሸ ፊታውራሪ ተብለው አዛዥ ሆኑ። ከጉጃም ከሸሸው የጠላት ጦር አብዛኛው ከግንደ በረትና ከጉራጌ አገር አርበኞች ጋር እየተናነቀ እኩሉ በወለጋ፣ እኩሉ በጂማ በኩል ወደ ኢሉባቡር ተጓዘ። በዚህም ላይ ከከፋ ጊሚራ፣ ከጋሞ ጉፋ፣ ከማጂ ወደ ጎሬ ዘመተ።

የኢሊባቡር አርበኞች በእነ ባላምባራስ ገዳሙ ግዛው እና ወንድሞቻቸው፣ በእነ አቶ ወዳጀ ዲሣሣ፣ በእነ አቶ ሞረዳ ጥልም መሪነትና አስተባባሪነት ያቀርበን ወንዝ እንዳይሻገር፣ ተሻግሮም ሳምቤንና የጉራይሌን ኮረብታ እንዳይዝ በብርቱ ተናነቁት። በንጉሠ ነገሥቱ ትዕዛዝ በፊታውራሪ /ራስ/ መስፍን ስለሸ የሚመራው ነፃ አውጭ ጦርም ደርሶ ጎሬን ተቆጣጠረ። ከዚያም ወደ ሣምቤና ጉራሌሌ ሄዶ ለአርበኞቹ ድጋፍ ሰጠ። የጠላትም ጦር የጉራይሌን ኮረብታ ይዞ በብረት ተከላከለ። ከዘጠኝ የመዓልትና የሌሊት ጦርነት በኋላ መሣሪያውን ከምሮ እጁን ሰጠ።[7]

ከሰኔ 12 እስከ 14 ቀን 1933 ዓ.ም ቢሉ፣ ወለጋ ከተካሄደው ጦርነት ያመለጠው የጠላት ጦር ወደ ኢሉባቡር ተሻገረ። ጦሩ በደሌ ላይ ለሻለቃ /ኮሎኔል/ ወርቁ አየለ እጅ መስጠት ሲጀምር፣ በፊታውራሪ /ራስ/ መሥፍን ስለሸ የሚመራውም ጦር ደርሶ ከምርኮው ተሳተፈ።

በጀነራል ጋዜራ የሚመራው የጠላት ጦር ደግሞ ወደ ጮራ ተጓዘ። አሱንም የአጋፋሪ /ፊታውራሪ/ ከበደ ይርዳው ጦር ደርሶ ሰኔ 17 ቀን ኮሪ ላይ ታላቅ ጦርነት ተደረገ። ድል ለኢትዮጵያ ሆነና 333 ከፍተኛ የጣልያን መኮንኖች ከዘጠና ከባድ መኪናና ከሰባት አውቶሞቢል፣ ከሃያ ሁለት የመኪና መጐተቻ ጋሪ ጋር ተማረከ። ነገር ግን ጀነራል ጋዜራ አሁንም እጁን አልሰጥም ብሎ ወደ ጎሬ ተሸጋገረ፣ የገባን ወንዝ ድልድይ ሰበረ። ከዚያ ደግሞ ወደ ወለጋ ተሻግሮ የሶረን ወንዝን ድልድይ ሰበረ።

በዚህ ጊዜ ከጂማ፣ ከማጂ፣ ከሰፋ የሸሸው የጠላት ጦር ቀደም ብሎ ጎሬ ገብቶ ነበር። በፊታውራሪ ወርቅ ዓለማየሁ ፋሪስ የሚመራው ነፃ አውጭ ጦር በደረኒና፣ በሰቦ አድርጐ ጎሬ ከተማ ደረሰና ሰኔ 26 ቀን 1933 ዓ.ም የነፃነት መዓዛ የሸተተው አርበኛና ተስፋ የቆረጠው የጠላት ጦር ግንባር ለግንባር ገጠሙ። ድል የኢትዮጵያ ሆነ። ከኢትዮጵያ ወገን ከአምስት መቶ በላይ ሰው ሲሞት፣ ከጠላት ወገን ግን የመተውና የቆሰለው በድምሩ ሰባት ሺህ ሁለት መቶ ሠላሳ አራት ነበር። እንደዚሁም አሥራ ዘጠኝ ሺህ ሰባት መቶ ሃምሳ መኮንንና ወታደር በሕይወት ተማረከ። በኢሉባቡር የተካሄደው ፍልሚያ በዚህ ዓይነት ተፈፀመ። በጦርነቱ ላይ አርባ ሦስት የውሃ መትረየስ፣ አንድ መቶ ሃምሳ ድግን መትረየስ፣ እጅግ ብዙ ጠመንጃና ጥይት ተማረከ።[8]

ማጣቀሻ ፅሑፎች

1. ከበደ ተሰማ፣ *የታሪክ ማስታወሻ* ፣ገጽ 164።
2. ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፣ *ሕይወቴና የኢትዮጵያ አርምጃ 1ኛ መጽሐፍ*፣ ገጽ 25-7።
3. "የኢሉባቡር ታሪክ"፣ የኢሠፓ ኮሚቴ ጥናት፣ ገጽ 30-1።
4. ታደሰ ሜጫ፣ *ጥቁር አንበሳ*፣ ገጽ 65-116።
5. ሕይወት አደሩ፣ *ያቺ ቀን ተረሳች*፣ ገጽ 65።
6. ታቦር ቀሚ፣ *አባ ቦራ፣ የደጃዝማች ገረሱ ዱኪና የሲሎች አርበኞች ታሪክ*፣ ገጽ 77-95።
7. "የኢሊባቡር ታሪክ"፣ ገጽ 30-1።
8. ታደሰ ዘወልዴ፣ ገጽ 364-4።

ምዕራፍ ሃያ አራት
በወለጋ የተካሄደ የአርበኝነት ሥራ

ጣልያን በኢትዮጵያ ላይ ወረራ ከመጀመሯ አስቀድሞ፣ ክርስትናን ትምህርት የሚያስተምሩ፣ ወንጌል የሚሰብኩ አስመስላ ሰላዮች ዘለሰማራችባቸው ክፍላተ ሀገራት አንዱ ወለጋ ነበር። ከዚህም የተነሣ በዚህ ክፍለ ሀገር የአርበኝነት ሥራ ማካሄድ ቀላል አልሆነም። ያም ሆኖ መልካም የአርበኝነት እንቅስቃሴዎች ለማድረግ ተሞክሯል።

የሆለታ ጦር ትምህርት ቤት ምሩቃን ቡድን ከሆለታ በመንቀሳቀስ በአምቦ፣ በጌዶ፣ በቦኒያ አድርጐ ነቀምት ገባ። ደጃዝማች ሀብተማርያም ኩምሣ በክብር ተቀበሉት። በአቅዋሙ ስለተደሰቱ ደመወዝ ለእያንዳንዱ ሰው ተመደበለት። አደላደሉም ለወታደር በወር 3 ብር፣ለሃምሣ አለቃ በወር 5 ብር፣ለመቶ አለቃ በወር 8 ብር፣ ለሻምበል በወር 12 ብር፣ ለሻለቃ በወር 15 ብር ነበር።

ጦሩ ስሙን "ጥቁር አንበሳ" ብሎ ሰየመ። አሥር አንቀጽ ያለው የመተዳደሪያ ደንብ አወጣ። የጦር አለቆችም መረጠ። እንቅስቃሴውን በአካባቢው ሁሉ አስፋፋ።ከሀገሩም ሰዎች አንዳንዶች ተጣብረው ከጐኑ ቆሙ።

ጠላት የተደራጀ ጦር መኖሩን ሲረዳ አካባቢውን በአይሮፕላን ያስመረምር ጀመር። ጦሩ ግን ስለተደበቀ፣ አንዳች ምልክት አልታየም። ስለዚህ በሁኔታው ጠላት ተደናገረ። በአየር ላይ በመነፅር ሊረዳው ያልቻለውን የአካባቢውን ውስጣዊ ሁኔታ የሚያጠና ቡድን በ3 አይሮፕላኖች ላከ። አይሮፕላኖቹም ሰኔ 18 ቀን 1928 ዓ.ም በነቀምት አየር ላይ ከአንጣበቡ በኋላ ከነቀምት በስተምሥራቅ ቦኒያ ከተባለው ቦታ የኢትዮጵያ ፆንግሥት አሠርቶት ከነበረው አይሮፕላን ሜዳ ላይ አረፉ። የማረፋቸውም ወሬ ከቀትር በኋላ በ10 ሰዓት በወታደሩ ዘንድ ተሰማ።

አይሮፕላኖቹ ከማረፋቸው አስቀድሞ በደጃዝማች ሃብተ ማርያም አጥር ግቢ ወረቀት ጥለው ኖሮአል። የጣሉትም ወረቀት በቦኒያ አርፈው እንደሚያድሩ ገልፆ በማሥፈሩ ጥዋት ጣልያኖቹ ወደ ነቀምት መሄጃ በትሎችን እንዲልኩላቸው የሚጠይቅ ኖሮአል። በስልክም ተነግሮአቸው ነበር። ጥቁር አንበሳ ይህንን ሁኔታ እንደተገነዘበ አስቸኳይ ስበሰባ አድርጐ አይሮፕላኖቹ ላይ አደጋ ለመጣል ወሰነ። ይህንንም ለደጃዝማች ሀብተማርያም ገለፀላቸው። ነገር ግን እሳቸው ከጣልያኖቹ በደረሳቸው ጥያቄ ከሕዝብ ጋር ተመካክረውበት የጣልያኖቹን ጥያቄ ለመቀበል ተወስኖ ስለነበር፣ የጥቁር አንበሳን ሐሳብ ለመቀበል አዳገታቸው። ጥቁር አንበሳ ግን በውሣኔው ፀና።

ሌሊቱን ወደ ቦኒያ ሄዶ አይሮፕላን ማረፊያውን በሽምቅ ከበበ። ሊነጋ ፈጥኖ በአይሮፕላኖቹ ውስጥ በመግባት በዚያ ያገኛቸውን ጣልያኖች ፈጅቶ በውስጡ የነበረውን መሣሪያ ካወጣ ሽኋላ አይሮፕላኖቹን አቃጠላቸው። የጦር

ማዕረጉ መቶ አለቃ የሆነ አንድ ጣልያናዊ ቄስ ከሁለት ኢትዮጵያውያን ባንዶች ጋር ትናንትናውኑ ከአይሮፕላኑ ወጥተው ለስለላ ወደ መንደር ሄደው ስለነበር ከሞት ሲድኑ፣ ሌሎቹ 12 ጣልያኖች ግን ተገድለው ተቃጠሉ።

በዚህ ጊዜ የጥቁር አንበሳን ሰጥቃት መዘጋጀት ያዩት ደጃዝማች ሀብተማርያም ወደ ግንቢ ሄዱ። እዳሪ ለመውጣት ሄዶ የነበረ አንድ ሌላ ጣልያናዊ በጥይት ተመትቶ በጥቁር አንበሳ ሲያዝ፣ ቄስ መቶ አለቃ በሩሱ ግን በፊታውራሪ ሞኣ ደባቂነት ድኖ ወሬውን ለጣልያኖች ነገረ። ሌላ አንድ አይሮፕላን ነጂ የነበረውን መኩንን ገበሬዎች አግኝተው በጦር ስለወጉት ከጥቂት ቀን በኋላ ሞተ። በጥይት ቆስሎ የተያዘው ወታደር ግን ተሰቃይቶ በሰምንተኛው ቀን በገዛ እጁ ራሱን ገደለ።

በግምቱ እሑድ ጣልያኖች ነቀምት አካባቢ በነበረው የጥቁር አንበሳ ሠፈር ላይ በሦስት አይሮፕላን ቦምብ በመጣል፣ በሌሎች ሁለት አይሮፕላኖች የመትረየስ ተኩስ ድብደባ አካሄዱ። በጦሩ ላይ ግን አንዳች ጉዳት አላደረሱም።

ከዛ ደጃዝማች ሀብተማርያም ከግንቢ ተመልሰው ነቀምት ገቡ። ነገር ግን በአላቸውና በጥቁር አንበሳ ሠራዊት መካከል ስምምነት ሊገኝ አልቻለም። እሳቸው ከሕዝቡ የቀረበላቸውን ሐሳብ መቀበል ግድ ሆነባቸው። ጥቁር አንበሳ ከነበረው አቅዋሙ ንቅንቅ አልልም አለ። ስለዚህ ደጃዝማቹ ጥቁር አንበሳ አካባቢያቸውን እንዲለቅላቸው ጠየቁ። ሠራዊቱም በጉዳዩ ደጋግሞ ከመከረበት በኋላ ያለሕዝቡ ፈቃድ መቆየት ውጤት እንደማያስገኝ በመገንዘብ፣ በሰልፍ ሆኖ በደጃዝማች ፊት በማለፍ ከተማውን ጥሎላቸው ወጣ። ሲወጣም

"እናት ኢትዮጵያ ውዲቱ፣ ውዲቱ፤
ላንቺ የማይረዳ ሳለ በሕይወቱ፣
በረከትሽን ይንሳው እስከ እለተ ሞቱ።"

እያለ፣ ድምፁን ከፍ አድርጐ በመዘመር ነበር።[1]

ደጃዝማች ሀብተማርያም እንደዚህ ባለ ሁኔታ ነቀምትን ለጣልያን አስረከቡ። እነሱም ይዘው በመግደል ዋጋቸውን ከፈሉላቸው። በዛ የነበሩት ሌላኛው ኢትዮጵያዊ፣ ብላታ ደራሳ ግን በሱዳን በኩል ወጡ። ትግሉም ቀጠለ።[2]

በ1929 ዓ.ም በእነዚህ ሁኔታዎች ምክንያት በወለጋ የመቀዝቀዝ መልክ አሳይቶ የነበረው የአርበኝነት ተጋድሎ በ1930 ዓ.ም እንደገና ተቀሰቀሰ። ጥቅምት 13 ቀን 1930 ዓ.ም ጉድሩ ከዋ ላይ ግጭት ተደረገ። ከዚያም ከሜጫ የተሻገረው አርበኛ ወደ ሀሮ ጭብር ከተማ በገባ ጊዜ ሕዝቡ በእልልታ ተቀበለው። የፊታውራሪ አፈሣ ልጅ አቶ ደርጉ አፈሣ፣ እንደዚሁም ደጃዝማች ደስታ እስቴና ቀኛዝማች ገሠሠ ከአርበኞቹ ጋር በመቀላቀል ድጋፍ አስገኙ።

በዚህ ጊዜ ነቀምት የሠፈረው የጠላት ጦር በሕዝቡ ላይ ተፅዕኖ አሳደረ። ከዚህ የተነሣ ከሆርና ከአሞሩ ሕዝብ ከፊሉ አርበኞችን ሲደግፍ፣ ከፊሉ ደግሞ ለጠላት አመነ። ሲባኖስ ወንዝ ላይ አሞሩና ጊዳ ከሚባለው ቦታ ውጊያ ተካሄደ። አሥራ ሰባት ያህል ባንዶች ሞቱ። በሻለቃ /ራስ/ መሥፍን ስለሺ የሚመራው አርበኛ ከሆሮ ወደ ሲሙ አያና ሄደ። በግራዝማች ዘውዴ አስፋው የሚመራው አርበኛ ደግሞ ህዳር 21 ቀን 1930 ዓ.ም አያና ገበያ አካባቢ ከደረሰበት የአየር ጥቃት አምልጦ ወደ ኢባንቱ ሄደ። በወቅቱ የኢባንቱ ሕዝብ በጠላት ተሰብኮ ነበር። ስለዚህ በዚያ የነበረውን አማራ ወደ ሆሮ በመውሰድ ለመፍጀት ያስቡ ስለነበሩ ከእልቂት አዳናቸው።

አርበኛው ከጊዳ አሞሩ ሲንቀሳቀስ ጠላት በበኩሉ ሊባኖስ ላይ ጠብቆ ታህሣሥ 2 ቀን 1930 ዓ.ም እሑድ ዕለት ጦርነት ገጠመው። በደጃዝማች ዘውዴ አስፋው የሚመራው አርበኛ መንገዱን በጦርነት እየጠረገ ተጓዘ። ሰባት ያህል የጠላት ወታደር ገደለ።

በሻለቃ /ራስ/ መሥፍን የሚመራው ጦር ከሊሙ፣ ደጃዝማች ዘውዴ ደግሞ ከኢባንቱ መጥተው ጀርቲ ከተባለው ቦታ ላይ ተገናኙ። ጠላት ይህንን ሲሰማ ስለዘመቱባቸው ታህሣሥ 16 ቀን 1930 ዓ.ም ጦርነት ተደረገ። ጥር 13 ቀን 1930 ዓ.ም መንፍሬት ላይ መጠነኛ ውጊያ ተካሄደ። የአካባቢው ባንዳ በበኩሉ የካቲት 7 ቀን ደንጉሮ ከተባለው ቦታ ላይ አደጋ ጥሎ ነበር። አርበኞቹ እየተከላከሉ አምልጠው ወጡ።

የካቲት 11 እና 12 ቀን ጂማ ገነቲ ላይ ጦርነት ተካሄደ። ከጠላት ወገን አርባ ያህል ሰው ሳይሞት አልቀረም። የጠላት ከበባ እየጠነከረ ስለሄደ ዘወለጋ ይንቀሳቀስ ከነበረው አርበኛ በሻለቃ /ራስ/ መሥፍን የሚመራው ቡድን ወደ ጉጃም ለመሻገር አሰቡ። በሆሮ በኩል ወደ ኣጉል ሄዶ ከደጃዝማች ነጋሽ በዛብህ ጋር ተላላክ።[3]

በዚህ ዓይነት አርበኛው ጉዞውን ቀጥሎ ከወለጋ ወደ ጉጃም ሊሻገር ሲንዝ አጋምሣ ላይ ጠላት የካቲት 13 ቀን 1930 ዓ.ም አደጋ ጣለበት። አደጋ የጣለው ይኸ የጠላት ጦር በውስጡ የዓረብነት ትውልድ ያላቸው እንዲሁም የሲቢያ (ጡሩምቡሌ) ወታደሮች እና የከሰላ (በተለምዶ አጠራር፡- ሻንቅላ) ወታደሮች ነበሩበት። ብዛቱም ከአርበኞቹ እስከ ሃያ አጠፌታ ይገመታል።

አርበኞቹ በብርታት ተዋጉ። ጠላት ለማደፋፈር ብሎ ወታደሩን አረቄ አጠጥቶት ስለነበር የጨበጣው ውጊያ ለኢትዮጵያውያን ሠመረ። እርስበርሱ እስከ መተላለቅ አደነጋገሩት። ጦርነቱ ከጥዋቱ 2 ሰዓት የተጀመረ እስከ 9 ሰዓት ድረስ ቆየ። አርበኛው አልበገር ስለአለ ጠላት ጥሎ ሄደ። አርበኛውም ሠነዶን ተሻግሮ የካቲት 15 ቀን 1930 ዓ.ም ጉጃም፣ ቡሬ አፋፍ ወጣ።[4]

በዚህ ዓይነት ከወለጋ ወደ ጉጃም የተሻገረው ጦር ጥቂት ቆይታ ከአደረገ በኋላ ምክር ተያዘ። በምክሩም አርበኛው ,ከሁለት ተከፈለ። በሻለቃ /ራስ/ መሥፍን ስለሺ የሚመራው ታልቁ ቡድን ከንጉሠ ነገሥቱ መመሪያ

ለመቀበል በሚል ሽፋን ወደ ሱዳን መሰደድን መረጠ። በግራዝማች ዘውዴ አስፋው የሚመራው ትንሹ ቡድን ግን ወደ ባዕድ አገር አንሄድም አለ። ሚያዝያ 27 ቀን 1930 ዓ.ም ጐጃም ክፍለ አገር ቁሜ ከተባለ ቦታ ሁለቱ ቡድኖች ተሰነባብተው በሰላም ተለያዩ።

ከዚያ ወዲያ ከጐጃም ወደ ወለጋ ተመልሶ የሚሻገረውን አርበኛ ጠላት አላስገባም ብሎ ያዘ። ከጐጃምም የጠላት ጦር ገሥግሦ ደረሰ። ከዛው ከአባይ ሸለቆ ሚያዝያ 30 ቀን ታላቅ ውጊያ ተደረገ። ከወለጋ ወገን ያለውን የጐጃሙ፣ ከጐጃም ወገን ያለውን አርበኛ የወለጋው እያሸጋገረ በመድፍና በመትረየስ ደበደበው። አርበኞች በበኩላቸው በብርታት እየተዋጉ ከዓባይ ወንዝ ገብተው ውሃ ጠጡ። ከብቱም ሰውም ትንፋሽ አገኘ። ምንም ወሩ ሚያዝያ ቢሆንም የበልግ ዝናም ነበርና የዓባይ ውሃ ቀላል አልነበረም። እስከ ወገብ ይደርስ ነበር። አርበኛው የወለጋውን ወገን ካላጠቃ በስተቀር ሌላ ማምለጫ እንደሌለው ስላወቀ በርትቶ ተዋጋ። "ቆራጥና ጭስ መውጫ አያጣም" እንደሚባለው በሩን ሰብሮ፣ ጠላትን አባርሮ ወጣ።

እዚህ ላይ አንዳንዶች በአሰቃቂ ሁኔታ ከበረሃው ላይ በውሃ ጥም እየደከሙ ቀርተዋል። ሌሎች ከወንዙ ከገቡ በኋላ ደግሞ ጥቂቶቹን ውሃ ወስዷቸዋል። ሴት፣ ልጅ እና አዛውንትም ተማርከዋል። ይሁን እንጂ አርበኛው ከጥፋት ሊድን ችሏል።

አርበኛው የአግር ጉዞውን በዚህ ዓይነት ቀጥሎ አጉል በረሃ ገባ። ይህ ቡድን ወደ ጐጃም በተሻገረ ጊዜ ይከተለው የነበረውን የጠላት ጦር ለማገድ አካባቢውን በእሳት አቃጥሎት ስለነበር፣ አሁን ተመልሶ በሚመጣበት ጊዜ ከአመድ ላይ ደረሰ። ከቃጠሎው የተረፈው ጉቶና ስንጥር፣ የበረሃው ረሞጫ እጅግ አሰቃየው። ሥፍራው በረሃ ከመሆኑ ጋር ገደላማ ስለሆነ በከብት ለመጓዝ አያመችም። የውሃ መትረየሱን የተጫነችውን በቅሎ ማጓጓዝ እጅግ ከባድ ሆነበት። ጦሩ እንደምንም ታግሎ ጨዲቲ ከተባለው ወንዝ ደርሶ ውሃ ጠጣ። ከብትም፣ ሰውም እንደገና ትንፋሽ አገኘ። አቶ አጉናፍር ብቻ በፅኑ ታመው እዚህ በረሃ ላይ በአሰቃቂ ሁኔታ ቀሩ።

አርበኛው ጉዞውን ቀጠለ። የሚበላ እህል ስለጠፋ ሰው ያብጥና ይነፋ ጀመር። ምግብ ለማምጣት የተላኩት ሰዎች ከአንድ ሣምንት በኋላ ጥቂት እህል ይዘው ተመለሱ። ሰው አሱን በመብላት ከአልቂት ድኖ በራዳ ወደተባለው ቦታ ጉዞውን ቀጠለ።

ቡድኑ በራዳ ሲደርስ አቶ ነገሬ ገመቹ የተባሉ አርበኛ መልካም አቀባበል አደረጉለት። የሚበላም የሚጠጣም ሰጡት። አንዱ ችግሩ የእንቅልፍ ማጣት ስለነበር አቶ ነገሬ ሰዎቻቸውን ቃፊር አቁመው የመተኛት ዕድል ሰጡት። ነገር ግን ጠላት ከጉድሩ አዲስ ጦር አንቀሳቅሶ ደረሰባቸው። አርበኞች እየተከላከሉ ከጉዳት አምልጠው ግንቦት 11 ቀን 1930 ዓ.ም ወደ ግንደ በረት ተሻገሩ።[5]

ከዚህ በኋላ በወለጋ ሊካሄድ የነበረው የአርበኝነት ተጋድሎ እንደገና ቀዘቀዘ። ንጉሥ ነገሥቱ ተመልሰው በመጡ ጊዜ፣ የጠላት ጦር ለራሱ መከላከያ ሊያደርገው ያሰበው የወለጋን ግዛት ነበር። በዚህም የተነሣ በርካታ የጠላት ጦር ወደዚያ ተልኮ ነበር።

ንጉሠ ነገሥቱ በበኩላቸው ሰኔ 5 ቀን 1933 ዓ.ም ለነቀምት ሕዝብ አዋጅ አስነገሩ። አዋጁም ጠላት በሕዝብ ላይ ያካሄደውን ጭፍጨፋ ከገለፀና በጉግና በሃይማኖት እየለያየ ያደረሰውን ጥፋት ከአስገነዘበ በኋላ፣ ስለወደፊቱ አስተዳደር ፍንጭ የሚሰጥ ነበር። "...ጥረታችን የዘር ልዩነት ሳይደረግ፣ ሁሉም እንደ ችሎታው ከሕይወቱ በሚሠራው ሥራ ዋጋው እንዳይጠፋ፣ ራሱ እንዲጠቀም ነው..." ይል ነበር። ፊታውራሪ /ደጃዝማች/ ከበደ ተሰማ አስተዳዳሪ ሆነው መሾማቸውንም ይገልፃል።

በጦር በኩል ደግሞ ሻለቃ /ራስ/ መስፍን ስለሽ ፊታውራሪ ተብለው ተልከው ነበርና፣ ቢሉ በተባለው ቦታ ከሰኔ 12 እስከ 14 ቀን 1933 ዓ.ም ሥርነት ተካሄደ። ጠላት ድል ሆኖ ወደበደሌ ሄደ። በጀነራል ጋዜራ የሚመራው የጠላት ጦር የዴዴሳን ወንዝ ድልድይ ሰብሮ ወደ ግንቢ ተሻገረ። ከዚያም ወደ ደምቢደሎ ቀጥሎ ከዛየር ለመጡ የቤልጅግ ወታደሮች እጁን ሰጠ።[6]

ማጣቀሻ ፅሑፎች

1. ታደሰ ሜጫ፣ *ጥቁር አንበሳ*፣ ገጽ 46-60።
2. Greenfield, Ethiopia, p.245.
3. ታደሰ ዘወልዴ፣ *ቀሪን ገረመው*፣ ገጽ 340-344
4. መሉሰው ምትኩ፣ *ከሸዋ እስከ ሱዳን ጠረፍ*፣ ገጽ 36-60።
6. ታደሰ ዘወልዴ፣ ገጽ 345-351።
8. ከበደ ተሰማ፣ *የታሪክ ማስታወሻ*፣ ገጽ 429-432።

ምዕራፍ ሃያ አምስት
ግንደ በረትና ሜጫ የተካሄደው ትግል

ንጉሠ ነገሥቱ ወደ ውጭ አገር መሄዳቸው ሲረጋገጥ፣ አዲስ አበባ ውስጥ የነበረው የኢትዮጵያ ጦር እጁን ማውጣት ነበረበት። የጠላት አመጣጥ በደብረ ብርሃንና በናዝሬት በኩል መሆኑ ታውቆአል። የሲዳሞው ጦር ለብዙ ጊዜ እንደሚመክት ስለአልታወቀ የጂማ በር አላስተማመነም። ስለዚህ ከአዲስ አበባ ለመውጫ የተመረጠው በር የወለጋ በር ሆነ። ጥቂቶች የዛው ተወላጆች ደግሞ ወደ ቡልጋ ገቡ።

በወለጋ በር ከውጣው ጦር በመቶ አለቃ ወልደ ዮሐንስ የሚመራው አንዱ ቡድን ሚያዝያ 26 ቀን 1928 ዓ.ም ገፈርሣ ላይ ከባንዳ ጋር ግጭት አጋጠመው። ቢሆንም ጉዳት ሳይደርስበት ጥሎት አለፈ። የኢትዮጵያ የጦር መሪዎች ከአዲስ አበባ ወጥተው በወጨጫ፣ በመናገሻ ጫካዎች አድፍጠው መጠባበቅ ያዙ።

የጠላት ጦር ወደ ወለጋ ለመሄድ ሲጓዝ በግንቦት ወር መጀመሪያ ወልመራ ላይ በሻለቃ /ራስ/ መስፍን የሚመራው የኢትዮጵያ ጦር ግንባር ለግንባር ገጠመው። ምንም ጠንከር ቢዋጋ የኢትዮጵያ ሠራዊት የጠላትን ጦር ሊመልሰውና ጉዞውን ሊያስቆመው አልቻለም። አንድ ጀነራልና ብዙ ወታደሮች ግን ገደሉበት። የጀነራሉ ሐውልት እስከ 1966 ዓ.ም ድረስ ገፈርሣ በመንገድ በስተሰሜን ቆሞ ይታይ ነበር። ከማይጨው በኋላ ደፍሮ ግንባር ለግንባር የገጠማቸው ሰው አልነበረምና ጣልያኖች ይህንን ቦታ ሁለተኛ ማይጨው አሉት።

ጠላት የአካባቢውን ሕዝብ በስብከትና በትዕዛዝ ተፅዕኖ አድርጉበት ስለነበር በያለበት የባንዳ ኃይል ተንቀሳቀሰ። ሰኔ 12 ቀን አዳበርጋ፣ ሰኔ 18 ቀን ደግሞ ሜታ ዋዩ ግጭት ተደረገ። ነገር ግን በአርበኛው እምብዛም ጉዳት አልደረሰበትም።

በመቀጠል አርበኛው ሙሌ ከሣንድ ፎርድ ቤት የሠፈረውን የጣልያን ወታደር ለማጥቃት ዕቅድ አዘጋጀ። ነገር ግን እቅዳቸውን አስቀድሞ በመስማት ጠላት ወደ አዲስ አበባ ሸሸ። እነሱም ተከታትለው ሐምሌ 5 ቀን 1928 ዓ.ም ዕለተ እሑድ ወግዲ ከምትባል ቦታ ገጠሙት። ከጥዋት እስከ ምሽት የቆየ ውጊያ ተካሄደ። ብዙ ወታደር ፈጁበት፤ ምርኮም አገኙ። ከእነሱም ወገን አምስት ሰዎች ሲሞትባቸው፣ አንድ ሰው ቆሰለ።

ሐምሌ 17 ቀን 1928 ዓ.ም በሜታ ቢታ አካባቢ መስቀሌ በተባለው ቀበሌ ጠላት አርባ በሚሆኑ አርበኞች ላይ አደጋ ጣለ። ቢሆንም ስድስት መትረየስ ከበቂ ጥይት ጋር እንደዚሁም በቂ የነፍስ ወከፍ መሣሪያ ስለነበራቸው ከበባውን ሰብረው አመለጡ። ብዙ የጠላት ወታደሮች ሞቱ፣ ሌሎች ቆሰሉ። ከአርበኞች ወገን ሁለት ሞቱ፣ ሌሎች ጥቂቶች ቆሰሉ።

እዚህ ላይ የሚጠቀስ አስፈላጊ ጉዳይ አለ። ይኸ ጦርነት በአርበኞች ላይ ያደረሰው ጉዳት እንደተገለፀው ቁጥር የሚገባ አልነበረም። በዚህ ውጊያ ምክንያት ግን እነደጃዝማች ፍቅረማርያም በደብረ ብርሃን በር፣ እነደጃዝማች ባልቻ በጂማ በር፣ እነደጃዝማች አበራ በጉጃም በር፣ አዲስ አበባን ሲያጠቁ ከግንደ በረት በወለጋ በር መከራ ሳይደረግ ቀረ። እናም ተባብሮ አዲስ አበባ ለመግባት የነበረውን እቅድ አከሸፈ።

ወደ ግንደ በረትና ሜጫ ተጋድሎ ስንመለስ ጠላት መስከረም 12 ቀን 1929 ዓ.ም ወረ ጃርሶ ላይ አደጋ ጥሎ በአርበኞች ላይ መጠነኛ ጉዳት አደረሰባቸው። ከዚህ በኋላ በአርበኞች መካከል ምክር ተደረገ። ምክሩም በምን በምን ቦታና ዘዴ ጠላትን ማጥቃት እንደሚቻል ነበርና የሀሳብ ልዩነት ተፈጠረ። በሻለቃ /ራስ/ መስፍን የሚመራው እኩሉ ሠራዊት ወደ ምዕራብ እንሂድ ሲል፣ በባላምባራስ /ራስ/ አበበ የሚመራው ደግሞ ከማሀል ሀገር እንዋጋ አለ። ሁሉም እንደፍላጐቱ እንዲያደርግ ከስምምነት ላይ ተደርሶ እንደዚሁ ተደረገ።

ጣልያን በመጠናከር ላይ የነበረውን የአርበኞች እንቅስቃሴ በእንጭጩ ለመቅጨት ከአዲስ አበባና ከአምቦ፣ ከደብረ ብረሃን፣ ከጉጂም፣ ከወሰሙም ሞምር ጦር አንቀሳቀሰ። የጠላት ጦር የመጣው በግንደ በረት በኩል ስለነበር አርበኞች የሙገርን ወንዝ ተሻግረው የሰላሌ ክፍል ከሆነች ውልጮ ከምትባለዋ ቦታ አድፍጠው ጠበቁት። ጦርነቱ ታህሣሥ 11 ቀን 1929 ዓ.ም ከየዋቱ በ1 ሰዓት ተከፍቶ ታላቅ ውጊያ ተደረገ። ብዙ መሣሪያ በአርበኞች እጅ ገባ። ባላገሩ ሞምር ተከፋፈለው።

ወደ ምዕራብ የሄደው አርበኛ ወደ ወለጋ ስለተሻገረ፣ የቀረው እስከ 1929 ዓ.ም የበጋ ወራት አካባቢ ድረስ ጥቂት ፋታ አገኘ። ነገር ግን ክረምቱ ሲገባ ጦርነቱ እንደገና ተቀጣጠለ። ሐምሌ 18 ቀን 1929 ዓ.ም ቨልቢ ላይ ጦርነት ተደረገ። ውጊያውም በጠመንጃና በመትረየስ ብቻ ሳይሆን በጥንቱ የመዋጊያ መንገድ በሥለት፣ በሰይፍና በጉራዴ ሞምር ተካሄደ። ጦርነቱ ከቀኑ 7 ሰዓት ጀምሮ እስከ ሌሊቱ ድረስ ተካሄደ። በዚህ ጦርነት ላይ ከአርበኞቹ ወገን ብዙ ሰው ሞቷል። ነገር ግን ከጠላት ወገን የደረሰው ጉዳት ከዛ የሚበልጥ እንጂ የሚያንስ አልነበረም። በዚህ ጦርነት አንድ ትልቅ የጭነት ዛባሻሎል የተባለ የውሃ መትረየስ፣ ሌላ ዘጠኝ ድግን መትረየስ ተማረከ። አንድ ሺህ አልቤንና ከአቅፍ በላይ የሆነ የምንሽር ጠመንጃ እንደዚሁ ተማረከ። ሰው የተቻለውን ያህል አነሳ። ውጊያውም ከቀኑ 9 ሰዓት ተጀምሮ ሌሊቱን ሁሉ ቀጠለ። አርበኞቹ ድል አድርገው የጠላትን ጦር መሪ ሜጀንትላት በመቁረጥ ባላገር ጌጤ እንዲጫወትበት አደረጉ።

ነሐሴ 28 ቀን 1929 ዓ.ም ሌላ የጠላት ጦር በዚሁ በሸኖ ኢየሱስ በኩል መጣ። አርበኞች ምቹ ቦታ ይዘው ጠብቁው ጥፋት አደረሱበት። በተነሳው ሽብር አንድ የእንጨት ድልድይ ተሰብሮ ሰባ አምስት ጣልያኖች

ውሃ ውስጥ ገብተው አለቁ። ነሐሴ 29 ቀንም ጠላት ለማጥቃት መከራ አድርጐ ነበር። እሱው ራሱ ተመልሶ ተጠቃ እንጂ፣ በአርበኞች ላይ ጉዳት ሊያደርስ አልቻለም።

መስከረም 6 ቀን 1930 ዓ.ም ውዴማ ላይ ጦርነት ተካሄደ። ጦርነቱ ከጠዋቱ 4 ሰዓት ተጀምሮ እስከ 11 ሰዓት ተኩል ቆየ። የማታ ማታ ድሉ የአርበኞች ሆነ። ብዙ መሣሪያና ዕቃ ተማረከ። ጠላት ነጭና ጥቁር ወታደሮች አነባብሮ ቀብሮ ጥሎ ሸሸ። በማሳደዱ ባላገሩ እየቆፈረ ቢያወጣው ብዛቱ አስገራሚ ሆነ። መስከረም 27 ቀን ደግሞ ጂማ ገነት ላይ ጦር አሠፈረ። ጦሩም 12 ሺህ የተገመተ ሲሆን የመጣውም ከአዲስ አበባና ከነቀምት ነበር። አርበኞቹም ምሽጉን ተጠግተው ከቀትር በኋላ ገጠሙት። ሁለት መዓልትና ሁለት ሌሊት ወጉት። በመጨረሻ ጠላት ሲያይልባቸው ወደቆላው አፈገፈጉ።

ነገር ግን በዚህ ጦርነት ከተገኘው ምርኮ ይልቅ ያመለጠው ሳይበልጥ አልቀረም። ሁኔታውም እንዲህ ነው። ጀነራል ማርቲኒና ራስ ኃይሉ በጦርነቱ ተሸንፈው እጃቸውን ለመስጠት ይቃረባሉ። በንግግሩ ወቅት ደጃዝማች አውራሪስ እንዲቀርቡላቸው ይጠይቃሉ። ሰው በመምረጣቸው የተበሳጩ አርበኞች የዘለፋ ቃል ይናገራሉ። ጀነራል ማርቲኒና ራስ ኃይሉ ደንግጠው መዋጋትን ይመርጣሉ። አጋጣሚ ዝናምም መጣ፤ መብረቅም ወርዶ አምስት የጣልያን መኮንኖችን ገደለ። ቀኑም መሸ። ቢዋጉም አርበኞች ቀደም ብሰው ያጡትን የምርኮ ዕድል መልሰው ማግኘት የማይቻላቸው ሆነ። ራስ ኃይሉና ጀነራል ማርቲኒ አመለጡ። በኋላ ላይም አርበኞች ተስፋ ባለመቁረጥ ተከታትለው ለመማረክ ሞከሩ። ማሚቴ ወልደሰንበት የተባለችው የራስ ኃይሉ ገረድ ተማርካ ነበርና ተጠየቀች። መስኩብ ጠመንጃ እንጂ ደረቅ ብረት እንደሌላቸው ገለፀች።

ሐምሌ 1 ቀን 1929 ዓ.ም ጦርነት ተጀመረ። ጀነራል ባሊኒ ኩሚ የሚባለው የጣልያን ጦር አዛዥ ሸኖ ኢየሱስ ላይ አጥብቆ ተዋጋ። አርበኛውም ታላቅ ምርኮ ሸተቶት ነበርና በኃይል ተዋጋ። ጦርነቱ እስከ ሐምሌ 4 ቀን ድረስ ቀጥሎ በአቅራቢያው የነበረውንም ያዘ። ከአርበኞቹም ከጠላትም ብዙ ሰው ሞተ። ጠላት ቡቴሌግራም ጠይቆ አዲስ ጦር አስመጣ። ጦርነቱ እንዲቆም በአርበኛ መሪዎች ተወሰነ።

አርበኞች ጉድሩ ሳሉ ጠላት ከወለጋ፣ ከሲዳሞ፣ ከከፋ፣ ከአምቦ በሁለት ጀነራሎች የሚመራ እስከ 30 ሺህ የሚሆን ጦር አቀረበ። አርበኞች አንዱን ጀነራል ገድለው ድል አድርገው አበረሩት። ብዙ ነጭና ከሲቢያ የመጡ አረብ ወታደሮች አለቁ።

ጠላት ወደ ጉዶ ምሽግ ሲገባ አርበኞች ከቆላው ወጥተው ከሜዳ ላይ ሠፈሩ። ጠላት ይህንን ሲያይ በአይሮፕላን ሊያጠቃቸው ሞከረ። ጥቅምት 5፣ ቀን 1930 ዓ.ም ጥዋት ሁለት አይሮፕላን አምጥቶ አከባቢውን አስደበደበ።

በተለይ አርበኛው በሠፈረበት ቦታ በአንድ ትልቅ በርሜል የጋዝ መርዝ ጣለ። በርሜሉ ገና በአየር ላይ እንዳለ መርዙን መርጨት ስለጀመረ ሠራዊቱ መርዝ መሆኑን ተረድቶ በመበታተኑ ጥቂት የጋማ ከብት ከመግደሉ በስተቀር በሰው ላይ ጉዳት ሳያደርስ ቀረ።

የአርበኛው ቡድን እየተጠናከረ ሲሄድ በሕዝብ ዘንድ ይበልጥ ተቀባይነት አገኘ። አርበኛው ከሚዋጋበት አገር ይልቅ ጣልያን የሠፈረበት ይበልጥ ይጐዳ ጀመር። ስለዚህ አርበኞቹን ሂዱልን ትውልድ አካባቢያችን አታስጠፉብን የሚለው ወገን እየተቀነሰ "ኑልን አድኑን" የሚለው እየበዛ ሄደ። የጨለለያ ሕዝብ መክሮ ኑልን ሲል፣ በባላባቱ በፊታውራሪ በፈቃዱ መርኒያ በኩል ጋበዛቸው።[1] እነሱም በመቀበል ሄደው ሀገሩን በማረጋጋት ረዱት። እነሱም ራሳቸው ለተወሰነ ጊዜ እፎይታ አገኙ።

ጠላት አዲስ ጦር አደራጅቶ ዘመተ። አርበኞችም ግንቦት 17 ቀን 1930 ዓ.ም ከቲሴ ላይ ጦርነት ገጠሙት። ጦርነቱ በማግስቱም ቀጠለ። ከአርበኞች በስተጀርባ የነበረው አገር በረሃ ስለነበር ለመከላከል አላመቻቸውም። ስለሞጥር አርበኞች ሞቱ። ከጠላት ወታደሮችም ብዙዎች ወደቁ። አርበኞች የተደረገባቸውን ከበባ ሰብረው ወደ አቡና ቆላ ገቡ። ጠላት ተከታተለ። ሌላ ሁለተኛ ከበባ ሠራባቸው። የተከማቸውን የአርበኛ ቡድን በሰላዮች አማካኝነት ተረድቶ ፈጅቶ ለመገላገል ጥረት አደረገ። አርበኞችም ሐሳቡን አውቀው ነበርና በርትተው ተዋጉ። ቢሆንም በታተናቸው። ገሚሶቹ ወደ ሰሳሌ ተሸጋገሩ፣ ሌሎች በዚያው በነበሩበት አካባቢ ትግላቸውን ቀጠሉ።

በግንደ በረት በረሃ የቀሩት አርበኞች ድካም ስለበዛባቸው እና ብዙ ሰው ስለተለያቸው ቁጥራቸው ወደ አንድ መቶ ዝቅ አለ። ከጠላት መሰወርና ዘሽምቅ መሥራት ግድ ሆነባቸው። በአንባሩ ደግሞ ባንዳ እጅ እጃቸውን ይዞ ለጠላት በመስጠት ሊሸለምባቸው አሰፈሰፈ። የአርበኛው አስተባባሪ ደጃዝማች ዘውዴ አስፋው ነበሩ። ሽክሙ ስለከበደባቸው የውሃ መትረየሳቸውን አቶ ኮሪ ገመዳ ዘንድ አደራ አስቀምጠው የጉደርን ወንዝ ተሻግረው ወደ ወለጋ ሄዱ።

በግንደ በረት ሲከላከል የቆየው አርበኛ ግንቦት 25 ቀን 1930 ዓ.ም ምክር አደረገ። በዚህም ምክር እንደ ቀድሞው ሁሉ የሐሳብ መለያየት ደረሰ። ዘደጃዝማች ዘውዴ አስፋው የሚመራው በዚያው አካባቢ በሕቡዕ ሥራውን መቀጠልን መረጠ። ጥቂቶቹ ሰላማዊ ሕይወት የሚያገኙ መስሎአቸው ወደ ጠላት ገቡ። ግንቦት 17 ቀን 1930 ዓ.ም ከዲጉ ወደ አምቦ ወጡ። ጠላትም አየተከታተለ ወጋቸው። ቡተለይ ግንቦት 19 ቀን በተደረገው ውጊያ አርበኞች በጠላት ላይ ጉዳት አደረሱ።

በአገር ውስጥ ሥራውን ለመቀጠል የወሰነውን ቡድን ግን ጠላት ተከታትሎ ሳይደርስበት ከአንድ ዓመት በላይ ቆየ። ዲጉ ቆላ መሆናቸውን አውቆ ጠላት መስከረም 20 ቀን 1931 ዓ.ም አደጋ ጣለባቸው። ነገር ግን ሊያጠፋቸው ሳይችል ቀረ። ቢሆንምጭክትትሉን ያማጠናከር መሪውን ጠላት

በጠቋሚ ግንደበረት ውስጥ አስያዛቸው። ባላምባራስ ወልደ ፃድቅ የተባለው ሀገር ወዳድ በጠላት መሣሪያንት ሁኔታውን የሚያጣራ በመምሰል አስቀርቦ አርበኞችን አስጠነቀቀ። እንዲያመልጡ የሰጣቸውን ምክር ግን ባለመቀበል ከጠላት እጅ እንደገና ወደቁ።

ጠላት ስለመጣ መበሪ ላይ ጥቅምት 5 ቀን 1930 ዓ.ም ጦርነት ተደርጐ ድል የአርበኞች ሆነ። ነገር ግን ሰተከታታይ ሥራ መዘጋጀት ስለአስፈለገ ምክር ተያዘ። ከቡልጋ በመጡት በእነ ባላምባራስ ተሻገርና በግንደ በረት አካባቢ ሲኖሳከሱ በቆዩት አርበኞች መካከል የአስተያየት ልዩነት ተፈጠረ። ከቡልጋ የመጣው አርበኛ የለመደው በተራራና በሸንተረር በወንዝና በሸለቆ ውስጥ ተሰማርቶ መዋጋት ሲሆን፣ በሜዳ ላይ መዋጋት አልሆንልህ አለው። በግንደ በረት አካባቢ በሜዳ ላይ የቆየው ደግሞ በፈረስ እየጋለበ መዋጋት እንጂ፣ በእግሩ ብዙ መንገድ መጓዝ ከበደው። ስለዚህ ጥቅምት 6 ቀን 1932 ዓ.ም በዋለው ምክር ሁሉም እንደ ፍላጐቱ እንዲያደርግ ከስምምነት ላይ ተደረሰና ባላምባራስ /ፊታውራሪ/ ተሻገር ወደ ቡልጋ ለመመለስ ወደ ሰላሌ ተሻገሩ። እዛ ከሆለታ የተንቀሳቀሰ የጠላት ጦር መጣባቸው። አርበኞችም ጥቅምት 12 ቀን 1932 ዓ.ም መዳላ ከተባለው ቦታ ገጥመው በመውጋት ወደ ኋላው መለሱት። ከዚያም ወደ ሙገር ቆላ ወርደው ወደሐሮ ተሻገሩ።

ኃይል እንደተቀነሰባቸው ባወቀ ጊዜ ጠላት በግንደ በረት አካባቢ በነበሩ አርበኞች ላይ ጦርነት አጠነከረባቸው። አርበኞችም ፋታ ለማግኘትና እንደገና ለመጠናከር የሚረዳቸውን ዘዴ በማሰብ ለጠላት የአርቅ ፊት አሳዩት። በተደረገውም ድርድር ፋሽስቶች ከሆለታ ወዲያ አልፈው በልጅ ከበደ ብዙነህ ላይ ደረሱባቸው። እንዲሁም ልጅ ከበደ ከሆለታ በላይ ላይደርሱ ሀዳር 14 ቀን 1931 ዓ.ም ስምምነት ተደረገ። ከዚህ ስምምነት ላይ የተደረሰው በባላገሩ ላይ የደረሰውን ችግር ለማቃለል ታስቦ ጭምር ነበር። ከዚህም በስተቀር አዋጁ ሕዝቡ በጥቅም መጋጨቱን ትቶ አንድነቱን እንዲያጠናክር ነበር። እንዲሁም ስምምነቱ አንዱ የአንዱን ወሰን በመተላለፍ እንዳይዘራረፍ ለማስቻል እና ለመምከር ነበር። ጠላት በመጣ ጊዜ ተባብሮ ለመውጋት ሕዝባዊ ስምምነት ለማስገኘት ታስቦ ነበር።

ፋሽስቶች በቃላቸው መጽናት አይሆንላቸውም። ወር ሳይሞላቸው ስምምነቱን በመጣስ ታህሣሥ 5 ቀን አምስት መኮንኖች ደበሌ ወንዝ ወርደው ለጦር ሥራ የሚረዳ ካርታ ሊሠሩ ተገኙ። እጃቸውን ለመስጠት ፈቃደኞች ባለመሆናቸው ተገደሉ። ገብረ ማርያም የተባለ መሪአቸው ብቻ አመለጠ። ገብር ማርያም ጦር ይዞ ስለመጣ ቆላ ቱሊ ከተባለው ቦታ ታህሣሥ 7 ቀን ጦርነት ተደረገ። ሁለት የጠላት ወታደሮች ሞቱ አንድ ቆሰለ። ልጅ ከበደ ብዙነህ ራሳቸው አመሉጡ። ነገር ግን አሽከራቸው ሞተ፣ እንደዚሁም ብዙ መሣሪያና ዕቃ ተማረከባቸው።

ሀዳር 17 ቀን 1931 ዓ.ም የግንደበረቱ ቡጋጅ፣ በጀልዱ፣ በሆሌ በኩል እንደዚሁም የአዲስ አበባው በቀጨማ፣ በጉሮ በኩል መጣባቸው። አርበኞቹም በሦስት ረድፍ የመጣባቸውን የጠላት ጦር ተጋጥመው ሀዳር 17 ቀን 1931 ዓ.ም ወጉት። የጠላት ኃይል ስለአየለ ሀዳር 20 ቀን ወደ ሰላሌ ተሻገሩ። አርበኞች ባይበገሩለትም ጠላት ማጥቃቱን አልተወም። ታህሣሥ 12 ቀን አዲስ ጦር ሠርቶ መጣ። አርበኞችም ግንባር ለግንባር ገጥመው ወጉት። አርባ ሰባት ባንዶች ማምለጥ ሲሳናቸው እየሸሹ ከአንድ ታላቅ ዋሻ ውስጥ ተደበቁ። አርበኞቹ ሦስት የእጅ ቦምብ በመጣል አቁስሰው አስደንግጠው ማረኩአቸው። ነገር ግን ከማረኩአቸው በኋላ አንዳች ሳያደርጉአቸው መሣሪያቸውን ገፍፈው በነፃ ለቀቂቸው። ጥር 9 ቀን ደግሞ ከሸኖ እያሰሰ የጠላት ጦር ስለመጣ እሳ ጉራ ከተባለው ቦታ ውጊያ ተካሄደ።

የካቲት 10 ቀን ከአምቦ፣ ከአዲስ አበባና ከሰንዳፋ የጠላት ጦር እንደገና መጣ። ታላቅ ውጊያ ተካሄደ። ላቀው ይፍሩ፣ አሰላ ተመናኝተሀና አሥማር የተባሉ ሦስት አርበኞች ተሰማ ገላን በተባለ ባንዳ ተገደሉ። ስመጥር አርበኞች ነበሩና ተሰማ ራሳቸውን ቆርጦ ሰጣልያን በማቅረብ ተሸለመባቸው። የቀረውን አስከሬናቸውን አርበኛው ሊባስ ተክለሃይማኖት ወስዶ ቀበራቸው።

ጠላት በአርቅ ሰበብ የአርበኞችን ልቡና ሰማሳላት ያደረገው ሙከራ አርቅ መፍረሱን በዚህ አካባቢ የነበሩት አርበኞች ከራስ አበበ ጋር በመላላክ ወዲያው ሰምተው ለጦርነት ተዘጋጁ። ጠላትም ብዛታቸውንና ያሉበትን ቦታ በአርቁ ወራት አጥንቶ ነበርና በፍጥነት ደምሰሶ ለመገላገል ጥረት አደረገ።

ጦርነቱ ሚያዝያ 8 ቀን ተከፍቶ እስከ 13 ቀን 1931 ዓ.ም ድረስ ቀጠለ። ነገር ግን ለጠላት አንዳች ውጤት አላስገኘለትም። ከግንቦት 1 እስከ 5 ቀን እንደዚሁ ጥረት አደረገ። አልተቃናለትም። ግንቦት 29 ቀን ያደረገውም ሙከራ ከሽፈበት። እንዲያውም አርበኞች እስከ ምሽጉ ድረስ ገብተው ይወጉት ጀመር። እንዲያውም የክርስትና ጠላ ለመጠጣት ከአንድ ባንዳ ቤት ገብተው የነበሩን አንድ ሻምበልና አንድ መቶ አለቃ ከስምንት ወታደሮቻቸው ጋር ፈጁበት። ይህ አድራጐት በባንዳና በጣልያን መካከል የነበረውን ግንኙነት ለመስበር ሆን ተብሎ የተደረገ መሆኑን ማጤን ይገባል።

ጠላት ከጌዶና ከነቀምት ሌላ ጦር አምጥቶ ከበባ አደረገ። አርበኞቹም ሊባስ ላይ ገጠሙት፣ በጠላትም ላይ ጉዳት አደረሱ። የካቲት 17 እና 20 ቀን ሲጋ በተባለ ቦታ በተደረገ ጦርነት ሁለት ባንዶች ሲገደሉ በድምሩ ስድስት ባንዶች ተማረኩ። የእነ ላቀው ይፍሩ በባንዶች እጅ መገደልና ራሳቸው መቆረጥ የአርበኛውን ደም አፍልቶት ነበርና እንደ ወትሮው በሰላም አልተላቀቀም። ሁሉም በሞት ተቀጡ።

ጣልያን ይህንን የአርበኛ ቡድን ከኢላማው ውስጥ አስገብቶት ነበርና ብሰው እያሰለለ፣ ከአዲስ አበባና ከአካባቢው ካሉቴ ምሽጐች ጋር በሬዲዮ እየተነጋገረ አጥብቆ ተከታተለው። ከፀጆ ጉራንደ ምሽግ ወጥቶ ሊያጠቃቸው

መጣ። አርበኞቹም ጥቅምት 17 ቀን 1932 ዓ.ም ጦርነት ገጥመው ሠላሣ ስምንት ወታደር ገደሉበት። እሱም ይህንን ባየ ጊዜ ተመልሶ ወደ ውጣበት ምሽግ ገባ።

ጠላት አርበኞቹን ለማጥቃት መጣ። እነሱም መጋቢት 19 ቀን 1932 ዓ.ም ቡርቃ በዲማ ከተባለ ቦታ ጠብቀው ገጠሙት። ኡርጋ ወንዝ ላይ በሚያስደንቅ የጦር ሥልት ወግተው መለሱት።

በአንድ የመቶ አለቃ የሚመራ ጦር በአካባቢው ሲዘዋወር መንዳደር ፋሱ ላይ ታየ። ሜጢ ቆላ ሲደርስ ሚያዝያ 15 ቀን ፊት ለፊት ገጠሙት። የጦር መሪውንና ብዙ ወታደር ገድለው፣ አሥራ አምስት ምንሽር ጠመንጃና አንድ አልቤን መትረየስ ማረኩ። ባላገርም በየጥሻው ውስጥ ከወደቀው የጠላት ወታደር ብዙ መሣሪያ ወሰደ። አሥራ ስድስት በቅሎዎችም ተማረኩ።

ግንቦት 6 ቀን እንጭኔ ጊዮርጊስ፣ ደንሴ ማርያም ላይ ጦርነት ተደርጐ አርበኞቹ ጠላትን አሳፍረው መለሱ። ግንቦት 16 ቀን አልጌ በተባለው ቀበሌ እንደዚሁም ሰኔ 9 ቀን ደብደቤ ወንዝ ላይ ከባንዶች ጋር ግጭት ተደርጐ ባንዶች ዋጋቸውን ተቀበሉ።

የ1932 ዓ.ም ሲጀምር ዘመኑ የነፃነት ወጋገን የታየበት ነበርና የአርበኛው መንፈስ በአዲስ ስሜት ተነሳሳ።

ጥቅምት 3 ቀን 1933 ዓ.ም አደነገዶ ላይ በተደረገው ጦርነት አርበኞች ቀናቸው። ጥቅምት 17 ቀን ደግሞ ከጐጃም የመጣ ጦር ውልጮ አዳበርጋ ላይ ገጠማቸው። በዚህም አርበኞች ቀናቸው። የመጣው የጠላት ጦር ወደ ኋላው ተመልሶ ወለንኮሜ ሠፈረ። የሚሸሸውም የሞቱትና የቆሰሉበትን ወታደሮች ከአገሬው ለመሠወር ከነመሣሪያቸው እየሰበሰበ በአሳት አቃጠለ። ይህኛው ግብር ከሌላውም የመረረ ሆነ።

ህዳር 26 ቀን ሌላ ጦር ከአዲስ አበባና ከሆለታ ቢመጣባቸውም አርበኞችም በልበ ሙሉነት ወጉት። የጦር አዝማቹ በቅሎውን አስግርከ፣ እሱም ራሱ በሩሱ ገደል ገብቶ በአሳር በመከራ ከሞት ተረፈ።

አርበኞች የጥቂት ጊዜ እረፍት እንደ አደረጉ ልጅ ባዩ ተክለ ወልድ የንጉሠ ነገሥቱን መልዕክትና ፎቶግራፋቸውን ይዘውላቸው ደረሱ። ታሳቅ ደስታ ሆነ፣ ልባቸውም ይበልጡኑ ተፅናና። ነገር ግን ልጅ ባዩ ሥራውን በመቀጠል ሲጓዝ ወደ ዲሬ ከተባለው ቦታ አረጋ ዳዲ በተባለ ከሃዲ ተገደለ። አርበኞች አስክሬኑን አንስተው ለመቅበር ሲሞክሩ ግጭት ተፈጥሮ ብዙ ባንዶች ሞቱ። በዚህም የንጉሠ ነገሥቱ መምጣት ወሬ ይበልጡኑ ተዛመተ። ጥር 1 ቀንም ቀርዩ አዳበርጋ ድረስ የጠላት ጦር መጣ። ነገር ግን ደፍሮ ጦርነት አልከፈተም።

የንጉሠ ነገሥቱ መምጣት በይፋ እየታወቀ ሲሄድ የአርበኛው ወኔ አየለ። የጠላት ልብ ደግሞ ተሰበረ። ከጐጃም የሸሸው የጠላት ጦር የዐባይን ወንዝ ተሻግሮ ዳገቱን በመውጣት ጉሐ ጽዮን ደረሰ። ሃሳቡ አዲስ አበባ

ከአለው ጦር ጋር ተቀላቅሎ ለመመለስ ነበር። ነገር ግን እንደዚያ አልሆነም። ጠላት አዲስ አበባ ላይ ለመዋጋት አስቦት የነበረውን ዕቅድ ተው። ምክንያቱንም ይህንኑ በሚመለከት በሌላ ምዕራፍ እናየዋለን።[2] አሁን ግን የዚህ ዕቅድ መሰወጥ ያስከተለውን ችግር እንመለከታለን።

ይህ ከጐጃም የተንቀሳቀሰው የጠላት ጦር ገብረ ጉራቻ ሲደርስ ተበተነ። አንዱ ቡድን ወደ መርሐቤቴ አመራ፣ አንዱ ደግሞ ወደ ደቡብ አዘቀዘቀ። ሐሳቡ በአዲስ ዓለም በኩል አቋርጦ ተፍኪ ከሚጠብቀው ወገኑ ጋር በመቀላቀል ወደ ጂማ ከዚያም ወደ ጉራ ለመሄድ ነበር። ነገር ግን አርበኛው እርምጃ በእርምጃ ይወጋው ጀመር። ከሰላሌ አርበኞች ጋር እየተተናነቀ የሙገርን ወንዝ ተሻግሮ ሜጫ ክልል ሲገባ፣ የዚያ አካባቢ አርበኞች በፋንታቸው ይጠዘጥዙት ጀመር።

በአንድ ኩሉኔል የሚመራ ጦር ከገብረ ጉራቻ በሐሮ በኩል አድርጉ አደሞጃ ደረሰ። አርበኞቹም የካቲት 10 ቀን ግንባር ለግንባር ገጠሙት። የማያሳልፉት ሆነ። ወደ ተፍኪ ለመጓዝ የነበረውን ሐሳብ ለውጦ ወደ አዲስ አበባ ተጓዘ። ያለቀው አልቆ የተረፈው አዲስ አበባ ገባ።

አርበኞች የካቲት 17 ቀን አድአ በርጋ የኪዳነ ምሕረትን በዓል በፈንጠዝያ ከአከበሩ በኋላ በማግስቱ የካቲት 17 ቀን ከጐጃም የመጣውን ጦር እየተከታተሉ ሊወጉት ዋሉ። የካቲት 29 ቀን ደግሞ ሌላ አዲስ ጦር ከጐጃም የካ ከተባለው ቦታ ደረሰ። ኤቢሣ ከተባለው ሥርጥ ላይ ገጥመው ወደ አድአ በርጋ እንዳይሄድ አገዱት። እፊት የቀደመውን የጠላት ጦር በማስታየት ፈጅተው የተቻላቸውን ያህል መሣሪያ አነሱ።

የጠላት ጦር ሌላ አዲስ ጦር ስለደረሰለት ሠፍሮበት ከነበረበት ቦታ ተንቀሳቀሰ። አርበኞችም ከወደፊቱ ቀድመው ምቹ ቦታ በመያዝ ጉፍሳላ አደበርጋ ከተባለው ቦታ ገጠሙት። ጠላትም መንገዱን ለመቀጠል ስለአልቻለ ሠፈር አደረገ። አርበኞቹ ከየካቲት 1 ቀን እስከ 5 ቀን ድረስ ያለ ዕረፍት ወጉት። ጠላት ወደ ጂማ ለመሄድ የነበረውን ሐሳብ ለውጦ የካቲት 6 ቀን 1933 ዓ.ም በበዲና በመ·ሉ በኩል ወደ አዲስ አበባ አመራ።

መጋቢት 15 ቀን ከዚያው ከጐጃም ሌላ ፈረሰኛ ጦር መጣ። አርበኞቹም ሞጆ ላይ ገጥመው ብዙ ሰውም ፈጁበት። ይህንን ድርጊት የተመለከቱ ባንዶች ከጠላት ገሸሽ አሉ። ወደ ድል አጥቢያ አርበኝነት ገቡ።[3]

መጋቢት 17 ቀን በዚያው መንገድ በአንድ ኩሉኔል የሚመራ ጦር ደረሰ። አርበኛውም የአስተናጋጅነት ሥራውን ቀጠለ። ብዙ የጠላት ሠራዊት ገደሉ። ነገር ግን ኩሉኔሉ የእጅ ቦምብ እየወረወረ በመከላከል አልሞት ብሎ እንደገመሬ ዝንጀሮ እየተጐማለለ አቃተ። አንዲት ነጭ በግ ማስከተሉን አርበኞቹ አጢነው ነበርና አሱን ትተው በግዋን በቅድሚያ ገደሉአት። እሱንም ወዲያው አከታትለው በመተኩስ ገደሉት። ይህም የጠላት መኩንኖች

ከጭንቀታቸው ጽናት የተነሣ በጥንቆላ ሥራ እስከማመን ደርሰው እንደነበር ያሳያል።

ከጉጃም ሲጓዝ ያደረ ሌላ ጦር መጋቢት 26 ቀን ከዚያው ቦታ ደረሰ። አርበኞቹ መንገዱን በጥይት ስለአጠሩበት ግን ገብቶት ሠፈረ። ጦርነቱ መጋቢት 27 ቀን እና 28 ቀንም ቀጠለ። የእንግሊዝ ጦር በገፈርሣ በኩል አልፎ በዱ ከተባለው ቦታ ድረስ መጥቶ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ አውለበለበ። የጠላትን የጦር መሣሪያ ከተረከበና አዛዡን ጀነራል ከማረከ በኋላ ወደ አዲስ አበባ ተመለሰ። የእንግሊዝ መኰንን ወደ አዲስ አበባ ከመመለሱ አስቀድሞ ለአርበኞቹ ንግግር አደረገላቸው። በንግግሩም በትግላቸው ከዚያች ቀን ጀምሮ ነፃነታቸውን ማግኘታቸውን አረጋግጦ፣ የንጉሠ ነገሥታቸውን መምጣት እንዲጠባበቁ ምክር ሰጣቸው።

የድል ጠረን ሲሸታቸው የሜጫ አርበኞች በበኩላቸው የአዲስ ዓለምን ምሽግ መስበር ፈለጉ። ቀደም ብሎ በ1932 ዓ.ም የጀልዲን ምሽግ የመቱበትን ሥልት በማጠናከር ዕቅድ አወጡ። ወይዘሮ ሸዋረገድ ገድሌ የምስጢር ሥራ የማካሄድ ተግባራቸውን አጠናከሩ። ህዳር 21 ቀን የአዲስ ዓለም ማርያም ክብካብ ነው። ማታውኑ ተቃርበው ሌሊቱን በመጓዝ ከከተማው ገብተው በአቶ ዓለማየሁ ቤት ተደብቀው ዋሉ። ህዳር 22 ለ23 አጥቢያ ተዘዋውረው ሁኔታውን አጠኑ። አርበኛው በሙሉ እንዲመጣ ጥሪ ተላልፎ ህዳር 24 ቀን ገባ።

በባላምባራስ /ደጃዝማች/ ዘውዴ ጥላሁንና በልጅ /ጀነራል/ ጃገማ ኬሎ የሚመራው ይህ ቡድን ህዳር 25 ማታ ተዘጋጀ። ጠመንጃ ያለው ጠመንጃውን ፈተሸ። ጀሌው የወይራ ዱላና የክትክታ ቆመጡን አዘጋጀ። ከሁለት ተከፍለው በሁለት አቅጣጫ ተሰማርቶ ሲጠባበቅ ቆይቶ፣ ትዕዛዝ ሲደርሰው ሥራውን ቀጠለ። እሥረኞቹን ከወህኒ ቤት ያለምንም ችግር ማስወጣት ተቻለ። የጦር መሣሪያ መጋዘኑ ተከፍቶ ተዘረፈ። አንድ ኩሱኔልና ሰባ አምስት ጣልያኖች ተገደሉ። አንድ አርበኛ ቆስለው በኋላ ሞቱ። አንድ ገበሬ በጥይት ተመታ። ሌላ ችግር በአርበኞች ላይ አልደረሰም።

ጠላት ጥቂት ከአገገመ በኋላ አርበኞቹን ለመከታተል ተንቀሳቀሰ። እነሱም ነቅተው ይጠብቁት ነበርና ወሰንኮሜ ቱሉቡኾ ከተባለው ሥፍራ ግንባር ለግንባር ገጠሙት። ብዙ ሰው ቢሞትና ቢቆስልባቸውም ድሉ የእነሱ ሆነ።

ጠላት በአዲስ ዓለም ምሽግ መሰበር የደረሰበትን ውርደት ለመክፈል በአርበኞች ላይ ተንቀሳቀሰ። እነሱም በመሸሽ ፈንታ ወደ እሱ ገስግሰው ወላንኮሜ ቱሉ በኾ ከተባለው ቦታ ወጉት ጨፈጨፉት። ወደ ማታ ድሉ የእነሱ ሆነ። ጠላትም ወደ ኋላው ተመለሰ።



ልጅ ጃግማ ኬሎ(ከመሃል) ከአርበኞች ጓዶቻቸው ጋር።

ፈረስ የያዘ የፋሽስት ጦር ቀደም ብሎ ወደ አምቦ ሄዶ ነበር። በርጋ ከተባለው ወንዝ ሲገባ በባላምባራስ /ደጃዝማች/ ዘውዴ የሚመሩት አርበኞች ገጠሙት። ጦርነቱ ከመጋቢት 24 እስከ 27 ቀን 1933 ዓ.ም ድረስ ቀጠለ። በመሳልትና በሌሊት በተካሄደው ጦርነት ያለቀው አልቆ የተረፈው የጣልያን ጦር አዲስ ዓለም ገባ። ከአዲስ አበባ ለዕርዳታ የመጣውን የጦር ኃይልና ብረት ለበስ አርበኞቹ ተሸከርካሪ ጠዘጠዙት። ከአለፈው የባሰ አልቂት አደረሱበት።

ጠላት ማጣፊያው ስለአጠረበት ባልተሰባበሩት ጥቂት ብረት ለበስ መኪናዎቹ እየተንጠለጠለ ወደ አዲስ አበባ ሄደ። በባላምባራስ /ደጃዝማች/ ዘውዴ ጥላሁን የተመራው አርበኛ አዲስ ዓለምን ሚያዝያ 26 ቀን 1933 ዓ.ም ነፃ አውጥቶ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ተከለ።[4]

በልጅ /ጀነራል/ ጀገማ የሚመራው ሌላው የአርበኛ ቡድን ደግሞ ሆለታ ላይ የነበረውን የጠላት ምሽግ ከቦ መተናፈሻ በማሳጣት ከወጋው በኋላ በምሽጉ ውስጥ ገብቶ ሰወሬ ነጋሪ ሳይተርፍ ድራሹን አጠፋው።

እዚህ ላይ አንድ ነጥብ ሊታወቅ ይገባል። የዚህ አካባቢ አርበኞች የጠላትን መንገድ በማጠር ወደ አዲስ አበባ እንዲገባ ያስገደዱት፣ ወደ ጅማ ዘመዴድ በዛ እንዳይከማች እና በዚያ ታላቅ ጦርነት ለማካሄድ እንዳይቻለው ነው። ዕቅዳቸው አዲስ አበባ ገብቶ እንዲታጐርና በዚያው እንዲማረክ መሆኑ ሊታወቅላቸው ይገባል።

<u>ማጣቀሻ ዕሑፎች</u>

1. ሙሉሰው ምትኩ፣ *ክሽዋ እስከ ሱዳን*፣ ገጽ 30-32።
2. አዲስ አበባ፣ የሚለውን ምዕራፍ ይመልከቱ።
3. ታደሰ ዘወልዴ፣ *ቀሪን ገረመው*፣ ገጽ 419-452።
4. ገዛኢ ከማሁ፣ ገጽ 504-514።



ልጅ ጃገማ ኬሎ(ከመሃል) ከአርበኞች ጓዶቻቸው ጋር።

ምዕራፍ ሃያ ስድስት
በመርሐቤቴና ስላሌ የተካሄደ ትግል

ሚያዝያ 26 ቀን 1928 ዓ.ም የጠላት ወታደር ከደብረ ብርሃን ወደ አዲስ አበባ በሚያደርገው ረጅም ጉዞ ቢታክትም በድል አድራጊነት ስሜቱ ተበረታቶ ሳለ፣ በቀኛዝማች ኃይሉ ማርያም ማሞ የተቀሰቀሰ የተባበሩ የአርበኞች ቡድን ጫጫ ሱኪ ሣራቤ ከተባለው ቦታ ላይ አደጋ ጣለበት። አርበኞች አምስት ካሚዮኖች ሠብረው ስድስት መትረየሶች፣ ብዙ ሣጥን ጥይት፣ መድኃኒቶችና የወታደር ልብስ ነጠቁ። ይህንን በማድረጋቸው ልባቸው ደነደነ። ግንቦት 1 ቀን የተደረገባቸውን ከበባ በቀላል ጥሰው አመለጡ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በእንሣሮ አካባቢ ሌላ የአርበኞች እንቅስቃሴ ተጀመረ። እሱ ደግሞ የሚመራው በልጅ ሥዩም ንብረ ሕይወት ነበር። እነሱም በቆላው ተቀምጦ ጠላት እስኪመጣ ከመጠበቅ ይልቅ፣ ከደጋው አገር እየወጡ ምሽጉን እየከበቡ መውጫ መግቢያ ማሳጣት እንደሚያስፈልግ አመኑ፣ እንደዚሁም አደረጉ።

በወቅቱ ወደ አዲስ አበባ የሚጓዘው የጠላት ወታደር በመንገዱ ላይ ያገኘውን ቤት ማቃጠልና ሀብቱን መዝረፍ ያዘ። በባህምባራስ /ራስ/ አበበ አረጋይ የሚመራው የአርበኛ ቡድን ግንቦት 24 ቀን 1928 ዓ.ም ጅሩ ዋዩ ስክላ ግንባር ለግንባር ጦርነት ገጠመው። ጠላትም ብዙ ሰው ከአስፈጀ በኋላ ሸሸ። ከዚያ በኋላ ለአራት ወር በዚያች አካባቢ ዝር አላለም።

ሐምሌ 23 ቀን 1928 ዓ.ም አሰሌ ጅሩ ምክር ተጀመረ። በምክሩ ላይ አኩሉ ወደ ግንደ በረት ከዚያም ወደ ጠረፍ እንሂድ ሲል፣ እኩሉ ደግሞ ወደ መንዝ ተሻግረን እንዋጋለን አለ። ሁኔታው በአርበኛው መካከል ልዩነት እንዳይቀሰቅስና የርስበርስ ግጭት እንዳያስነሳ ስለአሰጋ በጥንቃቄ ተያዘ። ነገሩም ውሣኔ ሳያገኝ እየተጠና ሰነበተ። ወደ ሣህል አገር ገብቶ ለመዋጋት ያሰበው ታላቁ ቡድን ጋጂ ደምቢ ከተባለው ቦታ ሠፈረ። በሻለቃ /ራስ/ መሥፍን ስለሺ የሚመራው ቡድን ግን በታላት ቅሬታ ተሰናብቶ ከእነሱ ተለይቶ ገዙውን ቀጠለ።

የ1928 ዓ.ም ተፈጽሞ የ1929 ዓ.ም ባተ። የአርበኞችም ኃይል ጥቂት በጥቂት መጠናከር ጀመረ። የጠላት አገዛብ በአካባቢው ሕዝብ ላይ የፈጠረው ድንጋጤ ተቀነሰ።

ጣልያን መረሐቤቴ ለመግባትና መራኛ ምሽግ ለመሥራት ሞከረ። በመቶ አለቃ /በደጃዝማች/ ገለታ ቆርቾ አስተባባሪነት የሚንቀሳቀሰው የአርበኞች ቡድን አናስገባም ብሎ መከተ። ጥቅምት 1 ቀን 1929 ዓ.ም ግንባር ለግንባር ገጥሞ ተዋጋ። ጣልያን ጦርነቱን በምድር ብቻ ለመግፋት ስለአልቻለ አካባቢውን በአይሮፕላን ደበደበ። በጠላትም በአርበኞችም ላይ ብዙ

ጉዳት ደረሰ። ቢሆንም አርበኞች ሰባት ጠመንጃ ማረኩ። ነገር ግን ጠላት ውሎ አድሮ እንደአሰበው በዛ ቦታ ላይ ምሽግ ሠራ።

ጥቅምት 11 ቀን ደራ ዱግዳ ላይ ከፍ ያለ ጦርነት ተደረገ። በልጅ /ደጃዝማች/ አበበ ሽንቁጥ የሚመራው የአርበኛ ቡድን አሸንፎ ጠላትን እስከ ሦሽጉ ድረስ አባረረው። በዚሁ ቀን ወደ ጅሩ የተሻገረውን ጦር አርበኛው እስከ ደራ ዱግዳ ወግቶ ወደ ኋላ መለሰው። ከቀናት በኋላ ግን የጠላት ጦር እየገፋ ወደ ማሕል አገርና በየገጠሩ መሠራጨት ጀመረ። የጣልያን ጦር በገጠር መሠራጨት የጠላትን ኃይል እንደሚያጠነክር በአንባሩ ግን የአርበኞችን ኃይል እንደሚቀንስ በጠላትም በወገንም ዘንድ የታወቀ ነበር። በተለይም በየደረሰበት ምሽግ መመሸጉ አሳሳቢ ጉዳይ ሆነ። አርበኛው ይህንን የጠላት የኃይል ግንባታ ለመቋቋም አሰበ።

ስለዚህ ጠላት ዝንጀሮ ውሃ ሲደርስ አርበኛው ህዳር 25 ቀን 1929 ዓ.ም ገጠመው። ስርጠሰስ ከተባለው ቦታ ቀኑን ሙሉ ጦርነት ተካሄደ። ሦንም ጠንክሮ ቢዋጋ የጠላትን ኃይል ጥቂት በጥቂት መቀነስና እርምጃውን በየደረሰበት ማዘግየት እንጂ፣ አርበኛው የጠላት እርምጃ ሲያግደው አልቻለም። ጠላት ግን ከግንደ በረትና ከሜታ ሮቢ ሌላ ኃይል ደረሰለት። በዚህ ሁኔታ ጦርነቱን መቀጠል በወገን ላይ ጉዳት ማብዛት ሆኖ ስለተገኘ አርበኛው ወደ ቆላው አፈገፈገ።

በሌላ በኩል ደግሞ የስላሌ ሕዝብ መሪ አድርጐ የተከተለው የራስ ካሣን ልጆች ደጃዝማች አበራንና ደጃዝማች አስፋ ወሰን ካሣን ነበር። ነገር ግን እነሱ ወደ ጠላት ለመግባት ማሰባቸው በአርበኛው ዘንድ ጥርጣሬ አሳደረ። ማስረጃም እየተገኘ ስለሄደ ታሳሳቅ አርበኞችና ሽማግሌዎች፣ ባለቤታቸው ወይዘሮ ከበደች ሥዩም ጭምር ደጃዝማች አበራ ካሣን እንዲያነጋግሩአቸው ተደረገ።

አርበኞችም ታህሣስ 10 ቀን 1929 ዓ.ም ቅዳሜ ጥዋት ደጃዝማቹን አነጋገሩአቸው። እንዲያስተባብሩአቸውም ጠየቁአቸው። እሳቸው ግን ጠላት የነሱን ከተማ ለመያዝ የወሰነ መሆኑን ገለፀ። በስተማይቱ ላይ መዋጋት ሕዝብ ማስጨረስ መሆኑን፣ ጠላት አንዳች ምክንያት ከአገኘ ሕዝቡን ከመጨረስ ወደ ኋላ እንደማይል አስታወቁ። ከዚህ በኋላ ከተማይቱን ለቅቆ ለመውጣት በጉባኤው በድምፅ ተወሰነ። ደጃዝማች አበራ ፈቃደኞች የሆኑ አሽከሮቻቸውን አስከትለው ከፍቼ ከተማ ወደ ደገም ሄዱ። ቀራ ካራ ከተባለው ቦታ ለመዋጋት ታሰቡ። እሱም ሳይሆን ቀረና ሰንበሌጥ ወደተባለው ቦታ ሄዱ። ከዚያም ታህሣሥ 11 ቀን ሰልሚ ደረሱና ጦርነቱ በመርሐቤቴ እንዲሆን በምክር ተወሰነ።

የጣልያን መንግሥት ይህንን እየተረዳ የራስ ካሣን አሽከሮችና ባለምዋሎቻቸውን ከአምስት መቶ የማያንሱ ሰዎች ይዞ አሰረ። "ደጃዝማች አበራ ካሣና ደጃዝማች አስፋወሰን ካሣ እጃቸውን ካልሰጡ እረሸናቸዋለሁ።

ሁለቱ ወንድማማቾች እጃቸውን ከሰጡ ሹሜ ሽልሜ ከአባታቸው ርስተጉልት አስቀምጣቸዋለሁ" አለ። በዚህ ጉዳይ የሕዝቡ ልብ ታወከ። ሁለቱ ወንድማማቾች እጃቸውን እንዳይሰጡ በአርበኞቹ ዘንድ ምክር ተያዘ። ወገኖቻቸው የታሠሩባቸው ደግሞ እጃቸውን እንዲሰጡ ወተወቱ።

ታህሣሥ 11 ለ12 አጥቢያ ከነደጃዝማች አበራ ዘንድ ታላቅ የምክር ሌሊት ነበር። ጥርጣሬው ይፋ ወጣ። ክርክሩ ከጣልያን እንግባ፣ የሰም ጦርነቱን እንቀጥል የሚል ሆነ። በምክሩ ላይ የተገኙት ሻለቃ /ራስ/ መሥፍን ስለሽና ሌሎችም የአርበኛ መሪዎች ወደ ጠላት እንዳይገቡ አጥብቀው መከሩአቸው። ለራሳቸው ለደጃዝማቹ ሕይወት አስጊ መሆኑን በማስረዳ ገለውላቸው። ጠላት ሁለቱ ደጃዝማቾች እጃቸውን ከአልሰጡ የሰላሌን ሕዝብ እንደሚፈጅ አስፈራርቶ ነበርና ደጃዝማቾቹ ለጣልያን እንዲገቡ የሚፈልጉ የአባታቸው አሽከሮች ጭምር ተቃውሞ አነሱ። ሁኔታው ተካርሮ የርስበርስ ግጭት እንዳይፈጠር ከሚያሳስብበት ደረጃ ደረሰ። ደጃዝማቹ ለጣልያን ለመግባት ወሰኑ። አርበኞቹ እንዲሁም ባለቤታቸው ቆራጥዋ ወይዘሮ ከበደች ሥዩም ጥለዋቸው ሄዱ።

ሁለቱ ወንድማማቾች ታህሣሥ 12 ቀን 1929 ዓ.ም ጥዋት ጉዞአቸውን ወደፍቼ ከተማ ጀመሩ። በልበ ሙልነት የወረዱትን ቁልቁለት በተሰበረ ልብ ዳገት መውጣት ሆነባቸው። ከፍቼ ከተማ ገቡ። ጠላት በሰላም ተቀብሎ ለንስሐ ሳያበቃ ሳያውል ሳያሳድር ዕለቱን በተከበሩበት አደባባይ ሁለቱንም ወንድማማቾች በመትረየስ ረሸናቸው።[1] ግራዚያኒም "ወንድማማቾች አበራና አስፋወሰን ካሣ በጦርነት ተማርከው በሰጠሁት ትዕዛዝ መሠረት ፍቼ አደባባይ ላይ በጥይት ተደበደቡ። አገራችን የምትያከው ስናልቅ ነው ያሉት ቃል ተፈፀመ" የሚል ቴሌግራም ወደ ሞሶሎኒ አስተላለፈ። ይህ አገዳደል ለአርበኞች ትልቅ ትምህርት ሰጠ። ጣልያን ቃሉን የማያከብር ቀጣፊ መሆኑ በይፋ ተገለፀ። የሀገር ፍቅር ከሀገር ጋር የሚኖር እንጂ ከሰው ጋር ተገድሎ የሚቀበር አይደለምና ጦርነቱ ቀጠለ።

ጣልያን ሁለቱን ወንድማማቾች ከገደለ በኋላ፣ አርበኞችን ከአካባቢው ለማጥፋት በሙሉ ኃይሉ ተንቀሳቅሶ አካባቢውን እያሰሰ ጉሐ ጽዮን ደረሰ። አርበኞችም ታህሣሥ 28 ቀን 1929 ዓ.ም ረቡዕ ገጠሙት። ነገር ግን አጥብቀው ቢዋጉም ውጤት ማግኘት ሳይችሉ ስለቀሩ ወደ አባይ ቆላና ወደ ሙገር ወንዝ ወረዱ።

ጣልያን በፍቼ አካባቢ እነ ደጃዝማች አበራ ካሣን አስጨንቆ በነበረበት ወቅት፣ በውልጮ ደግሞ አርበኛው ጣልያንን አስጨንቆ ነበር። ጠላት ሕዝቡን እየፈጀ፣ ቤቱን እያቃጠለ፣ ከብቱን እየዘረፈ መጣ። ይህንንም የሚያደረገው ሕዝቡን አስደንግጦ አርበኞችን አንዳይደግፍ ለማድረግ መሆኑ ግልፅ ነበር። ግንደ በረትን ጨርሶ ወደ ደጋው ሲወጣ አረሁ ላይ አርበኛው

ታህሣሥ 11 ቀን 1929 ዓ.ም ገጠመው። በጠላት ላይ ጉዳት ደረሰበት። ስድስት የሲቢያ (ጡሩምቡሌ) ወታደሮች ከብዙ ባንዳዎች ጋር ተገደሉ። ብዙ ምርኮ ተገኘ። ውልጮ አፋፍ ላይ ምሽግ ለመሥራት የነበረውን ሃሳብ ትቶ ሸሸቱን ቀጠለ።

የፍቼው የጦር አዛዥ እንደ እነደጃዝማች አበራ ካሣ ይታለሉለት መስሎት መልዕክቱን አሻሯደደ። ታህሣሥ 16 ቀን በቀኛዝማች አሸኔ፣ ታህሣሥ 20 ቀን ደግሞ በአዛዥ ባህሩ እጅ ላከ። እነሱ ግን ባለማወላወል እምቢታቸውን ገለፁ። እሱም አማላጅ የላከው ጦር እያዘጋጀ ነበርና ለማጥቃት ተንቀሳቀሰ። አርበኞች በበኩላቸው ጠላት የሚገኝበትን ሁኔታ በማጥናት ሌመን ከቀኛዝማች ሣህሌ ምስጋናው ቤት ግብር ሲበላ ጥር 5 ቀን ደርሰው አደጋ በመጣል ጥቃት አደረሱበት። የተፈለገው ዋና ሰው ገደል ተንከባልሶ ቢያመልጣቸውም አስራ ሁለት መውዜር ጠመንጃ ከስምንት ሺህ ጥይት ጋር እንደዚሁም እንድ ጉራዴ ማረኩ። ይህ የአርበኞች ሥራ ከአምቢታቸው ይበልጥ አናደደው። ሴላ ጦር ሠርቶ መጣ። እነሱም እሬሬ ከተባለው ቦታ ግንባር ለግንባር ገጥመው ወግተው ድል አድርገው አባረሩት።

ጠላት እንደገና ለማጥቃት ሴላ መከራ አደረገ። አርበኞችም ያያ ተጨማ ላይ ጥር 11 ቀን ቅዳሜ ከጥዋቱ በአራት ሰዓት ገጠሙት። ጀምበር እስክትጠልቅ ድረስ ወጉት። አሥር ሰዓት ገደማ ቀኛዝማች ኃይለማርያም ማሞ የገዛ ቤታቸውን እሳት ለኩሰው ከለዎቻቸው ጋር ቦታ ይዘው ጠበቁት። ጠላት ቤቱን ያቃጠለው የእሱ ወታደር መስሎት ሲገሰግስ ደረሰ። እሳቸውም ሰወሬ ነጋሪ ሳያስተርፉ ጨረሱት። በጠላት ወገን አዝማቾች ሆነው የመጡትም ጀነራል ትራኪያ፣ ጀነራል ፍጃና ኩሶኔል ሮሰኒ ስለነበሩ የእነሱ መገደል ውርደት ሆነበት። አርበኞችም ድል አድርገው ከዚያው ሰነበቱ።

ጠላት በዚህ ቁጭት ሴላ ፈረሰኛ ጦር አመጣ። አርበኞችም በዚሁ ያያ ቀጨማ ከተባለው ቦታ ሳይነቃነቁ ጠብቀው ጥር 21 ቀን ረቡዕ ገጠሙት። አሥራ አምስት ሰው ገድለው ድል አድርገው አባረሩት።

ታህሣሥ 12 ቀን ተጀምሮ የነበረው ምክር ሲብላላ ስንብቶ ነበርና ጅሩ ላይ ቀጠለ። በስንዳንድ ሁኔታዎች ላይ ከስምምነት ተደረሰ። ዋና ዋናዎቹ ነጥቦች፣

- በቀለብና በስንቅ አርበኛው እንዳይጉዳ ማድረግ፣
- ሕዝቡን እርስበርሱ ማስማማት፣
- እንደ ልቤ ልሁን ባይን ሥርዓት ማስያዝ የሚሉ ነበሩ።

ከዚህም በስተቀር አርበኛው በየአለቃው እየተዳደረ አንዱ ሌላውን እየረዳ እንዲሠራ፣ የጦር አለቆች በበላይነት እንዲመሩ ተወሰነ። አለቆችም ተመረጡ። የተመረጡትም አለቆች ባላምባራስ /ራስ/ አበበ አረጋይና ሻለቃ /ራስ/ መሥፍን ስለሽ ነበሩ።

የወታደሩ ቀለብ ጉዳይ ከሁሉም በላይ አሳሳበ። ባላምባራስ /ራስ/ አበበ ይህንን ችግር በተመለከተ ሐሳብ አቀረቡ። ሐሳቡም የራሳቸው አባት እንደዚሁም የደጃዝማች መሸሻ ወልዴ ሀብት ለአርበኛው ይሰጥ የሚል ነበር። ሁለቱም ባለሀብቶች የኢትዮጵያ መንግሥት ባለሥልጣኖች ስለነበሩ ሐሳቡ ድጋፍ አገኘ። ሃሳቡ ተቀስቅሶ የነበረውን የውስጥ ልዩነት አቀዘቀዘው።

ከዚህ ውሳኔ ላይ ከተደረሰ በኋላ አርበኛው በደጃዝማች መሸሻ ቤት ላይ ከበባ አድርጉ ጥር 22 ለ23 ቀን 1929 ዓ.ም አጥቢያ ሌሊት ተኩስ ተሳሄደ። ደጃዝማች ጥዋት ተያዙና በጥበቃ ሥር ቆይተው ለፍርድ ሲቀርቡ፣ ለቀረበላቸው ጥያቄ ተገቢና ትክክለኛ መልስ ለመስጠታቸው የአርበኛውን ቁጣ አባባሱ። ሥራቸው ሲመረመር ጠላትን ደስ ለማሰኘት ሲሉ ዘጠኝ የሀገር ተጋዳዮች እየያዙ በገበያ ላይ መስቀላቸው በማስረጃ ተረጋገጠባቸው። ሌሎች ሃያ ዘጠኝ ተጋዳዮች ከቤታቸው ውስጥ አስረው ተገኙ። በቤታቸው ውስጥ ብዙ ወርቅና ብር፣ ከጠላት የተቀበሉት ብዙ ሣጥን አረቂ ተገኘ። በሕይወት ይኑሩ የሚል ሰው ታጣ። ይህም ሁሉ ሆኖ አርበኛው እጁን አላነሳባቸውም። ፍርድም አልፈረደባቸውም።

ደጃዝማች መሸሻ በጥበቃ ሥር እንደአሉ ልጃቸው የጣልያን ጦር ይዞ ለዕርዳታ ደረሰ። ጦሩ ከሰላሌና ከደብረ ብርሃን ነበር። ከአርበኛው ጋር ለስድስት ሰዓት የቆየ ውጊያ አካሄደ። ጠላት እንደ አሰበው ደጃዝማች መሸሻን ማስለቀቅ ሳይችል ወደየመጣበት ተመለሰ። ነገር ግን በጦርነቱ ላይ ብዙ ሰው ሞተ፣ ሌላ ብዙ ቆሰለ። ይህ ሁኔታ የአርበኛውን ቁጣ እንደገና ቀሰቀሰው። የደጃዝማቹን ሕይወት ማዳን አልተቻለም። ገና ፍርድ ሳይሰጥ ሠራዊቱ በጉራዴ በጣጥሶ ጣላቸው።

ጠላት እንደገና ሌላ ጦር አሠናድቶ ለማጥቃት መጣ። አርበኞች የካቲት 3 ቀን 1929 ዓ.ም መረሬ ከተባለው ቦታ ገጥመው ወጉት። እሱም ተዘጋጅቶ የመጣበት ጉዳይ ነበርና አርበኞቹን ለመፍጀት ከበባ አደረገ። አርበኞቹ ሦስት መቶ ስድሣ የጠላት ወታደር ገድለው ከበባውን ሰብረው በሙውጣት ከሰላሌ ወደ አዳበርጋ መሬት ሲሻገሩ፣ የጦር መሣሪያ ምርኮ መሰብሰቡ ሥራ እስከ አሥራ አምስት ቀን ዘለቀ።

የካቲት 10 ቀን ናሌ ከሚባለው ቦታ ጠላት አደጋ ጥሎ ብዙ ሰው ገደለ ብዙም ማረከ። ቢሆንም ዋናው አርበኛ ቡድን ከበባውን ሰብሮ አመለጠ። በማግሥቱ የካቲት 11 ቀን 1929 ዓ.ም ደግሞ ሌላ ጦር እንደገና መጣ። አርበኞች ሙገር በቾ ጉንጋ ከተባለው ቦታ ወግተው ድል አድርገው አባረሩት። ጠላት በዚያ አካባቢ የነበረውን አርበኛ ለመደምሰስ ጥረት በማድረግ ላይ እንደአለ በግራዚያኒ ላይ የተጣለው አደጋ በሬዲዮ ተሰማ። በድንጋጤው ጽናት የተነሣ የጀመረውን ሥራ ትቶ ከአዲስ ዓለም የመጣው የጠላት ጦር በግራር በኩል አቋርጦ ወደ ፍቼ ሲሄድ፣ ከአዲስ አበባ የመጣውም ከበቾ ውጊያ ወደ አዲስ አበባ ተመለሰ።

ቢሆንም ጠላት አርበኞችን አድኖ ለማጥፋት የያዘውን ሥራ ስለቀጠለ፣ አርበኞችም ትግላቸውን ቀጠሉ። የካቲት 24 ቀን 1929 ዓ.ም ጆኒሌ ማርያም ጦርነት ተደርጉ ከሁለቱም ወገን ብዙ ሰው ሞተ ቆሰለም።

በሌላ በኩል ደባ ላይ ሀፍሮ የነበረው የኢጣልያ ጦር የኮላሽን አምባ ለመያዝ ተንቀሳቀሰ። አርበኛው ደግሞ ይህቺን አምባ ላለማስያዝ አሰበ። ይህቺ አምባ ስሙጥር ስለሆነች የአርበኛ መያዝ ሀገሩን ተስፋ ከማስቀረጡም በላይ በዚያ አካባቢ የሚካሄደውንም የጦርነት ሚዛን ወደ ጠላት እንዲያዘነብል የሚያደርግ ነበር። ስለዚህ በራታውራሪ /ደጃዝማች/ ክብረ ሥላሴ የሚመራው አርበኛ ከየካቲት 16 ቀን 1929 ዓ.ም ጀምሮ ለስምንት መዓልትና ሌሊት ተዋጋ። አርበኛው የጠየቀው ዕርዳታ ሳይደርስለት ጠላት ተጨማሪ ጦር ስለአገኘ ጥሶ ገባ። ክላሽ ተያዘች። ከሁለቱም በኩል ብዙ ሰው አለቀ።

በቀኛዝማች ኃይለማርያም ማሞ የሚመራው አርበኛ ደግሞ መጋቢት 18 ቀን 1929 ዓ.ም ከደብረ ብርሃን የመጣውን የጠላት ጦር ደጼቱ ላይ በድንገት ገጠመው። ጠላትም ሰባት የውሃ መትረየስ ጠምዶ፣ በከራ አባ ገሙ በኩል ደግሞ አንድ ሺህ ፊረስኛ አስነስቶ ተዋጋ። ምንም ኃይሉ ከባድ ቢሆን አርበኞችን መቋቋም ስለአልቻለ ወደ መጣበት ተመለሰ። ነገር ግን ጠላት በዚህም አልበቃውም። በማግስቱ መጋቢት 19 ቀን እንደገና ገጠማቸው። ያንለትም ቢሆን አልቀናውም። ቢሆንም ሰው ስለተዳከመ አርበኞች ወደ ጠፊት ጋራ ተሻገሩ።

አርበኞች ሁሞ፣ ሞረት እንደአሉ የጣልያን ጦር መጣ። በአግር ጦር ብቻ መቋቋም እንደማይቻለው አውቆ አካባቢውን በአይሮፕላን አስደበደበ። አርበኞች እግረኛውን የጠላት ጦር መጋቢት 26 ቀን 1929 ዓ.ም የደብረ ዘይት በዓል በሚከበርበት ዕለት ገጠሙት። ጦርነቱ ከጠዋቱ ሁለት ሰዓት ጀምሮ እስከ ስምንት ሰዓት ቆየ። ጠላት የሚመረጠውን ቦታ ይዞ ነበርና ተመቸው። ብዙ አርበኞችንም አበላሸ። ድፍረት በመበዙም ምክንያት ብዙ ሰው አለቀ። የአርበኛው እንቅስቃሴ ለመድፍና ለመትረየሱ የማይሳት ዓላማ ሆነ። ጊዜው ደግሞ ፆም ስለነበር ራብና ጥማቱም የዚያኑ ያህል ጉዳው። መጋቢት 26 ቀን በእንዲህ ተውሎ በማግስቱ ደግሞ ጠላት የዶባን በር አልፎ ከዘሩ ላይ ተጠባባቂ ጦር አድርጉ ጠበቃቸው። ነገር ግን በጦርነት ጥሰውት አለፉ።

አርበኛው በዜና ማርቆስ እንዳለ ጣልያን በኮለኔል ጋሬሊ እና በሻለቃ ጀርዳም መሪነት ከአሥራ አምስት ሺህ የማያንስ ሌላ ጦር ከሰላሌና ከደብረ ብርሃን ላከ። አርበኛውም ሚያዝያ 10 ቀን 1929 ዓ.ም ደረት ለደረት ገጥሞ ተዋጋው። ጦርነቱ ቀኑን ሙሉ ውሎ እስከ ሌሊቱ አምስት ሰዓት ቆየ። በዘመንጃ ብቻ አልተወሰነም፣ በጩበጣ እና በስለት ጭምር ሆነ። በአንድ ወቅት ቅልቅሉሹ ለስለትም ሳይመች ስለቀረ በለይኑ ጭምር ከጠላት ጋር ተሞሻለቀ። ምርኮው እጅግ ብዙ ሆነ። ሁለት ትልልቅ መድፍ፣ አንድ

ፊያት ነጭ መትረየሰና ሌሎች ድግን መትረየሶች፣ ብዙ አልቤን ጠመንጃና ጥይት ተማረከ። አንድ አይሮፕላን በጥይት ተጣለ። በውስጡ የነበሩት ሰባት የጠላት ወታደሮች ከተማረኩ በኋላ አርበኞችን ተንኩሰው ኖሮ እንደ አልሆነ ሆኑ። አንድ ሻለቃና አንድ መቶ አለቃ ጣልያናውያን ከብዙ ወታደሮቻቸው ጋር ተገደሉ።

በማግስቱ ሚያዝያ 12 ቀን 1929 ዓ.ም አርበኞች ጠላትን ማጥቃት ቀጠሉ። ካቢ ጥግ የነበረውን የጠላት ጦር አበረሩ። እንደዚሁም ጉናት ከተባለው ሠርጥ ላይ አርባ ባንዶች ማረኩ። አሥራ ስድስቱ ዕለቱን ጉዳያቸው ተመርምሮ ስለተፈረደባቸው በጥይት ተደበደቡ። የፍርዱ ሥራ በማግስቱም ቀጥሎ ሌሎቹ ሁሉ በጥይት ሲደበደቡ አንድ ብቻ አመለጠ።

አዳበርጋ አቤሣ ከተባለው ቦታ ከፋ ገደ ከተባለው ቀንደኛ ባንዳ ላይ ሚያዝያ 2 ቀን 1929 ዓ.ም አርበኞች አደጋ ጥለው አምሣ የመውዜር ጠመንጃና ሁለት ፍሻሌ ሽጉጥ ማረኩ። ትንሣኤንም ከዛው ሰው ቤት ዋሉ። ይህ በእንዲህ እንደአለ በሁለት የመቶ አለቆች የሚመራው የጠላት ጦር መጣ። አርበኞችም ሚያዝያ 22 ቀን ዓሊ ዲራ ከተባለ ቦታ ገጥመው በመትረየስ በማግለብለብ ወደ ኋላው መለሱት። ከጠላት ወገን ሠላሣ ወታደሮች ሲሞቱ በአርበኞች ላይ የደረሰ ጉዳት አልነበረም።

የዚህ ጦር አመጣጥ ምክንያት አርበኛውን ስለ አስገረመውና ስለ አስገነገነው፣ ጓዝ ለመጠበቅና ደጀን ለመሆን ከኋላ ቀርቶ የነበረው አርበኛ የከፋ ገዳን ቤት ፈተሸ። የጠላት ዕርዳታ እንዲደርስለት ስለመጠየቁ ማስረጃ አልተገኘም። ሌላ አስገራሚ ነገር ግን ተገኘ። እሱም ስለሀገራቸው የመቆርቆር ስሜት ያላቸውን ሰዎች ሁሉ እየተከታተሉ በስቅላት የሞት ፍርድ ለመፈፀም የሚያስችል ሥልጣን ለከፋ ገዳና ለወርዶፋ ቆርቾ ጠላት የሰጠበት ወረቀት ከቤቱ ተገኘ። በዚህ አርበኛው ተቆጥቶ የከፋ ገዳን ቤተሰብ በሙሉ ገድሎ ቤቱን አቃጠለው።

ጠላት ሌላ ከበባ አካሄደ። ጦሩ ባንዳ ቢበዛውም በሁለት ጣልያናውያን ኮሎኔሎች ስለተመራ ቀላል አልነበረም። አርበኞችም ምንም ቀኑ ማዕዶት ቢሆንና ቀደም ብለው በአካሂዱአቸው ጦርነቶች ገና ያላገገሙ ቢሆኑ፣ አይተው ሊተውት አልፈለጉም። ሚያዝያ 23 ቀን ከጥዋቱ በአምስት ሰዓት ላይ ያያ ሐሮ ከተባለው ቦታ ገጠሙት። ጠንክረው ተዋጉ። ነገር ግን ጠላት አየለና ከመካከላቸው ገብቶ በታተናቸው።

ቢሆንም የአርበኛው ጦር ከተበታተነበት ተሰብስቦ ተማከረ። ጦሩ በአንድነት መንቀሳቀሱ ጠላትን ለማጥቃት ምቹ ሆኖ ሳለ፣ ሌሎች ችግሮች ስለ መኖራቸው በምክክሩ ወቅት ላይ ተረዱ። ከእነዚህም አንዱ የማንኛውም አካባቢ ገበሬ ብዙ ሠራዊት ለብዙ ጊዜ እየቀሰበ ለማኖር መቸገሩ ሲሆን፣ ሌላው ችግር ደግሞ ጠላት በአየለ ጊዜ ሁሉንም የመደምሰስ ዕድል ማግኘቱ ነበር። የርስበርስ አለመስማማትም አልታጣም። በእነዚህ ምክንያቶች

አርበኛው ወደ ልዩ ልዩ ቦታ እንዲከፋፈል ተወሰነ። አንድ ቡድን ወደ መርሐቤቴ ተሻገረ። ሌላው ደግሞ ወደ ግንደ በረት ሄደ።

ግንቦት 1 ቀን 1929 ዓ.ም ባንዶች ለአርዳታ የመጡ አርበኞች በመምሰል ቀርበው በድንገት አደጋ በመጣል በአርበኛው ላይ የሞትና የመቁሰል አደጋ አደረሱ። በመሆኑም ቀኛዝማች ኃይለ ማርያም ማሞ ግራ አይናቸውንና ቀኝ እጃቸውን ተመቱ። ጦርነቱን መቀጠል ስለአልተቻለ አሽከሮቻቸው ወደ መ·ገር ቆላ አውርደው ማስታመም ያዙ።

ጠላት የቀኛዝማች ኃይለማርያምን ሁኔታ በሰላሮች አማካኝነት ሰምቶ ጦር አሠናድቶ ወደዛው ዘመተ። አርበኞቹ ምክር አድርገው ከመዋጋት ይልቅ የለሰልቾቸውን ሕይወት ማዳን እንደሚብስ ስለተገነዘቡ በበቅሎ አስቀምጠው እየደገፉ ወደ ገርቢ ከዚያም ወደ አደበርጋ መዳሌ ወሰዱአቸው። ከዚያም ተበታትኖ የነበረው አርበኛ እንዲሰበሰብ ጥሪ ተላለፈና ከስምንት መቶ በላይ ሠራዊት ተሰበሰበ። እሳቸውም ማገገም ጀመሩ። የአርበኛው መንፈስም እንደገና ተጠናከረ። ቀኛዝማች ለማነጣጠር ይረዳኛል በማለት በግራ ዓይናቸው መቁሰል ቀለዱ። ነገር ግን የቀኝ እጃቸው መመታት እንደዚህ የሚያዋዛ አልነበረም።

ጠላት የኮሳሽን ምሽግ በምን ዓይነት ትግል እንደያዘ ቀደም ብለን ተመልከተናል። የዚህ አምባ መያዝ እንደተፈራው የአርበኛውን ሞገስ ቀነሰ። ኃይሉንም የሚያዳክም ሆነ። ስለዚህ አርበኛው ምሽጉን ለማስለቀቅና አካባቢውን ከጠላት ቁጥጥር ነፃ ለማድረግ አሰበ። አስቦም አልቀረ ጥር 19 ቀን 1929-ዓ.ም በምሽጉ ላይ አደጋ ጣለ። ነገር ግን መከራው የታሰበውን ውጤት ሳያስገኝ ቀረ፣ ብዙ ሰውም ተጐዳ።

ጠላት በዚሁ ወር በግንቦት 25 ቀን 1929 ዓ.ም ሚዳ ላይ ወ/ሮ ከበደች ሥዩምን ከበቡ። በመቶ አለቃ /ደጃዝማች/ ገለታ ቆርቾ የሚመራው አርበኛ ፈጥኖ በመድረስ ጋፋች ከተባለው ቦታ ከቀኑ በስድስት ሰዓት ገጠመው። ጦርነቱም እስከ አሥራ ሁለት ሰዓት ተኩል ቆየ። ብዙ ባንዳ አለቀ። በአርበኞች ላይ የደረሰው ጉዳት መጠነኛ ነበር። በዚህ ሁኔታ ወይዘሮ ከበደችን ከምርኮ ለማዳን ተቻለ። እሳቸውም ታሪኩ አበራ የተባለውን ልጃቸውን ወረግቡ ነበሩና ማጓጓዙ ቀላል አልነበረም። አርበኞች ለማጥቃት ሲቃረቡ ጠላት በአንድ ወገን ሰብሮ በመውጣት አመለጠ። አርበኞች በማግስቱም ማጥቃታቸውን ቀጥለው ቅቤና ከተባለው ቦታ ተዋጉ። በዛም ብዙ ባንዳ ሞተ። ጥቂት አርበኞች ወደቁ። ወይዘሮ ከበደችም ጠላት ለመታረቅ ያቀረበላቸውን ጥያቄ ረግጠው ከአርበኞች ጋር ሰኔ 3 ቀን ጉዞ ጀመሩ።

ይሽ በእንዲህ እንዳለ ሌላ የጠላት ጦር ቤቱንና ቤተክርስቲያኑን እያቃጠለ፣ የራያ ሠራዊት አስከትሎ ወንዱን ሕያሰለበና የሴቱን ጡት እያስቆረጠ መጣ። አርበኞችም ሊዲዎ ከተባለው ቦታ ግንቦት 25 ቀን 1929

ዓ.ም ግንባር ለግንባር ገጥመው ወጉት። በጦርነቱም ላይ አራት ከጠላት ወገን በኩል የዘመቱ ከነሰበን ጠመንጃዎቻቸው ተማረኩ። ምርኮኞቹም በጠላት ተገድደው ከመዝመት በስተቀር ሌላ በደል ፈጽመው ስለአልተገኙ መሣሪያቸውን አስረክበውና ምክር ተቀብለው በሰላም ተሰቀቁ።

በዚሁ ጊዜ የጠላት ጦር በሌላ ግንባር በባላምባራስ /ራስ/ አበባ ላይ ዘመተ። እሳቸውም እነዋሪ ላይ ገጥመው ተዋጉት። በታንክና በአይሮፕላን እየተደገፈ የሚዋጋቸውን የጠላት ጦር ስምንት ቀን ሙሉ መክተው ተዋጉት፤ ድልም አደረጉት። ከሁለቱም ወገን ብዙ ሰው አለቀ። ምንም ለጊዜው ድል አድርገው ቢመልሱት ሌላ ጦር ሠርቶ እንደገና እንደሚመጣባቸው በማወቅ ወደ መርሐ ቤቴ ተሻገሩ።

የቀኛዝማች ኃይለማርያም ማሞን መቁሰል ቀደም ብሰን ተመልክተናል። ጠላት ይህንን ተረድቶ አዲስ ጦር ሠርቶ መጣባቸው። እሳቸውም ከመሸሽ ይልቅ መዋጋት መረጡ። በአልጋ አስከ ጦርነቱ ቦታ ድረስ ውስጫኝ ብለው ግንቦት 26 ቀን 1929 ዓ.ም ዲሬ ከተባለው ቦታ ገጠሙት። ሠራዊታቸው አንድ መትረየስ አስጨብጦ አንድ ወታደር ጠባቂ ትቶላቸው ከጦርነቱ ገብቶ በኃይል ተዋጋ። ሁለት ጣልያናውያን ሻምበሎች ገድሎ፤ አንድ የወሬ ማስተላለፊያ ሬዲዮና ልዩ ልዩ የጦር መሣሪያ በብዛት ማረከ። የዚያ አካባቢ ሕዝብ አርበኝነቱን ማጠናከር የቻለው በዚህ ቀን በማረከው መሣሪያ ነው። ጠላትም በበኩሉ ብዙ ሰው ገደለ፤ አቶሰለ። አቶ ገብረፃድቅ ጀፈሌ የተባለውን አርበኛ ማረከ። ነገር ግን ሊገድለው ሲዘጋጅ አጋፋሪ /ፊታውራሪ/ ሞላልኝ ግዛው የተባሉ ጓደኛው ገስግሰው ደርሰው ሊገድለው የነበረውን ጠላት ገድለው አስለቀቁት። ጓደኛ ይሏል እንደዚህ ነው።

ወደ ዋናው ታሪክ እንመለስ ጠላት ብዛ ጦር አስከትቶ በቁርጥ በቁርጥ ከፋፍሉ በሌላው የአርበኛ ቡድን ላይ መጣበት። በሻለቃ /ራስ/ መሥፍን ስለሽ የሚመራው አርበኛ ግንቦት 25 ቀን 1929 ዓ.ም ይድና በተባለው ቦታ ገጠመው። ከቀኑ ከስድስት ሰዓት አስከ ፀሐይ ጥልቀት ወግቶ ብዙ ጣልያኖች ፈጅቶ፣ ድል መትቶ አባረረው። የንጉሠ ነገሥቱ ባለሟዋል የነበረው ቀኛዝማች ተክለ ማርቆስ ከጠላት ጦን ሆኖ ሲዋጋ ውሎ ቀስሎ እመለጠ።[2]

እዚህ ላይ አንድ የታሪክ ማስታወሻ ላክል። የአርበኞችን መልእክት ይዘው ቀጨማ ከተባለው ቦታ ተነስተው ሲጓዙ፤ ከሆለታ የዘመተ የጣልያን ጦር ግንቦት 2 ቀን ማረካቸው። በዚህ ጊዜ አጋፋሪ /ፊታውራሪ/ ሞላልኝ በጥርጣሬ በመከታተል ከቦታው ደርሰው በጠላት ላይ አደጋ በመጣል ምርኮኞቹን አስለቀቁ። በተካሄደው ውጊያ አጋፋሪ /ፊታውራሪ/ ሞላለኝ ራሳቸው ቆሰሉ። አርበኞች ጓደኞቻቸው ደርሰው የተጣጣፈ ጦርነት ተካሄደ። ጠላት ድል ሆኖ ሲሸሽ አሥራ ሁለት ወታደሮች ከነመሣሪያቸው ተማረኩ።

እንደዚሁም ሌላ አሥራ ሁለት ጣቃ ካኪ ተማረኩ። ለባንዳ መስበኪያ የተጫነ ነበር። ምርኮኞቹ መሣሪያቸውን አስረክበውና ምክር ተቀብለው ተሰቀቁ።

ጠላት ከመርሐ ቤቴ ወደ ግንደ በረት የሚሻገረውን አርበኛ ለመደምሰስ ገሠገሠ። በመቶ አለቃ /ደጃዝማች/ ገለታ ቆርቾ የሚመራው አርበኛ የጀግና የወንጭት ወንዞች ከሚገናኙበት ቦታ ሰኔ 1 ቀን 1929 ዓ.ም ደርሶ አደጋ በመጣል ወጋው። ከጠላትም ከአርበኞችም ብዙ ሰው ሞተ። በዚህ ውጊያ ላይ ብዙ አርበኞች በጠላት እጅ ቢማረኩም፤ ጠላት እነባላምባራስ /ራስ/ አበበን የመከታተልና የማጥፋት ዓላማውን ለማደናቀፍ ተቻለ።

ሰኔ 7 ቀን 1929 ዓ.ም ጠላት አርበኞችን ለማጥቃት ስለመጣ፣ አርበኞች ጸሎታ ከተባለው ቦታ ሊገጥሙት ተዘጋጁ። ነገር ግን ጠላት ሁኔታውን በመገምገም ተኩስ ሳይከፍት ወደ ኋላው ተመለሰ። ይህ ሁኔታ ከታሪክ ውስጥ የሚጠቀስበት ሌላ ምክንያት ስለለለ እንጂ የጠላትን ፍርሐት ለማሳየት ብቻ አይደለም። በዚሁ ቀን አርበኞች የሠፈሩት ወይዘሮ አየ አንበሳ ቤት ነበር። ይህቺ ሴት የጠላትን መምጣት በሰማች ጊዜ "ከወንዶቹ ቤት ሲቀመጡ ያልነካቸው አሁን የሴት ቤት ነው ብሎ አገሩን ለመዝረፍ ነው የመጡት" ብላ ለማንያ አንድ የታጠቀ ወታደር ይዛ ከሞቀ ቤትዋ በመውጣት ከአርበኞቹ ጋር ተቀላቀለች።

ከመርሐቤቴ ወደ ግንደ በረት ከዚያም ወደ ወለጋ ሊሄድ የአሰበው የአርበኞች ቡድን፤ ሰላሌ ውስጥ በየደረሰበት ግጭትና ጦርነት አጋጠመው። ሰኔ 9 ቀን 1929 ዓ.ም ጀርሶ በር ላይ፣ ሰኔ 10 ቀን ደግሞ ወቦ ከተባለው ቦታ፤ እንደዚሁም በማግስቱ ሰኔ 11 ቀን 1929 ዓ.ም በቀንደኛ ባንዳ ቤት ላይ አደጋ ተጥሎ ከነልጆቹ ተያዘ። ከተለያዩ አርበኞች ላይ እየታለለ የገፈፈው የመውዜር ጠመንጃ፣ ሦስት ቱሩቅ የሚያሳዩ መነጽሮችና ሁለት አውቶማቲክ ጠመንጃዎች ተማረኩ። በርካታ አርበኞች ስለነበሩ በቀኛዝማች ኃይለማርያም ማሞ የሚመራው ጦር ተጠናከረ። ዓለማየሁ ካሣ የተባለውን አርበኛ ሰላሌ ላይ ገድሎ ጠመንጃውን ቀምቶ ይኖር የነበረው ደምሴ መርሻ የተባለው ባንዳ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ በተተከለበት ጉባኤ ጥፋቱ ስለተረጋገጠበት በፍርድ ተገደለ። እነ ወርዶፋ ቆርቾ ግን ጠመንጃ ከመንጠቅ በስተቀር ሰው ሰለሰለገደሉ አልተገደሉም።

በቾ ጉረንዳ በተባለው ቦታ ሠፍሮ የነበረውን የጠላት ጦር አርበኞች ሰኔ 24 ቀን 1929 ዓ.ም አደጋ ጣሉበት። በጦርነቱ ሁለት ሻምበሎች፣ ሁለት የመቶ አለቆች፣ አንድ ሃምሳ አለቃና አንድ ወታደር ጣልያናውያን ተገደሉ፤ ብዙ ባንዳ ሞተ። ነገር ግን የባንዳው ሞት ከቁጥር አልገባም። ባንዳዎችም በፋንታቸው በሚያውቁት ቦታ ከጀርባ ዞረው በአርበኛው ላይ መጠነኛ ጉዳት አደረሱበት።

ጣልያን በዚህ ወራት ዘዴ አድርጐ የያዘው ወንዱን ብልቱን የማሰለብና ሴቷን ጡቷን ማስቆረጥ ነበር። ለዚሁ ብሎ ከራያና አዘቦ ብዙ

ባንዳ መልምሎ ጨቤ እያስታጠቀ፣ ጠመንጃ ከያዘው ወታደር ጎላ አስልፎ ነበር። የዚህ ቡድን ተግባር ሰላማዊውን ሰው ከላይ እንደተገለጸው በመስለብ፣ አብያተ ክርስቲያናትን በማቃጠል እምነቱን መደምሰስ ነበር። ሁኔታው እጅግ መራር ሆነ። እንደዚህ ያለ አልቂት ሲካሄድ እያዩ ዝም ማለት አልተቻላቸውምና፣ የመርሐቤቴ አርበኞች ሰኔ 11 ቀን 1929 ዓ.ም ግንባር ገጠሙት። የዚህ የሰለባና የጡት ቆረጣ ፕሮግራም ኃላፊ የነበረው ሼህ ሡልጣን፣ ኩሬ ውሃ በተባለው ቦታ ተማረከ። ያካሄደው የጭካኔ ሥራ ከባድ ስለነበር ፍርዱ ቀላል ሆነ። አሳስራለሁ፣ ዋጋውን እሰቱን አገኘ፣ ተገደለ። ዘርፎት የነበረውም ንዋየ ቅድሳት ለየባለመብቱ ቤተክርስቲያን ተመለሰ።

የሸዋው ባንዳ ክልቡ እንዲዋጋለት ሲል ጣልያን ፊታውራሪ አያሌውን ደጃዝማች ብሎ ሾመው። አያሌውም ሺህ ያህል ሰው ሰበሰበለት፣ በርትቶም ተዋጋለት። አርበኛው ደግሞ ከዚህ ከሃዲ የሚገላገልበትን መንገድ ፈለገ። ከቺሣ ከተባለው ቦታ ሰኔ 19 ቀን 1929 ዓ.ም ጦርነት ገጠመው። አያሌው ይዞት የመጣውን አንድ ሺህ ባንዳ ይዞ ተዋጋ። ነገር ግን ሊያጠቃም ሊያመልጥም አልቻለም። ተገድሎ፣ ተቆርጦ በገበያ ላይ ተሰቀለ። ብዙ ባንዳም ሞተ፣ ቆሰለ። የተረፈውም ተበተነ። ከአርበኞችም በኩል ጥቂት ሰው ሞተ፣ ቆሰለ።

ዋናው የጣልያኖች መሣሪያ ራስ ኃይሉ ነበረ። እርሱም መጠሪያውን ወልዱ ለንጉሥ ተክለ ሃይማኖት አሰኝቶ ነበር። የነጩ መኮንንና ወታደሮች ከኋላ ደጀን ሆነው፣ እርሱን ከፊት አስቀድመው ከጦሯም ዓባይን ተሻግረው መጡ። ምንም ሠራዊታቸው ቢበዛ መመከት አልቻሉም። ሙገር ላይ ግጥሚያ ተደርጐ አርበኛው አሸነፈ። በዚሁ ጊዜ በባላምባራስ /ራስ/ አበበ የሚመራው ቡድን ሜታ ላይ ተዋግቶ ተመሳሳይ ድል አገኘ።[3]

ጳጉሜን 3 ቀን 1929 ዓ.ም ጠላት ሌላ አዲስ ጦር አሠናድቶ መጣ። የነጭ ወታደር በብዛት ያለበት ነበር። የነጭ ወታደር የበዛው የባንዳ መግተልተል ምንም እንደማይፈይድ በጠላት ዘንድ እየታወቀ በመሄዱ ሳይሆን አልቀረም። አርበኛው ይህንን ጦር ጅሩ ኩሣያ ከተባለው ቦታ ገጠመው። ጠላትም እንደልማዱ ሰባት አይሮፕላን አስነሰቶ አስደበደበው። ነገር ግን አርበኛው አልተበገረለትም። አሳሩን አሳይቶ አባረረው። እሱም ሬሣና ዕቃውን እያዝረከረከ ወደ ፍቼ ሄደ።

መስከረም 4 ቀን 1930 ዓ.ም የፍቼው የጠላት ጦር የደብረ ብርሃኑን ጨምሮ መጣ። አርበኞቹም ቦታ ቦታ ይዘው አንጥፈው በመጠበቅ አደጋ ጣሉበት። የደገምን ተራራ ተተግነው ጉዳት አደረሱበት። የሌመንን ወንዝ እንዳይሻገር ከለከሉት። እሱም አመጣጡ ሳያዩት አደጋ ጥሎ ለማጥቃት እንጂ ለመዋጋት አልነበረምና ሸሽቶ ወደ መጣበት ተመለሰ።

ጠላት ሌሊቱን ሲገሠግስ አድሮ መስከረም 10 ቀን ጥዋት ሚልኪ ከተባለው ቦታ ደረሰ። አሁንም የጠላት ሀሳብ በአርበኞች ላይ አደጋ ለመጣል እንጂ በእሱ በራሱ ላይ አደጋ እንደሚጣልበት አልጠረጠረም ነበርና ጥቂት ተኩስ እንደተደረገ ጥሎ ሄደ። መስከረም 11 ቀን ጉሓ ጽዮን ላይ መሽጐ ተቀምጦ የነበረው የጠላት ጦር አርበኞችን ለማጥቃት ወጣ። እነሱም ገጠሙት። የፍቼው ጦር እስኪደርስለት ወደ ኋላው ተመልሶ ሠፈረ።

የጠላት ሃሳብ በዚያ አካባቢ የነበረውን አርበኛ ለእንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለመደምሰስ ነበርና መልሶ አጠቃ። መስከረም 12 ቀን 1930 ዓ.ም የፍቼና የደብረ ብርሃን የጠላት ጦር ተባብሮ በእነ ባላምባራስ /ራስ/ አበበ ላይ ወረጃርሶ ያያ ያበና በተባለው ቦታ አደጋ ጣለባቸው። ቀኛዝማች ባንተ ዳኘ እና 26 አርበኞች ሞቱ፣ ሌሎችም ቆሰሉ። በዚህ ቀን ጉልጂ አፋፍ ላይ ሌላ ጦርነት ተካሂዶ ጥቂት አርበኞች ቆሰሉ፣ ሌሎችም ተማረኩ።

መስከረም 14 ቀን 1930 ዓ.ም ጠላት ዜጋ ወደም በተባለው ቦታ እንደአለ በአርበኛው ላይ አደጋ ጣለ። ከበባም አድርጐ ስለነበር ለምርኮ አቃረበው። ሦስቱ ጀግኖች የክቡን ሰንሰለት ለመስበር በቁርጠኝነት ተነሱ። በጀግንነት ተዋግተው እንደአሰቡት አደረጉ። የክበቡን ሰንሰለት ሰብረው ወገኖቻቸውን ከእልቂትና ከምርኮ አዳኑ። እነዚህም ጀግኖች ባሻ /ደጃዝማች/ ተሰማ አርጌጤ፣ ባላምባራስ /ፊታውራሪ/ ተሸገር ግዛውና ወንድማቸው አጋፋሪ /ፊታውራሪ/ ሞላልኝ ግዛው ነበሩ። በእኔ አስተያዬት፣ ምስጋና ይገባቸዋል።

መስከረም 16 ቀን 1930 ዓ.ም ይህ የአርበኛ ቡድን ወደ ካቢ ለመውጣት ጉዞ ጀመረ። ውላ ገባን ከተባለው ቦታ እንደሠፈረ፣ የተኩስ ድምጽ ተሰማ። ጠላትም ኃይሉን አጠናክሮ ቢሻ ሚኬ የተባሉትን ታዋቂ አርበኛ ገደለ።

ለማስታወሻነቱ ያህል በዚህ ቀን ስለተፈፀሙ አስደናቂ ነገሮች እንድጠቅስ ይፈቀድልኝ። የጨበጣ ውጊያ ሲካሄድ አጋፋሪ /ፊታውራሪ/ ሞላልኝ አሥር የጠላት ወታደሮች በአንድ ጉርሻ መትረየስ ፈጁ። ከወደቁት የጠላት ወታደሮች አንዱ መትረየስ የያዘ ነበር። መትረየሱን ለማንሳት ልጅ የማነ ብርሃን አባከራን ቢሄድ ወንድሙ ሆኖ አገኘው። ሁኔታው ሳያስቅቀው አልቀረም። ባላምባራስ /ራስ/ አበበ ደግሞ የቢሻ ሚኬን ሞት እንደ ስሙ ስለ ተናደዱ፣ በሩጫ ከጠላት ጦር ውስጥ ገብተው ወበሪ ከተባለው ቦታ አንድ ጣልያናዊ መቶ አለቃ እና ስድስት ባንዶች ገድለው በገላጋይ ብዛት ተመለሱ።

የዕለቱ ጦርነት እንዲህ ትርምስና ግርግር የበዛበት ነበር። አርበኛው ጠላትን ማባረሩን ቀጥሎ እስከ ወበሪ ድረስ አሳደደው። ከጠላት ወገን በዚህ ቀን ጦርነት ሁለት መቶ አሥር ወታደሮች ተገደሉ። ውጊያው እንደ ኳስ ቅብብሎሽ ሆኖ ነበረና የጠላት ጦር በካራ አባገመ በኩል መጣ። በዚያ የነበረው አርበኛ በሚያስደንቅ የጦር ሥልት ወግቶ አባረረው።

በዋዩ አካባቢ የነበረውን አርበኛ ከጥቃት ለማዳን ቀኛዝማች ቁምቢ ከምሴ የተባለውን የባንዶች መሪ ማስታገስ አስፈለገ። ይህ ሰው ከአርበኞች ጋር ሊሠራ ከማለ በኋላ ከድቶ፣ በዘወርዋራ መንገድ ብዙ አርበኞችን ያስፈጀ ነበር። መስከረም 18 ቀን 1930 ዓ.ም ተዘመተበት። እሱም ሞተ፤ ቤቱም ተቃጠለ። አሥር ያህል ጠመንጃና ሁለት በቅሎች እንደዚሁም በአንድ ቤት ሙሉ የተደረደረ ሣሙና ተገኘ። የሣሙናው ክምር እሱነቱን እንዲያፀዳለት ሳይሆን፣ ወንጮቹን ላስጠፋበት የተሠጠው ሽልማቱ መሆኑ ነው።

የአርበኛው ቡድን ጥቂት ዕረፍት ከአደረገ በኋላ መስከረም 24 ቀን ከዋዩ ወደ ታላቅ አምባ ሄደ። መስከረም 26 ቀን 1930 ዓ.ም አንድ ቡድን እስከ ደብረ ብርሃን ጥግ ተጠግቶ የጠላትን መተላለፊያ እንዲያጠና ተላከ። ቡድኑ ተልእኮውን ከአከናወነ በኋላ፣ ከነጋድራስ ቂርቆስ ቤት ሠላሣ አፈንስት መውዜር ከእነ ጥይቶቻቸው፣ እንዲሁም ሌሎችም ትጥቆች ከተቀበሩበት አውጥቶ ተመለሰ። ይህም ጀሌዎችን ለማስታጠቅ ረዳ።

መስከረም 27 ቀን አርበኛው ሳይቆይ፣ ጊዜውን (በማለዳ) ወደ ደንገዜ በማምራት የመራር ውሃን ወንዝ ተሻገረ። ቀደም ብሎ፣ ታህሳስ 12 ቀን 1929 ዓ.ም ጅራ በምክር በተወሰነው መሠረት መንገቲ ገባ።

ጥቅምት 1 ቀን 1930 ዓ.ም ደራ ላይ መሽጉ ተቀምጦ ለነበረው የጠላት ጦር ስንቅና መሣሪያ ለማቀበል መጣ። ይህንን፣ ከወገኖቹ ይልቅ ጣልያንን ሲረዳ የተንቀሳቀሰውን የጠላት ባንዳ፣ አርበኛው ባሶ ከተባለው ወንዝ ላይ በጥይት ፈጀው። ብዙ ባንዳም ገደል እየገባ የሞተ ሲሆን፣ ብዙ ስንቅና አምስት ምንሽር ተማረከ።

አርበኞች ሚዳ ወረዳ፣ ደንገሬ ከተባለው ቦታ መሽጉ ተቀምጦ የነበረውን ጠላት ለማጥቃት አሰቡ። በህዳር 1930 ዓ.ም አደጋ ጥለው ሙሉ ቀን ውጉት። ታህሣስ 10 ቀን 1930 ዓ.ም ደግሞ ሻለቃ ከስቲላ በሚባለው አዛዥነት የመጣባቸውን የጠላት ጦር ከሌሊቱ 10:00 ሰዓት ደፈጣ አድርገው በመውጋት፣ ጠዋት ሲነጋ ወደመጣበት እንዲመለስ አደረጉ።

ጥር 19 ቀን 1930 ዓ.ም ግዛው ጭንቅሉ የተባለው ባንዳ ተገደለ። አርሱም የአርበኞችን ምሥጢር በስለላ እያጣራ ለጠላት በመንገር ብዙ ጉዳት ያደረሰ ነበር። አብረውት የነበሩት ባንዶችም ተማረከ። አርበኛው ግን ጉዳት አላደረሰባቸውም።

በዚህ ጊዜ ወረይሉና ሚዳ የነበረው የጠላት ጦር መርሐቤቴ ለነበረው ወገኑ መሣሪያና ስንቅ ለማቀበል ተንቀሳቀሰ። አርበኞች አካሄዱን በማጥናት ወንጭት ወንዝ ላይ ገጥመው ለቁጥር ያታከተ ባንዳ ፈጁበት። ነጭ ግን ደጀን ስለነበረ ሊያገኙት አልቻሉም። ስለዚህም ባንዳውን ተገን በማድረግ ሸሽቶ ሚዳ ምሽግ ገባ። የተማረከው የጦር መሣሪያ እጅግ ብዙ ነበር። ባላገሩ ጭምር ተከፋፈለው፣ ሕዝብ በሙሉ ባለ መሣሪያ ሆነ። ይህም የአርበኞችን ክንድ አጠነከረ። ይህንን ጥቃት ለመበቀል ፈጥራ ላይ የነበረው የጠላት ጦር

ተንቀሳቀሰ። ሆኖም አርበኛው ግንባር ለግንባር ገጥሞ አሳሩን አብልቶ መለሰው።

ጠላት የማጥቃት ሥራውን ለመቀጠል እንደገና ተንቀሳቀሰ። አርበኞችም ደሃሀላ ከተባለው ቦታ ወጉት። ጦሩን እየመራ የመጣውን ሀብታሙ የተባለውን ባንዳ ማረኩት። እሱም ሳያንገራግር ተማረከ። የመጣው ጦር በያለበት ፈረጠጠ። ብዙ የእጅ ቦምብና መሣሪያ ተማረከ። ነገር ግን በሀብታሙ ላይ አርበኛው አንዳች ጉዳት አላደረሰበትም። ለአመክሮ በጥበቃ ላይ እንዳለ ሌላ ጦርነት ሲያጋጥም አምልጦ ከጠላት ገባ። ጦር በመጣ ቁጥር ለጠላት ቀዳሚ በመሆን ሲያስቸግር ቆየ። ከአለመፀፀቱም ይልቅ የሚገርመው ግን፣ ነፃነት ከተመለሰም በኋላ በጦር ሠራዊት ባልደረብነት ሊቀጠር መቻሉ ነው።

በክረምቱ ወራት ወንጭትና ገሾማ የተባሉት ወንዞች ሞልተው ሰው በማያሻግሩበት ጊዜ፣ ደንገሬ ከተባለው ቦታ መሽጉ ተቀምጦ የነበረውን የጠላት ጦር አርበኞች ከበቡት። በነሐሴ ወር 1930 ዓ.ም የተፈጠረበትን ቀን አስኪረግም ድረስ አስጨንቀው ወጉት። ይህንን ቂም ለመበቀል ጠላት ወረጎ በተባለው ቦታ በነበረው በአርበኞች ቡድን ላይ ነሐሴ 1 ቀን 1930 ዓ.ም ከንጋቱ 11:00 ሰዓት አደጋ ጣለ። አደጋ የተጣለበት ቡድን ራሱን ለማዳን በርትቶ ተከላከለ። አገሪት በተባለው ቦታ የነበረው ሌላው የአርበኛ ቡድን ፈጥኖ በመድረስ እዳነው። በአጥቂው የጠላት ጦርና በረዳቱ መካከል ጣልቃ ገብቶ በማጥቃት፣ ረዳቱን ጦር ወደመጣበት በመመለስ አስለቀቀው።

ሌላው የአርበኛ ቡድን ደግሞ ነሐሴ 1 ቀን 1931 ዓ.ም ፈጥራ ላይ የነበረውን ምሽግ አልፎ ቡዮና እረመሽት ከሚባለው ቦታ የጠላትን ወታደሮች ገድሎ፣ የተረፉትን በማባረር አካባቢውን ከጠላት ነፃ አደረገ።

በመርሃቤቴ አውራጃ ወረሞ በተባለ ቦታ በነበረ ደምሴ ስሜ በተባለ የባንዶች መሪ ላይ እርምጃ መውሰድ አስፈለገ። እርምጃ እንዲወሰድ ያስፈለገው የመርሃ ቤቴንና የሚዳን ሕዝብ በሙሉ እየዘረፈ፣ ለጠላት መረ በመሆን በአርበኞች ላይ ጉዳት እያደረሰ ለለአስቸገረ ነበር። እሱም ጥፋቱን ተረድቶት ከሕዝብ ተለይቶ ምሽግ ሠርቶ ይቀመጥ ነበር። መስከረም 3 ቀን 1931 ዓ.ም ከንጋቱ 12:00 ሰዓት ላይ አደጋ ተጣለበት። እሱም የቻለውን ያህል ተከላከለ አለውጤት የዘመን መለወጫ ዕለት ተገደለ። ከወረይሉ የመጣለትም የጠላት ጦር አሣሩን አይቶ ተመለሰ። ብዙ መሣሪያም በአርበኞች ተማረከ።

የመረሃቤቴ አርበኞች ክረምቱ ሳይወጣ፣ የወንዞቹ ውሃ ሳይጐድልና መራቱ ሳይደርቅ፣ ሚዳ መራኛ ከተባለው ቦታ መሽጉ ተቀምጦ የነበረውን ጠላት ለማጥቃት አሰቡ። ዓላማቸው ምሽጉን ሰብረው ለማለቀቅ ነበር። በመስከረም ወር ከንጋቱ በ11:00 ሰዓት የማጥቃት ተግባራቸውን ቀጠሉ። ጠላትም አጥብቆ ተከላከለ። ሊመልሷቸው እንደአልቻለ ሲረዳ በአይሮፕላን

አስደበደበ። እነሱ ደግሞ ወደኋላ አፈግፍገው ቦታ ይዘው ቆዩ። ከዚያም አይሮፕላኑ ሲመሰስ ወደቦታቸው ሄዱ።

በዚሁ ዓመት ደራ ወረዳ፣ ሀሮ ቡተባሰው ቦታ መሽጉ ተቀምጦ የነበረውን ጠላት ደጋግመው በመውጋት አብርረው፣ ጉንዶ መስቀል በተባለው ቦታ መሽጉ ከነበረው ጋር አቀላቅለውታል።

የመርሃቤቴ አርበኞች ከባላምባራስ /ራስ/ አበበ ጋር ለመመካከር ከመርሃ ቤቱ ተንቀሳቀሱ። ጥቅምት 27 ቀን 1931 ዓ.ም ጭምብራ ላይ ተገናኙተው ተነጋገሩ። ዋናው ሐሳብ አርበኞች በያሉበት ሆነው ጠላትን በተቀነባበረ ሁኔታ ለመውጋት፣ አርስበርሳቸው ለመረዳዳት የሚችሉበትን መንገድ መቀየስ ነበር። ይህ ምክር መልካም ውጤት አስገኝቶአል።

ጠላት በበኩሉ በዚህ አጋጣሚ በመጠቀም ቀደም ብሎው አስለቅቀውት የነበረውን የኮላሽ አምባ መልሶ ለመያዝ ሞክረ። አርበኞቹም ጠንክረው ተከላከሉ። ነገር ግን ሠራዊታቸው በከፊል እንጂ ሙሉ በሙሉ አልተከታተላቸውም ነበርና ጠላትን መመለስ አልቻሉም። እንደ አሰበው የኮላሽን አምባ መልሶ ያዘ። ሌላው የአርበኛ ቡድን ደግሞ ጥቅምት 27 ቀን 1931 ዓ.ም ከጠላት ጋር መጠነኛ ውጊያ አካሄደ።

ጠላት አርበኞችን ለማደን ተንቀሳቀሰ። ባላገሮቹ ሁኔታውን ነግረው አስጠነቀቁ። አርበኞችም ላምዋሽ ከተባለው ቦታ ጥቅምት 19 ቀን 1931 ዓ.ም ገጠሙት። ውጊያው ከቀኑ ስድስት ሰዓት ጀምሮ እስከ አሥር ሰዓት ቆየ። በዚህ ጊዜ ብዙ የጠላት ወታደር ወደቀ። አዝማቹ ጣልያናዊ መኮንንም ቆሰለ። ተሸክመውት ሲሸሹ መኮንኑን ለመንጠቅ ቡተደረገው ሙከራ ውጊያው ቀጥሎ፣ ጠላት ጋሬት የተባለውን ምሽግ ለቆ ዞማ ምሽግ ከሌሊቱ በአምስት ሰዓት ባሳር ገባ። የአልቤንና የምንሸር ጠመንጃ ቡበዛት ተማረከ።

ጠላት አርበኞችን ለማጥፋት በአደረገው ሙከራ ታህሣሥ 18 ቀን 1931 ዓ.ም በልበሊት ላይ ጦርነት ተካሂዶ ብዙ አርበኞች ሞቱ። ጠላት በዚህ በአገኘው ድል ተደፋፍሮ በአራት ማዕዘን ከበባ አደረገ። ከበባውም በበልበሊት፣ በሰሌ፣ በመርሐ ቤቴ ምዕራብና በፌጥራ ነበር። ጥቂት ሰው ቢሞትና ቢቆስልባቸውም አርበኞቹ ከበባውን ሰብረው ወጡ። ከበባውን ለመስበር የቻሉትም በረድፍ በረድፍ ሆነው በመዋጋትና ሰብሮ የወጣው ገና ያልወጣውን ለማስለቀቅ የሚያስችል የጀርባ ውጊያ በማካሄዱ ነው። እንደዚሁም ለእርዳታ የመጣው የጠላት ጦር ያልፍበት የነበረውን ጫካ በእሳት በማቃጠል እርስበርሱ እንዳይረዳዳ በማድረግና መሪውን በመግደል ነበር።

በሚያዝያ ወር 1931 ዓ.ም ጠላት እረመሽት ከተባለው ቦታ የነበረውን አርበኛ ለማጥቃት ሙከራ አደረገ። አርበኞቹ አጥብቀው ተከላከሉ፤ የእርዳታ ጥሪም አስተላለፉ። ቀደም ብሎ በተደረገው ስምምነት መሠረት

ጭምብሬ፤ ዘሪት ከተባሉት ቦታዎች አርበኞች ፈጥነው በመድረስ ጠላትን ከጀርባው እየወጉ የተከበበውን አርበኛ አዳኑ።

ሰኔ 26 ቀን 1931 ዓ.ም ጠላት መርሐቤቴ ቁምአምባ ከተባለው ቦታ መጣ። አርበኞቹም ግንባር ለግንባር ገጠሙት። ወጊያው ከሌሊቱ 11 ሰዓት ጀምሮ እስከ ቀኑ 9 ሰዓት ድረስ ቆየ። ሁለት ጣልያናውያን የጦር መኮንኖች ቆስለው በቃሬዛ ተወሰዱ። ሃምሣ ሦስት ባንዳ ሞተ፤ ሌላ አርባ ሦስት ባንዳ ቆሰለ። አርባ ሰባት ጠመንጃ ተነሳ። ጥቂት አርበኞች ሞቱ፤ ሌሎችም ቆሰሉ።

የ1931 ዓ.ም ዘመን በዚህ ዓይነት ተፈጸሞ የ1932 ዓ.ም ትግል ቀጠለ። ጦርነቱ ውሎም ላያድር በመከሸረም ወር ተጀመረ። ከፈጥራ ምሽግ ውስጥ የነበረው የጠላት ጦር ከምሽጉ ወጥቶ ወደ እንሣሮ ይጓዝ በነበረው አርበኛ ላይ ተኩስ ከፈተ። አርበኛውም መክቶ ግንባር ለግንባር ገጠመው፤ ተጨፋጨፉ። ብዙ የጠላት ወታደር ወደቀ። የተረፈው ከወጣበት ምሽግ ተመልሶ ተከተተ።

ከአዲስ አበባ ዕለት ዕለት የሚደርሰው ትዕዛዝ ጤና ነስቶት ነበርና፤ ጠላት አርበኞች የሄዱበትን ዱካ እየተከታተለ አካባቢውን ያስስ ጀመር። ከአርበኝነት ሥልት አንዱ ጠላትን ከቦታ ቦታ በማዘር ማድከም ስለነበር ብዙ አንከራተቱት። ሞረት ቆላ፣ ዝግብ ከሚባለው በረሃ ላይ ሲደርስ ጥቅምት 1 ቀን 1932 ዓ.ም ገጠሙት። የጠላት ጦር ሥፍር ቁጥር አልነበረውም፤ የሚመራውም በአንድ ጄነራል ነበር። በምብና ጥይት እንደ ነጐድጓድ ወረደ። በመንከራተት የደከመው የጠላት ወታደር ሬሣ ተረፈረፈ፤ ብዙ አርበኞችም ወደቁ። ይህኛው ጦር ሲገባደድ ሌላ አዲስ የጠላት ጦር ደረሰ። እሱንም ደርሶ መዋጋት ሞኝነት ስለሆነ፤ አርበኞቹ መንገድ በመስበር ወደ መርሐቤቴ አፋፍ ወጡ።

ጠላት የማጥቃት ዘመቻውን ቀጠለ። ከምብ በምትባል የእንሣሮ ወረዳ፤ መጪ ከሚባለው ቦታ ጥቅምት 10 ቀን 1932 ዓ.ም ብዙ አርበኞች በጀግንነት እየተዋጉ ወደቁ። የጠላትም ጦር በአጋጠመው ዕድል ተጠቅሞ በርትቶ ተዋጋ፤ ከበባም አደረገ። ይህ ቀን በዚያ አካባቢ ለነበሩ አርበኞች ክፉ ነበር። በአቅማቸው ሙሉ ተከላከሉ። አጥብቀው በመከላከላቸውም ከማለቅና ከመማረክ ዳኑ። ነገር ግን ከግንቦት 10 ቀን 1928 ዓ.ም ጀምረው ጠላትን ሲያርበደብዱት የቆዩት ጀግናው ልጅ ሥዩም ገብረሕይወት ሞቱ። አሽከሮቻቸውም ሬሣቸውንና መሣሪያቸውን ለጠላት ሳያስነኩ ሞረት፤ ሰገድ ሚካኤል ቤተክርስቲያን ወስደው በክብር ቀበሩአቸው።[4]

በወቅቱ ከጉጃም በኩል የሚነፍሰው ወሬ ለአርበኛው የልብ ልብ ይሰጠው ጀመር። ክረምቱ በአርበኛው ላይ የኑሮ ችግር እንጂ የጠላት ጥቃት አላመጣበትም። ለአዲስ ትግል መዘጋጃ ሆነ። የ1933 ዓ.ም የመጀመሪያዎቹ ሦስት ወራትም በዚህ አካባቢ ለነበረው አርበኛ ብዙ ፈተና አላስከተለበትም።

ሀዳር 9 ቀን 1933 ዓ.ም ለሸዋ ሕዝብ የተነገረው አዋጅ ከጉጃም ተላከ።[5] ይህም የንጉሠ ነገሥቱን መምጣት አበሠረ።

በአላ አካባቢ የማሚጠጫው፣ ዋናው ጦርነት በታህሣሥ ወር 1933 ዓ.ም መርሐቤቴ፣ አደሬ ከተባለው ቦታ ላይ ተካሄደ። እኩሉ አርበኛ በአደሬ፣ እኩሉ ደግሞ በስንደዶ በኩል ሆኖ ጠላቱን ቀጠቀጠው። ጦርነቱ ሁለት መዓልት ወሰደ። ጣልያን አርበኞቹን ማሸነፍ ቢያቅተው በአንድ በኩል ጦር ልኮ ጉበል ከተባለው በረሃ የነበረውን ሴትና ልጅ፣ ጓዝ አስማረከ። አርበኞቹ ከዚያም ገስግሰው ደርሰው ተዋጉ። ጠላትም ወደኋላው ተመለሰ። ነገር ግን ምርኮኞቹን ማስለቀቅ አልተቻለም።

ከጉጃም የሸሸው እስከ ስድሣ ሺህ የሚገመት የጣልያን ጦር የዓባይን ወንዝ ተሻግሮ ጎሐ ጽዮንን አልፎ ገርባ ጉራቻ ሲደርስ፣ ከሁለት እንደተከፈለ እና አንዱ ወደ ደቡብ ተቀልብሶ ወደ አዲስ ዓለም እንደሄደ፣ ሌላው ደግሞ ወደ ሰሜን ታጥፎ ወደ መርሐቤቴ እንደገባ ቀደም ብለን ተመልክተናል። በመሆኑም በእነሱ ላይ የመጣውን የጠላት ጦር ማስተናገድ የመርሐቤቴ አርበኞች ዕድል ፈንታ ሆነ።

ወደ ሰሜን የወጣው የጠላት ጦር ሐሳብ ገቦማ የተባለውን ወንዝ ተሻግሮ በደራ፣ ካራምኾግ አደርጉ ወደ ወረይሉ ተሻግሮ ደሴ ለመግባት ነበር። ደሴ መያዙን ሲረዳ ደግሞ እኩሉ ወደ ጉንደር፣ ገሚሱ ወደ አምባላጌ ጉዞውን ቀጠለ። ኢትዮጵያን ለመውረር የመጣበትን አቅጣጫ ይዞ ወደ ሰሜን አቀና። ይህ እንደታወቀ ከንጉሠ ነገሥቱ ለአርበኛው ትዕዛዝ ተላለፈ።

ይህንን የአርበኞች ጥቃት ለማስታገስ ጠላት መጋቢት 23 ቀን 1933 ዓ.ም እረመሽት በተባለው ቦታ በአርበኞች ላይ አደጋ ጣለ። አርበኞችም ሸሽቶ ከምሽጉ እስኪገባ ድረስ እያባረሩ ወጉት። በዚሁ በመጋቢት ወር 1933 ዓ.ም የስቅለት ዕለት አርበኞች መራኛ የተባለውን ምሽግ ለማስለቀቅ ጥቃት አካሄዱ። ውጊያው የተካሄደው ቀደም ብሎ ለቅቆት ወደ ወረይሉ ሄዶ የነበረው የጠላት ጦር ተመልሶ መጥቶ ምሽጉን እንደገና በመያዙ ነበር። አርበኞቹ በርትተው በመዋጋት ድል አድርገው መልሰው አባረሩት።

የንጉሠ ነገሥቱ ጉጃም መግባት እንደታወቀ፣ ባንዳው ከጠላት እየከዳ ከአርበኛው ጋር ተቀላቀለ። ብዙ የቀድሞ ባንዶች አሁን ደግሞ ከአርበኞች ጉን በመቆም፣ ጌታቸውን ጣልያንን መልሰው በመውጋት ደማቸውን ለሀገራቸው ለማፍሰስ ተሠለፉ። በሁለት ወገን ሞቱ ማለት ነው።

ምዕራፍ ሃያ ሰባት
የመገናኛ መሥመርን መቆጣጠር

የጣልያንን የጦር አንቅስቃሴ መጉዳት ከሚቻልበት መንገድ አንዱ ከአዲስ አበባ እስከ ጂቡቲ የተዘረጋውን የባቡር ሐዲድ መሥበር ሆነ። ስለዚህ ከአዲስ አበባ ከተማ ወጥተው በአካባቢው የተሰማሩ፣ የቴክኒክ እውቀት የነበራቸው ወጣቶች በዚህ ሥራ ላይ ተሰለፉ። ሕዝብ ተባበራቸው፣ መጠለያ ሰጣቸው። እንግዳ የሆኑበትን አንዳንድ የቴክኒክ ሥልቶች ከእነሱ እያጠና እኩም ራሱ የበኩሉን አደረገ።

ቡድኑ የባቡር ሐዲዱን በመንቀልና የስልክ መሥመሩን በመቁረጥ የጥቃት ሥራውን ጀመረ። በሥራው ገበሬውም ተባበረ። የራሱን ዘዴ ጨመረበት። ከሰዋራ ቦታ ታሳሳቅ ድንጋይ በሐዲድ ላይ በመጋረጥ፣ የስልኩን ሽቦ በጥሶ ከሰል በተቀባ ገመድ በማሠር፣ ገበሬው ሊያደርሰው የሚችለው ጥቃት ሆኖ ተገኘ። ጥቂት ሽፍቶች በአካባቢው እንዲታዩ በማድረግ በእነሱ እያመካኘ ውስጥ ውስጡን ሥራውን ቀጠለ።

በዚህ ዓይነት ከአዲስ አበባ ወጥቶ ሕዝቡን ተገን በማድረግ የተንቀሳቀሰው ቡድን፣ ከአዲስ አበባ እስከ ጅቡቲ የተዘረጋውን የባቡር ሐዲድ ማጥቃት ጀመረ። ጥቃቱ የሚካሄደው ከአዲስ አበባ ቅርብ በሆኑ ቦታዎች ስለነበር፣ ጠላት እጅግ አስቸገረው። ከማጥቃቱ ሥራ የመጀመሪያው በተጠቀሰው ቀላል ዘዴ የስልክ መሥመሩን መበጣጠስ ሆነ። ድልድይ መስበር፣ ከገደላማ ቦታ ላይ ትልቅ ድንጋይ በእልህ እያንከባለሉ ከሃዲድ ላይ ማስቀመጥ፣ ወዘተ...፣ ሌሎቹ ዘዴዎች ነበሩ።

በባቡር ላይ አደጋ መጣል፣ ሰኔ 29 ቀን 1929 ዓ.ም ተጀመረ። ቦታው በአቃቂና በሞጆ መካከል ነበር። ባቡር የመምታቱ፣ ሀዲድ የመስበሩ፣ ስልክ የመበጣጠሱ ሥራ የሚካሄደው በቡልጋና በሸንኮራ ገበሬ ድጋፍ እንጂ በራሱ አልነበረም። እንደጠቀስኩት ሥራውን የሚያካሂዱት ከአዲስ አበባ ወጥተው በአርበኝነት ሥራ በተሠማሩ የተማሪ ወጣቶች ነበር። ሥራውም የሚካሄደው በዘመናዊ ሥልት ነበር።

ስለዚህ ከሐምሌ 1 ቀን 1928 ዓ.ም ጀምሮ የሐዲዱን ጥበቃ ጀነራል ግራዚያኒ ራሱ ያዘ። ነገር ግን ከአርበኞች የሚሰነዘረውን ጥቃት ሊገታው አልቻለም። ሐምሌ 2 ቀን 1928 ዓ.ም አዳማ ከተማ፣ ሐምሌ 4 ቀን እና 5 ደግሞ ከአዲስ አበባ 439 ኪሎ ሜትር ከሚርቅ ቦታ በባቡር ላይ አደጋ ጥሰው፣ በሁለት ጎታቾች፣ እንዲሁም በስምንት ሃላፊዎች ላይ ጉዳት አደረሱ። በዚሁ በዓ.ም፣ ሐምሌ 4 ቀን ከምሽቱ ሦስት ሰዓት ሞጆ አካባቢ በሌላ ባቡር ላይ አደጋ ጣሉ፣ ስልኩንም በጣጠሱ። ሐምሌ 9 ቀን 1928 ዓ.ም ከድሬዳዋ ወደ አዲስ አበባ የሚጓዘውን ባቡር ዱከም ላይ አርበኞች አደጋ

ጥሰው ጉዞውን አቋረጡበት። በዚሁ ቀን አንድ ሌላ የአርበኛ ቡድን ከቀኑ በ11፡ 30 ሰዓት ሞጆ አካባቢ በሌላ ባቡር ላይ አደጋ ጥሎ ጉዳት አደረሰበት።

አርበኞች አዋሽ አርባ /ቦርደዳ/ በተባለው ቦታ በባቡር ላይ አደጋ ጥሰው በዚያ ከነበረው የጠላት ጦር ጋር ተዋጉ። ነሐሴ 7 ቀን 1928 ዓ.ም ደግሞ አዋሽ ባቡር ጣቢያ በሠፈረው በአንድ ጀነራል በሚመራ ጦር ላይ አደጋ ጣሉበት። ነሐሴ 9 ቀን ደግሞ አርበኞቹ መተሐራ ባቡር ጣቢያ ላይ አደጋ ጥሰው ጣልያናውያን ወታደሮች ገድለው ተመለሱ። በማግስቱ ነሐሴ 10 ቀን ደግሞ አልከዲሱ በተባለው ቦታ በነበረው ባቡር ላይ አደጋ ጣሉ።

አርበኛው ሞጆን በመያዝ የባቡርን መሥመር ከነጭራሹ ለመዝጋት ተዘጋጀ። ነሐሴ 21 ቀን 1928 ዓ.ም ታሳቅ ውጊያ አካሄደ። የቡልጋ፣ የሸንኮራ፣ የምንጃርና የደቡብ ጉጃም ሰው ተባበረ። በጠላቱ ላይ የየአቅሙን ያህል ተራውን ተወጣ። ጊዜው ዝናም፣ መሬቱ ጭቃ፣ ሰማዩ ደመና ነበር። ጠላት በአይሮፕላን ለማጥቃት አልተመቸውም። ከሁለቱም ወገን ብዙ ሰው አለቀ። ነገር ግን የጠላት ኃይል ስለአመዘነ አርበኞቹ እንደ አሰቡት ሞጆን ለመያዝ ሳይችሉ ቀሩ። ቢሆንም መክራው ራሱ ጠላትን አስደነገጠው።

የአርበኞችን ጥቃት ለመከላከል ሲል ጣልያን ብዙ እግረኛ ወታደር ያሰማራል። አካባቢውን በአይሮፕላን ይደበድባል። ጫካውን በእሳት ያቃጥላል። ለባቡር ሐዲድ ጥበቃው ሥራ ጀነራል ግራዚያኒ 72 ከፍተኛ መኮንኖች፣ 113 ዝቅተኛ መኮንኖች፣ 1136 ወታደሮች መደበ። ነገር ግን ከንቱ ሆነበት። አርበኞች ማጥቃታቸውን ቀጠሉ። ነሐሴ 22 ቀን 1928 ዓ.ም ለዕረፍት ወታደሮች ጭኖ በሚጓዘው ባቡር ላይ፣ ከአዲስ አበባ 205 ኪሎ ሜትር ርቀት አደጋ ጥሰው ከባድ ጉዳት አደረሱበት።

ሁኔታው በእንዲህ እንደአለ የጣልያን የቅኝ ግዛት ሚኒስትር ኢትዮጵያን፣ ማለትም በዚያን ጊዜው አሠራራቸው የኢጣልያን የምሥራቅ አፍሪካ ቅኝ ግዛት እንዲጎበኝ በሮም ታሰበ። ጉብኝቱ እንዲደረግ የታሰበው በእንድ በኩል በኢትዮጵያ ውስጥ የተቀሰቀሰውን የአርበኝነት ሥራ ለማብረድ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ሰላም የተመሠረተ አስመስሎ በማሳየት የዓለምን ህብረተሰብ ለማወናበድ ነበር። አልተሳካላቸውም እንጂ ይህንን እንደተገነዘቡ አርበኞች ጥሩ እርምጃ ወሰዱ። መስከረም 29 ቀን ከምሽቱ 3 ሰዓት ላይ ከድሬዳዋ ሦስት ባቡሮች ተከታትለው ተነሱ። ግን የቅኝ ግዛት ሚኒስትሩ ሲኞር ሌሶና የተሳፈረው በየትኛው ውስጥ እንደነበር በአርበኞች ዘንድ አልታወቀም ነበር።

ባቡሮቹ ጉዞአቸውን ቀጥለው መስከረም 30 ቀን 1929 ዓ.ም ዱከም ደረሱ። ከዱከም አራት ኪሎ ሜትር ያህል እንደወጡ በመጀመሪያው ባቡር ላይ ከቀኑ በ7፡45 ደቂቃ አደጋ ተጣለ። አዲስ አበባ ሲገባ ለሚደረግለት አቀባበል እንዲመች ሲባል ከመጀመሪያው ላይ ሣይሣፈር አይቀርም በሚል መላምት ሳይሆን አልቀረም። ነገር ግን ሌሶና ከዚያ ውስጥ አልነበረም።

በአቃቂና በዱከም መካከል በነበረው ሐዲድ ላይ ሁለተኛ አደጋ ተጣለ። እሱ ደግሞ ሌሶና የነበረበት ባቡር ከመድረሱ ጥቂት ቀደም ብሎ ሆነ። ስምንት ኢጣሊያውያንን ቢገድሉም ሌሶናና አብሮት የመጣው ከቦሊ ጂሊ ጉዳት ሳያገኛቸው ቀረ። ትርፉ "ዋይ ነደ" ሆነ። ቢሆንም ሌሶና የአርበኞቹን ጥንካሬ ሳይገነዘብ አልቀረም።

ጥቅምት 5 ቀን 1929 ዓ.ም ጣልያን የኤረርን ተራራ ሲያስስ፣ አርበኞቹ ናዝሬት ከተማ አጠገብ አደጋ ጥሰው ጉዳት በማድረስ የሚደክመው በከንቱ መሆኑን ለጠላት በግብር ገለፁለት። ጀነራል ግራዚያኒ በአርበኞች የጦር ሥልት መበሳጠን አመነ። አምኖም የባቡርና ሐዲዱን ጥበቃ ለጀነራል ጋሊና ለቀቀ።

ጀነራል ጋሊና በዚያው እሱ በተሾመበት በጥቅምት 5 ቀን 1929 ዓ.ም ከጠዋቱ በአንድ ሰዓት አርበኞች በአንድ ባቡር ላይ አደጋ ጥሰው ጉዳት ማድረሳቸውን የሚገልፅ ሪፖርት በማንበብ ሥራውን ጀመረ። የአቅሙን ያህልም ተፍጨረጨረ። ቢሆንም በሐዲዱ ላይ የሚደርሰውን አደጋ ማቆም አልሆነለትም። ጥቅምት 6 ቀን 1929 ዓ.ም በአዋሽና በወልንጭቲ መካከል አደጋ ተጥሎ ባቡር ተጐዳ። አርበኞቹ የካቲት 7 ቀን በወልንጪቲና በበርጭታ መካከል 399 ኪሎ ሜትር ላይ ሐዲዱን ስለሠበሩት ባቡር መተላለፍ አቋረጠ። በዚሁ በጥቅምት 7 ቀን 1929 ዓ.ም ሌላ ባቡር በአዲስ አበባና በደብረ ዘይት መካከል ተመታ። የተመታው ደግሞ በመድፍ መሆኑ ጣልያኖችን አስደነገጠ።[1]

ይህ ቡድን ፈጥኖ ቢዳከምም፣ በጠላት ላይ ብዙ ጉደት አድርሶአል። ጦርነቱ እንደተጀመረ እንጂ እንዳላሰቀ አውሮፓ ሊረዳው በሚችል መልክ አስረድቶታል።

<u>ማጣቀሻ ፅሑፎች</u>

[1] ጳውሎስ ኞኞ፣ *የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦርነት*፣ ገጽ 173-178።

ምዕራፍ ሃያ ስምንት
በቡልጋና ሸንኮራ የተካሄደ ትግል

የቡልጋ ሕዝብ የኢትዮጵያን መሸነፍ ሲሰማ ደንግጦ፣ የንጉሠ ነገሥቱን ወደ አውሮፓ መሄድ ሲሰማ ደግሞ ተገረመ። የአንድ ጥቁር ሕዝብ ጉዳይ በነጭ አደባባይ ተሰምቶ ትክክለኛ ፍርድ ይገኛል ብሎ አላመነም። የንጉሠ ነገሥቱንም ጉዞ ከሽሽት ለይቶ አላየውም። ጠላት አንዳች ተቃውሞ ሳያጋጥመው አዲስ አበባን መያዙ አስቆጣው። ስለዚህ የበኩሉን ትግል ጀመረ።

ንጉሠ ነገሥቱ ከአዲስ አበባ በወጡበት ቀን ማግስት፣ ማለትም ሚያዝያ 25 ቀን 1928 ዓ.ም ቅዳሜ ዕለት፣ የሀገር ሽማግሌዎቹ ሕዝቡን በጥሩምባ በመቀስቀስ ኩረማሽ ዋሻ ውስጥ ተደብቆ የነበረውን የጦር መሣሪያ አስነሱ። የማሣሪያ ማንሳቱ ሥራ ከአጼ ምኒልክ አደራ በተቀበሉ ሽማግሌዎች ኃላፊነት ተካሄደ። እነሱም ግራና ቀኝ ቀመው ሕዝቡን በተራ እያስገቡ፣ የየመስክህን የሚል ምክር እየሰጡ በሥነ ሥርዓት መሣሪያ እንዲያነሳ አደረጉ። ሥራው ቅዳሜ ቀንና ሌሊት፣ እንደዚሁም እሑድ ቀንና ሌሊት በሰላም ተካሄደ። ሚያዝያ 27 ቀን ሰኞ ወደማታ ዋሻው ተቃጠለ። በቃጠሎው የዋሻው በር ስለተደረበ በየዋሻው የነበረው ሰው አብሮ ተቃጠለ። አንድ ቄስ ከሣጥን ላይ ለጥፍት የሄደው ሚፍ ሳይታይ ሣጥኑን እሳት በማቀጣጠሉ ነበር። እሳቱን ለማጥፋት ያልተቻለው ደግሞ ሣጥኑ ዲናሚት ተቀምጦበት ስለነበር በመፈንዳቱ ነው። ብዙ ሰው አለቀ። መሣሪያውን ያስነሱ የነበሩ ሽማግሌዎች ጭምር ገና ካልተነሳው መሣሪያ ጋር አብረው ተቃጠሉ።

የዚህን መሣሪያ ምሥጢር መመርመር ይገባል። አፄ ምኒልክ በአውሮፓ በኩል ስለ አድዋው ጦርነት የነበረውን ስሜት ያውቁ ነበርና፣ ኢጣልያ የአድዋን ውርደት አሜን ብላ፣ ከመቀበል አርፋ እንደማትቀመጥ ገመቱ። ተከታታይ ጥቃት እንደምታመጣ በማወቅ፣ በመከላከያ ረገድ አርምሻ ወሰዱ። ለነበሩአቸው ጠመንጃዎች በየዓይነታቸው ጥይት የሚያስሩበት ፋብሪካ አዲስ አበባ ላይ አቋቋሙ።[1] ይህ ብቻ አልነበረም የአፄ ምኒልክ ጥንቃቄ። ብዙ መሣሪያ ገዝተው ከአውሮፓ አስመጡ። የመጣውም በታጁራ ወደብ በኩል በምሥጢር ሲሆን፣ በረሃውን በግመል፣ ደጋውን በእጋሰስና በአህያ እየተጫነ ነበር። አስመጥተውም ኮረማሽ አስቀመጡት። ለማስቀመጫው አሥራ ሁለት፣ ለጥበቃው ኃላፊዎች አንድ፣ በድምሩ አሥራ ሦስት ቤት ከዋሻው አሠርተው ከዚያ በመልክ በመልኩ አስቀመጡ። አስከ ቦታው ድረስ ራሳቸው ሄደው አይተው ለሀገሩ ባላባቶች አደራ ሰጡ። አደራው መሣሪያው ለውጪ ጠላት መከላከያ እንጂ ለእርስበርስ ጦርነት እንዳይውል ነበር።

ከዚህ ላይ መነሣት ያለበት ጥያቄ፡- «መሣሪያው ለምን በማይጨው ጦርነት አልተሠራበትም?» የሚል ነው። ምክንያቱ በሌላ በኩል፣ በትክክል ባይታወቀም፣ የሀገር ሽማግሌዎች እንደሚሉት ግን መሣሪያው በዚህ ዓይነት፣ በዋሻ እንደአለ የሰገሌ ጦርነት ደረሰ። በወቅቱ ባለሙሉ ሥልጣን አልጋ ወራሽ የነበሩት ልዑል ራስ ተፈሪ፣ መሣሪያው ለጦርነቱ እንዲውል አዘዙ። ከአፄ ምኒልክ አደራ ተቀብለው የነበሩ ሽማግሌዎች ወደ አዲስ አበባ በመምጣት ለንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ስለ ተሠጣቸው የአደራ ቃል ነገሩ። ንግሥቲቱ የአባታቸውን የአፄ ምኒልክን ውሣኔ ያፀናሉ። በዚህ ልዑል ራስ ተፈሪ ይቀየማሉ። ሆኖም በንግሥቲቱ ውሣኔ መሠረት መሣሪያው በጦርነቱ ጊዜ ሳይሠራበት ቀረ።

የንግሥቲቱ ኃይል እየቀነሰ፣ የአልጋ ወራሹ የፖለቲካ ኃይል እያየለ ሲሄድ፣ ከአፄ ምኒልክ አደራ የተቀበሉት ሽማግሌዎች መሣሪያውን ከኮረማሽ ከተማ በስተደቡብ ምዕራብ ሦስት ኪሎ ሜትር ያህል ርቆ ከሚገኝ ዋሻ ሌሊት ሌሊት በምሥጢር አማዘው ደበቁት። የዋሻውንም በር በግንብ አሠርተው፣ መዝጊያ አስገጠሙለት። የማይጨው ጦርነት ጊዜ መሣሪያው እንዲነሳ ሽማግሌዎች ማስታወሳቸው አልቀረም። ነገር ግን አልተነሳም፣ በጦርነትም ጊዜ አልተሠራበትም።

እንደ ተገለፀው የኮረማሽ መሣሪያ ጥቂቱ ከተነሣ በኋላ የሀገር መከላከሉ ሥራ ቀጠለ። ቡልጋ ከኮረማሽ ያገኘውን መሣሪያ መፈተሽ፣ መጠራረግ ያዘ። በየመልከኛው እሁድና በበዓላት ቀን እየተሰበሰበ ይመክር ጀመር። የመጀመሪያው ጉዳይ የጉበዝ አለቃ መምረጥ ሆነ። የጉበዝ አለቃ በመምረጥ ላይ ብዙ ውጣ ውረድ አለ። አንዳንዱ ለምን አልተመረጥኩም በሚል ቅር ሊለው ሲችል፣ ሌላው ደግሞ እኔ አልችልም፣ ሌላ ሰው ምረጡ እያለ ያስቸግራል።

በእኔ አካባቢ የተፈፀመውንና እኔ ራሴ ያየሁትን እንደማስረጃ ባቀርበው ይቀለኛል። ምንም በዚያን ጊዜ ልጅ ብሆን ዛሬም ሁኔታው በትክክል ይታወሰኛል። ቦታው ቡልጋ ተድላ ማርያም፣ ሙገሬ ዛለ ሚጢ ይባላል። በዚያ የነበረው ሕዝብ መከረ። የአሰቤ አገር ሚካኤልና የሚጢ ማርያም ሕዝብ በሕብረት አንድ የጉበዝ አለቃ መረጠ። በዚህ ብዙ አልተቸገረም። ነገር ግን ምን ሊደረግ እንደሚገባ ንግግር ሲጀመር የሀሳብ ልዩነት ተፈጠረ። አንዱ ወገን እንሸፍት፣ ሌላው ወገን እንመን አለ።[2] ከብዙ ቀን ምክርና ክርክር በኋላ "እንሸፍት" በሚለው ሀሳብ ፀና። ነገር ግን አንድ አቶ ሀብተኢየሱስ የተባለው ሰው አልሸፍትም ብሎ እምቢ አለ። ሕዝቡ አደመበት። ከንጉሥ መንገድ እንዳይወጣ፣ እሣት እንዳይሞር፣ ከቤቱ ሰው ቢሞት ከቤተክርስቲያን እንዳይቀበር ተከሰከሰ ተወገዘ። ሚስቱ ጥላው ከሰው ተቀላቀለች። እሑድ ይህ ተመሰናበት በሦስተኛው ቀኑ ማክሰኞ ደወል ደውሎ ከሀገር ታረቀ። የዚያ

አካባቢ ሕዝብ ለአርበኝነት ተንቀሳቀሰ። ሆኖም ሕዝቡ በሙሉ ወዲያው እንደ ልብ ሆነ ማለት አይቻልም።

በዚህ ዓይነት የተንቀሳቀሰው ሕዝብ ፊታውራሪ ኃይሉ ሥላሴን በበረከት፣ ቀኝ አዝማች ታቲን በድንጋይጥራ፣ ግራዝማች አብርሃምን በቡርቃ፣ አለቃ /ፊታውራሪ/ ወልደፃድቅ ዘውዱን በመገሬ ዛለ፣ ፊታውራሪ መኩሪያን በሽላኪ የጣር አለቃ አደረገ። ሌላውም ሁሉ በየአካባቢው እንደዚሁ አደረገ። ወደ ሽንኮራ ወደ ምንጃር የትብብር ደብዳቤ /ጥሪ/ ተላለፈ። ሽንኮራ በሙሉ ተባበረ፤ ምንጃርም በመጠኑ። በቡልጋ የመጀመሪያዋ የአርበኝነት ጥይት ጦስኝ በተባለው ቦታ በአለቃ /ፊታውራሪ/ ወልደፃድቅ ዘውዴ ሰኔ 9 ቀን 1928 ዓ.ም ተተኮሰች። ጠላት እስከተባረረበት ዕለት ድረስ አልበረደችም።

ወዲያው በፊታውራሪ መኩሪያ የሚመራው አርበኛ፣ ሽለጌ የፊጠን ጥማ ተንተርሶ፣ በሽምብራ ምድር በኩል ከመጣው የጣልያን ወታደር ጋር ተዋጋ። ከደብረ ብርሃን አዲስ አበባ የሚጓዘውን ሰውና ዕቃ በመንገድ ላይ እያደፈጠ በመውጋት ብዙ ጉዳት አደረሰበት። ጠላትም በበኩሉ ይህንን አርበኛ ቡድን በአንጭጩ ለመቅጨት ሞከረ። በኃይል እንደዛ ለማድረግ ግን አልተቻለውም። ሁለት ጊዜ ጦርነት አካሂዶ ሁለት ጊዜም ከተሸነፈ በኋላ ዘዴውን ለውጦ ዕርቅ ጠየቀ። አርበኞች በሰላም እጃቸውን ከሰጡ ምንም ዓይነት ጉዳት እንደማይደርስባቸው ማረጋገጫ ሰጠ። በአስታራቂነቱ ካህናትም ገቡበት። በዚህ ዓይነት አርበኛው ተታሎ በሐምሌ ወር 1928 ዓ.ም እጁን ለጠላቱ ሰጠ። ጠላትም ደብረ ብርሃን ወሰዶ ፊታውራሪ መኩሪያን ከአርባ አንድ ባልደረቦቻቸው ጋር በመትረየስ ረሸናቸው።

ጦርነቱ በሌላውም የቡልጋ አካባቢ ተጀመረ። ጥቅምት 14 ቀን 1929 ዓ.ም አስቤ አገር፣ ወህኒ በተባለው ቦታ ጠላት በአርበኞች ላይ አደጋ ጣለ። በአለቃ /ፊታውራሪ/ ወልደፃድቅ ዘውዴ የሚመራው አርበኛ ተኩሱን በተኮሰ ተከላክሎ ራሱን ከጉዳት አዳነ። አለቃ ወልደፃድቅ በሕይወታቸው ለመጀመሪያም፣ ለመጨረሻም ጊዜ ጥይት ከሽፋሽፍታቸው ላይ ጨረፈቻቸው።

በሽንኮራም እንደዚሁ እንቅስቃሴ የተጀመረው በዛው በ1929 የመጀመሪያዎቹ ወራት ነበር። ጣልያን በሽንኮራ በኩል አልፎ የያዘውን የአርበኛ ሠራዊት ከአልበተነ የባቡሩ መሥመር ጤና እንደማያገኝለት ተረዳ። አማካሪ ባንዶችም አላጣም። ስለዚህም የማጥቃት እርምጃ ወሰደ። የጠላት ጦር ብዙ የነጭ ወታደር፣ የአፍሪካ ቅኝ ግዛት ወታደሮች[3] እና ብዙ ባንዳ ነበረበት። ከአርበኞች ወገን በደጃዝማች ፍቅረማርያም የሚመራው ሠራዊት መጠነኛ ብዛት ነበረው። እነፊታውራሪ /ደጃዝማች/ በቀለ ሀብተሚካኤልና እነ ሻለቃ /ደጃዝማች/ በቀለ ወያም ተባብረውት ነበር።

አርበኞች ጥቅምት 12 ቀን 1929 ዓ.ም ገጠሙት። ቦታው ከባልጭ ከተማ በስተደቡብ ራምቡቲ የተባለው ነበር። ጦርነቱ ከጥዋት ጀምሮ ሲካሄድ ዋለ። ከጠላትም ከአርበኞችም ብዙ ሰው ሞተ፣ ቆሰለ። ጠላት አየለ።

የተረፈው አርበኛ ተበታተነ። በፊታውራሪ /ደጃዝማች/ በቀለ ሀብተገብርኤል የሚመራው፣ ከአርሲ የመጣው ቡድን ተመልሶ ወደ አሩሲ ሸሸ። ደረቅ ጦር ስለነበረ በደጃዝማች ፍቅረማርያም የሚመራው ቡድን ወደ ምንጃር ወረደ።[4] ገብተው በገዙም፣ መሬቱም ጭቃ ነበርና፣ ሊያመልጥ አልቻለም። ከፊሉ ሞተ፣ ከፊሉ ቆሰለ ወደቀ፣ ከፊሉ ተማረከ። ጠላትም የተማረከውን አርበኛ ኤጂሬ ወስዶ በ30 እና በ40 እየከፈለ በቤት ውስጥ እጅ፣ እጁን የፊጥኝ በማሠር አያጉረ መርገዝ ረጨቤት። ቶሎ ያልሞቱት እያንቋረሩ ስለአቃቱ፣ ጥቅምት 21 ቀን በአሳት አቃጠላቸው።[5]

ጀግናው ደጃዝማች ፍቅረማርያም ይናዱ በዚህ ጦርነት ላይ ወደቁ። እንዳልሞቱ ግን ተነገረ።[6] ከጦርነቱ ድነው እንደወጡና ወደ ሣማ ሰንበት ዋሻ እንደገቡ ለቤት አሽከሮቻቸው መነገሩን በዕለቱ የሰሙ ሰውም አሉ።[7] የጣልያኖቹም ማስታወሻ የሚያመለክተው እንደዚሁ የተዘበራረቀ ነገር ነው። ጋዜጠኛው ቺሮ ማሺሲ ጥቅምት 19 ቀን 1929 ዓ.ም በዓፈው ማስታወሻ "ባቅረማርያም በሐዲዱ አካባቢ ተገደሉ..."ይላል። እንደገና ጥቅምት 23 ቀን በዓፈው ማስታወሻው ደግሞ አንዱ አስካሪ /የቅኝ ግዛት ወታደር/ ሞንቅላታቸውን ቆርጦ አዲስ አበባ እንደአመጣ፣ የሚያውቁአቸው ሰዎች የአሳቸው ራስ መሆኑን ስለአረጋገጡ ለወታደሩ ገንዘብ እንደተከፈለው ገልያአል። የተገደሉበት ቦረ ኤረር ተራራ አጠገብ ከምትገኝ ሌቾ ከተባለች ቦታ እንደሆነም ይነገራል። ውሎ አድሮ መጋቢት 30 ቀን 1929 ዓ.ም በተዓፈ ሌላ ማስታወሻው ደግሞ አርሲ ውስጥ እንደሞቱ አድርጐ ያመለክታል። መነደሩንም "የጣልያን ሹማምንት አስከ ቦታው ደረስ ሄደው እንደ አዩ ይገልፃል።[8] ዋናው ነገር ደጃዝማች ፍቅረማርያም በአንድ ልብ ፀንተው በጠላት እጅ መውደቃቸው ነው። ይህንን ጠላትም፣ ወገንም አምኖበታል።

እንዲሁም፣ እንደተገለፀው ጦርነቱ ላይ እነ ፊታውራሪ /ደጃዝማች/ በቀለ ሀብተሚካኤል እና እነ ሻለቃ /ደጃዝማች/ በቀለ ወያ፣ እንደዚሁም የቡልጋ ውጣቶች የተሳተፉበት ታላቅ ጦርነት ነበር። ደጃች ፍቅረማርያም ራሳቸው ውጊያ ከጀመሩበት ቦታ ማፈግፈግ የማይፈልጉ፣ የንጉሠ ነገሥቱን ወደ አውሮፓ መሄድ እንኳን አጥብቀው የተቃወሙ ሰው ነበሩ። አዲስ አበባን ባጠቁ ጊዜ እንኳን፣ በጣቢያው ቆይቶ ሌላ ጊዜና ቦታ ቢፈለግ እንደሚሻል ሀሳብ ቢቀርብላቸው "ማይጨውም የተሸነፍነው እንዲሁ ተብሎ ነው..." ብለው በእልህ ጦርነቱን እንደከፈቱ በታሪክ ተመዝግቧል።[9] ስለዚህ በጦርነቱ ላይ መሞታቸው ይበልጥ አስተማማኝ ነው። ከጦርነቱ ተመልሰው ወደ ሳማ ሰንበት ዋሻ ሄዱ የሚለው እውነትነት ያለው አይመስልም። ሠራዊቱ እንዳይደነግጥ የተፈጠረ ማደናገሪያ ሳይሆን አልቀረም።

ያም ሆነ ይኽ፣ የአርበኞችን እንቅስቃሴ የደጃዝማች ፍቅረማርያም ሞት አላቀዘቀዘውም፤ እንዲያውም ይበልጡኑ ተጋጋመ። መጋጋሙ ጠላትን አስገነገነው። ከአካባቢው ባንዳ እየመረጠ፣ መሣሪያ እየሰጠ ማዘጋጀት ጀመረ።

በቡልጋ ፊታውራሪ ተሰማ ከተማ፣ በምንጃር ፊታውራሪ አስፋው ሀብተማርያም፣ በበረከት ፊታውራሪ ተክለ ሃይማኖት /በኋላ ተፀፅተው በአርበኝነት የሞቱ/ ጉዳይ አስፈፃሚዎች ሆኑለት። ሥራውም በመጠኑ ተቃናለት። ይህ ሁኔታ በሕዝብ መካከል የሐሳብ ልዩነት ቀሰቀሰ። ጉዳዩ በምክር የሚፈታ አልሆነም። ባንዳነት ካልገባውም አብዛኛው ደገኛ ለጠላት አመኖ አደረ። አብዛኛው ቆለኛው ሸፈተ። ስለዚህ አርበኛ ለመሆን የወሰነው ደገኛ ቆላ ወረደ። ለጠላት ያመነ ቆለኛ በበኩሉ ደጋ ወጣ። በዚህ ዓይነት ማናቸውም ወገን፣ ውሳኔውን ለመፈፀም የሚያመቸውን የተግባር ቦታውን ያዘ።

ጠላት በበኩሉ አካባቢውን የመቆጣጠር አዝማሚያ አሳየ። አርበኞች ይህንን ሁኔታ የማይታገሱ ሆኑ። በመሆኑም ህዳር 10 ቀን 1929 ዓ.ም ጦርነት ተከፈተ። እንደ ሽፍቶች ይታዩ የነበሩት አርበኞች በዚህ ቀን ግንባር ለግንባር ገጠሙት። ተኩሱ የተከፈተው ወዶ አይጉበር ከተባለው ተራራ ላይ ነበር። ይህ ቦታ የተመረጠው ታስቦበት እንጂ፣ እንዲያው በአጋጣሚ የሆነ አልነበረም። ቡልጋ እንደማይገበር፣ ጣልያን ቁርጡን እንዲያውቀው ነበር። ጦርነቱ በማግሥቱ ቀጥሎ ዋለ። ጠላትም እንደ አልሆነለት አውቆ ወደ መጣበት ተመለሰ። አርበኞችም የቅዱስ ሚካኤልን በዓል አስቤ አገር አከበሩ።

ጣልያን ደጃዝማች ፍቅረማርያምን ከአጠና፣ ሠራዊታቸውን ከበተነ በኋላ፣ አረርቲ ላይ ምሽግ ቆረቆረ። ወደ ተድላ ማርያም ለመሻገርም ከጀለ። በዚሁ በህዳር ወር መጨረሻም ሰበርና ዮሐንስ ላይ ጦርነት ተደረገ። ከሁለቱም ወገን ሰው ሞተ። በዚሁ ወር በአለቃ /ፊታውራሪ/ ወልደፃድቅ ላይ፣ ጋይ ሜዳ ከተባለው ቦታ ጠላት ድጋሚ አደጋ ጣለ። ተከላከለው ስለመለሱት ጉዳት ማድረስ አልቻለም።

እንዲህ እያለ የአርበኞቹ ኃይል ጠነከረ። ጣልያን ይህንን በማየት በረከትንና አካባቢውን በአይሮፕላን አስደበደበ። ድብደባውን በታህሣስ ወር 1929 ዓ.ም በመጀመሪያው ሣምንት ድንጋይ ጥራ በተባለው ቦታ ጀመረ። በየቀኑ አራት አራት አይሮፕላን እየላከ የቦምብ መአት አወረደ። በመጀመሪያው ቀን በሕዝብ ላይ ታሳቅ ድንጋጤ ወደቀ። ነገር ግን ጠላት በዚያ ሁሉ ድብደባ ያደረሰው ጉዳት አንድ ላምና ሦስት አህዮች መግደል ብቻ ሆኖ ስለተገኘ፣ ሕዝቡ ከደረሰበት ድንጋጤ ፈጥኖ አንሰራራ። ለአይሮፕላን መሸበሩም ቀረ።

ይህ የአይሮፕላን ድብደባ ግን አርበኞችን አስገነገነ። ያስገነገነበት ምክንያትም ድብደባው የተካሄደው በዋናው የአርበኞች አስተባባሪ፣ በፊታውራሪ ኃይለሥላሴ ቤት ላይ ሳይሆን፣ በአንዱ ቡድን መሪ በቀኛዝማች ታቺ ቤት ላይ በመሆኑ ነው። ስለዚህ ፊታውራሪ ኃይለሥላሴ ከጠላት ጋር የውስጥ ግንኙነት እንደሌላቸው በግብር ማረጋገጥ ግድ ሆነባቸው። ጠላት ይህንን ድብደባ ያካሄደው በማን ጠቋሚነት እንደ ሆነ ለማወቅ ጥናት ተደረገ።

በተገኘው ፍንጭ መሠረት እርምጃ ተወሰደ። የድብደባው አቀነባባሪ የነበረው ባሻ በላይነህ ባንዳ ታህሣሥ 19 ቀን 1929 ዓ.ም ሙገሬ ዛላ፣ አለአሴ ከነበረው ቤቱ ተከበበ። እጁን እንዲሰጥ ቢጠየቅ ፈቃደኛ ባለመሆኑ ተገደለ።

የዚህ ሰው መገደል ጠላትን አስቆጣ፣ በተለይም ፊታውራሪ ተሰማ ከተማን። ጠላትም አዲስ ጦር ሠርቶ ታህሣሥ 25 ቀን ሙገሬ ዛላ ገባ። አርበኞችም በየአለቡበት በሕዝብ በጥሪ ተሰብስበው በማግስቱ ታህሣስ 26 ቀን 1929 ዓ.ም እመይት አገር ግንባር ለግንባር ገጠሙት። ጦርነቱ ከንጋት እስከ ምሽት ዋለ። አርበኞቹ የጀግንነት ተግባር ሠሩ። ብዙ የጠላት ወታደር አለቀ። ጠላትም የሕዝቡን ቤት በማቃጠልና ከብቱን በመዝረፍ አፀፋውን ተበቀለ። ከአርበኞችም ጥቂቶቹ ሞቱ። የደጃዝማች ፍቅረማርያምን አሚሟት ወሬ ከአመጡት ሦስት ሰዎች ሁለቱ በዚህ ጦርነት ወደቁ። ጠላት ወደ መጣበት ወደ አንኰበር ሸሸ፣ አርበኞችም ወደበረከት ወረዱ።

ጠላት ላይውል ላያድር በአርበኞች ላይ ሌላ አዲስ ጦርነት ከፈተ። ይህኛው ደግሞ በበረከት በኩል ነበር። ጠላት አዲስ ጦር ነው ያቀረበው። አርበኞቹ ግን እነዚያው በአመይት አገር ጦርነት የደከሙት ብቻ ነበሩ። ቢሆንም በቆራጥነት በረከት ላይ ገጠሙት። ታህሣሥ 28 ምና 29 ዓ.ም መሉ ቀን ተዋጉ። ከሁለቱም ወገን ብዙ ሰው አለቀ። ጦርነቱ ከእመይት አገርም የከፋ ነበር። ስለዚህ አርበኞቹ አካባቢውን ለቅቀው ወደ ወይናደጋው ጠጡ። ጠላትም ወደ ቦታው ተመለሰ። በሁለም ላይ ድካም ጠንክሮ ነበርና አንዱ ሌላውን ለማባረር አልሞከረም።

አርበኞች እንዶዬ በተባለው ቦታ ሠፍረው ጥቂት ዕረፍት ከአደረጉ በኋላ ምክር ተጀመረ። የሐሳብ ልዩነት ተፈጠረ። አንዱ ወገን "ሰግደድ ብለን ከደረሰብን ጉዳት እናገግም፣ በየአለበት ከሚገኙ አርበኞች ጋርም እንላላክ" ሲል፣ ሌላው ወገን ደግሞ "ጊዜው ፋታ የሚሰጥ አይደለም በርትተን እንከላከል፣ ካልቻልን አካባቢውን ለቅቀን እንውጣ" አለ። አስታራቂ ሐሳብ ጠፋ። ምክንያቱም ሳይታወቅ የምክሩ አቀነባባሪና አማካሪ በሻህ የተባለ ሰው ሆነ። እሱም እስከ ሦስት ቀን ድረስ ከቤቱ እንዲቆዩ አበክሮ አሳሰበ። የሚበዛው ሰው በዚህ አጉል ምክር አመነ። የበሻህ ውትወታ በሞገደኛው በአለቃ /ፊታውራሪ/ ወልደፃድቅ ዘውዴ የሚመራውን ቡድን አስገነገነ። ቡድኑ በዚህ ነገር አልስማማም ብሎ በሰላም ተሰናብቶ ጥር 1 ቀን 1929 ዓ.ም ተሰይቶ ወደ ሙገሬ ዛላ ሄደ። በፊታውራሪ ኃይለሥላሴና በባሰምባሪስ ይልማ ወልደኢየሱስ የሚመራው የአርበኞች ቡድን ከዚያው ከበሻህ ቤት ቀረ።

ይህ በሻህ የተባለው ጠንቋይ፣ ከጣልያን ጋር በምሥጢር ተላልክ ኖሮ፣ በእሱ ምክር አምነው ከቤቱ ውስጥ የተቀመጡትን አርበኞች ጥር 2 ቀን 1929 ዓ.ም አስያዛቸው። ጣልያንም ሹማምንቱን በሰንሰለት፣ ሠራዊቱን በገመድ የፊጥኝ እንደታሠሩ ወደ አንኰበር ወሰዳቸው። የአንኰበሩ ገዥ ጥር 10 ቀን የጥምቀት ዕለት በአደባባይ ግመትረየስ ፈሸናቸው። ከአሥር ያልበለጡ

አባላት የነበሩት በአለቃ /ፊታውራሪ/ ወልደፃድቅ ዘውዴ የሚመራው ቡድን ግን የአርበኝነት ሥራውን ቀጠለ። በተደጋጋሚ ወና፣ እመይት አገር፣ በረከት ላይ የተካሄዱት ጦርነቶችና የእነ ፊታውራሪ ኃይል ሥላሴ በጠላት እጅ ተይዞ መገደል፣ በሕዝበ ልቡና የነበረውን ፍርሃት እንደገና እንዲያነረሽ ስለአደረገው የአርበኞች ሥራ እንደሸፍትነት ተቆጠረ። አርበኞች ግን ትግላቸውን ቀጠሉ።

ከዚህ ላይ እኔ ራሴ ስለማውቀው፣ ጠቅሼው ስለነበረው፣ በግል ፊቃዱ አርበኝነት ስለገባው አንድ ጀግና አብራርቼ ልገልጽ ይገባኛል። ስሙ በየነ ወልደገብርኤል ሊባል፣ የትውልድና የአርበኝነት ቦታው በረከት፣ ዋጩ ነበር። ጓደኞቹ በዚህ ጦርነት ሲያልቁና ሲቧታተኑ፣ እሱ ብቻውን ተጋድሎውን ቀጠለ። በእመይት አገሩ ጦርነት ጊዜ አንድ ለበን ጠመንጃ ማርኮ ናስ ጠመንጃውን ስወጠ። ነገር ግን ከለበኑ ጋር ያገኘው፣ በውስጡ የጉረሰውን አሥር ጥይት ብቻ ነበር። ዝናሩ፣ የጠላት ወታደር እንደታጠቀው አምልጦታል። ጠላት በየነ የነበረበትን ቦታና ሁኔታ አውቆ ከበበው። በየነም የካቲት 13 እና 14 ቀን 1929 ዓ.ም ሁለት ቀን ሙሉ በአንዲት ዋሻ ውስጥ ሆኖ ብጀግንነት ብቻውን ተዋጋ። ስምንት ሰው እንደገደለ ሽለላውን አቆመ። ቦታው ርጭ ጭጭ አለ። ጠላት ገብቶ ቢያይ አርበኛው ዘጠነኛዋን ጥይት ጠጥቶ ሞቶ ተገኘ። ታዲያ አንድዋን ጥይት ለምን ተዋት? ብሎ ለሚጠይቅ፦ ዘጠነኛዋ ብትከሽፍ፣ ለመጠባበቂያ እንድትሆነው ብሎ መሆኑ ነው።

ወደ ዋናው ጉዳይ ልመልሳችሁ። በዚህ ጊዜ ላይ አለቃ /ፊታውራሪ/ ወልደፃድቅ ዘውዴ ሰው ማስተባበራቸውን ቀጠሉ። ጠላት ይህንን ሰምቶ አካባቢውን መበርበር፣ መፈተሽ ያዘ። በቅዱስ ሚካኤል ላይ የነበራቸውን ተአምኖ በማወቅ፣ የአሰቦ አገር ሚካኤልን መንበር ጭምር አስገልጦ አየ። ነገር ግን ሕዝቡ አጥብቆ ስለደበቃቸው አላገኛቸውም።

ከዚህ ላይ ደግሞ የአንድ ሌላ ካህንን ብልሀት መጥቀስ ያስፈልገኛል። ደብተራ ወልደማርያም ይባላሉ። ቦታቸው በረከት ቡርቃ ከተባለው አገር ነው። አለቃ /ፊታውራሪ/ ወልደፃድቅን ደብቀዋል ተብሎ በጠላት ትእዛዝ ሜጢ፣ አቶ ደጀኔ ወልዴ ቤት ይታሠራሉ። የታሠሩበትን እግር ብረት ሰብረው አወጧቸው። ናዝሬት (አዳማ) በመሄድ፣ ፊታውራሪ ተሰማ ከተማ በሕዝብ ላይ የሚያካሄዱትን ጭፍጨፋ በማስረዳት ከሥልጣናቸው ተሽረው፣ ሸኖ ከተማ በግዞት እንዲቀመጡ አስደረጉ። በተጨማሪ አሥራ ሦስት አገር ያምሱ የነበሩ ሌሎች ባንዶች፣ ቆስጤ አገር ተወስደው መቃብራቸውን ራሳቸው ቆፍረው በጥይት እንዲደበደቡ በማድረግ ለአካባቢው አርበኞች ሁሉ አብነት ያለው ሥራ ሠሩ። በአርበኞች ላይ የነበረው ውጥረት ተቀነሰ።

ትግሉ በገለፅኩት ሁሉ መልክ የቀጠለ ቢሆንም፣ ከጥር 1 እስከ ሐምሌ 20 ቀን 1929 ዓ.ም የነበረው ጊዜ፣ በዚያ አካባቢ ለነበሩ አርበኞች እጅግ ከባድ ነበር። በመሆኑም ለጠላት ያላመኑ ወገኖች በሙሉ፣ ሴት፣ ወንድ፣ ልጅ፣ አዋቂ፣ ካህን፣ መሃይምን ሳይሉ፣ በሀሳብና በሥራ መተባበር

ነበረባቸው። እኔም እንኳን በሕፃንነት አቅሜ የሥራ ድርሻ ነበረኝ። ሥራዬም ለገበሬዎች የምወስድ እያስመሰልኩ ለእጮቼ ለአለቃ /ፊታውራሪ/ ወልደፃድቅ ዘውዴ ስንቅ ማቀበል ነበር። የሚያስደንቀው ነገር ይህንን ሥራ ለማካሄድ እናቴን ወ/ሮ ፀዳለ አባ በለውን ከባለቤቻው ከአቶ ደጀኔ ተክሌ፣ አባቴን አለቃ ዘሥሐንስ ዘውዴን ከባለቤታቸው ከወይዘሮ ዘነበች ተክለሃይማኖት አፋትቼ ማንም ሰው ሳይለማ ለማስታረቅ መቻሌ ነው። ይህንን ማድረግ የተገደድኩት የእንጀራ አባቴ ከጐኑ፣ የእንጀራ እናቴ ከጠቃ አገር የወረዱ ደገኞች ስለነበሩ፣ ሠፊ እያፈተለከ ስለአቃተ ነበር። በዚህም የስንቅ ማቀበሌ ሥራ ተቃና።

የስንቁ ማቀበል ሥራ ቢቃናም፣ በእኔ ላይ ግን ሌላ ችግር ተከተለ። መጀመሪያ የእንጀራ አባቴ፣ ቀጥሎም የእንጀራ እናቴ ንብረቶቻቸውን በማጣታቸው ባደረባቸው ቁጭት፣ ምስጢሩን በፊታውራሪ ተሰማ ከተማ በኩል ለጣልያን አደረሱ። ጣልያንም በበኩሉ እኔን እንዲያስረክቡት አቶ ተክሌ ቢረሴ የተባሉት ሽማግሌ፣ ቅድም አያቴን ያዘ። ቅድም አያቴ ግን እኔን ለጠላት ማስረከብ ስላልፈቀዱ፣ ዳዊት አገር የተባለ መልከኸኝነታቸውን ነጥቆ ታደሰ ሱተባለ ባንዳ በመስጠት አዘረፋቸው። እሳቸውም በዚህ ብስጭት ሞቱ።

አለቃ /ፊታውራሪ/ ወልደፃድቅ ዘውዴ የጀመሩት ሰው የማስተባበሩ ሥራቸው ተቃናላቸው። እነ ግራዝዝማች/ፊታውራሪ/ አጐናፍር ባዩ፣ እነ አዩ/ቀኛዝማች/ ስንቅነህ፣ እነ አቶ /ፊታውራሪ/ ኃይሌ/ኃይሰ ራጉኤል/ ወልደፃድቅ፣ ሌሎችም በብዛት ተባበሩአቸው። የጠላት ክትትል ስለጠነከረ በሰኔ ወር አለቃ /ፊታውራሪ/ ወልደፃድቅ ዘውዴ እንደሞቱ አድርጐ ማውራት አስፈልጐ እንደዛው ተደርጎ ነበርና፣ አለመሞታቸውን ሲረዳ ጠላት ከፍተኛ ሥጋ አዘመተ።

ይህ ጦርነት ወሳኝነት ስለነበረው ዝርዝሩን ማየት አስፈላጊ ነው። አርበኞች በዝያን ሰዓት የነበሩት ሀገረ ማርያም ጭቁ ቆላ ነበር። ጠላት ሊመጣ ጥቂት ሰዎች እየተከሱ እንዲሸሹ አደረጉ። ጠላትም ለማባረር ወደደቡብ የሚፈስሰው ወንዝ እንደደጋን ተጠምዝዞ ወደ ምሥራቅ ከሚዞርበት ጐኖ ውስጥ እንዲገባ አደረጉት። በአንፃሩ አርበኞች ገሸ ምድር የሆነውን የደብረ ብርሃን ጥግ ያዙ። የጣልያን ወታደር እዚያ ላይ ሲደርስ አደጋ ጣሉበት። በየጫካው ውስጥ ሆነው በጥይት ጠዘጠዙት፣ መውጫ መግቢያ አሳጥተው ፈጁት። አገሬው በጉራዴ፣ በጦር፣ በአንካሴ፣ በጩቤ፣ በዱላና በመጥረቢያ ሳይቀር የጠላትን ወታደር፣ በተሰይም ባንዳውን ከተከተው። ከጠላት ወታደር ከሦስት መቶ በላይ ሞተ፣ ሌላም ብዙ ቆሰለ። የቀረውም መሣሪያውን እየወረወረ፣ ዝናሩን እና ጀበርናውን ከወገቡ እየፈታ እየጣለ ሸሸ። አገሩን ከድቶ፣ ክአርበኝነት ወደ ባንዳነት ገብቶ፣ በአውቃለሁ ባይነት ጠላትን እየመራ ያመጣው ጨፌቃ ይገዙ የተባለው ባንዳ ተገደለ። ከወገንም ሦቱት ሰው ሞተ። ከስድስት መቶ በላይ እንደ ወውዜር፣ ሰበን፣ ቤልጅግ ያሰ ደረቅ ብረትና አንድ አውቶማቲክ ክላሽንኮቭ ተማረከ። ቡልጌ ከአረማዝ

የዘረፈውንና ከአባቱ የወረሰውን እንደ መስኮብ፣ ወጂግራ፣ ሰናድር፣ ናስ ማሠር የመሳሰሉትን ብረቶችን ጣለ። የማረከውን ደረቅ ብረት ጨቡጠ።

አርበኞች የቆላውን ሀገረ ማርያምን፣ የተድላ ማርያምን፣ የክትበወይራን፣ የሙገሬ ዘለን፣ የበረከትን ሕዝብ አስተባበሩ። ከጠላት ጉን ሆኖ የወጋቸውን ከትንቢት እስክ ገርም ገብርኤል ድረስ ያለውን አገር አቃጠሉት። ከዚያም ወደ ቆላው ወደ በረከት ወረዱ።

በአለቃ /ፊታውራሪ/ ወልደፃድቅ የሚመራው ቡድን እዳንዴ ገባ። አውፋ አቤኩ በሻህ ቤት ሲበላ፣ ሲጠጣ አደረ። በሻህም የሆነለት መስሎት ፍራዳ አርዶ እየጠበሰ፣ እየቀቀለ አስተናገደ። ጥዋት ቁርስ ከተበላ በኋላ ፍርድ ተያዘ። በሻህ እንደምን ከጠላት ጋር እንደተላላከና ግንኙነቱ በአነማን አማካይነት እንደነበረ ተናዘዘ። አንድ ሰው የሚራራለት ጠፋ። ነሐሴ 17 ቀን እሱም በተራው በፍርድ በጥይት ተደበደበ።

እንግዳ እሸት የተባለ የልጅ ኢያሱ ልጅ በአብዬ ገዳም መድኃኒዓለም አለቃ በአባ ይርዳው እጅ እንደአለ ያውቁ ነበርና፣ አለቃ /ፊታውራሪ/ ወልደፃድቅ ዘውዴ የበሻህን ፍርድ ካስፈፀሙ በኋላ ወደ ገዳሙ አመሩ። ከዚያም መነኩሴውን አባ ይርዳውን በማላመን፣ ውጣቱን መሥፍን እንግዳ እሸትን ነሐሴ 19 ቀን 1929 ዓ.ም ወደ ጦር ሠፈራቸው ወደ መክፈሌ ወሰዱት። አባ ይርዳውም ማታውኑ እስከ ጦር ሠፈር ደረስ መጥተው ወጣቱ የልጅ ኢያሱ ልጅ መሆኑን ለአርበኞቹ አረጋገጡ። ያሰበው ሀሳብ እንደማይቃና ያላቸውንም ሥጋት ሕልማቸውን በማዝር ገለፁ።

ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በተጣሰባቸው አደራ ምክንያት ጥቂት ቢያቅማሙም የሀገር ጉዳይ መሆኑን በማየት በወጣቱ መሥፍን መንገሥ ተስማሙ። አለቃ /ፊታውራሪ/ ወልደፃድቅ ዘውዴ ውጣቱን መሥፍን እጅ ከአደረጉ በኋላ በአካባቢው ለነበሩ አርበኞች ጥሪ አስተላለፉ።

አርበኛው ወከረሴ ከተባለው ቦታ ነሐሴ 20 ቀን 1929 ዓ.ም ተሰብስቦ ምክር ተያዘ። ጥያቄው የአርበኝነትን ሥራ ለማጠናከር በሚችልበት ጉዳይ ላይ አተኮረ። አርበኝነትን ለማጠናከር አንድ በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት ሊኖረው የሚችል መሪ መምረጥ ማስፈለጉ ታመነበት። በአለቃ /ፊታውራሪ/ ወልደፃድቅ ዘውዴ የሚመራው ቡድን ያቀረበው ሀሳብ የልጅ ኢያሱን ልጅ ማንገሥ ሆነ። ተቃውሞ ተነሳ። ተቃዋሚውም ደግሞ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከዓለም መንግሥታት ማህበር ዕርዳታ ለመጠየቅ ወደ አውሮፓ ሄደው ሳለ፣ የእሳቸው ቁርጥ ሳይታወቅ ሌላ ንጉሥ ማንገሡ እንደምን ይቻላል? የሚል ሆነ። ጠንካራ ክርክር ተካሄደ። ንጉሥ እናንግሥ የሚለው ሀሳብ አመንጭና አራማጅ የነበሩት አለቃ /ፊታውራሪ/ ወልደፃድቅ ዘውዴ የዚህን ጉዳይ አስፈላጊነት አጥብቀው አስረዱ። ክርክሩ እየጠነነ በሄደ ጊዜ "አንድ ሰው ሽሽቶ ስለሄደ ሁላችን እናልቃለንን?" ብለው ጠየቁ። እናንግሥ የሚለው ሀሳብ ተደገፈ። ከምክር በኋላ አዲስ ንጉሥ እንዲነግሥ ተወሰነ።

ንጉሥ እናንግሥ የሚለው ሀሳብ ያሸነፈባቸው ምክንያቶች፣

1ኛ. በፊታውራሪ ኃይለሥላሴ የሚመራው ቡድን ጥር 2 ቀን 1929 ዓ.ም በጣልያን እጅ ወድቆ ለእልቂት የተዳረገው በሕዝብ ዘንድ ድጋፍ ያለው መሪ ባለመያዙ እንደሆነ ከልምድ በመታየቱ።

2ኛ. ጣሊያን ኃይልዋን አጠናክራ ሕዝብ በገሐድ መፍጀትዋ። ከየካቲት 12-14 ቀን 1929 ዓ.ም አዲስ አበባ፣ ከዚያም እንደ ደብረ ሊባኖስ፣ ዝቋላ ገዳም፣ ደብረ ብርሃን ላይ የታየው እልቂት።

3ኛ. ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ወደ ስደት ከሄዱበት ከሚያዝያ 25 ቀን 1928 ዓ.ም ጀምሮ ምንም ወሬ አለመሰማቱ።

4ኛ. የጣልያንን በኢትዮጵያ ላይ ገዥነት ብዙ የውጭ አገር መንግሥታት ማወቃቸው ነበሩ።

በኋላ ላይ ግን፣ የንጉሠ ነገሥቱ ለመንግሥታት ማህበር ሰኔ 23 ቀን 1929 ዓ.ም አቤቱታ ማቅረባቸው እየተሰማ በሄደ ጊዜ፣ አዲሱ ንጉሥ ቀስበቀስ ደጋፊ እያጣ መጣ። የአርበኛውም ጀሮ ወደ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ እየቶበቆበ፣ ልቦናውም ቀስበቀስ ወደ አሳቸው እየተመለሰ ሄደ። የአዲሱ ንጉሥ ጉራ እየቀዘቀዘ ሀዲ በመጨረሻው ላይ እንዴት እንደፈረሰ ወደፊት እናያለን።

የንግሡ ዝግጅት ተካሄደ። የደጃዝማች ወልደገብርኤል የክበር ልብስ ወጣ። የአካባቢው ካህናት በወክፈሌ ሚካኤል ተሰብስበው በአንድ ወገን ሰንቱታት በሌላ ወገን ማህሌት ተቆመ። በሦስተኛ ወገን የሥርዓተ ንግሡ ሀሉት ተደረሰ። እንግዳ እሸት የተባለው የአሥራ አምስት ዓመት ወጣት፣ መልአከ ፀሐይ ኢያሱ ምኒልክ ተብሎ፣ እሑድ ነሐሴ 24 ቀን 1929 ዓ.ም፣ እንደ ኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት፣ ሥርዓተ መሐላ ፈጽሞ ሥጋ ኢየሱስ ተቀበለ። ቅብአ መንግሥት ተቀብቶ ከነገሠ በኋላ ሥርዓተ ቅዳሴ ተካሄደ።

የቤተክርስቲያኑ ሥነ ሥርዓት እንደተፈፀመ፣ ነጋሪት እየተጐሸመ የአርበኛ ሠራዊት እየተመመ ወደ ሀገሩ መልሰኛ ቤት ጉዞ ሆነ። ከቁርስ በኋላ የመጀመሪያው ሹመት በነጋሪት ተሰጠ። ቀኛዝማች ኃይሉ ወልደመድህን የደጃዝማች ተብለው የወጣቱ ንጉሥ ሞግዚት ሆኑ። ግራዝማች አጉናፍር ፊታውራሪ፣ አለቃ ወልደ ፃድቅ ቀኛዝማች፣ አቶ ስንቅነህ ቀኛዝማች፣ አቶ ኃይሉ ወልደፃድቅ ግራዝማች ተባሉ። በማምንቱ ነሐሴ 28 ቀን 1929 ዓ.ም ደግሞ ሰሁለተኛ ጊዜ የማረሚያና የማጠናከሪያ ሹመት ተሰጠ። ቀኛዝማች ወልደፃድቅ ፊታውራሪ ተባሉ። ሌሎችም አርበኞች ተሾሙ።[10]

በሸዋ ለነበሩ አርበኞች የትብብር መጠየቂያና እንዲመጡ የመጥሪያ ደብዳቤ ከአዲሱ ንጉሥ ተላለፈ። ለባለምባራስ /ራስ/ አበበ አረጋይ የተፃፈውን ደብዳቤ አቶ ኪዳኔ አደረሱ ይባላል። እኔ የማውቀው ግን አቶ ይፍሩ አየለ የተባለ የፊታውራሪ ወልደፃድቅ ባልደረባ መውሰዱን ነበር። ባለምባራስ

/ራስ/አበበም መንዝ ሚጋ ከተባለ ቦታ ተነስተው በጦጦሲ በጠራ አድርገው ከደጃዝማች ዘውዴ አባክራን ጋር በመምጣት፣ አግግርት ፍንጥርጌ ከተባለው ቦታ ጥቅምት 8 ቀን 1930 ዓ.ም ለንጉሥ መልአከ ፀሐይ ኢያሱ ምኒልክ ገቡ። የመልአከ ፀሐይ መንግሥት በልጅ ኢያሱ ሳይ ሴራ ለሠሩ ወገኖች ጭንቅ ሆነ።

ሽንኮራ፣ ምንጃር፣ ቅንብቢት እስከ አንኮበር ድረስ የአርበኝነት ሥራ ያዘ። ከአርሲም ፊታውራሪ መኮንን ወልደጊዮርጊስና ፊታውራሪ ከበደ ወልደጊዮርጊስ መጡ። ከጥቂት ጊዜ በኋላም ደግሞ ቀኛዝማች ኃይለማርያም ማሞ መጡ። /ፊታውራሪ/ ወልደ ዓድቅ ዘውዴ ከጥቂት ግብረ አበሮቻቸው ጋር በታጋይነት መልክ የጀመሩትን ሥራ በሰቃ ዋጨ ጦርነት አማክኝነት ዳብሮ ወደ ሽፍትነት የደረሰው፣ ከዚያም ሀገር የመከላከሉ ሥራ ንጉሥ መልአከ ፀሐይን አንግሦ ወደ ክፍተኛው የአርበኝነት ሥራ ተሸጋገረ። ማንም አራመቻ ቢጥልበት፣ የማይጠፋ ታሪካዊ ሥራ ተካሄደ።

ንጉሠ ነገሥት መልአከ ፀሐይ ኢያሱ ተብሎ በወቅቱ ነግሦ በነበረው ንጉሥ የተሸሙ እና በእሱ የተሰጣቸው የማዕረግ ዓይነት ከብዙ በጥቂቱ፦

ባላምባራስ አበበ አረጋይ የራስ ማዕረግ፤
ቀኛዝማች ኃይሉ ወልደመድህን የደጃዝማች ማዕረግ፤
ፊታውራሪ ዘውዱ አባ ኮራን የደጃዝማች ማዕረግ፤
ቀኛዝማች ኃይለማርያም ማሞ የደጃዝማችነት ማዕረግ /አልተቀበሉም/
ቀኛዝማች ከበረ ኃይለሥላሴ የደጃዝማችነት ማዕረግ፤
ለአለቃ ወልደፃድቅ ዘውዴ የፊታውራሪነት ማዕረግ፤
ሰባሻ ደባልቄ ተክሌ የፊታውራሪነት ማዕረግ፤
ለአቶ መኮንን ወልደጊዮርጊስ የፊታውራሪነት ማዕረግ፤
ለአቶ ከበደ ወልደጊዮርጊስ የፊታውራሪነት ማዕረግ፤
ለአቶ ከበደ ካሣ የፊታውራሪነት ማዕረግ፤
ለአቶ አጐናፍር ባዩ የፊታውራሪነት ማዕረግ፤
ለአቶ አበበ ወልዴ የፊታውራሪነት ማዕረግ፤
ለአቶ ሀብቴ ሥላሴ የፊታውራሪነት ማዕረግ፤
ለአቶ ኪዳኔ ወ/ጊዮርጊስ የፀሐፌ ትዕዛዝነት ማዕረግ፤
ለአቶ ስሌ የፊታውራሪነት ማዕረግ፤
ለአቶ በለጠ የፊታውራሪነት ማዕረግ፤
ለአቶ ተሰማ ጉርሿ የፊታውራሪነት ማዕረግ፤
ለአቶ መኩሪያ የቀኛዝማችነት ማዕረግ፤
ለአቶ ወዳጆ ጉርሙ የቀኛዝማችነት ማዕረግ፤
ለአቶ ለማ ሽቀጣ የቀኛዝማችነት ማዕረግ፤
ለአቶ ታፈሰ አባናዳ የቀኛዝማችነት ማዕረግ፤
ለአቶ ወንድምሲያምረኝ የቀኛዝማችነት ማዕረግ፤

ለአቶ መኮንን አበረቱኝ የቀኛዝማችነት ማዕረግ፤
ለአቶ ገብረመስቀል ኃይሌ የቀኛዝማችነት ማዕረግ፤
ለአቶ ልኬለህ የቀኛዝማችነት ማዕረግ፤
ለአቶ መኮንን የቀኛዝማችነት ማዕረግ፤
ለአቶ ገላግሌ የቀኛዝማችነት ማዕረግ፤
ለአቶ ፍቅሬ ወልደሰማያት የቀኛዝማችነት ማዕረግ፤
ለአቶ ሺፈራ የቀኛዝማችነት ማዕረግ፤
ለአቶ ፈጠነ የቀኛዝማችነት ማዕረግ፤
ለአቶ አባይነህ አፍራሳ የቀኛዝማችነት ማዕረግ፤
ለአቶ ኃይሌ ወልደኪዳን የቀኛዝማችነት ማዕረግ፤
ለአቶ ሐጐስ የቀኛዝማችነት ማዕረግ፤
ለአቶ ጋሸ የቀኛዝማችነት ማዕረግ፤
ለአቶ ሺፈራው ዱባለ የቀኛዝማችነት ማዕረግ፤

የኢቲማ ተክለ ሃይማኖት ገዳም አበምኔት የነበሩት መምህር በላይ፣ ለእጨጌነት በአርበኛው ተመረጡ። እሳቸው እጨጌ ገብረጊዮርጊስ ተብለው የመንፈሳዊውን ሥራ ማካሄድና ካህናቱን የማስተባበር ሥራ ቀጠሉ። አዲስ አበባ የደብረ ሰላም እስጢፋኖስ የመጽሐፍ አስተማሪ የነበሩት መምህር ጽጌ የንጉሥ መልአከ ፀሐይ ፍትሐ ነገሥት አውጭ ሆኑ። የአኮርሚቱ /ኩሎኔል/ ኪዳኔ ወልደጊዮርጊስ ለፀሐፌ ትእዛዝነቱ ሥራ ተመረጡ።

የአርበኞች በዚህ ዓይነት መጠናከርና በአዲስ ኃይል መንቀሳቀስ ጣልያንን አስንገነጋ። ወደ አውሮፓ የሄዱትን ቀዳማዊ ኃይለሥላሴን አስደነገጠ። ሊየሩሳሌም የነበሩትን እጭጌ ገብረ ጊዮርጊስንም አሰጋ። ዝርዝሩ ወደፊት በየረድፉ ይገለፃል።

ጣልያን በኃይል ተንቀሳቀሰ። እንደልማዱ የነጩን መኮንንና ወታደር ከኋላ ደጀን አድርጎ፣ ባንዳውን አስቀደመው። ከባንዳው በኋላ ከኤርትራ፣ ከሊብያና ከሶማልያ ያመጣቸውን የቅኝ ግዛት ወታደሮች ከአዘቦ ከተመለመለ ራያ ጋር አቀላቅሎ ምድሩን እያሰሰ፣ አካባቢውን ከአይሮፕላን እያደባየ መጣ። ወንዱን እያሰለበ፣ የሴቱን ጡት እየቆረጠ፣ ኢሰብአዊ በሆነ መንገድ ሰው እየፈጀ፣ ቤተክርስቲያኑን፣ ቤቱን፣ የእህልና የገለባ፣ የሣር ክምር ሳይቀር እያቃጠለ መጣ። ታላቅ እልቂት በሕዝብ ላይ ደረሰ። የጣልያን ሐሳብ ኢትዮጵያን ከምድር ገጽ ማጥፋት መሆኑ በግልጽ ታወቀ።

ጣልያን ጦር ያመጣው ከሞጀ፣ ከአዲስ አበባ፣ ከሰላሌ፣ ከሸኖ፣ ከደብረ ብርሃንና ከደሴ ነበር። ሁሉንም በየቦታው አዘመተ። ዋናው ጦር ከደብረ ብርሃንና ከደሴ የመጣው ነበር። እሱም በቀንበሩ፣ በጠራ፣ በአግግርት፣ በቅንብቢት፣ በመጠዩስ አድርጐ በደብር በኩል ሀገረ ማርያም ገባ። ከዚያም በደንሌ፣ በመከኒሣ አልፎ በጉርጌ ፀኩል ወደበረከት ተሻገረ። አርበኞች በየጉራቸው ተዋጉ። ሲጫጣ ከፊት፣ ሲጓዝ ከግራና ቀኝ፣ ሲያልፍ

ከኋላው እየተከሱ ብዙ ወታደር ጨረሱበት። አርበኞች በዚያን ሰሞን ከተዋጉባቸው ቦታዎች ዋና ዋናዎቹ ደሻት፣ ቀምበሬ፣ መሶቢት ደብር፣ ሰቃዋጨ፣ ድንጋይ መዘጊያ፣ ከተም ወይራ፣ ቀሬ ወንዝ ናቸው።

ህዳር 1 ቀን 1920 ዓ.ም ቡርቃ ከተባለው ቦታ ታላቅ ጦርነት ተደርጉ፣ ፊታውራሪ መኮንን ወልደጊዮርጊስ ከብዙ ጀግኖች ጋር ወደቁ። ጣልያንም የፊታውራሪ መኮንንን ራስ ቆርጦ ደብረ ብርሃን በመውሰድ ጊጤ ተጫወተበት። ራስ መቂረጥ፣ በቡልጋ፣ በአላቸው ተጀመረ። ከጠላትም ብዙ ወታደሮችና ጥቂት መኮንኖች ሞቱ።

ህዳር 7 ቀን 1930 ዓ.ም ከስድስቱ፣ ከአዲስ አበባና ከአራቱ ማዕዘናት፣ ቁጥሩ እጅግ በርከት ያለ የጣልያን ጦር መጣ። አርበኞችም ደፈጣ አድርገው ለአነሱ አመች ከሆነ ቀሰበት ውስጥ እስኪገባላቸው ድረስ ጠበቁት። በሽ ዱባለ የተባሉ ጀግና በመጀመሪያይቱ ጥይታቸው አዛገቦን ኩሎኔል ከተቀመጠበት በቅሎ ዘነጠፉት፣ ሌሎችም አርበኞች ሌሎችን ነጮች እየሰዩ በመምታት ጨረሱአቸው። ብቻውን ሲቀር፣ ባንዳው ትርምስምሱ ወጣ። በዚያ ላይ ኃይለኛ ዝናም ዘንሞ መሬቱን አጨቀየው፣ ወንዞችን በውሃ ሞሳቸው። ብዙ የጠላት ወታደር አለቀ። ብዙ መሣሪያም ተማረከ። ይሆንን የጀግንነት ሥራ የሠራው፣ በቀኛዝማች ኃይለማርያም ማሞ የሚመራው አርበኛ ነበር።

ኩርፎ በተባለው አካባቢ ከጥቅምት 9 ቀን እስከ ህዳር አጋማሽ 1930 ዓ.ም ድረስ ብዙ ከባድ ውጊያዎች ተካሄዱ። ባላምባራስ /ራስ/ አበበ ከሠራዊታቸው ተለይተው ጠፍተው ስለሰነበቱ፣ በባልደረቦቻቸው ዘንድ ከባድ ድንጋጤ ወድቆ ነበር። ቀደም ብሎ በተደረገ ጦርነት ቀኝ እጃቸውን ቆስሰው ነበርና ችግሩ ቀላል አልነበረም። ነገር ግን ህዳር 12 ቀን 1930 ዓ.ም ስለተገኙ ደስታ ሆነ።

ባላምባራስ /ራስ/ አበበ አረጋይ በጠፉበት ጊዜ ሠራዊታቸው ይፈልጋቸው ነበር። ሠራዊቱ እሳቸውን ይፈልግ በነበረ ጊዜ ወደዳማ ከተባለ ቦታ ከቀኛዝማች ዘውዴ ተክለጊዮርጊስ ቤት አንድ ባለወርቅ መርገፍ የኢትዮጵያ ሠንደቅ ዓላማ ህዳር 11 ቀን አገኘ። በዚህም ታላቅ ደስታ ሆነ። ያም የሰንደቅ ዓላማ በጦርነት ጊዜ ሁሉ የአርበኛው አርማ ሆኖ ኖረ። አሁንም አዲስ አበባ በጥንታዊ ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማህበር ጽ/ቤት ለታሪክ መዘክርነት ተቀምጦ ይገኛል።

ባላምባራስ /ራስ/ አበበ ከሠራዊታቸው ጋር በተለዩበት ጊዜ ከበሻ አሳየ ጋር መስረዳ አቶ ተሰማ የተባለ ገበሬ ደብቆ አቆያቸው። እሳቸው ከሠራዊታቸው ጋር ተመልሰው እንደተቀላቀሉ ጦርነቱ ቀጠሉ። በተለይ ፊሣ በተባለው ቦታ ላይ ያካሄዱት ጦርነት፣ በቡልጋ ሕዝብ ዘንድ ሲታወስላቸው የሚኖር ነው። በሀገር ላይ የጨፈረውን የጣልያን ጦር በዚያ ቦታ ፊሣ በፊሣ አደረጉት። የአዘቦም አሮሞ የሸዋን ቁላ እንደተሸከመ በየጫካው ተራገፈ።

በዚህ ወቅት ንጉሥ መልአከ ፀሐይ ኢያሱ ጌልጌላ ነበሩ። ከዚያም ወደ መገሬ ዛላ መጥተው ጭንቁት ማርያም አቶ ተክለ ወልድ ቤት ሠፈሩ። ባላምባራስ /ራስ/ አበበም መጥተው እንደገና በተገናኙ ጊዜ ደስታ ሆነ። ትግሉ በተጠናከረ ሁኔታ ቀጠለ። ከጦርነቱ ከብደት የተነሳ በያለበት ተበትኖ የነበረው አርበኛ እንደገና ተሰበሰበ። ቁስለኛው በተቻለ መጠን አገገመ። ደጃዝማች አውራሪስ ከአነልጀቻቸው ከመንዝ መጡ። ልጅ ደስታ ሽዋ አርካብህና ባሻ ተሰማ እርገጤ ከይፋት መጥተው ለንጉሡ እጅ ነስተው ሁለቱም ፊታውራሪ ተባሉ። ከጉራጌ አገርም ሻለቃ /ደጃዝማች/ በቀለ ወያ መጥተው ሳይቆዩ ወደ ሥፍራቸው ተመለሱ።

በታህሣሥ ወር 1930 ዓ.ም የአርበኛ መሪዎች ተማክሩ። ምክሩ ጦርነቱን ለመመለስና የጠላትን ኃይል ለመቀነስ ስለሚቻልበት መንገድ ነበር። የአርበኛውም በአንድ ቦታ መከማቸት የፈጠረው ችግርና የሰጠው ጥቅም ከተመዛዘነ በኋላ፣ ሁሉም በየአለቃው እየተመራ በየአገሩ ቢዋጋ፣ ትግሉንም በተባበረና በተቀነባበረ መንገድ እንዲያካሂደ ማድረግ የተሻለ ሆኖ ተገኘ። ባላምባራስ /ራስ/ አበበ አረጋይ በስተቀር የመጣው ጦር ሁሉ ወደየመጣበት አገር ተመለሰ።

በዚሁ በታህሣሥ ወር 1930 ዓ.ም በፊታውራሪ ወልደፃድቅ የሚመራው ቡድን ተድላ ማርያም፣ ቁንጮ አገረ ገብርኤል ላይ ከጣልያን ጋር ተዋጋ። ጦርነቱ የተከፈተው ሞላሎ ከተባለው የከሰም ወንዝ መልካ ላይ ነበር። ጣልያን ከብቱን ውሃ ሲያጠጣና ሰራዊትም ውሃ ሊቀዳ ከአረርቲ ውስጥ ወረደ። አውራሪዱ በአርበኞች ዘንድ በደንብ የተጠና ነበር። ጠላት መትረየሶች ደጅን አስጠምዶ፣ ጥቂት ወታደሮች ደጅን ሆነው እንዲጠብቁ አድርጉ፣ ሠራዊቱ በሰላም ከወንዙ እንዲገባ አደረገ። አርበኞቹ ከተድላ ማርያም ወገን ያለውን ተዳፋት ይዘው በዝምታ ጠበቁና ጠላት ከውሃው ላይ ሲወድቅ አደጋ ጣሉበት። የመጀመሪያው ተኩስ ደጀን የነበረውን የጠላት ወታደር በመጨረስ መትረየሶቹን ዝም አሰኘ። ሁሉም ተዘረረ። በተጋጋመ ሁኔታ ከጥዋቱ 4:00 ሰዓት እስከ ቀኑ 9:00 ሰዓት በቆየው ጦርነት ብዙ አርበኞች ወደቁ። ነገር ግን ከጠላት ወገን የወደቀው ብዙ አጠፌታ ነበር። ድል የአርበኞቹ ሆነ። አንድ አልቤን መትረየስ፣ ብዙ ምንሽርና አልቤን ጠመንጃ ከእነጥይቱ፣ ከብዙ አጋሰስ ጋር ተማረከ።

የአርበኞቹ እንቅስቃሴ የጣልያንን መንግሥት አስገነነው። ባዶሊዮ እንዲሸርና በምትኩ የአስተዳደር ችሎታ ያለው አንድ መሥፍን እንዲሾም ሞሶሎኒ ለንጉሡ፣ ለሣልሣዊ ኢማኑኤል ሀሳብ አቀረበ። ከሁኔታው አሰፈሪነት የተነሳ የጣልያንን ዘውድ የሚያረክስ እንዳይሆንበት ቢሰጋም፣ ንጉሡ ከጳጉሜ 4 ቀን 1929 ዓ.ም ጀምሮ ሲያውጠነጥን የቆየውን ሀሳብ ሰለተቀበለው፣ ዱክ አሚዲዮ ደአምስታ ተሹሞ ታህሣሥ 17 ቀን 1930 ዓ.ም አዲስ አበባ ገባ። ከሞሶሎኒ የተሰጠዉ መመሪያ፡-

1ኛ.ጣልያኖች ከቅኝ ግዛት ህዝቦች መቀላቀላቸው ውርደት ስለሆነ፣ ለጣልያን ንፁህ ዘር ጥበቃ እንዲያደርግ፣

2ኛ.ስለጦርነቱ ሮም የሚደርስው ሪፖርት የተጋነነ ስለሚመስል እርግጠኛውን እንዲያስታውቅ፣

3ኛ.የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት በገንዘብ ረገድ ራሱን እንዲችል እንጂ ከጣልያን ሀገር ገንዘብ እንዳይጠይቅ፣

4ኛ.በሃይማኖቶች ምክንያት የሚታየውን ችግር እንዲያቃልል፣

5ኛ. አገረ ገዥዎች ሙሉ ሥልጣን እንዲኖራቸው እንዲያደርግ ነበር።

የባዶሊዮ ተሸሮ የዱክ ደ አምስታ መሾም ግን፣ በአርበኞች ስሜት ላይ እንዳች ልዩነት አልፈጠረም። ታህሣሥ 23 ቀን የማጠቃለያ ጦርነት ተደርጉ አንድ ኢጣልያዊ መኰንንና ብዙ ወታደር ተገደለ። መከኒሣ፣ በዳንሳ ደግሞ ሌላ ጦርነት ተደርጉ፣ የአርበኞች ቡድን በጠላት ላይ ጉዳት አደረሰ። በፊታውራሪ ወልደፃድቅ የሚመራው ቡድን ሱንበ፣ አራግቻ ከተባለው ቦታ በመኪና በሚተላለፉ ጣልያኖች ላይ አደጋ ጥሎ ዘጠኝ ካሚዮን ሰባበረ። ብዙ ጣልያኖች ገደለ።

ፊታውራሪ ወልደፃድቅ ዘውዴ (ገፅ 183 ይመልከቱ) የአንዱን ጣልያን ጭንቅላት ቆርጠው ዘቅዝቀው በማንጠልጠል ፎቶግራፍ ተነሱበት።[11] ነገር ግን ዘዴው ሳይታወቅ ስለቀረ በካሚዮኖቹ ላይ በሽራ ተሸፍኖ ተጭኖ የነበረው መሣሪያና ስንቅ ሳይዘረፍ ቀረ። ምሥጢሩ በታወቀ ጊዜ በአርበኞች ዘንድ ታላቅ ቁጭት ሆነ። የፊታውራሪ መኰንን ወልደጊዮርጊስን ደም እንደተበቀሉላቸው እንዲረዳው ፎቶግራፉን ለደብረ ብርሃኑ ገዥ ላኩለት። ጣልያንም በዚያ አካባቢ የአርበኛ ጭንቅላት ዳግመኛ መቁረጡን ተው።

የካቲት 1 ቀን 1930 ዓ.ም ተድላ ማርያም፣ ስድስላ አገር አርበኞች ምክር አደረጉ። ምክሩም ወደ ጨኖ ወርዶ በዚያ የነበረውን ጠላትና ግብረአበሮቹን ማሳፈር ነበር። በሃሳቡ ስምምነት ስለተደረገ አርበኞቹ በገና መምቻ በኩል አድርገው በጠቋሚ ሺህ ዓሊም ከተባለው የባንዶች መሪ ቤት ደርሰው ከበቡ። ያሰብዙም ችግር ከቤቱ ገቡ። በተጠቆሙት መሠረት፣ በቤቱ ውስጥ ሃያ ዘጠኝ መውዜር፣ አንድ ምንሽር፣ አንድ ባለካርታ ሰበን ጠመንጃና አንድ ተገንጣይ ቤል ሽጉጥ ከእነ ጥይቶቻቸው፣ እንዲሁም ብዙ ሣጥን ብርና ልብስ ተገኘ። የታረዘ አርበኛ የወገቡን ዝናር በጥይት ገጠገጠ። ኪሱንም ሞላ፣ አገሩንም አሣመነ፣ ጠላትን አሣፈረ።

በዚህ ጊዜ ንጉሥ መልአከ ፀሐይ ኢያሱ ከሙገሬ ዛላ ወደ ሰቆቃው ሄደው ነበርና፣ ራስ አበበና ቀኝዝማች ኃይለማርያም ማሞ ከእነ ሠራዊታቸው ወደዚያው ሄዱ። ሁኔታውን በንቃት ይከታተል ስለነበረ፣ ጣልያን ቶሎ ብሎ ከአዳማና ከሞጆ ጦር አንቀሳቀሰ። ሀሳቡ ወደ ቡልጋ ተሻግሮ አርበኞችን ማጥቃት ነበር። አርበኞቹም ተዘጋጅተው ጠበቁት። ወንዙን አናሻግርም ብሎ

ከመተናነቅ ይልቅ፣ ከሰምን ከተሻገረ በኋላ ማጥቃት የተሻለ ሆኖ አገኙት። አንዲሁም አደረጉ። በፊታውራሪ ሽበሽ ዓለማየሁና በፊታውራሪ አማረ የሚመራው አርበኛ የካቲት 11 ቀን 1930 ዓ.ም ገጠመው። ውጊያው ለሦስት ቀን ቀጠለ። በመጨረሻም ከቀኛዝማች ኃይለ ማርያም ማሞ ሠራዊት አንድ ክፍል ለእርዳታ ስለደረሰ ድል የአርበኞች ሆነ። አንድ የጣልያን ባንዲራና ልዩ ልዩ መሣሪያ ተማረከ። ሰንደቅ ዓላማው በአደባባይ ተቃጠለ።

በፊታውራሪ አጉናፍር ባዩ የሚመሩ አርበኞች መጋቢት 6 ቀን 1930 ዓ.ም የጨፌ ደንላን ምሽግ አጠቁ። የምሽጉ ኃላፊ የነበረውን አንድ የመቶ አለቃ ጣልያን ገድለው ራሱን በመቁረጥ ለሕዝብ መሳለቂያ አምቡር ገበያ ከኮሶ ግንድ ላይ ሰቀሉት። ሦስት መውዜር ጠመንጃ ገፈው ወደ ሠፈራቸው ተመለሱ።

አርበኛው በየፊናው ጠላትን በማጥቃት መያውን ማሳየት አመጣ። አንዳንዴ በተናጠል፣ ልላ ጊዜ ብቻ ስብቻ፣ ወይም ከሚያምናቸው ጓደኞቹ ጋር እየሆነ ጠላትን ማጥቃት ያዘ። አንዳንዱ ከምሽግ ተሾልኮ እየገባ ሲያጠቃ፣ ሌላው ከድቶ የመጣ እየመሰለ መያውን ማሳየት አመጣ። ሌሎች ሥልቶች እያቀላቀለም ቀጠሉ። በመንገድ ላይ እያደፈጠ እንዲሁም በጉዞ ላይ እየተቀላቀለ ቦታና ጊዜ በመምረጥ እያጠቃ፣ እየገደለ፣ መሣሪያ እየገፈፈ ይመለስ አመጣ። መጥቶም በአለቃው ፊት ግዳይ እየጣለ ይፎክራል። አለቃውም በክብር እየተቀበለ፣ ለንጉሡ እያቀረበ የማዕረግ ስም ያስጠዋል። ሥልቱም ከሰው ሰው፣ ከቦታ ቦታ፣ ከጊዜ ጊዜ እየተራቀቀ ሄደ። ለእነዚህ ሥራዎች ማስረጃ ያስፈልጋቸዋል።

መገሬ ዛላ አለኸሌን መንገሻ ወልደፃድቅ የተባለ ወጣት ነበር። ጠላት በገባ ጊዜ ገና የአሥራ አምስት ዓመት ማርተጋሻ ነበር። በአርበኝነት ጊዜ ሰው ብሎ መሣሪያ የሚሰጠው ዘመድ ስለአጣ፣ እንደሚከተለው አደረገ። አዲስ አበባ ገብቶ አክስቱን ተለማመጠ። እሳቸውም አንድ እሩቅ የሚያሳይ መነጥር፣ የጠላት ወታደሮች የሚያደርጉአቸውን ሦስት የእንገት ፋሻዎች፣ አንድ የጨርቅ የቅልጥም ገንባሌ፣ ሁለት የእጅ ቦምቦች ከጠላት ወታደሮች ሰርቀው ሰጡት። እነዚያን ይዞ አገሩ በመግባት በእነሱ እየተጠቀመ በጉዞ ከደከመ የጠላት ወታደር ጋር ወደ ማታ እየተቀላቀለ፣ በድምሩ አሥራ ስምንት ሦንሸር ከብዙ እጅ ቦምብና ጥይት ጋር በመቀማት በፊታውራሪ ወልደፃድቅ የሚመራው አንድ ቡድን አባል ሆነ። ባላምባራስ ተባለ። ይህ ሰው በጠላት ላይ የመጀመሪያውን አደጋ የጣለው ገበያ ነበር።

ታደሰ አበበ የተባለ ሌላ ወጣት በበኩሉ አንድ አሮጌ ውጂግራ ይዞ ጊና አገር ስጠላት የክዳ መስሎ ገባ። ጣልያንም እምኖ አዲስ ምንሽር ጠመንጃ ሰጠው። ስድስት መሣሪያ ገፎ በማምለጥ ከፊታውራሪ ደባልቄ ተክሌ ጋር ተቀላቀለ።

አባቱ አጋዬን ዘምተው የሞቱበት አቶ ደመና ከተማ የተባለ ሌላ ወጣት፣ አርሲ ከነበሩ አርበኞች ጋር ተንቀሳቅሶ በዚያ የነበረው አርበኛ ወደ ዳር አገር ሊሄድ አብሮ መሄድ ደስ ሳይሰው ቀረ። ናዝሬት መጥቶ ለጣልያን ባንድነት ገብቶ ጥቂት ረገጠ። ቋንቋም ትንሽ አጥንቶ አንድ ምንሽር ጠመንጃ ተቀበለ። መተሐራ አጠገብ የነበራቸውን ምሽግ እንዲጠብቅ ከተመደበው ጦር አባል እንዲሆን ተደረገ። ስድስት ሰዎች አስከድቶ፣ ሁለት ጣልያኖች ገድሎ በረከት በመሸገር ከአጉቱ ከፊታውራሪ ወልደሃድቅ ዘውዴ ጋር ተቀላቅሎ አርበኝነቱን ቀጠለ።

በዚህ ዓይነት በተናጠል፣ በግለሰብ የሚካሄደው የማጥቃት ዘዴ በጠላት ላይ ቀጥሎ እያለ በቡድን፣ በቡድን እየሆኑ ግንባር፣ ለግንባር በመግጠም የመውጋቱ ሥራ ተጋጋመ። አንዱ ሥልት ለሌላው ሥልት ደጋፊ፣ ጦር ክፋች እየሆነ ሄደ። ለምሳሌ አንድ የአርበኞች ቡድን መጋቢት 8 ቀን 1930 ዓ.ም እቲሣ፣ ጥጥ አምባ በጠላት ላይ አደጋ ጥሎ ደህና ሥራ ሠራ። ሌላው ቡድን ደግሞ መጋቢት 12 ቀን ጨመሪ በነበረ ጠላት ላይ አደጋ ጣለ።

ይህ ተደጋጋሚና ተደራራቢ ጥቃት ጠላትን ቆጠቆጠው፤ አዲስ ጦር አዘጋጅቶ መጣ። እንደ ሥርዓቱ ብዙ ባንዳ አስቀድሞ፣ ነጩ ከኋላ ሆኖ ነበር። አርበኞች ትንሽ ተካክሰው ስለሸሹለት፣ የአሸነፈ መሰለው። ሊጨርሳቸው ማባረር ያዘ። አርበኞች የሸሹለት ለእነሱ ከሚመች ወጥመድ ቦታ ለማስገባት ነበር። ዘዴአቸው ያዝላቸው። ከቀሰበት ውስጥ አስገብተው በጥይት ቆሉት። ፊረሰኛውን ከፈረሱ ላይ አወረዱት፣ እግረኛውን ማሳ ለማሳ በጥይት እያባረሩ ሰቀሙት። ፎክሮ የመጣው ጀነራል፣ እንደ ዋለ ቀረ። ከአርበኞች ወገን የሞተው እጅግ ጥቂት ነበር። አንደት የሚያርስ ሥራ ሠሩ። በተገኘው ድል የተደሰቱ ሦስት የኮርማሽ ባሳሮች ሦስት ሺህ ጥይት አምጥተው በራሳቸው ፈቃድ ለአርበኞች በነፃ ሰጡ። ሽልማትና የግራዝማችነት ስም አገኙ።

ንጉሥ መልአከ ፀሐይ የትንሣኤን በዓል ሚያዝያ 12 ቀን ክትም ወይራ፣ ጀሉ አገረ ማርያም ጨፋ አከበሩ። ግብር ሊበላ ሰነበተ። የዳግም ትንሳኤ ሌሊት ከጀሉ አገረ ማርያም ሙሉ ሥርዓተ ፀሎት ተደርሶ ንጉሠ ነገሥት ተባሉ። በእጨጌው ገበሬ ሠናይነት ቀረቡ። ከዚያ መልስ ሠፍረውበት ወደ ነበረው ወደ ባሻ ደምሴ ተክሌ ቤት ሄዱ። ከዚያም ሰነበቱ።

አርበኛው እንዲሰበሰብ ተጠርቶ ነበርና፣ ከቀኛዝማች ኃይለ ማርያም ማሞ ሠራዊት በስተቀር ሌላው ተሰበሰበ። ከሚያዝያ 20 ቀን 1930 ዓ.ም ጀምሮ ምክር ተያዘ። ምክሩ ስለጦር አመራርና ስለአስተዳደር ሳይሆን አልቀረም። ስብሰባው ጨፌ በባሻ ደምሴ ተክሌ ቤት ነበር። ዋናው ስብሰባ በአዳራሹ፣ የውስጥ ስብሰባዎች ደግሞ በአልፍኙ ውስጥ እንደ ነበረ እኛ ማቲዎቹ ከቅጥር ግቢው ውስጥ ሆነን አይተናል። ነገር ግን ንግግሩ

በምስጢር በመሆኑ እንደሌላው ጊዜ ዝርዝሩን የማወቅና ክርክሩን የመስማት ዕድል አልነበረንም።

ሚያዝያ 20 ቀን ሰኞ ለንጉሡ እጅ ከመንሳት በስተቀር ሌላ ጉዳይ የተካሄደ አልመሰለም። ዋናው ንግግር ሚያዝያ 21 ቀን ማክሰኞ ተጀመረ። በምክሩ ላይ የነበሩ፤

ንጉሠ ነገሥት መልአከ ፀሐይ ኢያሱ፣
ደጃዝማች ኃይሌ መልደመድህን ሞግዚት፣
ፊታውራሪ ዘውዴ አባኮራን፣
ባላምባራስ አበበ አረጋይ፣
ቀኛዝማች ከበረ ኃይለሥላሴ፣

የፊታውራሪነት ማዕረግ ያላቸው የጦር መሪዎችም ነበሩ። የምክሩ ሁኔታ የተገለፀው ሚያዝያ 28 ቀን 1930 ዓ.ም በተሰጠው ሹመት ብቻ ነው። ሹመቱም ከዚህ እንደሚከተለው ነበር።

1ኛ.ባላምባራስ አበበ አረጋይ ራስ ተብለው ጠቅላይ የጦር አዛዥ፤
2ኛ.ፊታውራሪ ዘውዴ አባኮራን ደጃዝማች ተብለው የጎላ አገር ጦር መሪ፤
3ኛ.ቀኛዝማች ከበረ ኃይለሥላሴ ከንቲባ /የቤተ መንግሥት ኃላፊ/፤
4ኛ.ፊታውራሪ ወልደሃድቅ ዘውዴ የፊታውራሪ ገቅ አርጌንና የፊታውራሪ ሞገሴን ጨምረው የቡልጋ ጦር አስተባባሪ ሆነው ነጋሪት እየተጎሰመ በአዋጅ ተሾሙ።

ራስ አበበ አረጋይ ባለወርቅ ቀይ ካባ፣ ደጃዝማች ዘዉዴ የወርቅ ዝምዝም ያለበት ጥቁር ካባ፣ ፊታውራሪ ወልደሃድት ከደረቱ ላይ የወርቅ ፈርጥ ያለበት ሰማያዊ ካባ ለብሰው ከሜዳው ወጡ። የከንቲባ ከበረ አለባበስ ዘውል አይታወሰኝም። ወታደሩ በረጅሙ ተሰልፎ ነበርና በዚያ መካከል አልፈው እዚያው ጨፋ ወደ ሠፈሩባቸው ቤቶች በአጀብ ገቡ። ፊታውራሪ ወልደሃድቅ ዘውዴ ራስ አበበን ከሠፈሩበት ቤት አድርሰው ሰበርን በረት አቶ አሻግሬ ቤት ነበሩና ወደዚያው ሄዱ። ፊታውራሪ ገቅ አርጌ በማግስቱ ጥዋት በረት ድረስ መጥተው በድልድሉ ማስማማታቸውን በመግለጽ፣ ምሣ በልተው ከፊታውራሪ ወልደሃድቅ ተሰናብተው ወደቡልጋ ዙሩ። የፊታውራሪ ሞገሴን መምጣት አላስታውስም። የጨፋ ሹመት የተሰጠው ሚያዝያ 21 ቀን ጀምሮ በተደረገው ምክር ብቻ አይመስልም። ሰብዙ ጊዜ ሳይታይበት አልቀረም። የሹመቱ መሰጠት የአርበኞችን አቅዋም ያጠናከረም ያዳከመበትም ሁኔታ አለ። አጠናካሪ ገፅታው ግልፅ ነው። ብዙም አያከራክርም። አርበኛው ልቡ ተጽናና፣ ገበሬውም አመነ፣ ተባበረ። ከተሿሚዎቹም በተለይ ራስ አበበ፣ ደጃዝማች ዘውዴና ከንቲባ አበራ ደስ አላቸው።

ነገር ግን ሹመቱ የፈጠረው የደስታ ስሜት ብቻ አልነበረም። ቅሬታም አንጂ። ምንም የቡልጋን አርበኞች እንዲምሩና የፊታውራሪ ገቅ አርጌንና

የፊታውራሪ ሞገሴን ሠራዊት እንዲያስተባብሩ ቢፈቅድላቸው፣ ደጃዝማች አለመባላቸው ፊታውራሪ ወልደፃድቅን ቅር አሰኛቸው። ቢሆንም ቅሬታቸውን ትተው ሥራቸውን ቀጠሉ። ለራስ አበበም ትብብራቸውን አላጐደሉባቸውም። ነገር ግን የቀኛዝማች ኃይለማርያም ማሞ አቋም የተለየ ነበር። ከስብሰባው ላይ አልተገኙም። የእንኮበርን፣ የዳውሌንና የበረከትን ጦር ይዘው የደጃዝማችነት ማዕረግ አሉበት ደብረ ከብድ ድረስ ቢላክላቸው እንኒን አልተቀበሉም። ለሰዎቻቸውም የማዕረግ ስም እንዲሰጥ ዝርዝር ማቅረብ አልፈቀዱም። እኛ የተነሳነው ለሀገራችን ነፃነት ለመከላከል እንጂ እርስበርሳችን ለመሻኘም አይደለም አሉ ተባለ። ይህ አባባል እውነት ነበረው። ለሀገሩ በነፃ የሚያገለግለውን አርበኛ የአገሌ ታዛዥ ጭፍራ ሁን ማለት አግባብ አልነበረም። ይህ ስሜት የአርበኛውን ልብ ለመከፋፈል ለተነሱ ኃይሎች በር ሳይከፍት አልቀረም።

የሹመቱ አሰጣጥ ደግሞ የራሱ የሆነ ችግር ነበረበት። የአርበኝነቱ ሥራ የሚንቀሳቀሰው ሀገር ወዳድ በሆኑ ተራ ሰዎች ነበር። ብዙዎቹ ጀግኖች ከሥራቸው በስተቀር የሚመኩበት የዘር ሀረግ አልነበራቸውም። የሚከፈላቸው ደመወዝ፣ የሚሰጣቸው ድጋፍ አልነበረም። ጠመንጃዎቹ እንኳን ከጣልያን የማረኩአቸው እንጂ ከመንግሥት የተሰጡአቸው አልነበሩም። ሹመቱ ግን በዘር ሆነ። ምንም በተሰይ በራስ አበበ ጀግንነትና ብልህነት ቅር የተሰኘ ባይኖር፣ ሠራዊቱ በሙሉ ልብ አልተደሰተም።



የአርበኞች አውራ ራስ አበበ አረጋይ።

ብዙም ሳይቆይ የአስተዳደር ችግር ተፈጠረ። ለምሣሌ ፊታውራሪ ወልደፃድቅ ዘውዴ የተወለዱበትና አርበኝነቱን የቆረቆሩበት፣ ቤተሰቦቻቸው የሚኖሩበት ሜጢ የተባለው ሀገር ለፊታውራሪ ደባልቄ ተሰጠ። ሁለቱን ፊታውራሪዎች ለማጋጨት ሆን ተብሎ የተጠነሰሰ ሴራ ነበር። እውነትም እነዚህ ሁለት ወንድማማቾች ሌላ ምንም የሚያገናኛቸው ነገር ሳይኖር

አርስበርሳቸው ለጦር ተሰላልፈው እስከ መዋጋት ደረሱ። ሌላውንም በዚህ ሹመት ምክንያት የተፈጠረውን ችግር ወደፊት እናያለን።

ከዚህም በስተቀር በስደት ላይ የነበረውን መሳፍንት ሳያሳስብና ቀዳማዊ ኃይለሥላሴንም ሳያሰጋ አልቀረም። ኢየሩሳሌም የነበሩትን እጨጌ ገብረጊዮርጊስን ጭምር። የውስጥ አርበኞች በኃይል ተንቀሳቀሱ። የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ደጋፊዎች እዚያው እጨጌ ውስጥ እየጻፉ፣ በሣሙና ላይ ተቀርፆ በተሠራ ማሕተም እያተሙ፣ ከንጉሠ ነገሥቱ ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የተላከ እያስመሰሉ ለአርበኛው የሚያስነብቡም ነበሩ። እንዲሁም ለራስ አበበ፣ ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የሚደርሱ መልዕክቶች እየበረከቱ ሄዱ። ዋናው ጥያቄ "በአንድ አገር ሁለት ንጉሠ ነገሥት እንደምን ይሆናል?" የሚል ነበር። ለዚህ ከባድ ጥያቄ የጭምቱ የራስ አበበ ምላሽ "ይታሰብበታል" ሆነ።[11] ሁኔታው ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የውጭ አገር ዕርዳታ ማግኘት ጋር በቀጥታ የተያያዘ ሆነ።

ሹመቱ ያስከተለው ችግር ይህ ብቻ አልነበረም። የጣልያንን መንግሥት አስደነገጠው። ለመጀመሪያ ጊዜ የአርቅ ሐሳብ በማቅረብ የሰላም እጁን ዘረጋ። ሙሴ ቀስተኛን በአማላጅነት ላከ። ሙሴ ቀስተኛ የሥራ ሚኒስቴርና ባልደረባ በመሆን ኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ ጊዜ የቆየና፣ በየመሳንንቱ ቤት እየዞረ ሲበላና ወግ ሲያጠና አርባ ዓመት የኖረ የስዊስ ተወላጅ ነበር። እሱም ከአዲስ አበባ ተነስቶ በሸንኮራ፣ በሰቃ ዋጩ፣ በተድላ ማርያም ዞሮ ሹመቱ ከተሰጠበት አካባቢ በአንድ ሣምንት ጊዜ ደረሰ። እሱ ተድላ ማርያም ሲደርስ፣ ንጉሠ ነገሥት መልአከ ፀሐይ ወደ ቀይ አፈር ሄደው ነበር። እሱም እግረ መንገዱን ሀገሩን እያጠናና እየሰለለ ተጉዞ ንጉሠ ነገሥቱ ከአሉበት ደረሰ።

ገሊላ ደርሶ፣ በወቅቱ ንጉሠ ነገሥት ተብለው ነግሠው ከነበሩት መልአከ ፀሐይ ኢያሱ ተገናኘ። መልዕክቱንም አስረዳ። እስከ ሦስት ቀን ድረስ በባላምባራስ ምላልኝ ግዛው እጅ ሰንብቶ፣ የተቆረጠ መልስ ሳያገኝ ሚያዝያ 30 ቀን 1930 ዓ.ም ወደ ደብረ ብርሃን ሄደ። ለደብረ ብርሃኑ ገዥ ከሰጠው ምክር ዋናው ምሽግን ማብዛትና ማጠናከር እንደሆነ ወዲያው ከአርበኞች ዘንድ ተሰማ።

ጣልያን የአቀረበው የእርቅ ሀሳብ በአርበኞች ዘንድ ሌላ የሀሳብ ልዩነት ፈጠረ። ብዙው ሰው ድካም ተሰምቶት ነበርና፣ በተገኘው ዕድል ዘመጠቀም መታረቅና የወደፊቱን ሁኔታ ማጥናት ይሻላል የሚል አስተሳሰብ ያዘ። ሌላው ወገን ደግሞ የዕርቁ ሀሳብ አዘናጊና ትጥቅ አስፈች ሊሆን እንደሚችል ሰጋ። በዕርቃታ እንዲታሰብበት ስለአስፈለገ በቶሎ ከውሣኔ ላይ ሳያደረስ ቀረ። ለሙሴ ቀስተኛም የተቆረጠ ምላሽ ሳይሰጠው የቀረው በዚህ ምክንያት ነበር።



የኦርዋሮች አውራ ራስ አበበ አረጋይ።

ጠላት ሃሳቡ እንደአልሰመረለት ሲረዳ ከጐንደር፣ ከጐጃም፣ ከወሎ፣ ከትግራ፣ ከሐረር ጦር ሰብስቦ አዲስ አበባ፣ ደብረ ብርሃንን እና ናዝሬትን (አዳማን) ዋና፣ ዋና የጦር ሠፈር በማድረግ አዘመተ። ከደብረ ብርሃን የተንቀሳቀሰው የጠላት ጦር በጫጫ፣ በደጀን ጥሬ መጣ። አርበኛውም ግንቦት 12 ቀን 1930 ዓ.ም አለበር አጠገብ ገጠመው። ጦርነቱ ከጥዋቱ አምስት ሰዓት ጀምሮ እስከ ምሽቱ አንድ ሰዓት ድረስ ቆየ። አርበኛው ብዙ የጠላት ወታደር ፈጀ። ሁለት መትረየስና ሌላም መሣሪያ ማረከ። ከእሱም ወገን ፊታውራሪ ተወንድ በላይነህን እና ሌሎችም ብዙ ጀግኖች ሞቱ፣ ሌሎች በርካቶችም ቆሰሉ።

አርበኞቹ ጠላት እስከ አለበት ድረስ ሄደው ግንቦት 13 ቀን 1930 ዓ.ም ውጊያውን ቀጠሉ። ድል አድርገው በመመለስ ወደ ኋላ ሲገፉት፣ ይዘት የነበረውን ሰውን የመጨረስ፣ ቤትና ቤተክርስቲያን የማቃጠል ሥራውን ለጊዜው አስጥለውት ወደ ገሊላ ወረዱ። እሱም በማግስቱ ግንቦት 14 ቀን አፋፍ ላይ ጠምዶ የቀይ አፈር ላይ ሆኖ ቆላውን በመድፍ ሲደበድብ ዋለ። ድብደባው ስለአለለቻቸው አርበኞቹ ወደ ቆላ ወረዱ። ከዚያም በአጡራ ጨባቃ አድርገው አይራራ ወንዝ ላይ ሠፍረው እስከ ግንቦት 28 ቀን ድረስ ዕረፍት አደረጉ። ከብቱም ሰውም ውሃ ጠጣ።

ራስ አበበ ከአይራራ ተነስተው በዳውሌ በኩል አድርገው ወደ ቡልጋ ለመሄድ ታሞ ከተባለው ቦታ ገቡ። ቀኛዝማች ኃይለ ማርያም ማሞ ደግሞ ከገሊላ ተነስተው ወደ ቡልጋ ለመዞር ጉዞ ቀጠሉ። እሳቸውም ገሊላ በነበሩበት ጊዜ ለሠራዊታቸው ግብር ሲያበሉ መሰንበታቸውን የሚያስታውሱ አሉ። ነገር ግን ከጠራ በሮች በኩል የሚጓዝ የጠላት ጦር ሰቃ ከተባለው ቦታ አጋጠማቸውና ግንቦት 25 ቀን በተካሄደው ውጊያ እግራቸውን በጨረፍታ ተመቱ።

ግንቦት 26 ቀን 1930 ዓ.ም ጊና አገር አጠገብ፣ ወልዶ ሰሞት ከተባለው ቦታ ታላቅ ጦርነት ተደረገ። ይህ ወልዶ ሰሞት የተባለው ቦታ በደጋውና በቆላው አገር መካከል እንደግድግዳ የቆመ ገደል ነው። አርበኞች የገደሉን ጫፍ ይዘው በአማርኛ ሜዳ ላይ የሚርመሰመሰውን የጠላት ወታደር በጥይት ጨፈጨፉት። ፊታውራሪ ሽበሽ ዓለማየሁን ጨምሮ ብዙ ጀግኖች እዛ ወደቁ። አርበኞች የሞቱትን ቀብረው፣ በድንጋይ ጥራ በኩል አድርገው የቁሊሎን ተራራ በመጠጋት መርቆሬ አገር ሠፈሩ።

ጠላት አርበኞች በቆላው የሚያደርጉትን ጉዞ ለማደናቀፍ ለውኃ በደጋው በሙጥማየስ ዙሮ፣ በቁንጥሌ ስብሮ ግንቦት 28 ቀን 1930 ዓ.ም መገሬ ዛላ ገባ። በአርበኞች በኩል ላለማስገባት የተደረገው መከራ ውጤት ሳያስገኝ ቀረ። በማግስቱ ግንቦት 29 ቀን 1930 ቤትና ቤተክርስቲያን ሲያቃጥል፣ ሰው ሲረጅ ዋለ። አቶ አበራ የተባለ የምስለኔ አገር ሰው አንድ ካርታ የቤልጅግ ጥይት በኪሱ ውስጥ ስለተገኘበት፣ አሱን ጠላት ከግንድ ጋር

የፈጥኝ አስሮ፣ በላዩ እንጨት አስቀልሎ፣ በእሳት አቃጠለው። በዋዜማው እንደ መምሬ አባት የተባሉ ቄስ ከአማኑኤል ቤተክርስቲያን ጋር አቃጥሎ ነበርና፦ «አርክ /ጣልያን/ አብሬ መምሬ አይልም፣ አያውቅም።» ተባለ።

በዚህ ወር የተካሄደው የጣልያን ዘመቻ ባለብዙ ፈርጅ፣ ክባድ እንዲሁም ጭካኔ የተሞላበት ነበር። የበረከት ሽማግሌዎች እንዲያነጋግሩት ጥሪ አደረጉ። እነሱም አስቀድሞ በሙሴ ቀስተኛ የተደረገውን ሙከራ ሰምተው ነበርና ለዕርቅ ጉዳይ ይሆናል በማለት ቀረቡ። እሱ ግን ኡመር አሊ ከሚባል ሰው የቀረበለትን ሰብቅ በመስማት ብቻ እርስበርሳቸው በገመድ አስተሳስሮ ሦስት ቀን ሙሉ በረሃብና በውሃ ጥም ከአሰቃያቸው በኋላ፣ ግንቦት 28 ቀን 1930 ዓ.ም በመትረየስ ጨረሳቸው። ሬሣቸውም እንዳይታይ ጋዝ አርከፍክፎ በእሳት አቃጠላቸው። ጠላት ከተባረረ በኋላ ከእነኚሁ መካከል ስማቸው ታውቆ ሊመዘገብ የቻለው የሦስት መቶ ሰማንያ ሦስቱ ብቻ ነው።[12]

እነዚህ ሰዎች ያለቁት በታላቅ የክህደት ሥራ ስለሆነ ለጨን ይገባል። ጣልያን ሽማግሌዎችን የጠራው አርግጥም ሀገሩን እንዲያረጋጉለት ነበር። ነገር ግን ከላይ ስሙ የተጠቀሰው ኡመር አሊ የተባለው ከሐዲ፣ ቀደም ሲል ፊታውራሪ ከበደ ወልደጊዮርጊስ፣ የወንድማቸውን የፊታውራሪ መኮንን ወልደጊዮርጊስን ደም ለመበቀል ሲሉ፣ ገድሉ ጭንቅላታቸውን አስቆርጦ ደብረ ብርሃን በመውጣት የተጫወተቡትን ጣልያን ገድሰው፣ ጭንቅላቱን ቆርጠው፣ ሦስት ቀን ሙሉ ጊጤ ሲጫወቱበት ሰንብተው፣ ስድስቶ ከተባለው ቦታ ከትንጭብ ግንድ ላይ፣ በዓይኑ ጉድጓድ ተክለውት ሄደው ነበርና፣ እሱን አንስቶ ከድብኝቱ ውስጥ በመደበቅ አቆይቶ አዲስ ለመጣው ጣልያን በሥጢር አስረከበ። አስረክቦም ይህንን ሥራ የሠሩት የእነዚህ አሁን ለአስታራቂነት የቀረቡት ሽማግሌዎች ልጆች መሆናቸውን አሳበቀ። ጣልያኑም ራሱን የተቆረጠው ወንድሙ ነበርና ነገሩን ሳያጣራ፣ ሽማግሌዎችን ከላይ ዙሪያገባቸው ዓይነት ረበረባቸው። ሆኖም ሬሳውን ማቃጠል ሲጀምር ዘጠኝ ሰዎች ከጥይቱ ድብደባ ድነው ኖሮ ሮጠው አመለጡ። ምሽቱም አገዛቸው።[13] የጣልያኑም መኮንን የወሰደው እርምጃ ጭካኔ የተሞላበት ቢሆንም በእሱ ላይ ድ ሳም። ክህደቱን ባካሄደው በኡመር አሊ እንጂ። የሚያስቆጨው ነገር ደግሞ ጠላት ከተባረረ በኋላ ከሃዲው ኡመር አሊ ማንም ላይነካው እንደተጀነነ መኖሩ ነው።

የጠላት አመጣጥ ክባድ ነበርና፣ ደግሞም ፋታ የሚገኝበት የክረምቱ ወራት ለመግባት ገና አንድ ወር ቀርቶት ነበርና፣ አርበኞች ጋደራ ላይ ስብሰባ አድርገው ተማከሩ። ሙሴ ቀስተኛ ስለጠላት የሰጠው ሪፖርትና የጠላት አመጣጥ ተገመገመ። ከወሎ፣ ከትግራ፣ ከጐንደር፣ ከጐጃም ሰባ ሁለት ሺህ ወታደር አስመጥቶ ደብረ ብርሃን ላይ ማስፈሩ ታወቀ። ከዚህም በስተቀር ከሐረር ሌላ ጦር አምጥቶ ናዝሬት ላይ አስፍሮ ነበር። ይህ ሁሉ ከታየ በኋላ ሙሩ በየበሩ ተደለደለ። ራስ አበበና ደጇዝማች ዘውዴ በቁሱ አገር፣ ቀኛዝማች

ኃይለማርያም ማሞ በወልዴ አገር በኩል ተመደቡ። የጠላት ጦር በብዛት መጣ።

ቀኛዝማች ኃይለማርያም ማሞ የነበሩበትን ከጠቋሚ በመረዳት ሌላውን ትቶ ወደ እሳቸው አመራ። ቀኛዝማች ኃይለማርያምም የጠላትን አመጣጥ ከገበሬ ሰምተው ተዚጋጁ።[14] ግንቦት 29 ቀን 1930 ዓ.ም ሾላ ገበያ ደብር ከተባለው ቦታ ጦርነት ተደረገ። ጦርነቱ ከቀትር እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ቆየ። አርበኞቹ ጠመንጃና መትረየሶቻቸው ሲግሉ በውሃ እያቀዘቀዙ የጠላትን ወታደር ረፈረቃት። ጠላትም በመትረየስና በጠመንጃ በመድፍ አጥብቆ ተዋጋ። ግንቦት 12 ቀን ተማርኮ ከአርበኞች ጋር ቆይቶ የነበረ የጠላት ወታደር እንደገና ተመልሶ ከወገኖቹ ተቀላቀለ። ሁኔታውን አስረዳ። ጠላት ማፈግፈግ በጀመረ ጊዜ ቀኛዝማች ኃይለ ማርያም ማሞ በደረታቸው ተኝተው ይዋጉ ከነበረበት ቦታ ቀና ሲሉ ግንባራቸውን ስለተመቱ በቅጽበት ሞቱ። ሙሉ ቀን ተኝተው ሲዋጉ ከዋሉበት ቦታ ቀና ያሉት አንድ የጠላት መትረየስ ተኳሽ ሞቶ ሊማረክ ተጋልጦ ነበርና፣ እሱን ለማንሳት የአርበኞችን ዓይን ለማዳለጥ ነጭ መሐረብ እያረገበ የመጣውን ጣልያን የገደሉበት አቶ ኃይለሥላሴ ዓለሙ የተባለ አርበኛ ለማመስገን ነበር። የሞቱትም 370 ጥይት ከተኮሱ በኋላ መሆኑ በታሪክ ተመዝግቦአል። ሌሎችም ብዙ አርበኞች ሞቱ፤ ቆሰሉም። የተነሰብትን ፅድል ፈንታ ተቀበሉ። መሉቀን በዋለው ጦርነት፣ ራስ አበበና የደኛዝማች ዘውዴ አንዳችም ዕርዳታ አለማድረጋቸው የቀኛዝማች ኃይለ ማርያምን ሰዎች አሳዘነ። ተሰይተው ወደ ግንደ በረት ለመዞራቸውም ምክንያት ነበር። ለጠላት ግን አንድ እፎይታ ሆነ።

ግንቦት 30 ቀን 1930 ዓ.ም በዚሁ በሾላ ገበያ አካባቢ አልፎ አምባ ፈላ ጦርነት ተደረገ። ጦርነቱ በሁለት ገጽ የተከፈለ ነበር። የደብረ ብርሃኑ የጠላት ጦር በኩቱ አድርጉ በሾላ ገበያ፣ የከረሣሹ ደግሞ ከሰምን ተሻግሮ በመስኖ ማርያም መጣ። አርበኞቹ በሁለቱም ወገን በርትተው ተዋጉ። ቀን ሲመሽ በሰቻት በኩል አድርገው ወደ ሞታያለ ሄዱ።

ሁለት መቶ ያህል ባንዶች፣ በሁለት አዝማቾች እየተመሩ ሰኔ 4 ቀን 1930 ዓ.ም መጡ። ሐሳባቸው አጥቅተው ሰጌ ታቸው ለጣልያን ግደይ በመጣል ለመፎከር ነበር። ብዙ ባንዳ በየጊዜውና በየቦታው መጥቶ እንደ ሁኔታው ተመልሶአል። በአርበኝነት ሥራ ላይ የተሰየ ውጤት ከአሳየው በስተቀር አብዛኛው የባንዳ ዘመቻ አላስፈላጊ እንደ መሆኑ በዚህ መፀሐፍም አልተነገረም። ይኼኛው የባንዳ ዘመቻ ግን ሊጠቀስ የሚያስፈልግበት ምክንያት አለ። ስለዚህ እንደሚከተለው፣ በአጭሩ እጠቅሰዋለሁ።

አርበኛው በፍጥነት ከበባቸው። ተኩስ አልከፈቱምና፣ መከበባቸውን እንዲያውቁት አደረገ እንጂ አልነካቸውም ነበር። ነገር ግን ጉዳዩ በዚሁ አላበቃም። ባንዶቹ መልእክት ወደ ጌታቸው በራዲዮ አስተላልፈው ኖሮ አይሮፕላን መጥቶ አካባቢውን ይማትር ጀመር። አቶ መኮንን ሽፈራው

የተባለው ሰው ቀደም ብሎ ከጠላት ከድቶ ከአርበኞች ጋር ተቀላቅሎ ነበርና፣ ዘዴውን በማወቅ ነጭ ሸማ መስቀያ አንጥፎ አሳየው። አይሮፕላኑም ምልክቱን አይቶ ለባንዶች የመጣውን እርዳታ አርበኞው ሠፈር ላይ አራገፈ። አራግፎ ሲጨርስ ቀኛዝማች አበበ በዛ የተባለ ጀግና በመውዜር ጠመንጃ አይሮፕላኑን መታው። ነጂው ከነአይሮፕላኑ እንደ ምንም አዲስ አበባ ደርሶ ሌላ አይሮፕላን በማምጣት አካባቢውን በቦምብ ደበደበው። ሆኖም አጣጣሉ ብብስጭትና በፍርሃት ስለነበረ ቦምቡ የትም ተበተነ። በአርበኞች ላይ አንዳች ጉዳት አላደረሰም።

ባንዶቹ ይህም አልበቃ ብሎአቸው ሌላ ቴሌግራም ስለአስተላለፉ፣ ጠላት በአይሮፕላን መልእክት በተነሳቸው። መልእክቱም፣ "...ከቦታው እደገኛነት የተነሳ መጥተን ልንረዳችሁ አንችልም። ጦር ይቀርባል። በሦስት ቦታ መድፍ ይተኮሳል። በዚያን ጊዜ ክቡን ሰብራችሁ ውጡ" የሚል ነበር። መልእክቱን አርበኞቹ አግኝተውት ነበርና፣ ባንዶቹ መውጣት አልቻሉም። ሰወሬ ነጋሪ ሳይተርፉ፣ የውሃ ሽታ ሆነው ቀሩ። ከዚህም በስተቀር አሥራ ስድስት ሺህ ጥይትና ብዙ ፍርኖ፣ ሻይ ቅጠል፣ ዱቄት አገኙ። ምሥጢር ያለባቸው ፅሑፎችም ተገኙ። ፈንጠዚያ ሆነ።

ከታች በሀገረ ማርያም፣ ከላይ በፋሪ በኩል የጣልያን ጦር መጣ። አርበኞቹም በሁለቱም ወገን ገጠሙት። በሁለቱም ወገን ድል እየመቱ ወደየመጣበት መለሱት። ብዙ በቅሎች፣ አረቄና ስንቅ እንደ ተጫነ ተማረከ።

አርበኞች ወደ በረከት ሄዱ። ጠላትም ታቹን በሣርአምባ፣ ላዩን በወና መጣ። አርበኛው በሦስት ወገን ንጉሡን ይዞ ወደ ቡልጋ ተመለሰ። ሁለተኛው ወደ መስጊድ ሄደ። ሦስተኛው እንዶዲ ሠፈረ። እንዶዲ የሠፈረው ቡድን ሰኔ 12 ቀን 1930 ዓ.ም ኮካ ከተባለው ቦታ ከጠላት ጋር ተዋጋ። ጥሩ ጦርነት ነበር። ሴት ወይዘሮዎች ሳይቀሩ በጠመንጃና በመትረየስ ሲዋጉ ዋሉ። የትልቁ የውሃ መትረየስ እግር ሳይደርስ ቢቀር፣ አርበኞች መትረየሱን ከወይራ ግንድ ባላ ላይ አስደግፈው ሲሰሩበት ዋሉ። ጠላትም ወደ መጣበት ተመለሰ።

ራስ አበበን ጠላት አይሉባቸው ነበርና ሌሊቱን ምክር ተደርጉ ሠራዊቱ አሳቸውን ለመቀበል ወደ ወክፈሌ ሄደ። ይህ በመሆኑ ጠላት የሌባ መስቀያን ተራራ ሰኔ 13 ቀን ያዘ። ራስ አበበ ወደ ቡልጋ ሲጓዙ ቡርቃ ከተባለው ቦታ ከጠላት ጋር ተገናኝተው ውጊያ ተካሄደ። ሌላው ቡድን ደግሞ ነባሮች ከሌላ አምባ ተዋግቶ አሸነፈ። አንድ አልቤን መትረየስና ስንቅ ማረከ። ሀገሩ በመጎዳቱ ምክንያት ምግብ እንደልብ አይገኝም ነበርና ስንቅና ክብት መማረኩ ረዳው።

በጉንቢንሣ በኩል አንድ በጀነራል የሚመራ የጠላት ጦር መጣ። አርበኞውም በጠነከረ መንፈስ ሰኔ 15 ቀን 1930 ዓ.ም ገጥመውት ወጉት። የጠላት ጦር በሶማሌና በሊቢያ ወታደር የተሞላ ነበር። እሱንም ድል አድርገው የጀነራሉን የማዕረግ ልብስ አስጥለው አባረሩት። የጠላት ጦር

ማሣሪያውን ከማሸላ ጉድጓድ እየጨመረ፣ ሬሣውን እያቃጠለ፣ ሽሽቶ በጮባ በኩል ወደ ምንጃር ተሻገረ።

በፊታውራሪ ወልደፃድቅ ዘውዴ የሚመራው አርበኛ ከመሣሪ በመንቀሳቀስ ሸላ ገበያ ጉርፍ ሐምሌ 19 ቀን 1930 ዓ.ም ከጠላት ጋር ጦርነት አደረገ። አንድ መድፍ ከነጥይቱ ጋር ማረከ። የዚህ መድፍ ጉዳይ ምስጢር እንደሆነ ቀረ። መድፉ መማረኩ መማረክ ነው። የተማረከውም በፊታውራሪ ወልደፃድቅ ዘውዴ መሆኑ እርግጥ ነው።[15] ነገር ግን በዚህ ምርኮ ምክንያት የተካሄዱት ወሬዎች አስገራሚ ናቸው።

በመድፉ ምርኮ ሲፈክር አደረ። ጠባዩን የሚያውቅ ስለአልነበር አባላቱ አልተመረመረም። በማግስቱ ጥዋት ሲታይ ቁላው ወልቆ ባዶውን ተገኘ። ማታ አይተነዋል የሚሉ ብዙዎች ናቸው። በሌላ በኩል ደግሞ መድፍ ከመማረኩ በፊት ጣልያኑ የሚያብለጨልጭ ነገር ሲወረውር ታይቶአል የሚሉ ተነሱ። ሲወረውር ታይቶአል የተባለው ቦታ አንድም ሳይቀር ተበረበረ፣ አልተገኘም። ሲሉ ሰማሁ እንጂ አየሁ የሚል ስለጠፋ ወሬውም ራሱ አባት የሌለው ሆነ። መድፉም ባዶ ስለሆነ ሳያገለግል ቀረ። ስለዚህ ተፈታቶ የሰው ሬሣ በመምሰል በሣጥን በብርሃን ዮሐንስ ተቀብሮ ቀረ። ጠላትን ለማስደንገጥ ሲባል ሌላ የመድፍ አፈሙዝ ከጥቁር እንጨት በምስጢር ተፈለፈለ። የፈለፈሉትም የሙገሬው አናጢ ግራዝማች ሽንቁጤ ወርውሬ ነበሩ። የተፈለፈለው የእንጨት አፈሙዝ ጅሉ አገረ ማርያም ከቤተክርስቲያኑ ሥር ከግንድ ጋር ታስሮ የመድፍ ጥይት ተቆረቆረበት። ጥይቱ ካከምሱር ላይ በቤልጅግ ጥይት በባላምባራስ መሰኳይ ሥዩም ተመታ። የመድፉ ጥይት ተተከሰ። ድምፁም ልክ የመድፍ ድምፅ ነበር። እስከ ጉና አገርና ሰደስት ከተማ ድረስ ተሰማ። ጥይቱም ሰለሰ፣ ዋዲያት ከተባለ ቦታ መታ። ሐቁ ይህ ሆኖ ሳለ፣ ከጠላት መባረር በኋላ ደግሞ መድፉን የማረኩት የቀኛዝማች ኃይለማርያም ማሞ ሰዎች እንደነበሩ ተደርጉ ተነገረ። ያሳዝናል።

አንዱ ጦር ሲሸነፍበት ሌላ ማቅረብ የጣልያን ሥርዓት ስለሆነ፣ ሌላ ጦር አመጣ። ዓላማው አርበኞችን ለመጨረስ፣ ካልተቻለም አታክቶ ለመበተን ነበር። ጦሩም ከሐረር፣ ከሞጆና ከደብረ ብርሃን የተንቀሳቀሰ ነበር። የደብረ ብርሃኑ በሸላ ገቢያና በደብር በኩል፣ የሞጆው በዶፋ፣ የሐረርጌው በዶይታ መጣ። አርበኞቹም ቦታ ቦታቸውን ተከፋፈሉ። ከማሸ የመጣው ለፊታውራሪ አርጋው ቁንጮና ለፊታውራሪ አጐናፍር ተሰጠ። የሐረርጌው ለራስ አበበ ሆነ። በዚህ ዓይነት ሰኔ 21 ቀን 1930 ዓ.ም በሦስቱም ግንባር በአንድ ጊዜ ገጠሙት። አንዱ የጠላት ጦር ሌላውን እንዲረዳ ስለተደረገ በሦስቱም ግንባር ጠላት ድል ሆነ። ጥሩ ሥራ ተሠራ። ቀኛዝማች ገብረኪዳን ጉም የተባለ ጀግና አንዱን አዝማች በትግል ጥሎ፣ በሽጉጥ ገድሎ ተቀባበት።

ሐምሌ 19 ቀን 1930 ዓ.ም አርበኞች ከምሽጉ አጠገብ ሄደው ጣልያንን ገጠሙት። ወደምሽጉም እንዳይገባ፣ ገሚሶቹ በአቋራጭ በሩን ለመያዝ አስጨንቀው ስድስት ጣልያኖች ገደሉ። ባንዳ ኩቱጦር አልገባም። ልዩ ልዩ የጦር መሣሪያ ተማረከ።[16]

ከቡልጋ መልስ ሆነ። ንጉሠ ነገሥት መልአከ ፀሐይ ኢያሱ ሰበርንጎ፣ አሰፍ አገር፣ አቶ ታረሱ ቤት ሠፈሩ። ከዚያም ፍርድ ተሰጠ። የጦር ምክርም ተደረገ። የፍርዱ ጉዳይ እሱን በሚመለከተው ክፍል ይነገራል። አሁን የጦር ምክሩን ሂደትና ውጤት እናያለን። ሠሣኝነት ያለው ውጤት ያስከተለ ምክር ነውና፣ በጥልቅ ሊመረመር ይገባል።

ጠላት አርበኞችን ከአጠቃባቸው ስልቶች አንዱ፣ ቁልፍ በሆኑ ቦታዎች ምሽግ በመመሸግ ጦር ማስቀመጥ ነበር። በዚህ ሥልት መሠረት ጠላት በደጋው ሸኖ፣ ኮርማች፣ ጫጫ፣ ደጃች፣ መሰቢት፣ ጊና አገር፣ ሸላ ገበያና ወጨብያ መሽጎ ነበር። በሸንኮራ በኩል ጨፈ ደንላ፣ ባልሥ፣ በምንጃር ደግሞ አረርቲ፣ ጮባ መሸጣ ላይ ምሽግ ሠራ። ይህ አልበቃው ብሎ ከቆላው ውስጥ ገባ። ገብቶም በረከት ላይ ስድስቶ፣ ማህሙድና ጂፋር ከተባሉ ቦታዎች፣ እንደዚሁም ጉቤንሣ ላይ መሸገ።

የአኩፎ አገሩ ምክር፣ ይህንን ገምግሞ ምን ይሻላል በሚል ጥያቄ ላይ ያተኮረ ነበር። በረከት የነበሩትን ሦስት ምሽጎች ለማጥቃትና ለመደምሰስ ተወሰነ። የጦር ዝግጅት፣ የወታደር ድልድል ተደረገ። ሦስቱ ምሽጎች አንድ መደዳ ላይ ናቸው። እርስበርሳቸው መደጋገፍም ይችላሉ። ከዚህም በስተቀር ቦታው ለአይሮፕላን ድብደባ አመች ነበረ። ድልድሉ የተሠራው ይህ ሁሉ እየታወቀ ነው።

በድልድሉ ዋናው ምሽግ ስድስት ነበር። በዚህ ግንባር የተሰለፉት የወጣቱ ንጉሠ ነገሥት ሞግዚት ደጃዝማች ኃይሉ ወልደ መድህን ነበሩ። የጂፋር ምሽግ ለፊታውራሪ ወልደፃድቅ ተሰጠ። እሱም በጥንካሬ ሁለተኛው ነበር። ራስ አበበ የመሐመድን ምሽግ ያዙ።

ወታደሩ ሚጢ ገርማን በእርጋታ ተሻግሮ ቁሊሱ ከተባለው ተራራ ሥራ መርቆሬ አገር ተሰበሰበ። ጣልያን ከምሽጉ ውስጥ ሆኖ ይጠባበቅ ነበር። የአርበኞቹን የማጥቃት ዘመቻ ማወቅ አለማወቁ አልተረጋገጠም። አውቆ ቢሆን ኖሮ የአይሮፕላን ሽፋን ቀደም ብሎ ያዘጋጅ ነበር። ቢሰማም እጅግ ዘግይቶ መሆን አለበት።

ጦርነቱ ከሌሊቱ በ11 ሰዓት በአርበኞች ተከፈተ። የጠላት ጦርም ምሽጉን ለመከላከልና ከቻለም አርበኞቹን ለማባረር ከምሽጉ ወጥቶ ተዋጋ። ታላቅ ውጊያ ተካሄደ። አርበኞች ምሽጉትን ለመያዝ ተቃረቡ። በተለይም ፊታውራሪ ወልደፃድቅ ዘውዴ የጂፋርን ምሽግ ለመስበር ተቃርበው ሳለ ወደ አሥር ሰዓት ገደማ አምስት አይሮፕላኖች መጥተው በቦምብና በመትረየስ ድብደባ አካሄዱ። ጠላት እየሸሸ ከጅሽንቹ ተሸገሸገ። በሜዳው ላይ ውጊያ

አርበኞች ብዙ የጠላት ወታደር ፈጅተው ነበር። አሁንም ደግሞ አርበኛው ወደ ምሽጉ ሲጠጋ አነሱ በተራቸው ፈጁት። ምንም አንዱ በጥይት ተመትቶ ቢመለስ፤ አራቱ አይሮፕላኖች ድብደባቸውን ቀጥለው ብዙ ጉዳት አደረሱ። አርበኛው ቁስለኛውን እየያዘ ተመለሰ። አብዛኛው ሬሳ ከዚያው ከወደቀበት ቀረ። በከንቱ የፈሰሰ ደም ሆነ። ቢሆንም አምስት ጣሊያኖች ተገደሉ። ሁለት መትረየስ ተማረከ። ከፍ ሲል የተጠቀሱት ነጉሠ ነገሥትም ሠራዊታቸውን አስከትለው ወደ ዲቤና ዞማ ሄዱ።[17]

ውጤቱ ሲታይ የአኩፎ አገር ምክር ጤናማ አልነበረም። እነዚህ ሦስት ምሽጐች ጠንካሮች ነበሩ። እነሱን ለማጥቃት ከመሞከር ይልቅ መታገሡ በቀለለ ነበር። ከዚህ አንፃር ሲታይ ምክሩ ጀግና የቆመበት እንጂ፤ ሽማግሌ የተቀመጠበት አይመስልም። የጦር ድልድሉም ትክክል አልነበረም። በዋናው በስድስት ምሽግ መሰለፍ የነበረባቸው ዋናው የጦር አዛዥ ራስ አበበ እንጂ ደጃዝማች ኃይሉ አለነበሩም። ለእሳቸው በሞግዚትነታቸው ወጣቱን ንጉሥ መጠበቅ ይበቃቸው ነበር። አርበኛው ሊያገግምና ሰተኩታዩ ዘመን ትግል ሊዘጋጅ ይችልበት በነበረው በክረምቱ ወራት፤ ለዚህ ዓይነት ለጉስቁልና ተዳረገ። ጦርነቱንም የድንጋይ ውቅር አድርጐ ገመተው፤ እንደዛውም አሰው።

ለሁሉም የሠራዊቱን ልቡና እንደገና መልሶ ለመገንባት ጥረት ተደረገ። መጠነኛ ሹመትም ተሰጠና መስከረም 16 ቀን 1931 ዓ.ም ዞማ በተባለው ቦታ ታላቅ ሰልፍ ተደረገ። ከሠራዊቱ ብዛት የተነሣ ሰልፉ ከ8 እስከ 12 ሰዓት ቆየ። በወቅቱ ንጉሠ ነገሥት መልዐክ ፀሐይ በመባል ነግሠው ለነበሩት፤ ከአዲስ አበባ ተሰፍቶ የመጣ ነው ተብሎ አዲስ የማዕረግ ልብስ ለብሰው በዓሉን አከበሩ። ሌሊቱን ግን ባልታወቀ ምክንያት ታመው አደሩ።

ይኸ በእንዲህ እንዳለ፣ ጣልያን ከመስከረም 18 ቀን 1931 ዓ.ም ጀምሮ በዲቤ አካባቢ ታላቅ ጦርነት አካሄደ። የወጣቱን ንጉሠ ነገሥት መታመም ሰምቶ ሳይሆን አልቀረም። አርበኞች የታመሙትን ንጉሠ ነገሥት በቃሬዛ፣ በምሥጢር ከቦታ ወደ ቦታ እያዘዋወሩ በርትተው ተዋጉ። ዕድሜአቸው ይቀራረብ መልካቸውም ይመሳሰል ነበርና፤ አቶ /ደጃዝማች/ አሉላ በቀለ፤ በሊቀ መኳስነት ከንጉሡ በቅሎ ላይ ተቀምጠው ለሕዝብ ይታዩ ነበር።[18]

ወጣቱ ንጉሥ በዚህ ዓይነት ሲሰቃዩ ሰንብተው፣ መስከረም 27 ቀን 1931 ዓ.ም ሌሊት ወደ ገና መምቻ ሲወስዱአቸው አረፉ። ጠላት አውጥቶ አንዳይጫወትባቸው በመስጋት፤ አርበኞች እና መኳንንቶቻቸው በቃሬዛ ወስደው በታላቅ ክብር በሥውር ቀበሩአቸው።[19] ለወጣቱ ንጉሠ ነገሥትም፤ በነገሠበት በወክፈሌ ሚካኤል፤ መስከረም 30 ቀን 1931 ዓ.ም ውሎ ተዋለላቸው፤ ፀሎተ ፍትሐትም ተደረገላቸው። «በአንድ ሀገር ሁለት ንጉሥ እንደምን ይሆናል?» የሚለው ጥያቄ መፍትሔ አገኘ።

የወጣቱ ንጉሠ ነገሥት ሞት በአርበኛው ላይ ታላቅ ድንጋጤ ሲያደርስ፤ ለጣልያን ደግሞ አንድ እፎይታ ሆነ። በወቅቱ ለንደን ለነበሩት ተዳማዊ ኃይለሥላሴና በሀገር ውስጥ በነበሩ ደጋፊዎቻቸው ዘንድ እንደዚሁ እፎይታ እንደሆነ መናገር አያስፈልግም። ምንም ያህል ሳይቆይ፤ ሞግዚታቸው ደጃዝማች ኃይሉ ወልደመድህንና የገንዘብ ኃላፊያቸው የነበሩት በጅሮንድ ወልደ ዮሐንስ ሞቱ። ዝርዝሩን ወደፊት እንደርስበታለን። ቀድሞ የአቲሣ ገዳም አበምኔት የነበሩት፤ እጨጌ የነበሩት መምህር በላይ መነኑ። መጨረሻ የታዩት የረር አካባቢ አንዲት ዋሻ ውስጥ ነው።

የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ወዳጅና ጉዳይ አራማጅ የነበሩት ደጃዝማች መንገሻ ወሰኔ በበኩላቸው ደብረ ብርሃን ሄደው ለጠላት ገቡ። የሚገርመው የልጅ ኢያሱ ወዳጅ የነበሩት የደጃዝማች መኮንን ወሰኔ ልጅ፤ ገብረክርስቶስም አብረው መሄዳቸው ነው። ሌሎች አሽከሮቻቸው ተበታተኑ፤ በጦርነቱ አለቁ። አንዳንድ የተረፉትም ስካራሞች ሆነው ቀሩ። የቤተ መንግሥት ኃላፊ የነበሩት ከንቲባ /ደጃዝማች/ ኃይለሥላሴና ፀሐፌ ትዕዛዝ የነበሩት ፊታውራሪ /ከሎኤል/ ኪዳኔ ወልደጊዮርጊስ ግን ተረፈው በህይወት ኖሩ። እንዲያውም በተዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግሥት ሞገስ ሳያጡ፤ ሹመት ጭምር አገኙ።

ከዚህ ላይ ስለ ንጉሠ ነገሥት መልአክ ፀሐይ ጥቂት መናገር ይገባል። አልነገሡም የሚሉ አሉ። ይህ አባባል እዚህ አዲስ አበባ ከተገባ በኋላ የተሰማ ነው። እውነት አይደለም፤ ነግሠዋል። በቅድሚያ በረከት፣ ወክፈሌ ሚካኤል ነሐሴ 21 ቀን 1924 ዓ.ም በካህናቱ እጅ ቅብአ መንግሥት ተደርጉላቸው፤ መልአክ ፀሐይ ኢያሱ ተብለው በንጉሥነት ደረጃ ነግሠዋል። ንጉሥ የተባሉትም ንጉሠ ነገሥትነቱን ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ለመጠበቅ ታስቦ ሳይሆን አልቀረም። ደግሞም ሚያዝያ 1930 ዓ.ም ክስም ወይራ፤ ጀሎ አገረ ማርያም በእጨጌ ገብረጊዮርጊስ እጅ ተቀብተው ንጉሠ ነገሥት ተብለው ነግሠዋል። ይህም አርበኛው በአመራራቸው ስለአመነበት መሆኑን መገመት ይቻላል። መንገሣቸውን መላው አርበኛ በዓይኑ ያየው፤ በጆሮው በወቅቱ የሰማው ነገር ነው። ልጅ መልአክ ፀሐይ እየተባለ የተፃፈው ከፍርሐት የተነሣ ነው። ስለዚህ አልነገሡም የሚለው የአዲስ አበባ ከንቱ ወሬ መሆኑን ያሳያል።

ሌሎች ደግሞ መንገሳቸውን ያምኑና የልጅ እያሱ ልጅ አልነበሩም ብለው ይጠራጠራሉ። ይህም እውነት አይደለም። ልጅ እያሱ በአንድ ጋብቻ የወኑ ስለአልነበሩ፣ ይህ ሃሜት በልጆቻቸው ሁሉ ያለ ነው። ነገር ግን መልአክ ፀሐይን በተመለከተ የተወራው ትክክል አይደለም። የተወራውም ጠላት ከተባረረ በኋላ እዚህ አዲስ አበባ ነው። ልጅ መሆናቸውን በወቅቱ ሠራዊቱም ሕዝቡም አምኖበታል፤ ስላመነበትም በወቅቱ አንግሷቸው ነበር።

መልአክ ፀሐይ ኢያሱ ተብሎ የነገሡው ወጣት እንግዳ እሸት ኃይሌ የተባለው ልጅ ነው። በዚህ ጥያቄ ላይ ተነጋግረናል። የተገኘውም አብዙ ገዳም

መድኃኔአለም፣ አብ ምኔት አባ ደርበው እጅ ነው። ጥያቄው እንግዳ እሸት ማነው? የሚል ነው። ከሀገር ሽማግሌዎች የተገኘው ቃል እንዲህ የሚል ነው። ልጅ እያሱ ከሥልጣን በወረዱ ጊዜ፣ በ1909 ዓ.ም ሐረር ከተማ ነበሩ። ወሬውን እንደሰሙ ከአዳል ባላባቶች የአንዱን ሴት ልጅ ይዘው ወደ አባታቸው ወደ ንጉሥ ሚካኤል ሄዱ። ተይዘው ሰላሴ፣ ፍቼ በቀዩበት ጊዜ ይህች ልጅ ከእሳቸው ፀነሰች። እርግዝናዋ እንደታወቀ ወይዘሮ ፀሐይ ወርቅ ዳርጌ ወሰድዋት። በታመነ ሰው ወደ ቡልጋ ከትም ወይራ፣ ጨፋ ርስታቸው ላኩአት። የተላከውም ሰው ከፍቺ እስከ ቅየ ከቢቶ ወስዷት ከደጃዝማች መኮንን ወሰኔ ቤት ለጥቂት ቀን አረፍት ከአደረገች በኋላ ሜጢ ወረዳ፣ ከወይዘሮ ተመናኙ ተክሌ ቤት አረፈች። የወይዘሮ ፀሐይ ወርቅ ሹም የነበሩት አቶ ኃይሌ ሜጢ ድረስ በመውጣት ተረክበው ወደ ቤታቸው ወሰዱአት። ያደረሳትም ሰው ወደ አዲስ አበባ ተመለሰ። ያች አዳል ልጅ ብዙም ሳትቆይ ወንድ ልጅ ወለደች። በ1916 ዓ.ም አካባቢ ስሙም እንግዳ እሸት ተባለ። እሱም የአቶ ኃይሌ ልጅ እንዲመስል ተደርጐ፣ የሚስታቸውን ጡት እየጠባ አደገ። ጀሎ አገረ ማርያም ክርስትና ተነሣ። እናቱም እንደተጠናከረች በሸኜ፣ በበረከት በኩል ወደ ዘመድዎቿ ሄደች። ዘመድዎቿም መልአከ ፀሐይ በነገሡ ጊዜ ገልፀዋል። አርበኞችንም ደግፈዋል።

ወይዘሮ ፀሐይ ወርቅ ደርቤ በተያዙ ጊዜ እንግዳ እሸት ኃይሌ ማን እንደሆነ በልዑል ራስ ተፈሪ መኮንን ዘንድ ታወቀ። የአብዬ ገዳም መድኃኔዓለም አለቃ ሆነው አዲስ ለተሾሙት ለአባ ይርዳው ተሰጠ። ጨፌ የነበረው ፀሐይ ወርቅ ሁዳድ፣ በቀድሞው ሥሪት ከነበረበት ከጀሎ አገረ ማርያም ተነቅሎ፣ ከአሥር አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ከማያንስ ርቀት ላይ ለነበረው ለአብዬ ገዳም መድኃኔዓለም፣ በራስ ተፈሪ ትዕዛዝ ተሰጠ። አባ ይርዳው የኋላ እሸትን በመጠበቅ ለሚሰጡት ውለታ መክፈያ መሆኑ ነው። የጀሎ አገረ ማርያም አለቃ የነበሩት ለአለቃ ውሂበም ምሥጢሩን በመደበቅ ለፈፀሙት በደል፣ ወይም መርምረው ባለማወቅ ላሳዩት ቸልተኝነት ቅጣት እንደነበር ማጤን ይገባል። መልአከ ፀሐይ በነገሡ ጊዜ ሁዳድ እንደቀድሞው በጀሎ አገረ ማርያም ተመለሰ።

መልአከ ፀሐይ እያሱ የመንግሣታቸውና የልጅ እያሱ ልጅ የመሆናቸው ጉዳይ ከተረጋገጠ በኋላ ቀጥሎ የሚነሣው ጥያቄ "ምን ምን ሠሩ?" የሚለው መሆን አለበት። የመልአከ ፀሐይ ኢያሱ መንግሥ የአርበኝነትን ሥራ በሸዋ ላይ በእጅጉ እንደ አጠናከረ ጥርጥር የለውም።መልከ ቀና፣ ደመ ፀራድ፣ እርጋታ ያላቸውና ከሰው ጋር ተባብረው የሚሠሩ እንጂ እኔ ባልኩ የማይሉ፣ በሥጋ ወደሙ የፀኑ ነበሩ።[20] በአባታቸው ዘመን ሰውን ያሰለቸው የመንቀሻቀሻ፣ የጭካኔ ጠባይ አልታየባቸውም። ዕድሜአቸውን ያሳጠረባቸውም ይሽው የሀገሩ ባህልና ሥርዓት፣ እንዲሁም የጦርነት ጊዜ ላይ መሆናቸው፣ ወቅቱ ከሚፈቅደው በላይ ነገርን አስገበው የሚይዙ

መሆናቸው፣ በዙሪያቸው የተተበተበባቸውን የነገር አሸክላ መፍታት አቅቶአቸው ሳይሆን አልቀረም።

ወደሠሩት ሥራ ስንመለስ ብዙ ሹመቶች ሰጥተዋል። ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ባለሥልጣኖች መካከል በሀገር መከላከል የቆመ ሰው በወቅቱ እምብዛም ያለመገኙቱን ያህል፣ መልአከ ፀሐይ ከሸሙት መካከል አድሙን ሰውጦ ከጠላት ጉን የቆመ አልታየም። ራስ አበበ በቡልጋ አርበኛ ዘንድ ሙሉ ተቀባይነት ያገኙት በመልአከ ፀሐይ እያሱ ራስ ተብለው ከተሾሙ በኋላ ነው። በመሆኑም ዕድሜአቸው እና ጊዜው ይፈቅድ የነበረውን ያህል መልካም ሥራ ሠርተዋል።

ስለ አሠራሩ ከተነሳ፣ የወጣቱ ንጉሠ ነገሥት የሥራ አመራር የቤተ መንግሥት ሥነ ሥርዓትን የተከተለ ነበር። የሥራ ድልድል የሚደረገውም እየተጠናና እየታሰበበት እንጂ በጅምላ፣ በአንድ ጊዜ አልነበረም። ምንም አንዳንዱ ቀደም ብሎ የተጠቀሰ ቢሆን፤ በሞቱበት በመስከረም ወር 1931 ዓ.ም የነበረውን የሥራ ድልድል እንደገና ማየት ጠቅላላ ሁኔታውን ለመገንዘብ ይረዳል።

- ቀኛዝማች ኃይሉ ወልደ መድህን ደጃዝማች ተብለው የንጉሡ ሞግዚትና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ
- በፊት ፊታውራሪ አማረ አየለ፤ ቡኋላ ደግሞ ራስ አበበ አረጋይ የጦር ሚኒስትር
- ቀኛዝማች ስንቅነህ ሊጋባ
- ቀኛዝማች ሺመላሽ የልፍኝ አስክልካይ
- ፊታውራሪ ታደሰ ጌታብቻህ የግቢ ሚኒስትር
- አዛዥ መኮንን ተክለአብ ዋና አዛዥ
- ፊታውራሪ ኪዳኔ ወልደጊዮርጊስ ፀሐፊ ትዕዛዝ
- ግራዝማች አሉላ መርጌ የልፍኝ አሽከሮች ሹም
- ባላምባራስ ገብረዓድቅ ተክለአብ አልባሽ
- ግራዝማች ይትባረክ ፋንታ የንጉሡ የክብር ልብስ አዘጋጅ
- ቀኛዝማች በቀለ ወልደመድህን የአንጋችች ሹም
- መምህር ቀፀላ የፍትሕ ነገሥት አውጭ
- አቶ ወልደማርያም የንግሥት ዘውዲቱ በገና ደርዳሪ አጫዋች ነበሩ።

የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማህበር የወጣቱን ንጉሥ መዝግበሳቸዋል። አመዘጋገቡም መሥፍኑን እስከ ጠላት ወረራ ድረስ አባ ደርበው በእንክብካቤ እንደ አሳደጉአቸው፣ ነገር ግን የተገኙት አህያ ሲያግዱ ነው በማለት ነው። ይህንን ነገር አለቃ /ፊታውራሪ/ ወልደፃድቅ ዘውዴ ያውቁ ስለነበር፤ መልአከ ፀሐይ እያሱ የቅዱሥነት ሥልጣን ቢይዙ ኢትዮጵያን ነፃ

ለማውጣት ቆርጠው ለተነሱ አርበኞች እንደሚረዳ እንደ አሳመኑና ወጣቱ መሥፍን መልአክ ፀሐይ ተብለው በወክፈሌ ሚካኤል ካህናት ነሐሴ 21 ቀን 1929 ዓ.ም ሥርዓተ ንግሣቸው እንደተፈፀመ ያረጋግጣል። ማኅበሩ በመዘገበው የህይወት ታሪካቸው ላይ፡- በቡልጋ አርበኞች ምርጫ ወቅቱን እየጠበቀ ሹመት ወይም የማዕረግ እድገት እየተሰጠ በጠቅላላው የሸዋን አርበኞች እየመሩ ከቆዩ በኋላ መስከረም 27 ቀን 1931 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት እንደተለዩ ይገልፃል።

ቀጥሎ የሚነሳው ጥያቄ መልአክ ፀሐይ ሊያሱ ባይሞቱ ኖሮ ምን ይሆን ነበር? የሚል ሳይሆን አይቀርም። ጥያቄው መልካም ሆኖ ሳለ፣ ለዚህ ጥያቄ አንድ ብቻ መልስ ያለ አይመስልም። እንባቢ የራሱን ሀሳብ የመደርደር ሥልጣን ይኖረዋል። በብዙዎች አመለካከት መልአክ ፀሐይ እያሱ እስከ ሰኔ 1932 ዓ.ም ቆይተው ቤሆን ኖሮ ፣ ሞሶሎኒ ከሂትለር ጉን በቆመ ጊዜ እንግሊዞች የሚደግፉት መልአክ ፀሐይን ሲሆን ይችል ነበር። ይህ ቢሆን ኖሮ ደግሞ በኋላ ላይ አርበኛ አይንገላታም፣ አይወድቅም ነበር። ሥርወ መንግሥቱም ወደ ምኒልክ ቤት ይመለስ ነበር። መንግሥቱም የበለጠ ሕዝባዊና ሀገር ውስጥ በቀል ይሆን ነበር።

የመልአክ ፀሐይ እያሱን ነገር እንዲህ ከአጠነፈፍን በኋላ፣ ወደ ጦርነቱ ጉዳይ እንመለሳለን። የቡልጋን ሕዝብ የሀገር ፍቅር ስሜት የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መሄድ እንዳሳቀዘቀዘው፣ የመልአክ ፀሐይ እያሱ ሞትም አላበረደውም። ሕዝቡ ትግሉን ቀጠለ። ጣልያንም በበኩሉ ጊዜ ያጋጠመው መስሎት አርበኞችን የማውደም ዘመቻውን አፋፋመ።

ጠላት ከቆቦ እስከ መስጪ ያለውን ቦታ ያስያ ጀመረ። አርበኞችም በተቻላቸው መጠን ተከላከሉ። ብዙዎች ሞቱ፣ ተመለሱ። በዚህ ወራት በአርበኞች ዘንድ የነበረው ችግር አሰቃቂ ሆነ። ጦርነቱ ከመቼውም ይልቅ ከበደ። ጠላት የንጉሠ ነገሥቱን መሞት አውቆ ነበርና። ገበሬው አልቆና ተበትኖ ነበርና ረሃብ ሆነ። በዚህ ሁሉ ላይ እንቅጥቅጥ የተባለ የወባ ወረርሽኝ ተነስቶ ሕዝቡን ፈጀው። የተረፈውንም አደከመው።

ራስ አበበ የተረፈውን ጥቂት ሠራዊት ይዘው ፍቅሬ ግንብ ወጡ። እዚያም ጠላት ደረሰና መስከረም 28 ቀን 1931 ዓ.ም ታላቅ ጦርነት ተደረገ። እስከ መስከረም 29 ቀን ድረስ በመዓልትና በሌሊት ተዋጉ። ጠላት ገደሉን ሲጠጋ አርበኞች ከላይ ሆነው ናዳ እየለደዱ፣ መርግ እየለቀቁ፣ የእጅ ቦምብ እየወረወሩ ፈጁት። ናዳና መርግ ጠላትን አሸዋ የተሞላበት እያስመሰለ፣ እፍረት እያወረደ፣ አንዱን ባንዱ ላይ ቀለለው። ጠላት ሰባት አይሮፕላኖች አስመጥቶ አስደበደበ። እንደ አልሆነለት ባየ ጊዜ አዲስ ጦር አመጣ።

ጣልያን በአባ ማስያስ አማካኝነት በተካሄደ ጥናት መሠረትና መነሻነት ስለፍቅሬ ግንብ ብዙ ነገር ያውቅ ነበር።[21] ስለዚህ ራስ አበበ ከዚች ተራራ ላይ በወጡ ጊዜ ከወጥመዱ እንደገቡለት አድርጐ ሳይገምት አልቀረም። በዚህ

ምክንያት ጦርነቱ ከባድ እንደነበር ማወቅ ይቻላል። ሰርዳታ የመጣው የጠላት ጦር የቀረበው በውቢር፣ በቱንዴ፣ በቅጣው፣ ቆላውን ደግሞ በአዋሽ ነበር። ጠላት ያካሄደው፣ አርበኞችን ለእንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለመፍጀት ሙሉ ከበባ ነበር። በወጣቱ ንጉሠ ነገሥት ሞት የተደናገጠው አርበኛ ራስ አበበን ደግሞ እንዳያጣ እርስ በርሱ እየተረዳዳ ተዋጋ። በልጅ አየለ ኃይሌና በልጅ ይበርታ ጣዲቁ የሚመራው አርበኛ ከደብረ ብርሃን መሥመር የወጣውንና እመምሕረት የነበረውን ገጠመው። በመስጪ የመጣውን በልጅ ደስታ ሽዋ አርካብህ የሚመሩት ያዙት። የቀረውን ከራስ አበበ ጋር የተከበበው አርበኛ ተጋጠመው።[22]

ከዚህ ላይ መጠቀስ የአለበት አንድ ራስ አበበ የተናገሩት አነጋገርና የሰጡት አመራር አለ። ፍቅሬ ግንብ ዙሪያውን በገደል የታጠረና ላዩ ሜዳ የሆነ፣ መሶብ የሚመስል ቦታ ነው። ራስ አበበ ለመከላከል የተዘጋጁት በዚያ ላይ ነው። መከበባቸውን ነገሩአቸው። የአምባው መግቢያ ዋና በር በጥብቅ እንደ ተያዘ፣ በአግር መተላለፊያ የሆነውም በር እንዲሁ እየተጠበቀ መሆኑን፣ በመንጠላጠል አንድ ሰው የሚወርድባትም ሥርጥ እንኳን ሳትቀር በጠላት ታውቃ እየተጠበቀች መሆንዋን አስረዷቸው። በማንኛውም በር አብሮ ለመውጣት እንደማይቻልም ነገሩአቸው። እጅ እንስጥ ለማለት ሳይሆን አልቀረም። ጀግናው ራስ አበበ "...ታዲያ ሞትን እንጠበቀው..." ብለው በዋናው በር ሠብሮ እንዲወጣ ለሠራዊቱ ትዕዛዝ ሰጡ። ጠላት ሠፈር ያደረጉ እንዲመስለው፣ እሳት በብዛት አስነድደው ከብቱን ዙሪያውን፣ ሰዉን ከመካከል አድርገው ወጡ። ከጥቂት ከብትና ከሦስት ሰው በስተቀር ሌላ ሳይሞት አመለጡ።

ከፍቅሬ ግንብ ጦርነት በኋላ ቡልጋ፣ ጋፍራ ላይ ስብሰባ ተደረገ። በስብሰባው ላይ የቡልጋን ጦር የቆረቆሩት ፊታውራሪ ወልደፃድቅ ዘውዴና ሌሎችም የጦር መሪዎች ተገኝተው ነበር። የወጣቱ ንጉሠ ነገሥት ሞት የፈጠረው ሁኔታ፣ የጣሊያን ጦር መጠናከርና አርበኞች እርስበርሳቸው አለመስማማታቸው አሳሳቢ ከነበሩት ጉዳዮች ዋና ዋናዎቹ ሳይሆኑ አልቀሩም። ከመንዝ፣ ከተጉለትና ከመርሐ ቤቴ አርበኞች ጋር መመካከርም አስፈላጊ ሆነ። በሌላው በኩል ቡልጋን በተጠናከረ ሁኔታ መከላከል አስፈለገ። ስለዚህ የቡልጋ አርበኞች በሀገራቸው ላይ ትግላቸውን እንዲቀጥሉ፣ ራስ አበበ ወደ መንዝ ሄደው በዚያ ያለውን አርበኛ እንዲያስተባብሩ ተወሰኖ፣ ጥቅምት 6 ቀን 1931 ዓ.ም ተነሱ። በጠራ በኩል አድርገው የመኪና መንገዱን በሽኖና በሠርቆሬምስ መካከል አቋርጠው ኘአ ደረሱ። ከዚያም ወደ ደንባ ተጓዘው በሽደማ፣ በሱጣ ሰገድ አድርገው ተገሰቱ ገቡ። ከዚያም ወደ ቡልጋ ዞሩ።

ጠላት አርበኞችን ለማጥፋት የሞከረው የተጠቀሱት ንጉሠ ነገሥቱ በሞቱባት አካባቢ ብቻ አልነበረም፣ በሁሉም አካባቢ ጥቃት አካሂዶ ነበር። ጥቅምት 3 ቀን 1931 ዓ.ም ሰቋርንሃ ጦርነት ተደረገ። በፊታውራሪ

ወልደፃድቅ የሚመራው ቡድን ሌላ ሁለተኛ መድፍ ለመማረክ ተቃርቦ ለትንሽ አመለጠው። ሌላው ጦርነት ደግሞ ጉርማ አገር ነበር። ጣልያንን ቀስበት ከሆነች ቦታ እስኪገባላቸው ጠብቀው ዙሪያውን በመክበብ በጥይት ጠዘጠዙት። የጦር አዝማቹ መኮንን ቆስሎ አመለጠ።

የጨፌ ሹመት በአርበኞች መካከል የፈጠረው ቅሬታ ያኔም ስላልበረደ በአንድ ወገን መስቀል እየቆመ በሸማግሌ እርቅ ሲካሄድ፣ በሌላ ወገን ጠቡን የሚያጋግሙ የውስጥ አርበኞች በፊታውራሪ ገዙ አርጋቸውና በፊታውራሪ ምገሌ መኩሪያ መካከል ጠብ ፈጠሩ። የአንዱ ወታደር ጠመንጃ ይዞ ሌላው በማደሩ ነው የሚሉ አሉ፣ የአንዱን ሚስት ሌላው በመቀማቱ ነው የሚሉም አሉ። ብቻ በማይረባ ነገር መሆኑ ነው። ጠቡ እንደ ተሰማ ፊታውራሪ ወልደፃድቅ ዘውዴ ከሰበርንሃ በፍጥነት ተንቀሳቀሰ። ሙጣማያስ ሲደርሱ የፊታውራሪ ገዙ አርጋቸው ሞት ተሰማ። ህዳር 12 ቀን 1931 ዓ.ም መሆኑ ነው። አንድ ሣምንት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ፊታውራሪ ምገሌ መኩሪያ ሞቱ። የፊታውራሪ ገዙ አርጋቸው አሽከር ገደላቸው ተባለ። ዋናው ነገር በምናምንቱ ነገር እነዚያን የመሰሉ ጀግኖች አርስበርሳቸው ማለቃቸው ነው።[23]

ወደ ጦርነቱ ሁኔታ ስንመለስ፣ የስድስቱን ምሽግ ለመስበር የተደረገው ሙከራ አለመቃናት፣ አርበኛውን አስመረረው እንጂ ተስፋ አላስቆረጠውም። ጠላትን ለማስደንገጥና ስንቅ ለማግኘት፣ የሕዝቡን ልቡና ለማጠናከር፣ ባንዳውን ለመበተን ይረዳል በሚል ምሽግ መስበር አስፈላጊ እየመሰለ ታየ። ከተቻለም በውስጡ የነበረውን ጠላት ደምሶሶ ምሽጉን መያዝ ታላቅ ቁም ነገር ሆነ። ፊቱንም ቢሆን የስድስቱን ሦስት ምሽግ ከማጥቃት፣ የጊና አገር ምሽግ እንዲመታ የታሰበው በዚህ ምክንያት አልነበረም። ምሽጉ እንዲመታ የታሰበው ብዙ መሣሪያ መኖሩ በጠቋሚ ስለተደረሰበት ነበር። ከመሣሪያው መጋዘን የሚያደርስ መሪም ቀደም ብሎ ከምሽጉ በመውጣት እስከ ጭብጠ ማርገፊያ መጥቶ ከአርበኞቹ ጋር ተቀላቅሎ ነበር። ይህም ሁሉ ሆኖ አርበኛውን ከድንጋይ እየከሰከሰ ለማስጨረስ ሆን ተብሎ የተሠራ ሥውር ደባ አለ ብሎ የሚያጣራ ክፍል ነበር። በመጨረሻው ግን ምሽጉን ለመስበር ተወሰነ። በፊታውራሪ ወልደፃድቅ አስተባባሪነት፣ የፊታውራሪ አርጋው ቁንጮ እና የፊታውራሪ ዳርጌ ሰዎች ተነሱ። ፊታውራሪ ደባልቄ ተክሌም ለመተባበር ተስማሙ።

የጊና አገር ምሽግ ከመገዘገዝ ተራራ በስተ ሰሜን ምሥራቅ፣ አምስት ኪሎ ሜትር ያህል ርቆ ከገደል አፋፍ ላይ የሚገኝ ነው። የመሶቢት አነስተኛ ምሽግ ደግሞ ከእሱ በስተሰሜን፣ አሥር ኪሎ ሜትር ያህል ርቃ ትኖሶች። ከዘበጠ ቦታ ስለሆነች፣ ለጊና አገር ዕርዳታ የመስጠት አቅምዋ ውስን ነው። ስለዚህ ከቁጥር አልገባችም። ዝግጅቱ ተጠናቅቆ ለማጥቃቱ እንቅስቃሴ በታህሣሥ ወር 1931 ዓ.ም ተካሄደ። ፊታውራሪ ዳርጌ ቀደም ብለው ሞተው ስለነበር፣ ሠራዊታቸው የሚመራው ቀኛዝማች ቱፋ እና ቀኛዝማች ቱሉ

በተባሉ እንደራሴዎች ነበር። ጦርነቱ ሲከፈት ቀኛዝማች ቱሉ የተባሉት፣ በአርሱ ይታዘዝ የነበረውን ሠራዊት ይዘ፣ ሰተት ብሎ ከጊና አገር ምሽግ ገብቶ ከጣልያን ጋር በሰላም ተቀላቀለ። ማለትም፡- አስቀድሞ የተሠራ የውስጥ ግንኙነት ኖሮታል። ፊታውራሪ ደባልቄ በታሰበው ጊዜ፣ ከተወሰነላቸው ቦታ ሳይደርሱ ዘገዩ። ጠርጣራው ፊታውራሪ ወልደፃድቅ ይህንን ሁኔታ ካጤኑ በኋላ ጥሩምባ በማስነፋት፣ ከጦር ግንባር ተጋፍጠ የነበረውን ሠራዊት ተከትለ አቁሞ ወደ ኋላ እንዲመለስ በማዘዝ ከአልቂት አዳኑት።[24] ፊታውራሪ ቱፋ የተባሉት ግን አሰፋ የተባለውን የፊታውራሪ ዳርጌን ልጅ ይዘው ወደ ጠላት ሳይገቡ የአርበኝነት ሥራቸውን ቀጠሉ።

ከመካኒሣ የተንቀሳቀሱት የአርበኞች ቡድን ሽንኮራ ተሻግረው ታህሣሥ 25 ቀን 1931 ዓ.ም የራሪቲን ምሽግ አጠቁ። በምሽጉ ውስጥ ታኅኖነው ከነበሩት የጠላት ወታደሮች፣ በተለይም ባንዶች ብዙ ገደሉ። መሣሪያ በመጠኑ፣ ከብትም በብዛት ማረኩ። ነገር ግን የምሽጉ አዛዥ የነበረው ሌሊት ተሾልኮ በማምለጥ ባልደ ምሽግ ገባ። ጥቂት ባንዶችም አምልጠው ከአሊልቱ ምሽግ ሄዱ። አርበኞቹም ምርኮአቸውን ይዘው ወደ ፀደታ ተሻገሩ።

የራሪቲን ጥቃት ለመበቀል ጠላት ከምጆ አዲስ ጦር አንቀሳቀሰ። የጠላትን አመጣጥ ሲመለከት ይይታ ለነበረው ዕርዳታ ደረሰለት። ጣልያንም ይህንን ሲያይ ወደመጣበት ተመለሰ።[25]

በመጋቢት ወር 1931 ዓ.ም ራስ አበበ ከመንዝና ከተጉለት እንደገና ወደ ቡልጋ መጡ። ከመጋቢት 12 ቀን 1931 ዓ.ም ጀምሮ ሮርቹ ጊዮርጊስ ምክር ተካሄደ። የምክሩ ዓላማ የወቅቱን የጠላትንም፣ የወገንንም ሁኔታ ገምግሞ አዲስ የጦር ዕቅድ ለመንደፍ ነበር። በተጉለት የተጀመረው የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማህበር መቋቋም ጉዳይም አንዱ ሆነ። ራስ አበበ ይሆንን ማህበር ያቋቋሙት ቀደም ብለው በሞቱት በመልአክ ወሐይ እያሱ ምትክ አንግሱኝ ለማለት ነው ብሎ የተጉላመጠ አልጠፋም። ስምምነቱ የሚገለፀው ልዩ ልዩ መሣሪያ ተቀምጦ «ይህ ቢስት፣ ይህ አይሳተኝ።» እያሉ በመራመድ እንዲሆን ተደርጉ ነበርና፣ በማህበሩ መቋቋም ስምምነት ተደረገ።[26]

የካቲት 23 ቀን 1931 ዓ.ም የአድዋን በዓል በጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ለማክበር አርበኞች ተሰባስበው ስለ ነበር፣ ጠላት በአርበኞች ላይ አደጋ ለመጣል ከጅሎ ነበር። አርበኞቹ ጠርጥረው ነበርና ከወጥመዱ አመለጡ፣ ሳይሳካለት ቀረ።

ጣልያን አርበኞችን በጥቃቅን ነገር ሸንግሎ ከእጁ ለማስገባት ሲያደባ ነበርና፣ በሚያዝያ ወር 1931 ዓ.ም ሽማግሌዎች ላከ። ሐሳቡ ሙሴ ቀስተኛ ይምሮት የነበረውን ለመቀጠል ነበር። ንግግሩ ማህበረ በኩር ላይ ተደረገ። መልእክተኞች ሆነው ከመጡት ውስጥ ደጃዝማች ቁኮንን ወሰኔና ነጋድራስ

ተሰማ እሸቴ ተገኝተውበታል። እነሱም በንግግሩ እምብዛም እንደ አልተጫኑ በኋላ ተሰማ። ተመልሰው ሄዱ። አርበኞቹም ወደ ጌልጌላ ወረዱ።

ራስ አበበ በጌልጌላ ቆይታቸው ጊዜ ከአካሄዱት ሥራ አንዱ የወታደራዊ ሥልጠና እንዲካሄድ ማድረግ ነበር። ከየሠራዊቱ ሰተውጣጡ ሦስት መቶ ለሚያህሉ ወጣቶች የአሮር ጊዜ ሥልጠና ተሰጠ። ሥልጠናውም ተከላክሎ ራስን ስለማዳን፣ ጠላትን ስለማጥቃት፣ ስለስለላ ሥራና መረጃ አሰባሰብ፣ ስጠላት የተሳሳተ መረጃ መስጠት ስለሚቻልባቸው ዘዴዎችና ልዩ ልዩ መሣሪያዎች እየፈቱና እየጠረጉ ስለመገጠም፣ የጐደለ የመሣሪያ አካልን ከሌላ መሣሪያ አዛውሮ ስለመግጠም ነበር። ሰልፍና እርግጫም ይጨምር ነበር። አሠልጣኞች፣ ቀደም ብሎ ከሠለጠኑት፣ በሕይወት የቆዩት ነበሩ።[27]

ጠላት በግንቦት ወር 1931 ዓ.ም መገሬ ዛላ፣ ቅጭንፍር ከተባለው ቦታ በነበሩት ፊታውራሪ ወልደሃይቅ በሚመሩት አርበኞች ላይ ጠንክራ ከበባ አደረገ። አመጣጡ በልዩ አቅጣጫ፣ የደረሰውም ሳያስቡት በድንገት ነበር። ዓላማው አርበኞቹን ከብቦ ለመፍጀት ሲሆን፣ ሊቃናሰት ምንም ያህል አልቀረውም። ሆኖም አርበኞች በርትተው ተከላክሉ፣ በልዩ ልዩ ሥልት ተጠቀሙ። ከፉሪ ተራራ የሚወርደውን እንደ ቡድን፣ አርበኛው ከታች ሆኖ በጥይት ሰግሙ ያዘው። ሌላው ቡድን ከሜጢ፣ በምስለኔ አገር በመጣውና ከጀሉ አገር መጥቶ ጉርባ አገር በደረሰው መከክል ጣልቃ ገብቶ ሰጥቂት ጊዜ ፊትና ኋላ በመተኮስ ውጊያ ከከፈተ በኋላ ተሸልኮ ሜጢ ዝርማ በመግባት፣ የጠላትን ጦር እርስበርሱ አዋጋው። የተራራውንም እሱ ራሱ ተመልሶ ጨረሰው። ሦስተኛው ከቁንጥሎ በልግ የወረደውን ግንባር ሰግንባር ገጥሞ በመውጋት ወደ መጣበት መለሰው። አርበኞቹ እንደዚህ አድርገው ጣልያን በስንት ብልሀት የሠራውን ከበባ አፈራረሱበት።

ከወጣቱ ንጉሠ ነገሥት ከመልአከ ፀሐይ እያሱ ሞት በኋላ፣ በእሳቸው ባለሟሎችና በደጋፊዎቻቸው ላይ ችግር እንደተፈጠረ ቀደም ብዬ ገልጫለሁ። ከፍ ሲል ከጠቀስኳቸው ደጋፊዎቻቸውና ባለመዋሰቻቸው ሌላው ደጃዝማች ኃይሉ ወልደመድህን ዋናው ነበሩ። በጅሮንድ ወልደዮሐንስም ቀረቤታ ነበራቸው። እነኚህ ከራስ አበበ ጋር ስምምነት ስለአጡ፣ ተሰይተው ጉዞ ጀመሩ። ሐሳባቸው ወደ ጉራጌ ሀገር ሄደው እዚያ ከነበሩ አርበኞች ጋር በመቀላቀል የአርበኝነት ሥራቸውን ለመቀጠል ነበር። የመንገድ መሪ ይዘው ጉዞአቸውን ቀጠሉ። ደቦ ጐጀ ሊደርሱ መሪአቸው ሰኔ 15 ቀን 1931 ዓ.ም ከአንድ ከተቃጠለ ግንብ ቤት ውስጥ አስገብቶ አካባቢውን ልሰልል በሚል ምክንያት ተለያቸው። ሌሊቱን የጠላት ጦር መጥቶ ጨረሳቸው። ሰባ ሰው ሞተ። ንጋቱ ወልደ ዮሐንስ ከተባለ ልጅ በስተቀር የተረፈ የለም። ሀገሬው ቀበራቸው።[28]

ሰኔ 22 ቀን 1931 ዓ.ም ለጠን ላይ ጠላት ብዙ ጦር አቅርቦ ከባድ ጦርነት ተደረገ። የሚመራውም ጂቦ በተባለ ሻለቃ ነበር። ይህ ጂቦ የተባለው

ጣልያን ቀደም ብሎ ቡልጋ ውስጥ ወንድሙ ተገድሎበት ስለነበር ደሙን ያመወጣት ፍላጐት ነበረው። በአርበኞች ወገን ራስ አበበ ራሳቸውና ደጃዝማች አሠራሪስ ዱሉ ከነልጆቻቸው መከቱ። ግሩም ጦርነት ተካሄደ። ብዙ የጠላት ወታደር አለቀ። ዝቶ የመጣው ጂቦም እሱ ራሱ ሞቶ ከቡልጮች ንዝንዝ ተገላገለ። ብዙ ወንድሞቻቸው ቢሞቱም፣ ብዙ መሣሪያ አርበኞች ማረኩ።

በሰኔ ወር መጨረሻ 1931 ዓ.ም ጌልጌላ ላይ ጦርነት ተደረገ። ጠላት ብዙ ጦር አምጥቶ ነበርና ጨፋና ወሌንሶ ላይ የጦፈ ውጊያ ተካሄደ። አርበኞች ሰው ቢጐዳባቸውም መልካም ሥራ ሠሩ። ብዙ የጠላት ወታደር ፈጁ፣ መሣሪያና ስንቅም ማረኩ።

ይህ ሁኔታ ጠላትን ስለአስቆጣው፣ ስመበቀልና ሃፍረቱን ለመሸፈን ሞከረ። እንደ ገና አዲስ ጦር አመጣ። አርበኞችም አብራም አራዳ ጠብቀው እንደ ፊት ወቁት። በሐምሌ ወር 1931 ዓ.ም ያገኙት ምርኮ ስከረምቱ ወራት ስንት ሆናቸው።[29]

በቡልጋ የ1931 ዓ.ም ትግል በዚህ ዓይነት ተጠናቅቆ የ1932 ዓ.ምቱ ተጠለ። በጠላት ዘንድ የተገመተው አርበኞች የ1931 ዓ.ምን እንደማያልፉ ነበር። ጠላት ደጋግሞ አዳዲስ ጦር በማምጣት በርትቶ የተዋጋውም ለዚህ ነበር። በአውሮፓ የፖለቲካ ተፅዕኖ ጠንክሮበት ነበርና፣ ደግሞም ለጦርነቱ ማካሄጃ የሚያወጣው ወጭ ከብዶት ነበርና፣ የጦርነቱ ማለቅ ለምሶሎኒ መንግሥት እጅግ አስፈላጊ ነበር። አርበኞቹን በመጨረስ ጦርነቱን መፈፀም እንደአልቻለ ከጊዜ ብዛት ገባው። ስለዚህ የ1932 ዓ.ም ዋና ፕሮግራም የሰርቅና ማፈጋጋት ጉዳይ ሆነ።

ነሐሴ 21 ቀን 1931 ዓ.ም ተጀምሮ የነበረው የአርቅ ንግግር መስከረም 7፣ ከዚያም ጥቅምት 30 ቀን 1932 ዓ.ም ማህበረ በኩር ቀጠለ። በንግግሩ ላይ ከጣልያን ወገን በአስታራቂነት የቀረቡት ሽማግሌዎች በየጊዜ ይሰዋወጡ ነበር። ደጋግመው የመጡት፣

ሀ. ኢጣልያውያን፣
ጀነራል ናዚ ጥቂት ጊዜ
ጀነራል ፍራንክ
ሻለቃ ለኮቲ

ሌሎች ብዙ የጦር መኮንኖችና የሲቪል ሹማምንቶች ነበሩ። ወደ መጨረሻው ላይ ጠቅሳላ ቁጥራቸው ወደ ሃምሳ ተገምቶአል። የሚመጡትም በመኪና ነበር።

ለ. ኢትዮጵያውያን ደግሞ፣
ራስ ስዩም መንገሻ
ደጃዝማች መኮንን ወሰኔ
ፊታውራሪ ኃይለሚካኤል ዘውዴ ነበሩ።

በእያንዳንዱ ስብሰባ አባላቱ ከሰባት ሰባት ቦታ ይፈተሹ ነበር። ለጥንቃቄ ብቻ ሳይሆን ለማዋረድና ለማበሳጨት፣ ለማሰልቸት ጭምር። ከሁሉም የሚያሳዝነው በዚህ መናኛ ሥራ የኢትዮጵያውያኑ መተባበር ነበር።

በአርበኛው ወገን በንግግሩ ላይ የሚቀመጡት ራስ አበበና ፊታደኞች የሆኑ የጦር መሪዎች ነበሩ። በሐሳቡ ያልተስማሙት አብዛኛውን ጊዜ ከንግግሩ አልገቡም፣ አርበኛው ለብቻው እርስበርሱ በሚነጋገርበት ጊዜ እንጂ።

ከጣልያን ወገን የሚቀርቡት ሐሳባች እንደ መልእክተኞቹ ሁሉ በየጊዜው ይለዋወጡ ነበር። በጥቅምት 30 ቀን 1932 ዓ.ም የቀረቡት፣

- ለአርበኛው ጠቅላላ ምሕረት እናደርጋለን፣
- ቀለብና ልብስ እንሰጣለን፣
- ለአርበኛው ያለበትን አካባቢ የማስተዳደር ሥልጣን እንሰጣለን፣
- ቁስለኞችን እናክማለን፣
- ሀገር እናለማለን፣

የሚሉ ሲሆኑ፣ ከአርበኛው ወገን የቀረቡት ደግሞ፣

1ኛ. እሥረኞች ይለቀቁ ወደሞቃድሾ፣ ኤርትራና ሮማ የተወሰዱት ጭምር፣

2ኛ. የዳኝነት ሥራ የሚካሄደው በኢትዮጵያውያን ይሁን፣

3ኛ. አርበኞች ከአለባቸው አካባቢዎች የነበሩ ምሽጎችን እንዲያነሳ፣

4ኛ. ሕዝብ ከጣልያን ባለሥልጣኖች ፈቃድ /በርሜስ/ ሳያስፈልገው እንደ ፈለገ እንዲንቀሳቀስ፣

5ኛ. የሰው ንብረትና ሀብት ያለ ሕግ እንዳይወረስ፣

6ኛ. ከአርቅ በኋላ በጅሩ አውራጃ፣ ጫሳ ቀኛዝማች አድማሴ መንገሻንና ባላምባራስ ተምትምን ያለአንዳች ጥፋት ያሰሕግ ከእነሰዎቻቸው ያስፈጃቸው ኩለኤል ሱሬንሲኒ፣ በኢትዮጵያ ፍትሐ ነገሥት፣ በሞት እንዲቀጣልን የሚሉ ነበሩ።

እነዚህም የጣልያን መንግሥት አቅርቦአቸው ከነበሩት ሐሳቦች በተጨማሪ መሆናቸው ነው።[30]

ነገር ግን በእነዚህ ነጥቦች ንግግር ተደረገ እንጂ ከስምምነት አልተደረሰም። ሁለቱም ወገኖች ስምምነቱን ራሱን አልፈለጉትም። አርበኛው በአርቁ ጉዳይ አንድ ልብ አልነበረም። ጠንካራ ተቃውሞ ነበር። ስምምነት ማድረግ ማለት ጦርነቱን ትቶ እጅ መስጠት ማለት ነው። ጣልያኖችም ቢሆኑ ጦርነቱን ማቀዝቀዝ እንጂ፣ ሽፍቶች ብለው ከሚገምቱአቸው ጋር ውል መዋዋል አልፈለጉም። ከቡልጋ አርበኞች ጋር ተተዋዋሉ በመንዝ፣ በአንኮበር፣ በመርሐ ቤቴ፣ በግንደበረትና በጉራጌ አገር ሳለው አርበኛ ሁሉ የሚፀና ይሆናል። ደግሞም በጉንደር፣ በጉጃም፣ በትግራና በወሎም ያለው ተመሳሳይ ጥያቄ ያቀርባል። ይህ ብቻም አይሆን። በዓለም ሀብረተሰብ ዘንድ የአርበኛው ሕልውና በይፋ ታወቀ ማለት ነው።

በሁለቱም ወገን የተያዘው ፈሊጥ ጦርነቱን እያቀዘቀዙ ጊዜ መውሰድ ሆነ። ይህ ዘዴ ለሁለቱም ወገን ጠቃሚም፣ አስፈላጊም ነበር። አርበኛው ፋታ በማግኘቱ ለአራት ዓመት ከደረሰበት ያላሰለሰ ቅጥቃጤ ያንሠራራል። የንጉሠ ነገሥቱን የቀዳማዊ ኃይለሥላሴን ሐሳብና የዓለምን ፖለቲካ ይገመግማል። እርይታ የሚያስገኝ ሁኔታ በንግግሩ ውስጥ በማስገባት ከኢትዮጵያ ሕዝብ ድጋፍ የማግኘት እድሉን ያጠናክራል። ጣልያን ደግሞ ከአንዳችም ማዬታ ሳያገባ ለዓለም ህብረተሰብ ጦርነቱ እንደ አሰቀ አድርጐ የማቅረብ ዕድል ይኖረዋል።

ለማንኛውም ነገር ድርድር በተካሄደባቸው ነጥቦች ዙሪያ አንዳንድ እርምጃ መውሰድ ግድ ነበር። በአርበኞች ወገን ተኩስ ቆመ። ጠላትም በአርበኞች ወደ ተያዙ አካባቢዎች አዲስ ጦር ማጋዙን ተወ። ቁስለኞችን ተረክቦ አከመ። እርቅ ከከፈተ በኋላ አቶ ኃይለ ገብርኤል በላይነህ የተባለውን የፊታውራሪ ወልደፃድቅ ዘውዴ አሽከር አሥመራ ድረስ ወሰደ፣ የተጐዳ ቁስሉን አክሞ፣ አድኖ፣ መልሶ አምጥቶ ጊና አገር አድርሶ ከጓደኞቹ እንዲቀላቀል ፈቅዶ ሰቀቀው። በስንቅ ረገድ የፍርኖ ዱቄት፣ ሻይ ቅጠል፣ ሰካር በገፍ ሰጠ። ልብስም በመጠኑ። መሣሪያ ለጨበጠ አርበኛ ከመስከረም እስከ መጋቢት ወር 1932 ዓ.ም ደመወዝ ከፈለ። ድልድሉም፡- ለወታደር በወር አሥራ ሁለት፣ ለሹማምንቶቹ በወር እስከ ሦስት መቶ ሊራ ነበር። እሥረኞች ከሀገር ውስጥም ለይናሪም ተፈቱ። ዳኝነት በኢትዮጵያዊያን እንዲካሄድ ተደረገ። በአስተዳደሩም ሥራ ኢትዮጵያውያን የተሻለ ተሰሚነት አገኙ። አዲስ በተቋቋመው የመርካቶ ከተማ ሀሐፊ ትዕዛዝ ወልደመስቀል ኃላፊ ሆኑ።

በማህበረ በኩር ማርያም በኩል የዕርቅ ንግግር ከተደረገ በኋላ አንድ የአርበኞች ቡድን በእርዳታ አውቶሞቢል ከእነጀነራል ፍራንክ ጋር እስከ አዲስ አበባ ድረስ መጣ። የቡድኑ መሪ ፊታውራሪ ደምሴ ወልደአማኑኤል ሲሆኑ፣ ከንቲባ /ደጃዝማች/ አበራ ኃይለሥላሴ፣ ቀኛዝማች /ፊታውራሪ/ በቀለ ዘውዱ ነበሩበት።[31] የቡድኑ ተልእኮ በኢትዮጵያ ተወራሪነቱና በጣልያን ወራሪነት ላይ የጎላም መንግሥታት ማህበር የነበረውን አቅዋምና የአውሮፓ ኃያላን መንግሥታት የያዙትን አመለካከት ማጥናት፣ ወደ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መልእክት ማስተላለፍ፣ የጣልያንን ጦር ጥንካሬ መገምገም፣ የሕዝቡን አስተሳሰብ መሰብሰብ ነበር። ያመጡት ወሬ የተጠነቃቀረ ባይሆንም ተስፋ የሚሰጥ ነበር።

በተከታታይ የሚነፍሰው ወሬ የጣልያንኔ መንግሥት ውድቀት፣ የኢትዮጵያን ነፃነት የሚያመለክት አየሆነ በመሄዱ፣ የአርበኛው ልብ

ተጠናከረ። የውስጥ አርበኞችም ተንቀሳቀሱ። ምክርም ይለግሱ ጀመር። ሁኔታው በአንዴ ተለውጦ፣ አብዛኛው እጅ አትስጡ ባይ ሆነ። በደመወዝ ከተቆጠረው ባንዳ በስተቀር፣ ሌላው ለጠላት መሣሪያ መሆኑን ተወ።

በዕርቅ ላይ አርበኛው የነበረው አመለካከት ሲብላላ፣ የተቃዋሚው ክፍል እያየለ ሄደ። ሐሳቡ ስብጥርጥር ያለ እና እልህ የተቀላቀለበት ነበር። አብዛኛው የሚለው እንሞታለን ሆነ። በፊታውራሪ ወልደሃድቅ ዘውዴ አካባቢ የነበረውን ሐሳብ ብንመለከት ስለጠቅላላው አስተሳሰብ ፍንጭ እናገኛለን። የእሳቸውና ከእላቸው ጋር የነበረው ቡድን አመለካከት «አርቅ አዘናጊና ትጥቅ አስፈቺ ነው። ሰው ወደ ግል ኑሮው ከገባ ምኾት፣ ከቀመሰ እንደገና ወደ አርበኝነት አይመለስም። የጣልያኖች ዓላማ ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛት ይዘው ሕዝባቸውን ማስፈር ነው። ስለዚህ አርቀ አይከበርም። ዕርቁ በማይከበርበት ጊዜ ደግሞ ዳኛ አይገኝም። ስለዚህ አርቅ አይጠቅምም።» የሚል ነበር። ይህ ሐሳብ ቀስ በቀስ ድጋፍ እያገኘ፣ ስለእውነትነቱም ማስረጃ እየተገኘ ሄደ። ለምሣሌ ጣልያኖች ሕዝቡን እየፈጁና እያባረሩ በአርሲና በጨርጨር ሠፈር፣ እርሻ መጀመራቸው ተሰማ።

ከዚህም በስተቀር የጠላት ጦር ዕርቁን ምክንያት በማድረግ ከየምሽጉ እየወጣ በየቦታው ይዘዋወር ጀመር። ጠላት ይህንን የሚያደርገው ለስለላ ጭምር እንጂ፣ ከአንዱ ምሽግ ወደ ሌላው ምሽግ ለመሄድ ብቻ አልነበረም። ዕርቁን ሳልተቀበሉት ወገኖች ይህ ሁኔታ ችግር ፈጠረባቸው አልዋጥላቸው አለ ገደብ አጣ። ማብቂያም ጠፋበት። ሲከለክሉአቸው ክስ ያቀርቡ ጀመር። ጣልያን የሚለው ይሰማል፣አርበኛው የሚለው አይደመጥም። ስለዚህም ግጭት ይፈጠር ጀመር። ከስድስቱ ምሽግ እየወጣ እስከ ድንጋይ ይንከዋረር የነበረውን የጠላት ወታደር ፊታውራሪ ደባልቄ ተክሌ ቢከለክሉ ሻለቃ ለኩቲ ለራስ አበበ አረጋይ ስሞታ አቀረበባቸው። በእሱ በኩል ግን ሥራ አልፈታም። ፊታውራሪ ዳርጌን ጉርጌ ጠራ ላይ ጥር 5 ቀን 1932 ዓ.ም ገደሉ።

ከዚህም አልፎ በጅሩ ወረዳ ጫሶ ላይ ቀኛዝማች አድማሴ ማነጃ የተባሉትን አርበኛ ያሰበደል፣ ያሰፍርድ፣ በግፍ ሃያ አንድ ራሳቸውን ገደላቸው። እንደዚሁም ባላምባራስ ተምትም የተባሉት ሌላ አርበኛ ከአሥራ ስደስት ሰዎቻቸው ጋር አይነበር ከተባለው ቦታ ያለአንዳች በደል ገደሳቸው። በራስ አበበ ጥያቄ የሰዎች አምዋምዋት ቢጣራም፣ በገዳዮቹ ጣልያኖች ላይ ምንም ዓይነት እርምጃ ሳይወሰድ ቀረ።[32]

ከጊና አገር ምሽግ ወጥቶ እስከ ሜጢ በመውረድ ያለአንዳች ምክንያት ሀገር የሚያስሰውን አንድ የጣልያን ጦር የፊታውራሪ ወልደሃድቅ ቡድን ምስለኔ አገር ከተባለው ቦታ በጦርነት ማረከው። የጣልያን ጦር የተመራው በአንድ ሻለቃና በአንድ መቶ አለቃ ነበር። የጣልያኖቹ ጥያቄ እኛ የመጣነው በሰላም ሲሆን ለምን ተኩስ ተከፈተብን ነበር። አርበኛውን ሳትጠይቁንና ሳንፈቅድላችሁ እኛ ግዛት ምን አመጣችሁ ሆነ። ጣልያኖች መልስ

አልነበራቸውም። ተኩስ በተከፈተባቸው ጊዜ እጃቸውን ከመስጠት በስተቀር ለመዋጋት አልተወላዱም ነበርና፣ በሰላም ከነመሣሪያቸው ተሰቀቁ። እነሱም ስሞታ ሳያቀርቡ ገሙ ብለው ቀሩ፣ ከምሽግ መውጣታቸውንም ተዉ።

የእርቁ ነገር በዚህ ዓይነት ሲሞቅ፣ ሲቀዘቅዝ ቆየና የደብዳቤ መለዋወጡ ጉዳይ ቀጠለ። ጀነራል ናዚ የካቲት 4 ቀን፣ ሻለቃ ለኩቲ የካቲት 5 ቀን፣ ሻምበል ጋሎቺ የካቲት 6 ቀን፣ ዶክተር ብሩዛ ማስም የካቲት 15 ቀን 1932 ዓ.ም ለራስ አበበ ዓፋሳቸው። ሁሉም "እጅግ የተከበሩ" እንጂ እንኳን "ራስ"፣ ባላምባራስም አላልዋቸውም። ይህም የጣልያን መንግሥት ራስነታቸው ላለማወቅ ያደረገው ጥንቃቄ እንደነበረ ሊታወቅ ይገባል።

በዚሁ ዓይነት የእርቁ ንግግር ሳይቋረጥ፣ በእሱ መሠረት የተወሰደውም እርምጃ ሳይሰናከል እስከ መጋቢት ወር ድረስ ቀጠለ። ነገር ግን የማመንታቱ ነገር ከዚህ የበለጠ መቀጠል አልቻለም። በጣልያን በኩል በአውሮፓ የነበረው የፖለቲካ አቅዋም ስለተበላሸበትና በአርበኞች በኩል ተቃውሞው እየጠነከረ ስለሄደ፣ ከአንድ ውሳኔ ላይ መድረስ ግድ ሆነ። መጋቢት 3 ቀን 1932 ዓ.ም አርበኞች እርስበርሳቸው በአካሄዱት ምክር ጀነራል ናዚን ጠልፈን በማገቻነት እንያዝ የሚል ሐሳብ ከፊታውራሪ ወልደሃድቅ ቀረበ። ውሣኔ ሳይሰጥበት ሰነበተ። ንግግሩን በአርበኞች በኩል ራስ አበበ፣ በጣልያን በኩል የሸዋው ገዥ ጀነራል ናዚ ሆነው እንዲጨርሱ ተወሰነ። ቀጠሮውም ለየካቲት 19 ቀን እንዲሆን ተቆረጠ። የሚፈፀመውም በሥጋ ሊየሱስ እንዲሆን ታሰበ፣ ጳጳሳትም ቀረቡ። ነገር ግን የጀነራል ናዚና የራስ አበቤ እምነት የተለያየ በመሆኑ ሥጋ ወደሙ ቀረና በመሐላ ብቻ እንዲሆን ስምምነት ተደረገ።

በአርበኞች ዘንድ የእርቅ ጉዳይ ሲገመገም፣ እንዲሁም ከውጫሌ ጀምሮ የተደረጉ ውሎች ሲጤኑ፣ የጣልያኖቹ አያያዝ ቢታይ፣ የዓለም መንግሥት ማህበር አቅዋም ቢገመት፣ የአውሮፓ መንግሥታት ስሜት ቢታሰብ፣ ጣልያኖች የነበራቸው የኃይል ሚዛን ቢገመት፣ የሕዝብ አስተያየት ቢገመገም፣ የውስጥ አርበኞች ምክር ቢሰማ፡- የእርቅን ጉዳይ የማይደግፉ ሆነው ተገኙ። በመሆኑም እርቅ ይቅር ከሚል ድምዳሜ ላይ ተደረሰ።

ሌላ ሐሳብ ቀረበ። ጀነራል ናዚ ለእርቅ ሲቀርብ ጠልፈን በመያዝ እናስቅበት የሚል ነበር። የሚያስከትለው ድብደባ ቢፈራም፣ ቀደም ብለው ከተካሄዱት እንደማይብስ ተገመተ። ሐሳቡ ውሳኔ ሳያገኝ የታሰበው ቀን፣ ማለትም፡- የካቲት 19 ቀን 1932 ዓ.ም፣ ደረሰና ጀነራል ናዚ ወሬውን ሰምቶ ቀረ። ሥራ አለብኝ ብሎ በማመካኘትም በእሱ ምትክ እንዲምልለት ጀነራል ፍራንክን ላከ። ጀነራል ፍራንክም በጀነራል ናዚ ምትክ ለመማል ቀረበ። ራስ አበበም ስለ እኔ ሆኖ የሚምለው በሚል አበበ የተባለውን የቀድሞ ጊዜ ባሪያቸው እንዲማማለው አዘዙ። ፍራንክ በዚህ ተናደደና ጥሎ ሄደ፣ እርቁም ፈረሰ።[33]

ከዚህ ላይ ሲደረስ ሁለቱም ወገኖች በደፈጣ መተያየታቸውን ትተው፣ ነገሩን ወደ ሽኩቻ አዞሩት። ሜጀር ለኩቲ ለራስ አበበ፣ ራስ አበበ ደግሞ ለጀነራል ናዚ በአንድ ቀን፣ ማለትም፡- መጋቢት 5 ቀን 1932 ዓ.ም፣ ተመሳሳይ ሐሳብ የያዙ ደብዳቤዎች ፃፉ። ራስ አበበ ለጀነራል ናዚ የፃፉት ደብዳቤ በሞረት፣ በጅሩ፣ በተጉለትም በኩል በደረሰው አደጋ የተነሳሳውን ሕዝብ ለማብረድ ተጨማሪ ጊዜ እንደሚያስፈልግ ገልፆ፣ የመሐላው ቀጠሮ እንዲተላለፍ የሚጠይቅ ነበር። እሱም በበኩሉ የቅኝ ግዛት ሚኒስትር ችሩቺ ወደ አዲስ አበባ እንደጠሩት ይገልፅና፣ አመጨረሻው ድረስ በሰላም እንዲጠብቁት የሚጠይቅ ነበር። ነገር ግን እሱ እንዳሰው አልሆነም። እርቁ ፈረሰ። ራስ አበበም በየቀኑ ይውተውታቸው ለነበረው ለሻለቃ ዶሚኩ ለኩቲ ቁርጠኛ መልስ ሰጡት። ለአርበኞቹም መመሪያ አስተላለፉ።

ለሻለቃ ለኩቲ በቁጥር 200 በፃፉለት የእርቅ ማፍረሻ ደብዳቤ፣ እሱ ቀደም ብሎ የካቲት 12 ቀን የፃፈላቸውን ደብዳቤ ይጠቅስና፣ በቀጥታ ወደ ጉዳዩ ይገባል። እንደ ወትሮው ሰላምታ አያቀርብም። ስለእርቁ መፍረስ ሲያብራራ "...በከንቱ የፈሰሰው የወንድሞቻችን ደም ተመርምሮ እውነተኛውን ነገር ከተረዳችሁት በኋላ ስለሞቱት /ስለተጐዱት/ ሰዎች ገንዘብ ተቀበሉ ብላችሁ የፃፋችሁልን ቃል በጣም ያሳዝናል። ስለዚህ ደማችንን ለገንዘብ የማንለውጥ መሆናችንን እንገልፃለን..." ከአሉ በኋላ ጥንቱንም የተፈራው ትክክለኛ ፍርድ እንዳይጐድል እንደነበር ገሰፁ። በመጨረሻም መልእክታቸው "...የእነዚህ ወንድሞቻችን ሞት ፍርድ በሚገባ እስኪፈፀም ድረስ...ጀነራል ናዚ እንዳይመጡ" በማለት አስታውቀው፣ ነገሩን ራሱ ጣልያን ላይ ደፈደፋት። እነዚህ ወንድሞቻችን የሚሉት በጠላት ተይዘው ከነሰዎቻቸው በጥይት የሞቱት ቀኖዝማች አድማሴ ማገሻንና ባለምባራስ ተምትምን ነበር። ምንም ፊታውራሪ ዳርጌ ጐርጂ የሞቱት በእርቁ ወራት ቢሆንና፣ ጦርነቱም የተቀሰቀሰው የጠላት ጦር ያለፊቃድ በአርበኞች ክልል ሲዘዋወር በተነሳ ግጭት ቢሆን፣ የሞቱት በጦር ሜዳ ላይ ስለነበር ክርክር አልቀረበበትም። "ጀነራል ናዚ እንዳይመጡ" ያሉት ደግሞ ጠልፈን መሳቂያ እናድርገው እያሉ ከሚጐተጉቱአቸው ለመገላገል፣ ማስጠንቀቂያ ከተሰጠው በኋላ መጥቶ አንዳች ነገር ቢደርስበት ጥፋቱ የሱ ራሱ እንደሚሆን ለማብሰር ሳይሆን አልቀረም። ይህ ደብዳቤ እንደደረሰ ጳጳሳቱና ካህናቱ ጽላታቸውን አንስተው ወደ አዲስ አበባ ተመለሱ።

የእርቅን ጉዳይ በዚህ ከጨረሱ በኋላ ለአርበኞች ከባድ ማስጠንቀቂያ ሰጡ። የማስጠንቀቂያውም ቃል "ይህ የፖለቲካ ትግል ሲፈርስ ከባድ ጦርነት እንደሚሆን እምናለሁና ለመሥዋዕትነት ዝግጁ ለመሆን መሣሪያችሁ ከእጃችሁ ሳይለይ ታጥቃችሁ ጠብቁ" የሚል ነበር።[34]

አሳቸውም እርቁ ይካሄድበት የነበረውን ማህበረ በኩርን ትተው ወደ ጌልጌላ ወረዱ። አርበኞችም የቅርቡ እየተመካከረ፣ የሩቁ እየተላላከ ዝግጅቱን

ቀጠለ። ከምስለኔ አገር ምርኮ በሰላም በመለቀቁ የምሥጢር ግንኙነት መሥርቶ የነበረው መቶ አለቃ ከርያ የተባለው ጊና አገር የነበረ ኢጣልያዊ መኰንን መጋቢት 6 ቀን 1932 ዓ.ም እርቅ መፍረሱን የሚገልፅ መልዕክት ላከ። በዚያው ቀን ማታ እሱ ራሱ ሞብጦ ማርጊፊያ ድረስ መጥቶ በአንድ ሰዓት ላይ አንድ ካርታ የመትረየስ ጥይት በሦስት ትንፋሽ በመተኰስ ርችት አሰምቶ ጊና አገር ገባ። የመልእክተኛው ቃልና የመትረየሱ ምልክት አንድ ሆነ። የእርቁ መፍረስ በአርበኛው ዘንድ ታመነ። እርቅን ተጠይፎ የነበረው ወገን ደስ አለው።

ጣልያኖች ሰላም በመፍጠር ሊያገኙት አቆብቁበውበት የነበረው ጥቅም በእርቁ መፍረስ ምክንያት ቀረባቸው። እርቁ ቢፀና ኖሮ፣

1ኛ. ሰላም መሥርተናል በማለት በአውሮፖ ለሚያናፍሱት የሀሰት ወሬ ማረጋገጫ ያገኙ ነበር።

2ኛ. ወታደሮችን በማሰናበት ለጦርነቱ ያወጡት የነበረውን ከፍተኛ ገንዘብ ክልማት ሥራ ላይ ለማዋል ይችሉ ነበር።

3ኛ. ከኢትዮጵያ የእርሻና የማዕድን ሀብት ወደ ሀገራቸው የማጋዝ ዕድላቸው ጠንካራ ይሆን ነበር።

ይህና ሌላውም ከሰላም ጋር ለእነሱ በኩል ይገኝ የነበረው ጥቅም ሁሉ ቀረ።

ከዛ በኋላ ጀነራል ናዚ አርበኞቹን እንዲያወድሙለት ጥሩ ትጥቅ ያላቸው የጣልያን ወታደሮች አሰማራ። ለወታደሮቹም መጋቢት 6 ቀን 1932 ዓ.ም ትዕዛዝ ሰጠ። ከጣልያን መንግሥት የቅኝ ግዛት ምክትል ሚኒስትር ከጀነራል ቲሩሲ የተቀበለውን ጥብቅ ትዕዛዝ አሳትሞ በአይሮፕላን በተነ። ማስታወቂያውም የጣልያን ኃይል ሁሉንም ለመልቀም የሚችል አስመስሎ፣ ተገዥነታቸውን ለገለጡ ሰዎች ሁሉ የሕይወት፣ የነፃነት፣ የሀብት ጥበቃ ስለሚደረግላቸው በፍጥነት ለጣልያን እንዲገቡ የሚመክርና ከግንቦት 7 ቀን በኋላ በጦርነቱ እየበረታና እየተጫነ እንደሚሄድ የሚያስረዳ ነበር። ፈሪ ተንደርድሮ ከምሽግ ገባ።

በአርበኞች ዘንድ ምክር ተደረገ። ፉከራና ቀረርቶ፣ ድንፋታ የበዛበት፣ እልህ ያየለበት ምክር ነበር። ሠራዊቱ የሀገሩን ጥፋት፣ የወንኑን ውርደት ከማየት ሞቱን የመረጠ መሆኑን በአዲስ መንፈስ እንደገና አረጋገጠ። የጦር ሥልትን በተመለከተ ፊት ለፊት መግጠም ሳይሆን ሠራዊቱ እየተከፋፈለ በሚያውቅ በሚያውቀው ቦታ ዳዋ እየሰበሰ፣ ቁጥጉን መከታ እያደረገ፣ በየወንዙ በየተራራው ሊዋጋ ተስማማ።

የጠላት ጦር በምድር፣ በሰማይ እያስገመገመ መጣ። ብዙ ፎክሮ ነበርና ጠንካራ ጡንቻ ማሳየት ነበረበት። ከአንኮበር እስከ ኮረማሽ፣ ከዚያም እስከ ምንጃር አፋፍ አሥራ ሦስት ክፍለ ጦር አሰለፈ። ጦሩም በጠቅላላው ከሁለት መቶ ሺህ ያላነሰ ሲሆን ግማሹ ከለቢያ፣ ከሶማልያና ከኤርትራ ቅኝ

ግዛቶች ተመልምሎ የሠለጠነና ከኢጣልያን አገር የመጣ ደንበኛ ወታደር ነበር። ሌላው ግማሽ ከኢትዮጵያ ውስጥ ተመልምሎ የሠለጠነ ባንዳ ነበር። ጦሩ የተሰበሰበው ከሐረር፣ ከጂማ፣ ከወለጋ፣ ከጐጃም፣ ከምንጃር፣ ከትግሬ፣ ከወሎና ከሸዋ ልዩ ልዩ ክፍል ነበር። በብዙ ጣልያናውያን ጀነራሎች፣ ኮሎኔሎችና መኮንኖች የሚመራ ነበር። ዓላማው ክረምቱ ከመግባቱ በፊት አርበኞቹን ጨርሶ ሀገር ሰላም ማድረግ ነበር። ጦርነቱ መጋቢት 10 ቀን 1932 ዓ.ም ተከፈተ። የጠላት ወታደር በረድፍ ፣ በረድፍ ቡልጋ ጉበቶ ይርመሰመስ ጀመር። ሠላሳ አይሮፕላኖች በየተራ ሀገሩን እየዞሩ ደበደቡ።

አንድ ክፍለ ጦር ብዙ ባንዳ አስከትሎ በኮሎኔል ሶሬንሲኒ እየተመራ በራስ አበበ የሚመራውን ጦር ለማጥቃት ወደ ጌልጌላ ወረደ። አሳቸውም የወሰልን ጉራ ይዘው ተዘጋጅተው ጠበቁት። በመጋቢት ወር መጨረሻ አካባቢ 1932 ዓ.ም ታላቅ ጦርነት ተደረገ። የጠላት ጦር የተሰለፈው በአራት አቅጣጫ ከበባ አድርጐ ነበር። ውጊያው ከጥዋቱ አራት ሰዓት እስከ ምሽቱ አሥራ ሁለት ሰዓት ተካሄደ። የጠላት ጦር እንደቅጠል ረገፈ። አርበኞች ጉዳት አልደረሰባቸውም፣ አንድ ሰው ብቻ ቆሰለባቸው። የሐረርጌው የጠላት ጦር፣ የሶማሌን ወታደር ይዞ በተሰለፈበት ወገን እሩምታ በመተኮስ አርበኞች ከበባውን ሰብረው ወጡ። የአዋሽን ወንዝ በመከተል አርባ ወደሚባለው ቦታ ተዛወሩ። የአፋር ሕዝብ ስንቅ ሰጣቸው። መክርም ለገሳቸው።[35]

በሙገሬ ዛላ የነበሩትን አርበኞች ለማጥቃት የመጣው ጦር፣ ቦምባርድ የተባለውን መሣሪያ ቁንጥሎ በልባ ከተባለው ተራራ ላይ ጠምዶ ከአለክሌ ጀምሮ ያለውን አገር፣ ማለትም፦ ጭንቂትን፣ ሥላሴ ገዳምን፣ ጉርባ አገርን፣ ምስለኔ አገርን፣ ሜጢንና አሰቤ አገር፣ ሰለሎን፣ ደበደቡ። እግረኛም አከታትሎ ላከ። አርበኛው የቁሊሎን ተራራ ይዞ ተከላከለ። በምባርድ የተባለው መሣሪያ ወደ ሰማይ እየተተኮሰ ተራራውን ዞሮ (በስውር ኢላማ) የሚመታ በመሆኑ፣ የቁሊሎን ተራራ ምሥራቃዊ ገፅ ክፉኛ ደበደበው። አልተሰመደም ነበርና ይህ አመታት አርበኛውን ለጊዜው አስደነገጠው። ነገር ግን እምብዛም ጉዳት አላደረሰም። አንድ ከፍለ ጦር ሜጢና ሰለሎ ገብቶ ሠፈረ። በዚህ ጊዜ አርበኞቹ ደጋ ወጥተው የገደሉን አፋፍ ዙሪያውን ከበው ይዘውበት ነበርና ከጭንቅ ውስጥ ገባ። ከአንድ ሣምንት ጭንቅ በኋላ በሦስት ረድፍ ተከፍሎ አንዱ ቀድሞውኑ በገባበት በሙገሬ ዛላ፣ ሁለተኛው በአሞሌ ገደል፣ ሦስተኛው በማይግደጊት ተነቃነቀ። አርበኞች በየቦታው ቦጥይት በመደብደብ ብዙ ምርኮ አገኙ።

ከደብረ ብርሃን፣ በሸላ ገበያ በኩል ጭቃ ቆላ የወረደው፣ ከናዝሬት (ከአዳማ) በምንጃር በኩል አድርጐ ተድላ ማርያም የተሻገረው የጠላት ጦር፣ በዚያ በነበሩ አርበኞች ላይ ጥቃት ለማካሄድ ሞከረ። ነገር ግን በከንቱ እየተደበደበ ምንም ፋይዳ ሳያገኝ፣ ያለቀው አልቆ፣ የተረፈው አገሩን አይቶ ተመለሰ።

በራስ አበበ መሪነት አዳል አገር የወረደው አርበኛ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴን መምጣት አልፎ መሐመድ ከተባለ የአዳል ባላባት ሰሙ። ምንም የአዳል ሕዝብ አርዳታ ቢያደርግላቸው ከሰው ብዛት የተነሣ ችግሩ ሲቃለል ስለአልቻለ ወደ ደጋው አገር፣ ወደ አንኮበር መውጣት አስፈለገ። ከልዩ አምባ አካባቢ ሲቃረቡ ጓዝ ከዚያ እንዳይቀር፣ ደረቅ ጦር አንኮበር ውኖቶ ምሽጉን በመምታት ስንቅ እንዲያመጣ ታሰበ። ራስ አበበ መሪ ሆነው ወደ አንኮበር ወጡ። ይህንን ሁኔታ ጠላት በስለላ ስለደረሰበት፣ በጓዝ ላይ አደጋ ጣለ። ከጥዋቱ አሥራ ሁለት ሰዓት ለጥቂት ሰዓት እንደተዋጋ፣ አመጣጡ ያሰብዙ ተቃውሞ ጓዝ ለመማረክ ስለነበር ተኩሱን አቁሞ እየበረረ ሄደ።

ጓዝ ይጠብቅ ከነበረው አርበኛ የሸሸው የጠላት ጦር ሌላ የአርበኛ ሠራዊት ከአለበት ቦታ ደረሰ። ተኩስ ሲካሄድ ፊታውራሪ ደስታ ሸዋርካብህ ጦር ይዘው ደረሱና ወደ አንኮበር ዘልቆ፣ ወደዚያ በዘመተው ሠራዊት ላይ ጉዳት እንዳያደርስ አገዱት። እውቅ አርበኞች ቢወድቁም፣ እዚያው እነበሩበት ቦታ አሳደሩት። በዚህ ጦርነት ወይዘሮ አስካለ ጉብና፣ የራስ አበበ እናት ከጥቂት ጓዝ ጋር ሲማረኩ፣ ምራቲቱ ወይዘሮ ቆንጂት በጀግንነት በመከላከል በአጠገባቸው የነበሩትን አራት ከባድ የውሃ መትረየሶች በጠላት ከመማረክ አዳኑ።

ራስ አበበ ደግሞ በጓዛቸው ላይ የተካሄደውን ጦርነት ሰምተው በግስጋሴ ሲመለሱ ከመንገድ ላይ ሌላ ጦር አገኙ። እሱንም አሳሩን አሳይተው ጓዝ ከነበረበት ቦታ ደረሱ። በአደጋው ምክንያት የተበታተነውም ሠራዊት እንደገና ተሰብስቦ ትግሉን ቀጠለ። ለጥቂም የምግብ ጉዳይ ችግር ፈጠረ። ስንቅ ለመፈለግ ወደ ዲቤ ተሻገሩ። ከዚያም ጌታ ገደል ከተባለው ቦታ ሲደርሱ ጠላት ከበባ አደረባቸው። አርበኞቹም ማንባር ለማንባር ገጥመው በመዋጋት ከበባውን ሰብረው ወጡ።

የደብረ ብርሃንና የአንኮበርን ባንዳ ያስቀደመ የጠላት ጦር ዱቤ በተባለው ጋራ በኩል ተጠግቶ ሌሊት በአርበኞች ላይ አደጋ ጣለ። ጦርነት ተከፍቶ ከሌሊቱ አራት ሰዓት ሲሆን የጨበጣ ውጊያ ተገባ። እሱም በከባድ ሁኔታ ከተካሄደ በኋላ አርበኞች ወደ ከሰም በረሃ ወረዱ።

በዚህ ጊዜ ላይ ጠላት ሌሊት አደጋ የመጣል ዘዴ አመጣ። ጉዳትም ያደርስ ጀመር። አርበኛው በበኩሉ መክሮ ለዚህ ዓይነቱ የጦር ሥልት ማፍረሻ የሚሆን ዘዴ ሠራ። ሌሊት እንደወትሮው ሁሉ መተኛቱ ቀርቶ ንሚሱ ለመዋጋት የሚያስችለው መሣሪያ ታጥቆ ቃፊር እየሆነ በደፈጣ ተበታትኖ እንዲጠብቅ፣ ጠላት በመጣ ጊዜ በየቦታው እንዲፈጀው፣ ተኩስ በተሰማ ጊዜ ዋናው ሠራዊት በፍጥነት ተነስቶ በተበታተነ መንገድ ከጦርነቱ ቦታ ደርሶ ቃፊሩን ተክቶና ረድቶ እንዲዋጋ ተወሰነ። ውሎ፣ አድሮ ደግሞ አርበኛው ሠፈር አስመስሎ አንድ ቦታ እሳት እያነደደ ከዚያ እንደተኛ

በማድረግ ጠላትን ከቀሰበት ውስጥ እያስገባ ቀጠቀጠው። ባንዳው በዚህ ሥልት ልቡ ቀለጠ። ጠላትም ብዙ ጉዳት ስለደረሰበት የቀኑንም፣ የሌሊቱንም ጦርነት ትቶ እየሸሸ እየገባ ተከተተ።

ጣልያን ይህ አላዋጣ ሲለው፣ ጦርነቱን በአይሮፕላን ለማካሄድ አሰበ። አርበኞች ያለበትን ቦታ በእግረኛ እያሰለሰና በአይሮፕላንም እያስመረመረ ከረመ። በነሐሴ ወር 1932 ዓ.ም ከቀኑ 10 ሰዓት ሁለት የጠላት አይሮፕላኖች መጥተው ዝቅ ብለው በማንገብገብ ከመረመሩ በኋላ ወሌንሶ ከተባለው ቦታ ሁለት በርሜል መርዝ ጥሰው ተመለሱ። መርዙም ሁለት ሰዎች ገደለ፣ አንድ ሌላ ሰው አቃጠለ። [36]

እርቅ ሲፈርስ ወዲያው የአርበኞችን ኃይል ለመደምሰስ ጣልያን የወሰደው እርምጃ ከንቱ ሆነ። ከዚህ ላይ ለወደፊት ተመራማሪዎች መነሻ እንዲሆን አንድ የተሰማ ወሬ መጥቀስ እወዳለሁ። በዚሁ ከተሰጡ ሪፖርቶች የተጠናቀረ ሪፖርት በዋናው አዛዥ በኩል ለሞሶሎኒ ይቀርባል። ይህ ሪፖርት ጦርነቱ እንደምን እንደተካሄደ፣ በእኑማን እንደተመራ፣ ምን ያህል ጦር እንደተሰማራ፣ ምን እንደተሠራ፣ ምን ያህል ጊዜ እንደወሰደ፣ ምን ዓይነት መሣሪያ በሥራ ላይ እንደዋለ ከአሰረዳ በኋላ ምክር ይሰግሳል። ምክሩም ሽፍቶቹ ያለበት አካባቢ የመሬቱ አቀማመጥ ወጣ ገባ በመሆኑ ለሽፍቶቹ የተመቸ መሆኑን አሳይቶ፣ ሽፍቶቹ ጥቂት መሆናቸውንና ቁጥራቸውም ከሃያ ሺህ እንደማይበልጥ ግምት ያቀርባል። እነሱም እየተዳከሙ በመሄድ ላይ መሆናቸውንና ከጊዜ በኋላ እንደሚጠፉ አስረድቶ፣ የኢጣልያን መንግሥት እነሱን ታግሦ በልማቱ ሥራ ላይ ቢያተኩር እንደሚሻለው ይጠቁማል። ነገር ግን ይህ ሐሳብ በሞሶሎኒ ዘንድ ተቀባይነት ቢያገኝ፣ ሽፍቶቹን ለመጨረስ አስቀድሞ መሬቱን መደልደል ያስፈልጋል በማለት ሪፖርቱ አስተያየቱን ይደመድማል።

ሞሶሎኒ ይህንን ሐሳብ ከተመለከተ በኋላ በጉዳዩ "ለምን አትደለድሉትም ታዲያ" ብሎ ዓፈበት ይባላል። ምንም ወሬው ገና በማስረጃ ባይረጋገጥ፣ ሊናቅ አይገባውም። ለቀልድ የተነገረም እንኳን ቢሆን ሊጤን ይገባዋል። የኢጣልያ ሹማምንት ስለጦርነቱ ምን ያህል እንደተጨነቁና በሐሳብም እንደተለያዩ፣ በሞሶሎኒ ዘንድ ግን የአርበኞች ማለቅ የተቆረጠ ነገር እንደነበር ያሳያልና።

የ1932 ዓ.ም ትግል በዚህ ዓይነት ተከናወነ። መስከረም ጠባ። የ1933 ዓ.ም የማጥቃት ፕሮግራም ውሎ፣ ሳያድር ተጀመረ። የ1932 ዓ.ም ክረምት ለአርበኞች ቸነፈር የተነሳበት፣ ረሀብ የፀናበት እና የሰውም ኃይል የተቀነሰበት፣ ፅኑ የመከራ ጊዜ ነበር። የሚቀጥለው ዘመን የእልቂት እንደሚሆን በማሰብ አንዳንዶች ቤተሰባቸውን በድብቅ ወደ አዲስ አበባና ወደ ሌሎች ከተሞች ላኩ። ይህም ተቀባይ ዘመድ፣ የኢጣልያን ባለ ሥልጣኖች ፈቃድ ስለሚያስፈልግ ቀላል አልነበረም።

በ1933 ዓ.ም የመጀመሪያው ጦርነት መገሬ ዛላ ላይ ተካሄደ። በፊታውራሪ ወልደፃድቅ ዘውዴ የሚመራውን አርበኛ ለማውደም የታሰመ ነበር። የጠላት ጦር በአንድ ጣልያናዊ መቶ አለቃ የሚመራ፣ በኤርትራ ተወላጅ ወታደሮች ያሉበትና ከአባባቢው በተመለመሉ ባንዶች የተሞላ ነበር። ከጊና አገር ምሽግ ሌሊት በመነሳት በቁንጥሉ፣ በልማ፣ በአስከሬ ወርዳ፣ ጭንቂት በነበረው አርበኛ ላይ በድንገት ደርሶ አደጋ ጣለበት። የሩረን አፋፍ የያዘው አሽቀልቁሎ በመተኩስ በመትረየስ አጠቃ። በጭብጦ ማርገፊያ የወረደው ደርሶ፣ የጀሎ አገርን በር ለመዝጋት አሰመ። አርበኞች በብርታት ተከላከለው የፋሪ ተራራን የያዘውን ባላምባራስ /ማራዝማች/ ኃይሌ ዳርጌና ባልደረቦቹ በጥይት አባረሩት። በሰሉ የመጣውን የአቶ ደመና ከተማ ባልደረቦች ዳቦ ማርገፊያን ይዘው በጥይት አገዱት። ነገር ግን በጭንቂት የመጣው አጠቃ። ሰውንም እስክ ጉሣገር ፊረስ ማሻ ድረስ አባረረው። ከአርበኞቹ ወገን አንድ ሰው ሞተ፣ ጥቂቶች ቆሰሉ። የፊታውራሪ ወልደፃድቅ ባለቤት ወይዘሮ በልዩ ብሩ ከሁለት ልጆቻቸው ጋር ተማረኩ። ከጠላትም ጥቂት ወታደር ሞተ፣ ቆሰለም። ነገር ግን እምብዛም አልተጉዳም።

ጣልያን ወዲያው አከታትሎ ለፊታውራሪ ወልደፃድቅ ዘውዴ መልእክት ላከ። መልእክቱም እጅህን ካልሰጠህ ልጆችህንና ሚስትህን እጨርሳቸዋለሁ የሚል ነበር። ሞገደኛው ፊታውራሪ ወልደፃድቅ አላደርገውም አሉ። የሽማግሌ ምክር፣ የቄስ ግዝት የማይመልላቸው ሆነ። ጠላት እንደአወቀ በምርኮኞቹ ላይ እሥር አፀና። ሰው እንዳያነጋግራቸው አድርጐ በአርበኞች -ላይ የማጥቃት እርምጃ በተደጋጋሚ ወሰደ። ከቀን፣ ቀን ውጤት አገኛለሁ በማለት መስከረም 15፣ 23 እና 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተከታታይና ተመሳሳይ ጥቃት አካሄደ። ሰው በወረርሽኝ በሽታና በረሃብ ተዳክሞ ነበርና፣ ብዙ ጉዳት አደረሰ። ቢሆንም የአርበኛውን ኃይል ሊሠብረው አልቻለም።

ጠላት ጥቅምት 9 እና 22 ቀን 1933 ዓ.ም በዚሁ በመገሬ ዛላ በሚገኘው የአርበኞች ቡድን ላይ የከፈተው የማጥቃቱ ሥራ በጣልያናውያን የሚመራ ቢሆንም፣ የሀገር ውስጥ ፖሊቲካ ጎረስ ሆነ። ሁሉም ጠላቱን በዚያች ቀውጢ ቀን ለመገላገል ሞከረ። ሂደቱም በከፍተኛ ደረጃ የተቀነባበረ ነበር።

የስንቅ ጉዳይ አሳሳቢ ሆነ፣ ነገር ግን የጊና አገርን ምሽግ ለመምታት የአርበኛው አቅም አልፈቀደም። ስለዚህ ጫሬ ላይ መሸገ የነበረውን የባንዳ ቡድን እየመታ ስንቅ ደጋግሞ አገኘ። ይህም ሆኖ በቂ ስንቅ ማግኘት አልተቻለም። ዝም ማለት ደግሞ የአርበኛውን አቅም የሚቀንስ ሆነ። በጉዳዩ ተመክረ፤ እናም የአርበኞች አቅም የተቀነሰ መስሎት የተዘናጋውን የጫጫን ምሽግ ለመምታትና ለመዝረፍ ተወሰነ።

አንድ ቡድን ተመርጦ ከመገሬ ዛላ ቢመንቀሳቀስ በመጣማያስ፣ በገርም አድርጐ በህዳር በመጀመሪያው ሣምንት 1933 ዓ.ም ከጫጫ ምሽግ

በመግባት አተራመሰው። ብዙ የጠላት ወታደር ገድሎ፣ ብዙ ስንቅ ማርኮ ክብት ነድቶ መጣ። ገበሬው ተከታትሎ እህልና ገንዘብ ስለአቀረበ አርበኛው በዚያ አገገመ። ይኸ በምሽጎች ላይ የተጣለው አደጋ፣ ጥቂት ጣልያኖችን እና ሀማሌኖችን እየተከተለ የሚያረተርተውን ባንዳ አስቀመጠው።

ጠላትም በበኩሉ እርምጃ ወሰደ። በዚሁ ሙገራ ዛላ በነበረው አርበኛ ላይ ሀዳር 8 እና 23 ቀን 1933 ዓ.መ ዘመተ። ነገር ግን በሱ በራሱ ባሰው፣ ብዙ ወታደር አለቀበት እንጂ አርበኞች አልተጐዱም።

ከዚህ በኋላ የንጉሠ ነገሥቱ መምጣት በይፋ እየታወቀ ሄደ። ነገር ግን የንጉሠ ነገሥቱ መምጣት ታወቀም ጣልያን አርበኞችን ለማውደም ከሚያካሂደው እርምጃ አልተገታም። ታህሣሥ 9 ቀን 1933 ዓ.ም በፊታውራሪ ወልደፃድቅ ዘውዴ በሚመራው አርበኛ ላይ ከረና አገር በመንቀሳቀስ ዘመተ። በዚህ ወራት የያዘው ፈሊጥ የውሎ ገባ ዘመቻ ማካሄድ ነበር። ቢሆንም በዚህ ዘመቻው ምንም ያህል ውጤት አላገኘበትም። ጥቂቶችን ገደለ፣ ሌሎችን አቆሰለ። ነገር ግን ከእሱ በኩል የወደቁት የወታደሮቹ ቁጥር ይበዛል።

ሁኔታው በእንዲህ እንዳለ ታህሣሥ 10 ቀን 1933 ዓ.ም ቡልጋ፣ በረከት በአርበኞች መካከል በተነሣ የርስበርስ ግጭት ጉዳት ደረሰ። ሪሀብ ፀንቶ ነበርና አርበኞች በአካባቢው የተገኘውን አንድ በሬ ለማረድ ፈለጉ። ባለቤቱ አቶ ዝናዬ በሬው እንዳይታረድበት ተከራከረ። የበሬው መታረድ አስፈላጊ ሆኖ ስለተገኘ፣ ለእሱና ለቤተሰቡ ድርሻ እንዲኖራቸው ተወስኖ እንዲታረድ ተስማማ። ነገር ግን ድርሻውን ሳይሰጡት ስለቀሩ በተነሣው ጠብ ፊታውራሪ አጐናፍርን፣ ፊታውራሪ ተክለ ሃይማኖትንና ባሻ ባዩን ከሌሎች ስደስት አርበኞች ጋር ፈጃቸው። በእንድ ሽንጥ ሥጋ ምክንያት ዘጠኝ ጀግኖች መውደቃቸው ያሳዝን ወይም ያሳፍር ይሆናል፣ ግን የተፈፀመ ነውና መባ አሰበት።

ለሌላው አገር ሕዝብ እንደተደረገው ሁሉ፣ ለሸዋም ሕዝብ ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሀዳር 9 ቀን 1933 ዓ.ም አዋጅ መጣለት። ለጠርጣራው ለሸዋ ሕዝብ የወጣው አዋጅ ለሌሎች ክፍላተ ሀገር ከተነገረው ለየት ያለ ነበር። ለሌሎች ክፍላተ ሀገር እንደተሰጡት አዋጆች ሁሉ ኢትዮጵያ እጀጯን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች በማለት ይጀምርና "... ቢዘገይም... የእንግሊዝ መንግሥት" የሚያደርግልን ዕርዳታ ሲፈፀም ታያላችሁ። ስለዚህ ጥርጥር ሳታገቡ በትዕግስት ጠብቁ..." ይላል። ይህ ብቻ አይደለም። በሸዋ አእምሮ ሲንከባለሉ የኖሩ ሌሎች ጥያቄዎችንም ያወሳል። በመቀጠል "...ከእንግሊዞች ጋር በመሆን በሃይማኖቱም ፀረ ማርያም የሆንኩ አይምሰላችሁ። የእኔ ሃይማኖት የተዋሀዶ ሃይማኖት ነው..." ይልና ወደ ፖለቲካ ጉዳይ ይሻገራል። አዋጁ ለበቀል ስለሚያነሳሳ ከሀድያንም ይናገራል። "...ስለኢትዮጵያ ጥቅም ነው እያሉ ለባዕድ የሚያገለግሉት..." ይልና ስም ከዘረዘረ በኋላ "...ያሰ

አንዳች ርህራሄ የተገባቸውን ቅጣት እንሰጣቸዋለን" ይላል። ይህ ብቻ አያደለም፤ ንጉሠ ነገሥቱ ስለራሳቸውም ጭምር ይናገራሉ። "...ስለኢትዮጵያ ጥቅም ነው የሚሉትስ ንጉሥዋን ከአጣች በኋላ ኢትዮጵያ ምን ጥቅም ለማግኘት ልትችል ነው?" ብሎ ይጠይቃል።

አዋጁ በአይሮፕላን ስለተጣለ ውሎም ሳያድር ከአርበኛው እጅ ገባ። ይህንን ያህልም ተብሎ፣ ሸዋ በአዋጁ የተነገረውን አላመነም። ከጥቂት የንጉሠ ነገሥቱ የቀድሞ ባለምዋሎች በስተቀር ዋናው አርበኛ ለብዙ ጊዜ ምላሽ አልሰጠም። ይህም ንጉሠ ነገሥቱ የካቲት 7 ቀን 1933 ዓ.ም ከቢልያ የጦር ሠፈራቸው ለአዛዥ /ደጃዝማች/ ከበደ ተሰማ ከፃፉት ደብዳቤ ለመረዳት ይቻላል። ደብዳቤውም "...የራስ አበበ ደብዳቤ ብቻ ሳይደርሰን በመቅረቱ ለልባችን እንቅፋት ሳይሆን አልቀረም..." ይላል።[37]

በንጉሠ ነገሥቱና በራስ አበበ አረጋይ መካከል የነበረውንም ሁኔታ ማጤን ይገባል። አርበኞቹን በመወከል ሦስት ሹማምንት ለንጉሠ ነገሥቱ ታህሣሥ 20 ቀን 1931 ዓ.ም ደብዳቤ ፃፉ። ሁኔታዎችን ከገለፁና ለእሳቸው ያላቸውን ታማኝነት "አርበኞች" በማለት ከአረጋገጡላቸው በኋላ ፀሐፊዎቹ ስማቸውን ሲዘረዝሩ፣

አርበኞችም ራስ አበበ አረጋይ
ደጃዝማች መንገሻ ወሰኔ

ፊታውራሪ ዘውዱ አባኮራን ብለው ፈርመዋል። ንጉሠ ነገሥቱ ከሰንደን ታህሣሥ 27 ቀን 1931 ዓ.ም በፃፉት መልስ የሰጡአቸው ማዕረግና ተራ፣

ይድረስ ከደጃዝማች መንገሻ ወሰኔ
ከፊታውራሪ ዘውዱ አባኮራን

ከባላምባራስ አበበ አረጋይ የሚል ነበር። የሥራ ፕሮግራም የተሰጠው ለነደጃዝማች መንገሻ ወሰኔ የተላከ ተብሎ ነበር። ሌሎች ከቁጥር አልገቡም። ንጉሠ ነገሥቱ ይህንን ሁኔታ ያስተካከሉት ሰኔ 20 ቀን 1931 ዓ.ም በፃፉት ሌላ ደብዳቤ ነው። ከዚያ መጨን የሚገባው ዘውዱ አባኮራን በታህሣሥ 20ው ደብዳቤ ከንጉሠ ነገሥት መልእክ ፀሐይ እያሱ ተቀብለውት የነበረውን የደጃዝማችነት ማዕረግ በፈቃዳቸው ለቀው ራሳቸውን እንደገና ወደ ፊታውራሪነት ማውረዳቸው ነው።[38]

በራስ አበበ የሚመራው አርበኛ እንደገና ወደ በረከት፣ ከዚያም ወደ ሰጠን ሄደ። ጠላት ታህሣሥ 3 ቀን 1933 ዓ.ም አብራም አረዳ ከተባለው ሥፍራ ከበባ አድርጐ ሊያጠቃው ሞከረ። አርበኛው ያለብዙ ችግር ከበባውን ሰብሮ አመለጠ።

ታህሣሥ 21 ቀን 1933 ዓ.ም ሠላሳ የሚያህሉ ወታደሮች ከጠላት ከድተው ከራስ አበበ ሠራዊት ጋር ተቀላቀሉ። የጠላት ጦር እየተዳከመና እየተረታ መሆኑን ነገሩ። መሐመድ ጁባር የተባሉውን ቀንደኛ ባንዳ አሥረው

ወደ ጭሣ ወሰዱት። ጠላት በአይሮፕላን ያካሄደው ድብደባ፣ በአግርም ያካሄደው ጦርነት አሳዳኞቸውም። ጭሣ ጀሉሌ እስከተባለው ቦታ ድረስ ቢመጣ አርበኞቹ ታህሣሥ 21 ቀን 1933 ዓ.ም ወጉት። ብዙ ጉዳት አደረሱበት። በእነሱ ላይ ግን እምብዛም ጉዳት ሳይደርስባቸው የሠራውን ከበባ ሠበሩበት።[39]

በዚሁ በታህሣሥ ወር 1933 ዓ.ም መገሬ ዛላ የነበረው አርበኛ የወጨብያን ምሽግ ሁለት ጊዜ መታ። የመጀመሪያው ዘመቻ ጥሩ ውጤት ሰጠ። ስንቅ በብዛት ተገኘ። ሁለተኛው ግን እንደ መጀመሪያው ቀላል አልነበረም። ጠላት በጥንቃቄ ጠበቆ ኖሮ በአርበኞች ላይ መጠነኛ ጉዳት አደረሰ። ቢሆንም ስንቅ ተገኘ። የተፈለገውም እሱ ነበር። ቅጥቃጤ ስለበዛበት አርበኛው መገሬ ዛለን ትቶ ፋሪ ዳዊት አገር አፋፍ ወጥቶ ሠፈረ። ከዚያ እንዳለ ንጉሠ ነገሥቱን እንዲቀበል ትዕዛዝ ስለደረሰው ወደ ደብረ ብርሃን ሄደ ከዚያም ወደ ሰላሌ ተጓዘ። አርበኞችን የማጥፋት መከራው ባልተቃናለት ጊዜ ጣልያን ሕዝቡን በአርበኞች ላይ ሊያስነሳባቸው ሞከረ። በጥር ወር 1933 ዓ.ም በመገሬ ዛለ አካባቢ ወረቀት በተነ። ወረቀቱም ታዋቂ አርበኞችን ማርኮ ላመጣ፣ ወይም ጭንቅላታቸውን ቆርጣ ላቀረበ ምን ያህል ገንዘብ እንደሚከፈል የሚያመለክት ነበር። ነግር ግን ሕዝቡ አልተቀበለውም። ስለዚህ ያንኑ ጦርነት ቀጠለ።

በራስ አበበ የሚመራው ቡድን ጥር 16 ቀን 1933 ዓ.ም ሳለ ጃናሞሬ ከተባለው ቦታ ከጣላት ጋር ተዋጋ። ከዚያም በኋላ ጥር 25 ቀን 1933 ዓ.ም እምቡር ማጭዴ ላይ ጠላት በሦስት አቅጣጫ ከበባ አድርጉ ለማጥቃት ሞክሮ ነበር። ነገር ግን ወታደሩን ከማስጨረስ በስተቀር አንዳችም ውጤት አላገኘበትም።[40]

በመገሬ ዛላ ግንባርም እንደዚሁ ጥቃት አካሄደ። ጥር 8 እና ጥር 23 ቀን 1933 ዓ.ም ከጎና አገር እየተነሣ የውሎ ገባ ዘመቻዎች አካሄደ። በዚህ ጊዜ አርበኛው ከወረርሽኙ በሽታ አገግሞ፣ ምግብም አግኝቶ ነበርና ጠንክሮ ተዋጋ። እሱ በጠላት ላይ እንጂ፣ ጠላት በእሱ ላይ ጉዳት አላደረሰበትም።

ራስ አበበ ወደ አገር ተመልሰው ሳለ በጥር ወር 1933 ዓ.ም ስለ ንጉሠ ነገሥቱ መምጣት ከአዛዥር /ደጃዝማች/ ከበደ ተሰማ ለራስ አበበ የተፃፈ ደብዳቤ ደረሰ። ደብዳቤውም ቀደም ብሎው ከኢየሩሳሌም ፅፈውላቸው የነበረውን ይጠቅስና "...አሁን ግን ይህንን ቃል የምፅፍልህ ግርማዊ ጃንሆይ ተሰደው ሲደክሙበት የነበረው ጉዳይ ስለተፈፀመላቸውና አገራቸው ድንበር ስለደረሱ ለኢትዮጵያ አርበኞቹ ሁሉ...የአዋጅ ቃል ለመናገር ተልኬ ስለመጣሁ ጐጃም መሬት ላይ ሆኜ ነው..." የሚል ነበር።[41] በአርበኛው ዘንድ ደስታ ሆነ። ሁሉም የደስታ ተኩስ ሲተኩስ ዋለ።

የንጉሠ ነገሥቱ መምጣት ሲሰማ፣ የጣልያን ጦር ከየተሠራጨበት ወደ ጠንካራ ምሽጉች መሰብሰብ ጀመረ። በረከት ያለው ማሕመድና ጂፋር

በተባሉት ታናናሽ ምሽጎች ተሰብስቦ ወደ ዋናው ወደ ሳይሰች ምሽግ ገባ። ወሊብያና የነበረው፣ ሾላ ገበያ ተከተተ። ከስድስትና ከሾላ ገበያ ደግሞ ጊና አገር ተጠራቀመ። የመሶቢቱም እንደዚሁ ከአደረገ በኋላ፣ በሕዝብ ዘንድ ተሰሚነት የነበራቸውን ሰዎች በኩቴና እጀቻቸውን ከርችም አሥሮ በቁልፍ በመቆለፍ፣ መሣሪያ ከተቀመጠበት መጋዘን ውስጥ ዘግቶ እሳት ለቅቆባቸው ከጊና አገር ወጥቶ መጋቢት 28 ቀን 1933 ዓ.ም ወደ ደብረ ብርሃን ሄደ።

በዚህ ወቅት ጠላት ዘዴ ብሎ የያዘው የከበባ ጦርነት ነበር። በራስ አበበ አረጋይ ከሚመራው የአርበኛ ሠራዊት ጋር የካቲት 4 ቀን 1933 ዓ.ም ዱቤ ላይ፣ የካቲት 29 ቀን 1933 ዓ.ም እምቡር ሥላሴ ላይ ጦርነት ተደርጉ በጠላት ላይ ጉዳት ደረሰ። አርበኞች እምብዛም ሳይጎዱ ወደ በረከት መሲል ሄዱ።

መገሬ አካባቢ ባሉት አርበኞች ላይ የካቲት 5 እና 13 ቀን 1933 ዓ.ም ጠላት ዘመቻ አደረገ። በተለይ የየካቲት 13 ቀኑ ውጊያ ክባድ ነበር። አርበኞች በጉርባ አገር፣ በምስለኔ አገር፣ በቅጭንፍር፣ በጭንቂት፣ በአለከሴ በጥይትና በእጅ ቦምብ ደበደቡት። ጠላት ቢሸሽም አላመለጠ። በየቀኑ የጦርነት ንዝንዝ ያሰለቸውና የነፃነት አየር የሸተተው የአርበኛ ሠራዊት ሴት ወንዱ፣ ልጅ አዋቂው ወጥቶ ቀጠቀጠው። በዚህ ግንባር ይህ ጦርነት የመጨረሻው ሆነ። ከመስከረም 7 ቀን 1933 ዓ.ም ጀምሮ 13 ጊዜ የዘመተው የጠላት ጦር ሌላ እንቅስቃሴ አላደረገም። እግዚአብሔር ይክበር ይመስገንና፣ በፈታውራሪ ወልደፃድቅ ለምንመራው አርበኞች፣ እንደ ሕማማተ መስቀል የሆነብን፣ በዘመኑ 13ኛው ጦርነት፣ የካቲት 13 ቀን 1933 ዓ.ም አከተመ፣ እኛም ዳንን።

በራስ አበበ የሚመራው ቡድን መጋቢት 12 ቀን 1933 ዓ.ም እምቡር ሥላሴ ከጠላት ጋር ተዋጋ። ጠላት በሁሉም በኩል ከቦ ስለነበር ጦርነቱ ወላፃ ነበር። አርበኛው ቀኑን መሉ ሲዋጋ ውሎ ከሌሊቱ በአንድ ሰዓት ሰብሮ ወጣ። ስምንት አርበኞቹ ሞቱ፣ አምስት ቆሰሉ፣ ሌሎች ሰባቱ ተማረኩ። ከዚያም አርበኞች ወደ ደቤ ተሻገሩ። በጠላት ላይ ብዙ ጉዳት ደረሰ። ለመቁጠር ጊዜ አልነበረም። ከዚህ በኋላ ለመዋጋቱ ማስረጃ አልተገኘምና፣ ይህ ጦርነት በራስ አበበ ለሚመራው ቡድን የመጨረሻው ሳይሆን አልቀረም። በቡልጋ የአምስት ዓመት ትግል በእንዲህ ተጠቃለለ።

ዋናው የቡልጋ አርበኛ በሽንኩራ፣ በጨፌ ደንግ አድርጉ ንጉሠ ነገሥቱን ለመቀበል ወደ ሰላሌ ሄደ። ሌላውም በየአቅጣጫው ወደዚያው አመራ። በፈታውራሪ /ኮሎኔል/ ተረፈ የሚመራው ቡድን ሰንዳፋን ከጠላት አስለቅቆ ያዘ። ሁሉም ንጉሠ ነገሥቱ አዲስ አበባ በገቡበት ቀን በሚያዝያ 27 ቀን 1933 ዓ.ም በተደረገው ሰልፍ በታላቅ ግርማ ተሳተፈ።

ማጣቀሻ ፅሑፎች

1. ጳውሎስ ኞኞ፣ *አጤ ምኒልክ*፣ ገጽ 355።
2. እንሽፍት ማለት ለሀገር እንከላከል፣ እንመን ማለት ደግሞ ለጣልያን እንግባ ማለት ነበር።
3. ከኤርትራ፣ ከሲብያና ከሱማልያ የመጣ ነበር። የቅኝ ግዛት ወታደሮች የሚለውን ምዕራፍ ይመልከቱ።
4. ከሃምሣ አለቃ የላቅ ጌታነህ የተነገረኝ።
5. ከቀኛዝማች ምስካይ ሥዩም ተክሌ በወቅቱ በአርበኞች የተነገረኝ።
6. ከአቶ ሞላ ገዘሙ የተነገረኝ።
7. ጳውሎስ ኞኞ፣ ገጽ 173-179።
8. Greenfield, P.222-238.
9. ዝርዝሩን በገጽ ላይ ይመለከቱታል።
10. ፎቶግራፍን ይመልከቱ።
11. ከመምሬ ደምሴ፣ አብዩ ሆይ ቄርሶስ የተነገረኝ።
12. ከሀገሬ ሽማግሌዎች በ1963 ዓ.ም የተነገረኝ።
13. አንዱ መምሬ ነሰበ የሚባሉ የድንጋይ ጥራ ጊዮርጊስ፣ ሌላው መምሬ አማረ የተባሉ የደመቀ ጊዮርጊስ ቄሶች ነበሩ። የቀሩትን የሰባቱን ስም ማግኘት አልቻልኩም።
14. ከአቶ /ሻለቃ/ አሰፋ ወልደፃድቅ የተነገረኝ።
15. ከባላምባራስ /ግራዝማች/ ኃይሌ ዳርጌ የተነገረኝ።
16. ታደሰ ዘውልዴ፣ *ቀሪን ገረመው*፣ ገጽ 97-113 እና 125-128።
17. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 143-47።
18. ከልማነ ወርቅ ተስፋዬ የተነገረኝ።
19. ታደሰ ዘወልዴ፣ገጽ 146።
20. ከዲያቆን /አቶ/ ቀፀላ የተነገሩኝ።
21. ታደሰ ዘወልዴ፣ *የአባሳሸኝ ዘመን*፣ ገጽ 28-33።
22. ታደሰ ዘወልዴ፣ *ቀሪን ገረመው*፣ ገጽ 146-8።
23. ከሃምሣ አለቃ ወልደ ጊዮርጊስ የተገኘ።
24. ከቀኛአዝማች ገብረመስቀል ኃይሌ የተነገረኝ።
25. ከፊታውራሪ ኃይሌ /ኃይለራጉኤል/ ወልደፃድቅ የተነገረኝ።
26. ከአቶ ወልደፃድቅ ሽንቁጤ የተነገረኝ።
27. ከወጣት /አቶ/ ንጋቱ ወልደዮሐንስ የተገኘ።
28. ታደሰ ዘወልዴ፣ *ቀሪን ገረመው*፣ ገጽ 133-135።
29. ከመምሬ /አባ/ ደምሴ አብየ ወልደ ቄርሶስ የተነገረኝ።
30. ከወጣት /ሻለቃ/ መልአኩ ብቀለ የተነገረኝ።

31. ፊሊቀ ዳኜ፣ *አምስቱን የመከራ ዓመትና ፍፃሜውን አጭር ማስታወሻ*፣ ገጽ 25-36 እና ገጽ 46።
32. ከመምሬ /አባ/ ደምሴ አብየ ወልደ ቄርሶስ የተነገረኝ።
33. ፊሊቀ ዳኜ፣ *5ቱ የመከራ ሰዓትና ፍፃሜውን አጭር ማስታወሻ*፣ ገጽ 45-51።
34. ታደሰ ዘወልዴ፣ *ቀሪን ገረመው*፣ ገጽ 182-188።
35. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 189-193።
36. ከበደ ተሰማ፣ *የታሪክ ማስታወሻ*፣ ገጽ 337-338 እና 362።
37. ፊሊቀ ዳኜ ፣ ገጽ 20-25።
38. ታደሰ ዘወልዴ፣ *ቀሪን ገረመው*፣ ገጽ 300-301።
39. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 301።
40. ዝኒ ከማሁ።
41. ዝኒ ከማሁ።

ምዕራፍ ሃያ ዘጠኝ
የአንኮበርና የይፋት ትግል

አንኮበር፣ በታጁራ የባህር በር ወደ ማህል አገር ለሚያደርሰው መንገድ መገናኛ ስለነበረች፣ ከዚህም በላይ ለሸዋ ነገሥታት መናገሻ ስለነበረች፣ ከኢጣሊያኖች ዘንድ የታወቀችና ትኩረት የተደረገባት ከተማ ነበረች። ከዚህም የተነሣ አባ ማሣያ የተባለ ጣልያናዊ ቄስ በሀገሩ ሕዝብ ዘንድ ስሙን አባ ማስያስ አስኝቶ ቀደም ብሎ ጥናት አካሄደ፣ ምጣቶሊክንም እምነት መሠረተ። መቀመጫውንም መጀመሪያ ልጥ ማሪፊያ፣ በኋላ ደግሞ ፍቅሬ ግንብ አደረገ። ይህንን ቄስ በመከተል እየገቡ ሌሎች ጣልያናዊች ልዩ ልዩ የፖለቲካ ጥናት እያጠኑ ወደ ሀገራቸው ላኩ።[1]

የጣልያን መንግሥት በእነዚህ ጥናቶችና በሌሎችም በየጊዜው በለበሰባቸው መረጃዎች እየታገዘ በ1928 ዓ.ም ወረራው ጊዜ ይህቺን ከተማ ለመያዝ ተፋጠነ። ከደብረ ብርሃን በስተምሥራቅ ያለውን አገር ለመያዝና በአንኮበር በታች ያለውን በረሃ ለመቆጣጠር፣ የአንኮበር መያዝ ለኢጣልያኖች ወሣኝ ሆኖ ተገኘ።

የኢትዮጵያ መንግሥት ከአዲስ አበባ ወደ ሰሜን ያሠራውና ጠላትም ተከትሎ የገባበት የመኪና መንገድ ይፋትን ከመንዝ ቆረጠው። ስለዚህ የይፋት ሕዝብ ትግሉን ከአንኮበር ጋር እንዲሆን አደረገ። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የቀረበውም በዚህ ዓይነት ነው።

የጠላት ጦር በኢትዮጵያ ሕዝብ ጉልበት በተሠራለት የመኪና መንገድ ሽማምንት በመኪናና በአውቶሞቢል፣ ካድሬዎች በሞተር ሳይክል፣ ሠራዊቱ በእግር ወደ ደብረ ብርሃን ይተማል። የይፋት አርበኞች ሁኔታውን በቁጭት ይመለከታሉ። እርስበርሳቸው እየተመራረጡ ይሿሿማሉ፣ ለሀገራቸው ነፃነት ለመሞት ይማማላሉ።

የአንኮበርና የይፋት ሁኔታ ይህ ሆኖ ሳለ፣ የይፋት አርበኞች ግንቦት 2 ቀን 1928 ዓ.ም አንዎኪያ በተባለው ሥፍራ በጣልያኖች ላይ አደጋ ጥሰው ብዙ የጣልያን የጦር መኮንንኖች ፈጁ። ሕዝቡ በዱላ ጭምር እየደበደበ ፈጃቸው። በዚህ ቀን ተኩሱን የከፈቱት አቶ ሞገስ ስሜና ባላምባራስ ሠይቆ መሆናቸው በታሪክ ተመዝግቦአል። የዕለቱ ጀግኖች መሆናቸው በሥርዓት ተረጋግጦላቸው የተቀቡት አቶ ገብረሕይወት ወልደ አማኑኤልና አቶ ማሞ አበበ ሆነ። ረጅሙና መራራው የሸዋ የአርበኝነት ትግል በእንዲህ ተጀመረ።

ከጠላት ደም ተቃብቶ መዝናናት የሰምና የይፋት ሕዝብ በዚያው ሌሊት ከየቤቱ ወጥቶ በር፬ አካባቢ ከመንገዱ ግራና ቀኝ አንጥፎ ጠበቀ። የጠላት ወታደር ከካሚዮን እየተሣፈረ ወደ አዲስ አበባ ይገሰግሳል። ሰባ አምስት ካሚዮን ከደፈጣው ቦታ እንደገባ አርበኛው ተኩስ ከፈተ። ሁሉም በየግንባሩ ባለው ካሚዎን ተሳፍረው የነበሩትን የጣልያን ወታደሮች በጥይት

ጠዘጠዛቸው። አደጋ የተጣለባቸው በድንገት በመሆኑ የጠላት ወታደሮች ብዙም አልተፈናፈኑም አሰቁ። ከሀዲም አልጠፋ። ዘውዴ መላት የተባለ ሰው አሥራ ሁለት ጣልያኖችን፣ አሥራ አንድ ቀን ሙሉ ደብቆ አካባቢው ሲረጋጋ ለወገኖቻቸው አስረክቦ ተሸለመባቸው።[2]

በጠላት ላይ ከባድ ችግር ከፈጠሩበት ጉዳዮች አንዱ ወደ ማህል አገር የሚጓዝበትን ይህንን መንገድ መጠበቅ ሆነ። ይህ መንገድ ከተዚጋ ወደ ማህል አገር ወታደር ለማስገባት፣ ለገባውም ስንቅና መሣሪያ ለማቅረብ አለመቻሉ በግልጽ ታወቀው። ብዛት ያላቸው አይሮፕላኖች እያስነሳ አካባቢውን በቦምብ ደበደቡ። ለማስፈራራት ጭምር ብሎ መርዝ ረጨበት። ከግንቦት 7 ቀን 1928 ዓ.ም ጀምሮ በዚያ አካባቢ ያለውን ኃይል አጠናከረ።[3]

ይህ ሁኔታ አርበኛውን አላስደነገጠውም። ይህንን መንገድ መቆጣጠር፣ ጠቅላላውን የጠላት ወረራ መግታት መሆኑን ስለተረዳ ትግሉን በይበልጥ አጠናከረ። ከግንቦት 10 እስከ 12 ቀን 1928 ዓ.ም በዚሁ ቦታ ግንባር ለግንባር ገጥመው ወጉት፣ ገዙውንም አገዱት።

የይፋት አርበኛ ሲያደልበት፣ ጠላት ከደብረ ብርሃን አንድ ባታሊዎን ጦር ወደ አንኮበር ላከ። ከይፋት እስከ ቡልጋ የተቀጣጠለውን እንቅስቃሴ ሽንጥ ለመቁረጥ፣ ጦሩ በፍጥነት ተንቀሳቀሰ። የአንኮበር ጀግኖች እነባላምባራስ ይልማ ወልደኢየሱስ በጀግንነት ተከላከሉ። ነገር ግን ከተማይቱን ማዳን አልተቻላቸውም። ብዙዎች ጠላታቸውን እየጨፈጨፉ ወደቁ። ጠላት ግንቦት 21 ቀን 1928 ዓ.ም የጎረቤላን ከተማ ያዘ።

አርበኞች በዙሪያው ባሉት ተራሮች ተሰማርተው ከደረሰባቸው ጉዳት ጥቂት ከአንሠራሩ በኋላ ሰኔ 3 ቀን፣ ከዚያም ሰኔ 20 ቀን ጀምረው ለአምስት ቀን ያለማቋረጥ ወጉት። አዝማች ሆኖ የመጣውን ጣልያናዊ ሻለቃ ገደሉት። ቢሆንም ጎረቤላን ማስለቀቅ አልቻሉም። ጠላትም ፈጥኖ ምሽግ ስለሠራ፣ ትንቅንቁ ጉዳት እንጂ ጥቅም የማይሰጥ ሆነ። አርበኞች ኮሎኔሉን ገድለው የመሳሪያና የስንቅ መጫኛ የነበሩትን አጋሰሶቹን ፈጁበት። አርበኞቹን ለማጥፋትና በሕዝብም ዘንድ ለማስጠላት፣ ጣልያን አካባቢውን በቦምብ ደበደበ። ::

የጎረቤላ መለቀቅ ለአርበኞቹ አስፈላጊ ሆነ። ስለዚህ እንደገና ለማጥቃት ተዘጋጁ። ሐምሌ 12 እና 13 ቀን 1928 ዓ.ም ልጅ አየለ ኃይሌ በጉረቤላ ምሽግ ላይ፣ ልጅ /ደጃዝማች/ ደስታ ሽዋርካብሀ በጥዬ፣ ባላምባራስ ይልማ ወልደኢየሱስ በቆብ አሰጥል ሆነው ሦስተኛ ዙር ጥቃት አካሄዱ። ጠላት አልተበገረም። እንዲያውም ብዙ ሰው ገደለባቸው። በባላምባራስ ይልማ ወልደኢየሱስ ከሚመራው ቡድን ብቻ ስድሣ ሰው ወደቀ። ጠላት ሌላ ድጋፍ ሰጭ ጦር በጀነራል ትራኪያ መሪነት ከደብረ ብርሃን ወደ ጉረቤላ ማንቀሳቀሱ ተሰማ።

አርበኞች የጦር ሥልት ቀየሱ። አዲስ የሚመጣውን የጠላት ጦር በመንገድ ላይ እንደ አስ ለማጥቃት አሰቡ። በፍጥነት ተንቀሳቅሰው ወሎ ፋርዳ የተባለውን ጉራ ይዘው ጠበቁት። ጀነራል ትራኪያ አርበኞቹን መቋቋም እንደማይችል አውቆ ከሐር እምባ ወደ ደብረ ብርሃን በመመለስ የአየር ድብደባውን አጠናከረ። ጉረቤላን ለማስለቀቅ በአርበኞች በኩል የተደረገው ሙከራ በዚህ አበቃ። ባላምባራስ ይልማ ወደ ቡልጋ፣ በረከት ዞሩ።

በይፋት አርበኛውን በማስተባበር ይመሩ የነበሩት ባሻ /ደጃዝማች ተሰማ አርገጤ ቆስለው ነበርና ጣልያን ይህንን ሰምቶ ሐምሌ 12 ቀን 1928 ዓ.ም በተኙበት፣ ወይራ አምባ በተባለው ቦታ ከበባ አደረገ። ብዙ አርበኞች ገደለ፣ አቆሰለ። ነገር ግን አርበኞቹ በርትተው ስለተዋጉ፣ ቁስለኛውን እንኳ ለማዳን ሳይችል ወደ መጣበት ተመለሰ።

የደብረ ሲናና የአካባቢው አዛዥ የነበረው ሻምበል ጳጉሜ 2 ቀን 1928 ዓ.ም ጦር አንቀሳቀሰ። ገሚሱን ወደ መንዝ፣ ሌላውን ገሚስ ወደ ይፋት አሠማራው። ወታደሩም ሕዝብ መጨረስ፣ ቤት ማቃጠል ያዘ። ይህንን ሀገር የማጥፋትና ሕዝብ የመፍጀት አርምጃ ለመግታት አርበኞች ተረባረቡ፣ በነጭዋ አምባ የወረደውን መንዘች፣ በገደልጌ የመጣውን ይፋቶች ደረት ለደረት ገጠሙት።

በዚህ ጦርነት ያስቸገረው የጠላት ጦር ብቻ አልነበረም፣ የባንዳው ጥርቅም አስቸግሮ ነበር። በባሻ /ደጃዝማች/ ተሰማ አርገጤ የሚመራው ቡድኖ የአቡነ አረጋዊን ኑጋሪት ከአደባባይ አውጥቶ አያስጉሸመ አዋጅ ነገረ። አዋጁም "...ተው ያገር ልጅ እንዴት እናት ሀገርህን ትዋጋለህ? ሃይማኖትህንስ ለም ታፈርሳለህ?" ብሎ የሚጠይቅና ንጉሠ ነገሥቱ መምጣታቸውን የሚገል ደብዳቤ መድረሱን የሚያበስር ነበር። ደብዳቤው እዚያው በአርበኞቹ የተዘጋ አንደነበር መገንዘብ አያዳግትም። በዚህ አዋጅ ልባቸው የተነካ ዘጠኝ መ ሃምሣ ባንዶች ከጠላት ወደ አርበኞች ዞረው ትግላቸውን ቀጠሉ።

ጦርነቱ በማማሥቱ ጳጉሜ 3 እና 4 ቀን 1928 ዓ.ም ቀጠለ መላቅጡ ጠፋ፣ ጣልያን በአይሮፕላን ቢቀጠቅጥም፣ ውጤት አላገኘም የጣልያንን የጦር አዛዥ ሲለፈልፍ አርበኞቹ በአፋ ጥይት ስለከተቱበት ፀ አለ። አቶ መኩሪያ የጣልያኑን ባንዲራ በጉራዴ ቆርጦ በማምጣት ሰለባ ጣለ ከሦስት ቀን ጦርነት በኋላ ጣልያን ስለተሸነፈ፣ የተንቀሳቀሰበትን ዓላማ ት ወደ ደብረ ሲና ተመለሰ። ከጠላት ወገን እጅግ ብዙ ሠራዊት አለቀ ከአርበኞችም ብዙ ጀግና ወደቀ።

የ1928 ዓ.ም ትግል በዚህ ዓይነት ተፈጽሞ የ1929 ዓ.ምቱ ቀጠለ የጣልያን ጦር ግፋይታ በተባለው አካባቢ የነበረውን አርበኛ ለማጥቃ ተንቀሳቀሰ። እንደ ተራ ሽፍታ በመቁጠር ጠላት እምብዛም ባለመጠንቀቁ በሽምቅ ጠብቆ ግንባር ለግንባር በመግጠም አነከተው። የጠላት ጦር እየሮ

ከደብረ ሲና ምሽግ ሲገባ፣ አርበኛው እየገሰገሰ አብሮ ከምሽጉ ውስጥ በመግባት ፓርቺሊ የተባለውን ምሽግ አስለቀቀው። በዛውም ምሽጉን ዘረፈ።

በብዙ ሺህ የሚቆጠር አዲስ ጦር ሮቤ ገባ። የተጣላ ታራርቆ፣ አርበኛው ለፍልሚያ ተዘጋጀ። ለማስረጃም ያህል መራራ ጥል ተጣልተው ለመጋደል ይፈላለጉ የነበሩት አቶ ሰብስቤ የተባሉ ሽማግሌና በላይነህ ይፍሩ የተባለ ሰው "...ስለምን ከቂም እንሞታለን" ተባብለው ታረቁ። በልጅ በላይነህ ይፍሩ የጦበዝ አልቅና ጠላታቸውን መስከረም 16 ቀን 1929 ዓ.ም እንጭኔ ከተባለው ቦታ ገጥመው ብዙ ጉዳት አደረሱበት።

ጠላት በያለበት ሰላይ አስቀምጦ ነበርና ከእነዚህ ሰላዮች አንዱ ጉዝ አምባ ከተባለ ቦታ አርበኞች እንደሚወጉት ነገረው። ጣልያን ይህቺን በር ለመያዝ ከሌሊቱ በአሥር ሰዓት ተንቀሳቅሶ በአሥራ አንድ ሰዓት ተኩስ ከፈተ። ይፋት በሞላ ተነቀነቀ። ሰንቁ አምባ፣ ክራባ፣ ወይራ አምባ፣ ገፋይታ፣ ወጀ ከተባሉት ቦታዎች ወጋው። ጣልያን መሸሽ ያልቻለውን ሴት፣ ሽማግሌና ሕፃን ፈጀ። በቤት እያጉረም አቃጠላቸው። በዚህ ውጊያ ሁሉቱም ወገን ስለደከመ፣ ተኩስ አቁመው ከመስከረም 15 ቀን ጀምሮ ሲሞት የሰነበተውን ሰው ሬሣ ቀበሩ።

ጣልያን ለጦርነቱ ሕዝብ ማስተባበር ያዘ። በዚህ ጉዳይ የሚረዱት ለአንኮበር አስተዳዳሪ ረዳት ሆነው በጠላት የተሾሙት ደጃዝማች ደምስሰው ነበሩ። ለጠላት ይህ ሥራ በመጠኑ ተቃናለት። ከበረከት እስከ ጨኖ ያለውን፣ በተለይም በፊታውራሪ አቡ ላሊለህ ባላባትነት ውስጥ የነበረውን የእስልምና ኃይማኖት ተከታይ ነዋሪ፣ እንዲሁም ፊታውራሪ ተክለ ሃይማኖትን ጭምር አስተባበረ። በጀነራል ትራኪያ መሪነት ከደብረ ብርሃን ተንቀሳቀሰ። አርበኞችም መከቱ። ታህሣሥ 19 እና 20 ቀን 1929 ዓ.ም ውቲ በተባለው ቦታ ታላቅ ጦርነት ተደረገ። ጦርነቱ ሰው ከማስጨረስ በስተቀር ጉልኅ ውጤት አለማስገኘቱን በመረዳት፣ አርበኞች ቦታውን ለቅቀው ጥር 1 ቀን ወደ ተጉለት ዞሩ።

ቡልጋ፣ በረከት ታህሣሥ 28 እና 29 ቀን 1929 ዓ.ም ስለተካሄደው ጦርነትና ስለ እነ ፊታውራሪ ኃይለሥላሴ መያዝ ቀደም በዬ ገልጫለሁ። በዚህ የአርበኞች ቡድን ውስጥ የአንኮበር ከተማን በጠላት ላለማስያዝ በጀግንነት ተዋግቶ ብዙ ሰው ከአለቀበት በኋላ ወደ ቡልጋ የዞረ ሠራዊት ነበረበት። የሚመራውም በባላምባራስ ይልማ ወልደኢየሱስ ነበር። ይህ ቡድን ከተማረከ በኋላ በደብረ ብርሃን ዞሮ ጥር 10 ቀን 1929 ዓ.ም አንኮበር ገባ። ይህ ሁኔታ ለጣልያን ታላቅ ፅድል ሆነለት። ተይዘው የመጡትን አርበኞች በሙሉ ጥር 11 ቀን 1929 ዓ.ም፣ የጥምቀትን በዓል ለማክበር ሕዝብ ከተሰበሰበበት በአደባባይ፣ በመትረየስ ረሸናቸው። ይህ ድርጊት ለአንኮበር ሕዝብ የማይረሳ ትምህርት ሰጠው።

ጣልያን በአንድ ወገን ጦር እያቀረበ፣ በሌላ ወገን ወደ እሱ እንዲገቡለት ያባብል ጀመር። አርበኞቹ ግን አልተታለሉለትም። ተዘጋጅተው በር፣ በር ይዘው ጠበቁት። እሱም በአንድ ጀነራል የሚመራ የሶማሌ ጦር በደብረ ሲና፣ አንድ ባታሊዮን በቡሎፋርዳ፣ ሌላ ባታሊዮን በጉቩር፣ አንድ ባታሊዮን በቁንዲ፣ ከደብረ ብርሃን ደግሞ በጀነራል ማሊቲ የሚመራ ጦር አመጣ። አርበኞቹ በየበሩ በጥይት ጠዘጠዙት። በቡሎፋርዳ በኩል የመጣውን ድል አድርገው አባረሩት። ነገር ግን ከደብረ ሲና የመጣው የሶማሌው ጦር አርበኞቹን ድል አደረጋቸው። ይህንን ሲሰማ ሸሽቶ ደብረ ብርሃን የገባው ጀነራል ማሊቲ እንደገና ተመልሶ በግስጋሴ ደረሰ። አርበኞቹም እንደ መጋቢት 7 ቀን 1929 ዓ.ም ግንባር ለግንባር ገጥመው በመውጋት ድል አደረጉት። ኮሎኔሉንና አንድ መቶ አለቃ ከብዙ ወታደር ጋር ገደሉበት። አሥራ ሁለት መትረየስና ከአምስት መቶ የሚበልጥ ጠመንጃ ከእነ ጥይቱ ማረኩበት። ቀደም ብሎ አቶ ሽንቁጤ ወልደማርያምና አባ ረታ የተባሉትን አርበኞች ራስ ቀርጦ ተጫውቶበት ነበርና፤ የመቶ አለቃውን ጭንቅላት ቀርጠው ጊጤ ተጫወቱበት።

ጠላት በይፋት በኩል ሌላ ጦር አመጣ። አርበኞቹም በመላላት ተሰባስበው ሚያዝያ 15 ቀን 1929 ዓ.ም አጋም በር በተባለው ቦታ ገጥመው በመውጋት ወደ መጣበት መለሱት።

ከዚህ በኋላ የጠላት የማጥቃት ሥራ ለጥቂት ጊዜ ታገሰ። በ1929 ዓ.ም የክረምት ወራት የቡልጋው አርበኛ ያልተጠበቀ ጥንካሬ ስለአሳየና ባላምባራስ /ራስ/ አበበም ወደዚያው ስለዘሩ፣ የጠላት የማጥቃት ኃይል ወደዚያ አዘነበለ። ቢሆንም የይፋት አርበኛ ሥራ አልፈታም። ጠላትን በየቦታው ማስጨነቁንና ሊቻለው ማጥቃቱን ቀጠለ።

ጠላት አሥራ ሁለት ባታሊዮን ጦር አስማርቶ የቡልጋን አርበኞች በሚወጋበት ጊዜ፣ የይፋት አርበኞች የበኩላቸውን ጥቃት በጠላት ላይ አካሄዱ። ግንቦት 11 ቀን 1930 ዓ.ም በድንገት በርዩ ከተባለው ቦታ ደርሰው ጠላት ወደ ቡልጋ ሊልክ አዘጋጅቶት የነበረውን ጦር መቱት። የቡልጋ ጉዞውንም አሰናከሉበት።

አርበኞች ወደ ባሶ ሄደው በርዮ በተባለው ምሽግ ላይ አደጋ መጣላቸውን ሲሰማ፣ ጣልያን አካባቢው ነፃ እንደሆነ ቆጥሮ ከአንኮበር ምሽግ በመውጣት ሕዝብ መፍጀትና ከብት መዝረፍ ያዘ። አርበኞቹ ይህንን እንደ ሰሙ ገስግሰው በመድረስ፣ ግንቦት 12 ቀን 1930 ዓ.ም ወግተው ድል በማድረግ እስከ ምሽጉ ድረስ አባረሩት። ዘርፎ በአንድ ቦታ አጉሮአቸው የነበሩትንም ከአምስት መቶ የሚበልጡ የቀንድ ከብቶች ለገበሬዎቹ ተመለሰላቸው።

አርበኞቹ ሰፍረውበት የነበረውን ሐር አምባ የተባለውን ቦታ ለማስለቀቅ ፈልጎ ጠላት ተንቀሳቀሰ። አርበኞችም እንቅስቃሴውን ቀደም

አድርገው አጢነውት ነበርና፣ ሰኔ 22 ቀን 1930 ዓ.ም ወ/ሮ አትላ አባ ዘማርያም አገር ገጥመው ተዋጉት። ጦርነቱም ከጥዋቱ ሦስት ሰዓት ጀምሮ እስከ ዘጠኝ ሰዓት ቆየ። ጣልያንን ድል አድርገው በማባረር፣ ለቁጥር የታክተ ቦምብና ጥይት ማረኩበት።

ኮሎኔል እሩሶ በሚባል አዛዥ የሚመራ ሌላ አራት ባታሊዮን ጦር መጣ። አርበኞችም ሰኔ 26 ቀን 1930 ዓ.ም ተዋጉት። ነገር ግን ሊመልሱት አልቻሉም። ስለዚህ አካባቢውን ተቆጣጠረ። አንድ ባታሊዮን ቁንዲ፣ አንድ ሌላ ባታሊዮን ውቲ ላይ ምሽግ አስመሸጉ አስቀመጠ። በዚህ አድራጉቱ የልብ ልብ ስለተሰማው "ግቡ! ያለዚያ ልታልቁ ነው" እያለ የማስፈራሪያ ወረቀት በተነ። የማባበያ ደብዳቤዎች ለአርበኞች መሪዎች ፃፈ። አርበኞችም ጊዜ ለማግኘት ሲሉ "እሺ እንገባለን" አሉት። በይፋትና በቡልጋ፣ በመንዝና በተጉለት ያሉ ጓደኞች ይዘው ለመግባት ረዘም ያለ ጊዜ እንዲሰጣቸው ጠየቁት። እሱም እውነት መስሎት ተስማማ፣ እነሱ ግን ሥራቸውን ቀጠሉ።

ውትወታው እንዳልያዘለት በተረዳ ጊዜ ጉጉፍና ዘምቦ የሚባሉትን አምባገኖች ለመያዝ ሞከረ። ከውቲ ጦር አንቀሳቀሰ። ቁንዲና ውቲ የተባሉት ቁልፍ ቦታዎች የተያዙባቸው አርበኞች ነሐሴ 10 ቀን 1930 ዓ.ም አደጋ ጥለው አማሩን አሳዩት። እሱም ተመልሶ ወደ ምሽጉ ገባ።

ጣልያን አካባቢውን ከቁጥጥሩ ሥር ለማስገባት የነበረው ፍላጐት ጠንካራ ነበርና እመ ምህረት የተባለውን ቦታ ለመያዝ ከቁንዲ ሌላ ጦር አንቀሳቀሰ። እሱንም ደግሞ አርበኞቹ ነሐሴ 15 ቀን 1930 ዓ.ም ወግተው ወደ መጣበት መለሱበት። ሁለቱም መሐራዎቹ ሲከሽፉበት ጣልያን አካባቢውን በአይሮፕላን አስደበደበው። ድብደባው አርበኞቹን ያደከመለት መስሎት አንድ ባታሊዮን ጦር አምጥቶ እመ ምህረት ላይ አሠፈረ። ለአርበኞች ይህቺ ቦታ አስፈላጊ ነበረችና ነሐሴ 18 ቀን 1930 ዓ.ም ከጥዋቱ ሦስት ሰዓት እስከ ሰባት ሰዓት ገጥመው በመውጋት አባረሩት። እሱም ቀድሞ ከነበረበት ከቁንዲ ምሽግ ሸሽቶ ገባ።

በእነዚህ ጦርነቶች መሳካት አርበኛው ልቡ ደነደነ። አዳዲስ ምሽግ እንዳይመሽግ መከላከል ብቻ ሳይሆን፣ የያዘውንም ምሽግ የማስለቀቅ መሐራ ተጀመረ። እሱም ታረቁ በከንቱ አትለቁ እያለ ስብከቱን አፈራረቀ። የአርበኞቹ መልስ አይለወጥም። ሠራዊታቸው ብዙ እንደሆነና የሚዋጋውም በያለበት እንደሆነ፣ ለመመላለስና ለመመካከር ረጅም ጊዜ እንደሚያስፈልጋቸው፣ ከጓደኞቻቸው ተነጥለው ብቻቸውን መታረቅ እንደማይችሉ የሚገልፁ ነበሩ። እሱም እውነት እየመሰለው መጓጓቱ አልቀረም። ነገር ግን አርበኞች ከዓላማቸው ፊቀቅ አላሉም። የወሎ ፈርዳን ለማስለቀቅ ከነሐሴ 28 እስከ 30 ቀን 1930 ዓ.ም ታላቅ ውጊያ አካሄዱ። ጣልያን በዚሁ ጊዜ በስድስት ምሽጐች ላይ ጦርነት እያካሄደ እንደነበር ይታወሳል። እሱም በእግር ጦር ሊያቅቱት፣ አይሮፕላን እያስመጣ አስደበደባቸው።

ጠላት ንጉሠ ነገሥት መልአከ ፀሐይን ለማጥፋት ያካሄደውን ጦርነት፣ እንደምን ወደ አንከበር እየተጠጋ እንደሄደ፣ ምንም በሕመም ምክንያት ቢሆን እሳቸውም የሞቱት በዚያው አቅራቢያ እንደ ነበርና የተቀበሩትም ሐርአምባ እንደነበር ቀደም ብሰን ተመልክተናል። ይህ ሁኔታ በይፋት አርበኞች ላይ የጠላትን ተፅዕኖ እንደ አበዛባቸው የታወቀ ነው። እነሱም በብርታት ተከላከሉ። ለራሳቸው ከመከላከልም አልፈው ወደ ፍቅሬ ግንብ የተጠጉትን የቡልጋ አርበኞች ደገፉ።

ጣልያን በርካታ ጦር አምጥቶ አካባቢውን አሰሰው አስቀጠቀጠው። በየቀኑ አይሮፕላን እያስመጣ በቦምብ አስደበደበው። ውጊያው ከመስከረም 25 እስ 30 ቀን 1931 ዓ.ም በየቦታው በፍቅሬ ግንብ፣ በለውቲ፣ በአይብስ፣ በቁንዲ፣ በሐር አምባ፣ በቆቦ፣ በእመ ምህረት፣ በዲቤ፣ በይረፍ ተካሄደ። አርበኞች ጠላታቸውን በየቦታው ረፈረፉት፣ ከእነሱም ብዙ ሰው ወደቀባቸው። ነገር ግን ጠላት እንደ አሰበው ድምሳሴ አልደረሰባቸውም፣ ተረፉ። የቡልጋው አርበኛ ወደ ቡልጋ ሲመለስ፣ የይፋቱ በወፍ ዋሻ በኩል ጥሶ ወደ ተጉለት ተዛወረ።

ህዳር 20 ቀን 1931 ዓ.ም ዝንጀሮ ገደል ከተባለው ቦታ ጠላት ከበባ አደረገባቸው። ሙሉ ቀን ቢዋጉም፣ ሊበትኑት አልቻሉም። ስለዚህ ህዳር 21 ቀን በሙሉ ኃይል ተንቀሳቅሰው በማጥቃት ክቡን ሰብረው ወጡ። ነገር ግን የአርበኞቹ መሪና አስተባባሪ ልጅ /ደጃዝማች/ ደስታ ሽዋርካብህ ቆስለው ወደቁ። ጓዶቻቸው እላቸውን በቃሬዛ ይዘው ሌሊቱን ወፍ ዋሻ ገቡ። ጠላትም ተከታትሉ ትንሽ ተታኩሶ ወደ ኋላው ተመለሠ። እነሱም ወደ ኋላ ሄዱ። እየተከታተለ ለማጥቃት ቢሞክርም፣ አርበኛው አየተዋጋ መለሰው።

ሌላ ጦር አዘጋጅቶ መጣ። ጠላት አርበኞችን ከሚያጠቃባቸው ሥልቶች አንዱ መሪዎቻቸው በታመሙና በቆሰሉ ጊዜ በመውጋት ነበር። በዚሁ ሥልት መሠረት በዚህ ቡድን ላይ ታህሣሥ 10 ቀን 1931 ዓ.ም ጥቃት አካሄደበት። አርበኛውም እየተከላከለ ወደ ዲቤ፣ ደጋጊ ወረደ።

ጠላት ደጋጊ ድረስ በመሄድ ታህሣሥ 28 ቀን 1931 ዓ.ም አደጋ ጣለባቸው። አርበኞቹም የነበሩበትን ቦታ በመልቀቅ አደጋውን ከአሳሰፉ በኋላ፣ ሲመለስ በመንገድ ላይ ጠብቀው አደጋ በመጣል ከባድ ጉዳት አደረሱበት። ብዙ የጦር መሣሪያም ማረኩበት። ከጠላት ጋር በመተባበር የወጋቸውን ባንዳም ጥር 5 ቀን ዋጋውን ከፈሉት።

ጣልያን ሌላ ጦር በማምጣት ሊያጠቃቸው ሞከረ። አርበኞች ቦታ በመለዋወጥ ከሚያዝያ 2 እስከ 15 ቀን 1931 ዓ.ም ድረስ ወጉት። አሱም የአጥቂነት ስሜት አድሮበት ነበርና ከደጋጌ እስከ ወሲል ድረስ እየተከታተለ ከወጋቸው በኋላ ክምሽጉ ገባ።

ሰኔ 15 ቀን 1931 ዓ.ም ጠላት አሱበት ድረስ መጥቶ አደጋ ጣለባቸው። አመጣጡ ከባድ ነበርና እየተከላከሉ ወደ አዳል በረሃ ገቡ።

አጠቃሁ ብሎ ተመልሶ ወደ ምሽጉ ሲገባ ሲጓዝ ጌታ ገደል ከሚባለው ሥርጥ ላይ እድፍጠው ጠብቀው ሰኔ 27 ቀን 1931 ዓ.ም አደጋ ጣሉበት። ከባድ ጉዳትም አደረሱበት።

ጌታ ገደል እስከተባለው ቦታ ድረስ መጥቶ ጠላት አርበኞችን ለማጥቃት ሞከረ። አርበኞችም ሰኔ 30 ቀን 1931 ዓ.ም ግንባር ለግንባር ገጥመው በመውጋት አባረሩት። ክረምቱ በመግባቱ ላይ ነበርና አካባቢውን ጥሶ ከመሄድ በስተቀር አማራጭ ስለአልነበረው ወደ አንከበር ገሠገሠ።

በዚህ የጦር ግንባር በነሐሴ ወር 1931 ዓ.ም ጥቃቅን ግጭቶችም ቢደረጉ፣ በአርበኞች ላይ እምብዛም ጉዳት አላደረሱም። እነሱ ግን ጠላትን ማጥቃታቸው አልቀረም። ነሐሴ 30 ቀን 1931 ዓ.ም ቆቦ ተሻግረው ጳጉሜ 1 ቀን ከጠላት ጋር ተዋጉ። ጳጉሜ 2 ቀን ወደ ጌታ ገደል ተመልሰው ለአዲሱ ዘመን ትግል እየተዘጋጁ ሳለ፣ መስከረም 2 ቀን 1932 ዓ.ም እርቅ መያዙን የሚያበስር ወረቀት ከራስ አበበ ደረሳቸው። ወረቀቱ "...ስምምነት ጀምረናል። እሱ ጦር እንዳያመጣ አድርገናልና እናንተም የዚህን ስምምነት ነገር ተጠባበቁ..." የሚል ነበር። እውነትም ጣልያን በዚያ አካባቢ ጦር ሳያመጣ ቀረ። የይፋትና የአንከበር አርበኞች ከመስከረም 2 እስከ መጋቢት 23 ቀን 1932 ዓ.ም ድረስ እፎይታ አገኙ። ሆኖም የእርቁ ጉዳይ እምብ ዛም ስለአልጣማቸው ከጠላት ጋር አልተቀራረቡም። በአንፃሩ ደግሞ ጠብ አልጫሩም፣ ዝም ብለው ተቀመጡ። የቆሰለው ዳነ፣ የታመመው አገገመ።

መጋቢት 5 ቀን 1932 ዓ.ም ከራስ አበበ ሌላ ደብዳቤ ደረሰ። የሚጠብቁት ነገር ነበርና ወዲያውኑ ሥራቸውን ቀጠሉ። ጣልያንን ከአሰሉ ተነስተው እስከ አልተኪ በር ወጥተው ጦርነት ገጠሙት። ድል አድርገው አበረሩት። መጋቢት 23 ቀን 1932 ዓ.ም አኩኩ አለሉ ከተባለው ቀበሌ ከጠላት ጋር ግንባር ለግንባር ገጥመው ከፍ ያለ ጦርነት አደረጉ። አደጋም አደረሱበት።

ከራስ አበበ ላይ ጦር ጠንክሮ ነበርና የይፋትና የአንከበር አርበኞች እላቸውን ለመርዳት ተንቀሳቀሱ። በዚህ ወቅት እነሱን ለማጥቃት ከወደ ጨና ከሚጓዝ ሌላ የጠላት ጦር ጋር በድንገት ተገናኙ። እሱ እንማን እንደሆኑ ባለማወቅ፣ እነሱ ባልተዘጋጁበት ቦታና ጊዜ በመሆኑ ሰላምታ ተሰጣጥተው ተላለፉ። የጠላት ጦር በመዘናጋት ሲሠፍር አርበኞቹ አደጋ ጥለው ውርደት አደረሱበት።

ከዚያም ወደ ወርቁ አገር ጉዞአቸውን በመቀጠል፣ ከፍ ሲል እንደተገለጣ በራስ አበበ ጓዝ ላይ መጋቢት 27 ቀን 1932 ዓ.ም የተጣለውን አደጋ ተከላከሉ። የጠላት ሐሰብ አርበኞችን ጠራርጐ ማጥፋት ነበርና መጋቢት 30 ቀን 1932 ዓ.ም ከሠፈሩበት ልብአርጌ ከሚባለው ቦታ ድረስ መጥቶ ወጋቸው። እነሱም ቦታ በመለወጥ ከአደጋው ከዳኑ በኋላ፣ ወደ ምሽጉ

ሲመለስ ከመንገድ ላይ አድፍጠው አደጋ በመጣል ብዙ መሣሪያና ጥይት ማረኩበት።

ከዚያም አርበኞች ሚያዝያ 7 ቀን 1932 ዓ.ም ሰዴ ወደሚባለው የአዳል በረሃ ወረዱ። ጠላትም እየተከታተለ ወጋቸው። ቀድሞም ውሃ ያለበትን ቦታ ያዘባቸው። ለማስለቀቅ ቢሞክሩም የማይበገር ሆነ። ሌላ ውሃ ሲፈልጉ ሌላ ጦር አጋጠማቸውና ተኩስ ከፍተው ሲዋጉ ጦርነቱ ከፊትና ከኋላ ሆነባቸው። ሥልታቸውን በመለወጥ በፍጥነት ሾልከው በመውጣት ሁለቱን የጠላት ጦር እርስ በርሱ አዋጉት። እስኪተዋወቁ ድረስ ከሁለቱም ወገን የተረፈው የጠላት ጦር ከውሃው ላይ ሠፈረ። ሠራዊቱ ውሃ ለመፈለግ ተበታተነ፤ የውሃ ጥሙን አርክቶ የሞቱትን ለመቅበር ሲሰበሰብ አሞራ በልቶአቸው አገኘ። ታላቅ ሀዘን ሆነ።

በአርበኞች ላይ ረሃብ ፀና፤ በዚህ ምክንያት በጠላት ምሽግ ላይ እየወደቁ ስንቅ መንጠቅ ግድ ሆነ። ለማጥቃት የተዘጋጀው የጠላት ጦር ራሱን መከላከል አስፈለገው። አርበኞች ሚያዝያ 14 ቀን 1932 ዓ.ም የቆቦን ምሽግ አጥቅተው ከዘረፉ በኋላ ወደ አይገብር ዞሩ። ጠላት ከዚያ ከበባ ለማድረግ ሲሞክር፣ ጋቺኔ ከተባለው ቦታ ተዋግተው ወደ አርቦዩ ሂዱ። አርቦዩ የነበረውን ወግተው ዘርፈው ወደ ጌታ ገደል፣ ከዚያም ወደ ወፍ ገደል ሄዱ። ጠላት የሚጥል የሚይዘውን፣ የሚጨብጥ የሚሰቀውን አጣ። ወዲያና ወዲህ መራወጡን ቀንሶ ከምሽጉ ተሰበሰበ።

ከምሽጉ ውስጥ ተሰባስቦ መቀመጡ ደግሞ ይበልጥ ለጥቃት አጋለጠው። አርበኞች ሚያዝያ 20 ቀን 1932 ዓ.ም ካራመገን የተባለውን ምሽግ አጥቅተው በመግባት ዘረፉት። ብዙ ወታደርም ፈጁበት። ግንቦት 8 ቀን 1932 ዓ.ም ደግሞ ቆቦ ምሽግ ገብተው አተራመሱት። ድል አድርገው እዚያው ተቀመጡ።

ይህ ሁኔታ ጠላትን አስመረረው። ጥቂት መሆናቸውን ስለሚያውቅ ጨርሶአቸው ሊገላገል ፈለገና ታላቅ ጦር አዘጋጀ። ከዚያም ጋቺኔ ከተባለው ቦታ ግንቦት 15 ቀን 1932 ዓ.ም ከበባ አደረገባቸው። አርበኞች ጨነቃቸው። ሁሳቸው አብረው በአንድነት በመጋፈጥ ፈንታ ከሁለት ተከፍለው ከበባውን ሠብረው ለመውጣት ሞከሩ። አልሆነላቸውም፤ እንዲያውም ብዙ ሰው አለቀባቸው። ሁኔታው ተስፋ አስቆራጭ ሆነ። ጊዜ መውሰድ ደግሞ ትርፉ እልቂት ነበር። ስለዚህ ተሷከረው በጎይል ገቡበት፤ ጥሰውትም ወጡ። ወደ አዳል በረሃ የወረዱ መስለው፣ ቀን ሲመሽ ተመልሰው ሳንተ ከሚባለው አገር ገብተው ተቀመጡ።

ከሰኔ 3 ቀን 1932 ዓ.ም ጀምሮ የሀገራቸው የፖለቲካ አቅዋም ስለተለወጠ፤ ይህ ጊዜ ለጣልያኖች ከወትሮውም የበለጠ ክባድ እንደነበር እውቅ ነው። ሌላው ቢቀር እስከ አሰብ የነበረውን በር ለራሳቸው ክፍት ማድረግ ነበረባቸው። ይህም የሚቻለው በአንክበርና በይፋት አካባቢ

የነበሩትን፣ እንደነሱ አስተሳሰብ ሽፍቶች፣ በማጥፋት ነበር። ስለዚህ ኃይላቸውን አጠናክረው አርበኞችን ማባረርና መፍጀት ያዙ።

ሰኔ 15 ቀን 1932 ዓ.ም ጣልያን አርበኞች አሱበት ድረስ መጥቶ ወግቶ ወደ አዳል በረሃ አባረራቸው። እነሱ ግን የውሃ ችግር እንዳያጋጥማቸው የቀበናን ወንዝ ተከተሉ። እንደገና ሰኔ 30 ቀን 1932 ዓ.ም ዱቤ ላይ ወጋቸው። ድል አድርገውም ወደ አዳል አገር አባረራቸው። ምንጊዜም አርበኞችን ተተናኩሎ የማያውቀው የአዳል ሕዝብ በዚህ የጭንቅ ጊዜ በይበልጥ ተባበራቸው፡ ረዳቸው። ስለዚህ በክረምቱ ትንሽ እፎይታ አገኙ። ነገር ግን ረሃቡ ክባድ፣ የወባው ንዳድ ጠንካራ ነበር። ቢሆንም አርበኞች በመጠኑ አገገሙ። ዘመን ተለወጠ።

አርበኞች መስከረም 7 ቀን 1933 ዓ.ም የቆቦን ምሽግ መትተው ስንቅ አገኙ። ያንን እየበሉ መስከረምና ጥቅምትን አዳል በረሃ ሰነበቱ። ጥቅምት 15 ቀን 1933 ዓ.ም ላንቶ ከሚባለው ሀገር ጠላት ቢመጣም፣ እምብዛም ጉዳት አላደረሰባቸውም። ወደ ወሲል ተሻገሩ።

ጋቺኔ ዋና የፍልሚያ ቦታ ሆነች ህዳር 10 እና 16 ቀን 1933 ዓ.ም በዚች ቦታ ጦርነት ተካሄደ። በሁለቱም ጦርነት አርበኞቹ ቀናቸው። ከዚያም በኋላ አሳብረው ወደ ጀሉሌ ሄዱ።

ከዚህ በኋላ ከጠላት ጉን የቆመው የባንዳ ጦር እየተናደ ሄደ። ታህሣሥ 21 ቀን 1933 ዓ.ም ሠላሣ ባንዶች ከጠላት ክድተው ከአርበኞች ጋር ተቀላቀሉ። ጠላትም የቻለውን ያህል ተፍጨረጨረ። ታህሣሥ 30 ቀን 1933 ዓ.ም ጀሉሌ ድረስ መጥቶ ወጋቸው። አርበኞችም ክበባውን ሰብረው አደሌራ ወደተባለው ቦታ ሄዱ። ከዚያም ጠላት ተከታትሎ ስለመጣ ጥር 16 ቀን 1933 ዓ.ም ላለ ደናሬ ላይ ታላቅ ጦርነት ተካሄደ። መሸናነፍ ስለአቃታቸው ሁለቱም ወገኖች ወደ ኋላቸው አፈገፈጉ።

የካቲት 4 ቀን 1933 ዓ.ም ዲቤ ድቁሰ ላይ ጠላት ከበባ አድርጉባቸው ነበር። ከበባውን ያለብዙ ችግር ሰብረው ወጡ። መጋቢት 12 ቀን 1933 ዓ.ም ቆቦ ወሌንሶ ጠላት ድጋሚ ከበባ አድርጉ፤ ከጥዋቱ ሦስት ሰዓት አንስቶ እስከ ሰባት ስዓት ተዋግተው ከበባውን ሰብረው ወጡ። አርበኞች በብዙ ድካም ወደ ዲቤ ተሻገሩ፤ ከዚያም ወደ ቀበና። ከመካከላቸውም ስምንት ሰዎች ሞቱ፤ አምስት ቆስለው ሌሎች ሰባት ሰዎች ተማረኩባቸው። ከዚያ ቁጥሩ አነስተኛ ሠራዊት መካከል፣ ይህንን ያህል ሰው በአንድ ጊዜ መውደቁ ቀላል አልነበረም። በተለይም የተማረኩትና የቆሰሉት ዕድል መጥፎ ሆነ።[1]

የጠላት ጦር እየቀለለ ሲሄድ አርበኞች ማጥቃት ያዙ። በፍጥነት ተንቀሳቅሰው መጋቢት 17 ቀን ማጭዴ ከተባለው አገር ወጥተው ሠፈሩ። መጋቢት 27 ቀን ላለ ጀናሞሬን፣ ከዚያም መጋቢት 28 ቀን አምባ ላይ የነበረውን የጠላት ጦር አባረሩ። ወዲያው ዕለቱን ዱዋይ ሜዳ የነበረውን

የጠላት ጦር አባረው ምሽጉን በመያዝ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ሰቀለው ሠፈሩ።

መጋቢት 29 ቀን 1933 ዓ.ም ንጉሠ ነገሥቱ ደብረ ማርቆስ መግባታቸውንና የኢትዮጵያ ሪዳት ጦር አዲስ አበባ መድረሱን የሚያበስር ደብዳቤ ከውስጥ አርበኞች ተላከላቸው። ይህንን ሰምተው ወደ ደብረ ብርሃን ሲወጡ በለድ ላይ የጠላት ጦር ገጠማቸው። እሱን አብርረው ከዚያው ሠፍረው አደሩ። ሚያዝያ 30 ቀን 1933 ዓ.ም ደብረ ብርሃን ገቡ። ከዚያም ወደ ሰላሌ ሄዶ ንጉሠ ነገሥቱን የመቀበሉ ሥራ ቀጠለ።

በዚህ ሁሉ የትንቅንቅ ዘመን በመሪዎች መካከል የመረዳዳትና የመተባበር መንፈስ እንጂ የግጭት እና የጠብ መንፈስ አልነበረም። በአንዳንድ ደግሞ በይፋትና በአንኮበር የተካሄደው የአርበኝነት ሥራ የተከናወነው በአንድ አስተባባሪ ሥር በተጠቃለለ መልክ አልነበረም። ከልጅ /ደጃዝማች/ ሽዋርካብህ በስተቀር ወደ ንጉሠ ነገሥት መልአክ ፀሐይ እያሱ የቀረበ የለም። ይህ ሁኔታ የሰጠውም ጥቅም ያስከተለውም ችግር ነበር። ጥቅሙ፦ ሁሉም በፍላጐቱና በአቅሙ መጠን መሥራቱ ሲሆን፤ ጉዳቱ፦ ከህብረት ሊገኝ የሚችለውን ጥንካሬ መቀነሱ ነው።

ማጣቀሻ ፅሑፎች

1. ታደሰ ዘወልዴ፣ *የአባላሸኝ ዘመን*፣ ገጽ 27-31።
2. ታደሰ ዘወልዴ፣ *ቀሪን ገሪመው*፣ ገጽ 271-272።
3. ጳውሎስ ኞኞ፣ *የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦርነት*፣ ገጽ 151።

ምዕራፍ ሠላሣ
የመንዝና ተጉለት ተጋድሎ

በሸዋ ዋናው የትግል ጉራ መንዝ ነበር። ተጉለትም በጥሩ ሁኔታ ተጋድሎአል። የአካባቢው ታዋቂ ሰዎች ከማይጨው ጦርነት እንደተመለሱ፤ ሕዝቡን በማስተባበር የጠላትን አመጣጥና የመከላከያውን ዘዴ ማስተማር ጀመሩ። በክብረ በዓል ቀን ታቦት እያቆሙ፣ በዕለተ ሰንበት መስቀልና ሥዕለ ማርያም እያቆሙ ተማፀኑ። ሀገር እንዳትጠፋ፣ ሕዝብ እንዳይዋረድ፣ ኃይማኖት እንዳይረክስ ለመኑ። በዚህ ጉዳይ ታላቁን ሚና የተጫወቱት ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ አልፈዋቸው የሄዱት ደጃዝማች አበበ አውራሪስ ነበሩ። የልጅ ግዛቸው ኃይሌ ቅልቅልም፣ ታላቅ አስተዋጽኦ አድርጐአል።

ሕዝቡ ተባበራቸው። ጀግኖች ለሀገራቸው፣ ለወገናቸውና ለኃይማኖታቸው ደማቸውን ለማፍሰስ ተነሱ። አንዱ ችግር ለሚሰበሰበው አርበኛ ምግብ የማግኘት ጉዳይ ሆነ። ቀድሞ ለዘማቹ ተዘጋጅቶ አማካይ በሆነ ቦታ እንዲከማች ተደርጐ የነበረው ለሠራዊቱ ተሰጠ። ከዚያም በላይ ሰው እንደፍላጐትና ችሎታው እንዲያዋጣ ተደረገ። የተደረገውም አስተዋጽኦ ከስንቅ ተርፎ ለመሣሪያና ትጥቅ መግዣ ጭምር አገልግሎአል። ግና ተባባሪና ደጋፊ የመገኙቱን ያህል፣ ከሐዲም አልጠፋም። እሱንም በታሪኩ ሂደት ውስጥ እናገኘዋለን።

የመጀመሪያው ግጭት የተነሣው ጠጅ ሣር፣ ግንቦት 28 ቀን 1928 ዓ.ም ነበር። ለጠላት የቆመ ባንዳ እየተዥጐደጐደ መጣ። ሐሳቡ በልጅ ግዛቸው ኃይሌ የሚመራውን አርበኛ ለማጥቃት ነበር። ሁኔታው እንደታወቀ በአርበኞች በኩል አስፈላጊው ጥንቃቄ ተደረገ። ይህ ጉዳይ በህዝብ መካከል የርስበርስ መቃቃር የሚያስከትል ስለነበር፣ ደም እንዳይፈስስ በአርበኞቹ በኩል ጥረት ተደረገ። ሆኖም ከአጥቂዎቹ ወገን ተኩስ ስለተከፈተ፣ ጥረቱ ውጤት ሳያገኝ ቀረ። አርበኞቹ በወሰዱት እርምጃ፣ ባንዶቹ አለቁ። በዚህ ዓይነት አምስት ዓመት የፈጀው ትግል በርስበርስ ግጭት ተጀመረ።

የ1928 ዓ.ም ክረምት ለመንዝና ለተጉለት አርበኞች የመዘጋጃና የመመካከሪያ ጊዜ ሆነ። የአርበኞቹን ሁኔታ ይከታተል የነበረው ጣልያንም ለማጥቃት ተዘጋጀ። ቀኛዝማች አገሩናፍር የተባለውን ባንዳ ፊታውራሪ ብሎ መሪ እንዲሆንለት አደረገ። ሐሳቡ ስላድንጋይን ለመያዝ ነበር። ይህ እንደታወቀ፣ መንዝ ተንቀሳቀሰ፤ ተጉለት ደገፈ፤ ይፋት ተባበረ። ከሦስቱም አካባቢ የመጣው ጀግና ቋጉሜ 3 ቀን 1928 ዓ.ም የጠላትን ጦር ጣርማ በር ላይ ግንባር ለግንባር ገጠመው። በጥይት አርፎጨሜ ሽነቀጠው። ጣልያን በመድፍና በመትረየስ ቢከላከልም፣ አርበኛው አየለ። አንድ ሻምበልና ሁለት ባለሌላ ማዕረግ ጣሊያኖች ገደለ። ብዙ የጦር መሣሪያ ማረከ። ጣልያን እስከ ሦስት ቀን ሬሣና ቁስለኛውን ሲያነሳ ከረመ።

አርበኞች አያያዛቸው ስለአስደነገጠው ጀነራል ትራኪያ ደብደቤ ዓፈ። ደብዳቤው አድራሻው ሰልጅ ግዛቸው ኃይሌ ሆኖ፣ "...ላደረስኩበን ጉዳት ጀግንነትህን አመስግንን አልፈነዋል። ነገር ግን ወደፊት ይህን የመሰለ ብልግና ሠርተህ ብትገኝ..." ይልና የድንፋታ መዓት ያወርዳል። ክዚያም አልፎ አርበኛው መስክረም 19 ቀን 1929 ዓ.ም ለጣልያን እንዲገባ ያዛል። አርበኛው ደብዳቤው ተነብቦለት ሁኔታውን ኩተገነዘበ በኋላ፣ ለሚቀጥለው ፍልሚያ ዝግጅቱን ቀጠለ። ጣልያን ቀን ቆርጦ፣ የሰጠውን ቀጠሮ ሳይጠብቅ፣ ጦር አዘጋጅቶ ሊመጣ መሆኑን ጠረጠረ።

ጠላት ደብረ ሲናና ደብረ ብርሃን የሚገኘውን ጦሩን አስክትቶ አንቀሳቀሰ። አርበኞችም ክየአሉበት ተጠራርተው መስክረም 18 ቀን 1929 ዓ.ም ምቹ ምቹ ቦታ ያዙ። መሶቢት የተባለውን ኬላ በቃፊር አስጠበቁ። ክዚያም ጣልያንን መስክረም 19 ቀን 1929 ዓ.ም ጥዋት ገጠሙት። ዋናው ቡድን ከግንባር ሲዋጋ፣ ሌላ ፈጣን ቡድን ክጀርባ ዞሮ በጥይት ጠዘጠዘው። ጠላት ክጀርባው የመጣበትን አርበኛ ደምስሶ ወደ ኋላው ለመመለስ ሞክረ። ክጀርባ ታዝሎበት የነበረው አርበኛም በር ለቀቀለት። ነገር ግን ከግንባር የገጠመው በኃይል እየተጠጋ አጠቃ። ጠላት እየተከተለ ሲያፈገፍግ፣ ክጀርባ ታዝሎበት ክነበረው ጦር ደጀን ላይ ወደቀ። በዚህ ዓይነት ክመሐል አስገብተው በጣልያን ጦር ተጫወቱበት። በጥይትም፣ ገደል በመግባትም ያለቀው አልቆ የተረፈው ወደ ገደል ላይ ተከማች።

ጦርነቱ በማግስቶ ጥዋት ቀጠለ። ከንጋቱ እኩል ሰዓት እስከ ምሽቱ ሦስት ሰዓት ተኩል ውጊያ ተካሄደ። ድሉ ባማያወላውል ሁኔታ የአርበኞች ሆነ። ብዙ ኢጣልያውያን ሞቱ። ከሦስት መቶ በላይ መሣሪያ ተማረከ። ብዙ ባንዳ አለቀ። በአርበኞች የደረሰው ጉዳት በጠላት ላይ ከደረሰው ጋር ሲመዛዘን አነስተኛ ነበር።

ጠላት ይህንን ውርደት ለመሸፈን አፋጣኝ እርምጃ አልወሰደም። አዲስ ጦር ወዲያውኑ አልላከም። ይህም የሁኔታውን አደገኛነት ለመገንዘብ፣ የሕዝቡን ልቡና ለማለዘብና ምቹ ጊዜ ለመጠበቅ፣ በቂ ዝግጅትም ለማድረግ አስቦ ላይሆን አልቀረም። ነገር ግን የአርበኞቹ አቅዋም እየጠነከረ እንጂ እየላላ አልሄደም። ስለዚህ ብዙ ጦር አዘጋጅቶ ተንቀሳቀሰ። አርበኞቹም ጥር 23 ቀን 1929 ዓ.ም ጣርማ በር ላይ ግንባር ለግንባር ገጥመው ወጉት፣ ድል አድርገውም ወደ መጣበት መለሱት።[1]

በጣርማ በር አካባቢ የሚካሄደውን ጦርነት ከመደገፍ ጋር፣ የተጉለት አርበኞች ራሳቸውን ማጠናከር ያዙ። ክሽም በተባለው ቦታ፣ በጐተራ የነበረውን የመንግሥት እህል በሕግና በሥርዓት ተከፋፈሉ። ይህም ሁለት ታላቅ ጥቅም ነበረው። አንደኛው ጥቅም፡- ለአርበኛው ድጋፍ መስጠት ሲሆን፣ ሁለተኛው፡- ክጠላት እጅ አለመውደቁ ነበር።

በተጉለት ውስጥ የአርበኝነት ሥራዎች ከተካሄዱባቸው ቦታዎች አንዱ ጂም ጉዳና ስጋጥ ነበሩ። ፍልሚያው፡- ጣልያን ሰላድንጋይን ለመያዝ፣ አርበኞች ደግሞ ላለማስያዝ ሆነ። ምክንያቱም ይህቺ ቦታ ወደ መንዝም ለመሻገር ሆነ ተጉለትን ለመቆጣጠር ምቹ በመሆንዋ ነው። ጣሊያን ለአድዋ ጦርነት (1888 ዓ.ም) በተዘጋጀ ጊዜ ኮንትአንቶኔሊ ባልታወቀ መንገድ ሰላድንጋይ ድረስ መጥቶ፣ ሰልሎ ሄዶ እንደ ነበርይታወቃል። በመሆኑም ጣልያኖች በዚች ቦታ ላይ ክፍተኛ ትኩረት አድርገው ነበር።[2] ይህቺን ከተማ ለመያዝ የተደረገው ትንንቅ ከባድ ነበር። ከተጉለት አርበኞች አንድ ፊታውራሪ ወንድምነህ ብቻ ከመሞታቸው በፊት፣ ሃያ ሦስት ጊዜ ከጠላት ጋር ውጊያዎች ተካሂደዋል። ክእነዚህም ውጊያዎች ክግማሽ የሚበልጡት በሰላድንጋይና በአካባቢዋ የተካሄዱ ነበሩ። ጠላትም ይህቺን ከተማ ለመያዝ ከአንድ ዓመት ያላነሰ መዋጋት ነበረበት።

ሰላድንጋይን በመያዝ ቀደም በሎ የደረሰበትን ሽንፈት ለመሸፈን ጠላት አዲስ ጦር ሠራቶ መጣ። አርበኞች የካቲት 16 ቀን 1929 ዓ.ም ገጠሙት። መከራ ሥቃዩን አሳይተው ወደ መጣበት መለሱት። ጣልያንም ይህቺን ከተማ መያዝ የግድ ስለሆነበት ደጋግሞ ተዋጋ። ለአርበኞቹም የሞት ሽረት ሆነባቸው። የካቲት 23 ቀን ታላቅ ውጊያ አካሂደው እንደገና መለሱት።

ጠላት አዳዲስ ጦር ማቅረቡን ቀጠለ። በኃይል ጥሶ ለመግባት ቁርጠኛ ሆነ። በክሀዲዎች ምክር እየታገዘ ማጥቃቱን ቀጠለ። የቀረበው ሲያልቅ፣ ሌላ አዲስ ጦር ይተካ ቀጠለ። በአንፃሩ ደግሞ ተተኪ የሌለው እየሞተ፣ እየቆሰለ፣ አንዳንዱም እየከዳ ስለሄደ፣ የአርበኛው ሠራዊት በመዳበር ፋንታ መሳሳት ጀመረ።

ጣልያን ከጉር፣ ከጣርማ በር፣ ከደብረ ሲና፣ ከደብረ ብርሃን፣ ከአሥመራም ሳይቀር ክፍተኛ ጦር አመጣ። መጋቢት 1 ቀን 1929 ዓ.ም አስክትቶ ሌሊቱን ተንቀሳቀሰ። ነቅተው ይጠብቁ የነበሩት አርበኞችም ከንጋቱ አንድ ሰዓት ላይ ገጠሙት። ጠላት ሲጨነቀው ወደ ደብረ ምጥማቅና ወደ ነጩ አገር አዘቀዘቀ። ሌላው ቡድን በጣርማበር፣ በበጉች ጋጥ ወደ ጉንች አምባ ሄደ። አርበኞች በየበሩ እየጠበቁ ደበደቡት። ሞቱም በመጥቀም ፊንታ ጉዳው። ጥቃት ስሰበዛበት ወደ ኋላው ተመለሰ። ከጠላትም፣ ከወገንም ብዙ ሰው ሞተ። አርበኞች ግን ድሉን አንጂ ሞቱንና ቁስለቱን ከቁም ነገር አልቆጠሩትም።

ይህም ሆኖ ጣልያን ሰላድንጋይን ለመያዝ መጣጣሩን አልተወም። አንድ ጊዜ በአንዱ፣ ሌላ ጊዜ በሌላው ቦታ ለማጥቃት ሞከረ። ቤት እያቃጠለ ይገዝ ጀመር። ጉራን ዋሻ ከተባለው ዳገት ላይ ሲደርስ ገጠሙት። ዳገቱን በአሳር በመከራ ሲወጣ በጥይት በመደብደብ፣ በጉልበቱ እየዳኸ የወጣውን ዳገት፣ በጉት እየተንደባለለ እንዲወርደው አደረጉት።

በመላጥና በከስካሽ ወንዝ ገብቶ እንደዚህም የዓሊ ልጆች የለቀበት ቦታ፣ ማለትም በሶስት ቦታ በማጥቃት ሰላድንጋይን ለመያዝ ሞከረ። አርበኞችም መሣቆ፣ አሞራ ወይራ ሆነው ጠበቁት። ሌላው ቡድን ደግሞ በጠሞሬ አፋፍ ሄዶ በመሰጥ በኩል የመጣውን ገጠመው። በሦስቱም በር መልካም ሥራ ተሠራ። በመሰጥ የመጣውን መንገዱን አጠፉበት። እሱም በበኩሉ ዘዴውን ለወጠ። የዛለን ገደል መክታ እየሰጠ በሽምሽምና በቁርቁር ወረደ። አርበኛው ደግሞ በጌላ ዋሻ በኩል አቋርጦ በጠላት ጀርባ በመታዘል ተጨማሪ ጦር እንዳያገኝ አገደበት። ሌላው ቡድን ደግሞ በመስቀሌ በር በኩል አጠቃ። የበጉች ጋጥ እስከሚባለው ቦታ ድረስ ወጥተው ገጠሙት። በበጉች ጋጥ በኩል የመጣው በመጫን አርበኞችን አስለቀቃቸው። የዛለን ገደል መክታ እየሰጠ በሽምሽም፣ በቀረጥ በኩል ወረደ። አርበኞችም ከቀለበት እንዳያስገባቸው ድርግሚት የተባለውን ቦታ ቀድመው ለመያዝ ሞከሩ። ከጠላት ወታደር ጋር እኩል ደርሰው የጨበጣ ጦርነት ሆነ። ከጨበጣው ጦርነት የደነገጠ ኢጣልያዊ ወታደር ጠመንጃውን ረስቶ ድንጋይ በመወርወር የአንዱን አርበኛ ጠመንጃ ሰይፍ ሰበረባቸው። ሽማግሌው አርበኛ ደግሞ የገዛ ጠመንጃውን ነጥቀው እሱ ራሱ እጉርሶ ረስቶት በነበረው ጥይት ገደሉት። አርበኛው ተገድዶ የመጣውን ወታደር መጨረስ ትቶ፣ መሪዎቹን መግደል ያዘ። ፊታውራሪ አጉናፍር፣ ቀኛዝማች አውላዬ አቶ አድምቂ የተባሉትን ቀንደኛ ባንዶች በቅጽበት ረፈረፋቸው። ጠላትም ከሞት የተረፈውን ወታደሩን ይዞ በበጉች ጋጥ በኩል በመግጠሙ ከጣልያንም ከአርበኞችም ብዙ ሰው ወደቀ። ይህ ሁሉ ተጋድሎ ሰላድንጋይን ላያድን ቀረ። መጋቢት 1 ቀን 1929 ዓ.ም በጣልያን እጅ ወደቀች። አርበኞችም የሞተውን ቀብረው፣ የቆሰለውን በቃሬዛ እየተሸከሙ ወደየሠፈራቸው ሄዱ። ጠላትም የሰላድንጋይ ካህናትን ገደለ። መጋቢት 4 ቀን 1929 ዓ.ም ደግሞ ጣልያን ግዙት ድረስ ተሻግሮ፣ ዝማም ድረስ ያለውን አገር አቃጠለው።

ጣልያን ሚያዚያ 26 ቀን 1929 ዓ.ም ከሰላድንጋይ ወደ መንዝ ለመግባት ተንቀሳቀሰ። ሞፈር ውሃን ተሻግሮ መንዝን ረገጠ። ሴቶች አሉ አሉ። አርበኞች ከባሬንታ፣ ከደንገዜ፣ ከአጉን፣ ከየአካባቢው ተሰበሰቡ። እመወይታ ደረሱና በየቦታው ተሠራጩ። ጠመንጃ ያላቸው መሣሪያቸውን ይዘው፣ ጠመንጃ የሌላቸው ጉራዴአቸውን፣ ጦራቸውን፣ አንካሴአቸውን ይዘው ተነሱ፣ ሴቶች በበኩላቸው ዘነዘናቸውን ይዘው ተነሱ። ጣልያን ከእስተያ ዳገት ሲደርስ ያዙት። ገሚሶቹ ግንባር ለግንባር ገጠሙት፣ ገሚሶቹ ደግሞ ከምዕራብ በኩል ዞረው በስተጉን ቆረጡት። በጥይት ቆሉት፣ በጉራዴ ጨፈጨፉት። በድንጋይ ውርወራ ራሱን እየነደሉ ጣሉት። ሴቶች አናቱን በዘነዘና ፈረከሱት፣ በመጥረቢያ ቆራረጡት። ጣልያንም ወደ መጣበት ወደሰላድንጋይ ተመለሰ። በሁለቱም ወገን ብዙ ሰው አለቀ። አርበኞች ብዙ መሣሪያ ማረኩ።

ይህ ሁሉ ሲሆን ሰላድንጋይ ያለው የጠላት ጦር ለወገኑ እርዳታ ማሰቡት አልቻለም። እስከ ገና መምቻ ወረደ። ሲያቸፈችፍ ውሎ ወደ ምሽጉ ተመለሰ። ጣልያን ይህንን የመሰለ ውርደት የደረሰበት በአርበኞቹ ብርታት ብቻ አይደለም። ከሰላድንጋይ ወደ መንዝ የሚያሻግረው የሞፈር ውሃ ወንዝ መልካ አንድ ብቻ በመሆኑና፣ ያውም በቀጭን መንገድ፣ ጥልቀት ባለው ቁልቁለት ወርዶ፣ በጠባብ መልካ ወንዙን ተሻግሮ፣ እንደገና በቀጭን መንገድ ረጅም ዳገት የሚያስወጣ ከመሆኑ ጋር፣ የመንገዱ ግራና ቀኝ በአጋም፣ በቀጋና በቀንጠፋ የታጠረ በመሆኑ ጭምር ነው። የሞፈር ውሃ ወንዝ እንደውሃው የሰው ደም ያናብልበታል እየተባለ ይነገር የነበረው ትንቢት ተፈፀመ። ሚያዝያ 26 ቀን 1929 ዓ.ም የጠላት ደም ከውሃው ጋር ተቀላቅሎ አናበለበት።

መንዝን በቀላል መያዝ እንዳይችል ጣልያን በውል ተረዳ። ጀነራል ትራኪያ ሴሊቱን ሌላ ጦር አንቀሳቀሰ። ደብረ ሲና ያለው ጦር ሰላድንጋይ እንዲገባ አደረገ። እሱ ራሱ የደብረ ብርሃንን ጦር ይዞ ከስካሽ ወንዝ ድረስ በመውረድ ሬሣና ቁስለኛውን አሰባሰበ። በዚህ ጊዜ አርበኞች ሌላ ጥቃት ለማካሄድ አላመቻቸውም። ምክንያቱም በአንድ በኩል ሠራዊቱ ከሚያዝያ 26 ቀን ጦርነት ገና ባለማገገሙ ሲሆን፣ ሌላው ምክንያት ደግሞ ጣልያን ላለ ምድርና ሞላሌ ምሽግ እንዲሠራ የሚፈልጉ ወገኖች ስለነበሩ ከጀርባቸው ጥቃት እንዳያደርስባቸው ጥንቃቄ በማድረግ ነበር።

ጣልያን መንዝን ለመያዝ ከአራት ማዕዘን ሲንቀሳቀስ ዋናው አዛዥ ጀነራል ትራኪያ ነበር። እሱም የደብረሲናንና የደብረ ብርሃንን ጦር ሰላድንጋይ ከነበረው ጋር ቀላቅሎ አዘመተ። ሁለተኛው ጦር ደግሞ ከማማ ምድር፣ በላሎ ምድር መጥቶ ሰፈድ ሚዳን ያዘ። ሦስተኛው ወገን ከወረይሉ ታቹን መጣ። አራተኛው ወገን ከጅሩ በአንባይ ተሻግሮ ጌራ ምድርን ከበበ። ሞፈር ውሃ በፊሰሰ ዋያት በመሰሰ መንዝን አጥለቀለቀው። ብዙ አይሮፕላኖች እያስነሳ አሥራ ሦስት ቀን ሙሉ ሀገሩን አስደበደበው። አርበኞችም በየወንዙ፣ በየተራራው፣ በየጉጡ ተጋደሉ። በጠላት ላይ ብዙ ብዙ ጉዳት አደረሱ፣ ብዙዎች በጀግንነት ወደቁ። ነገር ግን የጠላትን እርምጃ ሊያግዱት አልቻሉም። ነገ ለመሰለፍ፣ ዛሬ ማምለጥ አስፈለገ። ስለዚህ ከቦሩ ሜዳ ወጥተው ሄዱ። በሽህ ሱልጣን የሚመራውን የአዘቦ ራያ ጠላት አምጥቶ፣ ሽማግሌና ሕፃን ሳይቀር ወንዱን አስለበው፣ አሮጊትና ሕፃናት ሳይል ሴቱን ጡቱን አስቆረጠው። በሴቶች ላይ የተካሄደው ድፍረት ብዙዎችን የዕድሜ ልክ ህመማን አድርጉ በአሪማዊነቱ ሲታወስ ይኖራል። ጣልያን ይህንን በመሰለ ጭካኔ ሰውን ፈጅቶ ሚያዝያ 29 ቀን 1929 ዓ.ም መንዝ ገባ።

ጠላት መንዝ እንደገባ ሥራውን ቀጠለ እንጂ ድል አገኘሁ ብሎ አልተዘናጋም። ቃፊሩን አስተያ ላይ አቆመ፣ የሞላሌን ምሽግ ገንቡቶ

አጠናክረ። መንዝን ለመያዝ የረዱት ከሐዲዎች ውሎ አድሮ እንደማይተኙለት በማወቅ እያስከለለ በየምክንያቱ ፈጃቸው፤ የተረፉትን እያሠረ አንገላታቸው።

ምንጊዜም ቢሆን ሀገሩን፣ ወገኑን የከዳ በማንም ዘንድ ታማኝነትን አያገኝምና፤ በተራው ከሐዲ የሚጠፋው በክሐዲ እጅ ነው። በዚህ ዓይነት ጣልያን መንዝን ለመያዝ የረዱትን ከሐዲያን በልዩ ልዩ ዘዴ ካስገለለ በኋላ፡- ሞላሌ ያለው ጦር አገሩን ለመዘረፍ፣ ቤቱን ለማቃጠልና ሰዉን ለመፍጀት በሁለት ረድፍ ተንቀሳቀሰ። አርበኞችም በአንድ ወገን እመወታን፣ በሌላ ወገን ደንገዜ፣ ከዚያም ሲያልፍ ይሞድ ላይ ወጉት። ቤት ማቃጠሉን ለማስጣል፤ አርበኞች መሐል ለመሐል ጥሰው እየገቡ በጥይት ጠበጠቡት። የጠላት ወታደሮች ጭንቅ ሲይዛቸው፤ ከአርበኞቹ ጥይት ለማምለጥ ራሳቸው ከለኮሱትና ከሚነደው ቤት እየገቡ ሲቃጠሉ እንደታዩ በታሪክ ተመዝግቦአል። ለርዳታ የመጡት የጠላት አይሮፕላኖች በዚህ ትርምስምስ ውስጥ መለየት እያቃታቸው የገዛ ወታደራቸውን በቦምብና በመትረየስ ደበደቡት። አርበኞች በሚያስደንቅ ሥልት ወታደሩን ስለፈጁበት፤ ጣልያን ወደ ተነሣበት ወደ ሞላሌ ምሽግ ተመለሰ። የተመለሰውም የሞቱበትን ወታደሮች ሬሣ፤ ቁስለኛውን ሳይቀር በእሳት እያቃጠለ ነበር።

አርበኞችን ለመደምሰስ ጠላት አዲስ ጦር ማምጣቱ ተሰማ። አርበኞች በበኩላቸው ደንገዜ ላይ ተሰብስበው ምክር አደረጉ። በምክሩም ላይ ሁለት ሐሳብ ቀረበ። አንደኛው ሐሳብ፡- የጠላትን ጦር መክበድና የሀገሩን መጉዳት እያመዛዘነ፤ ቦታ ለውጠን ብንከላከል ይሻላል የሚል ነበር። ሁለተኛው ደግሞ፡- መንዝና ተጉለትን፤ ይፋትን ሰቅቀን አንሄድም፤ የሕይወታችን ፍፃሜ ከዚህ ይሆናል አለ። ሁሉም እንደየፍላጐቱ ለሀገሩ እንዲከላከል ስምምነት ተደረገ። ቦታ መለወዋ የመረጠው ቡድን፤ በአቶ ወልደመስቀል ተሸፀፅ መሪነት ወደ ጅሩ ሄደ። የዓደባይን ዥረት ይጠብቅ የነበረውን የጠላት ጦር ሰብሮ ግንቦት 3 ቀን 1929 ዓ.ም እነዋሪ ላይ ከባላምባራስ /ራስ/ አበበ ጋር ተቀላቀለ። በመንዝና በተጉለት ተጋድሎዉን መቀጠል የመረጠው ሠራዊት፤ በልጅ ግዛቸው ኃይሌ መሪነት በነበረበት ቆየ።

የአርበኞች መለያየት ለጣልያን ደስታ ሆነለት። በደቡብ ያሉ አርበኞችን ጨርሶ ሀገሪቱን በመሉ መያዙን የሚገልጽና ከሞት የተረፈው የመንዝ ሕዝብ በየአመዱ እንዲገባ የሚጋብዝ የጥሪ ወረቀት በመንዝና በተጉለት በአይሮፕላን በተነ። ፋከራው ከባድ ስለነበረ፤ መልስ መስጠትም ስለአስፈለገ፤ መልስ ተሰጠው። የተሰጠው መልስ ማስታወቂያዎቹ ደርሰው እንደታዩ፤ መላዋን ኢትዮጵያ ይገዛለሁ የሚለው ውሸት እንደሆነና ከአሥመራ እስከ አዲስ አበባ በመኪና የሚንቀሳቀሰው በመሸማቀቅ እንደሆነ ገልፆ "...እኛ የሸዋ ልጆች ስለውሸትህ የጥይት ሽልማት አናንናጽፍህልን..." የሚል የተስፋ ቃል የሚሰጠው ሆነ።

ጠላትም የመንዝን ሕዝብ ቁርጠኝነት ከተረዳ በኋላ ክባድ ጦር አንቀሳቀሰ። አርበኞችም ከሐምሌ 19 ቀን እስከ 20 ቀን 1929 ዓ.ም ደንገዜ ላይ ገጥመው፤ አሳሩን አሳይተው፤ ወደ መጣበት ወደ ሰላድንጋይ ምሽግ መለሱት። የጥይት ሽልማት ሊሰጡት የገቡለትን ቃል ኪዳን ፈፀሙ።

አርበኞችን ለመደምሰስ የተማመነበት ጦር አምጥቶ እየደጋገመ አዘመተ። ነገር ግን ሰባት ጊዜ ከአካሄደው ስብሰባ በአንዱም አርኪ ውጤት ሳያገኝ ቀረ። የጦርነቱ ድግግሞሽ አርበኞች አዲስ ስልት እንዲቀይሱ አስገደደ። ስለዚህም እርስበርሳቸው ቃል ኪዳን ተግባቡ። ቃል ኪዳኑም ሁሉም በየግንባራቸው የተመደቡበትን ሥራ እንዳይለቁ የሚገድብና ከመካከላቸው አንዱ ቢሞት ሌላው የሟቹን ቤተሰብ እስከ ሕይወቱ ፍፃሜ ድረስ እንዲከላከል የሚያስገድድ ነበር። በዚህ ዓይነት ቃል የተገባቡት የመንዝ ጀግኖች ከአሰቡበት ቦታ ፍቅቅ ሳይሉ ጠላትን አምስት ጊዜ ወጉት። እየደጋገመ የሰማሌ ጦር ቢያመጣም አልተበገሩለትም። የተግደረደረ መስሎት፣ ጠላት ከመሐል ቦታ ድንኳን አስጥሎ መዝናናት ያዘ። አርበኞች በሰላይ ከአጠሩ በኋላ በመነፅር ተመልክተው ማን ማንን እንደሚመታ ተከፋፍለው ከሩቅ በማነጣጠር፣ አንድ ላይ ሮምታ በመተኮስ፣ ሲዝናኑ የነበሩትን ከፍተኛ የጠላት የጦር መኮንኖች በአንድ ጊዜ ጨረሱአቸው።[3]

በመንዝና በተጉለት፣ በ1929 ዓ.ም የተካሄደው ጦርነት ከሞላ ጐደል ይህንን ይመስል ነበር። ጠላት ይቀዘቅዘልኛል፣ አርበኞችም ይደክማሉ የሚል ሐሳብ አድሮበት ነበር። ነገር ግን የ1930 ዓ.ም ሁኔታ የባሰ ሆነ። በዚህ ጊዜ ከቡልጋ ወገን መልእክ ፀሐይ ኢያሱ ስለመንገሡ በመንዝና በተጉለት አዲስ ወሬ ተሰማ።

በዚሁ ሰሞን፣ ቀደም ብለው በድንገት ተማርከው የነበሩት ፊታውራሪ ወንድምነህ ጓደኞቼን አባብዬ አመጣልሀለሁ የሚል ቃል ሰጣልያን፡ በመሰጠት ከተሰቀቀ በኋላ እንኳንስ ሌላ ሊያመጡለት፣ አሳቸው ራሳቸው የአርበኝነት ትግላቸውን ቀጠሉ።

በሰላይ አማካይነት ከሚያገኙት መረጃ አንዳንድ እየሳተ ስለአስቸገራቸው አርበኞች ራሳቸው ወደ ምሽግ እየቀረቡ ማጥናት ያዙ። በተጉለት አካባቢ የነበሩ አርበኞች በደብረ ብርሃን አካባቢ የነበረውን ሁኔታ እየቀረቡ አጠኑ፤ መስከረም 26 ቀን 1930 ዓ.ም እስከ ዘንዶ ጉር ድረስ ተጠግተው አጠኑ። አንደኛው ጥቅም፡- በአንድ የባንዳ መሪ ቤት የተደበቁ ሠላሳ አፈድስት መውዜር ከነዮቶቻቸውና ሌላም ለአርበኛው የሚያገለግሉ ጥሪቶች ማግኘታቸው ሲሆን፤ ሁለተኛው ጥቅም ደግሞ፡- የጠላትን ሁኔታ በቅርብ ማወቃቸው ነበር።

አርበኛው ከዚህ ጥናት በኋላ ወደ ዘንዶ ጉር አመራ። ገቦ ከተባለ ቦታ ጣልያንን ግንባር ለግንባር ገጠመው። ጣልያን በመድፍ ድብደባ የሚያካሂድበትን መሥመር በልዩ ልዩ ዘዴ እያለፈ በመጠጋት፤ ብዙ ጉዳት

አደረሰበት። ምርኮው ግን የሚያረካ አልሆነም፤ ልብስም ቢገኝ ብል የበላው ሆነ።

የገጠን ጦርነት ለመበቀል፣ በመስከረም ወር መጨረሻ 1930 ዓ.ም ጠላት ሌላ ጦር በሣጋ በኩል አመጣ። አርበኞች ለመቀረጥ እንዲመቻቸው ግንባር ቀደሙን ጦር ወደ እነሱ ወደራሳቸው ትተው ከመካከለኛው ጦር ላይ አደጋ ለመጣል ተማከሩ። ይል ከተባለ ቦታ አድፍጠው ጠብቀው እንደዚሁ አደረጉ፤ እየነጣጠሉ ደበደቡት። የጠላት ጦር ወደ መጣበት ወደ ሣጋ ሩጫውን ቀጠለ። አንድ ግራ የገባው የጠላት ወታደር መትረየሱን ትቶ እግሩን ተሸክሞ ሮጠ። አርበኞችም የእንጨት እግር ሠርተው በመትረየሱ ተጠቀሙበት። ጠላት ከወገኑ ብዙ ሰው ስለሞተበት፣ ሬሣውንና ቁስለኛውን ሳይቀር ከቤት ውስጥ እያገባ በማቃጠል ሽሽቱን ቀጠለ። ከአርበኞችም ብዙ ሰው ቆሰለ። ባላምባራስ /ራስ/ አበበ አረጋይም እጃቸው ላይ ቆሰሉ።

ጠላት እንደገና በአርበኞች ላይ ሳያስቡት አደጋ በመጣል ለማጥቃት ተንቀሳቀሰ። በራያው /ደጃዝማች/ ከፈለው ወልደፃድቅ የሚመሩ አርበኞች ሁኔታውን በቅድሚያ በማወቅ ምቹ ቦታ ይዘው ጠበቁት። ጥቅምት 16 ቀን 1930 ዓ.ም ቀያ ከተባለው ቦታ ገጥመው ደበደቡት። ጠላትም ወታደሩን አስፈጅቶ ሽሹቱን ቀጠለ።

ህዳር 18 ቀን 1930 ዓ.ም ደንገዜ ቆሎ ማርገፊያ ከጠላት ጋር ከፍተኛ ጦርነት ተደረገ። በልጅ ግዛቸው ኃይሌ የሚመሩት አርበኞች የጠላት ጦር ወደፊት እንዳይገፋ፣ ወደ ኋላውም እንዳይመለስ ሰግጠው በመያዝ ከህዳር 18 እስከ 22 ቀን ድረስ አራት ቀን ወጉት። በአይሮፕላን ቢያስደበድባቸውም፣ አልተበገሩለትም። እንዲያውም በአይሮፕላን የተጣለለትን ለባት ሣጥን ስንቅና መሣሪያ እየተሽቀዳደሙ በመልቀም ወሰዱበት። ከጦሩም ብዙ መሣሪያ ማረኩበት።

በደጃዝማች አውራሪስ የሚመራው አርበኛ፣ አዚያው ደንገዜ ሬንቻ ከተባለው ቦታ የነበረውን የጠላት ጦር ከብቦ አስጨነቀው። ውሃ እንዳይቀዳና ለስንቁ ማብሰያ እንጨት እንዳይሰብር ከልክለው ከህዳር 18 ቀን እስከ 24 ቀን 1930 ዓ.ም አሰቃዩት። በመጨረሻም ህዳር 28 ቀን ጦርነት አድርገው ጉዳት አደረሱበት፤ በአይሮፕላን እያስደበድባቸውም ብዙ ገደሉበት። ጠላትም ከጦርነቱ የተረፈውን ወታደሩን ይዞ ከክበባውን በማምለጥ ሰላድንጋይ ገባ።

ሁኔታው ሲከበድበት ጣልያን በጀነራል ማሊቲ የሚመራ ጠንካራ ጦር ላከ። አርበኞቹ ደንገዜ ላይ ታህሣሥ 12 ቀን 1930 ዓ.ም ደረት ለደረት ገጥመው ለአራት ቀን ወጉት። ብዙ ወታደር ፈጁበት። ጀነራል ማሊቲ የተቀመጠበት በቅሎ ተመትቶ ሲወድቅ፣ እሱ ለጥቂት አምልጦ ደብረ ብርሃን ገባ። የአርበኞች ልብ ደነደነ፤ አንዳንድ ባንዳም ከጠላት ወደ እነሱ ዞረ።[4]

የደንገዜ ጦርነት በዚህ አላበቃም። ለጣልያን ይህንን አካባቢ ከአርበኞች ማስለቀቅ አስፈላጊ ነበር። ለአርበኞቹም ደንገዜ ወሳኝ ቦታ ነበረች።

ስለዚህ ጣልያን አዲስ ጦር አመጣ። ከታህሣሥ 20 እስከ 26 ቀን 1930 ዓ.ም ብርቱ ጦርነት ተደረገ። ጣልያን ለማጥቃት አርበኞች ለመከላከል በብርታት ተፋለሙ። ከጠላትም፣ ከወገንም ብዙ ሰው ወደቀ። ጦርነቱን መቀጠል ሰው ማስጨረስ መሆኑ ስለታወቀ፣ አርበኛው ሽሽ /ላሉ ምድር/ ተሻግሮ ተቀመጠ። ሁለቱም ወገን ስለተዳከመ፣ ኩራኩሬ ያለው የጠላት ጦርና ሽሽ የሠፈረው አርበኛ ማዶ፣ ለማዶ እየተያዩ ሳይተኻኮሱ ሁለት ሣምንት ያህል ተቀመጡ።

ጣልያን መንገዘን የመያዝ እርምጃውን ቀጥሎ መሢ ደረሰ። ይህ መሢ የተባለው አካባቢ ደጋ ነው። በፊታውራሪ /ደጃዝማች/ ዳምጠው መሸሻ የሚመራው አርበኛ ጥር 28 ቀን 1930 ዓ.ም ገጠመው። ሲወጋው ውሎ፣ ሲወጋው አደረ። በማግስቱ በልጅ ግዛቸው ኃይሌ የሚመራው አርበኛ ለእርዳታ ደረሰ። በጠላት ላይ ተከነበለበት። የጠላት ወታደርም እንዳይተኩስ ቆፈን፣ እንዳይሸሽ ብርክ ያዘው። ሁለት ነጮች ከጥቂት ወታደር ጋር ሲያመልጡ፣ አብዛኛው በጥይትና በጉራዴ አነከቱት። ጣልያንም የተረፈውን ጦር ይዞ ወደኋላው ተመለሰ የመሢ እልቂት በአካባቢው ሕዝብ ዘንድ ሲታወስ ይኖራል።

ጣልያን ተደጋግሞ በደረሰበት ውርደት ተቆጨ። በቂ ጦር ለማዘጋጀት ጊዜ ፈጀበት። ስለዚህ በየካቲት፣ በመጋቢትና በሚያዝያ በዚህ አካባቢ ጦርነት ማካሄድ አልቻለም። አርበኞች እረፍት አደረጉ፤ የቆሰለው አገገመ። ጠላትም አስተማማኝ የመሰለውን ጦር አዘጋጅቶ የወሎን ጦር በሰፈድ ሜዳ፣ የራያንና የጥሙጋን በምችግ፣ የጀሌንና የወረይሉን ባይገም አሳልፎ በአፍቅራ ላይ ሲያዘምት ተገቀሳቀሰ። የአርበኛው ቁጥሩ እጅግ ብዙ ስለነበር፤ ባለመተዋወቅ አርስበርሱ እንዳይጐዳዳ በበኩሉ ጥንቃቄ አደረገ። ጠላት አስቀድሞ መጥቶ ከላውን፣ ምችግን፣ ከወደኋላም የዱገምን በሮች እንዳይዝበት ተሽቀዳደመ። ከመድረሱም ገጥመው፣ ግንቦት 30 ቀን 1930 ዓ.ም ታላቅ ጦርነት ተደረገ። ጣልያን የአርበኛውን መጠንከር ሲያይ ከምድር በመድፍ፣ ከሰማይ በአይሮፕላን በቦምብ ደበደበው። አርበኛው ተጠንቶ የጨበጣ ውጊያ ተካሄደ። ከሁለት ቀን ፍልሚያ በኋላ የጠላት ጦር ከወዲያ ወዲህ ተራወጠ። ድሉ ለአርበኞች ሆነ።

በዚህ ጦርነት በጠላት ላይ ብዙ ጉዳት ደረሰ። ከአርበኞችም ወገን ብዙ ሰው ሞተ፣ ሌሳም ብዙ ቆሰለ። ቢሆንም ድል የእነሱ በመሆኑና ብዙ ምርኮ በማግኘታቸው ተጽናኑ። የምርኮን ነገር ስንመለከት በዚህ ጦርነት ላይ ከተከናወኑት ሥራዎች የአንድ የአርበኛንና የአንድ ባንዳን ጉዳይ ማውሳት ይገባናል። አንድ ወጣት አርበኛ ከአንድ ባላገር ቤት ገብቶ ባካሄደው ዝርፊያ ተከስሶ ጥፋቱ ከተመረመረ በኋላ ይቀጣል፤ መሣሪያውንም ይገፈፋል። ጀሌውን እንዳለ ይህ ከላይ የተገለፀው ጦርነት ይካሄዳል። ወጣቱ በደረሰበት ቅጣት ቅሬታ፣ ባዶ እጁን በመሆኑም ፍርሐት ሳይሰማው ከጦርነቱ ገባ። በድንጋይ ውርወራ ጠላቱን ገድሎ መውዜር ጠመንጃ ማርኮ ስለመጣ፣

በጓደኞቹ ዘንድ ተደነቀ። በዚህ ዓይነት የወንድ ሥራ በመሥራት፣ የዜግነት ግዳጁን ለመወጣት ቻቻ።

ከላይ በተጠቀሰው ጦርነት የተገኘው ምርኮ በሚሰበሰብ ጊዜ፣ አንድ ባንዳ ከስድስት መቶ ሬሣ ውስጥ ተሸጉጦ ተገኘ። ጨነኛ ነበር። አርበኞቹ ይዘው ሲመረምሩት ማንነቱ ታወቀ። በአርምኛ ቋንቋ ምክር ተሰጠው። ወደ ዘመዶቹ ሄዶ፣ የሀገር ሽማግሌዎች ሰብስበ፣ እንዲመክር ተነገረው። ቢሆንላቸው የሀገራቸውን ጠላት እንዲወጉ፣ ይህም ባይሆን አርፈው እንዲቀመጡ እንዲያደርግና የአርበኞችን ዓላማና ጥንካሬ እንዲነግር ታዘዘ። እሱም ተስማምቶ ወደ ሀገሩ ሄደ። ከዚያ ቀን ጀምሮ በእሱ ትውልዶ ቦታ የነበሩ ሰዎች በመንዝ ላይ አልዘመቱም።

ከዚህ ጦርነት በኋላ አርበኞች ስብሰባ አድርገው ተማከሩ። "...በአንድ ላይ ተከማችተን ብንቀመጥ በስንቅ እንጉዳለን፤ ብንበታተን በጠላት እንጠቃለን። ስለዚህ በየቦታችን ሆነን ነቅተን እንጠብቅ። ጠላት በመጣ እንረዳዳ" ተባባሉ። እንደዚሁም አደረጉ።

በመንዝና በተጉለት የ1930 ዓ.ም ትግል በዚህ ዓይነት ተፈጽሞ የ1931 ዓ.ም ተጀመረ። የአካባቢው ሁኔታ አስግቶት ነበርና፣ ጣልያን ክረምቱ እንደወጣ ማጥቃት ጀመረ። መስከረም 7 ቀን 1931 ዓ.ም ሲመጣ ሐሳቡ በአካባቢው ያሉትን አርበኞች አስደንግጦ በማባረር፣ ሣሊት አሻል ላይ ምሽግ ለመሥራት ነበር። አርበኞቹ ሐሳቡን አውቀውበት ነበርና፣ እነሱ ከአሉበት ድረስ እስኪመጣ ድረስ መጠበቃቸውን ትተው እሱ አለበት ድረስ ሄደው ገጠሙት። ውጊያው፦ ከምድር በመድፍና በቦምባርድ፣ ከሰማይ፦ በቦምብ እየተደገፈ በከባድ እግረኛ ጦር ከሐመሉ እስከ አሑድ፣ ለአራት ቀን ተካሄደ። ከግራ፣ ከቀኙ ብዙ ጠላት ወደመጣበት፣ ወደሰላድንጋይ ሸሸ። አርበኞች ለማሸነፍ የቻሉት የኋላኛው እንዳይጠጋና ለእርዳታ እንዳይደርስ በጥይት በማገድ፣ ከጦር ግንባር የገባው ደግሞ ወደፊት እንዳይገፋ እንዲሁም ወደኋላው እንዳይመለስ በጥይት ቆልፎ በመያዝ ነበር። ጭንቅ ሲሆንበት ያሰቀው እያለቀ ወደኋላ መመለስን መረጠ። አርበኞች ብዙ መሣሪያ አገኙ።[5]

ይህ በአንዲህ እንደለለ ንጉሠ ነገሥት መልአከ ፀሐይ መሞታቸው በዚያ ተሰማ። ራስ አበበም ወደ ተጉለት ዙሩ። ጠላት የማጥቃት ሥራውን በማጠናከር ጥቅምት 23 ቀን 1931 ዓ.ም ሌላ ጦር አምጥቶ ሣሊትን ለመያዝ ሞከረ። ሣሊት ላይ ምሽግ በመመሸግ በመስከረም 7 ቀን የደረሰበትንም ውርደት መሸፈን ነበረበት። አርበኞቹም እንደልማዳቸው ከየአሉበት ተሰባስበው ገጠሙት። ሙሉ ቀን ውጊያ ተካሄደ፤ ስመጥር አርበኞች እዛ ወደቁ። ከጠላትም ወታደር ብዙ አለቀ። አንዱም ወገን ሳያሸንፍ ወደየቦታቸው ተመለሱ።

ራስ አበበ ክቡልጋ ወደ ተጉለት በጥቅምት ወር 1931 ዓ.ም ዙሩ። በተጉለት ቆይታቸው የሠራዊቱን አንድነት ለማስተባበር ስለሚቻልበት መንገድ

ላይ ምክር ተደረገ። ቀደም ብሎ እምቦ ላይ ተመሳሳይ ምክር ተደርጉ እንደነበር የሚታወስ ነው። የጣልያን ሐሳብ የኢትዮጵያን ሕዝብ ፈጅቶ፣ የራሱን ሕዝብ አምጥቶ ማስፈር መሆኑ በዚህ ወቅት ሰቁል ጭምር ግልጽ ሆኖ ነበር። በአንዳሩ ደግሞ አርበኞች የሚጋደሉት ስለሀገር ነፃነት፣ ስለሃይማኖት ስለ ወገን ክብር መሆኑ ለአሀዳዊያን ጭምር እየታወቀ ሄዶ ነበር። በሦስተኛው ወገን የአርበኛውን አንድነት የሚያጠናክር አንድ አሰባሳቢ አካል ማስፈለጉ አውን ሆነ። በአራተኛው ወገን ደግሞ አርበኛው ሲሞት፣ ሲቆስል፣ ሲታመም የትም ወድቆ መቅረቱና ስሙም መታሰቢያ አለማግኘቱ ዕለት፣ ዕለት የሚታይ ጉዳይ ነበር። ስለዚህ አንድ የመተባበሪያና የመረዳጃ ማህበር መመሥረት አስፈላጊ ሆነ። አርበኞች እነዚህን ጉዳዮች በመመልከት ጥቅምት 23 ቀን 1931 ዓ.ም ተጉለት አንቀላፋኝ ላይ የጀግኖች ማህበርን መሠረቱ። የመተዳደሪያ ደንብም አወጡ።

የመተዳደሪያ ደንቡ ሃያ ሦስት አንቀጽ ያለው ሆኖ ዋና ዋና ነገሮችን የሚያመለክት ነበር። ከሚደርስባቸው ችግርና አደጋ አርስበርሳቸው እንዲረዳዱ፣ የሞተውን ለመቅበር፣ የቆሰለውና የታመመውን ለማስታመም፣ አርበኞችም ምንም ዓይነት ችግርና መከራ ቢያገኛቸው ሕይወታቸው እስኪያልፈ ከመከራከር በቀር ለጠላት እንዳይገዙ ወይም ወገናቸውን እንዳይክዱ፣ አንዱ አንዱን እንደ እናት ልጅ እንዲያየው፣ በደረሰበት አደጋ አይቶት ጥሎ እዳይሄድ በሰልፍም /በጦርነት/ ውስጥ ትቶት አጋልቦት እንዳይሸሽ፣ ማህበሩ የሚያወጣውን ምልክት እንዲይዝ፣ ሹማምንቶች እንዲመረጡና በዚሁ ደንብ መሠረት እንዲሠሩ፣ ሹማምንቱንም አርበኛው በፈለገ ጊዜ እንዲለውጣቸው፣ ማህበርተኛው በፍፁም ልቡ የማህበሩን ደንብ እንዲፈጽም፣ ከአሥር አንድ እንዲሰጥ፣ እርዳታ መቀበል የሚገባውን የተመረጡት ሹማምንት እንዲመርጡ፣ አጥፊን ማህበሩ በመሰለው እንዲቀጣ፣ የሚቾች ቤተሰቦች እንዲረዱ፣ ማህበሩ ደንቡን በመጨመር፣ በመቀነስ ወይም በማደስ እንዲያሻሽሉ፣ ማህበሩ የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት የሚሰጠውን ሕግና ደንብ፣ ትእዛዝም እንዳይቃወም፣ ማህበሩም "የጥንታዊት ኢትዮጵያ የጀግኖች ማህበር" እንዲባል የሚወሰን ሆነ።[6]

ከማህበሩ መቋቋም ጋር አብሮ መጤን ያለበት የጊዜው ሁኔታ ነው። ከወቅቱ ሁኔታዎች ዋና ዋናዎቹን ስንመለከት፦ ንጉሠ ነገሥት መልአከ ፀሐይ ሞተው አርበኛው መሪ ያጣበት፣ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ወደ ቀቢፀ ተስፋ የተቃረቡበት፣ ጣልያን በእርቅ ስም የሰውን ልቡና ለመከፋፈል የሚራወጥበት፣ አውሮፓውያን የኢጣልያን ትብበር ለማግኘት ሲሉ የኢትዮጵያን ጉዳይ ቸል ያሉበት፣ የዓለም መንግሥታት ማህበር ለመውደቅ የሚንገዳገድበት፣ የጀርመንና የጃፓን ኃይል የገነነበት ጊዜ ሆኖ እናገኘዋለን።

የማህበሩ መቋቋም የአርበኝነትን ሥራ አጠናክሮአል። አሁን ስለአለው ማህበርም መነሻ ሆኖአል። የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴንም ሥልት አርበኛው

መልሶ እንዲቀበል በማድረግ ረድቶአል። ስለዚህ ማህበሩን ያቋቋሙ አርበኞች በታሪክ ክብርም ምስጋናም ይገባቸዋል።

ምንም እንኳን በተደጋጋሚ በተካሄዱት ጦርነቶች ጉዳት ቢደርስበት፣ ጣልያን አርበኞችን ለማጥቃት የሰነዘረውን ክንዱን ሳያጥፍ እርምጃውን ቀጠለ። በራስ አበበ የሚመራው ሠራዊት ህዳር 27 ቀን 1931 ዓ.ም ምሑይ ላይ ለሦስት ቀን ውጊያ አካሄደበት። አንድ ኢጣልያዊ ከፍተኛ መኮንን ሞተ። ከበባው ጠንካራ ስለነበር ጣልያን ለወታደሩ ጥይትና ስንቅ በአይሮፕላን አምጥቶ ጣለ። ነፋስ አቅጣጫውን ለውጦ ነበርና ስንቁ ለአርበኞች ደረሰ። በውጊያው ላይ ብዙ የጠላት ወታደር አለቀ። ከአርበኞችም ጀግናች ወደቁ። አርበኞች ብዙ መሣሪያ ማረኩ።

የሸዋ አርበኞች ሐሳብ ከፍ ሲል በተጠቀሰው ዓይነት ተጠቃሎ እያለ የጠላት ጦር መጣ። አርበኛው ህዳር 5 ቀን 1931 ዓ.ም ዲርማ ከተባለው ቦታ ገጠመው። ከሁለቱም ወገን ብዙ ሰው ወደቀ። ራስ አበበም ከጉንጪቸው ላይ በጨረፍታ ቆሰሉ። የጠላት ኃይል አይሎ ነበርና ወደ ዋዩ፣ ከዚያም ወደ ገደማ ሄደው ሰፈ ሰንድ በተባለው ቁልልታ ላይ ሰነበቱ። ከዚያም በታህሣሥ ወር 1931 ዓ.ም ወደ ቀያና ዘረት ጉዞአቸውን ቀጠሉ።

ከዚያ እንደደረሱ ምክር ተጀመረ። ዋናው ሐሳብ ጀማ ላይ መሸጉ ተቀምጦ የነበረውን ጦልያን ለመውጋት ነበር። የዚህ ምሽግ መሰበር፣ ስንቅና ትጥቅ ለማግኘት፣ ቅዝቃዜ የታየበትን የወሎን ትግል መልሶ ለማቋቋም እንደሚረዳ ታስቦበት ሳይሆን አልቀረም። ነገር ግን ሐሳቡ በመንዝና በተጉለት አርበኞች ዘንድ ሥጋት ፈጠረ። ዋናው ጥያቄ- ከሆነስ ደግ ሳይቃናስ ቢቀር? የሚል ነበር። ሃምሣ አለቃ ታደሰ ባላይነህ እና መምሬ ጎሹሜ ወልደጊዮርጊስ ቀያ ድረስ በመሄድ የተዘጋጣቸውን ሥጋት ገለፁላቸው። ቢቀር እንደሚሻል አስረዱአቸው። ራስ አበበም ይህንን ምክር ሰሙ። የጀማን ምሽግ ለማጥቃት የነበራቸውን ሐሳብ በመተው ወደኋላ ተመልሰው መረው ላይ ሠፈሩ።

ጠላት በራስ አበበ በሚመራው አርበኛ ላይ ጥቃት ለማካሄድ በማሰብ፣ ከሞላሌ ተነስቶ በቆሎ ማርገፊያ በኩል አድርጐ ማያ ከተባለው አጠገብ፣ ፈረስ መጋለቢያ ሠፈረ። ወደስጥ ለመሄድ ያለበ በማስመሰል ሠራዊቱን ለማዘናጋት ትንሽ ከተጓዘ በኋላ አቅጣጫውን ለውጦ ራስ አበበ ወደ ነበሩበት ወደ ቀያ ገሠገሠ። ሐሳባቸው አወናብደው ክብ ለመሥራት ነበር። ውግር ማልቀሻ ከሚባለው መልካ፣ ሞፈር ውሃ፣ ከወንዝ ገባ። ውሃ ሲጠጣና ሲታጠብ፣ አርበኞቹ ድንገት ደርሰው አደጋ ጣሉበት። በጥይት ሲጨፈጭፉት ተርበተበተ። አንዳንዱም ከባሕር እየዘለለ እየገባ በገዛ እጁ ሞተ። የሚበዛው አርበኛ፣ ጥይት አለቀበት።

ከንጉሠ ነገሥቱ ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ደብዳቤ መምጣቱ በሕዝብ ጆሮ አስቀድሞ ተሞልቶ ነበርና፣ ወረው አተባለው ቦታ ድረስ እንዲሰበሰብ ለሕዝቡ ጥሪ ተላለፈ። ሴት ወንድ፣ ልጅ አዋቂ፣ ሳይል ሕዝብ ተሰበሰበ።

ከንጉሠ ነገሥቱ የመጣውን ደብዳቤ ራሳቸው አነበቡ። እልልታው ቀለጠ፣ መትረየስ በብዛት ተተኮሰ። ታላቅ ደስታ ሆነ። ከደስታቸው ጽናት የተነሣ ያለቀሱ ብዙዎች ነበሩ።[7]

ይህ ደብዳቤ ከንጉሠ ነገሥቱ፣ ከለንደን ታህሣሥ 27 ቀን 1931 ዓ.ም በቁጥር 69 የተፃፈው ሳይሆን አልቀረም። እሱ ከሆነ ንጉሠ ነገሥቱ ለኢትዮጵያ የመንግሥታት ሕግ እንዳይጐድልባት ለዓለም መንግሥታት ለማስታወቅ አውሮፓ እንደሚገኙ ይገልፃል። ቀደም ብሎ ከአርበኞቹ የተፃፈላቸው ደብዳቤ፡- ከጠላት ጋር በጀግንነትና በመተባበር የሚከሳከለው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላትን እስከመጨረሻው በመቃወሙ ቆርጦ፣ ለነፃነቱ የሚታገል መሆኑ ለዓለም ሕዝብና ለመንግሥታት ማህበር ለማስረዳት ቡበዙ እንደረዳቸው የገለጸ ነበር።[8] የንጉሠ ነገሥቱ ደብዳቤ ደርሶ አርበኞችን ማስፈንጠዙ እና ደብዳቤዉም ለሕዝብ ግልጽ መደረጉ፣ ቅስቀሳ ለማካሄድ መሆኑን ይገነዘቧል።

በዚህ የተነሣ ጥቃቱን እንደገና አጠናከረ። በጥር ወር 1931 ዓ.ም እንቅስቃሴ አደረገ። ጠላት የአርበኞችን እንቅስቃሴ ነቅቶ መጠበቅ ሥራው እንደመሆኑ፣ በአውሮፓ በመካሄድ ላይ የነበረው ሁኔታ አስጊ በነበረበት በዛን ጊዜ አርበኞች ማህበር ማቋቋማቸውን፣ ከንጉሠ ነገሥቱ ደብዳቤ ማግኘታቸውን፣ ሕዝብ ማስተባበራቸውን ሲሰማ፣ በቀላል እንዳይሰቃቸው አውቀው ተዘጋጅተው ነበርና ጀምጉዳ ከተባለው ቦታ ተዘጋጅተው ጠበቁት። አደጋ ጥሰው ከባድ ጉዳት አደረሱበት። ብዙ ወታደር ጨርሰው፣ ብዙ መሣሪያ ማርከው፣ ወደ መጣበት መልሰው አባረሩት።

ጠላት በተጉለት ሲንቀሳቀስ፣ አርበኞች ሞጆ ዋሻ ውስጥ ተከተቱ። ጠላት ይህንን ሰምቶ መጋቢት 15 ቀን 1931 ዓ.ም ከበባቸው። ሁኔታው አሰቃቂ ሆነ። ሰብረው ለመውጣት አቅማቸው የሚፈቅድ አልነበረም። አቶ ወልደ ገብርኤል የተባሉ ጀግና፣ በሕይወታቸው ቆርጠው እና ጥቂት ጓደኞቻቸውን ይዘው ፈጥነው በመድረስ ከበባውን በጦር ሰብረው ወገኖቻቸውን ከጥፋት አዳኑ። እንደ እኔ፣ ሊመሰገኑ ይገባቸዋል።

በዚሁ ወር ከአርበኞች ጋር በተደረገው ስምምነት ጠላት ደንገዜ፣ ሸሶ መሸጉት የነበረውን ምሽግ ለቅቆ ቆሎ ማርገፊያ፣ ማማ ምድር ወደሚባለው ሄደ። በኋላ፣ አርቅ በፈረስ ጊዜ፣ አርበኞች በዚህ ምሽግ ላይ ለስድስት ቀን ከበባ አካሄደው አሣሩን አሳይተውታል።

ራስ አበበ ወደ ተጉለት ተሻግረው፣ ከዚያም ወደ ቡልጋ፣ ለመዝ፣ ጉደአና ሰገድ ከተባሉት ቦታዎች መካከል ደረሱ። የጠላት ጦር ይህንን ሰምቶ ወደ አንቀላፊኝ ገሠገሠ። በሃምሣ አለቃ በላይነህ የሚመራው አርበኛ በሦሥስት ደርሶ አያፍሩባ ከተባለው ቦታ ላይ አደጋ ጣለበት። በረዶ እንደመታው ቅጠል አራገፈው፣ ራስ አበበን ለማጥቃት በማለት የተንቀሳቀሰበትን ዓላማውን አፈረሰበት።

እርቅ በፈረሰ ጊዜ ለጠላት ክንቱ ምክር እየመከረ፣ የባንዳን ሁኔታ እያጠናከረ፣ የሰላድንጋይን ምሽግ የሙጥኝ ብሎ ተቀምጦ የነበረውን፣ ወልደገብርኤል የተባለውን የጠላት መሣሪያ ማስታገስ አስፈለገ። በመሆኑም አንድ የአርበኛ ቡድን ከተጉለት ተንቀሳቅሶ ሚያዝያ 23 ቀን 1931 ዓ.ም በድንገት ደርሶ ፀጥ አድርጐት ወደ ቦታው ተመለሰ። አንድ ኢትዮጵያዊ በዚህ ዓይነት መገደሉ የሚያሳዝነው ይኖር ይሆናል። ባይገደል ግን እሱ በሚቆሰቁሰው ጦርነት እጅግ ብዙ ኢትዮጵያውያን መሞታቸው ይቀጥላል። እሱም ተመክሮ ያልታገሠ በመሆኑ ከዚህ መጥፎ ግብሩ አይታቀብም ነበር። ስለዚህ የተወሰደው እርምጃ ተገቢ ነበር። ለነገሩ የተመካበት ጠላትም ሳይከላከልለት ቀረ።

ወደ ዋናው ጉዳይ እንመለስ። ጣልያን ከሰላድንጋይና ከሣሊት ምሽግ ወታደር አዘመተ። በአንቀላፊኝ በኩል ወደ ዓባይ ቆላ ለመውረድ ሲግተለተል፣ አርበኛው አይካና ግፍጥጫ ከተባሉት ቦታዎች ጠብቆ በጥይት ሸነቆጠው። ጣልያንም ከሸንቆጣው የተረፈውን ወታደሩን አስከትሎ ወደ ምሽጐቹ ተመለሰ። ጣልያን ምሽግ እየሠራ፣ ባንዳ ምሽግ እየተጠጋ አስቸገረ። ይህንን ሁኔታ ለማስታገስ የመንዝ አርበኛ አርምጃ ወሰደ። ቡተለይም ሃምሣ አለቃ ታደሰ በላይነህ የሚመሩት የወደደውን በመምከርና በማስረዳት፣ እምቢ ያለውን በጦር ኃይል በማጥቃት ወደነፃነት ተጋድሎ እንዲመለስ ለማድረግ ሠራዊቱ በቡድን ተከፋፍሎ ተንቀሳቀሰ። ከመሣቆ ተነስቶ፣ በመዘዘ በኩል አድርጐ፣ ታቦርና ዳግማት ያሉትን ሽማግሌዎች አማከረ። የደምፍላት የደረሰበት አርበኛ በወሰደው የመልሶ ማጥቃት እርምጃ ብዙ ሰው አሰቀ። ብዙ ንብረት ወደመ። ባንዳው ንግግር ሰብሮ ተኩስ በመክፈቱ የሞተ ፌሣው ፍትሐት እንዳይደረግለት፣ ከቅጽረ ቤተ ክርስቲያን እንዳይቀበር ተከለከለ። ምንም አርምጃው ከባድ ቢሆን፣ በመቀጣጫነት ጠቀመ። ሰው በምክርም፣ በቀለብም ረዳቸው። በተለይ አቶ ሞገስ ተሰማ የተባለ የጭዋ ልጅ፣ የመኪና ስፈት እውቀት ስለነበረው፣ የተቀዳደደው ልብሳቸውን በነፃ በመጥቀም ረዳቸው። ታርዘው የነበሩትንም በገንዘቡ ልብስ እየገዛ አለበሳቸው።

ከደግነት እልቂት ከተረፉት ባንዶች መካከል ጥቂቶች ደብረ ሲና ሄደው የደረሰባቸውን ጉዳት ለጌታቸው፣ ለጣልያን ነገሩ። ጣልያን ጦሩን እያግተለተለ በመሶቢት ተጉዞ እናዥጋ አፋፍ ላይ መትረየሱን ጠምዶ አንፈቀፈቀው። ደግነቱ አካባቢው ድንጋያማ ስለነበር አርበኞች ከእነዚያ ሥር እየተጠለሉ ከመዓቱ እንኳን ዳኑ። ተኩስ ድምጽ ሳያሰሙ፣ ገደሉን እየሚጠሙ ወጥተው አፍንጫው ላይ የነበረውን ጡምና የተባለውን በር ያዙበት። ጣልያን ይህንን ሲያይ ምንም ሳይወላዳ ሰተት ብሎ ደብረሲና ምሽግ ገባ።

መንገዶች ተዘግተው፣ ገበያ በመጥፋቱ ምክንያት፣ በአርበኛው ላይ ረሃብ ፀና። ይህንን ችግር ለመወጣት ለጦርነት አመች የሆኑትን ገደላ ገደል

ቦታዎች እየተወ ሕዝብ ወደ ሠፈረበት አካባቢ መሄድ ግድ ሆነበት። ቀድሞውኑ ለም የሆኑትን ቦታዎች እየለቀቀ የሄደው አገር እንዳይጠፋ፣ ሕዝብ እንዳያልቅ ነበር። ስለዚህ አንዱ የአርበኞች ቡድን ቆብ አስጥል ሄዶ ተቀመጠ። ጠላት ደግሞ ገስግሶ ደረሰ። ወሬውን ስለሰሙ ሊከባቸው የመጣውን ጦር እነሱ ከብበው እንደራቻ ወቁት። ማር ማረፊያ ደረስ አባረሩት።

የቆብ አስጥልን ጦርነት ወሬ ሲሰማ ጠላት ሌላ ጦር ሠርቶ እዚያው ቆብ አስጥል፣ ግም ውሃ ድረስ መጣ። አርበኞች ቦታ ይዘው ጠብቀው ደንገተኛ አደጋ በመጣል ብዙ ወታደሮች ገደሉበት። ጠላት ስለአየለባቸው፣ ሌት አምባ ወደ ተባለው መንደር ወረዱ። ወይራ አልዲት ከተባለው ቦታ የነበረው ጠላት እንዳያጠቃቸው፣ አመጤ መቀመጫ የተባለውን ተራራ ተገን አድርገው ወደ ጸሐና ወጡ። ከቆብ አስጥል ጀምሮ ይከታተላቸው የነበረው ጠላት ገሥግሦ ደረሰባቸው። እነሱም እንዳልለቀቃቸው ባዩ ጊዜ ጥሰው መነጠሩት። እሱ በተራው ሲሸሽ፣ ጥፍጥፍ ድንጋይ ድረስ እያባረሩ በመሸንቆጥ ወንፈላቸውን ከፈሉት።

የቆሰሰውም፣ የታመመውም፣ ያገግም በዛ በነበረበት ጊዜ፣ ጠላት አደጋ ጥሎ ለመፍጀት ተሸልኮ መጣ። ወይዘሮ ብርቅነሽ ወልደሥላሴ አይተውት ኖሮ "ልጄ እንግዶችህ መጡልህ" ብለው ልጃቸውን ሃምሣ አለቃ ታደሰ በላይነህን ቀሰቀሱ። እሱም ባልደረቦቹን ቀስቅሶ አንጥፎ በመጠበቅ፣ ባልተጠበቀበት ቦታ አደጋ ጥሎ ጠላቱን አዋረደው። ብዙ ምርኮም አገኘ።

የጠላት ጦር ከሰላድንጋይ መጣ። አርበኞች መጋቢት 2 ቀን 1931 ዓ.ም ሬት ሚዳ ላይ ግንባር ለግንባር ገጥመው ታላቅ ጉዳት አደረሱበት። ጠላት ጦርነቱን ያካሄደው በምድር በመድፍ፣ በሰማይ በአይሮፕላን እየታገዘ ነበር። አርበኞችም አርስበርሳቸው ተጋገዙ። በእጃና የወረደውን የጠላት ጦር፣ በልጅ መኮንን ጉሽሜ አስተባባሪነት የሚንቀሳቀሰው አርበኛ ዲማ ላይ ገጥሞ በመሳሸም ኃይሉን ቀነሰው። በሌሎች ጉራዎች የተሰለፈውም የጠላት ጦር እንደዚሁ ውርደት ተቀብሎ ወደኋላው ተመለሰ። በዚህ ጦርነት ብቻ 83 ኢጣልያውያን ቆስለዋል። የሞተው ባንዳ ከቁጥር አልገባም።

መጋቢት 5 ቀን 1931 ዓ.ም ጠላት በራስ አበበ ሠራዊት ላይ አደጋ ጣለ፣ አርበኞችም መክተው ተዋጉ። ውጊያው ክጥዋቱ አራት ሰዓት እስከ ምሽቱ አሥራ ሁለት ሰዓት ቀጠለ። ቀን ሲመሽ አርበኞች በጀረት ሚት በኩል ወደ ናስ ወረዱ። ከዚያም መጋቢት 6 ቀን ወደ ቡልጋ ለመዞር ተነሱ።

ጠላት አርበኞችን ለማጥቃት ሌላ እንቅስቃሴ አድርጎ አሞራ ወይራ ከተባለው ቦታ ደረሰ። አርበኞቹ የቅዱስ ጊዮርጊስ በዓል እንዳይሰናከል ጠብቀው ሚያዝያ 24 ቀን 1931 ዓ.ም ገፍጥጫ ከተባለው ቦታ ላይ ገጠሙት፣ ከሁለቱም ወገን ሰው ሞተ። ጣልያንም ወደ አንቀላፊኝ ለመሄድ የነበረውን ሐሳብ ትቶ ወደ መጣበት ተመለሰ።[9]

በዚህ ወርና አመት፣ በቡልጋ የሚካሄደው ጦርነት ጠንክሮ ነበር። ጠላትም ከየአለበት ጦር እየሰበሰበ ወደዚያ ያስማቋረጥ ይልክ ነበር። ስለዚህ የመንዝ አርበኞች ይህንን ሁኔታ አጥንተው የማደናቀፊያ ስልት ቀየሱ። ከሰሜን የመጣውን ጦር ግንቦት 11 ቀን 1931 ዓ.ም ደብረ ብርሃን አጠገብ ልቺ በር እንደ ሠፈረ አደጋ ጥለው ጉዳት አደረሱበት። አርበኞችን በመበተን ወደ ቡልጋ የመሄድ ዓላማውን አሰናከሱበት።

በመንገዝ አካባቢ የነበረው አርበኛ የበጋውን ወራት በእንዲህ አሳለፈ። በክረምት ወራት ጠላት እምብዛም ስለማይንቀሳቀስ ከቀሰብ በስተቀር ሌላ ችግር አልነበረም። በነሐሴ የንጉሠ ነገሥቱ ደብዳቤ ከደረሰ በኋላ አርበኞች ከወሰዱት እርምጃ አንዱ ሕዝቡን ማሳመንና ማስተባበር እንደሆነ ተመልክተናል። በዚሁ መሠረት በልጅ ግዛቸው ኃይሌ የሚመራው ሠራዊት ከቀወት እስከ እናዥጋ፣ ከዚያም በደብረ ሲና አካባቢ አልፎና ሮቤን ተሻግሮ፣ የመኪና መንገዱን አቋርጦ እስከ ገደባ ድረስ ሄዶ አሣመነ። ሕዝቡም ያለ ችግር ተቀበለ። በሌላው ወገን የተሠማራው ቡድን ደግሞ ወደ ግድም ሄደ። ነገር ግን አቶ አልታየ የተባለ ባንዳ የአካባቢውን ሰው አሣብሮ ለመውጋት ስለከጀለ፣ አርበኞቹ በፍጥነት ደርሰው በጦር ኃይል እሱንና ጥቂት ተከታዮቹን ደመሰሱአቸው።

ክረምት እንደ መሆኑ መጠን የምግብ ችግር አጋጥሞ ነበር። ደግሞም ክረምት ሲጠባ የጠላት እንቅስቃሴ በአዲስ ኃይል ይጠበቅ ነበርና የመንዝና የተጉለት አርበኞች ምክር አደረጉ። በምክሩም ደጃዝማች አውሪሪስ ከነሠራዊታቸው በተወሰነላቸው አካባቢ እንዲሠፍሩ፣ ልጅ ተፈሪ ዳኜ ከባልደረቦቻቸው ጋር ተጉለትና ደንገዜ እንዲሆኑ፣ ልጅ ግዛቸው ኃይሌ ሰዎቻቸውን ይዘው ወደ ደጋው አገር ወደ አራድግ እንዲወጡ፣ ከጠላት ጥቃት የደረሰበት ቡቶሎ ድምፅ እንዲያሰማና ሁሉም እንዲረዳዱ ተወሰነ። በውሣኔው መሠረት ለመፈፀም አያት ሜዳ ላይ ተሰባስበው ወደየቦታቸው ሄዱ።

ነሐሴ 29 ቀን 1931 ዓ.ም ዲት ከተባለው ቦታ ከቁም ነገር ያልተቆጠረ አንድ መለስተኛ ግጭት ከጠላት ጋር ተደረገ። ውጊያውም እምብዛም ሳይቆይ፣ ደፍረው ተኩስ ከከፈቱት የጠላት ወታደሮች ሰባቱ ሲገደሉ የቀሩት ሸሽተው አመለጡ። ውጤቱ ግን ከባድ ሆነ። ከአርበኞች ወገን አንድ ሰው ሞተ፣ ሌላ አንድ ሰው ቆሰለ። የቆሰሉት አርበኛ ጀግናው ልጅ ግዛቸው ኃይሌ ሲሆኑ፣ የተመቱትም ከቆሰለው ከአሽከራቸው ሾልካ በወጣች ጥይት ነበር። እሱ ወዲያው ሲሞት፣ እሳቸው እስከ ጥቂት ቀን ድረስ ቆይተው ጳጉሜ 3 ቀን 1931 ዓ.ም አረፉ። ላሉ ምድር፣ ጠል እግዚአብሔር አብ በስማዕትነት ደረጀ ፍትሃተ ነፍስ ተደርጎላቸው ተቀበሩ። አስቀድሞ ለጦር ጓደኞቻቸው አያት ሜዳ በተባለው ቦታ የሰጡአቸው ምክር "...ለመሠረታችሁት ሥራዎች ደምዳሚዎች ሁሉ ..." የሚል ነበር። ጠላትን

ሠላሳ ሦስት ጊዜ ግንባር ለግንባር ገጥመው ያንቆራጠጡት ጀግናው ልጅ ግዛቸው ኃይሌ በእንደዚህ ያለ ሁኔታ የዜግነት ድርሻቸውን ተወጥተው አረፉ።[10]

በመንገዝና በተጉለት በ1931 ዓ.ም የተካሄደው ትግል በዚህ ዓይነት ተጠናቅቆ የ1932 ዓ.ምቱ ተተካ። የጠላት የጦር ሥልት ደግሞ ከመስፋፋት ይልቅ የያዙትን ወደ መጠበቅ ዞረ፣ ቀደም ብሎ ያደርግ እንደነበረው አዘውትሮ ከቦታ ወደ ቦታ መዘዋወሩ ተቀነሰ። ለባላገሩ አረፍት ሆነ። አርበኞችም በበኩላቸው ለመሰባሰብና እርስበርሳቸው ለመወያየት አመቻቸው። በሌላ በኩል ደግሞ ስንቅና ትጥቅ የመመንተፍ ዕድላቸው ተቀነሰ። ይህንን ችግር ለማቃለል ምሽጎችን መተምተም ነበረባቸው። ጠላት ደግሞ ጠቡ እንዲባባስ አልፈለገም። ስለዚህ ሊስላከላቸው ያልቻለውን ምሽጎች በአርቅ ስም እያደረገ ለቀቀ።

ቀድሞ በሽክሽክታ ይሰማ የነበረውን የእርቅ ወሬ፣ ጣልያን በሬዲዮና በጋዜጣ ያናፍሰው ጀመር። ደህናው ሰው ሁሉ ልቡ ተከፈለ። ቀኝዝማች ታደሰ በላይነህ፣ በእሳቸው አስተባባሪነት ስር የነበረውን ሠራዊት ለመምራት ሁነኛውን ነገር እሳቸው ራሳቸው ከራስ አበበ ጋር ተገናኝተው ቃል ለቃል መነጋገር አስፈለጋቸው። ስለዚህ በቀኛዝማች ታደሰ በራሳቸው የሚመራ ቡድን ወደ ቡልጋ ለመሄድ ከአስቶ በታህሣሥ ወር 1932 ዓ.ም ተነሳ። እምብራባርን አቋርጠው ጉር ሲደርሱ የጠላት ጦር ደም አይጠማሽ ከተባለው ቦታ ሠፍሮ አገኙ። እሳቸውን ለማጥቃት የተንቀሳቀሰ ጦር መሆኑን የኢጣልያንኛ ቋንቋ በሚያውቁት፣ አብረዋቸው በነበሩት አርበኛ፣ በግራዝማች አበበ አማካይነት ከንግግራቸው አረጋገጡ። ስለዚህ ድንገተኛ የጭለማ አደጋ በመጣል ሠፈሩን በጠበጡት። የጠላት ጦር እርስበርሱ ተዋጋ። ደም አይጠማሽ የጠላትን ደም በእጅጉ ጠጣች፣ እነሱ ግን እንኳን ሞቱ፣ ቁስለት ሳያገኛቸው መንገዳቸውን ቀጥለው በዝብ ዋሻ በኩል በማለፍ፣ አስቶ አምባ ገቡ።

አስቶ አምባ ሲደርሱ ደግሞ ሌላ የጠላት ጦር አጋጠማቸው። ደም አይጠማሽ ከደረሰው አደጋ ወገኑን ለመርዳት የተንቀሳቀሰ ሳይሆን አልቀረም። በዚህ ጊዜ ደግሞ አርበኞች ጠላት በአካባቢአቸው መኖሩን አላወቁም። ጠላት ግን እነሱ መቃረባቸውን አውቆ ተኩስ በመክፈት አደጋ ጥሎ አቶ ይመኔ ወልደ ዓድቅ የተባሉትን የቂሮ በረት አርበኛ ጣለ። እነሱም በጥይት ቅብቅብ በማራመጥ ዋጋውን ከፈሉት። ከዚያም ቡድኑ ጉዞውን ቀጥሎ፣ በድንበር አድርጉ የመኪና መንገዱን በማቋረጥ ላጀ ግንድ ወጣ። ከዚያም እንኮበርን ወደ ግራ ትቶ በቆራ መስክ በማለፍ፣ ጠለስ ከተባለው ቦታ፣ ፊታውራሪ በፍርዴ ሀብተማርያም ከተባሉት የቡልጋ አርበኛ ጋር ተገናኘ። ከእሳቸው ምክርና አረፍት ከአደረገ በኋላ ጉዞውን ቀጥሎ ጌልጌላ ላይ ከራስ አበበ ጋር ተገናኘ።

ራስ አበበ ቡድኑን በክብር ተቀብለው አነጋገሩት። ቀኛዝማች ታደሰ ከራስ አበበ ጋር በግል ለመነጋገር ጠይቀው ደጃዝማች ዘውዱ አባኮራን፣ ከንቲባ ከበረ ኃይለሥላሴና ቀኛዝማች የማነ አባኮራን ባሉበት የምሥጢር ንግግር ተካሄደ። ቀኛዝማች ታደሰም አመጣጣቸው ከመንዝና ከተጉለት አርበኞች ተልከው እንደሆነ፣ መንገዳቸውም እጅግ አስቸጋሪና ታላቅ መስዋዕት የተከፈለበት እንደሆነ ገለጹ። ዋናው ችግር ጣልያን ከራስ አበበ ታርቄአለሁ እያለ በሚነዛው ወሬ የሕዝቡ መንፈስ እንደተናወጠ አስረዱ። አገላለጻቸው እልህ የተቀላቀለበት ነበር። ንግግራቸውን "...እንደዚህ የመሰለው ሐሳብ እንኳንስ ለእኛ፣ ለተተኪውስ ትውልድ ቢሆን ምን ይጠቅማል? ይዘናትስ የምንንከራተተው ሞት የተፈረደባት ነፍስን አይደለም?" በሚል ጥያቄ ደመደሙ።

ራስ አበበም በጥሞና ከአዳመጡ በኋላ እርቁ ለዘለቄታ አለመሆኑን አስረዱአቸው። የቆሰሉት እስኪድኑ፣ የታመሙት እስቲያገግሙ፣ ጥይት ያለቀባቸው የጐደለባቸውን እስኪያምዋሉ፣ የጊዜ መፈለጊያ መሆኑን ገለፁላቸው። ለመንዝና ለተጉለት አርበኞች መልእክት እንደ ላኩባቸው ነግረዋቸው፣ አሳቸው ግን ሁኔታውን እስኪገነዘቡ እንዲቆዩ ጋበዙአቸው።

ከጣልያን መንግሥት መልእክተኞች ጋር ንግግር የሚደረግበት ቀጠሮ ደርሶ ነበርና፣ ራስ አበበ ከጌልጌላ ወደ ማህበረ በኩር ሲወጡ ቀኛዝማች ታደሰም አብረው ወጡ። የጄነራል ናዚና የጄነራል ፍራንክ ተወካይ ሻለቃ ለኮቲ፣ ጉዳይ ፈፃሚዎቹን ይዘ በመቅረብ ያለውን ሰሙ። የአርበኛውን ስሜት ገመገሙ። ከዚህ በኋላ ከራስ አበበ ተሰናብተው ወደ አገራቸው በመመለስ ያለምንም ችግር ከባልደረቦቻቸው ጋር ተቀላቀሉ።

የእርቁ ምሥጢር በታወቀ ጊዜ፣ የመንዝና የተጉለት አርበኛ ልቡ ደነደነ። ጠላትና ግብረ አበሮቹ ይዘሩት የነበረው ወሬ ፍሬቢስ መሆኑ ተረጋገጠ። በአርበኞቹ ዘንድ ሁኔታውን ሲሕዝብ ማስረዳት ስለሚቻልበት ዘዴ ምክር ተደረገ። ነገር ግን በዛ ረገድ ችግር አጋጠመ። በጠላት ስብከት ብዙ ሰው ተታልሎ ስለነበር ዝም ማለት የአርበኝነቱን ሥራ የሚጐዳ ሆነ። በይፋ ቢነገር ደግሞ ምሥጢሩ ለጠላት ደርሶ ሊያስገነግን ሆነ። በዚህ ላይ በክብረ በዓልና ሕዝብ በሚሰበሰብበት አደባባይ የአሱን ሐሳብ የሚቃወም ቃል እንዳይነገር ጣልያን ጥብቅ ቁጥጥር በሕዝብ ላይ ያካሂድ ነበር። ይህ ሁሉ ተመዛዝኖ በሁለቱም ወገን የነበረው አመለካከት ከባድ ስለነበር፣ በፊሊጥ እንዲነገር ተወሰነ።

በዚሁም መሰረት አዋጅ ተነገረ። አዋጁም አርበኞች ያቀረቡት ሐሳብ በጣልያን መንግሥት ተቀባይነት ካላገኘ እርቁ እንደማይፀና ራስ አበበም አጥብቀው እየተከራከሩ እንደሆነ፣ በጣልያን በኩሉ የተገደሉት የእነ ቀኛዝማች አድማሴና የእነ ባላምባራስ ተምትም ደም እንዲወጣ እንደተጠየቀ የሚገልጽ ነበር። ከዚህም በስተቀር ገና ቁርጡ ባልታወቀ ነገር ወሬ ሲያወራ

የተገኘ ቤቱ በእሳት እንዲቃጠልና ንብረቱ እንዲዘረፍ፣ ለጠላት ሲሰብክ የተገኘ በሞት እንዲቀጣ የሚወስን አዋጅ ወጣ። ምንም እንዳንድ ወሬኛ ውስጥ ውስጡን ቢያንሾካሹክ፣ ወሬው በይፋ መነገሩ ቀረ። የጣልያንም ፕሮፓጋንዳ ከሰረ።

የዚህ አዋጅ መነገር የሕዝቡን መንፈስ ስለለወጠበት፣ ጠላት ተበላጨ፤ አርበኞችን ከምድረ ገፅ ደምስሶ ለመገላገል አሰበ። ለዚህም አቶ ሣህሉ ወልደንብርኤል የተባለውን ባንዳ ምርኩዝ አድርጐ ተዘጋጀ። ግለሰቡንም ቀኛዝማች፣ ቀጥሎም ፊታውራሪ አለው። ከዚያም መጋቢት 5 ቀን 1932 ዓ.ም ድርገሚት አቦ በሚደረገው ክብረ በዓል ላይ አደጋ ለመጣል ተንቀሳቀሰ። ነገር ግን አቶ አጥናፌ ቀርቸ የተባሉ፣ ሰው በመላክ አርበኞች ወደ ክብረ በዓል እንዳይመጡ አደረጉ። ዕቅዱ ፈረሰ። በዕቅዱ መፍረስ የተናደደው ጠላት ወደ ምሽጉ ሲመለስ አርበኞቹ መሣቆ አዋጅ ከተባለው ቦታ ላይ አደጋ ጥሰው ክፉኛ አጐሳቆሉት።

የመንዝና የተጉለት አርበኝነት በእንዲህ እንዳለ፣ በቡልጋ ወገን እርቅ ፈረሰ፣ ወሬውም ወዲያው ተሰማ። አርበኞች ጠላት በተከታታይ ለሚወስደው እርምጃ ተዘጋጁ።[11]

የእርቅ ንግግር ይደረግ በነበረበት ወቅት፣ በጀነራል ናዚ ትዕዛዝ አንዳንድ ምሽጐች ለአርበኞች በተሰቀቁ ጊዜ፣ የላሎ ምድርን ምሽግ ልጅ ተፈሪ ዳኜ በየካቲት ወር 1932 ዓ.ም ተረክበው ነበር። እርቅ ከፈረሰም በኋላ አልለቀቁም ነበርና፣ ጣልያን አዘናግቶ ግንቦት 12 ቀን 1932 ዓ.ም ያዛቸው። እሳቸው በሰላም እንደተቀመጡ መያዛቸውን ምክንያት በማድረግ ስለተከራከሩ ቀውት እንዲቀመጡ ተወሰነ። የአያበርን ምሽግ እና መሣሪያ የተቀመጠበትን ቦታ ሲያጠኑ ከቆዩ በኋላ፣ በአንድ ጠመንጃና በጥቂት እጅ ቦምብ አደጋ ጥሰው አንድ ካፒቴንና አንድ መቶ አለቃ ከብዙ ሐማሴንና ባንዳ ጋር ገደሉ። አንድ ባለውሃ መትረየስና ብዙ ጠመንጃ ማረኩ። ከዚያም በዝማሞ፣ ባይሞድ አድርገው ጥሞናን ገብተው አርበኝነታቸውን ቀጠሉ።[12]

እርቅ በፈረሰ ጊዜ ባልተመቸ ሁኔታ ላይ ከነበሩት አርበኞች ቡድን አንደኛው፣ በፊታውራሪ ወንድሜነህ ይመራ የነበረው ነው። እሱም አደጋውን ለማሳለፍ ፈንጣጣ ዋሻ ገባ። ይህ ቡድን እስከ ደብረ ብርሃን ድረስ እየተጠጋ በማጥቃት ጠላትን ቆልፎ የያዘ ነበርና ጠላት ምሥጢሩን አውቆ ከበበው። ከበባው ጠንካራ ሆነ። አርበኞቹም አጥብቀው ተከራከሩ። የጠላት ጦር የተንቀሳቀሰው በሁሉም አካባቢ በመሆኑ፣ እነሱም መልእክት ለማስተላለፍ ስለአልተመቻላቸው፣ ዕርዳታ ሊደርስላቸው አልቻለም። ስለዚህም በሙሉ አቅማቸው እየተከላከሉ ከበባውን ሰብረው በመውጣት ከመጀመሪያው ዙር ወጡ፤ ከሁለተኛው ዙር ክብ ደረሱ።

አርበኞቹ ስምንት ብቻ ሲሆኑ የጠላት ጦር ግን እጅግ ብዙ ነበርና አጠገባቸው የነበረውን ወንዝ ያለጥይት ለመሻገር ከሁለት ተከፈሉ። አምስቱ

መትረየሱን ይዘው ወንዙን በመሻገር ከኋላ ሰቀሩት ጠለላ እንዲሰጡ፤ እነሱ እስኪሻገሩ ደግሞ ሦስቱ ከለላ እንዲሰጡ ተስማሙ። ሆኖም መትረየሱን የያዘው ቡድን ወንዙን ገና ሲሻገር በድንገት ከጠላት እጅ ስለወደቀ፤ ዕቅዱ ሳይሠራ ቀረ። ሁለተኛው ቡድን፤ በመጀመሪያው ቡድን ላይ የደረሰበትን አደጋ አላወቀም ነበርና ወደ ወንዙ ተዘቀዘቀ። እሱም የመጀመሪያውን ቡድን ከያዘው የጠላት ጦር ላይ ወደቀ። ነገር ግን እንደፊተኛው ቡድን በቶሎ አልተማረከም፤ አጥብቆ ተከላከለ። የቡድኑ መሪ ፊታውራሪ ወንድምነህ ቢቀስሉም ከአንድ ጉጥ ሥር ሆነው እስከ ስምንት ሰዓት ድረስ ተዋጉ። ጥይታቸውን በጠላት ላይ አፍስሰው ሲጨርሱ በጠላት እጅ ወደቁ። በበቅሎ ተቀምጠው የምርኮ ጉዞአቸውን ቀጠሉ። የጉዞአቸው መድረሻ ቀደም ብለው በተማረኩ ጊዜ ጓደኞቼን አባብዬ እመጣልሀለሁ ብለው አታልለውት ከነበረው ጣልያን ዘንድ ነበር። ይህ ደግሞ የሚቀበሉት ነገር አልነበረም። ስለዚህ ከአንድ የጠላት ወታደር ላይ ጠመንጃ ነጥቀው ለመታኮስ ሞከሩ፤ ጠመንጃው ጥይት አልነበረበትምና ሳይሆን ቀረ። በዚህ ጊዜ አያያዛቸውን ያየ የጠላት ወታደር የእጅ ቦምብ ወረወረባቸው። እሳቸውም የተጣለባቸውን ቦምብ ቀልበው በመወርወር ብዙ የጠላት ወታደሮች ገደሉ። የጠላት ወታደሮች በብዛት ስለተከሰባቸው በአንድ ጥይት ከግንባራቸው ላይ ተመትተው ሞቱ። ጠላትን ሃያ ሦስት ጊዜ ግንባር ሰግንባር ገጥመው የተዋጉትና መከራ ሥቃይ ያሳዩት ፊታውራሪ ወንድምነህ ገብረኪዳን፤ በሰላሳ ሰባት ዓመት ዕድሜአቸው፤ በእንዲህ ዓይነት የዜግነት ድርሻቸውን ተወጥተው፤ መጋቢት 8 ቀን 1932 ዓ.ም አረፉ።[13]

ክረምቱ ከመግባቱ አስቀድሞ ጣልያን አርበኞችን ከመንገዝና ከተጉለት ለመገላገል ተንቀሳቀሰ። ዋናው አማካሪው አቶ ሣህሉ ወልደገብርኤል ሆነ። ከተጉለት በጉራ ዋሻ፤ ከሰላድጋይ በአሞራ ወይራ፤ ከወይራ በቆብ አስጥል፤ ከታቦር በመዘገ፤ ከደብረ ሲና በመሰቢት በኩል ሌሊቱን ሲንኳተት አድሮ፤ ሰኔ 22 ቀን 1932 ዓ.ም ጥዋት፤ ወፍ ሲንጫጫ ተኩስ በመክፈት አደጋ ጣለ። አርበኞች ሁኔታውን እንደሰሙ እየተመካከሩ በሚያውቁት ሥርጥ እየተዘዋወሩ በጠመንጃና በመትረየስ ፊጁት። ከበባውን ሰብረው በመውጣት በወርቅ ዋሻ በኩል አድርገው በድንጋይ መዝጊያ አመለጡ። በግራና በቀኝ ያሉትን ሽንተረሮች መከታ እየሰጡ፤ የሚከታተላቸውን የጠላት ወታደር ረፈረፉት። ከበባውን ሰብረው ለመውጣት የተጠቀሙበት ሥልት ከባቢውን ራሱን ግራ አጋባው። ከእነሱ ወገን የሞተባቸውን ከጥሻ ውስጥ ደብቀው፤ አንድ ነጠላ ለአራት ወጥረው በመያዝ ሬሣ የተሸከሙ አስመስለው፤ ጉዞአቸውን ቀጠሉ።

ከሮቤ ወንዝ ለመድረስ ጥቂት ሲቀራቸው ጣልያን ሌላ አዲስ ጦር በካሚዎኖች አቀረበ። ከመሉ ቀን ውጊያ በኋላ ከአዲስ ጦር ጋር መግጠም አደገኛ ሆነ። አርበኞች በፍጥነት ተመካክረው በመኪና ከመጣና ትኩስ ጉልበት

ካለው ጦር ጋር መግጠማቸውን ጥለው፤ ወደ ዋሉበት ወደ አንጬኔ ተመለሱ። ይህም የእሸነፈ መስሎት በነበረው የጠላት ጦር ላይ ድንጋጤ ፈጠረ። እነሱም እየተከላከሉ ወደ ጃሎ አቀኑ። ከዚያ ሲደርሱ ደግሞ ጠላት በር፤ በሩን ይዞ ጠበቃቸው። ይህኛው ከበባ ደግሞ ከፊተኛውም ፀናባቸው። በዚህ ጊዜ ቀኛዝማች ታደሰ በላይነህ የወንድ ሥራ ሠሩ። ወደ ጣልያን ዘንድ ሄዶ "...እኔ ታደሰ በላይነህ ነኝ። በር ልቀቅልኝ..." ብሎ የሚነግር መልእክተኛ ላኩ። ጣልያንም ምንም ሳይወላዳ የያዘውን ቦታ ለቆ ደብረ ሲና ከምሽጉ ገባ። በዚህ ዓይነት ቁርጠኛ እርምጃ፤ ያ የተከበበ አርበኛ ከእልቂት ዳነ።

ሰኔ 22 እና 23 ቀን 1932 ዓ.ም ቀንና ሌሊት በተካሄደው ጦርነት ብዙ የጠላት ወታደር ረገፈ። ከአርበኞችም ወገን ብዙዎች ሞቱ። በተሰጠ የግራዝማች አጉናፍር ኪዳኔን አስከሬን ከተደበቀበት ዋሻ ሰኔ 24 ቀን 1932 ዓ.ም ጠላት አግኝቶ መሰጥ ከተባለው ቦታ እስከነበረው ምሽግ ድረስ በመውሰድ ሦስት ቀን ሙሉ ተጫወተበት።[14]

በ1932 ዓ.ም የመንዝና የተጉለት ሁኔታ እንደዚህ ከርሞ ክረምቱ ገባ። ክረምቱ ለአርበኞች የሕይወት፤ ለኢጣልያኖች የውድቀት፤ ለባንዶች የውርደት ነፋስ የነፈሰበት ነበር። በመሆኑም ሁሉም በየፊናው የሚዘጋጅበት፤ የሚመካከርበት ሆነ። የ1933 ዓ.ም ፍልሚያ ቀጠለ።

አርበኞች ጣልያን እነሱ እስከሉሉበት ድረስ አስኪመጣ መጠበቃቸውን ትተው፤ እሱ እስከሰሰበት ድረስ እየሄዱ ማጥቃት ያዙ። በልጅ ተፈሪ ዳኜ የሚመራው ሠራዊት በጥቅምት ወር 1933 ዓ.ም ቆሎ ማርገፊያ በነበረው ጠላት ላይ አደጋ ጥሎ ጉዳት አደረሰበት። ይኸው ቡድን ተጉለት ተሸግሮ ህዳር 23 ቀን 1933 ዓ.ም ዋሲያ ተራራ ላይ መሽጉ የተቀመጠው ጣልያን ላይ ሌሊት አደጋ በመጣል፤ በምሽጉ ውስጥ የነበሩትን ነጮችና ታማኞቻቸውን ባንዶች ገድሎ ብዙ መሣሪያና ስንቅ ነጠቀ። ልጅ ተፈሪ ዳኜ በተያዙ ጊዜ አብረው ተይዘው ከነበሩት መካከል እንደገና ወደ አርበኝነት ለመመለስ ፈቃደኛ ባለመሆን ከጣልያን ተጠግተው ይኖሩ የነበሩት፤ በጣልያን ተይዘው ደብረ ብርሃን ተወስደው ታሰሩ።

ይህ ቡድን እየተጠናከረ ከመሄዱ የተነሣ፤ በጠላት ላይ ጭንቀት በመፍጠር የማር ማረፊያን ምሽግ ቀን በቀን በኃይል ገብቶ መዘበረው። በዚህ ሁኔታ የተደናገጠው ጠላት፤ አካባቢውን ለመቆጣጠር ይረዳው ስለ መሰለው፤ ከአንድ ዓመት በፊት ለቅቆ የነበረውን፤ ሽሮ የተባለውን ምሽጉን ታህሣሥ 26 ቀን 1933 ዓ.ም ሌሊት ተሾልኮ በመግባት መልሶ ያዘው። የሽሮ ምሽግ እንደገና በጠላት መያዝ የማይዋጥላቸው ስለሆነ፤ በልጅ ተፈሪ ዳኜ የሚመሩት አርበኞች ከየአሉበት ተጠራርተው በማስቴ ታህሣሥ 27 ገጠሙት። የጠላት ወታደሮች ብዙ ነበሩ፤ አያሌ መትረየስም ጭነው ነበር። አርበኞች ግን ጥቂትና የያዙት ከነጠላ መሣሪያዎች ጋር አንድ ውሃ መትረየስ ብቻ ነበር። እሱውም ፔተግሪስ ዕሴት ገዝሩ ባለመገኙቱ ውግር

ከተባለ ቦታ በተገኘ ሌላ ዝናር የተገጠመ ነበር። በእሱው በርትተው በመዋጋት ሲያይሉበት፣ ጠላት አካባቢውን አሳት ለኩሶ በሞሱ ከለላ ለማምለጥ ሞከረ። አርበኞች እየተከታተሉ ሲያጠቁ ሞሱ ጋረዳቸው። ከሞሱ ወጥተው ጠላትን ለማጥቃት ሲገሰግሱ፣ ያደፈጠ አንድ የጠላት ወታደር ተኩሶ ስለመታቸው፣ የልጅ ተፈሪ ዳኜ ሕይወት በድንገት አለፈች። ሌሎች ጦርነቱን በመቀጠል ጠላትን ከአካባቢው አባረሩት።[15]

የጦርነቱ ሚዛን በኢጣልያ ላይ እንደ አደላ፣ እንዲሁም ንጉሠ ነገሥቱ እንደመጡ ታውቆ እያለ፣ በወዳጅ ዘመድ ምክር አልመለስ ብሎው እስከ መጨረሻው ለጠላት በታማኝነት የቆመ ባንዶች አልታጡም፣ በዛ አካባቢ ዋነኛው አቶ ግሀሉ ድፋዱ ይባል ነበር። በወገኖቹ ላይ ግፍ የሚሠራ ጨካኝ ሰው ነበርና፣ ጠላት መሰዋን ሾመው። እሱም ለጠላት መከታ ሆኖ ስለቆመ፣ ጠላትን ለማጥቃት፣ አስቀድሞ እሱን ማስወገድ ግድ ሆነ። አርበኞች ጥር 18 ቀን 1933 ዓ.ም በወሰዱት ቆራጥ እርምጃ ዋጋውን አገኙ።[16] በዚህ ዓይነት አካባቢው ለአርበኝነት ሥራ ክፍት ተደረገ፣ እነሱም ከመደበኛ ጠላታቸው ጋር ለመተናነቅ ቻሉ።

የንጉሠ ነገሥቱ ጉጃም መግባት እንደታወቀ አርበኞች ይህንኑ መጋቢት 17 ቀን 1933 ዓ.ም ለሕዝብ በይፋ ገለፁ። ወዲያው የሮቤን ወንዝ ድልድይ ይዘው የጠላትን መኪናዎች በመስበርና ወታደሮቹን በመጨረስ ከባድ ጉዳት አደረሱበት። የጣልያን ጦር ከማሕል አገር ወደ ሰሜን የሸሸው በዚህ በር ነበር። አርበኞችም በየቦታው እየተዘዋወሩ አደጋ ጣሉበት፣ ነገር ግን ሊበግሩት አልቻሉም። አንዱ ሲያልቅ ሌላው ይተካል። አዝማሪና ውዛ መሳት እንደ ተባለው ተረት ሆነባቸው። የእንግሊዝ ጦር አዲስ አበባን መጋቢት 27 ቀን 1933 ዓ.ም ሲይዝ ደግሞ ወታደር በመኪና እያሣፈረ በማባረር ስለወጋው፣ በዚያ መሥመር የሚጉርፈው የጣልያን ጦር ከመጠን በላይ ሆነ። አርበኛው ይህንን ጦር የማንድ አቅም አልነበረውም። ማንድ አስፈላጊ ሆኖም አላገኘውም፣ ለቀቀው።

በዚህ ጊዜ ጣልያን፣ እሱ ራሱ ከጣርማ በር በጨለንቆ በኩል ሠርቶት የነበረውን የመኪና መንገድ በደናሚት አፈንድቶ፣ እንደ አልነበረ አደረገው። የእሱ ሐሳብ የእንግሊዝን የማባረር ፍጥነት ለመቀንስ ነበር። ግን በቀኛዝማች ታደሰ በላይነህ የሚመራው አርበኛ ይህንን በተመለከተ ጊዜ፣ በጣርማ በር ተራራ ውስጥ ተፈልፍሎ የተሠራውን የመሬት ውስጥ የመኪና መንገድ ለማዳን ወሰነ። ጣልያን ዲናሚት ቀብሮ በማፈንዳት እንዳይዘጋው ተከላከለ። ለዚሁ ሥራ የተሠማሩትን ሠላሣ ስድስት ጣልያኖች በድንገት ደርሶ በመፍጀት ዋሻውን ከመፍረስ አዳነው።[17]

ማጣቀሻ ፅሑፎች

1. ታደሰ ዘወልዴ፣ *ቀሪን ገረመው*፣ ገጽ 209-219
2. ታደሰ ዘወልዴ፣ *የአባላሸኝ ዘመን*፣ ገጽ 31።
3. ታደሰ ዘወልዴ፣ *ቀሪን ገረመው*፣ ገጽ 210-241።
4. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 210-240፣ 87-94 እና 293።
5. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 241-252።
6. ፈለቀ ዳኜ፣ *5ቱን የመከራ ዓመትና ፍፃሜው*፣ አሞር ማስታወሻ፣ ገጽ 15-18።
7. ታደሰ ዘወልዴ፣ *ቀሪን ገረመው*፣ ገጽ 151-155።
8. ፈለቀ ዳኜ፣ ገጽ 21።
9. ታደሰ ዘወልዴ፣ *ቀሪን ገረመው*፣ ገጽ 458-463 እና ገጽ 155-158።
10. ዝኒከማሁ፣ ገጽ 254-264።
11. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 455-480።
12. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 266-267።
13. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 385-388።
14. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 486-488።
15. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 264-270።
16. ዝኒ ከማሁ።
17. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 491-497።

ምዕራፍ ሠላሣ አንድ
የጐጃም ጥዝጥዝ

ከጣልያን ወራሪዎች ጋር ትንቅንቅ ከተደረገባቸው አካባቢዎች አንዱ ጐጃም ነው። ይህ ክፍለ ሀገር ትንቅንቅ ያካሄደው ከወራሪው ጦር ጋር ብቻ አልነበረም። በውስጡም ከፍተኛ የአንድነት ማጣት ችግር አጋጥሞት ነበር። ከአጋጠሙት ችግሮች ዋና ዋናዎቹን መመልከት አጠቃላይ ግንዛቤ ይሰጣል።

አንዱ የጐጃም ሕዝብ ችግር የልኡል ራስ ኃይሉ አቅዋም ነው። እኝህ ልዑል የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ልጅ በመሆናቸው በሕዝብ ላይ የነበራቸው ሚዛን ከባድ ነው። በሌላ ወገን ልጃቸው ወይዘሮ ሰብለወንጌል ልጅ ኢያሱን አግብተው እመቤት ሆይ ዓለም ፀሐይን ስለወለዱ፣ በአማቻቸው ከአልጋ መውረድ ቅር ተሰኝተዋል። በሦስተኛ በኩል ደግሞ ልጅ ኢያሱን ከሰላሌ እንዲያመልጡ አድርገዋል ተብለው ግዛት ተካሂዶባቸዋል፤ ሀብታቸውንም ተወርሰዋል። በአማቻቸው ከአልጋ መውረድ ተቆርቁረው አሰመዋጋታቸው ከቁም ነገር አልተቆጠረላቸውም። በአራተኛው ወገን ደግሞ ጣልያኖች ክፍተኛ የሽንገላና የልምምጥ ሥራ አካሂደውባቸዋል። በጐጃም ላይ ሲያነግሡአቸው ቃል ገብተውላቸዋል። በእነዚህ ምክንያቶች ተሸንፈው ልባቸውን ወደ ወራሪው ወደ ጣልያን ሊያዘነብሉ ችለዋል።

የልኡሉ ከጣልያኖች ጋር የውስጥ ስምምነት ማድረጋቸው ሰቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ምሥጢር አልነበረም። ንጉሠ ነገሥቱ ወደ አውሮፓ ሲሄዱ፣ እስከ ድሬዳዋ ድረስ ይዘዋቸው ከሄዱት መሣፍንቶች አንዱ እሳቸው ነበሩ። ድሬዳዋ አድርሰው ያውርዱአቸው እንጂ፣ ንጉሠ ነገሥቱ ሌላ ክፉ ነገር አላደረጉባቸውም። እሳቸውም ባለፈው ጊዜ የሠሩት ሥራ ሁሉ በደል መሆኑን አምነው፣ ወደፊት በሚቻላቸው ሁሉ እየሠሩ የኢትዮጵያን ነፃነት ለመጠበቅ የመሐላ ቃል መስጠታቸው አልቀረም።[1] ነገር ግን ከቀድሞ ማብራቸው አልተመለሱም።

ሁለተኛም በደጃዝማች ገሠሠ በለው አሳዳሚነትና መሪነት ከጐጃም ጦር የሚበልጠው ጐንደር፣ ዳባት ከተባለው አገር ከጦርነቱ አስቀድሞ ተመልሶ አገሩ ገባ።[2] ገብቶም የጣልያን ጉዳይ ፈፃሚ ሆነ። የንጉሠ ነገሥቱ የማስፈራሪያ አዋጅ፣ የጳጳሱ የአቡነ ቄርሎስ ግዝት ውጤት ሳይሰጥ ቀረ።

እነዚህ ሁለት ታሳላቅ ሁኔታዎች የሕዝቡን አንድነት አላሉ። ከዚህ በተጨማሪ ኢጣልያ አቆብቁባ ከምትመለከታቸው ግዛቶች አንዱ ጐጃም ነበር። የሀገር ነፃነትን በተመለከተ የሕዝቡ አመለካከት እንደ መሪዎቹ ከጥቅም ጋር የተሣሠረ አልነበረም። ይህም በጠላት ዘንድ ጭምር የታወቀ ነበር።

የጐጃም ሕዝብ በዚህ ዓይነት ዝብርቅርቅ ውስጥ እንደለለ፣ የራስ እምሩ ጦር ከሽሬ፣ በጐንደር በኩል ተመልሶ ደረሰ። የጐጃም ሕዝብ እየረዳ፣ ስንቅና ከብት እየሰጠ ሸኘው። ያለ አንዳች ችግር ዓባይን አሻግሮ ወደ ወለጋ

ሸኘው፣ የቻለም አብሮ ሄደ። ይህ አደራረግ ለጣልያኖች አዲስ ምልክት ሰጣቸው። የጐጃም ሕዝብ ልቡ ከሀገሩ ነፃነት ጋር መሆኑን ተገነዘቡ፣ ስለዚህም ራስ ኃይሉን በአክብሮት ያዙ። ከፊትና ከኋላ በሞተር ሳይክል እያጀቡ፣ በአዲስ አበባ ከተማ መንገዶች ላይ አንፈላሰሰው።

ጣልያን ከጐንደር ወደ ጐጃም በመጓዝ፣ በጎርጎራ በኩል አድርጐ ዞሮ በሚያዝያ ወር ብቸና፣ በጦር ኃይል እየጣሰና መንገድ እየጠረገ አንደሪን፣ ዳሞትን ያዘ። ከዚያም ግንቦት 21 ቀን 1928 ዓ.ም ደብረ ማርቆስ ገባ። ከዚያም በየደረሰበት ውጊያ ገጠመው። የጐጃም ሕዝብ ከጠላትና ከግበረ አበሮቹ በየቀኑ የሚንቆረቆርበትን የክህደት ምክር ከምንም ሳይቆጥር ተጋድሎውን ቀጠለ። በከሐዲ መሪዎቹ ምትክ ሌሎች፣ እንደነ በላይ ዘለቀ ያሉ ሀገር ወዳድ ጀግኖችን መረጠ። አዳዲሶቹ መሪዎቹም በመንፈስ እየጠነከሩ ሄዱ። ሀቀኝነታቸውን፣ ለሕዝብ ታማኝ መሆናቸውን፣ ሀገር ወዳድ መሆናቸውን በግብር እያረጋገጡለት ሄዱ። አርበኞችም እስከ ሞት ድረስ ተከተሉአቸው። በአንፃሩ ግን ከሐዲዎቹ በሕዝብ ዘንድ እየቀለሉ፣ በኢጣልያኖችም ዘንድ እየተዋረዱ ሄዱ። ዝርዝሩን ወደፊት እናገኘዋለን።

በጐጃም ምድር የመጀመሪያው የጦር እንቅስቃሴ በግንቦት ወር 1928 ዓ.ም፣ ብቸና ላይ ታየ። በላይ ዘለቀ የተባለ ውጣት፣ በአንድ አደባባይ ላይ፡- "የሀገሬ ሰው ስማኝ! ጣልያን የሚሉት ነጭ ሀገራችንን ሊወር፣ ሚስትህን ልጅህን ሊደፍር፣ ሀብትህን ሊወርስ መጥቶአል። ብቸና ገብቶ መሣሪያ አስረክቡ እያለ ነው" በማለት ከባድ ጠላት መምጣቱን አስረዳ። ከዚያም አያይዞ የራሱን ውሳኔ ሰጠ። መሣሪያውን ለጠላት የሚያስረክበውን፣ ቤቱን እንደሚያቃጥልበት አስታወቀ። በላይ ዘለቀ ይህንን ያህል ታላቅ ውሣኔ ለሕዝብ ያስታወቀው፣ ከአራት መሰል ጓደኞቹ ጋር ሆኖ ነበር። የጐጃም ጀግና የሐሳቡን ትልቅነት፣ የልቡን ቆራጥነት እንጂ፣ የእሱን ልጅነት- አላየም። ብዙዎች ተከተሉት። እንደ አለውም አደረገ።

በዚህም ወቅት ለሀገራችን እንሙት በሚለው እና ለጣልያን ገብተን በሰላም እንኑር በሚለው መካከል ክርክር ተነስቶ ነበር። የክረምቱ መግባት የጠላትን እርምጃ ስለገታው፣ ሕዝብ በጉዳዩ ለማሰብ በቂ ጊዜ አገኘ። ነገር ግን ሕዝቡ ወደ አንድ ሐሳብ መጠቃለል አልቻለም፣ በየሐሳቡ ቆመ። አመንቺም ቀስ እያለ ሐሳቡን በማስተካከል፣ ከሁለት አንዱን ያዘ።

በቁጥር አነስተኛ የሆነው የአርበኛ ቡድን ጠላቱን በድፍረት መቋቋም ጀመረ። ግንቦት 12 ቀን 1928 ዓ.ም ከደብረ ማርቆስ ወደ ብቸና ይጓዝ በነበረው የጠላት ወታደር ላይ አደጋ ጥሎ አራት ጣልያናውያንና ሁለት ባንዶች ገደለ። አንድ ሌላ ኢጣልያዊ አቆሰለ። ከአርበኞቹም አንድ ሰው ሞተ፣ ሌላ አንድ ሰው ቆሰለ። ብዙ ጠመንጃና ጥይት፣ የእጅ በምብ በአርበኞች ተማረከ። ይህ ሁኔታ መሣሪያ መረከብ ያለበት ከጣልያኖች ወደ

ኢትዮጵያውያን እንጂ፣ ከኢትዮጵያውያን ወደ ጣልያን ላለመሆኑ ማስረጃ ሆነ።

ውሎም ሳያድር በረንቲንና ስምጨንን በሚያዋስነው ቀይ ወንዝ ላይ አርበኞች ሌላ አደጋ ጥለው አንድ ጣልያናዊ መቶ አለቃ ገደሉ። ሌሎች ሁለት መቶ አለቆች አቆሰሉ።[3] ጥቂት ጣልያኖችን እየተከተለ የሚገበሰበሰው ባንዳ ብዙ ነው። በተለይም ገበሬው እየተገደደ ስለሚዘምት እሱን መግደል አስፈላጊ ሆኖ አልተገኘም። ስለዚህ አርበኞቹ ጠዝጥዝ በሚሉት ዘዴአቸው ከሩቅ በመሸመቅ እያነጣጠሩ ነጩን ለይቶ መምታትን ያዙ። ይህም ጥሩ ውጤት ሰጣቸው። ጣልያኖችም በበኩላቸው አዝሚሚያው ስለአሰጋቸው የሽንገላ ሥራቸውን አጠናከሩ።

የ19 ዓመት ዕድሜ የነበረው በላይ ዘለቀ ከስምንት ያልበለጡ የሥጋ ዘመዶቹን ይዞ የሀገር መከላከል ሥራውን ቀጠለ። ቡቦችና አውራጃ በከና በተባለ ቦታ የጦር ማሠልጠኛ አቋቋመ። ሥልጠናው ልዩ ልዩ መሣሪያዎችና መፍታትና ጠርጉ መልሶ መግጠም፣ አነጣጥሮ በመተኮስ ረገድ ዓይንን ማጥራት፣ ራስን ከጉዳት መጠበቅ፣ ጠላትን ማጥቃትና ይህንን የመሳሰሉትን ዘዴዎቹ ያጠቃለለ እንደነበር መገመት ይቻላል። ሠራዊቱ እየዳበረና ማሠልጠኛው እየጠነከረ ሲመጣ፣ የበላይ ዘለቀ አመራርም እየሠመረ ሄደ። ማሠልጠኛው በስምንት መትረየስና በአርባ ሁለት ወታደሮች በመዓልትና በሌሊት ይጠበቅ ስለነበር አልተደፈረም።

በላይ ዘለቀ መኖሪያውን በዋሻ ውስጥ አደረገ። ዋሻውንም አንድ መቶ ሰባ ምልምሎች እየተፈራረቁ በመዓልትና በሌሊት ነቅተው ይጠብቁ ጀመር። ይህ ጀግና ወጣት ለጦርነት የሚቸኩል አልነበረም። ዝርዝር ጥናት አድርጉ የተሻለውን የማጥቂያ ዘዴ ይመርጣል፣ ሠራዊቱንም በመልካም ምክር ያነሳሳል፣ እነሱም በሙሉ ልብ ይከተሉታል።

የበከናን ጦር ሠፈር ሁኔታ ከአጠና በኋላ ጣልያን ጦር ሠርቶ መጣ። ሐሳቡ በድንገት አደጋ ጥሎ የአርበኞቹን ጅምር በእንጭጩ ለመቅጨት ነበር። ሁኔታውን የተረዳ አርበኛ ሰበላይ ዘለቀ ስለነገረው ፈጣን ምክር ተደረገ። አንዱ ሐሳብ ማሠልጠኛውን ለቅቆ፣ ሌላ የተሻለ ቦታ ይዞ መከላከል እንደሚሻል የሚያስገነዘብ ነበር። ነገር ግን በላይ ዘለቀ በዚህ ሐሳብ አልተስማማም፣ ግንባር ለግንባር ገጥሞ መዋጋትን መረጠ። ወደኋላ ማፈግፈግ ያባቶቹን ታሪክ ማሰደብና ለእሱም ለራሱ ውርደት መስሎ ታየው። ጦሩን በፍጥነት ሰብስቦ "ዛሬ እኛ የኢትዮጵያ አርበኞች በጣልያን ወራሪ ጦር አንገት ላይ የምንቆምበት የተመረጠ ቀን ስለሆነ "...ፀሐይና ጨረቃ እንኳን እኛ ጠላቶቻችንን ትቢያ እስክናደርግ ድረስ በሶማ በረሃ ላይ እንዲቆሙ አዝዣለሁ" ብሎ ከጦርነቱ ገባ። ሠራዊቱም መሪውን በመከተል የመጣበትን ጠላት እንደ ጥሩ ጠጅ አጣጥሞ ጠጣው። አራት መትረየስ፣ ልዩ ልዩ ጠመንጃና ጥይት ማረከ። አርበኛው ልቡ ደነደነ።

ጣልያኖች በሠፈሩባቸው አካባቢዎች ነዋሪ የሆኑ ሁሉ የጣልያንን ምሥጢር እና ሐሳብ እያጠኑ ለአርበኞች ያቀብሉ ጀመር። ጣልያን በከን ከተባለው የጦር ሠፈር የደረሰበትን ወርደት ሰመሸፈን ሌላ ጦር አዘጋጀ። ሐሳቡ በብቸና አውራጃ፣ ልዩ ስሙ አቢራ መልከ በተባለው የአርበኞች ሠፈር ላይ አደጋ ጥሎ ሰመደምሰስ ነበር። ለዚህም ብዙ ባንዶች ሰብስቦ አሰልፎ ነበር። የጠላት አመጣጥ እንደ ታወቀ በላይ ዘለቀ ሠራዊቱን አዘጋጀ። ከሌሊቱ አሥር ሰዓት ላይ ተኩስ ተከፈተ። ከፍተኛ ውጊያ ከተካሄደ በኋላ፣ ሠማ ነገም የተባለው ቀንደኛ ባንዳ ተማረከ። ብዙ የጣልያን ወታደሮች ሞቱ፣ ቆሰሉ። አያሌ መሣሪያ ተማረከ። ሰማ ነገም እናት አገሩን ከድቶ ከጠላት ጉን በመቆም የብዙ ኢትዮጵያውያን ወገኖችን ደም በማፍሰሱ፣ ተፈርዶበት በስቅላት ተቀጣ። በላይ ዘለቀም የተገኘው ድል ለትውልድ የሚሸጋገርና የታሪክ ገጽ ሲያስታውሰው የሚኖር፣ ሕያው ሙያ መሆኑን ገልፆ "...ወራሪ ጠላታችንን ከመላው የኢትዮጵያ ግዛት ላይ ጠራርገን እስክናወድም ድረስ... ሠፈ ትግል ከፊታችን ይጠብቀናል። ...እንደዚህ በፍቅር ተሳስረን መሞት ለኛ ሠርጋችን እንጂ ሞት አይባልም። ህያውነት ነው..." በማለት ጓደኞቹን ለበለጠ ትግል አነሳሳ።

ጣልያን የአርበኞችን እንቅስቃሴ ለመግታት አለመቻሉ እየታወቀው ስለሄደ፣ ገዥ በሆኑ ቦታዎች ላይ ምሽግ እየሠራ አካባቢዎችን መቆጣጠር ጀመረ። አርበኛው ይህንን ሲያይ ጠላት እሱ እስክ አሰበት ድረስ መጥቶ እስኪወጋው መጠበቁን ትቶ ራሱ ጠላት እስክ አሰበት ድረስ እየሄደ ማጥቃትን ያመረጠ።

ራስ ኃይሉን ማባባሉ ውጤት እንደ አሳስገኘለት አየ። ራስ ኃይሉም ጣልያን በወገን ላይ የሚያካሄደው ጭፍጨፋ እየጉመዘዘው ሳይሄድ አልቀረም። አለመግባባትም ተፈጠረ፣ ራስም ፊቱን ማክሰተር ጀመረ። ይህ የሰለቸው ጣልያናዊ አለቃው "ፊትህ የዝንጀሮ ይመስላል" ብሎ ቢያንጓጥጠው፣ ራስ ኃይሉ "የአንተ ደግሞ ቂጥዋን ይመስላል" ብሎ እንደመለሰለት ጉልቶ ይነገራል። ለነገሩ ታላቅ የድፍረት ንግግር ነበር። ስለዚህም ክብሩን እየቀነሰበት፣ በየጦሩ ሜዳ ያዘመተው ገባ። ግን ጦርነቱን በማስታገስ ወይም እሱ ራሱ ሞቶለት ፋታ ለማግኘት የፈለገው አለቃው አንዱን ማግኘት ሳይችል ሰለ ቀረ፣ ራስ ኃይሉን በእሥረኝነት ወደ ሮም ላከው።

ጣልያን በዚህ ክሳይ በተጠቀሰው ዓላማው መሰረት ደጀን ላይ መሸገ። በበላይ ዘለቀ የሚመራው አርበኛ ከበከና ተወርውሮ በመድረስ ከጥቅምት 1 እስከ 30 ቀን 1929 ዓ.ም ድረስ አንድ ወር ሙሉ ከብቦ ወጋው። ጣልያን መሸጉ የተቀመጠ ከመሆኑ ጋር፣ የነጭ ወታደርና ብዙ ባንዳ ነበረው። በአርበኞች በኩል ለጦርነቱ የተሠለፉት ያን ያህል ብዙ አልነበሩም። የአርበኞች ጥቃት ያስቆጣው ጠላት፣ ከአዲስ አበባ አይሮፕላን እያስነሳ

አካባቢውን አስደንደበ። ቢሆንም አርበኞች አልተበገሩም። ሃያ ሰባት ነጭ፣ በርካታ ሃማሌንና ባንዳ ገደሉ። ከእነሱም ወገን 300 ሞቱ፣ 130 ቆሰሉ። ከዚህ በኋላ አርበኞቹ ወደ ጦር ሠፈራቸው፣ ወደ በስና ተመለሱ።[4]

በሌላው ወገን ደግሞ በቡራና በዳሞት በኩል የንጉሥ ተክለሃይማኖት የልጅ ልጅ፣ ደጃዝማች ነጋሽ በዛብህ ጣልያንን ቀስፈው ያዙት። በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት የማግኘት ችግር ስለአልነበረባቸው፣ ሥራቸው ተቃናላቸው። ጣልያንም መሸጉ ከተቀመጠባቸው ቦታዎች ውጭ መንቀሳቀስ አልቻለም። ነገር ግን የጠላት ሐሳብ፣ እሳቸውንም እንደ ራስ ኃይሉ በሽንገላ ወደው እንዲገቡለት ለማድረግ መሞከር ነበርና፣ ያንኑ ከመሞከር አልተቆጠበም።

የበላይ ዘለቀን እንቅስቃሴ በቅርብ ለመመልከትና በተመቸም ጊዜ ለማጥቃት እንዲቀናው፣ ጣልያን ከብቸና ባሻገር ጦር አሠፈረ። ይህ ድግስ ለእነሱ መሆኑን የተረዱት አርበኞች ከጦር ሠፈራቸው ገስግሰው ህዳር 5 ቀን 1929 ዓ.ም አደጋ ጣሉበት። አራት መቶ ባንዶች ደምስሰው የጦር ሠፈሩን አቃጠሉበት።

በታህሣሥ ወር 1929 ዓ.ም ሻምበል ደቦኖ በሚባል ጣልያናዊ የሚመራ ጦር ብቸና ገባ። አርበኞች አርገሞር በተባለው ቦታ ስለጉዳዩ ምክር አደረጉ። እንበለው በሚለው አርበኛና የዲማ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ይቃጠልብናል በሚሉት ካህናት መካከል የሀሳብ ልዩነት ተፈጠረ። በላይ ዘለቀ ጉባኤ ሰብስቦ የሁለቱም ወገን ከተደመጠ በኋላ ለካህናቱ ሀሳብ ብልጫ በመስጠት ውጊያው እንዲቀር ተደረገ። ካህናቱም በፊናቸው ከባድ አደጋ ሊጣልበት መሆኑን የሚያስረዳ ወሬ በሚያምነው ወዳጁ በኩል እንዲደርሰው በማድረግ ቦታውን በቶሎ ለቅቆ እንዲሄድ አደረጉ።[5] በካህናቱም በአርበኛውም ወገን የተሰጠው ውሣኔ መልካም ወጤት አስገኘ። ሕዝብም በይበልጥ ከአርበኞች ጋር ተባበረ።

እሳቸውም እንደዚሁ በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት የማግኘት ችግር ያልነበረባቸው ልጅ /ራስ/ ኃይሉ በለው፣ ደምበጫን ይዘው ጣልያንን መተናፈሻ አሳጡት። የጣልያን ሀሳብ የጉጃምን መሣፍንት ሸንግሎ ወደ እሱ እንዲገቡ ማድረግ ነበርና፣ ከጠላት ወገን የሚሠነዘርባቸው ጥቃት እምብዛም መራር አልነበረም።

ፀጋ ዳሞትን፣ በፊታውራሪ /ደጃዝማች/ ኃይለ ኢየሱስ የሚመራው አርበኛ ተቀጣጠረ። ጠዝጥዝ በተባለው የሸምቅ ጦርነት በየቦታው የጣልያንን ጦር ይጠዘጥዘው ጀመር።

ደጃዝማች /ቢትወደድ/ መንገሻ በሕመም ምክንያት እያደረጉ ከጠበል ወደ ጠበል፣ ከአገር ወደ አገር እየተዘዋወሩ ሕዝብ ከአሳበሩ በኋላ፣ ዴንሣ በተባለው አገር ጦር ማንቀሳቀስ ጀመሩ። ሰኔ 19 ቀን 1929 ዓ.ም በዚሁ በተጠቀሰው ቦታ ጣልያንን ግንባር ለግንባር ገጥመው ወጉት። ባለቤታቸው ወይዘሮ ሰብለ ወንጌል ኃይሉም ባላቸው የአባታቸውን የራስ ኃይሉን ዓላማ

እንደማይክዱ ቁርጡን አወቁት። ጠላት ሕዝቡ አንዳልተገዛለት ባወቀ ጊዜ ቤቱን ማቃጠል፣ ከብቱን መዝረፍ ያዘ። በደጃዝማች /ቢትወድድ/ መንገሻ ጀምበሬ የሚመራው አርበኛ መልካና ዴንሣ፣ ደደቤ በተባለው ቀበሌ በሰኔ ወር 1929 ዓ.ም ጠላትን ግንባር ለግንባር ገጥሞ ተዋጋው።

አንድ የአርበኞች ቡድን ከጉንደር፣ ከሰማዳ ወደ ጉጃም ተሻግሮ በዚያ ከነበሩ አርበኞች ጋር ተቀላቀለ። ከዚያም ነሐሴ 7 ቀን 1929 ዓ.ም ሾተል ማጠቢያ ከተባለው ቦታ ከጠላት ጋር ተዋግቶ፣ ጠላትን ወደ መጣበት ወደ መርጦለማርያም አባረረው። ነሐሴ 12 ቀን 1929 ዓ.ም ጉምት በተባለው ቦታ አርበኞች ከጠላት ጋር ጦርነት አካሂደው ብዙ ጉዳት አደረሱበት። በእነሱም ላይ ግን ጉዳት ደረሰ፣ ብዙ ጀግኖች ወደቁ።

አርበኝነትን ለማጠናከር ከሚረዱት ዘዴዎች ዋነኛው በየቤተክርስቲያኑ ክብረ በዓል በሚደረግበት ጊዜ ለሕዝብ ንግግር በማድረግ ምክር መስጠት ነበር። በዚህ መሠረት ደጃዝማች /ቢትወደድ/ መንገሻ ጀምበሬ ነሐሴ 20 ቀን 1929 ዓ.ም ዴንሣ በተባለው አገር፣ በክበረ በዓል ላይ ለሚጫ፣ ለዴንሣ፣ ለአገው ምድር፣ ለአቸፈር፣ ለጉታና ለሰከሰ ሕዝብ ንግግር አደረጉ። በንግግራቸውም ጣልያኖች በሕዝብ ላይ የሚፈፀሙትን ግፍ ዘረዘሩ። በአንድ ሕፃን ማሳደጊያ ጉዳይ የተጣሉ አንድ ወንድና አንዲት ሴት ለዳኝነት ቢቀርቡ፣ የባህር ዳሩ አገረ ገዥ ሕፃኑን በሽጥ ጥይት እንደገደለ፣ ጎንደር ከጣና ባህር ዳርቻ፣ ቅራጠ ከተባለው ቦታ ካህናቱን በመትረየስ ፈጅቶ ቤተክርስቲያኑን በእሳት እንደአቃጠለ፣ ያለአንዳች ጥፋት 5 ሰው እንደሰቀለ፣ አባ ተስፋ ማርያም ዶተባሉትን መነኩሴ ክነነፍሳቸው ሳይሞቱ እንደቀበረ፣ ሀሳቡ ሕዝቡን በባርነት አስገድዶ ለባዕድ ባንዲራ አስግዶ፣ ሃይማኖትን አስክዶ ለመግዛት መሆኑን ዘርዝረው አስረዱ። ሕዝቡም አምርሮ ተከተላቸው።

የህዝቡን ትብብር በዚህ አይነት ካጠናከሩ በኋላ፣ ፈቡዕ ገበያ ከሚባለው ቦታ ሠራዊታቸውን ልከው በጣልያን ላይ ጦርነት አካሄዱ። የአራት ሻለቃ ጦር አውድመው፣ አንድ ሻለቃና አንድ መቶ አለቃ፣ ከ80 መትረየስና ከብዙ ጠመንጃ ጋር ማረኩ።[6]

ልጅ /ራስ/ ኃይሉ በለው የጠላትን ጦር በደምበጫ አካባቢ አላፈናፍን አሉት። በፊታውራሪ አያሌው መኮንን የሚመራው አርበኛ በባህር ዳር አካባቢ ያሰውን ያዘ። ልጅ /ደጃዝማች/ በላይ ዘለቀ ብቸናንና አስክ ደጀን ድረስ ያለውን፣ አልፎ፣ አልፎ አስክ ደብረማርቆስ አካባቢ እየተጠጋ አስቸገረው። ዳንግላ የደጃዝማች /ቢትወደድ/ መንገሻ ጀምበሬ ሆነ። ፊታውራሪ አያሌው መኮንን ባህር ዳርን ያዙ። ፊታውራሪ ዘለቀ ብሩ የፍኖተ ሰላምን አካባቢ ድርሻቸው አደረጉ። ቡሬን የደጃዝማች ነጋሽ በዛብህ ሠራዊት ተቆጣጠረው። ፊታውራሪ ታፈረ ዘለቀና ወንድሞቻቸው የበለሰን ወንዝና ዝብሰትን ተቆጣጠሩ። ልጅ አደራ ደብረ ማይን ያዙ። በልጅ ደምሴ ዓለማየሁ የሚመራው አርበኛ በዳሞትና በሞጃ፣ በፊታውራሪ በየነ በሻው የሚመራው

በማቸከል የጠላትን ጦር ጠበጠበው። ሕዝብ ለአርበኞች የሚሰጠው ድጋፍ ቀስ በቀስ አደገ።

የ1929 ዓ.ም ሁኔታ በዚህ ዓይነት አልፎ የ1930 ዓ.ምቱ ትግል ተደቀነ። በጥቅምት መር 1930 ዓ.ም ከደጉማ የተነሣው የጠላት ጦር ዘዝ ለመድረስ ሲሞክር አርበኛው ውጊያ ገጠመው። ከበስስ እስከ ቀላይ እየተከታተለ ወጋው። ነገር ግን አወዳደቃቸው የአርበኛውን ልቦና አሳደከመውም።[7] በወቅቱ የጉጃሞች የውጊያ ስልት "ጠዝጥዝ" የሚባለው እንደመሆኑ፣ በየሄደበት እየተከተሉ ማጥቃትና መሣሪያ መቀማት የተሻለ ዘዴ ሆኖ ተገኘ።

የጠላት ጦር የበክናን የአርበኞች የጦር ሠፈር ለማውደም ከጅሉ እንቅስቃሴ አደረገ። አርበኞች ሁኔታውን አስቀድመው አውቀው በመረዳት፣ ታህሣሥ 4 ቀን 1930 ዓ.ም ተንቀሳቅሰው የጠላትን ጦር ከቀለበት ውስጥ በማስገባት በጨበጣ ውጊያ አረፈረፉት። ሁለት መቶ ወታደሮች ደመሰሱ፣ ሌሎች ሃምሣ አቆሰሉ። አምስት መትረየስ፣ ሁለት መቶ ሃምሣ ጠመንጃ ከአሥር ሺህ ጥይት ጋር ማረኩ። በአርበኞች ላይ ግን ምንም የረባ ጉዳት አልደረሰም። በዚህ ዓመት ታህሣሥ 7 ቀን በብችና አውራጃ፣ ልዩ ስሙ ሙጋ በተባለ ቦታ የነበረውን የጠላት ጦር ሠፈር አቃጠሉ። በዚህም ሦስት መቶ ወታደሮችና ብዙ መሣሪያ አጋዩ፣ ሌሎች ሁለት መቶ ባንዳዎችም ማረኩ።[8]

የጉጃም አርበኞች በዚህ ላይ እንደአሉ፣ የሸዋ አርበኛ በወለጋ በኩል ዞሮ፣ ዓባይን ወንዝ ተሻግሮ የካቲት 19 ቀን 1930 ዓ.ም ቡሬ ከተማ ገባ። የሸዋን ሠራዊት ካህኑ በንሴብሆ፣ ወንዱ በሆታ፣ ሴቱ በአልልታ ተቀበለው። ደጃዝማች ነጋሽም፣ ነፍስን በሚመልስ ምግብ በረሃ የጎዳውን አርበኛ ነፍስ ዘሩበት። ታላቅ ደስታ ሆነ።

ይህም ስለተባለ ስጋት አልቀረም። ጠላት ኃይሉን በዚያው መጠን እንደሚያጠናክር፣ ጦርነቱም ከባድ እንደሚሆን፣ ሳይታሰም የተፈታ ነበር። ጣልያንም እንደዚሁ አደረገ። ጀነራል ጋሊኒን የበላይ አዛዥ አድርጉ፣ ከሸዋና ከጉንደር ሃምሣ ሺህ ጦር አመጣ። አርበኞችን ለማጥቃት ጣልያን ከአንጀባራ ምሽግ መንቀሳቀስ ጀመረ። አካሄዱ ቤት እያቃጠለ፣ ሀብትና ከብቱን እየዘረፈ፣ ወንድና ሴት ሳይለይ ሰዉን እየፈጀ መሆኑ ቀደም ብሎ በፈፀመው ግብር ተረጋግጦ ነበርና፣ ገዘም ብሎ መጠበቅ ሀገሩን ማስጠፋት ሆነ። ስለዚህ ወሬው እንደተሰማ አርበኛው ከቡሬ ተነስቶ የካቲት 26 ቀን 1930 ዓ.ም በግስጋሴ ከአንጀባራ ምሽግ ጥግ ድረስ ወጥቶ፣ ከወዲያ ወዲህ በመዘዋወር ተጠባበቀው። ጣልያንም የአርበኛውን ጥንካሬና ቁርጠኝነት ሲረዳ ተመልሶ ወደ ምሽጉ ገባ።

ጣልያን ከሸዋ፣ ከጉንደር፣ ከባህር ዳርና ከዳንግላ ጦር ወደ ሰከላ አዘመተ። አርበኛውም ከግምጃ ቤት ገስግሶ በመሄድ አድም ከተባለ ቦታ ሆኖ

ጠበቀው። መጋቢት 11 ቀን 1930 ዓ.ም በደጃዝማች ነጋሽ የታዘዘ ቡድን ሄዶ ገጠመው። በዚህ ውጊያ የጠላት ጦር ሲያመዝን፣ የሸዋው ጦር ደርሶ ከጠላት ጦር 300 የሚያህለውን በቅጽበት አረገፈው። ጠላት አይሮፕላን አስመጥቶ ቢያስደበድብም አርበኛው አልተበገረም። በሃምሣ ሺህ የሚገመት ጠላቱን በ700 ቤልጅግ ጠመንጃና በ1 መትረየስ አባረረው። በተከታታይ የመጣውን የጠላት ጦር መጋቢት 17 እና 18 ቀን 1930 ዓ.ም ሚጫና አቸፈር ላይ ወግቶ ጉዳትም አደረሰበት።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በደጃዝማች ነጋሽና በወይዘሮ ሰብለ ወንጌል መካከል ቅያሜ ተፈጠረ። እነ ደጃዝማች ገሠሠ ከድተው ከጦር ግንባር በተመለሱ ጊዜ የሸዋ ጦር እንደወጋቸው አየተደረገ ተነገረ። የራስ ኃይሉም ተፅዕኖ በረታ። በዚህ ምክንያት አርበኛው በጦር ላይ ነገር ተጨመረበት። ይህም ሆኖ የጉጃም ሕዝብ ድጋፉን አልቀነሰበትም። የህበሻ ልብ ይክፋፈል እንጂ፣ በወራሪው ጣልያን ጉዳይ ልቡ አንድ ነው።

ጀነራል ጋልያኒ ጦሩን እንደገና አሰባስቦ አንጀባራ ከተባለው ምሽግ ገቡ። አርበኛውም በበኩሉ ፈጠም ከተባለው ወንዝ ላይ ምሽግ ሠርቶ ጠበቀው። ጣልያን አርበኞች የነበሩበትን አካባቢ በአይሮፕላን ከአስደበደበ በኋላ ጉዞ ጀመረ። ከፍ ብሎ በተጠቀሰው ባላገር አርበኞችን ከጀርባቸው ለመውጋት መከጀሉ ስለታወቀ ከጣልያን ጋር ግንባር ለግንባር መግጠም የማይጠቅም ሆነ። ስለዚህ ጋልያኒ ሰተት ብሎ ቡሬ ከተማ ገባ። ከዚያም ጉዞውን ወደ ጉጃም ቀጠለ። በዚህ ሁኔታ አርበኛው ተበሳጨ። መጋቢት 18 ቀን 1930 ዓ.ም ኢማሉግ ላይ የተደረገው ውጊያ ሳይመልሰው ቀርቶ፣ ቡሬ ድረስ ሄዶ ገጠመው። አንድ ሻምበልና ብዙ ነጮች፣ ብዙ ባንዳም ገደለበት።

ከአርበኞች የነበረውን አማኔ የተባለውን ሀገር ጣልያን ሚያዝያ 20 ቀን 1930 ዓ.ም ሙሉ ቀን በአይሮፕላን ደበደበው። ብዙ ጉዳትም አደረሰ። ስለዚህ አርበኞቹ ጠልያ ወደ ተባለ ቦታ፣ ከዚያም ወደ ወንበራ ተጓዙ። ጣልያንም በሌሊት ጭምር አደጋ በመጣል ጉግሣ አስከተባለው ቦታ ድረስ ተከታተላቸው።

ጠላት አሰፋ ካሳ በተባለው ቀበሌ በነበሩ አርበኞች ላይ በ1930 ዓ.ም አደጋ ጣለ። አርበኞች ለመካላከል ቢሞክሩም መቋቋም አልቻሉም። መሪአቸው ልጅ አበራ በሪሁን በሮምታ በተተኮሰባቸው ጥይት ተመትተው ወደቁ። ሚስትየዋ ተተክተው ሲያዋጉ አሳቸውም ተመትተው ወደቁ። ጠላት የባልና ሚስቱን ራስ ቆርጦ አሰፋ በመውሰድ ጊጤ ተጫወተበት። የአሰፋና የአቸፈር አርበኞች ይህንን ሲሰሙ በፍጥነትና በአልሀ ተንቀሳቅሰው፣ የይስማላን ምሽግ መይመዱን አጠፉት።

በዚህም ጊዜ ላይ በአርበኛው መካከል እንደገና የሀሳብ ልዩነት ተቀሰቀሰ። ፍሬ ነገሩ እንሰደድ፣ እዚሁ እንዋጋ የሚል ነበር። የሸዋው እንጂ የጉጃሙ አርበኛ የስደት ፍላጐት ሲልነበረውምና፣ ከደጃዝማች ነጋሽ በዛብህ

ፊፋ ከተባለው ቦታ ዝም ብለው ተሰየ። የሸዋው ቡድን ጉዞውን ቀጥሎ ግንቦት 16 ቀን 1930 ዓ.ም ወንበራ ገባ። ወንበራ ላይ ምክር ተደርጎም አንዱ ወገን ወደ ሱዳን ጠረፍ እንሂድ አለ። የሰጠውም ምክንያት ሥራችንን እና ሁኔታችንን ለማስታወቅ፣ አርዳታና አመራር ለማግኘት የሚል ነበር። እንዲሁም ከደረስበት ቅጥቃጤ ጥቂት ዕረፍት ለማግኘትና የቆሰለው፣ የታመመው እንዲታከም የሚል ስለነበረበት፣ ወደ ሱዳን መሄድን የመረጠው በዛ። ሌላው ወገን ደግሞ ክፉውንም፣ ደጉንም በሀገሬ በረሃ እቀበለዋለሁ እንጂ ወደ ባዕድ አልሄድም ባይ ሆነ። ዕርቅ የማይቻል በመሆኑም፣ እያንዳንዱ እንደ ፍላጎቱ እንዲያደርግ ስምምነት ተደረሰ። ሚያዝያ 27 ቀን 1930 ዓ.ም ከሸዋ አርበኛ የሚበልጠው ተገምሶ ወደ ጠረፉ ለመሄድ ተነሣ።

የአርበኞችን መለያየት ጣልያን ደርሶበት ነበርና፣ በሀገር ውስጥ ለመዋጋት ባሰበው አርበኛ ላይ ከፍተኛ ክትትል አደረገ። ወደ ሸዋ ተመልሶ እንዳይገባ መንገዱን አጠረበት። ምንም ከጉንደር፣ ከሞጣና ከወለጋ የተሻገረው፣ ከዚያው ከጉጃም ከተውጣጣው ጦር ጋር በመተባበር ቢሆን፣ እነደጃዝማች ገሠሠ በክዱ ጊዜ ተዋግቶ ነበርና ለሸዋ ሠራዊት በጉጃም ምድር አርበኝነት መቀጠል የማይሆንለት ሆነ። የሀገሬውም አስተሳሰብ ተከፋፈለ። ባላገሩ ሀብቱን፣ ንብረቱን ለመጠበቅ ሲል ወደ ጠላት (ወደ ሠላማዊነት) አዘነበለ። አርበኛውም እየጐጠ ገባ። ከሸዋ የተሻገረው ከዚያ መቆየት የማይሆንለት ሆነ። ስለዚህ አንደገና ወደ ወለጋ ተመልሶ ለመሻገር ወሰኖ ጉዞውን በግስጋሴ ቀጠለ።

ሚያዝያ 30 ቀን 1930 ዓ.ም እሑድ ከዓባይ አፋፍ ሲደርስ ጠላት ቀድሞ ሲጠብቀው አገኘ። ይህንን በር አርበኛው በኃይል ሰብሮ ማለፍ ስለነበረበት፣ በብርታት ተዋግቶ ጦሩውን በማስለቀቅ ከወንዙ ገባ። በዚህ ጊዜ ከጉጃም ወገን አዲስ የጠላት ጦር ደረሰበት። ከወለጋ ወገን ደግሞ ሌላ ጦር መጣበት። ሁለቱንም እየተከላከለ ወንዙን ተሻግሮ ወደ ግንደበረት የሚያደርስ መንገድ ያዘ። በጦርነቱም፣ በውሃውም ብዙ ሰው አለቀበት።[9] ወደ ግንደበረት የሚወስደውን መንገድ ትቶ ወደ ወለጋ በረሃ ለበረሃ በመጓዝ፣ ለሀገሩ ሲል በፈቃዱ ከመረጠው ሥቃይ ውስጥ ገባ። ምክንያቱም ግንደ በረት በከባድ የጠላት ጦር ተይዞ ነበርና።

ሌላኛው፣ ወደ ሱዳን የሚሄደው ቡድን፣ ዝግጅት አድርጐ ጉዞውን ቀጠለ። ከዝግጅቱ ዋነኛው ቀኛዝማች እዬታ ከተባለው ሰው ጥቃት እንዳይደርስበት መጠንቀቅ ነበር። ይህ ሰው ልቡን ከጠላት አፋን ከአርበኞች አድርጐ፣ ምቹ ጊዜ በመጠበቅ ላይ ነበር። ይህንን ሁኔታ አርበኞቹ ተረድተውት ነበርና፣ ወደ ሱዳን በሚሄዱበት ጊዜ እጁን ይዘው ጉዞ ጀመሩ። ሀገሬውም ሊያድነው፣ ጣልያንም ሊደርስለት አልቻለም። እሱም ይህንን በተረዳ ጊዜ በደሉን አምኖ፣ በመሐላ እርቅ ሆኖ፣ ተለቀቀ። የታመነ መሪ

ለጥቶ ሸኛቸው። አርበኛው በሰላም መንገዱን ቀጥሎ ግንቦት 26 ቀን 1930 ዓ.ም ከተመኘው ከሱዳን ጠረፍ ደረሰ።[10]

ጣልያን በጉጃም ያሉ አርበኞችን ለማጥፋት በማሰብ በዋና ዋናዎቹ ላይ ማለሙን ቀጠለ። ልጅ በላይ ዘለቀ በዲማ ጊዮርጊስ፣ አቤ በተባለው ዋሻ ሱባኤ በያዙበት ጊዜ፣ አደጋ ጥሎ ለማጥፋት ከበባ አደረገ። እሳቸው ግን ከበባውን በኃይል ሰብረው በመውጣት አመለጡት። ለምጨን በተባለውም ቦታ እንደዚሁ ሆነ። ከዚህ በኋላ በበላይ ዘለቀ ሠፈር ምክር ተደረገ። የአርበኛውን ኃይል የሚያጠናክርና ለሥምሪቱ ሥምሪት የሚሰጥ ድልድል ተሠራ። እስከ ደጃዝማች ድረስ ሹመት ተሰጠ። ለእያንዳንዱ እንደሙያው፣ እንደጀግንነቱ ሹመት ሰጡ። ሁሉን ለእኛ ሰጠህ ለአንተስ ምን ቀረህ? ተብለው ቢጠየቁ፣ እናቴ "በላይ ብላኝ የለ" አሉ ይባላል።

በድልድሉ መሠረት አርበኛው በአሥራ አራት ደጃዝማቾች፣ በአምስት ፊታውራሪዎች የሚመራና አንድ በጀሮንድ ያለው ሆነ። ይህም ድልድል ሠራዊቱን አጠናከረው። እንማ በረንታ፣ እናርጅ እናውጋ፣ ጉበያ ሊበን፣ ቱንባት፣ አዋባል፣ ናይጭ የተባሉትን አምስት አካባቢዎች በቁጥጥር ሥር አዋሉ። የእሳቸውም የጦር ሰም አባ ኮስትር ሆነ።

ጫኔ ተረፈ የተባለ ሰው ከአርበኞች ከድቶ ለጣልያን ገባ። ከዚያም ግብረ አበሮቹን ይዞ በደጀን ወረዳ፣ ልዩ ስሙ ሸበል በረንታ በተባለ አካባቢ ከዋሻ ገባ። ይህ ሰው የአርበኞቹን ምሥጢር ያውቅ ስለነበር፣ ጠላትነቱ አደገኛ ሆነ። አርበኞች በነሐሴ 1930 ዓ.ም ከበባ አድርገው ሊያጠቁት ቢምክሩ ሳይሳካላቸው ቀረ። አደሙ የተባለውን አርበኛ ገድሎ አመለጠ። ይህ እንደ ተሰማ በላይ ዘለቀ ጦራቸውን ይዘው ገስግሰው በመድረስ፣ ነሐሴ 29 ቀን 1930 ዓ.ም አደጋ ጣሉበት። በተካሄደው ውጊያ ጫኔ ቆስሎ ሲያመልጥ፣ ብዙ ግብረ አበሮቹ ሞቱ። ሁለት መቶ ሰማንያ ጠመንጃና አራት መትረየስ ማርከው ወደ ጦር ሠፈራቸው፣ ወደ በከና ተመለሱ።

በዚሁ በ1930 ዓ.ም ወረካዩ ከተባለው ቦታ ላይ ታላቅ ጦርነት ተደረገ። የበላይ ዘለቀ ባለቤት ወይዘሮ ሸክሚቱ ዓለማየሁ ከሃምሳ አርበኞች ጋር ወደቁ። በእባ ኮስትር በላይ ዘለቀ የሚመራው አርበኛ፣ በዚሁ በነሐሴ ወር 1930 ዓ.ም ደብረ ወርቅ ጨጨ፣ አያልፉሽ ከሚባል ቦታ በጣልያን ላይ አደጋ ጣለ። ከማታው 12 እስከ ንጋቱ 12 ሰዓት በተደረገው ትንቅንቅ አንድ መቶ አለቃና ሠላሳ ሦስት ጣልያናዊያን ወታደሮች ከብዙ ባንዳ ጋር ተደመሰሱ። አንድ ቢዘንቲ የውሃ መትረየስ፣ ሃያ ሁለት አልመን መትረየስና ሰማንያ ሁለት ጠመንጃ ከእነጥይቱ ተማረከ።

የአርበኛውን ቡድን እናወድማለን በማለት እየፎከረ፣ ከደብረ ማርቆስ አንድ ክፍለ ጦር ተንቀሳቀሰ። በበላይ ዘለቀ የሚመራው ሠራዊት እንበሬ ከተባለው ቦታ አንጥፎ ጠብቆ አመድ አደረገው። የተረፈው የጠላት ጦር ትስሙ ተሰበረ፣ ፎክሮ ከወጣበት ከፉማ ተሾልኮ ገባ።

የሆነለት መስሎት ጣልያን ወደ ኮስታራው ወደ በላይ ዘለቀ መልዕክተኞች ላከ። መልእክቱም እሱ ልጃቸውን ከእሥራት ሊፈታላቸውና የጉጃምን ገዥነት ሊሰጣቸው ቃል የሚሰጥና፣ በላይ ዘለቀም በሰላም እንዲገቡለት የሚጠይቅ ነበር። ኮምጣጣው በላይ ዘለቀ ግን "...እናት አገሬን ለጥቅም መሸጥ...የሞት ሞት ነው..." በማለት መልእክተኞቹን ሰፍርድ አቀረቡአቸው። የጣልያን መልእክተኞች ሆነው የመጡት ሁለት ሹማምንቶች ብዙ አርበኞችን ያስጨፈጨፉ ነበሩና፣ ሠራዊቱ ይመት በቃ እየፈረደ በስትላት እንዲቀጡ ወሰነ። እጅጉ ለማ እና አደራ ያለው ወዲያው የአርቅ ጥያቄ ላቀረበላቸው ጣልያን ከመልእክተኞቹ ጋር በላከው አስተርጓሚው እጅ የመልስ ደብዳቤ ፃፉለት። ቃሉም "...ወደድክም ጠላህም ጉጃም የራሴ አገር ነው።...እናት አገሬን ኢትዮጵያን በአንድ ልጄ አልለውጣትም።...የተወለዳችሁበትን ቀን እንድትረግሙ ያደረግን ጀግኖች መሆናችንን እራስህ አትክደውም..." የሚል ኃይለ ቃል ነበረበት። ከዚህም በስተቀር ደብዳቤው በዚያው ቀን ብቸና አቅራቢያ የነበረውን ምሽግ የሚደመስስ ሠራዊት መላኩን የሚገልጽ ነበር። የብቸና ምሽግ ዕለቱን ተደመሰሰ። ሁለት መቶ የጠላት ወታደሮች ሞቱ፣ ሃምሳ ቆሰሉ፣ አንድ መቶ ተማረኩ፣ ምሽጉ ተዘረፈ። ልጅቱን ደግሞ ልመንህ ዋጋዬ የተባለው የደብረ ማርቆስ የወህኒ ቤት፣ ሰርቆ ቦከና በመውሰድ ለአባትዋ አስረከበ።

ይህ በአንዲህ እንዳለ ሻለቃ /ራስ/ መሥፍን ስለሽ ሚያዝያ 23 ቀን 1931 ከሱዳን ተመልሰው ጉጃም ገቡ። የመጡበትም ለጉጃም ሕዝብ ከንጉሠ ነገሥቱ ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የተላከ መልእክትና የመልእክት ማስተላለፊያ ሬዲዮ ይዘው ነበር። ሬዲዮውም ስከላ፣ ሣንጌ ከተባለው ቦታ ተቋቁሞ ሥራ ጀመረ። ይህንን ያየ ባንዳ ከጣልያን እየከዳ ከአርበኞቹ ጋር መቀላቀል ጀመረ። ሻለቃ /ራስ/ መሥፍንም ከደጃዝማች መንገሻ ጀምበሬ ጋር በአገው ምድር በደጋ ዳሞት፣ በሰከላ፣ በጣሊያ፣ በልጀምበራ፣ በአዴት፣ በሜጫ፣ በአቸፈር፣ በጉታ እየተዘዋወሩ ሕዝቡን አስተባበሩ። ሕዝቡም በየሥፍራው ያደፈጠውን የጣልያን ጦር ከተሸሸገበት ምሽግ እየቆሰቆሰ ያስቃየው ጀመር።[11]

ከሱዳን ጠረፍ የሚሰማው ወሬ የሕዝቡን ልቡና የሚቀሰቅስ እየሆነ ሄደ። ይህ ሁኔታ ጣልያኖችን አስጋቸው። በእሥራት ስም ወደ ሮም የተወሰደውን ራስ ኃይሉ ተክለ ሃይማኖትን ጣሊያኖች መልሰው አመጡት። ከአርበኞች ጋር በሚደረገው የእርቅ ንግግር፣ በሽምግልና እንዲገባ አደረጉት። ይህም እንደ አልሠራና ሁኔታው እየከበደ እንደሄደ ሲረዱ፣ ድርሻውን እንዲወጣ ወደ ጉጃም መልሰው ላኩት። ጣልያኖች በጉጃም ሕዝብ ላይ የመደለያ ወሬ አዘነሙበት። ጠላት በያለበት መግለጫ መስጠት፣ አዋጅ ማውጣት ያዘ። ለምሣሌ ግንቦት 10 ቀን 1931 ዓ.ም ጀነራል ሊዊጂ ፍሩሺ ባወጣው ቃል "የጉጃም ሕዝብ ስማ ስማ" በማለት ይጀምርና "ብሀሊናዬ ሁሉ እንድትታዘዙና እንድትገቡ ብጣጣር...አልሰማኝ አላችሁ..." በማለት ይማረር

እና፣ አሁንም እንዲገቡለት ልምምጡን ይቀጥላል። ነገር ግን የጉጃም ሕዝብ፣ ጠላት ልምምጥ ያበዛው እሱን ወድዶት ሳይሆን ተጨንቆ መሆኑን አወቀ።

ጣልያን በአማራው ሕዝብ ላይ የሚያካሂደውን ውትወታ በመቀጠል ነሐሴ 17 ቀን 1931 ዓ.ም ሌላ አዋጅ አወጣ። ይህ ደግሞ መሬት የሕዝብ መሆኑን መንግሥት በትክክል እንዳለወቀ፣ ጭቃ አበሱን እንዲቀበል፣ የወረዳ ገዥ ለመንግሥት ከሚገባው ከአሥር እጅ ሁለቱን እንዲወሰድ፣ ዳኝነትና አፈርሣታ እንደ ጥንቱ እንዲሆን፣ የነጭ፣ የጥቁር ማር፣ የምልምል፣ የበሬ ጫንቃ፣ የጢስ ጨው፣ የዓመት በዓል፣ የደምበኛ /የጦም/ ቆሎ እንደተፋቀ የሚገልጽ እና አማኝ የሆነ እስከ ጥቅምት 15 ቀን 1932 ዓ.ም ቀርቦ እንዲመዘገብ የሚያዝ ነበር። ይህንን ያላደረገ ከርስቱና ክጉልቱ እንደሚነቀል የሚገልጽ ነበር። ግን ይኸም እንደሌሎች አዋጆች ውጤት አልሰጠም።

የ1931 ዓ.ም ትግል በዚህ ዓይነት ተፈጽሞ 1932 ዓ.ም ባተ። ህዳር 12 ቀን 1932 ዓ.ም ከእንጀባራና ከቡሬ የጠላት ጦር ተንቀሳቀሰ። ዓላማው አሁንም አርበኞችን ለማጥፋት ነው። አርበኞች ፈጣም ከተባለው ወንዝ ላይ ገጠሙት። ውጤቱ ለጠላት ፈጣን ሆነበት። አንዱ ዋና የፍልሚያ ቦታ አቸፈር ሆነ። ጣልያኖች ባወጡት የጦር ማስታወቂያ፣ ይህ ቦታ ተደጋግሞ ተጠቅሶአል። በዚኅ ሽሞን የአውሮፕላን ጦርነት እየተጋጋመ ሲሄድ፣ ከእሱ ጋር በማስታከክ በአማራው አገር ስለሚካሄደው ጦርነት መግለጫ ያወጡ ጀመር።[12] ይህ ደግሞ ለአርበኛው የልብ ልብ ሰጠው። ትግሉን በበለጠ ብርታት ቀጠለ።

በኩሉኔል ቶሌራ የሚመራ የኢጣልያን ጦር መጣ። አርበኞችም ጳጉሜ 5 ቀን 1932 ዓ.ም አቸፈር፣ ዝብነት ላይ ገጠሙት። ከሱዳን በአዛዥ ከበደ ተሰማ አስተዳዳሪነት፣ በብርጋዴየር ላንድፎርድ መሪነት የመጣው የእንግሊዝ ነፃ አውጭ ጦርም በውጊያው ለመጀመሪያ ጊዜ ተካፋይ ሆነ። ጣልያን በአለው መሣሪያ ሁሉ ድብደባ አካሄደ። ነገሩ ግን ውጤት አላስገኘበትም።

ከዚህ በኋላ ወሣኙ የ1933 ዓ.ም ፍልሚያ ተጀመረ። የጉጃም አርበኛ ከንጉሠ ነገሥቱ በተሰጠው መመሪያ መሠረት መሥራት ጀመረ። በዚህ ግንባር የንጉሠ ነገሥቱ ወኪል አዛዥ ከበደ ተሰማ ሲሆኑ፣ በእንግሊዝ በኩል ብርጋዲየር ላንድፎርድ ነበሩ። ሆኖም ከእንግሊዝ ወገን የሚሰጠው እመራር የአነሱን የበላይነት የማጠናከር ባህርይ አመጣ። ይህ ደግሞ በኢትዮጵያውያኑ በኩል ቅሬታ ስለአስከተለ፣ በሀገር ውስጥ ዘዴ መሥራት ግድ ሆነ። ለማጥቃቱ ሥራ አዲስ ድልድል ተሠራ። በድልድሉም የአቸፈር ጦር በፊታውራሪ አያሌው መኮንን እየተመራ አስከ አሰፋ ድረስ እንዲገባ ተመደበ። የጉታ፣ የሰከላና የአንሹሽ አርበኛ በደጃዝማች መንገሻ መሪነት በስተግራ በኩል እንዲያጠቃ ተወሰነ። የኳኩራን የደርቤቲ አርበኛ በእነ ፊታውራሪ አደመ አስተባባሪነት የቋንግላን ምሽግ ከብቦ እንዲያጠቃ ታዘዘ።

ባህር ዳር የነበረው የጣልያን ጦር እንዳያመልጥ የሜጫ በር በአራት ፊታውራሪዎች በሚመራ የአርበኛ ሠራዊት እንዲታጠር ተደረገ። በዚሁ በታሰበው ዓይነት ተፈፀመ። ይኼኛው ሥልት በሀገር ውስጥ የጦር ዘዴ የተቀመመ በመሆኑ፣ ጥሩ ውጤት አስገኘ።

ንጉሠ ነገሥቱ ከሱዳን ወደ ኢትዮጵያ ስለሚገቡበት በር በአርበኛውና በነፃ አውጭው ጦር መካከል ምክር ተደረገ። ዝርዝር ጥናት ከተካሄደ በኋላ፣ በወንበርማ በኩል እንዲገቡ ከስምምነት ላይ ተደረሰ። ሃሣቡም በአዛዥ ከበደ ተሰማ ፊርማ ጥቅምት 4 ቀን 1933 ዓ.ም በተፃፈ ማስታወሻ ለንጉሠ ነገሥቱ ተላከ። ወንበርማ ለንጉሠ ነገሥቱ መግቢያ እንዲሆን የተመረጠበት ምክንያት፦

1ኛ.ጥቅጥቅ ያለ ጫካ ያለበት በመሆኑ ለጠላት አደሮፕላን አደጋ አለማስጋቱ፣

2ኛ.የጠላት ጦር ገብቶ እንዳያጠቃ ለማገድ ምቹ በመሆኑ፣

3ኛ.ቀደም ብሎም የጠላት ጦር ሊገባ ሞክሮ ተሸንፎ የቀረ በመሆኑ፣

4ኛ.ለእንግሊዝ አይሮፕላን ማረፊያ የሚሆን ሠፊ ሜዳ መኖሩ፣

5ኛ.ክባቢው የዓባይ ወንዝ በመሆኑ ሊሻገር አለመቻሉ፣ ነበር።

ንጉሠ ነገሥቱም ሃሳቡን ስለተቀበሉ፣ ዝግጅቱ ቀጠለ። ለአርበኞች የትብብር መጠየቂያ ደብዳቤዎች በየአስተባባሪዎቻቸው ስም ተፃፈ። አብዛኛው በአዛዥ ከበደ ተሰማ የተፈረመ ሲሆን፣ አንዳንዱ በንጉሠ ነገሥቱ የተፈረመ ነበር።[13] ጥሪው አብዛኛውን የጐጃም አርበኛ ሲያስደስት እንዳንዱን ቅር ማሰኘቱ አልቀረም። ለበላይ ዘለቀ የተፃፈው ደብዳቤ ሲደርስ የሆነውን መመልከት ግንባቤ ሊሰጥ ይችላል።

አባ ኮስትር ሁለት የጥሪ ደብዳቤዎች ደረሱአቸው፣ አሳቸው ግን ምላሽ ሳይሰጡ ቆዩ። መልስ ያልሰጡትም፦ «ንጉሡ ሀገራቸውን ለጠላት አስረክበው የከዱሉ ሰው ናቸው። አሳቸው ዘንድ መሄድ የለብኝም።» የሚል ጠንካራ አቅዋም ስለነበራቸው ነው። ለሦስተኛ ጊዜ ጥሪ ሲደርሳቸው፣ ጉዳዩን ለሠራዊቱ አቀረቡት። ደብዳቤው በአደባባይ ተነበበ። ሠራዊቱም በጉዳዩ ከመከረበት በኋላ፣ ከአንድ ድምዳሜ ላይ ደረሰ። ድምዳሜውም፦ "...ለእኛ አይጠቅመንም... የተጋደልነው ለአናት ሀገራችን እንጂ ሥልጣን ለመፈለግ አይደለም። ...ሀገራችን ከጠላት ከተላቀቀች በሰላም አርሰን እንበላለን..." የሚል ነበር። ይህ አመለካከት በሠራዊቱ መካከል የድምፅ ብልጫ ስለአገኘ፣ የንጉሠ ነገሥቱ ጥሪ ተቀባይነት አገኘ።[14]

የትብብር መቀስቀሻው ደብዳቤ ከንጉሠ ነገሥቱ በቀጥታ ከተፃፈላቸው ሰዎች አንዱ ራስ ኃይሉ ተክለ ሃይማኖት ነበር። ከንጉሠ ነገሥቱ ለተፃፈለት፣ ራስ ኃይሉ የሰጠው መልስ ይዘቱ አልታወቀም። ነገር ግን ከአዛዥ /ደጃዝማች/ ከበደ ጥቅምት 13 ቀን 1933 ዓ.ም ለተፃፈለት ደብዳቤ፣ በፀሐፊው በቀኛዝማች ተገኘ ፊርማ የሰጠው መልስ ጥሪውን መቀበሉን አያመለክትም።

አዛዥ /ደጃዝማች/ ከበደ በሰጡት ትንታኔ "...ምልክቱን ይሳኩብኝ ብዙ ለጠየቅሁዋቸው ጥያቄ በሚገባ መለሱልኝ..." ይላሉ እንጂ፣ ልዑሉ የሰጠው የአምቢታ (መልስ) ነው። አዛዥ /ደጃዝማች/ ከበደ ተሰማ ተቆራኝተዋቸው እንደነበር ከመጥቀስ ጋር፦ "... ከዚያ መከራ አውጥቶ ከሞት አትርፎ፣ ሀገሬን ሰጥቶ ለዚህ ሳበቃኝ ለኃያሉ የጣልያን መንግሥት ምን ውለታ ለመልስለት?..." ብሎ እስከ መጠየቅ የደረሰ ነበር። በግብር የታየውም፣ እስከ መጨረሻው ድረስ ከጣልያን ጐን መቆሙን ነው።

አዛዥ /ደጃዝማች/ ከበደ ተሰማ ለባንዳ መሪዎችም በርካታ ደብዳቤዎች ጽፈዋል። ከእነዚህም ደብዳቤዎች አብዛኞቹ ንጉሠ ነገሥቱ ከእንግሊዝ መንግሥት እርዳታ አግኝተው መምጣታቸውን፣ አሳቸውም ከንጉሠ ነገሥቱ ታዝዘው ጉጃም ምድር መግባታቸውን እያበሠሩ "...ሲሆን ሥራ ሠርተህ ራስህንና ወገኖችህን መክረህ ሰዓቱ ሳያልፍ ከጠላት ተለይ። እንዳትዘነጋና በኋላ ፀፀት እንዳይሆንብህ..." የሚል ምክር ያዘሉ ነበሩ። በብዙ ወገን ተቀባይነት አገኙ። ብዙ ሰው ከጣልያን እየከዳ ወደ አርበኞች ዞረ። ሰሆዱ ያደረ ነውና፣ አንዳንድ ሥራ በመሥራት በአዲሱ ሥርዓት ውስጥ ክብር ለማግኘት ተፍጨረጨረ።

ጣልያንም በበኩሉ ወሬ በመንዛቱ ረገድ ሥራ አልፈታም። የሀሰት ፕሮፓጋንዳ ይረጭ ጀመር። ንጉሠ ነገሥቱ በእንግሊዝ አይሮፕላን የሚያስበትኑትን ፅሑፍ የሚመስል እያዘጋጀ በአይሮፕላን በተነ። ከሚጣለው ወረቀት አብዛኛው በአርግጥም ንጉሠ ነገሥቱን የሚያጥላላ፣ የኢጣልያንን ድል አድራጊነት የሚነግርና የእንግሊዝን መሸነፍ የሚተነብይ ቢሆንም፣ አንዳንዱ ከጣልያን ይልቅ ለኢትዮጵያ የሚጠቅም ነበር። ለዚህ ሁኔታ ማስረጃ ሆኖ ሊጠቀስ የሚገባው ህዳር 9 ቀን 1933 ዓ.ም ለሸዋ ሕዝብ የተጣለው ነው። ይህ ወረቀት በጠላት የተበተነ ነው ከማለት ይልቅ፣ ከጠላት መባረር በኋላ የንጉሠ ነገሥቱን ክብር ለመጠበቅ ሲባል የተደረገ አሠራር ነው ማለቱ ይቀላል። ዝርዝሩን ከፅሑፉ ከራሱ መመልከት ይበቃል።

ንጉሠ ነገሥቱና መልእክተኛቸው አዛዥ /ደጃዝማች/ ከበደ ተሰማ ለዓፋአቸው ደብዳቤዎች ማስተባበያ ጣልያን ወረቀት መበተኑን ከዚህ በላይ አይተናል። አሁን ደግሞ ንጉሠ ነገሥቱና ወኪሎቻቸው፣ ጣልያን የበተነውን የሀሰት ወረቀት ሰማርከስ ሴላ ወረቀት እያዘጋጁ መበተን ነበረባቸው። የጣልያን ደብደቤ ቃል በፍፁም ሀሰት መሆኑን የሚገልፅ ያዋጅ ቃል በየገበያው እንዲነገር ተደረገ። ደብዳቤውም ለአርበኞች መሪዎች በብዛት ተፃፈ። ጉጃም የሁለትዮሽ ፕሮፓጋንዳ ሜዳ ሆነች፣ ምንም ተባለ ም ግን፣ የሕዝቡ ልብ በኢትዮጵያ ነፃነት ላይ ፀና።

ሴላው ሥራ በአርበኞች መካከል የነበረውን የርስበርስ መቃቃር ማስታገስና ሀገርን ነፃ በማውጣቱ ሥራ ላይ እንዲያተኩሩ የማድረጉ ሥራ ሆነ። ይህም አሰልችና አድካሚ ነበር። አስታራቂ የመኖሩን ያህል፣ ነገር

አጋጋሚም ነበርና የሀገሬው በነገር መታመስ ቀላል አልሆነም። በልጅ በላይ ዘለቀና በልጅ ኃይሉ በለው መካካል ያለውን ቅራኔ፣ በወቅቱ እርቅም ሊፈታው አልቻለም። ከልጅ አያሌው ደስታ ጥር 18 ቀን 1933 ዓ.ም ለአዛዥ /ደጃዝማች/ ከበደ ተሰማ የተፃፈውን መመርመር ግንዛቤ ያስጨብጣል። ከዚህ በተረፈ ግን የተደረገው ጥረት ጥሩ ውጤት ስለሰጠ የጐጃም አርበኞች የተባበረ ክንዳቸውን በጠላት ላይ አነሱ።

ጦርነቱ ተፋፋመ። ጥር 8 ቀን 1933 ዓ.ም ለጣልያን ባደረው በደጃዝማች ማሞ ኃይለሚካኤል የሚመራ 12 ሺህ የጠላት ጦር አርበኞችን ለማጥቃት በደጃዝማች ነጋሽ ላይ አደጋ ጣለ። አርበኞችም ከጥዋት እስከ ሰባት ሰዓት ወግተው ስለአባረሩት፣ ተመልሶ ቡሬ ገባ። ብቸና ከተማ የነበረው ጦር በአንድ መቶ ሃምሣ አራት ካሚዮን ተሳፍሮ ጥር 13 እና 20 ቀን 1933 ዓ.ም ደብረ ማርቆስ ገባ። ነገር ግን በወሎ ተሸግሮ ተባብሮ ለመመከት የሞከረውን የጣልያን ጦር በላይ ዘለቀ ወንድሞቻቸውን ልከው በመውጋት አቆሙት። ስለዚህ ምሥራቅ ጐጃም ላይ የነበረው የጠላት ጦር ብቻውን ቀረ።

ንጉሠ ነገሥቱ ጥር 12 ቀን 1933 ዓ.ም አሜድላ ከምትባለው የኢትዮጵያ ግዛት ገቡ። ይህም በጐጃም ሕዝብ ዘንድ በፍጥነት ታወቀ። የእንግሊዝን የበላይነት ለማጠናከር ይጣጣር በነበረው በሳንድፎርድ ምትክ ሀቀኛው ኮሎኔል/ጄነራል/ ሎርድ ዊንጌት የካቲት 8 ቀን 1933 ዓ.ም ተተካ። ለጐጃም ሕዝብም ከንጉሠ ነገሥቱ ምክር አዘል አዋጅና መመሪያ በተደጋጋሚ መጣለት። ምክሩም የጐጃም ሕዝብ በጐፍላ ጥጃ እንደምትታለብ ላም በራስ ኃይሉ እየተታለለ ከጣልያን እጅ እንደገና እንዳይወድቅ የሚያስገነዝብ ነበር። በተለይ የካቲት 12 ቀን 1933 ዓ.ም የወጣው "ፍርድና ሰላም ይገፍ ደርሻለሁ" በሚል ቃል የሚደመድም ነበር።[1]

ከንጉሠ ነገሥቱ ተልከው፣ ፊታውራሪ ብሩ ወልደገብርኤል የካቲት 17 ቀን 1933 ዓ.ም መሸንቲ ላይ ጦርነት አድርገው፣ በዚያ የነበረውን የጠላት ግምጃ ቤት ያዙ። ከዚያም በሜጫ፣ በሠርዶ አድርገው ባህር ዳር ገቡ። ጣልያን ሠርዶ መስክ እንደሠፈረ በፊታውራሪ ብሩ ወልደገብርኤል ሠራዊት ላይ መጋቢት 1933 ዓ.ም አደጋ ጣለ። ከፍተኛ ውጊያ ተካሄደ። በዚህ ወቅት በእንግሊዞች የተተኮሰ ቦምባርድ በጠላት አካባቢ የአሳት ቃጠሎ ስለአስነሣ፣ ጠላት ወደ መጣበት ተመለሰ።

አርበኛው በየደረሰበት ጣልያንን ይጠዘጥዘው ጀመር። ጣልያን ደግሞ የሚያዋጣውን እያጠና እንደየአካባቢው ሁኔታ ተገቢውን አደረገ። ትናንሽ ምሽጐችን እየለቀቀ ከትላልቆቹ ገባ። ከዚያም ከዋና፣ ከዋና ከተሞች ተሰበሰበ። የአርበኛው አገር የማስለቀቅ እርምጃ በዚያው መጠን

ተፋጠነ፣ የንጉሠ ነገሥቱም አመጣጥ ተቀላጠፈ። ጠላትም በአንዳንድ ቦታ አየተከማቸ ለመከላከል ሞከረ።

በባህር ዳርና በአካባቢው የነበረው ጣልያን፣ በአለው አቅም ተናንቆ የአርበኞችን ከበባ በመስበር ጐንደር ገባ። በምሥራቅ ጐጃም አካባቢ የነበረው ተሰብስቦ ደብረ ማርቆስን ላለማስነካት ሞከረ። ከተባለው ቦታ ላይ ጦርነት አካሄደ። ከሱዳን የመጣው የንጉሠ ነገሥቱ ጦር ከእንግሊዝ ነፃ አውጭ ጦር ጋር በመሆን፣ እንደዚሁም የጐጃም አርበኛ ከያለበት በመሰባሰብ፣ በአንድነት ጐን፣ ለጐን ሆኖ ተዋጋ፣ ድልም አደረገ።[15]

በጨረቃ ጦርነት ድል መሆናቸው በዚያ አካባቢ ለነበሩ ጣልያኖች ታላቅ ጭንቅ ፈጠረባቸው። ጀነራል ናዚ ከጐንደር በአይሮፕላን ገስግሶ ደብረ ማርቆስ ገባ። ነገር ግን ሌላ ጦር ሠርቶ መመከት አልሆነለትም። ዕቅዱ ከንቱ መሆኑን ሲረዳ፣ ጦሩንና የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ለራስ ኃይሉ ተክለ ሃይማኖት ትቶ፣ በመጣበት አይሮፕላን ወደ ጐንደር በረረ።[16]

ስለዚህ በምሥራቅ ጐጃም የነበረው የጣልያን ጦር ለንጉሠ ነገሥቱ ቦታ መልቀቅ ግድ ሆነበት። ከመማረክ ይልቅ ሀገሩን መልቀቁን መረጠ። ራስ ኃይሉ ተክለ ኃይማኖት፣ የደብረ ማርቆስን ከተማ እንዲጠብቅ አድርጐ ጣሊያን ወደ ሸዋና ወደ ወሎ ተጓዘ። በላይ ዘለቀ ከወሎ ወደ ጐጃም ለመሸገር የከጀለውን የጣልያን ጦር ለማገድ የሞከሩትን ያህል፣ ከጐጃም ወደ ወሎ የሚሸሸውን ጦር ለማቆም አልፈለጉም። ሀገር ጥሎ መሄዱ፣ ልበላይ ዘለቀ ጉዳይ ያለበት አልመሰላቸውም። ነገር ግን ዝም ብለው መልቀቃቸው ከጥፋት ተቆጥሮ በኮሎኔል /ጄነራል/ ዊንጌት በኩል ክስ እንዲመሠረትባቸው ለማድረግ ተሞከረ። ይህም በተከታታይ ለደረሰባቸው ግጭት ከርከርሻ (የነገር መነሳሻ) ሆነ።[17]

በጐጃም ከነበረው የጣልያን ጦር አብዛኛው ወደ ሸዋ ምድር ተሻገረ። አሁን የቀረው ደብረ ማርቆስን መያዝ ሆነ። በንጉሠ ነገሥቱ ድንጋጌ ውስጥ ምክር ተደረገ። ምክሩም ብዙም ሳያከራክር ለራስ ኃይሉ ተክለ ሃይማኖት መልዕክት እንዲላክና አሳቡ እንዲታወቅ ተቆረጠ። ወዲያው አዛዥ /ደጃዝማች/ ከበደ ተሰማ ተላኩ። አሳቸውም ራስ ኃይሉን አነጋግረውት "...እኔ የግርማዊነትዎ ቤት ጠባቂ ነኝና... ቤትዎን እንዲረከቡን" የሚል ቃልና አውቶሞቢሉን ከኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ጋር አድርጎ ላከ። በደጃዝማች /ራስ ቢትወደድ/ እንዳልካቸው መሪነት አሳሽ ተልኮ የሁኔታውን አስተማማኝነት ከአጠና በኋላ፣ ንጉሠ ነገሥቱ እሰቱን ገብተው በከተማይቱ አደባባይ ላይ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ተከሉ። በዚሁ ዕለት የእንግሊዝ ጦር፣ የኢትዮጵያን መናገሻ ከተማ አስለቅቆ አዲስ

አበባ መግባቱ ከምሽቱ በ3 ስዓት በንጉሠ ነገሥቱ፣ ለመኪንንቱ ተነግሮ ታላቅ ደስታ ሆነ።[18]

የኢትዮጵያ ነፃ አውጭ ጦር እየገፋ ሲመጣና ንጉሠ ነገሥቱ ከደብረ ማርቆስ ወደ መናገሻ ከተማዋ መግቢያቸው እየተቃረበ ሲሄድ፣ ፊታውራሪ ታምራት (የተባለ) ግበረ አበሮቹን ይዞ ጎንደር እና ጉጃምን እንዲያገናኝ በዓባይ ወንዝ ላይ ያሠሩትን ድልድይ ሠበረ። ሆኖም የድልድዩ አሠራር እጅ ጠንካራ ነበርና፣ ቢያስቸግረው ቅባ ኑግ እያስነጠረ፣ በላዩ እያፈሰሰ፣ ሲርስሰት በዶማ አስቆፈረው፣ በመራጃ አስደበደበው። በድልድዩ መካከል ታላቅ መናወጥ ሆነና የድልድዩ ቋሚ ሠረገላ ተሠበረ፣ ድልድዩ በከፊል ፈረሰ። ሊፈርስም ታምራትና ግብረ አበሮቹ ከታች፣ የድልድዩ ፍራሽ ከላይ ሆነው እየተምዘገዘጉ ከዓባይ ወንዝ ገብተው አለቁ።[19] ሕዝቡ፡- በታምራት ላይ ታምር ታየ በሚል ሁኔታውን ተረዳው።

ጠላት ከጉጃም ምድር ተባረረ፣ በሕዝብ ዘንድም ታላቅ ደስታ ሆነ። ሚያዝያ 13 ቀን 1933 ዓ.ም በደብረ ማርቆስ ከተማ ንጉሠ ነገሥቱ በተቀመጡበት አደባባይ ታላቅ ሠልፍ ተደረገ። መኪንንቱና አጨንፈው፣ የእንግሊዝ የጦር መኮንኖች ቦታ ቦታ ተሰጥቶአቸው በአደባባይ ተገኝተው ነበር። የጉጃም አርበኛ በየአስተባባሪዎቹ መሪነት እየተሰለፈ፣ 5 ዓመት ሙሉ የተጋደለበትን መሣሪያውን እያነገበ፣ በሽለላ፣ በቀረርቶ፣ በፉከራ በንጉሠ ነገሥቱ ፊት አለፈ። ዘግይቶ የደረሰውና ባለግርማው ሠራዊት የበላይ ዘለቀ ነበር። እሳቸው ራሳቸው ቁምጣ ሱሪ ለብሰው፣ አንገት ዝናራቸውን ታጥቀው፣ መውዜራቸውን ክትክሻቸው ላይ አድርገው ከሠራዊታቸው ማህል ነበሩ። እንደ ሥርዓቱ ፎክረው፣ እጅ ነስተው በአደባባዩ ከነበሩት መኪንንትና የጦር አለቆች ጋር ተቀላቀሉ። ሠራዊቱ እየፎከረ፣ እያቅራራ፣ እየሸለለ አለፈ። በላይ ዘለቀ ታላቅ ግርማ የተጐናፀፉት 133 ቢዘንት መትረየስ፣ 127 አልመን መትረየስ እንዲሁም ሙሉ ትጥቅ ያለው ሠራዊት ይዘው በመግባታቸው ነበር።[20]

ማጣቀሻ ፅሑፎች

1. ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፣ *ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ*፣ አንደኛ መፅሐፍ ገጽ 245።
2. ከበደ ተሰማ፣ *የታሪክ ማስታወሻ*፣ ገጽ 135።
3. አበራ ጀምበሬ፣ *አባ ኮስትር*፣ ገጽ 23-28 እና ገጽ 43።
4. ዘውገ ዘገየ፣ *አባ ኮስትር*፣ ገጽ 8-12።
5. አበራ ጀምበሬ፣ *አባ ኮስትር*፣ ገጽ 48።

6. ሞገስ ክፍሌ፣ *የሞሰሎኒ ምሥጢር*፣ ገጽ 143-146።
7. ገሪማ ታፈረ፣ *ጉንደሬ ቢጋሻው*፣ ገጽ 388-389።
8. ዘውገ ዘገየ፣ *አባ ኮስትር*፣ ገጽ 13።
9. ታደሰ ዘወልዴ፣ *ቀሪን ገረመው*፣ ገጽ 345-349።
10. ሙሉ ሰው ምትኩ፣ *ከሸዋ እስከ ሱዳን ጠረፍ*፣ ገጽ 38-48።
11. ታደሰ ዘወልዴ፣ *ቀሪን ገረመው*፣ ገጽ 360።
12. ገሪማ ታፈረ፣ *ጉንደሬ ቢጋሻው*፣ ገጽ 222-230።
13. ከበደ ተሰማ፣ *የታሪክ ማስታወሻ*፣ ገጽ 252-263።
14. ዘውገ ዘገየ፣ *አባ ኮስትር*፣ ገጽ 23።
15. ከበደ ተሰማ፣ *የታሪክ ማስታወሻ*፣ ገጽ 322-377።
16. መኮንን እንዳልካቸው፣ *መጽሐፍ የዓለምን ምሬት ማጣፈጫ ማር ነው*፣ ገጽ 353።
17. አበራ ጀምበሬ፣ *አባ ኮስትር*፣ ገጽ 189።
18. መኮንን እንዳልካቸው፣ ገጽ 353-354።
19. ገሪማ ታፈረ፣ *ጉንደሬ ቢጋሻው*፣ ገጽ 189።
20. ዘውገ ዘገየ፣ *አባ ኮስትር*፣ ገጽ 23።

ምዕራፍ ሠላሳ ሁለት
የወሎ ትግል

የልጅ ኢያሱ ምኒልክ ከአልጋ መውረድ ልባቸውን ከአቆሰለው አገሮች ዋናው ወሎ ነው። ከአላቸው ወገን ቆሞ በሸዋ፣ በጐራ፣ በሰገሌ፣ በወሎም መቅደላ ተዋግቶላቸዋል። ምንም የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሚስት፣ እቴጌ መነን አስፋው የልጅ ኢያሱ እህት፣ የወይዘሮ ሥሂን ሚካኤል ልጅ ቢሆኑ፣ ሰሜቱ አልበረደለትም። ብዙዎቹ መኳንንቶች በእሥራት በግዞት ላይ እንደቆዩ ነበሩ።

ወሎ የሰሜት ችግር እንደአለ፣ የጣልያን ወረራ ደረሰ። ጣልያን ብዙ የማባባል፣ የመሸንገል ሥራ አካሄደበት። ገንዘብና መሣሪያ እየሠጠ ከአሱ ጐን እንዲቆም ገ•ተገ•ተው። የደቡብ የኢትዮጵያ ጦር፣ በሳዩ ወደ ሰሜን ተንዘበት። ድል ሆኖ ሲመለስም፣ እንደዚሁ ተንዘበት። የጣልያን ጦር ደግሞ ደፍጥጦት በሳዩ ላይ ከሰሜን ወደ ደቡብ ወረደበት። ብዙዎች ከጠላት ወገን ቆሙ።

ምንም የልብ ቁስለት ቢኖርበት፣ ጦር ቢፈራረቅበት፣ የጠላትን አገዛዝ ወድዶ አሜን ብሎ አልተቀበለም። ጣልያንም በቦምብ ደበደበው፣ በአሳት ገሞራ ለበለበው እንጂ፣ ችግሩን አላየለትም። እንደ ወገን ቆጥሮ አልራራለትም። ከዚህ ሁሉ ችግር ጋር እየተናነቀ፣ ከጠላት ጋር ተጋድሎ ያዘ። ድርጅቱን ቀስ፣ በቀስ አጠናከረ።

ጥቅምት 12 ቀን 1929 ዓ.ም ጣልያን በተከዜ ወንዝ አካባቢ ያለውን አርበኛ ለመደምሰስ እያጥረመረመ መጣ። ከተከዜ ወንዝ ወደ ወሎ ወገን ያለውን ጠርዝ ያዘ። ከጉንደር ወገን የተንቀሳቀሰው፣ ከደጐማ ተነስቶ በበለሳ አድርጐ ሠፈረ። አርበኞች ከየአሉበት ተሰባስበው ቀጥ፣ ቀጥ እያሉ ከቆሙት የቂሊሣ ተራሮች ላይ ወጡ። የደመና ናሳጭ የሚመሰስል መርግ ከየአፋፉ ላይ ጠርዙን ብቅ እያደረጉ አጠመዱ። ብዙ ለመምሰል ሲመሸ በየቦታው እሳት አነደዱ። መሣሪያ ያለው መሣሪያውን ያዘ። መሣሪያ የሌለው ዱላውን፣ ጦሩን፣ ድንጋይና ወንጭፉን ይዞ ለውጊያ ተዘጋጀ። የጣልያን ጦርና አርበኛ ተፋጠጠ። ምንም ተራሮቻቸውን ጥግ ቢያደርጉ አርበኞች እጅግ ተሳትቀው ነበር። ሁለቱም ወገን ተብረክርክ ጦርነቱን የሚከፍት ጠፋ።

በዚህ ወቅት ባሳምባራስ ይግዛው አመራ የተባሉ ጀግና ተንደርድረው ከጣልያኑ ጦር ውስጥ በመግባት አንዱን ኢጣልያዊ ወታደር ያዙት። በትንቅንቁ ውስጥ አርበኛው ጣልያኑን በሽጉጥ መቱት፤ እሱም ጀሮአቸውን ነክሶ ያዘ። ሁለቱም ተያይዘው ሲወድቁ፣ ባሳምባራስ በሽጉጥ በመድገም ተገላገሉት። አርበኛው በየፊናው እየፈከረ ከጠላት መካከል ገባ። መርግና ናዳም ተላቀቁ። ብዙ ከተራኩቱ በኋላ፣ ድል የአርበኛው ሆነ። አምስት ታላላቅ አርበኞች ወደቁ፤ ከጣልያን ወገን ያለቀው ግን ይበዛ ነበር። ጣልያን ከያለበት እየካከመ ወደየመጣበት ተመለሰ። ድሉም የቂሊሣ ተራሮች ድል ተባለ።

በሳስታ የሚንቀሳቀሰውን አርበኛ ከሚያስተባብሩት መሪዎች አንዱ ደጃዝማች ወንድ በወሰን ኃይሉ ነበሩ። የራስ ካሣ ልጅ በመሆናቸው አገሩ አበረላቸው። እሳቸውም የተከዜን ወንዝ ይዘው ለብዙ ጊዜ ወዲያ ወዲህ ሳይሉ ተቀመጡ። ሁኔታቸው በግራዚያኒ የራሱን ትኩረት ስለሳበ ከነሐሴ 27 ቀን 1928 ዓ.ም(ስፕቴምበር 1 ቀን 1936 እ.ኤ.አ) ጀምሮ በእሳቸው ላይ ልዩ ክትትል እንዲደረግ የአካባቢውን ባለሥልጣኖች ይወተውት ጀመር። በዚህ ቀን በቁጥር 33 ያስተላለፈው ቴሌግራም "...ሳስታ... ብርቱ እንደመሆኑ መጠን... ሰው በሙሉ ያመጠ ነው። ስለዚህ...አገሩን በሙሉ በዘዴ መደምሰስ ያስፈልጋል።...ይልቁንም እንደ ዝናም በሰው ገላ ላይ የሚርከፈከፍ ጋዝ ተዘምቶ /ተመትቶ/ የተሞከረ አገር ስለሆነ ነው..." ይልና ስደጃዝማች ወንድ ወሰን ካሣ ደብዳቤ እንደፃፍላቸው፣ እሳቸው ግን እንዳልመጡ ይናገራል።

መስከረም 2 ቀን 1929 ዓ.ም (ሴፕቴምበር 12 ቀን 1936 እ.ኤ.አ) ባስተላለፈው ቴሌግራም ደግሞ፣ መስከረም 1 ቀን 1929 ዓ.ም፤ በዋዜማው መሆኑ ነው፤ ብልብላ በተባለው ቦታ የጣልያን ጦር ዘምቶ ብዙ አርበኞች ከነመሳሪያቸው ተማርከው በጥይት እንደ ተደበደቡ ያስረዳና፣ ደጃዝማች ወንድ በወሰን ካሣ ግን ከብልብላ ደቡብ፣ ስምንት ኪሎ ሜትር ያህል ርቀ ወደሚገኘው ወደ ነአስሎ ለአብ፣ ከዚያም ወደ ሳለበላ እንደሚያመሩ ይገልፃል። ከዚህም በስተቀር በዚሁ ቀን ለምክር ቤት፣ በቁጥር 15808 ባስተላለፈው ቴሌግራም፣ በማግስቱ ጥዋት፣ ማለትም መስከረም 3 ቀን 1929 ዓ.ም፤ በአሥመራ አይሮፕላን ማረፊያ ያሉት መጠባበቂያ አይሮፕላኖች ሁሉ የሳሊበላና የብልብላን ቀበሌዎች በኤፐሪት ጋዝ እንደሚመርዙት ይገልፃል።

ከብዙ ጉትጉታ በኋላ በወሎና በጉንደር የነበሩ የጣልያን ባለሥልጣኖች የግራዚያኒን ፈቃድ ለመፈፀም በደጃዝማች ወንድ በወሰን ኃይሉ ካሣ ላይ ተንቀሳቀሱ። በህዳር ወር 1929 ዓ.ም፣ ታድነው እንዲገደሉ የሚል ትዕዛዝ ከአማራ አገር ገዥ ወጣ። ከደብረ ታቦር በአንድ ኩሉኔል የሚመራ ጦር ወደ ተከዜ ዘመተ። ከበላሳ በአንድ መቶ አለቃ የሚመራ ሌላ ጦር፣ ከምዕራብ ወደ ምሥራቅ ተከዜን ተመልክቶ ዘመተ። የሰቆጣው ገዥ ከሰሜን ወደ ደቡብ በተከዜ ማዶ ተሰለፈ። ከወሎ፣ የጣልያን ጦር ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ ተሰልፎ፣ የተከዜን ወንዝ ከምንጩ ጀምሮ እየመረመረ ወረደ። ጭንቅ ሆነ።

የበጌምድር ሰው የደጃዝማች ወንድበወሰንን ነፍስ ለማዳን በሚችለው ሁሉ ሞከረ። ሕዝቡ ምሥጢር አመላለሳላቸው፤ መኳንንቱ የጠላትን ሹማምንት በምክር አላላተ። ወታደሩ የጣልያንን ክንድ አላላውስ ብሎ አጥብቆ ደበቃቸው፤ ምሥጢሩ እንዳይታወቅ አደረገላቸው። እሳቸው ወዴትም ሳይንቀሳቀሱ በተከዜ ወንዝ ውስጥ ተቀመጡ። የደብረ ታቦሩ፣ የበለሳውና የሰቆጣው የጣልያን ጦር ጥቂት ጊዜ ከአያቸውና አካባቢውን ከመረመረ በኋላ፣

ወደየቦታው ተመለሰ። ከወሎ የዘመተው ግን በየጊዜው እየተሰዋወጠ አደኑን ቀጠለ።

ከጊዜ ብዛት ረሃብ ከበደ፤ ከደጃዝማች ወንድወሰን ቃሬሮች አንዱ ምግብ ፍለጋ ወደ መንደር ሲሄድ፤ በባንዶች ተያዘ። ምሥጢሩን ለመጠበቅ የሚቻለውን ሁሉ አደረገ። የዚሁ አገር ሰው ነኝ አለ። ቤቱን እንዲያሳይ ተገድዶ ራቅ ወደ አለው ቤት ቢሄድ የሌላ ሰው ቤት ሆነበት። ሕዝቡ ቢጠየቅ፤ የሚያውቀው ሰው ታጣ። እንግዳ መሆኑ ስለታወቀ ወደ ጦር አዛዥ አቀረቡት። የጦር አዛዥ የነበረው ጣልያናዊ ሻምበል በሥቃይ እንዲመረመር ቢያደርግም፤ አልተበገረም። ወደ እሱ ወደ ራሱ አስቀርቦ አባበለው። ደጃዝማች የሚገኙበትን ቦታ ቢያሳይ ከፍ ያለ ሹመት፣ ገንዘብና ሽልማት እንደሚሰጠው እያደረገ ተሰማመጠው። ምሥጢሩን ካልነገረ ግን እንደማይሰቀው እየገለጸ አስፈራራው። ምንም ቢሆን ሰው ነውና፤ ሰውየው ተሸነፈ፤ ምሥጢሩን አወጣ።

የጣልያን ጦር ወደ ተጠቆመው ቦታ ፈጥኖ ሄደ። ከበባ አድርጎም ተኩስ ተከፈተ። ግራዝማች መሰሰ ሐማሴናይ እና አቶ ካሣ ወልደማርያም የተባሉት፤ በሁለት በር የተሰለፉት መትረየስ ተኳሾች ስለወደቁ፤ ሁለቱም በር ተከፈተ። የጨበጣ ውጊያ ተካሄደ። ደጃዝማች ወንድወሰን መሣሪያ በመለዋወጥ እየተታኮሱ በማሕል ገቡ። የተቻላቸውን ያህል የጠላት ወታደር አራገፈው ጥይት ሲያልቅባቸው፤ ቀጥ ብለው ቆሙ። በእጅ ቦምብ ብቻ የጨበጣ ውጊያ እንዲካሄድ አዘዙ። ከውጭ ዕርዳታ ሳይደርሰላቸው በመቅረቱ ሙሉ ቀን ተዋግተው ከምሽቱ አሥራ ሁለት ሰዓት ላይ ተማረኩ። መማረካቸው በጥሩንባ ተለፈፈ።

የጣልያን ወታደሮች ተማራኪውን ደጃዝማች ወንድወሰን (ኃይሉ) ካሣን፤ ከኢጣሊያው ጦር አዛዥ፤ ከሻምበል ዘንሉ አቀረቡአቸው። እሱም ወንበር አስመጣና አክብሮት በሚመስል አኳኋን ከወንበሩ ላይ አስቀመጣቸው። ዕድሜአቸውን ጠይቆ፤ ወዲያው ከወንበሩ ላይ እንደአሉ ከግንባራቸው ላይ በጥይት መትቶ ገደላቸው። ከዚያው ከወደቁበት ቦታ አፈርና ድንጋይ አስለብሶአቸው በፍጥነት ወደ ጦር ሠፈሩ ሄደ። ደጃዝማች ወንድወሰን በዚህ ዓይነት ታህሣሥ 1 ቀን 1929 ዓ.ም ሞቱ።

ግን ታሪካቸው በዚህ ብቻ አላበቃም። የአስከሬናቸው ውዝግብ ቀጠለ። ፎቶግራፍ ሳያነሳቸው በመቅረቱ ቅሬታ ስለተሰማው፤ በማግስቱ ጥዋት ወደ መቃብራቸው ሄዶ ከተቀበሩበት አስወጥቶ ፎቶግራፍ አንስቶአቸው ሄደ። በዚያ አካባቢ የነበሩት ሰዎች መልሰው ቀበሩአቸው። በሦስተኛ ቀን አሽከሮቻቸው ሬሣቸውን በሌሊት አውጥተው ከቅዱስ ሃርቤ ቤተክርስቲያን፤ ከመቅደሱ አግብተው በሰማዕትነት ደረጃ ቀበሩአቸው። የጦር አዛዡ ሻምበል ለሠራው የጀግንነት ሥራ የፎቶግራፍ ማስረጃ ብቻ በቂ እንደ ማይሆን ታወቀው፤ ከአለቆቹም ዘለፋ ደረሰበት። ራሳቸውን ለመቀረጥ ከመቃብራቸው

በኋላ፤ አስከሬናቸው ጠፋ። ሕዝቡን አስጨንቆ ያዘ፤ ሦላሳ ሠባት ሰው ገደለ። ስምንቱ ፊታውራሪዎች ነበሩ። በዚህ ዓይነት ምሥጢሩን አግኝቶ፤ ሬሳቸውን ለሦስተኛ ጊዜ አውጥቶ፤ ራሳቸውን ቆርጦ ወሰደ፤ በድናቸውን ከሜዳ ላይ ጥሎት ሄደ። ካህናቱም፦

ወሥጋሆሙኒ ለአግብርቲክ ለአራዊተ ገይም
ወከአው ደሞሙ ከመማይ አውዶ
ወኃጥኡ ዘይቀብሮሙ፣

በሚለው የዳዊት ምስባክ ፍትሐት አድርገው ለአራተኛ ጊዜ ተቀበሩ።

እዚህ ላይ ደጃዝማቹ ቦታ ሳይለውጡ ለምን ከአንድ ቦታ ተቀምጠው ጠላትን ጠበቁት? የሚለውን ጥያቄ ማንሳት ተገቢ ይሆናል። የላስታንና የበጌምድርን አገረ ገዥነት ሳላገኝ አልገባም ብለው ለእህታቸው ወረቀት ጽፈው ነበር ይባላል። ይህ እውነት ከሆነ፤ ከጣልያኖች ጋር የውስጥ ግንኙነት ነበራቸው ማለት ነው። ትንቅንቁም ሰሹመት እንጂ፤ ለሀገር ነፃነት አልነበረም ማለት ነው። ሆኖም እዚህ ላይ ክስማ በለው ግምት ያለፈ መናገር አይቻልም።

የጠላት ሀሳብ በዋግና በላስታ አካባቢ የክርሱን አርበኞች መደምሰስ ነበር። በዚሁ ሐሳብ መሠረት ከወሎ ጦር እንቀሳቀሰ። የወሎና የበጌምድር አርበኞች ተባብረው ጥቅምት 12 ቀን 1930 ዓ.ም ወገል ጤና ወግተው፤ አሸንፈው፤ ወደ መጣበት ወደ የጁ መለሱት። አርበኛው ኃይሉን አያሰባሰበ፤ እየተጠናከረ ሄደ። በዚያ አካባቢ ብቸኛ አስተባባሪ ሆነው የቆሙት ደጃዝማች ኃይሉ ከበደ ነበሩ። የዋግሹም ከበደ ልጅ በመሆናቸው ሕዝብ አበረሳቸው። አሳቸውም ሰቆጣን ከጣልያን አስለቅቀው ለመያዝ አለቡ። የሰቆጣ መለቀቅ በዚያ አካባቢ ለነበረው አርበኛ ማዕከል ሆኖ ጦርነቱን ለማስፋፋት የሚረዳ ነበር። ስለዚህ በሐሳቡ ሰው ተባበረ።

ሰቆጣን የማጥቃቱ ሥራ በጥቅምት 1930 ዓ.ም ተካሄደ። አርበኛው በብርታትና በብዛት አጠቃ። የጣሳትም ጦር መሸነፍ፤ አልቂት መሆኑን ስለተረዳ በአለው አቅም ሁሉ ተከላከለ። ጦርነቱ ተፋፍሞ ሲካሄድ፤ ደጃዝማች ኃይሉ ከበደ ከጠላት በተተኮሰ ጥይት ተመትተው ሞቱ። አርበኞች አስከሬናቸውን ማጻን ሳይቻላቸው ቀርቶ፤ በጠላት እጅ ወደቀ። ጣልያንም ራሳቸውን ቆርጦ ከአገር አገር እያዞረ ጊጤ ተጫወተበት። አስከሬናቸውን በሽምግልና ዕድሜ ላይ ለነበሩት ለአባታቸው ለዋግሹም ከበደ አቀረበላቸው። ዋግሹም ከበደ የልጃቸውን አስከሬን ተረክበው "ለመሆኑ ስንታችሁን ገድሎ ሞተ?" ብለው ጠየቁ። ጠላትም ሳይግደረደር፦ "ሺህ" ብሎ መለሰላቸው።[1] የደጃዝማች ኃይሉ ከበደ መሞት፣ ትግሉን አልገታውም። አሽከሮቻቸውና ባለቤታቸው ወደ ቤገምድር ተሻግረው ትግላቸውን ቀጠሉ። ልጃቸው፣ ልጅ ወሰን ኃይሉ በአግራቸው ተተኩ። እሳቸውንም ሕዝብ ተክተላቸው።

በበላይ ዘለቀ የሚመራው የጦጃም አርበኛ፣ በአንድ ወቅት ዓባይን ተሻግሮ፣ ወሎ ግዛት ልዩ ስሙ ዛሞድ ጫቀታ የነበረውን የጣልያን ጦር አጥቅቶ ነበር። በዛ የጠላትን ጦር ሠፈር በቦምብ አቃጥሎ፣ ጦሩን ደምስሶ፣ ሦስት የውሃ መትረየስ ከአንድ ሺህ ጠመንጃ ጋር ማርኮ ወደ ሠፈሩ ወደ በከና ተመልሷል።

ጥር 13 ቀን 1930 ዓ.ም ደግሞ ጓሜዳ ላይ ጦርነት ተደረገ። የጦርነቱ ዓላማ ማይንት፣ እጅበር ላይ የነበረውን የጠላት ጦር በማባረር አካባቢውን በአርበኛው ቁጥጥር ሥር ለማስገባት ነበር። በጦርነቱ በቀኛዝማች /ደጃዝማች/ መንግሥቱ ጉሹ የሚመራ አርበኛ ከበጌምድር ተሻግሮ ተካፋይ ሆኖ ነበር። ፎክሮ በመምጣት የገጠመውን የጠላት ጦር አርበኛው አሸንፎ፣ ብዙ ወታደር ፈጅቶ አባረረው። ሰባ አምስት ምንሽር ጠመንጃ ተማረከ። ከአርበኞችም ወገን ሰባት ጀግኖች ወደቁ። ስሁሰተኛ ጊዜ ወደዚሁ ቦታ በመነቃነቅ ግንቦት 2 ቀን 1930 ዓ.ም ሌላ አደጋ ጫቀታ በተባለው ምሽግ ላይ ጣለ። ብዙ የጠላት ወታደር ፈጅቶ፣ ሰባት መትረየስና ሦስት መቶ ጠመንጃ ከ50 ሺህ ጥይት ጋር ማርኮ፣ ምንም ጉዳት ሳይደርስበት ወደ ጦር ሠፈሩ ተመለሰ።[2] እነዚህ ሁለት ጦርነቶች የተሳኩት የአካባቢው የወሎ ሕዝብ ስለተባበረ መሆኑ ሊገለጽ ይገባል።

አርበኞች ላስታ፣ አብጣ የነበረውን የጠላት ምሽግ ሰብሮ ለማጥቃት ከየነበሩበት ተንቀሳቅሰው ሰኔ 8 ቀን 1930 ዓ.ም ምሽጉን አጠቁ። ጠላትም ጦሩን ከምሽጉ አስወጥቶ ከሜዳ ላይ ገጠማቸው። አርበኞች በኃይል ስለወጉት መሸሽ ግድ ሆነበት። ወደ ምሽጉ ለመግባት ሲፍገመገም አርበኞቹ ተቀላቅለው የጨበጣ ውጊያ በማካሄድ ከምሽጉ ተደባልቀው ገቡ። ከገቡም በኋላ ጠላትን አጥቅተው ወታደሩን በመፍጀትና በመማረክ ምሽጉን ያዙ። ብዙ ኢጣልያኖች ሞቱ። የተረፉትም ተማርከው፣ ከአርበኛው ጠቅላላ ጉባዔ ቀርበው፣ በፍርድ ተገደሉ። ሽምባሽ ዘለቀ የተባለው ባንዳ ግን በልዩ የርህራሄ አስተያየት ተሰቀቀ። ብዙ የጦር መሣሪያ ተማረከ። አሥራ አራት አርበኞች ሞቱ፣ ሌሎች አራት ቆሰሉ።

ጣልያን በሰሣን በማጥፋት እሥረኞችን የሚያሰቅቅ ጦር ባንቀሳቀሰ ጊዜ፣ በዋግና በላስታ የነበረውም ጦር እንዲረዳ ታዘዘ። በዚህ ትዕዛዝ የተንቀሳቀሰውን የጠላት ጦር የዋግ፣ የላስታና የሰቆጣ አርበኞች ከቃሊሣ እና ከቆላ መልዛ ከመጡ ወንድሞቻቸው ጋር በመተባበር፣ በሊፍላ በርና በአዘይ በር፣ በግንቦት ወር 1931 ዓ.ም ወግተው መለሱት። መሸጉ የተቀመጠውን የጠላት ጦር የዋግና የላስታ አርበኞች በግንቦት ወር 1931 ዓ.ም ወግተው ምሽጉን አስለቅቀዋል፤ ብዙ በመማደልም የጦር መሣሪያ ማርከዋል። በዚህ ጦርነት የቋሊሣ፣ የቆላ መልዛና የመና አርበኞች እንደረዱ በታሪክ ተመዝግቦአል።

ደጃዝማች ኃይሉ ከበደን በመግደሉ፣ ጭንቅላታቸውን ቆርጦ ለሀገር በማሳየቱ፣ ሀገሩን አስደንግጦ ጭጭ ያሰኘለት መስሎት ነበር። ነገር ግን የልጅ ወሰን ኃይሉ በእግራቸው መተካት አሰጋው። ቀስ በቀስ የአርበኞች መጠናከርም እያየለ ሄደ። ስለዚህ ሕዝቡን ለማረጋጋት ግንቦት 13 ቀን 1931 ዓ.ም አዋጅ አወጣ። የአዋጁን ሁኔታ በቅርበት መመርመር ደግ ነው።

አዋጁ የወጣው ከጉንደር ከተማ ሲሆን፣ የአማራው አገር ማዕከል፣ አድራሻው በተሰይ ለላስታና ለዋግ ሕዝብ ነበር። የተፈረመው በጀነራል ፍሩሽ የአማራ አገረ ገዥ ነበር። ቃሉም። "የኢጣልያ መንግሥት... የናንተን አገር ሕዝብ በብርቱ ከመቅጣት ደረሰ..." ይልና ያለፈውን ይተርካል። ከዚያም በማያያዝ "...ከቅጣት ያመለጡት ሰዎች ከቅጣት እንድትወጡ ያነሷሷችኋል። ...አንዳንድ መንደሮች ከተክዜ ያሉ ሲዋጉ ለተነሱት ሽፍቶች አገዙ..." እያለ የወቅቱን ሁኔታ ይዘረዝራል። ከዚያም በመቀጠል "...የኢጣልያ መንግሥት የሚገዛችሁ ሲጠቅማችሁ ነው እንጂ ሲጐዳችሁ አይደለም። ...እኔ ዕለት ዕለት የምሠራው...ሰላምና መልካም አኗኗር ለማምጣት ነው..." እያለ ይሸነግላል። ከዚያም ያ መልካም ሥራና ጥሩ ሥልት በጣልያን መሣሪያና ኃይል ተጠብቆ እንደሚኖር እያስረዳ ከፍተኛ ዛቻ ይዝታል። ነገር ግን አዋጁ የላስታና የዋግን አርበኞች አልበገራቸውም።

በአባታቸው በደጃዝማች ኃይሉ ከበደ እግር የተተኩት ልጅ ወሰን ኃይሉ እየተጠናከሩ ሄዱ። ሕዝብም አበረላቸው። ከላስታም አልፈው ከበጌምድር ጋር የነበራቸውን ግንኙነት ለማጠናከር ፈለጉ። ደጃዝማች ነጋሽ ወርቅነህ - እንዲያገኙአቸው አደረጉ። ሁለቱም የአርበኛ አስተባባሪዎች ሠራዊታቸውን ይዘው መሸሓ ከተባለው ቦታ ላይ ነሐሴ 20 ቀን 1931 ዓ.ም ተገናኙ። የሁለቱ መሪዎች መገናኘትና መመካከር በየሠራዊታቸው መካካል አዲስ ስሜት ፈጠረ። "...አንከዳም፣ ለሀገራችን ነፃነት እንሞታለን..." እያለ አንድ፣ በአንድ ከመሪዎቹ ፊት እየቀረበ መስቀል እየመታ ማለ። አርበኛው አንድ ልብ ሆነ።

ይህ ሁኔታ ጠላትን ስላሰጋው፣ በእንጭጩ ለመቅጨት ሞከረ። ብዙ ባንዳ ቆጥሮ፣ በወስከንቢት አካባቢ ያለውን ገበሬ አስከትሎ፣ ታላቅ ጦር ሠርቶ መጣ። አርበኞችም ከያሉበት ተሰብስበው መሸሓ፣ አይጠጠር ከተባለው ቦታ ነሐሴ 19 ቀን 1931 ዓ.ም ግንባር ለግንባር ገጠሙትና ከባድ ውጊያ ተካሄደ። ፊታውራሪ ደምስ የተባለው ቀንደኛ ባንዳ ከ41 ግብረ አበሮቹ፣ ከነመሣሪያቸው ተማረኩ። ልጅ ወሰንም ምርኮአቸውን ይዘው ወደ ጦር ሠፈራቸው፣ ወደ ቋሊሣ ተመለሱ።

ፊታውራሪ ኃይሉ ክብረት የደጃዝማች ኃይሉ ከበደ የቅርብ ወዳጅ ሲሆኑ፣ በማይጨው ጦርነት ደርሰባቸው የነበረው ቁስል እንደ ጠገገላቸው የጦር አዛዥ ለመሆን ቻሉ። ፊታውራሪ ኃይሉ እስከ ካርቱም ድረስ እየሄዱ መልዕክት ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ያቅተሳልፉ ነበር። ከዚህም በስተቀር የንጉሠ

ንጉሡን ፎቶግራፍ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ጠቅልለው ይዘው እንደኖሩ ይነገርላቸዋል።[3]

ሁኔታዎች በዚህ ዓይነት በመልካም ሁኔታ በመካሄድ ላይ እንደአሉ፣ መሸሐ ላይ የተደረገው ስምምነት እየሳለ ሄደ። ውሎ አድሮም በልጅ ወሰን ኃይሉና በደጃዝማች ነጋሽ ወርቅነህ መካከል መቃቃር ደረሰና ግንኙታቸው ተቋረጠ። ሁለቱም እየትውልዳቸው ተመለከቱ። ደጃዝማች ነጋሽ ወደ ሀገር ነፃነት ተመለከቱ፣ ልጅ ወሰን ሥልጣንን፣ የበላይነትን ተመኙ። ሰሰሜን አርበኞች የበላይ ለመሆን ከጀሉ።

ጥር 8 ቀን 1932 ዓ.ም ከልጅ ወሰን፣ ለደጃዝማች ነጋሽ ወርቅነህ አንድ ደብዳቤ ተፃፈ። የዚህ ደብዳቤ መዘዝ ከፍተኛ ስለሆነ፣ ይዘቱን ቀረብ ብሎ መመርመር ይጠቅማል። ወረቀቱ ማዕረግ ሳይጠቅስ ይድረስ ለዳግማዊ ነጋሽ ወርቅነህ ብሎ ይጀምራል። ሰላምታ የለበትም። ከፊታውራሪ ካሣ ነአኩቶ ጋር ስለተደረገው ግጭት ማዘናቸውን ይገልጽና፣ አሉባልታ ገብቶበታል ማለት ነው፣ "...በየዳ መኖቼ ልቀመጥ ነኝና ሣቢ ላይ ቤት አሠርተው የፎጋይን አበል አስገብተው እንዲቆዩኝ" ይልና፣ የቆላው የብረት አለቅነት በፊታውራሪ ካሣ ነአኩቶ ሆኖ እየታዘዘ እንዲቆይ የሚል ነበር።

ደጃዝማች ነጋሽ ወርቅነህ ይህ ወረቀት ሲደርሳቸው ጥር 10 ቀን 1932 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ መልስ ሰጡ። እሱንም በቅርበት ማየት የነገሩን ሁኔታ ለመገንዘብ ይረዳል። ደብዳቤው "ለበኩር ልጅ ወሰን" ብሎ ይጀምራል። ቢመጡ ደስ እንደሚላቸው ይገልጽና፣ ስለካሣ ነአኩቶ ሹመትና ስለ ቤቱ ሥራ የተሰማቸውን ቅሬታ ይገልፃል። የልጅ ወሰንን ሐሳብ አለመቀበላቸውን ያስረዳል። ምክንያቱንም ሲያብራራ "...እርስዎ በዋግ እኔ በስሜን ሆነን እየተረዳዳን ጠላትን ልንወጋ የተማማልነው ቀርቶ አዲስ ነገር በመፈጠሩ ነው..." ይላል።

ወዲያው ልጅ ወሰን በየዳ ተሻግረው ጥር 17 ቀን 1933 ዓ.ም ከደጃዝማች ነጋሽ ጋር ጦርነት ገጠሙ። ከቀኑ ስድስት ሰዓት እስከ ሌሊቱ ሦስት ሰዓት ቡበርቱ ተዋግተው ተሸነፉ። በሽማግሌ ብርታት በር ተለቆላቸው ከሞት፣ ከመቁሰልና ከምርኮ የተረፉ ሰዎቻቸውን ይዘው ሣህላ ወደ ተባለው ቦታ ሄዱ። ከሁለቱም ወገን ብዙ ሰው ወደቀ። ደጃዝማች ነጋሽ አሥራ ስምንት ሰው ቢሞትባቸውም፣ ድልና ብዙ ምርኮ አገኙ።[4]

የወገንን ኃይል የሚቀንስ፣ ክብሩን የሚያጐድፍ፣ የጠላትን ልብ የሚያደነድን፣ ወገንን የሚያሳዝንና መጥፎ የሆነ ሥራ ተሠራ። በዚህ ሥራ በታሪክ ፊት ተጠያቂ የሚሆኑት ልጅ ወሰን ኃይሉ ናቸው። አወዳደቃቸውም በከፊል ከዚሁ ግጭት በመነጨ ቅሬታ፣ ጠላት ባጠቃቸው ጊዜ ከስሜን አርበኞች ዕርዳታ ባለማግኘታቸው ሳይሆን አልቀረም። በዚህ ዝብርቅርቅ ውስጥ ለሀገር የመከላከል ሥራ ቀዘቀዘ። ልጅ ወሰን ኃይሉ በሚጽፉአቸው

ደብዳቤዎች ላይ "...የአርበኞች ጦር መሪ፣ ለነፃነቱ ተከራካሪ" እያሉ ይፈርሙበት የነበረው መፈክር፣ ከዳር ሳይደርስ ቀረ።

ሁኔታዎች በእንዲህ እያለ የንጉሠ ነገሥቱ መምጣት አየተሰማ ሄደ። በወሎ በኩል የሚሠራው ሥራ የሚያሳዝን መሆኑ ንጉሠ ነገሥቱ ይገነዘቡ ጀመር። የደጃዝማች ዮሐንስ ኢያሱ ምኒልክ ወደ ወሎ ለመሻገር መከጀል ደግሞ ሌላ ችግር ስለሆነ፣ ከንጉሠ ነገሥቱ ለአዛዥ /ደጃዝማች/ ከበደ ተሰማ ሀዳር 28 ቀን 1933 ዓ.ም መመሪያ ተሰጠ። መመሪያውም፡- "...ደጃዝማች መንገሻ አበያ...የተገኘውን ያህል መሣሪያ ተቀብሎ በቶሎ እንዲሄድ /ወደ ወሎ/ ...ዮሐንስ ወደ ወሎ ለመሄድ አስቀድሞ ወደ እኛ መጥቶ እንዲነጋገር..." የሚል ነበር። የካቲት 12 ቀን በዓፋት በሌላ ደብዳቤ ደግሞ ወደ ጐጃም እንዲመጣ እንደፃፉለት ገልፀዋል።[5]

የወሎ አርበኛ ይህንን ድጋፍ ሲያገኝ ስለተበራታ፣ ጠላትን ከየምሽጉ እያስወጣ አባረረው። በወሎ ከነበረው የጣልያን ጦር ጥቂቱ ወደ ጐንደር ሲሻገር የበዛው ወደ ደሴ፣ ወልድያ፣ ኮረም እየተጠቃለለ ወደ ሰሜን ገሠገሠ። ከጐጃም ወደ ሽዋ ከመጣው ደግሞ አንዱ ክፍል በለላሴና በመርሐ ቤቴ አድርጐ ደሴ በመግባት ተጠቃለለ። ጉዞውን ጀመረ።

ይህ አንደታወቀ ከምሥራቅ በሐረርጌ በኩል አዲስ አበባ ከገባው የእንግሊዝ ጦር አንዱ ክፍል አዲስ አበባ ሲጠብቅ፣ ሌላው ክፍል ወደ ሰሜን የወጣውን ጣልያንን እያባረረ ገሠገሠ። ደሴን አለለቀቀ። ከዚያም ዋናውን መንገድ ተከትሎ ወደ ትግራይ ውጣ። የወሎ አርበኛ ጠላቱን ከየተደበቀበት ጉጥ፣ ከየመሸገበት ምሽግ እያስወጣ በተንቃ፣ በደላንታ፣ በዋድላ፣ በሣይንት የነበረውን ጠላት በማባረር ጣልያንን ከማህሉ አገር ሰማስወጣት በተደረገው ትግል ዋና ሚና ተጫወተ።

ማጣቀሻ ፅሑፎች

1. Richard Greenfield, *Ethiopia a New Political History*, p.244
2. ዘውገ ዘገየ፣ *አባ ክስተር* ገጽ 14።
3. Greenfield, pp.185-244.
4. ገሪማ ታፈረ፣ *ጐንደሬ በጋሻው*፣ ገጽ 158-195 እና 215።
5. ከበደ ተሰማ፣ *የታሪክ ማስታወሻ*፣ ገጽ 325 እና ገጽ 372።

ምዕራፍ ሠላሳ ሶስት
የትግራይ ተጋድሎ

በ1928 ዓ.ም ጦርነቱ የተከፈተው ትግራይ ላይ ነው። በዚህ የተነሣ የጦርነቱ የመጀመሪያው ገፈት ቀማሽ እሱ ሆነ። የማሒል አገሩ ጦር በግሥጋሴ ቢዘምትም ለጥቃት አልደረሰለትም። በአድዋ፣ በሐውዜን፣ በመቀሌ፣ በጉንዲ ተራራ /ዋንቲ ጉንዲ/ ብቻውን ተዋጋ። የማሒል አገር ከደረሰለትም በኋላ በተንቤን፣ በሽሬ፣ በአምባራደም፣ በዓቢይ አዲ፣ በሰለክለካ፣ በአፍጋጋ፣ በደብረ ነጋድያን፣ በዛበን ቀርከሀታና በሌሎችም ብዙ ቦታዎች ከንጉሠ ነገሥቱ ጦር ጋር ቆሞ ደጋግሞ ተዋጋ። በማይጨው የጦር ሚዳም እንደዚሁ ድርሻውን ተወጣ።

ጠላት ከሌሎቹ ክፍላተ ሀገር ሁሉ አስቀድሞ የገባበትና በየቦታው የተጥለቀለቀበት ሀገር ትግራይ በመሆኑ የተነሣ፣ ጦርነቱ ያደረሰበት ጉዳት ከሁሉም የከፋ ነበር። የሰዉ አልቂት ከፍተኛ ነው፣ የሀብቱ ውድመት፣ አይነገርም። በዚህ ላይ ደግሞ የጠላት ስብከት እንዳንዶችን አታልሎ ነበር። የደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሣ መክዳትም ልብ የሚፈትን ነበር።

ቢሆንም የትግራይ ሕዝብ በቃኝ ብሎ ከትግሉ ጉራ አልወጣም፣ ጦርነቱን ቀጠለ። የትግራይ ሠራዊት ከማይጨው ሽንፈት በኋላ ወደ ማሒል አገር ከሚገዘው የኢትዮጵያ ጦር ጋር አብሮ ተጓዘ። ቦታ መርጠን፣ ጊዜ ለውጠን ደግመን እንዋጋለን የሚለውን ሐሳብ በማመን ቆይቶ፣ ላስታ ሲደረስ መከረ። በምክሩም ሀገራችንን ጥለን ወዴት እንሄዳለን አለ። ስለዚህም ተመልሶ በሀገሩ ላይ ሆኖ ለመከራከር ወሰነ። ሠራዊቱ ራስ ሥዩምን መሪ አድርጉ ወደ ሀገሩ ተመለሰ። ሙጃ ከሚባለው ቦታ ተነስቶ በላስታ አድርጉ ዘለምት ገባ። ጣልያን በሌሎች የአርበኞች መሪዎች ባደረገው ዓይነት በራስ /ልዑል ራስ/ ሥዩም መንገሻም ላይ ተፅዕኖ አሳደረ። ከአልገቡለት ሕዝቡን እንደሚፈጅ፣ ሀገሩን እንደሚያጠፋ ዛተ። ከገቡ ግን አሳቸውን በክብር እንደሚያስተዳድራቸው፣ ሕይወታቸውንም እንደማይነካ ቃል ገባ። በአርበኛው ዘንድ ምክር ተደረገ። በምክሩ ላይ ደጃዝማች ገብረ መድህን ዘርአ፣ ደጃዝማች ዓባይ ካሣ፣ ደጃዝማች ኃይለሥላሴ ገብረመድህን አንደም ከነሠራዊታቸው ተካፋይ ነበሩ።

እኩሉ እንግባ ሲል፣ ከፊሉ አይደረግም አለ። ክርክሩም እየጠነከረ ሲሄድ ራስ /ልዑል ራስ/ ወደ ጣልያን መግባትን የመደገፍ አዝማሚያ አሳዩ። በዚህ የተናደዱት ደጃዝማች ዓባይ ካሣ "የዮሐንስን ዘውድ ለቅቀው እንደምን ለጣልያን ይገባሉ" ብለው ተቆጡ። አሳቸው ግን በበኩላቸው አርበኝነት ቀጠሉ። ደጃዝማች ገብረ መድህን ዘራኡ አርባ ዓመት የገዛሁትን አገር ለጣልያን አልለቅም በማለት ቃላቸውን ጠብቀው በአርበኝነት ከጠላት ጋር ሲዋጉ ቆይተው፣ መርሐ ቤቴ፣ ሽዋ ሞቱ። በምክሩ ግን ሁሉም እንደፍላጐቱ እንዲያደርግ ተወስኖ በሰላም ሠራዊቱ ተለያየ።

ራስ /ልዑል ራስ/ ሥዩም ለጣልያን ህዳር 7 ቀን 1929 ዓ.ም ገቡ። ጣልያን በክብር ተቀብሎ ቃሉን በመጠበቅ ወደ አዲስ አበባ አመጣው። ከራስ ኃይሉ ቀጥሎ ባለሞዋል አደረገው።

ደጃዝማች ከበደ ካሣ፣ አቶ/ደጃዝማች/ ገብረ ሕይወት መሸሻ አርበኝነታቸውን ቀጠሉ። በየካቲት ወር 1929 ዓ.ም ራማ ላይ አደጋ ጥለው በጠላት ላይ ከፍተኛ ጉዳት አደረሱ።[1] በአቶ /ደጃዝማች/ ገብረ ሕይወት መሸሻ የሚመራው አርበኛ ከማይጨው ጦር ሜዳ በሰሪንጋ፣ በሣምሬ፣ በአበርገሌ አድርጉ ተከዜ ወንዝ ገባ። ከዚያም የተከዜ ወንዝን ተሻግሮ ፀለምት ወደተባለው አገር ገባ። ጥቂት እረፍት ከአደረገ በኋላ፣ ድማም ሚራ ከተባለው ቦታ ትግሉን ጀመረ። ከዚያም የወረኢሉ፣ የአሰቦና የተከዜ ወንዞች ከሚገናኙበት ቦታ የጠላትን ጦር ግንባር ለግንባር ገጥሞ መልካም ውጤት አገኘ።

በፊታውራሪ /ደጃዝማች/ ዓባይ ካሣ የሚመራው ጦር ከማይጨው ሽንፈት በኋላ በላስታ አድርጉ ወደጠለምት ሄደ። ከዚያም ተከዜን ተሻግሮ በተንቤን አውራጃ ወደ አበርገሌ ሄደ። መንገዱን ዘግቶ በመያዝ አላስገባም ያለውን የጠላት ጦር፣ የግራ ክንፉን በመስበር ወደ አምራ አመራ። ከዚያም ወርኤ ሽለቆ ገብቶ በየቦታው በመዘዋወር ጠላትን ማጥቃቱን ቀጠለ። በሰኔ ወር 1928 ዓ.ም በአድዋ አውራጃ ጉምቱ ከተባለው ቀብሌ በደረሰ የጠላት ጦር ላይ፣ ከየአቅጣጫው ተኩስ በመክፈት ጉዳት አደረሰ። በህዳር 12 ቀን 1929 ዓ.ም በክብረ በዓል ላይ አርበኞችን ለማጥቃት ጠላት በአንዳባገሪማ ደብርና በአንዳማርያም ሸዊቶ በኩል መጣ። አርበኛው ሁኔታውን ቀደም ብሎ በመረዳት በዓዲ ጭዋ በኩል የተኩስ ቅብብሎሽ እያደረገ፣ ከቦታ ወደ ቦታ በመፈናጠር በዓሉን ለማክበር ከመጣው ሕዝብ ነጥሎ አምባ ሰማዕታ ከተባለው ጫካማ ተረተር ጉትቶ አስገባው። ከዚያ በኋላ በተካሄደው ጦርነት ከጠላት ወገን ብዙ ሰዎች ተገደሉ፣ ሌሎች ብዙዎች ቆሰሉ። በጥር ወር 1932 ዓ.ም ደግሞ ይኸው የአርበኞች ቡድን ከአድዋ ወደ ተንቤን ሲጓዝ፣ ፍላፍል በሚባል ሽለቆ ውስጥ፣ እንዲሁም በሐምሌ ወር ደግሞ ወርኢ ድልድይ ላይ አድፍጦ በመጠበቅ ጥንቃቄና ፍጥነት በተመላበት አሠራር አደጋ በመጣል በጠላት ላይ ብዙ ጉዳት አደረሰ።

አምባላጌ ተራራ ላይ ወጥቶ የመሸገው ጦር የሚመራው በጣልያን ምሥራቅ አፍሪካ ገዥ በዱክ ደ አምስታ፣ እንደሁም በኤርትራና በትግራይ ገዥ በጀነራል ፍሩስኪ ነበር። የኢትዮጵያ ጦር የሚመራው በራስ /ልዑል/ ሥዩም ነበር። በምክትል አዛዥ በፊታውራሪ /ደጃዝማች/ ዓባይ ካሣ የሚመራው አርበኛ ወደ ተራራው ለመጠጋት አደባ አምባ ሲደርስ፣ የጠላት ጦር ተኩስ ከፈተበት፣ በመድፍ እያሸጋገረ ደበደበው። በግንባር በመጋፈጥ ፈንታ ከለላ በመያዝ እስኪመሽ ጠብቆ በጭለማ ሽፋን ግንባሩን በማስፋት ወደ

አፀላ ገንዝ ገባ። ከዚያም እንዳ ቂርቆስን በተረተሩ እየተሳበ ተጠግቶ፣ ሚያዝያ 10 ቀን 1933 ዓ.ም ተኩስ ከፈተ።

የአምባላጌ ጦርነት ከባድ ሆነ። ለኢጣልያኖች በ1933 ዓ.ም ይህንን ተራራ መልቀቅ በ1928 ዓ.ም የመያዙን ያህል ቀላል አልነበረም። ከማለቅ ወይም ከመማረክ በስተቀር ሌላ ሦስተኛ ምርጫ አልነበራቸውም። ስለዚህ የቻሉትን ያህል በርትተው ተዋጉ። ውጊያው እየተፋፋመ ሄደ። የእንግሊዝ ወታደር ከአዲስ አበባና ከአሥመራ ተጓጉዞ ደረሰ። ከሽዋ በእግሩ ከተጓዘው አርበኛ ከፊሉ ዱክ ደ አምስታን እያባረረ ወደ ጉንደር ሲሻገር፣ ከፊሉ አምባላጌ ወጣ። ጦርነቱ እስከ ሚያዝያ 30 ቀን 1933 ዓ.ም ላያቋርጥ ቀንና ሌሊት ተካሄደ። የኢትዮጵያ ሠራዊት በልዑል ራስ ሥዩም መሪነት በብርታት ተዋጋ። ረሃቡንና ውሃ ጥሙን፣ ብርዱን ከቁም ነገር አልቆጠረውም። ዓላማው ዱክ ደ አምስታን መማረክና አምባለጌን መያዝ ብቻ ነበር።

ግንቦት 1 ቀን 1933 ዓ.ም በእንግሊዞችና በጣልያኖች መካከል ንግግር ተካሄደ። ድርድሩ ጣልያኖች ከነመሣሪያቸው ለእንግሊዝ እጅ ሊሰጡ ሆነ። ይህ በምሥጢር የተደረገው ስምምነት በአርበኞች ዘንድ ሊሰማ ቁጣ አስነሳ። ጦርነቱ ቀጥሎ የጣልያኑ ጀነራል ከእነተከታዮቹ ተገደለ። ጦርነቱ አልበርድ ስላለ የእንግሊዙ የጦር አዛዥ ራስ /ልዑል/ ሥዩምን ማነጋገር ግድ ሆነበት። ለለውጊያውና ለለምርኮው ከፊታውራሪ /ደጃዝማች/ ዓባይ ካሣ ጋር እንዲነጋገር ከስምምነት ተደረገ። የኢትዮጵያ የአርበኞች አለቆችና የእንግሊዝ የጦር መኮንኖች ተነጋግረው ጣልያኖች እጃቸውን ሰጥተው ለጥበቃ ወደ እንግሊዞች እንዲተላለፉ፣ መኪናዎችንና መድፎችን እንግሊዞች እንዲረከቡ፣ መትረየስና ቀላል የጣር መሣሪያ የመሳሰለው ግን በማራኪዎች፣ በኢትዮጵያውያን እጅ እንዲሆን ከስምምነት ላይ ተደረሰ። ውጊያው በዚህ ስምምነት መሠረት ቆሞ ዱክ ደ አምስታና ጀነራል ፍሩስኪ እጃቸውን ሰጥተው የአምባላጌ ውጊያ ከፍፃሜ ደረሰ።[2] ጣልያን ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛት የመያዝዋ ዕቅድ በዚሁ ፉርሽ ሆነ።

<u>ማጣቀሻ ፅሑፎች</u>

1. ከጀነራል ቃለክርስቶስ አባይ የተገኘ።
2. የደጃዝማች ዓባይ ካሣ የሕይወት ታሪክ፣ የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች ማህበር ጽህፈት ቤት።

ምዕራፍ ሠላሣ አራት
የጉንደር ተጋድሎ

በወግ አጥባቂው በዳግማዊ ምኒልክ ወገንና በተራማጁ በንጉሥ ተፈሪ ተከታዮች መካከል የተቀሰቀሰው የሐሳብ ልዩነት፣ መጋቢት 22 ቀን 1929 ዓ.ም ቋና፣ አንቺም ከተባለው ቦታ አዋጋ።[1] ምንም በሥልጣን ሽሚያ የሚካሄድ የርስበርስ ጦርነት በኢትዮጵያ ህብረተሰብ ውስጥ የተለመደ ነገር ቢሆን፣ ይህ ጦርነት በጉንደር ሕዝብ ላይ የጣለው የስሜት ተፅዕኖ ቀላል አልነበረም። ለዚህም ልዩ ልዩ ምክንያቶች ነበሩ።

ጦርነቱ የተካሄደው ከሰማይ ከአይሮፕላን በሚጣል በምብ፣ ከምድር በመድፍ ነበር። እጅ ሰመስጠት ታስቦ የነበረው ሐሳብ በማንኛው ወገን ፈርሶ ተኩስ እንደተከፈተና ጦርነት እንደተካሄደ፣ ግልጽ አልነበረም። ራስ ጉግሣ ከሞቱ በኋላ ሬሳቸው ተቀራርጦ ነበር። ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ደግሞ በሦስተኛው ቀን፣ ማለትም መጋቢት 24 ቀን 1929 ዓ.ም ሞቱ።[2] ተድሞውንም ራስ ጉግሣ የተንቀሳቀሱት የኃይማኖት ሕጸጽ የተከሰተ መስሎአቸው ነበር። የቀድሞ ሚስታቸው እንደ መሆናቸው መጠን፣ የልዑል ራስ ተፈሪ አሰገዳጅነት በተቀሳቀለበት ሁኔታ የንጉሥነት ዘውድ መጫን (ባለ ሙሉ ሥልጣን አልጋ ወራሽነት ዘውድ መጫን)፣ በራስ ጉግሣ ልቡና ላይ ተፅዕኖ ማድረጉ አልቀረም።[3] ከዚህ ውጭ ለጎንደር ከጠሳት የቀረበለትም ሽንገላ ቀላል አልነበረም።

ጉንደር በእነዚህና በሌሎችም ጉዳዮች የተሰማውን ቅሬታ ጠጥቶ፣ ጣልያን ጉራ ሰብሮ በገባ ጊዜ የሀገር መከላከል ሥራውን ቀጠለ። የጣልያን ጦር መጋቢት 23 ቀን 1928 ዓ.ም ጉንደር ከተማ ገባ። የማይጨው ጦርነት ማግስት ማለት ነው። የገባው አንዱ ክፍል በጀነራል እስትራቹኒ መሪነት ከአሥመራ ተንስቶ፣ የመረብን ወንዝ ተሻግሮ ኡምሐጀር ከገባ በኋላ፣ በሽጸጽ በኩል ቀጥታውን መሥመር ይዞ በእግር በመንዝ ነበር። ይህ በር በኢትዮጵያ በኩል ተከላካይ ስለአልቆመበት ያለአንዳች ችግር ሰተት ብሎ ገባ። ገብቶም ሠፈሩን ቀድሞ የጣልያን ቆንሲል ከነበረበት፣ ቸቸላ ከተባለው ቦታ አደረገ። ሌላው ክፍል ደግሞ በጀነራል ጉቤቶ መሪነት ከሽሬ ተነስቶ የተከዜን ወንዝ በመሻገር፣ በዳባት አድርጉ በዚሁ ቀን ከቀትር በኋላ በአተማይቱ ገባ። ሠፈሩን ደብረ ብርሃን አጠገብ ሐዋርያት ከተባለው ቦታ አደረገ።

ጉንደር ደነገጠ። ቀደም ብሎ በተሰለፈ ትዕዛዝ መሠረት ለተሰበሰበው ሕዝብ ንግግር ያደረገው፣ ጥዋት የገባው ጀነራል እስትራችኒ ነበር። እሱም ብዙ ፎከረ፣ "...በሰማይም፣ በምድርም፣ በባህርም ያለው ሥልጣን ሁሉ ለኛ ተሰጥቶናል..." አለ። ሕዝቡ በቀጥታ ለጣልያን መንግሥት መገዛት እንደአለበት አስታወቀ። በአደባባይ የነበሩ የውጭ አገር ሰዎችን ትዝብት እንኳን ከቁም ነገር ባለመቁጠር፣ ሌሎች መንግሥታት ኃያላን ነን የሚሉት እውነት አለመሆኑን አስታወቀ። ከዚያም ሀገር የመያዙን ሥራ አፋጠነ።

ከአምሐጀር ተከፍሎ ጠረፍ፣ ለጠረፍ የተጓዘው ጦር ሚያዝያ 4 ቀን መተማ፣ ሚያዝያ 21 ቀን 1928 ዓ.ም ደብረ ታቦር ገባ።

ጉንደሬ ሁሉ በየአካባቢው እየተሰበሰበ መከረ። የሚያዋጣውን ዘዴ ያፈላልግ ጀመር። በጉንዳ መረባ፣ በአርማጭሆ፣ በጠገዴ፣ በጭልጋ፣ በጫቆ፣ በመተማ፣ በሠራቆ፣ በቋዩ ጋውላ፣ በአለፋ፣ በጃንዴ፣ በጸለሎ፣ በወልቃይት፣ በጠለምት፣ በወገራ፣ በጃንዋራ፣ በበለሣ፣ በከፋንዝ፣ በስሜን፣ በቦዛ፣ በቆላ ወገራ፣ በጭሀራ፣ በሰቀልት፣ በጉንደር፣ በጠደ፣ በደንብያ፣ በሚካኤል ደብር፣ በፎገራ፣ በመና መቅጣዋ፣ በቋሊማ፣ በመልዛ፣ በአብናት፣ በፋርጣ፣ በሐሙስ ወንዝ፣ በአሞራ ገደል፣ በጥናፋ፣ በምክሬ፣ በሰዴ፣ በሙጃ፣ በአፈረዋናት፣ በአንጦ፣ በእንደቤት፣ በውዶ፣ በጋይንት፣ በነገላ፣ በእስቴ፣ በወገራ፣ በከሰጌ፣ በድብ ባሕር፣ በተንከል በአዳኝ አገር፣ በሰሐሪ ያለ ጀግና የጉበዝ አለቃ እየመረጠ በበኩሉ ተንቀሳቀሰ።

ወሳኙ የመሣሪያ ጉዳይ ሆነ። ለዚህ ጉዳይ የተገኘው ዘዴ በእጅ ያለውን መሣሪያ ለጠላት አለማስገባት፣ እንደዚሁም በተገኘው ዓይነት መሣሪያ ከጠላት መንጠቅ፣ መማረክ ሆነ። ጠላት መሣሪያ አግቡ እያለ ያስተሳለፈው ትዕዛዝ ሳይፈፀምለት በመቅረቱ እሱ ራሱ ሕዝቡን እያስገደደ ለመሰብሰብ ከጭልጋ ተነስቶ ወደ ጫቆ ዘመተ። አርበኞቹ ቤዛሆ ከተባለው ቦታ ገድበው ቆዩና፣ ግንቦት 1 ቀን 1928 ዓ.ም ጦርነት ገጠሙት። ጣልያንም መሣሪያ ከሕዝብ መሰብሰቡ ቀርቶ ከእሱ ከራሱ ጦር 15 ጠመንጃና 5 በቅሎች ተማረኩበት። ይህም ለአርበኞች መልካም አጀማመር ሆነላቸው።

በመከላከሉ ሥራ ላይ የሚመቱትና የሚሞቱት የኤርትራ ልጆች፣ ሐማሌኖች ሆነው ስለተገኙ፣ በተያያዘም ግራዝማች /ራስ/ ውብነህ ጥቁር ሰው የገደለ ከገዳይ እንደማይቆጠርለት ስላወጁ፣ አቶ ብሬ ዘገየ ሣንጃ ወንዝ ላይ አንድ ኮሎኔልና ብዙ ጣልያናውያን ወታደሮች በሰኔ ወር 1928 ዓ.ም በመግደል በጉንደር የአርበኝነት ሥራ የመጀመሪያ ነጭ ገዳይ አሳቸው ሆኑ። ከዚያ በኋላ ነጭ የሚገድሰው እየበዛ ሄደ።

ግንቦት 5 ቀን 1928 ዓ.ም በጉንደር ከተማ ትልቅ በዓል ተደረገ። በበዓሉ ላይ ጀነራል አስትራቺኒ ከክሚዮን ላይ ወጥቶ ቆመ፣ "ዛሬ ከዚህ የተሰበሰባችሁት ቪቶሪዮ ኢማኑኤል የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መሆናቸውንና የኢጣልያ ነገሥታት በኢትዮጵያ ላይ ለትውልድ ትውልድ እያስተሳለፉ እንዲነግሥባት ወዳችሁና አምናችሁ እንድትፈርሙ ነው" አለ። እንዲሁ እንዲደረግም አደረገ። የጉንደር ሕዝብ የጣልያንን ዓላማ በግልጽ ተረዳ።

ጉንደር የአማራ አገር ዋና ከተማ ሆነች። የአማራው አገር ወሰን፣ ጉጃምን፣ በጌምድርን እንዲያጠቃልል ተደረገ። በጦርጉራ በጀንዳ፣ በይልጊ፣ በአለፋ፣ በቋራ፣ በጉባ፣ በማጣቢያ፣ በመተማ፣ በጉደቤ፣ በጉንደዋ፣ በጭልጋ፣ በትክል ድንጋይ፣ በሣንጃ፣ ባደንቀዝ፣ በደጐማ፣ በሚካኤል ደብር፣ በይፋግ፣ በጣራ ገዳም፣ በቁልቋል በር፣ በደብረ ታቦር፣ በአስቲ፣ በሰማዳ፣ በአንቆሻ፣

በጋይንት፣ በማቢ፣ ነገላ፣ በደብረ ሲና፣ በመቅጠዋ፣ በአጃ በፋሲለደስ፣ በአብናት፣ ኢጣልያውያን ገዥዎች፣ የጦር ባለሥልጣኖች ተመደቡ። የድልድሉ ዓላማ በተገኘው ዓይነት ዘዴ የአርበኞችን እንቅስቃሴ ከእንጭጩ ለመቅጨት ነበር።

አርበኛው፣ በጠላትን ሁኔታ ገነዘነ። የሀገር ውስጥ ጦርነት ከተነሣ በቀላል እንዳይለቀው አወቀ። ሕዝቡን እርስበርሱ የሚያለያይና አንድነቱን የሚበትን ስብከት ያዘ። ሰኔ 21 ቀን 1928 ዓ.ም ሻለቃ አጉሲኒ አውግሥቶ የደብረ ታቦርን ሕዝብ ሰብስቦ "...እስላሞች ኢትዮጵያ ሀገራችሁ ስትሆን በሃይማኖት ልዩነት የተነሣ ክርስቲያን ነን የሚሉት ሀበሾች የበታች አድርገው ክርስት ነቅለው ሲገዙአችሁና ሲያሰቃዩአችሁ ይኖሩ ነበር። ...ከእንግዲህ ...መከራችሁና ችግራችሁ፣ ጭንቀታችሁና ውርደታችሁ፣ ከእናንተ ተወገደ..." አላቸው።

ወደ ሁለተኛው ረድፍ ዞሮ ለድሆች እንዲህ አላቸው። "...ለመኪንንትና ለካህናት ገንዘባችሁንና ጉልበታችሁን ስትገብሩአቸው፣ ወዛችሁንና ደማችሁን ስታንጠባጥቡላቸው፣ የምትኖሩ ሕዝቦች ከዛሬ ጀምሮ መከራችሁ ተፋቀ። ...የእኩልነት መብት ይኸውና ዛሬ ወሰዳችሁ። ...ስለዚህ በቅንነት መገዛትና በታማኝነት ማገልገል ነው..." አላቸው።

ወደ መኪንንቱ ፊቱን አዞረ። ወደ አጠገባቸው ቀርቦ "...እናንተ የበጌምድር መኳንንትና ባላባቶች... የኢጣልያ መንግሥት የነበረባችሁን የተወላጅነት እኗኗር ከዛሬ ጀምሮ ሠርዞታል።... አንድ የሸዋ ሰው የበላይ ሆኖ ያዝዛችሁ ነበር። የሸዋ ሕዝብ ተገዥዎች ናችሁ እንጂ፣ እናንተ አማሮች ገዥዎች አልነበራችሁም።... ለቪቶሪዮ ኢማኑኤልና ...ለሞሶሎኒ በትክክል መገዛት ነው..." አላቸው።

ሌላው የጣልያን ሹም ደግሞ በሌላ ቀን የክርርንና የቨጋ አገርን፣ የጋባን፣ የጭልጋን ቅማንቶች ሰብስቦ ክቢሮው አስገብቶ በእነሱና በጣልያኖች መካከል ተመሳሳይነት ያለው አፈታሪክ እንደ አለ ተረከላቸው። በኢጣልያ ወገን ሬሙሰና ሬሙሉሶ የተባሉትን የሮማን ከተማ የመሠረቱትን ሁለት ወንድማማቾች አጥብታ ያሳደገቻቸው ተኩላ እንደሆነችና፣ እንደዚሁም የቅማንቶችን አባት አይነርን ሰስ አጥብታ እንዳሳደገችው አስረዳቸው። ከትልቅ ዋርካ ሥር ሰስ ቁማ የተሣለበትን ትልቅ ሠሌዳ አውጥቶ አሳያቸው። አርማቸው አድርገው በየወረዳው ለሚገኘው ሕዝባቸው እንዲያሳዩት አዘዛቸው።

በየቦታው ይህንን የመሰለ፣ ሕዝብን እርስበርሱ የማለያይ ስብከት ሰበከ። በዚህ ስብከት የተታለሉት ወገኖች ጥቂት አልነበሩም። ነገር ግን ሁሉን ማታለል አልተቻለውም። ጣልያን የሚለው "ለእኔ ተገዙ" መሆኑ ግልጽ ሆነ። ቅማንቶች መክረው ቀኖዝማች ጣሹ እንግዳን አፈ ጉባዔ በማድረግ "የኢትዮጵያ መንግሥት በነበረበት ጊዜ የመንግሥቱን ሰንደቅ ዓላማ ተጠግተን

እንናር ነበር። አሁን ደግሞ ድል አድራጊውን የጣልያንን ባንዲራ ተጠግተን... እንናራለን እንጂ፣... በአባቶቻችን ሲያያዘ ያልመጣውን አዲስ ነገር አንቀበልም..." አለው። ሌላውም የጠላትን ስብከት ከቁም ነገር ሳይቆጥር ትግሉን ቀጠለ።

አርሶ በሌው፣ የቀንበር በሬውን እየሸጠ ጠመንጃና ጥይት ገዛ። ጣልያን ይህንን ሲሰማ መሣሪያ ያለህ አግባ ብሎ አዘዘ። ገበሬውም አሮጌ ስናድር፣ ውጅግራና ናስማስር ከሦስትና ከአምስት ጥይት ጋር አስረከበ። ጭስ የጠገበ ጋሻና ጉራዴ አገባ። ጣልያንም አንጀቱ እያረረ ተቀበለ። ደረቅ ብረት አግቡ ቢል፣ ገበሬ የለንም ብሎ ጠቀጠቀ።

የአርበኞች እንቅስቃሴ እየበረታ፣ የሕዝቡ ልብ ከእሱ እየራቀ እንደሄደ ገባው። የዚህን ጊዜ ወደ ኃይል ሥራ ዞረ። ለመዘርዘር የሚያስቸግር ብዙ የግፍ ሥራ አካሄደ። ሕዝብ እየሰበሰበ በመትረየስ መረሸን፣ እግርን ወደላይ ራስን ወደታች እያደረጉ እየዘቀዘቁ መስቀል፣ ቤተክርስቲያንና የሕዝብ መኖሪያ ቤቶችን ማቃጠል፣ ምስጢር ታውቃለህ በሚል ሰበብ ሰውን በዱላ እየደበደቡ፣ በጅራፍ እየገረፉ መግደል የዘወትር ሥራ ሆነ።

አርበኛውም በበኩሉ ግድያውን አጧጧፈ። አቶ ተፈሪ በላይ ከጉንደር ወደ ስቲት የሚጓዝ ካሚዮን ሰብሮ፣ በውስጡ የነበሩትን ወታደሮች ገድሎ፣ መሣሪያቸውን ማረከ። መምሬ ጌጡ የተባሉ ቂስ የታሠሩበትን ፈትተው ስቲት መንገድ ላይ ሁለት አልቤን ጠመንጃ ነጠቁ። አቶ አሸቴ አውነቱ ከብዙ ወርቅና ብር ይልቅ አሥር ጠመንጃ መርጦ ከጉንደር ግምጃ ቤት ዘርፎ ወጣ። አቶ ተሰማ ድንገት ቆማ በሚባለው ሀገር በዱላ አምስት ጠመንጀ ማረከ፣ አቶ በየነ እምሬ ከፋርጣ ጦርነት ላይ በዱላ ጠመንጀ ማረከ። አቶ ብርሃኑ አብተው በካራ ጀምሮ ከአምስት የጦር ሜዳ ስምንት ጠመንጃ ማረከ። የወንድነት ትርጉም ነጭ መግደል፣ ጠመንጃ መማረክ ሆነ። በአያንዳንዱ ግዳይና ምርኮ የሚካሄደው ፉክራ አስገራሚ ሆነ።

በሐምሌ ወር 1928 ዓ.ም በግራዝማች /ራስ/ ውብነህ ተሰማ የሚመራው አርበኛ ካቶ ማውራ ላይ ገጥሞ ሁለት ቀን መሉ ወጋው። ብዙ ወታደርም ገደለበት። የጣልያን ወታደርም ወደ መጣበት ምሽግ ተመለሰ። በዛ፣ ከጠላት እንጂ ከወገን ማንም አልሞተም።

ካህናት የትግሉ ተካፋይ ሆኑ። አባ ገብረ ማርያም የተባሉት የወልቃይት መነኩሴ አራቱን ማዕዘን ባርከው፣ ሰው ለጠላት እንዳይገዛ ገዝተው፣ ግንባራቸውን ለመትረየሱ ሰጥተው በመትረየስ ተደብድበው ሞቱ። አድገርትያ ማርያም፣ ክሣደ ማርያም፣ ምድረ ወይዘሮ ሚካኤል የተባሉት ሦስት ቤተ ክርስቲያናት ሲቃጠሉ፣ በዚያ የነበሩ 55 ክርስቲያኖች እየተገደሉ ከሚነደው አሳት ተጣሉ።

የማህበረ ሥላሴ ጉዳይ ለየት ያለ ስለሆነ በጥልቀት ሊታይ ይገባል። ሁለት የጣልያን አይሮፕላኖች በገዳሙ አካባቢ እየበረሩ ሲቃኙ የነበረው

ሳይታወቅ ተሰናክሰው ወደቁ። የወደቁትም አንዱ ማርዘነብ፣ ሌላው ደግሞ ጉንደዋ ከተባሉት ቦታዎች ነበር። ከአንዱ ውስጥ የነበሩት ሲያልቁ፣ በሁለተኛው የነበሩት ሦስት ሰዎች ስለዳኑ በዚያ የነበሩ መነኮሳት ሬድተውና ሸኚ ሰጥተው ወደ ጉንደር ላኩአቸው። ጠላት በዚህ ተደስቶ ዱቄትና ስኳር ላክሳቸው። እነሱ ግን አንቀበልም ብለው መለሱ። ጣልያን በዚህ ቂም ይዞ፣ ከገዳሙ ገብቶ በየመካነ ፀሎታቸው እየዞረ 22 መናንያት በጥይት ገደለ። ከዚህም በስተቀር ቤተክርስቲያኑን ባቃጠለ ጊዜ ሁለት መነኮሳት በፈቃዳቸው አብረው ተቃጥለዋል።

የአርበኞችን እንቅስቃሴ በእንጭጩ ለመቅጨት የጠላት ጦር በየቦታው ተፍጨረጨረ። አርበኛውም እንደ አመጣጡ ይቋቋመው ጀመር። ነሐሴ 24 ቀን 1928 ዓ.ም ጥናፍ ከተባለው ቦታ ላይ ግንባር ለግንባር ገጠመው። ከጥዋቱ 5 ሰዓት እስከ ቀኑ 9 ሰዓት ቀጥ አድርጎ ወጋው። ጣልያንም ተመልሶ ደብረ ታቦር ገባ። በዚህ ቀን በተደረገው ጦርነት ሼህ አሊ የተባለው ቀንደኛ ባንዳ ተማርኮ ነበር። ነገር ግን እሱ መሆኑ ባለመታወቁ ተለቀቀ። ቢሆንም ተሰቀጠጠ።[4]

ጳጉሜ 4 ቀን 1928 ዓ.ም በልጅ አያናያ የሚመሩ አርበኞች ጫንቃ ከተባለው ቦታ ጦርነት ገጠሙት። ሠላሳ ሁለት የጠላት ወታደር በመግደልና መሣሪያ በመማረክ ደስ የሚያሰኝ ሥራ ሠሩ። ከእነሱ ግን እንኪን የሞተ የቆሰለም አልነበረም።

የ1928 ዓ.ም የጉንደር ትግል በዚህ ዓይነት ተፈፀመ። ከተነገሩት ቃላት፣ ከታካዔዱት ተግባራት የጉንደር ሕዝብ ግንዛቤ አገኘ። ያገኘውም ግንዛቤ የጣልያን ዓላማ፡-

1ኛ. ሀገሪቱን ለትውልደ ትውልድ የቅኝ ግዛት ማድረግ፣
2ኛ. ቤተክርስቲያናትን ማቃጠል፣ ካህናቱን መፍጀትና እምነቱን ማርከስ፣
3ኛ. ሕዝቡን መጨረስ፣
4ኛ. አንድነቱን አጥፍቶ እርስበርሱ ማፋጀት፣
5ኛ. በመሬቱ ላይ የእራሱን ሕዝብ ማስፈር፣

መሆኑን፣ ሰው በነገረው ብቻ ሳይሆን ከእነሱ ከራሳቸው ተረዳ፣ ከተግባራቸው አየ፣ ከቃላቸው ሰማ።

የ1929 ዓ.ም ትግል ከ1928 ዓ.ምቱ የበረታ ሆነ።

በመስከረም ወር 1929 ዓ.ም ሻለቃ ካሰሎኒ በተባለ መኮንን የሚታዘዝ ወታደር ወደ ደዋ ዘመተ። አርበኛውም ደንጉራ ከተባለው ቦታ ገጠመው። ደህና ውጊያ ከተካሄደ በኋላ ጣልያን አሸነፈ። የአርበኞቹ መሪ አቶ ከሆና ነጋሽ ከሦስት ባልደረቦቹ ጋር ተማረከ። አሥር አርበኞች ሞቱ። ጣልያን ምርኮኞቹን ወደ ጭልጋ ወሰዶ ብዙ ሥቃይ ከፈፀመባቸው በኋላ አይክል ላይ ሰቀላቸው። ነገር ግን በዚህ አደራረጉ ኖተናደደ አቶ ከፍአለ ብሩ

የተባለ፣ ከአደባባይ ላይ የነበረ ሰላማዊ ሰው፣ ከተሰለፉት የጠላት ወታደሮች ጠመንጃ ነጠቆ፣ 6 ወታደር ገድሎ በማምለጥ አርበኝነት ገባ።

በልጅ ብሬ ዘገየ የሚመሩት አርበኞች ጥቅምት 1 ቀን 1929 ዓ.ም ሣንጃ ከተባለው ቦታ የነበረውን ምሽግ አጠቁ። ከጠዋቱ በ1 ሰዓት ጀምረው ሲዋጉ ውለው፣ በ9 ሰዓት በጨበጣ ጦርነት ምሽጉን ሰብረው ገቡ። ብዙ የጠላት ወታደር ገደሉ፣ ሁለት ሹማምንት ማረኩ፣ የቀረው ሸሽቶ አመለጣቸው። እጅግ ብዙ ጠመንጃና ጥይት፣ የእጅ ቦምብ ስለተገኘ፣ ሴት ወንዱ ከአባባቢው ወጥቶ ለቀመው። መሣሪያው ለአርበኝነት ሥራ ጠቀመ። ከአርበኞች ወገን አምስት ሰዎች በጀግንነት ወደቁ፣ ጥቂቶቹም ቆሰሉ። ድጋሚ ጥቅምት 12 ቀን 1929 ዓ.ም ሲፍላ ከተባለው ቦታ ላይ ጦርነት ተደርጉ፣ ድል የአርበኞች ሆነ። ብዙ የጠላት ወታደርና አምስት አርበኞች ሞቱ።

የሣንጃ ምሽግ መስበር የጠላትን ኩራር ነካ። በአማራ አገር ገዥ ልዩ ትዕዛዝ 1500 ወታደር ዘመተ። አርበኛው ጥቅምት 19 ቀን 1929 ዓ.ም ደብረ ሲና ከተባለው ቦታ ግንባር ለግንባር ገጠመው። ብዙ የጠላት ወታደር አለቀ። ሲዋጋ ከሞተው ይልቅ ሲሸሽ ሰሃራ ከሚባለው ገደል ዓይኑ እያየ ገብቶ ያለቀው ሳይበልጥ አልቀረም። አቶ አዛገ አበራ፣ መቶ አለቃ ድፋስዩ የተባለውን የጦር አዛዥ መትረየስ ከሚተኩስበት ላይ ደርሰባት ሁለቱም እጅ ለእጅ ተያይዘው ከመሬት ወደቁ። አንዳቸውም ረዳት ሳያገኙ አዛገ አበራ ነጭ ገዳይ ብሎ ተነሳ። ሃያ ሦስት አርበኞች በጦሩ ሜዳ ሞቱ፣ ሌሎችም ቆሰሉ። ድል ግን የአርበኛ ሆነ። በዚህ ጦርነት አንድ ማርተጋሻ ልጅ፣ አንድ መቶ አለቃ ስለገደለ ጓደኞቹ ሁሉ ለዚሁ ዓይነት ሥራ ተነሳሱ።

የአርበኞች ኃይል የማይበገርለት ሲሆን፣ ጣልያን ከሽሬ ሌላ ጦር አመጣ። የዚህ አዲስ የመጣው የጦር ሥልት ከአርበኛው ሥልት ጋር ተመሳሳይ ስለሆነ ጦርነቱ ከባድ ሆነ። ከሁለቱም ወገን ብዙ ሰው አለቀ። ከአርበኞች ወገን ዋና ዋናዎቹ 17 ነበሩ። ከእልቂት የተረፈው የጠላት ጦር በአዝማቹ በደጃዝማች ፀሐይ መሪነት ጉንደር ገባ። አርበኞች ብዙ መሣሪያ ማረኩ። ሴት ወንዱ ወጥቶ ስምንት ቀን ሙሉ ከዱር ከገደል መሣሪያ ለቀመ።

በሌላው የጦር ግንባር ደግሞ በደጃዝማች ነጋሽ ወርቅነህ የሚመራው አርበኛ በጥቅምትና ታህሣሥ ወር 1929 ዓ.ም ግልቢና፣ አጥገባ እና ማጀ፣ እንደዚሁም ሎዋሪ ከተባሉት ቦታዎች ላይ በተደጋጋሚ ከጠላት ጋር ጦርነት አድርጉ መልካም ሥራ ሠራ። ብዙ ጠመንጃና ጥይት፣ ፈታውራሪ ደሴ ዘለቀ የተባለውን የባንዶች መሪ ጭምር ማረከ።

ጣልያን በጉንዳ መረባ አካባቢ የነበሩትን አርበኞች ለማጥፋት በአንድ በኩል የሚመራ ጦር አንቀሳቀሰ። በልጅ አንዳርጌ ደስታ የሚመራው ጦር ቀደም ብሎ ሰባ ስምንት ሰው በሰቀለበት በአስተርእዮ ሜዳ ላይ ገጠመው።

ጣልያን አፈግፍጉ ጭንጫያ ከተባለው ኮረብታ ላይ ወጣ። አዲስ ጦር በማስመጣት ከበባውን ሰብሮ ወጣ።

ሕዝብ መሣሪያ አላገባ ስለአለ፣ መሣሪያ በግድ የመረከብ ጥያቄ ለጠላት አንገብጋቢ ሆነ። ስለዚህ ጣልያን ብዙ ወታደር ይዞ ከጉንደር ወደ ውዶ ወረደ። ፈታውራሪ አየለ ቁንጪ ህዳር 15 ቀን 1929 ዓ.ም ብቻ፣ ለብቻ ገጠመው በያዙት መውዜር ብዙ ወታደር ገደሉበት። በመጨረሻው እሳቸው ራሳቸው ተመቱ። ሕዝቡ በጽዮን ማርያም ደብቆ ሲያስታምማቸው፣ ጠላት ዓለሙ ይመር በተባለ ሰላይ አማካይነት አግኝቶ ወደ ደብረ ታቦር ወሰዳቸው። እሳቸውም "ይህ ዛሬ በእኔ የደረሰው ነገ በእያንዳንድህ ላይደርስብህ አይቀርም" ብለው ሕዝቡን በማስጠንቀቅ ከእሥር ቤት ገቡ። ከዚያም በማገሥቱ የተዘጋጀውን ገመድ እሳቸው ራሳቸው፣ በእጃቸው ከአንገታቸው በማጥለቅ ለማዕትነትን ተቀበሉ።

ጣልያን በአርማጭሆና በጠገዴ ያሉ አርበኞችን ለመደምሰስ ብዛት ያለው ጦር አንቀሳቀሰ። አርበኛውም ህይወቱን ለሀገሩ ለመስጠት ተማማለ። ታህሣሥ 5 ቀን 1929 ዓ.ም ግመኛ ከተባለው ቦታ ገጠመው። አገሬውም ተባብሮ የመጣበትን ጠላት አባረረው። ብዙ የጠላት ወታደር ሞተ። ከአርበኞችም ወገን ከሁለት የጦር መሪዎች ጋር ብዙ ሰው ሞተ። ቢሆንም ከጥፋት ዳነ። ይህንን ሥራ የሠራውን አርበኛ ለማጥፋት፣ ጠላት በዚሁ በታህሣሥ ወር 1929 ዓ.ም ሌላ ጦር አንቀሳቀሰ። ጦሩ ከዳባት ተነስቶ ለአነሱ አመች ከሆነ፣ አልም ከአለው የአዴት ጫካ ውስጥ ሲገባ፣ አርበኞች ሥራቸውን ጀመሩ። ብዙ የጠላት ወታደር ገደሉ። የጦር አዛዥ ሆኖ የመጣው ሻምበል በባለምዋሉ በቀኛዝማች ተስፋዬ መደባይ አማካኝነት እጁን ለመስጠት ጠየቀ። የአርበኞቹ መሪ ልጅ ዳኘው ተፈሪ መሣሪያውን ከአስረከባቸው ምህረት አድርገው አስከ ዳባት ድረስ በሽኚ እንደሚልኩት ቃል ገቡለት። ሻምበሉ ወታደሮቹን በሙሉ አሳልፎ አርበኛው በተቀመጠበት አደባባይ በሰልፍ የክብር ሰላምታ እየሰጠ አልፎ የጦር መሣሪያውንና ተጥቁን አስረከበ። እሳቸውም ቃላቸውን ጠብቀው ሽኚ ሰጥተው በሰላም ዳባት እንዲገባ አደረጉ። መሣሪያውን ለሕዝብ አደሉ።

የሻምበሉን መከበብ የሰማው የወልቃይቱ ጦር አዛዥ፣ አለቃ ግራመሽ ለእርዳታ ቀደም ብሎ ተንቀሳቀሰ ነበር፣ ግን የእጅ መስጠቱ ሥራ ከተከናወነ በኋላ ደረሰ። የአዴት አርበኛ አዲስ በተረከበው ምንሽር እሱኑ ጠዘጠዘው። ሻለቃ ግራምሽ ሁኔታውን ሲረዳ ሽሽቱን ቀጠለ። ልጅ ዳኘው ወኔ ተቀስቅሰባቸው ጠላትን እያባረሩ ከዳባት ምሽግ ገቡ። ዋናውን ለመጣል ባደረጉት ሙከራ እጅ ለእጅ ተያይዘው ትንቅንቅ ገጠሙት። በኋላ ግን ብዙዎች ሆነው ታግለው ጥሰው ገደሉአቸው። ከእሳቸው ጋር ሌሎች ሦስት ታዋቂ አርበኞች አብረዋቸው ወደቁ። ልጅ ዳኘው በአልህ፣ ዝንጅት

ባልተደረገበት ሁኔታ ከምሽግ መግባታቸው፣ በዚህ ዓይነት ደግ ሳይወጣው ቀረ።

ጥር 10 ቀን 1929 ዓ.ም አርበኞች ቋራ ጋውላ ከተባለው ቦታ ጦርነት አድርገው አሥራ አምስት የጠላት ወታደር ገደሉ። መሣሪያም ማረኩ። ጥር 12 ቀን 1929 ዓ.ም ወደ መተማ በሚወስደው መንገድ ማብሰሬ በነበረው ምሽግ ላይ የሞልጋ አርበኞች አደጋ ጥለው ከንጋት እስከ ስድስት ሰዓት ተዋግተው ብዙ ወታደር ገድለው ሠላሳ ጠመንጃ ማረኩ። ከእነሱም ብዙ ሰው ሞተ፣ ብዙም ደግሞ ቆሰሉ።

ክልጅ ዳኘው ጦርነት ሽሽቶ ያመለጠውን አንድ ክፍል በቀኛዝማች /ቢትወደድ/ አዳነ መኩንን የሚመራው የጠገዴ አርበኛ ተቀብሎ እያጣደፈ ታህሣሥ 12 ቀን 1929 ዓ.ም መሥፈንቶ ላይ ከነበረው የጦር ሠፈር ከተተው። ከዚያም ከብቦ መከራውን ስለአሳየው አዛገፍ በባለምዋሉ በቀኛዝማች ጉላ አማላጅነት መሣሪያውን ለአርበኞች አስረክቦ ወልቃይትን ለቅቆ ቀብትያ ገባ። ጣልያን ለአርበኞች ያስረከበው ስምንት መቶ ጠመንጃ ቁጥሩ ካልታወቀ ጥይት ጋር፣ እንደዚሁም አንድ መቶ ዳውላ እህል ነበር። ጠገዴ ነፃ ሆኖ በቀኛዝማች /ቢትወደድ/ አዳነ አስተዳዳሪነት ይመራ ጀመር። ወልቃይትና ጠገዴንም ነፃ ለማውጣት ብዙ አስተዋጽኦ አደረገ።

መሣሪያውን ለልጅ ዳኛቸው አስረክቦ የተመለሰው የጣልያን ጦር ጉንደር ሲገባ በጦር ወንጀለኝነት ተከሰሰ። ቁስ "...እንድትዋጉ ተልካችሁ መሣሪያችሁን አስረክባችሁ ከመጣችሁ በነፍሳችሁ ትቀጣላችሁ..." የሚል ሆነ። ሻምበሉ ጥፋቱን አምኖ ቅጣቱን ተከሳሾቹ የሚቀበሉት እሱ ከመራው የበለጠ ወታደርና መሣሪያ ያለው ጦር ተልኮ ከቦታው ደርሶ የኢጣልያን ባንዲራ የሰቀለ እንደሆነ ብቻ እንደሚሆን ገልፆ ተከራከረ። በዚህ የተነሣ አዲስ ከባድ ጦር እንዲዘምት ታዘዘ።

አርበኛው ምሥጢሩን ሰምቶ ነበርና ከዚህ ነው መሞት የሚገባን ብሎ ቆረጠ። በአካባቢው የነበረው አርበኛ በሙሉ ተሰበሰበና አዴት ላይ ደረት ለደረት ገጠመው። ጠላት በመድፍ፣ ቡብዙ ዓይነት መትረየስና ቁጥሩ በበዛ ወታደር ተዋጋ። አካባቢውን አዘውትሮ በአይሮፕላን አስደበደበ። አርበኛው አልተበገረም፣ አጥብቆ ተጋደለ። የገጠሙት በሰሜን፣ በምዕራብ በደቡብ ሆነው ነበር። ከፍ ከአለ ቦታ እየወጡ አሽቆልቁለው በመተኮስ፣ የጥይት በረዶ ከሰማይ አወረዱበት። ነጋሪታቸውን ከጋራው ላይ ውጋ! ወጋ! ውጋ! እያሰኙ አሰሙቱ። የመሬቱ አቀማመጥ ለአይሮፕላን ድብደባ የማይመች ሆነ። ከአይሮፕላን የሚጣለውን ስንቅና ትጥቅ ነፋስ እያንገዋለለ ወስዶ ለአርበኞች ሰጠው። አርበኛው ጣልያንን ከወንዝ ውሃ አሳስቀዳ ብሎ ሰግሞ ያዘው። ወንዶች ልዩ ልዩ የጀግንነት ሥራ ሠሩ። ከምሽጉ ተጠግተው የጨበጣ ጦርነት አካሄዱ። አቶ ተክሌ አቁበ እግዚአ የተባሉ የሐማሴን ሰው ጣልያኑን ተናንቀው አጋድመው በጉራዴ ስለአረዱት እጅግ ተደነቁ። ጦርነቱ 12

መዓልትና 12 ሌሊት ወሰደ። ከሦስት መቶ በላይ ጣልያን ሞተ። የባንዳ ሞት ከቁጥር አልገባም። በልጅ ሐጐስ ተሰማ ግንባር የተገኘው ምርኮ የሰከረ አሣ መሰለ። ከአርበኞች ወገን ዘጠኝ ታዋቂ ጀግኖች ሞቱ፣ ብዙዎቹ ቆሰሉ። ጣልያን በመሳ ጉንደር የነበረውን ጦር አስከትቶ በማዝመት አዴት ላይ የተከበበበትን ጦር አወጣ። የጠገዴ አርበኞች ይህንን አሳዩ። ነገር ግን የጣልያን የጦር ፍርድ ቤት በተከሳሾች የሰጠው ብያኔ ውጤት ህቡዕ እንደሆነ ቀረ።

በእነዚህ መራር የአርበኛ እንቅስቃሴዎች ላይ ጣልያን አፀፋውን እርምጃ ወሰደ። በመረባ፣ በያይራ፣ በጃኒ ፈንቀራ፣ በአርማጭሆ በድምሩ አንድ መቶ አሥራ ዘጠኝ ሰው በአንድ ሰሞን ጨፈጨፈ። ከእነሱም አንድዋ ሴት ነበሩ። ሌሎች 50 ሰዎች በቋራ ወረዳ ገደለ። ጣልያን የጉንደር ከተማንም ቀስፎ ያዛት። ብዙ ጦር ከየአለበት አመጥቶ አሰፈረባት፣ ዙሪያውን በእሾህም ሽቦ አጠራት። ሰው የሚወጣ፣ የሚገባው በዘጠኝ በሮች ብቻ ሆነ፣ እነሱም፡-

1. በሙሽራ ድንጋይ፣
2. በቀሃ ኢየሱስ፣
3. በቸቸላ፣
4. በልደታ፣
5. በአበራ ጊዮርጊስ፣
6. በአዲስ ዓለም፣
7. በደረቦ፣
8. በአርባዕቱ እንስሳ፣
9. በደብረ ብርሃን።

ነዋሪዎቿ በከተማይቱ ዙሪያ ከአቡሩ አሥራ አራት ምንጮች ከአንዱም ውሃ እንዳይቀዱ ተከለከሉ። ለወታደሩ በቀን ከአንድ መቶ እስከ ሁለት መቶ ፍሪዳ ከፋሲለደስ ሜዳ ላይ እየታረደ፣ ደሙና ፊርሱ በአሸንዳ፣ ቀሃ ወንዝ እንዲገባ ተደረገ። ሀበሻ የሚጠጣው ከዚያ በታች ሆነ። ቤታችሁን እያፈረሳችሁ ቦታውን ለጣልያን ልቀቁ ተባለ። ጣልያኖች የሲጃራ ትርኪ ሽ በማስመሰል እሳት እየወረወሩ የበዙ ሰው ቤት አቃጠሉ። ሆቴል ቤትና ሲኒማ ቤት ሀበሻ እንዳይገባ ተከለከለ።

ጣልያን የአርበኞችን ኃይል መቋቋም የማይቻለው ሆነ። አጀ ከተባለው ቦታ የነበረው አገረ ገዥ በመልዛ፣ በመቅጠዋ፣ በመና፣ በቋሊማና በእበናት የሚኖረው ሕዝብ፡- 1ኛ. በአጅ የሚገኘውን መሣሪያ እንዲያስረክብ፣ 2ኛ አንድ ሺህ አምስት መቶ ወጣቶች መልምሎ እንዲሰጥ አዘዘ። ግንቦት 23 ቀን 1929 ዓ.ም ከምሽቱ አራት ሰዓት ሲሆን፣ አቶ ይግዛው የተባለ ሰው "ጦር በላህ" እያለ ሰፈፈ። ሕዝቡም በየሸንተረሩ እሳት በማንደድ እርችት አሳየ። ጣልያን ይህንን ሽሽቶ ደብረ ታቦር ገባ። ከዚያም አዛገፍ ወደ ጉንደር በመሄድ ከአማራ አገር መሪ መመሪያ ተቀበለ። አዲሱን መመሪያ ይዞ አጀ ሰኔ

5 ቀን 1929 ዓ.ም ገባ። እንደገባም ምህረት ተደርጐላችኋልና ግቡ የሚል ቃል አስነገረ። ሕዝቡ የተካሄደ ጦርነት ስለአልነበረ በመዘናጋት በብዛት ገባ። እሱ ግን ትእዛዝ የተሰጠው በምህረት አስመስሎ ከሰበሰበ በኋላ ሕዝቡን እንዲፈጅ ነበረና፣ ከሰኔ 12 እስከ 30 ቀን ድረስ ከሰበሰበ በኋላ ሴት ወንድ፣ ልጅ አዋቂ ሳይል በመትረየስ ፈጀው። እስከ አምስት መቶ የሚገመት ሰው አለቀ።

በወቅቱ፣ አካባቢውን አንበጣ ስለበላው፣ አርበኛውን በጦር ላይ ረሃብ ተደረበበት። ጠላት ይህንን በማወቅ ነጋዴ እንዳይተላለፍ ከለከለ። ስለዚህ አርበኛው የሚመገበው ሴንሣ፣ ሣዳ፣ ሜብሌ የሚባሉትንና የመሳሰሉትን ሥራ ሥሮች ሆነ። ወንዱ ለጦር ሲወጣ፣ ሴቱና ልጁ ሥሮችን እየፈለገ፣ እየማሰ ይለቅማል። ፋታ ሲገኝ ወንዱም ይፈልጋል።

አርበኛው በዚህ ሁኔታ ላይ እንደአለ፣ ጣልያን ወደ አርማጭሆ መውረድ ጀመረ። ሻለቃ ካሶሎኒ በተባለ መኰንን የሚመራ 15 ባታልዮን ጦር ተንቀሳቅሶ ጨግ ውሃ ላይ ሠፈረ። ይህንን ሁኔታ አርበኛው የሚታገሰው ስላልነበር፣ አትኪሮ በር ላይ ሰኔ 5 ቀን 1929 ዓ.ም ገጠመው። ታዋቂ ሃምሳ ዘጠኝ አርበኞች ሞቱ፣ ብዙዎች ቆሰሉ። ከጠላት ወታደርም እንደዚሁ ብዙ አለቀ። ነገር ግን ጣልያንን ማባረር ሳይቻል ቀረ።

ሐምሌ 1 ቀን ደግሞ የቀሩትን ለመፍጀት ሲዘጋጅ፣ አቶ በርሁን ፈረደ የተባለ ሰው የደበቀውን መውዜር ሚስቱ ስለአቀበለችው፣ ሐምሌ 5 ቀን ተኩስ ከፍቶ አዛዡን ጣልያን ገደለው። እሱንም ወንድሞቹ ረዱት። ወንዱም፣ ሴቱም፣ በአጠቃላይ ሕዝቡም ተባብሮ፣ በድንጋይና በዱላ፣ በአፈርና በቅጠል ጠላቱን ደብድቦ በማባረር ቦርድ ተይዘው የነበሩትን ሰዎች አዳነ። በዚህ ቀን ሠላሣ የሚያህል የጠላት ወታደር ተገደለ፣ መሣሪያም ተማረከ። ጣልያንም መቀጠዋ የእያዳ ማርያምን ቤተክርስቲያን አቃጠለ። ጠላት በአጥቢያው የነበረውን ሕዝብ ቤት እያዘጋ አነደደው። አንድ ሕፃን ከእሳቱ አምልጦ ቢወጣ፣ መልሶ ጨመረው።

በሐምሌ ወር 1929 ዓ.ም ጠላት ከዳባርቅ ተንቀሳቀሰ። በአንቃሽ፣ በወደበኝ አድርጉ የአቋሶን ወንዝ ተሻግሮ መረባ ደረሰ። በልጅ አንዳርጌ ደስታ የሚመራው አርበኛ አስተርአየ ከተባለው ሜዳ ላይ ገጠመው። ባለቤቲቱ፣ ወይዘሮ ከበቡሽ ጥሩንባ እያስነፉ የአካባቢውን ሕዝብ ቀሰቀሱ። ዋናውን፣ አዛዡን ጣልያን፣ ልጅ አንዳርጌ በመውዜር ሽንጡን ቀርጦ ገደለው፤ የባንዳው ሹም በሻ አበበም ተመትቶ ወደቀ። መሪዎቹ ሲያልቁ ባንዳና አርበኛ በጥሪ ተነጋገረ። ባንዳ "...ላትችል በከንቱ የሰው ደም ታፈሳለህ..." አለ። አርበኛ መልሶ "አንተ የአሕዛብ ሎሌ... በአገርህ ጣልያን ቢነግሥባት ትወድ ይሆን" ብሎ ጠየቀ። ጦርነቱም በዚሁ አበቃ።

ጣልያን ጉዞውን በመቀጠል ድርካዜ ደረሰ። ቆራጥ ጀግኖች ዘጠኝ ሆነው፣ ነሐሴ 17 ቀን 1929 ዓ.ም ገጠሙት። በመልዛ /ቆላ ደጋ/፣ በቋሊማ፣

በአብናት የነበረ አርበኛ እየተጠራራ ተሰበሰበ። ጠላቱን ከብቦ እንደ ንብ ጠዘጠዘው። ውጊያው ለአራት መዓልትና ለአራት ሌሊት ያለማቋረጥ ቀጠለ። ጦርነቱ ከጠላት ወገን ከአይሮፕላን በሚጣል ቦምብና በሚተኩስ መትረየስ፣ በምድር ደግሞ በመድፍና በመትረየስ፣ ቁጥሩ እጅግ በበዛ ወታደር ሲሆን፣ በአርበኞች ወገን በጥቂት ጥሩ ጠመንጃና በጐራዴ፣ በጦር፣ በዱላና በድንጋይ ነበር። በአምስተኛው ቀን ጠላት በሻምበል ብራንዲኒ የሚመራ አዲስ ጦር በመላክ የተከበበውን ጦሩን አውጣ። በዚህ ጦርነት ሠላሣ ሦስት አውቅ አርበኞች ወደቁ። በጠላት ወገን ሁለት ሻምበሎች፣ አምስት መቶ አለቆች ሞቱ። ብዙ ወታደር አለቀ። ጣልያን በሚሸሽበት መንገድ ላይ በአጋጣሚ እጁ የገቡትን ሃያ ስምንት ሰዎች በመትረየስ ፈጅቶ ሽሽቱን ቀጠለ።

ሻለቃ ፋሊቲ ታላቅ ጦር ይዞ ከደብረ ታቦር በመነሳት በመና፣ በመቀጠዋ አድርጉ ጉዞውን ቀጠለ። ሃሳቡ ከቋሊማ ቆላ አንስቶ እስከ ደጋው ድረስ ያለውን አገር ለማጥፋትና ሕዝቡን ለመፍጀት ነበር። ሁኔታውን አርበኞች ደርሰውበታል። ነገር ግን የአቅማቸውን ማነስና የጠላትን መበርታት እያመዛዘኑ ማመንታት አበዙ። ፍርሃት ማየሉን የተመለከተ አቶ ተሾመ የተባለ ደፋር "የፍርሃትመድኃኒት እኔ ላሳያችሁ" ብሎ ቀይ አፈር ላይ አንድ ጥይት ተኮሰ። ሻለቃ ፋሊቲ ለጦር በመዘጋጀት አካባቢውን በመንደር ሲቃኝ፣ ሴቶቹ በተራራ ላይ ሲተረማመሱ አየ። "ወንድ ልጅ ሴት ከአየ ይሞታል እንጂ አይሸሽም። ይህ ጦርነት የበረታ ነው። የበረታ ይዋጋ፣ የፈራ ይሸሽ። እኔ ግን እሞታለሁ እንጂ አልሸሽም፣ አልማረክም።" የሚል ቃል ተናግሮ ጦርነቱን ከፈተ። ጦርነቱ እንዳለውም የበረታ ሆነ። ወንዱ በጥይት ሲዋጋ፣ ሴቱ ከተራራው ላይ መርግ ለቀቀበት። መርጉ ሠራዊቱን ከመፍጀትና ከማስደንገጡም በላይ፣ ሬዲዮ የተጫኑትን አጋሰሶች ገደል ስለጨመራቸው ግንኙነቱ ተቋረጠ። ጦርነቱ ለአምስት ቀን ቆየ። የጠላት ወታደር መሣሪያውን እያመጣ ለአርበኞች እያስረከበ ሽሽቱን ያዘ። ሻለቃ ፋሊቲ ከጦርነቱ ላይ በጀግንነት ሲዋጋ ሞተ። በወታደሩ ፊት የገባውን ቃል ኪዳን ፈፀመ። ሆኖም ሞቱ አንድ ሣምንት ድረስ ለወገኖቹ ሳይሰማ ቀረ። በዚህ ጦርነት አንድ ባለውሃ መትረየስ፣ ስድስት ቀላል መትረየሶች፣ ሦስት መቶ አልቤን ጠመንጃ ከብዙ ጥይት ጋር ተማረከ። ጣልያን አካባቢውን፣ መጃ የተባለውን ቦታ ጭምር ለቅቆ ወጣ። አገሩም ከጠላት ቁጥጥር ነፃ ሆነ። ጦርነቱ የአርበኝነትን ሥራ አደረጀ። በዚህ ታላቅ ጦርነት የሞቱት አሥራ አምስት፣ የቆሰሉት ደግሞ ሰባት አርበኞች ብቻ ነበሩ። ከጠላት ወገን ብዙ ነበር።[5]

የጣልያን መግባት ሲሰማ የመና፣ የመቀጥዋ፣ የመልዛና የሐሙስ ወንዝ ሕዝብ የጉበዝ አለቆቹን መረጠ። በነሐሴ ወር 1929 ዓ.ም ቋሊማ፣ ድርካዜ ላይ ተዋጋ። ወደ ኋላ የሸሸው የጠላት ጦር ሁለት መድፍና እምስት ሺህ ወታደር ይዞ መጣ። አርበኛው ጦር ስለከበደበት ማገድ ተሳነው። ስለዚህ ጣልያን በማስጋሴ ጳጉሜ 1 ቀን፣ እብናት ገባ። ጳጉሜ 5 ቀን አገሩን

ለማቃጠልና ሕዝቡን ለመፍጀት ሲንቀሳቀስ አርበኛው ጦርነት ገጥሞ አስከ ደረባ ድረስ አባረረው። ጠላትም ተመልሶ እብናት ገባ። አርበኞች ብዙ መሣሪያ አገኙ።

የ1929 ዓ.ም የጎንደር ትግል በዚህ ዓይነት ተፈጽሞ የ1930ው ተተካ። ጣልያን ዓርብ ገበያ ላይ ሠፍሮ መሣሪያህን አግባ እያለ አዘዘ። ሕዝቡ መሣሪያ ከማግባት ቸል ቢል በመቀጠዋ፣ በመልዛ፣ በእብናትና በመና የደረሰው እንዳይደርስብህ እያለ ያስፈራራ ጀመር። ትዕግስት የማይበግረው ሆነ። ከሠፈሩም አልንቀሳቀስ አለ። የነገ አርበኛ መስከረም 2 ቀን 1930 ዓ.ም አርብ ገበያ ድረስ ሄዶ ገጠመው። በመትረየስና ቡጠመንጃ ጥይት ተለቀቀበት። እምብዛም ላይቆይ በእጅ በምብ ይደበድበው ጀመር። በዚያም የጨበጣ ውጊያ ተጀምና በዱላ ይነርተው፣ በጉራዴ ያወራርደው ያዘ። ወዲያው ምሽጉን ሰብሮ በመግባት አረደው። አምስት ጣልያኖች ከብዙ ወታደር ጋር ወድቀው ተገኙ። የተረፉት የጠላት ወታደሮች መሣሪያቸውን እያስረከቡ ተለቀቁ። ከአርበኞች ወገን አርባ ሦስት ታዋቂ ሰዎች ሞቱ፣ ሌሎች ሠላሳ ሰባት ቆሰሉ።

የአርብ ገበያ ጦርነት በደብረ ታቦር ሌላ ድንቅ ሥራ አስከተለ። ለጠላት ተቀጥረው በሊቢያ ሲዋጉ የነበሩ ኤርትራውያን፣ በኢትዮጵያ ላይ ያንኑ ሥራ ቀጥለው ነበር። የዓርብ ገበያ ምሽግ ሲፈታ፣ መሣሪያቸውን እያስረከቡ በመሸሽ ደብረ ታቦር ገቡ። ከዚያ ለነበረው አዛዥ የደረሰውን ሁኔታ ነገሩት። ይራራልናል ብለው እነሱም በርህራሄ እንደተለቀቁ አስረዱት። መቶ አለቃ ሚሳኖ ግን "...እናንተ ወገን ስለአላችሁ ተለቃችሁ መጣችሁ። ወገን የሌላቸው የእኛ ሹማምንቶች ከዚያው ሞተው ቀሩ..." ብሎ ከጦር ሜዳ ላይ በመሞት ፋንታ መሣሪያቸውን አስማርከው በመምጣታቸው ሰባ አራቱን ሰዎች ፊታቸውን እንዲያዞሩ አድርጎ በመትረየስ ፈጃቸው። ከጠላት ወዳጅ ይልቅ የወገን ጠላት እንደሚሻል በዚህ ታወቀ።

አርበኞች በተደጋጋሚ በአገኙአቸው ድሎች ተብራትተው፣ ደብረ ታቦርን ለማስለቀቅ ተንቀሳቀሱ። እስቴ ወረዳ ሲደርሱ፣ መክነ ኢየሱስ የነበረው ጣልያን ምሽጉን ለቅቆ ጉዞ ጀመረ። የመልዛ፣ የእብናት፣ የሐሙስ ወንዝ፣ የመቀጥዋ ሕዝብ በነቂስ ወጥቶ ከፊትና ከኋላ፣ ከቀኝና ከግራ ክብቦ በጥይት እየደበደበ ደብረ ታቦር አገባው። ይህንን ሲያይ፣ አገር ሲገዛ በየቦታው የተሠራጨው ጣልያን እየበረረ ደብረ ታቦር ተከተተ።

አርበኛው የደብረ ታቦርን ከተማ ከበበ። የጋይንር፣ የነገላ፣ የፋርጣ፣ የእስቴ፣ የሙጃ፣ የስማዳ፣ የቆማ፣ የጥናፋ፣ የሐሙስ ወንዝ፣ የመልዛ፣ የእብናት፣ የመቀጥዋ፣ የቋሲማ አርበኛ በጠላቱ ላይ ክንዱን ዘረጋ። ከመስከረም 15 እስከ 19 ቀን 1930 ዓ.ም ድረስ ተዋጋ። ጣልያንም በበኩሉ እየተከላከለ ከጎንደርና ከደሴ ረዳት ጠራ። ከጎንደር የመጣው የጠላት ጦር መሬቱን እያጥለቀለቀ በአገርና በፈረስ መጣ። አርበኛው ዓለም ሥጋ ላይ

ገጠመው። ፈረሰኛውን በጥይት ከፈረሱ ላይ ዘነጠፈው። ሳይሞት የሞተ እየመሰለ ከራሣ ውስጥ ከተደበቀው በስተቀር፣ እግረኛውን ለወሬ ነጋሪ ሳያስተርፍ ፈጀው። ብዙ ቀላል መትረየስና ጥይት፣ የእጅ ቦምብ ተማረከ። ያም ሆኖ ግን ደብረ ታቦርን ማስለቀቅ ሳይቻል ቀረ። ከአርበኞችም ወገን ዓርብ ገበያ፣ ዳንትና ገረገራ የወደቁትን ጨምሮ ሰባ አራት ታዋቂ አርበኞች ሞቱ፣ ብዙዎች ቆሰሉ።

በግራዝማች አረዳ ተሰማ አስተባባሪነት የሚንቀሳቀሰው የአርበኞች ቡድን መስከረም 15 ቀን 1930 ዓ.ም አማኒት ከተባለው ቦታ ላይ ጦርነት አካሂዶ የመጣበትን ጠላት መለሰ። በዚሁ ወርና ዘመን ጠላት ወደ ቋራ ለመሄድ በሚንቀሳቀስ አንድ የአርበኞች ቡድን ላይ አደጋ ጣለ። በጦርነቱ የአርበኞቹ መሪ ዓይናቸውን ተመቱ። ቢሆንም ሳራቆ ሄዶው በማገገም ከወር በኋላ የአርበኝነት ሥራቸውን ለመቀጠል ቻሉ።

ከደሴ የተጠራው ጦር የወሎን፣ የየጁን፣ የአምባሰልን ባንዳ አጋትሎ ተንቀሳቀሰ። በጀነራል ቶሲቲ እየተመራ በደላንታና በዋድላ አድርጎ ጋይንት፣ ጨጨሆ ከተባለው ቦታ ሠፈረ። አርበኞች ጋንጋ የተባለውን ተራራ ይዘው ጥቅምት 13 ቀን 1930 ዓ.ም ገጠሙት። ከወሎ የመጣው የጠላት ጦር የመጀመሪያው ነበርና ውጊያው ከባድ ሆነ። ጠላት በቦምባርድ፣ በመድፍና በመትረየስ፣ እጅግ ብዛት ባለው ሠራዊት በመዋጋት የገጠሙትን አርበኞች ከአለቃ እስከ ጭፍራ ደምስሶአቸው አለፈ። የደብረ ታቦሩ የጦር አዛዥ የአርበኞችን የጦር ሥልት ስለተላመደው የመጣለትን ረዳት እንዳይጨርስበት ሊቀበለው ወጣ። ክምር ድንጋይ ሲደርስ የፋርጣ፣ የስማዳ፣ የሰዴ፣ የሙጃ፣ የቆማ አርበኛ በየአለቃው እየተሰለፈ ወጋው። ቢሆንም የጠላት ጦር በኃይል እየገፋ ክምር ድንጊይ ደረሰ። ከደሴ የመጣውን ጦር ደግሞ የጋይንት አርበኞች በስተምዕራብ፣ የነገላ በስተሰሜን ሆነው ጠዘጠዙት። እሱም በእጅ በምብና በመትረየስ ብዛት ማህሉን ጥሶ ነፋስ መውጫ ደረሰ። የደብረ ታቦሩና የደሴው የጠላት ጦር ጉሎጊ ወንዝ ላይ ተገናኘ።

አርበኛውም በበኩሉ ተስፋ አልቆረጠም። ከወደ ወሎ ወገን የጋይንት፣ የነገላ፣ የመቂት አርበኛ፣ ከጎንደር ወገን ደግሞ የፋርጣና የስማዳ፣ የቆማ አርበኛ ገጠመው። የማዶና የማዶውን የጠላት ጦር በጥይት ሸነቆጠው። ጦርነቱ ዚአክ ለዚአየ የተባለውን የገንፎ አበላል አይነት ሆነ። ቢሆንም ጣልያንን ማገድ አልተቻለም። ሁለቱም ጦር ተቀላቅሎ እየተዋጋ ጥቅምት 15 ቀን 1930 ዓ.ም ደብረ ታቦር ገባ። በልጅ አበራ ረዳ የሚመሩ አርበኞች ጥቅምት 17 ቀን 1930 ዓ.ም ጭልጋ፣ መቀነት ኪዳነ ምህረት በጠላት ላይ አደጋ ጥለው ሃያ ጠመንጃ ከነጥይቱ ማረኩ።

ከጎንደር ወደ ደብረ ታቦር የሚወስደውን የመኪና መንገድ ዓለም ሥጋ ላይ አርበኞች መስከረም 29 ቀን 1930 ዓ.ም ቆርጠውት ስለነበር ጣልያን እሱን አልሶ ለመሥራት ሞጣ። ሀገሩን ለማላመን አላምን ካለም

ለማጥፋት የሚያስችለው ከፍተኛ ጦር እምጥቶ መደብና ውዶ ከሚባሉት ቦታዎች ላይ አሠፈረ። አርበኛው ኮካ የተባለውን በር ይዞ ሲቻለው እያጠቃ፣ ሳይቻለው እያፈገፈገ ተከላከለ። ጥቅምት 18 ቀን 1930 ዓ.ም ከጥዋቱ አንድ ሰዓት ጀምሮ ሙሉ ቀን ተዋጋ። አሞራ ገደል፣ አልጋ ጭንጫ ከተባለው ቦታ ለመገናኘት ተቃጥሮ፣ መደብና ውዶ ከተባሉት ሁለት ቦታዎች የተንቀሳቀሰው የጠላት ጦር፣ ከተቃጠረበት ቦታ ሳይደርስ መሸበት። ጥሶ ለመሄድም የማይቻለው ስለሆነ ደንጉርማ ከተባለው ተራራ ላይ ሠፍሮ አደረ። ምሽቱ ስለአገዛቸው ተከበው የነበሩት አርበኞች ሰብረው ወጡ። በዚህ ቀን በተደረገው ጦርነት ሼህ አሊ የተባለው ቀንደኛ ባንዳ ተገደለ። ከደብረ ታቦር እስከ ጨጨሆ በተደረገው ጦርነት አርባ አምስት አርበኞች ሞቱ፣ ሁለቱ የጦር ፊታውራሪዎች ነበሩ።

ጣልያን በጥቅምት ወር 1930 ዓ.ም አውሣ፣ ጀጉል ባንባ በተባለው ቦታ ላይ ጦርነት አደረገ። ላይቀናው ስለቀረ አውሣ ከነበረው ምሽጉ ተመልሶ ገባ። በድጋሚ ሊዘምት ሲዘጋጅ በአቶ ባሕታ አሥራት የሚመራው አርበኛ ሐሙስ ቀን የከበበ እስከ ዓርብ ማታ ድረስ ያለዕረፍት ወጋው። ጣልያንም በሌሊት አምልጦ መተማ ገባ። በዚህ ጦርነት አርበኞች አንድ የውሃ መትረየስ፣ አንድ ቢዛንቲ መትረየስ፣ አሥራ ስድስት ረዳጅም አልሜን ማረኩ። አሥራ አምስት ካሚዮኖች በእሳት እንዲቃጠሉ ተደረገ። ሦስት አርበኞችና አሥራ አምስት የጠላት ወታደሮች ሞቱ።

በስማዳ ወረዳ የነበሩትን አርበኞች ለመደምሰስ ጣልያን ጦሩን አንቀሳቀሰ። አርበኞችም ቀንበር በር ላይ ጠብቀው ሀዳር 13 ቀን 1930 ዓ.ም ጥዋት ገጠሙት። ቦታው ተመርጦ የተያዘ ነበርና ለአርበኞች አመቸ። ጦርነቱ እስከ ስምንት ሰዓት ቀጠለ። እረይ መንግሥቱ የተባለ በአንድ መዝገብ ሻርታ/መትረየስ፣ አምስት የጠላት ወታደሮች በመጣል፣ የዕለቱን ጀብዱ ጨበጡ። የጠላት ጦር አዛዥ ተከቦ አድሮ፣ በማግስቱ ጥዋት እጁን ሰጠ። ብዙ መሣሪያ ተገኘ። ከአርበኞች ወገን የቆሰለ አንጂ የሞተ አልነበረም።

የስማዳ፣ የጥናፋና የቆማ አርበኛ፣ አስቴ፣ ቁት አምባ የነበረውን የጠላት ጦር ህዳር 22 ቀን 1930 ዓ.ም አጠቃ። የጠላትን ጦር ከአካባቢው ለመንቀል ዙሪያውን ከብቦ፣ በአሰው መሣሪያና ኃይል ተዋጋ። በሦስተኛው ቀን ጠላት በላለበት ወገን ሰብሮ በመውጣት፣ ወደ ደበረ ታቦር ሸሸ። አርበኛው እየተከታተለ ቢወጋውም ከደብረ ታቦር ኮሎኔል አንጀሊኒ ፈረሰኛ ጦር ይዞ መጥቶ ስለረዳው ዳነ። በዚህ ቀን ብቻ 18 አርበኞች ሞቱ። መሰንበቻውን በተካሄደው ያለቀው ግን ብዙ ነው። ከቆማ አርበኛ ብቻ አርባ አምስት አርበኞች ሲሞቱ፣ ሌሎች ሰድሣ ሰባት ቆስለዋል። ሰዋት ተማርከው በጠላት እጅ ተገድሰዋል። ከጠላት ወገን የሞተው እጅግ ብዙ ነበር።

በህዳር ወር 1930 ዓ.ም ጠለምት አድ ወሰኔ ላይ የነበረው ጣልያን የአርበኞችን ቤተሰቦች ሰብስቦ አሥር ቤት አጐረ። ምሥጢሩ አርበኞቹ

ለዘመዶቻቸው ብለው ሲገቡ አብሮ ለመጨረስ መሆኑ ታወቀ። አርበኞች በፊናቸው ምሽጉን አጥቅተው ወገኖቻቸውን በኃይል የሚያስለቅቁበት ዕቅድ አዘጋጅተው ከሌሊቱ በስምንት ሰዓት አደጋ ጣሉ። ከንጋቱ በሦስት ሰዓት ጠላት ምሽጉን ለቅቆ ሸሸ። ከታሠሩት ስምንት ቤተሰቦች አንዲቱ ብቻ ስትቆስል የቀሩት በጤና ወጡ። ሁለት መቶ አልቤን ጠመንጃ ከነጥይቱ ከምሽጉ መጋዘን ተገኝቶ አርበኞች እጅ ገባ። ጣልያን እነዚህን አርበኞች ለማጥፋት ብዙ ጦርና ባንዳ አስከትቶ መጣ። አርበኞችም ጠለምት ወይላ ከተባለው ቦታ ገጥመው በመውጋት ወደ መጣበት መለሱት። ቦታው የመሬት አንጋዳ ስለሆነበት ጠላት ብዙ ጉዳት ደረሰበት። አርበኞች ከጥዋቱ አምስት ሰዓት ጀምረው እስከ ምሽቱ አሥራ ሁለት ሰዓት ድረስ ባካሄዱት በዚህ ጦርነት ከድል ጋር ብዙ ምርኮ አገኙ።

ቀደም ብሎ የደረሰበትን ሽንፈት ከሕዝብ መንፈስ ለመፋቅ ጣልያን ተንቀሳቀሰ። አርበኞች ምቹ ቦታ ይዘው በመጠበቅ ቤዛሆ ላይ ታህሣሥ 3 ቀን 1930 ዓ.ም ገጠሙት። የተወለደበትን ቀን እስኪረግም በጥይት ቀጥቅጠው አባረሩት። ሃምሣ ሰበን ጠመንጃዎች ማረኩበት።

ጣልያን ሃያ ሺህ ጦር ይዞ ከደብረ ታቦር ተነሣ። ስምንቱ ሺህ እጅጉ አያሌው በተባለ ሰው የሚመራ ባንዳ ነበር። የጦሩ ብዛት በሀገሩ ላይ ጭንቀት አሳደረ። አርበኞች የቻልነውን ያህል ሠርተን እንሙት ብለው ሰጦርነቱ ተዘጋጁ። ታሳቅ ፀሎት አድርገው ታህሣሥ 12 ቀን 1930 ዓ.ም ስምና ከተባለው ቦታ ላይ ግንባር ለግንባር ገጠሙት። ጦርነቱ ሲደራ ሽማግሌው፣ ሴቱ፣ ልጁ፣ አሮጊቱ፣ መንቀሳቀስ የማይችለው ሽባው ሁሉ በያለበት ሆኖ ጮኸ፣ በለው! ወጣልህ! ወረደልህ! በማለት ተንጫጫ። ጫጫታው ስለአስደነገጠው ባንዳው ተፈታ። የባንዳው መሪ እጅጉ አያሌውም ከፈረሱ ላይ ሆኖ ሽሽቱን ያዘ። መደበኛው የጣልያን ጦርም በሁኔታው በረገገና ሽሽቱን ያዘ፣ አርበኛው በየጉጡ በጥይት ጠበሰው። የጠላት ጦር ሲጨነቀው መሣሪያውን በጨርቁ ላይ እየደረደረ ለአርበኛው ያስረክብ ገባ። ገሚሱም ዓይኑ እያየ ገደል ገባ። አጋምና ቀጋ፣ ጉመሮና ቀንጠፋ እየጠለፈ ያስቀረው መሣሪያ ብዙ ነበር። በየቦታው የተደረደረውን መሣሪያ አርበኛው አነሣ። በየጥሻው የወደቀውን መሣሪያና በየሜዳው የፈሰሰውን ጥይት ሴቱ፣ ልጁ እየለቀመ በጠፍር፣ በገመድ እንደ አንጨት እያሠረ በመሸከም አጋዘው።

አርበኛው ልቡ እየደነደነ ስለሄደ፣ የማጥቃቱን ሥራ አጠናከረ። ጣልያንም በበኩሉ ባንዳን አበረታታ። ሰሜኔ ልጅ ሐደራ ረዳ የተባሉትን፣ አርበኛ የነበሩትን ሰው፣ በጓደኞቻቸው ላይ ያደረባቸውን ቅያሜ ተጠቅሞ አስክዳቸው። ከዚያም "ደኃዝማች ብትገድል ደኃዝማች፣ ፊታውራሪ ብትገድል ፊታውራሪ እልሀለሁ" የሚል ደብዳቤ ፃፈላቸው። ሞኝ እንደመሰሉት ገድዬ እሸማለሁ ብለው ሲውተረተሩ፣ የጥንፍራ አርበኛ፣ አዘነበ በተባለው ቦታ ላይ በተደረገ ጦርነት ማረካቸው።

በአዝማች ታጅበ ካሣ መሪነት የዘመተው ባንዳ፣ ካርዋ ላይ፣ በፊታውራሪ አሰፋው ኃይለማርያም የሚታዘዝ ጦር ይዞ የመጣው ጣልያን፣ ሱባ ላይ፣ በፊታውራሪ ኮከቤና በፊታውራሪ አውደው ፈለቀ እየተመራ የመጣው፣ ግልቢና ላይ፣ በፊታውራሪ መንገሻ የሚመራው፣ ጭንፍራ ላይ፣ በፊታውራሪ አሰፋው ኃይለማርያም አዝማችነት ሰሁለተኛ ጊዜ የዘመተው፣ ጥጉና ላይ፣ በመምህር ገብረዋህድ አስናቀው የሚታዘዘው ባንዳ፣ ደንቆላክ ረድ ላይ፣ በሙሉ ድል እየተመታ አለቀ። ዮሴፍ አባዘርጋው የተባለውን የባንዶች አለቃ ፊታውራሪ ከዴ የተባሉት አርበኛ ብቻ ገጥመው ገድለውት ሞቱ። የቆሰለውም ከጣልያን ማንገሚያ እንኒን ሳያገኝ ደምና መግሉን እያንጠፈጠፈ ከጥቅም ውጭ ሆነ። በዚህ ሁኔታ ባንዳ ልብ ወረደው። ጣልያን ጥሩምባ ባስነፋ ቁጥር፣ ማረጥረጡን ተወ።

ይህ ሲሆን ጣልያን መደበኛ ወታደር በየጦሩ ጉራ ማዝመት ያዘ። ጥር 5 ቀን 1930 ዓ.ም በሁመራ ወደ ቀብትያ ወታደር በካሚዮን ሲያመጣ፣ በፊታውራሪ መሥፍን ረዳ የሚመራው አርበኛ ከማጀ መልስ ከተባለው ቦታ በጥይት ጠመደው። ብዙ ጣልያኖች ሞቱ። ሳያንሣ ጥሉአቸው የሄዱ ሰባት ቁስለኞች ከሜዳ ላይ ወድቀው ሞሶሎኒንና የተወለዱበትን ቀን ሲረግሙ ታይተዋል። የተረፉት ጣልያኖች በመኪና ጉራውን ሰብረው ቀብትያ ገቡ። ጥር 10 ቀን 1930 ዓ.ም ደንቢያ ላይ እንደዚሁ ጦርነት ተደረገ። አርበኞች ደንቢያ ቸንከል ከተባለው ቦታ የነበረውን የጣልያን ምሽግ በዚህ ዕለት አጥቅተው ሸብር ለቀቁበት። በጦርነቱም ጥቂት ከብትና አሥር ጠመንጃ ከጥይት ጋር ማረኩ።

አርበኞች ከቀብትያ ወደ ኤርትራ የሚወስደውን መንገድ ለመቁረጥ ድልድዩን መሥበር ጀመሩ። ጣልያን በድብቅ መጥቶ ጥር 12 ቀን 1930 ዓ.ም እጣን አብኒ ላይ አደጋ ስለጣሰባቸው፣ በድንገት ጦርነት ተከፈተ። አርበኞች በፍጥነት ተበትነው በየሥርቻው በመግባት ተከላከሉ። ጣልያን ያሰበው በሥራ ላይ እንደአሉ ለመፍጀት ነበርና፣ እንዳመለጡት ሲያይ ተመልሶ ቀብትያ ገባ። በዚሁ በጥር 12 ቀን ሌላው የአርበኞች ቡድን ጭልጋ በነበረው የጠላት ምሽግ ላይ አደጋ ጥሎ አካባቢውን አሸበረ።

ጥር 1 ቀን 1930 ዓ.ም በግራዝማች ረዳ ተሰማ የሚመራው የጭልጋ አርበኛ፣ አንጓባ ላይ መሽጉ የነበረውን ጣልያን ከብቦ በብዙ አስጨነቀው። ይኸው የአርበኞች ቡድን የአይክልን ምሽግ ከብቦ ሲዋጋ ሰንብቶ፣ ሠብሮ ለመግባት እንደ አልተቻለው ሲገነዘብ ወደ ይዛ ተመለሰ። አንደዚሁም ሚያዝያ 25 ቀን 1930 ዓ.ም አውጋ፣ ወገሚት ወንዝ አደጋ ጥሎ፣ በጠላት ላይ ጉዳት አድርሶአል። ይህ ቡድን የሚጠቀምበት ሥልት በየአለበት፣ በየጊዜው አደጋ እየጣሉ ጠላትን ማጥቃት፣ ማበሳጨትና በሕዝብ ዘንድ የነበረውን ተአምር መቀነስ ነበር።

የጀንዋራ፣ የቆላ ወገራ፣ የአርማጭሆ፣ የጠገዴ፣ የደለሎ፣ የደብረ ሐዋርያ፣ የቀብትያ፣ የአውሣ፣ አርበኞች ተሰብስበው የወልቃይትን ሕዝብ ነፃ ለማውጣት ተማከሩ። ምክሩ 5 ቀን ወሰደ። የአድረመድን ምሽግ በመስበር በዚያ የነበረውን የጠላት ኃይል ለመደምሰስ ተወሰነ። ጣልያን ምክሩን ሰምቶ አድ ኮከብ ላይ ሠፈረ። አርበኛው ሌሊቱን ሲሣብ አድሮ የካቲት 30 ቀን 1930 ዓ.ም ከንጋቱ 11 ሰዓት አደጋ ጣለበት። ከባድ ውጊያ ተካሄደ። ከጠላት ሠራዊት እኩሉ ፈቱን ወደ ማይ ወላሞ፣ እኩሉ ወደ አውራ፣ እኩሉ ወደ አድረመጥ ሸሸ። አርበኛ እግር በእግር እየተከታተለ በጥይት ደበደበው። የጠላት ወታደር ሬሣ በአንዳንድ ቦታ እንደ ክምር ተቆልሎ ነበር። ከአርበኞች ወገን ሃምሣ ስድስት ታዋቂ አርበኞች ሞቱ። ከአድ ረመጥ በስተቀር ሌላው የወልቃይት ወረዳ ነፃ ወጣ። አርበኛው ነፃ ለወጣው ሀገር አስተዳዳሪ ፊታውራሪ መሥፍን ረዳን መርጦ ወደየስፍራው ተመለሰ። ጣልያን ይህንን ጦርነት ለመበቀል ልጅ አዋቂ፣ ወንድ ሴት ሳይል ብዙ ሰው ፈጀ። ብላንባ ከተባለው ቀበሌ ብቻ ሃምሣ ስምንት ነፍስ ገደለ።

የቋራው የጣልያን አገረ ገዥ በአካባቢው የነበሩትን አርበኞች የሚያጠፋለት ጦር ላከ። ጦሩ ጥቂት ባንዶች የተቀላቀሉበት መደበኛ ጦር ስለነበር ቀላል አልነበረም። አርበኞች ጀሆ ላይ ጠብቀው መጋቢት 17 ቀን 1930 ዓ.ም ገጠሙት። ከቀኑ ስድስት ሰዓት እስከ ምሽቱ 12 ሰዓት ወግተው መልሰው ወደ መጣበት አባረሩት። ጠላት ይህንን ጥቃት ለመመለስ ሌላ አዲስ ጦር ይዞ መጣ። በደጃዝማች አያና ቸኮል የሚመራው አርበኛ አዲስ የመጣውን ጦር ሠራቆ አባዩ ከተባለው ቦታ ላይ ገጠመው። ጦርነቱ ስለአየለ የአውሣ፣ የጫቆ፣ የተንከል፣ የአርማጭሆ አርበኞች ለአርዳታ በግሥጋሴ ደረሱ። ጣልያን ቀን ሲመሸለት ሌሊት አምልጦ ሟራ ገባ። አርበኛው ተከታትሎ ሄዶ ምሽጉን ከበበ። ከመጋቢት 25 እስከ ሚያዝያ 1 ቀን 1930 ዓ.ም በመዓልትና በሌሊት ሳያቋርጥ ወጋው። በሩን ሠብሮ በመግባት የአገረ ገዥውን ቤት የሚጠብቁትን ዘበኞች መሣሪያ እስከ መንጠቅ ደረሰ። ሆኖም ጠላት ከመተማ ሌላ ጦር አስመጥቶ ከባባውን አፈረሰ። አርበኞችም ምርኮአቸውን ይዘው ወደ ሠራቆ ተመለሱ። በዚህ ጦርነት ከጠላት ወገን ብዙ ወታደር ሞተ። ከአርበኞችም አምስት ጀግኖች ወደቁ።

ጣልያን ግንቦት 1 ቀን 1930 ዓ.ም ከጭልጋ ወደ መተማ ለመውረድ ተነሣ። ዋሊ ደባ ከተባለው ቦታ ሊደርስ አርበኞች ገጥመው በጦር ኃይል ወደ መጣበት ምሽግ መለሱት። ምርኮም አገኙ፣ በርካታ የጠላት ወታደር ገደሉ፣ አቆሰሉ። ከእነሱ የሞቱባቸው ሁለት ጀግኖች ብቻ ሲሆኑ አንዱ ቁስ ናቸው።

ወልቃይት የተባለው አገር ለማጥፋት ጣልያን በሻለቃ ፍራንቻሲ የሚመራ አምስት ባታልዩን ጦር ከወልቃይት አንቀላቀስ። ይህንን የመሰለው አገር የማጥፋት ዘመቻ መቆም ስለነበረበት ሰባት አርበኞች በደጃዝማች ደስታ ማሩ መሪነት ግንቦት 5 ቀን 1930 ዓ.ም አዲ ገርትየ ከተባለው ቦታ

ገጠሙት። ምንም ቦታው ምቹ ቢሆንላቸው አርበኞች የመጣውን ጦር ማገድ አልቻሉም። ስለዚህም እያፈገፈጉ እርምጃ በእርምጃ በመከላከል የሁለት ሰዓት መንገድ ሦስት ቀን እንዲወስድበት አደረጉ። የአካባቢው አርበኛ እየተባበራቸው ቁጥራቸው እስከ አርባ አምስት ደረሰ። አርበኛው በትንንቅ አንድ መትረየስ ማረከ። ያለማቋረጥ ከአፋፍ ላይ የሚተኮሱት የጣልያን መድፎች አንዳች ፍንዋት አላስገኙም። በዚህ ታላቅ ትንቅንቅ ስለተጠመደ ጠላት ከአሰበበት መድረስ ሳይቻለው ቀረ። ወደኋላው ተመልሶ አድ ረመጥ ገባ። አርበኛው ሁለት ሻምበሎች፣ አንድ መቶ አለቃ፣ አንድ ሃምሳ አለቃ ከብዙ ወታደር ገደለ። ሁለት መትረየስና ሠላሳ አምስት ጠመንጃ ከበርካታ ጥይት ጋር ማረከ። መትረየስ ለመንጠቅ በመተናነቅ በቻ ስምንት ጀግኖች ወደቁ። ሌሎች ብዙዎች በፍልሚያ ላይ ሞቱ፣ አገሩ ግን ከጥፋት ዳነ።

ወልቃይት፣ አድ ኮከብ በተደረገው ጦርነት ለደረሰበት ውርደት፣ ሰላማውያን ሰዎችን እንደ ማካሻ የመፍጀት ሥራው ሳያዋጣው ቀረ። አዲስ ጦር በማምጣት፣ በታማኝ የወልቃይት ሰላዮች እየተመራ የአዲገርትየን ቁልፍ በር አርበኞች ሳይለሙ አልፎ ምድረ ወይዘሮ ደረሰ። ለአርበኛው ዱብ ዕዳ ሆነበት። ደግሞም መሪው ልጅ ደስታ ማሩ ታመው ነበርና፣ ለጊዜው ተደነጋገረ። ሆኖም ልጅ ደስታ በቶሎ ተነስተው የአዋጊነት ሥራቸውን ያዙ። የጠገዴ፣ የደሰሎ አርበኛም ለዕርዳታ ደረሰ። አባ ብሩ፣ አባ ገብራይ፣ አባ ወልደ ሚካኤልና አባ ገብረ ማርያም የተባሉ መነኮሳት በመስቀሎቻቸው ምድሪቱን እየባረኩ፣ የሚሸሸውን እየገዘቱ ከማሀል ቆመው አዋጉ። የጣልያኑ ጦር አዝማች ራውጂኒ የተባለ ጉበዝ ኮሎኔል ነበር። እንደእሱ ያለ ተዋጊ አርበኞችን ንጥሞአቸው አያውቅም። የሠሩትን የጦር ብልሀት በመትረየስ እያስደበደበ ያፈርሰባቸው ነበር። ቢሆንም አርበኞች ተስፋ አልቆረጡም፣ በርትተው ተዋጉ። ጦርነቱ ሰኔ 10 ቀን የጀመረ ምንም ሳያቋርጥ እስከ ሰኔ 21 ቀን 1930 ዓ.ም ድረስ ቀጠለ። ኮሎኔል ራውጂኒ ምንም ጀግና ቢሆን መሸሽ ግድ ሆነበት። አርበኞች የያዙትን የወለል በር በኃይል ሰብሮ ጠገዴ መስፍናት ገባ። በጦርነቱ ጣልያን ቢሸሽም ድል የእሱ እንደሆነ ተቆጠረ። አርበኞች ተጠቅተው ነበር። ከጠላት ያለቀው እጅግ ብዙ ነው። ከአርበኞች ወገን አርባ ስድስት ሞቱ፣ ሌሎች ብዙዎች ቆሰሉ። ምርኮም አልተገኘም።

የአርበኞች ጥንካሬ ጣልያንን ስላስቆጣው፣ ክረምቱ ከመግባቱ በፊት ሊደመስሳቸው አሰበ። የጐንደሩ፣ በትክል ድንጋይ፣ የአምባ ጊዮርጊሱ፣ በመረባ፣ የዳባቱ፣ በጀንዋራ፣ የደባርቁ፣ በበዛ፣ የወልቃይቱ፣ በጠገዴ፣ የጭልጋው፣ በዋሲዳባ፣ ለመውረድ ማቀዱ በአሞራው ውብነህ ተሰማ። አርበኛውም በበኩሉ የጠላቱን ዕቅድ የማሰናከያ ዕቅድ አደራጀ። ዕቅዱም ጠላትን በየወጣበት በር እየወጉ ወደ የመጣበት መመለስ፣ ከተቻለም እየተከታተሉ ከምሽጉ በመግባት ማጥቃት! ይህንንም ለማድረግ እርስበርስ መረዳዳት ነበር። እንደ አቀደውም አደረጉ። ከጐንደር የተነሣውን

የአርማጭሆና የክች በዱር አርበኛ፣ በደጃዝማች ብሬ ዘገየ መሪነት፣ የጀኔ ፈንቀራ አርበኛ፣ በደጃዝማች ጫኔ መሪነት፣ በአምባ ጊዮርጊስ የመጣውን የመረባ አርበኛ፣ በደጃዝማች ዋናው አንዳርጌ መሪነት፣ በዳባት የወረደውን፣ በደጃዝማች ጌታው ዘረፉ መሪነት፣ በደባርቅ የወረደውን የቆላ ወገራና የበዛ አርበኛ፣ በደጃዝማች ሀጐስ ተሰማ መሪነት፣ በወሲደባ የወረደውን የጭልጋና የጫቆ፣ የሣቤራ፣ የአዳኝ አገር አርበኛ፣ በግራዝማች ረዳ ተሰማ መሪነት፣ በዳሞ የወረደውን የዳሞ አርበኛ፣ በደጃዝማች በላይ መኰንን መሪነት ገጠመው።

ከሜዳው ላይ ሲያቅተው፣ በሥልት እያፈገፈገ ከቆላው አስገባው። ሁለትና ሦስት፣ ሦስትና አራቱ በቡድን፣ በቡድን እየሆነ፣ ከዛፍ ላይ እየተሰቀለ፣ ከድንጋይ ውስጥ እየተቀረቀረ ተሰቀቀበት። ከአንዱ ቦታ ሲያጠቃ፣ ወደ ሌላ ቦታ እየተዘዋወረ በነፍሱ ተጫወተበት። የጣልያን ጦር ኃይልና ስንቁን፣ መሣሪያውን ሊጨርስ ወደየመጣበት ተመለሰ። በተለይ በበዛ የወረደው ግን፣ ድብል ገሣ ከተባለው ቦታ ላይ ሠፍሮ፣ እስከ መስከረም ድረስ ሲዋጋ ቆይቶ፣ የማይዘልቀው መሆኑን ሲረዳ ጥሎ ሄደ። አገሩ ከጥፋት ዳነ። ከጠላትም፣ ከአርበኞችም ወገን ብዙ ሰው ሞተ።

ሃያ አምስተኛ፣ ሰባ ሰባተኛና አርባ ስድስተኛ ተብሎ የተመደበው የጣልያን መደበኛ ጦር፣ አርበኞችን ለማጥፋት በአራት ተከፍሎ ዘመተ። አርበኛውም በአራት ቡድን ተዘጋጅቶ፣ አማኒት ላይ ሰኔ 22 ቀን 1930 ዓ.ም ገጠመው። ሁለት ቀን ሙሉ ወግቶ፣ ብዙ ወታደር ገድሎ፣ ወደ መጣበት መለሰው። ቦታው ስለተመቻቸው አርበኞች፣ እምብዛም አልተጉዱም። ሁለት አርበኞች ሲሞቱ አንድ ሰው ቆሰለ።

ደብረ ታቦር የነበረው የጣልያን ሠራዊት የጭካኔ ሥራውን በሕዝብ ላይ ለመሥራትና አርበኞችን ለመደምሰስ፣ የአምስት ወር ስንቅ ይዞ ከደብረ ታቦር ሰኔ 21 ቀን ተንቀሳቀሰ። ይህ ሁኔታ ከባድ ስለሆነ፣ አርበኛው ከየአለበት ተጠራርቶ ተሰበሰበ። የነገሌና የጋይንት፣ የፋርጣ አርበኛ ለሠርግ እንደተጠራ በደስታ ወጣ። ጠላት አሸማ ከተባለው ኮረብታ ላይ መድፍ እንዳይጠምድ ተከላከለ። የቤገምድር አርበኛም ደረሰ። ጠላትም ኪና ከተባለው ቦታ ተነስቶ፣ ፍቼ ከተባለው ቦታ ከነበረው ወገኑ ጋር ተቀላቀለ። በዚህ ጊዜ ጦርነቱ በረታ። ከከባድ ውጊያ በኋላ የጠላት ጦር ሽሽት ጀመረ። ምሽት ገላገለው። በበነጋታው ሰኔ 22 እና ሰኔ 23 ቀን 1930 ዓ.ም ጦርነቱ ቀጠለ። ሰኔ 24 እና ሰኔ 25 ቀን 1930 ዓ.ም ቀንም ውጊያው ሳይበርድ ሰነበተ። የቤገምድር አርበኞች ለአርዳታ የደረሱ ቢሆንም፣ አዛውር የነበረውን ምሽጉን ማስለቀቅ አልተቻለም። ጣልያንም ከምሽጉ ወጥቶ መንቀሳቀስ አልቻለም። ከጠላት ወገን ያለቀው ወታደር በጣም ብዙ ነበር። በአዛውርና በፍቼ ከሰኔ 22 እስከ 26 በተደረገው ጦርነት፣ ሃምሳ ሦስት ታዋቂ አርበኞች መሞታቸው

ተዘግቦአል። በመጨረሻም ጣልያን ሰኔ 26 ለ27 አጥቢያ ሌሊት ሸሽቶ ደብረ ታቦር ገባ። አርበኞች አልጠረጠሩም ነበርና ጉዳት አላደረሱበትም።

ጦርነቱን ለማፋፋም ባንዳውን ማስታገስ አስፈለገ። ባንዳውን ለማስታገስ የሚቻለው ደግሞ፣ እጅጉ አያሌው ሲካክም ሆኖ ተገኘ። ስለዚህ በስምንት የጎበዛዝት አለቆች የሚመራው ጦር በህብረት መከረ። እሺ ቢል በፍቅር፣ እምቢ ቢል በጦር የእጅጉ አያሌውን ትብብር ለማግኘት ተወሰነ። የአዝማቾቹ አለቃ የነበሩት አቶ ጊዜ በሀሳቡ ተስማምተው እንቅስቃሴ ተደረገ። የአርበኛው ቀዳሚ ጦር ደራ ሰኒ ከተባለው ቦታ ሲደርስ ከጠላት ጦር ጋር በ1930 ዓ.ም ተገናኝና ተኩስ ተከፈተ። ድብልቅልቁ ወጣ። አርበኛው በክፉል ሽሽት ጀመረ፣ ገሚሱ ቆሞ ተዋጋ። ጠላትም የነበረበትን ቦታ ጥሎ ፈረጠጠ። ነገር ግን አቶ እጅጉ አያሌውን መያዝ ሳይቻል ቀረ። ከጠላት ወገን በርካታ ባንዳ ሞተ። ከአርበኞች ሦስት ጀግኖች ወደቁ።

ጣልያን ጉራዲት የተባለውን ቦታ ለመያዝ፣ ከደብረ ታቦር ተንቀሳቀሰ። አርበኞች የጉራዲት መያዝ ሥራቸውን ወደ ኋላ የሚገታባቸው ስለሆነ፣ ተቃወሙ። የዘመተውን የጠላት ጦር በ1930 ዓ.ም ወሰላ ባሕር ላይ ገጥመው አጥብቀው ተዋጉት። ቢሆንም ጠላት በኃይል ጥሶ ገባ። ጉራዲት ላይ ጠንካራ ምሽግ ሠራ፣ የአይሮፕላን ሜዳም አዘጋጀ። ነገር ግን ሊጠቀምበት አልቻለም። አርበኞች በየቀኑ ወጉት፣ በጥይት ነዘነዙት። ጠላት ሊሰለቸው፣ በዚያው በመሸገበት ዓመት ጥሎ ደብረ ታቦር ገባ። በተደጋጋሚ በተካሄዱት የሽምቅ ውጊያዎች፣ ስምንት አርበኞች ሞቱ፣ ሌሎች አራት ቆሰሉ።

ጣልያን መፈናፈኛ ለማግኘት፣ የአርበኞችን ኃይል መቀነስ አስፈለገው። በለሣ ላይ ደጉማ ካለው ምሽጉ ብዙ ባንዳና መደበኛ ጦር አዘመተ። በአርበኛውም ላይ በ1930 ዓ.ም ተደጋጋሚ አደጋ ጣለ። ቢሆንም አርበኛው በፈጣን እንቅስቃሴ ራሱን ከጥቃት እያዳነ መልሶ ወጋው። ጣልያንም ሽሽቶ ከዚያው ከምሽጉ ተከተተ። ደጎማ ላይ የነበረው የጣልያን ጦር እንደገና ተንቀሳቀሰ። አርበኛው ነሐሴ 11 ቀን 1930 ዓ.ም ከምሽጉ ብዙም ሳይርቅ ገጥሞ፣ አዛዡን አቁስሎ አባረረው። ብዙ መሣሪያም ተማረከ።

አርበኛው በተደጋጋሚ በተካሄዱት ውጊያዎች ስለቀናው፣ አርምጃ በርምጃ ወደ ጉንደር ከተማ እየተቃረበ ሄደ። አርበኞች ከምሥራቅ በኩል በከተማይቱ ላይ አደጋ ለመጣል እንደሚችሉ ስለገባው፣ ሁኔታው የሚያሰጋው ሆነበት። ስለዚህ ጣልያን አምባ ማልዲባና ከተባለውና ከሌሎችም ጉብታዎች ላይ መድፍ ጠምዶ ይደበድብ ጀመር።

ሁኔታው በእንዲህ እንደለለ ልጅ /ደጃዝማች/ አሰጋኸኝ አርአያ፣ ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ወረቀት ይዘው በነሐሴ ወር 1930 ዓ.ም ደረሱ። ይህ አጋጣሚ በአንድ ወገን የአርበኛውን ልብ ሲያደነድን፣ በሌላ ወገን የአርበኞቹን

አያያዝ የሚያስረዳ ዕሑፍ ለዓለም መንግሥታት ማህበር እንዲቀርብ በማድረጉ፤ የጣልያንን ውሸተኛነት በዓለም ህብረተሰብ ፊት ለማረጋገጥ አስቻለ።

በደጃዝማች ዋናው ተሰማ የሚመራው አርበኛ ነሐሴ 25 ቀን 1930 ዓ.ም ጭህራ በነበረው ጣልያን አደጋ ጣለ። ጣልያንም አልበገርም ብሎ ሦስት መዓልትና ሦስት ሌሊት የፈጀ ጦርነት ተካሄደ። በመጨረሻው ጣልያን አካባቢውን ለቅቆ ጉንደር ገባ። በጉንደር የተካሄደው የ1930 ዓ.ም ትግል በዚህ ዓይነት ተፈፀመ። ውሎም ሳያድር የ1931 ዓ.ም ተወጠነ።

መስከረም 7 ቀን 1931 ዓ.ም የደንብያ አርበኞች ወቀራኮ ከተባለው ቦታ ሊያጠፉቸው የመጣውን የጠላት ጦር ግንባር ለግንባር ገጥመው በመውጋት ድል አድርገው ወደ መጣበት መለሱት። ሆኖም ጣልያንን እስከ ምሽጉ እየሄዱ መውጋት በአርበኞች ላይ ጉዳት አመጣ። ሙጃ አንቆሽ የነበረውን ምሽግ ለማጥቃት የተደረገው ሙከራ በዚህ ምክንያት ሳይሳካ ቀረ። ስለዚህ ፊታውራሪ በረደድ አስፋው እንታረቅ የሚል መልዕክት አስተላለፉ። ጣልያንም እውነት መስሎት ሰማይ አፋፍ ከነበረው ምሽጉ ወጣ። ከተመች ቦታ ሲደርስ አርበኞች ከፊት ከኋላ መስከረም 12 ቀን 1931 ዓ.ም ከበው ጠዘጠዙት። ጣልያን ሸሽቶ ከምሽጉ ገባ። ምርኮው ያማረ ሆነ።

መስከረም 14 ቀን 1931 ዓ.ም ቤዛሆ ላይ ጦርነት ተደረገ። ነገር ግን ምንም ያህል ሳይዋጋ ጠላት ወደ ኋላው ተመልሶ አይክል ከተማ ገባ።

በአማራ አገረ ገዥ፣ በጀነራል ማዜቲ የሚመራ ጦር ጥቅምት 25 ቀን 1931 ዓ.ም ጀምሮ ተንቀሳቀሰ። ስምንት ቀን ሙሉ ሳያቋርጥ ተጉዞ አምባ ጊዮርጊስ ሠፈረ። ከዚህ በኋላ የጦር አዛዡ ከጉንደር ሲነሳ ሊሸኘው በትዕዛዝ ለወጣው ሕዝብ ፎከረ። የኢጣልያንን መንግሥት የሚቃወመውን ሕዝብ ሥሩን ነቅሎ ዳግመኛ አንዳያቆጠቁጥ እንደሚያደርገው ገለፀ። እንቁላል፣ ዶሮ፣ ወተት፣ እንጀራ እየያዘ የቀረበውን ሕዝብ እያስፈጀ ጉዞውን ቀጠለ። በበለሣ አንድ መቶ፣ በአይበ ሰባ ሰላማውያን ስዎች ሴት ወንድ፣ ልጅ አዋቂ ሳይል ፈጀ። ማርያም ውሃ ላይ አንድ አርበኛ ብቻውን ገጥሞ የቻለውን የጠላት ወታደር ረፍርፎ ሞተ። ምንም ከአቅም አንፃር ጣልያንን መክቶ ለመያዝ ባይችል በደጃዝማች ዳኘው የሚመራው አርበኛም ወጋው። በጠቅላላው ሃምሣ ሰባት አርበኞች መውደቃቸው በታሪክ ተመዝግቦአል። ከእነሱም ውስጥ አራት ካህናት፣ ሦስት ሴት መነኮሳት ነበሩ። ይህንን ያህል የጭካኔ ሥራም አካሂዶ ጀነራል ማዜቲ ውጤት ሳያገኝለት ቀረ። እራሱም ከሹመቱ ተሽሮ፣ ጀነራል ሉዊጂ ፍሩሺ ተሾመ።

ጥቅምት 16 ቀን 1931 ዓ.ም በደጃዝማች ዳኘው ተሰማ የሚመራው አርበኛ ጣልያንን እንፍዝራዝ ላይ ወግቶ ድል አድርጉ፣ ዘርፎ አባረረው። ጠላት የሀገር ማጥፋት ሥራውን ቀጠለ። አርበኞች ተሰባበስበው በህብረት በለሣ ጉሰና ላይ ወግተው አባረሩት። የጣልያን አመጣጥ እብናትና ሲበን

ለማጥፋት ነበር። ድል ክአደረጉት በኋላ የሚሸሸውን የጠላት ወታደር አርበኛው ከሀዳር 28 እስከ ታህሥሥ 5 ቀን ድረስ ያለማቋረጥ ከበለሣ ጉሰና እስከ አርብ ድረስ እያባረረ ወጋው።

በኮሎኔል አንጀሊኒ የሚመራ ጦር ከደብረ ታቦር ተነስቶ ተንቀሳቀሰ። ጥፍርና አንበሳ በር ሲደርስ፣ አርበኛው ጦርነት ገጠመው። በአንድ ኮሎኔልና በሁለት ሻምበሎች ከሚመራው ጦር አንድም ሳያመልጥ በአርበኞች እጅ ተደብድቦ እንደወጣ ቀረ። አንዱ ሲያልቅ ጠላት ሌላ ጦር እየተካ እምብዛም እረፍት ሳይኖር ውጊያው እስከ ሀዳር 7 ቀን 1931 ዓ.ም ድረስ ቀጠለ። በዚህ ጦርነት ከተማረኩት መሣሪያዎች ዋነኛው በለሣ ላይ የተማረከው መድፍ ነበር። እሱም በአርበኛ እጅ እየተተኮሰ የጠላትን ምሽግ ለማፍረስና ለማቃጠል በጣም ረድቶአል። ጠላት በአካሄደው የአይሮፕላን ድብደባ የክልቢ አቦ፣ የጅማ ጊዮርጊስ፣ የጐልቶች ተክለ ሃይማኖት፣ የአብናት ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያናት ተቃጥለዋል።

አርበኞች ጣልያንን የውሂ ከተባለው ቦታ በሀዳር ወር 1931 ዓ.ም ገጥመው በመውጋት ድል አድርገው ወደ መጣበት መለሱት። በዚህ ጦርነት ላይ የታየው አንድ አስደናቂ ነገር፣ ግራዝማች ረታ የተባሉት አርበኛ አትኩሮ ይመለከታቸው የነበረውን፣ አሥራቴ ጥሩነህ የተባለውን ባንዳ ተንተርሰውት መውደቃቸው ነው።

በዚሁ በ1931 ዓ.ም ጠላት በደጃዝማች ዳኘው የሚመራው አርበኛ ላይ አደጋ ጥሎ ለመደምሰስ ከደጎማ ተንቀሳቀሰ። አላጌ በር የነበረው አርበኛ ምሥጢሩን ቀደም ብሎ ደርሶበት ነበርና፣ ጉሉ ምሽግ ላይ ሳያስበው ገጠመው። ጦርነቱ ከጥዋት ሦስት እስከ ቀኑ ዘጠኝ ሰዓት ወሰደ። ክሩቅ የነበሩ አርበኞች ተኩሱን በመስማት ለአርዳታ እየመጡ ተሳተፉ። ከጠላት ወገን 25 ወታደር ሞተ፣ ሰባት ቆሰለ። ከአርበኞች ወገን ግን ሁለት ሞቱ፣ አንድ ቆሰለ።

በሀዳር ወር 1931 ዓ.ም አጠቃላይ ስብሰባ ተጠራ። በየወረዳውና አውራጃው የነበረው አርበኛ ተወካዮችን ላከ፣ የቻለም መጣ። ስለ ጦር ሥልትና ጠላትን በበለጠ ለማጥቃት ስለሚቻልበት መንገድ ምክር ተደረገ። በምክሩም ከዚህ ቀጥሎ በተመለከቱት ነጥቦች ስምምነት ተደረገ።

1ኛ. በበጌምድር ያለውን ጠላት መደምሰስና ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ እስኪመጡ የመረረ ትግል መቀጠል፣

2ኛ. የአንዱ ክፍል አርበኛ በጠላት ሲጠቃ ሌላው እንዲረዳ፣

3ኛ. ጀግንነታቸው ለተረጋገጠላቸው የአርበኞች መሪዎች ሹመት እንዲሰጥ።

በዚህ ስምምነት መሠረት ግራዝማች አሞራው ውብነህ ራስ አሞራው ውብነህ ተብለው ጠቅላይ አዛዥ ሆኑ። በእሳቸውም ሃምሣ ሁለት ደጃዝማች፣ ዘጠና ስምንት ፊታውራሪዎች ተሾሙ። ሹመቱ የተሰጠው በአርበኛው ምርጫ

ሲሆን፣ የምርጫው መሥፈርት ከትልቅ መወለድ ብቻ አልነበረም። አብሮት የተሰለፈው ሠራዊት ብዛት፣ ሠራዊቱን የሚያስተዳድርበት ጥረት፣ የተጐዳን የሚረዳ፣ ለጋሥ፣ ልበ ሙሉና ደፋር መሆን ነበረበት። ለእያንዳንዱ ተሿሚ ሀገር እየተሰየ ተሰጠው። የሥራ ኃላፊነቱ በጦር የተጐዳውን መርዳትና ተሰይቶ የተሰጠውን አገር በጠላት አለማስደፈር ነበር። የዚህ ሹመት መስጠት የአርበኝነትን ሥራ በእጅጉ አጠናከረ። ለመሪዎቹ ክብርና ሞገስ ሰጠ። ጠላትን ደግሞ አስደነገጠው።

በአፀፋው ጣልያንም ሹመት ሰጠ። በእሱ በኩል ከተሾሙት ደጃዝማች አያሌው ብሩ ራስ ተባሉ። አሥራ ሰባት ደጃዝማች፣ ሦስት ክቫሰር፣ አንድ ቢትወደድ፣ አንድ ጽራግማሠራ፣ አንድ መልአከ ሕይወት፣ አምስት የአድባራት አለቆች በከፍተኛ ደረጃ ተሾሙ። ከእነሱም በታች ስድሳ አንድ ፊታውራሪዎች፣ አንድ አዝማች፣ አንድ አፈንጉሥ ነበሩ። የቀኛዝማች፣ የግራዝማችና የባላምባራስነት ማዕረግ የተሰጣቸው እጅግ ብዙ ነበሩ።

ለአርበኞች መሪዎች የተሰጠው ሹመት ሙቀትና ድምቀት ጣልያን ከሰጠው የበለጠ ሆነ። ጣልያን ሹመት ለመስጠት የተገደደው በአርበኞች በኩል የተሰጠውን ሹመት ለማርከስ አሥራ ሁለት ቀን ሙሉ ጦርነት አካሂዶ እንዳልተበገሩለት ካየ በኋላ ነበር።

ጣልያን ብዙ ሠራዊት ከጐንደር ሰብስቦና ከአሥመራ አስመጥቶ በአዲስ ኃይል አንቀሳቀሰ። በራስ ውብነህ የሚመራው አርበኛ ቦታ እየለዋወጠ ብዙ በማንከራተት ከአደከመው በኋላ፣ ዘመቻውን ትቶ ሊመለስ ሲዘጋጅ አርበኛው በዚያው በህዳር ወር 1931 ዓ.ም ጉረንክ ላይ አደጋ ጣለበት። ብዙ ወታደር ፈጀቶ፣ ካሚዮኖች እኩሉን አቃጥሎ እኩሉን ዘርፎና ሰባብሮ ወደ አምባ ጊዮርጊስ አባረረው።

ጣልያን ገበሬውን እያስገደደ ማዝመቱን ትቶ፣ መደበኛ ውታደር ብቻ ያዘምት ጀመር። ይህንን ለማድረግ ደግሞ የሚረዳው ጦሩን በክሚዮን ማንቀሳቀስ ሆነ። አርበኛው ይህንን ሲያይ መንገዱን መቁረጥ፣ ድልድዩን ማፍረሱን ያዘ። ይህ ደግሞ ለጦርነቱ ጊዜያዊ ጥቅም ቢሰጥም፣ ለሀገሪቱ ዘላቂ ጉዳት የሚያስከትል ሆነ። ስለዚህ ራስ አሞራው ውብነህ ተቃወሙ። "ጎዳናዎችንና ድልድዮችን ለመሥበር እጅህን አትዘርጋ" የሚል ትዕዛዝ ሰጡ። አርበኛው መኪናዎችን ወደ መሥበርና ማቃጠል ዞረ።

በአንድ ኮሎኔል የሚመራ ጦር ወደ ደጋ መልዛ ለመውጣት፣ ከአብናት ምሽግ ተነሣ። ጦሩ ከደጋው ላይ ከወጣ፣ ብዙ ጥፋት ሊያደርስ እንደሚችልና ለመከላከልም እንደሚያዳግት ታወቀ። ስለሆነም አርበኛው ጥር 1 ቀን 1931 ዓ.ም ገጥሞ ከቀኑ 6 እስከ ምሽቱ 1 ሰዓት ወጋው። ጣልያንም በማግስቱ ተመልሶ ከወጣበት ምሽግ ተከተተ። በዚህ ጦርነት ገበሬው በራውን እንደተጠመደ ትቶ፣ አርበኛውን ሲረዳና ከጉኑ ቆሞ ሲዋጋ፣ በሮችም ሞፈር ቀንበር ተሸክመው ሲንከዋረሩ ውለዋል። ጣልያን በበኩሉ ከጥር 1 እስከ 30

ድረስ አካባቢውን ቁጥራቸው እስከ 12 በሚደርስ አይሮፕላኖች ሳያቋርጥ፣ በየቀኑ ሲደበድብ ሰነበተ። በድብደባው የመበላ ኢየሱስና የግብጣዊት ማርያም ቤተ ክርስቲያኖች ተቃጠሉ።

ጦርነቱ እየተጋጋመ ሄደ። ግለቱ ጠላትን ለበለበው፣ የውስጥ እግር እሳት ሆነበት። በየሄደበት የሚፈጀው፣ በየመንደሩ የሚያስለፍፈው የሽንገላ ወሬ፣ ምንም ፋይዳ ሳያገኝለት ቀረ። ስለዚህ የእርቅ ሥራ በገሐድ ለማካሄድ አሰበ። ከጣልያን ይህንኑ ሥራ የሚያካሂዱ ሹማምንት መጡ። መጋቢት 19 ቀን 1931 ዓ.ም ከአማራ አገር የፖለቲካ ጉዳይ መሥሪያ ቤት፣ ከጉንደር ከተማ አዋጅ ወጣ። የአዋጁ ፍሬ ነገር፤

1ኛ. በእሪም በእሪሙ አምሾውን እንዲቀበል፣

2ኛ የመስቀል መሬቶች እንደቀድሞው እንዲሆኑ፣

3ኛ. ለተጐዱ አብያተ ክርስቲያናት ደመወዝ እንዲሰጥ፣

4ኛ. የአብያተ ክርስቲያናት አለቆች የሚሾሙት በመንግሥት እንዲሆን፣

5ኛ. ሊቃነ ካህናት የመቀጮና የዳኝነት ግንዘብ እንዲቀበሉ፣ ነበር።

ይህንኑ የሚያስፈፅሙ፣ ከፍተኛ የፖለቲካ ሥልጣን ያላቸው ሹማምንት በአገሩ ላይ ተሰማሩ። ይህ አዋጅ በሕዝብ ላይ አፍራሽ ተፅዕኖ እንደሚያስከትል ቢጉልህ በመታወቁ፣ አርበኛው በየግንባሩ ጦርነቱን አጋጋመ። ጣልያንም የሰላምና የማረጋጋቱን ሥራ በአንድ እጁ፣ ከአርበኞች ከሚደርስበት ጥቃት መከላከልን በሌላው እጁ ያዘ። በዚህም መሠረት ሚያዝያ 2 ቀን 1932 ዓ.ም አርበኞችን ለማጥቃት ከአይክል ምሽግ ተንቀሳቀሰ። አዋጅ ከአወጣና የሰላም ቡድን ከአሠማራ በኋላ ጥቃት መሠንዘሩ፣ ለጤና አልነበረም። አርበኛው መቀነት ከተባለው ቦታ ገጥሞ ጥቃቱን በጥቃት በመመለስ ወደ መጣበት ምሽግ አባረረው።

አርበኞች በበኩላቸው ከጠላት ጐን የቆሙትን ኢትዮጵያውያን ለማስከዳት ልዩ ጥረት አደረጉ። ከአቀወት ምሽግ ብዙዎች መትረየስና ሌላም መሣሪያ እንደያዙ፣ ጠላትን ከድተው ከአርበኞች ጋር ለመቀላቀል አሰቡ። ምሥጢሩን ጠላት ደርሰበት። ነገር ግን ከብዛታቸውና ከዝግጅታቸው የተነሣ ፈራ። ስለዚህ እሱ ከኋላ ደጀን ሆኖ በቆመበት ውጊያ፣ በደጃዝማች ታየ ጉላ አዛዥነት በአርበኞች ላይ አዘመታቸው። አብዛኛው አርበኛ ከስቲት ወደ ጐንደር የሚያመጣውን የመኪና መንገድ ለመሥበር ሄዶ ነበርና በአካባቢው የነበሩት ቁጥር ጥቂት ነበር። ቢሆንም አርበኞች በቆራጥነት ገጠሙት። ባንዳውን ለማስጨረስ ደንበኛው የጠላት ጦር ከውጊያ ሳይገባ በደጀንነት ቆየ። ባንዳው ቀደም ብሎ እንደመከረው ከጠላት ከድቶ ወደአርበኞች መቀላቀሉን ትቶ ተዋጋ። ቀኛዝማች አምይም ተስፋጽዮን የተባሉት አርበኛ ሦስት ወታደር ገድለው ሞቱ። በየጊዜው ልብ የሚነኩ ጽሑፎች በማውጣትና በቃል ምክር በመስጠት አርበኝነቱን ያጠናከሩ ነበሩና፣ ሞታቸው ጉዳት አስከተለ።

ሚያዝያ 18 ቀን 1931 ዓ.ም ሥልሚና ከተባለው ቦታ ጦርነት ተደረገ። በዚህ ጦርነት አንዳርጌ ወርቅነህ የተባለው ቀንደኛ ባንዳ ተማረከ። ግብሩ ሲመረመር 12 አርበኞች ገድሎ፣ ራሳቸውን ቆርጦ ቀንዲር በመውሰድ ለጣልያን ግዳይ እንደጣለ ስለተረጋገጠበት፣ በስቅላት ሞተ።

በጦርነቱ በኩል እንዲህ ሲደረግ፣ በሰላሙ በኩል የጠላት ስብከት በተጠናከረ ሁኔታ ቀጠለ። "...ሽማግሌው በሰላም እንዲቀበር፣ ሕፃናት እንዲያድጉ፣ ቤታችሁና ቤተክርስቲያናችሁ እንዳይቃጠል፣ ቀዬአችሁ እንዳይጠፋ ለጣልያን ግቡ እመኑ..." እያሉ መልዕክተኞቹ ሰበኩለት። የስብከቱን ሥራ በግብር ለማጠናከር ሁለት ኮሎኔሎች፣ አንድ ሻለቃና ሁለት መቶ አለቆች ያሉበት ቡድን በየቦታው እየዞረ "...ጦርነት ይቁም።...በመኪና ላይ አደጋ መደረጉ ይቅር።...የመንገድ ሠራተኞች በእናንተ እየተጠበቁ ይሥሩ።..." ብሎ ማነጋገር ጀመረ፣ አንዳንዶችም ተቀበሉአቸው። ቡድኑ ደጃዝማች ዳኘውን ለማነጋገር ከደብረ ታቦር በ1931 ዓ.ም በለሚ ደረሰ።

ይህ ሁኔታ ከቀጠለ አርበኞች የቋጠሩት ቁጥር ተፈታ ማለት ሆነ። ያም ሆኖ እያለ፣ ቡድኑ በለሚ ሲደርስ ተቀባይ በፊታውራሪ ደምስ ኃላፊነት ተላከ። አርበኛው እንግዶቹን አጅቦ ወረሐላ ገበያ ላይ ሲደርስ፣ በቀኛዝማች ኃይሉ እጅ ሌላ መልእክት ደረሰ። መልእክቱም እንግዶቹ "...በሰንሰለት ታሥረው ይቅረቡ" የሚል ነበር። ደብዳቤው ከተነበበ በኋላ አርበኛው ከበቅሎዎቻቸው አስወርዶ በሰንሰለት አሥሮ እየነዳ ከደጃዝማች ዳኘው ተሰማ ችሎት አደረሰላቸው።

መልእክተኞቹ ጉዳያቸውን እንዲያስረዱ ተፈቀደላቸው። ኮሎኔል በኔሊ "በእናንተና በኢጣልያ መንግሥት መካከል ያለው ጥል ቀርቶ ሁለቱም ወገን በስምምነት ሆኖ እንዲተዳደር..." አሉ። ከዚያም አያይዘ የኢጣልያን መንግሥት ቢፈልግ በሰሜን በአንድ ቀን ለማጥፋት እንደሚችል ገልፆ ደነፋ። ደጃዝማች ዳኘውም "...በእናንተና በእኛ መንግሥት መካከል ያለው ጥል ከጥንት ጀምሮ ተያይዞ የመጣ በመሆኑ እርቁ በእናንተ የሚወሰን አይደለም..." ብለው ከአሥር ቤት ከተቱአቸው። ኮሎኔል እንጀሊኒ ስቅስቅ ብሎ እንደ ሕፃን አለቀሰ። ለአርበኛው፣ እብናት ላይ ተሰብስቦ ነገሩን እንዲሰማና ውሣኔ እንዲያደርግ ጥሪ ተላለፈ።

በቀነ ቀጠሮው የቤጌምድር አርበኛ ተሰበሰበ። በምዕራብ ክፍል ያለው እዚያው በአለበት ጉዳዩን አይቶ ይገደሉ የሚል ውሣኔውን ላከ። ደጃዝማች ብሬ ዘገየ ገዳይ ጠፍቶ እንደሆነ ወደ እኛ ላኩአቸው የሚል የቁጣ መልእክት አስተላለፉ። ጉባኤው ነገሩን መረመረ። ለሰላማዊ ነገር የመጡ እንጂ በጦርነት ያልተማረኩ ስለሆነ ሊገደሉ አይገባም የሚለውን የደጃዝማች ሞላ መሸሻን አስተያየት በድምጽ ደገፈ። የእርቁን ጉዳይ ከፈለገ ጣልያን የደብረ ታቦርን፣ የይፋግን፣ የጣራ ገዳምን፣ የደጐማን፣ የአምባ ጊዮርጊስን ጦር አንስቶ ወደ ጐንደር እንዲወስድ፣ በእነዚህ ጅሽጐች የሚታኘውንም መሣሪያ ለሀገር

መጠበቂያ እንዲሆን ለአርበኞች እንዲያስረክብ ቀረጠ። ይሽው ቃል የአርቅ ሥራ ለማካሄድ ተልኮ መጥቶ አብሮ በተማረከው፣ በሻለቃ ኂኪኒ እጅ እንዲላክለት ተወሰነ። አሥረኞች በለሣ ደራማርያም ክነበረው አሥር ቤት ገቡ።

ሰጣሊያኑ የአማራ አገር ገዥ መልእክት ደረሰው። የአርበኛው ብዛት አሥራ ሁለት ክፍለ ጦር እንደሚሆን ተነገረው። እሱ ግን የቀረበለትን ሃሳብ በቀጥታ ሳይቀበል፣ የጠየቃችሁት ውል የሚፈፀመው የተያዙት አምስት ሹማምንት በተለቀቁ ጊዜ ነው አለ። አርበኞች የጣልያንን ቃል አምነው አሥረኞቹን ለመልቀቅ አልፈለጉም፤ ነገር ተካረረ። በመሀል ለአስታራቂነት የመጣው ሻለቃ ወደሀገሩ ተመልሶ ሄደ።

የአማራ አገር ገዥ፣ ጀነራል ፍሩሺ ግንቦት 12 ቀን 1931 ዓ.ም አዋጅ አወጣ። አዋጁ ኢጣልያ አርቅ ቢጠይቅ፣ አርበኞች እምቢ ብለው የአርቅ ሥራ ለመሥራት የተላኩትን ሹማምንት እንደ አሠሩአቸው ከዘረዘረ በኋላ፣ የኢጣልያ መንግሥት የኃይል ሥራ ለማካሄድ መገደዱን የሚያስረዳ ነበር፣ አያይዞም ሕዝብ ለደኃዝማች ዳኘው አሥረኞችን እንዲለቁ እንዲመክር፣ ምክሩን ካልተቀበሉት ወደ ኢጣልያ ሠራዊት እንዲጠጉ የሚያሳስብ ነበር። ለአስከዛሬውም ምሕረት እንደተሰጠ ያረጋግጥ ነበር። በዚህ ጊዜ የጉንድ ተክለሃይማኖት ካህናት አሥረኞች እንዲሰቀቁ መስቀል ይዘው ቆሙ። ነገር ግን ተቀባይነት ሳያገኙ ቀሩና ጦርነቱ ቀጠለ።

ጣልያን በአማራ አገር ያለውን ጦር አስከትቶ ተንቀሳቀሰ። አሥራ ስድስት ባታልዮን ጦር፣ ፈረሰኛ ጭምር አሰለፈ። አርባ የጦር አይሮፕላኖች አስነሰቶም አካባቢውን የቦምብ ውርጅብኝ አወረደበት። እግረኛው በእግር፣ ፈረሰኛው በፈረስ ሀገር የማጥፋት ሥራውን አካሄደ። በጀነራል ቶሲቲ የሚመራው ይህ ጦር ሴት፣ ወንድ፣ ልጅ፣ አዋቂ ሳይለይ ሕዝቡን ፈጀው። ደብረ ከተባለው ቀበሌ ብቻ ዘጠና ሰድስት ሰው ገደለ። ሌላው አልተቆጠረም። የዳሑሜ ማርያምን፣ የአረብሰና በአታን፣ የአርብአረገ ጊዮርጊስን፣ የሣንኪ ኪዳነ ምህረትን፣ የመንቲ መርቆሬዎስን፣ የአርባዕቱ እንስሳን፣ የደብረ ተክለሃይማኖትን፣ የጥሊ ኢየሱስን፣ የዛራይ ሰሆ ማርያምን አብያተ ክርስቲያናት አቃጠለ። የጦር ክብደት ስለአስበረገጋቸው፣ ወደ በለሣ የሚያወርደውን በር ይጠብቁ የነበሩት አርበኞች አወላወሉ። ቆራጥ አርምጃ ባለመውሰዳቸው አሥረኞቹ አመለጡ።

ከዚህ ሁኔታ ትምህርት ሊወሰድበት ስለሚያስፈልግ የታሪኩ ጥሬ ዘሩ ብቻ ተነግሮ ሊታለፍ አይገባም። ሊተችበት ይገባል። ፍርዱ ትክክል ነው፣ በሰላም፣ ለሰላም የመጡት ሰዎች ሊገደሉ አይገባም። እንኳን በሰላም የመጡትን፣ በጦር ሜዳ የተማረኩትንም ቢሆን ከተያዙ በኋላ መግደል አይገባም። በእስናት ጉባዔ የተሰጠው ፍርድ ትክክል ነው የተባለው ስለዚህ ነው።

ነገር ግን የእርቁ ሃሳብ ከባድ ነበር። አምስት ምሽጐች እንዲለቀቁ ማድረግ (መጨቅ) ቀላል አልነበረም። በዚህ ጀነራል ፍሩሺ ቢጨነቅ አግባብ አለው። በዚያ ላይ ደግሞ ጦሩ መሣሪያውን እንዲያስረክብ መጠየቁ ነገሩን በይበልጥ እንደአከበደው ሊታመን ይገባል። የጉንድ ተክለ ሃይማኖት ካህናትን ቃል አለመስማቱ ሌላው ስህተት ነበር። ከጣልያኖቹ ጋር አብረው የመጡ ኢትዮጵያውያን ሳይኖሩ አልቀሩም። ስለእነዚህ ሰዎች አንዳች አልተደረገም። ሀገራቸውን ክደው፣ የጠላትን ዓላማ ለማስፈፀም በመቆማቸው፣ እንግዲያው እነሱም በአብሩት ጉባኤ ፊት ሊቀጡ በተገባ ነበር። ይህ አለመደረጉ ጉድለት መኖሩን ያሳያል። የስህተቱ መደምደሚያ ጠላት እርቁን አፍርሶ ጦርነት ሲያነሳ፣ በእሥረኞቹ ላይ አንዳች እርምጃ አለመወሰዱ ነበር። የሰቀቁአቸው ሰዎች በርግጥ ወገናቸውን በድለዋል። ሕዝብ ምንም ፍንዋት በሌለው ነገር ማሰቁ ያሳዝናል። በምክሩ ሽማግሌ ያልተቀመጠበት፣ የአሥረኞቹ ጥበቃም፣ ጀግና ያልቆመበት የሚያስመስል አሳፋሪ ሥራ ተሠራ።

ጉዳዩ በእልህ ሳይሆን በሬሊጥ ቢያዝ ኖሮ፣ የተሻለ አማራጭ በተገኘ ነበር። እነዚህም አማራጮች፣ አንድም ፍርዱን አስፈርዶ የዕርቅ መደራደሪያ ነጥቦችን በማስፈፀም አቅም ደረጃ መጠን ማድረግ፣ አለበለዚያ ደግሞ የፍርዱን ሁኔታ ከተመለከቱ በኋላ በአመክሮ በሰላም መልቀቅ። ሌላው አማራጭ፡- አንድም ፍፃሜው እስኪታወቅ ድረስ አሥረኞቹን ወደ ሌላ ቦታ፣ ለምሣሌ ወደ ጉጃም ማዛወር፣ አለበለዚያ ደግሞ ጦርነቱ ቁርጥ ሆኖ በተነሳ ጊዜ፣ መግደል ነበር።

በጦርነቱ ግንባር ግን አርበኞች የሠሩት ሥራ አቃቂር የሚወጣለት አልነበረም። ጨውጫዊት ላይ አርበኛው በዚሁ በግንቦት ወር 1931 ዓ.ም የጣልያንን ጦር ከሴሊቱ ከአሥራ አንድ ሰዓት ጀምሮ እስከ ምሽቱ አንድ ሰዓት ወጋው። እንደገና ደግሞ በሁለተኛው ቀን በሁለት ክፍል ተመድቦ ገጠመው። አንዱ በጠላት ላይ አደጋ ጥሎ አንድ ሻለቃና አንድ አነጋጋሪ ገደለ። አነጋጋሪው የሞተው ጥይት በአፋ ገብታበት መሆኑ አስደነቀ። ጠላትም በበኩሉ ከልጅ ዮሐንስ ኢያሱ አሽከሮች ዘጠኙን ገድሎ፣ ራሳቸውን ቆርጦ፣ ደሳማ ወሰዶ ጊጤ ተጫወተበት።

የእርቁ ድርድር መውደቅ፣ ጠላት የኃይል ሥራውን ለመቀጠል ምክንያት ሆነው። ከጉንደር ሰባት ባታልዮን ጦር አንቀሳቀሰ። የፋርጣ፣ የመቀጥዋ፣ የስማዳ፣ የእስቴ አርበኞች ተጠራርተው አምጃ ላይ ግንቦት ወር 1931 ዓ.ም ገጠሙት። ሳባት መዓልትና ሰባት ሌሊት ያለማቋረጥ ወጉት። የጠላት ጦር ወደ ደብረ ታቦር ሽሽቱን ሲቀጥል፣ አርበኞች እየተከታተሉ፣ በመንገዱ ግራና ቀኝ እየሆኑ፣ በየጉቡ በጥይት ደበደቡት። ብዙ ወታደር ገደሉ። አንዳንድ የጠላት ወታደሮች እጃቸውን ለአርበኞች ሰጡ። ብዙ ምርኮም ተገኘ።

በጠገዴው የጦር ጉራ ደግሞ ሌላ መልካም ስራ ተሠራ። ጣልያን በግራዝማች /ቢትወደደ/ አዳነ መኮንን ላይ ግንቦት 25 ቀን 1931 ዓ.ም አደጋ ጣለ። አደጋ የጣለው ከሌሊቱ 11 ሰዓት በመሆኑ አርበኛው ራሱን ለማዳን ተበተነ። ወዲያው በሚተዋወቅበት ጥሪ ተሰብስቦ ሲነጋ ተንፋች ከምትባለው ቦታ ላይ ገጠመው። ቦታው ደጋና ውርጫማ ከመሆኑ ጋር እረግረግ ስለነበር ለአርበኛው አመቸ። አርበኛው በጥይት ሲጠዘጥዘው የጠላት ጦር ሽሽቱን ያዘ፣ አጋሰሱ ከእረግረጉ እየተዘረገፉ ቆመ። ስድሳ አጋሰስ ትጥቅና ስንቅ ተማረከ። ብዙ የጠላት ወታደር ሞተ። ከአርበኞችም አራት መሪዎችና ሃምሳ ያህል ጀግኖች ወደቁ።

በሌላው ግንባር ደግሞ ጠላት ደጃዝማች ሰጥ አርገው ዋሴን ለማጥቃት ተንቀሳቀሰ። ሆኖም አርበኞች ካላሰበበት ቦታ ወግተው አባረሩት። የመጀመሪያውን ጦር አዛዥ የነበረውን ጣልያን ገድለው፣ ከወታደሩ የሚበዛውን ገድለው ሲያባርሩት ሌላ አዲስ የጠላት ጦር ደረሰ። እሱንም ከ4 ሰዓት በላይ ወግተው አባረሩት። የሞተውን ጣልያን ራሣ ገደል ስለሰቀቁት የዳባቱ ገዥ መጥቶ ቢፈልግ አጣው። እንደገና ጥቂት የጠገዴ አርበኞች ተቃጥረው በመሄድ ዝዋ በተባለው ቦታ በነበረው የጠላት ጦር ላይ አደጋ በመጣል የተከናወነ ሥራ ሠሩ።

ከሣንጃ ጦርነት ሽሽቶ የተመለሰውን የጠላት ጦር አርበኛው አጋም ዱና ከተባለው ቦታ ገጠመው። ብዙ ጉዳትም አደረሰበት። ጫቅሌ አየለ የተባለ የ15 ዓመት ማርተጋሻ አንዱን የጠላት ወታደር ከኋላው ተንደርድሮ ከወገቡ ላይ ጨምድዶ ያዘው። በዚህ ጊዜ ሌላው አርበኛ ወታደሩን አነጣጥሮ በጥይት ስለመታው ትንቅንቁ አበቃና ልጁ መሣሪያውን ገፈፈ።

ደነማ የነበረው ጣልያን በደጃዝማች ዳኘው ተሰማ በሚመራው አርበኛ ላይ አደጋ ጣለ። አርበኞች ሰብዙ ሰዓት ተከላክለው መሰሉት ነገር ግን አቶ በላይ ወንዴ የተባለ ጀግና ዘጠኝ ባንዳ ጥሎ ወደቀ። ለጠላት ጦር መሪ ሆኖ የመጣው መርዕደ መሸሻ ቆሰለ።

በአርበኛው ዘንድ ረሃብ ሰለፀና፣ እህል ለመሸመት አንድ ቡድን በሰኔ ወር 1931 ዓ.ም ወደ ሱዳን ወረደ። አሜሀራን ተሻግሮ እንደሠፈረ፣ የጣልያን ጦር ወሰን ጥሶ ገባ። በተባሄደው የተኩስ ልውውጥ ቀኛዝማች መልኬ ዘለቀ እና፣ ከጠላት ወገን ደግሞ፣ ኢብራሂም ደውራ ሞቱ። የተረፉት አርበኞች በጋሰባት በኩል ተመልሰው ወደ ኢትዮጵያ ግዛት ገቡ።

በነሐሴ ወር 1931 ዓ.ም ወገራ ደንጉር በር ጣልያን በራስ ውብነህ ተሰማ ላይ አደጋ ጣለ። በልዩ ልዩ ሁኔታ ጦርነቱ ከሌሊት እስከ ምሽት ቀጠለ። ብዙ የጠላት ወታደሮችና ጥቂት አርበኞች ወደቁ። የጣልያኑ መሪ በጣቱ እየጠቆመ ለጌታው ሲያሳይ አርበኛው አነጣጥሮ በመተኮስ የቀሠራትን ጣቱን ከመካከልዋ በጠሰበት።

በአርበኛው ላይ የሚደርሰው ጉዳት፣ ቀላል አልነበረም፣ ዓይነቱም የተለያዬ ነበር። ብዙ ሰው በጦርና በበሽታ ይሞታል። መድኃኒት የለም። ሀገሩ እየጠፋ ስለሄደ ምግብ አተተ። ቤቱ፣ ቤተክርስቲያኑ፣ ክምር ሳይቀር ይቃጠልበታል። ነገር ግን ከሀገሩ ነፃነት በስተቀር ምንም ዓላማ ለሌለው አርበኛ፣ ይህ ምንም ማለት አልነበረም። የሚፍጨረጨረው ገድሎ ለመሞት፣ ጥሎ ለመውደቅ ብቻ ሆነ። ሳይገድሉ መሞት፣ ሳይጥሉ መቁሰል እንደ መከነን ተቆጠረ። የ1931 ዓ.ም ትግል በዚህ ዓይነት ተፈፅሞ የ1932 ዓ.ምቱ ተተካ።[7]

ከውጭ አገር፣ ከካርቱም በገደሪፍ በኩል፣ ኢትዮጵያውን ወደ ኢትዮጵያ ከሐምሌ ወር 1931 ዓ.ም ጀምሮ ገቡ። ከቡድኖች አንዱ በብላቴንጌታ ሎሬንዞ ትዕዛዝ፣ ሌላው ደግሞ በአቶ ሕይወት ጎደሩ የሚመራ ነበር። በክረምቱ በብዙ ቦታ ምክር ተካሄደ። እነዚህ ከውጭ አገር የተመለሱ ኢትዮጵያውያን አላማ በሦስት ይጠቃለላል። እነዚህም፡- በአርበኞች መካከል የመረዳዳትና የመተባበር መንፈስ መፍጠር፣ አርበኛው ሌላ መሪ ለማውጣት የነበረውን አዝማሚያ አስትቶ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴን መምጣት እንዲጠባበቅ ማድረግ፣ በኢትዮጵያ ጦርነቱ እንደቀጠለ መሆኑን ለዓለም ማህበር ለማስረዳት የሚያስችል ማስረጃ ማግኘት ነበሩ።[8] ይህ ከአውሮፓ በሱዳን በኩል የሚነፍሰው ወሬ የአርበኛውን ልብ አጠናከረው።

በአገር ውስጥ ግን ጣልያን የሀገር ማጥፋትና የሕዝብ መፍጀት ሥራውን አላቆመም፣ ያንኑ በመቀጠል መስከረም 1 ቀን 1932 ዓ.ም ከደብረ ታቦር ተንቀሳቀሰ። የጠላት ጦር በኩሉኔል አንጀሊኒ የሚመራና ብዛት ያለው ነበር። የዓርብን ወንዝ ተሻግሮ ከአጉበር በታች ያለውን ሰባቱን አገር አጠፋው። የመልዛ፣ የመቀጥወና የሐሙሳ ወንዝ አርበኛ በልጅ ዮሐንስ ኢያሱ እየተመራ በየወንዙ በየዳገትና ቁልቁለቱ እየቆረጠና እየነጣጠለ በጥይት ቆላው። ውቅቱ ክረምት ስለሆነ ወንዞቹና ጭቃው የጠላትን ጦር ብዙ አጠቃው። ዓርብ ወንዝ የወሰደው በጦር ሜዳ ከወደቀው አያንስም። በዚህም የጠላትን ጦር እንቅስቃሴ አርበኛው ወደ ኋላ ስለገታው፣ እስከ ህዳር ወር መንቀሳቀስ አልቻለም።

ሆኖም በእግር መንቀሳቀስ ሲያዳግተው፣ አካባቢውን በአይሮፕላን አስደበደበ። ከሁለት ወር ያላቋረጠ ውጊያ በኋላ በነጭ ድንጋይ በኩል ዞሮ ቁስቋም ከተባለው ሥፍራ ህዳር 7 ቀን 1932 ዓ.ም ገብቶ ሠፈረ። አርበኛውም ወደዚያው ሄዶ አብናት ከተባለው ሜዳ ላይ ከጥዋቱ 1 ሰዓት እስከ ምሽቱ 1 ሰዓት ድረስ ወግቶ ወደ ቁስቋም መለሰው። ብዙ ምርኮ ስለተገኘ በአርበኞች ዘንድ ታላቅ ደስታ ሆነ። ጠላት በየአለበት መበታተኑ ለአርበኞች ጥቃት እንደ አጋለጠው በመረዳት ትልልቅ ምሽጎችን እያጠናከረ ተቀመጠ። ዘመቻ የሚያደርገውም ብዛት ያለው ወር እያሠለፈ ሆነ። በዚህ

ምክንያት ጦርነት የሚያደርግባቸው ቦታዎች ተቀነሱ። ጊዜዎቹም አልፎ አልፎ ሆኑ። በአንፃሩ ግን የአይሮፕላን ድብደባውን አጠናከረ።

ቁስቋም የነበረው ጦር እንደገና ተንቀሳቀሰ። ሀሳቡ ወደ ደጋ መልዛ ለመውጣት ነበር። አርበኛው ደሪን ከተባለው በር ላይ ገጠመው። ውጊያው ከቀኑ ስድስት እስከ ምሽቱ አሥራ ሁለት ሰዓት ድረስ ቆየ። አርበኛው በጠላት ላይ ጉዳት አድርሶ ብዙ ምርኮ አገኘ።

በጀነራል ጉሊቲ የሚመራ ጦር እንደ ልማዱ ከጉንደር ከተማ፣ ከደብረ ታቦር እንደዚሁም ከዋግና ከላስታ ብዙ ጦር አሠልፎ ተንቀሳቀሰ። እንቅስቃሴው በሦስት ረድፍ ስለነበር ቀላል አልነበረም። አርበኛው የእንቅስቃሴውን ክብደት፣ የጦሩን ብዛት መጥኖ በየቦታው እየከፋፈለ እየነጣጠለ ጠዘጠዘው። ከየካቲት 1 እስከ 15 ቀን 1932 ዓ.ም ድረስ ያለማቋረጥ ሴት ተቀን ወጋው፣ ብዙ ጉዳትም አደረሰበት።

በዚህ ግንባር የነበረው ጦርነት በእንዲህ እንደ አለ በመተማ በኩል አርበኞች ሴላ ጦርነት ከፈቱ። ከካርቱም ወገን ለሚደረገው እንቅስቃሴ የመተማ በር መከፈት እጅግ አስፈላጊ ስለሆነ፣ በዚያ ያሉ ኢትዮጵያውያን አጥብቀው ያስቡበት ጉዳይ ነበር።[9] ይህ ሁኔታ ለጣልያኖችም ታውቆአቸው ስለነበር በሐሙስ ወንዝ፣ በአተከና በአጤ ጫማ ይዘውት የነበረውን ጦርነት ትተው ወደ መተማ ዘመቱ። ይህም ለአርበኞች ፋታ ሰጣቸው።

ሣህለ በሚባለው ቦታ የነበሩ አርበኞችን ለመደምሰስ ጣልያን ከደርጌ ምሽግ ተነሣ። በደጃዝማች ነጋሽ ወርቅነህ የሚመራው አርበኛ ሻ ከተባለው ወንዝ ላይ ገጠመው። ጦር ከጠላት ወገን አየለ ስለዚህ ለማሸነፍ ተቃርቦ የነበረው አርበኛ ሽሽት ጀመረ። የደጃዝማች ነጋሽ ትዕዛዝ፣ መምህር ፋንታዬ የተባሉት የፊንገራራ ተክለኃይማኖት ቁስ ግዝት የማይመልሰው ሆኖ ተቡተነ። ጥቂቶች ግዝት ጥሰን አንሄድም ብለው እስከ መጨረሻው ተዋጉ። አለቱ በጣልያን አሸናፊነት ተደመደመ። ብዙ ሰው አለቀ፣ እልቂቱም በአርበኛው ላይ አመዘነ። ከሞተና ከቆሰለው በስተቀር፣ ዘጠና ሰድስት ሰው ተማረከ። ከተማረኩት ውስጥ አሥራ ስድስቱ በሞት ተቀጡ፣ ሰማንያዎች ለአሥራት ወደ ናኩራ ተላኩ። ከኋለኞች መካከል፣ ሰባ አምስቱ በናኩራ አሥር ቤት አለቁ።

ሁኔታው አሰቃቂ ነበር። አርበኛው ሻጌ ከተባለው ቦታ ስብሰባ አድርጎ ወደ ፊት ምን ማድረግ እንደሚሻል መከረ። ሁለት ሀሳቦች ቀረቡ። አንደኛው ደጃዝማች ነጋሽ ያቀረቡት ነበር። እሱም "በየዳን ለቅቀን አደጋ እየጣልን እንዋጋ እንጂ፣ ግንባር ለግንባር እየገጠምን ሰው አናስጨርስ። ለጣልያን ለመግባት የፈለገም ይግባ!" የሚል ነበር። ሴላው ሃሳብ የቀረበው በፊታውራሪ ካሣ ንጉሤ ነበር። እሳቸው ደግሞ ያለ ሀብታቸውን በሙሉ እንደሚሰጡ አስታውቀው፣ እዚያው በየዳ ክበራቸው ላይ ማለቅ እንደሚሻል ገለፁ።

ፊታውራሪ አስፋው፣ ወንድማቸው ነበሩና፣ ለጣልያንም በምንም ምክንያት እንደማይገቡ በመሐላ አስታወቁ።

ሁኔታው በእንዲህ ዓይነት እየተበቀ ሲመጣ፣ ጠላት የቀቢፀ ተስፋ መፍጨርጨር ተፍጨርጨረ። በተሰይ ባንዳው የሕልውናው ፍፃሜ እንደተቃረበ ስለተረዳው፣ የሚቻለውን ሁሉ አደረገ። በፊታውራሪ አብርሃ ረዳ መሪነት፣ ጤና ከተባለው ቦታ፣ በደጃዝማች ታጅቦ ካሣ መሪነት፣ ካርዋ ላይ፣ በፊታውራሪ አስፋው ኃይለማርያም መሪነት፣ ሉባ ላይ፣ በፊታውራሪ ክክቤ መሪነት፣ ግልቢና ላይ፣ በፊታውራሪ መንገሻ ንብረመድህን መሪነት፣ ጭንፍራ ላይ፣ በመምህር ንብረዋህድ አስናቀው መሪነት፣ ደንቆላክ ላይ፣ በልጅ ሐደራ ረዳ መሪነት፣ አዘነበ ላይ ታላላቅ ውጊያ ተዋጋ። ቢሆንም ድል በተደጋጋሚ ለአርበኞች ሆነ። ባንዳም እንደ ጌታው፣ እንደ ጣልያን፣ ልብ ወረደው።

መጋቢት 5 ቀን 1932 ጣልያን ያንኑ የተለመደ ሀገር የማጥፋትና ሰው የመፍጀት ሥራውን ለማካሄድ ቁስቋም ከሚባለው ምሽጉ ወጣ። አርበኛው ደርጣ በር ላይ ጠብቆ አጥብቆ ስለወጋው ወደ ምሽጉ ተመለሰ። አሥር አርበኞች ሲሞቱ፣ ከጠላት ወገን ያለቀው ግን ብዙ ነበር። አርበኞች ቀላል መትረየስና ጠመንጃዎች ማረኩ።

ጣልያን በ1932 ዓ.ም በጠገዴ ሕዝብ ላይ ከመቸውም ይልቅ ድብደባ አበዛ። ሕዝቡ ስለሰለቸው፣ አርበኞችን ማቀፉን እንደ ቀነሰ ሰምቶ ነበር። ይህን ክፍተት ለመጠቀም በደሉል፣ ቡካ፣ በደብረ ሐዋርያ አድርጎ ዘለቀ። አርበኞች ጉዳዩን ቀደም አድርገው ተረድተውት ነበርና፣ ተዘጋጅተው ጠበቁት። በሦስት ረድፍ ተሰልፎ ከመጣው የጣልያን ጦር፣ ሁለቱ ግንባሩን እያጠፈ አፈገፈገ። ከሽሬ የመጣው ጦር ብቻ ምድረ ገበታ ላይ ተዋጋ። እሱውም ከስድስት ሰዓት ብርቱ ጦርነት በኋላ እየቀዘቀዘ ሄደና ተሸነፈ። ከሽሬ ባንዳ ብዙ ሰው አሰቀ፣ ከተረፈውም ብዙ ተማረከ። አለቃቸው ነጋሽ ንጉሤ ቆስሎ አመለጠ። አርበኞች ብዙ መሣሪያና ጥይት ማረኩ።

ውጊያው ከተደመደመ በኋላ ደጃዝማች አዳነ መኮንንና ደጃዝማች ሀጉስ ተሰማ በተቀመጡበት አርበኛው ጉባኤ አደረገ። በጦርነቱ የተማረከው መሣሪያ ተደረደረ፣ ጥይቱ ተከመረ። ምርኮኛ ታሠረ፣ ፍርድ ተጀመረ። እኩሉ ሀገራቸውን ከድተው፣ መገናቸውን ወግተዋልና ይቀጡ አሉ። እኩሉ መሪ ሆነው ከአድያቦ፣ ከሽሬ የመጡት ይቀጡ፣ ሴላው ተገድዶ የመጣ ነውና ይለቀቅ አለ። ብዙ ጊዜ የወሰደ የርስበርስ ክርክር ተካሄደ። ክርክሩ በጠነነ ጊዜ፣ ደጃዝማች ሐጉስ ተሰማ እስረኞቹ በአርበኞች እጅ ያለውን አገር ከጎበኙና፣ በየአለበት አርበኛው የሚያካሂደውን ትግል ከአዩ፣ ከተገነዘቡ በኋላ፣ በሸኚ ወደ ሀገራቸው ይግቡ፣ ይህም በእኔ በኩል እንዲፈፀም አሥረኞቹ ለእኔ ይሰጡኝ አሉ። አርበኛው በሙሉ ድምፅ ተስማማና ሰጣቸው። እሳቸውም እንደቃላቸው ስለአደረጉ ከትግሬ የሚዘምተው ባንዳ ተቀነሰ።

የጣልያን ጦር፣ በኪሮስ በኩል፣ የደረሰዜው ደግሞ፣ በመሽሐ በኩል ሄደው፣ ሁለቱም በየዳ ሲገናኙ ተነሱ። አርበኛው ከሦስት ተከፍሎ ለጦር ተዘጋጀ። አንዱ ክፍል በኪሮስ በኩል የመጣውን፣ ሌላው ክፍል በመሽሐ የመጣውን ሲወጋ፣ ሦስተኛው በደጃዝማች ነጋሽ ወርቅነህ አዛዥነት ለሁለቱም ክፍል በደጀንነት ትበሬ ከተባለው ቦታ ሆኖ እንዲጠባበቅ ተመደበ። ሁለቱም ጦር ውጊያ ገጠመ። በፊታውራሪ አበበ ወልደዳዊት የሚመራው አርበኛ ማይ ጠሐሉ ላይ ጠላትን ድል አድርጉ፣ አምስት መቶ ብረትና ሃያ ስምንት ሰው ማረከ። በመሽሐ ላይ የተዋጋው አርበኛ ግን ድል ሆነ። አለቃው ፊታውራሪ ነጋሽ መርሻ ቆስለው ተማረኩ። ከብዙ መፃፃፍ በኋላ ጣልያን ፊታውራሪ ነጋሽና ቀኛዝማች ዓለማየሁን ስለለቀቀ፣ ሃያ ስምንቱ ባንዶች ተፈቱ።

ወደ አደዛ ለመውረድ የተንቀሳቀሰውን የጠላት ጦር፣ በግራዝማች ረዳ ተሰማ የሚመራው አርበኛ ግንቦት 27 ቀን 1932 ዓ.ም ቢዛሆ ላይ ለአራተኛ ጊዜ ባካሄደው ውጊያ ድል አድርጉ መልሶታል።

ክፍ ሲል እንደ ጠቀስሁት፣ ራስ አሞራው ውብነህ በሕዝብ ተመርጠው የጠቅላይ አዛዥነት ሥልጣን ከተሰጣቸው በኋላ፣ በይበልጥ ኃላፊነት ላይሰማቸው አልቀረም። የመኪና መንገድ እንዳይኖርና ድልድይ እንዳይሠበር መመሪያ መስጠታቸውን ቀደም ብለን አንብበናል። የመተማን ምሽግ በመስበር በር ለመክፈት ከሱዳን ከመጣው ቡድን ጋር መነጋገራቸውም ይታወሳል። ከእንግሊዝ መንግሥት ጋር ግንኙነት በመፍጠር ርዳታ ለማግኘት ከሚስስ ሲልቪያ ፓንክረስትና ከሱዳን የእንግሊዝ አገረ ገዥ ጋር መማፋቸው ታውቆአል። ካርቱም በነበረው አገረ ገዥ በኩል የፃፉት ደብዳቤ፣ ሞሶሎኒ ከሂትለር ጋር መቆሙን ከአረጋገጠ በኋላ የተፃፈ እንደ መሆኑ፣ ከእንግሊዝ ጋር ለተደረገው ግንኙነት ጥሩ መቆናጥጥ ሊሆንላቸው ቻለ። ይህም ለመሆኑ፣ ድሮ ከነበረው የእንግሊዝ ጦር አዛዥ ሰኔ 9 ቀን 1932 ዓ.ም ከተፃፈላቸው ደብዳቤ ይዘት ለማወቅ ይቻላል። የአዛዡ ይህ ደብዳቤ፣ እሳቸው ሚያዝያ 13 ቀን የፃፉትን ደብዳቤ ይጠቅስና፣ መልዕክታቸው ወደለንደን መላኩን ይገልፃል። አያይዞም እንግሊዝ ምክርና እርዳታ ልትሰጣቸው መዘጋጀቷን ያረጋግጣል። ኢትዮጵያ ነፃነትዋን በቶሎ እንደምትቀዳጅ፣ የእንግሊዝ መንግሥት ተስፋ እንደአለው ያስረዳል።

ይህ ደብዳቤ አዲስ ተስፋ የሚሰጥ ሆኖ ሳለ፣ ሌሎች የትግሉን መቀናጀት የሚያውኩ ችግሮች አጋጠሙ። ራስ /አሞራው/ ውብነህ ከልጅ ዮሐንስ ኢያሱ ጋር መሣሪያ እስከ መማዘዝና እስከ መዋጋት ደረሱ። እሳቸው የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ደጋፊ ከመሆናቸው የተነሣ ሳይሆን አልቀረም። ከእንግሊዝ ጋር አዲስ የተጀመረውም ወዳጅነት አልጣማቸውም። እንግሊዞች ለሠራዊቱ መሣሪያ እየሰጡ፣ በዚያው ሰበብ አዛዥ መሆን ጀመሉ። ራስ ውብነህ በበኩላቸው ሕዝብ የሚፈልገው ንጉሠ ነገሥቱን እንጂ መሣሪያ አለመሆኑን ገለፁ። እንዲያውም የነጭ፣ ነጭ ጣልያን ምን አለኝ? ብለው

ሰብስባውን ሰብረው (ጥለው) ወጡ። ከአርበኛውም አብዛኛው የእሳቸውን ሐሳብ ደገፈ። እንግሊዞች በጉዳዩ ተቸገሩ። ስለዚህ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ እስከ 15 ቀን ድረስ ካርቱም እንደሚገቡ በምሥጢር ገለጡላቸው እና ቁጣቸውን አበረዱ። ጠቡም ቀዝቅዘ፣ የትብብሩ ሥራ ቀጠለ።

ጣልያን በበኩሉ አርበኛው ወደ እርሻው መሠማራቱን በመረዳት፣ በደጃዝማች ተድላ አበጋዝ ይመራ የነበረውን አርበኛ ለማጥቃት ከደብረ ታቦር ተንቀሳቀሰ። ደጃዝማች ተድላም በሞታቸው ቆርጠው፣ በአካባቢያቸው የነበሩትን ጥቂት አርበኞች ይዘው፣ ሰኔ 12 ቀን 1932 ዓ.ም አፈረዋናት ላይ ገጠሙት። ብዙ የጠላት ወታደር ገድለው፣ በሦስት ጥይት ተመትተው ወደቁ። ከቆሰሉ በኋላ እንኳን አምስት ጠላት ገድለው ሞቱ። ስድስት ባልደረቦቻቸው፣ የጌታችንን ሬሣ ጥሰን እንሄድም ብለው አብረዋቸው ሞቱ። በጠቅላላው አሥራ ሁለት ምርጥ አርበኞች ወደቁ። ሌሎች ሁለት ቆስለው አመለጡ። ደጃዝማች ተድላ አበጋዝ፣ ጠላት ሳይባረር ቤት አልሠራም! በማለት፣ ያለቤት የኖሩ ጀግና ነበሩ።

እንግሊዞች የኢትዮጵያን ጦር በመደገፍ የአየር ድብደባ የጀመሩ ጊዜ፣ ጣልያኖች ከፍተኛ ድንጋጤ አደረባቸው። ሰው በጊዜ ከቤቱ እንዲኩተት፣ መብራት እንዳያበራ፣ መስኮቶች ጥቁር ቀለም እንዲቀቡ አዘዙ። ሰራሳቸው ዋሻ ቆፈሩ። አይሮፕላን በመጣ ጊዜ ማንም ሰው እንዳይንቀሳቀስ አደረጉ። የተጠበቀው አደጋ ሰኔ 24 ቀን 1932 ዓ.ም ደረሰ። ዘጠኝ የእንግሊዝ አይሮፕላኖች ከቀኑ በ11 ሰዓት በሦስት፣ በሦስት እየተከፈሉ የአዘዞን አይሮፕላን ማረፊያ ደበደቡ። ጣልያኖች ብዙ ፀረ አይሮፕላን መሣሪያ ቢተኩሱም፣ አንዳች መፈየድ አልቻሉም። አይሮፕላኖቹ ሥራቸውን አከናውነው በደህና ወደ መጡበት ተመለሱ። ከባንዳ በስተቀር፣ ሕዝብ በደስታ ልቡ ተነካ። በወቅቱ ባንዳ ራሱን ከማዳን በተረፈ ሌላ አልተመኘም። የአይሮፕላን ማረፊያው የሌሊት ድብደባ ለብዙ ጊዜ ቀጠለ።

በጉንደር የነበሩትን ጣልያኖች ሰብስቦ፣ አሳልፎ ወደ መተማ አዘመታቸው። ነገር ግን ጭልጋ ሲደርሱ፣ እምቢ ብለውት ወደ ጉንደር ተመለሱ። ጣልያን ደጃዝማች ተድላ አበጋዝን ከገደለ በኋላ በአፈረዋናት በኩል ያለውን ኃይሉን ማጠናከር ያዘ። በደጃዝማች ካሣ ንብሬ የሚመራው አርበኛ ነሐሴ 7 ቀን 1932 ዓ.ም ደብረ ሲና ላይ ገጠመው። የጠላት ጦር የተሰልፈው በአምስት ረድፍ ነበር። አርበኞችም እንደእርሱ በአምስት ረድፍ ገጠሙት። አዝማቹ ደጃች ካሣ ከጥቂት ባልደረቦቻቸው ጋር ደጀን ሆነው ይጠባበቁ ሳሉ፣ በደጃዝማች እጅጉ አያሌው የሚመራ የጠላት አንድ ክፍል ጦር ባልተጠበቀ ቦታ ተጠግቶ ገጠማቸው። እሳቸውም በጀግንነት የጦሩ ማሕል ገብተው ተዋጉ። ክቡሩ ሜዳ በመግባታቸው፣ ሰይተው አወቁአቸውና በሮምታ ተኩስ መቱአቸው። በአርበኝነት ሥራ በቆዩበት ዘመን ሁሉ ተሸንፈው የማያውቁት ደጃዝማች ንብሬ ካሣ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ ድል ሆነው በጦር ሜዳ ላይ ሞቱ።

አሥራ ሁለት እውቅ አርበኞች ሞቱ፣ ሌሎች አምስት ቆሰሉ። ከቆሰሉት ውስጥ አራቱ ሴት አርበኞች ነበሩ። በሌሎች አምስት የጦር ጉራዎች የሞተና የቆሰለው እጅግ ብዙ ነው። ቢሆንም በዛ ውጊያ ከጠላት ወገን ያለቀው ይበልጥ ነበር።

ጣልያን በመሐል አገር የነበረውን ቦሩን ለማንገዝ እንዲረዳው የደሴ ጉንደርን መንገድ በፍጥነት ያሠራ ጀመር። መንገድ ሠራተኞቹን የሚጠብቅ ጦር በየቦታው አስቀመጠ። ጉንደር በተከማቸው የጠላት ጦር ላይ የመሐል ሀገሩ ከተጨመረበት በቀላል የሚበገር ስለማይሆን፣ የመንገዱ ሥራ በቸልታ የሚታይ፣ ከሀገር ልማት የሚቆጠር አልነበረም። ስለዚህ በደጃዝማች ዳኘው ተሰማ፣ በደጃዝማች በላይ ተሰማና በደጃዝማች ከበደ የሚመራው አርበኛ ክምር ድንጋይ ላይ ገጠመው። የጠላት ጦርም በቀላል መትረየሶች አብዝቶ በመተኮስ ተከላከለ። ቢሆንም ድል የአርበኞች ሆነ። አንድ ኮሎኔል፣ አንድ ሻምበልና ሦስት መቶ አለቆች፣ ከአንድ መቶ ሃያ አምስት ጣልያናውያን ወታደሮች ጋር ሞቱ። ምርኮ በጣም አመቸ።

ከእንግሊዝ ጠቅላይ ጦር ሠፈር ነሐሴ 15 ቀን 1932 ዓ.ም ለደጃዝማች ነጋሽ ወርቅነህ ደብዳቤ ደረሰ። ደብዳቤውም ሰላምታ ካቀረበ በኋላ፣ የሚያስፈልጋቸውን የጦር መሣሪያ የእንግሊዝ መንግሥት ሊሰጣቸው የተዘጋጀ መሆኑን የሚገልጽና ንጉሠ ነገሥቱ በቅርብ ጊዜ ከአርበኞች ጋር እንደሚሆኑ የሚያበስር ነበር። ደጃዝማች ነጋሽም ደስታውን ለሠራዊታቸው ገልፀው፣ እንደ አገልግሎቱና እንደጀግንነቱ እያዩ እስከ ፊታውራሪነት ድረስ የማዕረግ ስምና ሽልማት ሰጡት።[10]

የ1932 ዓ.ም የጉንደር ትግል በዚህ ዓይነት ተፈፀመ። የ1933 ዓ.ምቱ በላቀ ተስፋና በበለጠ ብርታት ቀጠለ።

የመስከረምና የጥቅምት ወራት ለአርበኞችም ለጣልያንም የመዘጋጃ ጊዜ ሆኑ። አርበኞች ከንጉሠ ነገሥቱ የሚላላኩበት፣ መመሪያ የሚቀበሉበት፣ መሣሪያ የሚያነሱበት ሆኑ። ጣልያኖችም በበኩላቸው ከትናንሽ ምሽጎች ወደ ታላላቅ ከተሞች እየተሰበሰቡ ለመጨረሻው ፍልሚያ መዘጋጀት ነበረባቸው።

ማጠቢያ ላይ የነበረው ጣልያን በሠራቱም ሆነ በሌላው አካባቢ የሚተላለፈውን አርበኛ፣ ስደተኛና የእንግሊዝ ጦር ለማገድ መከራ አደገ። ይህ መከራ በአስቸኳይ መገታት ስለነበረበት በቀኛዝማች ወርቁ ስንቄ የሚመራው አርበኛ ሀዳር 1 ቀን 1933 ዓ.ም ማጠቢያ ድረስ ሄዶ ገጠመው። መከራው የጣልያንን ጦር ከዚያ አካባቢ ለማባረር ነበር። ከጥዋቱ አንድ ሰዓት እስከ አሥር ሰዓት ተዋጉ። አዝማቹ ቀኛዝማች ወርቁ በጥይት ተመትተው ወደቁ። ጦርነቱ ዓላማውን ሳይመታ ቀረ።

በዚህ በህዳር ወር 1933 ዓ.ም በፊታውራሪ አስፋው ኃይለ ማርያም የሚመራው የጠላት ጦር ቅዱስ ያሬድ ተፈራ ላይ ቡተደረገ ጦርነት ተሸንፎ

ወደ መጣበት ተመለሰ። ብዙ አርበኞች ሞቱ፣ ቆሰሉ። ሆኖም ከጠላት ወገን ያለቀው ይበዛ ነበር። በመሸሐ በክል ሲካሄድ የቆየው ጦርነት በዚህ አከተመ።

መሸሐና ሰቆጣ የነበረው የጠላት ጦር ምሽጉን እየለቀቀ አዲአርቃይ ገባ። አዲአርቃይንም ለቅቆ ወደ ደረስጌ፣ ከዚያም ወደ ጉንደር ሄደ። በደጃዝማች ነጋሽ ወርቅነህ የሚመራው አርበኛ እግር በእግር እየተከታተለ ጣልያን የለቀቀውን ቦታ በመያዝ ሕዝቡን አረጋጋ።

አርበኛው ደረስጌ የነበረውን ጣልያን ለመውጋት ሲዘጋጅ፣ ጣልያንን የገዛ ባንዳው ከድቶ ውሃ አሳሰቀዳ፣ እህል አሳስገባ ብሎ ከበበው። በስፍራው የነበረው የጦሩ መሪ መቶ አለቃ ሸለቆ እጁን እንዲሰጥ ከለለቃው መመሪያ ቢሰጠውም፣ እሞታለሁ እንጂ ለገዛ አሽከሬ እጄን አልሰጥም ብሎ እምቢ አለ። በደጃዝማች ነጋሽ ወርቅነህ የሚመራው አርበኛ ሲደርስ፣ ጌታውን ማርኮ ሊፎክር ተዘጋጅቶ የነበረው ባንዳ ቦታ ለቀቀ። ደጃዝማች ነጋሽ ወርቅነህ ጣልያን ውሃ እንዲቀዳ ፈቀዱለት፣ አሥር ሰንጋ ላኩለት። ያንን በልቶ እና ውሀ ጠጥቶ ከጠገበ በኋላ፦ ሥጋ የሳክሁልህ፣ ውሃም የፈቀድኩልህ አስርቦ፣ አስጠምቶ ያዘኝ እንዳትል እንጂ ልለቅህ አይደለምና እጅህን ስጥ አሉት። መቶ አለቃ ሸለቆም ጀግናን የሚማርከው ጀግና መሆኑን ገልፆ፣ በሰላም እጁን ሰጠ። ስድሣ ስድስት መትረየስና ብዙ ጠመንጃ፣ እጅግ ብዙ ጥይትና የእጅ ቦምብ አስረከበ። ከሦስት ቀን እረፍት በኋላ አዲአርቃይ ለነበረው እንግሊዝ አሰረከበት።

ከንጉሠ ነገሥቱ የተሰጡአቸውን የሥራ ባልደረቦች ይዘው፣ ሻለቃ ረንግሮስ ክካርቱም በገዳሪፍ፣ በቆቡቲያ፣ በወልቃይት፣ በጠገዴ፣ ቆላ ወገራ፣ አጅሬ ከተባለው ቦታ ጥር 11 ቀን 1933 ዓ.ም ደረሱ። አርበኛውም በሰላም፣ በደስታ ተቀበላቸው። ሻለቃ ረንግሮስ ከኬንያ የዘመተው የእንግሊዝ ጦር አዲስ አበባ ሲገባ መቃረቡን፣ እሳቸው የተሰለፉበት የነበረው ጦር ቀድሞ ጉንደር ከተማ እንደሚገባ ያሳቸውን ተስፋ ገለው።

የዳባትን ከተማ ለመያዝ፣ ደጃዝማች አያሌው ብሩ ጠላትን ከድቶ ከአርበኛው ጐን እንዲሰለፍ ማድረግ ጠቃሚ መሆኑ ታወቀ። እሱም ንጉሠ ነገሥቱን በቅርብ፣ በመልክ የሚያውቃቸውን ልጅ ገሠሠን፣ ሄዶ አይቶ እንዲመጣና ለእሱ እንዲነግረው ላከው። በዚህ ምክንያት ጦርነቱ መካሄዱ ቀርቶ ወደ ካርቱም ጉዞ ተደረገ። ሻለቃ ረንግሮስ ራሳቸው ልጅ ገሠሠን ይዘው ከቆሳ ወገራ ወልቃይት በኩበት፣ ከወልቃይት በካሚዮን ተሰነይ ድረስ፣ ከተሰነይ በአይሮፕላን ካርቱም ገቡ። ነገር ግን ንጉሠ ነገሥቱ ከካርቱም ወደ ጉጃም ሄደው ስለነበር፣ ልጅ ገሠሠ ንጉሠ ነገሥቱን በዓይን ለማየት ሳይችል ቀረ። ቢሆንም የሚያውቁአቸውን መኪንንት በማነጋገር የንጉሠ ነገሥቱን መምጣት እውነተኛነት አረጋግጦ ተመለሰ። ደጃዝማች አያሌው ብሩ የንጉሠ ነገሥቱን መምጣት የሠማ ዕለት፣ ሌሊቱን ከጠላት ተሰይቶ ወደ መረባ ወረደ።

በፊታውራሪ ብሩ ወልደገብርኤል የሚመራው ጦር ጉንደር ክፍለ ሀገር ገባ። ጉርጮራ የነበሩ ጣልያኖች ጠቃሚ ዕቃዎችንና የጦር መሣሪያዎችን፣ ዲናሚቶችን ቄምር ከጣና ባህር ጨምረው፣ አንጋራ ከሚባለው ደሴት ተጠግተው የነበሩ ጀልባዎቻቸውን አስጥመው፣ እጃቸውን ለአንግሊዝ ሰጡ። ሰጡኣምና ሰበጌምድር መገናኛ እንዲሆን አፄ ፋሲል ያሠሩትን ደልድይ፣ ፊታውራሪ ታምራት ቀደም ብሎ ሰብሮት እንደነበር መግለጼ የሚታወስ ነው።

ከደሴ ወደ ጉንደር የሚጓዘው ጣልያን መጣ። ፊታውራሪ ብሩ እስቴ ላይ ሠፈር አድርገው ስለነበር፣ አንድ ቡድን ጦር ላኩ። የጠላት ኃይል ስለአየለ፣ አሸንፎት ደብረ ታቦር ገባ። ቢሆንም አንድ መቶ ሠላሳ ጠመንጃና ሰባት ካሚዮኖች ተማረኩ።

ደጃዝማች አያሌው ብሩን በተገለፀው መንገድ ከጠላት ማስከዳት እንደተቻለ፣ የዳባትን ምሽግ የማጥቃት ዕቅድ ተሠራ። ሠራዊቱ በምሥጢር ከምሽጉ እንዲጠጋ ከተደረገ በኋላ፣ ሚያዝያ 5 ቀን 1933 ከጥዋቱ በ12 ሰዓት ጦርነት ተከፈተ። በምሽጉ ውስጥ ድብልቅልቅ ሆነ። ባንዶቹም እየተታኮሱ ወጡ። በመሀሉ የጣልያኑ የጦር አዛዥ ዕርዳታ በራዲዮ ጠይቆ ናሮ ከደባርቅ አዲስ ጦር መጣ። እሱን ደግሞ ምሥጢሩን አውቀው ከመንገድ ላይ አንጥፈው ይጠብቁ የነበሩ አርበኞች፣ ወቅን ከተባለው ቦታ ገጠሙት። አዛዥ ኮሎኔል በኒሊን ገድለው፣ ጭኖ ያመጣውን መትረየስና ጥይት ቀሙት። ጦርነቱ ተጋግሞበት በመከላከል ላይ እንዳለ፣ በረዶ የቀላቀለ ኃይለኛ ዝናም ጣለ። ቢራራ ገላ የተባለው አርበኛ በየተራራው እየዞረ ጥሩምባ በኃይል ስለነፋ፤ ብዙ አርበኛ የተሰበሰበ መስሎት ጠላት ደነገጠ። ሰሜን ደርሰዊ ላይ የተከበበውን እንዲያስለቅቅ የተላከው ጦር እንዲመለስ ስለታዘዘ፤ በለገዝ ከተባለው ወንዝ ላይ ከደረሰ በኋላ ተመለሰ። ከጭልጋ፣ ከደንቢያና ከጉንደር ሌላ አዲስ ጦር ለዕርዳታ ደረሰ።

ከዛ በኋላ ጣልያን ስለበረታ፣ አርበኞችን በጥይት እየደበደበ አረቡር እስከሚባለው ወንዝ ድረስ አባረራቸው። በዚያ ውጊያ (ግራዝማች) አሥማረ ዘረፉ የተባለ ባንዳ ለጣልያን ረድቶ የመጣውን ሬዳት የአርበኛ ጦር አላሳልፍም ባይል ኖሮ፣ ድል የአርበኞች በሆነ ነበር።

በዚያ ሰሞን አርበኞች ፈንጠዝያ አብዝተው ነበርና፣ የአማራ አገር የምዕራብ ጦር አዛዥ የነበረው ኩሎኔል አሰፖዳ ለትንሣኤ በዓል እንደተሰበሰቡ አደጋ ጥሎ ለመፍጀትና ለመማረክ አሰበ። ደጃዝማች በዛብህ ግብር እንደሚያበሉ በሰላዮች አማካኝነት አጠና። እንደአሰበውም ሚያዝያ 13 ቀን 1933 ዓ.ም (የማዕዶት ዕለት)፣ ተንከል ኩተባለው ቦታ ላይ በማለዳ፣ በተንኮል አደጋ ጣለባቸው። ተሳክቶለት ቢሆን፣ እንግሊዞችንም ይማርክ ነበር። ደግነቱ ግን እንደዚያ አልሆነም። አደጋ ሲጣልበት አርበኛው በቅፅበት ተበተነ። ጉጣጉጡን ተጠግቶ በጥይት ጠዘጠዘው። አዲስ በሆነ ብልሀት፣ በጠመንጃው

አፈሙዝ ላይ የእጅ ቦምብ እያሠረ በመተኮስ ቦምቡን ከጥይት ኃይል ጋር እየወነጨፈ ደበደበው። ጦርነቱ ከጥዋቱ 1 እስከ ምሽቱ 12 ሰዓት ቀይቶ፣ በአርበኞች ድል አድራጊነት ተፈፀመ።

የዳባትን ምሽግ ለማስለቀቅ ከሚያዝያ 17 ቀን 1933 ዓ.ም ጀምሮ ለአምስት ቀን ጦርነት ተካሄደ። ብዙ አርበኞች ቢወደቁም፣ ባንዳውን ጨምሮ ከጠላት ወገን ያለቀው ይበልጣል። በመጨረሻው ጠላት ተሸንፎ ከፊሉ ደባርቅ፣ ከፊሉ ደግሞ አምባ ጊዮርጊስ ገባ።

በሌሎች ምሽጎች የነበረው ጣልያን ሁሉ ምሽጉን እየለቀቀ ሲሄድ፣ ጥላዩ በተባለው ቦታ የነበረው ዝም ብሎ ተቀመጠ። እጅህን ስጥ ተብሎ ቢጠየቅ አልሰጥም አለ። አርበኛው ተሰብስቦ በዚሁ በሚያዝያ ወር 1933 ዓ.ም በምሽጉ ላይ ጦርነት ከፈተ። ጣልያንም ዕርዳታ ስለጠየቀ በኮሎኔል ቶሬሊ የሚመራ አዲስ ጦር መጣለት። እኩሉ አርበኛ የጥላዩን ምሽግ ከብቦ ሲያስጨንቅ፣ ሌላው ቡድን ከጉንደር የመጣውን የጠላት ጦር ሣንቅ ጥቅም ከተባለው ቦታ ገጠመው። ታላቅ ውጊያ ተካሂደ፣ ደጃዝማች ጫኔ መሸሻ ሞቱ። የጥላዬ ምሽግ ጦርነት ቀጥሎ፣ ከጠላት ጦር ብዙው አልቆ፣ የተረፈው ለአርበኞች እጁን መስጠት ጀመረ። ኮሎኔል ቶሬሊ በበኩሉ ሣንቃ ጥቅም ላይ በለገኘው ድል ተደፋፍሮ ወደ ጥላዬ ገሰገሰ። ጦርነቱ ቀጥሎ ብዙ ከተቀጠቀጠ በኋላ፣ ጣልያን ተሸንፎ ሸሸቱን ያዙ።

የጉንደር አርበኞች ጦርነቱን በዚህ ዓይነት እንደያዙ፣ ንጉሠ ነገሥቱ ክካርቱም በአሜድላ፣ በቢላያ፣ በደብረ ማርቆስ አድርገው ሚያዝያ 27 ቀን 1933 ዓ.ም ከኢትዮጵያ መናገሻ ከተማ አዲስ አበባ ገቡ። የጦርነቱ ሥርዓት ተሰወጠ። ኢትዮጵያ በመንግሥትነት ቆመች፣ የጣልያን የቅኝ ግዛት ኃይሎች በተራቸው እንደ ሽፍታ፣ የግል ሕይወታቸውን ለማትረፍ ይሳደዱ ገቡ።

ማጣቀሻ ፅሑፎች

1. ተክለጻድቅ መኩሪያ፣ *የኢትዮጵያ ታሪክ*፣ ገጽ 164-165።
2. Greenfield, pp.162-163.
3. *ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፣ ሕይወቱና የኢትዮጵያ እርምጃ 1ኛ መጽሐፍ*፣ ገጽ 126-128።
4. *ገሪማ ታፈረ፣ ጎንደሬ በጋሻው*፣ ገጽ 15-49፣145-168።
5. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 66-80፣145-158፣174-182።
6. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 76-82፣124-138፣143-156፣161-162፣183-198፣213-219።
7. ጎይወት ጎዳሩ፣ *ያቺ ቀን ተረሳች*፣ ገጽ 170-171።
8. ዝኒ ከማሁ፣ 197-203።
9. *ገሪማ ታፈረ*፣ ገጽ137-162፣217-232።

ምዕራፍ ሠላሳ አምስት
የአዲስ አበባ የትግል አስተዋጽኦ

አዲስ አበባ የኢትዮጵያ መናገሻ ከተማ እንደመሆንዋ መጠን እንደ ማንኛውም ሀገር ዋና ከተማ የዓለምን ትኩረት ትስባለች። በውስጥዋ የሚካሄደው እንቅስቃሴ ሁሉ ክብደት አለው። በኢትዮጵያና ጣልያን ጦርነት ጊዜ የተጣለባት ትኩረት ደግሞ ከምንጊዜውም የበለጠ ነበር። እውነትም ሰጣልያን መግቢትም፣ መባረርም ወሣኝ ሆነች። ስለዚህ አዲስ አበባንም እንደ ሌሎች ክፍላተ ሀገር ሰይቶ መመልከት የታሪክ ግንዛቤ ያዳብራል።

በጦርነቱ ዋዜማ አዲስ አበባ ከተቆረቆረች 49 ዓመትዋ ነበር። የልዩ ልዩ ብሔረሰቦችዋ መኖሪያ ነበረች። ከሕዝብ መኖሪያ ቤቶች አብዛኛው ክዳኑ ሰንበሌጥ ነበር። የከተማው አካባቢ ከፍልውሃና ከዑራኤል በስተሰሜን፣ ከፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ድልድይ በስተምሥራቅ ያለውን ቦታ ይዞአል። በዚሁ አካባቢ የነበሩት የመኪና መንገዶች፣ አሁን በ1986 ዓ.ም ከሚታዩት ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ብቻ ነበሩ ያኔ የነበሩት። ስፋትም አልነበራቸውም። በከተማዋ የነበሩ፣ በጣት የሚቆጠሩ መኪናዎች ይንቀሳቀሱባቸው ነበር።

የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች፡- አንድ ባንክ፣ ጥቂት ንግድ ቤቶች በአዲስ አበባ ከተማ ተቋቁመዋል። የሕዝቡ ብዛት አንድ መቶ ሺህ ቢሆን ነው። ቅርብ በወጣው የባሪያ አዋጅ፣ ቡተለምዶ ባሪያ ይባል የነበረው የከተማው ነዋሪ ቁጥር ብዙ ነበር። በክፍለ ዘመኑ መጀመሪያ ላይ ከነበረው ወደ 20,000 ያህሉ ቢሞትም፣ ነፃ በመውጣትም ቀንሶአል። ቢሆንም ከ15,000 ምንም ያህል አይቀንስም።[1] በዚህ ላይ ደግሞ አሽከሩ፣ ገረዱ አለ። በዚህ ሁኔታ ከአዲስ አበባ ሕዝብ ከሲሶ የማያንሰው የራሱ ንብረት የሌለው፣ ተገዥ ነበር ማለት ነው። ከእነሱ ውጪ የውጭ አገር ሰዎች በከተማዋ ነበሩ።

የከተማይቱ ውስጣዊ ገጽታ እንደዚህ ይሁን እንጂ፣ ባላት ጉብረተሰብ ዘንድ የነበረው አመለካከት ከቀድሞ ሁኔታዋ ሲመዛዘን ደህና ነበር። ሀገሩ ተረጋግቶ፣ ሰላም ሰፍኖ፣ ሕገ መንግሥት ወጥቶ፣ ምክር ቤት ቆሞ ነበር። ባርነት ባይወገድም፣ የባሪያ ንግድ ቀርቶአል። ትምህርት ቤቶች ተስፋፍተው፣ የብዙ አገሮች ዲፕሎማቶች ተገኝተው፣ ዓለም አቀፍ ግንኙነቶች ተከፍተዋል። የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ተቋቁመው ዘመናዊ አስተዳደር ተመሥርቶባት ነበርና፣ በዓለም ጉብረተሰብ ዘንድ የነበራት ግምት ዝቅተኛ አልነበረም። ስለዚህ የአዲስ አበባ መያዝ ሰጣልያኖች አንድ ዋና ጉዳይ ነበር።

በማይጨው ጦርነት የኢትዮጵያ ድል መሆን በዓለም ሬዲዮ ጣቢያዎች ዕለቱን ተስፋፍቶ ስለተነገረ፣ አዲስ አበባም ሰማች። በከተማይቱ ላይ ታላቅ ድንጋጤ ወደቀባት። ደጃዝማች ወልደጻድቅ የከተማይቱን ጸጥታ በማስከበር ረገድ ጠንካራ አቅዋም ያዙ። የከተማው ሹማምንትና ሕዝቡም

ተባበራቸው። ንጉሠ ነገሥቱ የነበሩበት ጠፋ። ቢሆንም ከተማይቱ አልተናወጠችም። ንጉሠ ነገሥቱ ሚያዝያ 24 ቀን 1928 ዓ.ም ስደት እስኪሄዱ ደግሞ፣ የበለጠ መረጋጋት ሆነ። ከአዲስ አበባ እንደወጡ ግን ዝርፊያ ተካሄደ፤ ቤትም ተቃጠለ። ቢሆንም ከባድ ጉዳት አልደረሰም።

ማርሻል ባዶሊዮ 13,000 በሚሆን የጦር ሠራዊት ታጅቦ ሚያዝያ 27 ቀን 1928 ዓ.ም አዲስ አበባ ገባ። መግባቱንም በሬዲዮግራም ለሞሶሎኒ አስታወቀ። ለእሱ ክብርና ሞገስ ለማስግኘት የሚረዱ ዝግጅቶችም ተደርገዋል። ለባዶሊዮና ለመኪንንቶቹ መቀመጫ 193 ምርጥ ፊረሶች ከሮማ በመርከብና በመኪና ተጓጉዘው ቀርበዋል። ወደ ሁለት ሺህ የሚጠጉ ልዩ ልዩ መኪናዎች ተሰናድተዋል። ማርሻሉ አዲስ አበባ በሚገባበት ጊዜ በሰማይ ላይ አይሮፕላኖች እንዲያንጎራበቡ ተደርጓል። በርካታ ጋዜጠኞች ወሬውን ለዓለም ጉበረተሰብ ለማብሠር ተዘጋጅተዋል።

በዚህ ሁሉ በአዲስ አበባ ላይ ሐዘን አጥልቶባታል። በዚያው ማርሻሉ በሚገባበት ሰዓት ከባድ ዝናም ጥሎ፣ አካባቢው በጭቃ ተጨማልቆ፣ ወንዞች እስከገደፋቸው ሞልተዋል። እንባዉም የሰውን ፊት አጥቦታል። ሀገር ወዳድ ጀግኖች በየቦታው ጥግ እየያዙ የጠላትን ወታደር በጥይት መምታት ጀመሩ። ይህንን ለመከላከል የጣልያን ወታደሮች ያዩትን ሁሉ መግደል ያዙ። እስቲን ከአንድ ሺህ አምስት መቶ ያላነሱ ኢትዮጵያውያን ሞቱ።[2] ጣልያኖች ብመኪናም፣ በፈረስም፣ በእግርም እየተንቀሳቀሱ ማምሻቸውን የከተማይቱን ቁልፍ፣ ቦታዎች ያዙ፤ የቀረውን ደግሞ በማግስቱ ያዙ።

የኢትዮጵያ መያዝ ሮም ሌሊት ላይ ተሰማ። ሕዝቡ በማግሥቱ ጥዋት ተነቅንቆ ወጣ። ሞሶሎኒም፣ "ሮያሣ ቪንሲያ በተባለው አደባባይ ከተሰመደው ሰገነቱ ላይ ብቅ ባለ ጊዜ፣ ምድር እስክትቀልጥ ጫጫታ ሆነ። ሞሶሎኒ እጅግ ከፍ ባለ ድምፅ ተናገረ፡- "...ባለፈው 3000 ዓመታት ታሪካችን ውስጥ ኢጣልያ አኩሪና ታሪካዊ ሥራዎችን ሠርታለች። ይህ የዛሬው ግን...ከሁሉ የበለጠ ታሪካዊ ሥራ ነው... የሰላም መሠረት ዛሬ ተጣለ..." አለ።[3] እሱ ያን ይበል እንጂ፣ የዓለም ሕዝብ ከዚያ በፊት አይቶት ወደ ማያውቅ አዲስ ጦርነት እገባ መሆኑን አልጠረጠረም።

የጣልያን ጦር በገባ ጊዜ አዲስ አበባ በድን ሆነች። የንጉሣውያን ቤተሰብ እና መኪንንቱ በተከታታይ በመርከብ እየተሳፈሩ ወደ አውሮፓ ተጉዘአል። ንብረትና ገንዘብ የነበራቸው ድርጅቶች ተዘርፈዋል። ጀግኖች መሣሪያዎቻቸውን ይዘው በከተማይቱ አካባቢ ባሉ ተራሮች ለፍልሚያ ተዘጋጅተዋል። ሕዝቡም በስጋት ክከተማው ዙሪያ ተጠልሎአል። ከሦስት ቀን በኋላ ሰላማዊው የከተማይቱ ነዋሪ ወደየቤቱ መመለስ ጀመረ። ሬሣው እየተጠረገ የጽዳት ሥራ ተካሄደ።

በአርበኞች ዘንድ የሃሳብ መለዋወጥ ተደረገ። ዋናው ሃሳብ አዲስ አበባ የገባውን የጣልያን ጦር ሳይደፍጅ ደምስሴ ከተማይቱን ከጠላት ይዞታ

ለማስለቀቅ ነበር። ጣልያንን ኢትዮጵያን ያዝኩ ብሎ በዓለም ለነዛው ወሬ ማስተባበያ ስለሚሆን፣ የዚህ ጉዳይ ጠቀሜታ ትልቅ ሆኖ ተገኘ። "የኢትዮጵያ መሬትና በውስጡ የሚገኙ ሕዝቦች በሙሉ የኢጣልያ መንግሥት ተገዥዎች ናቸው። የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥትነት ለኢጣልያ ንጉሥና ለዘሮቹ ዞሮአል..." ብሎ ሞሶሎኒ ያወጣውን አዋጅም የሚያፈርስ ይሆናል፤ በሀገር ውስጥም ጠንካራ ጦርነት (ተቃውሞ) ይቀሰቅሳል። ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ገፅኔቭ፣ በዓለም ማኅበር ጉባዔ የሚኖራቸውን ተደማጭነት ያጠናክራል። ጣልያን በኢትዮጵያ ላይ ያገኘችውን ይዞታ ለማወቅ መንግሥታት የያዙትን አሽቅድድም ይገታል። የጣልያንን ጦር ያዳክማል።

ነገር ግን ይህንን የመሰለው ታላቅ ሥራ በተናጠል፣ በአንድ ቡድን ለማከናወን የሚቻል አይደለም። ስለዚህ በአዲስ አበባ ዙሪያ የነበሩ ኃይሎችን በጉበረት፣ በአንድ ጊዜ ለማንቀሳቀስ ተሞከረ። አዲስ አበባ የሚገባበት ጊዜ ለሐምሌ ማርያም፣ ማለትም በሐምሌ 21 ቀን 1927 ዓ.ም እንዲሆን ተወሰነ። የቡልጋ ጦር፣ በደጃዝማች ፍቅረማርያም አስተባባሪነት በሾላ በር፣ የመርሐ ቤቴ ጦር፣ በደጃዝማች አበራ ካሣ አዛዥነት በእንጦጦ በር፣ የገነት ጦር መኰንኖች፣ በአዛዦቻቸው መሪነት በጉለሌ በር፣ የደጃዝማች ባልቻ ጦር በስበታ እንዲገቡ ተመደቡ። የእነዚህ ኃይሎች መገናኛ ታላቁ ቤተ መንግሥት ላይ እንዲሆን ተወሰነ። መልዕክተኞች በያሉበት ተላኩ።

አዲስ አበባን መልሶ ለመያዝ የወጣውን ዕቅድ በሥራ ላይ ለማዋል ታላቅ ሙከራ ተደረገ። በደጃዝማች ፍቅረ ማርያም የተመራው ጦር ከሸንኮራ ተንቀሳቅሶ፣ የረርን ወደ ደቡብ በመተው ተጠጋ። አሁን ገርጂ በሚባለው አካባቢ አድርጉ በአብዋሬ በኩል በመግባት፣ በታላቁ ቤተመንግሥት የነበረውን የጠላት ጦር አጠቃ። የአንድ ሌሊትና የሁለት መዓልት ውጊያ አካሄደ።[4]

በደጃዝማች አበራ ካሣ የተመራው ጦር እንደተጠበቀው በእንጦጦ ገብቶ እስከ ሽሮ ሜዳ ድረስ ተጠጋ። ሆኖም ወደ ከተማ ሳይገባ ተመለሰ። በደጃዝማች አበራ አመራር ልልነት ሳይሆን አልቀረም። አቡነ ጴጥሮስ በዚህ ሁኔታ ማዋጋታቸውን ትተው ፍኖተ መስቀላቸውን ተሸክመው አዲስ አበባ ገቡ።

በገፈርሣ የመጣው ጦር እስከ ራስ ደስታ ሆስፒታል ድረስ አጥቅቶ ብዙም ሳይቆይ ተመለሰ። በደጃዝማች ባልቻ የተመራው ጦር እስከ አሮጌው አውሮፕላን ማረፊያ ድረስ ተጠጋ። በዚያ የነበሩ የጠላት አውሮፕላኖችን የማውደም ዕድሉ መልካም ነበር፤ ጦሩ ግን ዕድሉን ሳይጠቀምበት ቀረ። በሥልት መዓደል ሳይሆን አልቀረም። ከአዲስ አበባ ዙሪያ የመጣው አርበኛ ይህንን ሁሉ ሙከራ ሲያደርግ፣ የከተማው ነዋሪ እንዳች እንቅስቃሴ አላሳየም። እስከ ግንቦት 7 ቀን 1928 ዓ.ም ድረስ 11,353 ጠመንጃ፣ 53 መድፍ፣ 191 መትረየስ፣ 169 ሽጉጥ ለጣልያን አስረክቦ ስለነበር፣ እጁን አጣጥፎ በመቀመጥ ተመልካች ሆነ።[5]

አዲስ አበባን መልሶ ለመያዝ በተደረገው ሙከራ የተሰለፈው አርበኛ ብዛት በትክክል አልታወቀም። ግራዚያኒ 100,000 እንደነበረ በበኩሉ ገምቶአል። ከፍርሃት ቄምር የተደረገ ግምት ሳይሆን አልቀረም። አውሮፓውያን ከ10,000 እንደማያልፍ ግምት ሰጥተዋል። ይህም አነስተኛ ይመስላል። በዳጃዝማች ፍቅረማርያም መሪነት 10,000፣ በደጃዝማች ባልቻ 3,000፣ በደጃዝማች አበራ 5,000፣ በጉለሌ በኩል 2,000፣ በድምሩ 20,000 አርበኛ እንደተሰለፈ መገመት እምብዛም ስህተት አይሆንም። በአንፃሩ በጣልያኖች በኩል የነበረው ተከላካይ ኃይል 26,163 ነበር። እሱም በ2,060 የጦር መኰንኖች የሚመራና በ38 ጠንካራ ምሽጎች ውስጥ የተጠለለ ነበር።[6]

በዚህ ሁኔታ አርበኞች አዲስ አበባን መልሰው ለመያዝ ያደረጉት ሙከራ ከሸፈ። ለሙከራው መክሸፍ ልዩ ልዩ ምክንያቶች ነበሩት። በመጀመሪያ የማስተባበሩ ሂደት የተዋጣለት አልነበረም። ለተዋጊዎች መልእክት የደረሱት እየዘገዩ ነበር። በዚህ ላይ ጊዜው ክረምት በመሆኑ የሠራዊቱን እንቅስቃሴ የውሃ ሙላትና ጭቃ ጎተተው። እንደገናም የደጃዝማች አበራ ካሣ አመጣጥ በአንድ ልብ አልነበረም። በጉለሌ የመጣው ሠራዊትም እውቅ መሪ አልነበረውም። ባላምባራስ /ራስ/ አበበ ከነጭራሹም ዘመኩራው አልተሳተፉም። በእለቱም ከባድ ዝናም ስለዘነበ ሠራዊቱ ከመጎላለቆሉም በተረፈ፣ ክነጭ ቃታ መውዜር በስተቀር ሌሎች መሣሪያዎች በዝናሙ ምክንያት መተኮስ አልቻሉም። ከላይ እንደተጠቀሰው የከተማው ሕዝብ አልተፈናፈነም።

ምንም ግቡን ሙሉ በሙሉ ባይመታም፤ መከራው መልካም ውጤት አስገኘ። አዲስ ጦርነት መቀስቀሱን ለዓለም ጎበረተሰብ አበሰረ። በሀገር ውስጥም አርበኞችን አስተባበረ።

የአቡነ ጴጥሮስ መያዝ በጣልያኖች ላይ ሌላ ጭንቅ ፈጠረ። የጣልያንን መንግሥት እንዲደግፉ በብዙ ተለማመጡአቸው። ልምምጡም ውጤት ባላስገኘላቸው ጊዜ አስፈራሩአቸው። ቆራጡ ሊቀ ጳጳስ አልተበገሩም። ሕዝቡም፣ ምድሪቱም ለጣልያን መንግሥት እንዳይገዙ ገዘቱ። ጣልያን ምንም ሌላ ምርጫ ስለአጣ፣ ከአንድ ሣምንት ልምምጥና ማስፈራራት በኋላ፣ ሐምሌ 29 ቀን ለሞት አቀረባቸው። አሁን ሐውልታቸው ከሚገኝበት በስተደቡብ ምሥራቅ፣ ከቀድሞው ማስታወቂያ ሚኒስቴር አጥር አስጠግቶ አቆማቸው። አርሳቸውም ዓይናቸው እንዲሸፈን የተደረገውን ሙከራ ተከላከሉ፤ ፊታቸውን ወደ ግድግዳው እንዲያዞሩ የቀረበላቸውን ጥያቄም አልተቀበሉም። ቀጥ ብለው ቆሙ። በመትረየስ ጥይት አስደብደባቸው። በዚያም ሳይሞቱ ስለቀሩ፣ አስገዳዩ መኰንን በሽጉጥ ራስ ቅላቸውን በታተነው።

ንጉሠ ነገሥቱ አብረዋቸው ወደ አውሮፓ እንዲሄዱ ቢጋብዙአቸው "በጭቼን ለማን ጥዬ?" ያሉት፤ በእንጦጦ በኩል የመጣው አርበኛ የተንቀሳቀሰበትን ዓላማ ትቶ ወደ ጎሏ በተመልስ ጊዜ፣ ተሰይተው አዲስ አበባ

የገቡት እኚህ ኢትዮጵያዊ ሲቀ ጳጳስ፣ የጨረሱትን የሥጋ ጉዳይ፣ በግብር ፈጸሙት። በዚህ ድርጊቱ የጣልያን መንግሥት የቆመበትን የጭካኔ መሠረት ለመላው ዓለም በግብር አሳየ። የኢትዮጵያም ሕዝብ ቁርጡን አወቀው።

ጣልያንን በሙሉ ኃይላቸው ለመቋቋም ከቆረጡት ጀግኖች አንዱ ደጃዝማች ባልቻ ነበሩ። ክፔታቸው ከአጼ ምኒልክ እረፍት በኋላ በተካሄደው የሥልጣን ሽኩቻ ወድቀው ብዙ መንገላታት የደረሰባቸው እኚህ አርበኛ፣ በወቅቱ የሰማንያ ዓመት አካባቢ ሽማግሌ ነበሩ። ሆኖም የደረሰባቸውን መንገላታት ከቁም ነገር ባለመቁጠር፣ የዕድሜአቸውንም መሸምገል ባለማሰብ፣ ትግል ጀመሩ። መካር ቢቀርባቸው፦ "ጌታዬ ምኒልክ አልጋዬን ለማ ጥሰህ መጣህ ቢሰኝስ?" በሚል ጥያቄ ዘንተው። ጣልያንም በበኩሉ ሊያግባባቸው ሞከረ። ማስዮናዊ መስሎ ንብቶ፣ የአማርኛ ቋንቋ አጥንቶ፣ አገር ያምታታ የነበረ አንድ ጣልያናዊ ላከባቸው። እሱንም ደብቀው በያዝዋት አንዲት መሣሪያ፣ በጥይት ገደሉ። በዚህን ጊዜ የጣልያን መንግሥት አጸፋዊ እርምጃ ለመውሰድ ከበባቸው። ደጃዝማች ባልቻ አባ ነፍሶ ጣልያንን ብዙ ካስጨነቁት በኋላ በነሐሴ ወር 1928 ዓ.ም ተገደሉ።



የሁለት ትውልድ አርበኛ ደጃዝማች ባልቻ አባነፍሶ።

ምንም ግቡን ባይመታ፣ አርበኞች አዲስ አበባን ነጥቀው፣ መልሰው ለመያዝ ያደረጉት ሙከራ ጣልያንን አስደነገጠው። ከተማይቱን ከጅቡቲ ጋር የሚያገናኘውን የባቡር ሐዲድና፣ ከአሰብና ከአሥመራ ጋር የሚያገናኙትን የሰሜኑን የመኪና መንገዶች ለመቁረጥ የሚደረገው ርብርቦሽ ማለቂያ የሌለው ሆነ። ስለዚህ የከተማይቱን ጥበቃ ማጠናከር ግድ ሆነ። ጣልያን ብዙ ወታደር አስገባ፣ የከተማይቱን ዙሪያ በአሾህማ ሽቦ አጠረ። ሽቦው ርስበርሳቸው አራትና አምስት ሜትር ተራርቀው በተተከሉ፣ ጠምዛዛ አንጓ ባላቸው ብረቶች

ላይ ተተብትቦ የታሠረ ነበር። ወደ ከተማይቱ ለመግባትና ለመውጣት የሚቻለው በአሥር በሮች ብቻ ሆነ። ከእነዚህም ዋነኞቹ የአንጦጥ፣ የየካ፣ የገፈርሣ፣ የሰበታና የአቃቂ በሮች ሆኑ። በበሮቹም ላይ ከባድ ቁጥጥር ተደረገ። ያለይለፍ የፈቃድ ወረቀት ሰው መውጣት፣ መግባት ቀረ።



የሰማዕቱ የአቡነ ጴጥሮስ ሓውልት

በማሕል አገር የነበረው አርበኛ አዲስ አበባን ለመያዝ ያደረገው ሙከራ እንደ አልተቃና በታወቀ ጊዜ፣ በወቅቱ እንደ ንጉሠ ነገሥቱ አንደራሴ ሆነው በጦሬ ከተማ የሸሩት ራስ እምሩ ተንቀሳቀሱ። በራስ እምሩ የሚመራው ጦር ዓላማ በጦሬ፣ በወለጋና በአምቦ በኩል ተወርውሮ አዲስ አበባን ለማጥቃት ነበር። እሱም ሳይቻል ቀረ። ደጃዝማች ፍቅረ ማርያምም ሸንኮራ ወደቁ። አዲስ አበባን መልሶ የመያዝ ጉዳይ ሕልም ሆኖ ቀረ።

ከተማይቱን ከውጭ አገር ያላትን ግንኙነት ለማስቀረት በሰሜኑ የመኪና መንገድና በምሥራቁ የባቡር ሐዲድ ላይ ይካሄድ የነበረው ትግል በተካረረ መልኩ ቀጠለ። በተለይ በባቡሩ ላይ በቀከታታይ የተጣለው አደጋ



የሁለት ተውልድ አርበኛ ደጃዝማች ባልቻ አባነፍሶ።



የሰማዕቱ የአቡነ ጴጥሮስ ሓውልት

ብዙ የጣልያን ወታደሮች ጨረሰ። የጦር ሹማምንቱንም ማራ አጋባ። የጣልያን መንግሥት ለዚህ ችግር ማቃለያ መስለው የታዩትን እርምጃዎች ወሰደ።

ማርሻል ባዶሊዮ ወደ ሀገሩ እንዲመለስና በቦታው ጀነራል ግራዚያኒ እንዲተካ ግንቦት 24 ቀን 1928 ዓ.ም /ጁን 1 ቀን 1936/ ተሰጥቶ የነበረው ውሣኔ ተግባራዊ ሆነ። እንደሚታወቀው ግራዚያኒ በሲቢያ ሕዝብ ላይ ታላቅ ጭፍጨፋ በማካሄድ፣ በዚያ ሀገር ይካሄድ የነበረውን የነፃነት ንቅናቄ በማጥፋቱ፣ በጣልያን መንግሥት ዘንድ አመኔታን ያገኘ ጨካኝ ሰው ነበር። በወቅቱ፣ ለፍላጐቱ ማሳኪያ እንዲረዳው መሣፍንቱንና መኳንንቱን፣ የተማሩ ወጣቶችን ጭምር እንዲጨርስ ከሞሶሎኒ መመሪያ ተሰጠው። እሱም መሣፍንቱን፣ መኳንንቱን፣ ሊቃውንቱን በየአደባባይ እያንገዋለለ፣ ለጣልያን መንግሥት ያላቸውን ታማኝነት በሕዝብ ፊት እንዲገልጹ አስገደዳቸው። ከጥንት ቁሳራዊት ሮም ጀምሮ ሲሠራበት የኖረው፣ በጡንቻ በሰላም እንዲኖር የማድረግ ግብር /ፓክስ ሮማና/ በሥራ ላይ አዋለ።[7]

ጣልያኖች ደማቸውን ያፈሰሱበትን፣ የራሳቸውን ጥቅም የመገንባት ሥራ፣ በአዲስ አበባም ያዙ። ባሣር በመከራ የተቋቋመ ትምህርት ቤቶች ተዘጉ። የዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት፣ የጣልያን አየር ኃይል ሠፈር በመሆን ተገጣጣሚ ቤቶች በተጨማሪ ተሠሩለት። አሮጌው ትምህርት ቤት የወታደርና የቱስለኛ መታከሚያ ሆነ። የተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት የጣልያን ልጆች እንዲማሩበት ተደረገ። ከኢትዮጵያውያን፣ ስድስት የሚሆኑ የታላላቅ መኳንንት ልጆች ብቻ ጉለሌ፣ ደጃዝማች ይገዙ ሠፈር ለፋሽስት ልጆች ማስተማሪያ ከተሠራው ትምህርት ቤት ገቡ። ከእነሱም ውስጥ የራስ ጌታቸውና የራስ ሥዩም ልጆች ነበሩባቸው። ለሌላው ኢትዮጵያዊ የትምህርት ዕድል የለም።

የጣልያን መንግሥት ካተኮረባቸው ተቋማት ዋነኛይቱ የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ነበረች። የነበሩት አማራጮች ሁለት ሆኑ። አንድም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከግብጽ ተገዝነት ተላቅቃ፣ ራስዋን ችላ እንደምትተዳደር ሆኖ፣ አቡነ ቄርሎስ ሥራቸውን እንዲቀጥሉ። አለበለዚያ ደግሞ የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ሌላ ኢትዮጵያዊ ጳጳስ መርጣ ራስዋን እንድትችል ማድረግ ሆነ። ግብጻዊው ሊቀ ጳጳስ፣ አቡነ ቄርሎስ ርም ድረስ ሄደው ከተነጋገሩ በኋላ፣ ወደ እስክንድርያ ሄዱ። በአቡነ ዮሐንስ 10ኛ የተመራው የእስክንድርያ ሲኖዶስ ከሁለቱ ሃሳቦች አንዱንም ሳይቀበል ስለቀረ፣ ከቀድሞዎቹ ኢትዮጵያውያን ሊቃነ ጳጳሳት አንዱ፣ አቡነ አብረሃም የሊቀ ጵጵስናውን ሥራ በአገር አቀፍ ደረጃ እንዲይዙ፣ ታህሣሥ 21 ቀን 1929 ዓ.ም ተደረገ።[8]

ከተማይቱ መረጋጋት ስትጀምር፣ በወጣቶቹ ዘንድ ቁጭት እየበረከተ ሄደ። ካህናት አቁዋማቸውን በማጠንከር፣ ከላይ የሚንቆረቁረውን ስብከት እንዲሁም በተግባር እንዲውል የሚፈሰውን ትዕዛዝ፣ መቀበላቸው ቀረ።

ሁኔታዎች እየተካረሩ ሄዱ። ጣልያኖች ይህንን የተካረረ ስሜት ለማብረድ ጥረት በሚያደርጉበት ወቅት፣ የጣልያን ንጉሥ አልጋ ወራሽ ሚስት ስለወለደች ጥሩ አጋጣሚ ተገኘ። ግራዚያኒ ለድሆች ገንዘብ እሰጣለሁ በሚል ምክንያት ሕዝብ እንዲሰባሰብ አደረገ። መኪንንትና መሣፍንቱም የችሮታውን ሥራ እንዲያደንቁ ተጠሩ። በዚህ ምክንያት የካቲት 12 ቀን 1929 ዓ.ም፣ አሁን በዩኒቨርሲቲው ቅጥር ግቢ የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ኢንስቲቱት በሆነው፣ የበፊተኛው የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ቤተ መንግሥት፣ ታላቅ ሕዝባዊ ስብሰባ ተደረገ። 3,000 ያህል ድሆችና እጅግ ብዙ ሰው በተገኘበት በዚህ ስብሰባ ላይ፣ አብርሃ ደቦጭና ሞገስ አስገዶም፣ ሰባት የእጅ ቦምቦች በመወርወር፣ ማርሻል ግራዚያኒን ጨምሮ ሠላሣ የጣልያን ሹማምንትና የጦር አለቆች አቆሰሉ።

በዚህ ጊዜ ግራዝያኒ በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት በከተማይቱ የነበሩ የጣልያን የጦር ኃይሎች በሙሉ ኃይላቸው ተንቀሳቀሱ። በወቅቱ በከተማይቱ ላይ ሠፍረው የነበሩት ወታደሮች ከ85,000 አያንሱም። ከእነሱም 42% ጣልያናውያን ወታደሮች፣ ከእነሱም 47% ጥቁር ለባሾች የሆኑት፣ የታጠቁ ጣልያናውያን የፋሽስት ካድሬዎች ነበሩ፣ የተቀሩት ከኤርትራ፣ ከሲቢያና ከሶማሊያ የተመለመሉ የቅኝ ግዛት ወታደሮች ነበሩ። እነዚህም ሕዝቡን እንደአገኙ ጨፈጨፉት። ቤት እየዘጉ አቃጠሉት፣ እጁን ወይም እግሩን በሽቦ ከመኪና ጋር እያሠሩ፣ በመንገድ ላይ ጐተቱት። እልቂቱ፣ ዓርብ ዕለት የካቲት 12 እኩለ ቀን አካባቢ የጀመረ እስከ የካቲት 14 ቀን እሁድ ከቀትር በኋላ፣ እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ድረስ ቆየ። ሠላሳ ሺህ ሰው አለቀ፣ አራት ሺህ ቤት ተቃጠለ።[9]

ጣልያኖች አብረሃ ደቦጭ እና ሞገስ አስገዶምን ማደን ጀመሩ። መሣሪያ ደብቃችሁልል፣ አብርሃ ደቦጭና ሞገስ አስገዶምን አብልታችኋል፣ አጠጥታችኋል እያሉ በከተማዋ ላይ ጭፍጨፋ አነገሱ። ከደብረ ሊባኖስ፣ ከዝቋላና ከዜና ማርቆስ ገዳማት ከአንድ ሺህ ያላነሱ መነኮሳትና መነኮላስት ገደሉ። ጐንደር ማኅበረ ሥላሴንም አቃጠሉ። ሰባት ሺህ አሥረኞች ወደ ኤርትራ፣ ሶማሌና ኢጣልያ ተወሰዱ።[10]

አብርሃ ደቦጭና ሞገስ አስገዶም እነማን ነበሩ? አብርሃ ደቦጭ፣ ሞገስ አስገዶም እና ስብሐት ኤርትራውያን ነበሩ። በአሥመራ ትምህርት ቤቶች የጣልያን ቋንቋ ከተማሩ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ሥራ የያዙ ናቸው። በሕዝብ ዘንድ የነበረባቸው ጥርጣሬ ከባድ እንደ መሆኑ፣ አመጣጣቸው ለስለላ ሥራ በጣልያኖች ተልከው ሳይሆን አልቀረም። አብርሃ ደቦጭ የሚሠራው በጣልያን ለጋሲዮን ሲሆን፣ ስብሐት ደግሞ የጣልያን ወዳጅ በነበረችው በጀርመን ለጋሲዮን ነበር። እነዚህ ወጣቶች በጣልያኖች እየመረራቸው ሲሄድ ለወገኖቻቸው መቆርቆርና እርስበርሳቸው መመካከር

ጀመሩ። ከዚህም የተነሣ አብርሃ ደቦጭና ሞገስ አስገዶም የየካቲት 12 ቀኑን አደጋ ለመጣል በቁ።

ይህ አልቂት ሌላ አዲስ ሁኔታ ፈጠረ። የጣልያን ባለሥልጣኖች ስለሰላም የሚለፈልፉት ጉዳይ ሁሉ ከንቱ መሆኑ ተረጋገጠ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ለእልቂትና ለባርነት መዳረጉን አወቀ። በመሆኑም፣ ልብ ያለው ክጫካ ገባ። ይህም፣ መዳከም ጀምሮ የነበረውን አርበኝነት እንደገና መልሶ አጠናከረ። በየካቲት 12 ቀን ጉዳይ የአዲስ አበባ ካህናት አልነበሩበትም። ነገር ግን ጣልያኖች የአራዳ ጊዮርጊስን ለማቃጠል ሞከሩ። ይህ ባልተሳካላቸው ጊዜ ከዚሁ ከአራዳ ጊዮርጊስ፣ ከየካ ሚካኤል፣ ከኡራኤልና ከሴሎችም አድባራት ሊቃውንትን እያሠሩ ወደ ውጭ አገር ላኩአቸው። ይህም ካህናት ከአርበኞች ጋር እንዲያብሩ አደረገ። በጣልያን ላይ ክንዳቸውን ያነሱ ካህናትም ነበሩ። አለቃ መርሻ ከየካ ሚካኤል ወደ ቀበና ሄደው በገዛ ቤታቸው ውስጥ ሸፈቱ። አራት ጣልያን ገድለው ሞቱ። መምሬ በየነ የአራዳ ቅዱስ ጊዮርጊስን ይዘው ከባላምባራስ /ራስ/ አበበ አረጋይ ጋር ተቀላቀሉ። በአዲስ አበባ ከነበረውም ሕዝብ፣ ነፃነት ፈላጊው አርበኝነት ገባ።

የኢትዮጵያውያንና የጣልያውያን በአንድ ከተማ ውስጥ መኖር፣ ጉርብትና እና መቀራረብን ፈጥሮ አስቸገረ። የፋሽስት አስተዳዳሪዎች ከኢትዮጵያ ሴቶች ተጠንቀቁ። በመሆኑም ከየሴትኛ አዳሪው ጭን የሚፈላው ክልስ፣ በቅርብ ጊዜ ውስጥ ታላቅ ቅልቅሎሽ እንደሚፈጥር ታወቃቸው። ከዚህ ቅልቅሎሽ ሊገኝ የሚችለው ጥቅም አልታያቸውም። የዘር ርክሰት እንደሚያደርስ፣ ከአሱም ጋር መናቅ እና መዋረድ እንደሚመጣ ሆኖ ተሰማቸው። የየካቲት 12 ቀን አደጋ መከሰቱ፣ ለዚህ ችግር መፍቻ መስሎ የታያቸውን እርምጃ እንዲወስዱ ምክንያት ሆናቸው። ጥቁርና ነጭ የሚኖርበት ቦታ እንዲለይ አደረጉ። ቀድሞ ኢንዲጂኖ እየተባለ በአካባቢው ጎብረተሰብ ይጠራ የነበረው ሰፈር፣ ለጥቁር ዜጋ መኖሪያ እንዲሆን ተመደበ። በመሐንዲስ ተሸንሽኖ ለኢትዮጵያውያን መሥፈሪያ ሆነ። ከፊታውራሪ ሃብተ ጊዮርጊስ ድልድይ በስተምዕራብ ያለው የጥቁር፣ ከወንዙ በስተምሥራቅ ያለው የጣልያኖች መኖሪያ ሆነ። በእነሱም በራሳቸው መካከል ልዩነት ነበረ። ከንብርኤል በታች ያለውን ቦታ፣ ኢንቺስ የተባለው ድርጅት ቤት እንዲሠራበትና ለሽማምንት መኖሪያ እንዲሆን፣ ከሜክሲኮ አደባባይ በታች ያለው ቦታ ፎቶ እየተሠራበት የሕዝብ መኖሪያ እንዲሆን ተመረጠ።

ከየካቲት 12 ቀን 1929 ዓ.ም እልቂት በኋላ በሽማምንቱና በግራዚያኒ ላይ የሕዝብ ጥላቻ ተፈጠረ። በጣልያኖችም ዘንድ ሞገሱ ቀነሰ። ሊሶና የተባለው የጣልያን የቅኝ ግዛቶች ሚኒስትር ግራዚያኒ ከሹመቱ እንዲሻር ሞሶሎኒን ወተወተ። ቀድሞውንም ግራዚያኒ የተሾመው ሊሶና ሳይጠየቅ ስለነበረ፣ ጥያቄውን አልቀበልም ለማለት አስቸገረው። ግራዚያኒ ከደረሰበት የግድያ መከራ ቢድንም፣ ድንጋጤው የማይለቀው ሆነ። ቢሆንም

ራሱን ከውርደት ለማዳን፣ ጥፋቱ የሊሶና እንደሆነ አድርጉ ማሳየት ያዘ። አዲስ አበባ ውስጥ የነበሩ ካራቢኒየር የሚባሉት የደህንነት ኃይሎች ግራዚያኒን ደገፉ። ነገር ግን ግራዚያኒ ከሦስት መቶ ሃምሣ ቦታ ቆስያለሁ የሚል ዝማሬ ይዘ፣ አንዳች ማሻሻያ ማድረግ አቃተው። በጭካኔ ሥራው ገፋበት። ሁኔታው የማያስኬድ እየሆነ ስለቀጠለ፣ ግራዚያኒ ተሻረ። ቁስሉ አንዳይቆጠቁጠው የነጋሌ ጦር ሜዳ ማርሻል ተብሎ 500,000 ሊራ የጡረታ አበል ተቆረጠለት። የግራዚያኒ ደጋፊዎች ተቃውሞአቸውን ስለአጠናከሩ፣ ሊሶናም 100,000 ሊራ ካሣ ከሞሶሎኒ ተፈቅዶለት በሮም ዩኒቨርስቲ የቅኝ ግዛት ታሪክ ሊቅ ሆነ።[11]

ባላምባራስ /ጀነራል/ ተድላ መኮንን ከአዲስ አበባ ከተማ አምስት ጣልያኖች አፍነው መስደው ለገጣፎ ወንዝ አጠገብ ገደሉአቸው። ጣልያኖቹን የወሰዱአቸው፣ የአቡነ ተክለሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን ከሆነው አካባቢ መሆኑ ነው። በዋሻው ምድር ቤት ውስጥ ደጃዝማች መኮንን ወሰኔ ቀበረውት የነበረውን በርካታ ጠመንጃና ጥይት ወሰዱ። ደጃዝማች መኮንንን ግን ጣልያን ቀደም ብሎ ወደ አገሩ መስዶአቸው ስለነበረ፣ አርበኝነት እንዲገቡ ለማድረግ የተዘጋጀው ዕቅድ ከሸፈ። ሥራው የተቀነባበረው ኮተቤ በነበሩት በግራዝማች እንደሻው ነበር።[12]

በግራዚያኒ ምትክ፣ ዱክ አሜዲዮ ደ አምስታ፣ በሊሶና ምትክ ፓውሎ ቱሩዚ ተሾሙ። ዱካ ደ አምስታ ታህሣሥ 16 ቀን 1930 ዓ.ም /ዲሴምበር 26 ቀን 1937/ አዲስ አበባ ገቡ። ወዲያውም የአስተዳደሩን አረመኔነት ለመቀነስ ሙከራ አደረጉ። ሞኝ አበሻ፣ የተሻለ ነገር የተገኘ መሰለው። ነገር ግን የዱክ ደ አምስታ ዓላማ በለዘብተኛ አያያዝ ኢትዮጵያን ከዘላቂ መሥዋርት ውስጥ ለማስገባት ነበር። የዚህ መሥፍን መሾም ደጋፊም ተቃዋሚም ነበረው። ኢትዮጵያን ከፋሽስቶች ፊልቅቆ ወደ ኢጣሊያ ንጉሣውያን ቤተሰቦች የሚያገባ መሆኑ የማይቀር ሆነ። ፋሽስቶች ለሥልጣናቸው እንደ መሠሰታቸው፣ የንጉሣውያን ቤተሰቦች ደግሞ የኢጣልያ ዘውድ ከኢትዮጵያ ጣጣ ውስጥ እንዳይዘፈቅ ፊርተው ነበር።

የዱክ ደ አምስታ ሃሳብ ለጣልያን በርካታ ጥቅም ያስገኛል ተብሎ ተጠብቆ ነበረው። በኢትዮጵያ ውስጥ መረጋጋት ይፈጥራል፣ በአውሮፓ የነበረውን ጫጫታ ይቀንሣል፣ ለቦርነት የሚደረገውን ውጭ ወደ ልማት ሥራዎች ይመልሳል። አለመጠን የገነነውን የፋሽስት ፓርቲ ኃይል፣ በተለይም የሞሶሎኒን ሥልጣን ያቀዘቅዛል። ስለዚህ ዱካ ደ አምስታ ቀደም ብሎ ግራዚያኒ ያጨመላለቀውን አስተዳደር ለማሻሻል ሞከረ። የአዲስ አበባን ከተማ በ14,000 ስኴር ኪሎሜትር ውስጥ ለመክለልና ከሸዋ ለመነጠል ኅዳር 20 ቀን 1929 ዓ.ም /ኖቬምበር 11 ቀን 1936/ የወጣውን አዋጅ ሻረ። የሸዋን አንድነት መልሶ አጸና። ቢሆንም በወታደራዊ ሥራ ረገድ ምዕራብ፣ ሰሜን፣ ምሥራቅ ተብሎ በሦስት እንደ ተከፈለ ቆየ።

ጣልያኖች ከመግባታቸው በፊት በአዲስ አበባ ከተማ ሦስት ሲኒማ ቤቶች ነበሩ። እነሱም፦ ደጉል አደባባይ ከሚባለው አካባቢ አንዱ፣ አሁን የመብራት ኃይል ባለሥልጣን ከአለበት፣ ሁለተኛው ሲኒማ አምፒር ከአለበት፣ ሦስተኛው ደግሞ ከማዘጋጃ ቤቱ ፊት ለፊት ከሚታየው ባዶ ቦታ ላይ ነበሩ። ሶስቱም ጣልያኖች በገቡ ጊዜ ተቃጠሉ። በምትካቸው ዛሬ ሲኒማ ኢትዮጵያ የሚባለው ሲኒማ፣ ሮማ ተብሎ፣ ከነፃነት በኋላ ሲኒማ አድዋ ተብሎ የነበረው፣ ሲኒማ ማርኮኒ ተብሎ፣ አራት ኪሎ አሁን የሚይንስ ፋክልቲ ከአለበት ጠርዝ ላይ ሲኒማ አዲዮን ተብለው ለጣልያናውያን ተከፈቱ። ለአበሾች ደግሞ መርካቶ፣ ራስ ኃይሉ፣ አሁን ራስ የሚባለው ሲኒማ ቤት ተከፈተ።[13]

የወጣቱን ሃሳብ ለማረጋጋትና ጊዜውን የሚያሳልፍበት ዕድል ለመስጠት፣ ስፖርት ተስፋፋ። አራዳ፣ ስድስት ኪሎ፣ ቀበናና እንጦጦ የሚባሉ የእግር ኳስ ቡደኖች ተቋቋሙ። እነ አቶ ይድነቃቸው አሸቴ የስፖርት ሰው መሆን የጀመሩት፣ በዚያን ዘመን ነው። የብስክሌት ውድድርም ነበር።[14] በየአደባባዩ የወሬ ማድመጫ ሬዲዮ ተተከለ። የሮም ብርሃን የተባለ ወርሐዊ መጽሔት፣ እንደዚሁም ተሐደስት ኢትዮጵያ የሚል ሳምንታዊ ጋዜጣ ይታተሙ ጀመር። እንደ ቀድሞው ሁሉ፣ የመንግሥቱ የሥራ ቋንቋ አማርኛ ነበር።

የከተማዋ ሴቶች በበኩላቸው የራሳቸውን ሥራ አካሄዱ። አልጋቸውን እየዘረጉ፣ ፍራሻቸውን እያመቻቹ፣ መጨጊያ ያለው ወንበር እያዘጋጁ ተቀመጡ። ቤተሰቦቻቸውን ላይዙ ነጠላቸውን የመጡ ጣልያኖች ከዚያ የተፈጥሮ ወጥመድ ገቡ። ይህ ሁኔታ ችግር ፈጠረ። እንደገለፅኩት፣ ነጭና ጥቁር እንዳይቀላቀል የሚያግደው ሕግ ተጣሰ፣ ክልሶች በረከቱ። ጣልያናውያን ሚስቶች ተቆጡ። ከጣልያን ሠራዊት የሚበዛው በቀጥኝና ጨብጥ ተበከለ፣ ከአበሻውም እንደዚሁ። የጣልያኖች ምሥጢር ከከተማ እያፈተለከ ለአርበኞች ይደርሳል። በጠቅላላው ምሥጢር የመጠበቅ፣ የማሰብና የመሥራት አቅም ተቀነሰ።[15]

ሞሶሎኒ የገመተው ኢትዮጵያ ስትያዝ ልዩ ልዩ ሙያ ያላቸው ጣልያናውያን ተሸቀዳድመው ይገባሉ ብሎ ነበር። ነገር ግን እንደተጠበቀው አልሆነም። ጦርነቱ በመቀጠሉ ምክንያት፣ ብዙዎቹ ወደ ኢትዮጵያ ለመምጣት አልፈለጉም። ከፍተኛ ባለሙያዎች እንዲመደቡባቸው ከተፈቀዱት 2700 ሥራዎች ላይ የተገኙት ባለሙያዎች፣ 1,350 (50%) ብቻ ነበር።

በአቀጣጠርም ረገድ እንዲሁ ችግር አጋጠመ። የሚፈልጋቸውን እየመረጠ የመቅጠር ሥልጣን ጎዳር 5 ቀን 1930 ዓ.ም ቢሰጥም፣ የቅኝ ግዛት ጉዳይ ሚኒስትር መቅጠሩን ስለ ቀጠለ አዋጁ ሳይከበር ቀረ። ይህንን የባለሙያ እጦትና የአቀጣጠር ችግር ለማቃለል፣ ከጦሩ እየመረጡ መቅጠር ግድ ሆነ። ይህ ደግሞ የተዋጊውን ኃይል ቀነሰ። ለቁጥጥር ባለመመቸቱ ስንት

ሠራተኞች እንደተመደቡ ለማወቅ እንኳን አዳገተ። ቴሩቪ 6,943 ቢልም፣ ከ10,000 የሚያንሱ አልነበሩም። በዚህ ላይ ደግሞ ከተቀጠሩት ሠራተኞቹ ውስጥ 50%ቱ በቂ እውቀትና የሥራ ልምድ አልነበራቸውም።

በዛ ላይ ደግሞ አብዛኞቹ ቤተሰብ ስለሌላቸው ጠጭዎች፣ ሴሰኞች፣ ፍቅረ ንዋይ የተጠናወታቸው ሆኑ።[16] የጦር መኰንን ተብሎ የተመደበው ኢጣሊያዊ፣ በአርበኝነት ወንድምዋ የሞተባትን ኢትዮጵያዊት እቁባቱን ከማስተዛዘን የማይገታ ሆነ። እንዲህ መሰሎቹ ሁኔታዎች ሁሉ የዱካ ደ አምስታን አስተዳደር ከማጥ ውስጥ ከተቱት።

ሁኔታዎች በእንዲህ እንደአሉ፣ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ተቀሰቀሰ፣ እናም ነገሮች በፍጥነት ተለዋወጡ። ሞሶሎኒ ከሂትለር ጐን መቆሙን አስታወቀ። አሱም ወዲያው በሣልሣዊ ኢማኑኤል ትዕዛዝ ተይዞ ታሠረ። ሂትለር የአየር ወለድ ኃይል ልኮ አስፈታው። ወደ ጀርመን አገር አስወስዶ ከአነጋገረው በኋላ ወደ ጣልያን ሊመልሰው ሞከረ። ነገር ግን በጣልያን አገር ውስጥ የርስበርስ ጦርነት ተቀሰቀሰ። ጃፓን በፊናዋ ፐርል ሃርበር የተባለውን የአሜሪካን ወደብ በአይሮፕላን ደብድባ፣ በአምስት የአሜሪካን የጦር መርከቦች ላይ ጉዳት አደረሰች። ከዚያን ጊዜ አንስቶ አሜሪካን ከዳር ሆኖ ተመልካችነቷን ትታ፣ ከጦርነቱ ገባች።

ሁኔታዎች እየተሰወጡ ስለሄዱ፣ ሞሶሎኒም በግልፅ ከሂትለር ጐን መቆሙን ስለ አስታወቀ፣ እንግሊዝ ጦርነቱን ወደ አፍሪቃ አዞረችው። በዛው መሠረት በምሥራቅ አፍሪካ አዲስ የጦር ግንባር ተከፈተ። ሲቢያ የጦር ሜዳ ሆነች። ስዊዝ ካናል ለጣልያን መርከቦች ዝግ ሆነ። ምሥራቅ አፍሪካ ላይ የፈሰሰው የጣልያን ሠራዊት ብቻዉን ሆነ፤ ከአገሩ ጋር የነበረው ግንኙነት ተቋረጠ። በመቀጠል እንግሊዝ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴን ከስንደን አንቀሳቅሳ ካርቱም አስገባች፣ በደቡብ፣ ከኬንያ፣ ከምሥራቅ፣ በበርበራ ጦርዋን አንቀሳቀሰች። ከካርቱም በአሜድላ በኩል ንጉሠ ነገሥቱን ይዞ ጉጂም የሚገባ፣ በአሰላ በኩል ገብቶ አሥመራን የሚይዝና የቀይ ባሕርን የሚቆጣጠር፣ በእንግሊዝ የሚታዘዝ ጦር፣ ከዓለም ማዕዘናት አቀረበች። በምሥራቅ አፍሪካ የነበረው የኢጣልያን ሠራዊት፣ ከጠላቶቹ ጋር ተፋጠጠ፣ ለእልቂት ተጋለጠ። ዱካ ደ አምስታ የሚይዝ፣ የሚጥለውን አጣ።

የአዲስ አበባ ከተማ ሕዝብ ወሬውን ከዓለም ሬዲዮ ዕለት፣ በዕለት ይሠማ ነበር። የሰማው ላልሰማው እያሰማ፣ ሃሳብ ለሃሳብ ተዋወቀ። በጣልያኖች ላይ የነበረው አመለካከት ተለወጠ፤ እነሱም የከተማው አጠቃላይ ልቦና በጣልያኖች ላይ መለወጡ ታወቃቸው። የንጉሠ ነገሥቱ መምጣት ታወቀ። የነፃነት እንቅስቃሴ ጠነከረ፤ ባንዳ ከአርበኛ ጋር አበረ። ዱክ ደ አምስታ ገንዘብ በመርጨት፣ ሹመት በመስጠት፣ ወሬ በመንዛት፣ ሁኔታውን ለመቋቋም ሞከረ፤ ግን አልተቻለም። በምሥራቅ ያመጣው የኢትዮጵያ ነፃ

አውሮ ጦር ከሐረር አልፎ አዋሽን ተሻገረ። ንጉሠ ነገሥቱ ከቢልያ አልፈው ቡራ ገቡ። አዲስ አበባ ተጨነቀች።

ዱካ ደ አምስታ ውሣኔ ማድረግ ግድ ሆነበት። ምርጫው፡- አንድም መዋጋት፣ አለዚያም እጅ መስጠት ሆነ። መዋጋት ማለት፣ ሞት፣ በቅኝ ግዛት አገር ላይ እጅ መስጠት ደግሞ፣ የሞት ሞት ሆነበት። መዋጋት መረጠ። ለመዋጋት ደግሞ የኢትዮጵያውያንን ድጋፍ ማግኘት ግድ ሆነ። ራሱ መጠየቅ ውርደት ነበርና፣ የታማኞቹን ምክር አስጠየቀ። ተጠያቂዎች የታያቸውን፣ የሚጥመው የመሰላቸውን ነገሩ። የቀጨኔ መድኃኒ ዓለም አለቃ፣ አባ ገብረ መስቀል /አቡነ ዮሐንስ ዘትግራይ/ የተለየ ሃሳብ ነበራቸው። እሳቸውም "በአዲስ አበባ ከተማ ሕግን፣ ሴት፣ ሽማግሌ ሕመምተኛ አለ። በከተማው ላይ ጦርነት ሲከፈት ኢትዮጵያውያኑ አገራቸው ነውና ወደየወገናቸው ይሄዳሉ። የእናንተ ሰዎች፣ ጣልያኖች ወዴት ይሄዳሉ? ስለዚህ ከበረሃ ላይ እንኺ፣ ከከተማ ላይ ልትሞቱ አይገባችሁም" አሉአቸው። ንጉሤም በዚሁ አበቃ።[17]

ዱክ ደ አምስታ አዲስ አበባ ከተማ ላይ ለመዋጋት የነበረውን ሃሳብ ተው። ከከተማይቱ ወጥቶ ለመዋጋት ዝግጅት አልተደረገም። አዲስ አበባ ላይ ለመዋጋት በነበረው ዕቅድ ምክንያት ተላቅቆ በሩ ክፍት ነው። እንግሊዞች ከንጉሠ ነገሥቱ በፊት ለመግባት አዋሽን ተሻግረው ወደ አዲስ አበባ በመገስገስ ላይ ናቸው። ስለዚህ የዱካ ደ አምስታ ዕድል ወደ ሰሜን መሸሽ ብቻ ሆነ። ከተማይቱን ለእንግሊዝ እንዲያስረክብ ለከንቲባው ሥልጣን ሰጥቶ ወደ ደሴ፣ ከዚያም ወደ አምባላጌ ሸሸ። የጠላውን ውርደት አምባላጌ ላይ፣ የፈራውን ሞት ደግሞ ኬንያ አገር የሚቀበለበትን፣ የተቀበለበትን የመከራ ጉዞ ቀጠለ።

በኢትዮጵያ በኩል ሁኔታዎች ሌላ ቅርጽ ነበራቸው። የሸዋ አርበኞች አዲስ አበባን ለመያዝ አቆበቁበዋል። ነገር ግን አንድነት የላቸውም፣ ስደታቸውን እንደ ሽሽት የቆጠረባቸውና መልሶ ለመቀበል ቅሬታ የነበረው አርበኛ ቀድሞአቸው አዲስ አበባ መግባቱን ንጉሠ ነገሥቱ አልወደዱትም፣ በዚህ ላይ ደግሞ አርበኛው በከተማው ውስጥ ያሉትን ጣልያኖውያን በቁጭት ይጨርሳቸዋል የሚል ስጋት ተፈጠረ። ከየአለበት ተጠረቃቅሞ በንጉሠ ነገሥቱ ዙሪያ የቆመው ስደተኛ፣ የቢልያን በረሃ አቋርጦ በመኪናና በባቡር ወደ አዲስ አበባ የሚገሰግሰውን የእንግሊዝ ጦር ቀድሞ አዲስ አበባ ለመግባት አቅም አላገኘም። የጠላትን ጦር ጠራርጎ ከሀገር የማስወጣቱ ሥራ ወደ ኋላ ተትቶ፣ በንጉሠ ነገሥቱ የሚመራው ጦር የጠላትን ጦር እየቆራረጠ በመገስገስ ቀድሞ አዲስ አበባ እንዲገቡ፣ በቀና ልቡና ኢትዮጵያን ይረዱ ከነበሩት፣ ከኮሎኔል /ጄነራል/ ዊንጌት በእዛዥ /ደጃዝማች/ ከበደ በኩል በምሥጢር ቀርቦ የነበረው ሃሳብ ተቀባይነት በማጣት፣ ቀርቶአል።[18] በእነዚህ ምክንያቶች አዲስ አበባን የመያዝ ዕድል፣ የኢትዮጵያውያን ሳይሆን ቀረ።

በከተማው ውስጥ ፈንጠዝያ በዛ፣ ጣልያኖችን መፍራት ቀረ። ፈንጠዝያ ይካሄድባቸው ከነበሩ መጠጥ ቤቶች አንዱ መርካቶ ራስ ትያትር አካባቢ የነበረው የወይዘሮ እልፍነሽ ዘውዴ ቤት ነበር። ከዚያ የተሰበሰበውን ሰው ብዛት በማየት ራስ ጌታቸውና አቶ ዓምደ ሚካኤል ደሳለኝ ገቡ። ንግግር ለማድረግ በመሞከራቸው ጠብ ተነሣ። ሁለቱ የጣልያን ባለሥልጣኖች ወጥተው እንደሄዱ ጣልያኖውያን የከተማ ዘበኞች መጡ። ተኩስ ተከፈተ። ሰባት ኢትዮጵያውያን ሞተው ሌሎች አሥራ አምስት ቆሰሉ።[19]

ከመንግሥቱ ቡተሰጠው መመሪያ መሠረት የእንግሊዝ ጦር መጋቢት 28 ቀን 1933 ዓ.ም እሑድ ጥዋት አዲስ አበባን ያዘ። አሁን ዩኒቨርሲቲ ከሆነው ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ቤተ መንግሥት ገብቶ የእንግሊዝን ሰንደቅ ዓላማ ተከለ። የእንግሊዝ ሰንደቅ ዓላማ መተክሉ ደግሞ በሕዝብ ዘንድ ቁጣ አስነሣ። በዚያው ቀን ከቀትር በኋላ በ11 ሰዓት ጀነራል ዊዛራል በታላቁ የአፄ ምኒልክ ጊቢ ተገኝተው የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማም ተከሉ። በአቶ /ብላታ/ ጸዋት እቁበ እግዚእ አስተርጓሚነት ባደረጉት ንግግር "ይህ ቀን አዲስ አበባን ለእናንተ /ለሕዝቡ/ እንደገና መልሼ የያዝኩበት ቀን በመሆኑ የምኮራበት ነው። የያዝኩትም በምንም ዓይነት አዲስ የቅኝ ግዛት ጥርጣሬ በማያስከትል ሁኔታ ነው" በማለት ሕዝቡን አረጋጉ። የንጉሠ ነገሥቱም አዋጅ በዚያው በአደባባዩ ላይ ተነበበ።[20] ነዋሪውም በሰላምና በደስታ ወደየቤቱ ተመለሰ።

የእንግሊዝ ጦር የአዲስ አበባን ከተማ ከንጉሠ ነገሥቱም ከአርበኞችም አስቀድሞ መያዝ፣ ለእንግሊዞች የሚያስገኝላቸው ተደራራቢ ጥቅም ነበረው። አንደኛው ጥቅም በሰሜን አፍሪካ ለሚደረገው ጦርነት ለሚያንቀሳቅሱት ጦር መንገድ መክፈቱና ለማቀነባበር የሚረዳ ምቹ ቦታ መገኘቱ ነው። ሁለተኛው ደግሞ ምንግዜም በእንግሊዞች ዘንድ ዋጋ የሚሰጠውን የክብር አጠባበቁን ጉዳይ በማያጠራጥር ሁኔታ ያስተካከለላቸው። ሦስተኛው ደግሞ ንጉሠ ነገሥቱ ወደ ሥልጣን ሊመለሱ ይችላሉ ለሚለው ጥያቄ ጊዜ ይሰጣል። በጦርነቱ ወቅት እጃቸው የገባውን ነገር ከኢትዮጵያ ለማውጣት ይቻላል። በአዲስ አበባ የነበሩትን ጣልያኖውያንና ሌሎችም የውጭ አገር ሰዎች ሕይወት አዳንን በማለት፣ የዓለም ጉበረተሰብን አመኔታ ለማግኘት ይረዳል። እንደዚሁም ሆነ።

ማጣቀሻ ፅሑፎች

1. ላፒሶ ጌዲሌቦ፣ *የኢትዮጵያ የገባር ሥርዓትና ጅምር ካፒታሊዝም* ገጽ 39።
2. Richard Greenfield, *Ethiopia*, pp.228
3. ጳውሎስ ኞኞ፣ *የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦርነት*, ገጽ 146-147።
4. ከቀኛዝማች ምሥካየ ሥዩም በወቅቱ የተነገረ።
5. ጳውሎስ ኞኞ ።
6. Alberto Sabacchi, *Ethiopia under Mussolini*, pp.183

7. *Ibid.*,pp, 35-48.
8. ገሪማ ታፈረ፣ *ጦንደሬ ቢጋሻው*፣ ገጽ 83-103።
9. ጳውሎስ ኞኞ፣ ገጽ 158-161።
10. Sabacchi, p.189-194.
11. *Ibid.*, pp. 52-53.
12. ከቁስ ኃይለ ሚካኤል የተነገረኝ።
13. የራስ ትያትር መጽሔት፣ 1976 ዓ.ም ፣ገጽ 45።
14. የሮማ ብርሃን መጽሔት፣ የየካቲት 1932 ዓ.ም እትም።
15. Sabacchi, pp.167-174.
16. *Ibid.*, pp. 78-93.
17. ከብፁዕ አቡነ ዮሐንስ በ1958 ዓ.ም የተነገረኝ።
18. ከበደ ተሰማ፣ *የታሪክ ማስታወሻ*፣ ገጽ 373።
19. ከጀነራል መኮንን ደነቀ የተነገረኝ።
20. Greenfield, p.262

ምዕራፍ ሠላሣ ስድስት
የሴቶችና የልጆች ሚና

በኢትዮጵያና ጣልያን ጦርነት፣ የኢትዮጵያ ሴቶችና ልጆች ጥሩ ሚና ተጫውተዋል። የታሪኩን ሂደት ለመገንዘብ በዚህ ምዕራፍ ዋና ዋና ሥራዎችን እጠቅሳለሁ።

ለዘማች ሥንቅ የመሰነቅና ፈትሉ ልብስ የማዘጋጀት ሥራ፣ የሴቶች ሥራ ነበር። በሰሜኑም ሆነ በምሥራቅና በደቡብ የጦር ግንባር ጠላት ሠብሮ እስከገባበት ጊዜ ድረስ ሴቶች የጎሳ ተሳትፎ አላደረጉም፣ ከባሎቻቸው ጋር የዘመቱ እጅግ ጥቂት ነበሩ። ከቤተ መንግሥት ወጎን የዘመቱ ልዕልት ሮማነ ወርቅ ኃይለሥላሴ ብቻ ነበሩ። እቴጌ መነንም እንኪን ቢሆኑ ባላቸውን ጐትተው ወደ ውጭ አገር ከመውሰድ በስተቀር ሌላ ሥራ ለመሥራታቸው ተጨባጭ ማስረጃ የለም። ነገር ግን ጣልያን ድል አድርጐ ኢትዮጵያ ሲገባ ይህ ሥዕል ተሰወጠ። ሴቶች የዜግነት ድርሻቸውን መወጣት ያዙ።

ሴቶች በአርበኝነት ጊዜ ምግብ የማዘጋጀት ኃላፊነት ነበረባቸው። እህል በታጣ ጊዜ ፍራፍሬ በመልቀም፣ ሥራ ሥር በመማስ ምግብ ያዘጋጃሉ። ትንሽ ዕረፍት በተገኘ ጊዜ ጫብሌ ቆፍረው፣ የቀጋ ፍሬ ለቅመው ብርዝ ያዘጋጃሉ።[1] ጠጅ ይጠምቃሉ። እህል ከተገኘም ጠላ ጠምቀው ያቀርባሉ። ቁስለኛውን ሕመምተኛውን ማስታመም የእነሱ ሥራ ነበር። በተለይ የሕፃናትና የሽማግሌዎች ሕይወት በእነሱ እጅ ወደቀ። ይህም እጅግ ከባድ ነበር።

የጠላትን ሁኔታ ለመሰለል፣ ምሥጢራዊ መልእክቶችን ለማስተላለፍ፣ ሴቶች ከወንዶች የተሻለ ችሎታ አሳይተዋል። ለምሣሌ በውስጥ አርበኝነት ረገድ የአዲስ ዓለምዋን ወይዘሮ ሸዋረገድ ገድሌን መጥቀስ ይቻላል። እኚህ ሴት በአዲስ ዓለም አካባቢ ይንቀሳቀስ ለነበረው አርበኛ ምሥጢር ማቀበል ሥራ አድርገው ያዙ። ተከስሰው ከጦር ፍርድ ቤት በቀረቡ ጊዜ፦ "የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ወርዶ የኢጣልያ ባንዲራ ሲሰቀል አልቅሰሻል" ቢባሉ፣ "እምን አልቅሻለሁ" አሉ። በዚህ ብቻ አላበቁም "የእናንተ አገር ሴቶች በሰው አገር ቀንተው የጣታቸውን ቀለበት፣ የአንገታቸውን ሐብል እያወለቁ ኢትዮጵያን ለመውረር ለመጡት ሽፈቶች ሲያበረክቱ፣ እኔ አገሬ በባዕድ ሕዝብ ስትወረር፣ መንግሥት ጠፍቶ የአገሩ ሰንደቅ ዓላማ ወርዶ ሌላ ሲሰቀል...ማልቀስ ይነስብኝ?" የሚል ጥያቄ አቀረቡ። ከተግሣጽ ጋር አሰናበቱአቸው።

በሌላ ጊዜ ደግሞ "ለአርበኞች ስንቅ ታቀብያለሽ፣ ቀይ መስቀልን ትረዳለሽ" ተብለው ተከሰሱ። እሳቸው "ስለነፃነት... ከአገሬ አርበኞች ጐን ተሰልፈ ጠላቴን መውጋት ቀርቶ፣ የረሐብና የጥም መድኃኒት እያዘጋጀሁ መላኩ ቁም ነገር ሆኖ ነው የተጠየቅኩት?" ብለው ጠየቁ። በዚህም አልበቃቸውም። "ይህንን ባላደርግ... እንኪን እነሱ እናንተም ትታዘቡኛላችሁ..." አሉአቸው። ጣልያኑም "እንግዲያ እኛን አትወጂንማ?" ቢላቸው፣ እሳቸው ደግሞ "አዎን አልወዳችሁም። ማነው ጠላቱን የሚወድ?" ብለው አረጋገጡለት። ከትንሽ ቀን እሥራት በስተቀር ምንም አሳገኛቸውም።[2] አርበኞች የአዲስ ዓለምን ምሽግ ደጋግመው ለማጥቃትና ለመጨረሻም ለማስለቀቅ የቻሉት በቆፍጣናይቷ ወይዘሮ ሸዋረገድ ገድሌ ድጋፍ ጭምር ነው።

በሕክምና ሥራም የረዱ ብዙ ናቸው። ሰው በቆሰለ ጊዜ ደሙን አጥበው፣ መግሉን አጥበው፣ የተገኘውን የሀገር ባሕል መድኃኒት አድርገው፣ መግበው፣ ውሃ አጠጥተው ያድናሉ። የሞተባቸውም እንደሆነ ለማያውቁት ሰው ጭምር እርር ብለው አልቅሰው ቀባሪ ለምነው ያስቀብራሉ። በዚህ ያየሁትን ሁሉ ለመዘርዘር ከብዛቱ የተነሣ ይለነኛል።

ሕክምናን በተመለከተ ወይዘሪት /ወይዘሮ/ ስንዱ ገብሩና ወይዘሪት /ወይዘሮ/ ጽጌ መንገሻ ሊጠቀሱ ይገባል። ወይዘሪት ስንዱ ከአዲስ አበባ ከአባታቸው ከስንቲባ ገብሩ ጋር ጐሬ ከተማ ገቡ። ወይዘሪት ጽጌ መንገሻ ደግሞ ከወንድማቸው ከአቶ ይልማ መንገሻ ጋር አምቦ ከተማ፣ ከጥቁር አንበሳ ጦር ጋር ተቀላቀሉ። እነዚህ ሁለት ወጣቶች ጐሬ ከአለው ሀኪም ቤት ያገኙትን ያህል መድኃኒት ወስደው ጦሩ በየሄደበት ቦታ ሁሉ የህክምና አገልግሎት እስከ መጨረሻው፣ ማለትም ጦሩ እጁን እስከሰጠበት ቀን ድረስ በመርዳት አገልግለዋል። ደንበኛውን የቀይ መስቀል መለዮ አድርገው፣ እንደ ወንድ ኮትና ሁሪ ለብሰው፣ ቡሽ ባርኔጣ አድርገው በጦርነት ጊዜ የቆሰለውንና የታመመውን በማከም ታላቅ አስተዋጽኦ አድርገዋል።[3]

በጦር ሜዳም እንደ ወንድ ታጥቀው የተዋጉ ብዙዎች ናቸው። ከቡልጋ ወይዘሮ ልከየሰሽ በያን፣ ከመርሐቤቴ ወይዘሮ አሰለፈች ኩዘረ ሥላሴ፣ በወለጋ በኩል ወደ ሱዳን ከወጣው አርበኛ ወይዘሮ ከበደች ሥዩም እንዲሁም ወይዘሮ ወርቅነሽ ሲሣይ ሊጠቀሱ ይገባል።

ሴቶች በጦር ሜዳ ጀብዱ ለመሥራታቸው ማስረጃ ከአስፈለገ አንዲት ወይዘሮ የፊፀሙትን ማየት ይቻላል። ዊልያም ሚኪን የተባለ ታሪክ ፀሐፊ እንደተረከው የደጃዝማች ሀብተ ሚካኤል ሚስት ዶሎ በተባለው ቦታ የጠላት ጦር መምጣቱን ይረዳሉ። ሰው ተጉድቶ ነበርና

ባልየው ጦርነት ለመግጠም አመነቱ። ሴቲቱ የወንድ ልብስ ለብሰው፣ 150 ወታደሮች ይዘው በበቅሎ ገሥግሠው በጠላት ላይ አደጋ በመጣል ውጊያ ገጠሙ። የጠላት ወታደሮች በብርታት ስለተዋጉ፣ ሴቲቱ የደግንነት ሥራ ሠርተው ከዚያው ከጦር ሜዳው ሞተዋል።[4] ከዚህ በተጨማሪ ሴቶች ጦር ሲመጣ ቁቁ ይላሉ፤ ውጊያ ሲካሄድ እልል እያሉ ያበረታታሉ። እመሰክርብሀለሁ እያሉ በማሳቀቅ ወንዱን ከሸሸት እየተመለሰ ከጦር ሜዳ ገብቶ እንዲዋጋ ያደርጋሉ። ናዳና መርግ እየለቀቁ ጠላትን ያጠቃሉ። የጦር ሠፈር እንዳይደፈር ይጠባበቃሉ።

ምክራቸውም ቀላል አልነበረም። ደጃዝማች አበራ ካሣ ከውርደትና ከሞት የደረሱት የባለቤታቸውን የወይዘሮ ከበደች ሥዩምን ቃል ባለመቀበል ነው። ደጃዝማች ተሾመ ሽንቁጥ በአርበኝነት ጸንተው በመቆየት ሊከበሩ የቻሉት የባለቤታቸውን የወይዘሮ አለለፊች ክብረሥላሴን ምክር በመስማት ነው። የሴቶችን ብርታት ንጉሠ ነገሥቱም መስክረዋል። በትግራይ በተካሄደው ጦርነት አንዲት ሴት ጠላት አስገድዶ ሊያረክሳት ሲሞክር፣ በገዛ ጩቤው ልቡን ብላ ገድላ፣ መሣሪያውን ገፍፋ ከኢትዮጵያ ሠራዊት ጐን መሰለፍዋን ገልጸዋል።[5]

ጠላት የሴቱን ኃይል አልናቀም። በአገዳደል ረገድ በወንድና በሴት መካከል ልዩነት አላሳየም። ሴቶቹን ረሽኖአል። በአሥራትም እንደዚሁ ሴቶች በሀገር ውስጥም፣ በውጭ አገርም ከወንዶች እኩል ታሥረዋል። በጠቅላላው ሲታይ በሴቶች ላይ የደረሰው ግፍ በወንዶች ላይ ከደረሰው የከፋ ነበር። በጦርነቱ የሞቱት እጅግ ብዙ ናቸው። የቆሰሉትም እንደዚሁ። በምርኮ ከጠላት እጅ የወደቁ እንደሆነ የሚደርስባቸው የአካል ጉዳትና የሚሰማቸው የመንፈስ ርክሰት አሰቃቂ ነበር። ክብረ ንጽሕናቸውን ያጡም አሉ። አንዳንድ ሴቶች የወር አበባቸው ይከብድና ይፈጥንባቸዋል፣ ውርጃ ያጋጥማቸዋል። ለመውለድ የታደሉም አሉ። በምርኮም በአሥራትም ጊዜ ከአቅማቸው በላይ የሆነ የጉልበት ሥራ እንዲሠሩ ተገድደዋል። የዕድሜ ልክ ሀመምተኛ የሆኑም ጥቂት አይደሉም።[6]

ልጆች የሠሩትም ቀላል አልነበረም። በተለይ በዕድሜአቸው ከ10 ዓመት በላይ የነበሩት ይላላካሉ፣ የሚችሉትን ያህል መሣሪያ ይሸከማሉ፣ ዕቃ ያጓጉዛሉ። እንጨት ይሠብራሉ፣ ውሃ ይቀዳሉ፣ መኝታ ያዘጋጃሉ፣ ስንቅ ያቀብላሉ። ሴቶች በሌሉ ጊዜ ምግብ ያበስላሉ። ቀን ቀን ቃሬር በመሆን ሠራዊቱ እንዲያርፍ ያደርጋሉ። አንዳንዶችም መሣሪያ ጨብጠው ይዋጋሉ።

በአንዳንዱ ደግሞ የአርበኝነትን ሥራ ካከበዱት ነገሮች አንዱ የጓዝ መብዛት ነው። ሕፃኑ፣ ሴቱ፣ ሽማግሌው፣ አሮጊቱ፣ ቁስለኛው፣

ሕመምተኛው፣ ከተዋጊው ሠራዊት መለየት አይችልም። ከተለየ፣ ከጠላት እጅ ይወድቃል። በጣልያኖች ዘንድ ሕፃን፣ ሴት፣ ሽማግሌ፣ ቄስ፣ መነኩሴ ብሎ ነገር የለም። ነፍስ ያለው ፍጡር ከተያዘ፣ ምርኮኛ ነው። ምርኮኛ በሥርዓት እንዲያዝ በጀኔቫ ውል የተፈረመው ነጭ ነጭን ሲማርክ ብቻ ነው። ነጭ ጥቁርን ሲማርክ አይጸናም። ጥቁር ነጭን መውጋት በነጭ ዘንድ ፈጽሞ የማይታሰብ ጉዳይ ነው። ስለዚህ የተማረከው ሁሉ መገደል አለበት። በዚህ ምክንያት አርበኛው የሚንቀሳቀሰው ከተዋጊው ኃይል ሁለትም ሦስትም አጠፌታ የሚሆን ጓዝ ተሸክሞ ነው። ይህ ሁኔታ ደግሞ የምግብና የልብስ እጥረት ፈጠረ። የሠራዊቱንም የውጊያ ኃይል ቀነሰ።

ማጣቀሻ ፅሑፎች

1. ገራማ ታፈረ፣ *ጉንደሬ በጋሻው*፣ ገጽ 191።
2. ታደሰ ዘወልዴ፣ *ቀሪን ገረመው*፣ ገጽ 503-507።
3. ታደሰ ሜጫ፣ *ጥቁር አንበሳ*፣ ገጽ 102።
4. ጳውሎስ ኞኞ፣ *የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦርነት*፣ ገጽ 129-130።
5. ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፣ *ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ፣ 1ኛ መጽሐፍ*፣ ገጽ 217።
6. ተከለፃዲቅ መኩሪያ፣ *የኢትዮጵያ ታሪክ ከአጼ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ*፣ ገጽ 283።

ምዕራፍ ሠላሳ ስባት
የውስጥ አርበኞች ተጋድሎ

በጦርነት ላይ የመረጃ ሠራተኞች ቁልፈ ሚና ይጫወታሉ። አፄ ምኒልክ ዐድዋ ላይ ያሸነፉት፣[1] ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ማይጨው የተሸነፉት፣[2] በመረጃ ጉዳይ እንደሆነ በታሪክ አንብበናል። አሁን ደግሞ አርበኞች በዚህ ረገድ የነበራቸውን አቅዋም እንመለከታለን።

ጣልያኖች ኢትዮጵያን ሲይዙ ምሥጢር የማግኘት አቅማቸው በሚያስገርም ሁኔታ ተቀነሰ። በጦርነቱ ጊዜ ተበታትኖ የነበረው የሕዝቡ ሥነ ልቡና ተመለሰ። ስለ ሀገር ጉዳይ ማሰብ፣ መቆርቆር ጀመረ። የአርበኝነት እንቅስቃሴን መደገፍ ጀመረ። ጣልያንን ጎትተው ያመጡት እነማን እንደሆኑ አወቀ፤ ምሥጢሩን ከእነሱ ደበቀ። ከነፃነት ታጋዮች ጋር ያለውን ወገናዊነት አጠበቀ።

ይህ ሁኔታ የውስጥ አርበኝነትን ሥራ ፈጠረ። ብዙዎች ሀገራቸውን ኢትዮጵያን በውስጥ አርበኝነት እንዲረዱ አደረጋቸው። እነዚህ ወገኖች ለአርበኝነት ሥራ መቃናት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል። ሥራቸውን የሚያካሂዱት በማኅበርም በቡድንም፣ በተናጠልም በግለሰብም ሆኖ፣ የሚንቀሳቀሱትም ባመቻቸው ጊዜና ቦታ ነበር።

ጣልያን አዲስ አበባ እንደገባ 12 ወጣቶች ተሰብስበው ስለሀገራቸው ምን ማድረግ እንደሚገባቸው ተማከሩ። ጊዜ ካመጣው መንግሥት ጋር መስማማት የሚሻል የመሰለውም ነበር። ነገር ግን ተቀባይነት አላገኘም። የሀገር ፍቅር ያላቸው ወገኖች ተባብረው አንድ የምሥጢር ማኅበር አቋቋሙ።[3] ምንም የንጉሠ ነገሥቱ ፍቅር በልጦባቸው ከእነሱ ጋር በማይስማሙ፣ እንዲሁም ሰዎች ላይ አንዳንድ ከሀገር ፍቅር የራቀ ሥራ ቢሠሩም፣ ጠላትን ድል ለመምታት በተካሄደው ትግል መልካም አስተዋፅኦ አድርገዋል። አባላቱ ተስማምተው መጋቢት 27 ቀን 1930 ዓ.ም አንድ መተዳደሪያ ደንብ አወጡ። ደንቡ 12 አንቀፆች ያሉት ሲሆን፣ ዓላማው አገርህን ውደድ፣ ንጉሥህን አክብር፣ ወገንህን ጠብቅ የሚል ነበር። ማኅበሩ ፕሬዚደንት፣ ፀሐፌ ትዕዛዝ፣ አማካሪዎችና ተመልካቾች እንዲኖሩት ተወሰነ። አባል የሚሆኑ ሰዎች ማኅደራቸው ተመርምሮ ለኢትዮጵያ የመታመን ሥራ የሠሩ፣ ባይሠሩም ያልተቃወሙ ይሁኑ ተባለ (አንቀጽ 3)። ማኅበሩ ለኢትዮጵያ ሕይወታቸውን ላላሰቡ ሰዎች ልጆችና ቤተሰብ እንዲረዳ ተወሰነ (አንቀጽ 5)። የራስን ሀብትና ጥቅም ማደላደል ተከለከለ (አንቀጽ 9)፣ ምሥጢር ያወጣ እንዲጠፋ ተደነገገ (አንቀጽ 11)። ደንቡ እያደር ተሻሽሎ የውስጥ አርበኛው በደፈጣ አደጋ እየጣለ በጠላት ላይ የማይናቅ ጉዳት አደረሰ። የፖስቲካ እሥረኞችን፣ አቅም በፈቀደ ሙጠን ረዳ።

በተናጠል አርበኞችን ከሚረዱ ግለሰቦች ዋነኛዋ ወይዘሮ ሸዋረገድ ገድሉ ነበሩ። ጣልያኖች ሲገቡ ቤታቸውን ለቀይ መስቀል አስረክበው ትግል ጀመሩ። የጠላት ማስፈራራትና እሥራት አልበገራቸውም። አርበኞች የአዲስ ዓለምን ምሽግ ለመሥበር የቻሉት በእሳቸው ምሥጢር ሥራ ነበር።[4]

የውስጥ አርበኞች እርዳታ ያደረጉባቸው መንገዶች ብዙ ነበሩ። ለአርበኞች መድኃኒት በማቀበል፣ የታመሙትን በማስታመም፣ የቆሰሉትን ደብቆ በማሳከም ረድተዋል። ነገር ግን ዋናው ዕርዳታ ይህ አልነበረም። ዋናው እርዳታ የጠላትን ሐሳብና የእንቅስቃሴ ዕቅድ ለአርበኞች አስቀድሞ ማስታወቅ፤ ጠላትን በምክር፣ በማስረጃ አቀራረብ፣ በጥቆማም ማሳሳት ነበር። በዚህ አደራረግ የውስጥ አርበኞች በጠላት ያደረሱት ጉዳት ቀላል አልነበረም። በአንድ ወቅት ጀነራል ናዚ፦ "ወዳጅ መስላችሁ ከምትጉዱን ከእናንተ ይልቅ ጠላቶቻችንን እናመሰግናቸዋለን። ጠላትነታቸውን በግልጽ አስታውቀውናልና" በማለት አስተርጓሚዎቹን እስከ መውቀስ መድረሱ በታሪክ ተመዝግቦአል። ተይዘውና ተከሰው የሚቀርቡ ሰዎችን ወንጀል ማቅለል፣ ማስረጃውን ማጥፋት፣ እሥረኞችን መርዳት፣ ሲቻልም እንዲያመልጡ ማድረግ፣ የሚፈቱበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤ በድብቅ የታሠሩ ሰዎች ያሉበትን ለዘመዶቻቸው ማስታወቅና ዋስ ሆኖ ማስፈታት ዋና ዋናዎቹ ሥልቶች ነበሩ።

ወደ ዝርዝር ጉዳይ ሳንገባ በሸዋ የነበሩ አርበኞች ከአዲስ አበባና ከሌሎችም ከተሞች ትኩስ ወሬ ይደርሳቸው እንደነበረና በዚያም ጥሩ ውጤት እንደተገኘበት እንገነዘባለን።

አርበኞች ንጉሥ አንግሠው በአዲስ ኃይል ሲንቀሳቀሱ፤ የጣልያን የቅኝ ግዛት ሚኒስትር ሲሶና አዲሲቱን የቅኝ ግዛት ኢትዮጵያን በመገንጠት በሀገሪቱ ላይ ሰላም መሰራቱን ለዓለም የሚያስረዳ ጉብኝት እንዲያደርግ መወሰኑ ይታወሳል። የጉብኝቱም ጉዞ በአይሮፕላን ሳይሆን በባቡር እንዲሆን ተደረገ። ጉዞው በሦስት ተከታታይ ባቡሮች ነበር። የመጀመሪያው ባቡር መስከረም 30 ቀን 1930 ዓ.ም �ዱማ ደረሰ። ባቡሩ ከስተማይቱ 4 ኪሎ ሜትር ያህል ወጣ እንዳለ አርበኞች አደጋ ጥለው ብዙ ጣልያን ገደሉ። ሆኖም ሚኒስትሩ ከዚያ ባቡር ውስጥ አለመሆኑ እንደ ታወቀ፤ አቃቂ ከመድረሱ በፊት በሌላኛው ባቡር ላይ አደጋ ጥለው ብዙ ጣልያን ጨረሱ። ሚኒስትሩ ከዚያም ውስጥ አልነበረም።[5] ምናልባት በድሬዳዋና በናዝሬት መካከል ባቡር ሳይለውጥ አልቀረም። ምክንያቱም በወቅቱ የመጀመሪያውን አደጋ የጣሉት፤ አርበኞች በመጀመሪያው ውስጥ ስለመሆኑ ትክክለኛ ማስረጃ ደርሶአቸው ነበር።

እራሳቸው ከስተማ እየገቡ ምሥጢር የመሰብሰብ ሥራ ያካሄዱ ብዙ አርበኞች ነበሩ። በዚህ ዘዴ ሥሱጥ የነበሩት ዲማ ሰንበቴ ነበሩ። የእንቁላልና የዶሮ ነጋዴ እየመሰሉ እንደ ሸኖና ሰንዳፋ፤ አንዳንድ ጊዜም አዲስ አበባ

እየገቡ ምሥጢር በማግኘት አርበኞችን እያስተባበሩ በጠላት ላይ ብዙ ጉዳት አድርሰዋል።

ከጣልያኖች ከራሳቸው ጋር ግንኙነት መሥርተው መረጃ ማግኘት የቻሉ አርበኞችም ነበሩ። ለማስረጃም ያህል ቱኒቲ ኮሪያ የተባለ በጊና አገር ምሽግ የፖለቲካ ሹም የነበረ ጣልያናዊ እንዴት እንደተጠቀሙበት እጠቅሳለሁ። ይህ ሰው ዕርቅን ምክንያት በማድረግ በሙገሬ ዛላ አካባቢ ሲዘዋወር፣ ከጦር አዛዡና ከሠራዊቱ ጋር በፊታውራሪ ወልደሚካኤል ዘውዴ ተማረከ። ሳይገድሉትና ሳያጉላሉት በሰላም፣ ከነመሣሪያውና ከነሠራዊቱ ስለለቀቁት፣ ባለውለታ ሆኖ ምሥጢርም፣ መድኃኒትም ይልክላቸው ነበር። ዕርቅ በፈረሰ ጊዜ «ወልደሚካኤል ቪያ» በሚል አነጋገር፣ ያለአስተርጓሚ መልእክት በዘበኛው በኩል ስለላክባቸው፣ ምሥጢሩን በቅድሚያ አውቀው ተገቢውን ጥንቃቄ በማድረጋቸው ዕርቅ እንደፈረሰ ከደረሰው አደጋ ዳኑ።

ሙሴ ቀስተኛ አስታራቂ መስሎ ወደ ኦርሞ አርበኞች ዘንድ በቀረበ ጊዜ፣ ስለአርበኞቹ ልዩ ጥናት አካሄዶ ነበር። የሚደልልበትንም ዘዴ አዘጋጅቶ ነበር። ነገር ግን አርበኞቹ ስለእሱ ማንነትና ምንነት፣ ስለዓላማውና ስለአስተሳሰቡ ጭምር ያውቁ ነበር። እሱ ስዊስ ነኝ ቢልም፣ በእድዋ ጦርነት ተማርኮ አዲስ አበባ የኖረ ኢጣልያዊ መሆኑን፤ እነ ራስ ደስታ የነበሩበትን አካባቢና ሁኔታ በአስታራቂነት ቀርቦ ማስፈጀቱን፣ ባለምባራስ አበበ የራስነት ማዕረግ በተሾሙ በአንድ ሣምንት ውስጥ ከምንጃር እስከ ጌልጌላ ሄዶ በማነጋገር ሁኔታቸውን ሰልሎ ለጣልያኖች መረጃና ምክር በመስጠት እንዳስደበደባቸው፣ የኦሮሞው አርበኛ ያውቅ ነበር።[6] በመሆኑም አርበኛው ቆራጥ እርምጃ በመውሰድ፣ እሱ ከተሰለፈበት ሜራና ከሚያስከትልባቸው ጉዳት ራሱን አዳነ።

በጉንደር በክል የነበረው የውስጥ አርበኝነት ሥራ ዩተጠናከረና የውጭ አገር ሰውንም ያካተተ ነበር። ኳኃ ኃይሉ የተባሉ በሱዳን ሀገር፣ ዱካ በተባለው ቦታ የሚኖሩ የወላይታ ባላባትና ባለቤታቸው ወይዘሮ ደስታ አበባየሁ ያደረጉት ዕርዳታ ከሁሉም የላቀ ነበር። ጦርነት ሰልችቶት ከኢትዮጵያ ወደ ሱዳን የሚሰደደውን፣ ሱዳን በመግባት አገሣም ትግሉን ለመቀጠል ወደ ኢትዮጵያ የሚመለሰውን ሁሉ ረድተዋል። ለደካሙ ማረፊያ፣ ለረሐቡ ምግብ፣ ለጥሙ መጠጥ፣ ለእርቃነ ሥጋው ልብስ ሆነውታል። መንገድ መሪ፣ ሽኚ እየሰጡ አስተባልፈውታል። ለዚህ ሥራ ያዋሉት ገንዘብ ከ44 ሺህ ብር በላይ ተገምቶአል። ራሳቸው ከመርዳታቸውም በላይ የሱዳን ተወላጅ የሆኑ ወዳጆቻቸውን በማነቡራዊ ኑሮና በፍቅር እየጐተቱ፣ የኢትዮጵያን ጥቃትና የኢትዮጵያውንን ተጋድሎ እያስረዱ፣ አርበኞችን እንዲረዱ አድርገዋል።

ከዚህም በስተቀር በጋላባት፤ በገዳሪፍ፤ በክሰላና በካርቱም የነበሩ ኢትዮጵያውን በውስጥ አርበኝነት ሠርተዋል። ሥራቸው በጣልያኖች ዘንድ

እየታወቀ በብዙዎቹ ላይ ተደጋጋሚ ክስ ቀርቦባቸዋል፣ ወቀሳም፣ ቅጣትም ደርሶባቸዋል። ነገር ግን የተሠነዘረባቸውን ጥቃት እርስ በርስ በመረዳዳት ተወጥተውታል። ግዛው ውቤ የተባለ ሰው ስድስት አልቤን ጠመንጃ ከጠላት ወስዶ ቤቱ ሲፈተሽ ሳይገኝበት ቀርቶአል። ሳይገኝበት የቀረውም አንዱ ሀገር ወዳድ ጊዜ የለኝም በማለት ፍተሻውን ለማግስቱ በማሳደሩ ነው፤ ሌላው ደግሞ ምሥጢሩን በመንገሩና በአካባቢው የሚኖሩ ሴቶች ጠመንጃዎቹን ተከፋፍለው በመደበቃቸው ነበር።

በውስጥ አርበኝነት ከረዱ ቡድኖች ጠንካራው የኤርትራ ልጆች ነበሩ። እንደዛ ሊሆን የቻለበት ምክንያት፣ በአስተርጓሚነትና በልዩ ልዩ የጽሕፈት ቤት ሥራ በመመደባቸው ምሥጢር ለማግኘት መቻላቸው እና በኢጣልያኖች ዘንድ የመደመጥ ዕድል ስለነበራቸው ነው። ስለዚህ ብዙ ሥራ ሰመሥራት ችለዋል። ከጠላት ጉን የተሠለፉትን ወገኖቻቸውን በምሥጢር እየተጻጻፉ ወደ ኢትዮጵያ እንዲዞሩ አድርገዋል። ምሥጢር ወደ ውጭ አገር በማስተላለፍና ከውጭ አገር የሚያገኙትን ወሬ ወደ አርበኞች እንዲደርስ በማድረግ ረድተዋል። በአስተርጓሚነት የሚሠሩ ደግሞ በዘዴ በመሥራት ብዙ ሰው ከሞት አድነዋል። ለማስረጃም ያህል ፊታውራሪ ብጡል ሊሰቀሉ በቀረቡ ጊዜ፣ የቀበሩት መሣሪያ ሲኖር ስለሚችል መሰቀላቸው ቢቆይ ይሻላል ብለው ለጣልያናዊው መኰንን በማማከር አድነዋቸዋል። አቶ አስናቀ ፈለቀ የወሬ መቀበያና ማስተላለፊያ መሣሪያ ቀብረዋል ተብሎ በቀረበባቸው ክስ ሊገደሉ ሲፈሰጉ፤ ምሥጢሩ ስለተነገራቸው ሸሽተው ለማምለጥ ችለዋል። አቶ ተገኘ ዮሴፍ እንግሊዝኛ በማወቃቸው ሊገደሉ ታስቦ ዝግጅት እየተደረገ ሳለ ምክር ተለጥቶአቸው በመሸሽ ነፍሳቸውን ድነዋል። በዚህ ዓይነቱ ሥራ የእነ ቀኛዝማች ኪዳኔ መሰለ፣ ስብሐት አጽብሃ፣ ምህረተ አብቀልቲ፣ ደጃዝማች ሮዛሪዮ፣ ቢትወደድ አስፍሐ ወልደሚካኤል፣ ብላቴን ጌታ ሎሬንዞ ታዕዛዝ ስም በክብር ይጠቀሳል።[7]

የጉጃም አርበኞችም እንዲሁ የውስጥ አርበኝነት ሥራ አልተለያቸውም። በተለይም ደጃዝማች በላይ ዘለቀ። እሳቸውም በሚያገኙት ምሥጢር የመጠቀም ችሎታ ነበራቸው። ታህሣሥ 4 ቀን 1930 ዓ.ም አርበኞችን ለማፈን ጠላት ወደ በከና የሚንቀሳቀስበትን ሁኔታ ሰላዮቻቸው ስለነገሩአቸው፣ ዝግሰው ከሌሊቱ 10 ሰዓት ላይ ባሳሰበው ቦታ አደጋ ጥሰው ሊያጠፉት ችለዋል። እንደዚሁም ጠላት ታህሣሥ 9 ቀን አደጋ ሊጥልባቸው በመዘጋጀት ላይ መሆኑን ስለሰሙ፣ አስቀድመው ታህሣሥ 7 ቀን 1930 ዓ.ም ሙጋ በተባለው ምሽግ ላይ አደጋ ጥሰው ምሽጉን አቃጥለዋል። ግንቦት 2 ቀን 1930 ዓ.ም ወደ ወሎ ተሻግረው አንድ ቀንደኛ ባንዳ ቤት ተሰብስቦ ይዶልት የነበረውን የጠላት ጦር አውደመውታል። ለመታረቂያ ይዞአት የነበረችውን የሻሸወርቅ የተባለች ልጃቸውንም ከደብረ ማርቆስ ወህኒ አስርቀው ለመውሰድ ችለዋል።[8]

ብዙ ጀግኖች ከውስጥ አርበኞች ተመሣሣይ ደጋፍ ያገኙ እንጂ፣ ሂደቱ ሌላም መጥፎ ገጽታ ነበረው። ምክንያቱም በአርበኞች ውስጥ ተሰግስገው ጉጂ ሥራ የሚያካሂዱ አልታጡም። በዚህ ረገድ በጉራጌ አገር መንገድ እንመራለን ብለው፣ ገንዘብ ተቀብለው ራስ ደስታንና ሠራዊታቸውን ያስፈጁት፣ በቡልጋ ፊታውራሪ ኃይለ ሥላሴና ባልደረቦቻቸውን አስይዘው ያስጨረሱት፣ ተመሳጥረው ንጉሠ ነገሥት መልአከ ፀሐይን በመርዝ የገደሉት፣ ጀነራል ናዚን ጠልፎ በማገቻነት በመያዝ፣ ለአርቀ ድርድር መነጋገሪያ ለማድረግ የታሰበውን ዓላማ አስቀድመው ምሥጢሩን በመንገር ያከሸፉት፣ መንገድ እንመራለን በማለት ከተቃጠለ ግንብ ውስጥ አስገብተው ለጣልያን ባለሥልጣኖች ምሥጢሩን በመንገር ደጃዝማች ኃይሉ ወልደመድህንን ከነሰዎቻቸው ያስፈጁ ከሀድያን ይጠቀሳሉ።[9]

ማጣቀሻ ፅሑፎች

1. ጆርጅ አፍ ኤች በርክሌይ፣ *የዐድዋ ዘመቻና የአፄ ምኒልክ አነሣሥ*፣ ትርጉም ዳኘው ወልደሥላሴ፣ ገጽ 93።
2. ጳውሎስ ኞኞ፣ *የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦርነት*፣ ገጽ 116።
3. ታደሰ ዘወልዴ፣ *የአባሳሸኘ ዘመን*፣ ገጽ 60-79።
4. ታደሰ ዘወልዴ፣ *ቀሪን ገረመው*፣ ገጽ 503-515።
5. ጳውሎስ ኞኞ፣ ገጽ 176።
6. ታቦር ዋሚ፣ *አባ ቦራ፣ የደጃዝማች ገረሱ ዱኪና የሌሎች አርበኞች ታሪክ*፣ ገጽ 58-61።
7. ገሪማ ታፈረ፣ *ጉንደሬ ቢጋሻው*፣ ገጽ 154-156፣ 58-61፣ 173-174 እና 212-213።
8. ዘውገ ዘገየ፣ *አባ ሰስትር፣ የደጃዝማች በላይ ዘለቀ ታሪክ*፣ ገጽ 13-15 እና 22።
9. ድርጊቶቹን ከታሪካቸው ይመልከቱአል።

ምዕራፍ ሰላሳ ስምንት
የስደተኛው ትግል

ትክክለኛ ኢትዮጵያዊ ሽሽትን ከውርደት፣ ውርደትን ደግሞ ከሞት በላይ አድርጐ ይመለከታል። በአሰበት ቆሞ የመጣበትን መቀበልን ይመርጣል። አገሩን ለቅቆ የመሰደድ ልማድ ግን ፈጽሞ አልነበረበትም። አሁን ግን የተለመደ ሆኖአል።

ሚያዝያ 24 ቀን 1928 ዓ.ም የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ወደ አውሮፓ ሄዱ። ዝርዝሩ በሌላ ምዕራፍ ስለተገለፀ አልመለስበትም። ይህ ምዕራፍ የሚገልፀው የሠራዊቱን የስደት እንቅስቃሴ ነው።

ንጉሠ ነገሥቱ ሀገር ለቅቀው መሄዳቸው በመሣፍንቱና በመኳንንቱ ዘንድ ወዲያው ታወቀ። እንዲያውም አብዛኛው አስቀድሞ አውቆ እና አቅበቅቦ ይጠባበቅ ስለነበር፣ አዲስ ነገር አልሆነበትም። የተወሰኑት ንጉሠ ነገሥቱን ተከትለው ጥዋት በባቡር ወደ ጅቡቲ ወጣ። የኦጋዴን ጦር አዛዦች፣ በጅጅጋ አድርገው በሚቀጥሉት ጥቂት ቀናት ወደ በርበራ ሄዱ። በሐረርጌ፣ በአርሲ፣ በባሌና በሲዳሞ የነበሩት ደግሞ የሞተው ሞቶ የቀረው በወላይታ፣ በባኮጋዘር አድርገው ወደ ኬንያ ገቡ። በከፋና በጋሞ ጎፋ የነበረውም እንደዚሁ ሽሽቱን ቀጠለ። ከአዲስ አበባ በመርሐ ቤቴና በግንደ በረት ወደ ጉጂም የተሻገረው ደግሞ፣ በወንበራ በኩል አድርጐ ቡራ ሳይገባ ሱዳን ጠረፍ ደረሰ። ሌላ አንድ ቡድን በራስ እምሩ ታዝዞ ልብስና መድኃኒት ገዝቶ ሊያመጣ ከደባርቅ በመተማ በኩል ሱዳን ገብቷል።

የኢትዮጵያ ሠራዊት ባልለመደው ዓይነት ተበታትኖ ወደ ውጪ አገር በስደት መሄዱ አሳዛኝ ነበር። ጉዞው አድካሚ ከመሆኑ ጋር ብዙ ሰው በመንገድ ላይ አለቀ። ያጋጠመው ሌላው ችግር፣ አብዛኛው ወደ ተሰደደበት አገር ከገባ በኋላ፣ ሀገሩንና ምግቡን ባለመልመድ በልዩ ልዩ በሽታ ሞተ።

ስደት በዚያን ጊዜ ለኢትዮጵያ ሰው እንግዳ ነገር ነበር። ለተሰደደ ሰው መራብ፣ መጠማት፣ መታረዝ፣ መጠለያ ማጣት ያለ ነገር ነው። መታመምና መሞትም አለ። ሥራ አይገኝም፤ ቢገኝም አሠራሩ አይታወቅም። የሚገኘው ደግሞ እንደ ጽዳት፣ ዘበኝነት ያለ ነው። እሱም በፈረንጅ ፈቃደኝነት እና በእሱ ቁጥጥር ስለሆነ፣ ይከብዳል። ይሁን እንጂ ኢትዮጵያውያን ሀገራቸውን አልረሱም፤ ለሀገራቸው ያላቸው ፍቅር ጠነከረ እንጂ፣ አልተቀነሰም። ሁሉም በየአለበት ሀገሩን ለመደገፍና ወገኑን ለመርዳት፣ ጣልያንን ለማዋረድና ለመጉዳት የሚቻለውን አደረጉ።

ዋናው የስደተኛ ቡድን እንግሊዝ አገር የገባው ነበር። ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር ስለነበር፣ ቁጥሩም አነስተኛ ቢሆን ብርታት አገኘ። የኢትዮጵያን አቤቱታ ለዓለም ማኅበር ለማቅረብና ድምፅዋን ለዓለም ኅብረተሰብ ለማሰማት ጥረት አደረገ። አንዳንድ እንግሊዞችም ደገፉት። ከዚህ ላይ ስማቸው መጠቀስ ያለበት

ሚስስ ሲልቪያ ፓንክረስት ናቸው። እኚህ ወይዘሮ አትማቸውን አጠንክረው ለኢትዮጵያ ጉዳይ አዋሉ።



ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በስደት ሳሉ።

እየሩሳሌም የገባው ሰው ብዙ አልነበረም። ሦስት መቶ ቢሆን ነው። የሀገሩ ፍቅር እንዲሁም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ተመስጦም ነበረው። በገዳሙ ከነበሩት መነኮሳት አብዛኞቹ ተባበሩ። ገዳሙን ለመያዝ ጣልያኖች ያደረጉትን መከራ አከሸፈ። በገዳሙ ተሰቅሎ ይውለበለብ የነበረውን የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ለማስወረድ ያደረጉትን ጥረት ተናንቆ አሸነፈ። በገዳሙ ውስጥ የነበሩትን መዛግብት ለመውሰድ ያደረጉትን መከራ አከሸፈ። በወቅቱ በዛ ባለሥልጣን የነበረው የእንግሊዙ አገረ ገዥ፣ በገዳሙ ውስጥ እጁን ለማስገባትና እሱ የወደደውን ለማድረግ ያደረገውን መከራ አስቀረ። እየተከራዩ፣ ለኢትዮጵያ ስደተኞች የሚረዱባቸው ቤቶች ወደ ጣልያን እንዲዛወሩ እንግሊዝና ጣልያን የሠሩትን ሤራ በፍርድ ቤት ተከራክሮ አፈረሰ። ተስፋ የተባለውን ማኅበር አቋቁሞ የኢትዮጵያን ስደተኛ ወጣቶች ረዳ። ክአርብኞች ወደ አውሮፓ፣ ከአውሮፓ ወደ አርበኞች መልእክት በማስተላለፍ፣ ተጋድሎውን አጠናከረ።[1]

ሽሽቶ ከሄደው፣ በርከት ያለው ስደተኛ የገባው ወደ ሱዳን ነው። ምናልባት አሥራ አምስት ሺህ ሳይሆን አልቀረም። ቀደም ብለው በዚያ የነበሩ ጥቂት ኢትዮጵያውያንም ብዙ አስተዋጽኦ አደረጉ። በጋምቤላና በመተማ በኩል መልእክትም፣ ዕርዳታም አስገቡ። አንድ ቡድን ክካርቱም ልብስና መድኃኒት ገዝቶ በጋምቤላ በኩል እስከ ጉጂ አምጥቶ በራስ እምሩ



ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በስደት ሳሉ::

ለሚመራው አርበኛ አስረክበአል።[2] የኢትዮጵያን አርበኞች እንቅስቃሴ ወደ አውሮፓ በማሰማት እና ከአውሮፓ የሚገኘውን ወሬ ለአርበኞች በማድረስ ለጦርነቱ እገዛ አድርጓል። በሱዳን የነበሩ ስደተኞች በፈቃዳቸው ወደ ኢትዮጵያ እየገቡ የተዋጉበትም ጊዜ ነበር። ንጉሠ ነገሥቱም በዚያ በኩል ለመምጣትና ወደ ሀገራቸው ለመግባት ያገዛቸው፣ በሱዳን በርካታ የኢትዮጵያ ስደተኞች መኖራቸው ነው። ንጉሠ ነገሥቱ ካርቱም ገብተው አዲስ ጦር ለማዘጋጀት በጀመሩ ጊዜም ስደተኛው እገሏል።[3] ስደተኛው ወደ ሀገሩ ተመልሶ ከገባ በኋላ፣ ምድር ሰቅሰቆ ተዋጋ።

ሌላው ቡድን ወደ ኬንያ የተሰደደው ነው። ብዛቱ እስከ አሥር ሺህ ይገመታል። በኬንያ የእንግሊዝ ባለሥልጣኖች ኢትዮጵያውያንን እና ኤርትራውያንን ለያዩአቸው። ኢትዮጵያውያኑን ከሀሮ ወደ አሊሉሉ፣ ከዚያም ወደ ታቤታ አዛወሩአቸው። ታቤታ የተባለችው መንደር በኬንያና በታንዛንያ ድንበር ላይ የምትገኝ መንደር ናት። በዚች መንደር የአይጥ መንጋ ጉበቶ ችግር ፈጥሮ እንደነበረ ብዙዎች ያስታውሳሉ። ንጉሠ ነገሥቱ ካርቱም እንደገቡ በኬንያ ካለው የኢትዮጵያ ስደተኛ፣ ለጦር የሚያገለግለው ወደ ሱዳን መጣ።[4]

ሌላው ስደተኛ ቡድን ከአጋዴን የጦር ግንባር፣ ከጣልያን ጥቃት አምልጦ በጅጅጋ በኩል በርበራ የገባው ነበር። ይህ ቡድን በቁጥር አነስተኛ ነው፤ የቡድኑ ዋና ዋና ሹማምንቶች ወደ ኢየሩሳሌም ሲሄዱ፣ አብዛኛው ከዚያው ቀይቶ ነበር። አንዳንዱም ወደ የመን ተሻግሮ ከቆየ በኋላ፣ የነፃነት ጦርነት ሲጀመር ከእንግሊዝ ጦር ጋር ተቀላቅሎ እየተዋጋ ሐረር ገባ።[5]

የኢትዮጵያ ስደተኛ በየትኛውም በር ቢወጣ፣ የገባው ከእንግሊዞች እጅ ነበር። በዚያን ዘመን በኢትዮጵያ ዙሪያ ያሉትን የሱዳንን፣ የኬንያን፣ የሰሜን ሱማልያን፣ የፍልስጤምና የየመንን አገር በቅኝ ገዥነት የያዙ እነሱ ነበሩ። እንግሊዞች የጊዜው ሁኔታ በሚፈቅድላቸው መጠን የኢትዮጵያን ስደተኛ ረድተዋል። አንቀበልም ወይም አናስገባም አላሉትም፤ እየመለሱ ሰጣልያን አልሰጡትም። ሞሶሎኒ ያካሂድባቸው ከነበረው ተፅዕኖ አንፃር ሲታይ፣ የሚያስመሰግናቸው ነው። የየሀገሩም ተወላጆች ስደተኛውን አቅማቸው በፈቀደላቸው መጠን ደግፈውታል። ለታሪክ ጭምር፣ ይህንን መመስከር ይገባል።

ቀደም ብለው አሜሪካ ሄደው የነበሩ ኢትዮጵያውያን እንዲሁ የተቻላቸውን ያህል ተፍጨርጭረዋል። ለምሳሌ ወላጆቻቸው ሄደው ከዚያ የተወለዱ ክልሶች፣ እነ ሻለቃ ካሣ ሊጠቀሱ ይገባቸዋል። ዶክተር መልአኩ በያን ታላቅ ሥራ ሠርተዋል። በዚያ የነበረው ቡድን መስከረም 2 ቀን 1929 ዓ.ም "...ሀገራችንን የምንለቅ ሰዎች አይደለንም። ጠላቶቻችን የያዙብንን መሬት ለቅቀው እስኪወጡ ድረስ ተኩስ አይቆምም..." በማለት በይፋ አስታወቀ። "ምኒልክ" የተባለ ክበብ ተቋቋመ። ክበቡ ሃያ ሁለት ቅርንጫፎች

ነበሩት። የኢትዮጵያ ድምፅ የተሰኘ ጋዜጣም ተቋቋመ። በዚህ ጋዜጣ አማካይነት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚካሄደውን የአርበኝነት ሥራ ለአሜሪካን ሕዝብ ለማስታወቅ ተቻለ።[6] ይኽ በመሳካቱ ደግሞ፣ አሜሪካ ለጣልያን የምትሰጠውን ድጋፍ ቀነሰ።

በፈረንሣይ አገርም ጥቂት የኢትዮጵያ ተማሪዎች ነበሩ። የኢትዮጵያ አምባሳደር የጣልያንን ጥሪ ተቀብለው ወደ አዲስ አበባ ሲመጡ፣ ወጣት አክሊሉ ሀብተወልድ ግን በዛ የጉዳይ ፈፃሚነቱን ሥራ ቀጠሉ። ከባድ የፖለቲካ ተፅዕኖና ብዙ የገንዘብ ችግር ቢደርስባቸውም፣ ፈረንሣይ ራስዋ በጀርመን እስክ ተወረረችበት ጊዜ ድረስ፣ ኤምባሲው ሳይዘጋና ኢትዮጵያ በፈረንሣይ መንግሥት ዘንድ የነበራት ዕውቅና ሳይሠረዝ እንዲቀጥል አደረጉ። ኤምባሲውም፣ በዓለም መንግሥታት ማኅበርና ለንደን በነበሩት በንጉሠ ነገሥቱ መካከል እንደ ድልድይ ሆኖ አገለገለ።[7]

በሌሎች አገሮች የነበሩ ኢትዮጵያውያንም የየአቅማቸውን ያህል ተፍጨርጭረዋል። በጂቡቲ በኩል የነበሩት መልእክት በማስተላለፍ ረድተዋል። ግብጾች ከኢትዮጵያ ይልቅ ወደ ጣልያን ስለአደሉ፣ በዚያ የነበሩ ኢትዮጵያውያን ስደተኞች አስተዋጽኦ የማድረግ አቅማቸው ውስን ነበር።

በውጭ አገር በተካሄዱት ትግሎች አስገራሚው በጣልያን፣ በራስዋ አገር ውስጥ የተካሄደው ነበር። በዛ የማበሳጨቱም ሥራ አንዱ የትግል መሥመር ነበር። በእሱ ደግሞ እሥረኞችም እንኳን አልተመለሱም። ለምሣሌ ራስ እምሩ በፖይዛ ደሴትብቁም እሥር ላይ በነበሩበት ጊዜ፣ ከሞሶሎኒ ተልከው ሐመጡ ሁለት የኢጣልያ ከፍተኛ ሹማምንት ወንበር እንዳይቀርብላቸው በማገድ፣ እሳቸው ተቀምጠው እነሱ ቆመው እንዲያነጋግሩአቸው አስገድደዋቸዋል። አዲስ አበባ የሚገኘው ቤት ንብረታቸው እንዲመለስላቸው ሞሶሊኒ መወሰኑን ሹማምንቱ እንደ ቆመ ቢነግሩአቸው "...የእኔ የነበረው ሁሉ የኢትዮጵያ ነፃነት ሲጠፋ አብሮ ጠፍቶአል። የጣልያን መንግሥት ለወደደው ይስጠው" በማለት አናደዱአቸው። ሌፖሪ ወደምትባል የእሥራታቸው ደሴት ሲጓዙ ደግሞ፣ ሻንጣቸውን ላለማስፈተሽ ቁልፉን አልሰጥም አሉ። በልመና ሲሰጡ ከሻንጣቸው ውስጥ ቀድሞ የተሸሰሙት ከፍተኛ የጣልያን ኒሻን አላግባብ ተጥሎ ተገኘ። በሥርዓት እንዲያስቀምጡ ቢጠየቁ ለእሳቸው ኒሻኑ ከአፈር አንድ እንደሆነ ገልጸው፣ ቢፈልጉ እንዲወስዱት ለፈታሾቹ ፈቀዱላቸው። ፈታሾቹ ተናድደው መፈተሻቸውን ተዉ።[8]

ጣልያኖችን ከማበሳጨት፣ ራስ ኃይሉም እንኳ አልቦዘኑም። ሮም ከተማ በቆዩበት ጊዜ ማንኛቸው ሽንታቸውን እንደሚችሉ ለማየት ከራስ ሥዩም ጋር ተወራርደው፣ አንድ እሁድ ከጥዋት ጀምረው ከተማዋን ሲዞሩ ከዋሉ በኋላ፣ ውሃ ከሚንፎለፎልበት ፒያሣ ቬኔሲያ ከሚባለው አደባባይ ከቀትር በኋላ በአሥር ሰዓት ደረሱ። ከአደባባዩ ሳይ ሽንታቸውን ሸኑ። በዚህ

ምክንያት ተይዘው ሃያ ሁለት ሊሬ ተቀጡ። ሆኖም ያላቸው ገንዘብ ባለ አንዳንድ ሺህ ሊሬ ብቻ ስለሆነና ፖሊሱም መመንዘር ስላልተቻለው፣ ራስ ሥዩም አንዱን ሺህ ሊሬ ከፍለው፣ ሽንተው ሄዱ ይባላል። ራስ ኃይሉ አዲስ አበባ በነበሩት ጊዜ የጣልያኖች አያያዝ እያስቀየማቸው ሲሄድ ፊታቸው ሲያኮሳትሩ፣ አለቅዬው «ፊትህ የዝንጀሮ ይመስላል።» ቢላቸው «የአንተ ደግሞ ቂጥዋን ይመስላል።» ብለውት እንደነበር ጠቅሻለሁ።

በግዞት ላይ የነበሩ ሌሎች እሥረኞችም ጣልያኖችን በነገር ለመጐንተል ቸል አላሉም። እነዚህ ፈሊጠች ግን ኢትዮጵያውያን በጣልያናውያን ያላቸውን ጥላቻና ንቀት ከመግለጽ በስተቀር ሌላ ፋይዳ አልነበራቸውም። ቢሆንም በታሪክ መጠቀስ ስለሚገባቸው፣ እጠቅሳለሁ።

ከእነኚ፣ ኢትዮጵያውያን በጣልያኖችና በኢጣልያ በራስዋ ላይ ከፈፀሙት ሁሉ ግን የበቁ ሥራዎች አሉ። እነሱም፡- ዘርዓይ ደረስና ሻምበል አብዲሣ አጋ የፈፀሙትን የሚያህል እና የሚመስል፣ እንዲሁም የሚስተካክል የለም። ዝርዝሩን መመርመር ይገባል።

ዘርዓይ ደረስ ሰኔ 7 ቀን 1930 ዓ.ም /ጁን 14 ቀን 1938 እ.ኤ.አ/ በሮም ከተማ፣ በአንድ የመንግሥት አደባባይ ላይ በጉራዴ ብዙ ጣልያኖች ጨፈጨፈ። የመንግሥቱ ባለሥልጣኖች ነገሩ ውርደት ስለሆነባቸውና በምሥጢር ስለያዙት ስንት ሰው እንደሞተ በውል አልታወቀም። እጅግ ቢያንስ አምስት ሬሣ ከአደባባዩ መለቀሙ እርግጥ ነው።[9] ቁጥሩን እስከ አሥራ ስምንት የሚያደርሱም አሉ። በትርምሱ ጭምር ብዙዎች መቁሰላቸው እውነት ነው።

ዘርዓይ ደረስ የኤርትራ ተወላጅ የሆነ፣ በወቅቱ የ24 ዓመት ወጣት ነበር። በዚህ ከላይ በተጠቀሰው ታሪካዊ ቀን በመንግሥት አደባባይ ህዝብ የተጠራው በዶጋሊ ያሰቁትን አምስት መቶ ጣልያናውያን ለማሰብ ነበር። በስብሰባው ላይ ሣልሣዊ ኢማኑኤልና ሙሶሊኒም ይገኙ ነበር።

ዘርዓይ ደረስ ከአደባባዩ እንዲገኝ የተደረገው የኢትዮጵያን ልዩ ልዩ የወግ ዕቃዎች ይዞ ፒያሣ ዲ ፒያሞንቲ በተባለው አደባባይ ለማላገጫነት እንዲቆም ነበር። ከያዛቸው ዕቃዎች አንዱ በዶጋሊ ጦርነት በጥር ወር 1871 ዓ.ም /1879 እ.ኤ.አ / ራስ አሉላ አባ ነጋ ጀብዱ የሠሩበት ጉራዴ ነበር። ዕቃዎቹን ይዞ እንዲሄድ ከመታዘዙ በስተቀር፣ ለመሳለቂያነት መቆም እንደ አለበት ለዘርዓይ ደረስ አልተገለጸለትም ነበር።

ዘርዓይ ከአደባባዩ ሲደርስ እንግዳ ነገር አጋጠመው። ቀድሞ አዲስ አበባ ባቡር ጣቢያ መግቢያ አደባባይ ተተክሎ የነበረውና፣ አሁን ተመልሶ በቀድሞ ቦታው (በለገሃር) የሚገኘው የይሁዳ አንበሳ ሀውልት፣ የሮም ከተማ ሕዝብ በዓል ሊያከብር በተሰበሰበበት አደባባይ ላይ ቆሞ አየው። በዛ ግን ከሃውልቱ ላይ ሁለት ግልገሎች የምታጠባ ተኩላ ተቀምጣበታለች፣ በአንበሳው መስቀል ላይ ደግሞ የጣልያን ባንዲራ ተሰቅሎአል። የኢትዮጵያ

ሰንደቅ ዓላማ ከመሬት ላይ ተጥሎአል። በዙሪያው ከተጻፉ መፈክሮች መካከል "...የይሁዳ አንበሳን ልጆችሽ.. እንደ ፍየል ጭራውን ጠምዝዘው አምጥተው ከአግርሽ ሥር ያሰግዱታል" የሚል ጥቅስ ከብዙ ነውረኛ መፈክሮች መካከል ይታያል። ሕዝቡ እያስካካ ምራቁን በአንበሳው ላይ በመትፋት ያፈዛል።

ዘርዓይ ደረስ ሁኔታውን በመገረም ሲመለከት ማርሻል ግሪዮ ኢሶን የተባለ የዘበኞች አለቃ ወደ እሱ ቀርቦ መመልከት እንደማይችል ነገረው። መናደዱን አይቶ ሳይሆን አልቀረም፣ ከዚያ አካባቢ ሊያባርረው ሞከረ። ዘርዓይ "...እናንተ የምታዩትን እኔ የማላይበት ምን ምክንያት አለ" ሲል ጠየቀ። የዘበኞቹ አለቃ ጥያቄውን ከድፍረት በመቁጠር "ከእንግዲህ አንበሳ የለም። ...ለተኩላዋ ልትሰግድና ልታመልካት ይገባሀል" አለው። ዘርዓይም ይህ እይደረግም አለ። ክርክሩ ከረረ። ግሪዮ "ከእንግዲህ አንበሳው የተኩላዋ አሽከር መሆኑን ልነግርህ እወዳለሁ።...ያውም ንጽሕናውን ያሻሸል እንደሆነ....." አለ። ዘርዓይም በአልህ ተከራከረ። አንበሳው ከአንድም ሁለት ጊዜ ሰብሮ ድራሻቸውን እንደ አጠፋው ገለጻለት። ግሪዮ ደግሞ "...ከጀርባው ላይ ወጥታችው አላዩት፣ የአንበሳውን ቁርጥ ይወቁው..." የሚል ትዕዛዝ ለወታደሮቹ ሰጠ። ሕዝቡ ጭምር ከአንበሳው ላይ ለመውጣት ተተረማመሰ።

ዘርዓይ ደረስ ሥራውን የጀመረው በዚህ ጊዜ ነው። በያዘው ጉራዴ ጣልያኖችን ጨፈጨፋቸው። የዘበኞች አለቃ ማረሻል ግሪዮ ኢሶን በአንበሳው ዙሪያ እንደከበቡት አንከራትቶና እንደ ሕፃን አስለቅሶ፣ በአንበሳው እግር ሥር አስግዶ፣ እጅና እግሩን ቆራርጦ ከመሬት ጣለለት። የሌሎችንም ሬሣ እየተጐተተ በአንበሳው ሀውልት ሥር ሬሬፈው። እሱም ራሱ ከዚያች ንቅንቅ ሳይል ቁጭ አለ።

በከተማው ሽብር ተነሣ። "ኢትዮጵያ ሰብራ ገብታ ሕዝቡን በጉራዴ ፈጀችው።...ጠላትህን ቶሎ ታጥቀህ ራስህን ተከላከል..." ተብሎ ታወጀ። በያለበት ተኩስ ተከፈተ። በአደባባዩ ላይ በመተረማመስ ከአለቀው በተጨማሪ፣ በከተማይቱ ውስጥ እርስበርሱ ተሳለቀ።

ዘርዓይ ደረስ ጭፍጨፋ የጀመረበት ትክክለኛው ሰዓት አልተመዘገበም። ከጥዋቱ ወደ አራት ሰዓት አካባቢ ሳይሆን አልቀረም። ሽብሩ ቀኑን ሙሉ ውሎ ክቀትር በኋላ በአሥር ሰዓት ተኩል ላይ አገርዋ ሰላም መሆንዋ፣ ሽብር የተነሣው አንድ ዕብድ በሽታው ተነስቶበት እንደሆነ የሚገልጽ አዋጅ ተለፈፈ። የአዋጁ ቃል ይህ ብቻ አልነበረም። "... ወደ ፒያሣ ኢዝድራ ሄዳችሁ እጁን ያዙ..." የሚል ትዕዛዝም ነበረበት። በዚህ ትዕዛዝ ምክንያት የከተማው ሕዝብ እንደገና ተነቅንቆ ወጣ።

ዘርዓይ ደረስ ሰውነቱ እንደ ነብር ተነፋ። በተኩላዋ ሀውልት ላይ ቁሞ በመሙሀ ሕዝቡን ዝም አሰኘው። "...በየቤታችሁ እየዘርኩ ብዙ ሰው አርድ ነበር። ግን እኔን አሥሮ የያዘኝና አኮራምቶኝ የዋለው የአንበሳው ፍቅር ነው። ደግሞም አሟሟቱ ከአንበሳው ሥር እንዲሆንልኝ ፈልጌ ነው።...ወንድ

ይምጣና ይማርክኝ" አላቸው። ከተኩላዋ ላይ ወርዶ አንበሳውን እየዳሰሰ ቆመ።

አውቶማቲክ መሣሪያ የያዙ ወታደሮች በሞተር ሳይክል፣ በሁለት አቅጣጫ በመምጣት ተኩሰው መቱት። ጉራዴውን መዝዞ እንደገና ወደ ሕዝቡ ገሠገሠ። ከተማይቱ በተኩሱና በሽሽቱ ምክንያት እንደገና ተሸበረች። ዘርዓይ ተመልሶ ቢወድቅም ሊቀርበው የደፈረ የለም። ለአዲስ ሥራ እንደገና ተንቀሳቀሰ። ከወደቀበት ጉራዴውን ይዞ ተነሣ። ከመሬት ወድቆ የነበረውን የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ በማንሳት በደሙ ለውሶ ከአንበሳው ላይ ሰቀለው። ከተኩላዋ ላይ የነበረውን የጣልያንን ባንዲራ ሕዝቡ እያየ አወረደው። ቀድዶ ከመሬት ጣለና በእግሩ ረገጠው። ሊያስጥለው የሞከረ አልነበረም። አንበሳውን እየሳመ አነጋገረው። ምን እንደሚለው የሰማ የለም። ወታደሮቹ እንደገና በሮምታ ተኮሱ፤ እሱም ወደቀ። በዘርዓይ ደረስ ጀግንነት የተካሄደው የሮም አደባባይ ትርኢት በዚህ አለቀ። ከተማይቱ ምትሐት የመታትን ያህል ጭው አለች። ዘርዓይ ደረስ ታላቅ የጀግንነት ሥራ ሠራ። ሁኔታዎች አልገጠሙለትም እንጂ፣ የዲፕሎማቲክ ቡድን እስኪሰበሰብ፣ ሚልሣዊ ኢማኑኤል እና ሞሶሊኒ እስኪደርሱ ታግሦ ቢሆን ኖሮ ምንኛ ደግ ይሆንለት ነበር!

የዘርዓይ ደረስ ታሪክ በዓለም ተሰማ። የጣልያን ጋዜጦች ዕብድ ነው፣ የተጐዳው ሰው ትንሽ ነው እያሉ ቢዋሹ፣ አድማጭ አላገኙም። ሲልቭያ ፖንክረስት የዘርዓይ ደረስን አድራጐት ለዓለም አስረድተው፣ አያይዘውም "ኢትዮጵያ በቅርብ ጊዜ...ጥንታዊ ክብርዋን እንደምትመልስ አልጠረጥርም..." የሚል ትንቢት አበሰሩ።[10] ወዳጆቹ በሥራው ኮሩ፣ ስለመከራው አዘኑለት። ጠላቶቹ የተገላገሉት መሰላቸው። በገዛ ሀገሩና ወገኑ መካከል ጀብዱ ይሰሯል፣ ግን በሰው አገር እና በቅኝ ገዥ ሕዝብ አደባባይ ላይ ይህንን ለሠራ ምን ስም ይሰጠዋል?

ዘርዓይ ይህንን ሁሉ ሠርቶ፣ በስድስት ጥይት ተመትቶ መትረፉ ለጣልያኖች ራስ ምታት ሆነባቸው። በሮም ከተማ ከነበሩት ሀኪም ቤቶች ሁሉ ብልጫ ከነበረው ሀኪም ቤት አስገቡት። እየዳነ ሄደ። ሐምሌ 15 ቀን 1930 ዓ.ም /ጁላይ 22 ቀን 1938/ ሞሶሊኒ በጭፍጨፋው የቆሰሉትን ለመጠየቅ ከሀኪም ቤቱ ሲደርስ፣ ማሪዮ ኢሶን ሞቶ ሲገነዝ ደረሰ። እጅግ ተቆጥቶ ያመጣለትን ኒሻን ሰጥቶ ዘርዓይ ወደተኛበት ክፍል ሄደ። ድኖ ስለአገኘውም ይበልጥ ተናደደ። "አንተ ነህ ሮምን የደፈርካት?" ብሎ ጠየቀው። በሚገባ ታክሞ እንዲድን ለሀኪሞቹ አደራውን ሰጠ። እሱን በሞት መቅጣት፣ የጣልያንን ሰም በመላው ዓለም አየር ላይ መበተን መሆኑን ገልጾ፣ በዳነ ጊዜ በቃልም፣ በጽሑፍም ይቅርታ እንዲጠይቅ፣ የአእምሮ ሕመምተኛነቱ እንዲረጋገጥ፣ እንዲሁም ዘረዓይ ራሱ እንዲያምን እንዲደረግ ትዕዛዝ ሰጠ።

ፕሮፌሰር ፋውስቶ ኮንስታንቲኒ የተባለው ዋና ሀኪም የሞሶሊኒን ትዕዛዝ በሥራ ላይ ለማዋል በብርቱ ተጣጣረ። ብዙ ቀን አባበለው፤ በመጨረሻው አንድ ወረቀት እንዲፈርም አቀረበለት። ደብዳቤው ስለተደረገለት ሕክምና እመስገኖ "በአምስት መቶ ወታደሮች አደባባይ ላይ በድንገት ታምሜ በሰዎች ሕይወት ላይ ስለ አደረስኩት በደል... ይቅርታ እጠይቃለሁ። ...በስድስት ጥይት የተበሳሳው ሰውነቴና አንጐሌም ድኖ በቅርብ ቀን ለመውጣት ተስፋ ሰጥቶኛል /ሀኪሙ ማለቱ ነው/..." የሚሉ አዋራጅ ቃላትን ያዘለ ነበር። ዘርዓይ ደረስ ደብዳቤውን ከሀኪሙ ነጥቆ ቀድዶ መልሶ ከፊቱ ላይ በተነበት። ቀደም ብሎ ስለዚሁ ጉዳይ በተደረገ በአንድ ክርክር ላይ "በእናንተ አፍ እውነት የሚነገርበት መቼ ይሆን?" በሚል ቃል ቢገሰጸው እንኳን ያልታገሰለት ፕሮፌሰር ፋውስቶ ኮንስታንቲኒ የሀፍረት ማቅ ለብሶ ወጣ። ዳግመኛ አልተመለሰበትም።

ራሱ በመተናነቅ ፈንታ ፕሮፌሰሩ ሁለት ኢትዮጵያውያን ላከበት። አንዱ ስሙ ያልተጠቀሰ /ደጃዝማች ታዬ ጉልላቱ ሳይሆን አልቀረም/ አንዱ ደግሞ ወልደ ሚካኤል የተሰኘ መነኩሴ ነበር። ሁለቱ ሰዎች የዘርዓይ ደረስን አቋም ለማስለወጥ የሚቻላቸውን ያህል ደከሙ። የጣልያንን መንግሥት ኃያልነትና የእሱን ውጣትነት አያገናዘቡ ብዙ አባበሉት። እሱ ግን አልተቀበላቸውም። ከመኝታው ተነስቶ ቁጭ ቡማለት መጀመሪያ ለደጃዝማቹ መልስ ሰጠ። "..እንደርስዎ ያለ...ለማንም ጭንት ማጓጓዣ፤ አንበሳ መሆን የለበትም ነበር" አላቸው። "ለእነሱ ክብር፤ ለእነሱ መስፋፋት ከቶ የአናንተ አጠንጣኝነት ምንድነው?" ሲል ጠየቃቸው። እሳቸው ግን መልስ የላቸውም። ቀጥሎም "...እንሰሶች እንኳን ጌቶቻቸውን ይወዳሉ። ...አናንተ ግን...ቅሌታችሁን ተሸክማችሁ ትዞራላችሁ" ብሎአቸው ወደ መነኩሴው ዞረ። "...የእግዚአብሔር እንደራሴ መስለው በጥቁር ጨርቅ ይምነሸነሻሉ።" "...የሰውን የአኩልነት ኑሮ ለማጥፋት ከላይ ተልካችሁ የመጣችሁ መቅሰፍቶች ናችሁ" አላቸው። "ቅስናዎን ይተውት። ..ተራ መሐይምን መስለው እንደ ሴሎች ባንዶች ቢያገለግሉ ይበልጣል" ብሎ መከራቸው። በመጨረሻም "...ከአጠገቤ ውጡ" አላቸው። እነሱም ቀለል፣ ቀለል እያሉ ወጡ። ዳግመኛ ይህንን ዓይነት ጥያቄ ለዘርዓይ ደረስ አልቀረበለትም።

ጉዳዩ ወደ መደበኛ ፍርድ፣ መስከረም 3 ቀን 1931 ዓ.ም /ሴፕቴምበር 14 ቀን 1938/ ቀረበ። መደበኛ ፍርድ ቤቱ ወደ ጦር ፍርድ ቤት መራው። በጦር ፍርድ ቤቱ መስከረም 12 ቀን 1931 ዓ.ም /ሰፕቴምበር 23 ቀን 1938/ ቀረበ። ዳኞች በጭካኔአቸው የታወቁ ሦስት ኮሎኔሎች ነበሩ። ስማቸው አልተገለጸም። ነገር ግን ሳንታሪክስ፣ ዲማንደቶርና ኢንሒራ ሳይሆኑ እንደ አልቀሩ ተገምቶአል። ሕዝብ እጅግ በብዛት ተሰብስቦአል። ዓቃቤ ሕጉ አስቶፖኒ ነው። ዘርዓይ ደረስ ብቻውን ቀረበ። ሥርዓቱ፣ ዕለቱን ፍርድ ሳይሰጥ፣ ፍርዱም ሳይፈጸም እንዳያድር የሚያስገድድ ነበር።

ዓቃቤ ሕጉ አሥራ አንድ ወንጀሎች በእሱ እንደተፈጸመ ገልጾ፣ ዘርዓይ ደረሰ "በቤንዚን ተቃጥሎ እንዲሞት ወይም እጁ ታሥሮ በሠረገላ እየተጐተተ በከተማው እየዞረ ለሕዝብ እንዲታይ" ተብለው በተሰይ ለቅኝ ግዛት ዜጐች ከወጡት ሁለት አንቀጾች በአንዱ እንዲቀጣ ሃሳብ አቀረበበት። እነዚህን ሁለት አንቀጾች የጠቀሰው ሌላ የባሠ ባለመኖሩ እንጂ፣ ለዘርዓይ በደል በቂ ናቸው በማለት አለመሆኑን አስረዳ። የክሱ አቀራረብ ኢጣልያ ተደፍራለች፣ አንድ ማርሻልና ብዙ ወታደሮች ሞተዋል፣ በዚሁ ምክንያት ከተማ ተረብሾ እንደ ነበርና የሞተና የቆሰለው እንዳልታወቀ የሚገልጽ ነበር።

የቀረቡበት ክሶች ፍሬ ነገር ከዜኒቶ ሞሶሊኒ የተፈቀደ የይሰፍ ፊርማ ይዞ ወታደሮች በማዘናጋት የጦር መሣሪያ /ጕራዴ/ ይዞ አደባባይ ገብቶአል። ክፍተኛ ረብሻ በማስነሳት ወታደሮቹንና ሰላማዊ ሰዎችን ፈጅቶአል። የጣልያንን ክብር ደፍሮአል፣ በተፈጥሮ አሥር ሺህ ጊዜ የሚበልጡትን የጣልያኖችን ታሪክ አደፍርሶአል። የጣልያንን ፖለቲካ ለማጣረስ አስቦ ተነሳስቶአል። ከመንግሥታችን የተጣለበትን ኃላፊነት አንኳሶ ጥሎአል፣ የመንግሥት ምሥጢር አባክኖአል። ጣልያኖችን የጨፈጨፈበትን ጕራዴ የወሰደው እስኩድሪን አታልሎ ነው። የጣልያንን ባንዲራ ከራሱ ቀሰበት አውርዶ ረጋግጦ ከመጣሉም በላይ፣ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ በራሱ ደም ቀብቶ ሰቅሎአል። ተፈሪ ለዘለዓለም ይኑር፣ የኢጣልያ ፋሽስት መንግሥት ይውደም በማለት የኢጣልያ መንግሥት ላይ ጥላቻ አሳይቶአል የሚሉ ነበሩ። ክሶቹ፣ እውነታቸው በሁሉም ዘንድ የታወቀ በመሆኑ፣ ማስረጃ የሚጠየቅበት አልነበረም።

ሰብሳቢው ዳኛ ሌሎቹን ሳያማክር አስተያየቱን ሠነዘረ። "...ኢጣልያ አንዳችም ጉዳት አልደረሰባትም። ...ኢጣልያ...ልጆችዋን ወደ ሜዳ ልካ የጦርም የትምህርትም ሐዋርያ ሆነው ይገኛሉ" አለ። የሕዝቡ ጫጫታ ተነሣ። እሱ ግን "ዝሆንን በቁንጢጥ...ባንድ ጥፍር በማይሞላ ሰው ሕመም የተነሣ ይህንን ያህል ልንተችበት አይገባም" አለ። ቀደም ብሎ ጆሮውን ሳይኮረኵር አልቀረም። ጫጫታውን፣ ፉጨቱን፣ ውሸቱን ከምንም ሳይቆጥር "አንድ ዕብድ የምንቀጣበት አንቀጽ በዚያው በአንጐል ሕመምተኞች ቦታ ተቀሳቅሎ እንዲኖር ብቻ ነው" በማለት ፍርዱን ደመደመ። ሌሎች ሁለት ዳኞች በዚህ ፍርድ ሳይስማሙ ቀሩ። "...እኛ ዕብድ መሆኑን አናምንም። ...በተጠቀሰው አንቀጽ ይፈረድበትና አሟሟቱን እንመልከት" አሉ። ዓቃቤ ሕጉ በሁለቱ ዳኞች ሃሳብ ልቡን አደንድኖ "እሱን ዕብድ ሰው ነው የሚል ራሱ ያበደ ነው" አለ። ችሎቱን ከመድፈር አልተቆጠበበትም። የሕዝቡ ጭብጨባ ከዳር እስከዳር አስተጋባ።

ዳኞች ፊት ሊያደርጉት ይገባ የነበረውን ሥራ ጀመሩ። እርስበርሳቸው ተመካክረው የወንጀሉን መነሻ ለመመርመር ተስማሙ። ዘርዓይ ቃሉን እንዲሰጥ ተፈቀደለት። የጣልያንኛ ቋንቋ አጥርቶ ማወቁ፣ ጕዳዩን እንደ ልቡ

ለማስረዳት ጠቀመው። ጎሊና የሚሠረሥረውን ነገሩን ቀጠለ። "ምን እንድል ነው የምትሹት? አብድ ነኝ እንድል ነው ጤነኛ?" ብሎ ዳኞቹን ጠየቃቸው። መልስ የለም። ሊደነፋ ነፍሥና ሥጋን ለመለያየት የተመረጡ በሚመስል አቀራረብ ወደ ዓቃቤ ሕጉ ዞሮ፦"...አንተ እንደምትሰውና እንደምታስወራው መሆኑን ሳረጋግጥልህ እደሰታለሁ። በእውነቱ የእኔ ዶክተር አንተ ብቻ ነህ" አለው። ሐኪሙ ከሞሶሊኒ ተሻርክ ዕብድ ነው ማለቱን፣ ሰብሳቢውም ዳኛ ይህንኑ ማስተጋባቱን አጋለጠ። ሞሶሊኒ የጣልያንን ዕድል በር ሊከፍት የተፈጠረ አስመስሎ፣ በኋላ ግን ሮምን ጥቁር ታሪክ አልብሷት እንደሚሄድ ተነበየ።

ሕዝቡ ይገደል! ይሰቀል! ይቃጠል! አለ። እሱ ግን በድፍረት ንግግሩን ቀጠለ። ብዙ ከወቀሳቸው በኋላ "...እኔ ሙሉ ጤነኛ ነኝ" አላቸው። ከእነሱ በስተቀር ምንም ሕመም እንደሌለበት ገለጸላቸው። የግፍ ሥራቸው ቢበዛበት ጥቂት ሰዎች ማረዱን አምኖ፣ እርዱ እንዳለጠገበው፣ እንዲያውም በሽታ እንደሆነበት አረጋገጠላቸው። "...ያገርን መውደድ ቋንቋ ካወቃችሁ አገራችንን እንድንጠላ፣ እርስበርሳችን እንድንጣላ ...ለምን ታስገድዱናላችሁ?" ብሎ ጠየቃቸው። አሁንም መልስ የለም። እሱ ላይ ለመፍረድ ከሺህ ሕዝብ በላይ መሰብሰቡን አሳይቶ፣ የፋሽስት ወሮበሎች በእሱ አገር በሚሊዮን የሚቆጠር ሕዝብ ሲፈጁ ዳኛ እንደ ሌለባቸው ገለጸ። "ግን" አላቸው "የእነሱ /የኢትዮጵያውያን/ አጥንትና ደም ዋጋ ሲኖረው፣ የእናንተ ስም እየገማ መሄዱ ዛሬ አይታያችሁም። ...ዘለዓለም በታሪካችሁ አቀርቅራችሁ ትኖራላችሁ" አላቸው። ከዚያም አመስግኖ በጣሊያን ሰው ላይ ይህንን ያህል ትዕግስት ሲያይ የመጀመሪያው መሆኑን ነገራቸው።

በመጨረሻም "የኢጣልያን ባንዲራ ይውደቅ! የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ በክብር ትኑር! ንጉሥ ተፈሪ በድል አድራጊነት ይኑር! የይሁዳ አንበሳ ምንግዜም ድል ከሱ ይሁን!" ብሎ ንግግሩን ደመደመ። ችሎቱ አንደ ትያትር ሆነ። ሕዝቡ ከመጠን ያለፈ ጮኸ። ተተራመሰ። ዳኞቹ የሚሰማቸው ስለአጡ ተናደዱ። ዓቃቤ ሕጉ "...ሮማ ማልቀስና ማዘን የሚገባት ዛሬ ነው " አለ። ሰብሳቢው ዳኛ ተሸነፈ። በቤንዚን ተቃጥሎ ይሙት በሚለው ፍርድ ሦስቱም ዳኞች ተስማሙ። ንቀቱንና ድፍረቱን የሚያሳይበት፣ ስሜቱን የሚገልጽበት ዕድል ለዘርዓይ ደረስ በመስጠታቸው ሁሉም ተጸጸቱ። ኩሉኔል ሳንታሪክስ የተባለው ሰብሳቢ ዳኛ "አሞራ በራሳችን ላይ ተቀምጦ ረፈጡን እስከሚጥልብን ድረስ ተኝተናል" አለ። ዘርዓይ በፀጥታ ይመለከት ነበር።

ችሎቱ በዚህ ዓይነት ላይ እንዳለ አዲስ ነገር ተፈጠረ። ሁለት የፖሊስ መኮንኖች ችሎቱን ሰብረው ገቡ። ከሁለቱ አንዱ ወታደራዊ ሰላምታ አቀረበና አንዲት ጥቁር ፖስታ ለሰብሳቢው ዳኛ ሰጠ። ሰብሳቢው ዳኛ ፖስታውን ቀድዶ ሲመለከት የሞሶሊኒን ፊረማ ስለለየ በድንጋጤ ኩሽሽ አለ። ከሞሶሊኒ የተላከ ደብዳቤ መሆኑን በመግለጽ ደጋግሞ ለራሱ ከአነበበው በኋላ

ለሕዝቡ አሰማው። ሞሶሊኒ በዚህ ደብዳቤው የገለጸው ለአንድ እብድ ዋጋ በመስጠት በጭቅጭቅ መዋላቸውን እንደሰማ ከገለጸ በኋላ ብርቱ ወቀሳ ይወቅሳቸዋል፡ "...በአርባ ሚሊዮን ደንቆሮ መካከል ተፈጥሬ እናንተን ጥዋት ማታ ማስተማሩ ሰለቸኝ" የሚል ስሞታ ከአሰማ በኋላ፣ "...ለዕብድ ያቋቋምኩት ወንጀለኛ መቅጫ የለኝምና...ወደ አንኮል በሽተኞች ሐኪም ቤት ሄዶ እንዲቀመጥ ይሁን። ...በዕብደቱ እንጂ በሌላ መልክ ሮማንንና ሕዝብዋን አንደ አልደፈረ አንዲታወቅ" የሚል ውሣኔ የያዘ ነበር። ከዚህም በስተቀር ማንም ሰው ዘርዓይ ደረስ ያደረገውን ቢያነሣ በገመዱ እንደሚገባ ይገልጽና፣ ጳጳቹ ወደ ሞሶሊኒ በፍጥነት እንዲቀርቡ የሚያዝ ነበር።

ዘርዓይ ደረስ የአርበኝነትና የፖለቲካ ሥራውን በጣልያን አገር፣ ከዚህ በላይ በተገለጸው አይነት አከናውኖ ወደ አሥራት ኑሮው ተሸጋገረ። ቀጣይ ታሪኩን ከድል በኋላ ትግል በሚለው ምዕራፍ ይመልከቱ።

ዘርዓይ ደረስ ግን ማን እንደነበረ ማወቅ ይገባል። ዘርዓይ በአዲ ሐይስ፣ ከተማ በተባለች ቦታ በ1908 ዓ.ም ተወልዶ ሐዘጋ ያደገ የኤርትራ ልጅ ነው። አሥመራ ከተማ ከገባ በኋላ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶን ትምህርት ያስተማሩት ርዕሰ ደብር ዕቁበ እንድርያስ እንደሆኑ እሳቸው ራሳቸው ለእኔ ለዚህ ታሪክ ፀሐፊ ነግረውኛል። እሳቸውም በጐንደር፣ በትግራይ፣ በጐጃምና በሳስታ እየተዘዋወሩ ድጓ፣ ጸመ ድጓ፣ አቋቋም የተማሩ ስለነበሩ፣ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ትምህርት ብቻ ሳይወሰኑ የኢትዮጵያን ታሪክና ሥርዓት በማስጠናት የሀገር ፍቅር ስሜት ሳያሳድሩበት አልቀሩም። እሱም ብልህ ተማሪ ስለነበር፣ በትምህርታቸው እስከ ሕይወቱ ፍፃሜ ሠራበት።

ከቤተ ክህነት ትምህርት በኋላ ዘርዓይ በሚልማዊ ኢማኑኤል ስም በተከፈተ፣ አሥመራ ከተማ በነበረ ትምህርት ቤት እስከ መሰስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ድረስ ያለውን ትምህርት ተከታተለ። ከዚያም አዲ ኡግሪ ተዛውሮ ጥቂት ከተማረ በኋላ፣ ኮረም በነበረ የሚሲዮን ትምህርት ቤት፣ ቤአስተማሪነት ሥራ በ1920 ዓ.ም ተሰጠው። የአስተማሪነት ሥራ የተሰጠው የኢትዮጵያ ፍቅር እያየለበት ስለሄደ፣ ሀሳቡን ወደ ሌሎች ወጣቶች ለማዞር እንጂ እሱን ለመጥቀም አልነበረም። በዚሁ ዓመት በግንቦት ወር መቀሌ በሚደረግ ስብሰባ ላይ እንዲገኝ ስለታዘዘ ሄደ። በየመንገዱ ዳር በጦርነቱ የሞቱ ኢትዮጵያውያን ሬሣ በብዛት ማየቱ፣ የሀገር ፍቅር ስሜቱን አጋግሎ እንደ በሽታ ወደ ህመምነት ተለወጠበት። ወደ ሥራው በተመለሰ ጊዜ ስሜቱን ለተማሪዎቹ መግለጽና ስለሀገራቸው ስለ ኢትዮጵያ ጉዳይ ማስተማር፣ ከዚያም አልፎ መከራከር አመጣ። ይህ ይሁኔታ ለጣልያኖች ስለከበዳቸው ከሥራው ተባረረ።

ሁኔታው በቤተሰቡ ላይ ሥጋት ስለፈጠረ ተዳረ። ዓለማሽ የተባለች ልጅ ከሰገነይቲ አገባ። የደጃዝማች አዳል ወገን ነበር። ዘርዓይ እንደ በሽታ

ዘልቆት በገባው የሀገር ፍቅር ስሜት ምክንያት ከሁለት አጣብቂኝ ውስጥ ገባ። አንዱ ከወገኖቹ፣ ሌላው ደግሞ ከጌቶቹ ወገን የተሰነዘረ ነበር። ሁለቱም ከባድ ነበሩ። ኤርትራውያን የጣልያኖች ሰላይ አድርገው ቆጠሩት። እሱ የሚናገረው፣ እነሱን ለማውጣጣት መሰላቸው። ጣልያኖች ልቡ በሀገሩ ፍቅር እንደተቃጠለ አወቁ። የቅኝ ግዛት ዜጐቻቸውን እያነሳሳባቸው መሆኑን ተረዱ። እሱም በበኩሉ ኢትዮጵያን መደገፉን ቀጠለ። ለነጮች ዝቅተኛ ግምት ከመስጠቱም በላይ፣ የማንንም ማስጠንቀቂያ ከቁም ነገር ሳይቆጥር "ነብረ ሚካኤላውያን" የሚል ማኅበር አቋቋመ። የማኅበሩ ዓላማ ኢትዮጵያን በጠላትዋ እጅ ስለወደቀች በጸሎትም፣ በመንፈስም ከኢትዮጵያውያን ጐን መቆም ነበር። የማኅበሩ የስም አጠራር የተመረጠው፣ የበላይ ጠባቂ ከነበሩት ከአባ ገብረ ሚካኤል ስም በመያያዙ ሳይሆን አልቀረም። ከዚያም አልፎ ተቃውሞውን ቢጋዜጣ መግለጽ ጀመረ።

ደውዲያች ከተባለው የኤርትራ ገዥ ዘንድ ቀርቦ የቃል ጥያቄ ተደረገለት። የጣልያንን ለቅኝ ግዛት ዜጐች የሚሰጠውን ትምህርት ማጠናቀቁ፣ ባለትዳር መሆኑ ታውቀ። በቋንቋም ረገድ ኢጣልያንኛ፣ ትግርኛ፣ አማርኛ፣ ዓረብኛ አጣርቶ ማወቁ፣ ከዚህም በስተቀር ኦሮምኛ፣ ሱማልኛና አገውኛ የሚያስጠናው ቢያገኝ ማወቅ እንደሚፈልግ ግልጽ ሆነ። ለጣልያኑ አገረ ገዥ ይህንን ዓይነቱን ሰው በአሥመራ ውስጥ ከማስቀመጥ ወደ ሮም መላክ የተሻለ ሆኖ ታየው። በአስተርጓሚነት ሥራ በጣልያን፣ በቅኝ ግዛት ሚኒስቴር ውስጥ እንዲሠራ ወደ ሮም ላከው። ዘርዓይ ወደሮም የተላከው፡- የደረጃ ዕድገት በመስጠት የጥላቻ ስሜቱን ለማቀዝቀዝ፣ ጉዳት ሊያደርስበት ከሚችል አካባቢ ከአሥመራ ለማራቅና በችሎታው ለመጠቀም ሳይሆን አልቀረም።

የዘርዓይ ወደ ሮም መሄድ ካባድ ነገር ሆነ። ከቤተሰብ መለየቱ አንዱ ሲሆን፣ የሚከተለው የፖለቲካ አቅጣጫ የፊጠረው ሥጋት ሌላው ነበር። ቢሆንም ጉዞውን ቀጥሎ በመስከረም 1929 ዓ.ም ሮም ገባ። ከበቂ ደመወዝ ጋር የተመሬጠበትን የአስተርጓሚነት ሥራ በቅኝ ግዛት ሚኒስቴር ውስጥ ያዘ። ለአንድ ቅኝ ግዛት ዜጋ ሊያገኝ የሚቻለውን ከፍተኛ ደረጃ አገኘ።

ነገር ግን ይህ ሁሉ ሥጋዊ ፀጋ ለዘርዓይ ደረስ መንፈላዊ እርካታ አልሰጠውም። ስለዚህ በዚያ ከነበሩ የጣልያን ደጓዝማቾች ጋር ክርክሩን ቀጠለ። በጥቅምት ወር 1929 ዓ.ም አሥመራ ለነበረ ገብረ ሕይወት ለተባለ ጓደኛው የጻፈው ደብዳቤ ከብዙ ማስረጃዎች አንዱ ይሆናል። ዘርዓይ በዚህ ደብዳቤው በኑሮው በኩል ምንም የተጓደለበት ነገር እንደሌለ ከአረጋገጠ በኋላ፡- "...አሥመራ ውስጥ አልፎ አልፎ ይዘጋ የነበረው ልማኔ ተከፍቶአል። ካሬ ሮምን እንደ ቅኝ ግዛቱ ነው የማያት ..." ብሎአል።

የጉራዴውንም ጉዳይ መመልከት ይገባል። ራስ አሉላ በጥር ወር 1871 ዓ.ም /ጃንዋሪ 1878 እ.ኤ.አ/ ዶጋሊ ጦርነት ላይ ታጥቀውት በዋሉት

ጉራዴ ነው ዘርዓይ ደረስ ሰኔ 7 ቀን 1930 ዓ.ም /ጁን 14 ቀን 1938/ የደብዳ ሥራ የሠራው። ጉራዴው ከእጁ የገባው አስኩድሪ የተባለ ጣልያናዊ ወዳጁ ከሮም ወደ ናፖሊ እንዲወስድለት ከሞሶሊኒ ስለተፈቀደለት ነው። የሞሶሊኒን ፈቃድያገኘው ደግሞ አስኩድሪ ራሱ እንዲያመለክት በዘዴ በማስማማት ነው። አስኩድሪ ጉራዴውን ወደ ሮም የወሰደው የመቀሌ ገዥ በነበረ ጊዜ ደጃዝማች በየነ የተባለ እወደድ ባይ ስለሰጠው ነው። ደጃዝማች በየነ ጉራዴውን ለአስኩድሪ የሸለመው በአፄ ዮሐንስ ቤተ መንግሥት በወግ ዕቃነት ተጠብቆ ይኖር ከነበረበት ቦታ ወስዶ ነው።[11]

ሌላው በጣልያን አገር አስደናቂ የጀግንነት ሥራ የሠሩት ሻምበል /ኩሎኔል/ አብዲሣ አጋ ናቸው። እሳቸው ደግሞ በኢጣልያ በረሃዎች ሸፍተው ከቦታ ወደ ቦታ እየተዘዋወሩ የአርበኝነት ሥራ አካሂደው በመጨረሻ ከድል አድራጊው የእንግሊዝና የአሜሪካን ጦር በክብር ተቀላቅለዋል። ሲቀላቀሉም በሻምበል አዛዥነት ጦራቸውን ነጭ ጥቁር ሳይባል ሁሉም በግራ ክንዱ ላይ የኢትዮጵያን፣ በቀኝ ክንዱ ላይ ደግሞ የእንግሊዝን ሰንደቅ ዓላማዎች እንዲያሥር አድርገው በማሰለፍ ነው። ከዚህም በኩተቀር ልዩ ልዩ የጦር መሣሪያ አስረክበዋል። ዝርዝሩ እንደሚከተለው ነው።

የዕቃው ዓይነት	ከጣልያን የተማረከ	ከእንግሊዝ የተላከ	ድምር
1ኛ. ልዩ ልዩ መትረየስ	254	40	294
2ኛ. የልዩ መሣሪያ ጥይት	327,923	16,354	344,277
3ኛ. የእጅ ቦምብ	9,080	400	9,280
4ኛ. ልዩ ልዩ ጠመንጃ	253	-	253
5ኛ. አውቶማቲክ ሽጉጥ	10	-	10
6ኛ. ካሜራ	2	-	2
7ኛ. ኮምፓስ	90	-	440
8ኛ. ጂፕ መኪና	350	-	15
9ኛ. ብረት ሰበስ መኪና	15	-	2
10ኛ. ጩቤ	2	-	104
11ኛ. የወታደር ሬዲዮ	104	-	9
12ኛ. የቴሌግራም ሬዲዮ	7	2	3
13ኛ. ከባድና ቀላል መኪናዎች	3	-	103
14ኛ. የብረት ባርኔጣ	103	-	17,731
15ኛ. ደናሚት	17,731	-	350
16ኛ. የኢጣልያ ካርታ	-	-	4
17ኛ. የጦር ሚዳ መነጽር	-	-	20
18ኛ. ሞተር ሳይክል	-	-	1

እንደዚሁም ብዙ ልብስና ልዩ ልዩ ዕቃ። የተቀበሉአቸውም የእንግሊዙ ጦር ጠቅላይ አዛዥ ፊልድ ማርሻል ቫይከውንት ሞንትጎሞሪ ነበር። የምስክር ወረቀትና ሜዳልያም ተሸልመዋል። ከዚህ በላይ የተገለጸው ውጤቱ ሲሆን፣ የሻምበል /ኩሎኔል/ አብዲሣ አጋ የፈጸሙት ሥራ ከዚህ የሚከተለው ነው።

በሆለታ የጦር ትምህርት ቤት የአጭር ጊዜ ትምህርት እንደ እገኙ ኢትዮጵያ ድል ሆነች። ኢትዮጵያ ድል ስትሆን አብዲሣ አጋ በ15 ዓመት ማርተጋሻ ወታደር ነበሩ። ስለዚህም የጥቁር አንበሳ ጦር አባል ሆነው ወደ ምዕራብ ኢትዮጲያ ተጓዙ። በወለጋ በኩል ኢሉባቡር ደርሰው፣ ከዚያም ተመልሰው በጎጅብ ጦርነት በጥይት ቆሰሉ። በዚያውም ላይ የራስ እምሩ ጦር አጄን ሲሰጥ እሳቸውም አብረው እጃቸውን ሰጡ።

ጣልያን ከምርኮኞቹ ወታደሮች ጋር አብሮ አምጥቶ ጂማ እሥር ቤት ከተታቸው። ከዚያም ወደ አዲስ አበባ መጥተው በእሥራት ከቆዩ በኋላ የቁም እሥረኛ ሆኑ። በቁም እሥረኝነት ጥቂት ጊዜ እንደ ቆዩ፣ የካቲት 12 ቀን 1929 ዓ.ም በግራዚያኒ ላይ በደረሰው አደጋ ምክንያት እንደገና ተይዘው ብዙ ድብደባ ከደረሰባቸው በኋላ፣ እሳቸውን በመኪና በማጓጓዝ ምዕዋ ወስደው ከመርከብ ላይ አስፈሩአቸው። ከምዕዋ ወደ ደናኔ ወሰዱአቸው። ደናኔ ሳሉ ኢጣሊያኖች እሥራ ስምንት የሆለታ ጦር ትምህርት ቤት መኰንኖችን፣ የገዛ መቃብራቸውን አስቆፍረው በመትረየስ ከደበደቡአቸው በኋላ፣ የተረፉትን ሠላሳ በመርከብ አሳፈሩአቸው። ወታደር አብዲሣ አጋ ከእነዚህ እሥረኞች መካከል አንዱ ነበሩ።

እሥረኞቹ ናፖሊ ሲደርሱ በአውቶቡስ አጓጉዘው አኞኖ ከተባለው የጦር ሠፈር አስገቡአቸው። በእዚያ እንደ አሉ ኢጣልያ ከጀርመን ጐን ስመቆም ወሰነች። ጦርነቱ በጣልያን አገር ሲቀሰቀስ፣ በእንግሊዝ አይሮፕላኖች የተበተነ ጽሑፍ አግኝተው አነበቡ። በዚህ ደግሞ ሌላ ድብደባ ደረሰባቸው። በዚህ ተናደው ወራውን የነገረባቸውን አሳባቂ ደበደቡ። በዚህ ደግሞ ከጦር ሠፈሩ ተወስደው ከናፖሊ፣ ባዶሊዮ ወህኒ ቤት ገቡ።

የሰው ቅልጥም በሚመስለው የኢጣልያ አገር ላይ ጦርነት ክጫማው ጀምሮ ወደ ሀገሪቱ አካል ወደ ሰሜን መንደድ ሲጀምር፣ ጣልያኖች በናፖሊ የነበሩትን እሥረኞች ወደ ሰሜን ኢጣልያ አጓጉዙ። ከእነዚህ እሥረኞች አንዱ ወታደር አብዲሣ አጋ ነበሩ። ሊቲ በተባለው ወረዳ ትሪያ ቀበሌ ከሚገኝ እሥር ቤት አገቡአቸው። የአግር ጉዞው ብዙ እሥረኞች የተሰቃዩበት ነበር። አስተሳሰባቸው እደገኛ መሆኑ በጣልያኖቹ ዘንድ ስለታወቀ፣ አንድ ክፍል ውስጥ ብቻቸውን ተዘጋባቸው። ዕብድ

ብለው እጆቻቸውን በሰንሰለት አሠሩአቸው። በልመና እጆቻቸው ሲፈቱላቸው በአጠገባቸው የነበሩትን ጣልያኖች ደብድበው እንጀታቸውን ከማራስ ጋር ዕብደታቸውን በግብር አረጋገጡ። ከፖሊስ እሥር ቤት ሆነው ሀኪም ቤት እየተመላለሱ እንዲታከሙ ተደረገ። ከፊተኛው ሁኔታቸው ይህ የተሻለ ሆነ። ከዚያም ወደ ፍርድ ቤት እንዲቀርቡ ሌቺ ወህኒ ቤት ገቡ።

ከሌቺ ወህኒ ብዙ የዩጐዝላቭ፣ የእንግሊዝ፣ የመስኮብ፣ የአሜሪካ ዜጐችና አረቦች አገኙ። ከእነዚህ ሰዎች መካከል የዩጐዝላቪያው ተወላጅ ጁሲዮ ኢታቺክ የሚባሉ ሰው ነበሩበት። እኝህ ወታደር አብዲሣ በአቀረቡት ሃሳብ መሠረት ከእሥር ቤቱ አምልጠው ለመውጣት ተስማሙ። የእንግሊዝ አይሮፕላኖች ቦምብ በሚጥሉበት ጊዜ ከወህኒ ቤቱ አመለጡ። ያመለጡትም ያገኙትን ብርድ ልብስ ቀዳደው በመቀጣጠል አንዱን ጫፍ በመስኮት ላይ በማሰር ከነበሩበት ፎቅ ላይ ተንጠልጥለው በመውረድ ነው። ከእሥር ቤት ያመለጡት ሦስት ኢትዮጵያውያንና አምስት ዩጐዝላቫውያን ነበሩ። ሁሉቱ ሌሎች ኢትዮጵያውያን ካሣዬ አብጤና ከርሎ አቦ መጋል የሚባሉ ነበሩ።

ስምንቱ ሰዎች ከእሥር ቤት አምልጠው ጫካ ከገቡ በኋላ ከሁለት ከብት ጠባቂ ሰዎች ላይ ሁለት ረሽ ነጠቁ። ሁለቱን ረሽ ጠመንጃዎች ለመንጠቅ የቻሉት አንዱን ሰው ገድለው፣ ሁለተኛውን አቁስለው ነበር። ከዚያም ካዛቪንቺኖ ወደ ተባለው ተራራ ወጡ። ከዚያም በጣልያን መንግሥት ላይ ከሸፈቱ አርበኞች ጋር ተቀላቀሉ። በዚህ ጊዜ ቁጥራቸው ወደ ሠላሳ ከፍ አለ። ነገር ግን የነበሩአቸው መሣሪያዎች አንድ አልቤን ጠመንጀ ከአሥራ ሁለት ጥይት ጋር፣ ሁለት ረሽ፣ አንድ ፍሻሌ ሽጉጥ ከስድስት ጥይት ጋር፣ ሦስት የእጅ ቦምቦች ነበሩ። የጐደለው በዱላና በድንጋይ ማሟላት ነበረበት።

አንድ የአየር ኃይል መኮንን ከገደሉና አንድ ወህኒ ቤት ከአቃጠሉ በኋላ ከዛ ሎሬንስ ወደ ተባለው ተራራ ወጡ። ከለላ እየሰጠ የሚከተላቸውን የጣልያን መንግሥት ጦር ጋር ኡያሮ በተባለችው መንደር አካባቢ ተዋግተው ሃምሣ ሁለት ፋሽስት በመግደል ድል አድርገው አባረሩአቸው። ከእነሱም ወገን ሁለት ሰዎች ቆሰሉባቸው፣ አሥራ ሦስት ሰዎች ሞቱባቸው።

ቲቶ ነጩ /ቢያንካ/ የሚሉት ሰላያቸው ፍሩንታሌ በተባለው ሜዳ ላይ የጀርመን አይሮፕላን ማረፉን ነገራቸው። ወታደር /ኩሎኔል/ አብዲሣ አጋ ጂሊዮ አታቺክ ከተባለው ዩጐዝላቫዊ ጋር ሃያ ሦስት ወታደር ይዘው ወደተባለው ሜዳ ሄደው በጀርመኖቹ ላይ አደጋ ጣሉ። አይሮፕላን ነጅው

አይሮፕላንዋን ይዞ ሊያመልጥ በሌሎቹ ላይ ጉዳት አደረሱባቸው። ከጀርመኖቹ አንዱ መቶ አስቃና ሦስት ወታደሮች ተገደሉ፣ ሌሎቹ እጃቸውን ሰጡ። ከእነሱም ወገን ከርሎ አባመጋል የተባለው ኢትዮጵያዊ ሞተ። እነሱም የከርሎን ሬሣና እንደዚሁም የማረኩአቸውን የፋሽስት ወታደሮች ይዘው ኡያሮ ወደ ተባለው የጦር ሠፈራቸው ተመለሱ።

በምርኮኞቹ ላይ ፍርድ ተያዘ። ግብራቸው ከተመረመረ በኋላ በሞት እንዲቀጡ ተወሰነ። ውሣኔው ለምርኮኞቹ ሲገለጽላቸው፣ ጀርመናዊው ሻምበል ሃሳቡን ለመግለጽ እንዲፈቀድለት ጠየቀ። በተፈቀደለት ጊዜ ፋሽስቶች በአርበኞቹ ቀራጥነት እንደተደናገጡ፣ ይልቁንም የወታደር /ኩሎኔል/ አብዲሣ ጀግንነት ገንኖ እንደሚነገር ከአስረዳ በኋላ፣ የደረሰባቸውን ሁኔታ ለአለቃው በራዲዮ ለማስታወቅ እንዲፈቀድለት ጠየቀ። ተፈቅዶለት ለአለቃው ከአስረዳ በኋላ ደግሞ እጆቻቸውን ላይታሠሩና ዓይኖቻቸውን በጨርቅ ላይሸፈኑ እንዲገደሉ ጠየቀ። ይህም በተፈቀደለት ጊዜ የወገቡን ሽጉጥ፣ የሱሪውን ቀበቶ፣ የእጁን ሰዓት ለወታደር /ኩሎኔል/ አብዲሣ አጋ ሸልሞ፣ ግንባሩን ሰጠ። በእሱና በወታደሮቹ ላይ የሞት ፍርድ ተፈጸመባቸው።

በሌላ ቀን ጠላት ሳንቢር በተባለው ተራራ ላይ አርበኞችን ለማጥቃት ሞከረ። የኢትዮጵያ፣ የእንግሊዝ፣ የፈረንሣይ፣ የዮጐዝላቪያና የሌሎችም አገር ሰዎች ያሉበት የአርበኛ ቡድን በጥይት ቆላው። በሳንጃ እየቀደደ ገደል ሰቀቀው።

አርበኞቹ ኃይላቸውን ከለጠናከሩ በኋላ የውጊያ ሥልታቸውን ከመከላከል ወደ ማጥቃት አዞሩ። ከዕለታት አንድ ቀን ከአንድ ቤተክርስቲያን የካህናት ልብስ ወስደው ለአሥር የራሳቸው ወታደሮች አልብሰው ሣንላ ባሪኖ፣ ደሌ ማርኬ ከተባለችው ከተማ አስገቡ። ከዚያ የነበሩትን የፀጥታ ጠባቂዎች ፈጅተው፣ በእጃቸው የነበረውን መሣሪያ ማረኩ። ምርኮውም አንድ መቶ አሥር ጠመንጃ፣ አራት ሺህ ሰባት መቶ ሰባ ዘጠኝ ጥይት፣ አንድ ካሚዮን፣ ሁለት ሬዲዮኖች እና አራት ሠራተኞቻቸውን ያጠቃልል ነበር።

ስንቅና ትጥቅ ለማግኘት ከገበያ እየገቡ መቅረጥ ያዙ። ፍሩንታሌና ትሪያ ከተባሉት ሁለት ገበያዎች፣ ከብዙ የምግብ ሸቀጣ ሸቀጥ ጋር 1761 ክባድና ቀላል መሣሪያ፣ 4 የእጅ ቦምብ፣ 3,836,231 ጥይትና 44,003,213 ሊሬ አገኙ። ከሸፍቶቹ ውስጥ ኢትዮጵያዊ መታየቱ እጅግ አስደንጋጭ ሆነ። ከገበያዎቹ የሚገኙት የስልክና የኤሌክትሪክ መሥመር እየበጠሱ ከመሆኑም በስተቀር፣ ለቅቀው ሲሄዱ ደግሞ ድልድዮችን በድናሚት ማፍረሳቸው በመንግሥት ላይ ችግር ፈጠረ።

በወታደር /ኩሎኔል/ አብዲሣ የሚመራ አንድ ቡድን ቢያጉራ ከተባለው መንገድ ላይ አድፍጦ በመጠበቅ፣ ኩሎኔል ትሩንቢንቲ የተባለውን የጦር መኰንን ከአንድ ሹፌርና ከሁለት ወታደሮቹ ጋር ገድሎ 3 ቀላል አውቶማቲክ፣ 328 ጥይት፣ 3 የእጅ ቦምብና ልዩ ልዩ ደብዳቤዎች ማረከ።

የኩሎኔል ትሩንቢንቲን መገደል ሲሰማ፣ ጣልያን ሌላ ጦር ላከ። እሱንም አርበኞች ሣንቢቲና ከተባለው ተራራ ላይ ገጥመው አራት ቀን ከወጉት በኋላ፣ ሌላ አዲስ የጀርመን ጦር ደረሰ። በብርታት ሲከላከሉ የአንግሊዝና የአሜሪካን ጦር ስለደረሰላቸው ድሉ የአርበኞች ሆነ። በዚህ ጦርነት በሻምበል ጃሊዮ ኢታቺክና በወታደር አብዲሣ አጋ የሚመራው ቡድን ጥሩ ውጤት ማሳየቱ ታውቋል።

በዚያ የጦር ሜዳ የተሠለፈው፣ በአራት ክፍል የተመደበ ነበር። በአንደኛው ቡድን 250 አሜሪካኖች፣ በሁለተኛው ቡድን 300 እንግሊዛውያን፣ በሦስተኛው ቡድን ከ400 ያላነሱ ዩጐዝላቫውያን ነበሩበት። ሦስቱም የሚታዘዙት የየራሳቸው ዜጋ በሆኑ መኰንኖች ነበር። አራተኛው ክፍለ ጦር የልዩ ልዩ አገር ዜጐችን ያካተተ ሲሆን 380 ወታደሮች ነበሩበት።

የአሜሪካኑ ጦር የሚመራው በአንድ አሜሪካዊ የመቶ አለቃ ነበር። የእንግሊዝ ጦር ደግሞ ሻለቃ ፋይ በተባለ ሲሆን፤ የዩጐዝላቫውያኑን የሚመሩት ሻምበል ጃሊዮ ኢታቺክ ነበር። አራተኛው ቡድን ብቻ የሚመራው በራሱ ዜጋ አልነበረም። በኢትዮጵያዊው በሻለቃ አብዲሣ አጋ ነበር። ሻለቅነቱንም ያገኙት ከዚያው ከጦር ሜዳው ላይ መሆኑ ነው። ጣልያንም እነዚህን መሪዎች ይዞ ላመጣ፣ ወይም ራሳቸውን ቆርጦ ላሳየ የወርቅ ኒሻንና አንድ መቶ ሺህ ሊሬ እንደሚሸልም በሕዝብ መገናኛ አስታውቆ ነበር። በዚህ ጊዜ ማርሻል ባሉምባሪኒ የተባለ ሰው አርበኞችን ማሳደድ ያዘ። በዚሁ ሥራው ላይ እንዳለ በሻለቃ አብዲሣ አጋ ቡድን ስለተያዘ፣ ለፍርድ ቀርቦ የመጣበትን ምክንያት አንድ በአንድ ዘርዝሮ ከአስረዳ በኋላ በጥይት ተደበደበ።

አሥራ ሁለት የጣልያን ጉሪምሶች ፊታቸውን ሬንጅ ተቀብተው፤ ሌሎች 8 ደግሞ አውቶማቲክ መሣሪያ ይዘው በድምሩ 20 ሆነው አንድ ኮሚቴ ዘረፉ። ሻለቃ ድርጊቱን ሰምተው በመከታተል ሽጉጥ፣ ቀላል መትረየስ፣ የእጅ ቦምብና 7,240 ጥይት ማረኩ። ከዚህም በስተቀር 98,749 ሊሬ፣ 54 ጀንያ ምግብና 41 በቅሎዎች አገኙ። ይህም ለአርበኝነቱ ሥራ ጠቀመ፤ ወንጀለኞቹንም በሞት ቀጡ።

በዚህ ዓይነት ትንቅንቅ ውስጥ እንዳሉ ፋሽስቶች ድል ሆነ። ሮም በነፃ አውጭው ጦር ተያዘች። ሻለቃ አብዲሣ አጋ በክብር ሮም ገቡ።

አብዲሣ አጋ ማን ነበር። አብዲሣ በ1916 ዓ.ም ወለጋ፣ በነጆ ቀበሌ ተወለደ። ዕድሜው ለትምህርት በደረሰ ጊዜ ከአንድ የሚሲዮን ትምህርት ቤት ገብቶ የእንግሊዝኛ ትምህርት ጀመረ። አባቱ በእጃቸው የሰው ሕይወት ስለአለፈባቸው ወደ አዲስ አበባ ሲመጡ፣ እሱም ወደ አዲስ አበባ መጣ። ወጣቱ አብዲሳ አባቱ በፍርድ ሲገደሉ መራር ሐዘን ደረሰበት።

ከዚያ በኋላ በገነተ አዲስ ከተቋቋመው የጦር ትምህርት ቤት ገባ። በዕድሜው ገና 14 ዓመቱ ስለነበረ ለጥቂት ጊዜ ከአዛዡ ከኩሎኔል በላይ ጋር ቆይቶ፣ በቦይስካውት ክፍል ተመድቦ አማርኛ የማንበብና የመጻፍ፣ እንደዚሁም እንግሊዝኛና ሰልፍ ተማረ። ልዩ ሥልጠናው ከባድ መሣሪያ መፍታትና መግጠም ነበር። ይህንን ትምህርት እንደ አጠናቀቀ ጣልያን ኢትዮጵያን ወረረች። አብዲሣ አጋም የጥቁር አንበሳ ሠራዊት አባል ሆኖ የአርበኝነት ሥራውን ቀጠለ።[12]

ዘርዓይ ደረስና አብዲሣ አጋ ወደ ጣልያን አገር የሄዱት፣ ዘርዓይ በሹመት/በሥራ ቅጥር፣ አብዲሣ በእሥራት እንጂ በስደት አልነበረም። ታሪካቸውን በዚህ በስደተኞች ምዕራፍ ውስጥ ያስገባሁት፣ የፈፀሙት የጀብዱ ሥራ ከሹመኞችና ከእሥረኞች ይልቅ፣ ወደ ስደተኞች የተቃረበ ሆኖ ስለአገኘሁት ነው።

ሌላኛው፣ ሻለቃ በልሁ የሚባሉት ደግሞ የወሰዱት እርምጃ፣ ለየት ያለ ነው። ተሰድደው ካርቱም ገቡ። የእንግሊዝ ባለሥልጣኖች የንጉሠ ነገሥቱ የአልፍኝ አስከልካይ መሆናቸውን በማወቅ ሞምር በክብር ተቀበሉአቸው፤ ቅር የሚያሰኝ ነገር አላሳዩአቸውም። ነገር ግን ክብሩና ምቾቱ ለእሳቸው አንዳች አልነበረም። በእውናቸውም፣ በሕልማቸውም የምትታያቸው ኢትዮጵያ ሆነች። ስለዚህ ቢጋምቤላ በኩል ተመልሰው ጉሬ በመግባት ከራስ እምሩ ጋር ተቀላቀሉ። ሰምን ተመልሰው እንደመጡ ቢጠየቁ "...ሰው...መሞቱ አይቀርም። እኔም... በጸሎት ለመኖር ብችልም ...ሞት እንደማይቀርልኝ አውቃለሁ። በጠላት እጅ ብሞትም ደሜ ወደመነጨችበት አፈር ትመለሳለች። ሥጋዬንም...አሞሮች ቢካፈሉት...ተመልሰው የአገሬ አፈር ይሆኑ የለምን?" አሉ። እንደእሱትም ሕይወታቸውን ለሀገራቸው በጀግንነት ሰጡ።[13]

በጠቅላላው ስደተኞች ለኢትዮጵያ ነፃነት በቂ አስተዋጽኦ አድርገዋል። ቢሆንም አርበኛውን አይተካክልም። የአርበኛው አስተዋጽኦ ይልቃል። አርበኛው አንዳንድ ጊዜ ከመንዝ ወደ ተጉለት፣ ከዚያም ወደ

በልጋ ይዘዋወር፤ እንደዚሁም ከወሎ ወደ ጉንደር፣ ከጉንደር ወደ ጐጃም ይዘዋወር እንጂ፣ እግሩን ለቅቆ አልሄደም። ከቦታ ወደ ቦታ በመዘዋወሩም የስደተኝነት ስሜት አልተሰማውም።

እውነታው ይኽ ሆኖ ሳለ፣ የጀግኖች ማኅበር ደንብ በመቅድሙ ላይ ግን የኢትዮጵያ ጀግኖች ለጠላት አንገዛም በማለት መላ ንብረታቸውንና ቤተሰቦቻቸውን ጥለው በዱር፣ በገደል እየተሰደዱ ስለ አገራቸው እና ስለ ንጉሠ ነገሥታቸው ክብር መዋጋታቸውን ይገልጻል።[14] ይህ አባባል የአርበኛውንና የስደተኛውን ስሜት ለማስተላለፍ፣ እንዲሁም የስደተኛውን ገበና ሸፍኖ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ሞገስ መልሶ ለመገንባት ሆን ተብሎ በጥበብ የተዘጋጀ ሳይሆን አልቀረም።

ማጣቀሻ ፅሑፎች

1. ከበደ ተሰማ፣ *የታሪክ ማስታወሻ*፣ ገጽ 172-201።
2. ሀዲስ አለማየሁ፣ *ትዝታ*፣ ገጽ 100-139።
3. ሕይወት ጎደሩ፣ *ያቺ ቀን ተረሳች*፣ ገጽ 33-165።
4. ከአቶ አሸቴ ባዩ፣ የኬንያ ስደተኛ የተነገረኝ።
5. ከብርጋዴር ጀነራል ከበደ ዋጋዬ የተነገረኝ።
6. ጳውሎስ ኞኞ፣ *የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦርነት*፣ ገጽ 69።
7. አክሊሉ ሀብተወልድ ለደርግ የሰጡት ጽሑፍ።
8. ሀዲስ ዓለማየሁ፣ ገጽ 215-229።
9. Greenfield p.242.
10. New Times and Ethiopian News.
11. ይልማ ማናዬ፣ *ዘርዓይ ደረስ*፣ ገጽ 16-129።
12. መርሥዔ ኀዘን አበበ፣ *በኢጣልያ በረሃዎች*፣ ገጽ 5-62።
13. ታደሰ ሜጫ፣ *ጥቁር አንበሳ*፣ ገጽ 76-77።
14. ጥንታዊት ኢትዮጵያ አገራዊ የጀግኖች ማኅበር፣ መሠረታዊ ደንብ ገጽ 27።

ምዕራፍ ሰላሣ ዘጠኝ
የአርበኝነት ስልት

በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ንጉሥ የነገሠው፣ ክርስቶስ ሊወለድ 2 ሺህ 482 ዓ.ም ሲቀረው ነው። የንጉሡም ስም ሰብታህ ነበር። ሌሎች ግኙቶች ደግሞ ክርስቶስ ሊወለድ 2800 ሲቀረው በዓባይ ሸለቆና በቀይ ባህር የንግድ ሥራ እንደነበር ይጠቁማሉ።[1] አንድ ሥርወ መንግሥት በአንድ ሀገር ላይ የሚመሠረተው፣ ኅብረተሰቡ ለበርካታ ምዕተ ዓመታት አብሮ ኖሮ በደንብ ከተዋወቀ በኋላ ነው። እነዚህ ሁኔታዎች የሚጠቁሙት ኢትዮጵያ በመንግሥትነት ከ5 ሺህ ዓመት ያላነሰ ዘመን እንደኖረች ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በዚህ የረጅም ጊዜ ታሪክ ብዙ ውጣ ውረድ አጋጥሞታል። የዮዲትን /ጉዲትን/ ዘመን ዕልቂት ተቀብሎአል። በግራኝ መሐመድ መሣሪያነት የአቶማን፤ ማለትም፡- የቱርክ ወረራ፤ ተካሂዶበታል። ነገር ግን በ1928 ዓ.ም እንደ ደረሰበት ዓይነት ጠቅላላ ሽንፈት ደርሶበት አያውቅም። ነገሥታቱም አብረውት ቆመው፣ አብረውት ይወድቃሉ እንጂ፤ አንድም ከዛ ቀደም ጥሎት የሄደ በታሪክ አያውቅም። ስለዚሁ ሁለመናው እንግዳ ሆነበት። ራሱን እንደተመታ ሰው ዓይነት ጭውታ ደረሰበት። ብዙም ጊዜ ሳይወስድበት ነቃ።

ንጉሠ ነገሥቱ ወደ አውሮፓ የሄዱት የጦርነት ባህል የሚያውቁትን ኢትዮጵያውያንን ተራራና ጫካ ተማን አድርገው እየተከላከሉ እንዲቆዩ አዝዘው እንደሆነ በታሪክ ተመዝግቦአል። መንግሥቱ ወደ ጉሬ ተዛውሮ በአጥቻ ወልደጻድቅ መሪነት ጠላትን እንዲከላከል ተደርጉ ነበር። ጎሳም ራስ ስዩም በአንደራሴነት እንዲሠሩ ተጽፎላቸዋል። ነገር ግን በውስጥ መመሪያ እንጂ በይፋ ለሕዝብ አዋጅ አልተነገረም። ስለዚህ የሆነውን ሁሉ ኢትዮጵያዊ በራሱ ጥረት እንደ አደረገው ከመቁጠር በስተቀር ሌላ አማራጭ የለም። በኢትዮጵያ የተካሄደውን የሚመስል የአርበኝነት ሥራ ከዛ ቀደም በሌላ አገር ተካሄዶ የሚያውቅም አይመስልም። ስለዚህ ሁሉም ነገር አዲስ ነበር።

የኢትዮጵያ ጀግኖች አዲስ የጦር መላ ፈጥረው፣ አዲስ የጦር ስልት ቀይሰው፣ ሀገራቸውን ከጥፋት፣ ወገኖቻቸውን ከእልቂትና ከባርነት ለማዳን ተነሣሱ። ለታሪክ ምርምር ከሚጠቅሙት ነገሮች አንዱ እነዚህ ጀግኖች የተጠቀሙባቸውን ዘዴዎች ማጥናት ነው። እኛም ከአርበኝነት ሥልቶችና ዘዴዎች ዋና ዋናዎቹን ከዚህ እንደሚከተለው እንመለከታለን።

ሥልቱ በወቅቱ ስም እንኳን አልነበረውም። ጐጃሜ የጠዠጥዝ ጦርነት አለው። ሸዋ ሽፍትነት አለው። የደቡብ ጦር ሀገር መከላከል

አለው። እድመኛ ያሉም ነበሩ። ግን የስም ልዩነት ሳያደናግራቸው ሁሉም አንድ ዓይነት ሥራ ሠሩ። ጠላትን በመግደል፣ ለሀገር መሞት። እየዋለ እያደረ አርበኝነት ተባለ። አርበኝነት ማለት ለሀገር፣ ለወገን ሲሉ ከውጭ ጠላት ጋር መጋደል ማለት ሆነ።

የአርበኝነትን ሥራ ለማንቀሳቀስ ውሣኙ ጉዳይ በዓላማው ሕዝብ እንዲያምንበት ማድረግ ነው። ሕዝብ ያመነበት ነገር ይዋል ይደር እንጂ ውጤት ማስገኘቱ አይቀርም። ስለዚህ የአርበኝነትን ሥራ ያቋቋሙ መሪዎች፣ ሕዝብ ሁኔታውን በትክክል እንዲያውቅ ጥረት አደረጉ። በተለይ በመጀመሪያው ወቅት ከባድ ሆነ። ብዙ ከባባድ ጥያቄዎች ነበሩ።

1ኛ. ንጉሠ ነገሥቱ፣ ሠራዊቱ ያልቻሉትን እኛ ገበሬዎች እንደምን እንችለዋለን?

2ኛ. በምድር በሰማይ እሳት ለብሶ፣ እሳት ጐርሶ የመጣ ጠላት እንደምን ይቻላል?

3ኛ. ለማን ብለን እንሞታለን? /በተለይ ንጉሠ ነገሥቱን የሚቃወሙ/

4ኛ. መሸፈት ከእልቂት በስተቀር ምን ውጤት ያስገኛል?

5ኛ. ልጆቻችንና ቤተሰቦቻችንን ለማ ትተን እንሸፍት?

6ኛ. ሀገር ያለማን? የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

እኔ በነበርኩበት ቡልጋ፣ ሙገሬ ዛላ፣ ሜጢ ከተባለው ቦታ የደረሰውን ሁኔታ እንደማስረዳ አድርጌ ባቀርብ ይሻለኛል። ብዙ ቀን ጥሩንባ እየተነፋ ስብሰባ ተካሄደ። የጉበዝ አለቆች ተመረጡ። ለገበሬ ሀገር ማለት ያለበት አካባቢ ማለት እንደ መሆኑ፣ ዋናው ጉዳይ ቤትን፣ ንብረትን፣ ሀገርን መጠበቅ ሆነ። ሀገር የሚለውን ከዚህ ጠባብ ስሜት አላቅቆ ወደ ኢትዮጵ ደረጃ ከፍ ለማድረግ ችግር ሆነ። ከሜጢ ቢያልፍ፣ አካባቢው ከሚጠራበት ከሙገሬ ዛላ አላልፍም አለ። ከብዙ ምክር በኋላ ለጠላት ማመን እንዲቀር፣ የቻለ ለኢትዮጵያ እንዲከላከል፣ የማይችል አርፎ እንዲቀመጥ ስምምነት ተደረገ። በዚህም ሃሳብ አቶ ሀብተ ኢየሱስ የተባለ ሰው አልስማማም እንዳለ፣ ሰው እሳት እንዳያስጭረው፣ ከቤቱ ሰው ቢሞት ከቤተክርስቲያን እንዳይቀበር፣ ከንጉሥ መንገድ በስተቀር አሱም ከብቱም እንዳይረግጥ አድማ እነደ ተመታበት፣ እሱም የሰውን ማምረር ሲረዳ በሦስተኛው ቀን ምሕረት ጠይቆ ከሕዝብ ጋር መቆሙን ገልጫለሁ።

ሌላው ከፍተኛ ጉዳይ የመሣሪያ ጉዳይ ሆነ። በሀገሪቱ ውስጥ በቂ መሣሪያ አልነበረም። ከነበረው ጥቂት መሣሪያ አብዛኛው በልዩ ልዩ መንገድ ከጠላት እጅ ገባ። ከጠላት እጅ የገባው መሣሪያ ትክክለኛ ቁጥር

አልታወቀም። የተገኙት ማስረጃዎች ጥንቅር ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘረውን ያመለክታል።

ልዩ ልዩ ጠመንጃ.....396,779
ቀላል መትረየስ.....1,457
መድፍ.....222
ሽጉጥ.....2,428

ይህ ቁጥር በተወሰነ ጊዜ ገቢ የሆነውን እንጂ ሁሉን አያመለክትም። በጠላት እጅ ከገባው መሣሪያ በተለይ ጠመንጃ እጅግ ብዙ ነው። እኔ በበኩሌ ከ700,000 ያንሳል ብዬ አልገምትም።

በዚህ ዓይነት ባዶ እጁን የነበረው አርበኛ፣ ያለው ጠመንጃውን ይዞ ተነሳ። የሌለው ጉራዴ፣ ጩቤ፣ ጦር፣ አንካሴ፣ ዱላ ይዞ በጠላቱ ላይ ተንቀሳቀሰ። መሣሪያ ከጠላት ላይ መቀማት፣ መማረክ ትልቅ ጥበብ ሆነ። አርበኛው በተናጠልና በቡድን እየሆነ ይህን የመሣሪያ መንጠቅ ሥራ በልዩ ልዩ ዘዴ ተያያዘው። በአንድ ጠመንጃ ዙሪያ ሦስትና አራት ሆነው ይሰለፋሉ። አንዱ አነጣጥሮ የጠላት ወታደር ሲጥል ሁለት ሦስቱ ሮጠው መሣሪያውን ይገፍፋሉ። አርበኛ እንደዚህ እያደረገ መሣሪያ አከማቸ። ጠላቱን በገዛ መሣሪያው መልሶ ወጋው። ሳይጠቀምበት የቀረው በታንክና በአይሮፕላን ብቻ ነው።

- ጣልያን ከሕዝብ የነጠቃቸው መሣሪያዎች

የመሣሪያው ዓይነት	አስዲስ አበባ[2]	ሐረርጌ[3]	አንኮበር[4]	ኢትዮጵያ[5]	ድምር
ጠመንጃ	11,353	1,420	447	383,559	396,779
መትረየት	191	24	4	1,238	1,457
መድፍ	53			169	222
ሽጉጥ	169			2,259	2,428

ሌላው ጥያቄ የሥልጠና ጉዳይ ሆነ። መሣሪያውን ማርኮ እንደምን እንደሚጐርስ፣ እንደምን እንደሚተኩስ ባለማወቅ ይቸገራል። ጥቂትም ልምድ ቢኖረው አንድ ጥይት ጐርሶ በሚተኩስ እንደ ውጅግራና መስኩብ ስለመሳሰሉ መሣሪያዎች ነው። ከጣልያን የሚማረከው ምንሽርና አንዳንድ ጊዜም አልቤን ጠመንጃ ነው። እነሱ ደግሞ አጐራረሳቸው ለየብቻ ነው። አልቤን ከቀኝ ወደ ግራ ሲፈለቀቅ፣ ምንሽር ከፊት ወደ ኋላ ይሞለቀቃል።

የመትረየስ አጕራረስና አተኳኮስ ደግሞ የረቀቀ ጥበብ ይጠይቃል። ይህንን ጥበብ ያወቀ ሳላወቀ ያስጠናል።

እዚህ እስተማ የምናየው የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ለገበሬው የጦር ትምህርት መስለሙ አይታየውም። እሱ ለጌጥ ሰይስሙላ የሚደረግ ዘጥዘጥ ነው። በገበሬ ዘንድ ስሙ አርግጫ ነው። ለገበሬ የጦር ትምህርት ማለት ጥይት በትክክል በፍጥነት ማጉረስ፣ ጠመንጃ አነጣጥሮ መተኮስ ነው። ተኩሶ መሳት ውርደትም ራስንም ለአደጋ ማጋለጥ ነው። ስለዚህ ዓይኑን ያላጣራ ሰው እንዲተኩስ ከዋና ጦርነት ካልሆነ በስተቀር አይፈቀድለትም። ከዚያ ቀጥሎ ደግሞ ጠመንጃ ፈትቶ፣ ጠርጉ፣ መልሶ መግጠም ማወቅ ያስፈልጋል። ራስን ከአደጋ የመከላከልና ጠላትን የማጥቃት ሥልት ማወቅ ይጠቅማል። ስለመሣሪያ አጠቃቀም በማስረዳት ረገድ ከጣልያን እየከዱ ከአርበኞች የተቀላቀሉ የኤርትራ ልጆች ረድተዋል። ሌላውን ዘዴ ባንድነት ገብቶ አጥንቶ መመለስ ነው። ዘዴአቸው የተለያየ ነው። እንቅልፍ በወሰደው ጊዜ አንዱ እንዳይመነትፈው ሰይፉን አገጩ ሥር አገዳውን ከጭንና ጭኑ መካከል አድርጉ፣ አፈሙዙን ወደ ቂጡ ዘቅዝቆ፣ ቃታውን ደረቱ ላይ ለጥፎት ይተኛል። ከማያምነው ሰው ጋር አይተኛም። ሲሄድም ሰይፉን ከፊቱ፣ እጁን ከቃታው ላይ አድርጉ ነው። ዝናም ሲመጣ ዘቅዝቆ ያነግተዋል። ወንዝ ሲሻገር ከፍ አድርጉ ይይዘዋል። ለአንድ ቤተሰብ አንድ መሣሪያ በቂ ነው። አያያዝና አጠቃቀሙን ሴቶቹም፣ ወንዶቹም፣ ልጆቹም ጭምር ያጠኑታል።

ዋናው የጦር ሥልት የፈለጉትን ሥራ በመረጡት ጊዜና ቦታ፣ አመች በሆነ ዘዴ መሥራት፤ ሳይቻል ሲቀር መተው ነው። በመደበኛ ጦርና በአርበኝነት ሥራ መካከል ያለው ልዩነት ይህ ነው። በአርበኞች ዘንድ አያንዳንዱ ጦርነት የተለየ ዓላማ አለው። ዓላማውም ተኩስ ከመክፈቱ በፊት ተመክሮ ይወሰናል። ጦርነቱ ያንን የተወሰነውን ዓላማ መምታት በሚያስችል ዓይነት ይካሄዳል። ለባንዳ ጦር መድኃኒት አነጣጥሮ በመተኮስ አለቅየውን መግደል ነው። አለቃው ሲወድቅ ጀሌው ይበተናል። መሣሪያ ለመንጠቅ ከሆነ ቀን መሸት ሲል ከኋላ ያለውን ጥቂት ወታደር ከወገኑ ቆርጦ መጨረስ ነው። ከወጥመድ ለማስገባት ከሆነ አስቀድሞ ቦታ ከያዙ በኋላ ጥቂት ሰዎች እየተኮሱ እንዲሸሹ ማድረግ ነው። ለማጥቃት ከሆነ ምቹ ቦታ ይዞ በርትቶ መዋጋት ነው። ስንቅና ጥይት ለመቀማት ከሆነ አጋሰሶቹን፣ አሀዮቹን በጥይት መደብደብ ነው። ኃይሉን ማስጨረስ ከተፈለገ ከምሽቱ ወደ አንድ ሰዓት ላይ ዙሪያውን ክቦ ጥቂት ጥይት መተኮስ ነው። ሌሊቱን በሙሉ መድፍና መትረየሱን ሲያዥጎደጉዱው ያድራል። አንድ መንገድ ይዞ እንዲሄድ

ለማስገደድ ከመንገድ ወጣ ያለውን በጥይት መዘንጠፍ ነው። ይህ ዘዴ የቤት ቃጠሎን ለመግታትና ሰላማዊ ሰዎችን ከአልቂት ለማዳን ብዙ ጊዜ ረድቶአል።

የሠራዊቱ የልብ አንድነት ለጦርነት አስፈላጊ ነው። በአንድ የጦር ግንባር የሚሠለፉ ሰዎች እርስበርሳቸው የሚተማመኑ መሆን አለባቸው። ወንድሙን ከጦር ላይ ትቶ የሚሄድ ሰው እንደ ከሀዲ ይቆጠራል፤ አቀብሎ ሸሽ ይባላል። ዳግመኛ አብሮት የሚሰለፍ አያገኝም። ጦርነት ከመጀመሩ በፊት የተጣሉ መታረቅ አለባቸው። ካልታረቁ ከጦርነት መግባት አይገባቸውም። ወገን ወገኑን እየጣለ በመሸሹ ብዙ ጉዳት ደርሶአል። ቀኛዝማች ኃይለማርያም ማሞ ከሞት የደረሱት በዚህ ዓይነት ነው የሚል ክሳድ ሀሜት አለ።

ቦታ የመምረጥ ችሎታ ታላቅ ነገር ነው። ሕዝብ እንዳይጐዳ ጦርነት የሚደረገው በመንደር ላይ እንዳይሆን መጠንቀቅ ያስፈልጋል። ሥርጥ ይዞ መዋጋት፣ አንጥፎ ጠላት ከወጥመድ እስኪገባ መጠበቅ ጥበብ ነው። ለጠላት ምቹ ከሆነ ቦታ ላይ ለመከላከል ካልሆነ በስተቀር መዋጋቱ ከጉቱ ነው። በደኛዝማች ፍቅረ ማርያም የተመራው አርበኛ የተጠቃው ተስማሚ ቦታ ባለመምረጥ ነው። ደኛዝማቹ በማይጨውም የተሸነፍነው እንዲሁ እየተባለ ነው በማለት ምቹ ጊዜና ቦታ እንዲፈለግ የቀረበላቸውን ጥያቄ ላይቀበሉት ቀሩ።[6] የከሰምን አፋፍ ለቅቆ በጭለማ በመጓዝ ራምቡቲ ሜዳ ወጣ። ሃሳቡ በጠላት ላይ አደጋ ለመጣል ነበር። የጭለማና የጭቃው ጉዞ አዘገየው፣ አደከመው። ለጥቃት ተጋለጠ፤ አለቀ።

ለጦርነት አንዱ ዘዴ ሠራዊቱን መበተን ነው። ከመበተኛዎቹ መንገዶች አንዱ አለቅየውን መግደል ነው። ነገር ግን የጣልያን ጦር በዚህ ሥልት እምብዛም አይጠቃም። አለቅየው ሲወድቅ ምክትሉ በቦታው ተተክቶ የአዛዥነቱን ሥራ ይይዛል። ቢሆንም ጦሩ ይላላል።

የአርበኝነት ሥራ፣ ማዕከላዊ እዝ አይችልም። አስተባባሪ እንጂ አዛዥን አይቀበልም። ማዕከላዊ እዝ ድንግርግር ያበዛል። ከዚህ ይልቅ አርበኛው በቡድን በቡድን እየሆነ እንደተመቸው መዋጋትን ይመርጣል። አያድርስ እንጂ አንዱ ቡድን ቢያልቅ፣ ሌላው ቡድን ይድናል። በሌላው በኩል ደግሞ በቡድን ተከፋፍሎ መዋጋት ጠላትን ለመበተን ያግዛል። አንዱ ቢጠቃ ሌላው ያጠቃል። አርበኞችን ለድል ከአበቁአቸው ሥልቶች አንዱ ሁሉም በየፊናው መሥራቱ ነው።

ጠላትን አጠቁበት ቦታ መቀመጥ ደግ አይደለም። የተገኘውን ምርኮ ሰብስቦ ወደ ሌላ ቦታ ዘወር ማለት ነው። ያለዚያ ጠላት አጸፋዊ የማጥቃት እርምጃ ሊወስድ ይችላል። ጦርነት ብተደረገበት ቦታ ላለውም

ሕዝብ የእፎይታ ጊዜ መስጠት ያስፈልጋል። ለአርበኛው ቀሰብ ለማግኘትና እንዲያገግም ለማድረግ ይረዳል። ከድል በኋላ መጀነን አያስፈልግም። ድምጥን አጥፍቶ መቀመጥ እንጂ። መግደርደር የሚያስፈልገው በተሸነፉ እንጂ ባሸነፉ ጊዜ አይደለም። ነገር ግን ይህ ሁኔታ ከኢትዮጵያውያን ባህልና ስሜት ጋር ሥምረት የለውም። ጀብዱ የሠራ ሰው መሸለል መፎከር ይወዳል። አይጠቅመውም። ለተከታታይ ጥቃት ያጋልጠዋል።

ጠላትን ማጥቃት ከተቻለ ማጥቃት፣ ከአልተቻለ መሸሽ ነው። ማመንታት አይጠቅምም። ከመጠን ካላለፈ በስተቀር በአርበኝነት ሥራ መሸሽ ነውር አይደለም። ከበዛ ግን ግምትን ዝቅ አድርጎ፣ ጠላትን ያደነድናል፣ ወገንም ይንቃል። የሸሸ አርበኛ በሌላ ጊዜ ጀብዱ ሠርቶ ክብሩን መልሶ ማደስ ነበረበት። በአንዳንድ ደግሞ ጀብደኝነት ከጥፋት ያደርሳል። በጀብድነት አሠራር ብዙዎች አደጋ ደርሰባቸዋል። ከጉራጌ አገር አርበኞች የደጃዝማች ገበረማርያምንና የሻለቃ /ደጃዝማች/ በቀለ ወያን አቋም ማመዛዘን ለዚህ አባባል የበለጠ ማንዛቤ ይሰጣል።

የጠላት ሃሳብና ዓላማ፣ እንቅስቃሴ አስቀድሞ ማወቅ ጠቃሚ ነው። የመሪውን ባሕርይ፣ ዓላማና ዕቅድ እንዲሁም የጦሩን ብዛትና የያዘውን መሣሪያ ማወቅ ጥሩ ነው። መሪው የራሱ የሆነ ዓላማ ከአለው አደገኛ ነው። ካልወደቀ በስተቀር ያንን ግቡን ሳይመታ አይመለስምና ያንኑ በቶሎ ማስተናገድ ይበጃል። ነገር ግን የሚንቀሳቀሰው ትዕዛዝ ለመፈፀም ያህል ከሆነ ራስን ከመንገዱ ማግለል እንጂ መተናነቅ አያስፈልግም። እፊት እፊቱ ጥቂት ሰዎች እየተከሱ እንዲሸሹ ማድረግ፣ ድል አድርጌ መጣሁ ለማለት ይመቸዋል። በአንዳንዱ ደግሞ በይበልጥ ማጥቃት ይህንን መሳዩን ነው የሚሉ አሉ፤ ግን ሊያጠቁት መከላከሉ አይቀርምና፣ ብርታት ይጠይቃል።

አገርን ከመጠበቅ አኳያ መተላለፊያ በሮችን ሁሌም መቆጣጠር አስፈላጊ ነው። ኢትዮጵያ የታወቁ በሮች አሉአት። በጉንደር እንደ ሊማሊሞና ጣራ ገዳም፣ በትግሬ እንደ አምባሰጌ፣ በወሎ እንደ አላማጣና መቅደላ፣ በሸዋ እንደ ጣርማ በር፣ በሐረርጌ እንደ ካራማራ፣ በባሌ እንደ ሰብሰቤ ዋሻ የመሳሰሉ በሮች አሏት። በ1928ቱ ጦርነት በተከፈተ ጊዜ በኢትዮጵያ ጦር ላይ ብዙ ጉዳት የደረሰው እነዚህ በሮች ላይ ባለመዋጋት ነው። በኋላ አርበኛው በአካባቢው ያሉ ሽንተረሮችን በደንብ ተጠቅሞባቸዋል። የማውቀውን ለመጥቀስ ያህል፦ እንደ መገዘዝ ያሉ ተራሮች የጠላትን እንቅስቃሴ በመመልከቻነት፣ እንደ ሙገሬ ዛላ ያሉ ደኖች በመደበቂያነት፣ እንደ ከሰም ያሉ ወንዞች የጠላትን ጉዞ በመግታት፣ እንደ ፍቅሬ ግንብ ያሉት ገደሎች በመከላከያነት አገልግለዋል።

በአርበኝነት ዘመን ካየሁትና ከተረዳሁት፣ የተኩስ አከፋፈትን መቆጣጠር ጠቃሚ መሆኑን ነው። ባልተገባ ጊዜና ቦታ ተኩስ መክፈት፣ ራስን ለዋቃት ማጋለጥ ነው። በማይጨው ጦርነት፣ ውድቀት ካስከተሉት ነገሮች አንዱ የተኩስ አከፋፈቱ ትክክል ካለመሆኑ የተነሣ መሆኑን አርበኛው ዘውትር በምሬት ሲያስታውስ ኖሯል። ተኩስ በጠላት ከተከፈተ፣ የመከላከል ሥልት መከተል ይቀላል። ለማጥቃት መሞከር ውጤት ላያስገኝ ይችላል። የመረዳዳት ጉዳይ ውሣኝ ነው። እርስበርሳቸው ከማይስማሙ በአንደኛው ላይ ጥቃት በደረሰ ጊዜ ሌላው እየደረሰ ያዳነበት ጊዜ በአርበኝነት ሥራ ውስጥ ብዙ ነው።

ጠላትን የማጥቃት ዘዴ ማወቅ ጠቃሚ ነው። አንዱ የሚጠቃበት ዘዴ ሌላ ከሚያጠቃበት የተለየ ነው። እንደተኛ በመጥረቢያ አንገቱን የቀረጠፉ አሉ። ከዛፍ ላይ ተንጠልጥለው ለሚያጠቁ አሞራው /ራስ/ ውብነህ ለአበነት ሊጠቀሱ ይችላሉ። ሰላማዊ ሰው የሰለበውን የጠላታ ወታደር መልሰው ስላለበ ራያው /ደጃዝማች/ ከፈለው ተባሉ። በዱላ ደብድበው የገደሉ፣ ድንጋይ ወርውረው የፈነከቱ ብዙ ናቸው። ከጠላቱ ጋር በአንድ ጊዜ ተኩሶ ጠላቱ ሲሞት እሱ ወድቆ የዳነ አለ። ጠላቶቻቸው ነቅሎ የወረወረባቸውን የእጅ ቦምብ ቀልበው መልሶ በመወርወር የገደሉ በርካታ ናቸው። በዚህ ዓይነት እሱም፣ ጠላቱም ሰባት፣ ሰባት ጊዜ ተወራውረው፣ በስባተኛው የገደለው አርበኛ በታሪክ ተመዝግቦአል። ተአምር ነው። ነገር ግን መጤን ያለበት ቁም ነገር ውጤት የሚገኘው እያንዳንዱ በራሱ ዘዴ ሲሠራ መሆኑ ነው።

በአንዳንዱ በጎብረት መሥራት አስፈላጊ ነው። በተናጠል ብዙ ጠላትን ማጥቃት አይቻልም። ጠላት ብዙ መድፍ ነበረው። ክሩቅ እያሽጋገረ ይደበድባል። ስለዚህ አርበኞች ጠላታቸውን ለማጥቃት በቀረቤታ መዋጋት አለባቸው። በቀረቤታ ለሚደረግ ጦርነት ደግሞ ያሉት መትረየሶች በጣት የሚቆጠሩ ናቸው። ለጥይት ቁጠባ ሲባል እነሱም የሚሠራባቸው አንዳንድ ጊዜ ብቻ ነው። በሮምታ፣ በነፍስ ወከፍ መሣሪያ ተኩስ በመተኮስ፣ መትረየስ የሚሠራውን ሥራ መሥራት እንደሚቻል በብዙ የጦር ሜዳ ተረጋግጦአል።

ብዙ ጊዜ አያጋጥምም እንጂ፣ የጠላትን ወታደር አርስበርሱ ማዋጋት አስደሳች ውጤት ያስገኛል። በሁለት ወገን ከሚንቀሳቀስ የጠላት ጦር መካከል ገብቶ፣ ግራና ቀኝ እየተኮሱ መግደልና ጦርነቱ ሲጋጋም ተሸልኮ የመውጣትን ጥበብ ማወቅ ያስፈልጋል። የመሣሪያውም ዓይነት ጠላት ከያዘው የተለየ መሆን አለበት።

ከጠላት ጥበብ ራስን ማዳን ከጥበብ የበለጠ ጥበብ ነው። ከጠላት የተማረከ እህል ለውሻ መስጠትና ውጤቱ እስኪታወቅ መጠበቅ ያስፈልጋል። ጠላት የሰቀቀውን ቦታ ተሽቀዳድሞ መያዝ አደገኛ ነው። ከጠላት የተላከ ልብስም አደጋ አስከትሎአል። በእርቅ ጊዜ ለፊታውራሪ ወልደፃድቅ ዘውዴ ከጣልያን አንድ ሙሉ ገበርዲን ልብስ ተላክላቸው። ወደዱትና ለበሱት። ከጥቂት ቀን በኋላ ሁለቱም እጆቻቸው ሽባ ሆኑ። እንኪን መሣሪያ ሊጨብጡ፣ ቆርሰው መጉረስ አቃታቸው። ከሦስት ወር በኋላ ፱ሙሪ ዣላ አማኑኤል ጠበል ዳኑ። ንጉሥ መልአክ ፀሐይ ኢያሱም ከአዲስ አበባ አዲስ የክብር ልብስ ተላክላቸው። የ1931 ዓ.ምን የመስቀል በዓል አሱን ለብሰው አከበሩ። ነገር ግን መስከረም 17 ቀን ተቀበሩ።

በሽሽት ጊዜ ዱካን ማጥፋት፣ ከጠላት ክትትል ያድናል። አርበኞች በዚህ ዘዴ ተጠቅመውበታል። አንዱ ዘዴ ጥቂት ሰዎች እየተታኮሱ ጠላት ወደሚሄድበት አቅጣጫ እንዲሸሹና ዋናው ሠራዊት ወደ ጀርባ እንዲዞር ማድረግ ነው። ቦታው አሽዋማ ከሆነ፣ በኋላ ያለው ሰው ጨረቅ እንዲጐትት ማድረግም ይረዳል። ሣርና ለንበሌጥ የሆነም እንደሆነ የተኛውን እየመሰሱ ማቆም ይመረጣል። አንድ መሥመር ይዞ ከወንዝ መግባት፤ ውሃ ሰውሃ ጥቂት ሄዶ ወደ ኋላ በሌላ መንገድ መመለስም ረድቶአል። ዋናው ዘዴ ግን አብሮ አለመንዝ፣ መበተን ነው።

የአርበኝነት ሥልት በአንድ ጊዜ ጠላትን ማሸነፍ አይደለም፣ ይልቁንም ጊዜ በመውሰድና ጦርነቱን በማርዘም የጠላትን አቅም አሳጥቶና አስመርሮ ማባረር ነው። ለዚህም መሪዎቹን መግደል፣ ረዳቶቹንና ሰባቂዎቹን ማውደም፣ የጦር ሥልቱን ማዘበራረቅ፣ ሠራዊቱን በተለይም ባንዳውን መበተን፣ የሕዝብ አመኔታ ማሳጣት ያስፈልጋል። ስለዚህ ልበ ሰፊነት፣ ቆራጥነት፣ ትዕግስት ያስፈልጋል። ብዙ ሰው አልህ ይይዘውና ምንዳቤው፣ መከራው ያስመርረውና ራሱን ፈጥኖ አደጋ ላይ ይጥላል። ብዙ አርበኞች በዚህ ዓይነት ወድቀዋል። ፈተናው ብዙ ነው። ሁኔታው አስመራሪ ነው። ከወዳጅ ዘመድ ያራርቃል፤ ከሰው ይለያል። ወደ አውሬነትም ያቃርባል። ዕለት ዕለት መግደልና መሞትን በማሰላሰል ለእብደት ያዳርሳል። ረሀብ፣ ጥማት፣ እርዛት፣ የመጠለያ እጦት፣ በመዓልትና በሌሊት መንገላታት የዘወትር ጉዳዮች ናቸው። ተስፋ ሳይቆርጡ ሁሉን ችሎ መቀጠል ያስፈልጋል።

የአርበኝነት ሥራ ከተካሄደባቸው ሥራዎች ዋና ዋናዎቹ ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ናቸው። ለወደፊትም ሊጠቅሙ ስለሚችሉ ሊጤኑ ይገባቸዋል። ችግር ዳግመኛ አይደርስም ብሎ ማሰብ መታለል ነው። እነዚህ ስልቶች ያረጁ ያፈጁ ናቸው ብሎ መገመት ሞኝነት ነው። በሌላ

በኩል ደግሞ እነዚህ ሥልቶች በሁሉም ቦታ፣ ሁልጊዜ ተሠርቶባቸዋል ማለት አይደለም። ሌሎች ሥልቶች አልነበሩም ማለትም አይደለም። ከእነዚህ የተሻሉ ሌሎች ሥልቶች አይቻለው። እነዚህንና እነዚህን በመሳሰሉ ሥልቶች በመሥራት መሆኑን ለመግለጽ ያህል ነው።

በሰሜንና በምሥራቅ የተካሄዱትን የዋናዎቹን ጦርነቶች ሥልት መመልከት ደግ ነው። ኢትዮጵያውያን ለሀገራቸው ለመከላከል የበኩላቸውን፣ የተቻላቸውን ሁሉ አድርገዋል። ያልተደረገ ነገር ቢኖር ሳይቻል የቀረ ብቻ ነው። ነገር ግን የጦር ሥልትን በተመለከተ አንዳንድ ጉዳዮችን ማንሳትና መወያየት ግንዛቤን ለማዳበር ይረዳል። ወረራው ገሀድ በሆነ መንገድ የተጀመረው መስከረም 23 ነው፤ ኢትዮጵያ ድል የሆነችው መጋቢት 22 ቀን 1928 ዓ.ም ነው። እንደጨዋታ ሥርዓት ብናየው ከመስከረም 23 ቀን በፊት የነበረው እንደ እንቁርቁሶ፤ ከመጋቢት 22 ቀን በኋላ ያለው እንደ መንፈራገጥ የሚቆጠር ይሆናል።

በዋና ዋናዎቹ ጦርነቶች ላይ አንዳንድ ስህተቶች ተፈጽመዋል። በየትኛውም ሥልት ቢሠራ በጦርነቱ ኢትዮጵያ ታሸነፍ ነበር አይባልም። ነገር ግን በተሻለ ሥልት ቢሠራ ኖሮ የተሻለ ውጤት ይገኝ ነበር። የኢትዮጵያን አወዳደቅ የተፋጠነው፣ የጣልያን ኃይል ጠንካራ መሆኑ ብቻ አልነበረም። በዘዴ አለመሥራትና በሥልት አለመጠቀም ጭምር ነበር። እነዚህንም በአጭሩ ከዚህ እንደሚከተለው እንመለከታለን።

ከስሕተቶቹ አንዱ ጦር በማዕከላዊ ዕዝ ተቀፍድዶ መያዙ ነበር። ከሺህ አምስት መቶ ኪሎ ሜትር በላይ ተራርቀው ባሉ ሁለት ታላላቅ የጦር ግንባሮች አገሪቱ ተቀስፋ ሳለ፣ በዛን ጊዜ፣ ሁሉን በአንድ ዕዝ ለመምራት መሞከር ትክክል አልነበረም። ሌላው የአቤቶ ኢያሱ ሞትና መርዶ በጦርነቱ ዋዜማ መፈጸሙ፣ የተረጋጋው የሕዝብ ስሜት እንደገና በመበጥበጡ ታላቅ ጉዳት አድርሶአል። በወቅቱ ከአንድ መቶ የማይበልጡ ካሚዮኖች ለሚንቀሳቀሱባት ኢትዮጵያ፣ ከአዲስ አበባ እስከ ኮረም የመኪና መንገድ መሥራት አስፈላጊ አልነበረም። በአንድ በኩል አላስፈላጊ ወጭ አስከተለ። እንዲቆፍር የተገደደውን ሕዝብ አስመረረ። ውጤቱ፣ የጣልያንን አገባብ ማፋጠን ሆነ። ሌላው ጉልህ ስሕተት፡- አፄ ምኒልክ አስመጥተው ኮረማሽ ያስቀመጡት መሣሪያ ለጦርነቱ እንዲሠራበት አለመደረጉ ነበር። በትዕዛዝ ረገድ፡- መጋቢት 21 ቀን ሰኞ ጦርነት እንዲደረግ ታዝዞ ጦሩ ከሠልፉ ከገባ በኋላ ወደ መጋቢት 22 ቀን ማክሰኞ እንዲዛወር መደረጉ፣ ጦሩን ለሙሉ ቀን የአይሮፕላን ድብደባ አጋለጠው። ማለትም፡- ለስንቱ እልቂት ዳረገው። ንጉሠ ነገሥቱ ለእቴጌይቱ ያስተላለፉት ደብዳቤ የጦርነቱን ምሥጢር ለጠላት አሳልፎ ሰጠ። ሞልአክቱ መተላለፉ ራሱ

ትክክል አልነበረም። በዘመናዊ የጦር ሥልትም፣ በጥንታዊ ባህልም ቦታ የለውም። ከዚሁ ጋር ሊነሳ የሚገባው፣ የጦር በሮች አስቀድሞውኑ አልተጠበቁም። በሰሜን አምባላጌ፣ በምሥራቅ ካራማራ፣ በነፃ ሰጠላት ተለቀቁ።

የጦርነቱ ምክር የሚመክረውና ዕቅድ የሚነደፈው በውጭ አገር ሰዎች መሆኑ ታላቅ ድክመት ነበር። ታላቅ ጉዳትም አድርሶአል። ሌላው ለጦሩ ስንቅ አልቀረበለትም። መሣሪያውም በዋሻ እንደታጨቀ መቅረቱን ብዙዎች በምሬት ያስታውሳሉ። በጥቃቅን ሽንገላ ከጠላት ጉን በመቆም፣ ከመሣፍንቱና ከመኳንንቱ ብዙዎቹ የክህደት ሥራ አካሄዱ። በምሥራቅ ጦር ግንባር ነፋሻውን ደጋማ አገር መከላከል ሲገባ ጦሩ ዶሎና ቆራጌ ገብቶ እንዲያልቅ መደረጉ ሳይጠቀስ ሊታሰፍ አይገባውም።

ደግ ሥራ የተሠራው በደፕሎማቲክ ረገድ ነው ቢባልም፣ እሱም እንኳን አላጣውም። ችግሩን ሰዓለም ማህበር ማቅረብ፣ መክራከር፣ ዕርዳታ መጠየቅ ላይ ብቻ መመካት ተገቢ አልነበረም። ሌላው ችግር ንጉሠ ነገሥቱ ከጣልያን ጋር ያካሄዱት የነበረው የምሥጢር ንግግር ነበር። ምንም ንጉሠ ነገሥቱ የተደረገባቸውን ተዕዕኖ በመቋቋም ኢትዮጵያን ከውርደት ቢያድኑ፣ ንግግሩ መደረጉ ራሱ በታሪክ ፊት አሳፋሪ ጉዳይ እንደሆነ ይኖራል። ሌላው ጉድለት ደግሞ ጣልያን ሲባረር አርበኞች አዲስ አበባ እንዳይገቡ መታገዳቸው ነው። በጣልያኖች ላይ ጉዳት ያደርሱ ነበር ከሚለው ክንቱ ወሬ ይልቅ፣ የከተማይቱን ጸጥታ በመርዳት ጠብቀው ሊያቆዩ ይችሉ ነበር ማለቱ የበለጠ እውነትነት አለው። የሚያሻዝና ደግሞ ኢትዮጵያ ፊጥና በጦርነት የወደቀችው በእነዚህ ምክንያቶች መሆኑ ነው።

ማጣቀሻ ዕቃዎች

1. ላጲሶ ጌ. ድሌቦ፣ *የኢትዮጵያ ረጅም የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ*፣ ገጽ 21።
2. እስከ ግንቦት 7 ቀን 1928 ዓ.ም ድረስ ብቻ።
   ጳውሎስ ኞኞ፣ *የኢትዮጵያና የጂጣልያ ጦርነት*፣ ገጽ 150።
3. እስከ ነሐሴ ወር 1928 ዓ.ም ብቻ። ጳውሎስ ኞኞ፣ ገጽ 154።
4. ግንቦት 21 ቀን 1928 ዓ.ም ብቻ፣ ጳውሎስ ኞኞ፣ ገጽ 151። ከመስከረም 30 ቀን 1929 እስከ ሚያዝያ 6 ቀን 1932 ዓ.ም ድረስ።
5. Sabacchii, *Ethiopia under Mussolini*, p.180.
6. Greenfield, *Ethiopia*, p.238.

ምዕራፍ አርባ
የአርበኞች የርስበርስ ግንኙነት

የአርበኞች ዓላማ አንድ ነበር፣ ኢትዮጵያን ነፃ ማውጣት። የዚህ ዓላማ ሌላው አማራጭ ሞት፣ ቅኝ መገዛት ነው። በዚህ ጉዳይ የወላወለ ከአርበኛ አልተቆጠረም። በዚህ ዓላማ ጸንተው የዘለቁ እጅግ ብዙ ናቸው። የኢትዮጵያ መንግስት በትግል የሞቱት 78,500 እንደነበሩ ገምቶአል። ሳያንስ አልቀረም። ነገር ግን ሌላ ማሰረጃ የለምና፣ በዚሁ መጽናቱ ይሻላል።

በዚህ ዓላማ ጸንተው የአምስቱን ዓመት ተጋድሎ የፈጸሙት 20,000 ይሆን ይሆናል። ሌላው የንጉሠ ነገሥቱን መምጣት ሲረዳ፣ ቃላቸውን ሲሰማ ከጣልያን እየከዳ የገባ ነው። የራሱን ጉዳይ ያካሄደ እንጂ ለሀገር እንደሞተ ለመቁጠር ያዳግታል። ቢሆንም እስከ መጨረሻይቱ የጣልያን ሕቅታ፣ ማለትም የተመደበበት ጦር እስኪፈርስ ሽንጡን ገትሮ ወንኑን ከተዋጋው በብዙ እጅ ይሻላል።

የሞተው 78,500 ከነበረና በሕይወት ቀን የወጣው 20,000 ከሆነ ወደ 100,000 ያህል አርበኛ ተንቀሳቅሶ ነበር ማለት ነው። ይህንን ያህል ሰው በአቀፈ ሠራዊት ውስጥ አንዳንድ የሥነ ሥርዓት ጉድለት ማጋጠሙ አይቀርም። አፍ ከአጅ ይጣላል እንዲሉ፣ በአርበኞች መካከልም እንደዚሁ ሆኗል። መሰማማትና መጣላት፣ መረዳዳትና መጋጨት፣ በልዩ ልዩ መልክ፣ በልዩ ልዩ ጊዜና ቦታ ተከስተዋል።

መረዳዳቱ መልካም ነበር። አንዱ በተጠቃ ጊዜ ሌላው ገስግሶ ይደርስለታል። በዚህ ዓይነት የጦር ጓደኞቻቸውን ያዳኑ እጅግ ብዙ ናቸው። ነገር ግን አደጋው ከለሰፈ እምብዛም አይታሰብም፣ ይዘነጋል። ቢሆንም አርበኞች እርስበርሳቸው ይረዳዱ እንደነበረ፣ ከሚጋጩበት ጊዜ ይልቅ፣ የሚረዳዱበትና የሚደጋገፉበት ጊዜ ይበዛ እንደነበረ እመን ነው።

ምንም ሕይወታቸውን ለሀገራቸው ክብርና ለወገናቸው ነፃነት መሥዋዕት ለማድረግ ቢቆሙ፣ ምንም የግል ጉዳያቸውን፣ ሕልውናቸውን ጭምር ወደ ጐን ቢተው፣ አርበኞች አልፎ አልፎ እርስ በርሳቸው መጋጨታቸው አልቀረም። ሥጋ ለባስያን ስለሆኑ የሚያጋጩአቸውም ነገሮች ነበሩ። በሴት ክንፈር፣ በልጅ ነገር፣ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በመሬት ድንበር ተጋጭተዋል። የጉርስና የልብስ ጉዳይ ያጋጫል። የክብርና የሥልጣን ውድድር፣ የመሣሪያ ቅብብሎሽ ያጣላል። አንድ አርበኛ የቀድሞ አለቃውን ትቶ ከሌላው ጋር ሲሰለፍ ሁለቱን አለቆች ያቃቅራል። የክልል ጉዳይም እንዲሁ፣ ለአንዱ መጥን ከሚወጣበት ቤት፣ ሌላው የጠየቀ እንደሆነ ያቃቅራል። የክፍለ አገር ክልልም እንደዚሁ ነው። አንዱ በደሙ ያስከበረውን አካባቢ፣ አገር ሌላው ልንካ ቢል አይሆንም። ነፃረ ሠሪዎችና አሰሪዎችም

ትክክል አልነበረም። በዘመናዊ የጦር ሥልትም፣ በጥንታዊ ባህልም ቦታ የለውም። ከዚሁ ጋር ሊነሳ የሚገባው፣ የጦር በሮች አስቀድሞውኑ አልተጠበቁም። በሰሜን አምባላጌ፣ በምሥራቅ ካራማራ፣ በነፃ ለጠላት ተሰቀቁ።

የጦርነቱ ምክር የሚመክረውና ዕቅድ የሚነደፈው በውጭ አገር ሰዎች መሆኑ ታላቅ ድክመት ነበር። ታላቅ ጉዳትም አድርሶአል። ሌላው ሰጦሩ ስንቅ አልቀረበለትም። መሣሪያውም በዋሻ እንደታጨቀ መቅረቱን ብዙዎች በምሬት ያስታውሳሉ። በጥቃቅን ሽንገላ ከጠላት ጉን በመቆም፣ ከመሣፍንቱና ከመኳንንቱ ብዙዎቹ የክህደት ሥራ አካሄዱ። በምሥራቅ ጦር ግንባር ነፋሻውን ደጋማ አገር መከላከል ሲገባ ጦሩ ዶሎና ቆራጌ ገብቶ እንዲያልቅ መደረጉ ሳይጠቀስ ሊታለፍ አይገባውም።

ደግ ሥራ የተሠራው በደፕሎማቲክ ረገድ ነው ቢባልም፣ እሱም እንከን አላጣውም። ችግሩን ሰዓለም ማህበር ማቅረብ፣ መክራከር፣ ዕርዳታ መጠየቅ ላይ ብቻ መመካት ተገቢ አልነበረም። ሌላው ችግር ንጉሠ ነገሥቱ ከጣልያን ጋር ያካሂዱት የነበረው የምሥጢር ንግግር ነበር። ምንም ንጉሠ ነገሥቱ የተደረገባቸውን ተፅዕኖ በመቋቋም ኢትዮጵያን ከውርደት ቢያድኑ፣ ንግግሩ መደረጉ ራሱ በታሪክ ፊት አሳፋሪ ጉዳይ እንደሆነ ይኖራል። ሌላው ጉድለት ደግሞ ጣልያን ሲባረር አርበኞች አዲስ አበባ እንዳይገቡ መታገዳቸው ነው። በጣልያኖች ላይ ጉዳት ያደርሱ ነበር ከሚለው ከንቱ ወሬ ይልቅ፣ የከተማይቱን ጸጥታ በመርዳት ጠብቀው ሊያቆዩ ይችሉ ነበር ማለቱ የበለጠ እውነትነት አለው። የሚያሻዝና ደግሞ ኢትዮጵያ ፈጥና በጦርነት የወደቀችው በእነዚህ ምክንያቶች መሆኑ ነው።

<u>ማጣቀሻ ዕሑፎች</u>

1. ላጲሶ ጌ. ድሌበ፣ *የኢትዮጵያ ረጅም የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ*፣ ገጽ 21።
2. እስከ ግንቦት 7 ቀን 1928 ዓ.ም ድረስ ብቻ።
   ጳውሎስ ኞኞ፣ *የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦርነት*፣ ገጽ 150።
3. እስከ ነሐሴ ወር 1928 ዓ.ም ብቻ። ጳውሎስ ኞኞ፣ ገጽ 154።
4. ግንቦት 21 ቀን 1928 ዓ.ም ብቻ፣ ጳውሎስ ኞኞ፣ ገጽ 151። ከመስከረም 30 ቀን 1929 እስከ ሚያዝያ 6 ቀን 1932 ዓ.ም ድረስ።
5. Sabacchii, *Ethiopia under Mussolini*, p.180.
6. Greenfield, *Ethiopia*, p.238.

ምዕራፍ አርባ
የአርበኞች የርስበርስ ግንኙነት

የአርበኞች ዓላማ አንድ ነበር፣ ኢትዮጵያን ነፃ ማውጣት። የዚህ ዓላማ ሌላው አማራጭ ሞት፣ ቅኝ መገዛት ነው። በዚህ ጉዳይ የወላወለ ከአርበኛ አልተቆጠረም። በዚህ ዓላማ ጸንተው የነበሩ እጅግ ብዙ ናቸው። የኢትዮጵያ መንግስት በትግል የሞቱት 78,500 እንደነበሩ ገምቶአል። ሳያንስ አልቀረም። ነገር ግን ሌላ ማስረጃ የለምና፣ በዚሁ መጽናቱ ይሻላል።

በዚህ ዓላማ ጸንተው የአምስቱን ዓመት ተጋድሎ የፈጸሙት 20,000 ይሆን ይሆናል። ሌላው የንጉሠ ነገሥቱን መምጣት ሲሪዳ፣ ቃላቸውን ሲሰማ ከጣልያን እየከዳ የገባ ነው። የራሱን ጉዳይ ያካሄደ እንጂ ለሀገር እንደሞተ ለመቁጠር ያዳግታል። ቢሆንም እስከ መጨረሻይቱ የጣልያን ሕቅታ፣ ማለትም የተመደበበት ጦር እስኪፈርስ ሽንጡን ገትሮ ወገኑን ከተዋጋው በብዙ እጅ ይሻላል።

የሞተው 78,500 ከነበረና በሕይወት ቀን የወጣው 20,000 ከሆነ ወደ 100,000 ያህል አርበኛ ተንቀሳቅሶ ነበር ማለት ነው። ይህንን ያህል ሰው በአቀፈ ሠራዊት ውስጥ አንዳንድ የሥነ ሥርዓት ጉድለት ማጋጠሙ አይቀርም። አፍ ከእጅ ይጣላል እንዲሉ፣ በአርበኞች መካከልም እንደዚሁ ሆኗል። መስማማትና መጣላት፣ መረዳዳትና መጋጨት፣ በልዩ ልዩ መልክ፣ በልዩ ልዩ ጊዜና ቦታ ተከስተዋል።

መረዳዳቱ መልካም ነበር። አንዱ በተጠቃ ጊዜ ሌላው ዝምታ ይደርስለታል። በዚህ ዓይነት የጦር ጓደኞቻቸውን ያዳኑ እጅግ ብዙ ናቸው። ነገር ግን አደጋው ከአለፈ እምብዛም አይታሰብም፣ ይዘነጋል። ቢሆንም አርበኞች እርስበርሳቸው ይረዳዱ እንደነበረ፣ ከሚጋጩበት ጊዜ ይልቅ፣ የሚረዳዱበትና የሚደጋገፉበት ጊዜ ይበዛ እንደነበረ እሙን ነው።

ምንም ሕይወታቸውን ለሀገራቸው ክብርና ለወገናቸው ነፃነት መሥዋዕት ለማድረግ ቢቆሙ፣ ምንም የግል ጉዳያቸውን፣ ሕልውናቸውን ጭምር ወደ ጉን ቢተው፣ አርበኞች አልፎ አልፎ እርስ በርሳቸው መጋጨታቸው አልቀረም። ሥጋ ለባሽን ስለሆኑ የሚያጋጩአቸውም ነገሮች ነበሩ። በሴት ከንፈር፣ በልጅ ነገር፣ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በመሬት ድንበር ተጋጭተዋል። የጉርስና የልብስ ጉዳይ ያጋጫል። የክብርና የሥልጣን ውድድር፣ የመሣሪያ ቅብብሎሽ ያጣላል። አንድ አርበኛ የቀድሞ አለቃውን ትቶ ከሌላው ጋር ሲሰለፍ፣ ሁለቱን አለቆች ያቃቅራል። የክልል ጉዳይም እንዲሁ፣ ለአንዱ መጥን ከሚወጣበት ቤት፣ ሌላው የጠየቀ እንደሆነ ያቃቅራል። የክፍለ አገር ክልልም እንደዚሁ ነው። አንዱ በደሙ ያስከበረውን አካባቢ፣ አገር ሌላው ልንካ ቢል አይሆንም። ነገረ ሠሪዎችና አሰሪዎችም

አልጠፉም። ስለዚህ ብዙ ዓይነት ግጭቶች ታይተዋል። ለትምህርት ያህል አንዳንዱን እንጠቅሳለን። ሁሉን መዘርዘር አይቻልምና።

በልጅ ወሰን ኃይሉና በደጃዝማች ነጋሽ ወርቅነህ መካከል ለጥቂት ጊዜ መተባበር ታየ። ሁለቱ የጦር አለቆች መሸሐ በተባለው ወንዝ ላይ ተገናኝተው ለመረዳዳት በተስማሙ ጊዜ በሠራዊቱ ዘንድ ታላቅ ደስታ ሆነ። ሕዝቡም ለሀገሩ ለመሞት ቁርጠኝነቱን በመሐል አረጋገጠ። ነገር ግን ምንም ያህል ሳይቆይ የሁለቱ የጦር አለቆች ግንኙነት እየሻከረ ሄደ። ልጅ ወሰን ለደጃዝማች ነጋሽ ጥር 8 ቀን 1932 ዓ.ም አንድ ደብዳቤ ጻፉ። ደብዳቤውም "...በየዳ መጥቼ ልቀመጥ ነኝ። ሣቢ ላይ ቤት አሠርተው፣ የፍጋይን አበል አስገብተው እንዲቆዩኝ። የቆላውም የብረት አሰቱነት በፊታውራሪ ካሣ ነአኩቶ ሆኖ እየታዘዙ እንዲቆየኝ ይሁን" የሚል ነበር።

ደጃዝማች ነጋሽ በዚህ ቅር ተሰኙ። ጥር 12 ቀን 1932 ዓ.ም በጻፉት የመልስ ደብዳቤ "...ቤቴን እንዲያሠሩልኝ ሲሉ የጻፉትን አልተቀበልኩትም። ምክንያቱም ...እየተረዳዳን ጠላትን ልንወጋ የተማማልነው መሐላ ቀርቶ አሁን አዲስ ነገር በመፈጠሩ ነው..." አሉ። ስሙ ታውቆ፣ ክብሩ ተጠብቆ የኖረውን ስሜንን ለዋግ ማስገዛት ስለሚሆን እንደማይደረግ ገለጹ። ጠቡ የሰዎች ብቻ ሳይሆን አገርንም ቀላቀለ። ልጅ ወሰን ደጃዝማች ነጋሽን ለመውጋት ተንቀሳቀሱ። ጥር 12 ቀን 1932 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ ፊታውራሪ አስፋው ኃይለማርያም የተባለውን የባንዶች አለቃ ትብብር ጠየቁ። ደጃዝማች ነጋሽን እንደርሳቸው ያለውን ባለበት አገር ሳይ እንደሚቆሙ ቃል ገቡላቸው። ፊታውራሪ አስፋው የተጻፈለትን ደብዳቤ ለጌታው ለጣልያን ሰጠ። ጣልያን ምሥጢሩን ለደጃዝማች ነጋሽ ገለጸ። ጥር 17 ቀን 1932 ዓ.ም በ6 ሰዓት በሁለቱ አርበኞች መካከል ጦርነት ተከፈተ። እስከ ምሽቱ 3 ሰዓት ቆየ። ከሁለቱም ወገን ብዙ ሰው አለቀ። ልጅ ወሰን ተሸነፉ።[1] የደጃዝማች ነጋሽ አመለካከት በሀገር ነፃነት፣ የልጅ ወሰን አስተያየት በግል ሥልጣንና ክብር ላይ ያተኮረ ነበር። ያሳዝናል።

በዚያው በጎንደር በአቶ ሕይወት ጎደሩና በደጃዝማች ብሬ የተነሣው ቁርሾ፣ አቶ ሕይወትን እስከ መታሠር፣ መሣሪያ እስከ መገፈፍና እስከ መንገላታታትም አደረሳቸው። ችግሩ የተፈጠረው በነባሩና በዘመናዊው የጦር ሥልት ላይ በተመሠረተ የአመለካከት ልዩነት ነበር። ደንበኛው የኢትዮጵያ የጦር ሥልት ምሥጢርን ሳይንቁ መደበቅ ሲሆን፣ ዘመናዊው ዘዴ ለዓለም ጎብረተሰብ መግለጽ ነው። አቶ ሕይወት ፎቶግራፍ ማንሳት፣ ማስታወሻ መጻፍ ያዙ። ይህ አሠራር ከእንግሊዝ ቁንሲል ሠራተኞንታቸው ጋር ተያይዞ ሰላይ አሰኛቸው። በዚያን ሰዓት ማለትም ከመስከረም እስከ ሰኔ 3 ቀን 1932 ዓ.ም ድረስ እንግሊዝ ከጣልያን ጋር ያላትን የጥቅም ትስስር እያጠናከረች ስለነበረ ይህ ጉዳይ ቀላል አልነበረም።[2] አርበኛውን አስገነጠሉ።

አለመግባባት ትክክለኛነት ያለው ነበር። በግኙቱ ደም አልፈሰሰም፤ ሕይወት አልጠፋም።

በዚያው በጎንደር በደጃዝማች ዮሐንስ ኢያሱና በአሞራው /ራስ/ ውብነህ መካከል በነሐሴ ወር 1931 ዓ.ም አለመግባባት ተፈጥሮ ነበር። ነገር ግን ክፉ ውጤት እስከሚያስከትልበት ደረጃ አልደረሰም።[3] ከክፉ ያልተደረሰው ደግሞ በደጃዝማች ዮሐንስ ትዕግስት ነው ሊባል ይቻላል። ይህኛው ግጭት ደግሞ በፖለቲካ የተነሳ እንደሆነ በታሪክ ተመዝግቦአል። በንጉሥ ጥያቄ ላይ ይሆን?

በጐጃም አርበኞች መካከል የነበረው አለመግባባት ቀላል አልነበረም። አዛዥ /ደጃዝማች/ ከበደ ተሰማን "...አርበኞችም አንድ ነገር ይጐድሳቸዋል። ይኸውም ስምምነትና ፍቅር ነው..." ብለው ለንጉሠ ነገሥቱ ሪፖርት እስከ መስጠት አስመርሮአቸው ነበር። በልጅ /ራስ/ ኃይሉ በለውና /በደጃዝማች/ በላይ ዘለቀ መካከል የነበረው ጠብ ከባድ ነበር። ጠቡ የተነሣው በአገር አገዛዝ ሽሚያ ነበር። እስከ መሣሪያ ግጭት አድርሶአል። ጠቡን ያበረደው የንጉሠ ነገሥቱ መልእክተኛ በነገሩ ስለገቡበት ነው፤ ያውም አንድ ጊዜ ውጊያ ተካሂዶ ብዙ ሰው ከአለቀና ሲሌላ ለሁለተኛ ዙር ከተሰላሰሉ በኋላ።

በቢትወደድ ነጋሽ በዛብህና በደጃዝማች መንገሻ ጀምበሬ መካከልም እንደዛው ያለ ጠብ ተቀስቅሶ ነበር። እነሱም አንድ ጊዜ ከተዋጉ በኋላ በጎንደር ወር 1933 ዓ.ም የታረቁት፤ በአዛዥ /ደጃዝማች/ ከበደ ተሰማ በኩል የንጉሠ ነገሥቱ ቃል ስለደረሳቸው ነበር። የታረቁትም "...ስለኢትዮጵያና ስለንጉሠ ነገሥቱ ስንል ጠባችን ቀርታል" በማለት ሆነ። ጠቡ የተቀሰቀሰው በአገር ግዛትና ከአንዱ እየከዱ ሰሌላው በሚያብሩ ጭፍሮች ምክንያት ነበር። በደጃዝማች መንገሻ አቦዬና በልጅ አበራ ይማም መካከልም ተመሳሳይ ሁኔታ ታይቶአል።[4] በደጃዝማች ነጋሽና በወይዘሮ ሰብለ ወንጌል መካከልም ቅያሜ ለመፍጠር ነገረ ሠሪዎች ወዲያ ወዲህ ማለታቸው አልቀረም ነበር።[5]

በሸዋ አርበኞች መካከል የነበረው የሃሳብ ልዩነት ደግሞ ይበልጥ የከረረ ነበር። ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው፣ ንጉሠ ነገሥት መልአክ ፀሐይ በሚያዝያ ወር 1930 ዓ.ም ታላቅ ሹመት ሰጡ። ይህ ሹመት በአርበኞቹ መካከል የቀሰቀሰው ጠብ ሳይበርድ እስከ ጦርነቱ ፍፃሜ ድረስ ቆየ። ብዙ ጉዳትም አደረሰ። ቀኝዝማች ኃይለማርያም ማሞ የተሰጣቸውን የደጃዝማችነት ማዕረግ ሳይቀበሉ ሞቱ። ሹመቱን ከተቀበሉት መካከልም፣ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴን መንቀሳቀስ እንደሰሙ ሹመታቸውን ትተው በቀድሞ ማዕረጋቸው መጠራትን የመረጡ አሉ። ለምሣሌ ደጃዝማች ዘውዱ አበኩራን ፊታውራሪ እያሉ ጽፈዋል። በአንጻሩ ደግሞ ፊታውራሪ ወልደፃድቅ ዘውዴ ደጃዝማች ባለመሰኘታቸው ብዙዎችን ያስገነገነ ቅሬታ አሳይተዋል። ቢሆንም ይህ ሁኔታ የርስበርስ መቃቃር እንጂ፣ የርስበርስ ሚናቆር አላስከተለም።

በሌላ በኩል በፊታውራሪ ገዛኸ አርጋቸውና በፊታውራሪ ምገሴ መኩሪያ መካከል ደንገተኛ ጠብ ተቀስቅሶ ፊታውራሪ ገዛኸ ተገደሉ። በጥቂት ቀናት ውስጥ ደግሞ ፊታውራሪ ምገሴ ተገደሉ። የጠቡ ምክንያት በቤትም፣ በመሣሪያ ንጥቂያም ነው ይባላል። ከመሞታቸው በስተቀር ግን በግልጽ የታወቀ ነገር የለም። ሁለቱ ወጣት የጦር መሪዎች በከንቱ መውደቃቸው እጅግ ያሳዝናል።

በዚህ ክላይ በተገለፀው ሹመት ጠንቅነት ፊታውራሪ ወልደፃድቅ ዘውዴ የተወለዱበትና አርበኝነት ያቋቋሙበት አገር ሜጢ፣ ሰፊታውራሪ ደባልቄ ተክሌ ተሰጠ። የፊታውራሪ ደባልቄ አስተዳደር አላስፈላጊ ተፅዕኖ አስከተለ። የቆሰለ እንጂ የሞተ ባይኖርም፣ ውሎ አድሮ ግን ሁለቱን ፊታውራሪዎች አዋጋ። በኋላ ያስከተለው ክስና ክርክር ደግሞ ሌላ ጠብ ለማስነሳት ምንም አልቀረውም። በራስ አበበ የአስተዳደር ችሎታ ቀዝቀዘ።

ይህ መዘዘኛ ሹመት ታላቁን ማዕረግ ሳገኙት ለራስ አበበ አረጋይም አልተመቻቸውም። እሳቸው የተሰጣቸውን የራስነት ማዕረግ ሲቀበሉ፣ ቀኛዝማች ኃይለ ማርያም ማሞ አልቀበልም ማለታቸው፣ በመልአከ ፀሐይና በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ደጋፊዎች መካከል ውስጥ ውስጡን ይካሄድ የነበረውን ትግል ወደ ገሐድነት አቃረበው። አንዱ ያገኘሁትን ሹመት አለቅም ሲል፣ በአንዛሩ ደግሞ ሌላው ከነጭራሹም አልቀበልም ማለቱ። ሌላው ደግሞ መጀመሪያ ተቀብሎ ቆይቶ መልቀቁ፣ ሌላው ደግሞ ሹመት ላያገኝ በመቅረቱ ቅሬታ ማሳየቱ የጉዳዩን ፍንጭ አመላከተ። ይህ ሁሉ በሠራዊቱ አመለካከት ላይ የፈጠረውን ምስቅልቅል፣ በአጭር ጽሑፍ ለመግለጽ ያዳግታል። በዚህ ላይ የወጣቱ ንጉሥ የመልአከ ፀሐይ ኢያሱ ሞት ሲጨመር ከናካቴው ዝብርቅርቁ ወጣ።

የሞግዚትነት ሥራቸው በወጣቱ ንጉሥ ሞት ሲያከትም፣ በደጃዝማች ኃይሉ ወልደመድኅን የሚመራው አርበኛ ከሠራዊቱ ጋር፣ በተለይም ከጦር አለቆቹ ጋር መጣጣም አቃተው። ይህ ሠራዊት ከቡልጋ ወጥቶ ወደ ጉራጌ አገር ለመዞር ተንቀሳቀሰ። ሃሳቡ ቢቻል በጉራጌ አገር ከአሉ አርበኞች ጋር ተቀላቅሎ ሥራውን ለመቀጠል፣ ይህ ባይቻል ወደ ኬንያ ለመጓዝ ሳይሆን አልቀረም። ነገር ግን ከአንዱም አልደረሰም። የጀሬ ሲደርስ መሪ የነበረው ሰው ከአንድ ከተቃጠለ ግንብ ቤት ከጉቶት ዙሪያገቡን ቃኝቼ ልምጣ በሚል ምክንያት ወጣ። ቀን መሽቶ ነበርና አርበኛው መንቀሳቀስ አልቻለም። ቀን ሙሉ ሲጓዝ ስለዋለ ድካም ተጫጫነው። ሌሊቱን በጠላት ተከበበ። የተቻለውን ያህል ተከላከለ፣ ነገር ግን ሰብሮ መውጣት አልቻለም። ሰኔ 15 ቀን 1931 ዓ.ም አለቀ። አንድ ንጋቱ ወልደዮሐንስ ከሚባል ልጅ በስተቀር ምንም ሰው አልተረፈም። ከግንቡ ውስጥ የተረፈረፈውን የሰባ ስምንት ሰው ሬሣ የአካባቢው ገበሬ በማግሥቱ አንስቶ ቀበረ። [6]

ንጉሥ መልአከ ፀሐይ ኢያሱ እንደሞቱ ሠራዊቱ አገነገነ። ደጃዝማች መንገሻና ልጅ /ፊታውራሪ/ ገብረክርስቶስ መኩንን ለጥያቄ ከራስ አበበ ዘንድ እንዲቀርቡ ተጠየቁ። ፊታደኞች ባለመሆናቸው ተኩስ ተከፍቶ ሦስት አርበኞች ሞቱ። እነሱም ደብረ ብርሃን ገብተው እጃቸውን ሰጡ። ጣልያንም በየርስታቸው እንዲቀመጡ ፈቀደላቸው። በተለይ ከእነዚህ ሰዎች ባገኘው እርግጠኛ ምሥጢር ጄነራል ናዚ መሰቢት ሮርች ለተቀጠረው የእርቅ ንግግር ሳይቀርብ ቀረ፤ እሱን ጠልፎ ለመውሰድ ታስቦ የነበረው ሃሳብ በዛው ከሸፈ።

በነሐሴ ወር 1931 ዓ.ም መካኒሣ፣ ዳሮት አገር በተባለው ቦታ፣ በቀኛዝማች ኃይለማርያም ማሞና በባላምባራስ /በፊታውራሪ/ ተሻገር ሰዎች መካከል ተኩስ ተከፍቶ ሰባት ሰዎች ሞቱ። የቀኛዝማች ኃይለማርያም ሰዎች ሀገሩን ለቀው ወደ ግንደበረት አካባቢ ሸሩ።

በልጅ /ደጃዝማች/ ብዙነሽና በልጅ ገርቢ መካከል የተነሣው ጠብ ለብዙ ጊዜ ሲያስቸግር ቆይቶ ነበር። ችግሩ ሊቃለል የቻለው በእነ ባላምባራስ /በራስ/ አበበና በፊታውራሪ ተሻገር ብርታት ነው።[7]

ከሁሉም የሚያሳዝነው በአንድ በሬ የሸንጥ ሥጋ ዘጠኝ አርበኞች ታህሣሥ 10 ቀን 1933 ዓ.ም በረስት፣ ወዳዲማ ማለቃቸው ነው። ጥንቱኑ ቁርሾ ሳይኖርበት አልቀረም። የዕለቱ ጠብ የተነሣው እንደዚህ ነው። አርበኞች የአንድ ሌላ አርበኛ በሬ ለማረድ ይይዛሉ። ባለበሬው ይቃወማል። የሠራዊቱን መራብ ከአስረዱት በኋላ ለእሱም አንድ ሸንጥ ሥጋ ሊሰጡት ተስማምተው በሬው ታረደ። ሸንጡን ሥጋ ለባለቤቱ ሳይሰጡ መልሟ እድርገው ስለበሉት ጠብ ተነሣ። ትኩስ ሥጋ በልተው እንደተንፈረዘዙ አቶ ዝናዬ የተባለው የበሬው ባለቤት በመውዜር ጠመንጃ ዘጠኙን ረፈረፋቸው። ፊርቶ ባይተዋቸው ሌሎቹንም ሊጨርሳቸው ይችል ነበር። እንዳቸውም አልተንፈራገጡም። ከሞቱት ውስጥ ፊታውራሪ አንሳናፍር ባዩ፣ ፊታውራሪ ተክለ ሃይማኖትና ባሻ ባዩ ነበሩበት። አቶ ዝናየም ወደ ጣልያን ሳይገባ፣ የሸፍታ ሸፍታ ሆኖ፣ ከሚስትና ከልጅ ጋር አርበኝነቱን ቀጠሉ። ሰው አልፈረደበትም። የጨረሳቸው ደም የሚያፈላ ቃል ስለተናገሩት ነበር።[8]

ሌላው አሳዛኝ ነገር በአንድ እንጀራ ምክንያት በተነሣ ጠብ አንድ ልጃገረድ ገድሎ አቶ ላውጋው የተባለውን ገበሬ ስለአቆሰለ በገበሬዎቹ የተገደለው አርበኛ ነው። ይህ የተደረገው ደግሞ መገራ ዛላ፣ ሜጢ ከአለቃ ገብረ መሢህ ቤት ነው። ጠቡን የቀሰቀሱት እመት እግዚአ ሲረያ የሞተችው ልጅ አያት ናቸው።

አንዳንዱ በዚህ ዓይነት ተብጣብጦ የሸዋ አርበኛ አንዱ ከሌላው ላይገናኝ እየቀረ፣ በየፊናው ትግሉን የቀጠለበት አጋጣሚ አለ። እንደዛ በሆነ ጊዜ ካህናትና የሀገር ሽማግሌዎች በብርታት የሸምግሌና ሥራ ባያካሂዱ ኖሮ፣ በየጊዜው በየቦታው በተነሣው ጠብ ብዙ ሰው ያልቅ ነበር። ምናልባትም አርበኛው ከአነጭራሹ ተፈትቶ ፈድል ሳይበቃ ይቀር ነበር። በሸምግልና

የቀዘቀዘውን ጠብና ሊያደርስ ይችል የነበረውን ጉዳት አሁን ለመዘርዘር አይቻልም። በሌላ በኩል አርበኛውን እርስበርሱ ማበጣበጥን ሥራ አድርገው የያዙ ነበሩ። ደስ የሚለው ግን፣ አርበኛው ይህንን የመሳሰለውን ችግር ሁሉ ችሎ ለሀገሩ ነፃነትና ለወገኑ ክብር እስከ መጨረሻው መጋደሉ ነው።

ማጣቀሻ ፅሑፎች

1. ገሪማ ታፈረ፣ *ጦንደሬ ቢጋሻው*፣ ገጽ 158-159።
2. ሕይወት ጎደሩ፣ *ያቺ ቀን ተረሣች*፣ ገጽ 233።
3. ገሪማ ታፈረ፣ ገጽ 144።
4. ከበደ ተሰማ፣ *የታሪክ ማስታወሻ*፣ ገጽ 262፣ 272፣ 283 እና 296።
5. ሙሉ ሰው ምትኩ፣ *የአርበኝነት ትግል ከፋሽስት ጋር*፣ ገጽ 43።
6. ከአቶ ንጋቱ ወልደ ዮሐንስ ዘውዴህ የተነገረኝ።
7. ታደሰ ዘወልዴ፣ *ቀሪን ገረመው*፣ ገጽ 425-426።
8. ከአቶ /ሻለቃ/ አሰፋ ወልደፃድቅ የተነገረኝ።

ምዕራፍ አርባ አንድ

በአርበኞች ዘንድ የነበረ የፍርድ ሥራ

ብዙ ሰው አርበኝነት የውንብድና የቅሚያ ሥራ ይመስለዋል። እንደዚህ አስመስሎው ለማሳየት የሞከሩም በርካታ ናቸው። በወቅቱ ሠፊ ልማን አግኝተው ነበር። ነገር ግን ይህ አመለካከት ትክክል አይደለም። በአርበኝነት ጊዜ ሕግና ፍትሕ ነበር። ለአብነት ያህል ከተፈጸሙት የፍርድ ሥራዎች ጥቂቶቹን እንገልጻለን።

ሚያዝያ 12 ቀን 1929 ዓ.ም ሰላሌ፣ ጉርጉርቱ በተደረገ ጦርነት 40 ባንዶች ተማረኩ። ለፍርድ በአርበኛው አደባባይ ቀመጡ። ሀገራቸውን ኢትዮጵያን ከድተው ከወራሪው ከጣልያን ጦር ጐን የተዋጉ ከሀዲያን ስለሆኑ ሊቀጡ ይገባል የሚል ክስ ቀረበባቸው። እያንዳንዱ የፈፀመው ታወቀ። ሁለት ቀን የፈጀ ፍርድ ተሰጠ። ሃያ ሦስቱ በብርታት ለጠላት የተዋጉና ቀደም ብሎም አርበኞችን የገደሉ ስለሆኑ በሞት ተቀጡ። አሥራ ሰባቱ ከጠላት ጐን ከመቆም በስተቀር ሌላ በደል ስለአልፈፀሙ መሣሪያ ሰጥቷት ቀን በመሸከም ተቀጥተው በአመክሮ ተሰቀቁ።[1]

ባሻ ጠውቱ የተባሉ አርበኛ አንድ ባንዳ ማረኩ። ተማራኪው በጎዳር ወር 1930 ዓ.ም ቡልጋ መገዘዝ፣ ጫሬ ከአርበኞች ችሎት ቀረበ። ክጠላት ወገን ሆኖ እናት ሀገሩን መውጋቱ በማሰረጃ ተረጋገጠበት። ማስረጃውም ከኪሱ የተገኘ እሱ ራሱ የጻፈው ማስታወሻ ሆነ። አገልግሎቱን ለጌታው ለጣልያን በማቅረብ ሊሸም ሊሸለምበት ያዘጋጀው ነበር። በጽሑፉ ላይ አቃጠልኩኣቸው የሚላቸው የ158 አብያተ ክርስቲያናት ስም ዝርዝር ተገኘ። ቁጥሩን ሳያጋንነው አልቀረም። ሆኖም ማቃጠሉ ማቃጠል ነበር። ተፈረደበት በሞት ተቀጣ።[2]

ደጃዝማች መሸሻ ተወንድ በላይ ተይዘው ጥር 23 ቀን 1929 ዓ.ም ለፍርድ ከአርበኞች አደባባይ ቀረቡ። የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ከፍተኛ ባለሥልጣን ሆነው ሣለ ክጠላት መቆማቸው ክሀደት መሆኑ ተነገረባቸው። በወቅቱ ብዙ ሰው ለጠላት የገባ በመሆኑ መማባታቸው የማያስቀጣቸው ሆነ። ቢጠየቁ ምላሽ ሳይሰጡ ቀረ። አንዳንድ መልስ ቢሰጡም ሠራዊቱን የሚያበሳጭና ፍርድ የሚያጣምም ሆነ። ሽምግልናቸውን ክግምት አግብቶ አርበኛው ንግግራቸውን ሳይዘከርባቸው ቀረ። ሆኖም ተቃዋሚ ስለበዛባቸው ሥራቸው ተመረመረ። ለሀገሩ የሚጋደለውን አርበኛ ጣልያንን ደስ ለማሰኘት ጅሩ ገበያ ላይ አስቅለሃል የሚል ማስረጃ ቀረበባቸው። ስንት ሰው እንደ አሰቀሉ ቁጥሩ በትክክል አልታወቀም። እስከ ዘጠኝ የሚያደርሱትም አሉ። ነገር ግን በተለያየ ቀን አርበኛ በገበያ ላይ ማሰቀላቸው ተረጋገጠባቸው። ይህም ሆኖ አርበኛው በሸማግሌው ላይ የሞት ፍርድ አልፈረደባቸውም። ነገሩ ሳይቆረጥ ታላቅ የጣልያን ጦር መጣ። ድብልቅልቅ ያለ ጦርነት ተደርጐ ጣልያን ተሸንፎ ሸሸ። ብዙ አርበኞች ሞቱ፤ ብዙዎች ቀሰሉ። ጣልያንን

መርቶ ያመጣው የደጃዝማች መሸሻ ተወንድ በላይ ልጅ መሆኑና የመጣውም አሳቸውን ለማስለቀቅ እንደነበረ ታወቀ። አርበኛው ትዕግሥቱ አሰቀ። በሕይወት ይኑሩ የሚል አንድ ሰው ጠፋ። በጉራዴ በጣጥሶ ጣላቸው።[3] በትዕግሥት የተያዘው የፍርድ ሥራ በደም ፍላት መፈጸሙ ያሳዝናል። ቢሆንም አርበኛው ትክክለኛ ፍርድ ለመስጠት ያደረገውን ጥረት ማጤን ይገባል።

ንጉሠ ነገሥት መልአከ ፀሐይ ኢያሱ ከትም ወይራ፣ አኩፍ አገር አቶ ቸሬ ቤት በነበሩ ጊዜ፣ አምስት አርበኞች ተከሰው ከችሎት ነሐሴ 23 ቀን 1930 ዓ.ም ቀረቡ። ክሱም ብር አምጡ እያሉ ሁለት ገበሬዎች በእሳት ጠብሰዋል የሚል ነበር። ሁለቱ መጥበሳቸው፣ አንዱ ዝም ብሎ ቆሞ ማየቱ፣ ቀሪዎች ሁለቱ ጠበሳው ይካሄድበት የነበረውን ቤት ለቀው መውጣታቸው በምስክር ተረጋገጠ። ፍትሐ ነገሥት በመምህር ቀጸላ እጅ ወጣ። ሕግና ማስረጃ ከተሰማ በኋላ የአርበኞች መሪዎች አንድ በአንድ እየተነሱ ተቹ። ቆሞ የተመለከተው አርባ ጅራፍ ተገረፈ። ሁለቱ ቤቱን ጥለው የወጡት በነፃ ተሰቀቁ።[4]

ጣልያን የእናቴን የወይዘሮ ፀዳለ አባበለውን አያት የአቶ ተክሌ ቢረሴን፣ ዳዊት አገር የተባለውን መልከኽነት ታደሰ ሰተባለ ባንዳው ስጠው። ጣልያን ይህንን ያደረገው እኔ ለአለቃ /ፊታውራሪ/ ወልደዓድት ዘውዴ ስንት አቀባይ መሆኔን በሰላዮቹ አማካኝነት አጣርቶ አምጡ ብሎ ቢጠይቅ፣ ሽማግለዉ ቅድም አያቴ አልስጥም በማለታቸው ነበር። መልከኽነቱ በአዋጅ ለባንዳው የተዛወረ ስለሆነ ለእኔ በአዋጅ እንዲመለስ አስፈለገ።

ጉዳዩ ለንጉሠ ነገሥት መልአከ ፀሐይ ጭንቅት አቶ ተክለወልድ ቤት በነበሩ ጊዜ በጥር 5 ቀን 1930 ዓ.ም ቀረበ። ቀኛዝማች /ደጃዝማች/ ከበረ ኃይለሥላሴ በመቃወማቸው ክርክር ተነሣ። የቀኛዝማች ከበረ ሃሳብ "ከዚህ ያለነው ለሀገራችን ነፃነት ለመከላከል እንጂ መሬት ለመከፋፈል አይደለም። መሬት መከፋፈል ከተጀመረ ማብቂያ አይኖረውም። ሠራዊቱን ከጥቅም ክፍፍሎሽ ውስጥ ያስገባል" አለ። "የመሬት ክፍፍሎሽ ይጀመር ቢባልም እንኳን፣ እንዴት በዚህ አንድ ፍሬ ሕፃን ይጀመራል?" ብለው ጠየቁ። የእኔ ቤተሰቦች ደግሞ "ጥያቄው የመሬት ክፍፍሎሽ አይደለም። ጣልያን የነቀለው ይመለስለት የሚል እንጂ" አሉ። የደጃዝማች ኃይሉ ወልደመድኅን ሃሳብ ከቀኛዝማች ከበረ የተለየ ሆኑ። "ከሁላችን ነጥሎ መሬቱን ከነቀለው፣ ስለዚህ ልጅ አገልግሎት ጣልያን ያወቀው ነገር አለ ማለት ነው። ሕፃን ነው ተብሎ እንደተነቀለ ይቅር አይገባም። ይመለስለት" አሉ። ክርክሩ ጠነከ። ንጉሠ መልአከ ፀሐይ አኩፍ አገር አቶ ቸሬ ቤት በነበሩ ጊዜ ነሐሴ 24 ቀን 1930 ዓ.ም ለሁለተኛ ጊዜ ቀረበ። ራስ አበበ ለእኔ የመመለሱን ሃሳብ ስለደገፉ ተፈረደልኝ። በጸሐፊ ትዕዛዝ /ኮሎኔል/ ኪዳኔ ወልደጊዮርጊስ የተሣፈ ደብዳቤ ተሰጠኝ።[5]

በኅዳር ወር 1931 ዓ.ም ተድላማርያም፣ ነርጉ ከፊታውራሪ ወልደዓድት ችሎት ቀረበ። ወንጀሉ አርበኞችን አባብሎ የማስከዳት ሥራ አካሄዶአል የሚል ነበር። አረርቲ ከነበረው ጣልያን ለግራዝማች ዳኜና ለባልደረቦቻቸው የተጻፈ ደብዳቤ ከኪሱ፣



ሁለት ጠርሙስ ነጭ አረቂና ፊራንካ ከትከሻው ተገኘበት። ደብዳቤ የተጻፈላቸው ሰዎች ስማችንን ለማጥፋት፣ በጦር ባልደረቦቻችን ዘንድ እምነት ለማሳጣት የተካሄደ ሴራ ነው በማለት በተፈራጅነት ቆመ። አርበኛው ይሙት በቃ ስለፈረደበት ተሰቀለ።[6]

ቡልጋ፣ ጭቃ ቆላ ሰኔ 21 ቀን 1931 ዓ.ም በተደረገው ጦርነት ብዙ የጠሳት ወታደሮች ተማረኩ። ሰኔ 23 ቀን ሰፍርድ ከአርበኛው ጉባዔ ቀረቡ። ከሐረርጌ የመጡ ባንዶች ነበሩ። ሁልጊዜም ይደረግ እንደ ነበረው፣ ራስ አበበ አረጋይ "እናንተ ኢትዮጵያውያን ሁናችሁ እንዴት ሀገራችሁንና ሰንደቅ ዓላማችሁን ትወጋላችሁ?" ብለው ጠየቁአቸው። በወቅቱ ይኼን ዓይነቱ ጥያቄ በአርበኞች ዘንድ የተለመደ ነው። ለተማራኪዎች አመክሮ ለመስጠትና ይቅርታ እንዲጠይቁ፣ በዚህም አርበኛው ከቁጣ ወደ ትዕግሥት እንዲመለስ ለማድረግ ነው። ተማራኪው ተገድደን ነው፣ ተሳስተን ነው፣ ባለማወቅ ነው ይላል። አርበኛው የተለየ ጥፋት ያልተገኘበትን ይለቀዋል። ነገር ግን ያን ዕለት

እንደዚህ ሳይሆን ቀረ። የተለየ ነገር ተፈጠረ። ከተማራኪዎቹ አንዱ "እናንተ ሌቦች፣ ምን ሰንደቅ ዓላማና ምን ሀገር አላችሁ" አለ። ሌላም ብዙ የስድብ ቃል ተናገረ። ሌሎች ምርኮኞች ዝም አሉ። እነሱ ከመጡበት የምሥራቅ ኢትዮጵያ አካባቢ የሚኖሩ ዜጐች አነጋገር እንደዚህ ግድየለሽ መሆኑን ያጤኑ ማንም የለም። ሰውየው የተናገረው የሁሉንም ሃሳብ እንደ አጠቃለለ ተቆጠረ። ከአርበኞቹም ወገን ይህ የሁላችሁ ቃል ነውን? ብሎ የጠየቀ ወይም አንድ በአንድ እንዲናገሩ ሃሳብ ያቀረበ የለም። በዚሁ ብቻ በደምፍላት ፍርድ ተሰጠ። ሁሉም በጥይት ተደበደቡ።[7] ለነገሩ የተናጋሪው ድፍረት ከባድ ነው፤ እውነትም ሊቀጣ ይገባዋል። ነገር ግን ሌሎች ሃሳባቸውን ላይጠየቁ መገደላቸው ያሳዝናል።

በወንጀል ተይዘውና በጦር ሜዳ ተማርከው ለሚቀርቡ ለምች ትክክለኛ ፍርድ ከመስጠቱም በላይ፤ አርበኛው የመተዳደሪያ ደንብ እያወጣ በሥራ ላይ ያዋለበትም ጊዜና ቦታ አለ። ለምሣሌ ማናቸውም ወንጀል ለጠቅላላው አደባባይ ይቀርባል። አለቃው በሥልጣኑ አንዳች ነገር አያደርግም። አርበኛውም በነፃ ተከራክሮ በድምፅ ይወስናል። ተቃዋሚ ከአለ፣ ፍርድ አይፈጸምም። በመንዝ ልጅ ግዛቸው ኃይሌ ለአርበኞች አንድ የውስጥ ደንብና ሕግ አውጥተው ነበር። የወጣውም ደንብ የሁለት ዕዳ ከፋይ የሆነው ገበሬ ያለ አግባብ እንዳይነካ የሚከለክል ነበር። ደንቡን የተላለፉ ቅጣት ደርሰባቸዋል።[8]

ለባንዶች ጭምር ፍትሕ የታየላቸው፣ እየተማረኩ በምክርና በማስጠንቀቂያ የተሰቀቁ እጅግ ብዙ ናቸው። እዚህ ላይ ግን የአንድ ሰው ጉዳይ መጥቀስ እወዳለሁ። ፊታውራሪ ተሰማ ከተማ ይባል ነበር። ቤቱ ቡልጋ የቁር፣ ልዩ ስሙ ክንንባር ከሚባል ቦታ ነበር። ለጣልያን ዋና ጉዳይ ፈፃሚ ሆኑ። በወናና በእመየት አገር በራሱ አዛዥነት በአርበኞች ላይ ዘምቶ ረጅም ጊዜ የወሰደ ውጊያ አካሄደ። ብዙ ሰው አስፈጀ። የተማረከውንም ከተማ አሱ ራሱ ወስዶ እየሠጠ፣ አሥራ ሦስት ሰዎች ቤት ተዘግቶባቸው ተቃጠሉ። አያያዙ አርበኛውን የማያፈናፍን ሆነ። በአርበኞች በኩል ተመከረ። በበቅሎ እየተቀመጠ ወዲያ ወዲህ በሚልበት ጊዜ ላይ፣ እሱን በረጅም መውዜር መዘንጠፉ ብቸኛውና ቀላሉ መፍትሄ ሆነ።

ነገር ግን አርበኛው እንደዚህ ማድረግ አልፈለገም። በንጉሠ ነገሥቱ ጊዜ በልጅ ኢያሱ ምኒልክ ምክንያት ታሥሮ ብዙ መንገላታት የደረሰበት መሆኑንና በዕድሜው አረጋዊ መሆኑን አሰበ። ክሶ ለማሠር ወሰነ። ከጣልያን እጅ እንደሚደርስ ተደርጐ አንድ የሃሰት ወረቀት በስሙ ተጻፈለት።[9] ቃሉም የጻፈው ወረቀትና የላከው ገንዘብ መድረሱን እየገለፀ ምስጋና የሚያቀርብ ነበር። ደግሞም ለአቀረቡልን ጥያቄ መክረን መልስ እንሰጣለን የሚል ቃል ነበረበት። ወረቀቱ ሽኖ ጣልያን እጅ በአንድ በተማረከ ሰው እጅ ደረሰ። ሽማግሌው ቢጠየቅ ሽፍቶቹ እንዲገቡ ለማባበል ብሎ እንደሆነ ስለገለጸ ሌላ

ቅጣት ሳይደርስበት ቀረ። ሆኖም ሰኖ ከተማ በግዞት እንዲቀመጥ ተወሰነበት። ቡልጋ ለአርበኞች እንቅስቃሴ ነፃ ሆነች።

በጐንደርም ተመሳሳይ ፍርድ ተሰጥቶአል። ጐንደር ፀገዴ በምድረ ገበታ ጦርነት ዕለት በ1932 ዓ.ም ብዙ የሽሬ ባንዶች ተማርከው ለአርበኛው ጉባዔ ቀረቡ። በጦርነቱ ብዙ አርበኞች ወድቀው ነበርና የምርኮኞቹ ይቀጣሉ አይቀጡም ጉዳይ እጅግ አከራከረ። እኩሉ ሀገራቸውን ኢትዮጵያን ከድተው ለጠላት ሬድተው፤ ወገኖቻቸውን የኢትዮጵያን አርበኞች ወግተዋልና ሞት ይገባቸዋል አለ። እኩሉ ደግሞ መሪ ሆነው ያመጡአቸው ይቀጡ እንጂ፤ ተገድድው የመጡ ገበሬዎች ሊቀጡ አይገባም አለ። ትግራይ ቀደም ብሎ የጠላት ጦር የገባበትና ብዙ ጉዳት የደረሰበት አገር መሆኑ ጭምር ከግምት ውስጥ ገብቶ፤ ምርኮኞቹ ሊቀጡ አይገባም የሚለው ወገን አመዘነ። ተዘዋውረው የአርበኛውን ሁኔታ እንዲያዩና በሸኚ ወደ ሀገራቸው እንዲላኩ ተወሰነ። በአመክሮ ተሰቀው አገራቸው እንዲገቡ ተደረገ።[10] ፍርዱ ፖለቲካ ጉረሰ ቢሆንም ሊመሰገን ይገባዋል።

በጐንደር ከተካሄዱት የፍርድ ጉዳዮች ሁሉ አርበኛውን እጅግ ያከራከረው ለአስታራቂነት የመጣ አንድ የጣልያኖች ቡድን ጉዳይ ነበር። ጦርነቱ እያየለባቸው ሊሄድ ጣልያኖች የቦሩን ሥራ ወደ ነገር ለማዞር ሞከሩ። ከሮም ለዚሁ ጉዳይ ተብሎ በተላከ የፋሽስት ፓርቲ አባል የተቀነባበረ አንድ ቡድን በጐንደር አሰማሩ። ቡድኑ ሁለት ኮሎኔሎች አንድ ሻለቃና ሁለት መቶ አለቆች ነበሩበት። ይህ ቡድን ኮሎኔል በኒሶና ኮሎኔል አንጀሊኒ በሚባሉ መኮንኖች እየተመራ ወደ በለሳ መጣ። ቡድኑን ወረሐ ላይ ፊታውራሪ ደምስ ተሰማ ተቀብለውት በጉዞ ላይ እንደአለ፤ ተለዋጭ ትዕዛዝ በቀኛዝማች ተስፋ ኃይሉ እጅ ስለደረሰ እጃቸውን በሰንሰለት ታሥረው ከደጃዝማች ዳኜው ተሰማ ችሎት ቀረቡ።

አርበኛው በደጃዝማች ዳኜው ተሰማ ሰብሳቢነት ጉባዔ ሠርቶ ተከራክረባቸው። የጉንድ ተክለ ሃይማኖት ገዳም ካህናትና መነኮሳት ስዕልና መስቀል ይዘው፤ ለአርቅ የመጣ ሰው መነካት የለበትም ብለው ቆሙ። ገሚሱ አርበኛ ጣልያኖቹ የአርበኛውን ኃይል ለመቀነስ የመጡ ስለሆነ፡ ይገደሉ አለ። ከፊሉ ደግሞ ለአርቅ የመጣ ሰው በምን ሕግ ይገደላል አለ። ነገሩ በአንድ ከፍል ብቻ ሊወሰን ስለአልቻለ መላው የበጌምድር አርበኛ አብናት ላይ ጉባዔ አድርጐ እንዲወሰን ጥሪ ተላለፈ። ብዙዎቹ ተሰበሰቡ። አንዳንዶቹም ሰው እየመረጡ ላኩ። ደጀዝማች ብሬ ዘገየ "...የሚገድል ሰው ጠፍቶ እንደሆነ ለኛ ላኩልን..." የሚል ደብዳቤ ጻፉ።

ሆኖም አብናት ላይ ጠቅላላ ጉባዔ ተደረገና እሥረኞቹ ቀረቡ። ቃላቸውን ተጠይቀው የአርቅ ሥራ ለመሥራት መምጣታቸውን አስታወቁ። አርበኛው የግራ ቀኙን ሃሳብ ከመረመረ በኋላ "...ለሰላማዊ ነገር የመጡና በጦርነት ያልማረክናቸው ስለሆነ ሊገደሉ አይገባቸውም" ብሎ በድምፅ ብልጫ

ፈረደ። ነገር ግን በነፃ አሰቀቃቸውም። እርቅ ከፈለጉ የደብረ ታቦርን፣ የይፋግን፣ የጣራ ገዳምን፣ የደጉማን፣ የአምባ ጊዮርጊስን ጦር አስነስተው እንዲወስዱና በእነዚህ ቦታዎች የሚገኘውን የጦር መሣሪያ ለአርበኛው እንዲያስረክቡ ሲል ወሰነ። ይህ አስኪፈጸም ጣልያናውያኑ ታስረው እንዲቆዩ ስለ ወሰነባቸው፤ እናም በለሣ፣ ደራ ማርያም ከአለው እሥር ቤት ገቡ።

ይህ ጥያቄ ጐንደር ከተማ ለጣልያኖች ሲደርስ፣ ታላቅ ችግር ፈጠረ። የሰላም ጥረቱ ተቀባይነት ሲያጣ ለአስታራቂነት ከሮም የመጣው ሹም ፅሰቱን ወደ ሀገሩ በአይሮፕላን በረረ። እጅግ የሚያሳዝነው ከላይ በተዘረዘረው ዓይነት በሕግና በፖለቲካ የተያዘውን ነገር፣ ጠላት በአሥራ ስድስት ሬድፍ /አስካዶሪ/ ፈረሰኛ ጦር አሰልፎ፣ አርባ አይሮፕላን አስነስቶ ታላቅ ጦርነት በማካሄድ፣ አሥረኞቹን በጥቂት ወላዋዮች ትብብር ጭምር ነጥቆ ለመውሰድ መቻሉ ነበር። ምንም የነገሩ ሂደት ተጣምሞ ከሚያስቆጭ ፍፃሜ ላይ ቢደርስ፣ ፍርዱ ትክክል ነበር።[11]

በጉጃም ከተከናወኑት የፍርድ ሥራዎች ሊጠቀስ የሚገባው፣ ተማርካ የታሰረችውን የሻሽ ወርቅ በላይ የተባለችውን ልጃቸውን እናስለቅቃለን በሚል ምክንያት ከደጃዝማች በላይ ዘለቀ ዘንድ የመጡት ባንዶች ጉዳይ ነበር። የጣልያን ደብዳቤ በአርበኞቹ ጉባዔ ላይ ከተሰማ በኋላ፣ ልጅ በላይ ከጣልያን መንግሥት ጋር መታረቅ ሀገራቸውን መሸጥ መሆኑን ገልጸው፣ በምንም ዓይነት የእርቁን ሃሳብ እንደማይቀበሉ አስታወቁ። ለእርቁ አማላጅ ሆነው የመጡት ባንዶች በኢትዮጵያ አርበኞች ላይ ይሙት በቃ ይፈርዱ የነበሩት ቀኛዝማች እጅጉ ለማና ቀኛዝማች አደራ ያለው ስለነበሩ፣ በእነሱ ላይ ፍርድ ተያዘ። አርበኛውም እነዚያ ሁለት ባንዶች በአርበኛ ላይ እየፈረዱ ደም ሲያፈስሱ የኖሩ፣ የጦር ጓደኞቹን ከምድር ገጽ የጠረጉና የጨፈጨፉ ስለሆኑ እና ሞት ይገባቸዋል ብሎ በሙሉ ድምፅ ስለወሰነ በ1930 ዓ.ም በቦከና አደባባይ በስቅላት ተቀጡ። አብሮአቸው የመጣው አስተርጓሚ ግን በደል ስለአልተገኘበት ተሰቀቀ።[12]

በጉራጌ አገር የነበሩ አርበኞች የሚከተሉትም ሥልት ተመሳሳይ ነበር። ካርቱም ከተባለው ውጊያ በርካታ የወለኔ ታጣቂዎችና የሸንቅላ ባንዳዎች በሐምሌ ወር 1930 ዓ.ም ተማረኩ። ሀገራቸውን ኢትዮጵያን ከድተው ከጠላት ጐን ቆመው በመዋጋታቸው ቆሴ በተባለው ገበያ በአደባባይ ተሰቀሉ።

የቡልጋን አካባቢ በአስታራቂነት ስም እየተዘዋወረ ለጣልያን ምሥጢር ይሰበስብ የነበረው መሴ ቀስተኛ ከደጃዝማች ገረሱዱኪ ዘንድ ደረሰ። አርበኛው በጉባዔ ተሰብስቦ የመጣበትን ጉዳይ እንዲናገር ፈቀደለት። የመሴ ቀስተኛ አመጣጥ ከተሰማ በኋላ የአርበኛው ድምፅ ከሁለት ተከፈለ። አንደኛው ወገን ለእርቅ ከመጣ ሊቀጣ አይገባም ሲል፤ እኩሉ ደግሞ ሊቀጣ ይገባል አለ። በክርክሩ ጊዜ የመሴ ቀስተኛ መሰሪ ተልዕኮ አርበኞች በትውልድ ሀገራቸው የሚያደርጉትን ትግል የሚያዳክም መሆኑ ተነገረ። ቀድሞ ከራስ

ደስታ ዳምጠውና ከደጃዝማች ገብረ ማርያም ዘንድ ሄዶ እንደነበረ፤ ኋላ ከራስ አበበ አረጋይ ዘንድ ሄዶ ይህንኑ ሥራውን እንደአካሄደ፤ አሁንም የመጣው ይህንኑ የማሳሳትና የስለላ ሥራውን በመቀጠል እንደሆነ ስለተገለጸበት፣ ይቀጣ የሚለው ወገን አመዘነ። እሱም አቁሮ በተባለው ቦታ መስከረም 19 ቀን 1931 ዓ.ም በጥይት ተደበደበ። አብረውት የመጡት ሽማግሌዎች ግን በደል ስለአልተገኘባቸው በደህና ተመለሱ።[13]

በአርበኝነት ጊዜ ሕግ ይከበር ነበር። ወንጀል የሠራ አይለቀቅም፤ ለፍርድ ይቀርባል። ችሎት በሚገባ ተሰናድቶ፣ ፍርድ ይደረጋል። ከሳሽ፣ ተከሳሽ ይከራከራል። ምስክር በወንጌል፣ በመስቀል እየማለ ይመሰክራል። ተቺ ይተቻል። በአደባባይ ያለ ሰው ሁሉ በየተራ እየተነሳ ያለ አንዳች ተፅዕኖ «ይፍረድብኝ፣ ሠይፍ ይፍረድ» እያለ ይፈርዳል።[14] የሃሳብ ልዩነት በተፈጠረ ጊዜ ብዙሃኑ የደገፈው ወገን ይጸናል እንጂ፣ አለቃ ባለ ብቻ አይወሰንም። ስለአርበኞች ሕግ አክባሪነት ብዙ ማስረጃ ማቅረብ ይቻላል። ነገር ግን አንባቢ ልቦናው የሚያምን እስከሆነ ይኸው ይበቃል። ምንም እንኳን በአርበኝነት ጊዜ የተሰጠ ፍርድ ሁሉ ትክክለኛ ነበር ባይባልም፣ ከነባት በኋላ የታየውን ያህል ጭቆላ ግን አልነበረም።

ማጣቀሻ ፅሑፎች

1. ታደሰ ዘወልዴ፣ *ቀሪን ገረመው*፣ ገጽ 38።
2. ከአቶ /ሃምሣ አለቃ/ ወልደ ጊዮርጊስ የተነገረኝ።
3. ሙሉ ሰው ምትኩ፣ *የአርበኞች ትግል ከፋሽስት ጋር*፣ ገጽ 16-17።
4. ጸሐፊው ራሱ ያየው።
5. አባሪ 41.1 ይመልከቱ።
6. ጸሐፊው ራሱ ያየው።
7. ታደሰ ዘወልዴ፣ ገጽ 137።
8. ታደሰ ዘወልዴ፣ ገጽ 248።
9. ደብዳቤ የተጻፈው በአለቃ /ፊታውራሪ/ ወልደሣድቅ ዘውዴ ነበር።
10. ገሪማ ታፈረ፣ ገጽ 136-137።
11. ገሪማ ታፈረ፣ ገጽ 212-214።
12. ዘውገ ዘገየ፣ *አባ ኦሰትር፣የደጃዝማች በላይ ዘለቀ ታሪክ*፣ ገጽ 19-20።
13. ታቦር ቀሜ፣ *አባ ቦራ፣ የደጃዝማች ገረሱ ዱኪና የሌሎችም አርበኞች ታሪክ*፣ ገጽ 57-61።
14. ሠይፍ ይፍረድ የሚባለው "ነፍሰ ባልገደለ ሰው ላይ ይሙት በቃ ተፈርዶ፤ የተፈረደበት ሰው በሠይፉ ሲመታ የተመታው ቀርቶ ቁሞ ይመለከት የነበረው ነፍሰገዳይ ጭንቅላት ተቆረጠ" የሚል ጽኑ እምነት ስለአለ ነው።

ምዕራፍ አርባ ሁለት
የጣልያን የግፍ ሥራዎች

በዓለም ላይ ብዙ ጦርነቶች ተካሄደዋል። በጦርነት ደግሞ አሸናፊና ተሸናፊ መኖሩ ያለ ነገር ነው። ጣልያኖች ራሳቸው ብዙዎቹን ወግተዋል፣ ድል አድርገዋል፣ ገዝተዋል፣ እንግሊዞችን፣ ግሪኮችን ጭምር። እንደ ኢትዮጵያ የጨከኑበት በታሪክ ውስጥ ያሰ አይመስልም።

በመጀመሪያ ደረጃ ለጦርነቱ ከቅኝ ግዛት ፍላጐት በስተቀር ሌላ ምክንያት አልነበራቸውም። የ1888 ዓ.ምቱን ጦርነት የጀመሩት ኢጣሊያኖች እንደ መሆናቸው፣ በዚያኛውም ሆነ በዚህኛው ኢትዮጵያ የበደልቻቸው ምንም ሁኔታ የለም። ጦርነቱንም በራሳቸው ፍላጐት ከከፈቱ በኋላ በሥርዓት አሳካሄዱትም። ፍጹም ጭካኔና አረመኔነት አሳይተዋል። ወታደር ብቻ ሳይሆን ልጅ አዋቂ፣ ሴት ሽማግሌ፣ ቁስ መነኩሴ ሳይል በመላ የኢትዮጵያውያንን ዘር ከምድር ገጽ ለማጥፋት፣ ከመሪ እስከ ተራው ሕዝብ ድረስ ተባብረው በሙሉ ኃይላቸው ተጣጥረዋል። ለዚህ አንድና ሁለት የለውም። በዓለም የተከለከለ መርዝ እየረጩ ሰውና አራዊትን አንድ አድርገው ፈጅተዋል። ይህ አፈሳፀም ዓለም የተገረመበት ግፍ ነው። በፈቃዳቸው ራሳቸውን ለሀገራቸው ነፃነት መስዋዕት አድርገው አቅርበዋልና፣ ወደ ጦርነቱ ገብተው ጦርነቱ በተደረገበት ቦታ ላይ በተፈፀመው እልቂት የሞቱትን በግፍ እንደ ተገደሉ አይቆጠርም። በዚህ ምዕራፍ የምንመለከተው፣ በተለይ በሰላማዊው ሰው ላይ የተፈፀመውን ግፍ ነው።

በአምስቱ ዓመታት፡- 17,500 ሴቶችና ሕፃናት እንደሞቱ፣ ተማርከው እንደ ተገደሉ 24,000፣ በእሥር ቤት ደግሞ 35,000 እንደ የሞቱ ተመዝግቦአል። በድምሩ በሦስቱ ዓይነት አሟሟት የሞቱት 76,500 ናቸው ማለት ነውን? ይህ ቁጥር እጅግ አነስተኛ ነው። እንደኔ ከ300,000 ሲያንስ አይታየኝም። ከየካቲት 12 እስከ 14 ቀን በተካሄደው እልቂት የሞቱት ሰዎች ብዛት 30,000 ሊሆን ይችላል። ቢበልጥም ከዚያ በትንሽ ነው። በስደትና በረሃብ የአለቁት 300,000 የሚደርስ ሳይሆን አይቀርም።[1] ስለዚህ በአምስቱ ዓመት ከ600 ሺህ እስከ 700 ሺህ ይደርሳል። በዚህ ላይ ደግሞ 2,000 አብያተ ክርስቲያናትና 525,000 ቤቶችን ጠላት እንደአቃጠለ ተዘግቦአል። ይህ እውነት ሊሆን ይችላል።

የጣልያኖች ጭካኔ የሚለካው በፈጁት ሰው ብዛትና ባቃጠሉት ቤተክርስቲያንና ቤቶች ብቻ አይደለም። ከአገዳደላቸው ጭምር ነው። ቤት እየዘጉ በእሳት ያቃጠሉአቸው ብዙ ናቸው። መርዝ ያርከፈከፉባቸው አያሌ ናቸው። እጅ ወይም እግራቸውን በሽቦ እያሰሩ በመኪና የጐተቱአቸው

በርካታ ናቸው። እጃቸውን ከአንድ መኪና፣ እግራቸውን ከሌላ መኪና ላይ አሥረው መኪናዎቹን ግራና ቀኝ በመንዳት የበጣጠሱአቸውም አሉ። ከአነነፍሳቸው የተቀበሩ አሉ። ምንም እንኳን የመስቀል ቅጣት በጥንት ዘመን የተለመደ ነው ሊባል ቢችልም፣ ይኼኛው በጠቅላላው የኢትዮጵያን ህዝብ ከምድር ገጽ ለማጥፋት ሲሉ ያላደረጉት ነገር የለም። ወንዱ አንዲሰለብ፣ ሴትዋ ጡትዋን እንድትቆረጥ አድርገዋል። የእሥራት ሥርዓታቸው ደግሞ እጅግ የከፋ ነበር።

በአጠቃላይ ስለፋሽስት ጣልያኖች ጭካኔ ይህንን ያህል ከአወሳን በኋላ፣ ለናሙናም እንኳን ቢሆን አንዳንድ ሥራዎቻቸውን ማየት ይገባናል። በአንድ ቦታና ጊዜ ከተካሄዱት እልቂቶች ዋነኛው ከየካቲት 12 እስከ 14 ቀን 1929 ዓ.ም አዲስ አበባ ላይ የተካሄደው ነው። ተደጋግሞ እንደተገለፀው ያለቀው ሕዝብ ከ30,000 ቢበልጥ እንጂ አያንስም። በአገዳደሉም ረገድ ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት የጭካኔ ሥራዎች አብዛኛቹ ተፈጽመዋል። ለግርግሩ በቂ ምክንያት ነበር። ይህ አይካድም። ከ8-10 ያህል ቦምቦች ተጥለዋል። ሠላሳ ያህል ጣልያኖች ቆስለዋል። ሁሉም ሹማምንት ነበሩ። የተጣሉው አደጋ ቀላል አይደለም። ሊሻኝ ጢስ ወጋኝ ባይሆን ኖሮ ጣልያኖች በመላ ከተማዋ ሦስት ቀን ሙሉ እልቂት ባላካሄዱም ነበር። ምንም ለጣልያኖች ጨኽትና ግርግር ባሕርያቸው ቢሆን፣ ከሁለትና ሦስት ሰዓት የበለጠ ሊሸበሩ፣ ከስድስትና አራት ኪሎ ያለፈ እልቂት ሊያካሂዱ ባልተገባቸውም ነበር። ሆን ተብሎ የተካሄደ ጭካኔ ነው። በድጋሚ ሌላ አንዳች አደጋ አልደረሰም ነበርና።

ከደብረ ሊባኖስ ገዳም ከ350 የማያንሱ መነኮሳት ገደሉ። የቀሩትን ደግሞ ወደ ደብረ ብርሃን ወሰደው ከዚያ ሲደርሱ 42 ገደሉ። ከጋቋላ ገዳም 100፣ ጐንደር ከማኅበረ ሥላሴ በየጊዜው ካሳሄዱት ግድያ ከ150 ያላነሱ መነኮሳት ፈጁ። ሰበቡ ሕዝብ አነሳስታችኋል፣ መሣሪያ ደብቃችኋል ነበር። የጣልያኖቹ ጥርጣሬ ሙሉ በሙሉ ውሸት ነው ወይም እውነት ነው ለማለት ያስቸግራል። አሳዛኙ ነገር ከዳኛ ፊት ሳይቀርቡ፣ ጥፋታቸው ሳይረጋገጥ በጥርጣሬ ብቻ ማለቃቸው።

በጦር ሜዳ የተማረከ ሰው አይገደልም። ጣልያኖች ግን የማረኩትን አለቀቁም፣ ገደሉ። ከሥራቸው ሁሉ የከገፋው ደግሞ «አንነካህም፣ ግባ» እያሉ፣ በቁስ መነኩሴ እያባበሉ አስገብተው፣ ብዙ ሰው ፈጁ። ለዚህ የክህደት ግብራቸው በመርሐ ቤቴ የደጃዝማች አበራና ደጃዝማች አስፋው አገዳደል ማስረጃ ነው። እንደዚሁም በቡልጋ የሸለቆውን ፊታውራሪ መኩሪያን አስገብተው ደብረ ብርሃን ወስደው በነሐሴ 1928 ዓ.ም 42 ራሳቸውን ገደሉአቸው።

የብዙ አርበኞችን ራስ እየቆረጡ በአደባባይ ጊጤ ተጫውተውበታል። በቡልጋ ይህ ሥራ የተጀመረው በፊታውራሪ መኮንን ወልደጊዮርጊስ መሆኑን ጠቅሻለሁ። ከዚያ በኋላ አርበኛውም የጣልያንን ጭንቅላት እየቆረጠ በየገበያው ያዞረው ጀመር። ለምሣሌ ያህል ፊታውራሪ ወልደፃድቅ ዘውዴ አራጊቻ ብዙ መከና ሰብረው ከፈጁአቸው ጣልያኖች ውስጥ የአንዱን ጭንቅላት ቆርጠው ጌጥ አጫውተውበታል።

ጉጂም፣ ባህር ዳር አንዲት ሴት በአንድ ልጅ ምክንያት አንድ ሰው ከስሳ ከአገረ ገዥው ዘንድ አቀረበች። ቀሰብ ሥፈር ለማለት ነበር። ሕግ አዋቂው ጣልያን ልጁን በሽጉጥ ገድሎ እንዲካፈሉት አዘዛችው። በጌምድር ውስጥ ደግሞ አባ ተስፋማርያም የተባሉትን መነኩሴ ሳይሞቱ ከነነፍሳቸው ቀበራቸው። [2]

ቡልጋ፣ መገሬ ዛላ፣ ምስለኔ አገር አቶ አብራ የተባለው ሰው አንድ ካርታ የመውዜር ጥይት ስለተገኘበት፣ ከግንድ ጋር አሥሮ፣ እንጨት ከሳዩ ቆልሎ እሳት ለቀቀበት።[3]

አቶ እንግዳ ዘውዴ የተባሉትን ጉንደር የዱርጦ ሰው፣ ያለ አንዳች ጥፋት ይዞ ሆዳቸውን በካራ ቀደዳቸው። ይህም የማይበቃው ሆኖ ቁርበታቸውን ገፍፎ ከራስ ቅላቸው ሲደርስ፣ እንደ ፍየል ዘቅዝቆ ሰቀላቸው።

አንድ የጣልያን የጦር መኮንን በጦርነት ሞቱ። የእሱን ደም ለመመለስ ከ150 ያላነሱ የአገሩ ሰዎች ተገደሉ። ከእነዚህ አሥራ ስድስቱን አንድ ቤት አጉሮ እሳት ለቀቀባቸው። ሦስት ሰዎችና አንድ ሕፃን ሰብረው ከቤቱ ወጡ። ሰዎቹ ሲያመልጡ ሕፃኑ ተያዘ። እንደገና መልሶ ከእሳቱ ጨምሮ አቃጠለው።[4]

ቡልጋ፣ በረከት የአንድ ጣልያን ጭንቅላት ተቆርጦ ከወደቀበት ወሬኛ አንስቶ ሰጠው። ሦስት መቶ የአገሩን ሰዎች በገመድ አሥሮ ሦስት ቀን ሙሉ በረሃብና በውሃ ጥም ከአሰቃያቸው በኋላ፣ ሜንሶ ወንዝ ላይ በመትረየስ ደበደባቸው። ይህም አልበቃህ ብሎ ጋዝ አርከፍክፎ አነደዳቸው።

የጣልያኖች የግፍ ሥራ ተነግሮ አያልቅም። ለማስረጃ ያህል ለምን እንዲህ እንደሆነ ብንመለከት ይሻላል። ሦስት ምክንያቶች አሉት። አንደኛው ጣልያናውያን በኢትዮጵያውያን ላይ ያላቸው ቂም ሲሆን፣ ሁለተኛው የሞሶሊኒ ጨካኝነት ነው። ሦስተኛው በወቅቱ የነበረው የርዕዮተ ዓለም ሁኔታ ነው። እነዚህን ሦስት ነጥቦች አብሰሉ ማየት በኢትዮጵያ ላይ ለተፈፀመው ግፍ ምንጩ ምን እንደሆነ ፍንጭ ይሰጣል።





ራሳቸን ለማቃጠል ቤንዚን በበርሜል ቀረበ



በመርዝ የተቃጠለ የኢትዮጲያዊ እግር





ራሳዎችን ለማቃጠል ቤንዚን በበርሜል ቀረበ



በመርዝ የተቃጠለ የኢትዮጲያዊ እግር



በመርዝ የተቃጠለ የኢትዮጲያዊ እጅ።

በመጨረሻው ነጥብ መጀመር ይሻላል። በዚያን ዘመን በኢጣልያ የፋሽስት፣ በጀርመን የናዚ፣ በራሺያ የኮሚኒስት ፓርቲዎች ሰፍነው ነበር። እነዚህ ሦስት የፖለቲካ ፓርቲዎች የየራሳቸው የሆነ ርዕዮተ ዓለም ነበራቸው። አመለካከታቸው ለዓለሙ ሰውኖ ስለሚያስፈልገው አዲስ ዓይነት የአስተዳደር ሥነ ሥርዓትና የአመራር ሥልት እንዲቀየስ የሚያምኑ ነበሩ። በርዕዮተ ዓለም ይለያያሉ። ነገር ግን በአንድ ነገር ይስማማሉ። ይህም ሃሳባቸውን በኃይል የማስፈፀም ጉዳይ ነው። በኃይል መጠቀም እንደማይቀርና እንደሚያስፈልግ በመጀመሪያ ያመኑ ፋሽስቶች ነበሩ። እውነት በመናገራቸው ሊመሰገኑ ይገባቸዋል። የናዚና የኮሚኒስት ርዕዮተ ዓለም አራማጆች የልባቸውን ሳይገልጹ፣ ሰላማዊ በሆነ መንገድ ሃሳባቸውን በሥራ ላይ እንደሚያውሉ ልፈፋቸውን ቀጠሉ። በግብር ሦስቱም አንድ መሆናቸው በኋላ ተገለጸ። ፋሽስቶች ኢትዮጵያውያንን፣ ናዚስቶች አይሁዶችንና ከቁጥጥራቸው ሥር ያስገቡአቸውን የአውሮፓ ሕዝቦች፣ ራሺያዎች በራሳቸው ሕዝብ ላይ የአረመኔነት ሥራ ፈጸሙ። በወቅቱ የፋሺስቶችን የግፍ ሥራ ገፈት በመቅመስ ረገድ ኢትዮጵያ የመጀመሪያዋ ሀገር ነበረች። ከዚሁ የግፍ ሥራ ለመገላገልም የመጀመሪያዋ እርስዋው ሆነች።

ኢጣልያ ከፋሽስት ፓርቲ ርዕዮተ ዓለም ጋር አብሮ የተፈተለ የቂም ሸማ ተጐናጽፋ ነበር። ይህም ቂም በኢትዮጵያ ላይ ሆነ። ተደጋግሞ እንደተገለጸው የቂሙ መንሥዔ የአድዋ ጦርነት በኢትዮጵያ ድል አድራጊነት መጠናቀቁ ሆነ። የክብር፣ የሞገስ፣ የኢኮኖሚ ጥያቄዎች አብረው ተፈተሉ። ሞሶሊኒ ለሥልጣን የበቃበት ርዕዮተ ዓለም የጣልያንን ሕዝብ ችግር የማይፈታለት ሲሆን፣ የኢጣልያ ሕዝብ ኢትዮጵያ ላይ

እንዲያተኩር አደረገው። ለሕልውናው አስተማማኝነት በለለው ሁኔታ ውስጥ ገብቶ እንዲሰዋ፣ የኢጣልያን አገር ለመገንባት ኢትዮጵያውያንን ከምድረ ገጽ ማጥፋት አስፈላጊ እንደሆነ አድርጐ አሳየው። ሂትለር የአይሁዶችን ጥፋት፣ ስታሊን የቀድሞዎቹን ነገሥታት ወገኖች ማውደም ለአዲስ እርምጃ አስፈላጊ መሆኑን እንደ አሳዩአቸው ዓይነት ማለት ነው።

ከዚህ በተጨማሪ ሞሶሊኒ በተፈጥሮው ጨካኝ ሰው ነበር። የቀድሞዎቹን ጓደኞቹንና በኋላም የተነሱበትን ተቀናቃኞቹን በጭካኔ አጥፍቶአቸዋል። ዓለምን ለማንቀጥቀጥ የበቃውም በጭካኔው እንጂ በፖለቲካ ጥበቡ፣ በአስተዳደር ችሎታው አልነበረም። በዚህ የተፈጥሮ ጨካኝነቱ ላይ የጭካኔ ሥራ ለማካሄድ ቆርጦ የተነሣው የፋሽስት ፓርቲ መሪ ሆነ። ስለዚህ በአለው የተፈጥሮ ስሜትና ከፓርቲው በሚደረግለት ድጋፍ አንድ ላይ ተደምሮ፣ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ተነግሮ የማያልቅ የግፍ በረዶ አዘነመበት።

በኢትዮጵያ ውስጥ የነበሩ ጣልያኖች በኢትዮጵያውያን ላይ የወደዱትን የማድረግ ሥልጣን ነበራቸው። የጦር መሪዎቹም በቀረበላቸው መሣሪያ ሁሉ እንዲጠቀሙ ተፈቅዶላቸው ነበር። ለዚሁ ሲባል ልዩ ልዩ ዓይነት ቦምብና መርዝ ተሠርቷል። ይኼን የሚጠራጠር ካለ፣ መርዙን የመርጫው መኪና ተሠርቶ አይሮፕላኖች ላይ የተገጠመው ኋላ ምን ሊደረግበት ነው? ኢትዮጵያ ላይ እንዲጣል፣ ኢትዮጵያውያንን እንዲፈጅ አልነበረም? ብሎ ራሱን ይጠይቅ። በመሆኑም ጣልያናውያን የሠለጠኑበትን፣ የታዘዙትን ሠሩ። ከሠለጠኑበት፣ ከታዘዙት የጭካኔ ሥራ አንዳች አላጐደሉም። በትክክል ያንኑ ፈጸሙ። የተዘጋጀውም መሣሪያ እጅግ በጣም ጥቂቱ ይከሸፍ፣ አንዳንዱ ይሳት እንጂ ለተዘጋጀበት ሥራ አገልግሎት ላይ ዋለ።

ይህ አባባል ታሪክን ማጐምዠዝ የሚመስላቸው የዋሆች አይጠፉም። የዚህ ዓይነት ስሜት ያደረባቸውን ወገኖች፣ ከየዋህ አመለካከታቸው ለመመለስ፣ እንዲሁም ለማገዝ ሲባል አንዳንድ ዘገባዎችን መጥቀስ ይገባል። ጀነራል ደቦና ተሸሮ ጀነራል ባዶሊዮ የተተካው ደቦኖ መርዝ መርጨት፣ ቦምብ መጣል አያስፈልግም በማለቱ ነው።[5] ሞሶሊኒ ለባዶሊዮ ከሮም ወደ አሥመራ በቁጥር 1070 ጥር 17 ቀን 1928 ዓ.ም /ጃንዋሪ 26 ቀን 1936/ ባስተላለፈለት የምሥጢር ቴሌግራም "...ወደፊት ለምታደርገው ጦርነት በእጅህ በሚገኘው በማናቸውም ዓይነት የጦር መሣሪያ እንድትዋጋ ሙሉ ሥልጣን ሰጥቼሀለሁ።..." ብሎታል። በምሥጢር ቁጥር 144 ባስተላለፈለት በሌላ ቴሌግራም ደግሞ እንዳለው "...ጦርነቱንም በቀረበልህ በማንኛውም የጦር መሣሪያ እንድታደርግ



በመርዝ የተቃጠለ የኢትዮጲያዊ እጅ።

ስፈቅድልህ ድሉ የኛ መሆኑን በማረጋገጥ ተስፋ እያደረግሁ ነው።" ማርሻል ባዶሊዮ ደግሞ ለጀነራል ግራዚያኒ በምሥጢር ቁጥር 1897 ባስተላለፈለት ሌላ ቴሌግራም "...በእጅህ በሚገኘው በማንኛውም ዓይነት መሣሪያ፤ በቦምብ በመርዝም፣ በሚቀርብልህ ዓይነት መዋጋት አለብህ..." ብሎታል። የማይጨውን ጦርነት ድል ካደረገ በኋላም ግድያው እንዲቀጥል ሞሶሊኒ ትዕዛዙን አንቀረቀረ። በምሥጢር ቁጥር 5007 ለባዶሊዮ ከሮም ወደ ደሴ ባስተላለፈው ቴሌግራም "...ማናቸውም ኢትዮጵያውያን የጦር መሣሪያ በእጃቸው ይዘው የሚገኙት ሁሉ ያለፍርድ እተያዙበት ሥፍራ በጥይት እንዲደበደቡ..." አዘዘ።

ጣልያን ኢትዮጵያን እንደያዘች ጀነራል ባዶሊዮ ተሸሮ ጀነራል ግራዚያኒ ከግንቦት 24 ቀን 1928 ዓ.ም /ጁን 1 ቀን 1936/ ጀምሮ የኢትዮጵያ ገዥ ሆኖ ተሾመ። የተሸመውም ግራዚያኒ በጭካኔ ሥርዓት የአስተዳደር ሥራዎችን መሥራት እንደሚችል የሲቢያ ገዥ በነበረበት ጊዜ በግብር አረጋግጦ ስለነበር ነው። እሱም የጭካኔ ሥራውን ወዲያው ጀመረ። በፐሮቶኮል መዝገብ ቁጥር 3386 ከአዲስ አበባ ለሥራ ኃላፊዎች ሁሉ ቅጂ በመስጠት ነሐሴ 26 ቀን 1928 ዓ.ም /ሰፕቴምበር 1 ቀን 1936/ በጻፈው ደብዳቤ፤ "...ካህናት የሚአመጡትን ማናቸውንም የመማለጃ ቃል ሳይቀበሉ በሚገባ የመበቀል ሥራ በላስታ አውራጃ ሕዝብ ላይ ያለአንዳች ርህራሄ እንዲፈጸምበት ደጋግሜ አረጋግጣለሁ።..." የሚል መግለጫ ሰጠ። ከዚህም በስተቀር የላሊበላና የበልበላ ቀበሌዎች በኤፓሪት ጋዝ እንዲመርዙት ማድረጉን፣ በዝቋላ ተራራና ግርጌ አየር ኃይል የጭካኔ ሥራ እንዲሠራ ማዘዙን በሪፖርት ገልጿል። እንደዚሁም አዝማሪዎች፣ ቃሲኞች፣ ሺካዎች፣ ሰባኪዎች፣ ደቡተሮች እየተያዙ በጥይት እንዲደበደቡ ትዕዛዝ መስጠቱን አረጋግጦአል። ሞሶሊኒ በፐሮቶኮል መዝገብ ቁጥር 19960 በጻፈው ደብዳቤ "...በተናጋሪዎችና በሰባኪዎች ላይ የተደረገው የሞት ፍርድ መፈፀም የሚገባው ነው..." ሲል አሠራሩን አጽድቆታል። የደብረ ሊባኖስን መነኩሳት ትንሽ፣ ትልቅ፣ ሴት፣ ወንድ ሳይባል ከገዳሙ መሪ ጭምር በጥይት እንዲደበድቧቸው አዞአል።

የሞሶሊኒን አመራር፣ የባዶሊዮን የጦር ሥልት፣ የግራዚያኒን የአስተዳደር ሥርዓት በፊርማቸው ከአስተላለፉአቸው ጽሑፎች ተመልክተናል። ሁሉም የበቀልና የጭካኔ ናቸው። ይህንን በአንድ ወይም በሌላ አመለካከት ማደብዘዝ ወይም ማጋነን አያስፈልግም። ማተኮር የሚያስፈልገው ዓላማቸው ምን ነበር ከሚለው ጥያቄ ላይ ነው። ዓላማቸውን ሁሉም ገልጸዋል። በእኔ አመለካከት በተሻለ ሁኔታ የገለጸው ጀነራል ግራዚያኒ ነው። እሱም "...የሲቪል ሠራተኛም ሆነ ወይም የጦር

አስተዳደር ሹማምንቶች አንዳችም ሰብአዊ ርኅራኄ ማድረግ የለባቸውም። እኛ በፊታችን ልናገኘው የሚገባን አንድ መነሻ ብቻ ነው። ይኸውም የኢትዮጵያን ግዛት በእጃችን ልንጨብጠውና ልንመራው የተነሳንበትን ብቻ ነው" አለ። እነሱ ይመሩበት የነበረው ትክክለኛው ነገር ይህ ነው። እናሠለጥናለን የተባለው ሃሰት ነው።[6] ለወደፊቱም ቢሆን ይህን ነጥብ መሳት፣ ትልቅ መሳሳት ነው።

ማጣቀሻ ፅሑፎች

1. ጳውሎስ ኞኞ፣ *የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦርነት*፣ ገጽ 225።
2. ሞገስ ክፍሌ፣ *የሙሶሊኒ ምሥጢር*፣ ገጽ 145።
3. ፀሐፊው ራሱ የሚያውቀው።
4. ገሪማ ታፈረ፣ *ጉንደሬ በጋሻው*፣ ገጽ 38 እና 176።
5. ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፣ *ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ 1ኛ መጽሐፍ*፣ ገጽ 213።
6. ሞገስ ክፍሌ፣ ገጽ 71-134።

ምዕራፍ አርባ ሰስት
የእሥረኞችና የእሥር ቤቶች ሁኔታ

ኢትዮጵያውያን ከጣልያኖች እጅ ከተቀበሉአቸው የግፍ ሥራዎች አንዱ እሥራት ነው። እሱንም ለይቶ መመልከት ትምህርት ይገኝበታል። ስለዚህ ዋና ዋናውን ከዚህ እንደሚከተለው እንቃኛለን።

የእሥራቱ ሥርዓት እንደሌሎቹ የጣልያን ሥርዓቶች ሁሉ ግፍ የሞላበት ነበር። ምን ያህል ሰው እንደታሠረ ቁጥሩ በትክክል አልታወቀም። ብዙ አይደሉም እንጂ፣ ታሥረው የተፈቱም አሉ። የአንድና የሁለት ወር እሥራት እንደ አመክሮ ቢቀጠር ቅር አያሰኝም። ሦስት ወርና ከዚያ በላይ የታሠረው ግን ሁኔታው ሊጤንለት ይገባል። ስለዚህ ከሦስት ወር በላይ የቆየው እሥረኛ ብዛት ከ50,000 እስከ 60,000 እንደሚደርስ ቢገመት እምብዛም ስህተት አይሆንም።በእሥር ቤት የሞቱት ሰዎች ብዛት 3,500 እንደሆነ ተመዝግቦአል።[1]

ጉዳዩ (ዋናው ነጥብ) ያለው ከእሥር ቤቶቹ ሁኔታና ከአስተሳሰሩ ሥርዓት ጭምር እንጂ፣ ከእሥረኛው ብዛት ብቻ አይደለም። ኢትዮጵያውያን የታሠሩት ኢትዮጵያ ውስጥ ብቻም አልነበረም። ጣልያን በዚያን ጊዜ ተገዛቸው በነበሩ አገሮች፦ በሶማልያ፣ በኤርትራ፣ በጣልያን ጭምር ብዙ ኢትዮጵያውያን ታሥረዋል። ቢሆንም አብዛኞች የታሠሩት ኢትዮጵያ ውስጥ ነው።

በዋና ከተሞች ሁሉ እሥር ቤቶች ነበሩ። የአዲስ አበባው፣ አፍንጮ በር ባሻግር የነበረው ዘብጠያ፣ ዋናው ነበር። በወቅቱ በተለይ ጎንደር፣ ደብረ ታቦር፣ መተማ፣ አሥመራ፣ ሰጥሐይቅ፣ ደሴ፣ ደብረ ብርሃን፣ አዲስ ዓለም፣ ሐረር፣ ድሬዳዋና ጂማ የነበሩት በጣም ሥራ በዝቶባቸው ነበር። በተለይ በንጠር እስር ቤቶች የሚካሄደው ግፍ በከተማ እሥር ቤቶች ከሚካሄደውም የባሰ ነበር። በገጠር፣ በከተማና በውጭ ሐገር እስር ቤቶች ከተፈጸሙት የግፍ ሥራዎች፣ አንዳንዶቹን ከዚህ እንደሚከተለው እንመለከታለን።

ጎንደር፣ ጠገዴ አቶ መብራቱ ወንዲያ የተባለ ሰው እግሩን ወደላይ ራሱን ወደታች ተደርጎ ተዘቅዝቆ ታሥሮ አደረ። ጥዋት ሲወጣ ከጓደኛው ጋር ሲነጋገር ስለታየ፣ ምሥጢር አወጣ በሚል ጥርጣሬ በጥይት ተገድሎ በእሳት ተቃጠለ። ቀኛዝማች ዘለቀ ደስታ በጅራፍ እንደተገረፉ ቀኑ መሸ፣ እንደተገረፉ ሌሊቱ ነጋ። አቶ ሽርብ ተክላ በድብደባ ሞተ። አቶ ወልደ ገፈን ሽፍታ አሳድረሃል በሚል ምክንያት አሥራ ሁለት ራሱን እጅና እግራቸውን በሰንሰለት ታሥረው በእሳት ተቃጠሉ። ምርመራ የሚካሄደው በዱላ ነው። በድብደባ የሞተው ሰው እጅግ ብዙ ነው። ሥቃዩ እጅግ መራር ስለሆነ ላልሞተው ስሜቱ ለዕድሜ ልክ የማይረሳ ነው።

ጣልያኖች የምርመራ ወጥመዳቸው የተዘረጋው በሥጋ ላይ ብቻ አልነበረም። ምስክር አቁሞ ክነፍስ አባቱ ፊት ተናዘዝ ይለዋል። የነፍሱን ጉዳይ አስቦ እውነቱን ይናገራል። በዚያው አምኖአል ተብሎ ይገለጻል። ለእሱ ታማኝ የሆኑትን ቁሶች አቅርቦ እሥረኞቹን እንዲያናገሩ ያሣቸዋል። እነሱም "...ሳትናዘዙ ብትሞቱ ኃጢአት ነው። ብትናዘዙ ግን የኢጣልያ መንግሥት መሐሪ ነው ይምራችኋል።..." እያለ ይቀለምዳል። ቢቻል ለመማር፣ ካልሆነም ለመጽደቅ እውነቱን ይናገራሉ። ሃሰትም ቢሆን የተጠየቀውን የሚነግር ሊኖር ይችላል። እውነትና ሀሰት በጣልያኖች ዘንድ ልዩነት የለውም። የሁሉም ፍፃሜው ያው ሞት ነው። በደብረ ታቦር ወህኒ ቤት በየቀኑ ከአሥር ያላነሰ ሰው ይገደል ነበር።

የአንዱ እሥር ቤት ሁኔታ ስለሌሎችም እሥር ቤቶች ሀሳብ ይሰጣል። የጉንደር እሥር ቤት ዙሪያውን በሾክ የታጠረ ነበር። ቤቱ ግድግዳ እንጂ ጣራ አልነበረውም፤መውጫ መግቢያ ደጃፍ የለውም። እሥረኛ ከለበሰው ኮትና ሱሪ በስተቀር ሌላ የለውም። ዝናም ሲዘንም አሥረኛው እርስ በርሱ ይጠጋጋል። ፀሐይም ሲበረታ እንደዚሁ መጠጋጋትና የበረታው ለያዘመው ከለላ መሆን ነው። ሰው በብዛት ይሞታል። ሬሣውን እሥረኞቹ በአጥር አዘልለው ይጥሉታል። ሬሣ አንሺዎች ወዲያው ያነሱታል። በዚህ እሥር ቤት የታሠረው ከጉጃምና ከጉንደር የተሰበሰበ ነበር። ከሥቃዩ ብዛት የተነሣ ግደሉን እያለ ይጮሀል።

ጣልያን ለሥቃዩ ተጨማሪ እንዲሆን በዚሁ ዓይነት እንግልት እንዲሞቱ ያደርጋል። ጎንደር፣ ቁስቋም ዛኒ ገደል ላይ የነበረው እሥር የበለጠ አስቸጋሪ ነበር። ከዚህ ሁሉ ችግር አንዳንድ እሥረኞች አጥሩን በመዝለል ያመልጡ ነበር። ጣልያኖች እሥረኞች ምሕረት እንዳያገኙ በሚሰጡት አጣዳፊ ትዕዛዝ በስም መሳሳት የተገደሉም አሉ። ለምሣሌ ጎንደር ከተማ በእልታወቀ ቦታ በሥውር የታሠሩ አለቃ ወልደቂርቆስ መርሻ የተባሉ ሰው ምሕረት ቢደረግላቸው፣ ትዕዛዙ ከመድረሱ በፊት በተመሰደው አስቸኳይ እርምጃ በእሳቸው ፈንታ አለቃ ማርቆስ የተባሉ ጐጃሜ ተገደሉ። በራሳቸው ሥራ ጥፋት ሳይገኝባቸው ልጅህ፣ ወንድምህ በመንግሥት ላይ አምጸአል በመባል በጣልያን እየታሠሩ የተንገላቱ እጅግ ብዙ ናቸው። የተገደሉም አሉ።[2]

በአዲስ አበባ ከየካቲት 12 ቀን 1929 ዓ.ም ግርግርና አሪመኔያዊ ጭፍጨፋ በኋላ፣ ጣልያኖች ከሞት የተረፈውን ሰው እየሰበሰቡ በፈረስ ቤት፣ በአቃቂና ከደጃዝማች ውቤ ሠፈር ከነበረው እሥር ቤት አጎሩት። ራስ ደስታና ደጃዝማች በየነ መርድ ሲሞቱ ከጉራጌ አገር የተማረከውን፣ ራስ እምሩ ኃይለሥላሴ እጅ ሲሠጡ ጦጀብ እጅ የሰጠውን ጨመሩበት። እንደ አለቃ ዓለሙ ያለ የከተማ ቀልደኛ ሳይቀር ስበሰበ። ጠንቋዩን፣ ሰባኪውን፣ ቃልቻውን፣ ባሕታዊውን፣ ካህናቱን አከሉበት። እንደዚህ አድርገው ከሰበሰቡት አሥረኛ ከፊሉን ወደ ሞቃዲሾ፣ ከፊሉን ወደ ኤርትራ፣ ከፊሉን ወደ ኢጣልያ

ወሰዱት። የእያንዳንዱን አሥረኞች ቡድን ሁኔታ ማየት አጠቃላይ ግንዛቤ ሊሰጥ ይችላል።

ወደሞቃድሾ የተወሰደው ቡድን መጋቢት 12 ቀን 1929 ዓ.ም ከየቦታው ተሰብስቦ ኑፉ ሥልክ ተከማቸ። በማግስቱ መጋቢት 13 ቀን 120 ካሚዮን አቅርበው በአርባ በአርባ እየቆጠሩ አሳፈሩት። በጠቅሳሳው ከ4,800 እስከ 5,000 አሥረኛ መሆኑ ነው። ወንድና ሴት፣ ልጅና አዋቂ፣ ሕመምተኛና ሽማግሌ አልተመረጠም። ጠባቂ ዘበኞች አብረው ተሳፍረው ጉዞው ቀጠለ። መንገዱ ከአዲስ አበባ ድሬዳዋ፣ ከዚያ ሐረር። ከሐረር በጅጅጋ፣ በቀበሪ ደሐር፣ በምያሌ በኩል አልፎ ሞቃድሾ መግባት ነው። በመንገድ ላይ የነበረው አበሳ እጅግ ከባድ ነበር። ልጆዋ በክንድዋ ላይ ሙቶ የቀኑ ጉዞው አስኪያበቃ ድረስ ሬሣ ታቅፋ የተጓዘች ሴት ነበረች። በየመንገዱ ያለቀው ሰው ብዙ ነው። አሥረኛ በዚህ ዓይነት ተጉዞ ሚያዝያ 30 ቀን 1929 ዓ.ም ደረሰ።

በዚያ የነበረው ቆይታ ደግሞ በመንገድ ላይ ከታየው አበሳ የበረታ ሆነ። ሀገሩ ቆላማ ከመሆኑ ጋር ከህንድ ውቅያኖስ ባህር ጠርዝ ላይ ስለሆነ፣ አርጥበት የቀላቀለ ከባድ ሙቀት አለው። እንደ መቀቀል ያለ ሆነ። እንጨት ሰብሮ፣ ውሃ ቀድቶ ተሸክሞ ማምጣት፣ በሐሩር ፀሐይ ቂጣ ጠፍጥፎ መብላት ትንሽና ትልቅ አላለም። በዚህ ላይ ደግሞ በየምክንያቱ በሰማሌ ዘበኛ መረገጥ መደብደብ አለ። ከአንድ ዓመት በኋላ ደግሞ የትኩሣትና የተስቦ፣ የተቅማጥ በሽታ ገብቶ በአራት ወር ውስጥ 1,000 ሰው ገደለ። መግደል ብቻ ሳይቀር እያቃዠ፣ እያስከዳ አሰቃየው።

ከአንድ ዓመት ተኩል ቆይታ በኋላ ጣልያኖች አዲስ ፈሊጥ አመጡ። ለአንድ ሰው ለመተኛ አንድ ሰሌን፣ ለመብሊያ አንድ ሣህን፣ ለውሃ መጠጫ አንድ ክብያ መስጠታቸውና የበቆሎ ጹቁት ሰቀሰብ በነፃ መሥፈራቸው ቆጫቸው። አሥረኛው ሠርቶ ይብላ አሉ። አሥረኞቹ ጀናሲ ወደሚባለው አንድ መቶ አሥራ ሰባት የእርሻ ሁዳድ /ኮንሴሲዮን/ ወደ አሰበት ቦታ ተወሰዱ። ለእያንዳንዱ ሁዳድ እንደፍላጐቱ አርባም አምሳም ሰው ተደለደለሰት። ሥራው በደማ መቆፈር ሙዝ መትከል ነው። በኮንትራት የተሰጠውን ሥራ ከጨረሰ ጥቂት ገንዘብ ስለሚሰጠው ራቱን ይበላል። ያለዚያ ጦሙን ያድራል።[3]

በዚህ ዓይነት መከራቸውን ከአዩ በኋላ፣ የሞተው ሞቶ የተረፉት አሥረኞች ተለቀቁ። የተለቀቁትም ጣልያን ከአርበኞች ጋር ለመታረቅ ድርድር በጀመረ ጊዜ፣ ከአርበኞች ወገን ከቀረቡለት ጥያቄዎች አንዱ አሥረኞች እንዲለቀቁ የሚል ስለነሆነበት ነበር። በዚህ ምክንያት በ1932 ዓ.ም ስለፈታቸው ተመልሰው አገራቸው ገቡ።

ሁለተኛው በርካታ ቡድን የተላከው ወደ ኤርትራ ነበር። በኤርትራ የታሠሩት ናኩሩ፣ ናቅፋ ነበር። የተወሰዱት በየጊዜው ከየቦታው ስለነበር

ቁጥራቸው በትክክል አልታወቀም። እስከ አንድ ሺህ ሳይደርሱ አልቀሩም። ሆኖም እዚህም ሥፍራ አሥራቱ ችግርና መከራ የሞላበት ነበር። እንግሊዞች ሀገሩን ከያዙ በኋላ ልዑል መኮንን ኃይለሥላሴ ከንጉሠ ነገሥቱ ታዝዘው በየአሥር ቤቱ እየዞሩ በመርመር፣ ኢትዮጵያውያንንም ኤርትራውያንንም በብዛት እንዳስፈቱ በ1949 ዓ.ም ልዑልነታቸው በሞቱ ጊዜ አብረው የተፈቱ ኤርትራውያን እያዘኑና እያለቀሱ ነግረውኛል።

ሴላው የአሥረኛ ቡድን የተወሰደው ወደ ጣልያን ሀገር ነው። ወደዚያ የተወሰዱት እንደነራስ እምሩ፣ ራስ ኃይሉና ራስ ሥዩም ያሉ መሣፍንት፣ እንደነልጅ ይልማ ዴሬሣና አቶ ሐዲስ ዓለማየሁ ያሉ የተማሩ ወጣቶች፣ እንደነልዕልት ሮማነ ወርቅ ኃይለሥላሴ የመሳሰሉ ንጉሣውያን ቤተሰቦችና እንደነዘርዓይ ደረስና ሻምበል አብዲሣ አጋ የመሳሰሉ የጦር ሰዎች ነበሩ። የታሠሩትም አዚናራ፣ ፖንዛ፣ ሊፖሪ፣ ሎንጉቡክ፣ በመሳሰሉት ቦታዎች ነበር። አንዳንዶችም ሮም ቆይተዋል። አሥራቱም በሌሎች ቦታዎች የታየውን ያህል የሚያሰቃይ አልነበረም።[4]

ችግሩ መገደሉ መታሠሩ ብቻ አልነበረም። ሥርዓታቸው ቅጥ ያጣ መሆኑ ጭምር እንጂ። አንዳንድ ሁኔታዎችን ለማስረዳ እንጠቅሳለን። ጐንደር አቶ ንጋቱ ሪታ የተባለ ሰው ልብስህ ለምን እደፈ ተብሎ በጥይት ተደብድቦ ሞተ። ሴላ ልብስ አለኝም ለማጠብም አልተመቸኝም ማለቱ አላዳነውም። ሌላው ዘለቀ ኃይሉ የተባለ ቆፍጣና ወጣት ደግሞ ያማረበት መስሎት ነጭ ሱሪ ታጥቆ፣ ነጭ እጀ ጠባብ አጥልቆ፣ ነጭ ኩታ ለብሶ ከተማ ቢወጣ ተደበደቡ። እሱ በጫማ፣ ልብሱም ከጭቃ ጋር ተረጋገጠ።[5]

በጎዳር ወር 1933 ዓ.ም ቡልጋ መገዘዝ፣ ጌሬ በተደረገው ጦርነት፣ ገብረዓድቅ ደመና የተባለ የ14 ዓመት አርበኛ ተማረከ። ዕድሜው 14 ወይም 15 ዓመት ቢሆነው ነው። በምርመራ አሳብበው በድብደባ ብቻ ገደሉት።[6]

ጣልያኖች የፈጸሙትን የግፍ ሥራ የሚያጣራ አንድ ኮሚሽን አዲስ አበባ ላይ ተቋቋመ። ለዚህ ኮሚሽን ቃል ከሰጡት ሰዎች አንዱ ብላታ በቀለ ሀብተሚካኤል፣ ደናኔ አሥር ቤት በነበሩ ጊዜ የሚሰጣቸው ምግብ ብዙ ትላትሎች የሚታዩበት ደረቅ ቂጣና ሻይ እንደነበር፣ በምግብ ብላሽነት ምክንያት በየቀኑ አራትና አምስት ሰው ይሞት እንደነበር አስረድተዋል። ሌላው ምስክር አቶ ሚካኤል ተሰማ ደግሞ የሚሰጣቸው ደረቅ ጋሲጣ እንደነበርና በውሃ ጥም ምክንያት የጨው ውሃ መጠጣት ግድ ስለነበረ፣ በጠቅሳሳው ከ6,500 አሥረኞች ውስጥ 3,175 ሰው ማለቁን አስረድተዋል። ከዚህ በስተቀር በሥራ ቦታ ድካም የሚያሳዩ ሰዎች፣ እጆቻቸውን የኋሊት እየታሠሩ እስከ ሰባት ቀን ከቤት ጣሪያ ላይ ይንጠለጠሉ እንደነበር አመልክተዋል።[7]

በአጠቃላይ ሲታይ ኢትዮጵያውያንና ጣልያናውያን ተጻራሪ ባሕርያት አሉአቸው። ኢትዮጵያዊ ጸተኛ፣ ጨልያናዊ ችኩል ነው። በኢትዮጵያውያን

ዘንድ ጭምትነት፣ በጣልያናውያን ልፍሰፋ ያበዛል። ኢትዮጵያዊ ትዕግስተኛ ሲሆን፣ ጣልያናዊ ቁጡ ነው። እነዚህ ሁኔታዎች በሁሉም ኢትዮጵያውያንና በሁሉም ጣልያናውያን ላይ ሁልጊዜ ባይታዩም፣ በአብዛኛው ሁኔታው እንደዛ ነው። ሁሉቱ ወገኖች በተጋጠሙ ጊዜ፣ እነዚህ ተጻራሪ ስሜቶች፣ ባሕርያት ሳይከሰቱ አልቀሩም። ያም ቢሆን ግን ለጣልያኖች ጭካኔ በቂ ምክንያት አይገኝለትም።

ማጣቀሻ ዕሑፎች

1. ጳውሎስ ኞኞ፣ *የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦርነት*፣ ገጽ 225።
2. *ገሪማ ታፈረ፣ ጉንደሬ በጋሻው*፣ ገጽ 28-35፣ 153-172 208-211።
3. ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፣ *የኢትዮጵያ ታሪክ ለአፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ*፣ ገጽ 279-284።
4. ሐዲስ ዓለማየሁ፣ *ትዝታ*፣ ገጽ 204-252።
5. ገሪማ ታፈረ፣ ገጽ 29 እና 211።
6. እኔ ራሴ የማውቀው።
7. ጳውሎስ ኞኞ፣ ገጽ 159-160።

ምዕራፍ አርባ አራት
የድርጅት ጥያቄ በአርበኞች ዘንድ

ኢትዮጵያውያን ከአለባቸው ችግር፣ በድርጅት ተባብሮ መሥራት ነው። ሁሉም የወደደውን ሥራ በወደደው ዓይነት፣ ለአሉ ባሰኘው ጊዜና ቦታ መሥራት ይፈልጋል። የቻለውን ሠርቶ ለራሱ ስም ማውጣት፣ ክብር ማግኘት ይፈልጋል። ለድርጅት ደንታ የለውም። ሕግ የሚያከብረው፣ ሥርዓት የሚጠብቀው፣ ትክክል መስሎ እስከታየውና መብቱ እስከ ተከበረለት ድረስ ነው። ማዘዝ እንጂ መታዘዝ አይወድም። የበላይ እንጂ የበታች መሆንን አይቀበልም። በዚህ ውስጣዊ ባሕርይ የተነሣ፣ በሕግ ሳይሆን ለሰው ሲገዛ ይኖራል።

ለሰው የሚገዛው ደግሞ ለማንም አይደለም፤ አሱ ለወደደው ነው። ሰውን የሚወድና የሚጠላባቸው መሥፈርቶች አሉት። ከቦታ ቦታ ቢለያዩም መሥፈርቶቹ አንድ ዓይነት ናቸው። አንድ ሰው በኢትዮጵያውያን ዘንድ ክብርና ሞገስ ለማግኘት በኃይማኖቱ ጽኑዕ መሆን አለበት። ብርቱና ጀግና መሆን ያስፈልጋል። ቸር፣ ትሁት፣ ሰው አክባሪ፣ ሕግ አዋቂ፣ ሥነ ሥርዓት አጥባቂ መሆን አለበት። አውነተኛና ትዕግስተኛ መሆን ያስፈልገዋል። እነዚህን ያምዋላ፣ የቅርብ የሕዝብ አመኔታ ያገኛል። በአንጻሩ ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚጠላና የሚጠየፋቸው ነገሮች፣ ከዚህ በላይ ከተገለጹት ባሕርያት ውጭ የሆኑትን ነው። በኃይማኖት ጽንአት የሌለው ሰው ለምንም ጉዳይ አይታመንም። ፍቅረንዋይ የተጠናወተው ሰው እምነት አይጣልበትም። ትዕቢተኛ፣ እብሪተኛ አይወደድም። ፈሪ አይከበርም። ችኩልና ቆጭባራ፣ ቁጡ፣ ለመረጎት አይመረጥም። የጭዋና የባለጌ መለያ መሥፈርቶች እነዚህ ናቸው። መልክና ሙሰና (ማለትም፡- የሚስብ ገፅታ) ተደራቢ ጸጋዎች ናቸው።

በአርበኝነት ሥራ ውስጥ በሰው አመራረጥ ረገድ እነዚህ መሥፈርቶች እውን ነበሩ። ከሌላው ተለይቶ ለአንዱ የሚያብረው፣ በአብዛኛው በእነዚህ መለኪያዎች መሠረት ነው። በግል ጠብ ወይም ግጭት ካልሆነ በስተቀር፣ በሌላ ምክንያት ከአለቃው አይለይም። አንዳንድ ነገረ ሠሪዎች በአካሄዱአቸው ተንኰሎች የተነሣ ካልሆነ በስተቀር፣ ከዚህ ውጭ በሆነ ምክንያት የተለያዩ አርበኞች አላየሁም።

ጣልያን ኢትዮጵያን በወረረች ጊዜ በንጉሠ ነገሥቱ ከሚመራው ማዕከላዊ መንግሥት በቀር ሌላ ምንም ጠንካራ፣ ሀገር አቀፍ ድርጅት አልነበረም። አሳቸው አገር ጥለው በሄዱ ጊዜ፣ ያው አንዱ ማዕከል ጠፋ። በየግል ጥረታቸው የሕዝብ አመኔታ አግኝተው የነበሩት ታላላቅ የጦር መሪዎች ቀደም ብሎ በተካሄደው የሥልጣን ሹኩቻ ረግፈው ስለነበር፣ አልተገኙም። አዲስ የተኮለኮሉት ሹማምንት ደግሞ የሕዝብ አክብሮት

ስለአልነበራቸው ለመሪነት ብቁ ሳይሆኑ ቀሩ። ስለዚህ አመራርን በተመለከተ ሀገር ባዶ ሆነች።

አርበኞች አዲስ መሪ ለማውጣት ተፍጨረጨሩ። የገጠሩ ሕዝብ ከንጉሥ በስተቀር የሚያውቀው ነገር የለም። የተማረው ወጣት በበኩሉ ድርጅት ማቋቋም ፈለገ። የቀዳማዊ ኃይለሥላሴም ወገኖች ሌላ መሪ እንዳይመጣ ውስጥ ውስጡን ነገር ማካሄድ ያዙ። ሁኔታው ፋታ የሚሰጥ አልሆነም። ጣልያን የነበረውን ባህላዊ አቅዋም በፍጥነት ማፈራረስ ያዘ። ሁሉም በየበኩሉ የሚሻል የመሰለውን አደረገ።

የቀድሞውን የፊውዳሉን ሀገር በአዲስ ሕዝባዊ አስተዳደር ለመተካት በማሰብ፣ አቶ /ብላታ/ ታከለ ወልደሐዋርያት ሪፓብሊክ መንግሥት ለማቋቋም ሞከሩ። ነገር ግን ጉዳዩ በሀገሪቱ ላይ የጥፋት ጥላ በአንጣበበት ጊዜ ሊፈፀም የሚችል አልሆነም። በሀገር ውስጥም፣ በሱዳንና በኬንያ በነበሩ ስደተኞች ዘንድም ተደጋግሞ ቢሞከር፣ ውጤት ሳያስገኝ ቀረ። የሥርዓት ለውጥ ለማምጣት መሞከር በሰላም ጊዜ እንጂ በጦርነት ጊዜ አይደለም። በጦርነት ጊዜ የሚሻለው፣ ቀድሞ በነባረውና ሕዝብ በለመደው ሥርዓት መሥራት መሆኑ ታዬ።

ይህ ማለት የአቶ /ብላታ/ ታከለ አመለካከት ስህተት ነበር ማለት አይደለም። ጣልያን ኢትዮጵያን ለመውረር ምክንያት ያደረገችው "ኋላቀር ናት፣ ባሪያ ይሸጥባታል፣ ሞቆና ይካሄድበታል። እኔ ላሠለጥናት ይገባኛል" በሚል ምክንያት ነበር። በሀገር ውስጥ ጉዳይ ደግሞ በለማራውም ሆነ በተቀረው ክፍለ አገር የገባር፣ የጉልት፣ የቄሰኛ ሥርዓት ባለመሻሻሉ ችግር ነበር። ከዚህም በስተቀር በንግሥ ምክንያት በሸዋ፣ በጉንደር፣ በትግሬ መሣፍንት መካከል የነበረው የግለሰብና የቡድን ትንንቅ ሳይቀዘቅዝ፣ የጉጃምና የወሎ ተጨምሮ በየጊዜው ጠብ እየተቀሰቀሰ ያስከተለው ጠንቅ ሕዝቡን አስቸግሮት ነበር። በደቡብ ደግሞ የነፍጠኛው ሥርዓት ሠፍኖ አፍላ ደረጃ ላይ ደርሶአል። የባሪያ ሽያጭና የዛው ንግድ ሥራ በወረቀት ደረጃ እንደቀረ ቢቆጠርም፣ በሕይወት ውስጥ ገና ሕያው ነበር። በቤተክህነትና በቤተመንግሥት መካከል የነበረው ትሥሥር በመላላት ፈንታ ጠበቀ። የአደባራት አለቆች የሚሾሙት በንጉሠ ነገሥቱ ሆነ።

የሪፐብሊክ መንግሥት አቋቁሞ እነዚህን ሁኔታዎች መለወጥ ታላቅ ጠቀሜታ ነበረው። በአንድ በኩል የአውሮፓ አገሮች ስለኢትዮጵያ የነበራቸውን ዝቅተኛ አመለካከት ለውጦ በአዲስ አመለካከት ለመተካት ያስችላል። በሌላ በኩል በሀገር ውስጥ የነበረውን ጠንካራ ባሕላዊ አገዛዝ ያስወግዳል። እንዲሁም ከአዲሱ ሥልጣኔ ጋር ተጣምሮ በማቆጥቆጥ ላይ ያለውን ብዝበዛ በአንጭጩ ይቀጫል። ባርነትንና ጭቆናንና ያስቀራል። ንጉሠ ነገሥቱን በሀገር ክህደት ተጠያቂ አድርጉ ዘውድን ይገረስሳል። በዘውድ ሽሚያ ምክንያት በሚቀሰቀሱ ጦርነቶች የሚያልቀውን ሕዝብ ያድናል።

ከጣልያን ጋር በመዋጋት ለሀገር የመከላከሉ ጉዳይ የአማራው ብቻ መሆኑ ቀርቶ የጠቅላላው ሕዝብ እንዲሆን ያደርገዋል። የአቶ /ብላታ/ ታከለ ወልደሐዋርያት ሃሳብ ለብዙ ጊዜ ሲያነጋግር፣ ሲያመካክር የቆየው በዚህ ሁሉ ምክንያት ነበር። ግን በወቅቱ ሊፈፀም አልቻለም።

አርበኛው በነሐሴ ወር 1928 ዓ.ም አምቦ አካባቢ ባደረገው ስብሰባ ከውስጡ መሪዎችን መረጠ። ባላምባራስ /ራስ/ አበበ አረጋይን ጠቅላይ የጦር አዛዥ አደረገ። ግራዝማች /ደጃዝማች/ ዘውዱ አስፋውና መቶ አለቃ /ጀነራል/፣ ኢሣያስ ገብረሥላሴ ደግሞ ሕዝብ አስተባባሪ ሆኑ። አቶ /ብላታ/ ታከለ ወልደሐዋርያት የጸሐፊነቱን ሥራ በደስታ ተቀበሉ። የምክር ቤት አባላትም አብረው ተመረጡ። በዚህ ውስጥ ደግሞ መቶ አለቃ /ጀነራል/ ዓብይ አበበና መቶ አለቃ /ጀነራል/ መርዕድ መንገሻ ነበሩበት።[1] ይህኛውም ድርጅት ውጤት አልሰጠም።

የድርጅትን አስፈላጊነት በወቅቱ የተረዱት ሌሎቹ ሰዎች፣ የሆለታ ጦር ትምሕርት ቤት ምሩቃን ነበሩ። ከሆለታ የጦር ትምህርት ቤት የተንቀሳቀሱት በሌተና ኮሎኔል ክፍሌ ነሲቡ መሪነት ነበር። ኮሎኔሉም በፈረንሣይ አገር የጦር ትምህርት የተማሩ ስለነበሩ፣ ወጣቶቹ መኮንኖች እምነት ጣሉባቸው። እሳቸውም በጦር ትምህርት ቤቱ ኃላፊነት ላይ የነበሩ መኮንኖች በዚያው ሥራቸው እንዲቀጥሉ በማድረግ፣ ጦሩን መርተው ለቀምት አገቡት። ከዚያም በየጊዜው ስብሰባ እየተደረገ ይመክር ነበርና አንድ ምክር ቤት ተመርጦ ተሰየመ። የጦሩም ስያሜ ጥቁር አንባሳ ተባለ። ስኔ 29 ቀን 1928 ዓ.ም በተደረገው ስብሰባ የጥቁር አንበሳ አርማና መተዳደሪያ ሕግ ወጣ። ድንጋጌው ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴና ከወራሾቻቸው ሌላ ላለማወቅ ወሰነ። ዶክተር ዓለመወርቅ በየነ የአርማው ፕሬዝዳንት ሆኑ። ሌሎች ሃያ ሰባት የምክር ቤት አባላትም አብረው ተመረጡ። ለጦር አሠልጣኝነት ደግሞ ሌሎች አሥራ ዘጠኝ ተመረጡ። የሥልጠናው ሥራ የበላይ አለቃ በላይ ኃይለአብ ሆኑ።[2] ይህ ጦር በዚህ ዓርማ ሥር ጸንቶ ቆየ። ጉደብ አጄን እስከሰጠበት ቀን ድረስ በጥንካሬ ለሀገር ተከላከለ።

ራስ እምሩ ከሰሜን ጦር ግንባር ተመልሰው ጉንደር እንደገቡ፣ ጀግኖች ጥቂት በጥቂት እያሉ አበሩላቸው። ከጉጃምም መጠነኛ ሰው ተከተላቸው። የወለጋና የኢሉባቡር ሰራዊት አበረሳቸው። ጉራ በገቡ ጊዜ በቂ ድርጅት ነበራቸው። ንጉሠ ነገሥቱ የእንደራሴነቱን ሥልጣን ሰጡአቸው። ራስ እምሩም መደበኛውን ሠራዊታቸውን በአንድ ወገን፣ የጥቁር አንበሳን ጦር በአንድ ወገን በመምራት፣ ተከትሎአቸው የነበረውን ሰላማዊ ሕዝብ ለማዳን ሲሉ በታህሣሥ ወር 1929 ዓ.ም ጉደብ ላይ እጃቸውን እስከ ሰጡበት ጊዜ ድረስ በታላቅ ችሎታ አመራር ሰጡ።

ሌላው ድርጅታዊ እንቅስቃሴ የተካሄደው በቡልጋ ነው። በወቅቱ ከተደረጉት ሙከራዎች ሁሉ የተሻለ ውጤት ያስገኘው እሱ ስለሆነ በቀረቤታ

መመልከት ይገባል። በቡልጋ ውስጥ አርበኞች እርስ በርሳቸው በመመራረጥ የመጣውን ጠላት በመከላከል ንጉሠ ነገሥቱን ለመጠባበቅ ምክሩ። የበረከቱን ፊታውራሪ ኃይለሥላሴን መረጡ። በእሳቸው መሪነት በወና፣ በአመየት ሀገር፣ በበረከት ታላላቅ ጦርነቶች ከአካሄዱ በኋላ፣ አሳቸው ጥር 2 ቀን 1929 ዓ.ም ከጠላት እጅ ወደቁ። መጀመሪያ ወደ ደብረ ብርሃን፣ ከዚያም ወደ አንኮበር በከፍተኛ መንገላታት ከተወሰዱ በኋላ፣ ጥር 10 ቀን 1929 ዓ.ም ከጦር ጓደኞቻቸው ከእነባላምባራስ ይልማ ወልደኢየሱስ ጋር በጠላት እጅ ተገደሉ። ጠሩም ተበተነ። በዚህ ጊዜ አለቃ ወልደፃድቅ ዘውዴ ብቻ ከሁለት ወታደሮቻቸው ከአቶ /ቀኛዝማች/ ገብረመስቀል ኃይሴና ከአቶ ጨፍቂ ይገዙ ጋር ቀሩ። አሽከራቸው እንድረስና አቶ ዘለቀ ወልደ ጻድቅም አብሮ ነበር። ጨፍቄም ከድቶ ለጣሊያን ገባ።

አለቃ /ፊታውራሪ/ ወልደፃድቅ ዘውዴ ከጥር 2 እስከ ሰኔ 30 ቀን 1929 ዓ.ም ያለውን ጊዜ ሦስት ራሳቸውን ሲታገሉ ከቆዩ በኋላ፣ ክረምቱ ሲገባ ጓደኞቻቸውን አሰባሰቡ። እነ /ቀኛዝማች/ ስንቅነህ፣ እነ ግራዝማች /ፊታውራሪ/ አጉናፍር ባዩ አበሩላቸው። ሐምሌ 21 ቀን 1929 ዓ.ም ጭቃ ቆላ የተደረገውን ጦርነት መርተው ድል አገኙ። በዛ ውጊያ ከስድስት መቶ በላይ ደረቅ ብረት ተማረከ። በርካታ ሠራዊት አበረሉላቸው። ከመኪና መንገድ በስተምሥራቅ ያለውን አገር ሕዝብ አስተባበሩ።

ይህ ድል በጠላት ፊት ብዙም እንደማይቆይ ቀደም ብሎ በእነ ፊታውራሪ ኃይለሥላሴ ላይ በደረሰው ሁኔታ ታይቶ ነበርና፣ በተገኘው ድል ከመኩራራት ይልቅ አንድ ድርጅት ማቋቋም እንደሚሻል ታወቀ። በአርበኛው መሪዎች መካከል በረከት አካባቢ ልዩ ልዩ ስብሰባዎች ተካሄዱ። መስከረም ሲጠባ ጣልያን በአዲስ ኃይል እንደሚመጣ የታወቀ ነው። ይህ ከሆነ የገበሬው ተሳትፎ ይቀንሳል፣ ሠራዊቱም ለጥቃት ይጋለጣል። ከአርበኛው መካከል አንዱን መሪ ማድረግ፣ አድናቂ እንጂ ደጋፊ አላስገኘም። ንጉሠ ነገሥቱ ዕርዳታ ይዘው ይመጣሉ የሚሰው ተስፋ ከአንድ ዓመት ከሦስት ወር ትግል በኋላ እየሻከረ ሄደ። አንድ ሕዝብ የሚከተለው መሪ ማውጣት ግድ ሆነ።

ነሐሴ 20 ቀን 1929 ዓ.ም ቅዳሜ፣ ወክፊሌ በተደረገ የአርበኛ መሪዎች ጉባዔ ላይ ይህ ጉዳይ ለንግግር ቀረበ።

አለቃ /ፊታውራሪ/ ወልደፃድቅ ዘውዴ አዲስ ሃሳብ አቀረቡ። እሱም "የልጅ ኢያሱን ልጅ እናንግስ" የሚል ነበር። እጅግ አከራከረ። የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ደጋፊዎች ተቃወሙ። በንጉሥ ላይ ንጉሥ እንዴት ይሆናል አሉ። በጭንቅ ጊዜ አገር ጥሎ ለሄደ ንጉሥ መከራከር የሚያስከብራቸው አልሆነም። ሌላ ንጉሥ መንገሱ ሲሰማ፣ ጣልያን ሊያጠፋን ይነሳል ያሉም ነበሩ። መልሱ አሁን ምን እያደረገን ነው? ሆነ። ክርክሩ ጠነነ። አለቃ /ፊታውራሪ/ ወልደፃድቅ ዘውዴ "ንቡ ሰዎች፣ አንድ ሰው ስለሸሸ ሁላችን እናልቃለን?" አሉ። ይህቺ ጥያቄ ሰተኑሣው ክርክር መዝጊያ ሆነች።

ለአርበኝነትም፣ ለእሳቸው ሰራሳቸው ሕይወትም ውሣኔ ሆነች። ክርክሩ አከተመ። አርበኛው በሃሳቡ ተስማማ።

አለቃ /ፊታውራሪ/ ወልደፃዲቅ ዘውዴ ይህንን ሃሳብ ያቀረቡት፣ እንግዳ እሸት ኃይሌ በሚል ስም ይታወቅ የነበረውን የልጅ ኢያሱ ምኒልክን ልጅ በአብዬ ገዳም ከአባ ይርዳው እጅ ወስደው ስለነበር፣ ነጋሢውን የማግኘቱ ጉዳይ አላስቸገረም። ስለዚህ ውጣቱ እንግዳእሸት ነሐሴ 21 ቀን 1929 ዓ.ም መልአከ ፀሐይ ኢያሱ ምኒልክ ተብሎ ነገሠ።

ንጉሠ ነገሥት መልአከ ፀሐይ ኢያሱ ምኒልክ ከነሐሴ 21 ቀን 1929 ዓ.ም ጀምሮ በተከታታይ ሹመት ሰጡ። አለቃ ወልደ ፃደቅም ፊታውራሪ ተባሉ። ከተሰጡት ሹመቶች ታላቁ ለባሳምባራስ አበበ ሚያዝያ ወር 1930 ዓ.ም ጀሉ አገረ ማርያም የተሰጠው ነበር። ምንም ንጉሡ መስከረም 27 ቀን 1931 ዓ.ም አንኮበር፣ ቆቦ ቢሞቱም፣ ሥራቸው ሕያው ሆነ።[3] የሾሙአቸው ሹማምንት የአቋቋሙት ሠራዊት ሃሳቡን ሳይለውጥ፣ ዓላማውን ሳያጥፍ እስከ መጨረሻው ተዋጋ። ኢትዮጵያንም በዓለም አሳወቃት፣ ለድል አበቃት።

ነገሩ ተሸፋፍኖ ይቅር እንጂ በጐንደርና በወሎም ልጅ ዮሐንስ ኢያሱ ምኒልክን ለማንገሥ መክራ እንደ ተደረገ አንዳንድ የታሪክ ማሰረጃዎች አሉ። ሰኔ 8 ቀን 1930 ዓ.ም ላስታ፣ አብጣ ተክለሃይማኖት ተገናኝተው በልጅ ዮሐንስ አመራር ለመጠቃለል ተስማሙ። ስብሰባውን ያቀነባበሩት ደጃዝማች ገብሬ ነበሩ። ብላታ ታከለ ወልደሐዋርያትና ብላታ ደሬሣ ጉብጽ አገር ዘውድ እስከ ማሠራት ደርሰዋል።[4] በመሥፍኑ ድንገተኛ ሞት ቀዘቀዘ እንጂ፣ በውጪ አገር በነበሩ ስደተኞችም መካከል የልጅ ግርማ ኢያሱ ሁኔታ ልዩነት መፍጠሩ አልቀረም።

የበጌምድር አርበኞች በየአለቡት ከመከሩ በኋላ አጠቃላይ ስብሰባ አደረጉ። በጠቅላላው ጉባዔ ላይ በሦስት ነጥቦች ላይ ስምምነት ተደረገ። ስምምነት የተደረገውም አንደኛ በመራራ ተጋድሎ ንጉሠ ነገሥቱን ለመጠበቅ ተስማሙ። ይህ አባባል በጉዳዩ የንጉሠ ነገሥቱ እጅ እንደነበረበት ያመለክታል። ሁለተኛው ነጥብ አርስበርስ ለመረዳዳት ተስማሙ። ሦስተኛው ጀግንነታቸውን በግብር ላረጋገጡ አርበኞች የማዕረግ ስም እንዲሰጥ ተደረገ። በዚሁ ስምምነት መሠረት ግራዝማች አሞራው ውብነህ ራስ ተብለው ጠቅላይ የጦር አዛዥ ሆኑ።[5] ይህ አካሄድ አርበኛውን ለጊዜው ያጠናከረው ቢሆንም፣ የተጠበቀውን ያህል ድርጅቱ ጽንአት አላገኘም።

ሕዝብ በበኩሉ ማኅበር እያቋቋመ ለሀገሩ ተከላከለ። በየቦታው የጉበዝ አለቃ እየመረጠ ተዘጋጀ። በጉጃም የዲማ ጊዮርጊስ፣ የደብረ ወርቅ ማርያም ማኅበር አቋቋመ። እንደዚሁም ጉታ፣ ገበርማ ከተባለ ሥፍራ ሕዝባዊ ማኅበር አቋቋመ። በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ወጣቶች የተሰፋ ማኅበር የሚል ተቋቁሞ፣ ስደተኞችን የተቻለውን ያህል ረድቶአል።[6]

አብዛኞቹ የአርበኛ ቡድኖች በሠራዊቱ የሚመረጡ፣ ወይም ከኮር አለቆች የተውጣጡ የጦር ምክር ቤቶች ነበሩአቸው። በንጉሠ ነገሥት መልአከ ፀሐይ ኢያሱና በራስ እምሩ የሚመሩት ሠራዊቶች ጠንካራ ምክር ቤቶች ነበሩአቸው። ነገር ግን ምክር ቤቶቹ መልአከ ፀሐይን ከሞት፣ ራስ እምሩን እጅ ከመስጠት አላዳኑም። እስከ መጨረሻው ድረስ ሠራዊታቸውን በመምራት ለድል ከአበቁት ምክር ቤቶች አንዱ በበላይ ዘለቀ የተመራው የአርበኛ ምክር ቤት ነው።[7]

ከማኅበራት ሁሉ የተሻለ ውጤት ያስገኘው ጥቅምት 23 ቀን 1931 ዓ.ም ተጉለት፣ ሣሲት ላይ የተመሠረተው ማኅበር ነው። ውጤቱ የተሻለ መሆኑ ደግሞ አመሠራረቱ እንደምን እንደ ነበር እንድንመረምር ይጠይቀናል።

ንጉሠ ነገሥት መልአከ ፀሐይ ኢያሱ ምኒልክ መስከረም 27 ቀን 1931 ዓ.ም አርፈው በሸዋ አርበኞች መካከል መናጋት እንዳይደርስ አስግቶ ነበር። በንጉሡ ህልፈት የተፈጠረው ስሜት፣ በወቅቱ በቡልጋና በመንዝ እንደጋለ ቆየ። ጠላትም በዚህ አመች ሁኔታ ሰመጠቀም፣ በዛ አካባቢ አርበኞችን ከምድር ገጽ ለማጥፋት ተንቀሳቅሶአል። ከዚህ ችግር ገለልተኛ የነበረውና ቀዝቃዛ ስሜት የነበረው በተጉለት አካባቢ ሆነ። ስለዚህ የአርበኛ መሪዎች በዚያ ተሰብስበው ስለወደፊቱ የትግል አቅጣጫ መከሩ፣ አዲስ ማኅበርም አቋቋሙ።

የማኅበሩ ዋነኛ ዓላማ በአርበኛው መካከል የመረዳዳትና የመተባበር፣ የመደጋገፍ ስሜት ማዳበር ሆነ። "ወገንህን ጠብቅ" በሚል ሃሳብ ላይ የተመሠረተ ነው። አንድ አርበኛ ሌላውን አርበኛ እንደ እናቱ ልጅ እንዲያየው፣ በአደጋ ጊዜ ጥሎት እንዳይሄድ፣ በሰልፍም ውስጥ ጥሎት እንዳይሸሽ አባላቱን ቃል ያስገባል። የማኅበሩ ስም "የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች ማኅበር" እንዲሆን፣ አንድ የክብር አለቃ፣ አንድ ዋና አለቃ፣ አንድ ዋና ፀሐፊ፣ አንድ ዋና ገንዘብ ያዥ፣ ከሦስት እስከ ሰባት አማካሪዎች እንዲኖሩት መተዳደሪያ ደንቡ ይደነግጋል። በሃያ ሁለት አንቀጽ የተቀመረው የማኅበሩ ደንብ እያንዳንዱን አባል በመሐላ የመተማመኛ ቃል እንዲገባ ያደርጋል። ዋስ ያስጠራል። የመተማመኛ ቃሉ፣

1ኛ. ምንም ቢቸግረን ወንድሞቻችንና ጓደኞቻችንን አንከዳም።

2ኛ. የሀገራችንን ነፃነትና ክብርዋን የሚጎዳ ሥራ በማናቸውም ምክንያት አንሠራም።

3ኛ. የንጉሠ ነገሥቱን መንግሥት መቃወም የለብንም። የሚሉ ፍሬ ነገሮች የያዘ ነው። ቀደም ብዬ እንደጠቀምሁትና እንደሚታመነው፣ የንጉሠ ነገሥቱ እጅ ሳይኖርበት አልቀረም። ይህም በሦስተኛ ተራ ቁጥር ከተነገረው ላይ ይታያል። ጥቅምት 23 ቀን መደንገጉም አንዱ ምልክት ነው።[8]

በጊዜ ሂደት እንደታየው፣ ይህ ማኅበር ከሌሎቹ የተሻለ ውጤት አስገኘ። ለማኅበሩ ጽንአት ከሰጡት ነገሮች ዋነኛው፣ አከራካሪ ከሆኑ የፖለቲካ ጉዳዮች ራሱን ማራቁ ይመስላል። ለምሳሌ መንግሥትን በተመለከተ ሕግ እንደሚያከብር ከመግለጽ በስተቀር፣ ስም ጠርቶ የእገሌን መንግሥት አላለም። ማኅበሩ ጥቅምት 23 ቀን 1931 ዓ.ም ቆመ ቢባልም፣ ደንቡ እስከ ጥር 1 ቀን ድረስ በጽሑፍ ተቀርጾ አልወጣም። ይህም በደንቡ አጻጻፍ ላይ ጥንቃቄ እንደተደረገበት ያመለክታል። ይህንን ማኅበር ያቋቋሙ ሰዎች ምስጋና ይገባቸዋል። ማኅበሩ ጦርነቱን በአሸናፊነት ከመወጣቱም በላይ፣ እስከ ዛሬም ድረስ መንግላታት ለበዛበት አርበኛ መጠለያ ሆኖአል።

ማጣቀሻ ፅሑፎች

1. Richard Greenfield, *Ethiopia*, p.243.
2. ታደሰ ሜጫ፣ *ጥቁር አንበሳ*፣ ገጽ 25-28።
3. እኔ ራሴ የማውቀው።
4. ሕይወት ጎደሩ፣ *ያቺ ቀን ተረሣች*፣ ገጽ 237-240።
5. ገሪማ ታፈረ፣ *ጉንደሬ ቢጋሻው*፣ ገጽ 137-140።
6. ከበደ ተሰማ፣ *የታሪክ ማስታወሻ*፣ ገጽ 254፣ 335 እና 195።
7. ዘውገ ዘገየ፣ *አባ ኮስትር*፣ ገጽ 16።
8. ከፊ ኢትዮጵያዊ፣ *የአርበኞች ትግል ክፋሺስት ጋር*፣ ገጽ 13-19።

ምዕራፍ አርባ አምስት
ጤናና ምግብ

በጦርነቱ ጊዜ እጅግ አስፈላጊ ከሆኑት ነገሮች አንዱ የጤናና የሕክምና ጉዳይ ነው። በኢትዮጵያና በጣልያን ጦርነት፣ ጤናና የሕክምና ችግር በኢትዮጵያ ወገን እጅግ ከባድ እንደሚሆን ቀደም ብሎም ተገምቶ ነበር።

በንጉሠ ነገሥቱ ፈቃድ የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማኅበር ሐምሌ 1 ቀን 1927 ዓ.ም አዲስ አበባ ተቋቋመ። ለማኅበሩ እንቅስቃሴ መጀመሪያ፣ ሁለት መቶ ሺህ ብር ተሰጠው። እሱም በዓለም የቀይ መስቀል ማኅበር በኩል የአርዳታ ጥያቄ ለልዩ ልዩ አገሮች አስተላለፈ። የእንግሊዝ፣ የስዊድን፣ የሆላንድ፣ የኖርዌ፣ የግብፅ የቀይ መስቀል ማኅበሮች ሐኪሞች፣ መድኃኒት፣ የሕክምና መሣሪያ፣ አምቡላንስ፣ ድንኳን ላኩ። የፈረንሣይ፣ የጀርመን፣ የጃፓን፣ የቱርክ፣ የአሜሪካን፣ የመስኮብ፣ የግሪክ፣ የአውስትራልያና የሌሎችም ሀገሮች የቀይ መስቀል ማኅበራት በገንዘብም፣ በመድኃኒትም የተቻላቸውን ያህል ረዱ።

የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል እነዚህን ዕርዳታዎች የማስተባበርና ለጦሩ የሕክምና ሥራ መስጠቱን ጀመረ። ሐኪሞችን በሰሜንና በምሥራቅ፣ በደቡብ የጦር ግንባሮች አሠማራ። የስዊድን አምቡላንስ ቡድን በቦረና በኩል፣ የእንግሊዝና የሆላንድ በማይጨው ጦር ግንባር ተደለደሉ። የግብፅ፣ በጅጅጋ በኩል ገባ። የተቻላቸውን ያህል የኢትዮጵያን ሠራዊት ረዱ።[1] ጣልያኖች የቀይ መስቀል ቡድኖቹን አስመርሮ ለማባረር፣ እግረ መንገዳቸውን በጦርነቱ ላይ ለሚፈጽሙት ግፍ ምስክር እንዳይኖር ለማድረግ፣ ሆነ እያሉ በብዙ ቦታ በአይሮፕላን ደበደቡአቸው።

የስዊድን አምቡላንስ ቡድን አይሮፕላን ከራሱ መንግስት አገኘ። መድኃኒት በእሱ እየተጓጓዘ እንዲደርስለት ተደረገ። ከአይሮፕላን ነጂዎቹ ዋነኛው ሻምበል ጉስታፍ የተባሉት የስዊድን መሥፍን ነበሩ። እሳቸውም በበጐ ፈቃደኝነት ጎዳር 27 ቀን 1928 ዓ.ም ከጅቡቲ ቢድሬዳዋ በኩል አዲስ አበባ ገብተው፣ ከረዳታቸው ከአቶ ተስፋዬ ጎይሌ ጋር በድምሩ ሰባ አምስት በረራ በማድረግ የቀይ መስቀል እርዳታ ለገሱ። ቡኋላ፣ አይሮፕላኑ ኮረም አርፎ በምድር ላይ እንዳለ፣ ጣልያኖቹ በቦምብ አቃጠሉት። አብራሪዎቹ ለጊዜው ከአይሮፕላኑ ውጭ ስለነበሩ ከሞት ተረፉ። መሥፍኑ እንደገና ወደ አዲስ አበባ በመመለስ የዕርዳታ ሥራቸውን ቀጠሉ። የመጨረሻ በረራ ያደረጉት በጥቅምት ወር 1929 ዓ.ም ጉሬ ድረስ በመብረር ነበር።

ወይዘሪት ስንዱ ገብሩና ወይዘሪት ጽጌ መንግሻ ከጉሬ ሐኪም ቤት የቻሉትን ያህል መድኃኒት በመውሰድ፣ በራስ እምሩ ይመራ የነበረውን ጦር በእጅጉ ረድተዋል።[2]

ጣልያኖች እሸንፈው አዲስ አበባ ሲገቡ የዓለም ቀይ መስቀል ማኅበር ከሀገር ወጣ። የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማኅበር ፈረሰ። የሚገርመው ደግሞ አንዳንድ ጣልያናውያን ሀኪሞች ለጊዜው ኢትዮጵያውያን የጦር ቁስለኞችን እየተቀበሉ አከሙ።

ለዚህ አባባል እንደ ማስረጃነት የሚጠቀሰው የደሴ ሀኪም ቤትና አዲስ አበባ እቴጌ መነን ትምህርት ቤት የነበሩት ሀኪሞች ናቸው። ለማስረጃ ያህል ባሻ ደምሴ ወልደማርያም የተባሉ የአዲስ አበባ ሰው በማይጨው ጦርነት ቆስለው ሳሉታ፣ ኩል መስክ ከአንድ ገበሬ ቤት ቆይተው ደሴ ገቡ። ደሴ ሲደርሱ ጣልያኑ እንደሚያክማቸው ስለተረዱ ወደ ሐኪሙጋ ሄደው መታከም ይይዛሉ። ከሐኪሙ ጋር ከመለማመዳቸው የተነሣ ከዕለታት አንድ ቀን ጣልያኑ "ለመሆኑ የት ነው የቆሰልከው?" ይላቸዋል። እሳቸውም ያደረገውን ያድርገኝ ብለው ማይጨው መሆኑን ነገሩት። እሱም መልሶ "ከየትኛው ወገን ሆነህ?" ደግሞ ጠየቀ። እሳቸውም አንድ ጊዜ ቆርጠዋልና "ከኢትዮጵያ" ብለው መለሱ። ቀጥሎ የነበረው ጥያቄ "የት ጋ ነበርክ"? እሳቸውም የተሰለፉበትን ጉራ ቢነግሩ "ከዚያማ እኔ ነበርኩ። እንዴት አልተገናኘንም ታዲያ" አላቸው። እሳቸውም ብንገናኝማ አንዳችን አልነበርንም በማለት ቁጭታቸውን ገለጹለት። እሱም ቁስላቸው እስኪድን አክሞ፣ ገንዘብ ሰጥቶ ወደ አዲስ አበባ ላካቸው።[3]

ከዚህ ዓይነቱ አስገራሚ አጋጣሚ ባለፈ፣ አርበኛው በጣልያኖች የመታከም ዕድል አልነበረውም። ቁስለኛ ለሕክምና ቢቀርብ፣ በማሲቃየት መርምረው ይገድሉታል እንጂ አያክሙትም። እንዲያውም አባቱ አርበኛ የሆነ ሰው ልጅ ቢታመም፣ ወደ ሐኪም ቤት አይሄድም ነበር። ከዚህ የተነሣ የቡልጋው አርበኛ የደጃዝማች ኃይሉ ወልደመድኅን ልጅ ከራሱ ላይ ቢፈነክት መታከም ባለመቻሉ፣ ብዙ ጊዜ ሊሰቃይ ችሏል። ስለሆነም፣ ሐኪሞቹ መሐላቸው ለዜጎቻቸው ብቻ ነበር ወይ? ያስብላል።

በአርበኛው ላይ የደረሰው የጤና ችግር ብዙ ነው። በመርዝ ጋዝ ይለበለባል፣ በጥይት ይመታል፣ በሚንጃና በጩቤ ይወጋል፣ በቦምብ ፍንጣሪ ይቆስላል። ሲሸሽ ወይም ሲያበር ይወድቃል፣ ጭር ይዞረዋል፣ ይሠበራል፣ እሾህ ይወጋዋል፣ ጋሬጣ ይገሸልጠዋል። ጫማ የለውም። በረሀብ ሰውነቱ ይከክማል፣ ባልተስማማ ምግብ ምክንያት የትውከትና የተቅማጥ ሕመም ይይዘዋል። ወባ ያመዋል። እንደተሰበ፣ ፈንጣጣ፣ ኩፍኝ ያለ ተላላፊ በሽታ ደግሞ ልጆችን ይፈጃል። ቂጥኝና ጨብጥም አለ።

ለኢትዮጵያውያን የነበረው ህክምና የሀገር ባህል ነው፣ ሌላ አልነበረም። በመርዝ ጋዝ ለለበለበው ሰው ቁስሉን ጨቃሚ በሚባል እንጨት ፍሬ ቶሎ ቶሎ ማጠብ ነው።[4] ይበልጥ እንዳይገሸላለጥ በጨርቅ ሳያስሩ አየር እንዲያገኝ ማድረግ ያስፈልጋል። ታላቁ ጥንቃቄ ዝንብ እንዳይነካው ከማድረጉ ላይ ነው።

ቦርይት ለተመታ፣ በሣንጀ ለተወጋ፣ በጩቤ ለተሰለበ፣ በቦምብ ሰቆለለ መጀመሪያ ደሙን ማቆም ነው። ደሙን ለማቆም የተረፈውን ሥጋውን ከግራና ከቀኝ ጉትቶ ማሠር፣ የሚያውቅ ሰው ከተገኘ ደምን የሚያቆም ቅጠል በጥሶ ከቁስሉ ላይ መጭመቅ ነው። ከዚያ በኋላ የአጠፋሪስ ፍሬ እያሣረሩ፣ እየወቀጡ መደምደም ነው። ከሁሉም ይበልጥ የሚያስቸግረው የተሰለቡ ስዎችን ማስታመም ነው።

ብረት የሆነ ነገር ያልነካውን ቁስል፣ ማለትም እንቅፋት የመታውን፣ ጋሬጣ የገሸለጠውን የሚያድነው የተጠቃሹ የራሱ ሽንት ነው። ለወለምታና ለሥር መዞር በቅባት መታሸት ነው። በሩጫ ብዛት ቡቃ የሚወርዳት ሴትም ካለች፣ ለእሷም እንደዚሁ ነው። በክረምት ወራት እግርን በሞቀ ውሃ አዘውትሮ መታጠብ ነው። ያለዚያ ጮቅ ይይዛል፤ ጭቃው እግርን ይቆራርጣል። እንደ ጥቅምት ባለ የብርድ ወራት በጥዋት ደጋ ከተወጣ የእግር ንቃቃት ያጋጥማል። ለእሱ ደግሞ የሚሻለው የዶሮ ስብ ከማር፣ ከቅቤ ጋር ተሰውሶ በእሳት በማቀጣጠል ፍላቱ እንዲወርድበት ማድረግ ነው። ፍላቱ ከጤናማው አካል ላይ እንዳያርፍ ቁርበት ወይም ሌጦ በቁስሉ ልክ በስቶ ማልበስ ነው። እሾህ ውስጥ እግሩን ለወጋውም መድኃኒቱ ይኸው ነው። ለስብራት ይጠቀሙበት የነበረው በተቻለ መጠን ሁለቱን ወገን አገጣጥሞ ማሠር ነው። ይህ የተለየ ችሎታ ያለው ወጌሻ ይጠይቃል።

በልዩ ልዩ ምክንያት የተቅማጥ ተውሳክ ይነሳል። ቡና መጠጣት ያስታግሰዋል ብለው የሚያምኑ አሉ። ህመምተኛው አቅም ካለው ኮሶ መጠጣትም ይረዳዋል። ለወባ ሽምብራና ነጭ ሽንኩርት ከተጣራ ቅቤ ውስጥ ተዘፍዝፎ ሲረጋ ያንኑ ጥዋት፣ ጥዋት መብላት ኩክ እንዳትሠራበት ይከለክላል ተብሎ ይታመናል።

የተጠማ ሠራዊት ውሃ ጅው አድርጐ እንዳይጠጣ፣ ቀስ ብሎ ጉንጭ በጉንጭ እንዲጠጣ፣ እርቦት ጠኔ የጣለው ወይም በረሃብ የተጐዳ ሰው ምግብ ጥቂት በጥቂት መብላቱ እንዲያገግም ይረዳል። ለትንታ ቶሎ ከተቀመጡበት መነሳት ያስፈልጋል። ቆሎ በሽታ የለውም፣ ንፍሮ ግን አያጣውም። ለአደረ ንፍሮ መድኃኒቱ እንደገና መቀቀል ወይም ማገንፈል ነው። እርጐ መጠጣት አደገኛ ነው። ማርም በመጠኑ ካልሆነ ሆድ ይቀበትታል፤ በቀበተተ ጊዜ መድኃኒቱ የሞቀ ነገር መጠጣት ወይም ሆድን እሳት ማስመታት ነው።

ሌላው የምግብ ጉዳይ ነው። ከዱር፣ ከጫካ የሚለቀም ፍራፍሬ፣ ሥራ ሥር በሚሆን ጊዜ የሸላ፣ የአጋም፣ የቀጋ ፍሬዎች ደህና ናቸው። በደቡብ አገሮች ቦይና፣ ጉደሬ የሚባሉ አሉ። በገናሌ ወንዝ ከውጊያ የተመለሰው ጦር ቆኒ እና ቀሎ ቀጭ የተባሉ ፍሬዎች መብላት ነበረበት። ዋናው የአርበኛው ምግብ የከብትና የአውሬ ሥጋ ሆኖ ነበር። ቆቅ፣ ጅግራ፣ ድኩላ የመሳሰሉት አራዊት በጣም ረድተዋል።[5]

በአርበኛው ላይ የወረደ አንድ ቸነፈር በተለይ መጠቀስ ይገባዋል። አርበኛው እንቅጥቅጥ ይለው ነበር። የቡልጋን አርበኛ የፈጀ፣ የተረፈውንም ያቀጨጨና አቅመ ቢስ ያደረገ እሱ ነው። ባህርዩ እንደ ወባ ያለ ነው። ጊዜ እየለየ ያንቀጠቀጣል። ከአንቀጠቀጠ በኋላ በኃይል ያተኩሣል፤ ከመጠን በላይ ያልባል። የዚህ ደዌ መፈራረቅ ሰውየውን ያከረፋዋል። ያስርበዋል፤ በልቶ ግን አይጠግብም። ወይም አላስበላ ብሎ ይደብተዋል። በአገር የሌለ ምግብ አምጡ ያሰኝዋል። ያቃዠዋል፤ አንዳንዱንም ያሳብደዋል። አፋቸውን ያጣመመባቸው አሉ። አንዳንዶች ከዚህ በሽታ በጠበል ድነዋል። እንደ ልክፍት መሰሉ የታየበትም ጊዜ አለ። ህመሙ እየቆየ የሚቀሰቀስ ከሆነ ህመምተኛው የመዳን ተስፋ አለው። እየፈጠነ ከተነሣበት ተስፋ የለውም። የገደለውን ገድሎ ከሞት የዳነውን ቀጫጫ፣ አቅመ ቢስ ያደርጋል።

ሌላው በሰው የተጫወተው ቁስል፣ ጫጉዮ ነው። የቆላ ቁስልም ይሉታል። አንድ ጊዜ ከያዘ ደጋም ቢወጡ አይለቅም። ከሰው ወደ ሰው የሚተላለፈው በዝንብ ነው። በትንሹ ይጀምርና ቁስሉ መሀሉ ይጉደጉዳል። እዥም፣ ደምም አይወጣውም። ሥጋን ይበላል፣ አጥንትን ይፈረፍራል። ፋታ አይሰጥም፣ በመሳልትና በሌሊት ያሰቃያል። ያገኙና የቻሉ ክብረ ሰማይ ደምድመውበታል። ጥዋት ጥዋት መታጠብ ያስታግሰዋል። አጥንት የሰበረበት፣ በጣጥሶ የገደለበት ሁኔታ ታይቶአል። አቶ ኃይለ ጉብርኤል የተባለውን አርበኛ ለሞት ከአቃረበው በኋላ፣ በእርቅ ጊዜ ጣልያን አሥመራ ወስዶ አክሞ ከዚህ ደዌ አዳነው። ስለዚህ በህክምና ረገድ መድኃኒት አለው ማለት ነው። በህበሻ ግን አንዳች አልተገኘለትም።

ከአራዊት ጅብ እና ክፋቱ ሊነገርለት ይገባል። በተለይ በ1932 ዓ.ም ቡልጋን ጅብ አጥለቀለቀው። በአሥርና በአሥራ አምስት መንጋ፣ በቡድን እየሆነ አገሩን አነጠነጠበት። ብዙ ሰው በላ። በተለይ ሙገሬ ዛላ በሚባለው፣ ጭንቂት ጥቂቶችን ከጀመራቸው በኋላ በመተረየስ ተኩሶ ማስለቀቅ ተችሎአል። ጀሎ አገር ግን በአንድ ሌሊት ሃምሣ ሁለት ህመምተኞች ጨርሶ በላ። ጥይት ሲተኮስበት መሬት ላይ በመንደባለል የተመታ በመምሰል ያስካካና ሊቀርቡት ጠልፎ ይዞ ይሄዳል። በዚያን ጊዜ በታየው ዓይነት ብዛት፣ ከዚያ በፊትና ከዚያም ወዲህ ታይቶ አይታወቅም።

ማጣቀሻ ፅሑፎች

1. ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፣ *ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ*፣ 1ኛ መጽሐፍ፣ ገጽ 175-176።
2. ታደሰ ሜጫ፣ *ጥቁር ለንበሳ*፣ ገጽ 66-67 እና 106።
3. ባሻ ደምሴ ወልደ ማርያም ያጫወቱኝ።
4. ታደሰ ዘወልዴ፣ *ቀሪን ገረመው*፣ ገጽ 192-193።
5. ሰይፉ አምበሉ፣ *የታሪክ ቅርስ*፣ ገጽ 83-85።

ምዕራፍ አርባ ስድስት
ከሀዲዎችና የክህደት ሥራቸው

በኢትዮጵያና በጣልያን ጦርነት ታሪክ ውስጥ እንደ ኩሶ የሚመረው ክፍል፣ የከሀዲዎችንና የክህደት ሥራቸውን የሚመለከተው ነው። ኮሶን ካልጠጡት በስተቀር እንደማያሽር፣ ይህንንም ነገር በደንብ ካልመረመሩትና ካልተገነዘቡት፣ ከሀገር አይጠፋም። ወደፊትም እየተደጋገመ ሊደርስ ይችላል። ስለዚህ የቱንም ያህል መራር ቢሆን፣ ታሪክ ነውና መመልከት አለብን።

ማናቸውም ክህደት፣ ምንግዜም ያው ክህደት ነው። ቢሆንም ደረጃው ይለያያል። በአንድ ሰው ላይ ከተፈፀመ ክህደት፣ በብዙ ሰው ላይ የተፈፀመ ክህደት ይሰያል። በንጉሥና በሀገር መሪ ላይ የተፈፀመ ደግሞ በብዙ ሰው ከተፈፀመውም ይበልጣል። በሕዝብ መካከል ብጥብጥና እልቂት ያስከትላልና፣ በሀገር ላይ የሚፈፀም ክህደት ግን ከሁሉም በላይ ነው። ከጠቅላላ ጥፋትም ያደርሳል፣ በዓይነቱም ከሁሉም ይልቃል። የከሀዲው እውቀትና ደረጃም ከግምት መግባት አለበት። ተራ ሰው ቢከድ ይቀላል። በአንድ መንግሥት የተሾመና የተሸለመ፣ የተማረ ሰው ሲከድ ያስገርማል። ያስደንቃል። የሚያደርሰውም ጉዳት በዚያው መጠን ይሆናል።

በጦርነቱ ጊዜ በኢትዮጵያ ላይ የደረሰው ክህደት ከባድ ነበር። የጀመረውም ጦርነቱ ከመከፈቱ አስቀድሞ ነበር። በአጠቃላይ ቢታይ ዋነኞቹ የክህደት ተዋናዮች የንጉሠ ነገሥቱ ባለሟሎችና ከፍተኛ ሹማምንቶች ነበሩ። የሚያፍሩት፣ የሚፈሩት እንዳልነበረ ይገመታል። ገና በአገር ደህና አዲስ አበባ ከነበረው የጣልያን ሌጋሲዮን ጋር ግንኙነት የፈጠሩም ነበሩ። አበል የተቆረጠላቸው ወይም ድጐማ ይሰጣቸው የነበሩ እንደማይታጡ ብዙ ማስረጃ ጭምር ነበር።

የክህደቱን በር የከፈተው የትግሬው መሥፍን ደጃዝማች ኃይለሥላሴ ጉግሣ ነው። ከእሱ ቀድመው ሰጣልያን የረዱ አልነበሩም ማለት አይደለም። በገሀድ ከኢትዮጵያ ወጥቶ አሥመራ በመሄድ፣ ጥቅምት 1 ቀን 1928 ዓ.ም ከጣልያን ጦር ጐን ለመቆም የመጀመሪያው ሰው ሆነ። የእሱ ክህደት የጦርነቱን ሚዛን በአንድ ጊዜ ወደ ጣልያን አዞረው። በኢትዮጵያ ወገን የነበረውን ማንኛውንም ምሥጢር ለጠላት ሰጠ። ከ1200 ጠመንጃና ከ8 ያላነሰ መትረየስ አስረከበ።[1] ከአዲስ አበባ እስከ ኮረም የተሠራውን መንገድ ፕላን ሰጠ። የትግሬን ልቡና ከፋፈለ። ለሌሎች ከሀድያን በር ከፈተ።

ከደጃዝማች ኃይለሥላሴ ጉግሣ ቀጥሎ የክህደት ሥራ ያካሄደው የጐጃሙ ደጃዝማች ገሠሠ በለው ነው። እሱ ወደ ጣልያን አልገባም። ነገር ግን እነ ፊታውራሪ ታምራትን፣ እነ ፊታውራሪ ገሠሠ ጉግሣን፣ እነፊታውራሪ ዘለቀ ካሣን፣ እነ ፊታውራሪ ዘለቀ ወሌን አሳብሮ ወደ ኋላው በመመለስ ጎጃም ገቡ።[2] የንጉሠ ነገሥቱ አዋጅ፣ የጳጳሱ ግዝት አላገደውም። እነዚህ ሹማምንት ከጦር ግንባር መመለስን እንደ ሽሽት፣ እንደ ክህደት አልቆጠሩትም። ነገር ግን የሀገሪቱን የጦር ግንባር ሰበሩት። ሞሶሊኒ "...የመርዙንና የጢሱን፣ የቦምቡንም ነጐድጓድ እየተመራሩ የካዱ ይመስላል..." ብሎ እስከ መፎከር አደረሰው።[3] እነሱ የተመለሱት ግን አንዳች ደርሶባቸው አልነበረም። ንጉሠ ነገሥቱ ቢቸግራቸው ለሠራዊቱ ምሕረት አድርገው፣ አለቆቹ ታድነው እንዲያዙ አዘዙ። ሌላ ትግል ተፈጠረ። እነሱም ላይያዙ ቀሩ።

ጣልያኖች የሬዲዮ መልእክት መጥለፊያ መሣሪያ አበጅተው፣ በአማርኛ ቋንቋ የሚተላለፉ መልእክቶችን ወደ ጣልያንኛ የሚተረጕሙ ሰዎች ቀጥረው፣ በቁጥር የሚተላለፉ የምስጢር መልእክቶችን የሚፈቱ ሰዎች መድበው፣ ከኢትዮጵያ ጦር ግንባሮችና ከአዲስ አበባ የሚተላለፉ መልእክቶችን ይወስዱ ነበር። ከዚህም በስተቀር የሬዲዮ ቴሌግራፉን ሥራ የሚመራው ሲቢሊንስኪ የተባለ ፈረንጅ ነበር፣ በመሆኑም ማንኛውም ምሥጢር በእጃቸው እንደገባ የሚቆጠር ነው። ኢትዮጵያውያን ስልክኞችም በገንዘብ እየተገዙ ሆነ ብለው ምሥጢር እያሳለፉ ይሰጡ ነበር። ጣልያኖች በተለይ ከጥር 10 ቀን 1928 ዓ.ም በኋላ ማንኛውንም የሬዲዮ ግንኙነት መቆጣጠር ችለው ነበር። በዚህ ሁኔታ የተጠራጠረው ንጹሁ ኢትዮጵያዊ የስልክ ሠራተኛ፣ አቶ ሙሌ ብርሃኔ በትኩሱ ሰሥራው ኃላፊ፣ ለአቶ ወርቁ ይታጠቁ ነገሩን አስታወቁ። የቃሉ አስተላለፍ አመታት የጣልያኖች እጅ እንደ አለበት አስረዱ። ነገር ግን አንዳች አልተደረገም።[4] ስለዚህ በክህደቱ ሥራ አቶ ወርቁም አለበት ማለት ነው።

ጣልያኖች የማርትሬዛ ብር አሰርተው ለኢትዮጵያ መሣፍንትና መኳንንት እየከፈሉ፣ በጦርነቱ እንዲተባበሩአቸው ልቡናቸውን ይሰልቡ ነበር። ለማስረጃ ያህል አንድ ሁኔታን እጠቅሳለሁ። በአንድ ወቅት ጣልያኖች ኤርትራ ላይ አንድ ወታደራዊ ትርኢት አድርገው ለሕዝብ አሳዩ። ትርኢቱን የተመለከቱ የኤርትራ ሹማምሌሞች ዝም አሉ። ጣልያናዊው አገረ ገዥ "የማሸነፍ ዕድላችን ምን ይመስላችሁአል?" ብሎ ጠየቃቸው። ሹማምሌሞቹ "የኢትዮጵያ ወታደር ልባም ነው" ቢሉት፣ "ለእሱም 46 ሚሊዮን ሊሬ አዘጋጅተናል" አላቸው።[5]

ጣልያኖች በዚህ ዓይነት የሚያካሂዱትን ሥራ ንጉሠ ነገሥቱም ሳያውቁ አልቀሩም። በአንድ ወቅት አንድ በጣልያን ሌጋሲዮን የሚሠራ አንድ ሀገር ወዳድ፣ አበል የሚከፈላቸውን ኢትዮጵያውያን ዝርዝር አቀረበላቸው። ከጥቂት ቀን በኋላ ጣልያኑ ሊፈልገው ከቤቱ ሄደ፣ ከውሃ ጉድጓድ ተደብቆ ቆይቶ፣ ቡልጋ በመግባት ሕይወቱን አዳነ። አሥመራ የነበሩት የኢትዮጵያ ቆንሲል፣ አቶ ወዳጀ አሊ በበኩላቸው አዲስ አበባ ድረስ መጥተው፣ ደጃዝማች ኃይለሥላሴ ጉግሳ ከጣልያኖች ደመወዝ እንደሚከፈለው ቢገልጹ፣ ንጉሠ ነገሥቱ የሰጡት መልስ "...የኢትዮጵያ መካንንት አብዛኛው ከጣልያን ገንዘብ ይቀበላል። ይህም የጣልያንን ኢኮኖሚ ለመጉዳት እንጂ እኛን ለመክዳት አይደለም..." የሚል እንደነበር በታሪክ ተመዝግቦአል።[6]

መጋቢት 21 ቀን 1928 ዓ.ም ፊታውራሪ ተድላ የተባለ የማይጨው ሰው፣ ለጦሩ መንገድ ከንጉሠ ነገሥቱ ክራሳቸው ተጠየቀ። እሱ ግን እሽ በማለት ፈንታ ገንዘብና መሣሪያ እንዲሰጠው ጠየቀ። ተሰጠው። የጠየቀው ከተሰጠው በኋላ ደግሞ "...ዛሬ ነው የምታውቀው" ከነጭራሹ እምቢ አለ። በዚህ ጊዜ ንጉሠ ነገሥቱ "አይ እግዚአብሔር ከእንደዚህ ያሉ ሰዎች ጋር ያኖርከኝ" ብለው አማረሩ።[7] ጣልያን ለኢትዮጵያውያን ገንዘብ መስጠቱ የእሱን የራሱን ኢኮኖሚ የሚጉዳ እንጂ፣ ሕዝብ ከእኛ የሚያስከዳ አይሆንም ብለው ያመኑት አመለካከት ስሕተት እንደነበር በዚያች ሰዓት ሳይረዱት አልቀሩም።

ሌላው ታላቅ ስሕተት የተፈፀመው በልዑል ራስ ኃይሉ ተክለሃይማኖት ነው። የእሱ ክህደት ቀደም ብሎ የታወቀ ስለነበር እንግዳ ነገር አልሆነም። ጣልያኖችን ወደ ኢትዮጵያ ለማስገባት የሚቻለውን ሁሉ አድርጓል። ንጉሠ ነገሥቱ ወደ ስደት ሲሄዱ እሱንና ራስ ገብረ ሕይወትን ድሬዳዋ ድረስ ወስደው ሰቀቋአቸው። ራስ ኃይሉም ባለፈው ሥራው ተጸጽቶ ለወደፊት በሚቻለው ሁሉ የኢትዮጵያን ነፃነት ለመጠበቅ የመሐላ ቃል ሰጥቶ ነበር።[8] ሆኖም ግን አንዳች መሻሻል አላደረገም። ሽንጡን ገትሮ እስከ መጨረሻው ድረስ ለጣልያን መንግሥት ተዋጋ። ንጉሠ ነገሥቱ ለንግግር ቢጋብዙት የሰጠው መልስ "...ከዚያ መከራ አውጥቶ ከሞት አትርፎ፣ ሀገሬን ሰጥቶ፣ ለዚህ ላበቃኝ ለጣልያን መንግሥት ምን ውለታ ልመልስለት?..." የሚል ነበር።[9] በጣልያን በመጋዙ፣ ሮም ድረስ ተወስዶ እዛ በመቆየቱ ቅር አላለውም።

ሌላው ከሀዲ ቀኛዝማች ተክለማርቆስ ወልደገብርኤል ነበር። ሹመቱ በአዋጅ አይሰጠው እንጂ፣ የጸሐፌ ትዕዛዝነቱን ሥራ ያካሂድ የነበረ፣ የንጉሠ ነገሥቱ ባለምዋል ነበር። ጥውመልሣን ከመሆኑ የተነሣ

በንጉሠ ነገሥቱ ዘንድ ከፍተኛ ተደማጭነት ነበረው። ጣልያኖች ኢትዮጵያን በያዙ ጊዜ ዋና ባለምዋል ሆነ። የሰላሌ ገዥነት ተሰጠው። በአርበኞች እጅ ግንቦት 25 ቀን 1929 ዓ.ም ቢቆስልም፣ ከጉዳት ሳይቆጥረው አገልግሎቱን ሰጠላት ቀጠለ።[10]

በሀገር ውስጥ የተሰገሰገው ፈረንጅ ለጣልያን መሣሪያ ሆኖ በኢትዮጵያ ላይ ያደረሰው ጉዳት እጅግ ነው። እርግጥ አንዳንድ የውጭ አገር ሰዎች ለኢትዮጵያ ረድተዋል። በሱዳን ኪጂ ኃይሉ ከዚህ ላይ መጠቀስ ይገባቸዋል።[11] የዲፕሎማቲክ ሹማምንት ሳይቀሩ፣ አብዛኛው የውጪ ዜጋ ግን ቀጥ ብሎ ለጣልያን ረዳ። ለምሳሌ የፈረንሣይ አምባሳደር ከሥራው ውጭ ለጣልያኖች መረጃ ይሰጥ ነበር። ትምህርት ቤት እየከፈቱ፣ ለስም ያህል ክሊኒክ እየከፈቱ በኢትዮጵያ ይኖሩ የነበሩ የውጭ አገር ሚስዮኖች፣ ለጣልያን አገልግሎታቸውን በብቃት ሠጡ። በተለይም የካቶሊክ እምነት ተከታዮች፣ ጣልያን ድል አድርጉ በገባም ጊዜ ሥራቸውን ቀጠሉ። እንዳቸውም ቅሬታ አላሳዩም። የስዊድን ወንጌላዊት ሚስዮን ብቻ ሰግቶ ወጣ። የሚያስገርመው የውጭ አገር ሰዎች ይህንን መሥራታቸው አይደለም። እዚህ የነበሩት የውጪ ዜጎች ይህንን ሁሉ ሲያደርጉ፣ ከልካይ ቀርቶ ታዛቢ እንኳን አልነበረባቸውም። በንጉሠ ነገሥቱ ዘንድ ተቀባይነት አለማግኘቱ እንጂ፣ የውጭ አገር ሰዎች ይውጡ እየተባለ በየጊዜው፣ በገሀድ ጥያቄ ቀርቧል።[12]

በኢትዮጵያ ቤተ መንግሥት ዘንድ ውትሮ ምክር የሚመክረው ከኢትዮጵያውያን ነበር። በተለይም በዳግማዊ ምኒልክ። ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዘንድ ግን እንዲህ አልነበረም። ጦርነቱን መቋቋም የሚቻለው በዘመናዊ ዘዴ ነው ብለው ስላመኑ፣ ብዙ የውጭ አገር አማካሪዎች በዙሪያቸው ከለከሉ። የሚሰሙትም የእነሱን ምክር ብቻ ስለሆነ፣ የተማሩ ኢትዮጵያውያን ሃሳባቸውን የእነሱ ሃሳብ አስመስሰው እንዲያቀርቡላቸው እስከ መለማመጥ ደርሰው ነበር። ከእነዚህ ነጭ አማካሪዎች ዋነኛው ኮሎኔል ኮኖቭሌቭ የተባለው ራሺያዊ ነበር። ሌላው የንጉሠ ነገሥቱ ባለምዋልና ምሥጢረኛ ፖሊሱግ የተባለው ነው። እነዚህና ሌሎችም ፈረንጆች ምሥጢራችንን ሙልጭ አድርገው ስለሰጡአት፣ ጣልያን ልታሸንፍ በቃች።[12]

እነዚህ የውጭ አገር ሰዎች ለጣልያኖች የረዱበት መንገድ ባለብዙ ፈርጅ ነበር። እኩሎች ለጣልያን ወሬ በማቀበል፣ እኩሎቹ ለንጉሠ ነገሥቱ አሳሳች ምክር በመስጠት ጉዳት አደረሱ። ከዚህ ላይ ሳይጠቀስ የማይታለፈው፦ ከአዲስ አበባ እስከ ኮረም የተሠራው የመኪና መንገድ ጉዳይ ነው። መንገዱ የተሠራው በአሳሳች የፈረንጅ ምክር እንደነበር

አለማመን መታለል ነው። እኩሎቹ ደግሞ በየመኪንንቱ ቤት እየዞሩ የጣልያንን ትልቅነት በማውራትና የሰውን ልብ በመስለብ ብዙ ጉዳት አደረሱ። ምሳሌ፦ ሙሴ ቀስተኛው ነው።

በወቅቱ የዋጅራትና ሌሎችም የአካባቢው ዜጐች ከማይጨው በሚመላለሰው ሠራዊት ላይ የማፍ ሥራ ፈፀመብት። መሣሪያውን ቀሙት፤ ልብሱን ገፈፉት፤ ጨፈጨፉት።[13] ከጣልያን ገንዘብ እየተቀበሉ፤ በጠላት ስብከት እየተደለሉ የፈፀሙት ሥራ ቢሆንም፤ ለእነሱ ግን እንደ ክህደት መስሎ አልታያቸውም። የልጅ ኢያሱን ደም የተበቀሉ መሰላቸው። ታላቅ መታለል። ከወገናቸው የገፈፉትን መሣሪያ እየታሠሩ፤ እየተደበደቡ ለጣልያን አስረከቡ።

ጣልያኖች አዲስ አበባ ሲገቡ በምሥጢር ተይዞ የነበረው የክህደት ሥራ በገሀድ ውጣ። የዛን ጊዜ ደግሞ ቀጣዮቹ ከሀዲዎች ደጃዝማች አበራ ካሣና ደጃዝማች አስፋው ወሰን ሆኑ። ከወንድሞቻቸው ከእነ ሻለቃ /ራስ/ መሥፍን ሰለሺ ምክር ይልቅ፤ የጠላታቸውን የግራዚያኒን ቃል አምነው ከሠራዊታቸው ተሰይተው ገቡለት። እሱም ሳያውል ሳያሳድር፤ ዕለቱን በመግደል ዋጋቸውን ከፈላቸው። በአገዳደል ቢያዋርዳቸውም በጦር ሜዳ እንደ ሞቱ አድርጐ በማውራት አከበራቸው። ነገር ግን ዓለሙን ማታለል አልቻለም።

የደቡቡን የኢትዮጵያ ጦር ከአስጠቁት ነገሮች አንዱ መንገሻ ያለው እና ባዩ የተባሉት ሁለት ከሀዲዎች ለጠላት በሰጡት ምሥጢር ነው።

በራስ ደስታ ዳምጠው የሚመራው አርበኛ የጣልያንን ጦር ቀስፎ በመያዝ ከአቆየው በኋላ፤ እቅም እያነሰው ስለሄደ ወደ ኬንያ ለመውጣት አሰበ። ሁለት ሰዎች መንገድ ለመምራት ተስማምተው፤ ሰባ ብር ተቀብለው፤ ጦሩን የአንድ ቀን መንገድ ከመሩት በኋላ ሌሊቱን ተመሣጥረው፤ ጠላት መርተው አመጡበት። ሠራዊቱም አለቀ። ራስ ደስታ ዳምጠውም ሞቱ።[14] ከእነዚህ ከሀዲዎች እሽታ፤ የፊታውራሪ ተድላ እምቢታ ይሻላል።

አቡነ አብርሃም የተባለው የጐንደርና የጐጃም ጳጳስ በወቅቱ ጐንደር ነበር። ደሙ ከኢትዮጵያ ቢሆንም፤ ልቡ ከጣልያን ነበርና ወደ ዘመቻው ለመሄድ ንቅንቅ አላለም። ከጦር ሜዳ ለተመለሰው ሠራዊት ልብስ መግዣ እንዲሆን የተላከውን እና በአደራ እንዲያስቀምጥ የተሰጠውን ሠላሳ ሺህ ብር እንዲመልስ ቢጠየቅ፤ ጣልያን ድል አድርጐ ሲገባ "...እንተ ዘንድ የተቀመጠውን ገንዘብ አምጣ ቢለኝስ?" በማለት ከለከለ።[15] እውነትም ለእጅ መንሻ ሆነው፤ ጣልያን ሲገባ የኢጣልያ ምሥራቅ አፍሪካ ሊቀ ጳጳስ አደረገው። እሱም "...ታላቁ የኢጣልያ

መንግሥት በረቂቅ እውቀት፤ በሰፊ ቸርነቱ የተዋህደ ሃይማኖትን ...የወንጌልን ቤተሰብ በክርስቶስ እያበዛ እንዲሄድ ነፃነትን ለሰጠ ለዚህ ታላቅ መንግሥት፤ ሰላማዊ ሆኖ መገዛት የሚገባ መሆኑን አሳስባችኋለሁ..." እያለ በየአደባባዩ ሰበከለት።[16] በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ካህናት፤ መነኮሳት ማለቃቸው፤ ከ2000 በላይ አብያተ ክርስቲያናት መቃጠላቸው፤ ለእሱ አንዳች ጉዳዩ አይደለም። ነፃነት የሚሰው እሱ ከእስክንድርያ መላቀቁን ሆነ።

ጣልያን አዲስ አበባ እንደገባ ከሀድያን በዙሪያው ተኮለኮሉ። ስድስት ራሶች፤ አንድ ጳጳስ፤ ሦስት ሡልጣኖች፤ አንድ ሼህ፤ አራት ደጃዝማቾች ያለአንዳች ችግር ገቡለት። በየአደባባዩ እያቆመ ቃላቸውን በመሐላ ተቀበላቸው። አስፈረማቸው። ደመወዛቸውንም እንደ አገልግሎታቸው እያየ ቆረጠላቸው። ከፍተኛው ደመወዝ፤ የዋና ታማኙ የራስ ኃይሉ ተክለሃይማኖት፤ ትንሹ ደግሞ፤ የደጃዝማች ታዬ ጉልላት ነበር።[17] ግራዚያኒ እንደዚህ ሲያደርግ፤ ናዚም በበኩሉ በጎንደር ለታማኞቹ የወር ምንዳ ቆረጠላቸው። በእሱ በኩል ደግሞ ታላቁ አረጋይ በክር ሲሆን አነስተኛው አጋጀ ፀሐይ ነበር። በሌሎች አራት ግዛቶች የነበረው አልታወቀም። መታየት ያለበት እነዚህ ሰዎችና መሰሎቻቸው ሀገራቸውን ኢትዮጵያ መሸጣቸው ነው።

በገጠር ስለነበረው ሁኔታ ደግሞ ለመጻፍ ይከብዳል። ደጃዝማች መሸሻ ተወንድ በላይ በጅሩ፤ ደጃዝማች ማሞ ኃይለ ሚካኤል በጐጃም፤ ደጃዝማች ሃብተ ማርያም በነቀምት፤ አባ ጀቢር አባጅፋር በጂማ፤ ደጃዝማች ዓመዴ በወሎ፤ ደጃዝማች አያሌው ብሩና አናዛዥ መነኩሴ አባ ተክለማርያም በጐንደር፤ ፊታውራሪ ተሰማ ከተማ በቡልጋ፤ ወሩ በላይነህና አሊ ዑመር በበረከት፤ ፊታውራሪ ሣህሉ ወልደገብርኤል በመንዝ፤ አቶ አበበ ዘገኑ እና አቶ ሰሙ በደብረ ብርሃን፤ በመርሐቤቴ ደግሞ ንዳው ጭንቅሎ፤ አፈቋሣር አፈወርቅ ሳይጠቀሱ አይታሰፉም። ግብረ አበሮቻቸውም አሉ። እነዚህ ሰዎች የፈፀሙትን በደል ለመዘርዘር እጅግ ያስቸግራል። ሆኖም የአንዳንዶቹን አንዳንድ ሥራ እጠቃቅሳለሁ።

ደጃዝማች መሸሻ ዘጠኝ አርበኞች በገበያ ላይ አሰቅሏል። ደጃዝማች ማሞ ኃይለ ሚካኤል ራሱ ለጣልያን የጦር አዝማች በመሆን አዋግቷል። የእነዚህና የመሰሎቻቸው ደጃዝማችነት፤ ጣልያን የሰጣቸው ማዕረግ ነው። የጥቁር አንበሳ ጦር ተንከራትቶ ከምርኮ የወደቀው ደጃዝማች ሀብተማርያም ከወለጋ ሳለአስወጣው ነው። ሌላ በደል አልፈፀመበትምና፤ የእሱ ይቀላል።

አባ ጀቢር የአማራ ጭንቅላት በሠላሳ ብር አየገዛ ብዙ ሰው አስፈጅቶአል። ደጃዝማች አመዴ ሕዝብ እያነሳሳ፣ ከማይጨው በሚመለሰው ጦር ላይ አዝማች እየሆነ በሰጠው አገልግሎት፣ ከጣልያን ከደጃዝማችነት ማዕረግ ደርሶአል። አባ ተክለ ማርያም እሥረኞች ለሀገራቸው የሠሩትን እንደ ኃጢአት እያናዘዘ ብዙ ሰው አስፈጅቶአል። ማህሉ ወልደገብርኤል ግራዝማች አጉናፍር የተባሉትን አርበኛ በአሰቃቂ ሁኔታ ከመግደሉም በላይ፤ ሰው በሲባጐ እያሠረ፣ ይበልጥ እንዲያጠብቀው ውሃ ያፈስስበት ነበር። ፊታውራሪ ተሰማ ከተማ አሥራ ሦስት ሰዎች ቤት ተዘግቶባቸው እንዲቃጠሉ አድርገዋል። ወሩ በላይነህ በፊታውራሪ ኃይለሥላሴ የሚመራውን አርበኛ በማታለል አሲዞ አስፈጅቶአል። አሊ ዑመር ሦስት መቶ ሰማንያ ሦስት ሰው ሜንሶ ወንዝ ላይ አስፈጅቶአል። አበበ ዘገኑ በአርበኞች ላይ ብዙ ጉዳት አድርሶአል። አቶ ሰሙ ንጉሥ ሰጠላት በሰጠው ረቂቅ ምሥጢር የራስነት ማዕረግ ተሰጥቶታል። ንዳው ጭንቅሎ እስከ ዕለተ ሞቱ አርበኞችን ሲፈጅ የኖረ ሲሆን፣ አፈወርቅ አፈቄሣር የተባለው በስንቱ አይደለም፤ በሰጠው አገልግሎት ነው።

ከዚህ በመቀጠል ደግሞ የክህደት ሥራዎችን ዓይነት እንመለከታለን። መሣፍንቱና መኳንንቱ ለጠላት ምሥጢር በማቀበል፣ የጦር ሥልት በማስጠናት፣ የአስተዳደር ምክር በመስጠት፣ የክዱት ጳጳሳት በመገዘት፣ መነኮሳትና ካህናቱ በስንቱ ስብከት ጠላትን ባያሴው ረድተዋል። ራሳቸው ለጣልያን ጦር፣ በተለይም ለባንዳው በመሪነት እየቆሙ ያዋጉ ብዙዎች ናቸው። በጣልያን አደባባይ ላይ እየተቀመጡ አርበኛ ተይዞ በቀረበ ጊዜ ፍርድ እያከበዱ ያስገደሉ አያሌ ናቸው። እንዲህ የሚያደርጉት ለጌታቸው ያላቸውን ታማኝነት በግብር ለማረጋገጥ ነበር። ከታዘዙት በላይ የጭካኔ ሥራ ያካሄዱ እጅግ ብዙ ናቸው። ግደሉ ሲባሉ ያሰቃያሉ። አሰቃይቶ በሙተው ህይወቱን ለማትረፍ በሆነ ደግሞ አንድ ነገር ነው። እነሱ ግን አሰቃይተውም ይገድላሉ።

እነዚህ ሰዎች በዓላማ አንድ ናቸው። ፍላጐታቸው ጥቅምና ክብር ነው። ጣልያን ገንዘብ እንደ ልብ እያፈሰ ይሰጣል፣ ይሸማል፣ ይሸልማል። በመሆኑም ሠርቶ ማደር የማይችልና የማይፈልገው ክህደት ሥራ ገባ። እንዲህ ባለ አቅሙ፣ እናት አገሩን እየሸጠ፣ የገዛ ወንድሙን እያጋለጠ፣ በላ።

ለመሆኑ እነዚህ ሰዎች ለክህደት ሥራቸው ምን ምክንያት ይኖራቸዋል? መቼም ለጥቅም፣ ለክብር ብለን ነው አይሉም። የሚደረድሩአቸው ሌሎች ምክንያቶች ነበሩአቸው። በደቡብ ከነበሩት፣ በዛ

ከተጠቀሱት ምክንያቶች ዋነኛው የጐሣ ልዩነትና የጥቅም ግጭት ነው። ነዋሪው ሕዝብ ነፍጠኛውን እንደ ጠላት ቆጠረው። ለዚህም የማይናቅ ምክንያት ነበረው። እምነትም አንድ የልዩነት ምንጭ ሆነ። ራያ ከጣልያን ጦር ጐን ቆሞ ታላቅ የሰለባ ዘመቻ ያካሄደው፣ በእምነት ምክንያት ጭምር እንጂ በጠላት ስለተደለለ ብቻ አልነበረም። ካቶሊኮች ደግሞ ወገን የመጣላቸው መሰላቸው። የግለሰብ ቂምም ሚና ነበረው። በግል ጉዳዩ ጠላቴ የሚለው ሰው አርበኛ ከሆነ፣ አይለቀኝም ብሎ እሱ ባንዳ ይሆናል። ሁሉም ሞኝነት ነበር።

የጣልያን ወረራ ለኢትዮጵያ ልማት ያስገኛል ብለው የሚያምኑና ይህንኑ የሚሰብኩም ነበሩ። ከሁሉም በላይ የተታለሉት እነዚህኞቹ ናቸው። ጣልያን ለሸንገላ ሲል ያደረገው አንዳንድ ነገር በሕዝብ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ቀላል ስለ አልነበረ ጭምር፣ እየተገደደ የዘመተው ገበሬ ፍርድ የለበትም። ከተርታው ህዝብ መካከል የወጡ ሰዎች ከፈጸሙት በደል ይልቅ፣ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ሹማምንትና መሣንንት የነበሩ የፈፀሙት ክህደት ይበልጥ ሊያስገርም ይገባል። ከዚህ ጋር ተጣምሮ መታየት ያለበት ነጥብ፣ የሚጐዱት ከጠላት ወገን የቆሙት ጭምር መሆናቸው ነበር። ባንዳም ቢሆኑ አርበኛ፣ ከጦር ሜዳ ከገቡ ሞት አይቀርም። ለሀገሩ ነፃነት፣ ለወገኑ ክብር የሞተ ሰማዕት ነው። ለባዕድ የሞተ፣ ለሆዱ እንጂ ሌላ ለምን ሞተ?

በአርበኝነትና በባንድነት የቆሰለውን ሠራዊት ቁጥር ማወቅ ቢቻል በጣም ጥሩ ነበር። ነገር ግን ይህንን በተመለከተ አስተማማኝ ማስረጃ የለም። ቢሆንም መሞከር አይከፋም። በጠላት ላይ ክንዳቸውን ያነሱ አርበኞች ጥቂት ናቸው። ቁጥራቸውም ከጊዜ ወደ ጊዜ፣ ከቦታ ቦታ ይለያያል። በጠቅላላው ሲታይ በ1928 ዓ.ም ከሚያዝያ አስከ ነሐሴ ባለው ጊዜ ውስጥ 40,000 ሠራዊት በአርበኝነት እንደተንቀሳቀሰ፣ በ1929 ዓ.ም ኃይሉ ቀንሶ ወደ 30,000 ዝቅ እንዳለ መገመት ይቻላል። ከዚያ በኋላ እንደገና አንሰራርቶ በ1930 ዓ.ም ወደ 80,000 ከፍ እንዳለ፣ በ1931 ዓ.ም ደግሞ እንደገና ተዳክሞ ወደ 60,000 ዝቅ እንዳለ፣ በ1932 ዓ.ም በአርቁም ጭምር ተመናምኖ ወደ 40,000 አንደ ወረደ ቢገመት አምብዛም ስህተት አይሆንም። የንጉሠ ነገሥቱ መመለስ ሲሰማም ባንዳ ተገልብጦ ከአርበኛ ጋር ተቀላቀለ። የድል አጥቢያ አርበኛ በዛ። በ1933 ዓ.ም ከጥር እስከ መጋቢት በነበረው ጊዜ 200,000 ሠራዊት በጣልያን ላይ እጁን ሳያነሣ አልቀረም።

የባንዳው ቁጥርም እንደዚሁ ከፍና ዝቅ ይላል። በ1928 በዋናው ጦርነት ጣልያን ከኢትዮጵያውያን 20,000 ያህል ሰው ከጐኑ ሳያሰልፍ

አልቀረም። ጣልያን አገር እንደገባ ሥራ አድርጐ የያዘው ገበሬውን እየሰበሰና እያስታጠቀ ማዝመት ሆነ። በ1929 ዓ.ም የባንዳ ቁጥር 100,000 ሳይደርስ አልቀረም። በ1930 ዓ.ም ጦርነቱ በቀላል እንደማያልቅ ለጣልያን ግልጽ ነበር። በዚህ የተነሣ የባንዳ ምልመላውን በይበልጥ አጠናከረ። እስከ 200,000 ሳያደርሰው አልቀረም። የ1931 ዓ.ም በጣልያኖች ዘንድ ሥጋት የተቀሰቀሰበት ጊዜ ስለነበር፤ የባንዳን ኃይል ለማጠናከር ርምጃ ወስደው እያስገደዱ ገበሬ በማዝመት የባንዳ ሠራዊት አዘጋጁ። በዚህ ዘመን የባንዳ ቁጥር እስከ 300,000 እንደደረሰ መገመት እምብዛም ስህተት አይሆንም። ከዚህ ወዲያ አላደገም። እየቀነሰ ሄደ። በ1932 ዓ.ም ከ200,000 አልበለጠም። በመጨረሻው የፍልሚያ ዘመን የባንዳ ቁጥር ይቀንስ እንጂ ከጦር ሜዳው አልወጣም። እስከ መጋቢት ወር ድረስ 100,000 ያህል ባንዳ ለጠላት ሳይረዳ አልቀረም። ከዚያ በኋላ ግን በፍጥነት ቀንሶአል። ከሚያዝያ ወር በኋላ ከጣልያን ጐን የቆመው ከ20,000 ይበልጥ አይመስልም። አንዳንዱ እስከ መጨረሻው ጊዜ ድረስ ከጣልያን ጐን ቆሞ የተዋጋ አለ። በአምባለጌ፣ በወለጋ፣ በከፋና በኢሉባቡር፣ በመጨረሻም በጉንደር እስከመጨረሻው ለጣልያን የተዋጋለት ባንዳ ቁጥር ከ10,000 አያንስም።

አርበኛው የሚዋጋው ሚስቱን፣ ልጁን፣ ያለውም አሽከሩን እንደያዘ ነበር። ስለዚህ ለአንድ አርበኛ ሦስት ቢያንስም ሁለት ጀሌ ይከተለዋል። ከባንድነት ከድቶ የገባው ግን አብዛኛው ደረቅ ጦር ነበር። ማለትም ጓዝ አልነበረውም። ስለዚህ ከ240,000 እስከ 300,000 ሰዎች በጓዘኝነት፣ በጀሌነት ሳያገለግሉ አልቀሩም። በዚህ የጓዝ ቡድን ውስጥ የቀድሞ ባሮችም ነበሩ። በጣልያን ላይ ያላቸው ጥላቻና ለጌቶቻቸው የነበራቸው ታማኝነት፣ ከአርበኞቹ ዘመዶች በላይ ነበር። ይህንን ሁኔታ እኔ ራሴ ያየሁ ስለሆነ፣ መመስከር ይገባኛል።

አርበኝነትን ከመሠረቱ ሰዎች አብዛኞች በዚያው በጦርነት ጊዜ አለቁ። በሕይወት ቆይቶ ለሚያዝያ 24 ቀን 1933 ዓ.ም የበቃ እጅግ ጥቂት ነው። በእኔ ግምት ከ10,000 አይበልጥም። የሞተውን ወደ 78,500 ሰው ጨምሮ፤ 88,500 አሥረኛውንና ስደተኛውን ጨምሮ፤ 180,000 ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ሳያወላውል በዓላማው ጸንቶ የዜግነት ግዴታውን ተወጥቶአል ማለት ይቻላል።

የውስጥ አርበኞች ሥራ አርበኝነትን ረድቶአል። መረጃ በመስጠት፣ ሲቻልም መሣሪያ በማቀበል፣ አንዳንድ ጊዜ መድኃኒት በመላክ በብዙ ደክመዋል። እነ ወይዘሮ ሸዋረገድ ገድሌና ኬጀ ኃይሉ የሚጠቀሱ ናቸው። ከዚህ ላይ መጠቀስ ያለበት ሌላው ነጥብ ደግሞ በቀዳማዊ ኃይለ

ሥላሴ ላይ ቅሬታ ባላቸው አርበኞች ላይ ጥቃት እንዲደርስ ያደረጉ ወገኖችም እንደነበሩ ነው። የደጃዝማች ፍቅረ ማርያም አሟሟት ዱካ መጥፋት፣ የደጃዝማች ኃይሉና የባልደረቦቻቸው አልቂት ለዚህ አባባል ማስረጃ ሆነው ሊታዩ ይችላል። በፊታውራሪ ወልደፃድቅ ዘውዴ ላይ ከመስከረም 7 ቀን 1933 ዓ.ም እስከ የካቲት 13 ቀን 1933 ዓ.ም ጣልያን የዘመተባቸውና በተለይም የባንዳ ናዳ የወረደባቸው በዚህ ዓይነት ዘዴ እንደነበር እውቅ ነው።

ከወልወል እስከ ጉንደር በተደረገውና ከ1927 እስከ 1934 ዓ.ም በቆየው የኢትዮጵያና የጣልያን ጦርነት ጊዜ፣ በኢትዮጵያውያን መካከል የተስተዋሉ የአምነትና የክህደት ሥራዎች ሲታዩ፣ አስገራሚ ገጽታ አላቸው። የንጉሠ ነገሥቱ ሹማምንቶች፣ መኳንንቶች፣ ባለሙዋሎች ከጣልያን ጐን ቆሙ። ለሀገራቸዋ የተዋጉላት፣ የሞቱላት፣ በንጉሠ ነገሥቱ ዘንድ ሞገስ አጥተው የታሠሩ፣ የተገረፉ ሆኑ። ለአብነት ደጃዝማች አውራሪስ ዱሉ፣ ደጃዝማች ባልቻ እና ደጃዝማች በየነ ይጠቀሳሉ። ሌላው ሕዝብ እንደ ልማዱ፣ እንደ ሥርዓቱ ኑሮውን ቀጠለ።

<u>ማጣቀሻ ፅሑፎች</u>

1. ጳውሎስ ኞኞ፣ *የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦርነት*፣ ገጽ 53።
2. ተክለ ፃድቅ መኩሪያ፣ *የኢትዮጵያ ታሪክ፣ ከአጼ ቴምድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ*፣ ገጽ 221።
3. ሞገስ ክፍሌ፣ *የሙሶሊኒ ምሥጢር*፣ ገጽ 70።
4. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 90-99።
5. ከርዕሰ ደብር ዕቀቦ እንድርያስ፣ አሥመራ የተነገረኝ።
6. ጳውሎስ ኞኞ፣ ገጽ 52።
7. ከበደ ተሰማ፣ *የታሪክ ማስታወሻ*፣ ገጽ 445።
8. ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፣ *ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ 1ኛ መጽሐፍ*፣ ገጽ 245።
9. ሙሉ ሰው ምትኩ፣ *የአርበኞች ትግል ከፋሽስት ጋር*፣ ገጽ 25-26።
10. ገሪማ ታፈረ፣ *ጉንደሬ ቢጋሻው*፣ ገጽ 154.156።
11. Greenfield, *Ethiopia*, p.194-204.
12. ከበደ ተሰማ፣ ገጽ 447-449።
13. ተክለ ፃድቅ መኩሪያ፣ ገጽ 267።
14. ሰይፉ አበበ፣ *የታሪክ ቅርስ*፣ ገጽ 63 እና 184-185።
15. ሐዲስ ዓለማየሁ፣ *ትዝታ*፣ ገጽ 103-104።
16. ገሪማ ታፈረ፣ ገጽ 83-84።
17. Sabacchi, p.137 እና 155.

ምዕራፍ አርባ ሰባት
ግጥምና ቅኔ

የኢትዮጵያ ሕዝብ አስተያየቱን የሚገልጽባቸው ብዙ ባህላዊ መንገዶች አሉት። በቤተክርስቲያን ቅኔው ይፈሳል። በገጠር ሴቱ፣ ወንዱ ይዘፍናል። በአደባባይ ፉከራ ይካሄዳል። በመንገድ፣ በጉዞ ላይ ሽለላ፣ ቀረርቶ አለ። በመንደር እንጉርጉሮው አይቀርም። በክብረ በዓል፣ በሰርግና በድግስ ቤት አዝማሪ ግጥሙን ያንቆረቁራል። በመኪንንት ቤት በገና ደርዳሪ፣ በሀዘን ቤት ሙሾ የተለመደ ነበር።

በጦርነቱም ጊዜ እንደዚሁ ነበር። ቅኔዎቹ ሕይወትን በመንፈሳዊ አመለካከት ይገልፃሉ። ሴቶች ባሎቻቸውን በዘፈን ያደፋፍራሉ። ሲበረታ ያሞግሳሉ፤ ሲፈራ በነገር ይጐንጣሉ። ሠራዊቱም እየሸለለ ራሱን ያጽናናል። ሲያስፈልገውም አለቆቹን ይወቅሣል። አንዳንዱ በግልጽ ይናገራል። ሌላው በምሥጢር በነገር ይወጋል። በጠላት ጊዜ ይሰሙ የነበሩ ግጥሞች የማደፋፈሪያና ማበረታቻ፣ የትንቢት መናገሪያ፣ የተግሣጽና የምክር ዘይቤ ነበራቸው። በአለቆች ዘንድ ይደመጡ፣ በሕዝብም ዘንድ ይሰሙ ነበር። አንዳንዶቹን ተጥሎ እንመለከታለን።

የጠላት ወረራ እየተቃረበ ሲሄድ፣

"አፈራ ደድሆ፣ አፈራ ደድሆ፣
የፈራነው ነገር መጣ ድሆ ድሆ" ተባለ።

በጦርነት ወቅት፣

"አህያ መጣች ተጭና ቂንጣ፣
ኃይለሥላሴ እጅህን አውጣ" አለ።

የአርበኝነት እንቅስቃሴ ሲጀመር ጀግናው፣

"አልበላንም፣ አልጠጣንም፣ አልጠናም ክንዳችን፣
እንዲሁ እንሞታለን ለነፃነታችን" አለ።

ጣልያን ድል ባረገ ጊዜ፣

"በማይጨውስ ቢሆን መች ይገባ ነበር፣
በአጋዴን ቢሆን መች ይገባ ነበር፣
በሰማይ ላይ ገባ ባላወቅነው አገር" ተባለ።

የንጉሠ ነገሥቱ መሄድ በተሰማ ጊዜ፣

"ፍርድ ለማግኘት ነው በዳኛ መግጠም፣
ዋቢ አናሳልፍም ሳንፈጣጠም" አለ።

የየካ ደብረ ሣህል አብምኔት አለቃ በላይ፣

"ተመልሰሽ ግቢ ተማሪ ቤት ቅኔ፣
ከወንዶቹ ጋራ መዋሌ ነው እኔ" ብለው ቀበና ሸፈቱ።

ነጋድራስ ተሰማ እሸቴ ጣልያን እንዲዘምሩ ቢያስገድዳቸው፣

"የሀገሬ ልጆች በከንቱ አለቃችሁ፣
ጊዜው እንዳመጣ ባንድነሆን ብላችሁ" አሉ።

ጣልያንና አርበኛ በተፋዘዙ ጊዜ፣

"ወይ አነሱ አይመጡ፣ ወይ እኛ አንሻገር፣
መልካው ጦም አደረ የሁለት ፊሪ አገር" አሉ።[1]

ማመንታት በፀዘ ጊዜ አንድ ሽላይ፣

"እንሂድ አርበኞች ወርደን እናምሰው፣
ምን ይመክተናል ማተብ የሌለው ሰው" ብሎ ሸለለ።[2]

ለእነ ጀዝማች ኃይሉ ወልደመድኅን፣

"የነአጅሬን እህል አልበላም እርሜ ነው፣
ያዘራው መትረየስ፣ ያበቀለው ደም ነው" ተብሎ ተሰቀሰ።[3]

ባንዳን ምን ማድረግ እንደሚሻል ግራ በገባ ጊዜ፣

"በለው በምንሽር፣ በለው በምንሽር፣
እንዳይሄድ እንዳይቀር፣ እንዳይሞት እንዳይሽር" ተባለ።

ደጃዝማች ኃይለሥላሴ ጉግሣ በከዳ ጊዜ፣

"ምንኛ ይረግሙህ አዜ ዮሐንስ፣
የጃላተ ሙሴን ሥርዓት ስታፈርስ" ተባለ።[4]

ለጣልያን የሚገባው በበዛ ጊዜ፣

"ጉበዝ ይሙት፣ ጀግና ይሙት፣
- ፈሪ ይቁም ቢሻው፣
አተላ መሸከም ይችላል ትከሻው" ተብሎ ተሸለለ።

ስለ ገንዘብ ወዳዶች፣

"ለገንዘብ የሚሞት፣ ይቅር አይወለድ፣
አይበጅም ለሀገር፣ አይሆንም ለዘመድ" ተብሎ ተገጠመ።

ጣልያን ራያን አዝምቶ ሽዋን ባስለበ ጊዜ፣

"ኢትዝክር ለነ አበባነ ዘትካት፣
ፍጡነ ይርከበነ ሣልስ እግዚአ፣
አስመ ተመንደብነ ፈድደ" የሚለው ምስባክ ተሰበከ።

የደብረ ታቦርን ሕዝብ ጣልያን በመትረየስ በፈጀ ጊዜ አንድ ሊቅ፣

"ወአግባእከነ ድኅሬነ በ ፀርነ፣
ይብልዑነ ከመ አባግዕ፣
ወተማስጡነ ጸላእትነ፣
ወዘርከነ ውስተ አሕዝብ፣
አስመ አህመምከነ በብሔርነ በብሔርነ ኢትዮጵያ፣
ወደፈነነ ጽላሎተ ሞት" አሉ።[5]

አቡነ ጴጥሮስ በተገደሉ ጊዜ፤

“የበጮች አረኛ ጴጥሮስ ሐዋርያን፣
ተኩላ ቢመጣበት ሲነጥቅ በጮቹን፣
ተኩላ ሲፈጃቸው ዓይኔ አያይም ብሎ፣
ከበጮች በፊት ሞተ ተከልሎ” ተባለላቸው።[6]

ፊታውራሪ ኃይለሥላሴ ዘረፉ በተገደለ ጊዜ፣

“በአገሌም በአገሌም አትዘክሩበት፣
ኃይለሥላሴ ነው በጋሻው ያራበት” ተብሎ ተገጠመ።

የወንድምዋን ራስ ጣልያን ቆርጦ ያዞረባት ሴት፣

“የፋሽስት ትምህርት ምን ያህል ከባድ ነው፣
የወንድሜን ራስ እንደዚህ ያዞረው” አለች።

ሙሶሊኒ አርበኞች እንዲደመሰሱ ማዘዙ ሲሰማ፣

“ጌታው ሙሶሊኒ ምን አትበጠበጠው፣
አልነገረውም ወይ ከአድዋ ያመለጠው” ተባለ።[7]

የደቡብ ጦር የጠላትን ማየል ባየ ጊዜ፣

“ጠላት ከሚጠጣው የሀገሬን ውሃ፣
የእኔ ደም ይቀዳ በዱር በበረሃ” አለ።[8]

የጥቁር አንበሳ ጦር የሚተምመው፣

“በለው! በለው! አትለውም ወይ፣
ጥቁር አንበሳ አይደለህም ወይ?” እያለ ነበር።[9]

ጥቁር አንበሳ ከወለጋ እንዲወጣ በተገደደ ጊዜ፣

“እናት ኢትዮጵያ ውዲቱ ዉዲቱ፣
ላንቺ የማይረዳ ላለ በሕይወቱ፣
በረከትሽን ይንሳው እስከ ዕለት ሞቱ።”[10]

መከራ በጸና ጊዜ አርበኛው፣

“ጠላትሽ ተዋርዶ ስምሽ እስኪከበር፣
እንሸከማለን የመከራ ቀንበር” አለ።[11]

በነጮች ላይ ጥላቻ በተነሣ ጊዜ፣

“አንግዲህ ባገሬ ነጭ ጤፍ አይብቀል፣
አረም ነው እያሉ ከሥሩ ነው መንቀል” ተባለ።[12]

በእርቅም ጊዜ ሁኔታው ያላማረው ሰው፣

“ሽዋ ሆድክን አትስጥ ያለሠረገላ፣
ባስፈለገህ ጊዜ ሽተት ወደ ቆላ።
አሁን ይሰጥና ዳቦ ለሁለት፣
የዛሬ ሣምንት አጋይን ዝመት” ተብሎ ተገጠመ።[13]

አለቃው ከጦር አጋፍጦት የሸሸበት ወታደር፣

“የጭዋ አስተኛንት እንደዚህ ነወይ?
ራስን ወደ ታች እግርን ወደ ላይ” አለ።[14]

ጣልያን በተደናገጠ ጊዜ፣

“ተጉዞ ተጉዞ ነጭ እንደ ደመና፣
መመለሻው ጠፋው ያገሩ ጐዳና” ተብሎ ተገጠመበት።[15]

የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መመለስ ከመሰማቱ ቢያንስ ከአንድ ዓመት በፊት፣

“አህያ መጣች ተጭና ጓሣ፣
ኃይለሥላሴ ሙቶ ተነሣ” ተባለ።

ጃንሆይ ጐጃም መግባታቸው ከተሰማ በኋላ ጣልያን ለአቶ ተሰማ ደባልቀው ሹመት ሊሰጥ እዝማሪ፣

“ማን አግኝቶ ያውቃል እንዲህ ያለ ሹመት፣
ከተሰማ በላይ ደጃዝማችነት” ብሎ አሸሚጠጠ።

በጦርነቱ በወደቁ ጀግኖች ነጻነት ሲመሰክ፣

“የተዘራው ደምህ መቼ ከንቱ ቀረ፣
ነፃነት አፍርቶ ስምህ ተከበረ” ተባለላቸው።

በጠላት ላይ ድል በተገኘ ጊዜ፣

“ደሙን ያፈሰሰ ልቡ እየነደደ፣
በአርበኝነት ታጥቆ ጠላት ያስወገደ፣
ንጉሡን አገሩን ክብሩን የወደደ፣
ነፃነቱን ይዞ መልካም ተራመደ” የሚል የሰንደቅ ዓላማ መዝሙር ወጣ።

ነፃነትን ባስመለሱ ጊዜ ለንጉሠ ነገሥቱ ብዙ ደጋግ ግጥም ተገጠመላቸው። ከእነዚህም አንዱ በከፊል፣

“የይሁዳ አንበሣ አንተ ንጉሣችን፣
በድል መለስክልን ከሞት አገራችን፣
ሞት እንዳያገኘን ዘለዓለም ኑርልን።
አቸናፊው ንጉሥ የይሁዳ አንበሳ፣
መድፍህ የብስን አልፎ ጐጃም ላይ ቢያገሳ፣
እንኳን የሰው ወገን ደስ አለው እንስሳ” የሚል ነበር።[16]

ባንዳ የንጉሠ ነገሥቱ ባለምዋል መሆን ሲጀምር አርበኛ፣

“እናት ኢትዮጵያ ሞኝ ነሽ ተላላ፣
የሞተልሽ ላለ የገደለሽ በላ” አለ።[17]

ንጉሠ ነገሥቱ ይህቺን ቃል ባለማድመጥ ተታለሉ።

ማጣቀሻ ፅሑፎች

1. ታደሰ ዘወልዴ፣ *ቀሪን ገረመው*፣ ገጽ 119።
2. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 11።
3. ከአቶ ኃይለ ማርያም ወልደ ኪዳን የተገኘ።
4. ተክለፃድቅ መኩሪያ፣ *የኢትዮጵያ ታሪክ ከአፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ*፣ ገጽ 230።
5. ገሪማ ታፈረ፣ *ጐንደሬ ቢጋሻው*፣ ገጽ 151።
6. መኮንን እንዳልካቸው፣ *መጽሐፍ ማር ነው*፣ ገጽ 103።
7. ታደሰ ዘወልዴ፣ ገጽ 91።
8. ሰይፉ አባ ወሎ፣ *የታሪክ ቅርስ*፣ ገጽ 49።
9. ታደሰ ሜጫ፣ *ጥቁር አንበሳ*፣ ገጽ 72-73።
10. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 60።
11. ከግራዝማች ከበደ አርጋው ቀንሎ የተገኘ።
12. ታደሰ ዘወልዴ፣ ገጽ 493 እና 493።
13. ከግራዝማች ኃይሌ ዳርጌ የተገኘ።
14. ከሻለቃ ክፍሌ ደርሴ የተገኘ።
15. ገሪማ ታፈረ፣ ገጽ 160።
16. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 255 እና 258።
17. ዩፍታሔ ንጉሤ፣ *የአማርኛ ሰዋሰው*፣ መርሥዔ ሐዘን ወልደ ቂርቆስ።

ምዕራፍ አርባ ስምንት
የጣልያኖች ፖሊሲ

ኢትዮጵያን ድል ካደረገ በኋላ የጣልያን መንግሥት ለሀገሩ አዲስ ስም አወጣ። ሀገሩን የኢጣልያ ምሥራቅ አፍሪካ /አፍሪካ ኦሪየንታሌ ኢታሊያና/ አለው። ይህ ስም አጠራር ኢትዮጵያ የሚለውን ቃል ከምድር ገጽ ለማጥፋት ነበር። ለውጪዎች፣ ኢትዮጵያ የሚለው ስም ይከብዳቸዋል። ዓረብ ሀበሽ ይላል። ፈረንጅ አቢሲንያ ይላል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስሙ መጠቀሱ ይቀፋቸዋል፣ በተለይም ለእንግሊዞች። ሞሶሊኒ የሞከረው በዚሁ ስም አጠራር የተጨነቁትን ሁሉ ለመገላገል ነበር።

ደግሞም ልዩ፣ ልዩ አዋጅ አወጣ። ለሲብያ፣ ለኤርትራና ለሶማሊያ ጭምር በማስመሰል፣ ለሁሉም ቅኝ ግዛቶች ፖሊሲ ቀረጸ። ነገር ግን ዋና ዓላማው ኢትዮጵያ ነበረች። አንድ ሕግ ያወጣል፣ እሱ ሳይሠራ ሲቀር ሌላ ያስደግመው ገባ። በዚህ ዓይነት አንዱን ሕግ ሌላው እያፈረሰው፣ አንዱን ፖሊሲ ተከታዩ እየጣሰው ሄደ፣ ዝብርቅርቁ በዛ። ችኩሉ የጣልያን መንፈስ ከጊዜው አስቮኳይነት ጋር እየተጣመረ በጥድፊያ ላይ ጥድፊያን ተከተለ። በመሆኑም ዝግ ብሎ የሚራመደውን የኢትዮጵያን ሕዝብ አመለካከት ለመለወጥና ከእሱ ሥርዓት ውስጥ ለማስገባት አቃተው። ኢትዮጵያን ከእሱ ሥርዓት ማግባት ሲያቅተው፣ እሱ ራሱ ወደ ኢትዮጵያ ባህልና ሥርዓት መግባት ያዘ። ከዚህ ድምዳሜ የሚያደርሱትን ነገሮች ቀጥሎ እንመለከታለን።

ጣልያኖች ለጦርነት ቸኩሉ። በፖለቲካ ተፅዕኖ ቀጥሎው ቢሆን ኖሮ ብዙ ጥቅም ያገኙ ነበር። ምክንያቱም በዚያን ጊዜ በነበረው ዓለም አቀፍ ሁኔታ ኃይላቸው ሚዛን አግኝቶ ስለነበር፣ ብዙ ተቀናቃኝ አልነበረባቸውም። የእንግሊዞችን ሽምግልና ተቀብለው ቢሆን ኖሮ፣ ቅጥያ ሊያገኙ ግዛትም ላያጡ ይችሉ ነበር። ኢትዮጵያም ይህንን ዓይነቱን ተፅዕኖ ለመቋቋም አቅም አታገኝም ነበር። የዓለም ጉብረተሰብም ጣልያንን ግፈኛ አድርጐ አይቆጥራትም ነበር። ኢኮኖሚዋ ተበላሽቶ አዘቅት አያወርዳትም ነበር። ምናልባትም በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጊዜ ከጀርመን ጐን እንድትቆም የሚያስገድዱአት የፖለቲካ ሁኔታዎች አይፈጠሩም ነበር። ምናልባትም የኢማኑኤል ንግሥና ወድቆ የሳቮይ ሥርወ መንግሥት አይነቀልም ነበር። እንኳን አልሆነ እንጂ፣ ያ ዓይነቱ ሁኔታ ለኢትዮጵያ ከጦርነቱም የከፋ ይሆንባት ነበር።

በጦርነቱ ጊዜና ድል ከአደረገችም በኋላ ጣልያን በኢትዮጵያውያን ላይ የጭካኔ ሥራ አካሄደች። ዓለም ያወገዘውን ዓይነት የአረመኔነት ግብር ሠራች።[1] በዚህ ምክንያት የዓለምን ሕዝብ ድጋፍ አጣች። ኢትዮጵያውያንን ከእልህ አስገብታ ጦርነቱ ከሽምቅ ፍልሚያ ውስጥ እንዲገባ አስገደደችው። በሌላ አነጋገር በውጭ አገር የሚካሄደውን የኢትዮጵያን የፖለቲካ አቅዋም

አጠናከረች። በሀገር ውስጥ ደግሞ የአርበኝነት ሥራ በገዛ ራስዋ ላይ አቋቋመች፣ አበረታች።

ጣልያን በሕዝቦች መካከል የዘር ልዩነት አነሳች። ኦሮሞውን፣ ትግሬውን፣ ጉራጌውን፣ ሱማሌውን፣ ወላይታውን ሌላውንም ከሰማንያ በላይ በሚሆነው ጐሣ መካከል የርስበርስ መጠላላት ሥራ ቀሰቀሰች። ዓላማዋ የቅኝ ግዛትን በምንም ሁኔታ የማይቀበለውን አማራውን ለማስጨረስ ነበር።[2] ነገር ግን ሳይሠራ ቀረ። የኢትዮጵያ ህዝብ በጐሣ ቢለያይም በሀገር ጉዳይ አንድ መሆኑን በግብር እያረጋገጠ ሲሄድ፣ የኢጣልያ ድካም መና ሆነ።

የዘር ልዩነትን በኢትዮጵያውያን መካከል እያራመደች፣ ጣልያናውያን ንጹሕ ደም ያላቸው ስለሆኑ ከሌላው ዘር ጋር እንዳይቀላቀሉ ከለከለች። በመኖሪያና በሥራ ቦታ፣ በመዝናኛና በአደባባዮች እንዳይቀላቀሉ አደረገች።[3] ይህ ድርጊት ኢትዮጵያውያን የራሳቸውን ጉዳይ በራሳቸው ዘዴ እንዲሠሩ ምቹ ሁኔታዎችን ፈጠረ። እንዲሁም በወቅቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ በእነሱ ላይ ያደረበትን ጥላቻ፣ ንቀት ይበልጥ አከረረው። የጣልያን የአስተዳደር ጉድለት ገሐድ ወጣ።

ሌላው በኢትዮጵያ ሕዝብ ልዩነት ለማነሳሳት የሞከረችበት መንገድ ኃይማኖት ነበር። በክርስቲያኑ ላይ እስላሙን ለማነሳሳት ልዩ ጥረት አደረገች። እስላሞች መጨቆናቸውን በመግለጽ ብዙ ወተወተች። በጣልያን አገር ከካቶሊክ ተከታዮች በስተቀር ሌላው የፖለቲካ ቦታ እንደሌለው እንዳልታወቀባት ሁሉ፣ በአፍዋ ይህንን ዓይነት የኃይማኖት ቁርሾ እየቀሰቀሰች፣ በቀኝ እጅዋ ጳጳሳት እየገደለች፣ አብያተ ክርስቲያናት እያቃጠለች፣ ካህናትንና መነኮሳትን እየፈጀች፣ በግራ እጅዋ ደግሞ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንን የሚያጠናክር የሚመስል ተራ ሙከራ አደረገች። ለጳጳሳት ሹመት ሰጠች፣ ሥርዓተ ቤተክርስቲያንን በተመለከተ ሕግ አወጣች።[4] የእስክንድርያ ቤተክርስቲያን ድርጊቱን አወገዘች። ከባንዳና ከሥርዓቱ ተጠቃሚዎች በስተቀር፣ ሕዝብ አዳዲሶቹን ጳጳሳት እንደርኩሳን አድርጉ አያቸው። ይህም ሳይሠራ ቀረ።

ጣልያኖች መሬት ለመያዝና የእርሻ ሥራዎች ለማቋቋም ተጣደፉ። ጐንደር ዳባት ላይ፣ ሸዋ ሆለታ ላይ፣ አርሲ ጐንዴ ላይ፣ ሐረርጌ ሂርና ላይ ታላላቅ እርሻ አቋቋሙ። ብዙ ገንዘብ ወጭ አደረጉ። እሱም የተጠበቀውን ጥቅም ሳያስገኝ ቀረ። በኢትዮጵያውያን ገበሬዎች ዘንድ የመሬት ንጥቂያ መሆኑ በግብር ስለተረጋገጠ ተቃውሞን አጠናከረ።[5] እንደሌላው ሁሉ በዚህም ረገድ የተደረገው ሙከራ ውጤቱ መክራ ሆነ።

አስተዳደሩን በዘር ልዩነት ላይ በተመሠረተ አከፋፈል ቀየሰችው። ትግሬ ወደ አሥመራ ተከለለ፣ አማራ፣ ጐንደር፣ ሱማሌ፣ ሞቃድሾ፣ ኢሣና አፋር ሐረር፣ ኦሮሞ-ሲዳማ፣ ጂማ ሆነ። በነባሩ የአገር ስም የሚጠራው ሸዋ

ብቻ ሆነ። እሱንም ለመገነጣጠል ልዩ ጥረት ተደረገ። ይህም የተጠበቀውን ያህል ሳይረዳ ቀረ።

በመስከረም ወር 1930 ዓ.ም ጣልያኖች ፖሊሲአቸውን መለወጥ ጀመሩ። በግራዚያኒ ቦታ ዱክ ደ አምስታ እንዲተካ ታሰበ። ከዓላማዎቹ አንዱ የጣልያን ንጉሣውያን ወገኖች አስተዳደር፣ ከፋሽስቶች የጭካኔ ሥራ የተለየ መሆኑን በግብር ማሳየት ነበር። ንጉሡ ኢማኑኤል ጦርነቱን እንዳልፈቀደ፣ ጳጳሱ መርዙን እንዳልባረከ፣ መሣፍንቱ በጦርነቱ እንዳልተሳተፉ ሁሉ!

ግራዚያኒ እንዲሻርና በምትኩ የአስተዳደር ችሎታ ያለው አንድ መሥፍን እንዲሾም፣ ሞሶሊኒ ለንጉሡ ለሣልሣዊ ኢማኑኤል ሃሳብ አቀረቡ። ከሁኔታው አስፈሪነት የተነሣ የጣልያንን ዘውድ የሚያረክስ አንዳይሆንበት ቢሰጋም፣ ንጉሡ ከጳጉሜ 4 ቀን 1929 ዓ.ም ጀምሮ ሲያውጠነጥን የቆየውን ሃሳብ ስለተቀበለው ዱክ አሚዲዮ ደ አምስታ ተሾመ። ታህሣሥ 17 ቀን 1930 ዓ.ም /ዲሰምበር 26 ቀን 1937/ አዲስ አበባ ገባ። መስፍኑ ከሞሶሊኒ የተሰጠውን መመሪያ በድጋሚ ለማስታወስ፡-

1ኛ. ጣልያኖች ከቅኝ ግዛት ሰዎች መቀላቀላቸው ውርደት ስለሆነ ለጣልያን ንጹህ ዘር ጥበቃ እንዲያደርግ።

2ኛ. ስለጦርነቱ ሮም የሚደርሰው ሪፖርት የተጋነነ ስለሚመስል እርግጠኛውን እንዲያስታውቅ።

3ኛ. የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት በገንዘብ ረገድ ራሱን እንዲችል እንጂ ከጣልያን ሀገር ገንዘብ እንዳይጠይቅ።

4ኛ. በኃይማኖቶች ምክንያት የሚታየውን ችግር እንዲያቃልል።

5ኛ. አገረ ገዥዎች ሙሉ ሥልጣን እንዲኖራቸው እንዲያደርግ ነበር።

ነገር ግን ባዲሊዮ ተሸሮ የዱካ ደ አምስታ መሾም በአርበኞች ስሜት ላይ አንዳች ልዩነት እንዳልፈጠረ ተመልክተናል።

እሱም አዲስ አበባ እንደገባ ሁኔታዎችን ለማሻሻል ሞከረ። ሕዝብን ለማረጋጋትና ጦርነቱም ሥርዓት እንዲይዝ ለማድረግ ሞከረ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ስለጣልያን ዓላማ እውነተኛ ትምህርት አግኝቶ ነበርና አዲሱ ሽንገላ ሳይቆነጥጥ፣ ሥር ሳዩዝ ቀረ።

በጣልያኖች ዘንድ ባለምዋልነት ለማግኘት ሌጠአቸውን ገልብጠው የነበሩትና፣ በአስክንድርያው ፓትርያርክ ክሹመታቸው እንዲሻሩ፣ ክህነታቸው እንዲፋቅና ከቅድስት ማርቆስ ቤተክርስቲያን የተለዩ እንዲሆኑ የተወሰነባቸው አቡነ አብርሃም ሞቱ። ዱክ ደ አምስታ በዚህ አጋጣሚ በመጠቀም፣ በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ አክብሮት የነበራቸውን የአዲስ ዓለሙ የሐዲስ መምህር፣ አለቃ አሸቱን ሊቀ ጳጳስ ሆነው እንዲመረጡ አደረጉ። እሳቸውም ጳጉሜ 5 ቀን 1931 ዓ.ም በፒየሮፍራንክ ሲባሲቢነት በተካሄደ ጉባዔ

ተመርጠው፤ መስከረም 7 ቀን 1932 ዓ.ም ሥርዓተ ጵጵስና ተክበረላቸው። አቡነ ዮሐንስ ተባሉ።

ጹክ ደ አምስታ አሜደዮ ዲ ሳቮያ በሚል የማዕረግ ስም፤ ሐምሌ 21 ቀን 1934 ዓ.ም ስለኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ሕግ አወጣ። ሕጉም ስለሊቃውንት ጉባዔ፤ ስለ ሊቀ ጳጳሳት፤ ስለ ጳጳሳት፤ በጳጳሱ ስለሚታዘዙ ሹሞች፤ ስለ ቤተክህነት ዋና ፀሐፊ፤ ስለ እጨጌ፤ ስለ ሊቃነ ካህናት፤ ስለ መንፈሳዊ ምክር ጉባዔ፤ ስለ ሀገረ ስብከት አከፋፈል፤ ስለ ሀገረ ስብከት መሻሻል፤ ለጣልያን ንጉሥና ለወራሾች ስለመታዘዝ መሐላ፤ ስለ ቤተክርስቲያን ክብር፤ ስለ ቤተክርስቲያን ሥነ ሥርዓት፤ ስለ ልብሰ ተክህኖ፤ ለሊቀ ጳጳሳቱ ስለሚሰጠው ክብር፤ ለእጨጌው ስለሚሰጠው ክብር፤ ለየአውራጃው ጳጳሳት ስለሚሰጣቸው ክብር፤ ስለማተሚያ ቤትና ስለተማሪ ቤት፤ ስለዜና ቤተክርስቲያን ጋዜጣ፤ ስለ ኃይማኖት ትምህርት ደንብ፤ ስለ ኃይማኖት ትምህርት ቤት፤ ስለገንዘብ ሥራ አካሄድ፤ ስለ ገዳማት እና አብያተ ክርስቲያናት አሰቆች፤ ስለ ሥልጣነ ክህነት አሰጣጥ፤ ስለአዳዲስ ቤተክርስቲያን ሥራ፤ ስለ ኢየሩሳሌም ገዳማት አሰቆች አሟሟም፤ በጠቅላላው ሠላሳ ስድስት አንቀጽ ነበረው።

በደንቡ ውስጥ የኢጣልያ ሥራ በትክክል ተጠብቆአል። የአጠባበቁም ሥልት ለቤተክርስቲያኗ ለመጥቀም ሲባል የተደረገ እንዲመስል ጥንቃቄ ተደርጐአል። ቤተ ክርስቲያኒቱን ለመጥቀም እንዲመስል በአዋጁ ውስጥ የተዘበዘበው ነገር ረጅም ነው። ዝርዝሩን ከለዋጁ መመልከት ነው። እኛ ግን የጣልያን ሥልጣን ለመጠበቅ የተደረገውን ጥንቃቄ እንዳስሳለን።

አንቀጽ 2፦ በሊቃውንት ጉባዔ የሚቀመጡት አባላት ቁጥር በቄሣር እንደራሴ ይወሰናል፤

አንቀጽ 3፦ ዋና ፀሐፊው በቄሣር እንደራሴ ይሾማል፤

አንቀጽ 5፦ እጨጌው በቄሣር እንደራሴ ይሾማል፤

አንቀጽ 6፦ የመንፈሳዊ ምክር ቤት መማክርት በቄሣር እንደራሴ የሚሾሙ ናቸው፤

አንቀጽ 7፦ አሥሩ ሀገረ ስብከቶች ሸዋ፣ ኤርትራ፣ አማራ፣ ጉጃም፣ ወሎ፣ ወለጋ፣ ወላሞ፣ ሐረር፣ አዲስ አበባና ደብረ ሊባኖስ ናቸው፤

አንቀጽ 10፦ጳጳሳት በሊቃነ ጳጳሳት ፈቃድ፣ በቄሣሩ እንደራሴ አዋጅ ይሾማሉ፤ ኤጲስ ቆጳሳት እንዲመረጡ የሚያዘው፣ ከተመረጡም በኋላ የሚሾመው የቄሣሩ እንደራሴ ነው፤

አንቀጽ 11፦ የቤተክርስቲያን ሹማምንት ሁሉ ሲሾሙና ሥራቸውን ሲረከቡ ለቄሣርና ለወራሾች ታማኝ ሊሆን ይምላሉ፤

አንቀጽ 13፦ የቤተክርስቲያኒቱ ሥርዓትና ደንብ የቄሣሩ እንደራሴ አይቶት ይወጣል፤

አንቀጽ 14፦ ልብሰ ተክህኖ የቄሣር እንደራሴ ከአየው በኋላ ይወጣል፤

አንቀጽ 20፦የኃይማኖት ትምህርት ደንብ የቄሣሩ እንደራሴ አይቶ ይቀበለዋል፤

አንቀጽ 23፦ ስለገንዘብ አያያዝና ስለ ሥራ አካሄድ የተለየ ደንብ ይወጣል፤

አንቀጽ 27 እና 28፦ አገረ ገዥው የቤተክርስቲያን አለቃና የገዳም መምህር፣ አማካሪዎች ይሾማል፤

አንቀጽ 33፦ አዲስ ቤተክርስቲያን እንዲሠራ የሚፈቅድ አገረ ገዥው ነው፤

አንቀጽ 34፦ እየሩሳሌም ላሉ ገዳማት ሁሉ የቄሣሩ እንደራሴ መምህርን ይሾምላቸዋል፤ መባሉን ልብ እንበል።[6]

ይህ ሁኔታ በኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ተከታዮች ዘንድ ከፍተኛ ግንጋኔ ፈጠረ። የጣልያን ፍላጐት የኢትዮጵያን ቤተክርስቲያን በልዩ ልዩ ዘዴ ጉትቶ፣ ሮም ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ሥር ለማስገባት ስለመሆኑ ጥርጣሬ አሳደረ። ለዚህም አራት ዋና ዋና ምክንያቶች ነበሩ። ከእነዚህ አንደኛው በኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያንና በሮም ካቶሊክ መንበር መካከል የነበረው ታሪካዊ ግንኙነት ነበር። ሁለተኛ የሮም ካቶሊካዊ ሊቀ ጳጳስ አባ ፓየስ 11ኛ፣ ለኢትዮጵያ መደብደቢያ የተዘጋጀውን የጦር መሣሪያ መባረካቸው። የአስክንድርያ መንበረ ጵጵስና ክውግዘት የደረሰው፣ የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ የነበሩት አቡነ ቄርሎስ ሮም ሄደው ከካቶሊኩ ሊቀ ጳጳስ ጋር ከተነጋገሩ በኋላ በመሆኑ ነው። አራተኛ ደግሞ አዲስ አበባ ላይ ስለኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የወጣው ሕግ የጣልያንን የበላይነት ማጠናከሩ ነበር። ሁኔታውን በትክክል ለመረዳት እነዚህን አራት ነጥቦች አንድ በአንድ መመርመር ያስፈልጋል።

1ኛ. ከቀድሞ ጀምሮ በኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያንና በሮም ካቶሊክ መንበር መካከል ከፍተኛ ቅራኔ አለ። ልዩነታቸው ለ/ፐፖስቲካ አመለካከት በቀላል የሚጠናቀቅ አይደለም። ዝርዝሩን ለማወቅ በአለቃ አያሌው ታምሩና በአባ አየለ ተክለሃይማኖት መካከል የተካሄደውን ክርክር ማጥናት ያስፈልጋል። ከዋና ዋናዎቹ አንዱ የክርስቶስ ልደት ሦስት ነው፣ ሁለት ነው የሚል ሲሆን፤ የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን በሁለት ልደት ታምናለች። የሮም ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ይህንን አታምንም። ሌላው ክርክር በክርስቶስ ለውነትና መለኮትነት ላይ የተመሠረተው ደግሞ፤ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ባህርይ መለኮትና ባሕርይ ትስብዕት ጻግመኛ በማይለያይ ሁኔታ አንድ ሆነዋል ትላለች። እምነትዋንም አውነተኛ /አርቶዶክስ/ ተዋህዶ ትለዋለች። የሮም ካቶሊክ ቤተክርስቲያን በዚህም አታምንም። ሦስተኛው ክርክር ቁለ ሥጋ ኢየሱስ ነው። የኢትዮጵያ

ቤተክርስቲያን በጊዜ ቅዳሴ ሕብስቱ ወደ ሥጋነት፣ ወይኑ ወደ ደምነት ይለውጣል ብላ ታምናለች። ስሙንም ሥጋ ኢየሱስ፣ ሥጋ ወደሙ ትሰዋለች። የሮም ካቶሊክ ቤተክርስቲያን በዚህም አታምንም። ከዚህ በተረፈ የሥልጣን ጉዳይም አለ። የሮም ካቶሊክ ቤተክርስቲያን በኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ላይ ጥላዋን ለመጣል ትፈልጋለች። የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ደግሞ አጥብቃ ትከላከላለች።[7]

2ኛ. አባ ፓየስ 11ኛ ለኢትዮጵያውያን መፍጃ የተዘጋጀውን መርዝ ጋዝ፣ በምብ፣ መድፍና መትረየስ ቀርቦላቸው በአደባባይ መቧረካቸው ሌላው ጉዳይ ነው። ከዚህም ጋር ቀደም ብለው ወደ ኢትዮጵያ በመግባት ሚሲዮናውያን የሠሩት ደባ በኢትዮጵያውያን ዘንድ የታወቀ መሆኑ ነው። ይህ ገሀድ ስለሆነ ማስረጃ ማቅረብ አይጠይቅም። ከአድዋ ጀምሮ በገሀድ ሲታይ የኖረ ነው።[8] በአምስቱ ዓመት ወረራ የባሰ እንጂ የተሻለ አንዳች ነገር አልታየም።

3ኛ. የአቡነ ቄርሎስ ወደሮም እንዲሄዱ መገደድና፣ የአሳቸውም በሮም ካቶሊክ መንበረ ጵጵስና ባለሥልጣኖች ጋር ተነጋግረው ሳይስማሙ መቅረት ነው። አሳቸው ሳይስማሙ የቀሩት በሥልጣን ጥያቄ ሞምር እንጂ፣ በእምነት ልዩነት ብቻ አልነበረም። ቢሆንም ሲቀ ጳጳሱ ያልተቀበሉትን ነገር ካህናቱም፣ ምእመናኑም መቀበል አልቻሉም። በዚህ ላይ ደግሞ የመንበረ ማርቆስ ዘአለ እስክንድርያ ውግዘት ተጨመረ።[9]

4ኛ. ዋናው ጉዳይ ዱክ ደ አምስታ ስለ ቤተክርስቲያን አስተዳደር ያወጣው አዋጅ ሆነ። እሱም ቀደም ብሎ በዚሁ ምዕራፍ ውስጥ የተነገረ ስለሆነ መድገም አያስፈልግም።

ጣልያኖች ከዚህ ጠቃሚ ከሚመስል እርምጃ በአንጻሩ፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ አብያተ ክርስቲያናትን ማቃጠልና ማጥፋት ቀጠሉ። ለማርከስ፣ በየሄዱበት ጦራቸውን የሚያሠፍሩት ከቤተክርስቲያን ውስጥ ሆነ። ለማስረጃ ያህል በጉንደር ከተማ የሩፋኤልን ቤተመቅደስ የፈረስ ማሠሪያ አደረጉት። ቡልጋም ጊዮርጊስን እንደዚሁ አድርገዋል። ጦሩ ሲንቀሳቀስ ደግሞ አቃጥሎት ይሄዳል። በድምሩ 2,000 ቤተክርስቲያኖች አቃጠሉ። ከዚህም ጋር እጅግ ብዙ መጻህፍት፣ ንዋየ ቅድሳት፣ ቅርሳቅርሶች ዘረፉ፣ አጠፉ። የአርባዕቱ እንስሳን ቤተክርስቲያን አፍርሰው ማገዱት። የሠለስቱ ምዕትን ጽሕፈት ቤት አደረጉት። ፋሲለደስ ቤተክርስቲያንነቱ ቀረ።

በሦስተኛው አንጻር ደግሞ የራሳቸውን የካቶሊክ ቤተክርስቲያን ለማስፋፋት ጥረት አደረጉ። በአዲስ አበባና በሌሎችም ከተሞች ቤተክርስቲያኖች ሠሩ። ይህ ሁኔታ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን እምነት ተከታዮችን አስቆጣ። የካቶሊክ እምነት ተከታይ የሆኑ ኢትዮጵያውያንንም አበሳጨ። ለምሳሌ በጉንደር አባ ካሣን ናላቸውን አዙሮ

አሳበዳቸው።[10] እስላሞችንም አስገነገኑ። እንዲያውም ከክርስቲያኖች ጋር አቀራረባቸው።

ሌላው ችግር ቀደም ብሎ በብዙ ሽንገላ ከጉኑ እንዲቆሙ ያደረጋቸውን የኢትዮጵያ መሣፍንትና መኳንንት ማስተዳደር ሆነ። ለብዙዎች ደመወዝ ቢቆረጥላቸውና ባለምዋልነት ቢሰጣቸውም፣ የወገኖቻቸው እልቂትና ሰቆቃ፣ የጣልያኖች ቅጥፈት የጎሊና ዕረፍት እየነሣቸው ሄደ። በየአደባባዩ እየቆሙ በገዛ ሕዝባቸው መንጓጠጥ ሰለቻቸው። ምነው? ለምን? እያሉ መጠየቅ አመጡ። በአንዳንድ ጉዳይ አለመስማማታቸውን መግለጽ ጀመሩ። እነሱም በተራቸው ወደ እሥር ቤት ተጋዙ። ታላቁ ታማኝ ልዑል ራስ ኃይሉ ተክለሃይማኖትም አልቀረ። ምሀረት እንደተደረገላቸው ማረጋገጫ የተሰጣቸው እነ ራስ ሥዩምና ራስ ጌታቸውም ከዚያው ገቡ። በዚህም በኩል የተደከመው ድካም መና ሆነ።

የጣልያኖች ሌላው ችግር በእነሱ ዘር፣ ማለትም፡- በጣልያናውያን፣ እና በኢትዮጵያውያን መካከል ያለው ግንኙነት የሚያሳስባቸው ሆነ። ጣልያናውያን ከኢትዮጵያውያን መደቀላቸው የዘር ሥጥመት እንደሚያመጣ አድርገው በተገነዘቡ ጊዜ፣ ጥቁርና ነጭ በምንም እንዳይገናኝ ሕግ አወጡ። ኢትዮጵያውያን ተቆጡ። ለነገሩ ጣልያኖች ሕጉን ሳያከብሩ ቀሩ፣ ሹማምንቱና ወታደሮቹ እንደየደረጃቸው ከኢትዮጵያ ሴቶች ጉያ አንወጣም አሉ። ከአሥር ሺህ የማያንስ ክልስ ተወለደ። ይህ ነገር ሊታገድ እንደማይችል በተረዱ ጊዜ፣ ሕጉን በሕግ ሳይሆን በአሠራር ሻሩት። ጣልያንና ሀበሻ ይበልጡኑ ተቀላቀሉ። ዝብርቅርቁ ወጣ።

ጣልያኖች በቀድሞው ሥርዓት በሕዝብ ላይ ከብዶ የነበረውን ነገር ማቃለል የሚያስችል እርምጃ መውሰድ ደጋፊ እንደ ሚያስገኝላቸው ቀደም ብለው በጥናት አረጋግጠው ነበርና፣ አገር እንደገቡ በዚህ ረገድ ፈጣን እርምጃ ወሰዱ። ባሪያ ያለምንም ጥያቄ ለዘለቄታ ነፃ ወጣ። ለጉልተኛ፣ ለመልከኛና ለሻለቃ ሁዳድ ማረስ፣ ማር መቅዳት ቀረ። በአማራው አገር ሲሦ ለእንጋሽ፣ ሲሦ ለቀዳሽ፣ ሲሦ ላራሽ የሚለው ሥርዓት ፈረሰ።

ነገር ግን ይህ ሥርዓት ተሽክሞት የነበረው አበሳ ወደ ጣልያን መንግሥት ወደራሱ ዞረ። ናላውንም አዞረው። ጣልያን ራሱ የሠራውን ሥርዓት ከመጋቢት 1931 ዓ.ም ጀምሮ በአዋጅ ከማፍረስና የቀድሞውን ሥርዓት እንደገና መልሶ ከመገንባት ገባ። ባለሪም አምሾ እንዳይቀበል፣ የመስቀል መሬቶች እንደ ቀድሞው እንዲሆኑ ተደረገ። አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት ደመወዝ ይወጣላቸዋል ተባለ። የቤተክርስቲያን አለቆች ስለኃይማኖት ጉዳይ ዳኝነት እንዲያዩ ተፈቀደ። መሬት እንደ አገሩ ሕግና ልማድ የሕዝብ መሆኑን የጣልያን መንግሥት በአዋጅ አወቀ። ሞቃ አበል እንዲቀበል ተፈቀደ። ዳኝነትም፣ አፈርሳታም እንደ ጥንቱ ሆነ።[11] ይህ ሁኔታ በነባሩ

ሥርዓት ተጠቃሚ የነበሩትን ወገኖች እምብዛም ሲያስደስት፣ ሌሎች ደግሞ ተቃሎላቸው የነበረውን ሽክም መልሶ ስለ ቆሰለባቸው ይብልጥ አስቆጣቸው።

በእነሱ አመለካከት ሽፍታ ከነበረው ጋር ያጋጠማቸውን ቅራኔ በንግግር ለመፍታት ሞከሩ። ከአርበኛው የቀረበላቸው የመደራደሪያ ነጥብ ከባድ ሆነ። ነገር ግን በገዛ እጃቸው የጀመሩት ስለሆነ በጉዳዩ መግፋት ግድ ሆነባቸው። አፈፃፀሙ በአርበኞች ጥያቄ ሳይሆን በጣልያን መንግሥት ችሮታ የተፈጸመ እንዲመስል እያደረጉ፣ አንዳንድ የእነሱን ጥቅም የሚቃረን ሥራ ሠሩ። እሥረኞች ተፈቱ። ቤታቸው፣ ንብረታቸው ተመለሰላቸው። የዳኝነት ሥራ ከኢትዮጵያውያን እጅ ተመልሶ ገባ። ጣልያናውያን ለሚኖሩበት ቤት ኪራይ ከመክፈል ገቡ። በቅኝ ግዛት ታሪክ ውስጥ አድርገውት የማያውቁትን ሹመት ለኢትዮጵያውያን ሰጡ። የሠራተኛን ደመወዝ ከፍ አደረጉ። ለአስተርጓሚ በወር ከ55-150 ሊሬ መክፈል ጀመሩ። ለአርበኛውም ደመወዝ መክፈል ስንቅ መስጠት ያዙ። ገንዘባቸውን በልዩ ልዩ መንገድ ረጩ። የኢትዮጵያውያንን ልብ በገንዘብ ለመግዛት የሚችሉ መስሎአቸው የነበረው ይኸ አመለካከት ለመጀመሪያው ጊዜ ጥቂት ቢያግዛቸውም፣ ሳያዛልቃቸው ቀረ።

ሌላው ሙከራቸው አንዳንድ የልማት ሥራዎች የሚያካሂዱት ኢትዮጵያን ለማሳደግ፣ ኢትዮጵያን ለማልማት እንደሆነ አድርጎ ማሳየት ነበር። ተሐድሶ ኢትዮጵያ በሚል ጋዜጣና የሮማ ብርሃን በሚል መጽሔታቸው ድልድይ፣ የመንገድ ሥራ ያሳዩ ጀመር። እሱን እየፈጹ መሬቲቱን የሚያለሙት ለማን ጥቅም እንደሆነ ለማወቅ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ጊዜ አልወሰደበትም።

የባንዳ አስተዳደርም በበኩሉ ችግር ፈጠረ። በመጀመሪያ ደረጃ ገበሬ ከጦር ሜዳ ተፈጥሞ ወጣ። ባንዳም ይከዳ ጀመር፤ ያለውም ከልቡ የማይዋጋ ሆነ። በደመወዝ መንቀሳቀሱ ቀረ። የደንብ ልብስ አስፈለገው። ወጭው እየበዛ፣ አገልግሎቱ እየተቀነሰ፣ ታማኝነቱ እየቀዘቀዘ ሄደ። ለአርበኞች ደመወዝ መቆረጡ፣ ክብር መሰጠቱ፣ እንክብካቤ መደረጉ አስቆጨው።[12] ይህ አሠራር የአርበኛውን ልብ በማደንደንና የባንዳውን ቅስም በመስበር ጣልያንን ይበልጥ ጉዳው።

ባለቅኔ የሚቀኘው፣ አዝማሪ የሚያዘምረው፣ አልቃሽ የምታሞሸው ስለጣልያን ጭካኔ፣ ፈሪነት፣ አታላይነት ሆነ። በአንፃሩ ደግሞ የአርበኞችን ጀግንነት ያሞግሱ ጀመር። ጠንቋዩ፣ ትንቢት ተናጋሪው፣ ባህታዊው የሚናገረው ስለጣልያን በጎ መጥፋት ሆነ። የጣልያን ፕሮፓጋንዳ በጋዜጣ መፃፉ፣ በመጽሔት መውጣቱ፣ በሬዲዮ መነገሩ አንዳች የማይፈይድ ሆነ። ጣልያኖች ከአሰቃ እስከ ጭፍራ ግራ ገባቸው።

ሙሶሊኒ ከሂትለር ጐን መቆሙን በገለጸ ጊዜ፣ የሮማው ራስ ዞረ። ከሥልጣን የመውረዱ ጉዳይ ደግሞ አዲስ አበባ የነበሩትን ጣልያኖች

ስላስደነገጠ፣ በበርበራና በሱዳን በኩል ጦርነት ከፈቱ። የጦርነቱ ሚዛን ወዲያው በእነሱ በራሳቸው ላይ አዘነበሰ። ከአጥቂነት ወደ ተከላካይነት ዞሩ። የሰሜን አፍሪካው ጦርነት፣ የሰዊዝ ካናል በእንግሊዞች መዘጋት፣ ኢትዮጵያ ላይ የፈሰሰውን ጣልያን ከእናት አገሩ ቆረጠው።

ዱክ ደ አምስታ እና ናዚ ሁኔታውን በፖለቲካና በፈሊጥ ለመያዝ ሞክሩ። በኢትዮጵያ ባሕል መሠረት ሹመት ሰጡ። በደብረ ብርሃን አቶ ስሙ ንጉሥ፣ በጐንደር ደጃዝማች አያሌው ብሩ ራስ ተባሉ። ለብዙዎች የደጃዝማችነትና የፊታውራሪነት ማዕረግ ተሰጠ። ነገር ግን አንዳች አልጠቀመም።

ጣልያን ከውድቀት የደረሰችውና ኢትዮጵያን እንደ ቅኝ ግዛት ለመያዝ የተነሳችበትና የተዋደቀችለትን ግብ ያጣችው፣ በአብዛኛው የተሳሳተ ሕግ በማውጣትና የተሳሳተ ፖሊሲ በመከተል ጭምር ነው። እንደ አጀማመሯ፣ በኃይል ዝግጅትና በጦር አሰላለፍ ኢትዮጵያ ከምንጊዜም አትደርስም ነበር።



የጣልያን ምስራቅ አፍሪቃ አስተዳዳሪ ልዑል ደ ኤስታ።

ጣልያን፣ ኢትዮጵያን ለመያዝ የነበራት ጉጉት እጅግ ከፍተኛ ስለ መሆኑ፣ ሞሶሊኒ በምሥጢር ለባዶሊዮ በጻፈለት ደብዳቤ ብዙ ምክር ከሰጠው በኋላ "...የሆነው ሆኖ፣ ወይም ያለቀው አልቆ ድሉ የኛ መሆን አለበት" ማለቱ ያንኑ ያረጋግጣል።[13] ይህ ቁርጠኝነት ምንም ሳይበርድ እስከ መጨረሻው ድረስ ቀጠለ። የጣልያን ጦር ያለመለቀቸት የኢትዮጵያን ሕዝብ እየፈጀና ራሱም እያለቀ እስከ መጨረሻው ተጋደለ። ነገር ግን ያ ሁሉ የጣልያኖች ድካም፣ በመሪዎቹ ደካማ አመለካከት መና ሆኖ ቀረ።

እርግጥ ዋናው ስህተታቸው፣ የአድዋ ውድቀታቸውን በመርሳት ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛት ለመያዝ እንደገና ሞሞከራቸው ነው። ከዚህ



የጣልያን ምስራቅ አፍሪቃ አስተዳዳሪ ልዑል ደ አኦስታ።

ስህተታቸው ተምረው ወደፊት ኢትዮጵያን ከመተናከል ይታቀቡ ይሆን? እንጃ!

ማጣቀሻ ፅሑፎች

1. *ገሪማ ታፈረ፣ ጦንደሬ ቢጋሻው፣* ገጽ 28፣ 35፣ 65፣ 72፣ 152፣ 175፣ 205፣ 206።
2. *ዝኒ ከማሁ፣* ገጽ 23-25።
3. *ጳውሎስ ኞኞ፣ የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦርነት፣* ገጽ 186-190።
4. *ገሪማ ታፈረ፣* ገጽ 83-102።
5. Alberto Sabacchi, *Ethioipia under Muossolini*, pp.101-114.
6. *ገሪማ ታፈረ፣* ገጽ 96-101።
7. *አያሌው ታምሩ፣ መኾ ተሰመደና ክተኩላ ዝምድና።*
8. *ታደሰ ዘወልዴ፣ የአባላሸኝ ዘመን፣* ገጽ 27-31።
9. *ገሪማ ታፈረ፣* ገጽ 83።
10. *ዝኒ ከማሁ፣* ገጽ 71-72።
11. *ዝኒ ከማሁ፣* ገጽ 223-225።
12. *ተክለፃድቅ መኩሪያ፣ የኢትዮጵያ ታሪክ ከአፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፣* ገጽ 291-294።

ምዕራፍ አርባ ዘጠኝ
የኢጣልያ የምሥራቅ አፍሪካ አስተዳደር

በ1920 ዓ.ም አካባቢ ጣልያን በሊቢያ፣ በኤርትራ፣ በሶማሊያ ላይ የነበራት ይዞታ የተረጋገጠበት ጊዜ ነበር። እነዚህን አገሮች የያዘችበትን መንገድ ጥቂት መመርመር፣ ስለቅኝ አገር አያያዝ የነበራትን ሥልት ያስረዳል።

ከሁሉም ያስቸገራት ሊቢያን መያዝ ነበር። አገሩን ከቁጥጥር ሥር ማዋል የቻለችው ከብዙ ጦርነት በኋላ ነበር። ለጦርነቱም ከጣልያን አገር የሚጫነው ወታደር የማይበቃ ሆኖ፣ ከኤርትራና ከሶማሊያ ብዙ ወታደር እየቀጠረች ማጋዝ ነበረባት። ግራዚያኒም በጨካኝ ሥርዓት ሕዝብን መፍጀት የሚቻልበትን ዘዴ ያጠናው ከዚያ ነበር። ጣልያን ከዚህ ሁኔታ በኃይል ስለመጠቀም ልምድ አግኝታለች።

ኤርትራን ግን የያዘችው በአብዛኛው የሀገሩን ባለሥልጣኖች በመሸንገል ነው። መዋጋት የነበረባት ከትግራይ እየተወረወረ ከሚሄደው፣ በራስ አሉላ ከሚመራው ከኢትዮጵያ ጦር ጋር ብቻ ነበር። ምዕዋንም በነፃ በ1877 ዓ.ም የተረከበችው ከእንግሊዝ ነበር። ሰሜኑን ኤርትራን በዚህ ዓይነት እጅ ስታደርግ አስብን ያገኙት ደግሞ ቀደም ብላ በስምንት ሺህ ብር በመግዛት ነበር። የገዛችው ሩባቲኖ በተባለ አንድ የንግድ ኩባንያ ስም፣ ጁስፔ በተባለ ሚሊዮናዊ ደላላነት፣ ኢብራሂምና ሐሰን መሐመድ ከሚባሉ ሡልጣኖች ነው። ጣልያን ከኤርትራ አያያዝ ያገኘችው ትምህርት፣ አዘያ በሽንገላና በግዥ ብዙ ነገር ማግኘት እንደሚቻል ነው።[1]

ጣልያን ደቡብ ሶማሊያን የያዘችው ልዩ፣ ልዩ ሡልጣኖችን በመደለልና በገንዘብ በመግዛት ነው። ለአሥር ከረጢት ሩዝ የተሰወጡ ደሴቶች መኖራቸው በታሪክ ተመዝግቦአል።[2] ጣልያን ከሶማልያ ያገኘችው ልምድ በየዓመቱ በሚከፈል ግብር መሰል አከፋፈል፣ አንድ የሆነን አገር እርስበርሱ ነጣጥሎ መግዛትና ቅኝ ግዛት መመሥረት እንደሚቻል ነው።

ጣልያን ጎዳር 26 ቀን 1929 ዓ.ም ወልወል ላይ ግጭት ያነሳችው፣ ከክባድ ትጥቅ ጋር አነኂህን የቅኝ አያያዝ ልምዶችዋን መነሻ አድርጋ ነው። እዚህ ግን ይኼ እስከ ጎዳር 1934 ዓ.ም፣ በድምሩ ስድስት ዓመት አስጉዞ፣ ጉንደር እጅ እንደሚያስጣት አልጠረጠረችም ነበር። በዚህ ምዕራፍ የምንመለከተው ሌላው ነጥብ ይህ ጉዞዋ በአስተዳደር ዓይን ሲታይ ምን እንደሚመስል ነው።

ማርሻል ባዶሊዮ ሚያዝያ 27 ቀን 1928 ዓ.ም አዲስ አበባ ገብቶ፣ ግንቦት 1 ቀን 1928 ዓ.ም /ሜይ 9 ቀን 1936/ ኢትዮጵያን የኢጣልያ ቅኝ ግዛት የሚያደርጋት አዋጅ ሮም ወጣ። ሣልሣዊ ኢማኑኤል የኢትዮጵያ ንጉሠ

ነገሥት ተባለ። የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ሥልጣን ለኢማኑኤልና ለልጅ ልጆቹ እንደተዛወረ ለዓለም ኅብረተሰብ ተገለጸ። ሰኔ 8 ቀን 1928 ዓ.ም /ጁን 15 ቀን 1936/ የኢጣልያ ምሥራቅ አፍሪካ ግዛትን የሚመሠር ት አዋጅ ወጣ። ይህም ኢትዮጵያን፣ ኤርትራንና ሶማሊያን የሚያጠቃልል ሆነ። የኢትዮጵያም ቅርጽ ከጂቡቲና ሰሜን ሶማልያ በስተቀር ጥንታዊ ይዘቱን አገኘ። ጣልያንም በኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖሩት ልዩ ልዩ ሕዝቦች ናቸው ብላ ታወራበት በነበረው አፍዋ፣ አንድ ሕዝብ ነው አለች።

በእነዚህ አዋጆች መሠረት ስድስት አስተዳደሮች ተመሠረቱ። ኤርትራ ትግራይን ጠቅልላ አሥመራ፣ ደቡብ ሶማሊያ አጋዴንን ጠቅልላ መቃድሾ እንዲሆኑ በማድረግ ሁለቱ የቅኝ ግዛት አገራት፣ የቅኝ አገር ሆነው የቆዩበትን፣ የአገልግሎት ዋጋቸውን ተከፋፈሉ። ቀጥሎ የተደለደሉት አማራው፣ ጉንደር፣ ሸዋ፣ አዲስ አበባ ሆነው ነበር። ወዲያውም አፋርና ኢሣ፣ ሐረር ሆኑ። በመጨረሻም ኦሮሞ- ሲዳማ ጂማ ሆኑ። ከሸዋ በስተቀር በቀድሞ የሀገር ስም የተመደበ አልነበረም። ሁሉም በዘር ነበር። ይህም ሆነ ተብሎ የተደረገ ነበር።



የጣልያን ምሥራቅ አፍሪካ አስተዳደር ካርታ።

በሮም ከተማ የኢጣልያ መንግሥት መሥሪያ ቤቶች ለአዲሱ ቅኝ ግዛት በሚያመች ዓይነት ተዋቀሩ። የኢጣልያ ምሥራቅ አፍሪካ ሚኒስቴር ተቋቋመ፣ ሥልጣንም ተሰጠው። የመሥሪያ ቤቶቹ በአዲስ አቅድ መደራጀት መልካም ሆኖላቸው ሣለ፣ የአሠራር ችግር ተፈጠረ። በውጭ ጉዳይና በምሥራቅ አፍሪካ ሚኒስቴር፣ እንደዚሁም በጦር ሚኒስቴርና በገንዘብ ሚኒስቴር፣ በሌሎችም ሚኒስትሮች መካከል የሥራ መጓተት ተፈጠረ። የየበኩላቸውን ሥራ በሚመለከት እንደ እርሻ፣ ንግድና እንዱስትሪ ሚኒስቴር

ያሉ መሥሪያ ቤቶች እጃቸውን ለማስገባት ሞከሩ። የጥቅምና የሥልጣን፣ እሱንም ተከትሎ የሰው ፀባይ በልዩ ልዩ ጉዳዮች ገባ። ኢትዮጵያ ውስጥ የጦርነቱ መቀጠል ይህንን የሥራ ተጓተት አስረረው። በዓለም ማኅበር ጉባዔ የተነሳው ክርክር ጥልፍልፍ ችግር ፈጠረ። ችግሮች ደግሞ የሞሶሊኒን ጩኸት ፈርተው ንቅንቅ የማይሉ ሆኑ። የባለሥልጣኖች የርስበርስ መመቀኛኘትና ተቃርኖ ጠነከ። ሊሰና በሚባለው የአፍሪካ ጉዳይ ሚኒስትርና የኢትዮጵያ ገዥ በነበረው በግራዝያኒ መካከል የተነሣው ጠብ ብዙ ከአጨቃጨቀ በኋላ፣ ሊሰና ከሥራው ተባርሮ በቦታው ግራዝያኒ እስኪተካበት ድረስ ቀጠለ።[3]

አዲስ አበባ ላይ በነበሩ ባለሥልጣኖች ልዩ፣ ልዩ እርምጃዎች ተወሰዱ። ከድል በኋላ የቀጠለውን፣ አሳፋሪ የሆነባቸውን ጦርነት በቶሎ ለመጨረስ አጣዳፊ ሥራ ተያዘ። እሱውም፡- የጣልያንን ቅኝ ግዛት የሚቃወመውን ሁሉ መጨረስ፤ ሀገራቸውን ለመከላከል ይንቀሳቀሱ የነበሩ ኃይሎችን መደምሰስ ሆነ። ከግንቦት 1928 ዓ.ም እስከ ጥቅምት 1931 ዓ.ም በቆየው በዚህ የኃይል ሥራ በመቶ ሺህ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ተገደሉ፣ አካለ ጉዶሉ ሆኑ፣ አሥር ቤት ታጐሩ። ይህ የኃይል አሠራሩ ግራዝያኒን ራሱን ወደ 350 ቦታ አቀሰለው። የኃይሉ ሥራ እንደ አሳዋጣ ቁርጡ ሲታወቅ፣ የጣልያን አያያዝ ወደ ሰላምና መረጋጋት ዞረ። በጣልያን ከሀዲነት ከአድዋ ጀምሮ ልቡ የቆሰለው የኢትዮጵያ አርበኛ ይህንንም የማይቀበል ሆነ። ከጣልያን ከራሱ ባገኘው ሥንቅ ከህዳር እስከ መጋቢት 1932 ዓ.ም ያገገመው አርበኛ፣ በሚያዝያ ወር ያንኑ የቀድሞውን ጠንካራ ጦርነቱን ቀጠለ።

ጣልያኖች አዲስ አበባ ሲገቡ፣ ከአገሩ ተወላጆች ጋር በመወዳጀት ተቀሳቀሱ፣ በመዋደድ ተዋለዱ። ይህ ሁኔታ ለቅኝ ግዛት የማይመች ሆነ። የቅኝ ገዢውን የጣልያንን ንጹህ ደም መጠበቅ አስፈለገ። የዘር ልዩነት አዋጅም ወጣ። እንደ አዲስ አበባ፣ አሥመራ፣ ሞቃድሾ፣ ጐንደር፣ ሐረርና ድሬዳዋ ባሉ ከተሞች ነጭና ጥቁር የሚኖሩባቸው የከተማ ክልሎች ተለዩ። ቀደም ሲል እንደገለፅኩት በአዲስ አበባ ወሰኑ የፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ድልድይ ሆነ። ነገር ግን ነጩ ከጥቁሩ ተለይቶ መኖር አቃተው። ሰው ከሰው ጋር በሚኖረው ተፈጥሯዊና ሌላም ግንኙነት፣ ይኼው ቅርርብ ከተደነገገው ሕግ ውጭ ቀጠለ። ከፖሊሲው በተቃራኒ ግንኙነቱ ከጦር ወደ ሰላም የመዞሩ ሁኔታ፣ ለፖሊሲው መሰወጥ አንዱ ምክንያት ሆነ። በጣልያን መንግሥትና በአርበኞች መካከል የተጀመረው ዕርቅ መፍረስ፣ ይህንን ትሥሥር ሳያፈርሰው ቀረ። ስለዚህ ከአሥር ሺህ ያላነሱ ክልሶች ተወለዱ።

በኢትዮጵያውያን መካከል በብሔረሰብ ስሜት ላይ የተተከለ ልዩነት ለመፍጠር የጣልያን መንግሥት ጥረት አደረገ። ወሳይታን፣ አማራን ፍጅ ቢሉት፣ ሳይፈጅ ቀረ። ምክንያቱም ሸዋ፣ ጐንደር፣ ጐጃምና ወሎ ካልዘመትን፣ ከዚህ ያሉትን ባላባቶች ብንፈጅ ምን ውጤት ይገኛል በሚል



የጣልያን ምሥራቅ አፍሪካ አስተዳደር ካርታ።

ምክር በመስማማታቸው ነው። የሰላሌው ባላባት ደግሞ ሕዝቡ አንዳንድ ቁና ጤፍ አምጥቶ እንዲያቀላቅል ካደረጉ ቡኋላ፣ እያንዳንዱ ሰው የራሱን ጤፍ መርጦ እንዲወስድ በማዘዝ የጣልያን ትዕዛዝ ሊፈፀም የሚችል አለመሆኑን አስገነዘቡ። ይህንን በመላለስ ዘዴ የኢትዮጵያ መሪዎች ስለአመከኑት፣ የጣልያን መንግሥት የተማመነበት ሕዝብን አርስ በርሱ የማጣላት ሥልት ከሸፈ።

ሌላው ጣልያን የተጠቀመበት ዘዴ የእምነት ልዩነትን ማክረር ነበር። ሥልቱ የእምነት እኩልነት የሚል እንዲሆን ተደረገ። በመጀመሪያ ለጦርነቱ ቡራኬ የሰጡት አባ ፒኦ በኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ሥልጣን እንዲያገኙ ማድረግ ተሞክረ። የግብፁ ጳጳስ ሳይስማሙ ቀሩ። ሁለት ኢትዮጵያውያን ሲቃነ ጳጳሳት፤ አቡነ ጴጥሮስና አቡነ ሚካኤል፤ በዚህ ጥያቄ ላይ የሰማዕትነትን ጽዋ ተቀበሉ። አንድ ሊቀ ጳጳስ፣ አቡነ ይስሐቅ ከአሥር ቤት ዝ። ከአራቱ ኢትዮጵያውያን ሊቃነ ጳጳሳት የቀሩት አንዱ፣ አባ አብርሃም ብቻቸውን ቢጮኹ እሚሰማቸው ጠፋ። ከዚያ ቀጥሎ እስላሙን በክርስቲያኑ ላይ ለማስነሳት ልዩ ጥረት ተደረገ። እሱም ውጤት ሳይሰጥ ቀረ። ይህ ስልት እንደገና ተለውጦ የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያንን በማጠናከር ሕዝቡን ለመሸንገል ተሞክረ፤ ግን አልሆነም።

ሌላው የኢትዮጵያን ሕዝብ ልቡና ማመሳቀያ መሣሪያ፣ መገናኛ ብዙሀን ነበር። የቄሣር መልእክተኛ የተባለ ሣምንታዊ ጋዜጣ፣ የሮም ብርሃን የተባለ ወርሐዊ መጽሔት ተቋቋመ። ተሐድሶ ኢትዮጵያ የምትባልም ነበረች። አንዳንድ የልማት ሥራዎችን፣ በተለይም መንገዶችንና ድልድዮችን በፎቶግራፍ የሚያሳዩ ነበሩ። ሮም፣ የኢትዮጵያ መንግሥት አምባሳደር የነበረው አቶ አፈወርቅ አፈቄሣር ተብሎ እንደጌቶቹ ተናገረ። በፓሪስ አምባሳደር የነበረው ብላታ ወልደማርያም አየለም እንደዚሁ። ነገር ግን ጣልያን አንዳች ውጤት አላገኙትም።

የወጣቱን ልቡና ለመስለብ፣ የእስፖርት እንቅስቃሴ ተጠናከረ። አራዳ፣ ስድስት ኪሎ፣ እንጦጦ፣ ኮንስሳታና ቀበና የተባሉ ቡድኖች በአዲስ አበባ ከተማ ተቋቋሙ። የኢትዮጵያውያን ጨዋታ ተዘወተረ። በጋዜጣም ይወጣላቸው ጀመር። ወጣት ይድነቃቸው ተሰማንና ሌሎች ጥቂት መሰሎቻቸውን ለኢትዮጵያ ከማበርከት በስተቀር፣ የኢጣልያንን ጉዳይ የሚተኩስ ውጤት ግን ከዛ አልተገኘም።

በሊዳማ ክፍለ አገር ለመኢንንት፣ ለሹማምንትና ለባላባት ልጆች ትምህርት ቤት ተሠራ ተብሎ በሠፊው ተወራ። አዲስ አበባ ጉለሌ በነበረው ፓሪን ቺፒዮ፣ አሁን የፖሊስ ክበብ በሆነው፣ ስድስት የመሣፍንት ልጆች ገብተው ይማሩ እንደነበር ይታወሳል። ነገር ግን አንዳች አልፈየደም።

በአማርኛ ቋንቋ ላይ ክርክር ተቀሰቀሰ። ፊደል ይቀነስ ተብሎ በአቶ ወልደ ሩፋኤል በቀረበ አስተያየት መነሻነት ክርክር ተካሄደ። በአቶ አማረ

አክሊሉ የተሰጠው መልስ "በዐይን ዋዛ" የሚል ሆነ። ከአቶ ወልደሥላሴ ሐሰን የተሰጠውም አስታራቂ ሃሳብ ውጤት አልሰጠም። ቀደም ብሎ በግራኝ መሐመድ አማካይነት በተካሄደው የቱርክ ወረራም ጊዜ እንደነበረው አማርኛ የመንግሥት የሥራ ቋንቋ መሆኑ ቀጠለ። ትዕዛዞችና ደንቦች የሚወጡት፣ ጋዜጦችና መጽሔቶች የሚታተሙት፣ ሬዲዮ የሚናገረው በአሱ እንደ ሆነ ቀጠለ።[4]

የራሳቸውን ገቢ ለመጨመር፣ ጣልያኖች በኢትዮጵያ ላይ የልማት ሥራዎች ለማካሔድ ታላቅ ሙከራ አደረጉ። ከልማት ሥራዎቹ ዋነኛው የመንገድ ሥራ ሆነ። በደሴ በኩል ወደ አዲስ አበባ የተሠራውን መንገድ እስከ አሥመራ ለማገናኘት፣ እንዲሁም ከአሥመራ ጉንደር ሥራ ቀጠለ። ከአዲስ አበባ ድሬዳዋ፣ ሐረር፣ ጅጅጋ፣ ቀብሪ ደሐር፣ እንዲሁም ከፊርፊር እስከ ሞቃድሾ መንገድ ተሠራ። ከሞቃድሾ ደሎ እስከ አርቤንና ጥርጊያ መንገድ ተከፈተ። ከአዲስ አበባ እስከ ጂማ፣ ከአዲስ አበባ አስከ ጌራ፣ ከአዲስ አበባ እስከ ጉሐጽዮን፣ ከደብረ ማርቆስ እስከ ዓባይ እንዲሁም ከደብረ ማርቆስ እስከ ቡሬ፣ ከአሰብ እስከ ኮምቦልቻ፣ መንገድ ተሠራ። እንደ ጣልያን መንግሥት ሂሣብ በጠቅላላው 7.46 ሚሊዮን ሜትር ካሬ መንገድ ተሠርቶ አልቆአል። ከዚሁ ውስጥ 34,000 ካሬ ሜትር በአስፋልት ተነጥፎአል። አራት ታላላቅ ድልድዮችና 1504 አነስተኛ ድልድዮች ተሠርተዋል። መንገዶቹ የተሠሩትም በ17 ሚሊዮን የሥራ ቀናት ነው ተብሎአል።[5] ትናንሽ የገጠር ከተሞችም መንገድ ተከፍቶላቸዋል። ለነገሩ ይህ አሀዝ የተጋነነ ነው። የተባለውን ያህል ተሠርቷል ቢባል እንኳን፣ የታቀደለትን ግብ ከማሳካት አኳያ ግን፣ ውጤቱ ትንሽ ነው። ለኢጣልያ አልጠቀማትም እንጂ፣ ኢትዮጵያ ካገኘችው የጦር ካሣ አንዱ መንገድ ነው።

ሌላው የልማት ሥራ የተጀመረው በአርሻው መስክ ነበር። የዚህ ክፍል ልማት አላማ ባለብዙ ፊርጅ ነበር። መሬት የጠበበውን የጣልያን ገበሬ በኢትዮጵያ ላይ ሰፋፊ መሬት በመስጠት እንዲያርስ ለማድረግ፣ እንደዚሁም ባለሀብቶች በኮንሴሽን መሬት እየተረከቡ ሠፋፊ እርሻ እንዲያቋቁሙ፣ በዚህ ዓይነት በኢትዮጵያ ለሠፈረው የጣልያን ሠራዊት በቶሎ ምግብ እንዲያገኝና አልፎ ተርፎም ወደ ኢጣልያ እንዲጓዝ ነው። በዚህ ጉዳይ በከፍተኛ ደረጃ ስለታሰበበት፣ ስለ መሬት ይዞታ አንድ ጥናት ተካሄደ። ይህ ጥናት እንግሊዝ፣ ፈረንሣይ፣ ቤልጅግ፣ ጀርመን በቅኝ ግዛቶቻቸው ያቋቋሙትን የመሬት ይዞታ ሥርዓት በሠፊው ከዳሰሰና ከቀደምቶቹ የጣልያን ቅኝ ግዛቶች፣ ማለትም፡- በሲቢያ፣ በኤርትራና በሶማልያ፣ የተተከለውን ሥርዓት ካጤነ ቡኋላ የሰጠው ምክር፡- "...የንጉሡን፣ የመኢንንቱንና አንገዛም ያሉትን ወገኖች መውረስ ይቻላል" የሚል ሆኖ፣ ለሌላውን ግን ለመውረስ ገንዘብ መክፈል እንደሚያስፈልግ የሚጠቁም ሆነ።[6] በዚህ መሠረት የንጉሠ ነገሥቱና የእነራስ ብሩ መሬት ተወረሰ። በጉንደር፣ ዋጅራት፣ ወገራና ፎገራ፣ በጐጃም፣

አቸፈር፣ በሐረር፣ ጨርጨር፣ በአርሲ፣ ገንዳ፣ በቦረና፣ ነገሌ፣ በከፋ፣ ቦንጋ፣ በሸዋ፣ ወላይታና ቢሾፍቱ፣ እንዲሁም በአዋሽ ሸለቆ ታላላቅ የእርሻ ሥራዎች ተጀመሩ።

ነገር ግን ከንጉሡና ከመኳንንቱ የተወሰደው መሬት አልበቃም። ሌላ በርካታ መሬት አስፈለገ። የተፈለገው ምን ያህል እንደሆነ የተገለጸ ነገር የለም። ሕዝብ እንዳያስደነብር በምሥጢር መያዝ እንደነበረበት መገመት ይቻላል። ቢሆንም አንዳንድ ምልክቶች አሉ። ከዋጅራት 180,000፣ ከአሮሞ-ሲዳማ 200,000 ሄክታር እንደነበር ታውቆአል። ከዚህ በመነሳት ቢያንስ 300,000 ጋሻ፣ ማለት 1.2 ሚሊዮን ሄክታር ላይከጀል እንዳልቀረ መገመት አምብዛም አያሳስትም።

ጉዳዩ በዕቅድ ደረጃ እንደዚህ ሆኖ ሳለ፣ በአፈፃፀም ችግር አስከተለ። መሬት ማግኘት ቀላል አልሆነም። ገበሬ ተገዥነትና ጭሰኝነት እንደሚቀርለት ተሰብኮ ነበርና፣ ከአነጭራሹ መሬቱን ልቀቅ ሲባል ተቃውሞ አነሳ። ባለርስቱ ደግሞ ገንዘብ ተቀብሎ መልቀቅ አልፈለገም። አንዳንዱም ገንዘቡን እየተቀበለ ጫካ ገባ። ትልቅ ምስቅልቅል ተፈጠረ። ለመሬት ማስለቀቂያ የሚከፈል ገንዘብ ማግኘት ለኢጣልያ መንግሥት ባለሥልጣኖች ቀላል አልነበረም። የተገኘውም ጥቂት ገንዘብ በትክክል በሥራ ላይ ሊውል አልቻለም። ለምሣሌ ሮም ያሉት ባለሥልጣኖች ለዚህ ጉዳይ 600 ሚሊዮን ሊሬ አውጣን ሲሉ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት ማስረጃዎች የሚያመለክቱት 1,127,175 ሊሬ /18.8%/ እንደተከፈለ ነው። ቀሪው 81.2% ተደለልና ተጓተተ በበዛበትና ከሮም እስከ አዲስ አበባ፣ ከዚያም እስከ (ጠቅላይ) ግዛቶችና አውራጃዎች በተዘረጋው ቢሮ ውስጥ ሰጥም ቀርቶአል ማለት ነው።

መሬት እንደምንም ሲገኝ ደግሞ ገበሬ ጠፋ። የጣልያን ገበሬ በየቀኑ መርዶ ወደሚመጣበት አገር መሄድ አልፈለገም። ማምጣት የተቻለው 3,200 ገበሬዎች ብቻ ሆነ። የግል ባለሀብቶችም ጥሪታቸውን ቁርጡ አልታወቀበት አገር ውስጥ መጣል አልፈለጉም። እነዚህኑ ጥቂት ተብሰው የተገመቱትን ገበሬዎች ማቋቋም ደግሞ ተጨማሪ ወጭ ጠየቀ። ለዚህ ጉዳይ ደግሞ ሌላ 850 ሚሊዮን ሊሬ እንደተከፈለ የሮም ባለሥልጣኖች መዝግበዋል። ስንቱ ለመጣው ገበሬ እንደ ደረሰ አልታወቀም። ይህም ሁሉ ሆኖ እርሻዎቹ ውጤት አላሳዩም። ደብረ ዘይት ከነበሩት ዲዮዲ ከተባሉ ሁለት ወንድማማች ገበሬዎች በስተቀር፣ ሌላው ሁሉ ከሠረ። ሁለቱ ወንድማማቾችም ከአካባቢያቸው የኢትዮጵያ ገበሬዎች ለመስማማት ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ነበረባቸው።

በእነዚህ ጥልፍልፍ ችግሮች ስለተያዘ፣ የቅኝ ገዢው የግብርና ልማት ውጤት ሳይሰጥ ቀረ። የምግብ እጥረት ተፈጠረ። እንኂን ወደ ኢጣልያ መጫን፣ እዚህ ያለውን የጣልያን ሰፋሪ መመገብ ሳይቻል ቀረ። በዓመት 100 ሺህ ቶን ይገኛል የተባለው፣ በዓመት 43 ሺህ ቶን ብቻ ሆነ። ሌላውን፣

ቀሪውን በውጭ ምንዛሬ ጭምር እየተገዛ፣ ከጣልያን አገር ወደ ምሥራቅ አፍሪካ መጫን ግድ ሆነ።[7]

ሌላው የልማት መስክ የኢንዱስትሪ ይሆናል ተብሎ ነበር። የግብርናውንም ሥራ ጨምሮ 40 ያህል ኩባንያዎች ገቡ። የኢንዱስትሪው ዘርፍ፣ ከግብርናው የተሻለ ሳይሆን አልቀረም። ምክንያቱ፦ በስተሞች አካባቢ የሚካሄድ ሥራ በመሆኑ፣ የፀጥታ ችግር ላያጋጥመው ይችላል። በተረፈ ሁኔታው ተመሳሳይ ነው። እንደ ሲሚንቶና የመጠጥ ፋብሪካ የመሳሰሉ ፋብሪካዎች ተከፈቱ። ቢሆንም ወደ ጣልያን አገር ሊላክ የቻለ ያለ አይመስልም፣ ጥቅም ያስገኙም አይመስልም። በተረፈ ግን ለብዙ ኢትዮጵያውያን የቴክኒክ ሙያ በማስጨበጥ ረገድ ታላቅ ጥቅም ተገኝቶአል። ከዛን ጊዜ አንስቶ ኢትዮጵያውያን የቴክኒክ ዕውቀት ማገኘታቸው በየቦታው የሚታይ ስለሆነ፣ ማሰረጃ የሚጠይቅ ጉዳይ አይሆንም።

የንግድ ሥራ በመጠኑ ስኬታማ ሳይሆን አልቀረም። በተለይም የሆቴል ሥራ። በወቅቱ 1,436 ጣልያናውያን በንግድ ሥራ መሠማራታቸው ተመዝግቦአል። የንግድ ሥራ ከሕዝብ ጋር የጥቅም ግጭት ባለመፍጠሩ ብዙ ችግር አላስከተለም። በአዲስ አበባና በሌሎችም ከተሞች ሆቴል ቤቶች ተቋቁመው ሥራ ቀጥለው ነበር። በከተሞች ውስጥ በመሆናቸው፣ የጦርነቱ ወላፈን አልነካቸውም። ቢሆንም ሻጭም፣ ገዥም ሆነው የቆሙት በአብዛኛው ጣልያናውያን ራሳቸው ስለነበሩ፣ ወደ ኢጣልያ የሚፈስስ ትርፍ የተገኘ አይመስልም።

ከመንገድ ቀጥሎ ጣልያኖች ጥሩ ሥራ የሠሩት በሕንፃ ረገድ ነው። በአዲስ አበባ፣ በጐንደር፣ በሐረር፣ በድሬዳዋ፣ በጂማና በሌሎችም ከተሞች ጥሩ ጥሩና ጠንካራ ግንብ ቤቶች ሠሩ። ለእነሱም ቢሆን ቦታ የማግኘቱ ጉዳይ ቀላል አልሆነላቸውም። አብረውት የሚኖሩትን የከተማውን ሰው ቅር ላለማሰኘት የቦታ ግምት መክፈላቸው አልቀረም። እሱንም ቢሆን ለኢትዮጵያ ጥለው ሄዱ እንጂ አልተጠቀሙበትም።

ኢጣልያ ለቅኝ ግዛት አስተዳደሯ እንዲጠቅማት በማሰብ፣ በኢትዮጵያ ላይ የልማት ሥራ ለማካሄድ ልዩ ልዩ ጥረት አድርጋ እንደነበር፣ ከላይ የተዘረዘሩት ሁኔታዎች አስረጅዎች ናቸው። ነገር ግን እራሷ ጥቅም አላገኘችባቸውም። ጥቅም ላታገኝ የቀረችባቸው ምክንያቶች በእያንዳንዱ የልማት ዘርፍ የተገለፀ በመሆኑ እንደገና መድገም አያስፈልግም። ይህም ቢባል የደከመችበት የልማት ሥራ በከንቱ ፈሰሶ አልቀረም። ከጦርነቱ በኋላ ለኢትዮጵያ መከፈል ለነበረበት የጦር ካሣ (በከፊል) ማጣጫ ሆኗታል።

ሌላው የኢጣልያ ችግር የቢሮው ሥራ ነበር። በድምሩ 1,725,320 ካሬ ኪሎ ሜትር ሥፋት ያለውን የምሥራቅ አፍሪካ ቅኝ ግዛት ማስተዳደር ቀላል አልሆነላትም። ለማንያ የሚሆኑ ኮሚሽነሮች፣ 260 ያህል አገረ ገዥዎች /ሬዚደንትስ/፣ 226 ምክትል አገረ ገዥዎች፣ ከነዚህም ጋር 2470

ከፍተኛ ችሎታ ያላቸው ሠራተኞች አስፈለጉ። ነገር ግን ከጣልያን አገር ማስመጣት የተቻለው 1350 ማለትም ግማሹን ሠራተኞች ያህል ብቻ ሆነ። የመካከለኛ ደረጃ እውቀት ያላቸው ሌሎች 2,157 ቢያስፈልጉም፣ እነዚህንም እንኳን በበቂ መጠን ማስመጣት አልተቻለም። የመጡት 85% ብቻ ነው። ከነዚሁ ሹማምንትና ሠራተኞች መካከል ቤተሰብ ያስመጡት እጅግ ጥቂት ስለነበሩ፣ ሥነ ልቡናቸው ከባድ የመንግሥት ሥራ ተዕዕኖ መሸከም አላስቻላቸውም። በዚህ ላይ ደግሞ ፍቀረ ንዋይ አደረባቸው። ልምድና ችሎታ የሌላቸውም በረከቱ። ለነዚህ ሁሉ መኖሪያ ቤትና ቢሮ ማዘጋጀት፣ ነዋሪ ዕቃ ማደራጀት ግድ ሆነ።

ሥራውን ሜካናይድ ግድ ስለሆነባቸው ኢትዮጵያ ውስጥ ካሉት የጦር መኰንኖቻቸው መካከል ችሎታ ያላቸውን እየመረጡ ለመደልደል ሞከሩ። በወቅቱ ከነበሩት 2000 መኮንኖች መካከል 79% ለውድድር ቀረቡ። ከእነዚህም 504ቱ የዩኒቨርስቲ ዲግሪ ያላቸው ነበሩ። በሌላ በኩል መኮንኖቹ እየመረጡ ባለው ቦታ ሁሉ መመደብ ጦሩን የሚያራቁት ሆነ። ጥቂቶቹን አዛውሮ ሌሎችን መተው ደግሞ፣ ቀሪዎቹን ቅር ማሰኘት ሆነ። በአነስተኛ ሥራዎች ኢትዮጵያውያንን መቅጠር ችግሩን በመጠኑ ቢያቃልልም፣ በምሥጢር አጠባበቅ ረገድ አስተማማኝነት አጣ። በዚህ ላይ በቂ ችሎታ ያላቸው አልተገኙም። ከአሉትም ጥቂት ኢትዮጵያውያን ባለሙያተኞች ውስጥ፣ ማናቸውም ሰጠላት ለመሥራት ፈቃደኞች አልሆኑም። ስለዚህ የመንግሥቱ ሥራ አካሄድ ውስጡ ስምረት ሊያገኝ አልቻለም።

የቅኝ ግዛቱ ዋና ዓላማ ኢትዮጵያ ላይ ትርፍና ምርት አስገኚ ሥራዎችን በማካሄድ ለኢጣሊያ ጥቅም ለማግኘት ነበር። ነገር ግን ሁኔታው የተገላቢጦሽ ሆነ፣ ከኢትዮጵያ ገንዘብ ወይም የምግብ እህል ወይም ሌላ ዕቃ ወደ ኢጣልያ የሚያግዝ ሳይሆን፣ በየዕለቱ የሚካሄደው ሥራ መዋዕለ ንዋይ ከኢጣልያ ወደ ኢትዮጵያ የሚያስፈስስ ሆነ። ማነጃ ጠፋበት። በኢትዮጵያ ምክንያት በዓለም መንግሥታት ማኅበር ጉባዔ የተነሳው ንትርክ፣ የጣልያን መንግሥትን ጤና ነሳው። ኢትዮጵያ ውስጥ ጦርነቱ ቀጠለ። ተስፋ የተጣለባቸው የልማት ሥራዎች ሁሉ አንዳች ውጤት ሳይሰጡ ቀሩ። ወጭው አለመጠን እየበረከተ ሄደ።

በሌላ በኩል የምዝበራውን ነገር መቆጣጠሪያ ጠፋበት። የሮም አይሮፕላን ማረፊያ፣ ወደቦችና ባቡር ጣቢያዎች ከኢትዮጵያ በሚጋዙ ሣጥኖችና ሻንጣዎች ተጣበቡ። ማርሻል ባዶሊዮ ወደ ሀገሩ የገባው በ300 ሣጥን የታሸገ ዕቃ አግተልትሎ ነበር፣ ወርቅ ጭምር። የኢጣልያ የጉምሩክ ሠራተኞች እንደዚያ ያለ ጉዝ አይተው ስለማያውቁ፣ ጭንቅ ተፈጠረ። በሞሶሊኒ ልዩ ትዕዛዝ ሳይፈተሽ እንደታሸገ ገባ። ግራዚያኒም ነፃ 79 ሣጥን ይዞ ገባ። ሌሎችም ሹማምንቶች እንደዚሁ። ይህ ብቻም አልነበረም። ለባዶልዮ አንድ ሚሊዮን፣ ለግራዚያኒ ግማሽ ሚሊዮን ሊሬ በየዓመቱ

እንዲከፈላቸው ተወሰነ። በዚህ ላይ ደግሞ የሮም ባለሥልጣኖች ኢትዮጵያ ውስጥ ሥራ ለመሥራት ከመንግሥት ጋር ውል ከሚዋዋሉት ከብንያዎች ጋር የመደለል ሥራ ተጧጧፈ። ለምሣሌ ሲሶና በተባለው የአፍሪካ ጉዳይ ሚኒስትር ትዕዛዝ አስካሌራ በተባሉ ወንድማማቾች ላይ የቀረበባቸው ክስ፣ ከዲቦኖ ጋር በመስማማት ከኢጣልያ መንግሥት 50 ሚሊዮን ሊሬ ያለአግባብ ወስደዋል የሚል ነበር።

በዚህ ሁሉ ምክንያት የምሥልቅ አፍሪካ ቅኝ ግዛት ወጭ እየናረ ሄደ። የበጀት ድልድል የማይገድበው ሆነ። አዲስ አበባ ላለው የሚልዣዊ ኢማኑኤል እንደራሴ እስከ 5 ሚሊዮን፣ በውስጡ ላሉት አገረ ገዥዎች እስከ 2 ሚሊዮን ሊሬ በዓመት ከበጀት በላይ ለማዘዝ የሚያስችላቸው ሥልጣን ቢሰጣቸውም፣ ያም ሳይበቃ ቀረ። ለምሣሌ በ1929 ዓ.ም /1936-37/

ሀ. ጠቅላላው ከጣልያን አገር የሚገኘው የመንግሥት ገቢ 18,581 ቢሊዮን ሊሬ እንደሚሆን ተገመተ።

ለ. ለምሥራቅ አፍሪካ ቅኝ ግዛት ማስተዳደሪያ እንዲመደብ ከአፍሪካ ጉዳይ ሚኒስትር የተጠየቀው 5 ቢሊዮን ሊሬ ነበር።

ሐ. ነገር ግን ወጭ የተደረገው 19,136 ቢሊዮን ሊሬ ሆነ።

የሮም ባለሥልጣኖች በዚህ ሲደነቁ ለ1932 ዓ.ም /1939/ የበጀት ዘመን፣ በዱክ ደ አዎስታ የተጠየቀው በጀት 4.8 ቢሊዮን ሊሬ ሆነ። በገንዘብ እጦት ምክንያት ተቀንሶ 1.371 ቢሊዮን ሊሬ ብቻ ነበር።[8] በዚህ የተነሣ ኢጣልያ እጅግ የከበረ ዋጋ ያላቸውን ሥዕሎቿን ከሙዚየም እያወጣች የውጭ ምንዛሪ ለማግኘት ለውጭ አገር ሰዎች እስከ መሸጥ ደረሰች።[9]

የወታደሩ አስተዳደር ደግሞ ሌላ ራስ ምታት አመጣ። የአውሮፓ ኑሮ ምቾትና ልስላሴን ያዘወተረ ነው። የጣልያናውያን ኑሮም እንደዚሁ ነው። በአሁኑ ጊዜ በሀገራችን ከተሞች የተለመደም ቢሆን የኑሮውን ዘይቤ በቀረቤታ ማየት አይከፋም። በአውሮፓ ምግብ ከመኝታ ሲነሱ ጀምሮ ተመልሶ አስኪተኙ በተደጋጋሚ ይካሄዳል። ጥዋት ቁርስ ደንብ ነው። ከብርቱካን ጭማቂ ጋር የእንቁላል ወይም የሥጋ ጥብስ በዳቦ ይቀርባል። ሻይ በወተት ይቀርባል። ረፋዱ ላይ ሻይ በብስኩት አለ። ምሣ ሁለትና ሦስት ዓይነት ሆኖ ፓስታ ይኖራል። ማዋዣው የወይን ጠጅ ነው። ቡናም አለ። ወደ ማታ ሻይ ከብስኩት ጋር አይቀርም። ማታ ራት ሾርባ ከስስላሳ ምግብ ጋር ይሆንና የአልኮል መጠጥ ይኖራል። በአንዳንድ ምሽት ዳንስ ጨዋታ ወይም ትያትርና ሲኒማ ይታያል። የልብስ ጉዳይ ደግሞ አለ። የቀን ልብስ የሚሞቅ፣ የማይሞቅ ሆኖ ሙሉ በሙሉ ልብስና ሸሚዝ፣ ከራባት አለው። ሲሀን ሦስት ካልተቻለም ሁለት መለወጫ ይኖራል። ለእግር ጫማ ከእሱም ጋር የእግር ሹራብ አለ። ለራስ ባርኔጣ ይደረጋል። በዚሁ ላይ ካፖርት ይኖራል። የሌሊት ልብስ ደግሞ ጥንድ አንሶላ ከነመለወጫ፣ በቂ ብርድ ልብስና ፍራሽ አለ። ሙሉ የሣሎን፣ የመኝታ ቤትና የምግብ ቤት ዕቃ አለ። ተከራይቶም እንኳን

ቢሆን በቂ መኖሪያ ቤት አይጠፋም። መኪና የግሉም እንኪን ባይሆን በሕዝብ ትራንስፖርት መጠቀም ይቻላል። በዚህ ሁሉ ላይ ቆንጆ ሚስት፣ ተወዳጅ ልጆች አሉ።

የኢጣልያ ጦር ወደ ኢትዮጵያ የተጓዘው በሰኔ 1927 ዓ.ም ነው። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ከላይ የተዘረዘረው ፀጋ ሁሉ በሞሶሊኒ ቅዠት ተጠቅልሎ ሮማ ቀረ። የጣልያን ወታደር ጨፍሮ ወደ ኢትዮጵያ የመጣው፣ ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ ጦርነቱን ጨርሶ ወደ ሰላማዊ ኑሮው ሊመለስ ነው። ነገር ግን ጦርነቱ የማያልቅ ሆነ። በአደንቋሪው የሞሶሊኒ አሽቃባጮች ጩኸት እየተንተተ የጣልያን ወታደር ኢትዮጵያ ላይ በመዝመቱ ያገኘው መሞት፣ መቁሰል፣ በመዓልትና በሌሊት መንገላታት፣ መራብ፣ መጠማትና መታረዝ ብቻ ሆነ። ዋናውን፣ የ1928 ዓ.ም ጦርነት በሙሉ ልቡ በጀግንነት ተዋጋ። የ1929 ዓ.ም ጦርነት ስሜቱን ጠጥቶ በብርታት አካሄደ። በ1930 ዓ.ም ይቃለልልኛል ብሎ ሲጠብቅ፣ እንዲያውም ይባስ ሆነበት፣ ቢሆንም ቻለው። በ1931 ዓ.ም ግን ትዕግስቱም፣ ጉልበቱም፣ ፍላጐቱም ተቀነሰ። በ1932 ዓ.ም መዋጋቱን ተወ። ክለጥቂነት ይልቅ የተከላካይነትን ሚና መጫወት ጀመረ። እንዲያዉም የአርበኞች ኃይል በተራው እየከበደበት፣ ጥቃትም እየበዛበት ሄደ። የ1933 ዓ.ም፡ ወሳኙ ጦርነት ሲከፈት፣ የኢጣልያ ጦር ፍፁም በቅቶት መንቀሳቀስ ከማይችልበት ደረጃ ላይ ደርሶ ነበር። የወታደሩን ቁጥር ከ240 ሺህ ወደ ግማሽ ሚሊዮን ከፍ ማድረግ፣ ወጭ ከማብዛትና የአስተዳደር ችግር ከማከበድ በስተቀር አንዳች ውጤት ሳይሰጥ ቀረ። ባለሥልጣናቹ ለአርቅ የተጣደፉት በፖለቲካው ሁኔታ ተገድደው ብቻ አልነበረም። ይልቁንም በዚህ፣ በዚህ ሁሉ ምክንያት ተገድደው ነው።

ማጣቀሻ ፅሑፎች

1. ተክለፃድቅ መኩሪያ፣ *የኢትዮጵያ ታሪክ ከአፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ*፣ ገጽ 54-57።
2. Pierre Petrides, *Boundary Questions Between Ethiopia and Somalia*, p.28-108.
3. Alberto Sabacchi, *Ethiopia under Mussolini* pp, 43-62.
4. የቁጥር መልእክተኛ ሁለት ጋዜጦች ከሚያዝያ 1 እስከ 14 ቀን 1932 ዓ.ም።
5. ጳውሎስ ኞኞ፣ *የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦርነት*፣ ገጽ 202።
6. Giuseppe Ziliotto, *Libri Fondiae Nelle Colonie*, pp. 316-331.
7. Sabacchi, pp. 95-114.
8. *Ibid.*, pp. 43,114.
9. Stanely Cooperman, *Benito Mussolini*, pp. 18-123.

ምዕራፍ ሃምሣ
የቅኝ ግዛት ወታደሮች ሚና

እንደማንኛውም የቅኝ ግዛት ጦርነት፣ የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦርነት የተካሄደው በቅኝ ግዛት ወታደሮች ጭምር ነበር።

ኢጣልያ በጦርነቱ ጊዜ በኢትዮጵያ ላይ ስለአሰለፈችው ወታደር ብዛት የታሪክ ጸሐፊዎች ግምት ይለያያል። በኢትዮጵያ ላይ በቆየችበት ወቅት የነበራት ጦር ብዛት ደግሞ ከጊዜ ወደ ጊዜ ይለያያል። ቢሆንም አንዳንድ የታመኑ ነገሮች አሉ። ጄነራል ደቦኖ መስከረም 23 ቀን 1928 ዓ.ም የመረብን ወንዝ የተሻገረው 250,000 ወታደር አሰልፎ ነው። ከዚሁ ውስጥ 65,000 ኤርትራውያን ነበሩ። በደቡብ በኩል ደግሞ 33,000 የቅኝ ግዛት ወታደሮች ነበሩ። ቆይቶ ደግሞ 5,000 ያህል ሱማሌዎች ተጨመሩ። የጣልያናውያኑ ብዛት ግን አልተገለጸም። ሞሶሊኒ ሰኔ 3 ቀን 1932 ዓ.ም ከጀርመን ጐን የቆመው በኢትዮጵያ ላይ 350,000 ጦር አሳፍሮ ነው። እነዚህን አሀዞች ይዘ አንዳንድ ግምት መሥራት ብዙ አያሳስትም። ስለዚህ ከመጋቢት እስከ ሰኔ 1928 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ፣

	በሰሜን ግንባር	በደቡብ ግንባር	ድምር	%
ጣልያናውያን	180,000	11,000	191,000	64
ሊቢያውያን	10,000	8,000	18,000	6
ኤርትራውያን	60,000	5,000	65,000	22
ሶማሊያውያን	-	26,000	26,000[1]	8
ድምር	250,000	50,000	300,000	100

ይህ ቁጥር ከ1928 ዓ.ም በኋላ አልቀነሰም፣ ጨመረ እንጂ። ከኢትዮጵያም ውስጥ እየተመለመሉ ባንዶች ገቡ። እስከ ጦርነቱ ፍፃሜ የነበረው የጣልያን ጦር በትክክል አልታወቅም። በግልጽ የሚታወቀው ጣልያኖች ከሀገር ውስጥ ባንዳ በብዛት እየመለመሉ ማሰለፋቸው ነው። የእሱም ቁጥር በትክክል አልታወቀም። ጠላት ገበሬም እያስገደደ ለጦርነት ያሰለፈበት ጊዜ ብዙ ነው። ነገር ግን እሱ ከቁጥር አይገባም። አዲስ ጦር ከጣልያን አገር አልመጣም። ከአለውም ብዙ ሰው ወደ ሲቪል ሥራ ተዛውሮአል። ይህም የቅኝ ግዛቱ ወታደር እንዲበረክት አድርጐአል። ጠቅላላው ጦር ከዚህ እንደሚከተለው ሳይሆን አልቀረም።

	ከውጭ የገባ	ባንዳ	ድምር	የባንዳው %
በ1928 ዓ.ም /ክፕር-ነሐሴ/[2]	220,000	-	250,000	-
በ1929 ዓ.ም	220,000	30000	250,000	12
በ1930 ዓ.ም	250,000	50000	300,000	17
በ1931 ዓ.ም	250,000	100000	350,000	28
በ1932 ዓ.ም	250,000	100000	350,000	28
በ1933 ዓ.ም	200,000	50000	250,000	20
በ1934 ዓ.ም /ከመስከረም-ጎዳር/	30,000	10000	40,000	25

እነዚህ ወታደሮች የራሳቸው የሆነ የእዝ ሠንሠንለት ነበራቸው። ከነጮች በታች ሆነው አመራር የሚሰጡት አለቆች ሽምግሸ ይባላሉ። ከሽምግሸ በታች ቡልቅባሾች፣ ከእነሱ በታች ደግሞ መንጣዞች አሉ። ይህ ስም አጠራር ከሊብያ ወታደሮች የተቀዳ ሳይሆን አልቀረም። ደመወዛቸው፣

የቅኝ ግዛት ወታደር	200
ለመንጣዝ	225
ለቡልቅባሽ	250
ለሹምባሻ	300 ሊራ በወር ነበር።[3]

የደረጃ እድገት የሚሰጠው የሥራ ውጤት እየተገመተና የአገልግሎት ዘመንም እየታየ ነበር። ነገር ግን የመካንነት ማዕረግ አይሰጣቸውም። የምክትል መቶ አለቅነት እንኳን። እስከ 1930 ዓ.ም ድረስ ወታደራዊ አገልግሎት ግዴታ ነበር። ከዚያ በኋላ ወድዶ ለተቀጠረ ብቻ ሆነ። ከኢትዮጵያ ውስጥ በተቀጠረ ባንዳና ከውጭ በመጣ ወታደር መካከል በደመወዝ አከፋፈል ረገድ ልዩነት አልተደረገም።

በደመወዝ ላይ ደግሞ የወር ቀሰብ ይሠፈር ነበር። የወር ቀለቡ ደግሞ በቂ ዱቄት፣ ሻይና ሰኳር፣ ጨው ይጨምራል። በጦርነት ጊዜ ለአንድ ቡልቅባሽ ሠራዊት በሣምንት አንድ በሬ ይሰጣል።

በአስላለፍ ረገድ አንድ መንጣዝ 10 ወታደር፣ አንድ ቡልቅባሽ 2 መንጣዝ፣ አንድ ሹምባሽ እስከ 12 ቡልቅባሽ ይይዛል። ወታደር የሚቀጠረው የአካል ብቃትና የመንፈስ ንቃት እየተመጠነ ነው። ሥነ-ሥርዓትን በተመለከተ ሰላማዊ ሰውን በተለይም ሴቶችን መድፈር ወንጀል ነው፣ ሌብነትና ውሸት ያስቀጣል። ከጦር ግንባር መሸሽ ያስገድላል። ትጥቅን በተመለከተ ለእያንዳንዱ የቅኝ ግዛት ወታደር አንድ ባለሳንጃ ምንሽር ጠመንጃ ከበቂ ጥይትና ከአራት የእጅ ቦምብ ጋር ይሰጠዋል። የጣልያኑ ወታደር

ባለሳንጃ አልቤን ጠመንጃ ከበቂ ጥይት ጋር፣ እንደዚሁም አራት የእጅ ቦምብ ይይዛል። እያንዳንዱ መንጣዝ አንድ አልቤን መትረየስ አለው። ለአንድ ሹምባሽ አንድ ውሃ መትረየስ አለው።[4]

ኤርትራውያን የተዋጉት በጣልያን ወገን ብቻ ሆነው አልነበረም። ጥቂቶች ከኢትዮጵያም ጐን በመቆም ተዋግተዋል። ስድስት መቶ በቦረና ግንባር ገቡ። ሌሎች 350 ከጥቁር አንበሳ ጦር ጋር ተሰለፉ። ሌሎች ደግሞ ከየግንባሩ እየከዱ ከኢትዮጵያውያን ወንድሞቻቸው ጋር ተቀላቀሉ። እኔ በነበርኩበት የአርበኝነት ግንባር እንኪን 4 ነበሩ። መሪአቸው አቶ ምስጋናው በየነ ይባል ነበር። እሱም በዚያው በአርበኝነት ዘመን የባላምባራስነት ማዕረግ አገኘ። በርካታ ኤርትራውያን የቻሉትን ያህል እየተዋጉ ከሞት የተረፉት ወደ ኬንያ ተሰደዱ። የብላቴን ጌታ ሎሬንሶ ታእዛዝ፣ የአብርሃ ደቦጭና የሞገስ አስግዶም፣ እንደዚሁም የዘርዓይ ደረሰ ስም ከዚህ መጠቀስ አለበት። ሌሎችም በኢትዮጵያ ምክንያት በጣልያኖች እጅ በእሥራት የማቀቁ በግዞት የተንገላቱ ብዙ ናቸው።[5]

ጣልያኖች በቅኝ ግዛት ወታደሮቻቸው፣ በተለይም በኤርትራውያን በደንብ ተጠቅመውባቸዋል። ንጉሠ ነገሥቱ ስለዚህ ጉዳይ ሲገልጹ፣ "...በዚያም /በኢጣልያ/ በኩል ከእኛ ወታደሮች ጋራ በርትተው የሚዋጉት የኤርትራ ወታደሮች ነበሩ እንጂ ጥቁር ለባሾች ጣልያኖች ጥቂት ነበሩ። ጥቁር ሸሚዝ ለባሾች ጣልያኖች ግን የሚለለፉት በጣም ርቀው በስተኋላ ስለነበር እነሱን ለማግኘት /ለመግደል/ ብዙ ችግር ነበር..." ብለዋል።[6] ጀነራል ባዶሊዮ ደግሞ ስለኤርትራ ወታደሮቹ በሰጠው ሪፖርት "...አሁንም እንደገና መልሰው ጀግንነታቸውን፣ ታማኝነታቸውንና ከዓላማችን ጋር ያላቸውን ጽኑ ግንኙነት በተግባር ገለጹ..." ብሎአል። የሚያስልፉአቸውም በአልኮል መጠጥ እያሰከሩ ነበር።[7]

እነኚህ የቅኝ ግዛት ወታደሮች አገልግሎታቸው መና አልቀረባቸውም። ከ1950 ዓ.ም ጀምሮ ከኢጣልያ መንግሥት የአገልግሎት ዋጋ ተከፍሏቸዋል። አሥመራ ባለው ቆንሲል በዚያን ጊዜ ይከፈል የነበረው፡- ለወታደር 70፣ ለመንጣዝ 90፣ ለቡልቅባሽ 130፣ ለሹምባሽ 200 በወር ነበር። ከዚህም በስተቀር የአካል ጉዳት የደረሰባቸው ተከፍሎአቸዋል። እግሩ ለተቆረጠ እስከ 80000 ብር እንደተከፈለ ተመዝግቦአል። የጤና እንክብካቤም ይደረግላቸዋል። በዚህም የተነሣ ለኢጣልያ መንግሥት በሰጡት አገልግሎት ይመኩበታል እንጂ፣ ብዙዎች እንደሚጠብቁት፣ የሚያዝኑበት ወይም የማይደሰቱበት ጉዳይ አይደለም። በኢትዮጵያም ወገን ሆነው የተዋጉት የኤርትራ ተወላጆች የድካማቸው ዋጋ አልቀረባቸውም። በመንግሥት ሥራም ከከፍተኛ ደረጃ የደረሱ አሉ። ሻሸመኔ ያለው የሥመጥር ሐማሴን የዚህ ውጤት ነው።[8]

ከዚህ ታሪካዊ ሁኔታ አንዳንድ ትምህርት ሰጭ ግንዛቤዎችን መጨበጥ ይገባል። በታሪኩ ውስጥ እንደተገለጸው በኢትዮጵያ ላይ በ1928

ዓ.ም በሰሜንም በደቡብም ከተሰለፈበት ጦር እጅግ ቢያንስ 36%፣ ከዚያ ቀጥሎ እስከ ጎዳር 1934 ዓ.ም በቀጠለው ጦርነት ደግሞ ከ12% እስከ 28% የኤርትራ ተወላጆች ነበሩ። ሂደቱም በኢትዮጵያ ላይ ባሰብዙ ፈርጅ ጉዳት አስከተለ። ከጉዳቶቹም ዋና ዋናዎቹ፡- መጀመሪያ ላይ የጦርነቱ ሚዛን ለጣልያን እንዲያደላ ማድረጉ፣ የአገሪቱን የሰው ኃይል መቀነሱ፣ የርስበርስ ተቃርኖ መፍጠሩ ናቸው።

ማጣቀሻ ፅሑፎች

1. Luigi Frusci, *In Somalia Sulfurs Meridiale*, pp,19-40.
2. በጦርነቱ 30,000 ከጥቅም ውጭ እንደሆነ ቢገመት።
3. ከኢትዮጵያ ውስጥ ለተቀጠረ ወታደር።
4. ከግራዝማች ኃይለ ንጋቱ ይማም የተነገረኝ።
5. ኃይሉ ገብረኢየሱስ፣ መድረክ መጽሔት፣ ገጽ 69-83።
6. ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፣ *ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ፣ 1ኛ መጽሐፍ*፣ ገጽ 22-30።
7. ሙሉሰው ምትኩ፣ *የአርበኞች ትግል ከፋሽስት ጋር*፣ ገጽ 32-370።
8. Araya Habtay, *The Role of Eritrean Askaris In the Italo-Ethiopian War*, pp, 5-46።

ምዕራፍ ሃምሣ አንድ
የአውሮፓ ሁኔታና የኢትዮጵያ የዲፕሎማቲክ ሥልት

ኢጣልያ ኢትዮጵያን ለመውረር በተንቀሳቀሰች ጊዜ የዓለም ሁኔታ በመዋዠቅ ላይ ነበር። ከ1921 ዓ.ም /1929/ ጀምሮ ከፍተኛ የኢኮኖሚ ድቀት ደርሶ ስለነበር የአውሮፓ አገሮች እምብዛም አላንሠራሩም። በፖለቲካም ረገድ ሞሶሊኒ በኢጣልያ፣ ሂትለር በጀርመን፣ ስታሊን በራሺያ ሕዝቦች በመጨፈር ላይ ነበሩ። ማለትም በኢጣልያ ፋሽዝም፣ በጀርመን ናዚዝም፣ በራሺያ ኮሚኒዝም ሠፍነው ነበር። በዚህ ላይ ደግሞ የጃፓኑ ጦረኛ ቡድን ተንቀሳቀሰ።

ሁሉም ዓላማ ነበራቸው። በሀገራቸው ውስጥ ያለውን ችግር ለማቃለል መሞከር ተራራ እንደ መግፋት ያለ ጠጣር ሆኖባቸዋል። ቀላል ሆኖ ያገኙት የሕዝቦቻቸውን ስሜት ወደ ባሕር ማዶ አሻግረው እንዲመለከቱና በርስበርስ ጥላቻ እንዲያያዙ ማድረግ ሆነ። ጣልያን በኢትዮጵያ ላይ አተኮረች። የንጉሡንና የጳጳሱን ሥልጣን መቀናቀን ያዘች። ጀርመን በመጀመሪያው የዓለም ጦርነት የደረሰባትን ውርደት መበቀል ፈለገች፣ የሰላሙን ውል በማፍረስ ያጣቻቸውን ነገሮች መልሳ ማግኘት ፈለገች። በሀገር ውስጥ ጉዳይ ደግሞ አይሁዶችን የሕዝብ ጠላት አደረገች። ራሺያ በአካባቢዋ ያሉትን ሀገሮች ጠቅልላ መያዝ ፈለገች። በሀገር ውስጥ ጉዳይ ደግሞ የቀድሞዎችን ነገሥታት ወገኖች አድሀርያን ብላ ለእርድ አቀረበች። ጃፓን በአዲሱ ቅርምት ከሩቅ ምሥራቅ አገሮች ደህና ድርሻ ለማግኘት ጓጓች። አሜሪካን ደግሞ ገለልተኛ ነበረች። ፕሬዚዳንት ዊልሰን በመጀመሪያው የዓለም ጦርነት ፍፃሜ ላይ በአስታራቂነት መግባታቸው እንደታጥአት ተቆጥሮ ለሁለተኛ ጊዜ የመመረጥ ዕድላቸውን ስለአጠሩባቸው፣ ፕሬዚዳንት ሩዝቨልት ተመሳሳይ ዕድል እንዳይደርስባቸው ሰግተዋል። የአውሮፓ ታናናሽ አገሮች የየራሳቸውን ሕልውና ከመጠበቅ ባሻገር አንዳች የማድረግ አቅም የላቸውም። ላቲን አሜሪካ አፍሪካና እስያ በቅኝ ግዛት ውስጥ ወድቀዋል።

የዓለም መንግሥታት ጉባኤ በቅርቡ የተቋቋመ ማኅበር ነው። መንግሥታትን የማግባባት፣ ሲጋጩ የማስታረቅ፣ ቅራኔዎችን ሰላማዊ በሆነ መንገድና በመንግሥታቱ በራሳቸው ፈቃድ ለመፍታት አቅም አልነበረውም። ዋና ዋናዎቹ ተዋንያን እንግሊዝ፣ ፈረንሳይ፣ ጀርመን፣ ራሺያ፣ ጣልያንና በመጠኑ አሜሪካን ናቸው። ከቀሩት አገሮች አንዳንዶቹ የአርጋጅ አርጋጅ ናቸው። አብዛኞቹ የትርዕይቱ ተመልካቾች ናቸው። ከአፍሪካ አገሮች የማሀበሩ አባላት ኢትዮጵያና ላይቤሪያ ብቻ ናቸው። ላይቤሪያም የአሜሪካ ተቀጽላ ናት። በአጠቃላይ ሲታይ በወቅቱ የዓለም ማኅበር የመላላት ባሕርይ

ይታይበታል። ለዚህ አስተዋጽኦ ያደረጉት ነገሮች ደግሞ የአንግሊዝ ወላዋይነት፣ የፈረንሣይ ግድየለሽነት፣ የጀርመን ጦረኝነት፣ የአሜሪካን ገለልተኝነት፣ የራሺያ አለመረጋጋት፣ የኢጣልያ ቅኝ ግዛት ፍላጉትና የጃፓን ተስፋፊነት ነበሩ።

ይህም ሁሉ ሆኖ ከመጣባት ጠላት የዓለም ኀብረተሰብ እንዲታደጋት ኢትዮጵያ ውትወታዋን ቀጠለች። ንጉሠ ነገሥቱ በዓለም ማኅበር ላይ ጽኑ እምነት አደረባቸው። ብዙ እንዳይታመኑ የቀረቡላቸውን ምክሮች አልተቀበሉም። የጣልያን አያያዝ ለኢትዮጵያ አስጊ መሆኑን ግንቦት 8 ቀን 1927 ዓ.ም አስታወቁ። መልእክታቸው "...ኢጣልያ አገራችንን ለመውሰድ ያላትን ምኞት ...አሳቋረጠችም። ...ይኸው ምኞትዋ... በሥራዋ እየተገለጸ መታየት ጀመረ። ...በወሰኖቻችን አቅራቢያ የጦር መሣሪያ በብዛት ማከማቸት ጀመረች።..." የሚሉ ኃይለ ቃላት ያዘለ ነበር። ኅዳር 26 ቀን 1927 ዓ.ም የተደረገው ግጭት ጠቡን አረጋገጠ። ስለዚህም ሁለቱም ወገኖች ሽማግሌዎች እንዲመርጡ ተወሰነ። ኢትዮጵያ አንድ ፈረንሳዊና አንድ አሜሪካዊ መረጠች። ኢጣልያ ሁለት የራስዋን ዜጐች መረጠች። ሽማግሌዎቹ "ነወልወል ግጭት ኢትዮጵያም ኢጣልያም ኃላፊ ሊሆኑ አይችሉም" የሚል ሸፋፋ ውሣኔ ሰጡ።

እንግሊዝና ፈረንሣይ የእርቅ ሃሳብ አቀረቡ። የፈረንሣይ ሚና ከመናጆ ያለፈ አልነበረም። ዋናውን የነገር ድር ያጠነጠነችው እንግሊዝ ነበረች። መሳሪያዎቹ ሆርና ላቫል የተባሉት የሁለቱ አገሮች የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ነበሩ። የእርቁ ሃሳብ በየጊዜው ተሰዋውጦአል። የተሰዋወጠውም በኢትዮጵያ ላይ ይበልጥ ተፅዕኖ እያሣደረ ነበር። ለመጨረሻ ጊዜ የቀረበው ሃሳብ፣

1ኛ. ኢትዮጵያ አክሱምን ብቻ አስቀርታ እስከገባ ወንዝ ያለውን አገር ለኢጣልያ እንድትለቅ፣

2ኛ. የአውሣ መሬት ለኢጣልያ እንዲሆን፣

3ኛ. ከአጋዴን እስከ ቆራሄ ያለውን አገር ለኢጣልያ እንድትሰጥ፣

4ኛ. እንግሊዝ በበርበራ በኩል የዘይላን የባሕር በር ለኢትዮጵያ እንድትሰጥ ነበር።[1]

የእርቁ ዓላማ ኢትዮጵያን ከጠቅላላ ጥፋት ለማዳን እንደሆነ ለማስመሰል ብዙ የነገር ሥራ ተካሄደ። የሀገርን አንድነት የሚነካ በመሆኑ በኢትዮጵያ በኩል ተቀባይነት ሳያገኝ ቀረ። በዚህ ረገድ ንጉሠ ነገሥቱ ምሥጋና ይገባቸዋል። አድዋ ላይቀርላቸው ኤርትራን ቆርሰው በመስጠት አፄ ምኒልክ የፈጸሙትን ስሕተት ሳይደግሙት ቀሩ።

በዓለም መንግሥታት ጉባኤ መወሰድ ከነበረባቸው እርምጃዎች አንዱ በአጥቂዋ ቡጣልያን መንግሥት ላይ የጦር መሣሪያና የኢኮኖሚ ማዕቀብ መጣል ነበር። ኢትዮጵያ ይህ እንዲደረግ ደጋግማ አሳሰበች። ማኅበሩ ለሁለቱም ሀገሮች መሣሪያ እንዳይሸጥ የሚከለክል ውሳኔ አሳለፈ። ኢጣልያ ራስዋ መሣሪያ በብዛት በመሥራት ላይ መሆንዋ እየታወቀ፣ ይህንን የመሰለ

ውሣኔ የተሰጠው ለኢትዮጵያ መሣሪያ እንዳይሸጥላት ለማገድ የተሠራ ደባ ነበር። እንግሊዝ ስዊዝ ካናልን ብትቆጣጠር ችግሩ ሊቃለል ሲችል አንዳች አላደረገችም። በኢኮኖሚም በኩል ማዕቀቡ የይስሙላ ነበርና አንዳች አልፈየደም።

ኢትዮጵያ በዚህ ዓይነት የነገር አሽክላ ተተብትባ ከጣልያን እጅ ወደቀች። የአውሮፓ መንግሥታት ተሽቀዳድመው ኢጣልያ በኢትዮጵያ ላይ ያላትን ይዞታ አወቁ። የአሜሪካ፣ የሄይቲ፣ የራሺያና የሜክሲኮ መንግሥታት እውቅና ሳይሰጡ የወረራው ዘመን አለፈ። ምስጋና የሚገባው ታላቅ የፖለቲካ ብስለት ነው። እንግሊዝ እስከ ሚያዝያ 1931 ዓ.ም ተግደርድራ ከዚያ በኋላ አወቀች። የፈረንሣይ መንግስት በጀርመን እስከተወረረበት ቀን እውቅና ሳይሰጥ ቆየ። በኢትዮጵያ ውስጥ የነበሩ ሚሲዮኖችና ሚሲዮናውያን ሁሉ ሌጦአቸውን ገልብጠው ከጣልያን ጋር ተስማሙ። አብዛኞቹ ቀድሞውንም የጣልያን ሰላይ ስለነበሩ አፈፃፀሙ ሥምረት አገኘ። የስዊድን ሚስዮን ብቻ ሚስዮኑን ዘግቶ ከሀገር ወጣ።

ኢትዮጵያ ድል በመሆንዋ የዲፕሎማቲክ ትግል አላቋረጠም። ከኢትየጵያ ከወጡ በኋላ ንጉሠ ነገሥቱ ከኢየሩሳሌም ግንቦት 11 ቀን 1928 ዓ.ም ለዓለም መንግሥታት ማኅበር ቀጣዩን አቤቱታ አቀረቡ። አቤቱታውም "...የኢትዮጵያ ሕዝብ ፈጽሞ...ታይቶ፣ ተሰምቶ በማያውቅና በማይመዛዘን፣ ከሰው የተፈጥሮ ባሕርይ የተላለፈ የግፍ ጦርነት እንዳያልቅ..."በሚል ኃይለ ሰቆቃውን ከገለጸ በኋላ፣ ኢጣልያ የውል ግዴታዎችን ጥሳ ገዥ ነኝ የምትሰውንና ግዛት ማስፋፋትዋን ማኅበሩ እንዳያውቅላት የሚጠይቅ ነበር። ነገር ግን አንዳች ፋይዳ አላስገኘም።

በአውሮፓ ጋዜጦች ነፃነት እንዳላቸው፣ ነገር ግን ይህ ነፃነት የኢትዮጵያን ጉዳይ በእውነተኛ መልኩ ለመግለጽ አስችሎአቸው አያውቅም። የሮም ካቶሊክ ሊቀ ጳጳስ በኢትዮጵያ ላይ እንዲፈስ የተዘጋጀውን የመርዝ ጋዝና ሌላውን መሣሪያ ሁሉ ባርከው ጦርነቱን ሲፈቅዱ፣ ከስዊዲኑ ጋዜጣ ከአሌክሳንድሪያ በስተቀር አንዳች እንዳልተነፈሱ ሁሉ፣ ጣልያን በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ስለሚያካሄደው ጭፍጨፋ አንዳች አልተናገሩም። እንዲያውም የዓለምን ጀሮ የሚያደነቁሩት የጣልያን ወረራ እንደተቃና አዘውትረው በመግለጽ ነበር።

ንጉሠ ነገሥቱ ከለንደን ወደ ጀኔቭ በመሄድ ሰኔ 23 ቀን 1928 ዓ.ም የኢትዮጵያን አቤቱታ ለዓለም መንግሥታት ማኅበር አቀረቡ። ንግግር ያደረጉት በአማርኛ ቋንቋ ነበር። ንግግራቸው ወዲያው በአንግሊዝኛና በፈረንሣይኛ ቋንቋ እየተተረጐመ ለጉባዔው ተሰማ። ንጉሠ ነገሥቱ በዚህ ንግግራቸው በኢትዮጵያ የተካሄደውን በደልና በሕዝብ ላይ የደረሰውን አልቂት ለጉባዔው በቂ በሆነ አገላለጽ አስረዱ። ኢጣልያ በአይሮፕላኖችዋ ላይ የኢፕሪት መርዝ የሚረጭ መኪና አዘጋጅታ፣ ሰፊ በሆነ አገር ላይ ሞት

የሚያመጣ ረቂቅ ዝናም እንዳወረደችበት ገለጹ። ዋና የጦር መሣሪያ ያደረገችውም ይህንኑ እንደሆነ አስታወቁ። የመርዙ ዝናም የዘነበበትን ውሃ የጠጡ፣ መርዙ የነካውን ምግብ የተመገቡ ሰዎችም ከብቶችም በታላቅ ሥቃይ እንደሰቀቁ አስታወቁ።



ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በጄኔቭ ታሪካዊውን ንግግር ሊያደርጉ።

መስከረም 23 ቀን 1928 ዓ.ም ጀኔቭ የተቀመጠው የአሥራ ሦስት አገሮች ኮሚቴ "የኢጣልያ መንግሥት የማኅበሩን ውል ቃል ማፍረሱንና አጥቂ መሆኑን" እንደ አረጋገጠ ለጉባዔው አስታወሰ። ማኅበሩ "...ከሕግ ተሳልፎ የሚሠራ ሥራ እንዲፈረስ፣ በማኅበሩ የተጸፈው ቃል ሁሉ እንዲፈጸም እናደርጋለን" ተብሎ በጥቅምት ወር 1928 ዓ.ም ቃል ገብቶላቸው የነበረውን ጠቀሱ። መሣሪያ እንዳይገዙ መከልከላቸውን አወሱ። በማኅበሩ ደንብ "መንግሥታት እየተባበሩ በመረዳዳት ጸጥታ እንዳይጠፋ ያደርጋሉ የተባለው የአፈጻጸሙ ትርጓሜ ምን ይሆን?" ብለው ጠየቁ። መልስ የሰጠ አልነበረም። በመጨረሻም "...ከእግዚአብሔር መንግሥት በስተቀር የፍጡር መንግሥት ሁሉ አንዱ ከአንዱ አይበልጥም ...እግዚአብሔርና ታሪክ ለምትሰጡት ፍርድ ምስክር ሆነው ይመለከታሉ..." አሉ። የኢትዮጵያ መንግሥትና ሕዝብ በኃይል የተደረገባቸውን ነገር አለመቀበላቸውን፣ ሥርዓት እንዲሰፍን፣ የመንግሥታት ማኅበር ውል እንዲከበር፣ የሚገባቸው ሥልጣንና ግዛት እንዲመለስላቸው የሚቻላቸውን ሁሉ እንደሚያደርጉ ገለጹ። በኢትዮጵያ የደረሰባት በሌሎች ታናናሽ መንግሥታት እንደሚደርስ አስጠንቅቀው "...የኢትዮጵያ ነፃነት እንዳይጠፋ፣ ግዛትዋም እንዲከበር ምን ዓይነት ዕርዳታ ለማድረግ አስባችኋል?" ብለው በመጠየቅ ንግግራቸውን ደመደሙ።[2]

የንጉሠ ነገሥቱ ንግግር የዓለምን ሕዝብ ጎሊና በዘበዘ። በዓለም ጋዜጦችም ተስተጋባ። እውነትን የያዘና ለትክክለኛ ፍርድ የቀረበ ነበር። ለታናናሽም ለታላላቅም መንግሥታት ምክር የሰጠ ነበር። ነገር ግን የዓለም መንግሥታት አላደመጡም። ጀሮዎቻቸው በጸም ተሞልተው ነበርና።

ሙሶሊኒ የኃይል ሥራ ኢትዮጵያን ለመግዛት እንደ አላስቻሰው፣ የዲፕሎማሲውም ጉዳይ እንደከበደው በተገነዘበ ጊዜ ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ጋር የምሥጢር ንግግር ከፈተ። ለንደን ተጽዕኖ እንዲያደርግባቸው፣ ፓሪስ ያለው አምባሳደሩ ንጉሠ ነገሥቱ ሥልጣናቸውን ለመልቀቅ እንደተስማሙ አድርጎ አወራ። መሐመድ ኢክሪም ሪዛ የሚባል የግብፅ መሥፍንና አባ ግይሪል ሲ.ማርቲንጊል የተባለ የካቶሊክ ሲቅ ጳጳሱን በመወከል ከጉዳይ ገቡ። የሙሶሊኒ ሃሳብ መኖሪያ ቤት ገዝቶ በመስጠት እና አሥር ሚሊዮን ሊሬ /አንድ ሚሊዮን ፓውንድ/ በመክፈል የሥልጣን መልቀቂያ ውል አስፈርሞ ለመገላገል ነበር።[3] ነገር ግን ንጉሠ ነገሥቱ አልተበገሩም። "እኔ ላገሬና ለሕዝቤ ፍርድ ለመጠየቅ መጣሁ እንጂ፣ ሀገሬን ለመሸጥ አይደለም። የኢትዮጵያ ታሪክ በኢትዮጵያውያን ደም በተነከረ ጊዜ አያድፍም" አሉ። የእንግሊዝ ሊቀ ጳጳስ ሐውስ ኦፍ ሎርድስ በሚባለው ምክር ቤት ግንቦት 18 ቀን 1929 ዓ.ም ተገኝተው የንጉሠ ነገሥቱን ሃሳብ በመደገፍ ንግግር አደረጉ። ምክር ቤቱም የኢጣልያን ይዞታ ሳያውቅ ቀረ።[4] በዚህ አደራረግ ንጉሠ ነገሥቱ ኢትዮጵያን ክውርደት፣ ኢትዮጵያውያንን ከጥፋት አዳኑ።

ጣልያን ከጀርመን ጋር ወዳጅነትዋን ቀጠለች። ሁለቱ አገሮች በነገሥታት ይተዳደሩ በነበረ ጊዜ ተቀናቃኝነትና ለጠላትነት የሚያበቃ የጥቅም ግጭት ነበሩአቸው። ነገር ግን ፋሺዝምና ናዚዝም ከሰፈኑ በኋላ ከሚያጋጩአቸው ይልቅ የሚያፋቅሩአቸው ጉዳዮች በረከቱ። ለሂትለር ኢጣልያ በመጀመሪያው የዓለም ጦርነት ጊዜ በጀርመን ላይ ክፈጸመችው ክህደት ይልቅ፣ በመጭው ጦርነት የምትሰጠው ድጋፍ የሚበልጥ ሆኖ ታየው። ክህደት ለጣልያን የባህርይ ጉዳይ መሆኑን አልተገነዘበም። ሙሶሊኒና ሂትለር ስለዚህ ክህደት ቀደም ብሎ በሕዝብ መንፈስ ሠርጾ የነበረውን ስሜት ለመፋቅ ልዩ ጥረት አደረጉ። ሥልጣን በመያዝ ሙሶሊኒ ይቀድመው ነበርና ሂትለር ክብር ሰጠው። ጀርመንን እንዲጐበኝ ጋበዘው። በዚህም መሰረት ሙሶሊኒ መስከረም 14 ቀን 1930 ዓ.ም /ሴፕቴምበር 24 ቀን 1938/ በርሊን ሄደ። ሁለቱ መሪዎች ሦስት ሚሊዮን የጀርመን ወታደር በተሰለፈበት አደባባይ ላይ ቆመው ንግግር አደረጉ። ሙሶሊኒ በመካከላቸው የተገኘው የአንድ አብዮታዊ ሕዝብ መሪ በመሆኑ እንደሆነና፣ የፋሽስትን አብዮት ከናዚ አብዮት ጋር በጥብቅ እንዲቆራኝ ለማድረግ መሆኑን ገለጸ። ብዛታቸው እስከ አንድ መቶ አሥራ አምስት ሚሊዮን የሚደርሰው የጣልያንና የጀርመን ሕዝቦች ጠላቶቻቸውን አሸንፈው ዓለምን በአዲስ ሕግ ማስተዳደር እንደሚችሉ አስገነዘቡ። ሕዝቡም አመነ።



ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በጄኔቭ ታሪካዊውን ንግግር ሲያደርጉ።

ሞሶሊኒ ብድር ለመመለስ ሂትለርን ጋበዘው። ሂትለር ደግሞ ሚያዝያ 24 ቀን 1930 ዓ.ም /ሜይ 2 ቀን 1938/ ኢጣልያን ለመጉብኘት ሮም ገባ። ነገር ግን የሮሙ ጉብኝት እንደ በርሊኑ ለሁለቱ ወንበዴዎች መፈንጫ ነፃ አልተለቀቀም። የኢጣልያ ንጉሥ ሣልሣዊ ኢማኑኤል በርዕሰ ብሔርነቱ ሂትለርን ተቀብሎ ኩይሪርሲ በተባለው ቤተ መንግሥቱ አስተናገደው። ሙሶሊኒ በገዛ ግብግቡው ሁለተኛ ሰው ሆነ። በገዛ ዳቦዬ ልብ ልቡን አጣሁት እንዲሉ። ሂትለርን ለማነጋገር የቻለው በጉብኝቱ መጨረሻ ጊዜ ብቻ ነበር።[5] ሆኖም ጉብኝቱ ዓላማውን አልሳተም። በሁለቱ መንግሥታት መካከል ትብብር እንዲፈጠር የሚጠይቁ ብዙ ጉዳዮች በንግግሩ ወቅት ተከሰቱ። በጀርመን በኩል በቬርሳይ ቤተ መንግሥት በአንደኛው የዓለም ጦርነት በድል አድራጊዎቹ መንግሥታት አስገዳጅነት የተፈረመው ውል እንዲፈርስ ከፍተኛ ፍላጐት ነበር። ይህ ውል የኢጣልያን የግዛት ማስፋፋት ጥማት አላረካም ነበርና በመፍረሱ መስማማት አላዳገተም።

የቬርሳይ ስምምነት የመጀመሪያው የዓለም ጦርነት አክትሞ የተዘጋበት የመሆኑን ያህል፣ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት የተከፈተበት ቁልፍ ስለሆነ ዝርዝሩን መመልከት ብልህነት ይሆናል። ይህ ውል ከባድ የጦር ካሣ በጀርመን ላይ ጣለ። አከፋፈሉም በገንዘብ እንዲሆን ተደረገ። ይህ ሁኔታ የጀርመንን ኢኮኖሚ ገደል ለቀቀው። የጀርመንን ሕዝብ አስመርሮ የሂትለር መሣሪያ እንዲሆን አደረገው። ዳንዚንግ የተባለችውን ከተማ ከጀርመን ወደ ፖላንድ አዞሩአት። በአፍሪካም የነበሩት የጀርመን ቅኝ ግዛቶች ነፃነት በማግኘት ፈንታ፣ ከጀርመን ተነጥቀው ታንዛንያና ናምቢያ ለእንግሊዝ፣ ቤኒንና ቶጐ ለፈረንሣይ ተሰጡ። የእነዚህ ሁኔታዎች መስተካከል ለጀርመን አስፈላጊ ነበር። በጣልያን በኩል ደግሞ አልባኒያ ወደ ኢጣልያ አለመጠቃለልዋ፣ ናይሥና ሣቮይ የተባሉት ግዛቶች በፈረንሣይ እጅ መቆየታቸው ቁጭት ፈጠረ። ለዚህ ሁሉ ቅሬታ መቅረፊያና ሁለቱ መንግሥታት ለሚያደርጉት ትብብር መነሻው፣ ኢጣልያ በኢትዮጵያ ላይ ያላትን ገዥነት ጀርመን የማወቅዋ ጉዳይ ሆነ። ስለዚህ የኢጣልያ ንጉሥ ስለሙሶሊኒና ሂትለር ስምምነት አንዳች ለማለት አልቻለም።

ሁኔታው አስፈሪ ሆነ። እንግሊዞች ጣልያንን ማባበል ያዙ። ሃሳባቸው ሊሆን ከእነሱ እንድትሆን፣ ካልሆነም ገለልተኛ እንድትሆን ነው። በዚህም መሰረት ሚያዝያ 8 ቀን 1931 ዓ.ም ስምምነት ተፈራረሙ። ግብፅም ከስምምነቱ ገባች። መታረቂያዋ ኢትዮጵያ ነበረች። እንግሊዝና ግብፅ የሱዳን ጥምር ገዥዎች እንደሆኑ፣ ሱዳን ደግሞ ከኢጣልያ የምሥራቅ አፍሪቃ ቅኝ ግዛት አዋሳኝ እንደሆነች በውሉ ተንጸባረቀ። ዋናው ጉዳይ "እንግሊዝ በዓለም መንግሥታት ማኅበር ላይ የኢትዮጵያን ሁኔታ ትጨርሳለች" የሚለው ቃል ነበር። እውነትም እንግሊዝ ኢጣልያ ኢትዮጵያን በመያዝዋ ረገድ፣

መንግሥታት የየበኩላቸውን እርምጃ ቢወስዱ እንደማትቃወም በማኅበሩ ጉባዔ ላይ አስታወቀች። እርስዋ ራስዋም የኢትዮጵያን በኢጣልያ መያዝ አወቀች።[6]

ነገር ግን የኢጣልያ፣ የጀርመንና የጃፓን ወዳጅነት ዳበረ። ወደ ጓደኝነትም ፈጥኖ ተሸጋገረ። ሙሶሊኒ በኢትዮጵያ ላይ ያለውን ይዞታ ካላወቁለት፣ ማናቸውንም የዓለም ማኅበር የሚያቀርበውን ሃሳብ እንደማይቀበል አስታወቀ። ጀርመን ከአብሰባዎች መቅረት አብዝታ ነበርና፣ ጀርመን ቦማትካፈልበት በማናቸውም ስብሰባ ኢጣልያ እንዳትገኝ አደረገ። በወቅቱ በእስፔን ሀገር ጦርነት በመካሄድ ላይ ስለነበር፣ ጣልቃ መግባት ወደ አዲስ ሁከት ያመራል አለ። ጃፓን በቻይና ላይ በምትፈጽመው ሁሉ ኢጣልያ እንደምትደግፋት አስታወቀ። እነዚህን ሃሳቦቹን ጽፎና ፈርሞ በሕዝብ መገናኛ እንዲገለጹ አደረገ።[7] እንዲሁ እንዲሁ ብለው ሦስቱ መንግሥታት ማለትም ጣልያን፣ ጀርመንና ጃፓን የዓለም ማኅበርን ከነጭራሹ ለቅቀው ወጡ።

ሂትለር የጦር ክንዱን አንስቶ ታናናሽ ሀገሮችን የመዋጥ ሥራውን ነሐሴ 25 ቀን 1931 ዓ.ም /ሴፕተምበር 1 ቀን 1938/ ጀመረ። ኢትዮጵያ ጣልያንን የተቋቋመችበትን ሩቡን ያህል የተቋቋመ የለም። መሪዎቹም አንድ በአንድ እየበረሩ እንግሊዝ አገር ገቡ እንጂ ለዓለም ማኅበር ስሞታ አላቀረቡም። ለንደን በየዕለቱ በአይሮፕላንና በበራሪ ፈንጂዎች ትደበደብ ጀመር። ዓለሙ ተናወጠ። ሙሶሊኒ ከማንኛው ወገን እንደሚሆን ጨነቀው።

ጀርመን መላውን አውሮፓን ከያዘችና ለንደንን በአይሮፕላን እንጀትዋ እስኪርስ በመደብደብ እንግሊዝን ከአስደነገጠች በኋላ፣ ጦርነቱ እንዲቆምና የሰላም ስምምነት እንዲደረግ ጠየቀች። ይህ ጥያቄ ተቀባይነት አግኝቶ ቢሆን ኖሮ፣ የዓለም ካርታና የፖለቲካ አቅጣጫ ይለወጥ ነበር። ነገር ግን እንግሊዝ ጥቃትዋን ጠጥታ አይደረግም አለች። "ድል እስክምናገኝ ድረስ ጦርነቱ ይቀጥላል እንጂ አይቆምም" አለች። ቆራጥ መንግሥትና ጠንካራ ሕዝብ እንዲህ ነው። እንደ አለችውም ጦርነቱ ቀጠለ። ዓለም አሁን ያለበትን ገጽታ የያዘበት በር ተከፈተ። የኢትዮጵያም ነፃነት አብሮ ተስፋ ፈነጠቀ።

ጀርመን እያየለ ሲሄድ በፈረንሣይ አገር በማርሻል ፔቴ የሚመራ መንግሥት ተቋቋመ። አዲሱ መንግሥት ከጀርመን መንግሥት ጋር ስምምነት ተፈራረመ። በዚህ ስምምነት መሠረት የፈረንሣይ የምድር፣ የባሕርና የአየር ኃይል፣ ወደቦችም ጭምር በጀርመን እጅ ሆኑ።

ከእንግሊዝ ወይም ከጀርመን መሆኑን ሙሶሊኒ በገሐድ እንዲያስታውቅ ሂትለር አስጨነቀው። አሥራ አራቱ ሚኒስትሮች ከሁለት ተከፈሉ። ሰባቱ፣ አማቹን ክንትቺያኖን ጨምሮ፣ ከእንግሊዝ እንሁን አሉ። ሌሎች ሰባት ከጀርመን መሆንን መረጡ። ስለዚህ ሙሶሊኒ ራሱ መወሰን ግድ ሆነበት። ምክንያቶቹ ጀርመን ጉረቤታችን ነው፣ የርዕዮተ ዓለም ጓደኞችን ነው፣ በትግላችን ሁሉ ደግፎናል፣ የኃይል ሚዛን አግኝቶአል። በቅርቡ ደግሞ የአውቶሚክንም ምሥጢር ያገኛል የሚሉ ነበሩ። ተቃዋሚዎች ሚኒስትሮች

ተቃውሞአቸውን ስለአጠነከሩበት ሰባቱንም፣ አማቹን ጭምር፣ አስገደላቸው። ልጁ ተናድዳ ሄዳ በባልዋ እጅ የነበሩትን ምሥጢሮች በስዊስ በኩል አሣልፋ ለእንግሊዞች ሰጠችበት።[8] በዚህ ዓይነት ኢጣልያ ከጀርመን ጐን ለመቆም ስለወሰነች፣ ይህ ውል ለእሷም የሚጸና ሆነና የጅቡቲ ወደብና እስከ አዲስ አበባ ያለው የባቡር ሐዲድ ጭምር ከኢጣልያ እጅ ገባ።[9] የጀርመንና የጣልያን ጠላት የሆነ አገር ዜጋ ይባረር የሚል ሕግ ስለወጣ፣ ፓሪስ የነበረው የኢትዮጵያ ኤምባሲ ተዘጋ። ሠራተኞቹም በማርሴይ በኩል ወጡ።[10]

ኢጣልያ ከጀርመን ጐን መቆምዋን ስትገልጽ እንግሊዝ ፊጣን እርምጃ ወሰደች። ጦርነቱን ከአውሮፓ ወደ አፍሪካ አዞረችው። ቀዳማዊ ኃይለሥላሴን ከለንደን ካርቱም እምጥታ በጐጃም በኩል ጐጃም እንዲዝሙ አደረገች። የምሥራቅ አፍሪካ ጦር ከሞቃድሾና ከበርበራ ተነስቶ አዲስ አበባ እንዲገባ አሰለፈች። ሌላ ጦር ከካርቱም በከረን አልፎ አሥመራ በመግባት ቀይ ባሕርን እጅዋ ለማድረግ ተነሣች።

አሜሪካን ገለልተኝነትዋን አጠበቀች። ከጦርነቱ ለመግባት አልከጀለችም። በፕሬዚዳንት ዊልሰን የደረሰው እንዳይደርስባቸው ስለሰጉ ፕሬዚዳንት ሩዝቬልት አንዳች ከማድረግ ይቆጠቡ እንጂ፣ የጦርነቱን ባሕርይ ለሕዝባቸው ከማስረዳት አልቦዘኑም።[11] ለነፃነታቸው የሚዋጉትን ሕዝቦች መርዳት እንደሚገባ በማስረዳት ቅስቀሳ አደረጉ። ያዳመጣቸው ግን የለም። አዲሱ የእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስተር ሰር አንቶኒ ኤደን ስለጦርነቱ ለአሜሪካን ምክር ቤት ንግግር ቢያደርጉም፣ የጦር መሣሪያ ዕርዳታ ከማግኘት በስተቀር ሕዝቡን ወደ ጦርነቱ ለማስገባት አልቻሉም። ጦርነቱ ለአሜሪካንም ጤና እንደማይሰጥ የተናገሩት ትንቢት እስኪደርስ በትዕግስት መጠበቅ ነበረባቸው።

የአውሮፓና የአሜሪካ ሁኔታ በእንዲህ እንዳለ ከሩቅ ምሥራቅ ጮርናና ድምጽ ተሰማ። የጃፓን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በጥር ወር 1933 ዓ.ም ባደረገው ንግግር "...አሜሪካ ጃፓንን ስለምትረዳ በጃፓንና በአሜሪካ መካከል ሰላምና ፍቅር ሊኖር አይችልም..." አለ። ከፓስፊክ ውቅያኖስ ምዕራቡ ክፍል በጃፓን ሥልጣን ሥር ሊሆን እንደሚገባ አስታወቀ። የአሜሪካን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርም ወዲያው መልስ ሰጡ። "ከጃፓን ጋር ሰላም አይገኝም..." አሉ። ኢትዮጵያን ያቃጠላት አሳት ኢትዮጵያን መልሶ እንደሚፈውሳት ትንቢት ተናገሩ።[11] በዚያን ሰዓት ኢትዮጵያን ነፃ ለማውጣት ጦርነቱ በአራቱም የሀገሪቱ ማዕዘን ተቀጣጥሎ ነበርና ትንቢታቸው እውን ነበር። ጃፓን ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ፐርል የተባለውን የአሜሪካን ወደብ በድንገት በአይሮፕላን ደብድባ፣ በአሜሪካን የባህር ኃይል ላይ ከፍተኛ ጉዳት አደረሰች። አሜሪካንም ከጦርነቱ ሰተት ብላ ገባች።

ኢትዮጵያ ከነገር አሸክላ ሳትወድቅ በኢጣልያ ከደረሰባት ወረራ ነፃ ወጣች። አውሮፓ የኢትዮጵያን ነፃነት በሀፍረት መልሶ አወቀ። ቀዳማዊ

ኃይለሥላሴ በጀኔቫ የተናገሩት ትንቢት በትክክል ተፈፀመ። አድላዊ ዳኛ የሚያርስበትን ፍዳ ተቀበሉ። ሙሶሊኒ ወልወል ባቀጣጠለው እሳት መላው ዓለም ተጠበሰ።

ማጣቀሻ ፅሑፎች

1. ተክለፃድቅ መኩሪያ፣ *የኢትዮጵያ ታሪክ ከአፄ ቴምድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ*፣ ገጽ 211።
2. ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፣ *ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ 1ኛ መጽሐፍ*፣ ገጽ 178-182፣ ገጽ 253-264።
3. Alberto Sabacchi, *Ethiopia under Mussolin*, pp. 221-126.
4. ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፣ *ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ 2ኛ መጽሐፍ*፣ ገጽ 81-93።
5. Stanley Cooperman, *Mussolini*, pp.109-110.
6. ሕይወት ጎዳሩ፣ *ያቺ ቀን ተረሣች*፣ ገጽ 73።
7. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 326-349።
8. Mussolini's Twilight.
9. ሕይወት ጎዳሩ፣ ገጽ 354-362።
10. አክሊሉ ሀብተወልድ ለመርማሪ ኮሚሽን ያቀረቡት ጽሑፍ፣ ገጽ 12-16።
11. ሕይወት ጎዳሩ፣ ገጽ 389-396።

ምዕራፍ ሃምሣ ሁለት
የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የድል ጉዞ

የኢጣልያ የፖለቲካ አቅዋም እያጠራጠራቸው በሄደ ቁጥር፣ እንግሊዞች የመጠባበቂያ ዕቅድ ማዘጋጀት ያዙ። ካይሮ በነበራቸው ጦር ዕዝ ውስጥ ቢያስፈልግ የጣልያንን የቅኝ ግዛት ማፈራረስ የሚቻልበት ጉዳይ ጥናት ተደረገበት። አንዱ በሊቢያ በኩል ሲሆን፣ ሌላው በምሥራቅ አፍሪካ ላይ ያተኮረ ነበር። ከምሥራቅ አፍሪካ ቅኝ ግዛት አገሮች፣ ዋናዋ ኢትዮጵያ ሆነች።

በዚህ ጥናት በብርቱ ከታሰበባቸው ጉዳዮች አንዱ የመሪ ጉዳይ ነበር። ፈረንሣዮች መጠነኛ ቅሬታ ቢያሳዩም ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መሪነት ሌላ ተወዳዳሪ ሳይገኝለት ቀረ። ራስ አበበን ለመደገፍ ቢሞክር በኢትዮጵያ ውስጥ የርስበርስ ጦርነት የሚቀሰቅስ ሆነ። ስለዚህ ጣልያን ከጀርመን ጉን ከቆመች ቀዳማዊ ኃይለሥላሴን ይዞ ኢትዮጵያ ላይ ጦርነት ከመክፈት በስተቀር ሌላ አማራጭ ሳይገኝ ቀረ።

እንግሊዞች በዚህ ላይ እንደአሉ፣ ሙሶሊኒ ሰኔ 3 ቀን 1932 ዓ.ም ከሂትለር ጉን ለመቆም ወሰነ። ወጥመዳቸው ስለያዘላቸው እንግሊዞች ፈጣን እርምጃ ወሰዱ። በእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ውስጥ የኢትዮጵያ ጉዳይ ኃላፊ የነበረው ሚስተር ቶሚ ቶምሰን፣ ንጉሠ ነገሥቱ ባለሥልጣኖችን የሚያነጋግሩበት መንገድ አዘጋጀ። በታላቁ ምዕራባዊ ሆቴል ንግግር ከተደረገ በኋላ፣ ንጉሠ ነገሥቱ ወደ ሱዳን የሚሄዱበት መንገድ ተቀየሰ።

ንጉሠ ነገሥቱ ኢትዮጵያን ነፃ የማውጣት ጉዞአቸውን ለመጀመር ከእንግሊዝ አገር ሰኔ 17 ቀን 1932 ዓ.ም /ጁን 24 ቀን 1940/ ከሌሊቱ በ4 ሰዓት ከለንደን ተነሱ። ጉዞአቸው የጦርም የነገርም ሆነባቸው። ጉዞው በአይሮፕላን ሆኖ በረራው በምሥጢር ነበር። አይሮፕላን ነጂው እንኪን ከሚሄድበት አገር በስተቀር ስለመነገደኞቹ የሚያውቀው ነገር አልነበረውም። አይሮፕላኑም በውሃ ላይ ተንሳፋፊ ነበር። አይሮፕላኑ በፈረንሣይ አየር ላይ አቋርጦ ማልታ ደሴት ላይ ማረፍ ነበረበት። የጀርመን አይሮፕላኖች የፈረንሣይ አገርን፣ የጣልያን አይሮፕላኖች ደግሞ የሜዲቴራኒያን ባህርን አየር በመቆጣጠር ላይ ነበሩ። በተአምር አንዳቸውም ሳያዩአቸው ቀርተው ማልታ ደሴት ላይ አረፉ። ሌላው አስገራሚ ነገር የማልታ አይሮፕላን ማረፊያ ከጥቂት ጊዜ በፊት በጣልያን አይሮፕላኖች ተደብድቦ መገኘቱ ነው። በቶሎ ነዳጅ ሞልተው በረራቸውን ወደ ግብፅ ቀጠሉ። በማግስቱ ከቀትር በኋላ አስክንድርያ ገቡ። ነገር ግን በግብፅ የነበሩ ባለሥልጣኖችን ለማነጋገር ሁኔታው አላመቸም። በማግስቱ የበረራው ጉዞአቸውን ቀጥለው ሰኔ 19 ቀን

ከሱዳንና ከግብፅ ጠረፍ ላይ ከምትገኝ ዋዲ ሐይፋ ከተባለች ትንሽ ከተማ ገቡ።

የንጉሠ ነገሥቱ ጉዞ በምሥጢር በመሆኑ ባለሥልጣኖች አይሮፕላኑ ከአስክንድሪያ አስኪነሳ አልተገለጸላቸውም ነበር። በሰሙ ጊዜ ደነገጡ። አንቀበልም ለማለት ቃጣቸው። ግልጹ ምክንያታቸው ከኢጣልያ ምሥራቅ አፍሪካ ጋር ያጋጨናል የሚል ሲሆን፣ ንጉሠ ነገሥቱን ያለመቀበል ሌላ ምሥጢር ሳይኖርበት አልቀረም። ከእንግሊዝ አገር ይዞአቸው ከመጣው ቡድን ጋር ንግግር ተደርጐ ከስምምነት እስኪደረስ ድረስ ንጉሠ ነገሥቱ ዋዲ ሐይፋ መቆየት ነበረባቸው።

ከዚያ እንደ አሉ እንግሊዞች አንድ ዓይነት ውል እንዲፈርሙላቸው ለማድረግ ከጀሉ። ጠርጣራው ንጉሠ ነገሥት ከመካንንቶቻቸው ጋር መክረው እንደሚፈርሙ ገለጹ። መካንንቱን ከየአሉበት ሰብስበው አመጡላቸው፣ ካርቱም ከተማም አስገቡአቸው። ካርቱም ሲደርሱ ደግሞ ስለ ጦር እንጂ ስለ ፖለቲካ ጉዳይ የማይነጋገሩ ሆኑ። ኬንያ ያሰው ስደተኛ አንዋጋም ብሏል አሉዋቸው። ከለንደን ጌታ ሎሬንዞ ታዕዛዝን ልከው ችግር አለመኖሩን አረጋገጡ። እንግሊዞች በደቡብ ኢትዮጵያ ብጥብጥ ለማስነሣት ያዘጋጁትን ብሮክ ሳህርስት በተባለ ኩሎኔል የሚመራ አንድ ቡድን አንቀሳቀሱ። ንጉሠ ነገሥቱ እንዲያነጋግሩት ቢጠየቁ አላደርገውም አሉ። ንግግር ቡሀሰይ ስለ ጦርነቱ ጉዳይ ብቻ እንዲሆን፣ የፖለቲካ ጉዳይ ንግግር የሚደረገው አዲስ አበባ ከገቡ ቡኋላ እንዲሆን አደረጉ። እነዚህ ሥራዎች ኢትዮጵያን ከእንግሊዝ የነገር ጭጉጉት አላቀቋአት።

ንጉሠ ነገሥቱ የመጀመሪያውን የጦር አመራር በዋዲ ሐይፋ ሰጡ። የመጀመሪያው ዙር ንግግር ሰኔ 21 ቀን 1932 ዓ.ም ተጀመረ። እንግሊዞች በእጃቸው ያሰው መሣሪያ እጅግ አነስተኛ መሆኑን ገለጹ። ሊገኝ የሚችለው 176,000 ጠመንጃ፣ 4 ሞርታሮች፣ 400 መትረየስ፣ 60 ጸረ ታንክና 45 ከጣልያኖች የተማረኩ ታንኮች እንደሆኑ ተገለጸ። ይህ አካሄድ በአንድ ወገን የተስፋ ጭላንጭል አሳይቶ በሌላ ወገን ይሆንን በመሰለ ተስፋ አስቆራጭ ሁኔታ ንጉሠ ነገሥቱን አንዳች ውል ለማስፈረም ሳይሆን አልቀረም። ነገር ግን ንጉሠ ነገሥቱ ከዚች ውየመድ አልወደቁም። በአየሩሳሌም፣ በጁቡቲ፣ በከሰላ፣ በኬንያና በሌሎችም በታዎች የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ስደተኞች በቅድሚያ እንዲመጡላቸው ጠየቁ። ይሆንላቸው መስሎአቸው እንግሊዞች ጥያቄአቸውን ፈጸሙላቸው። አሳቸውንም ሰኔ 25 ቀን በመኪና ወደ ካርቱም ወስደው ከካርቱም ሃያ ስምንት ማይልስ ከሚርቅ በነጭ ዓባይ አጠገብ ከምትገኝ ደቦል አውልያ ከምትባል ቦታ እንዲቆዩ አደረጉ።

ንጉሠ ነገሥቱ ሱዳን እንደገቡ የመጀመሪያው ሥራ መምጣታቸው በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ እንዲታወቅ ማድረግ ሆነ። በዚህ ጉዳይ እንግሊዞች ተባበሩ። ንጉሠ ነገሥቱም በካርቱም ሬዲዮ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ

መልእክት አስተላለፉ። የመጀመሪያው ቃል "ይህ የምትሰሙት የእኔ የንጉሠ ነገሥታችሁ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ድምፅ ነው..." በማለት ጀምሮ፣ የተመኙትን ዕርዳታ አግኝተው የደረሱለት መሆኑን የሚያበሥር ነበር። በተጨማሪም የእንግሊዝና የፈረንሣይ አይሮፕላኖች በኢትዮጵያ አየር ላይ እንደሚያንጎራብቡ ገልጸው፣ የጣልያን አገረኛ ወታደር ከኢትዮጵያ ጀግኖች እንደማያልፍ አሰረዱ። ባንዶችን በተመለከተ "...ከእንግዲህ ወዲህ የጣልያን መሣሪያ በመሆን አገራችሁን የምትበድሉ ለዘራችሁ ከታሪካችሁ የማይፋት እርግማን ታቆያላችሁ..." አሉ።

በሐምሌ 1 ቀን 1932 የመጀመሪያው አዋጅ ተጽፎ በአይሮፕላን ተበተነ። አዋጁ ብዙ ታላላቅ ጉዳዮችን ያካተተ ሆኖ ለኢትዮጵያ ሕዝብና ሽማምንት፣ ለኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች፣ ለሌርትራውያንና ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የተላለፈ ነበር። አጠቃላይ ይዘቱ "...የምሕረት ፊቱን ወደ እኛ ስለመለሰ እግዚአብሔርን እናመሰግናለን..." ይልና ለእያንዳንዱ ወገን መመሪያ ይሰጣል። "...በአፋችሁም ለጠላት መሣሪያ አትሁኑ። ...ስለ ሀገራችሁ ጥቅም በሥራ በርቱ። ...ከመረብ ወዲያ ወይም ወዲህ ያላችሁ ሁሉ ከኢትዮጵያውያን ወንድሞቻችሁ ጋር ተባበሩ። ...ነፃና ሀብታም በሆነች በአንዲት ኢትዮጵያ ውስጥ ነፃነት፣ እኩልነት፣ አንድነትና እውቀት ያለው ሕዝብ ሆናችሁ እንድትኖሩበት እንፈልጋለን። ...የጣልያንን ጦር ለመደምሰስና የኢትዮጵያን ሙሉ ነፃነት መልሶ ለማቋቋም ነው እንጂ፣ እንግሊዞች በአገራችን የሚፈልጉብን ነገር የለም..." የሚል ነበር። በመጨረሻም የኢትዮጵያ ሕዝብ እንግሊዞችን በወዳጅነት እንዲቀበላቸው አደራ ነበረበት።

እንግሊዞች ከኢትዮጵያውያን ጋር በመሆን "ባንዲራችን" የሚል ሣምንታዊ ጋዜጣ በሱዳን አቋቋሙ። ከንጉሠ ነገሥቱ አዋጅ ጋር በተከታታይ እየታተመ በአይሮፕላን ተበተነ። አይሮፕላን ቢወድቅ ለነጂዎቹ መታወቂያ እንዲሆናቸው የተለየ ቅጂ በአይሮፕላኖቹ ውስጥ ለዘወትር እንዲቀመጥ ተደረገ። አዋጁ በትግርኛም ተተርጉሞ ተበተነ። ባንዲራችን የተባለው ጋዜጣ ለሃያ ስምንት ሣምንታት በተከታታይ ታትሞ ተበተነ። አዋጁና እነዚህ ጽሑፎች ቢበዛት መቱተናቸው የኢትዮጵያን ህዝብ ለአዲስ ትግል ቀስቀሰው።

ወደ ኢትዮጵያ ስለሚደረገው ጉዞ ምክር ሐምሌ 5 ቀን 1932 ዓ.ም በኢትዮጵያውያን መካከል፣ በንጉሠ ነገሥቱ ለብሳቢነት ተጀመረ። የወቅቱ አዲስ ነገር፣ የፈረንሣይ በጀርመን እጅ መውደቅ ነበር። በስብሰባው ላይ አጪጌ ንብረ ጊዮርጊስ /ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ/፣ ፊታውራሪ ብሩ ወልደገብርኤል፣ ደጃዝማች አበበ ዳምጠው፣ ደጃዝማች /ራስ/ አደፍርስው፣ አቶ /ፀሐፊ ታዕዛዝ/ ወልደጊዮርጊስ ወልደዮሐንስና አቶ /ብላቴን ጌታ/ ሉሬንዞ ታዕዛዝ ተገኝተው ነበር። አቶ /ብላቴን ጌታ/ ሉሬንዞ ታዕዛዝ ኢትዮጵያ ውስጥ በቆዩበት ጊዜ የተንዘበዙትን ካሳወቁና ቀደም ብሎ ከገባው የእንግሊዝ ጦር መሪ በኮሎኔል /ብርጋዲየር ጄነራል/ ሳንድፎርድ ሐምሌ 4 ቀን የተፃፈው ቃል

ከተሰማ በኋላ፣ በጉዳዩ ከእንግሊዝ ባለሥልጣኖች ጋር ንግግር ተወሰነ። አሁን ግን ጊዜው የተሰወጠ ነገር ስለአመጣ በጥቂት "መርምሮ እንዲመጣ ተቀርጦአል፣ በማለት ስብሰባውን ደመደሙ።[1]

ከእንግሊዙ የሱዳን አገረ ገዥ፣ ከሰር አስቲዋርት ሲመስ ጋር በቆይታ፣ በተሰይ ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር ሐምሌ 6 ቀን ንግግር አደረጉ። ንግግሩ እንግሊዞች እንደፈለጉት በፖለቲካ ጉዳይ ላይ ሳይሆን፣ ንጉሠ ነገሥቱ ባቀረቡት የጦር ጉዳይ አተኮረ። ስለጦርነቱ በተደረገው ንግግር ከእንግሊዞቹ ወገን የቀረበው መግለጫ ቀደም ብሎ በዋዲ ሐይፋ የተነገረውን መልሶ የሚያስተጋባ ከመሆኑ ጋር፣ የጣልያንንም የኃይል አቅዋም ያስረዳ ነበር። በጣልያን በኩል 900,000 ወታደር እንደ ተሰለፈ፣ ከዚሁ ውስጥ የሚበዛው ነጭ ሲሆን፣ የሠለጠኑም ባንዶች ከጠላት ጐን የተሠለፉ መሆናቸውን የሚያሰረዳ ነበር። በመሣሪያም ረገድ 200 አይሮፕላኖች እንደአሉና ጣቢያቸውም አዲስ አበባ፣ አሥመራ፣ ጉርአ፣ ጉንደርና ድሬዳዋ እንደሆነ ተገለጸ። የእንግሊዝ አይሮፕላኖች በጉንደርና በጉጃም ለሚገኙ አርበኞች ድጋፍ ለመስጠት ቦታ እንደሚርቃቸው ተነገረ። በሱዳንና በኢጣልያ ምሥራቅ አፍሪቃ ግዛት መካከል ያለውን 1200 ኪሎሜትር የወሰን ድንበር የሚጠብቁ 4,500 ሱዳናውያን ወታደሮች እንደ አሉ፣ የእንግሊዝ ወታደሮች 2,500 ብቻ እንደሆኑ ተገለጸ። ጀነራሉ ከሱዳን ወደ ኢትዮጵያ ስለሚገባው ጦር የሰጡት መግለጫ ቀድሞ በሠፊው ተዘጋጅቶ ነበር።

ከእንግሊዝ የሚገኘው ዕርዳታ 18,000 ጠመንጃ ብቻ መሆኑ በቁጥር ክታወቀ በኋላ፣ የኢትዮጵያ መኢንንት በንጉሠ ነገሥቱ ሰብሳቢነት ሐምሌ 7 ቀን ስብሰባ አደረጉ። አቶ /ብላቴን ጌታ/ ሉሬንዞ ታዕዛዝ "...ዓለም በጦርነት ስለተበጠበጠና ለእንግሊዝም ቢሆን ፍፃሜው ያልታወቀ ስለሆነ፣ የቀረን እዚህ ሆነን ከመጥፋት በአገራችን በኢትዮጵያ ገብቶ መሞት ነው..." ሲሉ ያቀረቡት ሃሳብ ተደግፎ ወደ ኢትዮጵያ ለመግባት ተወሰነ።[2] አንድ የኢትዮጵያና የእንግሊዝ ጥምር ቡድን ወደ ኢትዮጵያ እንዲገባ ተመደበ። በኢትዮጵያ በኩል አዛዥ /ደጃዝማች/ ከበደ ተሰማ ተመረጡ። በእንግሊዝ ወገን ኮሎኔል/ብርጋዴየር/ ሣንድፎርድ ሆኑ። እነሱም ፈጣን ዝግጅት ካደረጉ ቡኋላ ተንቀሳቅሰው መጠነኛ ጦር በመያዝ የሱዳንን ጠረፍ አቋርጠው ሐምሌ 25 ቀን 1932 ኢትዮጵያ ምድር ገቡ።

ሌላው ሥራ በውጭ አገር ያለውን የኢትዮጵያ ስደተኛ ማሰባሰብና ፈጣን ሥልጠና ሰጥቶ ሰጦርነት ማሰለፍ ሆነ። ስደተኞቹን ማስመጣት ቀላል አልሆነም። ካይሮ ከሚገኘው የእንግሊዝ ጦር አዛዥ ጀነራል ትዕዛዝ ማስተላለፍ አስፈለገ። ያም ተደርጐ ከኬንያ የእንግሊዝ ባለሥልጣኖች ተታውሞ ተነሣ። በአንድ ወገን ስደተኞቹ ለንጉሠ ነገሥቱ መዋጋት እንፈልግም ብለዋል ተባለ። በሌላ ወገን ደግሞ እንደምርኮኛ የሚቆጠሩ ስለሆነ እንደገና ከጦር ግንባር እንዳይገቡ የዓለም መንግሥታት ሕግ ይከላከላል

የሚል ሆነ። በመጨረሻ ደግሞ አንዋጋም ያሉት ኤርትራውያን ስደተኞች ናቸው ተባሉ። አቶ /ብላቴን ሎሬንሶ ታዕዛዝ ተልከው ጥቅምት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ሲ ደርሱ ሁሉም ነገር ተሰወጠ። አንዱም ወገን አንዋጋም አለማለቱ ስለተረጋገጠ አቶ /ብላቴን ጌታ/ ሎሬንሶ ታዕዛዝ ስደተኞቹ ከንጉሠ ነገሥቱ መጠራታቸውን ብቻ ጎዳር 3 ቀን ለኤርትራውያን ነገሩ። በኤርትራውያን መካከል ደስታ ሆነ። "...ለንጉሣችን ገብተን እንዳንዋጋ ከለከላችሁን፤ እንደ እንሰላም አሠራችሁን..." በማለት ብሶታቸውን ገለጹ። በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ጦር ግንባር 546 ኤርትራውያን ተሠለፉ።[3]

በምሥጢር ቁጥር 101 ወደ ኢትዮጵያ የተላከው ጦር ነሐሴ 14 ቀን ሠራቆ ደረሰ። ከዚያም በገደሪፍ፣ በደይካ፣ በወዲያ፣ በስሉል በጀምበርጌ ማሕደረ ሥላሴ ገባ። ከዚያም ጳጉሜን 4 ቀን 1932 ዓ.ም አቸፈር ገብቶ የጉጃምን አርበኞች ማስተባበር ያዘ።

የጣልያን መንግሥት በሱዳንና በሰሜን ሶማልያ ግንባር ጦር ከፈተ። አይሎም ጋላበትንና ከሰላን፣ እንደዚሁም በርባራን ያዘ። እነዚህን ቦታዎች መጠበቅ አስፈላጊ መሆኑ የኢትዮጵያ የጦር መኰንኖች አቅርበውት የነበረውን አስተያየት፤ የእንግሊዝ የጦር መኰንኖች ቦታዎቹ ለጦርነቱ አስፈላጊ አይደሉም በማለት የደረሱበት ድምዳሜ ትክክል አለመሆኑ ታውቀ። ጣልያኖች በአውሮፓ ጦር በመቀስቀስ አልባንያን ያዙ። በሰሜን አፍሪካም ክሲብያ ጦር አንቀሳቅሰው ከግብፅ ግዛት እስከ 150 ኪሎ ሜትር ድረስ ገቡተው ያዙ። ይህ ሁኔታ እንግሊዝን በማስቆጣት የኢትዮጵያን ነፃነት ፅድል ከፍ አደረገው።[4]

የእንግሊዝ መንግሥት ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ እንደ ገና ተቀባይነት የሚያገኙ አልመሰለውም ነበር። አመለካከታቸውን ሕዝባቸው ይቀበላቸው አይቀበላቸው፤ አርበኞች ይደግፉአቸው አይደግፉአቸው አይታወቅም የሚል አዝማሚያ የተከተለ ነበር። ዕርዳታም የሚሰጡአቸው አየመጠኑ ሆነ። ነገር ግን የንጉሠ ነገሥቱ በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት ብቻ ሳይሆን ተፈላጊነትም እንደ አላቸው በማስረዳ ተረጋገጠ። በአርበኞች መካከል "ንጉሠ ነገሥታችንን አምጡልን" የሚለው ወገን በዛ። ራስ ውብነህ ተሰማ የነጭ የነጭ ጣልያን ምን አለኝ ብለው ንግግር ሰብረው መውጣታቸው አንዱ ማስረጃ ነው።[5] ንጉሠ ነገሥቱም እንዲህ የማሰኙቱን ነገር በውስጥ አርበኞቻቸው በኩል ሳያካሄዱ አልቀሩም።

ጣልያኖች ደግሞ የተቃውሞ መቀስቀሻ ፕሮፓጋንዳቸውን አጠናከሩ። የጣልያን ፕሮፓጋንዳ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ወደ ሥልጣን ከተመለሱ ከእኛ ጋር የተባበረውን ሁሉ ይፈጃሉ። ጣልያኖች የፈጁት ሕዝብ ንጉሠ ነገሥቱ በመጡ ጊዜ ከሚፈጁት ጋር ሲመዛዘን ኢምንት እንደሚሆን የሚያስገነዝብ ሆነ። ንጉሠ ነገሥቱ የምህረት አዋጅ እንዲያወጡ ቢጠየቁ፤ ይህንን የመሰለ አዋጅ ከኢትዮጵያ ውጭ ባሉበት ጊዜ መስጠት እግባብ እንደማይሆን ገለጹ።[6] ጣልያኖች የእሳቸው ቃል በማስመሰል አንዳንድ ሹመት እንደሰጡ እያደረጉ

በአይሮፕላን አስበተኑ። ዓላማቸው እየተጠናከረ የመጣባቸውን የአርበኛውን አንድነት ለመበተን ነበር። ነገር ግን አድማጭ ሳያገኙ ቀሩ። የንጉሠ ነገሥቱ አቅዋም ይበልጡን ተጠናከረ።

መስከረም 17 ቀን 1933 እንደ ኢትዮጵያ ሥርዓት ክካርቱም የመስቀል የደመራ በዓል ተከበረ። ይህ የደመራ በዓል ከሌሎች ሁሉ የተለየ ነበር። የተለየ የሆነውም በሰው አገር የተደረገ ከመሆኑም በስተቀር ከኢትዮጵያ አርበኞች የንጉሠ ነገሥቱን በሕይወት መኖርና መምጣት በዓይናቸው አይተው እንዲያረጋግጡ ተልከው የተገኙበትና ከስደተኛውም የሚበዛው የተሰበሰበበት በመሆኑ ነበር። አጨዬ ገብረው ባርከው ንገሡ ነገሥቱ ደመራውን ባቀጣጠሉ ጊዜ በዚያ የነበሩ ኢትዮጵያውያን ልብ በሀገራቸው እንደገና በአዲስ ጋይ ነደደ።[7]

ነገር በእንዲህ እንደ አለ በካይሮ የእንግሊዝ ጦር አዛዥ የነበሩት ጀነራል ሚሸል ወደ ካርቱም መጡ። ንጉሠ ነገሥቱ የኢትዮጵያን ጉዳይ የሚዘረዝር ሰፊ ማስታወሻ አቀረቡላቸው። የማስታወሻው ይዘት በሦስት መልክ ይጠቃለላል። የመጀመሪያው ክፍል የተደረገላቸው ዕርዳታ በቂ አለመሆኑን ይዘረዝርና "...ይህንን ሁሉ መናገሬ ሲንሴር ካላቦራሲዮን እንደ ጉደለብኝ ለማስረዳት ነው።..." ይላል። ሁለተኛው ክፍል ደግሞ የታንክና የአይሮፕላን መምቻ መሣሪያ እንደሚያስፈልጋቸው ያስረዳል። ሦስተኛው የእሳቸውን ዓላማ የሚገልጽ ሆኖ "...የጦር ሠፈር አቁሜ ስለጦሩ የሚያስፈልገውን ነገር በቶሎ አያጣደፍሁ ማደራጀት አፈልጋለሁ። መንግሥታትንም ለማቆም ቆርጫለሁ..." የሚል ነበር። ነገር ግን ጀነራሉ የሰጡት መልስ ፀረ-ታንክም ሆነ፣ ፀረ-አይሮፕላን መሣሪያ ለኢትዮጵያ እንደማይገኝ የሚያስረዳ ሆነ። የሰጡትም ምክንያት "...ግብፅን፣ ሱዳንን፣ ካርቱምን፣ ኬንያን መጠበቅ አለብኝ..." የሚልና ፍሬ ቢስ ሐተታም የበዛበት ነበር።[8]

የንጉሠ ነገሥቱ ማስታወሻ የእንግሊዝ ባለሥልጣኖችን ቀሰቀሰ። አንድ ከፍተኛ ቡድን ጥቅምት 20 ቀን 1933 ዓ.ም ካርቱም ገባ። ቡድኑ የሚመራው በውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ በሰር አንቶኒ ኤደን ሆኖ ሰር አርቺባልድን፣ ፊልድ ማርሻል ስመትስን፣ ሚስተር ሚካኤል ራይትን፣ ከፖለቲካ ሰዎች እንደዚሁም ከከፍተኛ የጦር መኰንኖች ለፍተናንት ጀነራል ደኮንሰንን፣ ሌፍተናንት ጀነራል ካኒንግሐምንና ሌሎችንም የጨመረ ነበር። በሦስት ተከታታይ ቀን ጉባዔ ለጦርነቱ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች ከተመረመሩ በኋላ ከበጉ ውሣኔ ላይ ተደረሰ። ውሣኔውም፣

1ኛ. በጀነራል ፐላት የሚመራው ጦር በሰሜን በኩል ኤርትራ እንዲገባ፣

2ኛ. በጀነራል ካኒንግሐም የሚመራው ከደቡብ ኢትዮጵያ እንዲዘምት፣

3ኛ. በንጉሠ ነገሥቱ የሚመራው አነስተኛ ጦር በኢትዮጵያ አርበኞችና ስደተኞች እየታገዘ በተቻለም እንዲገባ ነበር።

የእንግሊዝ ባለሥልጣኖች ለንጉሠ ነገሥቱ ከፍተኛ ዕርዳታ እንደሚደረግላቸው ቃል ገቡ። ከዚህ ላይ መጠቀስ የሚገባው ጉዳይ ሰር አንቶኒ ኤደን ኢትዮጵያ በተወረረች ጊዜ እንግሊዝ ሳትረዳት በመቅረትዋ፣ ከሚስተር ማክማሃን ጋር የረዳት ሚኒስትርነት ሥራቸውን ለቅቀው የነበሩ የኢትዮጵያ ወዳጅ መሆናቸው ነው። ወደ ካርቱም የመጡትም ቀደም ብለው ጥቅምት 18 ቀን 1933 ዓ.ም /ኦክቶበር 29 ቀን 1940/ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴን መሪነት ማወቃቸውን ይፋ አድርገው ነበር።[9]

በዚህ ስምምነት መሠረት ሌላው የኢትዮጵያ ወዳጅ ሻለቃ አርዴ ዊንጊት /ጀነራል/ የንጉሠ ነገሥቱ የፖለቲካና የጦር አማካሪ ሆነው በጥቅምት ወር መጨረሻ ካርቱም ገቡ።[10] ውስጠ አዋቂ በመምሰል ራሳቸውን የእንግሊዝ የጦር አዛዥ እንጂ የኢትዮጵያ አማካሪ እድርገው መመልከት የተጠየፉት የኮሎኔል ሳንድፎርድ ጉዳይ በዚህ አከተመ።[11] ወታደር የማሠልጠኑ ሥራ ሰባ በተባለ ቦታ በዚያው በጥቅምት ወር ተጀመረ። ከሞት የተረፉት እንደ አነ ሻለቃ /ጀነራል/ ዓቢይ አበበ፣ ሻለቃ /ጀነራል/ መርዕድ መንገሻ፣ ሻለቃ /ጀነራል/ ነጋ ኃይለሥላሴ ያሉት የኢትዮጵያ የጦር መኮንኖች በማሠልጠኑ ረገድ ጥሩ ሚና ተጫወቱ። የተሰጠውም ሥልጠና በጉጉም በኩል ሠብሮ ለመግባት የተዘጋጀውን ዕቅድ ከግብ ለማድረስ አስቻለ።

ሁኔታዎች መፍታታትና መሻሻል ሲጀምሩ ከእንግሊዞች ወገን ሌላ የነገር አሸክላ ተዘረጋ። እሱም የበሮክለሀርስት ዕቅድ ነበር። የዚህ ኮሎኔል ሃሳብ ከእንግሊዝ ጉን ቆማችሁ ጣሊያንን ከወጋችሁ ከኢትዮጵያ ገሸፑዎች ነፃ እናደርጋችሁለን በሚል የመደለያ ቃል በደቡብ የኢትዮጵያን ብሔራዊ አንድነት ለመበታተን የተዘጋጀ ዕቅድ ነበር። ንጉሠ ነገሥቱ ይህንን ሃሳብ አልቀበልም፣ ሰውየውንም አላነጋግርም ብለው እምቢ አሉ። ካርቱም ከተሰበሰቡት አባላት አንዳንዶቹንም ቢያሳምን፣ ብሮክለሀርስት ሃሳቡ ሳይሳካለት ቀረ።

የእንግሊዝ ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ካርቱም ድረስ መጥተው ከንጉሠ ነገሥቱ ተነጋግረው የጦር ዕቅድ ከተነደፈም በኋላ፣ የእንግሊዞች አቅዋም ኢትዮጵያን በተመለከተ ግልጽ አልነበረም። ለማስረዳ ያህል ጠቅላይ ሚኒስትር ሰር ዊንስተን ቸርቸል ታህሣሥ 13 ቀን 1933 ዓ.ም /ዲሴምበር 23 ቀን 1940/ ለሲጣልያ ሕዝብ በሬዲዮ ያስተላለፉትን ቃል እንመለከታለን። አላቸውም አጥፊው ሙሶሊኒ መሆኑን ሲዘረዝሩ ኢትዮጵያ የዓለም መንግሥታት ማኅበር አባል እንድትሆን ስትጠይቅ እንግሊዞች አይሆንም ማለታቸውን፣ ሙሶሊኒ ስለደገፋት አባል ለመሆን መቻልዋን ከገለጹ በኋላ "...የኢትዮጵያ ጭቅጭቅ አሁን ኢጣልያና ብሪታንያ በሞት አፋፍ ላይ ከደረሱበት ሁኔታ ጋር ሲተያይ የቱን ያህል ነው?" የሚል ጥያቄ ያዘለ ነበር።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጉዳዩን በጥያቄ ብቻ አልተውትም። "በኢትዮጵያ ምክንያት የተነሳው ጠብ በመካከላችን ስተቀጣጠለው እሳት በቂ ምክንያት ያለመሆኑንና የማይደገፍ መሆኑን እገልፃለሁ። ቃሌም የሚቆይ ነው" ከሚል ድምዳሜ ላይ እደረሱት። ነገር ግን ጣልያን ከተሸንጠችበት ከጀርመን ብብት ውስጥ መውጣት ስለለልቻለች፣ የተጠበቀውና የተጠየቀው እርቅ ሳይገኝ ቀርቶ የኢትዮጵያን ነፃነት ያዘዘው ጦርነት ቀጠለ።

ከእንግሊዝ ባለሥልጣኖች ከእነ ሰር አንቶኒ ኤደን ጋር በተደረገው ስምምነት መሠረት ጦርነቱ በሦስት ገጽ በአንድ ጊዜ በጥር ወር 1933 ዓ.ም ተከፈተ። ዓላማው የጣልያን ጦር በሁሉም ቦታ ቀስፎ በመያዝ መደምሰስ ነበር። ሙሶሊኒ በ1928 ዓ.ም በኢትዮጵያ የሠራው የጦር ሥልት ዙሮ በአሱ በራሱ ላይ መጣበት። በዚህ ምዕራፍ በተሰይ በንጉሠ ነገሥቱ በሚመራው የጦር ግንባር የተደረገውን እንመለከታለን።

በሰባ የኢትዮጵያ ጊዜያዊ የጦር ትምህርት ቤት የተሰጠው አስቸኳይ ሥልጠና እንደተጠናቀቀ ሠራዊቱ በየጦር ግንባሩ ተደለደለ። ዋናው የጦር ግንባር ንጉሠ ነገሥቱ የሚሰለፉበት የጉጃም ግንባር ነበር። ሌላው ግንባር የጉጌሩ ሲሆን፣ ሌላ ሦስተኛ አነስተኛ ግንባር በአሶሳ በኩል ሆነ። ድልድሉ በፍጥነት ተጠናቀቀ። ጦሩም በንጉሠ ነገሥቱ ፊት በሰልፍ አያለፈ እንቅስቃሴ አደረገ። በተገኘው ዓይነት ትራንስፖርት ወደ ኢትዮጵያ ከተጠጋ በኋላ በእግር ተጓዘ። የበረሃው ጉዞ ከባድ ነበር። የአንዱን ቡድን ሁኔታ ማየት ትንሽ ፍንጭ ይሰጣል። ሦስት ቀን የሚወስድ ውሃ የሌለበት የእግር ጉዞ ማድረግ ነበረበት። በቂ ኮዳ አልነበረም። ሎሚ በብዛት መያዝ ግድ ሆነ። ሎሚውን ለመያዝ ታማኝ ሰው ሲፈለግ አቶ ጌታሁን ተሰማ ተመረጡ። ተገቢውን ጥንቃቄ አድርገው ለአያንዳንዱ ለሚገባው ሳይቀር የሚያስፈልገውን በማድረግ ቡድኑ በሰላምና በደህና አደገኛውን ቦታ እንዲሻገር አደረጉ።[12] ጦሩ በዚህ ዓይነት ተገዞ ጉጃም ምድር ለመቆናጠጥ ተዘጋጀ።

ዝግጅቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ስለጦርነቱ አከፋፈት ንጉሠ ነገሥቱ ከጀነራል ፕላት ተገናኝተው ተነጋገሩ። ንግግሩ ያተኮረው የንጉሠ ነገሥቱ የጦር ሠፈር በለያ ስለመሆኑ፣ በስንቅና ትጥቅ አቀራረብና ፊታውራሪ /ራስ/ ብሩ ወደ ቤጌምድር በሚሄዱበት ሁኔታ ላይ ነበር። የልዑል አልጋ ወራሽ አስፋው ወሰንና የልዑል መኮንን ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር አብሮ መሄድ እንግሊዞችን አሳሰበ። ግን መሆን ነበረበት። የኤርስክንና የብሮክለሐርስት ጉዳይ ከጀነራል ዊቨል እንደገና በቴሌግራም መጠየቁ ተነገረ። ነገር ግን ንጉሠ ነገሥቱ በቀድሞው ውሣኔአቸው ጸኑ። የእነዚህ ሁለት ሰዎች ተልዕኮ "...ለሁለቱ አገሮች የሚሆን አይደለም..." በማለት ደመደሙ።[13]

ንጉሠ ነገሥቱ ከካርቱም በአይሮፕላን አስከሮሰሪስ መጡ። ከዚያም የኢትዮጵያ ጠረፍ በሆነ የሱዳን ምድር ላይ አረፉ። ሠራዊታቸውን መርተው ከኢትዮጵያ ምድር በእግር ገብተው፣ አሜድላ በተባለች ቦታ የኢትዮጵያን

ሰንደቅ ዓላማ ጥር 12 ቀን 1933 ዓ.ም ተክሉ። ወዲያው ወርቃዊው የምሕረት አዋጅ በንጉሠ ነገሥቱ በቃላቸው ተነብቦ በጽሑፍ ተበተነ። ይህ አዋጅ ወርቃዊ የተባለው ብወርቅ ቀለም በመጻፉ ብቻ አልነበረም። ለበደሉ ሁሉ ሙሉ ምሕረት ሰጥቶ ኢትዮጵያውያንን እርስበርሳቸው ያስታረቀ በመሆኑ እንጂ። የአዋጁ ፍሬ ነገር "...እገርሀንና ወገንህን የበደልህ ሁሉ ባለፈው ጥፋትህ ምሬሐለሁ። ...በመጣው ጠላታችን ላይ ከዳር እስከ ዳር ክንድህን አንሳ ከኢትዮጵያ ጠርገህ አስወጣው..." የሚል ነበር። ይህ አዋጅ በባንዳ ልቡና የነበረውን ሥጋት ፍቆ በኢትዮጵያ ሕዝብ የመተባበር ስሜት እንደገና ፈጠረ። እንግሊዞችንም አረካ።

ከሱዳን ወደ ምዕራብ ኢትዮጵያ ከገባው ጦር አንዱ ክፍል በአሶሳ በኩል ዘምቶ ኩርሙክንና ጊዜንን ያዘ። ኃይሉ መጠነኛ ስለነበር ይህንን ጠባብ አካባቢ ከመያዝ በስተቀር ወደ ውስጥ ገብቶ ለጊዜው በጠላት ላይ ጉዳት አላደረሰም። ቢሆንም የኢትዮጵያ ጦር ከአዲስ አበባ ወለጋ በገባ ጊዜ ብዙ እገዛ አድርጉአል። በጦሩም ውስጥ የቤልጅግ መኰንኖች የኰንጉና የዛየር ተወላጆችም ነበሩበት።[14]

በንጉሠ ነገሥቱ የሚመራው ጦር ጉዞውን ቀጠለ። ከአሜድላ እስከ ቤላያ የነበረው ጉዞ እጅግ ከባድ ነበር። ቀደም ብሎ በተደገረ ጥናት 25,000 የጭነት ከብት እንደሚያስፈልግ ተገምቶ ነበር። ነገር ግን ሊገኝ የተቻለው 15,000 ብቻ ሆነ። ይህ ደግሞ ጉዞውን አስበደው። በዚህ ላይ በአገር ውስጥ የተገኘው እርካብ ጫማ አላስገባ ስለለስ የፈረንጅ እርካብ እንዲላክ ወደ ካርቱም የተላለፈው ቃል እንደ መሞካሸት ተቆጠረ። አስቸጋሪውን መንገድ ፊጽሞ ቢልያ ገባ። የንጉሠ ነገሥቱ ጊዜያዊ የጦር ሠፈር ከዚያ ሆነ።

ንጉሠ ነገሥቱ ኢትዮጵያ ምድር እንደረገጡ፣ ባንዲራችን በሚባለው በካርቱም በፊት በአቶ /ፕሮፌሰር/ ታምራት አማኑኤል፣ በኋላ ደግሞ በአቶ /ብላታ/ ሚራክ ጎሩይ እየታተመ በአይሮፕላን ይበተን በነበረው ጋዜጣ ወሬው (ዜናው) ተዛመተ። ጉጂም ቀደም ብሎ ገብቶ በአዛዥ /ደጃዝማች/ ከበደ ተሰማና በሻለቃ ዊንጌት /ጀነራል/ የሚመራው ጦር በጣልያኖች ላይ ጥቃቱን አጠናክረው። የጉጂም አርበኞች እርስበርሳቸው ትብበር እየፈጠሩ በየደረሰበት ጠዘጠዙት። ስለአርበኛው እንግሊዞች የነበራቸውን ንቀት ትተው "አርበኛ፣ ማለትም ፓትርዮት" ይሉት ጀመር። በጦር ጓደኝነቱ ተማመኑ።[15] ይህም ሆኖ እንግሊዞች ሥራ ማጓተታቸውና በነገር መጐንተላቸው አልቀረም።

በዚህ ላይ ደግሞ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ኢትዮጵያ ከገቡ በኋላ፣ ካርቱም ላይ የእንግሊዝ የምሥራቅ አፍሪካ ቅኝ ግዛቶች አስተዳደር ባለሥልጣኖች ኢትዮጵያ አስተዳደርዋ እንደምን ይሆናል? የሚል ጥያቄ አንስተው መነጋገራቸውና ከጠላት የተወሰዱ የቅኝ ግዛቶች አስተዳደር ሥር እንደተመደበች በምሥጢር ተሰማ። ነገር ግን ውሣኔውን ለንጉሠ ነገሥቱ ሊናገር የተላከው ብርጋዴር /ጀነራል/ ላቫ ፈርቶ ሳይናገር ወደ ሱዳን

ተመለሰ።[16] በእንድ በኩል ይህ ጉዳይ ከእነ ብሮክለሐረስት አስተሳሰብ ጋር ተደምሮ በኢትዮጵያ ወገን ታሳቅ ስጋት ሲቀሰቅስ፣ በሌላ ወገን ደግሞ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሰር አንቶኒ ኤደን ጥር 27 ቀን 1933 ዓ.ም /ፌብሪዋሪ 4 ቀን 1941/ ለንደን ለሐውስ ኦፍ ኮመንስ ያሰሙት ንግግር ለኢትዮያ ተስፋ የሚሰጥ ሆነ። የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ አነጋገር በቀና መንፈስ ላይ የተመሠረተ ሆኖ የኢትዮጵያን ነፃነት በተመለከተ "የግርማዊ የእንግሊዝ ንጉሥ መንግሥት በነፃነት የኢትዮጵያ መንግሥት እንደገና ተነስቶ እንዲታይ ይፈቅዳል። ለዙፋኑም የአፄ ኃይለሥላሴን ጥያቄ ያውቅላቸዋል።...የእንግሊዝ መንግሥት በኢትዮጵያ የመሬት ፍላጐት የሌለው መሆኑን ራሱ ያረጋግጣል..." የሚል ነበር። ነገር ግን ከማድመጥ በስተቀር በውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ቃል ምክር ቤቱ አልተነጋገረበትም። ስለዚህ የእንግሊዝ አቅዋም ገና ግልጽ አልነበረም።

የሆነ ሆኖ ጦርነቱ እየተቃና ሄደ። የጣልያን ጦር አዛዥ ናዚ በአይሮፕላን ከጉንደር ደብረ ማርቆስ በመብረርና የጦር መኩንኖች ሹምሽር በማድረግ ያዘጋጀውን ያህል ሳይመለከት ቀረ። ቡሬ፣ አንጀባራ፣ ፍናኖተ ሰላም፣ ማንኩሣ፣ ጂጋ፣ ደንበጫ የነበረው ወደ ደብረ ማርቆስ የዳንግላው ወደ ባሕር ዳር ሄደ። በአጭር ጊዜ ውስጥ አለፋ ጣቱሣ፣ አቸፈር፣ ዘጌ፣ ደብረ ማይ፣ መሸንቲና አዴት የነበረው ሌላውም ሁሉ ተከተለ።[17]

እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ /ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ/ ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር አሜድላ ገቡ። ኢትዮጵያ መሬት ሲገቡ በመስቀላቸው ግራና ቀኝ እየባረኩ የእግር ጉዞ ቀጠሉ። እንኳን በመኪና በበቅሎም አልተቀመጡ። እግራቸው የቻለውን ያህል ሙሉ ቀን እየሄዱ፣ አንዳንድ ግዜም ጦሩን እየቀደሙ እየተጓዙ ከመሬት እንደተኙ ደብረ ማርቆስ ደረሱ። ከዚያም በዚሁ ዓይነት ደብረ ሊባኖስ ገቡ።[18]

የንጉሠ ነገሥቱ ጊዚያዊ የጦር ሠፈር ከዚልያ ወደ ቡሬ ተዛወረ። ቡሬ ላይ ማረፊያ ሜዳ ተሠርቶ የአየር መገናኛ ተከፈተ። ቀደም ብሎ በታሰበው መሠረት ፊታውራሪ /ራስ/ ብሩ ወልደ ገብርኤል ክፊል ጦር ይዘው በባህር ዳር በኩል ወደ በጌምድር ተሻገሩ። ዋናው ጦር ከአርበኛው ጋር ተቀላቅሎ ወደ ደብረ ማርቆስ የሚጓዘውን የጣልያን ጦር ማባረር ቀጠለ። ከዚያ በኋላ ጠንካራ ጦርነት የተደረገው ጨረቃ በተባለው ቦታ ነው። ከጨረቃ ውጊያ በኋላ ሌላ ከባድ ውጊያ ሳያጋጥም ጦሩ ደብረ ማርቆስ አካባቢ ደረሰ። ጣልያኖች ከተማይቱን ለራስ ኃይሉ ትተው ሸዋ ተሸገሩ። እሳቸውም ሳያንገራግሩ ከተማይቱን ለአዛዥ /ደጃዝማች/ ከበደ ስለአስረከቡ ንጉሠ ነገሥቱ በሰላም መጋቢት 28 ቀን 1933 ዓ.ም ወደ ማታ ደብረ ማርቆስ ገቡ።

በኢትዮጵያና በእንግሊዝ ወታደሮች መካከል የነበረው ትብብር በጣም ጥሩ ነበር። መተባበር ብቻ ሳይሆን ከመተማመንም ደርሰው ነበር። ለማሰረጃ የአንድ መኰንን ታሪክ መጥቀስ ይገባል። አንድ መቶ አለቃ የተቀመጠበት

ፈረስ በጥይት ሲመታ እግሩ ላይ ስለወደቀበት ከቁርጭምጭሚት እስከ መሐል አጥንቱ ደቀቀ። ከጉልበቱ ሎሚ ያህተቀር የዳነ የለም። የሀኪምና እርዳታ ሊያገኝ ስለአልቻለ በኢትዮጵያዊ ወጌሻ ለመረዳት መፍቀዱን በጽሑፍ አረጋገጠ። አቶ ገብረሚካኤል የተባለ ወጌሻ አሽቶ በማለሚያ አስሮ አዳነው። መቶ አለቃው ራሱ ከጻፈውና አለቃው በወቅቱ ካስተላለፈው ሪፖርት በስተቀር መቶ አለቃው መቁሰሉን የሚያመለክት ምልክት እስኪጠፋ ድረስ ፈጽሞ ዳነ።[19]

የንጉሠ ነገሥቱ ደብረ ማርቆስ መግባታቸው፣ የጦር ሠፈር ከዚያ መደረጉ ታላቅ ነገር ሆነ። ራስ ኃይሉም ሳያንገራግሩ ለንጉሡ መግባታቸው ቀላል አልነበረም። የሸዋና የጐጃም አርበኛ አካባቢውን ከጠላት ይዞታ በቶሎ አስለቅቆ በር ሰመክፈት ይችል ስለነበር፣ ከደብረ ማርቆስ እስከ አዲስ አበባ የሚደረገው ጉዞ ከዓባይ ድልድይ ሥራ አለመፈጸም በስተቀር ሌላ አስጊ የጦር ችግር አልነበረበትም። ያውም ቢሆን በአይሮፕላን ሲበርሩ ስለሚችሉ መጋቢት 29 ቀን 1933 አዲስ አበባ መግባት ይችሉ ነበር። ነገር ግን እንደዚህ አልሆነም። ንጉሠ ነገሥቱ ከገዛ መናገሻ ከተማቸው እንዳይገቡ ታገዱ።

ንጉሠ ነገሥቱ ደብረ ማርቆስ ገብተው በአደባባይ ላይ ለተሰበሰበው ሕዝብ የደስታ መግለጫ ንግግር በማድረግ ላይ እንደ አሉ ለኮሎኔል ዊንጌት /ጀነራል/ ከካርቱም ቴሌግራም ደረሰ። ቴሌግራሙ በጀነራል ካኒንግሀም የሚመራው የምሥራቅ ነፃ አውጭ ጦር በዚያው ቀን አዲስ አበባ መግባቱን የሚያበስርና ለጊዜው ማንኛውም እንቅስቃሴ እንዲቆም የሚያዝ ነበር። ዊንጌት ይህ መልእክት እንደደረሰው ንጉሠ ነገሥቱ ወደ አዲስ አበባ የሚሄዱበት አይሮፕላን እንዲላክለት ወዲያው ጥያቄ አቀረበ። ነገር ግን ጥያቄው በካርቱም የእንግሊዝ ባለሥልጣኖች ዘንድ ተቀባይነት አለማግኘቱ ተገለጸለት። ውሣኔውን የሚቃወም መልእክት መልሶ ቢያስተላልፍ፣ እንዲያውም ንጉሠ ነገሥቱን በአሉበት ቦታ እንዲያቆይ የማያወላዳ ትዕዛዝ ከጥብቅ ማስጠንቀቂያ ጋር ተላለፈት። ከጀነራል ካኒንግሀምም እንደዚሁ የተሰጠው ምክንያት "አዲስ አበባ ውስጥ 25,000 ነጮች ስለአሉ አገሩ እስኪረጋጋ መቆየት አለባቸው" የሚል ነበር።[20]

ንጉሠ ነገሥቱ ወደ ደብረ ማርቆስ በመጓዝ ላይ ሳሉ ጀነራል ሳቫ ኢትዮጵያ ከጠላት ከተወሰዱ ቅኝ ግዛት አስተዳዳር ውስጥ መመደብዋን ለመንግር መጥቶ፣ መልእክቱን ለመንገር ሳይደፍር ወደ ካርቱም መመለሱን ቀደም አድርገን ገልጸናል። ሳቫ የካርቱም ውሣኔ ሳይነገር የተመለሰው፣ ንጉሠ ነገሥቱ ይህንን የመሰለውን ነገር እንደ ስድብ ስለሚቆጥሩት፣ ፈጽሞ እንደማይቀበሉት ከብር ጋዲየር ሳንድፎርድ በቁርጥ ስለተነገረው ነበር።

ለዊንጌት የደረሰው መልእክት ከሳቫ ተልእኮ ጋር ተደምሮ አዲስ ሥጋት ፈጠረ። በንጉሠ ነገሥቱና በመኪንኖቶቻቸው ዘንድ ምክር ተመክረ።

ምክሩ የጦርም የአስተዳደርም ሆነ። በምክሩ መሠረት ንጉሠ ነገሥቱ በደብረ ማርቆስ አደባባይ የአርበኞችን ሰልፍ ሲመለከቱ ዋሉ። ሰልፉም እጅግ ስለደመቀ ባንዳም ተሳተፈበት። በጦር ረገድ የንጉሠ ነገሥቱ ጦር በደጀንና በጉሐ ጽዮን በኩል እንዲያልፍ፣ በሻለቃ /ራስ/መሥፍን ስለሽ የሚመራው ጦር በደራ ተሻግሮ ወደ መርሐቤቴ እንዲዘልቅ፣ በአዛዥ /ደጃዝማች/ ከበደ የሚመራው ጦር ወደ ግንደበረት እንዲሻገር፣ ሞጣ ላይ ተቋርጦ የቀረውን የጠላት ጦር ልጅ /ራስ ቢትወደድ/ አንዳርጋቸው መሣይና ልጅ /ዋግሹም/ ወሰን ኃይሉ በአካባቢው ከሚገኙ አርበኞች ጋር ምሽጉን እንዲሠብሩ ተወሰነ። እንደዚሁም ተደረገ።[21]

አስተዳደርን በተመለከተ በደጃዝማች /ራስ ቢትወደድ/ መኮንን እንዳልካቸው መሪነት አንድ ቡድን ወደ አዲስ አበባ በአይሮፕላን ተልኮ የመግቢያውን ፕሮግራም እንዲያዘጋጅና ዐዋታውን እንዲያስተካክል ተደረገ። በልዑል መኮንን ኃይለሥላሴ የሚመራ ሌላ ቡድን ደግሞ በአይሮፕላን ወደ ሐረር ተላከ። ከዚህም በስተቀር ቀደም ብሎ የካቲት 27 ቀን 1933 ዓ.ም ተጀምረው ሲታሰብባቸው የቆዩ ሁለት ጉዳዮች ላይ ተመክረ። ከእነዚህም አንደኛው የባንዳን አስተዳደር ጉዳይ የሚመለከት ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ከእንግሊዝ መንግሥት ስለሚጠየቀው ዕርዳታ ነበር።

ስለ ባንዶች የተደረገው ምክር "...ባንዶቹ ከሹመት፣ ከማዕረግ እንዳይወርዱ ይመኛሉ..." በሚለው ጥያቄ ላይ አተኮረ። "ባንዶችን መማርና መተዳደሪያ ደንብ መስጠት ይሻላል" የሚል ሃሳብ በአንድ ወገን፣ "አስታራቂ ሃሳብ እስኪቀርብ ወደ አርበኞች ይላክ" የሚል ሃሳብ በሁለተኛ ወገን፣ "መንግስት ተረጋግጦ እስኪቆም ዝም ማለት ይሻላል" የሚል በሦስተኛ ወገን ቀረበ። በአዋጅ የገባ፣ ጣልያኖች ቢክዱት የገባ፣ በተለይ ተጽፎለት የገባና ደም የተቃባ ባንዳ ተለይቶ እንዲታወቅ ተወሰኖ እንደነበር ይታወሳል። ንጉሠ ነገሥቱ ደብረ ማርቆስ በቆዩበት ጊዜ ይህ ነጥብ አንድ የምክር ጉዳይ ሆነ። እስከ ጦርነቱ ፍፃሜ ድረስ የሚያገለግል ጊዜያዊ መተዳደሪያ ተበጀ።[22] ስለሆነም ከእንግሊዞች ስለሚጠየቀው ዕርዳታ በዚህ ወቅት ከአንድ ውሣኔ ላይ ለመድረስ ሁኔታው አመች አልነበረም።

ንጉሡ አዲስ አበባ የሚገቡት ሚያዝያ 27 ቀን 1933 ዓ.ም እንዲሆን ተወሰነ። ከዚህ ውሣኔ ላይ የተደረሰው የኢትዮጵያ ሞትም ትንሣዔም በአንድ ቀን በተከታዩ ትውልድ እንዲከበር ታስቦ እንደነበር ማጤን ይገባል። ይህንን የመሰለ ዝግጅት ከተደረገ በኋላ ንጉሠ ነገሥቱ ከደብረ ማርቆስ ወደ አዲስ አበባ ሚያዝያ 21 ቀን 1933 ዓ.ም ተንቀሳቀሱ። እንግሊዞች ደብረ ማርቆስ እንዲቆዩ ያደረጉት ለጤና አለመሆኑን ተገንዝበውት ነበርና፣ ጉዞአቸው በጥቃቅን ምክንያት የሚታገድ አልሆነም። ኮሎኔል ዊንጌትም ከእንግሊዝ የጦር አለቆች ይልቅ የንጉሠ ነገሥቱን ሃሳብ ደገፈ። የዓባይን ወንዝ ከበርሜልና ከብረታ ብረት በተሠራ መሸጋገሪያ ተሻግረው ፍቼ ደረሱ።

ንጉሠ ነገሥቱ ጥዋት ከፍቼ ከተማ ተነስተው እንጦጦ ደረሱ። ከዚያ ጀምሮ የሸዋ አርበኛ ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር አብሮ ከመጣው ጦር ጋር መንገዱ ግራና ቀኝ ተሠልፎ ነበር። ሕዝቡም በነቂስ ወጥቶ በመንገዱ ግራና ቀኝ በመሆን በደስታ በእልለታ፣ በሆታ ተቀበላቸው። ከደስታ ብዛት የሚያለቅሰው ይበዛ ነበር።

ንጉሠ ነገሥቱ ወደ ታላቁ ቤተ መንግሥት ተጉዘው እኩለ ቀን ላይ ደረሱ። ደርሰውም መኳንንቶቻቸውና የአርበኞች መሪዎች፣ የእንግሊዝ የጦር ሹማምንቶች በተገኙበት የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ሰቀሉ። ሰንደቅ ዓላማ በሚሰቀሉበት ጊዜ 21 ጊዜ መድፍ ተተኮሰ። ያ የኢትዮጵያ ትንሣዔ የተከበረበት ቀን ሚያዝያ 27 ቀን 1933 ዓ.ም ነበር። ከሚያዝያ 27 ቀን 1928 ዓ.ም ሞት ተነሣች።

ከዚህ በኋላ ንጉሠ ነገሥቱ በዚያ ለተሰበሰበው ሕዝብ ንግግር አደረጉ። ጀኔቭ ለዓለም መንግሥታት ማኅበር ሰኔ 23 ቀን 1928 ዓ.ም ከአደረጉት ንግግር ቀጥሎ ታላቁ ንግግር ይህ ነበር። እሳቸውም "የሰማይ መላእክት፣ የምድር ሠራዊት ሊያስቡትና ሊያውቁት ይቻላቸው ባልነበረ በዚህ በዛሬው ቀን ቸር እግዚአብሔር በመከከላችሁ ለመገኘት ስለአበቃኝ በሰው አፍ የሚነገር ምስጋና የሚበቃ አይደለም..." በማለት ንግግራቸውን ጀመሩ። አያይዘውም "...ይህ ቀን ለአዲሲቱ ኢትዮጵያ የአዲስ ታሪክ ዘመን መክፈቻ...ነው..." አሉ። በሀገሪቱ ላይ የደረሰውን መከራ፣ የአድዋን ጦርነት ጠቀሱ። በጣልያን ላይ የዓለም መንግሥታት ማኅበር እንደፈረደበት አወሱ። አገር የሚለማበትን፣ ሕዝብ የሚበለጽግበትን፣ ንግድ ትምህርትና ጥበብ የሚስፋፋበትን፣ የሕዝባችን ሕይወትና ሀብቱ የሚጠበቅበትን፣ ያገር አስተዳደርም ባዲሱ ሥልጣኔ ተሰውጦ ፍፁም የሚሆንበትን ሥርዓት እንዲሚመሠርቱ አስታወቁ። "...በአዲሷ ኢትዮጵያ ከእንግዲህ ወዲያ የማትነጣጠሉ፣ በሕግ ፊት ትክክለኞነትና ነፃነት ያላችሁ ሕዝቦች እንድትሆኑ እንፈልጋለን።..." አሉ። ለእንግሊዝ መንግሥት ታላቅ ምስጋና አቀረቡ። ከዚያም ከቤተመንግሥታቸው ገቡ።

አዲሱ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት በዚህ ቀን ቆመ። ንጉሠ ነገሥቱ ታላቅ አክብሮት አገኙ። የሚቃወሙአቸው ጭምር በፖለቲካ ጥበባቸውና በአመራር ችሎታቸው አደነቁአቸው።

<u>ማጣቀሻ ፅሑፎች</u>

1. George Steer, *Sealed and Delivered*, pp.16-31, 90-101, 232-233.
2. ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፣ *ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ 2ኛ መጽሐፍ*፣ ገጽ 190-215።
3. ኃይሉ ገብረኢየሱስ፣ *መድረክ*፣ ገጽ 69-75።
4. የድል መታሰቢያ፣ ገጽ 70።

5. *ገሪማ ታፈረ*፣ *ሥንደሬ ቢጋሻው*፣ ገጽ 232።
6. Steer, p.121.
7. *ገሪማ ታፈረ*፣ ገጽ 240-250።
8. ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፣ ገጽ 218-223።
9. Alberto Sabacchi, *Ethiopia under Mussolini*, p 217.
10. ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፣ ገጽ 250-253።
11. ከበደ ተሰማ፣ *የታሪክ ማስታወሻ* ገጽ 217።
12. ፊታውራሪ ስለሽ ዘረፉ ያጫወቱኝ።
13. ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፣ ገጽ 254-269፣ 271።
14. Steer, pp. 121-136.
15. ሕይወት ጎዳሩ፣ *ያ ቸ ቀን ተረሣች*፣ ገጽ 71፣ 400።
16. Leonard Mosely, *Haile Selassie*, p.267.
17. Steer, pp.129-148.
18. ከደጃዝማች አስፋው ሺህ አምጥ የተነገረኝ።
19. ከአቶ ገብረሚካኤል ከራሱ የተነገረኝ።
20. Mosley, pp.266-208.
21. ከበደ ተሰማ፣ ገጽ 409-416።
22. ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፣ ገጽ 291-306።

ምዕራፍ ሃምሣ ሶስት
ኢትዮጵያን ነፃ ለማውጣት የተንቀሳቀሰው የእንግሊዝ ጦር

ኢትዮጵያን ነፃ ለማውጣት የእንግሊዝ ጦር የተንቀሳቀሰው በሦስት አቅጣጫ እንደነበር ቀደም ብሎ ተገልጾአል። ከእነዚህም ንጉሠ ነገሥቱን በማገገዝ በጉጃም በኩል የገባው ጦር የሠራውን ሥራ ተመልክተናል። በዚህ ምዕራፍ ደግሞ በሌሎች ሁለት አቅጣጫዎች፣ ማለትም በሰሜንና በደቡብ የተሠማራው ጦር የሠራውን ሥራ እናያለን።

ኢትዮጵያን ነፃ በማውጣት ረገድ ከፍተኛውን ሥራ የሠራው ከናይሮቢ የተንቀሳቀሰው ነበር። አዲስ አበባ ቀድሞ የገባ እሱ ነው። ምንም የሰሜኑን ጦር ቢያግዘው የጠላትን ጦር አባርሮ አምባሰጌ ላይ የማረከ እሱ ነው። ስለዚህ የእሱን አካሄድ አስቀድመን እንመረምራለን።

ይህ በጀነራል ካኒንግሐም የበላይ አዛዥነት እየተመራ በምሥራቅ አፍሪካ ላይ የዘመተ ጦር፤ ከደቡብ አፍሪካ ጀምሮ ካሉት የእንግሊዝ ቅኝ ግዛቶች ተቀስቅሶ የተሰለፈው በሦስት ረድፍ ነበር። አንዱና ዋነኛው ጦር ከኬንያ በኪሲማዩ በኩል ደቡብ ሶማሊያ ገባ። ሁለተኛው ከየመን በኤደን በኩል አድርጉ በሰሜን ትንሽ ቀደም ብሎ በኢጣልያ ወታደሮች ተይዛ የነበረችውን ሰሜን ሶማሊያን አጠቃ። ሦስተኛው በደቡብ በኩል ወደ ኢትዮጵያ ገባ።

ጣልያንን ከምሥራቅ አፍሪካ ለማባረር የተፈለገው ኢትዮጵያን ነፃ ለማውጣት ተብሎ አልነበረም። የጦርነቱ ሚዛን በጀርመንና በኢጣልያ ላይ ለማክበድ እንጂ። የምሥራቅ አፍሪካ መያዝ ከሕንድ ውቅያኖስ እስከ ሜድትራንያን ያለውን የባህር መንገድ በእንግሊዝ እጅ ያስገባዋል። የኢጣልያ ከምሥራቅ አፍሪካ መባረር ጣልያኖችን ተስፋ ያስቆርጣል። ምናልባትም ከጀርመን ጉን መቆማቸውን በመተው ከጦርነቱ እንዲወጡ ያስገድዳቸዋል። ያለሥራ ኬንያ ላይ ሠፍሮ የነበረው ጦር ግዳጁን ከተወጣ ወደ ምሥራቅ አውሮፓ መጥቶ እንዲሰለፍ ማድረግ ያስችላል። ይህንንም ውጤት ማግኘት የሚቻለው ሁሉም ጦር በአንድ ጊዜ የተንቀሳቀሰ እንደሆነ ነው። ስለዚህ ሁሉም ጦር በአንድ ጊዜ ተንቀሳቀሰ።

በኪሲማዩ በኩል ሠብሮ ሞቃድሾ ለመግባት የተደረገው እንቅስቃሴ ከየካቲት 2 ቀን እስከ 8 ቀን 1933 ዓ.ም /ፌብሬዋሪ 10 እስከ 18 ቀን 1941/ ተካሄደ። ጣልያኖች ስድስት ብርጌድ ኢጣልያውያንና ሌላ ስድስት ብርጌድ የሀገር ተወላጆች ጁባ ወንዝ ላይ አሰለፉ። ዋናው የጣልያን ጦር ከወደብዋ በስተሰሜን ትንሽ ራቅ ብላ በምትገኝ ጂሊብ በተባለችው ቦታ ላይ ተሰለፈ። ይህ ጦር የካቲት 14 ቀን /ፌብረዋሪ 22 ቀን/ በተደረገው ግጥሚያ ድል ሆነ። ሠላሣ ሺህ ጦር በአንድ ቀን ውጊያ ድምጥማጡ ጠፋ። እኩሉ ሞተ፣ እኩሉ

ቆሰለ፣ ወይም ተማረከ። የቀረው ሸሽቶ ጫካ ገባ። የሞቃድሾ በር ተከፈተ። የጣልያን አየር ኃይል በደቡብ አፍሪካ አየር ኃይል ተመታ።

በመኪና የሚንቀሳቀሰው የእንግሊዝ ጦር የካቲት 17 ቀን /ፌብሪዋሪ 25 ቀን/ ሞቃድሾ ገባ። በአየሮፕላን ጣቢያው ሃያ አንድ የኢጣልያ አይሮፕላኖች ተቃጥለው ከሰላቸው ይታያል። የልዩ ልዩ ዕቃዎችና መሣሪያዎች ክምችት ተገኘ። ከሁሉም ጠቃሚው በከተማይቱ የተገኘው 400 ሺህ ሊትር ቤንዚን ሆነ። ቀጥሎ የሚደረገው ጉዞ ወደ ጅጅጋ ነበር። እዚያም ለመድረስ በአጋዴን በረሃ ውስጥ 1180 ኪሎ ሜትር መንገድ ማቋረጥ ብቻ ነው። የጦርነት ጉዳይ አሳሳቢነት የሰውም። ከድሬዳዋ እየተነሱ ለመከላከል የሞከሩትን የጣልያን አይሮፕላኖች ከሞቃድሾና ከኤደን በሚነሱ አይሮፕላኖች በማጥቃት፤ የእንግሊዝ መካናይዝድ ጦር መጋቢት 8 ቀን /ማርች 17/ ጅጅጋን ያዘ።

ከኤደን የተንቀሳቀሰው የእንግሊዝ ጦር መጋቢት 7 ቀን /ማርች 16 ቀን/ በርበራን ከጣልያን አስለቀቀ። ከዚያም ጅጅጋ ከዋናው ጦር ጋር በመቀላቀል መንገዱን ቀጠለ። የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ዲላኖ ሩዝቬልትም የሊቢያውን ጦርነት ለማቀላጠፍ ምሥራቅ አፍሪካን በፍጥነት ማስለቀቅ እንደሚያስፈልግ አስታወቁ።

የጣልያን ጦር በበኩሉ ካራማራ ላይ መሽጐ ለመከላከል ሞከረ። ነገር ግን አልቻለም። ከዚያም በባሌ ላይ ተከማቸ። እዚያም አንዳች ማድረግ አልቻለም። በቀላሉ ተበታትኖ ሁሉም በየፊናው ሽሽቱን ያዘ። ባንዳው ራሱ እየከዳ ይጠዘጥዘው ጀመር። ሌላው ቀርቶ እስከ መጨረሻው ድረስ በታማኝነት ይቆሙልናል ብለው ተማምነውባቸው የነበሩት ኤርትራውያንም እየከዱ ጣልያኖችን መልሰው ደበደቡአቸው። በጥይትና በቦምብ የሚያወርዱባቸው ውርጅብኝ ጣልያኖችን በእግር እንጂ በክብት መንቀሳቀስ ከሰከሰአቸው። ጣልያኖውያን ወታደሮች ተሸበሩ። ቢሆንም እሳት ከተባለው ቦታ ለሕይወታቸው ሲሉ በርትተው ሙሉ ቀን ተዋጉ። ያም ሆኖ መመከት አልቻሉም። በዚህ ዓይነት ጥሶ የእንግሊዝ ጦር መጋቢት 16 ቀን 1933 ዓ.ም /ማርች 26 ቀን 1941/ ሐረር ከተማ ገባ። ከዚያም መጋቢት 19 ቀን ድሬዳዋን ያዘ።[1] ነገር ግን የፊረንሳይ መንግሥት ስለአልፈቀደ በጅቡቲ ወደብ መጠቀም አልተቻለም።

ከኬንያ በጋሞ ጎፋ በኩል የገባው የእንግሊዝ ጦር በኢትዮጵያ ስደተኞች እየታገዘ ጨንቻ ገባ። ከዚያም ወደ ጅማ ተጉዞ ከአዲስ አበባ ከወረደው የኢትዮጵያ ጦር ጋር ተቀላቅሎ፤ በምዕራብ ኢትዮጵያ ተሰራጭቶ የነበረውን የጣልያን ጦር መመንጠር ያዘ።[2] በኬንያ ከነበሩት ስደተኞች መካከል ተመልምለው ወደ ሱዳን ያልሄዱት ጦር ተሰርቶ በፊታውራሪ /ደጃዝማች/ ወልደማርያም፣ በፊታውራሪ /ደጃዝማች/ ታደመ ዘለቀና

በፊታውራሪ/ደጃዝማች/ በቀለ ሀብተሚካኤል መሪነት በሞያሌ በኩል ወደ ኢትዮጵያ ገባ። ከዚያም የበኩሉን እየሠራ በያቤሎ አድርጉ ቦረና ነገሌን ያዘ።

ኢጣልያኖች አዲስ አበባን ላለማስያዝ ሊከላከሉ አሰቡ። ነገር ግን በዜጐቻቸው ላይ አንዳች ውጤት ለማግኘት አንደማይችሉ ከኢትዮጵያውያን አማካሪዎቻቸው በተረዱ ጊዜ በናዝሬትና በመተሐራ መካከል ባለው ቦታ ላይ ለመዋጋት ከጀሉ።[3] ነገር ግን ስመክላከያ አፍርሰውት የነበረውን የአዋሽን ድልድይ ጠባቂ ስለአላደረጉበት እንግሊዞች መልሰው በመሥራት ወንዙን ተሻግረው ስለነበረ ሳይቻል ቀረ። ስለዚህ ዱካ ደ አዎስታ አዲስ አበባን ለእንግሊዞች በሰላም እንዲያስረክብ የከተማይቱን ኃላፊ ወክሎ ወደ ሰሜን ጉዞውን ቀጠለ።

የአዲስ አበባ ከተማ ሁኔታ ክባድ ነበር። ዙሪያዋን በአርበኞች ተከባለች። ወታደራቸው ቀደም ብሎ ከተማይቱን ለቅቆ ስለወጣ፣ ሰላማውያን ጣልያኖች አርፈው ዕድላቸውን ከመጠበቅ በስተቀር መፈናፈን የሚችሉበት መንገድ አልነበራቸውም። ብስጭት የከበደው አርበኛ ገብቶ ነጮቹን እንዳያርዳቸው ተፈርቶአል። አዲስ አበባ ውስጥ ያሉ 25,000 ነጮች ጉዳይ እጅግ አሳሰበ። ከዚህም የተነሳ እንግሊዝ ጦርነቱን አሳቶምም ስለአለ ኃላፊነቱ የዱካ ደ አዎስታ ነው አለች። ጣልያን ደግሞ የእንግሊዝ ነው አለች።[4] በከተማይቱ ዙሪያ 35 ምሽጉች ተሠርተዋል። ደግሞም በእሾህማ ሽቦ ከተማዋን አጥረዋል። በጣልያኖች መኖሪያ አካባቢ ዋሻ ቆፍረው የአደጋ ድምፅ በተሰማ ጊዜ ዜጐቻቸውን ከዚያ እንዲሸሽጉ ማስጠንቀቂያ ሰጥተዋል። ነገር ግን ይህ ሁሉ ከንቱ ሆነ። በከተማይቱ ዙሪያ የነበረው አርበኛ አንዳች ጉዳት አላደረሰም። የከተማይቱን ፀጥታ ለመጠበቅ የቻለው አዲስ የገባው የእንግሊዝ ጦር አልነበረም። የንጉሠ ነገሥቱም ትዕዛዝ ብቻ አልነበረም። የአርበኛው ትዕግስትና የሕዝቡ ሥርዓት አክባሪነት እንጂ።

በጀነራል ዊዝሮል የሚመራው የእንግሊዝ ጦር አቃቂ ደረሰ። የቡልጋ አርበኛ በራስ አበበ እየተመራ የአዲስ አበባን ዙሪያ ያዘ። የኢጣልያ ሹማምንት ያለ አንዳች ጥያቄ ከተማይቱን ከማስረከብ በስተቀር አንዳች የሚያደርጉት አልነበራቸውም። የእንግሊዝ ጦር ሃምሣ ሺህ የጣልያን ጦር አራግፎ መጋቢት 28 ቀን 1933 ዓ.ም እሑድ ጥዋት አዲስ አበባ ገባ። ጀነራል ዊዝሮል ገነተ ልዑል ይባል ክነበረው ዛሬ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ከሆነው ቤተ መንግሥት ገብቶ የእንግሊዝን ሰንደቅ ዓላማ ተከለ።

ይህ ሁኔታ በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ ታላቅ ቅሬታ ፈጠረ። የነጭ ለነጩ ቅብብሎሽ ሆነ። ሌላ አዲስ ብጥብጥ ሊነሣ ተቃረበ። ብልሆቹ የእንግሊዝ መሪዎች ይህንን ሲገነዘቡ ፈጣን የማረጋጊያ እርምጃ ወሰዱ። እሱም የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ በታላቁ የአዜ ምኒልክ ቤተ መንግሥት ላይ መስቀል ነበር። ጀነራል ዊዝሮል ከቀትር በኋላ ወደ ታላቁ ቤተ መንግሥት ሄደው፣ የኢጣልያን ሰንደቅ ዓላማ አውርደው ክላዩ ላይ ቆመው የኢትዮጵያን

ሰንደቅ ዓላማ ሰቀሉ። ሰንደቅ ዓላማይቱን ከሰቀሉ በኋላ በአቶ /ብላታ/ ዳዊት ዑቁበአግዜአብሔር አስተርጓሚነት ንግግር አደረጉ። ባደረጉትም ንግግር ያቺ ቀን በመላ ሕይወታቸው ስትታወስ የምትኖር ታላቅ ቀን መሆንዋን ገልጸው፣ ንጉሠ ነገሥቱ በቅርብ ቀን ከመናገሻ ከተማቸው አዲስ አበባ እንደሚገቡ አረጋገጡ። ታላቅ ደስታ ሆነ።[5]

ከኬንያ በጀነራል ካኒንግሐም እየተመራ የተንቀሳቀሰው ጦር በዚህ ዓይነት ደቡብና ሰሜን ሶማሊያን በተለይም ኢትዮጵያን ነፃ አወጣ። አሁን ደግሞ በጀነራል ፕሳት መሪነት ክካርቱም በሰሜን በኩል የተንቀሳቀሰው ምን እንደ አደረገ እንመለከታለን።

በሰሜን የነበረው የኢጣልያ ጦር ከረን ላይ ሊሟሟት ተዘጋጅቶ ነበር። ከረን በሦስት ታላላቅ ተራሮች የተከበበች በመሆኗ ለመከላከል ምቹ ናት። ከዚያም አልፎ በአቆርዳትና በተሰነይ በተለይም በከሰላ አካባቢ የመከላከያ ዝግጅት አደረገ። በእንግሊዞችም በኩል ለማጥቃት ዝግጅት ተደርጉ ጦርነቱ በጥር 1933 ዓ.ም ተከፈተ።

ንጉሠ ነገሥቱ ቀደም አድርገው ሐምሌ 1 ቀን 1932 ዓ.ም በትግርኛ ቋንቋ አዋጅ ነግረው ነበር። አዋጁም በተሰይ ለኤርትራ ሕዝብ ያስተላለፈው መልእክት "...የሐማሴን፣ የአከለጉዛይ፣ የሠራየ፣ የበኒአምር፣ የሃባብ፣ ከመረብ ወንዝ ወዲህም ማዶም ያላችሁ ከኢትዮጵያውያን ወንድሞቻችሁ ጋር ተባበሩ። ለጣልያን መሣሪያ አትሁኑ። እናታችሁን ኢትዮጵያን አትተው። እንግሊዝን አትውጉ.." የሚልና እንግሊዞችን በፍቅር እንዲቀበሉአቸው የሚያሳስብ ነበር።[6] ይህ አዋጅ የኤርትራ አርበኞች በጣልያን እንዲነሱና እንግሊዝን እንዲደግፉ በማድረግ ረገድ በእጅጉ ረዳ። ለጦርነቱም አቶ /ደጃዝማች/ አሰጋኸኝ አርአያ የንጉሠ ነገሥቱ ወኪል ሆኑ።

ከዚህ የፖለቲካዊና ወታደራዊ ዝግጅት በኋላ፣ የእንግሊዝ ጦር በተሰነይ በኩል ወደ ኤርትራ ለመግባት ተንቀሳቀሰ። ተሠነይ በቀላሉ ተያዘች። ጣልያኖች ክጉንደር ጭምር ወታደር ወስደው በሬንቱ ላይ ለመመከት አስበውት የነበረው ከሸፈ። አቆርዳትን መያዘም አላስቸገረም። ከዚያ በኋላ ጦርነቱ እየጠጠረ ሄደ። የኢጣልያ አየር ኃይል የተቻለውን አደረገ። ነገር ግን ብዙም ሳይቆይ የእንግሊዝ አየር ኃይል የበላይነትን በማግኘቱ፣ በአካባቢው ያለውን የጣልያን ጦር እየደበደበ አደነዘዘው።

ከረንን የማስለቀቅ ፍልሚያ መጋቢት 6 ቀን 1933 ዓ.ም /ማርች 15 ቀን 1941/ ተጀመረ። ለሦስት ቀን ክባድ ሁኔታ ተካሄደ። ሎሬንሲኒ የተባለው የኢጣልያ ኮሎኔል ወጥሮ ያዘ። ከድካም የተነሣ ጦርነቱ ቀዘቀዘ። ሁለተኛው ዙር መጋቢት 16 ቀን /ማርች 25/ ተጀመረ። ሁለት ቀን የፈጀ ክባድ ፍልሚያ ከተካሄደ በኋላ ከረን ተያዘች። የተያዘችውም ሎሬንሲኒ ከሞተ በኋላ ነው። እንግሊዞች ከረንን የያዙት በሦስት ሺህ ወታደር ሕይወት መስዋዕትነት ነው። ከረን ከተያዘ በኋላ ችግሩ ቀለለ። አሥመራ መጋቢት 23 /አፕሪል 1

ቀን/ ተያዘች። ምፅዋ ደግሞ ሚያዝያ 1 /አፕሪል 8/ ቀን ከአሥር ሺህ ጣልያናውያን ምርኮኞች ጋር ተያዘች። ጦርነቱ ሲከፈት ጣልያን ዘጠኝ የመርከብ ማስጠሚያ መሣሪያ የተጫኑ መርከቦች /ዲስትሮየርስ/፣ ሰምንት የባሕር ውስጥ ጠላቂ መርከቦች /ሰብመሪንስ/ እና ሌሎችም ለልዩ ልዩ አገልግሎት የተዘጋጁ መርከቦች በቀይ ባሕር ላይ ነበሩአት። እነዚህን ሁሉ አጣች። ባሕሩ ለአሜሪካን መርከቦች ክፍት የሆነ ሰላማዊ አካባቢ መሆኑን ፕሬዚደንት ሩዝቬልት ገለጹ። በሕንድ ውቅያኖስና በሜዲትራኒያን ባሕር ያለው የውሃ መንገድ ለምዕራባውያን ሚያዝያ 4 /አፕሪል 11/ ቀን ተከፈተ።[7]

ከዚህ በኋላ ዋናው የእንግሊዝ ጦር ወደ ሊቢያ ወጣ። ከቀረው ጦር ከፊሉ ከአሥመራ በአዲካላ በኩል ወደ ጉንደር፣ ከፊሉ ደግሞ በአዲግራት በኩል ወደ አምባለጌ በመጓዝ ግዳጁን ተወጣ።

ኢትዮጵያን ነፃ ለማውጣት የተንቀሳቀሰው የእንግሊዝ ጦር ምን ያህል እንደ ሆነ በትክክል አልታወቀም። ኢጣልያ ከጦርነቱ የገባችው ባንዳውን ጨምሮ 350,000 ጦር በምሥራቅ አፍሪካ ቅኝ ግዛትዋ አከማችታ ነበር። አርበኛው ከባንድነት የከዳውን ጨምሮ 100,000 ቢሆን ነው። ስለዚህ የእንግሊዝ ጦር 100,000 ያህል ነበር ቢባል ብዙም ከእውነት የራቀ አይሆንም። አሰላለፉም፣

ሀ. ከካርቱም ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር በጐጃም፣ የኢትዮጵያን ስደተኞች ሳይጨምር 3,000፤

ለ. ከካርቱም በክሰላ በኩል 30,000፤

ሐ. ከካርቱም በአሶሳ በኩል 1,000፤

መ. ከናይሮቢ በሞቃድሾ በኩል፣ ስደተኛውን ሳይጨምር 60,000 ፤

ሠ. ከናይሮቢ በቦረና በኩል 5,000፤

ረ. ከናይሮቢ በጋሞ ጉፋ በኩል 1,000 ሳይሆን አልቀረም።

የክብር ጉዳይ ሆኖባቸው እንግሊዞች ተገቢ ግምት አይሰጡት እንጂ፣ የአርበኛው ኃይል ቀላል አልነበረም። ሰሞር ያደረገው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው። ዞሮ መሸነፉ አይቅር እንጂ፣ አርበኛው ባይኖር የጣልያን ጦር እንግሊዞችን ብዙ ያስቸግራቸው ነበር። ይህንን ሐቅ መካድ በታሪክ ፊት እውነት አይኖረውም። መሣሪያ ጨብጦ ከጣልያን ጦር ጋር ግንባር ለግንባር ገጥሞ የተዋጋው አርበኛ ቁጥር ከቦታ ቦታ፣ ከጊዜ ጊዜ ይለያያል። በ1933 ዓ.ም ለመጨረሻው ፍልሚያ የተሰለፈው ከ100,000 አያንስም።[8]

መሣሪያ የጨበጠ የአርበኛ ብዛት በየዘመኑ

አርበኞች	ለ1927 ዓ/ም ምርመራ የቀረበ	በ1928 ዓ/ም	በ1929 ዓ/ም	በ1930 ዓ/ም	በ1931 ዓ/ም	በ1932 ዓ/ም	በ1933 ዓ/ም
በጉንደር	15,000	1,000	2,000	6,000	10,000	7,000	25,000
በጐጃም	28,500	500	1,500	4,000	5,000	4,000	15,000
በትግራይ	3,400	500	200	500	400	300	2,000
በወሎ	2,250	500	100	300	200	-	1,000
በመንዝና ተጉለት	-	1,000	3,000	20000	10000	7,000	15 000
በይፋትና አንኮበር	-	500	1,500	5,000	3,600	2,500	5,000
በመርሐቤቴ ና ሰላሌ	-	500	1,500	5,000	4,000	3,000	5,000
በሁልጋና ሸንኮራ	-	15,000	10,000	30,000	20,000	11,700	20,000
በግንደበረት	-	500	200	3,000	2,500	1,500	4,000
በጉራጌ	-	3,000	5,000	5,000	4,000	3,000	5,000
በሸዋ	28,000	500	-	-	-	-	-
በወለጋ	-	10,000	300	300	200	-	1,000
በኢሉባቡር	-	1,000	-	-	-	-	1,000
በከፋ	15,000	-	-	-	-	-	-
በሐረርጌ	-	1,000	-	-	-	-	-
በአርሲ	500	-	-	-	-	-	-
በባሌና አርሲ		500	200	-	-	-	-
በጋምጐፋ	450	-	-	-	-	-	-
በሲዳሞ	550	5,000	3,000	200	100	-	-
ድምር	103,650	40,000	30,000	80,000	60,000	40,000	100000

ማጣቀሻ ፅሑፎች

1. ጳውሎስ ኞኞ፣ *የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦርነት*፣ ገጽ 207-211።
2. Winston Churchil, *The Grand Alliance*, p.6, 7, 16,17,79,90.
3. ከአባ ገብረ መስቀል /ብፅዕ አቡነ ዮሐንስ/ የተነገረኝ።
4. ሕይወቱ ጎደሩ፣ *ያቺ ቀን ተረሣች*፣ ገጽ 413።
5. ከአቶ ዓለመ ሥላሴ ጉላ የተነገረኝ።
6. ከበደ ተሰማ፣ *የታሪክ ማስታወሻ*፣ ገጽ 210-212።
7. Churchil, pp.88-90.
8. ሠንጠረዦን ይመልከቱ።

[1] የድል አጥቢያ አርበኞችን ጨምሮ።

ምዕራፍ ሃምሣ አራት
የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦርነት ፍፃሜ

ሙሶሊኒ ሰኔ 3 ቀን 1932 ዓ.ም ከሂትለር ጉን መቆሙን ለዓለም በይፋ አስታወቀ። ይህ መግለጫ ሲወጣ በኢጣልያ ላይ የፖለቲካ ሰማይ ተሰበረባት፣ የጦርነት እሳት ተቀጣጠለባት። ኢትዮጵያን ለማጥቃት እንዳሻት ትንደረደርበት የነበረው የስዊዝ ካናል የባህር ጉሮሮ ተዘጋባት። በአስፔይን ብጥብጥ ለመርዳት የተላከው የጣልያን ጦር እንደ ወጣ ቀረ። በአልባንያና በግሪክ ላይ የዘመተው ጦር በየተራ ተሸነፈ። በሊቢያ የነበረው ታላቅ ጦር ድል ተመታ። በምሥራቅ አፍሪካ የነበረው ሠራዊት ከጣልያን ጋር የነበረው ግንኙነት ተቋረጠ።

እንግሊዞች ከአፍሪካ፣ ከህንድ፣ ከሩቅ ምሥራቅ፣ ከአውስትራሊያና ከኒውዚላንድ ጦራቸውን ወደ ሰሜን አፍሪካና ከዚያም ወደ ማሕል አውሮፓ በፍጥነት ማንቀሳቀስ አስፈለጋቸው። የደቡቡን ግንባር ለማጠንከር። አንቅስቃሴው ወታደር ብቻ ሳይሆን ስንቅና ትጥቅም ይጨምር ነበር። ለዚህ እንቅስቃሴ የቀይ ባህር መለቀቅ ግድ ሆነ። የቀይ ባህር መለቀቅ ማለት ደግሞ የኢጣልያ ከምሥራቅ አፍሪካ ቅኝ ግዛትዋ መባረር ሆነ። ስለዚህ የኢትዮጵያ ነፃ የመውጫው ጦርነት በሦስት በር በአንድ ጊዜ ተከፈተ። ባለፉት ምዕራፎች እንዳየነው ንጉሠ ነገሥቱ ከለንደን ካርቱም ደርሰው በቢልያ በኩል ጉጃም ገቡ። የእንግሊዝ ጦር ከኬንያ በሞቃድሾና በበርበራ በኩል ሰብሮ ሐረር ገባ። ከካርቱም የተንቀሳቀሰው ጦር በክሰላ በተሰነይ አድርጉ የከረንን ጉራ ሰበረ። ቀይ ባሕር በእንግሊዝ የባሕር ኃይል ቁጥጥር ሥር ገባ። ጣልያኖችን አርበኛው በተጠናከረ ሁኔታ በየጎጡ አጠቃቸው። ከአሸናፊ ጉን በመቆም ጥቅሙን የማካበት ዘዴ የያዘው ባንዳ ካዳቸው። ከአርበኞችና ከነፃ አውጭው ጦር ጉን እየሆነ በገዛ መሣሪያቸው፣ እነሱ ባስተማሩት ዘዴ መልሶ ይወጋቸው ጀመር።

ይህ ሁኔታ በጣልያኖች ላይ ከፍተኛ ጭንቀት ፈጠረ። በተለይም በመሪዎቹ ላይ። ጀነራል ናዚ በአማራው አገር ያለውን ሁኔታ እየተዘዋወረ ከአየና ከገመገመ በኋላ፣ የተረፈውን ኃይል ሰብስቦ የጉንደርን ከተማና አካባቢ ያዘ። የወንድ ሥራ ለመሥራት የሞከረ እሱ ብቻ ነበር።

ከምሥራቅ የመጣው የእንግሊዝ ጦር አዲስ አበባ ለመግባት ሲያኮበኩብ፣ ዱካ ደ አመስታ ለከተማው ጥበቃ ወክሎ ወደ ሰሜን ጉዞውን ቀጠለ። ወደ ሰሜን የተጓዘው ተጨንቆ እንጂ ወዶ አልነበረም። አዲስ አበባ ላይ እዋጋለሁ ብሎ ቢፍደለደል በምሥራቅ የመጣው የእንግሊዝ ጦር ጣልያን ያፈረሰውን የአዋሽን ድልድይ መልሶ በመሥራት አዋሽን ተሻግሮ ሸዋ ምድር ገብቷል። አዲስ አበባ ላይ መዋጋት አርበኛው በሊያ የነበሩትን ጣልያናውያን ሴቶችና ልጆች እንዲፈተፍታቸው መንገድ መክፈት ሆነበት። ወደ ኢሉባቡር

መሄድም ጦሩን ከባህር በር ከማራቁም በላይ ጥቅጥቅ ከአለ ጫካ ወስጥ መስገሩ የሚያስጠቃው መሆኑን አወቀ። ስለዚህ ወደ ደሴ ሸሸ። ደሴ ሲደርስ ደግሞ ሌላ የባሰ ጭንቅ አጋጠመው። የእንግሊዝ ጦር እያባረረ ደረሰበት። አርበኛውም ተሰብስቦ ጠዘጠዘው። ወደ አሰብ መሄድ በጦርነቱ ጊዜ የመጣውን የጣልያን ጦር አፈር አስግጦ ያስቀረው የአፋር ሕዝብ እንደማይለቀው ተገነዘበ። ወደ ጉንደር የሚወስደው መንገድም በአርበኞች ተዘጋቦት። ስለዚህ ከዱካ ደ አምስታ ፊት ከተደቀኑት ውርደቶች ቀላሉ ወደ ሰሜን ተጉዞ አምባለጌ ተራራ ላይ ወጥቶ መሰቀል ሆነ። መጥፎ ምርጫ አልነበረም። ጀነራል ናዚ ግን አልወደደለትም። ከውየመድ እንደገባ ቆጠረው። ክሐረርጌ ሽሽቶ የመጣው፣ በማሕል ኢትዮጵያ የነበረው፣ ከጦጃም ወደ ሽዋ ከተሻገረው በመርሐቤቴ በኩል ወደ ሰሜን የወጣው፣ በወሎ የነበረው የጣልያን ጦር ጌታውን ተከትሎ አምባለጌ ወጣ።

ሦስተኛው ክፍል የጣልያን ጦር ወደ ኢሉባቡር ሄደ። ከእሱም ገሚሱ ከጦጃም ሸሽቶ ወደ ሽዋ ከተሻገረውና እንደዚሁም በደቡብ ክፍላተ ሀገር ማለትም በሲዳሞ፣ ቡጋሞንፋ፣ በከፋ የነበረው ነበር። በኢሉባቡር የነበረውም በዚያው ቦታውን አጠናከረ። በወለጋ የነበረውም ግንኙነት ፈጠረ።

ጠላት በዚህ ዓይነት ሲተረማመስ የእንግሊዝ ጦር መጋቢት 28 ቀን አዲስ አበባን ያዘ። ንጉሠ ነገሥቱ በጉጃም በኩል አድርገው ሚያዝያ 27 ቀን 1933 ዓ.ም ክመናገሻ ከተማቸው አዲስ አበባ ገብተው በትረ መንግሥታቸውን እንደገና መልሰው ጨበጡ።

ንጉሠ ነገሥቱ አዲስ አበባ ሲገቡ የጦርነቱ ሁኔታ ተሰወጠ። ኢትዮጵያ በመንግሥትነት ተመልሳ ቆመች። የኢጣልያ ጦር በተራው ሽፍታ ሆነ። የእንግሊዝ ጦር በኢትዮጵያ መንግሥት ረዳትነት በሦስቱም የጦር ግንባር ማለትም በኢሉባቡር፣ በጉንደርና በአምባሰጌ ተሰለፈ። ንጉሠ ነገሥቱ በሦስቱም የጦር ግንባር ከእንግሊዝ ጦር ጋር ተባብሮ ጠላቱን እንዲወጋ ሠራዊታቸውን አሠለፉ። በጉንደር በፊታውራሪ /ራስ/ ብሩ ወልደገብርኤል አዛዥነት የጉንደርና የጉጃም፣ እንደዚሁም ከሸዋ የተሻገረ አርበኛ ተሰማራ። በአምባሰጌ ግንባር የትግራይና የወሎ እንደዚሁም ከሸዋ የተላከ አርበኛ ከበበ። ወደ ኢሉባቡር በፊታውራሪ /ራስ/ መሥፍን ስለሽ፣ በወለጋ በፊታውራሪ /ደጃዝማች/ ከበደ ተሰማ የሚመራ ጦር ተላከ።

ኢትዮጵያ ጣልያንን በቶሎ ከሀገርዋ አስወጥታ ማባረር ነበረባት። የእንግሊዝ ጦርም በምሥራቅ አፍሪካ ያለውን ጉዳይ በፍጥነት አጠናቅቆ ለሰሜን አፍሪካው ጦርነት መድረስ ነበረበት። ስለዚህ ጦርነቱ በሁሉም ግንባር ተፋፋመ።

ፈጥኖ የወደቀው የአምባላጌው ግንባር ስለሆነ አስቀድሞ እሱን ማየት ይሻላል። በዚህ አውድ የትግራይ አርበኞች በየፊናቸው ተራራውን ከበቡ። ራስ /ልዑል ራስ/ ሥዩም እንደገና ተመልሰው በአርበኞች መካከል በመግኘት

የአርበኛውን ግንባር አጠናከሩ። ከአዲስ አበባ የወጣውና ከአሥመራ የመጣው የእንግሊዝ ጦር ደርሶ፣ ከተራራው ላይ ያለውን የጣልያን ምሽግ በመድፍ መደብደብ ጀመረ። አርበኛውም ቀስ በቀስ እየተሳበ ወደ ምሽጉ ተጠጋ።

ውጊያው ቀስ በቀስ እየጋለ ሄዶ ደንበኛው ጦርነት ሚያዝያ 29 ቀን 1933 ዓ.ም /አፕሪል 7 ቀን 1941/ ተከፈተ። በማግስቱ ሚያዝያ 30 ቀን እንግሊዞች አይሮፕላን ከአሥመራ እያስነሱ መደብደብ ያዙ። የጦርነቱ አስጨናቂነት ዕለት በዕለት እያደገ ሄደ። በራሱ በዱካ ደ አምስታ አገላለጽ ገሐነመ እሳት ሆነበት። በሦስተኛው ቀን ማለትም ግንቦት 1 ቀን 1933 ዓ.ም /ሜይ 9 ቀን 1941/ ጠላት ፈስገ እና አምባጉንጫ ከተባሉት ቦታዎች የነበሩትን ምሽጉች ለቀቀ። ግንቦት 2 ቀን ከሁለት መቶ ያላነሱ ባንዶች ከድተው ወደ ወገኖቻቸው ዞሩ። የእንግሊዝ አይሮፕላኖች ምሽጉን ለመናድ እያነጣጠሩ ይደበድቡ ጀመር። ግንቦት 3 ቀን አርበኛው የጣልያናውያኑን መታከሚያ ቤት ወሰደው። ግንቦት 4 ቀን አርበኞቹ ሰብቻቸው ማጥቃት ጀመሩ። ግንቦት 5 ቀን ድል መሆኑ እየተቃረበ ስለሄደ የጣልያን ወታደር በእላገፍ ላይ አጉረመረመ። ግንቦት 6 ቀን ዱካ ደ አምስታ የመጣው ቢመጣ ከነበረበት ቦታ ልውስ ላለማለት ወሰነ። ግንቦት 7 ቀን በተደረገው ቆጠራ ከእልቂት የተረፈው የጣልያን ጦር አንድ መቶ ሰባ ብቻ መሆኑ ተረጋገጠ። እንደ ዱካ ደ አምስታ ቃል በኢጣልያ ጦር ላይ ጭለማ ወደቀበት። የኢትዮጵያ እውነተኛ ታሪክ መዝገብ የሚገለጽበት ቀን ተቃረበ። ግንቦት 8 ቀን በተካሄደው ስሌት ምሽጉ በሠላሳ ሺህ ጥይት መደብደቡ ተረጋገጠ። በራሱ በዱካ ደ አምስታ አገላለጽ እልኩ ማለትም እዶቃው ደረሰ። የዕርቅ ንግግር እንዲጀመር ወሰነ።

ግንቦት 9 ቀን በጀነራል ትሬሣኒ አማካይነት የዕርቅ ድርድር ተጀመረ። አብረውት የነበሩት ሁሉ ከወጡ በኋላ ዱካ ደ አምስታ ወጥቶ አርበኞች በገሐድ በተቀመጡበት አደባባይ ለእንግሊዝ ጦር እጁን ሰጠ። ከዚህ በኋላ ግንቦት 10 ቀን ለቁስለኞች እርዳታ ተደረገ። ግንቦት 11 ቀን ክብረ በዓል ተደርጐ አንድ ቡድን የጥቁር /ኢትዮጵያ/፣ አንድ ቡድን የነጭ /እንግሊዝ/፣ አንድ ቡድን የቀይ /ሕንድ/ ወታደር ሰልፍ አሳየ። ጣልያን በመጋቢት ወር 1928 ዓ.ም ያለ አንዳች ችግር የያዘውን የአምባሰጌን ተራራ፣ ዱካ ደ አምስታ ግንቦት 12 ቀን 1933 አሣሩን አይቶ ለቅቆ ወጣ። ዱካ ደ አምስታም አንድ የወርቅ ኒሻን ማበቻ ጥብጣብ በእንግሊዙ ጦር አዛዥ በጀነራል ሜይን በአንገቱ ተጠልቆለት የምርኮኝነት ሥራ ጀመረ። በመኪና ወደ አሥመራ ከዚያም በአይሮፕላን ወደ ናይሮቢ ተወሰደ። እዚያም ከጦር ምርኮኞች እሥር እንደ አለ ሞተ።[1]

ሌላው የጦር ግንባር በኢሉባቡር ነበር። በሲዳሞ፣ በጋሞ ጐፋ፣ በአሩሲ፣ በባሌ የነበረው የጣልያን ጦር በሐይቆች አካባቢ ተሰበሰበ። በሞያሌ በኩል የመጣውና ከሞጆ የሄደው ፎር ተከተሰው። በፊታውራሪ /ደጃዝማች/

ገረሱ ዱኪና በሻለቃ በቀለ ወያ የሚመራው አርበኛ እየተከታተለ በየቦታው ቀጣው። የጠላት ጦር የአሞን ወንዝ ተሻግሮ ወደ ጅማ ተጓዘ። ከጦሻም ወደ ሽዋ የተሻገረው የጣልያን ባንዳ፣ ከብርቱ የአርበኞች ቅጥቀጣ ያመለጠው በተፍኪ፣ በወሊሶ እያደረገ የግቤን ወንዝ ተሻግሮ ጅማ ገባ። አንዱ ጦር የሚደርሰው ቀደም ብሎ የደረሰው ከተፈታ ወይም ከሸሸ በኋላ ስለነበር፣ ጅማ ላይ ለመዋጋት ያሰበው ሃሳብ ውጤት አላስገኘለትም። ስለዚህ ወደ በደሌ ሄደ።[2]

በዚያው የነበረውና ከምዕራብ ሽዋ ሸሽቶ የገባው የጣልያን ጦር ወለጋ ላይ ለመከላከል ሞከረ። በፊታውራሪ /ራስ/ መሥፍን ስለሽ ከሚመራው ጦር ጋር በግንቦት ወር 1933 ዓ.ም ገጥሞ አሥራ አራት ቀን ተዋጋ። ያለቀው አልቆ የተረፈው ወደ ነቀምቴ፣ ከዚያም ወደ አርጆ ሸሸ። ከዚያም የወዲሣን ድልድይ አፍርሶ ለሁለተኛ ዙር ጦርነት ተዘጋጀ። አባራሪው ጦር ደርሶ ሰኔ 12 ቀን 1933 ገጠመው። እስከ ሰኔ 14 ቀን ድረስ ከተዋጋ በኋላ ድል ሆኖ ወደ በደሌ በመሄድ እጁን ለኢትዮጵያ ጦር ሰጠ። በደሌ ላይ እጁን የሰጠው የጠላት ጦር ብዛት ከአንድ ሺህ አያንስም ነበር። አብዛኞቹ መኮንኖች ነበሩ።

ጀነራል ጋዜራ እጁን ላለመስጠት የመጨረሻ መከራ አደረጉ። ከሁለቱም ወገን ብዙ ጉዳት ከደረሰ በኋላ ድል ሆነ። ዘጠና ከባድ መኪና፣ ሰባት አውቶሞቢል፣ ሃያ ሁለት የመኪና መጐተቻ፣ በርካታ መሣሪያና ጥይት ተማረከ። ሆኖም ጀነራል ጋዜራ አሁንም እጁን ለመስጠት አልፈለገም። የገባንና የሦርን ድልድዮች በዲናሚት አፍርሶ ወደ ዩብዶ አመራ። የኢትዮጵያ ጦር ደርሶበት ትንሽ ከአንገራገረ በኋላ ወገን ያገኘ መስሎት እጁን ለቤልጅግ ጦር ሰጠ።

ከጅማ የሸሸው፣ ከማጂ የመጣውና የከፋው ጦር እየተጠረቃቀመ ወደ ጉራ ተጓዘ። የጉራ ከተማ በ1928 ዓ.ም መከላከያ እንድትሆን ተመርጣ እንደነበረችው ሁሉ፣ አሁንም በዚያ አካባቢ ለተከማቸው የጣልያን ጦር የመጨረሻ መፋለሚያ እንድትሆን ተመረጠች። የጠላት ጦር ከአርበኞች በየቦታው ከተቃጣበት ጥቃት እየተከላከለ፣ በዱረኒ በሱዴ አድርጉ በአማር በመከራ ጉራ ከተማ ገባ። የኢትዮጵያም ጦር ወዲያው ተከታትሎ ደረሰ።

ጦርነቱ ሰኔ 27 ቀን 1933 ዓ.ም ከጥዋቱ ለሁለት ሰዓት ሩብ ጉዳይ ተከፈተ። ከሁለቱም ወገን ከባድ ውጊያ ተደረገ። አልቂቱ እጅግ ከባድ ነበር። ከአርበኞች ወገን ከአምስት መቶ ሰው በላይ ሞተ፣ ብዙ ቆሰለ። ከጠላት ወገን ተሰልፎ ከነበረው 12,787 ወታደር መካከል ከአዛዡ በተሰጠው መግለጫ መሠረት ተርፎ በሕይወት የተማረከው 5,553 ብቻ ነበር። የቀረው ከዚያው ከጦር ሜዳው ላይ ተራግፎ ቀርቶአል ማለት ነው። ጊዜው ባያጥር ኖሮ ከዚያም የበለጠ እልቂት ሊደርስ ይችል ነበር። የጦርነቱ ክብደት ጊዜውን አሣጠረው። ከቀኑ ስድስት ሰዓት ሲሆን አቆመ።

ይህ የጦር ጉራ በኢትዮጵያ ሠራዊት ብቻ ተፈታ። ኢትዮጵያውያን አሸነፉ። ጣልያኖች ተሸነፉ። በዚያ የጦር ሜዳ የዋሉ ጀግኖች ነጭ አምራች ገበሬ ተባሉ። ይገባቸዋል። ከላይ ቁጥሩ የተጠቀሰውን የጣልያን ወታደር ጨርሰው 43 የውሃ መትረየስ፣ 150 ድግን መትረየስ፣ ቁጥሩ እጅግ የበዛ መሣሪያና ጥይት ማርከዋል። በጠቅላላው በኢሉባቡር አውድ የተማረከው የጦር መኮንንና ወታደር 19,750 ነበር። በምዕራብ ኢትዮጵያ የተካሄደው ፍልሚያ በእንዲህ ተፈጸመ። "በሰው እንበለው" የሚለው በፊታውራሪ /ራስ/ መሥፍን ስለሽ የሚመራው አርበኛ ዓርማ ዒላማውን መታ።[3]

የመጨረሻው የፍልሚያ አውድ ጐንደር ከተማ እንደምትሆን እየታወቀ ሄደ። ፊታውራሪ /ራስ/ ብሩ ወልደገብርኤል አርበኛውን እያስተባበሩ በንጉሠ ነገሥቱ የተመደበላቸውን ጦር እየመሩ ተጠጉ። ከዚያም የጦር ሠፈራቸውን ከእስቴ ወደ ምክሬ፣ ከዚያም ወደ አመሰ ወንዝ ሊማይ አዘዋወሩ። የእንግሊዝ ጦርም ተባበራቸው። አሳቸውም የእንግሊዝ ጦር፣ አርበኛውና ስደተኛው የደብረ ታቦርን ከተማ ከብቦ እንዲያጠቃ አዘዙ። ጦርነቱ ሰኔ 25 ቀን 1933 ዓ.ም ተከፍቶ በተቀላጠፈ ሁኔታ ተካሄደ። በምሥራቅ በእናቴቱ ማርያም፣ በምዕራብ በጠጋር ገብርኤል፣ በሌላው ቦታ ሁሉ የተሰለፈው ጥሩ ሥራ ሠራ። ጣልያኖች ደግሞ ባልተጠበቀ ሁኔታ አይሮፕላን አስነስተው ሊማዳ ከተባለው ቦታ በነበረው አርበኛ ላይ ብርቱ ጉዳት አደረሱ። በመሆኑም የደብረ ታቦር ከበባ ተጠናከረ። ደግሞም ከደብረ ብርሃን በደሴ በኩል የተላከው የሸዋ አርበኛ ከወሎ አርበኞች ጋር በመሆን በታንታ፣ በደላንታ፣ በዋድላ፣ በላስታ፣ በሣይንት የነበረውን የጠላት ጦር ድል እያደረገና ከየነበረበት ምሽግ እየነቃቀለ በዚሁ በሰኔ 25 ቀን 1933 ዓ.ም ደብረ ታቦር ዙሪያ ደረሰ።

ደብረ ታቦር የውጥር ተያዘች። ሕዝቡ ምሥጢሩን አስቀድሞ ተረድቶት ከተማይቱን ለቅቆ ወጥቶ ስለነበረ ጭንቁ የኮሎኔል አንጀሊኒ ሆነ። ሕዝብ ስንቅ ማቅረቡን ተወ። ጣልያን ከጐንደር ከተማ አህያ፣ ፈረስ፣ በቅሎ እያረደ ለጦሩ አበላ። ጭንቅ ሲበዛበት ከአለቃው ከጀነራል ናዚ የተሰጠውን ጥብቅ ትዕዛዝ ጥሶ የእጅ መስጠት ንግግር ከፈተ። ንግግሩ ከፍዳሜ ደረሰና ያለአንዳች ማወላወል ከእነሠራዊቱ እጁን ለፊታውራሪ /ራስ/ ብሩ ሰኔ 29 ቀን 1933 ዓ.ም ሰጠ።

ፊታውራሪ /ራስ/ ብሩ ለተሰቀቀው አገር አስተዳዳሪዎች መደቡ። ከጣልያን አብረው የተማረኩ ባንዶች ለአገራችን እንዋጋለን ስለአሉ ኃላፊ ሰጡአቸው። አካባቢውን በዚህ ዓይነት ከአረጋጉና ጦራቸውን ከአጠናከሩ በኋላ በብዙ ሥራዊት ታጅበው ከደብረ ታቦር ደጉማ ገቡ። በሜጀር ይገለስ የሚመራውም የእንግሊዝ ጦር አብሮአቸው ሄዶ በዚሁ ቦታ ሠፈረ።

ከዚህ በኋላ በፊታውራሪ /ራስ/ ብሩ ሠፊር ምክር ተደረገ። የጐንደር ዙሪያ ሦስት አራት ጊዜ ድርብርብ በሆኑ ተራሮች የተከበበች በመሆንዋ ናዚ

ሁሉንም ጦር አስፍሮባቸው እንደነበር ታወቀ። ሁሉን በአንድ ጊዜ ማስለቀቅ የሚቻል አልሆነም። ስለዚህ እያንዳንዱን ምሽግ እየነጠሉ መምታት እንደሚሻል ታመነበት። መጀመሪያ የሚደመሰሰው ቁልቁል በር ላይ የነበረው ምሽግ እንዲሆን ተወሰነ። የጐንደር አርበኛና እንደዚሁም ከንጉሠ ነገሥቱ የተላከው ስደተኛ በምሥራቅ ያለውን ተራራ ያዘ። ወደ ጐንደር ከተማ የሚወስደውን መንገድ ጭሀራ ላይ እንዲቆርጥ፣ በፊታውራሪ /ደጃዝማች/ ሀብተሥላሴ በላይነህ የሚመራው የሸዋ አርበኛ ማሕል ደንበያ ሠፈረ። ደጃዝማች ካሣ መሸሻ ምናልባት ከጐርጐራና ከጀንጓ የሚመጣ ረዳት የጠላት ጦር ቢኖር እንዲጠባበቁ ተደረገ። በሻምበል ማክለይን የሚመራው የእንግሊዝ ጦር ከጐንደር ከተማ ምሥራቅ ደንቀዝ ዓባይ ላይ ሠፈረ። የቁልቁል በርን ምሽግ ከብቦ ሁሉም በየበኩሉ በጠላት ላይ አደጋ መጣልና ራሱን መከላከል ሥራ አድርጐ ያዘ።

ይህ ሁኔታ ለጀነራል ናዚ ታውቆት ነበርና፣ ምንዛሮ ጫባ ከተባለው ተራራ ላይ በኮሎኔል ቶሬሊኒ የሚመራ ጦር ቀደም አድርጐ አሥፍሮ ነበር። ቶሬሊኒ የጦር ጥማት ስለነበረበት ቁልቁል በር ለተከበበው የጣልያን ጦር ስንቅ ሊያቀብል ከምሽጉ በካሚዮን ነሐሴ 12 ቀን ወጣ። ጉማሬ ከተባለው ቦታ ሲደርስ ጦርነት ገጠሙት። ከጥዋቱ 3 ሰዓት እስከ ምሽቱ 12 ሰዓት ከባድ ጦርነት ተካሄደ። ለሀገራችን እንዋጋለን ብሎ ለፊታውራሪ /ራስ/ ብሩ ቃል ገብቶ የተቀላቀለው የወሎ ባንዳ፣ ከሸዋ አርበኞች ጋር ሆኖ ጥሩ ሥራ ሠራ። የጥይቱ ውጊያ ወደ እጅ ቦምብ ሲዞር፣ በመቶ አለቃ /አባ/ ገሪማ ታፈረ አጣለጽ ምድር ቁልቢጥ ሆነች። ጦርነቱ የተካሄደበት ቦታ አንድ ትልቅ ከተማ የታታጠለ እስኪመስል ነደደ። ኮሎኔል ቶሬሊኒ ቀን ሲጨልም ሸሽቶ ከምንዛሮ ምሽጉ ገባ። የቁልቁል በር ከበባ ቀጠለ።

መለቀቅ ከነበረባቸው ቦታዎች አንዱ ጉርጉራ ነበር። አርበኞች የጠላትን ሽሽት ለመግታት ከከተማይቱ ወደ ጐንደር የሚወስደውን የመኪና መንገድ ከእንግሊዝ የተሰጣቸውን ፈንጅ ቀበሩበት። መቶ አለቃ ሶርዚዮ የጥይት ድምፅ መስማት አይወድምና፣ ጦር እገዛ የተቀበረውን ፈንጅ አስነሣ። አርበኞች ደግሞ ደሐና ከተባለው ቦታ አድፍጠው ጠብቀው፣ ፈንጂውን ያነሱትን ሃምሣ አለቃ ኖይቼንቲና ሌሎች 43 ወታደሮች ከነመቶ አለቃቸው ወዲያው ነሐሴ 29 ቀን 1933 ዓ.ም ጨረሱአቸው። ሃምሣ አለቃ ኖይቼንቲ በስም ተለይቶ በታሪክ መጠቀስ ያለበት ሰው ነው። ከጉጃምና ከጐንደር የሚማረኩትን አርበኞች የፊጥኝ እያሠረ ከነነፍሳቸው ጣና ባህር የሚጨምር ጨካኝ ነበር።

ጉርጉራን የማስለቀቁ ትግል ቀጠለ። ጣልያንም በበኩሉ አካባቢውን በፈንጂ አጥሮ ተቀመጠ። ፈንጂው እርስበርሱ በሲግሎ የተሳሠረ ነበረ። አደገኛ ስለሆነ፣ ደግሞም በጠላት ስለሚጠበቅ ፈንጂውን መፍታት አልተቻለም። ስለዚህ የእንግሊዙ ጦር አዛዥ ሻምበል ፔናሪክ ዘዴ ፈጠረ። ብቸኝ በሚባለው

ሜዳና በአካባቢው ያሉትን የዱር አራዊት አስከብቦ ወደ ጉርጉራ መራቸው። ከምሽጉ አቅራቢያ እንዲያድሩ አድርጐ ሌሊት ሲተኙ በአጠገባቸው ብዙ እሳት በማንደድ አስበረገጋቸው። ሲደነብሩ ሲባትሙን ስለበጣጠሱት ቦምቡ ሁሉ ፈነዳ። እነሱንም ጨረሳቸው። የቦምቡ አጥር ከተሰበረ በኋላ ጦርነቱ ቀጠለ። የጣልያኑ ጦር አዛዥ ያቀረበው የእርቅ ሃሳብ የማታለያ መሆኑ በአርበኞች ዘንድ ስለተደረሰበት ተቀባይነት ሳያገኝ ቀረ። የእሱ ሃሳብ የጐንደሩ ሁኔታ እስኪታወቅ ለመቆየት ነበር። አርበኛው በአካባቢው የነበሩትን መንደሮች ተቆጣጠረ። ጣልያንም መግቢያ መውጫ ሲያጣ ጠቃሚ ዕቃዎችንና የጦር መሣሪያዎችን ጣና ባህር ጨምሮ ተማረከ።

በጐንደር ክፍለ ሀገር ከተካሄዱት ጠንካራ ጦርነቶች አንዱ የውልክፈትን ምሽግ ለማስለቀቅ የተካሄደ ነበር። የተለየ ባህርይ ስለነበረው ለብቻው ተነጥሎ ቢታይ ይሻላል።

ጣልያን ከሚያዝያ 5 ቀን 1933 ዓ.ም ጀምሮ በተካሄደበት ጥቃት ተሸንፎ ዳባትን ከለቀቀ በኋላ፣ ውልክፈት በተባለው ተራራ ላይ የነበረውን ምሽግ አጠናከረ። ተራራው ስምንት ሺህ ጫማ የሚረዝምና ከባድ ቅዝቃዜ ያለበት ነበረ። ዳገቱ ቀጥ ብሎ የቆመ ከመሆኑ ጋር ሸርተቴ አፈር የነበረበትና ኮረኮንች ነው። ጣልያን ከባድ ጦር ከበቂ መሣሪያ ጋር አስቀምጦአል። ባንዶቹም እስከ መጨረሻው ለመከላከል ተዘጋጅተው ነበር። በዚህ ላይ ደግሞ ጣልያን መግቢያውንና መተላለፊያውን ሁሉ ፈንጅ ቀብሮበት ነበር። ስለዚህ ነፃ አውጭው ጦር ይህንን ሁኔታ አልፎ ምሽጉን ለመያዝ ከባድ ችግር ወደቀበት።

የውልክፈትን ምሽግ እንዲሰብር የተመደበው ጦር አዛዥ ሪንግሮስ የተባለ ሻለቃ ነበር። እሱም ችሎታ ስለነበረው ከኢጣልያ እየከዱ ለሀገራችን እንዋጋለን ያሉትን ባንዶች ተቀበሎና ሌሎችንም አስከድቶ፣ የሪንግሮስ ኃይል የተባለ ቡድን አቋቁሞ ከአንግሊዝ ከተመደበለት ጦር ጋር አስተባብሮ ይመራ ጀመር። በኢትዮጵያ ወገን ደግሞ ደጃዝማች አያሌው ብሩ ኃላፊ ሆነው የሀገሩን አርበኛ አስተባበሩ። የትግራይ አርበኛ በደጃዝማች ገብረሕይወት መሸሻ መሪነት ደረሰ።

ከዚሁ ዓይነት ዝግጅት በኋላ የውልክፈትን ምሽግ የማጥቃቱ ሥራ ተጀመረ። በሚያዝያ ወር ብቻ ስደስት ጊዜ ምሽጉን ለማጥቃት ታላላቅ ውጊያ ነበር፣ ግን ምሽጉ አልተበገረም። ቢሆንም ደባርቅ የነበረውን ምሽግ መስበር ተቻለ። ሌላው አርበኛ ሁሉ ተባብሮ እንደ ትግራይ አርበኛ ተልቡ ተዋግቶ ቢሆን ኖሮ፣ የውልክፈት ምሽግ በመጀመሪያው ዙር ውጊያ ተሰብሮ ጦርነቱ ያበቃና በተከታታይ ውጊያ ያለቀው ሠራዊት ይድን ነበር። ነገር ግን አብዛኛው አርበኛ ከተዋጊነት ይልቅ ተመልካችነት ስላበዛ፣ የውልክፈትን ምሽግ ለመያዝ የተደረገው መከራ ተወላከፈ። ከትግራይ አርበኛ ብዙ ሞተ። ሰማንያ አምስት ሰው ቀሰሰ።

የአርበኛው ችልተኝነት በእንግሊዞች ዘንድ ቅሬታ ፈጠረ። ተመክረና ተከታታይ ማጥቃት የሚደረግበት ዕቅድ ተዘጋጀ። ጣልያንም ስመ ጥር ባንዶቹን ሰውጊያ አቀረበ። ሁሰተኛው የውልክፊት ጦርነት ተካሄደ። ለባንዶቹ ጣልያን ብዙ ቦምብ እንደ አሸነማቸው ታውቆ ነበር። አርበኛው እያነጣጠረ ሲመታው እየፈነዳ ባንዶቹን ራሳቸውን ፈጃቸው። ጦርነቱ ከጥዋቱ አንድ ሰዓት እስከ ምሹቱ አሥራ ሁለት ሰዓት ቆይቶ ምንም ፋይዳ ሳያገኝ የሁሉቱም ወገን ጦር በየፊናው ተበተነ።

እጁን እንዲሰጥ ጥያቄ ቢቀርብለት፣ የጣልያኑ የጦር አዛዥ ኩሎኔል ጉኔላ ለዚህ ጉዳይ የሚጠየቁት ጀነራል ናዚ ናቸው አለ። ከጣልያን ከድተው ከኢትዮጵያ ጦር ጋር የተደባለቁት የቀድሞ ባንዶች፣ ጓደኞቻቸውን በስም እየጠሩ ምክር በመስጠት በአንድ ቀን አምስት መቶ ሰው አስከዱ። ተከትሎም የውልክፊት ምሽግ ከደብዓዚር በመድፍ እንዲደበደብ ተደረገ። ነገር ግን የጣልያን ጦር ጉድጓድ ቆፍሮ ከምድር ውስጥ ገብቶ ነበርና እምብዛም አልተጐዳም። ለሦስተኛ ጊዜ ምሽጉን የመስበር ሙከራ ተደረገ። ሆኖም አካባቢው በፈንጂ ታጥሮ ስለነበር መቅረብ አልተቻለም። ጥቂት በመገንተል የጠላት ጦር ከምሽጉ እንዲወጣ ተደረገ። ከአውላላ ሜዳ ላይ የእጅ ቦምብ ውርዋሮ ተያዘ። ጦርነቱ በሌላ ጊዜ ከተደረጉ ውጊያዎች የተሰየ ባሕርይ አሳየ። ሰምሃሌ አቶ ደሳለኝ የተባለ አንድ አርበኛና አንድ ባንዳ፣ እንድ የእጅ ቦምብ እንደኪስ እየተቀባበሉ እርስ በርሳቸው ተወራወሩ። እያንዳንዳቸው ሰባት ሰባት ጊዜ ከወረወሩት በኋላ፣ ቦምቡ በባንዳው ላይ ስለአረፈ ወደ ሰማይ አጉኖ ከአንድ ቁጥቋጦ ላይ ሰቀለው። እንግሊዞች እጅግ ተደነቁ። እንዲህም ተደርጉ ምንም ውጤት ሳያገኝ ቀረ። ብዙ አርበኞች ወደቁ።

አራተኛ ሙከራ እንዲደረግ ተወሰነና፣ ግንቦት 13 ቀን 1933 ዓ.ም ቆልቶ በባ በተባለው ቦታ ከነበረው ምሽግ ላይ ሌሊት አርበኞች አደጋ ጣሉ። አቶ በራሪ ጎላ የተባለ አርበኛ በመንገዱ ላይ ጠምዶበት የነበረው ቦምብ፣ ሰዕርዳታ በኳሚዮን የመጡትን አሥራ አምስት ጣልያኖች ፈጃቸው። ውጊያው ሞቅ ደመቅ ያለ ነበር። ያም ሆኖ አርበኞች ከጠላት አርድ ውስጥ እየገቡ ጉዳት ከማድረሳቸው በስተቀር ሌላ ውጤት አልተገኘም። የሻለቃ ሪንግሮስ ኃይል ግንቦት 15 ቀን ያደረገውም ሙከራ ውጤት አላስገኘም። በትግሉ አሥራ አራት ያህል ታዋቂ አርበኞች ወደቁ።

ለአምስተኛ ጊዜ ውልክፊትን ለመያዝ ተሞከረ። አርበኛው ጥቂት ዕረፍት ከአደረገ በኋላ፣ ሰኔ 15 ቀን 1933 ዓ.ም ከሌሊቱ በ10 ሰዓት በምሽጉ ላይ አደጋ ጣሉ። ጠንካራ ውጊያ ቢካሄድም የጠላት ጦር አልተበገረም። የሞተውን የቆሰለውን እየተራመደ ወደፊት ከማለት አልተመለሰም። ከጣልያን ከድተው አርበኛውን በማስተባበር ያዋጉ የነበሩት ደጃዝማች አያሌው ብሩ ቆስለው ተማረኩ። ጣልያን ሰፋክራ በጀው። በሰው ሽክም የቀረበው መድፍ ተማረከ። ሁለት ሀገር ወዳድ ወጣቶች በሁለት አጋሰስ ጥይትና ቦምብ ጭነው

ለኢትዮጵያ ጦር ሊያቀብሉ ሲመጡ ጠላት ስለደረሰባቸው፣ የተጫነውን ቦምብ በማፈንዳት ከመማሪያው ጋር እራሳቸውን አጠፉ። በጦርነቱ ሠላሳ ስምንት ሰው ሞተ። ሌላም ብዙ ቆሰለ። ሻለቃ ሪንግሮስ ጦሩን ይዞ ወቅን ወደ ተባለው ቦታ አፈገፈገ። ከዚያም ወደ ዘሪማ ወረደ።

ሻለቃ ሪንግሮስ ወደ አሥመራ ሄዶ ምክር ከተደረገ በኋላ፣ በአንድ ኩሎኔል የሚመራ አንድ ሺህ የሕንድ ወታደር የውልክፊትን ምሽግ እንዲሰብር ተላከ። ይህንን አስቸጋሪ ምሽግ ለማጥቃት ለስድስተኛ ጊዜ መከራ ተደረገ። ባንዳው ሕንዶችን ባደናገረ ሁኔታ በርትቶ ለጣልያን ተዋጋ። ሁለት ወንድሞቻቸውን ስለአቆሰሉባቸው ተናደው የሕንድ ወታደሮች በግሥጋሤ ደርሰው ሆድ ሆዳቸውን በሣንጃ በመውጋት እያፍተለተሉ በአየር ላይ ስለአንጠለጠሉአቸው ባንዶች ደነገጡ። የጦር አዛዦቸው በቦምብ ተመትቶ ስለሞተ ሕንዶች ደነገጡ። ቢሆንም በቶሱ አንሠራርተው የጠላትን ወታደር በመትረየስ እረፈረፉት። ምንም ውጤት ሳይገኝ ጀምበር ጠለቀች። ቢሆንም ብዙ ምርኮ ተገኘ። ሕንዶች በዚሁ ጦርነት በቃቸውና ወደ አሥመራ ተመለሱ። አርበኛው በየቀኑ መሠራጐዱን ቀጠለ።

ለሰባተኛው ዙር ጦርነት በአርበኞች ዘንድ ዝግጅት ሲደረግ ባንዳ ልቡ ወረደ። እስከ ዛሬ የምንዋጋው ከጥቁር ጋር ነበር፤ አሁን ግን የነጭ ጦር ስለመጣ በተራቸው ነጮች ይዋጉ ብሎ አደመ። ኩሎኔል ጉኔላ ጣልያናውንን ማስሰፍ ግድ ሆነበት። እሱ ራሱ አዝማች ሆኖ ቀረበ። አርበኞች እጁን በጥይት ስለሰበሩት ሽሹቱን ለቀቀው። ብዙ ጣልያኖች ቆሰሉ፤ ሌሎች ብዙ ተማረኩ። ጤናማው ምርኮኛ ቁስለኛውን እየተሸከመ በዛ ወደተባለው የኢትዮጵያ የጦር ሠፈር ወሰደ።

እንደገናም የስምንተኛው ዙር ጦርነት ተያዘ። ጣልያን ጫንቃ ከተባለው ቦታ ሆኖ ሴባ መውጫ የነበረውን የኢትዮጵያን ጦር ይጠባበቅ ነበር። የኢትዮጵያ ጦር ነሐሴ 18 ቀን 1933 ዓ.ም የተጠመደውን ቦምብ ሳይነካ በብልሀት አልፎ ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት አደጋ ጣለ። ጥይት ሳይተኩስ በእጅ ቦምብ ብቻ ተከላከለ። የጣልያን ጦር እጅን ሰጠ። ስድስት ጣልያኖች ሲሞቱ አንድ መቶ አምስት ተማረኩ። ከኢትዮጵያ ወገን ሠላሳ አንድ ሰው ወደቀ። ይህም ሁሉ ሆኖ የውልክፊት ምሽግ አልተነካም።

ዘጠነኛው ዙር ጦርነት ቀጠለ። የኢትዮጵያ ጦር ጫንቃ የተባለውን ቦታ ከያዘ በኋላ ወደ ዋናው ምሽግ ተጠጋ። ጣልያንም በበኩሉ የማጥቃቱን እርምጃ ለመግታት ነሐሴ 25 ቀን አደጋ ጣለ። ከድቼ ከርስዎ ሰው ልደባለቅ ነው በሚል ምክንያት ተጠግቶ፣ አንድ ባንዳ ቀኝዝማች ጣለው የተባሉትን ጀግና በጥይት ገደላቸው። አገዳደሉ የክህደት ክህደት ነበርና አሟሟታቸው ጓደኞቻቸውን አሰቀቀ። ይልቁንም ለሻለቃ ሪንግሮስ የኩሎኔልነት ማዕረግ ሲሰጥ ለአላቸውም ከአንግሊዝ መንግሥት ኒሻን አብሮ ደርሶ ነበርና፤

በአንገታቸው ማጥለቅ ቀርቶ በዓይናቸው ሳያዩት መሞታቸው እንግሊዞችን ቁምር አሳዘነ።

ሁኔታዎች በእንዲህ እንደ አሉ የውልክፈትን ምሽግ የሚይዝ በጀነራል የሚመራ ሌላ የኬንያ ጦር መታዘዙ ተሰማ። ይህ ደግሞ አዲስ ሹመት አግኝተው የተደሰቱትን ኮሎኔል ሪንግሮስን አስቆጣ። ድካማቸውን መና የሚያስቀርባቸው ሆነ። ስለዚህ በወታደሮቻቸው መካከል ቅስቀሳ አካሄዶ ውልክፈትን መያዝ ወይም ሞት አሸንአቸው። ምሽጉን ለመያዝ በሥልት የተቀነባበረ ሙከራ አደረጉ። ከበሩ ተባባሪዎች ውስጥ መሪ አዘጋጁ። ሁለት ዘበኞች ሌሊት ወደ ተራራው ጫፍ ያለ አንዳች ኮሽታ ኮሎኔሉ ራሳቸው የነበሩበትን ቡድን አወጡ። አብረዋቸው የነበሩት 12000 ወታደሮች በሰላም በሩን አለፉ። የመዋጊያ ድንጋጮቻቸውን በየግንባራቸው ኮሎኮሉ። ሲነጋ ምሽጉ ከአጠገባቸው መሆኑን አዩ። ጣልያኖች ከምሽጋቸው ወጥተው ይመላለሱ ነበር። ኢትዮጵያውያን ሰንደቅ ዓላማቸውን ከፍ አድርገው በብዙ ቦታ አውለበለቡ።

ጣልያን ይህንን ሲያይ ተኩስ ከፈተ። ኢትዮጵያውያን በጀግንነት ተዋጉ። እያንዳንዱ ሹም ቁልቱላውን በያለበት በረጅሙ አስነፋ። ድብልቅልቁ ወጣ። ኮሎኔል ጉኔላ እጅ ለመስጠት ፈቃደኛ ሆነ። በኢትዮጵያ ወገን በጸሐፈ ትዕዛዝ ኃይሌ ወልደ ሩፋ የሚመራ ቡድን በአሰበት ስብሰባ ንግግር ተደርጉ ከስምምነት ላይ ተደረሰ። በስምምነቱ መሠረት ኮሎኔል ጉኔላ መስከረም 18 ቀን 1934 ዓ.ም 7,655 ሰው እንደያዘ እጁን ሰጠ። መሣሪያውን አስረክቦ ዕለቱን ወደ ደብ ባህር ወረደ። ከዚያም ነጩ ወታደር 250 በሚሆን ካሚዮን ተጉዞ፤ አሥመራ ባልደሴራ ከሚባለው የጦር እሥር ቤት ታጉረ። የኮሎኔል ሪንግሮስ አመራር በመጨረሻ ግቡን መታ። ምስጋና ይገባቸዋል።

የውልክፈትን ምሽግ ለመያዝ በተደረገው ተጋድሎ ኢትዮጵያውያን ታላቅ አስተዋጽአ አድርገዋል። ነገር ግን የሚያሳፍርም ነገር ታይቶባቸዋል። እንደ ወትሮአቸው ከልብ ተዋግተው ቢሆን ኖሮ በመጀመሪያው ቀን ውጊያ ምሽጉ ይያዝ ነበር። ቢበዛም ከሁለት ወይም ከሦስት ቀን አያልፍም ነበር። በገዛ አረምዋ እባብ ይዛ አስፈራራች እንዳሉ፤ ኢትዮጵያውያን በዚያች ወሣኝ ቀን ችላ አሉ። ይህም በአንግሊዞች ዘንድ ከትዝብት ላይ ጣላቸው። ጦርነቱም የስድስት ወር ጊዜ እንዲወስድና የዘጠኝ ዙር ግጥሚያ እንዲጠይቅ ዕድል ሰጠው። የብዙ ሰው ደም ፈሰሰ።

ሌላም ከጉድ የሚቆጠር ነገር ነበር። ያንን ያህል መሥዋዕት ተከፍሎ 7,655 የጠላት ወታደሮች ሲማረኩ፤ 21.6 በመቶው ኢትዮጵያውያን ሆነው ተገኙ። እነዚህ እስከ ውልክፈት ምሽግ የመጨረሻ ሕቅታ ድረስ በክህደት ዐንተው ከጠላት ጐን በመቆም የተዋጉ በመሆናቸው፤ ሰፍርድ ቀርበው መቀጣት ሲገባቸው ተግሳጽ እንኳን ሳያገኛቸው ቀሩ። ይህም የማይበቃ ሆኖ

የተሰየ ጥበቃና እንክብካቤ ተደረገላቸው። ባለደሞቻቸው እንዳያጠቁአቸው በመኪና እስከ አድዋ ከተማ ተወስደው በነዓ ተስቀቁ። ንጉሠ ነገሥቱ ከመናገሻ ከተማቸው ገብተው መንግሥት እንደገና ከተቋቋመ ከአምስት ወር በኋላ እንደዚህ ሕግ መረገጡ ሳያስተዛዝብ አልቀረም።

ቀጥሎ መለቀቅ የነበረቡት የጀንዳ ምሽግ ነበር። በጉንደር የሚካሄደውን ጦርነት ወደ ፍጻሜ ለማድረስ ከጉጃም የተሳከው የእንግሊዝና የኢትዮጵያ ጦር በደንገል በር አድርጉ በግስጋሴ ደልጊ ደረሱ። ከዚያም በደንቢያ በኩል አድርጉ ጀብጀብና ወንበርዴን የተባሉትን ቦታዎች ጥጋት ያዘ። ዝግጅት ሲያደርግ ሰንብቶ መስከረም 27 ቀን 1934 ዓ.ም ሌሊት በምሽጉ ላይ አደጋ ጣለ። ኮሎሪኒ የተባለው የጣልያን መኰንን በጀግንነት ተከላከለ። የኢትዮጵያ ጦር አጠቃ። አሥር አለቃ ዘለቀ ጉየ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ከፍ አድርጉ በመያዝ ቀጥ ብሎ ቆመ። የመትረየስ ጥይት በዚያው እንደ ዝናብ ሲወርድ በመጨረሻም ሲመታ፤ ምንም ሳይወዛወዝ ሰንደቅ ዓላማውን ቀጥ አድርጉ እንደያዘ ተቀመጠ። የጠበቀ ጦርነት ተካሄደ ኮሎሪኒ ተማረከ። ከዚያ በኋላ ምርኮን መሰብሰብና ምርኮኛ መንዳት ሆነ።

ኮሎሪኒን ለመርዳት ከጃንጓ የመጣው ፊረስና ጦር ደረሰና አዲስ ጦርነት ተከፈተ። ሙሉ ቀን ሲዋጋ የዋለው የኢትጵያ ጦር ተዳክሞ ነበር። ቢሆንም በብርታት ተከላከለ። ሻምበል ታቲ የተባለ የእንግሊዝ መኰንን በጦርነቱ ሞቶ ነበርና፤ የእሱ ሬሣ የነበረበትን ቦታ የምትፈልግ አይሮፕላን ስለደረሰች የጠላት ጦር ደንግጦ ሽሽቱን ያዘ።

ጣልያንን ከየምሽጉቹ እየነቀሉ የማባረሩ ሥራ ቀጠለ። የኢትዮጵያ ጦር ጀንጓ ላይ የነበረውን ምሽግ ጥቅምት 3 ቀን 1934 ዓ.ም አጠቃ። ደንዲያ፤ ጉራምባ ላይ ተጋጠሙ። የጠላት ጦር ከሦስት ተከፍሎ በፊረስ መጣ። በላይ በኩል በደልኮ የተሸገረው ጦር ደህና አድርጉ ደበደበው። ተጫዋች በሚናህ ተብሎ የጨበጣ ውጊያ ተካሄደ። የጣልያን ጦር አዛዥ ወገጭ ከወንዙ ላይ ተገደለ። ምክትሉም ስለተደገመ ከሞት የተረፈው የጠላት ጦር ሽሽቱን ቀጠለ። ከጣልያን ወገን ሠላሳ አራት ሰው ሞተ። ሰባ ስድስት ቆሰለ፤ ስድሣ ተማረከ። ከኢትዮጵያ ወገን የሞተውም የቆሰለውም ጥቂት ነበር።

የኢትዮጵያ ጦር ድል ስለሸተተው እርምጃውን አፋጠነ። የጣልያንን ጦር ከጃንጓ አባረረ። ከዚያም በመከታተል በሰቀለት፤ በክልል፤ በሩፋኤል፤ በቆላ ድባ፤ በማርያም ደብር፤ በደርስጌ መሸጉ የነበረውን አንድ በአንድ እየወጋ ድል በማድረግ አስወጣው።

በዙሪያዋ የነበሩት ምሽጎች ሁሉ ከተለቀቁ በኋላ፤ የጉንደርን ከተማ ነፃ የማውጣቱ ዕቅድ ተዘረጋ። ከከተማይቱ አቅራቢያ ባሉት ተራሮች ላይ የነበሩት ምሽጉችም አንድ በአንድ በመደብደብ መለቀቅ ነበረባቸው። የቁልቁል በር መያዝ ወደ ጉንደር ከተማ ለመዝለቅ በር ክፋች ሆነ። ይህንን ምሽግ

ለመደምሰስ የመጨረሻው እንቅስቃሴ ጎንደር 5 ቀን 1934 ዓ.ም ተጀመረ። አርበኛና ስደተኛው ከእንግሊዝ ጦር ጋር በመተባበር በአራት በር ከበበ። አድፍጦ መጠበቅ ሲሰለችው በፊታውራሪ /ደጃዝማች/ ሀብተሥላሴ በላይነህ የሚራው ጦር ሰብሮ ለመግባት ሞከረ። በምሽጉ ዙሪያ የታጠረው ፈንጂ ፈንዳና ከቆሰለው በስተቀር ከሁለት መቶ በላይ ሰው አለቀ። ጥቂት እረፍት ከተደረገ በኋላ ጎንደር 12 ቀን ጦርነቱ እንደገና ቀጠለ። መነዛነዝ ሆነ። ይህ የሰለቻቸው ሦስት የእንግሊዝ ወጣት ወታደሮች በምቡ የተጠመደበትን ሲባጉ በመቀስ ቆርጠው ሲገቡ ጣልያን በመትረየስ ጨረሳቸው። ረዳቶቹ ምን ያህል መስዋዕትነት እየከፈሉ እንደሆነ ሲያይ፣ አርበኛውና ስደተኛው በያለበት ሥራውን ቀጠለ። የእንግሊዝ መድፎች ምሽጉን ደህና አድርገው ቀጠቀጡት። በአምስት ሰዓት በፊታውራሪ /ደጃዝማች/ ሀብተሥላሴ የሚመራው ጦር ፍርቋ በር የነበረውን ምሽግ ያዘ። በስድስት ሰዓት አንድ የእንግሊዝ ታንክ ወደ ምሽጉ ለመግባት ሞክሮ ሳይሳካለት ቀረ። በዘጠኝ ሰዓት ሌላ ታንክ መጥቶ እያባረረ ከምሽጉ ገባ። ኩሎኔል አጉሲኒ ነጭ ባንዲራ አሳይቶ እጁን ሰጠ።

ጣልያን የቁልቁል በርን ምሽግ ከለቀቀ ቀሪ ፍልሚያው ለጎንደር ከተማ ሆነ። የኢትዮጵያ ጦር እርምጃ በርምጃ ዐታ በማስለቀቅ ከበባውን እጠናከረ። ወታደርና መሣሪያ፣ ትጥቅና ስንቅ እንደ ልብ ለማቅረብ ጣልያን የሰበራቸውን ድልድዮችና ያበላሻቸውን መንገዶች መልሶ መሥራት አስፈለገ። ከውልክፌት ወደ ጎንደር ከተማ የሚወስድ መንገድ የተሰበረው ገደል፣ በበርሜል አፈር እየተሞላ እንዲደረደርበት ተደርጐ ተመልሶ ተሠራ። መድፎች ወጥተው በምሥጢር ተጠመዱ። ጎንደር ዙሪያ የነበሩት 29 የጣልያን አይሮፕላኖች ተደብድበው ወደሙ። በዚህ ሁኔታ ጀነራል ናዚ ከጀርመን ዕርዳታ የሚደርስለት ለማስመሰል የሚያደርገው ሙከራ ተበላሸበት። እንግሊዞች ዋናውን መንገድ በመተው ከአምባ ጊዮርጊስ በደንቀዝ በኩል አዲስ መንገድ አስከ ግራኝ በር ድረስ ከፈቱ።

የኃይል ድልድል ተሠራ። ልዑል አልጋወራሽ ኃይለሥላሴ ከአዲስ አበባ በደሴ፣ በአድዋና በአክሱም ዞረው ደርሰው ነበርና የአምባ ጊዮርጊስን በር ያዙ። ፊታውራሪ /ራስ/ ብሩ ወልደ ጻብርኤልና ጀነራል ፎክስ በአዘዞ ተሰለፉ። በትክል ድንጋይና በምባሻ ሽፈርድ እነ ቀኛዝማች ጣሹ እንግዳ ተመደቡ። ከወርገምበጭ በደበ በኩል አድርገው ደጃዝማች ብሩ ቃሲምና ሻምበል ካንፕል ተሠማሩ። ከአደባ በድፍጫ በኩል ደጃዝማች ሐጐስ ተሰማና ሻምበል ማክሊይን ተሰለፉ። ከጠዳ በፈንጠር ፊታውራሪ /ደጃዝማች/ ሀብተ ሥላሴ በላይነህና ሻምበል ፒልክቶ ተጠጉ። ከስቅሰት በልይታ ስምንት ደጃዝማቾች ሠራዊታቸውን ይዘው ተሰለፉ። ከኋላ አገር በቁስቋም በር ሦስት ደጃዝማቾች ቆሙ። የኢትዮጵያ ጦር የሚመራው በፊታውራሪ /ራስ/ ብሩ ወልደገብርኤልና በጀነራል ፎክስ ነበር። ጥንቃቄው የጐንደር ታሪካዊ ቅርሶች በጦርነቱ እንዳይጐዱ ብቻ ነው። የድሉ ጉዳይ አሳሳቢ አይደለም።

ጣልያንም በበኩሉ ለመጨረሻ ፍልሚያ ተዘጋጀ። ከጐጃም የወጣውን፣ ከወሎ የተሸገረውንና በጐንደር የነበረውን ጦር በሞላ አሰለፈ። ባንዳ ከግንባር ተሰለፈ። ከኤርትራና ከሶማሊያ የመጣው በማሕል ተመድቦ ነጩ ከውስጥ ሆነ። ሁሉም በቂ ምሽግ ነበረው። ምግብ ከገጠር እንዳይገባለት በመደረጉ ቢደክምም፣ ጦሩ የሚቻለውን ሁሉ ለማድረግ ዝግጁ ነበር።

ጊዜው በጣልያን ክባድ የፖለቲካ ደመና ያንዣበበት ነበር። የሰሜን አፍሪካው ጦርነት በጦር ኃይሎቹ አሸናፊነት ወደ መጠናቀቅ ተቃርቧል። በኢጣልያ አገር ታላቅ የፖለቲካ ማዕበል ተነስቶአል። ከሮም የሚሰጥ አመራር፣ ክብርሲን የሚደርስ ዕርዳታ አልነበረም። የሰሜን አፍሪካ ጦርነት በአንግሊዞች አሸናፊነት እየተጠናቀቀ ነው። ሊቢያ የነበረው የጣልያን ጦር ድምጥማጡ ጠፍቶአል። ባንዳ ልብ ስለወረደው የሚያስላስለው ነፍሱን የሚያድንበትን መንገድ ብቻ ነው። ንጉሠ ነገሥቱ አዲስ አበባ ገብተው አመራር ከያዙ ሰባተኛ ወራቸው ነው። አስተዳደራቸውን አጠናክረዋል። ስለዚህ የጐንደሩ ፍልሚያ ለኢጣልያ በአፍሪካ ምድር የመጨረሻዋ እስትንፋስ ናት።

ጎንደር 18 ቀን 1934 ዓ.ም ከጥዋቱ በአሥራ ሁለት ሰዓት ተኩስ ተጀመረ። መድፎች ከየአለበት አገሱ። ተከታትለውም መትረየሶች አስካኩ። ጠመንጃዎች ተንጣጡ። ውጤቶች መታየት ጀመሩ። እምቦዘና አጨናቅር የነበሩትን የጣልያን መድፎች፣ ወር ገምቦጭና አይባ ላይ የነበሩት የእንግሊዝ መድፎች ባፍባፋቸው ጥይት እየቀረቀሩ ፀጥ አሰኝአቸው። ብላጅግ ላይ የነበረው የጣልያን መድፍ ተካፓች ጥለውት ሄዱ። እንባ ማልዱባ ላይ የነበረው ቢሠራም፣ ብቻውን ውጤት ማስገኘት ሳይችል ቀረ። የእንግሊዝ አይሮፕላኖች ከዳባት እየተነሱ በጐንደር ከተማ አካባቢ የነበሩ የጣልያን የጦር ሠፈሮችን አቃጠሉ። የኢትዮጵያ ጦር ጐንደር ከተማ ለመግባት በየፊናው ተሽቀዳደመ። የእንግሊዝ ታንኮች ጣልያን ሠብሮት በነበረው የመገጭ ድልድይ ላይ መሻጋገሪያ ጥለው በመሻገር፣ የአዘዞን በር በመትረየስ ከፍተው ከጠዳ ወደ ጐንደር ገቡ።

የጣልያን ነጭ ወታደር /ሶልደቶ/ መንገዱን ይዞ ሲርመሰመስ፣ ታንኮች መተላለፊያ አጥተው ጥሩንባ እስክ መንፋት ደርሰው ነበር። ከከተማ በስተደቡብ የነበረው አርበኛ በፈንጠር አድርጐ፣ አዲስ ዓለምንና ፊት አቦን ከብዶ የነበረውን የጣልያን ጦር ሠብሮ፣ ከታንኮቹ ቀድሞ ጐንደር ገብቶ ምርኮ ጀመረ። በዚህ ጊዜ ናዚ አደባባይ ሊያሰኝ ነበር። የአርበኛውን አመጣጥ ሲያይ በፍጥነት ወደ መድኃኔዓለም ወጣና ነጭ ጨርቅ አሳይቶ የእጅ መረከቡ ሥራ ተጀመረ። አርበኛው ጉራያ ማስጫ ከግንቡ ሥር አደረ። የእንግሊዝ ታንክ ወደ አዘዞ ተመለሰ። ነገር ግን በምሥራቅ ወገን የተሰለፈው የኢትዮጵያ ጦር በደፈጣ የነበረውን የጠላት ጦር በኃይል ወግቶ ,ከአስለቀቀው በኋላ፣ ወደ

ከተማይቱ ለመግባት ሲሞክር ተቀብሮ የነበረው በምብ ፈንድቶ ጉዳት አደረሰበት። እርምጃውንም አዘገየበት።

ጎዳር 19 ቀን 1934 ዓ.ም ፊታውራሪ /ራስ/ ብሩ ወልደ ገብርኤል ከሜጀር ጀነራል ፎክስ ጋር ጉንደር ከተማ ገቡ። ባለህ እርጋ ተባለ። ረጋ። ናዚ አጽን በውል ለመስጠት ቢጠይቅ በጦር ኃይል ከተሸነፈ በኋላ ውል እንደማይገባለት ተነግሮት ያለ አንዳች ውል እጁን ሰጠ። በማግስቱ ልዑል አልጋ ወራሽ አስፋው ወለን ኃይለሥላሴ ጉንደር ከተማ ገቡ።

በኢጣልያ አጥቂነት በወልወል መንደር ጎዳር 27 ቀን 1927 ዓ.ም የተከፈተው ጦርነት፣ ከስድስት ዓመት በኋላ ጎዳር 1934 ዓ.ም በኢትዮጵያ አሸናፊነት ተጠናቀቀ። የጦርነት ፍፃሜ ያርገው።[4]

የኢጣልያን ጦር ከምሥራቅ አፍሪካ ጠራርጐ ለማስወጣት የተዘጋጀው ዕቅድ ሙሉ በሙሉ ግቡን መታ። ጠቅላይ ሚኒስትር ቸርችል ለንጉሠ ነገሥቱ በጻፉት ደብዳቤ "...በፋሽስትና ናዚስት ወንጀለኞች ከሀገራቸው ወጥተው ከተሰደዱ መሪዎች የመጀመሪያው እርስዎ እንደነበሩ ሁሉ፣ አሁንም ወደ ሀገርዎ በመመለስ የመጀመሪያው በመሆንዎ የተሰማኝን ታላቅ ደስታ፣ በእንግሊዝ ሕዝብና መንግሥት ስም ስገልጽልዎ ከፍተኛ ደስታ ይሰማኛል" የሚል ሆኑ።[5]

የኢጣልያን ጦር ከምሥራቅ አፍሪካ ለማስወጣት በተካሄደው ጦርነት የብዙ አገር ተወላጆች ተከፋይ ሆነዋል። ዋናውና አመራሩን የያዘው ጦር የእንግሊዝ ነው። በውስጡም የሕንድና የፓኪስታን፣ የደቡብ አፍሪካ ማለትም የናሚቢያ፣ የዙምባብዌ፣ የዛምቢያና የቦትስዋና ጭምር፣ ከምሥራቅ የኬንያ፣ የታንዛኒያና የኡጋንዳ፣ የሱዳን፣ የዛየርና የኮንጐ ብራዛቪል ሠራዊት ተዋግቶአል። እነዚህ ሁሉ ደማቸውን ለኢትዮጵያ ነፃነት አፍስሰዋል። ስለዚህ ክልብ እናመሰግናቸዋለን።

ማጣቀሻ ዕቱፎች

1. ሞገስ ክፍሌ፣ *የመሶሊኒ ምሥጢር*፣ ገጽ 161-163።
2. Richard Greenfield, *Ethiopia*, pages 263-264.
3. ታደሰ ዘወልዴ፣ *ቀሪን ገረመው*፣ ገጽ 362-364።
4. ገረማ ታፈረ፣ *ጉንደሬ ቢጋሻው*፣ ገጽ 266-294።
5. Winston Churchill, *The Grand Alliance*, p.90-92.

ምዕራፍ ሃምሣ አምስት
በጦርነቱ ውስጥ የእምነት ድርጅቶች ሚና

"ኢትዮጵያ ታበጽህ ዕደዊሃ ኅበ እግዚአብሔር።" በጦርነት ጊዜ የእምነት ድርጅቶች አቅዋም ወግኝነት አለው። ይህ ጉዳይ በመጻሕፍት የተገለጸ፣ በታሪክ የሚነበብ፣ በአበው የሚነገር፣ ዕለት ዕለቱም የሚታይ ነው። ማስረጃ ሊቀርብበት፣ ክርክር ሊካሄድበት አይገባም። ከዚህ የታሪክ መጽሐፍ ውስጥ መነሳት ያለበት ጥያቄ፣ "በኢትዮጵያና ኢጣልያ ጦርነት ጊዜ የእምነት ድርጅቶች አቅዋም እንደምን ነበር?" የሚለው ነው ። በየፊርጁ መመልከት ያስፈልጋል።

ሙሶሊኒ መስከረም 21 ቀን 1928 ዓ.ም /አክቶበር 2 ቀን 1935/ ለኢጣልያ ሕዝብ ንግግር አደረጉ። የንግግሩ ዓላማ የዓለም ማኅበር በመንግሥቱ ላይ ባደረገበት የኢኮኖሚ ጭቆና የኢጣልያንን ሕዝብ ቁጣ ለመቀስቀስ ነበር። ይህንን ንግግር ያደረገው በጀነራል ደቦኖ አዛዥነት 200,000 ወታደር ወደ ምሥራቅ አፍሪካ ከአዘመተ በኋላ ነበር። ሊቀ ጳጳሱ አባ ፓየስ 11ኛ ከየጦር መሣሪያው ዓይነት ቀርቦላቸው ቡራኬ ሰጡ።[1] በዓለም ላይ ካቶሊኮች በሙሉ የሊቀ ጳጳሱን ድርጊት በጸጥታ ተቀበሉ። አንድ ድምጽ ያሰማ የለም። ኢትዮጵያውያኑም እንኳን።

በአብዛኛው የካቶሊክ ተቆጣጣሪ የእንግሊዝ የፕሮቴስታንት ቤተክርስቲያን ናት። ለወትሮ ይህች ቤተክርስቲያን ጉዳዮችን ተመራማሪ በሆነ አመለካከት ታያለች። ድምዕዋንም ያለ ይሉኝታ ታሰማለች። ይህ ዘወትር የሚታይ ነገር ስለሆነ ማስረጃ ማቅረብ አስፈላጊ አይሆንም። ነገር ግን በ1928 ዓ.ምቱ የጣልያን ወረራ ጊዜ አንዳች አላለችም። አንዳች አላደረገችም። ቢሆንም እየቆጠቆጣት ሄደ። የእንግሊዝ የበላይ ምክር ቤት ሐውስ ኦፍ ሎርድስ ግንቦት 10 ቀን 1929 ዓ.ም /ሜይ 18 ቀን 1937/ በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ ተከራከረ። የእንግሊዝ ቤተክርስቲያን መሪ የሆኑት የካንተርበሪው ሊቀ ጳጳስ፣ ለምክር ቤቱ ኢትዮጵያን በመደገፍ ንግግር አደረጉ። ኢትዮጵያ መሬትዋን ቀንሳ ለዕርቅ ልትሰጥ እንደማታስብ ጠቅሰው ተናገሩ። ምክር ቤቱም የጣልያንን አጥቂነት ተገንዝቦ ይዞታዋን ሳያውቅላት ቀረ።[2]

የአሜሪካን አብያተ ክርስቲያናት የተረጋገጠ አቅዋም አልነበራቸውም። እንደዚሁም እንደ ካናዳ፣ አውስትራሊያ፣ ኒውዚላንድ። በጀርመን አገር የናዚ ተዕዕኖ ጠንክሮ ስለነበር አንዳች የማለት ዕድል አልነበራቸውም። የስካንድናቪያ አገሮች ማለትም የስዊድን፣ የኖርዌ፣ የዴንማርክና የፊንላንድ አብያተ ክርስቲያናት ዓለሙን በፀጥታ የሚመለከቱ እንጂ፣ እንደ ኢትዮጵያ ላለች ትንሽ አገር ብለው ከነገር አጣብቂኝ ውስጥ የመግባት ፍላጐት አልነበራቸውም።

የራሺያ ቤተክርስቲያን ኦርቶዶክሳዊት በመሆንዋ ለኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ቀረቤታ አላት። በወቅቱ የኮሚኒዝም ተፅዕኖ ነበረባት። ቢሆንም መንግሥቱ የኢጣልያ ደጋፊ ስለአልነበረ ድምፅዋን ለማሰማት የሚከለክላት ነገር አልነበረም። ነገር ግን ምንም ድምፅ አላሰማችም።

የእስልምና እምነት የራሱ ጉዳይ እስከ አልሆነ ድረስ ከሌሎች ጉዳይ አይገባም። ስለዚህ ስለኢትዮጵያ መወረር ድምፁን የሚያሰማበት ሁኔታ አልነበረውም።

በዓለም ዙሪያ የነበሩ የእምነት ድርጅቶች አቅዋም ከቃኘን በኋላ ወደ ሀገር ውስጥ እንመለሳለን። በዘመኑ በሀገር የነበሩት እምነቶች ሦስት ነበሩ። ኦርቶዶክስ ተዋህዶ፣ ካቶሊክና እስላም። የፕሮቴስታንቶች ቁጥር እጅግ አነስተኛ ነበር። ካቶሊኮች ኢትዮጵያውያንም ጭምር ከወራሪዋ ከኢጣልያ ወገን ሆኑ። እስልምና ከጠላት ወገን የሚነዛውን የጥላቻ ማኒሰሻ ፕሮፓጋንዳ ከመታገስ አልፎ በተከላካይነት የመቆም አቅም አልነበረውም። ስለዚህ ወራሪውን የመከላከል ዕድል ፈንታ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ሆነ። በዚያን ጊዜ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን በግብፅ ቤተክርስቲያን ሥር ነበረች። ሊቀ ጳጳሱ አቡነ ቄርሎስም ግብፃዊ ነበሩ። ደግሞም ከግብፅ መንግሥት እምብዛም ተፅዕኖ አልነበረባትም። ድምፅዋን ማሰማት ትችልም ይገባትም ነበር። ነገር ግን አንዳች አላደረገችም።

አቡነ ማቴዎስ ከአፄ ምኒልክ ጋር አድዋ ድረስ ዘምተው፣ የጦርነቱ ዕለት በነበሬ ሀናይነት ቀድሰው፣ ከጦሩ ግንባር ላይ ታቦታቸውን ይዘው በመቆም አዋግተው ነበር። ከዚያም በፊት የነበሩ ግብፃዊያን ጳጳሳት በጦር ጊዜ ከነገሥታቱ አይለዩም ነበር። ነገር ግን በወቅቱ የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ የነበሩት አቡነ ቄርሎስ እንዲህ አላደረጉም። ብቻ ከታህሣሥ 13 ቀን 1928 ዓ.ም ጀምሮ ለአንድ ሣምንት ጾም ጸሎት፣ ሀዘን እንዲደረግ፣ ታህሣሥ 8 ቀን 1928 ዓ.ም መልዕክት ለመላው ሕዝበ ክርስቲያን አስተላለፉ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ምእመናን ግን ምህላውን እስከ ዘለቂታው ተያያዙት።[3] እንደዚሁም ሊቀ ጳጳሱ አቡነ ቄርሎስ ጥር 9 ቀን 1928 ዓ.ም ለጉጃም ሕዝብ መልእክት አስተላለፉ። ጉዳዩ ከጦር ሜዳ ከድተው ወደ ሀገራቸው ስለተመለሱት ስለ እነ ደጃዝማች ገሠሠ ነበር። ቃሉን ማጤን ደግ ስለሆነ ፍሬ ነገሩን እንጠቅሳለን።

ደብዳቤው መንፈሳዊ ሰላምታ ከሰጠ በኋላ "...የጣልያኖች ሃሳብ... የኢትዮጵያን ሕዝብ እርስ በራሱ እያጣሉና እያፋጁ... ሰተት ብለው ገብተው ርስታችሁንና ገንዘባችሁን ሳሽከርኑት፣ ሴት ልጃችሁን ለግርድና ለማድረግ ነው..." ብሎ የወረራውን ዓላማ ያስረዳል። ከዚያም በማያያዝ የደጀች ገሠሠን ክህደት ያስረዳና፣ አገሩን ኢትዮጵያንና ንጉሠ ነገሥቱን የከዳውን ቢሞት ካህናት እንዳይፈቱት፣ በቤተ ክርስቲያንም እንዳይቀብሩት በታህሣሥ 8 ቀን

ያስተላለፉትን ውግዘት ይጠቅሳል። አያይዞም የርሱን ነገር እንዳይሰሙት፣ እንዳይከተሉት፣ እህል ውሃም እንዳይሰጡት፣ በቤታቸውም እንዳያሳድሩት ያዛል። ቀጥሎም መልእክቱ "ደጃች ገሠሠንና ሌላውንም እንደርሱ ያለውን ከሐዲ አትከተሉ። ጣልያኖችም ...በተንኮል የማታሰልና የሐሰት ቃል እየጻፉ በአውሮፕላን ቢበትኑላችሁ አትመኑ...ከጥንታዊ ንጉሠ ነገሥታችሁ ኢጣልያ የሚሻል እንዳይመስላችሁ አስጠነቅቃችኋለሁ። ...ምክሬንና ቃሌን ባትሰሙ ግን እንደ አርዮስ አወግዛችኋለሁ። ረግሜያችኋለሁ" በማለት ቃሉን ይደመድማል። ነገር ግን ሊቀ ጳጳሱ ወደ ጦርነቱ ሰመሄድ አልተንቀሳቀሱም። ንጉሠ ነገሥቱም የፈረንጅ አማካሪ ከማግበስበስ እንደ እኚህ ያሉትን ፅኑዕ መንፈሳዊ አባት ይዘው መዝመት ፀጋ ያስገኝላቸው ነበር።

በዚህ ዓይነት ቤተክርስቲያኒቱ ከውጭ ያለድጋፍ፣ ከሀገር ውስጥ ያለ ዕርዳታ ብቻዋን ቆመች። ከመንፈሳውያን አባቶች መካከል ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ፣ እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ/ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ/፣ ሊቀ ሊቃውንት ገብረ አብ ዘመቱ። በጦርነቱ ላይ ቆመ።

እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ ማለትም የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ፓትርያርክ ሰባት ሐዋርያዊ መልእክቶች አስተላለፉ። ከእነዚህ መልዕክቶች የመጀመሪያው ጎዳር 17 ቀን 1928 ዓ.ም ተሳለፈ። አሱም ክርስቲያኖች እንደ ሰማዕታት ደማቸውን ለሀገራቸው ለኢትዮጵያ እንዲያፈሱላት የሚጠይቅ ነበር። ደማቸውን የሚያፈሱት፣

1ኛ. ስለ ሃይማኖታቸው፣
2ኛ. ስለ ንጉሠ ነገሥታቸው፣
3ኛ. ስለ ሀገራቸው ነፃነት፣
4ኛ. ስለርስታቸው፣
5ኛ. ከራሳቸው ጀምሮ ስለወገናቸው፣ እንደሚሆን የሚያስገነዝብ ነበር። አያይዞም እነ ጌዲዮን፣ እነ ሳዶቅ፣ እነ ዮፍታሔ፣ እነ ሳምሶን፣ እነ ዳዊት፣ እነ ሣሙኤል ሌሎችም በሃይማኖታቸው ጸንተው በመዋጋታቸው ድል እንደ አገኙ፣ እነሱም በነፍስ በሥጋ ክብር እንደወረሱ የሚያስረዳ ነበር። በመጨረሻም "...ጣልያንን በማፍ ከያዘብን ርስታችን ለማባረር የማይረዳውን ሰው፣ ወደሱም ለመክዳት የሚመሳጠረውን ሁሉ...ካባቶቼ ከሐዋርያት ባገኘሁት ሥልጣን ገዝቻለሁ" በማለት ደመደሙ።[4] ምዕመናን ይህንን ቃል ሰሙ። ምህላም ተያዘ። ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስና እጨጌው ወደ ዘመቻው ሄዱ።

በጥንቱ ሥርዓት የውጭ ወረራ በመጣ ጊዜ ካህናት ታቦተ ሕጉን ይዘው በግንባር ይቆማሉ። ነገር ግን በሀገር ውስጥ ለሚካሄድ የርስ በርስ ጦርነት ታቦት አይቆምም። ከልጁ ከአቤሰሎም ጋር ይዋጋ በነበረ ጊዜ ካህናቱ የእግዚአብሔርን ታቦት ይዘው ወደ አሱ በመጡ ጊዜ ዳዊት "...በእግዚአብሔር ዓይን ሞገስ አግኝቼ እንደሆንሁ መልሶ አርሱንና ማደሪያውን ያሳየኛል። ነገር ግን አልወድህም ቢለኝ እነሆኝ ደስ የሚያሰኘውን ያድርግብኝ..." ብሎ

የእግዚአብሔርን ታቦት ወደ መኖሪያው ወደ ኢየሩሳሌም እንዲመልስ ሳደቅን አዘት ነበር።[5] ጦርነቱ ከጥፋት ወረራ ለመከላከል በመሆኑ በዚህ ሥርዓት መሠረት ኢትዮጵያዊው ሊቀ ጳጳስ አቡነ ጴጥሮስ አጨዜው ሦስት ታቦቶች ይዘው ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር ዘመቱ።

ወደ ማይጨው ጦርነት የዘመቱት ታቦቶች

ከተጉለት፣ የደብረ ዊዕ ድንበሮ /ማንባርዎ/ ቅድስት ማርያም፣

ከአዲስ አበባ፣ የአራዳ ደብረ ፅጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ፣

ከአዲስ አበባ፣ መንበረ መንግሥት ቅዱስ ገብርኤል ነበሩ።

ከእያንዳንዱ ቤተክርስቲያን አለቃውና አሥር ካህናት ዘመቱ። ገዛው ታቦታቱ ታዝሰው በእግር ነበር። በየዕለቱ ጥዋት ምህላ፣ ማታ የማስታኮት ፀሎት ይደረጋል። ታቦታተ ሕጉ በአደሩበት አካባቢ ከአለ ቤተክርስቲያን፣ ከሌለ በድንኳን ያድራሉ። በዕለተ ሰንበት እና በታቦቶቹ በዓላት ቀን ይቀደሳል።

ቀደም ብሎ በንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ዘመነ መንግሥት ከግብጽ ቤተ ክርስቲያን ጋር ንግግር ተደርጎ፣ አራት ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት በክይሮ ከተማ ተሹመው ስለነበር፣ የኢጣልያ ወረራ በተነሣ ጊዜ አንድ ግብጻዊ ሊቀ ጳጳስና አራት ኢትዮጵያውን ጳጳሳት ነበሩ። እነሱም፣

አቡነ ቄርሎስ ግብጻዊ ሊቀ ጳጳስ፣

አቡነ ጴጥሮስ ኢትዮጵያዊ ጳጳስ፣

አቡነ ሚካኤል ኢትዮጵያዊ ጳጳስ፣

አቡነ ይስሐቅ ኢትዮጵያዋ ጳጳስ፣

አቡነ አብርሃም ኢትዮጵያዊ ጳጳስ ነበሩ።[6]

ነገር ግን ከእነዚህ አምስት ሊቃነ ጳጳሳት ከኢትዮጵያ ሠራዊት ጋር በጦር ግንባር የቆሙ አቡነ ጴጥሮስ ብቻ ነበሩ። ሌሎች ጸጥ ብለው በየቤታቸው ተቀመጡ። ይህ ግብራቸው በተለይ ለኢትዮጵያኑ ጳጳሳት መንፈሳዊ አባትነታቸውን አረከሰው። የእያንዳንዱ ታሪክ በቦታው ላይ ተነግሮአል።

ከላይ ስማቸው የተዘረዘረው አራት ታቦታት እስከ ማይጨው ተጉዘው በጦርነቱ ግንባር ቆሙ። ከጦርነቱ ላይ ውለው ማታ ወደማደሪያቸው ተመልሰው ገቡ። ከዚያም ተጉዘው ከየቤታቸው በሰላም ገቡ። አንድም ካህን አልሞተም። ይህ ብቻ አይደለም። ሌላም ድንቃ ድንቅ ሥራ ታይቶአል። ጎንደር 27 ቀን 1928 ዓ.ም ደሴ ድንበሬ ማርያም ባለችበት ቦታ ከሚደርሰው ምሕላ ላይ ንጉሠ ነገሥቱ ተገኝተው ነበር። ታቦትዋ ያለችው ቀድሞ የጣልያን ቆንሲል ይኖርበት ከነበረው ቤት ነበር። ጣልያኖች በዚያች ዕለት ጥዋት 21 አይሮፕላኖች ልከው ቤቱንና አካባቢውን አስደበደቡ። ቅድስት ማርያም ባደረችበት ቤት ላይ ከሠላሳ ያላነስ ቦምብ ወደቀ። በአካባቢው ደግሞ ሌላ ሰባ። በአሥት ቤቱ ላይ የተጣሉት ቦምቦች እየተንከባለሉ ከመሬት ወደቁ። አንዳቸውም ሳይፈነዱ ቀሩ። ንጉሠ ነገሥቱ ቦምቦቹን ከአንድ ቦታ አሰባስበው

ከላያቸው ቆመው እግዚአብሔርን አመሰገኑ። ካህናቱንም የአናንተ ፀሎት እንደዚህ ያለ ድንቅ ሥራ ይሠራልና በርቱ ብለው አመሰገኑአቸው። በዚህ ቀን የጊዮርጊስና የገብርኤል ጽላቶች ደሴ መድኃኒዓለም ቤተክርስቲያን ውስጥ አድረው ስለነበር ከጸሎት ቤቱ አልነበሩም።[7]

በጦርነቱ ድል ለጣልያን እንደሚሆን የሚያሳዩ ልዩ ልዩ መንፈሳዊ ምልክቶች ነበሩ። ለምሣሌ ቡልጋ ሙገሬ ላለ የተባለ የመንግሥት ደን አለ። ከዚያ ደን ውስጥ የአምሃየስ ሽንጥ የሚባል መለሎ ረጅም ዛፍ ነበር። በዙሪያው ደግሞ ሌሎች ስድስት መለሎ ዛፎች ነበሩ። በዙሪያ ያሉት ስድስቱ በመካከል ከአለው ከዋና በውፍረትም በቁመትም ጥቂት ጥቂት ያንሱ ነበር። መጋቢት 21 ቀን ሰኞ በመንፈቀ ሌሊት እንደ መብረቅ ያለ ታላቅ ድምፅ ተሰማ። አካባቢው በድንጋጤ ከእንቅልፉ ተቀሰቀሰ። ድምፅ የተሰማው ዛፎች ሲወድቁ ናሮአል። ስድስቱም ተሰባብረው ወድቀዋል። የተረፈ የለም። ሕዝቡ ይህንን ሲያይ አዘነ፣ ደነገጠ። በነጋታው መጋቢት 22 1928 ዓ.ም ማክሰኞ ንጉሠ ነገሥቱ በቆመበት በማይጨው ጦር ግንባር ኢትዮጵያ ድል ሆነች።

ሙሶሊኒ የኢትዮጵያን ሕዝብ እርስ በርሱ ከፋፍሎ ለማጨራረስና ሀገሩቱን ለመግዛት የነበረውን ዓላማ ከግብ ለማድረስ በትሪፖሊ ከተማ በ1929 ዓ.ም አዋጅ አስነገረ። አዋጁም "የፋሽስት ኢጣልያ መንግሥት በሊቢያና በኢትዮጵያ ለሚኖሩ እስላሞች የሰላም ዋስትና ለመስጠት አስቦአል። ትክክለኛ ፍትሕና ብልጽግናም ለእስላሞች ያደርጋል። የነቢይ መሐመድንም ሕግ ያክብራል። ከዚያም በላይ ለመላው ዓለም እስላሞች ያለውን ሕግና መልካም አስተሳሰብ ሊገልጥ ይወዳል" የሚል ነበር። ከዚህም በስተቀር ብዙ የሮም ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ካህናት የወታደር ልብስ ለብሰው ከኢጣልያ ወታደር ጐን መቆማቸው ታውቆአል። ይህ ሁኔታ ሲታይ የሮም ካቶሊክ ካህናት መሣሪያ ጨብጠው ኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖችን በመጨፍጨፍ፣ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያንን በማቃጠል ሥራ ተሰማርተዋል ማለት የሚያስኝ አሳፋሪ የታሪክ ክስተት ነው።

ጣልያን አዲስ አበባ እንደ ገባ ንጉሠ ነገሥቱ ወደ አውሮፓ እንደሄዱ ሲሰማ ታላቁ ሥራ የዕርቅ ጉዳይ ሆነ። በሰውና ሰው፣ በአገርና አገር የነበረውን መቃቃር ለማብረድ ጥረት ተደረገ። በዚህ ረገድ ዋናውን ሚና የተጫወቱት ካህናት ነበሩ። መስቀል ይዘው በሽማግሌ የተያዘው እርቅ አስከፊዐም ይቆማሉ። ራሳቸውም ከሽምግልና ውስጥ ይገባሉ። እምቢ ያለውን ወገን ቀሳውስትና መነኮሳት ይገዝታሉ። ጥፋቱን አምኖ ሲመለስ ደግሞ ፀሎት አድርገው ግዝታቸውን ይፈታሉ። እርቅ በተደረገ ቁጥር ጸሎት አድርገው ይባርካሉ።

የኢትዮጵያ አርበኞች አዲስ አበባን ለማስለቀቅ በዘመቱ ጊዜ፣ አቡነ ጴጥሮስ ከደጃዝማች አበራ ካሣ ሠራዊት ጋር ተሰለፉ። በወታደሩና በእሳቸው መካከል ሁለት ልዩነቶች ነበሩ። ከእነዚያ ልዩነቶች አንደኛውና ዋነኛው፣

አሳቸው ቆራጥ ሠራዊቱ አመንቺ መሆኑ ነው። በዚህ የተነሣ ሠራዊቱ ወደ ኋላው ተመልሶ አሳቸው ግን ወደፊታቸው ተራመዱ። ሁለተኛው ልዩነት ሠራዊቱ የታጠቀው መሣሪያ፤ አሳቸው መስቀል መሆኑ ነበር። ሰተት ብለው ጣልያን ከነበረበት ገቡ። የጣልያንን ገዥነት ተቀብለው በሰላም እንዲኖሩ ቢጠየቁ አላደርገውም አሉ። "...ለኢጣልያ የተገዛችሁ ውግዝ ሁኑ። መሬትዋም አትገዛልህ። ገዝቻለሁ..." ብለው ጣልያንን ራሱን ጭምር አወገዙ። በኢጣልያውያን ዳኞች የተወሰነባቸውን የሞት ፅዋ ሐምሌ 23 ቀን 1928 ዓ.ም ተቀበሉ። ፊሳቸውም ወደ አልታወቀ ቦታ ተወስዶ ተቀበረ።

ሌላው ሰማዕት አቡነ ሚካኤል ነበሩ። አሳቸውም ከአርበኛው ጋር ከጉራ ከተማ በስተምሥራቅ በምትገኘው ሣምቤ ከምትባለው ቦታ በተደረገው ጦርነት ጎዳር 17 ቀን 1929 ዓ.ም ተያዙ። ወደ ጉራ ከተማ ተወስደው የጣልያንን መንግሥት ገዥነት አምነው በክብር እንዲኖሩ ቢጠየቁ፤ አላደርገውም በማለታቸው እንዲገደሉ ተወሰነባቸው። አሳቸውም ለጣልያን እንዳይገዛ ሕዝቡን ገዝተው በጥይት ተደብድበው ከቆሻሻ ቦታ ተቀበሩ።[8]

ግብፃዊው ሊቀ ጳጳስ አቡነ ቄርሎስ የጣልያንን አገዛዝ አልቀበልም፣ ከሮም ካቶሊክ ጋር አልስማማም ብለው አገራቸው ገቡ። ይህ የአምነት ልጆቻቸውን ከመከራ ላይ ጥለው መሄዳቸው፤ ክኅነት በጎላ የግብፅን ቤተክርስቲያን ከኢትዮጵያ ነቀለ። አባ አብርሃም የጣልያንን አገዛዝ ተቀብለው፤ ታህሣሥ 20 ቀን 1929 ዓ.ም የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ሆኑ። የግብጹ ፓትርያርክ የአቡነ ዮሐንስ 10ኛ ተግሳጽ አልመለሳቸውም። አባ ይስሐቅ ጣልያንን አልቀበልም አሉ። ግን አላወገዙም። ስለዚህ ኢሥራት እንጂ ሞት አልተፈረደባቸውም። አባ አብርሃም ሲሞቱ የአዲስ ዓለሙ መምህር ሐዲስ እሸቱ ሊቀ ብፁዓን አባ ዮሐንስ ተብለው መስከረም 7 ቀን 1932 ዓ.ም በቦታቸው ተተኩ።[9]

አርበኞች በእምነት ጸኑ። ደጃዝማች ፍቅረ ማርያም ጊዜና ቦታ እንለውጥ ብለው የጦር ጓደኞቻቸው ያቀረቡላቸውን ሃሳብ፤ "የማይጨው የተሸነፍነው እንዲህ ተብሎ ነው" በማለት ሳይቀበሉት ቀሩ። በዚያቹ በመረጡአት ቦታና ጊዜ ተራቸውን ተወጡ። ልጅ ግዛቸው ኃይሌ መንዝ "በእንድ ልብ ከጸናን መሥዋዕትነታችን ወደ እግዚአብሔር ፊት እንደሚቀርብ ጥርጥር የለውም" አሉ።[10] አለቃ /ፊታውራሪ/ ወልደሃይማኖት ዘውዱ ደግሞ "ለሃይማኖቴ እሞታለሁ። እናንተ እንዳሻችሁ ሁኑ" ብለው በአስቤ አገር ሚካኤል ዳዊት ላይ ጸፉ።

የደብረ ሊባኖስ ካህናት ለጠላት ሽንገላ የማይበገሩ ሆኑ። ጣልያን መሣሪያ ደብቃችሁአል የሚል ምክንያት ፈጥሮ 350 መነኮሳት በመቶረየስ ረሸነ። የተረፉትን ደግሞ ወደ ደብረ ብርሃን ወስዶ ዲያቆናት እንኳን ሳይተው 42ቱን ገደለ። ከዝቋላ ገዳምም ብዙ የወደቁ አባቶችን ጭምር ፈጀ። ከዜና ማርቆስ ገዳምም እንደዚሁ። ጐንደር ማኅበረ ሥላሴን አቃጥሎ መነኳሳቱን

ጨፈጨፈ። ይህ ሁኔታ ለእምነት አባቶች ጽንአት ሰጠ። ካህናትንም በይበልጥ አስተባበረ። ቡልጋ የወክፈሌ ቅዱስ ሚካኤል ካህናት እንግዳ እሸት የተባለውን የልጅ ኢያሱን ልጅ፤ መልአክ ፀሐይ ኢያሱ ብለው ነሐሴ 21 ቀን 1929 ዓ.ም በሥጋ ወደሙ አነገሡ። የእቲማ ገዳም አባ ምኔት መምህር በላይ፤ በመጽሐፍ ስማቸው እጨጌ ገብረ ጊየርጊስ ተብለው የቤተክርስቲያን ሥራ እንዲመሩ ተደረገ። የደብረ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ካህናት ጽላታቸውን ይዘው ከአዲስ አበባ በምሥጢር በመውጣት ከአርበኞች ጋር ተቀላቀሉ። የአርሲ የሑሩታ ማርያምና የጽሊላ ገብርኤል፤ እንደዚሁም ከጨንቻ የቅዱስ ጊየርጊስ ካህናት ታቦቶቻቸውን ይዘው ከሰደተኛው ጋር ኬንያ ገቡ። በዚያም ለሦስቱም ታቦቶች ለየብቻ መቃኛ ተሠርቶላቸው፤ ለተወለደው ጥምቀተ ክርስትና በመስጠት፤ የሞተውን በመፍታት ሲያገለግሉ እስከ ጦርነቱ ፍፃሜ ቆይተው ወደየቦታቸው ተመለሱ።[11]

በኢየሩሳሌም የነበሩ መነኮሳት የመድኃኔ ዓለምን ጽላት ይዘው፤ በጥር ወር 1929 ዓ.ም ለንደን ከንጉሠ ነገሥቱ ዘንድ ገቡ። የጸሎት ቤት አቋቋሙ። እስከ ጦርነቱ ፍፃሜ ከዚያ ቆይተው፤ ነሐሴ 23 ቀን 1933 ታቦታቸውን ይዘው አዲስ አበባ ገቡ። እሱም አሁንም ስደተኛው መድኃኒ ዓለም እየተባለ የሚጠራው የምስካየ ኅዙናን መድኃኒ ዓለም ነው።[12]

በኢየሩሳሌም የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ከስደተኞች ወንድሞቻቸው ጋር በመተባበር፤ የኢጣልያ መንግሥት በዚያ ያለውን የኢትዮጵያ ገዳም ለመውሰድ ያደረገውን ሙከራ አከሸፉ። የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ከገዳሙ ለማውረድ ያደረገውን ጥረት ዋጋ አሳጡበት። ከጠላት ጋር ለመተባበር በሞከሩት መነኮሳትና መነኮሳይያት ላይ ችግር ፈጠሩባቸው። ጠበቃ ገዝተው ከኢጣልያ ቆንሲል ጋር በሕግ ተከራክረው፤ ያለ ፍርድ ቤት ውሳኔ በባለሥልጣናች ትዕዛዝ በኢየሩሳሌም የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ስደተኞች መብትና ጥቅም እንዳይነካ አሳዛዙ።[13]

የአርበኞች እንቅስቃሴ እያየለባቸው ሲሄድ፣ ጣልያኖች በኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ላይ ጥቃት አካሄዱ። በድምሩ 2000 አብያተ ክርስቲያናት አቃጠሉ። ግንቦት 28 እና 29 ቀን 1930 ዓ.ም በሁለቱ ቀናት በእንድ አካባቢ ሰባት ቤተክርስቲያኖች ማቃጠላቸውን እኔ ራሴ አይቻለሁ። ቦታው ሙገሬ ዛለ ነበር። የአለ ከሴ እግዚአብሔርን፤ አማኑኤል ገዳምን፤ ሥላሴ ገዳምን፤ ጭንቂት ማርያምን፤ ጉርባ አገረ ማርያምን፤ ደሰ አገረ ማርያምን፤ አሰቤ አገር ሚካኤልን አቃጠሉ። ካህናቱን ከቤተ ክርስቲያኖቹ እያስወጡ፤ የደበቋአቸውን መጻሕፍት እና ንዋየ ቅድሳት ሲያቃጥሉና ሲቀዱ ታይተዋል።

ብዙ ቤተክርስቲያኖች ሳይቃጠሉ ቀሩ። ቡልጋ የቅዱስ ጊዮርጊስ አልቃጠል ስለአለ፤ ጣልያን አጠገቡ ምሽግ መሽጐ የአጋሰስ ማሠሪያ አደረገው። የድንጋይ ጥረና የአመየት አገር ጊዮሮጊስ እንደዚሁም የሰበርጐሐ

ዮሐንስ ቤተ ክርስቲያናች አሸንፈው ሳይቃጠሉ ቀሩ። የንሉ አገረ ማርያም በ25 መድፍ ቢደበድባት ሳትቃጠል ቀረች።[14]

ከሁሉም የሚገርመው ቅምብኪት፣ ገኑ ጊዮርጊስ የታየው ነው። በእግር ቀርበው በእሳት ቢለኩሱት አልቃጠል አለ። በመድፍም ቢመቱት የማይሆን ሆነ። በአይሮፕላን በቦምብ ደጋግመው ደበደቡት። ቦምቡ ወደ ሌላ ቦታ እየሄደ ወደቀ። ከዕለታት አንድ ቀን አንድ ቦምብ ከቅጽር ግቢው አርፎ ሳይፈነዳ ቀረ። ይህ የሆነው በጥቅምት ወር 1930 ዓ.ም በተካሄደው ታሳቅ ጦርነት ጊዜ ነበር። ቦምቡ የወደቀው ማክሰኞ ቀን ነው። አስክ ቅዳሜ ድረስ ሳይፈነዳ ቆየ። ለአሁድ ቅዳሴ ችግር ፈጠረ። ሁሉት ሽማግሌዎች ቦምቡን ለማውጣት በፈቃደኝነት ገቡ። በቁርበት ቀላጥም ተሸክመው አወጡት። ከቤተክርስቲያኑ በታች ከነበረ ቅብቅብ ውስጥ በጥንቃቄ አስቀመጡት። እነሱ ቦምቡን ባወጡ ጊዜ ካህናትና ምእመናኑ ከቤተ ክርስቲያን ገብተው እግዝዮታ ያደርሱ ነበር። ሽማግሌዎቹ ተመልሰው ከቤተክርስቲያኑ ሲገቡ ቦምቡ ፈነዳ። የተጠበቀውም እንደዚሁ ይሆናል ተብሎ ነበር። በዚያ የነበሩትን ከብቶች ቦምቡ ፈጃቸው። ሮጣ ገብታ ከቆመ ሰው ከተጠጋችው አንድ ገደር በስተቀር የዳነ ከብት የለም። ሰው ግን ከቤተክርስቲያን ገብቶ ዳነ።[15] እንደዚሁም ጣልያን በሽዋ፣ በጉንደርና በጦጀም አብያተ ክርስቲያናት ላይ ተመሳሳይ ጥቃት ፈጽሞአል። ሂደቱና አድራጉቱ ተመሳሳይ ነው።

ይህ ሁኔታ በኢጣልያውያን ላይ ከፍተኛ ጥላቻ ፈጠረ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ጣልያኖችን እምነት የሌላቸው አሕዛቦች አድርገ ቆጠረ። ቀደም ብሎ በሁለቱ ቤተክርስቲያናች ማለትም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያንና በሮም ካቶሊክ መንበር መካከል ጸንቶ የኖረው መቃቃር በይበልጥ ተካረረ። በአንባሩ ደግሞ በርካታ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን አለቆችና ካህናት ከጣልያን ጋር ተባበሩ። በስብከት የአርበኞችን ክንድ ለማላላት ሞከሩ። ምሥጢር ለበላት እያሳሰቡ ሰበኩ። ይህ ደግሞ በካህናት መካከል የተካረረ የአመለካከት ልዩነት ፈጠረ።

የአርበኞች መበርታትና የመልአክ ፀሐይ ኢያሱ ምኒልክ መንገሥ በሰንደን በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዘንድ ሥጋት እንደፈጠረ ሁሉ፣ የመምሕር በላይ እጨጌ መሆን ኢየሩሳሌም በእጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ /ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ/ ዘንድ ድንጋጤ ፈጠረ። ስለዚህም እጨጌው ከመጀመሪያው በተጨማሪ ሌሎች ስድስት ሐዋርያዊ መልእክቶች በተከታታይ አስተላለፉ። የተላለፉበትን ጊዜ፣ ቅርጻቸውንና ይዘታቸውን መመልከት አንዳንድ ግንዛቤ ይሰጣል።

የመጀመሪያው የእጨጌ መልእክት የተላለፈው ጎንደር 17 ቀን 1928 ዓ.ም እንደነበር ቀደም ብሰን ተመልክተናል። ሁለተኛው መልእክት ከእኚህ አባት የተላለፈው ሰኔ 20 ቀን 1931 ዓ.ም ነበር። በዚህ ጊዜ እጨጌነትን በተመለከተ ቡልጋ ውስጥ ሌላ ተለዋጭ እንቅስቃሴ እንደነበር ማጤን

ይገባል። ሦስተኛው መልእክት ደግሞ ሰኔ 27 ቀን 1931 ዓ.ም ነበር። ከአንድ ሣምንት በኋላ መሆኑ ነው። አራተኛው መልእክት በጎንደር ወር 1932 ዓ.ም ነበር። አምስተኛው ታህሣሥ 24 ቀን ስድስተኛውም በዚያው በታህሣሥ ወር 1932 ዓ.ም ነበር። ከጎንደር 17 ቀን 1928 ዓ.ም እስከ ሰኔ 20 ቀን 1931 ዓ.ም ሦስት ዓመት ከሰባት ወር ጸጥ ብሎ የነበረውን መልእክት ምን አንቀሳቀሰው?

ሌላው መታየት ያለበት የመልእክቶቹ አድራሻ ነበር። ሁለተኛውና ሦስተኛው ሐዋርያዊ መልእክቶች የተላለፉት ለኢትዮጵያ ሲቃውንት፣ ካህናት፣ ቀሳውስት፣ ዲያቆናት፣ መኳንንት፣ ባላባትና ሕዝብ ነበር። አራተኛው ከእጨጌው ጋር ልውል ራስ ካሣና ሌሎች ታላላቅ መኳንንቶች ሞምር ሰላምታ እንደሚያቀርቡ ተገልጦ፣ ለሃያ አንድ መኳንንቶች በየስማቸው የተጻፈ ነበር። አምስተኛው ሐዋርያዊ መልእክት ደግሞ በዚያው በታህሣሥ ወር 1932 ዓ.ም የተጻፈ አድራሻው በጠቅላላው ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሆነ ነበር። ላኪው... "እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ ዘመንግሥተ ኢትዮጵያ" ተባለ ለምን? ስድስተኛው ሐዋርያዊ መልእክት፣ በኢትዮጵያ አውራጃ ላለ ለአያንዳንዱ የአርበኛ አለቃ በዚያው በታህሣሥ ወር 1932 ዓ.ም ተጻፈ። ለባተኛው ደግሞ እንደገና ላኪው እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ ዘመንግሥተ ኢትዮጵያ መሆናቸውን የሚገልጽ ነው። አሁንስ ለምን?

የመልእክቶቹ ይዘት ተመሳሳይ ነበር። ከሦስት ጉዳዮች ላይ ጠቅላላ ትኩረት ተደርጐአል። አንደኛውና ዋናው ጉዳይ አርበኛው በርትቶ እንዲዋጋ በነገረ መለኮት ላይ የተመሠረተ ምክር መስጠት ነው። ሁለተኛው መልእክት ይህንን በተመለከተ...ጣልያን ...ዘራችንን፣ ሃይማኖታችንን፣ እያዋረደ፣ ሕዝባችንን በዓለም ፊት ነውረኛ ለማድረግ መስበኩን አተዘንጋ..." ይላል። ሊደመድምም "...እግዚአብሔር ኃይሉን እንዲሰጣችሁ...እንለምናለን" ይላል። ሦስተኛው መልእክት ቅዱስ ዳዊት "...እግዚአብሔር በሲ አሕዛብ ውስተ ርስትክ" የሚለውን መመልከት እንደሚገባ ያስገነዝባል።[16] አራተኛው ሐዋርያዊ መልእክት አንድም ቃለ እግዚአብሔር የለበትም። አምስተኛው መልእክት "...ስለ ሀገሩ የገደለም፣ የሞተም ስማዕት ነው..." ይልና ሙሴ ስለወገኑ እንደ ገደለ ይዘክራል። ስድስተኛው መልእክት "...ሁሉን የሚችል እምላክ የዳዊትን ሀብተ መዊዕ ይስጣችሁ..." ይላል። ሰባተኛውና የመጨረሻው ደግሞ ኤሳው ብኩርናውን ሳንዲት መበል እንደሸጠ ያስገንዝባል "...ለጠላት ወገን ሆኖ ወንድሙን የሚወጋውን፣ ለላይም ሆኖ ለጠላት የሚረዳውን፣ ...ሰባኪ ሆኖ...የሕዝቡን ልብ የሚያሰንፈውን መምህራንም፣ መነኮሳትም፣ ቀሳውስትም፣ ዲያቆናትም ቢሆኑ ከቤተ ክርስቲያን የተሰዩ ከሥልጣናቸውም የተሻሩ ናቸውና፣ የሊቀ ጳጳሳቱን /የአስክንድርያውን አቡነ ዮሐንስ 14ኛ ማለት ነው/ መሠረት አድርጌ በሥልጣነ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ የተለዩ እንዲሆኑ ገዝቻለሁ" በማለት ይደመድማል።



ይህ በዕል ካህናቱ በመንተጥተጥ ለጀኔራል ናዚ ፋሽስታዊ ሰላምታ እንዲሰጡት ያመለክታል ።

የመልእክቶቹ ሁለተኛ ጉዳይ አርበኛው በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥትነት ላይ እንዳያወላውል ማድረግ ነው። ይህንን በተመለከተ ሁለተኛው መልእክት ለኢትዮጵያ አርበኞች፣ ካህናትም ንጉሠ ነገሥቱ ለዓለም መንግሥታትና ሕዝብ እያመለከቱ እንደሆነ ማየት መስማታቸውን ያስረዳል። ስለንጉሠ ነገሥቱ በክርክር ላይ መሆን ያመለክታል። አራተኛው መልእክት "...ግርማዊ ንጉሠ ነገሥታችን ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ በተሠራው ግፍና በፈሰሰው ደም ስለሀገራቸው ነፃነት ለመከራከር የተሰደዱበት ጉዳይ መፈጸሚያው ጊዜ የደረሰ ይመስለናል..." የሚል ትንቢት በስም ለተጻፈላቸው መሳጉንት ይገልጻል። ለሕዝብ የተላለፈው አምስተኛው ግን ስለዚህ ጉዳይ አንዳች አይልም። ለአርበኛው አለቆች በስም የተጻፈው ስድስተኛው መልእክት ደግሞ "...በመከራው ጸንተህ ንጉሥህ ያዘዘውን ሥራ አገልግሎትህንም ፈጽም..." ብሎ የጴሞቲዎስን ሁለተኛ መልእክት ይጠቅሳል። ሰባተኛውና የመጨረሻው መልእክት "...ወይኩን ንጉሥ ዘትሠይሞ እምአኃዊኩ፣ ወኢይደሉ ከመትሚም ላዕለኒ ነኪረ..." ተብሎ በፍተሐ ነገሥት አንቀጽ 44 የታዘዘው በሃይማኖት ሰማይመሳሰል፣ በምግባር ሰማይተባበር መዝሙት የማይገባ መሆኑን እንደሚያሳይ የሚገልጽ ነበር። ብእሲ ነኪረ ያለውን "ባዕድ" ብሎ ተርጉሞታል።

የመልእክቶቹ ሦስተኛው ጉዳይ እጨጌው አገር ጥለው በመሄድ ሊያጡት የተቃረቡትን በትረ ሥልጣን እንደገና መልሶ የመጨበጥ ነበር። ይህንን በተመለከተ ሁለተኛው መልእክት ማለትም በተሰደዱ በሦስት ዓመት ከስባት ወር ከኢየሩሳሌም የጻፉት ስለአካሄዳቸው እንዲህ ይላል። በዘመቻው ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር እንደነበሩ ያወሳና "...አሁንም ስለ ኢትዮጵያና ስለ ሕዝባቸው ነፃነት በዓለም መንግሥታት ፊት ቀርበው ለመከራከርና ፍርድ ለመጠየቅ ወደ ኢሮፕ ሲመጡ አብሬ መምጣቴን ሰምታችሁ ይሆናል።

ይኸው እኔም በቅድስት ሀገር በኢየሩሳሌም ገዳማችን እንዳይደፈር፣ የሃይማኖታችን መሠረት እንዳይናወጥ በሀዘንና በጸሎት ተጠምጄ በሃሳብ ከእናንተ ሳልለይ እኖራለሁ..." በማለት ይጀምራል። ሦስተኛው መልእክት "በዓይነ ሥጋ ለመገናኘት ያብቃን" ብሎ በመደምደም ስለግላቸው ጉዳይ አያነሱም። አራተኛው መልእክት ብቻቸውን አለመሆናቸውን ለማስገንዘብ የዘጠኝ መሳጉንት ስም ይዘረዝራል። ነገር ግን ስለራሳቸው አይናገርም። በአምስተኛው መልእክት "...በሥጋዬ ከናንተ ጋራ ባልኖርም በልቡናዬ ከናንተ ጋራ ነኝ..." የሚለውን የቅዱስ ጳውሎስን ቃል ጠቅሰው፣ እሳቸውም በልቡናቸው ከኢትዮጵያን ጋር መሆናቸውን ገልጸዋል። በስድስተኛው መልእክታቸው ቅዱስ ጳውሎስ በክልዕ ተሰሎንቄ የጻፈውን በመጥቀሥ፣ እሳቸውም መልእክቶቹን በእጃቸው መጻፋቸውን ገለጹ። እንዲህም አሉ "...ይኸን ሰላምታ በእጀ ጻፍሁ። በምጽፈው ደብዳቤ ሁሉ ምልክቴ ይህ ነው። እንዲህ እጽፋለሁ..." አሉ። ሌሎች እጨጌዎች የሳቸውን አያስመስሉ እንዳይጽፋባቸው ይሆን? በወቅቱ የንጉሠ ነገሥት መልእክ ፀሐይ ኢያሱ እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ፣ የኢጣልያ መንግሥት እጨጌ ሐዲስ እሼቱ ነበሩና። በሰባተኛው መልእክታቸው ስለዚህ ጉዳይ አላነሱም።[17]

ጣልያኖች በፊናቸው ጦርነቱ ከውስጥ፣ ከውጭ እየከበደባቸው ሲሄድ ባለምዋሎቻቸው ሕዝቡን እንዲሰብክላቸው ጉትጉታቸውን አጠናከሩ። እውነትም ሳያፍሩ ሳይፈሩ ሰበኩላቸው። አንዳንድ ማስረጃ መጥቀስ ይበጃል። የኢጣልያ ምሥራቅ አፍሪካ ሊቀ ጳጳስ አባ አብርሃም የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር የቄሣርን ለቄሣር የሚለውን ቃል እየፈጸሙ መኖር እንደሚገባ አስታውቁለት። ንቡረ ዕድ ተክለ ሃይማኖት "...የኢጣልያ መንግሥት ኃይማኖት ያስለውጣል፣ ያገር ልማድ ያስቀራል እያለ የሚያወራ እሱ ራሱ ከሀዲ ነው።..." ብለው አስተያየታቸውን ገለጹ። እጨጌው ደግሞ "...ይህን ድህ ጠባቂ የሆነ ትክክለኛ መንግሥት ለዘለዓለም አትርልን..." አሉ።[18]

በአንዣሩ በገጠር ቄስ መኮሩዬው "ለሀገርህ ነፃነት፣ ለወገንህ ደህንነት ብትሞት በልዑል እግዚአብሔር ፊት ሰማዕትነት ይሆንልሀል። ሞተ ነፍሥን እንጂ፣ ሞተ ሥጋን አትፍራ" እያሉ ሰበኩ በቀኝም ሆነ በግራ የኢትዮጵያውያን ዕድል ሞት ሆነ። ሞት ከአርበኛውም ወገን ቢሆኑ ከጣልያንም ወገን አልቀረም። ያለው ዕድል ለየትኛው ወገን መሞት እንደሚሻል መምረጥ ሆነ። ከአርበኞች ጐን መሆን ሞት፣ ከጣልያን ወገን መሆን የሞት ሞት እንደሚያስከትል ግልጽ እየሆነ ሄደ። ስለዚህ ልባሞች ከሞት ሞት ይልቅ፣ ሞትን መረጡ።

አርበኛው በአምልኮተ እግዚአብሔር ጸና፤ የሃይማኖት አባቶችም ጠነከሩ። ራሳቸው ከጦር ሜዳ እየገቡ ቆሙ። ንጉሥ መልእክ ፀሐይ ሲሞቱ እጨጌአቸው የነበሩት ገብረ ጊዮርጊስ መነኑ። የራስ አበበ የነፍስ አባት የነበሩት መምሬ ደምሴ ቁርሎስ ቆስለው በመማረክ ደናኔ እሥር ቤት ገቡ።



ይህ ስዕል ካህናቱ በመንቀጥቀጥ ለጀኔራል ናዚ ፋሽስታዊ ሰላምታ እንዲሰጡት ያመለክ

በጉንደርም፣ በሥጃምም ከጦር ሜዳ እየገቡ ሲያዋጉ ብዙ ካህናት ከዚያው ከጦር ሜዳ ሞቱ።

እንደእኔ አስተያዬት ልዑል እግዚአብሔር እንደ ወትሮው ሁሉ ከተጠቂዎች ጉን ቆመ። ብዙ አንባቢያን በዚህ አባባሌ ልትስማሙ እንደምትችሉት በመገመት እቀጥላለሁ። ለመቆመም ብዙ ምልክት አሳየ። ምስጋና ለማቅረብ ያህል ጥቂቱን ማየት ይገባል። ዝናምና ደመና እየሆነ የጣልያንን አይሮፕላን እንቅስቃሴ ብዙ ጊዜ ገታ። የሚወድቀውም በምጣ በአፍንጫው ከሞቃ ውስጥ እየተገደገደ የማይፈነዳ ሆነ። ለጣልያን ወታደር የሚጣለውን ስንቅና ጥይት ነፋስ እያዞረ ለአርበኞች ሰጠው። ለምሣሌ በመንዝና በቡልጋ አይሮፕላኖች በቤተክርስቲያን አካባቢ ሲበሩ እየተበላሹ ወደቁ። እንደዚሁም ለምሣሌ ጉንደር በማህበረ ሥላሴ ጦርነት ጠሳት ሲያሸንፍ ከባድ ዝናም ይጥላል።[19] የባለምባራስ /ራስ/ አበበ ሠራዊት ከክርፎ ጦርነት ላይ ያመለጠው በዚህ ዓይነት ተአምር ነው። በየቤተክርስቲያኑ ያሉት ጠበሎች ከወትሮ የበለጠ ፈዋሽነት አገኙ። እኔም ከብዙም በአንድ ጊዜ በጠና ታምመን ሙገራ ዛላ በአማኑኤል ገዳም ጠበል ዳንን። ጀሎ አገር ገዳም ደጋ ያለ አንድ ሾላ 105 ነፍስ ለሦስት ወር መገበ። ታቦቶች የከዳውን ፈጥነው ይቀጣሉ። ለምሣሌ ቡልጋ አጋፋሪ አማምነው ላይከዱ በአስቤ አገር ቅዱስ ሚካኤል ማሉ። መሐላቸውን ባፈረሱ በሦስተኛው ቀን ሁለት ዓይናቸውን ታወሩ።[20]

እንደእኔ፣ በእነኛ ቀውጢ አመታት የነበርን ብዙዎቻችን፣ ኢትዮጵያ ከፋሽስት ወረራ ነፃ ልትወጣ የቻለችው በእግዚአብሔር ኃይል ነው ብለን እናምናለን። የአርበኝነት ትግል ከዳር የደረሰው በእግዚአብሔር አጋዥነት ነው። ይህንን አርበኞች ሁሉ መስክረዋል። በትግሉ ውስጥ የነበርን ሁሉ አምነናል። ንጉሠ ነገሥቱ ወደ ዙፋናቸው የተመለሱት በእግዚአብሔር ጥበብ ነው። እሳቸውም አዲስ አበባ በገቡበት ዕለት ሚያዝያ 27 ቀን 1933 ዓ.ም ያደረጉትን ንግግር የጀመሩት "የሰማይ መላዕክት የምድር ሠራዊት ሊያስቡትና ሊያውቁት ይቻላቸው ባልነበረ በዚህ ቀን፤ ቸር እግዚአብሔር በመካከላችሁ ለመገኘት ስለአበቃኝ በሰው አፍ የሚነገር ምስጋና የሚበቃ አይደለም..." በማለት ነበር።[21] እውነት ነው ልዑል እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ያፀናት፣ በማይመረመር ረቂቅ ጥበቡ የጥበበኞችን ሜራ አፍርሶ ኃይላቸውን ደምስሶ ነው። ለዚህ ታላቅ ቸርታው በሰው አፍ የሚነገር ምስጋና በቂ አይደለም።

የኢትዮጵያ ልጆች ይህንን እውነት ከልብ እንዲያምኑና እንዲረዱ ያስፈልጋል። ይህንን ካላደረጉ በዓለሙ ላይ አንዳች ብቃት አይኖራቸውም። በፈጣሪ፣ በእግዚአብሔር ካላመኑ ልፋታቸው ሁሉ መና ይሆናል። እነሱ የለፉበትን ጠላቶቻቸው ይበሉባቸዋል። በእግዚአብሔር ካመኑና ትዕዛዙን ከፈጸሙ ግን ማንም ኃያል፣ ማንም ጥበበኛ አንዳች አያደርጋቸውም።[22]

ልዑል እግዚአብሔር ለኢትዮጵያ ምን እንዳረገላት ለመገንዘብ ከሚያስችሉት ነገሮች አንዱ የጣልያን ባለሥልጣኖችን ፍፃሜ መመልከት ነው። ንጉሠ ነገሥት ኢማኑኤል ሣልሣዊ ከሥልጣኑ ወረደ። ሥርወ መንግሥቱ ተነቀለ። አባ ፖኦስ 11ኛ የካቲት 5 ቀን 1931 ዓ.ም ሞቱ። ዱቼ ቢኒቶ ሙሶሊኒ ሚያዝያ 21 ቀን 1933 ዓ.ም በሰሜን በኩል አምልጦ ወደ ስዊስ አገር ሊገባ ጥቂት ሲቀረው ተይዞ ተጨናገፈ። ዲንጉ በተባለች ትንሽ መንደር ውስጥ በአምስት የመትረየስ ጥይት ተደብድቦ ሞተ። አብራው የተገደለችው ክላራ ፔታቺ የተባለችው ታማኝ ቁባቱ ጋር ሬሣሳቸው የዝቅዝቂት ተሰቀለ። ሙሶሊኒ የተገደለው በገዛ ወገኖቹ በኢጣልያውያን ነበር። የሞተውም ጣልያኖችን ምን በደልኩና እያለ ነበር። ያቂቋመውም የፋሽስት ፓርቲ ክእሱ ጋር አብሮ ጠፋ። ማርሻል ግራዚያኒ በለቢያ በተካሄደው ጦርነት ኢጣልያን እንደከዳ ተቀጥሮ ከግበረ አበሮቹ ጋር እሥራት ተፈረደበት፤ የእሱ ድርሻ አሥራ ዘጠኝ ዓመት ሆነ። ዱካ ደ አምስታ አምባሰጌ ተማርኮ ኬንያ ከተወሰደ በኋላ ናይሮቢ አገር እሥር ቤት ሞተ። ክንትቺያኖ ኢጣልያ ከጀርመን ጉን ሆና ከጦርነቱ በመግባትዋ ባለመስማማቱ፤ ከሌሎች ስድስት ሚኒስትሮች ጋር በአማፁ በሙሶሊኒ ትዕዛዝ ተገደለ። በልዩ ልዩ ምክንያት እየተልፈሰፈሰ ኢትዮጵያን ያስወረራት የዓለም መንግሥታት ማኅበር ፈረሰ። የኢትዮጵያን መወረር የተሰቀቀው አውሮፓ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት እሳት ከዳር እስከ ዳር ተጠበሰ።

ማጣቀሻ ፅሑፎች

1. ተክለ ፃድቅ መኩሪያ፣ *የኢትዮጵያ ታሪክ ከአጼ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ*፣ ገጽ፣ 203-206።
2. *ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፣ ሕይወቱና የኢትዮጵያ አርምጃ፣ 2ኛ መጽሐፍ*፣ ገጽ 82-93።
3. ከኢትዮጵያ ምርምርና ጥናት ክምችት የተገኘ።
4. አክሊሉ ገብረ ክርስቶስ፣ *ዜና ባስልዮስ ሊቀ ጳጳሳት*፣ ገጽ 15-17።
5. *መጽሐፍ ቅዱስ*፣ ሳሙኤል ካልዕ፣ ምዕራፍ 15 ቁጥር 25-27።
6. አባ ጎርጎርዮስ፣ *የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ*፣ ገጽ 84-92።
7. ከመልአክ መዊፅ የተሳነ በንቲ የተነገረኝ።
8. "የኢሰባቡር ታሪክ"፣ የኢሠፓ ጥናት፣ ገጽ 31 /ያልታተመ/።
9. *የቄሣር መንግሥት መልእክተኛ*፣ ሣምንታዊ ጋዜጣ፣ ሐምሌ 14 ቀን 1932 ዓ.ም።
10. ታደሰ ዘወልዴ፣ *ቀሪን ገረመው*፣ ገጽ 214።
11. አባ ተክለ ማርያም፣ *የምስክየ ኅዙናን ንዳም ለመሠራረት*፣ ገጽ 19-34።
12. ከአቶ እሸቴ ባዩ የተነገረኝ።
13. ከበደ ተሰማ፣ *የታሪክ ማስታወሻ*፣ ገጽ 173-193።
14. እኔ ራሴ ያየሁት።
15. ከመምህር ገብረሕይወት ወልደፃድቅ የተነገረኝ።
16. *መዝሙረ ዳዊት* ቁ.73።
17. አፈ ሊቀ ሊቃውንት አክሊሉ ገብረ ክሮስ /የጽሑፍ ተጠባቂ/ ዜና ባስልዮስ ሊቀ ጳጳስ ገጽ 15-29።
18. ገራማ ታፈረ፣ *ጐንደሬ በጋሻው*፣ ገጽ 84-87።
19. ታደሰ ዘወልዴ፣ ገጽ 284።
20. በአቶ ወልደፃድቅ ሽንቁጤ የተነገረኝ።
21. ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፣ ገጽ 311።
22. አሪት ዘሌዋውያን፣ ምዕራፍ 26 ቁጥር ከ1-47።

ምዕራፍ ሃምሣ ስድስት
ጦርነቱ በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ላይ ያደረሰው ጉዳት

በማንኛውም ጦርነት ጊዜ ዝርፊያ ይካሄዳል። የሀብት ውድመት ይደርሳል። በኢትዮጵያና በኢጣልያ ጦርነት ጊዜ የተካሄደው ከሁሉም የከበደ ነው። ሁኔታውን በትክክል ለመገንዘብ የሚቻለው በሁለቱም ወገን የደረሰውን በማየት ሳይሆን አልቀረም። ችግሩ በቂ ማስረጃ አለመገኘቱ ነው። ቢሆንም የተገኙትን ጥቂት ማስረጃዎች መነሻ በማድረግ የደረሰውን ጉዳት ለመገመት እንሞክራለን።

የኢኮኖሚ ጉዳት የደረሰው በአራት ዓይነት ነው። አንዱ የሥልጣን ልውውጥ በተደረገ ጊዜ ባለሥልጣኖቹ ያካሄዱት ገፈፋ ነው። ሁለተኛው በእነዚያው የሥልጣን ሽግግሮች ወቅት ሕዝብ እርስበርስ ሲዘራረፍ የደረሰው ጉዳት ነው። ሦስተኛው በጦርነቶቹ ጊዜ የወደመው ሐብትና ንብረት ሲሆን፣ አራተኛው ደግሞ መንግሥቶቹ የሚጠቅም እየመሰላቸው ባካሄዱት ሥራ የደረሰው ኪሣራ ነው። የመጀመሪያዎቹ ሦስት ማለትም በገፈፋ፣ በዘረፋ፣ በውድመት ጉዳት የደረሰው በኢትዮጵያ ላይ ሲሆን፣ አራተኛው ማለትም ኪሣራ የደረሰው በጣልያን ላይ ነው።

ንጉሠ ነገሥቱ ወደ አውሮፓ የተሻገሩት አንድ መቶ አሥራ አንድ ሣጥን ወርቅና ብር፣ ሌላም ዕቃ ይዘው እንደሆነ በታሪክ ተመዝግቦአል። መኳንንቱም እንደዚሁ የቻሉትን ያህል ይዘው ነው የሄዱት። ይህንን ከስህተት ሙቁጠር አይገባም። ምክንያቱም ትተውት ቢሄዱ ከጠላት እጅ ገብቶ ይበልጥ ከሚያስጠቃ በስተቀር ሊጠቅም አይችልም ነበር። እንዲያውም ንጉሠ ነገሥቱ፣ መኳንንቱና መሣፍንቱ መትረፋቸው የኢትዮጵያን ትንሣዔ አስገኝቶአልና በጥቅም ላይ እንደዋለ መቁጠርም ይቻላል። ነገር ግን ከኢትዮጵያ ውጭ ሄዶ በሰው አገር የፈሰሰ በመሆኑ በኢኮኖሚ አመለካከት እንደጠፋ የሚቆጠር ነው። በዚህ ዓይነት 10 ሚሊዮን ብር ከሀገር ሳይወጣ አልቀረም።

የኢጣልያ ሹማምንትና የጦር አለቆች ኢትዮጵያ ሲገቡ ያካሄዱት ሥራ እንደ ገፈፋ ነው። ማንኛቸውም ምን ያህል እንደወሰዱ ማስረጃ የለም፣ ደረሰኝ እየሰጡ አይወስዱም። የታሪክ ጸሐፊዎቻቸውም ይህንን የመሳሰለውን ነገር አይጽፉም። ነገር ግን አንዳንድ ምልክቶች ታይተዋል። በማንኛውም ጉዳይ ከኢትዮጵያ ወደ ኢጣልያ የሚመለሱ ሁሉ ባዶ እጃቸውን አልሄዱም። ወደ ሀገራቸው የሚገቡት ብዙ ሀብት እየተሸከሙ ነበር። ለማስረጃም ያህል ማርሻል በዶሊዮ አገሩ የገባው ሦስት መቶ ሣጥን አጋትሎ ነው። ማርሻል ግራዚያኒም ሰባ ዘጠኝ ይዞ ነው። ከዚህም ጋር ባዶሊዮ በኢትዮጵያ ባንክ ከነበረው 1.7 ሚሊዮን የማርትሬዛ ብር ግሚሹን ሰግሎ ዘርፎ ነው።[1] ቀሪውንም ጭፍሮቹ ተከፋፍለውታል ማለት ነው። በአጠቃላይ ጣልያኖች

በኢትዮጵያ ላይ ከፍተኛ ገፈፋ አካሂደዋል። ይህም ገፈፋ በገንዘብና በሐብት ላይ ብቻ ላይ ያተኮረ አልነበረም። በታሪካዊ ቅርስ ላይ ጭምር እንጂ። ለዚህም የአክሱም ሐውልት የዚያን ጊዜ ተወስዶ እስከቅርብ ጊዜ አለመመለሱ፣ በባቡር ጣቢያ የሚገኘውም ይይሁዳ አንበሳ ሐውልት ወደ ሮም ተወስዶ እንደነበረ ማስታወሱ በቂ ይሆናል። ጣልያኖች ገፈፋ ያካሂዱት ሲገቡ ብቻ አልነበረም። ሲወጡም ነው።

ከዚህ ላይ አንድ ማስረጃ መስጠት ያስፈልጋል። ለዚህም መጥቀስ የሚገባው ደብዛው ጠፍቶ የቀረው አርባ ኩንታል ወርቅና አልማዝ፣ የሴሎችም ክቡር ዕቃዎች ጉዳይ ነው። የእሱም ታሪክ ባጭሩ ከዚህ እንደሚከተለው ነበር።

ጦርነቱ ከአሰቀ ከአሥራ አምስት በኋላ[2] ደቡብ አፍሪካ፣ ኬፕታውን ከተማ በመጠጥ ቤት ፒተር ሀሎራንና ዋከር የተባሉ ሰዎች ተገናኝተው ሲጨዋወቱ ተቀብሮ ስለቀረ ወርቅ ዋከር ለሀሎራን ነገረው። ወሬውን የሰማው ሀሎራን የጥቅም አጋኖነት ዘዴ የሚያውቅ ሰው ስለነበር በጉዳዩ ላይ ጥናት አደረገ። የሚያውቀውን ሦስተኛ ሰው ካርቴዝን በመጨመር ወርቁን አውጥተው እኩል ለመከፋፈል የሚችሉበትን መንገድ አሰበ። ወርቁ የተቀበረው በጣልያን አገር ነው። የተቀበረውም በአንግሊዝ ወታደሮች ነው። የተማረከው ከ17 የጀርመን ወታደሮች ሲሆን፣ ወሬውን እንዳያወጡ እነሱም አብረው ተቀብረዋል። ምሥጢሩን ከሚያውቁት የእንግሊዝ ወታደሮች አራቱ በልዩ ልዩ ምክንያት ሲሞቱ በሕይወት የቆዩት ሁለቱ ብቻ ነበሩ። እነሱም እርስበርሳቸው ለመገዳደል እየተፈላለጉ ናቸው። ሀሎራን በብዙ ምክር ሁለቱን የቀድሞ ወታደሮች እርስበርሳቸው አገናኛቸው። በእሱ ሃሳብ እንዲሰማሙ አድርጉ ወርቁን አውጥተው እኩል ለካፈሉ ተነጋገሩ። እሱም ወጭአቸውን ችሎ ራሱ ባሠራት መርከብ አንቀሳቀሳቸው።

በአትላንቲክ ባህር ላይ ተጉዘው ታንጀር ደረሱ። ከዚያም ስለ ወርቅ ገዢ ከአንድ ነጋዴ ጋር ተመካክረው ጉዞአቸውን በመቀጠል ሞንቴ ካርሉ፣ ከዚያም ራፖሉ ከተባሉቸው ትንሽ ወደብ ደረሱ። ከዚያ ደግሞ ፍራንሲስካ የተባለች የኢጣልያ መኳንንት ተወላጅ የሆነች ሌላ የጥቅም ተጋሪ ተገናኙ። ፍራንሲስካ የሙሶሊኒን መንግሥት በመቃወም በአርበኝነት ከተዋጋ አባትዋ ጉን ሆና የተዋጋችና የወርቁን ምሥጢር አውቃ ቦታውን በማፈላለግ ላይ ስለነበረች ከጥቅሙ ተካፋይነት ማገድ ሳይቻል ቀረ። እሷ ደግሞ ብቻዋን አልነበረችም። ሃምሣ የሚያህሉ የአባትዋን ጭፍሮች ይዛ ቀረበች። ከብዙ ክርክር በኋላ ወርቁ ከሦስት ሳይሆን ከአምስት ቦታ እንዲከፈል ማድረግ አስፈለገ። ይህም ሆኖ እያንዳንዱ ቅርጫ እስከ ሦስት ሚሊዮን ብር እንደሚደርስ ስለተገመተ፣ ክፍፍሉሽ ባያስደስትም ጠብ አላስነሳም።[3]

ሦስት ካሚዮኖች በመክራየትና ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶችን በመግዛት፣ ወርቁ ወደሚገኝበት ቦታ ጉዞ ተደረገ። ወራቱ ጥር ሲሆን ወርቁ

ታንጀር መድረስና ለገበያ መቅረብ የነበረበት ከመጋቢት የመጀመሪያ ሣምንት በፊት ስለነበር ሥራው አጣዳፊ ሆነ። ቡድኑ በአቅዱ መሠረት ከቦታው ከደረሰ በኋላ የአርስበርስ መጨራረስ አደጋ እንዳይደርስ የመሣሪያ ገፈፋ ተደረገ። መርዝና አደንዛዥ ነገር አለመኖሩ በርስበርስ ምርመራ ተረጋገጠ። ከዚያም ከዋሻው ውስጥ ተገባ። በዋሻው ውስጥ ሦስት ካሚዎኖች ቆመው ነበር። ከዋሻው ውስጥ የከተቱአቸው ወታደሮች ሃሳብ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ተመልሰው ነድተው ለመውሰድ ስለነበር አልተራገፉም። ከውጭ ወገን ከአለው ካሚዎን ሠላሣ፣ በመካከል ከአለው 10 ሣጥን ወርቅ፣ ከውስጠኛው ደግሞ ብዙ አልማዝና የንጉሠ ነገሥቱ ዘውድ፣ የጣልያን ወረቀት ሌሬና የእንግሊዝ ፓውንድ፣ ብዙ የጣልያን መንግሥት የምሥጢር ሰነዶች ተገኙ። ወርቅና አልማዝ ዘውዱ የኢትዮጵያ ነበር።

ቡድኑ የወረቀት ገንዘቡንና የምስጢር ሰነዶችን ትቶ ወርቅና አልማዝ ዘውዱን በካሚዮን ጭኖ ማንም ሳያየው ወጣ። ከዚያም በማቅለጥና በመጋዝ በመቁረጥ ወርቁን አስተካክለው። በጀልባው ጭኖ ምሥጢሩን አውቆ የተነሳሳበትን ሌላ የወንበዴ ቡድን እየተከላከለ ጉዞውን ወደ ታንጀር ቀጠለ። ወይዘሮ ፍራንሲስካም ባልዋን ትታ አቶ ሀሎራን አግብታ አዲስ በተገኘው ወርቅ ልትንደላቀቅ፣ ታላቁን የእንቁ ሐብል ተሸልማ፣ ሽማግሌ አባትዋን አስፈቅዳ ከቡድኑ ጋር አብራ ሄደች። ሕልማቸው እውን መሆን ጀመረ። ቢሆንም ይህ ወርቅ ከሀገሩ ወጥቶ ጦሱ ሰው እያባላ ነው። እኛንም ይዞን ይጠፋ ይሆን? እያሉ መሰጋታቸው አልቀረም።

ከሚዲትራንያን ባሕር ማዕከል ሲደርሱ ከባድ አውሎ ነፋስ ተነሳባቸው። ከእሱ እየተናነቁ ጉዞአቸውን ሲቀጥሉ አቶ ክሩፒክ የተባለ የመርከብ ወንበዴ ጠንካራ ቡድን ይዞ ደረሰባቸው። ከመጠነኛ ድብድብና ከጥቂት የተኩስ ልውውጥ በኋላ ንግግር ጀመሩ። የወርቁን ሲሦ እንስጥህ ቢሉት ግማሹን ካልሆነ ብሎ እምቢ አለ። በዚህ ንግግሩ ፈርሶ ትግሉ ቀጠለ። እነ ሀሎራን ከወንበዴው ቡድን ለማምለጥ ከረጋው ባሕር ወደ ኋላቸው ተመልሰው ማዕበል ከአየለበት ባህር ገቡ። ጀልባቸው መስጠም ስትጀምር ወንበዴዎቹ ደረሱባቸው። በዚያን ጊዜ ከወርቁ የተረፈው አሥር ኩንታል ብቻ ነበር። እሱንም ማዳን ሳይቻል ቀርቶ ከጀርባዋ ጋር አብሮ ሰጠመ። እነሱን ወንበዴዎቹ አዳኑአቸው።

ይህንን ያህል አታግሎ ከሜድትራኒያን ባሕር ውስጥ አስጠመው። አርባ ኩንታል ወርቅና አልማዝ ሙሉ በሙሉ የኢትዮጵያ አንጡራ ሀብት ነበር። ዘውዱም የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዘውድ ነበር። ወርቅና አልማዙ፣ ዘውዱ ከጣልያኖች በጀርመኖች ተዘረፈ። ከጀርመኖች በኢጣልያ አርበኞች ተማርኮ ቀድሞ የድኚ ማዕድን ይወጣበት ከነበረ ታላቅ ዋሻ ውስጥ ተደፈነ። ከዋሻው ውስጥ በአቶ ፒተር ሀሎራን ቡድን በምሥጢር ተፈልፍሎ ወጣ።

ከሀሎራን ቡድን ለመንጠቅ የክሩፒክ ቡድን ባኬሄደው ትንንቅ ለአንዳቸውም ሳይሆን ከሜዲትራንያን ባህር ውስጥ ሰጠመ።[4]

ከዚህ ላይ ገና ምላሽ ያላገኘው ጥያቄ ወርቅና አልማዙ፣ ዘውዱ ጭምር እንደምን ከጣልያኖች ገባ የሚለው ጥያቄ ነው። አንደኛ ነገር ከላይ የተዘረዘረው ክስተት እውነት እንጂ ልብ ወለድ አይደለም። ሁለተኛ ነገር ንጉሠ ነገሥቱ ወደ አውሮፓ ሲሄዱ ወርቅና ብሩ ከጠላት እንዳይወድቅ ተጭኖ ሄዶአል?[5] በጥድፊያው ጊዜ ጥቂትም ቢተርፍ አርባ ኩንታል ሀገር ውስጥ ሊቀር አይችልም። እጅግ ቢያንስ ለንጉሠ ነገሥቱ ዘውድ ጥንቃቄ መደረግ አለበት። ስለዚህ በጉዳዩ ተከታታይ ጥናት ሊደረግበት ይገባል።

ጣልያኖች በኢትዮጵያ ላይ ዝርፊያ ያካሄዱት ሲገቡ ብቻ አይደለም፣ ሲወጡም እንጂ። በድምሩ ኢትዮጵያ ውስጥ ወደ 250,000 የሚጠጉ ጣልያናውያን ነበሩ። እነዚህ የሄዱት የቻሉትን ያህል ተሸክመው ነው። እያንዳንዱ ኢጣልያዊ እጅግ ቢያንስ 200 ብር ይዞ ሳይሄድ አልቀረም። እጅግ ቢያንስ 50 ሚሊዮን ብር የሚያወጣ ገንዘብ ሀብት ወስደዋል ማለት ነው።

እንግሊዞች አዲስ አበባ ሲገቡ ዋና የተከላከሉት ንጉሠ ነገሥቱ ከመናገሻ ከተማቸው እንዳይገቡ፣ አርበኛውም ከከተማይቱ አካባቢ እንዳይደርስ ነበር። ይህ መከላከል ከፀጥታውና ከፖሉቲካው ጉዳይ የኢኮኖሚም ጉዳይ ነበረበት። መኪናዎችንና ልዩ ልዩ መሣሪያዎችን ነቃቅለው ወሰዱ። ከአዲስ አበባ እስከ አሥመራ የስልክ መሥመር የተዘረጋው ስምንት እጥፍ ነበር። እነሱ አራቱን ፈትተው ወሰዱ። በጦር ኃይል አሸንፈው የገቡበት አገር በመሆኑ ተው ማለት አልተቻለም፣ ተው ባይም አልነበረም። ምን ያህል እንደገፈፉ አይታወቅም። ጣልያኖች ሲወጡ የገፈፉትን ሳያህል ይቀር ይሆን? ሌላ ሃምሳ ሚለዮን ማለት ነው። ነገር ግን የዓለም አመለካከት እንግሊዞች በመግባታቸው ሲካሄድ ይችል የነበረውን ዝርፊያ እንደአስቀሩ ነው።

የኢጣልያ ጦር በየተዋጋበት አገር ዝርፊያ እንደ አካሄደ ነው የኖረው። በምግብ፣ በልብስ፣ በዕቃ ያካሄደው ዝርፊያ እጅግ ብዙ ነው። እያንዳንዱ ወታደር በቀን እጅግ ቢያንስ አንድ ስሙኒ ያህል ዝርፊያ ሳያካሂድ አልቀረም። በወረራ ግዳጅ ሥር በቆየበት በአምስት ዓመት ውስጥ እያንዳንዱ ወታደር ለ500 ቀን እንደተቀሰቀሰ ቢቆጠር፣ እጅግ ቢያንስ የ37.5 ሚሊዮን ብር ዝርፊያ አካሂዶአል ማለት ነው።

መጀመሪያ ጣልያኖች ሲገቡ፣ ኋላም እያነሱ ወጥተው እንግሊዞች ሲተኩ ሕዝብ እርስበርስ መዘራረፉ አልቀረም። በግንቦት ወር 1933 ዓ.ም ኢሕአዲግ እንደገባበት ጊዜ አይብዛ እንጂ። ከመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የተዘረፈው ከጠላት እጅ ከመግባት እንደዳነ እንጂ እንደተዘረፈ ባይቆጠር ይሻልም ይሆናል። ለምሳሌ የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ግምጃ ቤቱን ክፍቱን ትተውት እንደሄዱና በሦስተኛው ቀን ሲመለሱ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ሁሉ

እንደተወሰደ ባዩ ጊዜ ደስ እንደአላቸው "መልካም ሥራ ተሠራ" እንዳሉ ይነገራል። ቢሆንም ቢገመት ከ3 ሚሊዮን ብር ላያንስ ይችላል።

ጣልያኖች አገር በመግፈፍ ሕዝብ በመዝረፍ ብቻ አይደለም በኢትዮጵያ ላይ የኢኮኖሚ ጉዳት ያደረሱት። በገዛ ሕጋቸው የተወሰነሰትንም ነጥቀውታል። ለምሣሌ ከሕዝብ ለተወሰደ መሬት 6 ሚሊዮን ሴራ እንዲከፈል ከመንግሥታቸው ተፈቅዶ ሳለ፣ ለሕዝብ የተከፈለው 1,127,175 ሴራ ብቻ ነው።[6] ይህ ማለት ለኢትዮጵያ ገበሬዎች እንዲከፈል ከተወሰነው ገንዘብ ውስጥ 4,872,825 ሴራ ማለትም 2,175,300 ብር ነጥቀውታል ማለት ነው።

ሌላው ጉዳት ያካሄዱት ሥራ በማስፈታት ነው። ጣልያኖች የኢትዮጵያን ሕዝብ ሥራ ከአስፈቱበት መንገድ አንዱ እሥራት ነው። የኢትዮጵያ መንግሥት ከግምት አንብቶ ካሣ የጠየቀው በእሥር ቤት ላለቁት 35,000 ሰዎች ብቻ ነው። በእሥራት ከማቀቁ በኋላ የተሰቀቁ እጅግ ብዙ ናቸው። የእሥራታቸውም ጊዜ ረጉዝም ነው። ሃምሣ ሺህ ሰዎች እያንዳንዳቸው ለሁለት ዓመት ቢታሠሩ ሠርተው የሚጠቀሙበት 36.5 ሚሊዮን የሥራ ቀን አጥተዋል ማለት ነው። በዚያ ጊዜ ውስጥ 18 ሚሊዮን 250 ሺህ ብር ሊያገኙ ይችሉ ነበር።

ጣልያኖች ልዩ ልዩ የልማት ሥራዎች ሠርተዋል። እነዚህን ሥራዎች ያሠሩት የእነሱን ዜጐች ኃላፊ እያደረጉ ኢትዮጵያውያኑን ግን እያስገደዱ ነበር። በሥራው 32,000 ሰው ተካፋይ ሆኖአል። ከዚህ ውስጥ እጅግ ቢያንስ ሁለት ሲሦው ኢትዮጵያውያን ሳይሆኑ አልቀሩም። የእጅ መያ ለነበራቸው ወይም በዘያው በሥራ ላይ ልምድ ለአገኙ ጥቂቶች እንጂ፣ ለብዙሀኑ የጉልበት ሠራተኛ ለአብዛኛው ጊዜ ገንዘብ አልከፈሉም። በሥራው ላይ የተሰለፉት 21,300 ሠራተኞች እያንዳንዳቸው በዓመት ለ200 ቀን ለአራት ዓመት እንደሠሩ ቢቆጠርና፣ ሳይከፈላቸው የቀረው በቀን ሃያ አምስት ሣንቲም ሊሆን እንደሚችል ቢገመት፣ 8,520,000 ብር ተበዝብዞአል ማለት ነው።

ጣልያኖች በአርበኛው ላይ ለአምስት ዓመት ጦርነት ያካሄዱት ገበሬውን እያስገደዱ ሰጦርነት በማጋፈጥ ነው። ቀጥለው ደመወዝ እየከፈሉ ያዋጉአቸው እጅግ ጥቂቱን ነው። በድምሩ 920,000 ባንዳ እያንዳንዱ ለአንድ ዓመት አገልግሎአቸዋል።[7] የሙሉ ጊዜ እንኳን ባይሆን በተሰይ ለዘመቻ ለተንቀሳቀሰበት ጊዜ ሊታሰብለት ይገባል። እያንዳንዱ ባንዳ ለሁለት መቶ ቀናት እንዲዘምትላቸው ቢታሰብ 92,000,000 ብር በዝብዘውታል ማለት ነው።

አርበኛውም በእነሱ ወረራ ምክንያት ሥራ ፈትቶአል። የእሱም ሊታሰብለት ይገባል። አራት መቶ ሃምሣ ሺህ ሠራዊት ለአንዳንድ ዓመት በአርበኝነት ሥራ ተሳትፎአል። ይህ ሥራዊት ደግሞ ሥራ የፈታው

ሙሉውን ዓመት ነው። ስለዚህ ሠርቶ ሊገኝ የሚችለውን 82,125,000 ብር አጥቶአል።

የስደተኛውም ጉዳይ እንደዚሁ ነው በሱዳን 10,000፣ በኬንያ 5,000፣ በእየሩሳሌምና በሌሎች ቦታዎች 1,000 በድምሩ 16,000 ያህል ስደተኛ እንደነበር መገመት እምብዛም ከእውነት የራቀ አይሆንም። የሰደቱ ጊዜ በአብዛኛው ለአራት ዓመት ነበር። ስለዚህ እሷም 11,680,000 አጥቶአል ማለት ነው።

ሌላው ሊታሰብበት የሚገባው ቁስለኛው ነው። በጦርነቱ የቆሰለና ጣልያን ዘር ለማጥፋት ባካሄደው ዘመቻ የተሰለበ እጅግ ብዙ ነው። በእሥራትና በድብደባ የዕድሜ ልክ አካለ ጉዳሉ የሆኑ አሉ። ብዙው በዚያው በጦርነቱ ወቅት አልቋል። ቢሆንም የተረፈው ሠላሣ ሺህ አያንስም። በዚያን ወቅት ኢትዮጵያውያን ይኖሩበት የነበረው ዕድሜ ረዥም አልነበረም። አያንዳንዱ የአካል ጉዳተኛው ለአሥራ አምስት ዓመት በአካለ ጉዶሉነት እንደሚኖር፣ የአካል ጉድሉቱ የመሥራት አቅሙን በግማሽ እንደቀነሰበት ቢታሰብ 82,125,000 ብር አጥቶአል ማለት ይሆናል።

የዱር አራዊት ታላቅ ሃብቶች ናቸው። በጦርነቱ ጊዜ ብዙ አልቀዋል። ቁጥራቸው ስንት እንደነበረ የሚያስረዳ ምንም ነገር የለም። ሦስት ሚሊዮን ያህል እንደሞቱ ቢቆጠር ብዙ አያሳስትም ዓይነታቸውም ብዙ ስለሆነ ዋጋቸውን በአስተማማኝ ለመገመት ያመቻል። የጡጣም፣ የዝሆንም፣ የቀጭኔም፣ የአንበሳም ዋጋ በአማካይ ቢወሰድ ይሻል ይሆናል። ለአንድ አውሬ በአማካይ ግምት 20 ብር ቢሰጥ የ60,000,000 ብር ሀብት መድሞአል ማለት ነው። ከአዲስ አበባ እስከ ኮረም በሕዝብ ጉልበት የተሠራው መንገድ ግምት ከ300 ሚለዮን ብር አያንስም። ስለዚህ በአነስተኛ ግምት ጦርነቱ በኢትዮጵያ ላይ ከ3,980,135,500 ብር ያላነሰ የኢኮኖሚ ጉዳት አድርሶአል። (በተጨማሪ «አባሪ ሠሌዳ*» ይመልከቱ።)

ኢጣልያኖች ከሕዝብ የገፈፉት መሣሪያና ዋጋው

የመሣሪያው ዓይነት	ከአዲስ አበባ[11]	ከሐረርጌ[12]	ከአንክበር[13]	ከኢትዮጵያ[14]	ድምር	ዋጋ[15]
ጠመንጃ	11,353	1,420	447	383,559	396,779	79,355,800
መትረየስ	191	24	4	1238	1457	7,285,000
ሽጉጥ	169	-	-	2259	2428	121,400
ድምር						86,762,200

ሁኔታውን ለማሳየት ነው እንጂ፣ ጦርነቱ ያደረሰውን ጉዳት በምልአት ለማሳየት የሚቻል አይደለም። ለምሣሌ በሕዝቡ ላይ የደረሰው የሞራል ጉዳት በምን ይገመታል? በዓለም የተዋረደው ውርደት በምን ይገመታል? ከቤተክርስቲያን ጋር የተቃጠሉ ንዋየ ቅድሳት ለዘለዓለም የጠፉ ናቸው። ገንዘብ የተገኘ ዕለት ከሱት የሚገዙ አይደሉም። የአክሱምም ሐውልት አንዱ ነው።

ጦርነቱ በኢትዮጵያ ላይ ያደረሰውን የኢኮኖሚ ጉዳት ተመልክተናል። በተለይ በኢኮኖሚ ረገድ ስንመለከተው ኢትዮጵያ ያገኘችውም ጥቅም አለ። ጉዳቱን ተመልክተን ጥቅሙን ወደ ጉን ብንተው አመለካከታችን ምሉዕ አይሆንም። ስለዚህ የተገኘውንም ጥቅም አጣምረን መመልከት ይኖርብናል።

ኢትዮጵያ ከጦርነቱ የደረሰባት አንዱ ጉዳት በማኅበራዊ ጉዳይ ረገድ የደረሰው ለውጥ ነው። በዚህ ረገድ አስመራሪ የርክሰት ጉዳዮች ደርሰዋል። ታይቶና ተሰምቶ የማይታወቅ ህገ ወጥ የብልግና ሥራ ወደ ኢትዮጵያ ገባ። ወጣቱ ሰወላጆች መታዘዝ ተወ። ስካር፣ ሲጃራ ማጤስ ያዘ። አነጋገርም የጣልያንኛ ቃላትን በመቀላቀል ሆነ። የኢጣልያ ወታደር ከሴቶች ለመገናኘት የገባው እስኪወጣ ድረስ ይጠብቃል። ከሥራ ሰዓት ውጭ ዋናው ሥራ መጠጥና ፈቃደ ሥጋ መፈፀም ሆነ።[16] ይህ ሁኔታ በማኅበራዊ ጉዳይ ረገድ ከደረሱት ጉዳቶች አንዱ ገጽታ ነው።

ሂደቱ አንዳንድ ጠቃሚ ጉንም ነበረው። በሕግና በሥርዓት ሊፈታ ያልቻለው የባሪያ ነፃነት ጉዳይ ከግብ ደረሰ።[17] የባሪያ ቁጥር ከጎበረተሰቡ ከሩብ እስከ ሲሦ በሚገመትበት ሥርዓት ይህ ፈጣን ክስተት ቀላል አልነበረም። መሣፍንቱ፣ መኳንንቱ፣ ገባሩ እፎይታ አገኙ። ይህ እፎይታ ከጦርነቱም ቦኋላ እስከተወሰነ ጊዜ ድረስ ቀጠለበት። የገባር ሥርዓት ፈረሰ። ገበሬ ለመልከኛ፣ ለጉልተኛ፣ ለሻለቃ ሲሦ የመጥመድ ሥርዓት ተሻረ። ማር መቅዳት ቀረ።

በመኳንንቱና በመሣፍንቱ ወግ አጥባቂነት ተቀነሰ። ሠርቶ የመኖር መንፈስ ተቀሰቀሰ። የመማር የማወቅ ፍላጐት ከፍ አለ። ሰው ዘመናዊውን ያኗኗር ሥርዓትና የአሠራር ዘዴ ተለማመደ። ለወንዱ የመካኒክነት፣ የኤሌክትሪክ ሥራ፣ ግንበኝነት አናጢነት፣ ድንጋይ እያነጠፉ መንገድ መሥራት አስተማረው። ለሴቱ የጽዳት ሥራ፣ የአውሮፓውያን የምግብ አሠራር፣ የመስተንግዶ ሥርዓት አስለመደው። መንግሥታቸው ትምህርት ለኢትዮጵያውያን ለመስጠት ክጅሎት አይኑረው እንጂ፣ ጣልያኖች የቴክኒክ እውቀት ለመስጠት ትጉህን ነበሩ። በዚህ ሥራቸው ሊመሰገኑ ይገባቸዋል።

የአስፖርት እንቅስቃሴ ተጠናከረ። ምንም ዓላማው ወጣቱን ለሀገሩ ነፃነት እንዳይታገል ሽፋን ለመስጠት ቢሆን፣ እንደነ አቶ ይድነቃቸው ተሰማ ያሉትን የስፖርት ሰዎች ከትኩቶ ማሳደጉ ለኢትዮጵያ ጥቅም ሆነ። ሊኒማ

የማየት፣ ሬዲዮ የማድመጥ፣ ጋዜጣ የማንበብ ልምድም በከተማ ነዋሪው ወገን ዳበረ። ይህም ንቃት ሰጠ።

ኢጣልያ በኢትዮጵያ ላይ ካሰካሄደቻቸው የልማት ሥራዎች ሁሉ ከፍተኛው የመንገድ ሥራ ነው። መንገድ እስከየት እንደተሠራ ቀደም ብሎ ተገልጸአል። ከዚህ የምንመለከተው የወጭውን ሁኔታ ነው። በመንገድ ሥራ ረገድ ኢጣልያ ወጭ ያደረገችው ጠቅላላ ገንዘብ እስከ አንድ ቢሊዮን ብር እንደሚደርስ ይገመታል።

ጣልያኖች ጠቅላላ ቁጥራቸው 4007 የሚሆን ልዩ ልዩ እንዲስትሪዎች አቋቋመው ነበር። ለእነሱም በድምሩ 1,205,357,100 ብር እንደ አወጡ ተመዘግቦአል።

ሌላው የጣልያኖች የልማት ሥራ እንቅስቃሴ በእርሻ ነበር። ለባለርስቶች ግምት ከፍለዋል። ልዩ ልዩ የእርሻ መሣሪያዎች አስገብተዋል። ሦስት መቶ ሰባ ሦስት ቤቶች በእርሻዎቹ አሳባዚ አሠርተዋል። የአንዱን ቤት ዋጋ 75 ሺህ ሊሬ አነሱ ራሳቸው ገምተውታል። ስለዚህ ለእርሻ ሥራ ማሽነሪ 191,563,400 ብር እንቨስት ሳያደርጉ አልቀሩም።

ዋና ዋና ከተሞችን የሚያገናኝ የስልክ መሥመር ዘርግተዋል። ለፕሮፓጋንዳቸው ሥራ ማሳዬጃ ሬዲዮ ጣቢያና ማተሚያ ቤቶች አቋቁመዋል። ለዚህም ሃምሳ ሚሊዮን ያህል ብር ሳያፈስሱ የቀሩ አይመስልም።

ጣልያኖች ከአሳዬአቸው ሥራዎች እንደ መንገድ ሥራቸው ኢትዮጵያን የጠቀመ የለም። የሆቴል ሥራዎችም አገልግለዋል። በአዲስ አበባ፣ በሐረር፣ በድሬዳዋ፣ በጐንደር፣ በጅማ፣ በሌሎችም ቤቶች ተሠሩ። ገሚሶቹ ሸክላዎች፣ ከፊሎች ፎቅ ቤቶች ነበሩ። በድምሩ ከ3,000 የማያንሱ የከተማ መኖሪያ ቤቶች ሳይሠሩ አልቀሩም።

የተሠሩቱም፣

በአዲስ አበባና አካባቢው	1000.
በጐንደርና አካባቢው	500
በድሬዳዋ	700
በጅማና አካባቢው	300
በሌሎችም ትናንሽ ከተሞች	500
	3,000

እንደሆነ ይገመታል። ከጠላት መባረር በኋላ በትምህርት ቤትነት፣ በሃኪም ቤትነት፣ በልዩ ልዩ መሥሪያ ቤትነት፣ በመኖሪያ ቤትነት አገልግለዋል። እስከ ዛሬም እንደ አገሰገሱ ናቸው። የመሣሪያ ዋጋቸው፣ ከ133,928,500 ብር የማያንስ አይመስልም።

ከብዙ ክርክር በኋላ አርባ ሚሊዮን ብር የጦር ካሣም ከፍለዋል። የጦርነት ዓላማቸውን ለመፈፀምና የአስተዳደሩን ሥራ ለማካሔድ ከፍተኛ

ገንዘብ ወጭ አድርገዋል። እሱ የራሳቸው ጉዳይ ነው። ኢትዮጵያን የሚመለከት አይደለም። መጠኑን ወደ መገመትም አንገባም። እኛ የምንመለከተው ኢትዮጵያ ላይ በልማት ረገድ እንቨስት ያደረጉትን ብቻ ነው። እሱም ከ2,620,843,000 ብር አይበልጥም። /ሠንጠረዥ1/ በኢትዮጵያ ላይ ያደረሱት ጉዳት ግን ከ4,006,897,900 ብር አላነሰም። /ሠንጠረዥ 2/ ስለዚህ በኢኮኖሚ ረገድ ብቻ ከ1,446,054,900፣ በአጠቃላይ ከ1.5 ቢሊዮን ብር ያላነሰ ኪሣራ ኢጣልያ በኢትዮጵያ ላይ አድርሳለች። የዓለም ኅብረተሰብ አርባ ሚሊዮን ብር ካሣ የቆጠረው እንደ ልማዱ በኢትዮጵያ ላይ አድልቶ ነው።

ኢጣልያ በኢትዮጵያ ላይ እንቨስት ያደረገችው ገንዘብ

1. ለ6995 ኪሎ ሜት መንገድ ሥራ /በእንግሊዞች ግምት/[18]	1,000,000,000
2. ለ4007 ኢንዱስትሪዎች ማቋቋሚያ	1,205,357,100
3. ለእርሻ ሥራዎች መቋቋሚያ [19]	
ሀ. ለመሬት ግምት የተከፈለ	503,200
ለ. ለእርሻ ሥራዎች መቋቋሚያ	178,571,400
ሐ. ለ373 ቤቶች ማሠሪያ	12,488,800
ድምር	191,563,400
4. ለስልክ መሥመር መዘርጊያና ለሬዲዮ ጣቢያ-ማቋቋሚያ	50,000,000
5. ለ300 የከተማ ቤቶች ማሠሪያ	133,928,500
6. ኢጣልያ የከፈለችው የጦር ካሣ	40,000,000
ጠቅላላ ድምር[20]	2,620,843,000.

ማጣቀሻ ፅሑፎች

1. Alberto Sabacchi, *Ethiopia Under Mussolini*, p.47.
2. ጦርነቱ በአውሮፓ ያለቀው በሚያዝያ 1937 ዓ.ም ነበር።
3. አንድ ፓውንድ በአሥር ብር ምንዛሬ ሂሣብ።
4. ቢ.ዴዝሞንድ፣ ትርጉም ታደሰ በየነ አርገጤ፣ *የኢትዮጵያ አርባ ኩንታል ወርቅ የት ደረሰ?* ፣ገጽ 115-120፣ 156-159፣ 345-349።
5. ጆን ስፔንሰር፣ *ጥርሥ የገባች ሀገር* ፣ትርጉም መንግሥቱ ኃይለማርያም አርአያ፣ መዝገቡ ተክሌ ቢልልኝ፣ ገጽ 91።
6. Sabacchi, p.105.
7. ሠሌዳውን ይመልከቱ።
8. ጳውሎስ ኞኞ፣ *የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦርነት*፣ ገጽ 224-225።
9. ምንዛሬ አንድ አንድ ፓውንድ 10 ብር።
10. በጸሐፊው ግምት። የሥራ ዋጋ በቀን ሃምሣ ሂሣብ።
11. እስከ ግንቦት 7 ቀን 1928 ዓ.ም ድረስ ብቻ። ጳውሎስ ኞኞ፣ *የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦርነት*፣ ገጽ 150።
12. እስከ ነሐሴ ወር 1928 ዓ.ም ብቻ። ጳውሎስ ኞኞ ፣ገጽ 154።
13. ግንቦት 21 ቀን 1928 ዓ.ም ብቻ። ጳውሎስ ኞኞ ፣ገጽ 151።
14. ከመስከረም 30 ቀን 1929 እስከ ሚያዝያ 6 ቀን 1932 ዓ.ም።
    Sabacchi, p.180.
15. በፀሐፊው ግምት ጠመንጃ በ300፣ መትረየስ በ1000፣ ሽጉጥ በ50 ብር። መድፍ 222 ሲወሰድም የሕዝብ ባለመሆኑ አልታሰበም።
16. *ገሪማ ታፈረ*፣ ጐንደሬ በጋሻው፣ ገጽ 69-70።
17. ለጸበ ጌ ደሌቦ፣ *የኢትዮጵያ የገበሬ ሥርዓትና ጅምር ካፒታሊዚም*፣ ገጽ 67።
18. ጳውሎስ ኞኞ፣ ገጽ 202።
19. Sabacchi, p.100-104.
20. የምንዛሬ ሂሣብ፣
    ሀ. አንድ የእንግሊዝ ፓውንድ 10 ብር።
    ለ. አንድ ብር 2.24 ሊሬ።

ምዕራፍ ሃምሣ ሰባት

የጦርነቱ ጠቅላላ ግምጋሜ

በአጠቃላይ የጦርነቱን ሁኔታ መገምገም ግንዛቤን ለማዳበር ይረዳል። በማጠቃለያው ሂደት ውስጥ አንዳንድ ድግግሞሽ ቢያጋጥም መታገስ ነው።

ጦርነቱ በአሳዛኝ ሁኔታ ተካሂዶ ከተከለከለኛ ፈፃሜ የደረሰ ታሳቅ ገድል ነው። ጦርነቱ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት የተጫረበት ክብሪትና ይኸው ጦርነት ከፍፃሜ የደረሰበትን ድል ያበሠረ ነው። ይህንን አለማመን ታሳቅ የታሪክ ጭብጥ በዝንጋኤ መልቀቅ ነው።

ይህ ጦርነት በቅኝ ገዥነት በቆመው በነጩ ዘርና፣ በቅኝ ተገዥነት በሚማቅቀው ነጭ ባልሆነው ዘር መካከል ለምዕተ ዓመት ሲካሄድ ለቆየው ትንቅንቅ መደምደሚያ የሆነውን የነፃነት በር ከፈተ። በአድዋ ጦርነት የነጭ የበላይነት ከጥያቄ ላይ እንደወደቀ ሁሉ፣ በዚህኛው ጦርነት ደግሞ የነጭ የበላይነት ቀረ። የቅኝ አገዛዝ ዘይቤ ከመጥበቅ ወደ መሳላት፣ ከመያዝ ወደ መልቀቅ ዞረ። የጭቁን ሕዝቦች የነፃነት እንቅስቃሴ ተጀመረ። ይህንን አውነታ ዓለም መቀበል አይችልም። ይጐመዣዘዋል። ስለዚህ አንዳንድ ማሰረጃ ማቅረብ ግድ ይሆናል።

ጦርነቱ የተቀሰቀሰው በኢጣልያ አብራት ነው። ሌላ ምክንያት ኖሮ አይደለም። የተካሄደውም በኢጣልያ አጥቂነትና በኢትዮጵያ ተከላካይነት ነው።

በኢጣልያ ወገን ጦርነቱ በደንብ ታስቦበታል። የአርባ ዓመት ዝግጅት ተደርጐበታል። በፖለቲካ ረገድ በአውሮፓ ተቃውሞ እንዳይነሣ የዲፕሎማሲ እርምጃ ተወሰደ። ታሳቅ የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ ተካሄደ። ኢትዮጵያን ለማስነወር ያልተደረገ ነገር አልነበረም። የጣልያናውያንን ልቡና አንድ አድርጐ ለጦርነት ለማነሳሳት ጥረት ተደረገ። ሕዝቡም ተስማማ። ንጉሡ ኢማኑኤል ሣልሣዊ አሥመራ ድረስ መጥቶ ጉብኝት በማድረግ ሀሳቡን አፀደቀ። ቤተ ክህነቱ ተስማማ። ሲቀ ጳጳሱ ቡራኬ ሰጡ።

በመሣሪያ ረገድ ልዩ ዝግጅት ተደረገ። ከሽጉጥ እስከ መድፍ፣ ከበምብ እስከ መርዝ ድረስ ተዘጋጀ። የጐደለውም ተገዛ። ወታደር ከኢጣልያ፣ ከሊቢያ፣ ከኤርትራና ከሶማሊያ ተመለመለ ሠለጠነ። በመርከብ ተንቀሳ ኤርትራና ሶማሊያ ሠፈረ።

ኢትዮጵያ ውስጥ ሠርጐ በመግባት ልዩ ልዩ ምሥጢራትን ለማወቅ ጥረት ተደረገ። የሀገሪቱ መልከአ ምድራዊ ጥናት ለጦርነትም፣ ለሠፈራም፣ ለልማት ሥራም በሚረዳ መልክ ተካሄደ። ሕዝቡን እርስ በርስ በዘር፣ በጐሣ፣ በሃይማኖት ለመለያየት ታሳቅ ሙከራ ተደረገ። መሣፍንቱንና መኳንንቱን በጥቅም ለመደለል ተሞከረ። ለዚህ ሥራ ሚስዮናውያን በብዛት ተሰማሩ። በልዩ ልዩ ቦታ የተተከሉ ቆንስላዎችን በመተገን የዲፕሎማቲክ ሰዎች ተልእኮአቸውን በሚገባ አከናወኑ።

በኢትዮጵያ ወገን ሁኔታው በሰላም ለመኖር በሚደረግ ጥረት ላይ የተመሠረተ ነበር። ስል ሥልጣንና ጥቅም ሽሚያ እንጂ፣ ስለሀገር መከላከል ያሰበ የለም። ከ1900 ዓ.ም በኋላ ኢትዮጵያ የዝቅዝቂት ነው የተጓዘችው። ችግሩ በዳግማዊ አፄ ምኒልክ የረጅም ጊዜ ሕመም ጀመረ። ንጉሠ ነገሥቱ ከነጭ ሰው እጅ ወደቁ። በደዌ ላይ ጥልፍልፍ ነገር መጣባቸው። ለአልጋ ወራሽነት የተመረጡት ልጅ ኢያሱ ለተመረጠበት ሥራ ብቃት አላሳዩም። ችግሩ አፄ ምኒልክ ከሞቱም በኋላ ቀጠለ። ወጣቱን መሥፍን ከሥልጣን አስወርዶ ንግሥት ዘውዲቱን የመተካት ሥራ ተካሄደ። እሱም ብቻውን በቂ ሊሆን ስለአልቻለ፤ በቅርብ የሚረዳቸው ሌላ ወጣት መሥፍን አስፈለገ። ደጃዝማች ተፈሪ መኮንን ራስ ተብለው ባለሙሉ ሥልጣን አልጋ ወራሽ ሆኑ። ይህም የራሱ የሆነ ችግር ነበረው። ይህ የፖለቲካ ቀውስ የርስበርስ ግጭት አስከተለ። መንግሥት ከወሎና ከጐንደር ጋር ተዋጋ። ውጊያው በሸዋ ስም ተካሄደ። ነገር ግን ሸዋ በተደረገው ለውጥ አላመነበትም። የውስጥ ቀውስ አጋጠመው።

በዚህ ዓይነት ለውጭ ኃይል መግቢያ በር ተከፈተ። አፄ ምኒልክ "ልጅን የከዳ ርጉም ይሁን። ጥቁር ውሻ ይውለድ" በማለት የረገሙት እርግማን፣ "ነፋስ እንዳይገባባችሁ" ብለው የሰጡት ምክር አደማጭ ሳያገኝ ቀረ። በዚህ ሁሉ ምክንያት በሀገር መከላከያ ረገድ አንዳች ዝግጅት ሳይደረግ የ1928 ዓ.ም ጦርነት ተቀሰቀሰ። ጦርነቱ ሲቀሰቀስ በኢትዮጵያ እጅ ላይ የነበረው፤ በ1915 ዓ.ም አባል የሆነችበት የዓለም መንግሥታት ውል የተፃፈበት ወረቀት ብቻ ሆነ። የፈረንጅ መኳር ተሰበሰበ። ገሚሱ ረዳት በመምሰል፣ ሌላው አስታራቂ በመምሰል። አንዱም ለኢትዮጵያ የሚበጅ አልሆነም። በማወቅም ባለማወቅም አብዛኛው ኢትዮጵያን የሚጐዳ ሆነ።

ኢጣልያ በሰሜን ከአሥመራ በደቡብ ከሞቃድሾ እየተነሣች፤ እንደ አሰኛት በመንደርደር ኢትዮጵያን አጠቃች። በጥይት በቦምብ በመርዝ የኢትዮጵያን ሕዝብ ፈጀች። ድንበር ጥሳ በሁለቱም ወገን ገባች። የዓለም ማኅበር አንዳች ከማድረግ ስሞታ በማድመጥ ብቻ ሞቱን አሸለበ። እንግሊዝ ፈረንሣይን ተቀጽላ በማድረግ አስታራቂ በመምሰል ኢትዮጵያን የሚጐዳ፣ ኢጣልያን የሚጠቅም፣ የአንግሊዝን የራስዋን ጥቅም የሚያዳበር ሃሳብ ይዛ ብዙ ነገር አጠነጠነች።

ጣልያን ድል አድርጐ ሲገባ ንጉሠ ነገሥቱ አገር ጥለው ሄዱ። ከጣልያን ጋር የውስጥ ግንኙነት ያልነበራቸው መኳንንትና መሣፍንትም እንደዚሁ አደረጉ። አብዛኞቹ መኳንንትና መሣፍንት ወራሪውን ወድደው ለምደው ከእሱ ጐን ቆሙ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ብቻውን ፍኖተ መስቀሉን ተሸክሞ ሀገር የመከላከል ሥራውን ቀጠለ። በመሳልት በሌሊት ተዋጋ። አጥንቱን ከሰከሰ፣ ደሙን አፈሰሰ። ቀደም ብሎ በልዩ ልዩ ስም ገብቶ

ኢትዮጵያ ውስጥ የተሰገሰገ ነጭ ዘመዱን አገኘ። ፈነጠዘ። በተለይም ግሪክና አርመን።

የኢትዮጵያን ውድቀት ያፋጠኑት ነገሮች ብዙ ናቸው። የርስ በርስ አለማመስማማት ዋናው ነው። ሥልጣን በማዕከላዊ ደረጃ በጥብቅ መያዙም አንዱ ችግር ሆነ። በዚህ ላይ ደግሞ ክሽማምንቱ የሚበዙት ኢትዮጵያዊነታቸውን የሸጡ ከሀዲዎቹ ነበሩ። ተው ባይም አልነበራቸውም። ማንኛውም የቤተ መንግሥቱ ምሥጢር፣ የንጉሠ ነገሥቱ መልዕክት ቄሞር ለጣልያኖች ክፍት ሆነ።

በጦርነቱ አካሄድም ላይ ብዙ ጉድለት ነበር። ባለው የሰው ኃይልና መሣሪያ ለመጠቀም በቂ ጥረት አልተደረገም። ለኢትዮጵያ ተቆርቋሪነት ከነበራቸው መሪዎች አብዛኞቹ ከእሥራትና ከግዞት ገቡ። በሥልጣን የሚንቢቹት ከሀዲያን ሆኑ። ራስ ብሩን የመሰለ የጦር ሰው ከሥልጣን አስወርዶ በፊታውራሪነት መሸምቀቅ ለምን ነበር? ኮርማሽ የነበረው የጦር መሣሪያ ለሰገሌ ጊዜ ተፈልጐ ነበር። ለምን ለጣልያን ወረራ እንዲውል ሳይደረግ ቀረ? ከአዲስ አበባ እስከ ኮረም የመኪና መንገድ ተሠራ። ጠላት ሰተት ብሎ ገባበት። እንደካራማራ ያሉ የተፈጥሮ መከላከያነት ያላቸው በሮች ተሰቀው ጦሩ አጋዴን በረሃ ውስጥ ወርዶ አለቀ። አምባሰጌን የሚያህል የተፈጥሮ ምሽግ እንዴት በነፃ ለጠላት ተሰቀቀ? መጋቢት 21 ቀን 1928 ዓ.ም ጦርነት እንዲደረግ የተሰጠው ትዕዛዝ ተሰውጦ፤ ሠራዊቱን ለምን ለሙሉ ቀን የአየር ድብደባ አጋለጠ? ለጊዜው መልስ የለም። ነገር ግን እነዚህ ክሀተቶች ትውልድ የሚረሳቸው አይደሉም።

እያንዳንዱ ክፍለ ሀገር ምን እንደ አደረገ መመልከት ግንዛቤ ይሰጣል። ተቀፍድዶ ከታሠረበት ከማዕከላዊ እዝ ስለተለቀቀ፤ የኢትዮጵያ ጀግና ጠላቱን በራሱ ሃሳብና ዘዴ ገጠመው። የገዛ መሣሪያውን እየቀማ ተለቀቀበት። የፋሲሚያው ሥራ ጣልያን በገባባቸው በትግራይና በወሎ ተካሄደ። ዋና ዋናዎቹ የጦር ቦታዎች ጐንደር፣ ውሎ አድሮም ጐጃም ሆኑ። በሸዋ መንዝና ተጉለት፣ ቡልጋና ሽንክራ፣ ይፋትና አንኮበር፣ መርሐቤቴና ለላሌ፣ ግንደ በረትና የጉራጌ አገር ሆኑ። ኢሉባቡርና ክፋ ለመጀመሪያው ጊዜ ደህና አገዛማሚያ አሳዩ። ነገር ግን ወዲያው ቀዘቀዙ። በሐረርጌ፣ በባሌና በአርሲ የነበረው ጦር የተቻለውን ያህል ሠራ። ነፍጠኛ ወደ ስደት አመራ። ሲዳሞ በመጀመሪያው ጊዜ ታላቅ ሥራ ሠራ። ነገር ግን ዕድሜ አላገኘም። ጋሞ ጐፋ ወደ ኬንያ የተገዘውን ስደተኛ አገዘ። የተቻለውን ያህል ተዋጋ። ወለጋ የተቻለውን ያህል ተከላከለ። አፋር በቡልጋ፣ በእንክበርና በይፋት በኩል የነበሩትን አርበኞች ረዳ። በጐ ፈቃደኛ የሆኑ ኤርትራውያን ከጣልያን እየከዱ ከኢትዮጵያ ሠራዊት ጐን በመቆም የማይናቅ ድጋፍ ሰጡ።

አርበኞች ይህንን ይሥሩ እንጂ ድክመቶችም ነበሩባቸው። ከድክመቶቻቸው ዋነኛው በጋራ የሚመሩበት ድርጅት ለማቋቋም

አለመቻላቸው ነው። የነፃነት እንቅስቃሴን ከሚያጠናክሩ ነገሮች ዋነኛው የአስተባባሪ ድርጅት መኖር ነው። ነገር ግን አርበኞች እንደዚህ አላደረጉም። ሁሉም በየፊናው የወደደውንና የቻለውን አደረገ። ድርጅት እንዳያቋቁም አፍራሽ ኃይሎች ነበሩ። ከእነዚህ አፍራሽ ኃይሎች አንዱ ጣልያን ሲሆን፤ ሌሎቹ ደግሞ የቀድሞዎቹ የገዥ መገኖች ነበሩ።

ይህም ሆኖ አርበኛ አሰባሳቢ አካል ለመፍጠር ጥረት ማድረጉን አላቋረጠም። በቡልጋ የመልአክ ፀሐይ ኢያሱ ምኒልክ መንገሥ፣ የሆለታ መኮንኖች የጥቁር አንበሳን ድርጅት ማቋቋም፣ በወሎና በጐንደር ልጅ ዮሐንስን አስተባባሪ ለማድረግ መሞከር፣ በተገለሉት የኢትዮጵያ ጀግኖች ማኅበር መመሥረት የዚህ ጥረት አካል ናቸው። በጐንደር አርበኛ መከረና መርጦ መሪዎች ተሾሙ። በጐጃም ልዩ ልዩ ማኅበራት ተቋቋሙ። የሪፐብሊክ መንግሥት ለመመሥረት የሞከሩም ነበሩ። ነገር ግን ከአገር ባህል ጋር ሥምረት ስለአልነበረው ውጤት ሳያስገኝ ቀረ። ሌሎቹ ግን በተወሰነ መጠን ለተወሰነ ጊዜ ይሁን እንጂ ውጤት አስገኝተዋል። የአነራስ አበበ፣ የእነ ራስ ውብነህ፣ የእነ በላይ ዘለቀ ጥንካሬ በእነዚህ ድርጅቶች ተመሥርቶ የተገነባ ነው። ከዚህ ላይ ሊጠቀስ የሚገባው ቀዳማዊ ኃይለሥላሴም ወደ ሥልጣን የተመለሱት ደጋፊዎቻቸው በብርታት ስለሠሩ መሆኑ ነው። ከዚህ ሁኔታ ትምህርት ሊወሰድበት ይገባል። ድርጅት ዋና አጠናካሪ ኃይል ነው። ነገር ግን በሀገር ባሕልም ሥርዓት ላይ ካልተመሠረተ ዘለቄታ አይኖረውም። ይህ በደንብ ሊጤን ይገባል።

ሌላው የአርበኞች ድክመት የርስበርስ አለመስማማት ነው። በቁም ነገር ብቻ ሳይሆን በጥቃቅን ጉዳይ የተጋጨበት ሁኔታ ተስስቶአል። በሥልጣን ምክንያት ለተነሣው ጠብ ጎንደር የልጅ ወሰን ኃይሉና የደጃዝማች ነጋሽ ወርቅነህ፤ በሴት ምክንያት ለደረሰው ቡልጋ የፊታውራሪ ዝቅ አርጌና የፊታውራሪ ሞገሴ መኮሪያን እልቂት፤ በአሰባልታ ምክንያት ለሚነሣ ጠብ ቡልጋ በፊታውራሪ ወልደሃድና በፊታውራሪ ደባልቄ መካከል የተከሰተው ግጭት፤ ቃልን ባለማክበር ምክንያት ለሚደርስ ጉዳት ቡልጋ በረከት የእነ ፊታውራሪ አጐናፍር እልቂት ለአብነት ሊጠቀስ ይችላል። በዚያ ቀውጢ ቀን በጥቃቅን ምክንያት አለመግባባት እየተፈጠረ ኃይልን መቀነሱ ያሳዝናል። ለወደፊቱም ግንዛቤ ሊወሰድበት ይገባል።

ኢትዮጵያን ለማዳን የተደረገው ፍልሚያ በአንድ የጦር ሜዳ ማለትም በማይጨው ብቻ ማክተሙ ያሳዝናል። መጋቢት 21 ቀን ሊዋጋ ከሠልፍ የገባው በዚያው ቀን ተዋግቶ፤ ከኋላ ይጠብቅ የነበረው ጦር በማግሥቱ መጋቢት 22 ቀን 1928 ዓ.ም ደግሞ ቢሆን የተሻለ ውጤት ይታይ ነበር። ከዚህም በስተቀር በየቦታው ተበትኖ ቢሰላከል ጠላቱን መመለስ ባይቻል እንኳን፤ የጦርነቱን ዕድሜ ማስረዘምና የሀገሪቱን ሕልውና ከውድቀት ላይ የመጣሉ ፍጥነት ይቀነስ ነበር። በጦርነቱ ጊዜና ቦታ እየመረጥን ከቦታ ወደ

ቦታ እየተዘዋወርን በገዛታ እንዋጋ የሚለው አመለካከት ብስለት የሚሰኳው ጉዳዩ ከዚህ አንጻር ሲታይ ነው። የጦርነቱ በአንድ ጊዜ ማለቅ የአውሮፓ የጦር መሪዎችን ጭምር አስደንቆአል። ሁለትና ሦስት ዓመት የወሰደ ቢሆን፤ የአውሮፓም ልቡና ተለውጦ ኢትዮጵያን ወደ መደገፍ ይመለስ ነበር። በአንድ ቀን ድል የኢትዮጵያ ጦር ተበተነ። መበተኑ ከአልቂት አዳነው። ከአልቂት መዳኑ በመጠነኛ ሁኔታም እንኳን ቢሆን አርበኝነትን ለማቋቋም ረዳ።

ንጉሠ ነገሥቱንና መንግሥታቸውን የሚያስመሰግን ሥራ የተሠራው በውጭ ግንኙነት ረገድ ነው። የአጥቂውን በደል ለማሳየትና ለኢትዮጵያ ዕርዳታ ለማግኘት የተደረገው ጥሩ ነበር። ነገር ግን አሱም እንደሌላው ጉዳይ ሁሉ እንከን አላጣውም። የመጀመሪያው ችግር ንጉሠ ነገሥቱ በዓለም መንግሥታት ማኅበር ላይ የነበራቸው ትምምን እጅግ ጠንካራ ሆኖ መፈናፈኛ ማሳጣቱ ሆነ። ሌላው ችግር በሀገር ውስጥ የነበሩ የውጭ አገር ሰዎችን ለመቆጣጠር አለመቻሉ ነበር። እጅግ ቢያንስ የኢጣልያ ዜጐች ከሀገር መውጣት ነበረባቸው። ሌላው ችግር እንደ ሌላው ሥራ ሁሉ በውጭ ጉዳይም ከሐዲያን ተሰገሰጉበት። ሮም የነበረው አምባሳደር አፈወርቅ ገብረኢየሱስ አፈ ቋንጮር ተብሎ በኢትዮጵያ ያሻውን ተናገረ። ፓሪስን ያህል የፖለቲካ ማዕከል ወልደማርያም አየለ ለቀቀው። ከዚህ ሁሉ ጋር እነ አቶ /ብላቴን ጌታ/ ሎሬንዞ ትዕዛዝ በውጭ ጉዳይ ረገድ የሚደነቅ ሥራ ሠሩ።

ሀገር በጠላት እጅ በወደቀች ጊዜ ጥሶ መሐዲ ተገቢ ነው ተገቢ አይደለም የሚለው ክርክር ለረጅም ጊዜ የሚቆይ የታሪክ ሥራ ይሆናል። ከአሁኑ ትውልድ በዚህ ረገድ የሚጠበቅ ነገር የለም። ነገር ግን ሰተከታዩ ትውልድ ጥቅም ሲባል ጉዳዩ ሲነሣ ይገባዋል። ስለስደት ያለውን ክርክር ከዚህ ላይ ትተን በውጭ አገር የተሰደዱ ኢትዮጵያውያን የፊጸሙትን ወደ መመልከት እንሻገራለን።

በመጀመሪያ ደረጃ ንጉሠ ነገሥቱ ሦስት መልካም ሥራዎች ሠርተዋል። ከነዚህ መልካም ሥራዎች አንዱ በጀኔቭ ጉባዔ ላይ በመገኘት የኢትዮጵያን አቤቱታ ለዓለም ጎበረተሰብ ማሰማታቸው ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ሥልጣን እንዲለቁ በጥቅም ለመደለል ጣልያኖች ያደረጉትን ሙከራ ማክሸፋቸው ነው። በዚህ ጉዳይ ንጉሠ ነገሥቱ ፅንዑት ባያሳዩ ኢትዮጵያ እጅግ አስነዋሪ ከሆነ ነገር ላይ ትወድቅ ነበር። ሦስተኛው ቡጉ ነገር የነበረባቸውን የጦርና የነገር ወጥመድ በጥበብ አልፈው ኢትዮጵያን ለድል ያበቃ አመራር መስጠታቸው ነው። ወደ ቀድሞ ሥልጣናቸው ሊመለሱ የቻሉትም ስለዚህ ነው።

ሌሎችም ስደተኞች የተቻላቸውን ያህል አገራቸውን ረድተዋል። በለንደን የነበረው ቡድን ኢትዮጵያ በዓለም ጎበረተሰብ ዘንድ እንዳትረሣ ጥረት አድርጐአል። በፓሪስም የኢትዮጵያ ኤምባሲ ጀርመኖች እስከ ገቡበት ቀን ድረስ ሥራውን ቀጥሎአል። በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋህዶ

ቤተክርስቲያን ገዳም ሊተርፍ የቻለው በሰደተኛው ብርታት ነው። በሱዳን የነበረው ስደተኛ ነፃነትን ለማስመለስ ከተደረገው ፍልሚያ አስኪል ሆነ። በኬንያ የነበረው የተጣለበትን የኑሮ አሽክላ በጥቦሶ ከጦርነቱ በመግባት ድርሻውን ተወጣ። በአሜሪካ የነበሩትም ማኅበር በማቋቋምና ድምጻቸውን ከፍ አድርገው የኢትዮጵያን በደል ለሕዝብ በማሰማት፤ መንግሥቱ ይዞት የነበረውን ጣልያንን የመደገፍ አዝማሚያ አስጥለዋል። በጅቡቲና በበርበራ የነበሩም እንደዚሁ የተቻላቸውን አድርገዋል። ተሰደናል ብለው እናት አገራቸውን አልዘነጓትም፤ በተቻላቸው መጠን ተጋድሎዋል። ዘርዓይ ደረስና ሻምበል አብዲሣ አጋም ቁጥራቸው ከእነዚህ ተጋዳዮች ውስጥ ነው። የሀገራቸውን ክብር ለማስጠበቅ እሥረኞች ስንኪን ቸል አላሉም። ራስ እምሩ ለኢጣልያ ባለሥልጣኖች ያሳዩት ንቀት ከዚህ ሊጠቀስ ይገባል።

አዲስ አበባ የሀገሪቱ መናገሻ ከተማ እንደ መሆንዋ መጠን፤ ስለ ሀገሪቱ ነፃነት የበኩልዋን አስተዋጽኦ ማድረግ ነበረባት። ነገር ግን እንደዚህ አልሆነም። የጠላትን አገባብና ቆይታ የተቀበለው በጸጥታ ነው። ሐምሌ 21 ቀን 1928 ዓ.ም የውጭው ጦር ሰብሮ ለመግባትና ከተማይቱን ለማስለቀቅ መከራ በአደረገበት ጊዜ በከተማይቱ የውስጥ እንቅስቃሴ አልታየም። የካቲት 12 ቀን 1929 ዓ.ም ጣልያኖች ሴት ወንዱን ሲፈጁ ፍርግጥ ያለ የለም። ጠላት አዲስ አበባ የገባው ከአንድ ሺህ አምስት መቶ በላይ ሰው ገድሎ ነው። ነገር ግን የእነዚህ ሰዎች መከራ የግለሰብ እንጂ የተቀነባበረ አልነበረም።

በዐጉው በኩል ደግሞ ያልተገባ የፀጥታ መናጋት አልደረሰም። በከተማይቱ የሠፈረው የዲፕሎማቲክ ሰው አንዳች ችግር አልደረሰበትም። ጣልያኖች በገቡ ጊዜ አዲስ አበባ ላይ የታየው ሁኔታ ይህንን የሚመስል ሲሆን፤ ሲወጡም ምንም ችግር አልነበረም። የእንግሊዞችም አገባብ ሰላማዊ ሆነ። ንጉሠ ነገሥቱ የገቡት ከበቂ ዝግጅት በኋላ ስለነበር ማንኛውም ነገር ሠመረ።

ይህንን በመሰል አጠቃላይ ግምገማ ከሀዲያን በሀገራቸውና በወገናቸው ላይ የፈጸሙት በደል እንደገና መነገር አለበት። የኢትዮጵያ መካንነትና መሣፍንት በጣልያኖች ዘንድ ሞገስ ለማግኘት ያደረጉት ርብርቦሽ አስገራሚ ነው። ግብራቸው ሲመዘን ቀድሞውኑ የተመረጡት በክህደት ሥራ ችሎታቸው እየተመለመሉ ነበርን የሚያሰኝ ነው። የደጃዝማች ኃይለሥላሴ ክህደት የኢትዮጵያን ምሥጢር ለጠላት አሳልፎ ከመስጠት አደረሰ። የእነደጃዝማች ገሠሠ ከጦር ሜዳ መመለስ የሀገርን ሞገስ ቀነሰ። የአባ ጀቢር ጭካኔ የሚዘገንን ነው። በራስ እምሩ የሚመራውን ጦር ከውድቀት አደረሰ። የእነ ደጃዝማች አበራ ካሣ ለፈሰፋሳነት ስራሳቸውም ለወገኖቻቸውም ጥፋትን አስከተለ። በአዲስ አበባ የነበሩ ራስ ደጃዝማቾች ሽርጉድ ግድ ነው። ሀገርን ወገንን በመከራ በጭንቅ ጊዜ መክዳቱ እጅግ አሳፋሪ ጉዳይ ነው። መጭው ትውልድ ከአለፈው ትውልድ መማርና ማወቅ ያለበት ይህንን ነው።

በቤተክርስቲያን ውስጥ ለሀገር የመቆምም የክህደትም ሥራ ተካሄደ። የአባ አብርሃምን ክህደት ጽድስና የሰጡአቸው የአስክንድርያው ፓትርያርክ ውግዘት አልመለሰውም። ከሁሉ በላይ የሚገርመው ገና ጠላት ከመግባቱ በፊት ለዚሁ ሥራ ተዘጋጅተው፤ በአደራ የተሰጣቸውን ለኢትዮጵያ ጦር ልብስና መድኃኒት የሚገዛበትን ገንዘብ መክልከላቸው ነው። ከእምነት ወንድማቸው ከአቡነ ጴጥሮስ ጋር በሰማይ ቤት ሲገናኙ ምንኛ ትዝብት ይሆንባቸው? አባ አብርሃም ሲሞቱ አባ ዮሐንስ ተተኩ። በታሪክ ፊት የአሳቸውም ዕድል ከአባ አብርሃም አንድ ነው።

የደብረ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ፤ የመንበረ መንግሥት ገብርኤልና ከተጉለት የድንበሬ /ግንባርዋ/ ማርያም ማይጨው ዘመቱ። አቡነ ጴጥሮስና አጬጌ ገብረ ጊዮርጊስ በጦር ሜዳ ላይ ቆሙ። አቡነ ጴጥሮስ በአዲስ አበባ፤ አቡነ ገብርኤል በጎሬ በእምነት ጸንተው የሰማዕትነት ጽዋ ተቀበሉ። የገጠር አብያተ ክርስቲያናት ከአርበኛ ጋር ቆሙ። የአራዳ ደብረ ጽጌ ጊዮርጊስ ጽሳት በቡልጋ አዋጋ። ከአርሲ የሁሩታ ማርያምና የዲስላ ገብርኤል፤ እንደዚሁም ከጋሞ ጕፋ የጨንቻ ጊዮርጊስ ወደ ኬንያ ተወሰደ። ካህናት ለተወሰደው ጥምቀት ክርስትና በመስጠት፤ የሞተውን በመፍታት፤ የተጣላ በማስታረቅ፤ ለሀገርና ለወገን ጸሎት በማድረግ ታላቅ ዕርዳታ አደረጉ።

በኢትዮጵያ ላይ የደረሰው የኢካኖሚ ጉዳት ከአራት ቢሊዮን ብር አላነሰም። ጣልያን ኢትዮጵያ ላይ ለልማት አዋለች የሚባለው ገንዘብ 2.6 ቢሊዮን ብር ብቻ ነው። በዚያውም ኢትዮጵያ እምብዛም አልተጠቀመችበትም። ይህም ሆኖ ኢትዮጵያ ከ1.4 ቢሊዮን ብር በላይ እንደ ከሠረች ቀርታለች ማለት ነው። ዳግመኛ ተመልሰው በገንዘብ የማይገኙ ብዙ ቅርሶች ተዘርፈዋል፤ ተቃጥለዋል፤ ወድመዋል።

ጦርነቱ የኢትዮጵያን ነፃነት በዓለም ፊት መልሶ አረጋገጠ። ከነበረባት የውስጥ አንዳንድ የኋሊት ጕታች ኃይል አላቀቃትም። ለአዲስ ሥራ አዘጋጃት። በዚህ ዕድል ምን ያህል እንደ ተጠቀመችበት በቀጣዩ የታሪክ ምርመራ የሚታይ ይሆናል። አጠቃላይ ሁኔታው ይህ ሲሆን፤ ዝርዝሩንና ማስረጃውን ከዚሁ መጽሐፍ ውስጥ ማየት ያስፈልጋል።

ምዕራፍ ሃምሳ ስምንት
የአድዋና የማይጨው ጦርነት ንፅፅር

ታሪክ ነውና የአድዋንና የማይጨውን ሁኔታ ማነፃፀር ይገባል። ልዩነታቸው ይብዛ እንጂ አድዋና ማይጨው ተመሳሳይነትም አላቸው። ተመሣሣይነታቸውን ብናስቀድም የሁለቱም ጦርነት ዓላማ አንድ ነው። ጣልያን ቅኝ ግዛት አድርጌ ልግዛ፣ ኢትዮጵያ አይደረግም አልገዛም ነው። ጠብ አጫሪዋ በሁለቱም ጦርነት ጣልያን ነች። ምንም መራቶችዋ ተሸራርፈው የተወሰዱባት ቢሆን ኢትዮጵያ ጠብ አልቀሰቀሰችም።

የአድዋን ጦርነት የቀሰቀሰው ሚያዝያ 25 ቀን 1881 ዓ.ም ወሎ ውስጥ ውጫሌ በተባለ ቦታ የተዋዋሉት ውል 17ኛው ምዕራፍ ነው። ውሉ የተጻፈው በአማርኛና በጣልያንኛ ቋንቋዎች ብቻ ነው። አፄ ምኒልክ የፈረሙት በአማርኛ በተጻፈው ላይ ብቻ ነው። ነገር ግን በተሰይ ስለውጭ ጉዳይ በሚናገረው በአንዱ አንቀጽ ላይ ብቻ ልዩነት ተፈጠረ። ይህም በአማርኛው ጽሑፍ የኢትዮጵያ መንግሥት "ፈቃዱ የሆነ እንደሆነ" የሚለው ቃል፣ በጣልያንኛ ቋንቋ በተጻፈው ላይ "ይገባዋል" ይላል ስለተባለ ጠብ ተነሣ። ጣልያኖች ለአውሮፓ አገሮች አስተላልፈውት የነበረውን የሐሰት ወሬ አፄ ምኒልክ አስተባበሉ። ሁለቱም ወገኖች በአቋማቸው ጸኑ። ጦርነቱ ተነሣ።[1] በማይጨው ጊዜ ግን ጠብ የተቀሰቀሰው ኢጣልያ የኢትዮጵያ ግዛት ከሆነችው ከወልወል ውስጥ ገብታ በኢትዮጵያና በእንግሊዝ ሱማሌ መካከል ይካሄድ የነበረውን የወሰን ክልል ስለአገደች ነው። ቢሆንም ሁለቱም ጦርነቶች የተካሄዱት ኢጣልያ ወሰን አልፋ ከኢትዮጵያ ግዛት እየገባች ነው።

በአድዋ ጊዜ ኢትዮጵያ አፄ ምኒልክ፣ የማይጨው ጊዜ ኢጣልያ ቤኒቶ ሙሶሊኒ ነበሩአቸው። ሁለቱም ለጦርነቱ በቂ ዝግጅት አደረጉ። አፄ ምኒልክ የትግራን መኳንንት እነ ራስ መንገሻ ዮሐንስን፣ ራስ አሉላ አባ ነጋን፣ ራስ ሐጐስን ከእነ ሠራዊታቸው አስተባበሩ። የጅማን፣ የሌቃን፣ የቤኒሻንጉልን፣ የወላሞን የሌላውንም ጭሣ ባላባቶችና ሹሞች ድጋፍ አገኙ። ጐጃምን በንጉሥ ተክለ ሃይማኖት አማካይነት አስነሱ። ጐንደርን በእቴጌ ጣይቱ። አዲስ ከተያዘው ከደቡብ አገርም የሚበዛው ወገን ተባበራቸው። ወሎን በራስ /ንጉሥ/ ሚካኤል አማካይነት ያዙ። ሙሶሊኒም በማይጨው ጊዜ እንዲሁ አደረገ። የኢጣልያን ሕዝብ ለጦርነቱ በአንድ ልብ አስነሣ። ሌት ወንዱ፣ ልጅ አዋቂው እንዲተባበረው አደረገ።

በመሣሪያ ረገድ አፄ ምኒልክ ልዩ ጥረት አደረጉ። ከፈረንሣይ፣ ከኢጣልያ፣ ከግብፅ፣ ከሩስያ፣ ከእንግሊዝ መሣሪያ እየገዙ በታጁራ፣ በአሰብ፣ በዘይላ በኩል በሚራራ እያስጫኑ አስገቡ። በአድዋ ጦርነት ጊዜ በጠቅላላው ከ3,348,000 ጠመንጃና ከ9,410,000 ጥይት፣ ከ70 በላይ መድፎች ነበሩአቸው። ከጠመንጃዎቹ 15% እንደዚሁም ከጥይት 43% የተገዛው

ከጣልያን ከራስዋ ነበር። አፄ ምኒልክ ሠራዊታቸውን መሣሪያ ለማስታጠቅ ያደረጉት ጥረት የሚታወቀው፣ በ1868 እስከ 1870 ዓ.ም አካባቢ በእጃቸው የነበረው መሣሪያ ከ3,000 ይበልጥ አንዳልነበረ ሲታወስ ነው። በ1988 ዓ.ም የአድዋ ጦርነት አፄ ምኒልክ ከጣልያን ጋር ስመዋጋት የተሰለፉት፣

	ኢትዮጵያ	ጣልያን	ሚዛን
ወታደር	145,000	22,000	1ለ 6+
ጠመንጃ	110,000	17,000	1ለ 6+
መድፍ	42	56	3ለ 4

በሆነ የኃይል ሚዛን ነበር።[2]
በ1928 ዓ.ም የማይጨው ጦርነት፣

	ኢትዮጵያ	ጣልያን	ሚዛን
ወታደር	700,000	510,000	1ለ1 ቅርብ
ጠመንጃ	400,000[3]	782,320	1ለ2
መትረየስ	3,500	23,251	1ለ6+
መድፍ	200	2,608	1ለ13
ታንክ	ምንም	2,000	-
ጥይት	40,000,000[4]	1,289,416,100	1ለ32
የጦር አይሮፕላን	ምንም	300	-
ፀረ አይሮጵላን	50	ለላስፈለጋቸውም።[5]	ለኢጣልያን አሸናፊነት ዋናው ምክንያት ይህ ነበር።

ሁለቱ ወገኖች ከላይ እንደቀረበው ይዘው ስለነበረ ከአድዋ እስከ ማይጨው ኢትዮጵያ ምን ያህል ወደ ታች እንደዘቀጠች በጉልህ ማየት ይቻላል።

ሌላው መታየት ያለበት በመረጃ አሰባሰብና አጠቃቀም ረገድ የነበረው ልዩነት ነው። አፄ ምኒልክ በሁለት ዓይነት ጥበብ ሠሩ። ከትግራይ ሽማግሌዎች ጋር ቀደም ብለው በምሥጢር በመስማማት፣ ጣልያኖች ለጦርነቱ ሚካሄዳ ያዘጋጁትን ካርታ አበላሹባቸው። ያበላሹባቸውም የአንዱን ተራራ ስም ለሌላው ተራራ፣ የአንዱን ወንዝ ስም ለሌላው ወንዝ፣ የአንዱን ቤተክርስቲያን ስም ለሌላው ቤተክርስቲያን እንዲያስመዘግቡና ምስቅልቅሉ-

በታመኑ ወጣቶች እንዲጠና በማድረግ ነበር። ጀነራል አልቤርቶኒ ሊማረክና ሌሎች ሦስት ጀነራሎች የጦር እዛቸው ገብርቅርቁ ወጥቶ[6] የተሸነፉት በዚህ ጥበብ የተነሣ ነው። ሌላው የምኒልክ ጥበባቸው የጣልያኖች ሰላይ የነበሩትን የኤርትራ ተወላጅ አቶ አውዐሎምን መያዝ ነበር። ጣልያንን ለኢትዮጵያውያን በተመቸ ሁኔታ አምጥተው ከጦር ላይ አጋፍጠው ዘመር አሉ። ጣልያኑ አለቃቸው ጨንቆት "አውዐሎም" እያለ ደጋግሞ ቢጠራቸው፣ "በዋልክበት አያውለኝ" ብለውት ጉዞአቸውን ቀጠሉ ይባላል።[7] በማይጨው ጊዜ ግን ኢትዮጵያ አንዳችም ምሥጢር ከኢጣልያ አላገኙችም። ጣልያኖች ግን ማንኛውንም ምሥጢር ያገኙ ነበር። በንጉሠ ነገሥቱና በእቴጌይቱ መካከል ይደረግ የነበረውን የሃሳብ ልውውጥ ጭምር።

ዳግማዊ ምኒልክ ጦራቸውን ወደ አድዋ ያዘመቱት በምሥጢር ነው። ጥቂት የውጭ አገር ስዎች በመሣሪያ አጠቃቀም ረገድ ለጥቂት ኢትዮጵያውያን ሥልጠና ከመስጠት በስተቀር፣ ስለጦርነቱ ሁኔታ አንዳች ነገር የማወቅ ዕድል አልነበራቸውም። በአድዋ ጊዜ ማንኛውም ዝግጅት የተደረገው በምሥጢር ነው። ከመሣሪያው በስተቀር ማንኛውም የጦር ሥልት የኢትዮጵያ ነበር። በማይጨው ግን እንዲህ አልነበረም። ለመዋጋት የተሞከረው በፈረንጆች ዘዴ ሆነ። ምክር ከፈረንጆች ሆነ። ጦሩ በአዲስ አበባ አደባባይ ላይ ሰልፍ እያሳየ ዘመተ። እነዚህ ሁኔታዎች ለጠላት አጋለጡት። በማይጨው ጊዜ ትልቅ ተጋድሎ የተደረገው በዲፕሎማሲው ደረጃ ነው። በዓለም መንግሥታት ማኅበር ላይ ያልተገባ ተስምና ተደረገ። በአድዋ ጊዜ ግን ስሞታ ማሰሚያ አደባባይ አልነበረም። ስለሆነም እዚሁ መከናወን ነበረበት።

የአፄ ምኒልክ አዋጅ የሕዝብን ልብ በፍቅር የሚስብ እንጂ፣ ሥልጣንን የሚያሳይ ትዕዛዝ አልነበረም። አዋጃቸው "...ያገራ ሰው ካሁን ቀደም የበደልኩህ አይመስለኝም፣ አንተም እስካሁን አላስቀየምከኝም። ...ለልጅህ፣ ለሚስትህ፣ ለሃይማኖትህና ለእርስትህ ስትል እርዳኝ..." የሚል ቃል ይገኝበታል።

በአድዋ ጊዜ የአውሣ በር በደንብ ተጠብቆ ነበር። አምባሰጌ በኢትዮጵያ እጅ ነበር። እቴጌ ጣይቱ ሴት ወይዛዝርቱን ይዘው በድጋፍ ሰጭነት ቆመው ሠራዊቱን እያደፋፈሩ ነበር። ጳጳሱ አቡነ ማቴዎስ ታቦታተ ማርያምንና ጊዮርጊስን ይዘው፣ አክሱም ሥዕለ ማርያምን ይዘው፣ ሰንደቅ ዓላማቸውን ጨምረው፣ የጽዮን መልዕክተኞችን አፈት አፈት እያስነፉ ከጦርነቱ ግንባር ላይ ቆመው ነበር። ዳባ የለበሱ፣ የሰሌን ቆብ ያደረጉ እጅግ ብዙ መኳሳት ከጦሩ ግንባር ገብተው፣ ወደ ፍልሚያ የሚገባውን እያናዘዙ፣ የደከመውን እያወዛዙ አዋጉ። በዚህ ላይ ደግሞ የአፄ ምኒልክ ደግነት ሠራዊቱን ወንዱን ሴቱን መካኩሉውን እጅገነው። ስለዚህ ድል ለኢትዮጵያ ሆነ።

በማይጨው ግን እንዲህ አልነበረም።[8] በማይጨው ጊዜ ጦርነቱ አራት ታላላቅ በር አበጀ። በሰሜን በወሎና በጐንደር፣ በደቡብ በአጋዴንና በቦረና፣ አምስተኛው በር አየር ሆነ። ይህ ሁኔታ በጦርነቱ ሂደት ላይ ታላቅ ልዩነት አመጣ። ኢትዮጵያን ለመሸነፍ፣ ኢጣልያን ለማሸነፍ አበቃ።

ማጣቀሻ ፅሑፎች

1. ተክለፃድቅ መኩሪያ፣ *የኢትዮጵያ ታሪክ ከአፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ*፣ ገጽ 89-86። እና ገጽ 192-196።
2. ላጲሶ ጌ ዲሌቦ፣ *የኢትዮጵያ ረጅም የህዝብና የመንግስት ታሪክ*።
3. በአፄ ምኒልክ የተሰበሰበው ጭላም በረት ጭምር።
4. ለአንድ ጠመንጃ 100 ጥይት ሂሣብ።
5. የኢትዮጵያ ማስታወቂያ ሚኒስትር፣ የድል መታሰቢያ 25ኛ ዓመት፣ ገጽ 52።
6. ጀርጅ ኤፍ ኢች በርክሌይ፣ ትርጉም ዳኘው ወልደሥላሴ፣ *የአድዋ ዘመቻና የአፄ ምኒልክ አነሳስ*፣ ገጽ 92-115።
7. ከአቶ ገብረመስቀል ክፍለእግዚአ የተነገረኝ።
8. ገበረ ሥላሴ፣ *ታሪክ ዘመን ዘይርዋዊ*፣ ገጽ 218-268።

ምዕራፍ ሃምሣ ዘጠኝ
የኢጣልያ ሕልምና ውጤቱ

ኢጣልያ በቅኝ አገር አያያዝ ረገድ ምን ያህል እንደቀረች፣ ይህም ምን ያህል እንዳስቆጫት ቀደም ተገልጾአል። አዲሱ አስተሳሰብም በፋሽስት ፓርቲ አሜነይነትና በሙሶሊኒ መሪነት ይህንን ጉድለት ለማሞዋላት ብዙ ጥረት አደረገች። ዝርዝሩ ቀደም ብሎ ስለተገለጸ አሁን አንመለስበትም። በዚህ ምዕራፍ የምንመለከተው በተለይ በ1931 እና 1932 ዓ.ም አካባቢ የነበረችውን ኢጣልያ ይሆናል።

ይህ ዘመን የኢጣልያ ሁኔታ በደግ ነገር ረገድ ሊገኝ የሚችለው የተገኘበት ወቅት ነበር። ሕልም የነበረው የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት እጅ ከገባ አራት ዓመት ሆኖታል። በዓለም ጉባዔያት ተደማጭነት ተገኝቶአል። እንግሊዝም ጀርመንም ከእኔ ሁኚ ከእኔ ሁኚ እያሉ ማባበል አብዝተዋል። አብዛኞች አገሮች ኢጣልያ በኢትዮጵያ ላይ ያሳትን ገሸሽነት አውቀዋል። የዓለም መንግሥታት ማህበር ተዳክሟል። የ1931 ዘመን የተጀመረው በዚህ ዓይነት ደስ በሚያሰኝ ሁኔታ ነበር። ነገር ግን በዚሁ አልቀጠለም። ነገሮች እየተለወጡ ሄዱ፤ አለዋወጡም ፈጣንና ተደራራቢ ሆነ።

ኢጣልያ ይብቃኝ አላለችም፣ ተደራራቢ ጥቅም ፈለገች። ከፈረንሣይ ናይስንና ሳቮይን፣ ኮርሲካን፣ እንደዚሁም ከአፍሪካ ቅኝ ግዛቶችዋ ደግሞ ቱኒዝያንና ጅቡቲን መጠቅለል አማራት። ከአውሮፓም ትሪኤስትን መውሰድና አልባንያንና ግሪክን መያዝ ፈለገች። ከእንግሊዝ የአፍሪካ ቅኝ ግዛት ደግሞ ግብፅንና ሱዳንን፣ እንደዚሁም ሰሜን ሶማሊያን ከግዛትዋ ለመቀላቀል አሰበች። የዩጉዝላቭያንም ለመያዝ ከጀለች።

ይህ ሕልም እውን ቢሆን እውነትም ኢጣልያን አንድ ታላቅ መንግሥት ያደርጋታል። በአውሮፓ በቂ ግዛት ይኖራታል። የሜዲትራኒያንን ባሕር መቆጣጠር ትችላለች። የአድርያቲክ ባሕር ሙሉ በሙሉ የግልዋ ይሆናል። በቀይ ባሕር ላይ ማዘዝ ትችላለች። የነጭና የጥቁር ዓባይ ወንዞች የእሷ ይሆናሉ። ግዛትዋ ከአውሮፓ እስከ ሕንድ ውቅያኖስ ጣልቃ ገብ ሳይኖርበት ይዘረጋል።

ሁኔታው በሃሳብ ደረጃ አመርቂ ሆኖ ሳለ፣ በአፈጻጸም ግን ችግር አስከተለ። ይህ ዓይነቱ ሥራ በኃይል እንጂ በሰላም ሊሆን አይችልም። በዓለም ማኅበር ጉባዔ ላይ ጉምዘዛ ስሜት ፈጠረ። ሃሳቡን መደበቅ አልተቻለም። ምሥጢሩ ሊታወቅ በማኅበሩ አባልነት መቀጠል የማይሆን ሆነ። የዓለም ማኅበር አባልነትንም ተወች። ከእንግሊዝና ከፈረንሣይ ጋር ያለው ግንኙነት ከፍቅር ወደ ጦር ዞረ።

የሁለተኛው የዓለም ጦርነት ደመና እየከበደ ሲሄድ ከአንዱ ወገን መሆን የግድ አስፈለገ። ገለልተኛ መሆን አልተቻለም። ጊዜ ለማግኘት

የተደረጉት አንዳንድ ምርጫን የማዘግያ ዘዴዎች ተራ፣ በተራ አለቁ። ቁርጠኛ ውሣኔ ማድረግ ለነገ የማይባልበት ጊዜ እየተቃረበ ሄደ። ሕዝብ የመረጠው ምክር ቤት ቀደም ብሎ ተዘግቶ ስለነበር፣ ሁኔታዎች በፋሽስት ምክር ቤት ላይ ተፅዕኖ አመጡ። ምክር ቤቱም እርስበርሱ እየተከፋፈለ ሄደ። ከጀርመን ወይም ከእንግሊዝ መሆንን መምረጥ ባስፈለገ ጊዜ፣ ጉዳዩ ለፋሽስት ምክር ቤት ሊቀርብ አልቻለም። በሚኒስትሮች ምክር ቤት እንዲወሰን ማድረግ አስፈለገ።

ሙሶሊኒ ጉዳዩን ለሚኒስትሮች ምክር ቤት አቀረበ። ወደ ጀርመን አገር በምሥጢር ሄዶ የተነጋገረውንና ያየውን አስረዳ። በዚያን ጊዜ የፖለቲካ ውሣኔ የማድረግ ሥልጣን የነበራቸው ምኒስትሮች አሥራ አራት ነበሩ። ከእነሱም አንዱ የሙሶሊኒን ሴት ልጅ አግብቶ ሁለት ወንዶች ልጆች የወለደላት ካውንት /መሥፍን/ ቺያኖ ነበር። ሚኒትስሮቹ በሃሳብ እኩል በእኩል ከሁለት ተከፈሉ። ስባቱ ከእንግሊዝ፣ ሌሎቹ ስባት ከጀርመን እንሁን አሉ።

ሙሶሊኒ የሦስት ቀን ቀጠሮ ሰጣቸው። በቀጠሮውም የሚኒስትሮቹ ሃሳብ ያው ሆነ። ውሣኔውን እንዲያስታውቅ ከሂትለር የተሰጠው ቀነ ቀጠሮ ስለደረሰ ጉዳዮን ማዘግየት አልቻለም። ስለዚህ ውሣኔ መስጠት ግድ ሆነበት። ለነፍስና ለሥጋው የመጨረሻይቱ ማሕደት የሆነችውን ውሣኔ ሰኔ 3 ቀን 1932 ዓ.ም ሰጠ።

ውሣኔው ከሂትለር ጉን ለመቆም ሆነ። ከዚህ ውሣኔ ላይ የደረሰው ሦስት ታላላቅ ምክንያቶችን ምክንያት በማድረግ ነው። እነዚህም ምክንያቶች የኃይል ሚዛን፣ የርዕዮተ ዓለም ጓደኝነትና ጉርብትና ነበሩ። ምክንያቶቹንም ለሚኒስትሮቹ አስረዳ። በእሱና በመሰሎቹ ዘንድ ወሣኙ ነገር ኃይል መሆኑ፣ በዚያው ወቅት ጀርመን በኃይል የበላይነትን መያዙ፣ በዚያ ላይ ደግሞ የአውቶሚክን ምሥጢር ለማግኘት መቃረቡ ታመነበት። በርእዮተ ዓለም ደግሞ የጀርመን ለውጥ አራማጅነት ለርምጃው ክብደት ሰጠው። ጉርብትናውም እንደዚሁ። ነገር ግን እነ ቺያኖ በዚያው በቀድሞው ከአንግሊዝ አንሁን በሚለው ሃሳባቸው ጸኑ። ሙሶሊኒ በአማቹና በሌሎችም ሚኒስትሮቹ ላይ ጫኽኖ አስገደላቸው።

ከጦርነቱ ሲገባ የተገደሉት ሚኒስትሮች ደጋፊዎችና ሌሎች የእሱና የሃሳቡ ተቃዋሚዎች ተቃውሞአቸውን አጠናከሩ። ብጥብጥ ተነሣ። በመንግሥቱ ያመው ወንበዴዎች በዙ ጠነከሩ። ሙሶሊኒም መከላከሉን በሀገር ውስጥ ቀጠለ። ሕልሙን እውን ለማድረግ የሚያስችል ኃይል ያለው መሆኑን ለማስገንዘብ፣ አንድ ታላቅ የወታደር ሠልፍ ሮማ ላይ አሳየ። ከምሥራቅ አፍሪካ ለተመለመለው ብዛቱ ወደ ግማሽ ሚለዮን ለሚደርስ ወታደር ናሙና በማድረግ፣ ከኢትዮጵያ 12,000 ወታደሮች ወስዶ አሰለፈ።[1] የኢትዮጵያ ባንዳ መኳንንትም ሮም ሄደው ሰባለሥልጣኖች እጅ እንዲነሱ፣ ሀገርም እንዲጉበኙ

ተደረገ። የጀርመን የጦር መኰንኖች ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ጥናት አደረጉ።[2]

ሙሶሊኒ በውጭ አገር ጦርነት አልባንያን ያዘ። ግሪክን ወረረ። ቀደም ብሎ በተደረገው ስምምነት መሠረት በዩጉዛላቪያ፣ በኩልጋሪያና በሩማንያ ለመስፋፋት የነበረውን ዓላማ ገፋበት። በአፍሪካ በኩልም ግብፅን ለመያዝ ከአንድ መቶ ሃምሣ ኪሎ ሜትር በላይ በጦር ኃይል ሰብሮ ገባ። በጋለባት፣ በሙተማና በክሰላ በኩል ሱዳንን አጠቃ። ሰሜን ሶማሊያን ወረረ። የጀርመንና የኢጣልያ ወረራ መላውን አውሮፓ እንደ ሰደድ እሳት በያለበት ተቀጣጠለበት። የሙሶሊኒ ሕልም ወደ እውነት መለወጥ ጀመረ። ሬድዮና ጋዜጦች መጽሔቶች ይህንኑ ለማብሠር ተቅጨለጨሉ።

ነገር ግን ሁኔታዎች ወዲያው እየተለወጡ ሄዱ። ከላይ የተዘረዘሩት የጦር ግንባሮች አንድ በአንድ ተሰበሩ። እኛ ግን በተለይ የኢጣልያኑን እንመለከታለን። ጉዳያችን እሱ ነውና።

ከሰኔ 1931 ዓ.ም የቀጠለው የሙሶሊኒ ጭፍራ በጥቅምት እና ኅዳር 1932 ቀዘቀዘ። የፋሽስት ምክር ቤት እንደገና ተጠናከረ። ሙሶሊኒን ማገድ አልቻለም። መቆጣጠርም የማይሆንለት ሆነ። ስለዚህ ለመተባበር ሞከረ። ምክር ቤቱ በሀገሪቱ ጉዳይ መነጋገር ያዘ። ሙሶሊኒ የበኩሉን ግንዛቤ በተከታታይ አስረዳ። የምክር ቤቱ ስሜት እየሞቀ በሙሶሊኒ ላይ ያለው ተቃውሞ እየጠነከረ ሄደ። አንዳንድ ባለ ሥልጣኖች ከንጉሥ ኢማኑኤል ሣልሣዊ ጋር በምሥጢር ግንኙነት መሠረቱ። ማርሻል ባዶሊዮ የጦር ምክር ቤት /ቺፍ ኦፍ እስታፍ/ ሥራውን በፈቃዱ ሰቅቆ የሙሶሊኒ ተቃዋሚ በመሆን ቆመ።

ጦርነቱ በኢጣልያ ላይ አመዘነ። ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ከስንደን ካርቱም ገብተው ከሐምሌ 1 ቀን 1932 ዓ.ም ጀምሮ ኃይሎቻቸውን አንቀሳቀሱ። በኢትዮጵያ ሲንከተከተክ የኖረው ጦርነት መፍላት ጀመረ። እንግሊዞች የተወሰዱባቸውን ቦታዎች ለማስለቀቅ ተንቀሳቀሱ። ጀርመን እንደ ሀንጋሪ፣ ሩማንያ፣ ዮጉዝላቭያ ያሉ አገሮችን መውረሩ የጥቅም ግጭት ፈጠረ። የጣልያንና የጀርመንን ግንኙነት አሻከረ። ኅዳር 30 ቀን 1932 ዓ.ም /ዲሰምበር 10 ቀን 1940/ ሲዲ ባርራኒ በተባለችው ቦታ 113000 የጣልያን ወታደር ከሞላ ትጠቁ ጋር በእንግሊዝ ጦር ሰሜን አፍሪካ ተማረከ። ታራንቶ የተባለውም የሲቢያ ወደብ በእንግሊዝ አየር ኃይል ተደብድቦ ብዙ የጣልያን የጦር መርከቦች ወደሙ። ሙሶሊኒ በዚህ ሲገረም በርዲያ በተባለው ቦታ የነበረው 40000 ወታደር ታህሣሥ 26 ቀን 1933 ዓ.ም /ጃንዋሪ 5 ቀን 1941/ ለእንግሊዝ ወታደሮች እጁን ሰጠ። በጥር 10 /ጃንዋሪ 19/ ቀን ክሰላ ተያዘ። በአልባንያና በግሪክ በኩል የተከፈተው ጦር ፈጽሞ ተሰፋ የሌለው መሆኑን፣ ጀነራል ሶዶ የተባለው ታማኝ የጦር አዛዥ ለሙሶሊኒ አስታወቀው። ሰሜን ሶማሊያ ተመልሳ እንግሊዝ እጅ ገባች። የቁባቱ የክላሬታ

ፔታኪ ማርገዘና ማስወረድ ሙሶሊኒ አንድ ወር ሙሉ አልጋዋ ሥር ተኩራምቶ እንዲተኛ አደረገው። ሙሶሊኒ የመጣበትን አበሳ መቻል አቃተው ተርገደገደ። ብዙዎች የአእምሮውን ትክክለኛነት መጠራጠር አመጡ።[3]

ጣልያን በኢትዮጵያ ላይ የልማት ሥራ ለማንቀሳቀስ እንሸስት ያደረገው 2.6 ቢሊዮን ብር መና እንደቀረ ታወቀ። በሀገሪቱ ሰላም ለማስፈን የተደረጉት የእርቅና የሽንገላ ሥራዎች ሁሉ ከንቱ መሆናቸው ተረጋገጠ። ታላቁ የጣልያን ጭንቅ በምሥራቅ አፍሪካ አዲስ የተከፈተውን ጦር ማቋቋምና፣ በቅኝ ግዛቱ የሚገኙትን ከግማሽ ሚሊዮን የማያንሱ ኢጣልያውያን ነፍስ ማትረፍ ሆነ። ነገር ግን ለሙሶሊኒ የዚህ ጉዳይ ክብደት አልታወቅህ አለው። በደነ። ይህ መበደን ደግሞ የሕዝቡን ድጋፍ ከመቀነስ አልፎ ተቃውሞ አስነሳበት። በቀናው ጊዜ በዙሪያው የጨፈሩ ሁሉ ጥለውት ዘወር ስለአሉ፣ የአበሳውን ድምር ብቻውን መሸከም ግድ ሆነበት። ዕጣ ፈንታው በስንት ዓይነት ዘዴ የገነባውን የኢትዮጵያ፣ የኤርትራ፣ የሶማሊያ፣ የሲብያ ቅኝ ግዛቶች አንድ በአንድ ሲፈርሱ ቁጭ ብሎ ማየት ብቻ ሆነ። የሙሶሊኒ ኢጣልያ ሕልም ውጤቱ እንዲህ ቅጥፖ ሆኖ ቀረ። "ምንም ኃይል ሊሠብረው ሊያሸንፈው ቀርቶ ሊቋቋመው አይችልም" ተብሎ ታምኖበት የነበረውን የፋሽስትና የናዚስት ኃይል ኢትዮጵያ ልክ አድርጋ አንከታከተችው። ታዳጊ ኃይል መስሎ የነበረው የፖለቲካ እንቅስቃሴ ከሥር ከመሠረቱ ተነቅሎ ወደቀ። ሙሶሊኒ ከታማኝ ቁባቱ ጋር የዝቅዝቲት ተሰቀለ። ግብረ አበሮቹም አለቁ።

ማጣቀሻ ፅሑፎች

1. ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፣ *ሕይወቱና የኢትዮጵያ እርምጃ 2ኛ መጽሐፍ*፣ ገጽ 175።
2. በኪሾኖ ቪ. ዩኒቨርስቲ መምህር የተነገረኝ።
3. Stanley Cooperman, *Mussolini* p.124-141.

ምዕራፍ ስድሳ
የኢትዮጵያ የጦር ፍርድ ቤት

በአንድ ሀገር ላይ ጦርነት ተካሂዶ ከፍተኛ ሊደርስ የጦር ፍርድ የመስጠቱ ጉዳይ የነበረና ያለ፣ ወደፊትም ጦርነት እስከ አለ ድረስ የሚኖር ነገር ነው። የችሎቱ አመሠራረት፣ የዳኞቹ አመራረጥ፣ የሚሠራበት ሕግ ዓይነት ሊያነጋግር ይችላል። ይህንን የመሰለውን ጥያቄ ሰባስሙያዎች እንተወው። በኢትዮጵያ በጦርነቱ ጊዜ ብዙ ከሀዲዎች ብዙ ዓይነት የክህደት ሥራ መፈጸማቸው ማስረጃ እየነጠረ ቀደም ብሎ ተገልጾአል። የአሁኑ ጥያቄ "ታዲያ ምን ተደረገ?" የሚል መሆን አለበት።

ንጉሠ ነገሥቱ ጎዳር 9 ቀን 1933 ዓ.ም ከነርቱም ለሸዋ ሕዝብ ባወጡት አዋጅ "...ስለኢትዮጵያ ጥቅም ነው እያሉ ለባዕድ የሚያገለግሉት ለራስ ኃይሉ፣ ለራስ ሥዩም፣ ለራስ ጌታቸው፣ ለራስ ከበደ፣ ለራስ ገብረ ሕይወት፣ ለደጃዝማች አባውቃው ብሩ፣ ለደጃዝማች አመዴ አሊ፣ ለደጃዝማች አያሌው ብሩ፣ ለደጃዝማች ሃብተ ሚካኤል፣ ለደጃዝማች አምባቸው ገሠሠ፣ ለደጃዝማች መሥፍንና እነሱንም ለመሳሰሉት ያለ አንዳች ርኅራሄ የተገባቸውን ቅጣት እንሰጣችዋለን..." በማለት ዝተው ነበር።[1]

የታሪክ ጥናት ነውና ይህንን አዋጅ በየልዩ ልዩ ገጹ መመልከት፣ ጥያቄዎችንም ማንሳት ይገባል። ጉዳዩን በጥያቄ መጀመር ይሻላል።

1ኛ. በአዋጅ የሰዎችን ስም መዘርዘር ለምን አስፈለገ?

2ኛ. የሰዎች ስም ዝርዝር ማውጣት ከአስፈለገ የእነ ደጃዝማች ኃይለሥላሴ ጉግሣ፣ የእነ ቀኝዝማች ተክለማርቆስ፣ የእነ አፈቄሣር አፈወርቅ ስም ለምን ሳይጠቀስ ቀረ?

3ኛ. ጉዳዩ የሀገር ሰዎቹ በልዩ ዘር፣ አዋጁ ለምን ለሸዋ ተነገረ?

4ኛ. የመጨረሻውና ዋነኛው ጥያቄ፡- ታዲያ በፍርድ አሰጣጥ ረገድ ምን ተደረገ? መሆን አለበት። እንባቢ የራሱን መልስ መስጠት ይችላል። እኛ ግን የተደረገውን ነገር መመልከታችንን እንቀጥላለን።

የጦር ፍርድ ቤት ተቋቋመ። የፍርድ ሥራም ተከፈተ። ነገር ግን የተከሰሰው ኃይለሥላሴ ጉግሣ ብቻ ነው። ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሣ፣ የክህደት ሥራዎች ጀማሪ መሆኑ እርግጥ ነው። ለጣሊያን መንግሥት ስለሰጠውም አገልግሎት የራስነት ማዕረግ አግኝቶ ነበር። ሁኔታው እንደዚህ ሆኖ ሳለ የእርሱ ጉዳይ ብቻ ተሰይቶ በአደባባይ ፍርድ መስጠቱ ትክክል አልሆነም። ፍርዱ ሳይፈጸም መቅረቱ ደግሞ ሌላ አጠያያቂ ጉዳይ ውጣው። መታሰር ሌሎችም ታሠሩ። ለምሣሌ ራስ ጌታቸው አባተ። ነገር ግን ጉዳያቸው በአደባባይ አልታየም። ከዚህ ሌላ፣ የተሸለ የተደረገ ነገር ለምን የለም?

ለለዚህ በኢትዮጵያ ከጦርነቱ በኋላ በከሀዲዎች ላይ የጦር ፍርድ ተሰጠ ከማለት ይልቅ አልተሰጠም ማለቱ ይቀላል። ቀድሞውኑ አዋጁ በተገረበት አኳኋን የወጣው ከዚህ ሁኔታ ላይ እንዲያደርስ ታስቦ ሳይሆን አልቀረም። ምክንያቱም ወንጀለኞቹ ይቀጡ ቢባል ሸዋ ደም እንዲቃባ፣ አይቀጡ ቢባል ሀገሩን ሸዋ እንደተወ አድርጉ ለማሳየት። በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ በሀገርና በሕዝብ ላይ ከፍተኛ ወንጀል የፈጸሙ ሰዎች፣ አንዳችም ጥያቄ ሳይነሳባቸው በየቤታቸው እንደተቀመጡ ነባ ወጡ።

እርግጥ ኢትዮጵያ በዚያ ወቅት ብዙ ችግሮች ነበሩባት። መንግሥቱም አያሌ አጣዳፊ ሥራዎች ነበሩበት። በሥልጣን ላይ ከነበሩት ሰዎችም አንዳንዶቹ ከማክረር ይልቅ ማርገብ፣ ከማክበድ ይልቅ ማቅለል የተሻለ መሆኑ እንደሚመክሩ ግልጽ ይሆናል። ቢሆንም ሁሉንም ነባ መልቀቅ፣ ለሀገራቱ የወደፊት ሕልውና እንዲያ ያለ የሕግ ጥበቃ መስጠት መፍትሄ አልነበረም። እንደእኔ ይሻል የነበረው ሊቀጡ የሚገባቸውን አጣርቶና የሚቀጡትን የቅጣት ዓይነት ቀለል አድርጉ፣ ለቅጣቱም ደረጃ አውጥቶ፣ ፍርድ እንዲሰጥ ማድረግ ነበር።

ለምሣሌ፡-

ሀ. አልጋ የፈረሰው ንጉሠ ነገሥቱ ከሀገር በወጡ ጊዜ ነው። እስከዚያው ቀን ድረስ የኢትዮጵያ መንግሥት ነበር። በሀገር ላይ መንግሥት ባለበት ጊዜ ያጠፋ ሰው መቀጣት አለበት። ስለዚህ ከሚያዝያ 23 ቀን 1928 ዓ.ም ጥፋቱ የፈጸመ፣

ለ. በዚሁ ዓይነት አመለካከት ንጉሠ ነገሥቱ ወደ ኢትዮጵያ ከገቡ በኋላ ጥፋት የፈጸመ መቀጣት ነበረባቸው። እጅግ ቢያንስ ንጉሠ ነገሥቱ ከደረሰበት ቀን ጀምሮ የበደሉ፣

ሐ. ወንጀለኞቹ በኢትዮጵያ መንግሥት ውስጥ የነበራቸው አቅዋምም አንድ መለኪያ መሆን ነበረበት። በጦር ማዕረግ ፊታውራሪና ከዚያም በላይ የነበሩ፣ በሲቪል ሥራ ዴሬክተርና ከዚያም በላይ የነበሩ፣ አልጋ ከፈረሰ በኋላ ለጠላት በሰጡት አገልግሎት፣

መ. ለጠላት የጦር መሪ እየሆኑ ሠራዊት ያዘመቱ፣ ሰው የገደሉ፣

ሠ. ከኢጣልያ መንግሥት የራስ፣ የደጃዝማችነትና የፊታውራሪነት፣ እንደዚሁም በሲቪል ሥራ በዴሬክተርነትና ከዚያም በላይ በሆነ ሥራ የተመደቡ፣

ሌላው እንኳን ቢቀር ነውራቸው በሕዝብ እንዲታወቅና እነሱም አመክሮ እንዲያገኙ ማድረግ ቡተገባ ነበር። ይህ ሁሉ አልተደረገም። ይህ ባለመደረጉ በሀገራችን ላይ ማንም እየተነሣ ሲጨፍርባት ይኖራል። ከሁሉም በላይ የንጉሠ ነገሥቱን መንግሥት ከትዝብት ላይ የጣለው፣ ከእነዚህ ከሀዲዎች ብዙዎቹ ተመልሰው ከሥልጣን ላይ መውጣት ነው። ስለራስ

ኃይሉ ተክለሃይማኖት ነፃ መውጣት፤ ስለበላይ ዘለቀ ስቅላት ከመገረም በስተቀር ታሪክ ምን ሊል ይችላል?

ቀጥሎ የሚነሳው ጥያቄ፤ "ኢትዮጵያ በዚያን ጊዜ ለነበረችበት ሁኔታ ምን ሊደረግ ይችል ኖሮአል?" ይሆናል። ከፍ ብሎ ከሀ እስከ ሠ ድረስ በተዘረዘሩት ወንጀሎች የሚጠየቁ ብዛት ከሁለት ሺህ አይበልጥም። የዳኝነቱን ሥራ እንዲያዩ ለአርበኞች ዕድል ቢሰጣቸው፤ ትክክለኛ ፍርድ ሊሰጡ ይችሉ እንደነበረ እኔ ራሴ አውቃለሁ። ምንም ሕፃን ብሆን ብዙ ጊዜ የአርበኞችን ፍርድ አይቼ ነበርና በችሎታቸው አልጠራጠርም። በሕግም ረገድ ጉዳዩን በፍትሐ ነገሥት ሊፈቱት ይችል ነበር።[2]

አሸናፊዎቹ ታላላቅ መንግሥታት የጀርመንን የጦር ወንጀለኞች በፍርድ ቀጧቸው። የተከሰሱባቸው ወንጀሎች ሰላም በማደፍረስ፤ በጦር ወንጀለኝነትና በሰው ልጆች ባደረሱት አልቂት ነበር። በእነዚህ ሦስት ወንጀሎች፤

በአሜሪካን ከ1,814 ተከሳሾች 450፤
በእንግሊዝ ከ1,085 ተከሳሾች 240፤
በፈረንሣይ ከ2,107 ተከሳሾች 104፤
በጀርመን ከ12,846 ተከሳሾች 5,426፤

በድምሩ ከ17,852 ተከሳሾች 6,220፤ ማለትም 35% በመቶ በሞት ሲቀጡ፤ ሌሎች ብዙዎች የዕድሜ ልክ እሥራት ተፈርዶባቸዋል። በቀድሞዋ ሶቪየት ራሺያ 10000 ያህል ወንጀለኞች ከመወሰዳቸው በስተቀር ሌላ የታወቀ ነገር የለም።[3] በጃፓን የጦር ወንጀለኞች ላይም ተመሳሳይ ፍርድ ተሰጥቶባቸዋል። ነገር ግን የጣልያን የጦር ወንጀለኞች በኢትዮጵያ ላይ ስለፈፀሙት ወንጀል አንዳች አላሉአቸውም። የጥቁር ደም ለነጭ ምኑም አይደለምና። ይህም ሌላው የታሪክ ትዝብት ነው።

ማጣቀሻ ፅሑፎች

1. ከበደ ተሰማ፤ *የታሪክ ማስታወሻ*፤ ገጽ 337።
2. ፍትሐ ነገሥት።
3. ክፍለ ጽዮን ማሞ፤ ማለዳ ጋዜጣ፤ አንደኛ ዓመት፤ ቁጥር 2፤ ጥር 14 ቀን 1985 ዓ.ም፤ ገጽ 18።

ምዕራፍ ስድሣ አንድ
ከድል በኋላ ትግል

ኢጣልያ በኢትዮጵያ ላይ ያጋጠማት ችግር ከእርስዋ ጋር ከሀገር አልተባረረም። ገጹን እየሰዋወጠ ቀጠለ። ከድል በኋላ የነበረው ትግል ሁሉንም የሚጎንጥ ሆነ። ንጉሠ ነገሥቱንም እንኳን አልተወም። ምንም በድል አድራጊነት የገቡበት ሁኔታ አንጸባራቂ ቢሆን፤ በችግሩ ጊዜ ለጠላት አጋፍጠውት በሄዱት ሕዝብ መልሶ ሞገስ ማግኘት በአደባባይ የሚታየውን ያህል ቀላል አልሆነ አለ። በተለይ በአርበኞች ዘንድ አክብሮትና ፍቅር ማግኘት አልተቻለም። ማስፈራራቱ አሳዋጣም። መጨቆንና ማንገላታቱም ቅርታውን ይበልጡኑ አባባሰው። ከስደተኛው አብዛኛው በንጉሠ ነገሥቱ ፊት ሞገስ አገኘ። እንደ ግብር ጓደኛ ሆኖ ተቆጠረ። የውስጥ አርበኛም እንደዚሁ። ባንዳም የአዲሱ ዋጋ ተቋዳሽ ለመሆን ከጀለ። ኢጣልያን የተደረገለት እንክብካቤ ኑሮውን አሻሽሎት፤ አመለካከቱን ወደ ዘመናዊነት ለውጦለት ስለነበር በዚያው ዓይነት መቀጠልን ፈለገ። በጠቅላላው ሕዝቡ ከንጉሠ ነገሥቱ በልዩ ልዩ አዋጆችና ንግግሮች የተገለጹት የአስተዳደር ማሻሻያዎች እንደሚደረጉለት ተማምኖ ጠበቀ። እንደዚህ አልሆነም፤ አዳዲስ ችግሮች ተፈጠሩ።

እንግሊዞች በመቅደላ ዘመቻቸው ጊዜ እንደ አደረጉት ሰተት ብለው መውጣት-አልፈለጉም። ገሸርነት አማራቸው። የሚስተር ዊንስተን ቸርችል መንግሥት ጦርነቱን ለማካሄድ እንጂ፤ ንጉሠ ነገሥቱን ወደ ሥልጣን ለመመለስ የገባው ቃል አልነበረም። የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ የሚስተር አንቶኒ ኤደን ድጋፍ ብቻውን ብቁ አልሆነም። የእንግሊዝ ምክር ቤት ዘይቤ የኢትዮጵያ ጉዳይ ሲቀርብለት ለምቶ ዝም ሆነ። የእንግሊዝ ጦር አዛዦች ኢትዮጵያ ከጠላት ከተወሰዱ አገሮች እንደ አንድዋ በመቁጠር የፖለቲካ መረባቸውን ለመጣል ሞከሩ። ንጉሠ ነገሥቱ ግንቦት 2 ቀን 1933 ዓ.ም ለሰባት ሚኒስትሮች የሰጡትን ሹመት ተቃወሙ። ችግሩ በንጉሠ ነገሥቱ ሥልጣን ላይ ያተኮረ ብቻ አልነበረም። በሀገሪቱ ሕልውና ላይ ጭምር እንጂ።

1ኛ. እንግሊዞች "የተያዙ የጠላት ግዛቶች አስተዳደር" የሚል ስም ቀርጸው ኢትዮጵያን ከጣልያን ከነጠቁአቸው ከሶማሊያ፤ ከኤርትራና ከሊቢያ ጋር ቀላቅለው ማስተዳደር ጀመሩ።

2ኛ. ብርጋዴየር ለቭ የተባለ የፖለቲካ ሹም መደቡ። እሱም የእንግሊዝን ይዞታ ለማጠናከርና የኢትዮጵያን አትዋም ለማዳከም ብዙ ጥረት አደረገ። የማይታይ ሥውር እጅ ዘረጋ። ሲዳሞ ውስጥ በጀመጀም፤

ሐረርጌ ውስጥ በገሪቆጨር፣ በትግራይ ውስጥ ወያኔን እየቀሰቀሰ ብጥብጥ አስነሣ። በዙ ደም ፈሰሰ። ኢትዮጵያን ከእንግሊዝ ሕዝብ ዘንድ ለማስጠላት ታላቅ የፕሮፓጋንዳ ሥራ ተካሄደ። ባሪያ ይነገድበታል፣ ሀብትና ብጥብጥ በዝቶበታል ተባለ።

3ኛ. በጐንደር፣ በአምባሰጌ፣ በአጅባር፣ በወለጋና በኢሉባቡር ጦርነት ከጣልያን ጋር ቀጠለ። ከጣልያን የተማረከው መሣሪያ በእንግሊዞች ተወሰደ። እሱ ተዋግቶ የማረከውን መሣሪያ እንግሊዞች የሚወስዱበት ምክንያት ለአርበኛው የማይገባው ሆነ። ንጉሠ ነገሥቱም ማስጣል ስለአልቻሉ፣ የእነሱው ተባባሪ አስመስሎ አስገመታቸው።

4ኛ. ኢኮኖሚው የሚንቀሳቀሰው እንግሊዞች ለምሥራቅ አፍሪካ ግዛታቸው ባዘጋጁት ሽልንግ ሆነ። ዝርዝሩ ገንዘብ እንደ ዶቃ በገመድ እየተሰካ የሚንጠለጠል ስለነበር ስሙ ቀይ ቀዳዳ ተባለ።

5ኛ. የኤርትራን ሕዝብ ንጉሠ ነገሥትህን ይዘንልህ መጣን እያሉ፣ ንጉሠ ነገሥቱን አዋጅ እያናገሩ ከአዋጡት በኋላ፣ ድል ሲያገኙ እጅ አደረጉት። እንዲያውም ትግራይን ከኢትዮጵያ ገንጥለው ከኤርትራ በመቀላቀል፣ ግዛታቸውን ማስፋፋት የሚችሉበትን የነገር ድር ማጠንጠን ጀመሩ።

6ኛ. ከምሥራቅ አጋዴንን፣ ከምዕራብ ጋምቤላን አጥብቀው ያዙ።

7ኛ. ይህ አያያዛቸው ለእነሱ ሚዛን እስኪያስገኝ ድረስ በሁለቱ መንግሥታት መካከል ስምምነት እንዳይፈረም አዘገዩ።

8ኛ. የፍርድን፣ የፖሊስን፣ የትምህርትን፣ የውጭ ጉዳይን ሥራ እጃቸው አደረጉ።

በጠቅላላው ኢትዮጵያ አዲስ መሥገርት ውስጥ ገባች። ይህ ሁኔታ በኢትዮጵያ ውስጥ ድንጋጤን ፈጠረ። ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ከፈረንጅ ጋር ያላቸው ቀረቤታ ምን ጊዜም አስደስቶት የማያውቀውን የኢትዮጵያን ሕዝብ ከሥጋት ላይ ጣለው። ጉዞውንም ከድጥ ወደ ማጥ አደረገበት። ራስ አሞራው ውብነህ "የነጭ የነጭ ጣልያን ምን አለኝ" ያሉት ትክክል ሆነ። ሀገርን ከዚህ ሁኔታ ማላቀቅ ግድ አለ። የልማት ሥራዎች ማካሄድና አስተዳደርን ለማሻሻል ፋታ አልተገኘም። እንዲያውም ሀገሪቱን ከመፍረስ ለማዳን አሐዳዊውን አስተዳደር ለማጠናከር አስፈለገ። እንደዚሁም ተደረገ።

ኢትዮጵያን እንደገና የማዳኑ ሥራ በዝግታ መሄድና በትዕግሥት መያዝ ነበረበት። ቀድሞ በጣልያን የተመዘበረውን፣ ኋላ ደግሞ በእንግሊዝ ነገር የተተበተበውን መፍታት አስፈለገ። በዚህ ረገድ ከተወሰዱት እርምጃዎች ዋና ዋናዎቹ ከዚህ የሚከተሉት ናቸው።

ሀ. በተቻለ ፍጥነት የኢትዮጵያን የመከላከያ ኃይል ማቋቋም።

ለ. የራስን ገንዘብ ማሳተም። የሚታተመውም ገንዘብ ከአዲሱ የኢኮኖሚ ኃይል ማለትም ከአሜሪካን ገንዘብ ጋር ጤናማ ትሥሥር እንዲኖረው ማድረግ።

ሐ. በእንግሊዞች ለተያዙት ሥራዎች ማለትም ለፍርድ፣ ለፖሊስ፣ ለውጭ ጉዳይ ብቁ ኢትዮጵያውያን በመመደብ፣ መጀመሪያ በውስጥ ቀጥሎም በሙሉ ሥራውን መልሶ መረከብ።

መ. ከእንግሊዞች ጋር ሕጋዊነት ያለው፣ በእኩልነትና በወዳጅነት ላይ የተመሠረተ ስምምነት መፈራረም።

ሠ. ለልዩ ሥራ የሚፈለጉ ባለሙያዎችን ለማግኘት የሚያስችል የትምህርት ሥራዎች ማካሄድ።

ረ. በጦርነት ለደረሰው ጉዳት አሳማኝ ማስረጃ በማቅረብ የጦር ካሣ መጠየቅ።

ሰ. ቀደም ብሎው ከኢትዮጵያ የተወሰዱ ግዛቶችን ማለትም ኤርትራና ሶማሊያን ማስመለስ። እነዚህ ሥራዎች ቅድሚያ ተሰጣቸው።

ከእንግሊዝ የፖለቲካ ውሽንፍር ለመጠለል አንድ ተገን መያዝ አስፈለገ። የእንግሊዝ ጠቅላይ ሚኒስትርና የአሜሪካን ፕሬዚዳንት ሚስተር ሩዝቬልት፣ በምድረ ግብፅ በምሥጢር ተገናኝተው እንደሚነጋገሩ በኢትዮጵያ ቤተ መንግሥት ዘንድ ታወቀ። ንጉሠ ነገሥቱ አዲስ አበባ የተኙት የእንግሊዝ ባለሥልጣኖች ሳያውቁ ሌሊት በአይሮፕላን በርረው በመሄድ፣ መጀመሪያ ከፕሬዚዳንቱ በኋላም ከሁለቱ ባለሥልጣኖች ተገናኝተው ተነጋገሩ። ይህ ግንኙነት ለጊዜው የእንግሊዝን ባለሥልጣኖች ቅር ቢያሰኝም፣ ለኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት አዲስ በር ከፈተ። እጅግ ጠቀሜ የነበረው የእንግሊዝ አያያዝ ላላ።

በኢትዮጵያና በእንግሊዝ መንግሥታት መካከል ጥር 23 ቀን 1934 ዓ.ም አዲስ ውል አዲስ አበባ ላይ ተፈረመ። በዚህ ውል፦

- የሃያ ሚሊዮን ብር /የሁለት ሚሊዮን የእንግሊዝ ፓውንድ/ ብድር ተገኘ።
- በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች የእንግሊዝ ጃኖች እንዲቀመጡ ተወሰነ።
- እንግሊዞች የንጉሠ ነገሥቱን መንግሥት በአስተዳደር እንዲረዱ፣ የጦርና የፖሊስ ሀራዊት እንዲያሠለጥኑ ስምምነት ተደረገ።
- በጣልያኖች እጅ ያሉ ኢትዮጵያውን እሥረኞችና ምርኮኞች ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለሱ ተወሰነ።

- ከኢትዮጵያ ወደ ኢጣልያ የተወሰዱ የባህል ቅርሶች እንዲመለሱ ቃል ተገባ።
- በኢትዮጵያ በክል ደግሞ በሀገርዋ ውስጥ ለሚቆዩ የእንግሊዝ ወታደሮች ለሚያርፉበት ቦታ ኪራይ ላይጠየቅ ተወሰነ።[1]

የዚህ ስምምነት መፈረም ለእንግሊዝ እምብዛም አልጣማትም። ለኢትዮጵያ ግን ትልቅ ነገር ሆነ። ሦስት ታላላቅ ጉዳዮች መልካም ፍፃሜ አገኙ። እነዚህም፡

1ኛ. የኢትዮጵያ ነፃነት መታወቁ፣

2ኛ. የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ንጉሠ ነገሥትነት መረጋገጡ፣

3ኛ.ጣልያንን ለማባረር ለተደረገው ጦርነት ኢትዮጵያ ለእንግሊዝ የምትከፍሰው ገንዘብ አለመኖሩ። ለጊዜው መንቀሳቀሻ የሚሆን ገንዘብ መገኘቱም ቀላል ጉዳይ አልነበረም።

ሆኖም ውሉ ቢፈረምም የአፈፃፀም ችግር ነበር። የእንግሊዞች ተፅዕኖ በየሥራ ዘርፉ ሥር ሰድዶ ነበርና፣ ሰንኮፉን እየነቀሉ የማውጣቱ ሥራ ቀላል አልሆነም። ለማስረጃ በትምህርት ላይ ጭቆና ለማድረግ ያደረጉት ጥረት፤ በ1941 ዓ.ም በአዲስ አበባ መምህራን ማሠልጠኛ እንስቲትዮት ተማሪዎች አድማ ቀስቅሶ ኢንስቲትዩቱን ለቅቀው እንዲወጡ አስገደዳቸው። ከጦር ሠራዊት፣ ከፖሊስ፣ ከፍርድ ቤት እንዲወጡ የማድረጉ ሥራ ቀላል አልነበረም። የኢትዮጵያ ልጆች በዚህ ጉዳይ ተባበሩ፤ መልካም ሥራ ሠሩ። ይህ ጉዳይ በትዕግስትና በጥበብ ባይያዝ ኖሮ እንግሊዞች በሰላም አይወጡም ነበር። አለመግባባት ቢፈጠር ብዙ ደም ሊፈስና ምናልባትም የሀገሪቱ አንድነት ሊፈርስ ይችል ነበር። በዚህ ረገድ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ለሀገሪቱና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ታላቅ ውለታ ውለዋል። ሌላ መሪ የማይችለው ሥራ ሠርተዋል። ስለዚህ ሊመሰገኑ ይገባቸዋል።

የንጉሠ ነገሥቱ አቅዋም በመጠናከሩ አንድ ችግር ተቃለለ። ነገር ግን አዲስ በተቋቋመው መንግሥት ላይ ከባባድ ችግሮች ተደቀኑ። ሕዝቡ ደህይቶአል። ትንሽ ሀብት ያለው ከጠላት ጉያ ተሸጉጦ የነበረው ወገን ነው። ሕዝብ እርስ በርሱ ተቋስሎአል። ደም የተቃባው ብዙ ነው። በተለይም በአርበኛው መካከል ታላላቅ ቁስል አለ። አርበኛው በአዳዲሶቹ ሁኔታዎች ላይ አልተደሰተም። ከስደተኛውም አንዳንዱ ቅሬታ አድሮበታል። በዘመናዊ የመንግሥት ሥራ አካሄድ በቂ ችሎታና ልምድ ያለው ሰው እጅግ በጣም ጥቂት ነው። ከተማረው ሕዝብ ሦስት ሩብ በጣልያኖችና በእነሱ አገዛዝ አልቆአል። በየበረሃው የወደቁ አርበኞች አፅም እየተለቀመ ከቤተ ክርስቲያን መቀበር አለባቸው። የመኳንንቱ አዲስ አበባ

ቅድስት ሥላሴ ። ባንዳው ገንግኖአል። ንብረትም አካብቶአል። የአሠራር ሥልትም ከጠላት ቀስሞአል። ነገር ግን ታማኝነቱ አጠራጣሪ ታሪኩም አጸያፊ ነው። በሱ መደገፍ ላያዋጣ ይችላል። የተዘጉ ትምህርት ቤቶችን መልሶ መክፈትና ሌሎችም አዳዲስ መክፈት አስፈለገ። ትምህርት ቤት መክፈት ብቻ በቂ አልሆነም። ወላጆቻቸው በጠላት የተገደሉባቸውን፣ እነሱም ራሳቸው የአካል ጉዳት የደረሰባቸውን እየሰበሰቡ በአዳሪነት ማስተማር አስፈለገ።

ከዚህ ችግር ጎብረተሰቡም ድርሻ ነበረው። የአርበኛው ድርሻ ከሁሉም የበለጠ ሆነ። ችግሩም ፋታ ሳይሰጥ ንጉሠ ነገሥቱ ከመናገሻ ከተማቸው የገቡ ዕለት ጀመረው። እንደ አሻው፣ እንደ ችሎታው ይዞት በኖረው ችግር ላይ፤ ሌላ አዲስ እንግዳ ችግር ደረሰበት። ከማዕከላዊ ዕዝ ውስጥ ገባ። የአንዳንዶቹን ትዕዛዞች ምክንያት መረዳት አቃተው። ለማስረጃ ያህል አንዳንዱን እንመልከት። ንጉሠ ነገሥቱ አዲስ አበባ ሲገቡ፤ የቡልጋ አርበኛ ከመንገዱ ግራና ቀኝ ተሰልፎ ተቀበለ። ንጉሠ ነገሥቱ ከቤተ መንግሥታቸው ሲገቡ፣ እሱ ከከተማ ሳይወጣ እንዲያድር ታዘዘ። ሰልፉ በእንጦጦ በክል ስለነበር በዚያው በገባበት ወጥቶ እንጦጦ ብርድ ላይ ማደር ነበረበት። ከከሰም ቆላ ለወጣ የእንጦጦ ብርድ ቀላል አልነበረም። በከተማ የተወራው ምክንያት ፀጥታ እንዳይበላሽ የሚል ነበር። ለአርበኛው አልተነገረውም። አርበኛው ያገኘው ግንዛቤ በአዲሱ ሥርዓት - የማይፈለግ መሆኑን የሚያረጋግጥለት ሆነ። የሚበዛው በማግሥቱ ተበተነ። እንኳን አገራችን ነፃ ወጣች እያለ ተመልሶ አርሻው ገባ። ወደ ሀገሩ ያልተመለሰው በከተማው ዙሪያ ከረመ። በሰንዳፋና በአቃቂ ጭቃ ተዘፍቀው ክረምቱን እንደ አሳለፉ የሚናገሩ ብዙ ናቸው።

ንጉሠ ነገሥቱ ሐምሌ 16 ቀን 1934 ዓ.ም የአርበኝነት አገልግሎትን የሚመለከት አዋጅ ተናገሩ። አምስት ዓመት ለተዋጋና ምንም ለሌለው ሥራዊት አሥራ አምስት ወር መጠበቅ ቀላል አልነበረም። ቢሆንም ረዳ። የአዋጁ ፍሬ ነገር አምስት ዓመት የተዋጋ አርበኛ ወይም ስደተኛ አንድ ጋሻ መሬት በርስትነት ማግኘቱ /ቁጥር 2ኛ/፣ በጦርነቱ ወይም በአርበኝነት የቆሰለ ወይም ስደተኛ አንድ ጋሻ በርስትነት እንዲያገኝ /ቁጥር 3ኛ/፣ ባሎቻቸው በጦር ሜዳ ወይም በአርበኝነት የሞቱባቸው እኩል ጋሻ እስከ ዕድሜአቸው እንዲይዙ /ቁጥር 4ኛ/፣ አባቶቻቸው በጦርነት ወይም በአርበኝነት የሞቱባቸው በተለይ በሚቀምላቸው ትምህርት ቤት እንዲገቡ፤ የትምህርት ዕድሜያቸው የተላለፈባቸው ወንዶች በወታደርነት እንዲቀጠሩ፤ ለሴቶች ግማሽ ጋሻ መሬት እስከ ዕድሜ ልካቸው እንዲሰጣቸው /ቁጥር 5ኛ እና 6ኛ/ የሚል ነበር።[2] ይህ

አዋጅ ለስደተኞችና አርበኞች በአዲስ አበባ ወይም በየአውራጃው፤ ለክፍለ ሀገሩ ሁሉ ምንም ልዩነት ሳይደረግ እኩል እንዲደለደል ተፈቀደ።[3]

በጀኔቭ እንዲያ አጥብቀው ለኢትዮጵያ የተከራከሩት ብላቴን ጌታ ሎሬንዞ ታዕዝዝ በአዲሱ የሚኒስትሮች ድልድል ሹመት አልነበራቸውም። በሞስኮ አምባሳደርነት ተሹመው በጉዞ ላይ ሞቱ። ወሎና በጌምድርን በማስተባበር በአርበኝነት የተዋጉት ልጅ ዮሐንስ ኢያሱ፤ ሰዕድሜ ልክ እሥራት ወደ ጅማ ተወሰዱ። ሁኔታው ያላስደሰታቸው የመንዙ አባት አርበኛ ደጃዝማች አውራሪስ ዱላ አገራቸው ገብተው ሞቱ።

አዲሱ ሥርዓት ፅንዐት እያገኘ በሄደ ቁጥር በአርበኛው ላይ ክብደት አመጣበት። ወደ ቤተ መንግሥት ሲገባ፤ ከተፈቀደላቸው ጥቂቶች በስተቀር ትጥቅ መፍታት ሆነ። ይህ ጉዳይ ቀላል አልነበረም። አርበኛው የተዋጋው ከጣልያን ብቻ አልነበረም። ከባንዳም ጋር ነበረ። ደም ተቃብቶአል። አሁን ባንዳ የንጉሥ ባለምዋል እሱ ትጥቅ ፈቺ ሲሆን፤ ስጋትም ብስጭትም ገባው። ቀስ በቀስ እያለ አገሩ ገባ። ወገን ዘመድ አዲስ አበባ ውስጥ ያለው ትግሉን ቀጠለ። ንጉሠ ነገሥቱን እጅ መንሳት፤ ሚኒስትሮቻቸውን ደጅ መጥናት አስፈለገ። አብዛኞቹ ሚኒስትሮች በአርበኛው ዘንድ የታወቁ አልነበሩም። ቢታወቁም አክብሮት የሚሰጣቸው አልሆኑም። ከአዲሱ ሥርዓት ውስጥ ለመግባት አብዛኞቹ አርበኞች፤ ሚስቶቻቸውን እየተው በከተማ ሴት ወይዛዝርት ማግባት የተሻለ መስሎ ታያቸው። እንደዚሁም አደረጉ። ነገር ግን ችግሩ አልተቃለለም። መልኩን እየለዋወጠ ቀጠለ። በእኩሉ ከሳሽ ተነሳበት። እኩሉ በአገኘው መሬት ወይም ቤት ክርክር ተከፈተበት። "...የመንግሥታችንን ሥራ አሻሽለን ፍጹም እናደርገዋለን። የአበሻ አስተዳደር በአዲሱ ሥልጣኔ ይለወጣል።" "...ነፃና ሃብታም በሆነች ባንዲት ኢትዮጵያ ውስጥ ነፃነት፤ ትክክለኝነት...ያለው ሕዝብ ሆናችሁ እንድትኖሩባት እንፈልጋለን...[4] ተብሎ በንጉሠ ነገሥቱ የተነገረው አዋጅ ትርጉም አጣ።

የዳኝነት ሥራም እንደዚሁ ትርጉም አጣ። ከላይ በእንግሊዝ ክታች በባንዳ ተያዘ። አድልዎ፤ ሀሰት፤ ደባ ከፍርድ ገባ። የፍርድን ሥራ ለማስተካከል መምከርም አደገኛ ሆነ። አፈ ንጉሥ ገብረመድኅን ኃይለማርያም ከረጅም ጊዜ እሥራትና ከዕድሜ ልክ ግዞት የገቡት በዚህ ትንቅንቅ ነው። ከሁሉም የሚገመገዘው በበላይ ዘለቀ ላይ የተፈጸመው ነው። እሱን በቀረቤታ ማየት ይገባል። በላይ ዘለቀ ወደ አዲስ አበባ እንዲመጣ በንጉሠ ነገሥቱ በራሳቸው ተጠየቀ። ጉጃም ቆይቶ በዚያ የወደቁ አርበኞችን አጽም አያሰበሰበ ከቤተክርስቲያን ሲያስቀብር ቆየ። ንጉሠ ነገሥቱ አዲስ አበባ ከገቡ በኋላም እንደዚሁ መልእክት ደረሰው።

"አገሩን ለጠላት አስረክቦ ወደ ክበለሰ ሰው የምሄድበት ምክንያት የለኝም" የሚል የግል ስሜቱን በወዳጆቹ ምክር አስታግሶ ወደ አዲስ አበባ መጣ። ከፍ ብሎ የተገለጸው ዓይነት ትዕግሥት አስጨራሽ መንገላታት ደረሰበት። ከጥቅምት ወር ጀምሮ ደጅ ሲጠና ቆይቶ ሚያዝያ 8 ቀን 1934 ዓ.ም ለጉጃም አርበኞች ሹመት ተሰጠ። ልጅ ኃይሉ በሰው ራስ ተብሰው የጉጃም ገዥ፤ ደጃዝማች መንገሻ ጀምበሬ ደጃዝማች ተብለው የጉጃም እንደራሴ ሆኑ። በላይ ዘለቀ ደጃዝማች ተባለ። ነገር ግን ሀገር አልተሰጠውም። ደጅ ጥናቱን ቀጠለ። በሰኔ ወር የብቼና አውራጃ ገዥ ሆነ።

ወደ ጉጃም ተመልሶ የተሰጠውን አገር ማስተዳደር ጀመረ። ከሐምሌ 1 ቀን 1934 ዓ.ም እስከ ጥር 30 ቀን 1935 ዓ.ም ድረስ የሥልጣን ሹኩቻም ቢናር ሌላ ችግር አላጋጠመም። ከዚያ በኋላ ችግር ተፈጠረ። መንሥዔው የግብር አሰባሰብ ነው። እሱ ግብሩን አገሩን አስተዳድርበታለሁ ሲል፤ አለቆቹ ለማዕከላዊ መንግሥት አሰገባ ባይ ሆኑ። አከራከሮ ፍርድ ሰጭ አልነበረም። አለቆቹ ጦር አስልከው ግጭት ተፈጠረ። ከመንግሥት ወገን ሃያ አምስት ከእሱ ወገን አሥራ ሰባት ሰው ሞተ። አለቆቹ ክስ አቀረቡ። እሱ ባለፈው ዓመት የደረሰበት መጉላላት አልተረሳውም ነበርና፤ ወደ አዲስ አበባ ለመምጣት ፈቃደኛ ሳይሆን ቀረ። አለቆቹ እስከ ሃምሣ አንድ ሺህ የሚገመት የገበሬ ሠራዊት ላኩበት። እሱም ሶማ በረሃ ገባ። ጦሩ ተከታትሎ ስለደረሰበት የአሥራ አምስት ቀን ውጊያ ተካሄደ። ከመንግሥት ሠራዊት አምስት መቶ፤ ከእሱ ወገን አንድ መቶ የሚሆን ሰው ወደቀ። ንጉሠ ነገሥቱ "...በክፉ ባይህ ልጄን ልዑል መኮንን ይገሳኝ..." የሚል የመሐላ ቃል ያለበት ደብዳቤ በሊጋባ በቀለ በየነ እጅ ላኩ። እጁን ሰጠ።

አዲስ አበባ ለፍርድ ቀረበ። የተከሰሰባቸው ወንጀሎች በረከቱ። ንጉሠ ነገሥቱ የሾሟቸውን ባለሥልጣኖች አለመቀበል፤ ግብር ለመንግሥት እንዳይገባ መከልከል፤ ዐጥቃ ማደፍረስና የበርካታ ሰዎችን ደም ማፍሰስ ዋና ዋናዎቹ ሆኑ። ከጉጃም የተንቀሳቀሰውን የጣልያን ጦር ሳይዋጋ ወደ ወሎ እንዲሄድ ሰለአደረገ ሲቀጣ ይገባል ተብሎ ከኩሎኔል ዊንጌት /ጀነራል/ ቀርቦበት የነበረውም ክስ በንጉሠ ነገሥቱ እጅ መቆየቱ ይታወሳል። ወንጀሎቹ ከባድ ስለሆኑ፤ ባንዶቹም አጥብቀው ስለተከራከሩ፤ እሱም ሕግ ሊቀበለው በሚችል ዓይነት ስለአልተከላከለ ይሙት በቃ ተፈረደበት። የይሙት በቃው ፍርድ አርበኛውን ስለአስቆጣው ወደ ዕድሜ ይፍታሕ ተሰውጦ፤ ወሲሶ በደጃዝማች በቀሲ ወያ እጅ እንዲታሠር ተደረገ።

ሊያመልጡ ይችላሉ የሚል ጭምጭምታ ተሰማ ተብሎ፤ እሱና ዳኞቹ ወደ አዲስ አበባ መጥተው ደጃዝማች ውቤ ሠፈር በነበረው ወህኒ ቤት ውስጥ ታሠሩ። የተፈቀደላቸው ለምግብ በወር ዘጠኝ ብር፣ ለልብስ በዓመት ሃያ ብር ነበር ይባላል። የታሠረውም የጣልያን ሹም ሆኖ አሣሩን ሲያሳየው ከኖረው ከጣልያኑ ደጃዝማች ማሞ ኃይለሚካኤል ጋር ነበር። እነዚህ ሁኔታዎች ጐምዛዛ ሆነብት። ስለዚህ ለማምለጥ ያደረገው መከራ ሳይሳካ ቀርቶ ሱሉልታ ከተባለ ቦታ ተያዘ። በተደረገው መከራ ደግሞ ሌሎች ሦስት ያህል ሰዎች ሞተው ነበርና ወንጀሉ አለመጠን ከበደ። ለአርበኛውም አንዳች ለማለት አስቸገረው። ይሙት በቃ ተፈረደበት።

የአገዳደሉ ጉዳይ ደግሞ ሌላ ችግር አስከተለ። ወንጀሉ በተፈጸመበት ቦታ ብቸና እንዲሰቀሉ ተወሰነ። በብዙ መንገላታት ዓባይ ሲደርሱ ወንዙ የማያሻግር ሆነ። ያን ጊዜ ድልድይ አልነበረም። አይሮፕላን አልነበረም። ስለዚህ ውሣኔውን ማስፈፀም ሳይቻል ቀርቶ በሌላ ክባድ እንግልት ወደ አዲስ አበባ ተመለሱ። ጀግናው በላይ ዘለቀና ወንድሙ ጥር 30 ቀን 1937 ዓ.ም አዲስ አበባ ከተማ ተሰቀሉ። በላይ ዘለቀ የተሰቀለው መርካቶ አራተኛ ፖሊስ ጣቢያ አጠገብ እንደሆነና፤ የመጨረሻ ቃሉም "ኢትዮጵያ ወንድ አይበቀልበሽ" የሚል እንደነበር በወቅቱ በቦታው ላይ የነበሩ በምሬት ይናገራሉ።[5] ይህ ጉዳይ አገንግኖ የነበረውን አርበኛ ፀጥ አደረገው። የተፈለገውም ይህ ነበር።

በአርበኞች ላይ ከደረሱት ችግሮች አንዱ የክስና የክሳሽ ብዛት ነበር። አንዳንዱ በመሬት ሌላው በሥራ ምክንያት ነበር። በሥራ ምክንያት በአርበኞች ላይ የተነሱትን ክሶችና ያስከተሉትን መጉላላት በሙሉ ለመዘርዘር እጅግ ብዙ በመሆኑ፤ በደጃዝማች ገረሱ ዱኪ ላይ የደረሰውን ብቻ እንመለከታለን። ደጃዝማች ገረሱ ዱኪ በተራቀቀ ሥልት ጣልያንን የወጉ፤ መሴ ቀስተኛ የተባለውን የጣልያን ሰላይና ነገረ ሠሪ የገደሉ፣ ወደ ከፋ ተሻግረው የጋተሮንን፣ የአበልቱን፣ የአረንገማንና የጢሮን የጣልያን ምሽግ የሠበሩ፣ የጅማን ከተማ ከብበው ሰኔ 12 ቀን 1933 ዓ.ም የ800 ኢጣልያውያንን ምርኮ ኢትዮጵያን በመወከል የተቀበሉ የኢትዮጵያ ጀግና ነበሩ። አርበኛው የራስነት ማዕረግ ሰጥቶአቸው የነበረና፤ ንጉሠ ነገሥቱ ኖኖ ጊሸን ድረስ ሄደው ጎብኝተዋቸው በአዲሱ መንግሥት ውስጥ ከፍተኛ ቦታ እንደሚሰጣቸው ቃል የተገባላቸው ነበሩ።

ነገር ግን ከነፃነት መመለስ በኋላ ውስብስብ ችግር አጋጠማቸው። ተከታታይ ክስ ቀረበባቸው። የመጀመሪያውና በር ከፋቹ በአምስቱ ዓመታትና ጅማን በሚያስለቅቁበት ጊዜ የማረኩአቸውን መሣሪያዎች አላስረከቡም፤ በመንግሥት ላይ ተንኮል አስበዋል የሚል ነበር። ክሱ

አደባባይ ወጥቶ ክርክር ሳይደረግበት፤ መሣሪያዎቹ የነበሩበት ግምጃ ቤት በድንገት ተቃጠለ። ቢሆንም 14 መድፍ፣ 400 ባለውሃ መትረየስ፣ ብዙ ፈንጂዎችና ጠመንጃዎች፣ ብዙ ጥይት እንደነበረ ታውቆ ስለነበረ ቀላል አልነበረም። ቢሆንም ብልሁ ገረሱ ይቅርታ ስለጠየቁ ቅጣት አላገኛቸውም። ዞሮ ግን እዳፊው አልሰቀቃቸውም። ደጃዝማች በላይ ዘለቀ ወሊሶ በግዞት መቆየታቸው በዚህ ምክንያት ቄምር ሳይሆን አልቀረም። እሳቸውም ወደ ወላይታ ሶዶ ተሣወሩ። አብረው ከጣልያን ጋር የተጋደሉ አርበኞችም መሣሪያዎቻቸውን ተገፈፉ።

እንደገና የጋሞ ጉፋ ገዥ በነበሩ ጊዜ በራሣቸው ውሣኔ የመንግሥት ገንዘብ አውጥተዋል ተብለው ስለተከሰሱ፤ አዲስ አበባ ኮልፌ የነበረውን የአባታቸውን አርስት ለመሸጥ እስከማሰብ ተበሳጭተው ነበር። ከዚህ ሲያመልጡ ደግሞ ለመንግሥት የሚገባውን ታክስ ይቃወማሉ የሚል ሌላ ነገር ስለተደቀነባቸው ወደ አዲስ አበባ ተጠርተው ግዞት ገቡ። መበሳጨታቸውን የተገነዘቡ ሰዎች ከሐምሌ 1943 ዓ.ም የመፈንቅለ መንግሥት ሴራ ውስጥ አስገቡአቸው። እሳቸው ግን ምሥጢሩን ለንጉሠ ነገሥቱ በመንገርና አድመኞቹንም ከቤታቸው ጋብዘው በማስያዝ ከጥፋት ዳኑ። ከንጉሠ ነገሥቱ ባለምዋልነት አግኝተው የኢሉባቡር ጠቅላይ ገዥነትን ቢያገኙም፤ ከሕዝብ ትገበት መግባታቸው አልቀረም። ኢሉባቡር ደግሞ ደጃዝማች ኃይለሥላሴ ጉግሣን ለማስፈታት ከሚፈልጉ ሰዎች ጋር አሲረዋል፤ የፍርድ ቤቱን ፕሬዚደንት በድለዋል፤ ሠራተኞችንም ጨቁነዋል የሚሉ ክሶች ቀረቡባቸው።[6] ለክሶቹ አራማጅ መስለው ስለታዩአቸው የጠቅላይ ግዛቱን ዴሬክተር በጅራፍ ስለገረፉአቸው፤ ለጥቂት ጊዜ በእመክር ቆይተው የአርሲ ጠቅላይ ገዥ ሆኑ። ከዚያ እንደ አሉ የታህሣሥ 1953 ዓ.ም የመፈንቀለ መንግሥት መሪ ደረሱ። በአባትና ልጅ መካከል ምን አገባን የሚል ስሜት ስለገረዘዛቸውና መከራውን ለማክሸፍ ባለመተባበራቸው፤ በንጉሠ ነገሥቱ ዘንድ ሌላ ቅሬታ ስለተፈጠረ ሕግ መወሰኛ ምክር ቤት፣ ከጥቂት ጊዜ በኋላም ጡረታ ገቡ።[7]

ደጃዝማች ገረሱ ዕድለኛም ዘዴኛም ነበሩ። ብስጭት ይበዛባቸው፣ ቀደም ብሎ ቃል የተገባላቸው የጦር ሚኒስትርነት ሹመት አይሰጣቸው እንጂ፤ የደጃዝማች ገረሱ ዕድል እምብዛም ክፋ አልነበረም። ክስና ወቀሳ ቢበዛባቸውም ሌላ እንግልት አልደረሰባቸውም። እኛም ከዚህ የጠቀስነው በአርበኞች ላይ የነበረውን ውጣ ውረድ ለማሳየት እንጂ ተበድለዋል ለማለት አይደለም። ሌሎች እንደ እሳቸው ዕድለኛ አልነበሩም። አስመራሪ ጭቆና የተደረገባቸውና ተደጋጋሚ ሴራ የተሰራባቸው ሌሎች ብዙ አርበኞች ነበሩ። ከእነዚህም አንዱ ፊታውራሪ ዋልደፃድቅ ዘውዴ ነበሩ።

ከፖለቲካ ጉዳይ ውስጥ ስለአልገቡ ከቅጣቱ አልደረሱም። ነገር ግን እንኳን ጠቅላይ ገዥነት የወረዳ አስተዳዳሪነትም በዛባቸው። በ1954 ዓ.ም በተካሄደው የምክር ቤት ምርጫ በአማርት ወረዳ የተወዳደሩበት ሣጥን ወደ ሌላ ሰው ተገለበጠባቸው። ተገሰተ፣ ደብረክ በተባለ መሬታቸው አራት ባለጋራዎች ተነስተው ዕድሜ ልካቸውን አንገላቱአቸው። ከጽሕፈት ሚኒስትር በደብዳቤ እየታዘዘ ሲካሄድ የኖረው ይህ አራትዮሽ ክርክር ሲያበቃ የቻለው፣ ደርግ ተነስቶ የዙፋን ችሎትን በመዝጋቱ ብቻ ነበር። አርበኞችን እጅግ የጉዳና ያስመረራቸው ይህ ዓይነቱ ማብቂያና ማገጃ የሌለው ክስና ክርክር ነበር።

ደጃዝማች አውራሪስ ዱሉ ሁሉንም ነገር ትተው አገራቸው ገብተው በሀዘንና በብስጭት ሞቱ። እንደነ ቢትወደድ ነጋሽ የመሳሰሉት አርበኞች አልጋ የመገልበጥ መከራ አደረጉ። ይህ ደግሞ የአርበኞችን ኃይል ለማድቀቅ የሚካሄደውን ሴራ አጠናክረው።

ሌላው ችግር በአርበኝነት ጊዜ የተሰጡ ሹመቶች አለመጽናት ነበር። በሰሜን ሽዋ ንጉሠ ነገሥቱ መልአከ ፀሐይ ኢያሱ፣ ለባላምባራስ አበበ አረጋይ የራስነት፣ ለቀኛዝማች ኃይሉ ወልደ መድኅንና ለፊታውራሪ ዘውዱ አባ ኮራን የደጃዝማችነት ማዕረግ፣ ለሌሎችም ለብዙ አርበኞች የፊታውራሪነት፣ የቀኛዝማችነትና የግራዝማችነትና ማዕረግ ሰጥተዋል። አርበኞቹም ተቀብለው ሲጠሩበት ኖረዋል። የደጃዝማችነት ማዕረግ ቢሰጣቸው ሳይቀበሉ የሞቱ ቀኛዝማች ኃይለማርያም ማሞ ብቻ ነበሩ።[8]

የጐንደር አርበኛ መኳንንቱና ሊቃውንቱ ላይ ተሰብስቦ ከመክረ በኋላ፣ በልጅ ዮሐንስ ኢያሱ አማካይነት ለግራዝማች አሞራው ውብነህ የራስነት፣ ለሌሎች 153 ጀግኖች የደጃዝማችነትና የፊታውራሪነት ማዕረግ ሰጥቶ ነበር። አርበኞቹም ተቀብለው ሲጠሩበትና የጀብዱ ሥራም ሲሰሩበት ቆይተው ነበር።[9] ይሁን እንጂ የማስረጃው ደብዛ ጠፋ። በጎጃምም ደጃዝማች በላይ ዘለቀ ለብዙዎች የደጃዝማችነት፣ የፊታውራሪነት፣ የቀኛዝማችና የግራዝማችነት ማዕረግ መስጠታቸው እርግጥ ነው። ያልሸሙት አራሳቸውን ብቻ ነበር። በጉራጌ አገር ያለውም አርበኛ ተመሳሳይ እርምጃ ወስዶ በላምባራስ ገረሱን ራስ እንደ አሳቸው የሚያመለክቱ አንዳንድ አሻራዎች አሉ። እሳቸውም በበኩላቸው ለ775 አርበኞች ከግራዝማችነት እስከ ፊታውራሪነት ማዕረግ ሰጥተዋል። ከእነሱም አሥራ አንዱ ስመ ጥር የሀገር አስተዳዳሪነት ሥልጣን ጭምር የተሰጣቸው ነበሩ።[10]

በአጠቃላይ ለሦስት ጀግኖች የራስነት፣ ለጦር መሪዎች የደጃዝማችነት፣ ሌሎች ብዙ አርበኞች የፊታውራሪነት፣ የቀኛዝማችና

ግራዝማችነት ማዕረግ ተሰጥቶ ነበር። የእነዚህ ማዕረጐች አሰጣጥ ቀላል አልነበረም። የመሪነት ችሎታቸው፣ ለሀገራቸው ለመሞት የነበራቸው ቆራጥነት፣ የፈፀሙአቸው የጀብዱ ሥራዎች እየተመዘኑ ነበር። በመሆኑም እንደ አሉ መጽናት ነበረባቸው። ግን እነዚህ ሹመቶች በንጉሠ ነገሥቱ ዘንድ የልብ ተቀባይነት አላገኙም። የእያንዳንዱን ሰው ማዕረግ አጠናቅቆ ለመግፈፍ የሚቻል ባለመሆኑ ቀረ እንጂ ተወድዶ የተደረገ ነገር አልነበረም። ደጃዝማች ዘውዱ አበኩራን ደጃዝማችነታቸውን በፍርሀት ለቀቁ። አሞራው ውብነህና ገረሱ ዱኪ ወደ ፊታውራሪነት ወረዱ። የፊታውራሪ ወልደሣድቅ ዘውዴ ፊታውራሪነት በ1938 ዓ.ም ታደሰላቸው። ከሞቱ በኋላ በሰኔ 1962 ዓ.ም የተፈቀደው የደጃዝማችነት ማዕረግ ቀልድ ሆኖ ቀረ። ብዙ አርበኞች ሌላ ማዕረግ ሳያገኙ በእነዚያ በአርበኝነት ዘመናቸው በአገኙአቸው የማዕረግ ስሞች እንደተገደቡ ሞቱ። ይህ አደራረግ በንጉሠ ነገሥቱና በአርበኞች መካከል ትዝብት ፈጠረ። ጥላቻም አሳደረ። በዚህ ረገድ ንጉሠ ነገሥቱ አልተሳሳቱም ለማለት ያስቸግራል።

ባንዳም ለአርበኛ አልተኛለትም። አንዳንድ ቦታ በኃይል እስከ መሠናዘርም ደረሰ። ለምሣሌ ንብረባድቅ የተባለ ባንዳ በ"ልጋ፣ አሣግርት ልዩ ስሙ ሥራሮ የተባለው ቦታ፣ ፊታውራሪ ደብቁ ተክሌ የተባሉትን አርበኛ ሰኔ 10 ቀን 1936 ዓ.ም በዕለቱ ጋሻ ጃግሬዎቻቸው ከነበሩ ሁለት አርበኞች ጋር በጥይት ገደላቸው። ከጠላት የወሰደውን አንድ መትረየስና አስራ አምስት ብረት ለምን ገፈፈኝ ብሎ።

አብዛኛው በእልህ ከነገር ላይ የወደቀበት ጊዜም አለ። ቀኛዝማች በቀለ ግዛው የተባለው አርበኛ አንድ የእንግሊዝ መቶ አለቃ እሱን እንደ ሌላው ቅኝ አገር ሰው መስሎት፣ አዲስ አበባ ራስ መኮንን ድልድይ ላይ የወደቀን አንድ የፈረስ አሬማ ጉትት በማለት በአክሮባት ከፊቱ ላይ መታው። በቀለ ግን በያዘው መውዜር ከነመረቁ አጠጥቶት እጁን ለፖሊስ ሰጠ። እንዲያመልጥ ማድረግ የሚቻል የነበረ ቢሆንም፣ ገዳዩ አርበኛ ተመክሮ፣ በዋስ እንዲከራከር ማድረግ የተሻለ አማራጭ ሆኖ ተገኘ። ቀኛዝማች በቀለ ወንድሙን ፊታውራሪ ተሻገርን ዋስ ጠርቶ፣ ከተፈታ በኋላ ግን ትውልድ አገሩ፣ መርሐቤቴ ገባ። ሁኔታው እንግሊዞችን ስለአስቆጠና ንጉሠ ነገሥቱን ስለ አስቀየመ፣ ዳኛው ፊታውራሪ ኃይለራጉኤል ወልደፃድቅና ሁለቱ ወንድማማቾች ከግዞት ገቡ።

የጣልያን ባለምዋል የነበሩ ጸሐፊዎችና ዳኞች በዚያው ሥራቸው ቀጠሉ። አርበኛው ትምህርት ስለሌለው ካብ አይገባ ድንጋይ ሆነ። በልቡ ሀገሩን፣ በእጁ ጦሩን ይዞ ቆመ። ከማቅራራት በስተቀር እንዳች ማድረግ አልቻለም። አርበኛ ከባንዳ ዳኛ ችሎት መነጋገር አቃተው። ለማስረጃ ያህል

አንድ ምሳሌ ልጥቀስ፤ ፊታውራሪ ወልደፃድቅ ዘውዴ ከነጋድራስ ይምሩ ገብረሥላሴ ላይ አርበኝነትህን አስመስክር ቢባሉ ከበደ አበሞጣው፣ ቀኛዝማች ዳኜ፣ ፊታውራሪ ተሰማ ከተማ የተባሉትን ቀንደኛ ባንዶች ቆጠሩ። በዚህም ባለሥልጣኖቹ ቢበሳጩም፣ ሊቃወሙ አልቻሉም፤ ስለዚህ አርበኛው ከራሱ ውስጥ ከተመረጡ ዳኞች ዘንድ እየቀረበ እንዲያስመሰክር ማድረግ ግድ ሆነባቸው።

አርበኛው ከመንግሥት አንዳች ነገር ማግኘት ካስፈለገው፣ ለንጉሠ ነገሥቱ ያመለክታል። ይጠራሉት ተብሎ ሲታዘዝ፣ የጠየቀው ቤት ወይም መሬት ከሆነ፤ ለመንግሥት ሥራ የማይፈለግ፣ አስቀድሞ ያልተጠየቀና ያልተሰጠ፣ መንቀያ መትከያ መሆኑንና ሌሎችም ጉዳዮች እንዳገሩ ከጽሕፈት ሚኒስቴር ይታዘዛል። ይህ ትዕዛዝ በሀገር አስተዳደር በኩል ለክፍለ ሀገር፣ አውራጃ፣ ወረዳ፣ ምክትል ወረዳ ደርሶ እስኪመለስ እና ለጠያቂው መሥሪያ ቤት እስኪደርስ፣ እጅግ አሣር አለበት። በዚህ ዓይነት ሁለትም፣ ሦስትም ጊዜ የሚጠራበት ጊዜ አጋጥሞአል። ለምሣሌ እኔ ራሴ ከንጉሠ ነገሥት መልአክ ፀሐይ ኢያሱ ተፈቅዶልኝ በእጄ የነበረውን የዳዊት አገርን መልከኝነት፤ በየዓመቱ ለዘመን መለወጫ እያመለክትኩ ቆይቼ የተፈቀደልኝ በ1947 ዓ.ም ነው።

ይህንን ሲመለከቱ ብዙ አርበኞች ከተአቅቦ፣ ከብሕትውና ገቡ። እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ ተብለው ከንጉሠ ነገሥት መልአክ ፀሐይ ጋር የነበሩት መምህር መነኑ። መጨረሻ ጊዜ የታዩት የረር አካባቢ ነው። ግራዝማች ገድሰጊዮርጊስ ሀብተሚካኤል የተባሉት የቡልጋ አርበኛ ቅምብቢት እርሻ ገቡ። እሳቸው አርሰው ያላመረቱትን፣ ሚስታቸው ፈጭተው ያልጋገሩትን መብላት ተው። ቀኛዝማች ገብረመስቀል ኃይሌ ጉማ እንዲሸጥ አድርገሀል ተብሎ፣ በሐሰት ምስክር ከጠላት ንብረት ጥበቃ ኃላፊነቱ ተባረረ። ከዚያም የተሠረቀ አልጋ ገዝተሐል ተብሎ ተከሰሶ፤ በሐሰት ምስክር ተፈርዶበት ደብረ ብርሃን ወህኒ ቤት ታሠረ። ከዚያም በኋላ ከየትኛውም ከተማ ሳይገባ ባሰ ከተባለው ቦታ ኖረ። የሚደንቀው ይህ ሰው ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ከሥልጣን ሲወርዱ መቁረቡ ሲሞቱ መመንኮሱ ነው።

ከድል በኋላ በየመልኩ የተቀሰቀሰው ትግል የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያንንም ጠቀሰ። በጠላት ወረራ ጊዜ አደጋ ላይ ጥለዋት የሄዱትን ግብጻዊውን ሊቀ ጳጳስ መልሶ ለመቀበል ተጠየፈች። ለአጭር ጊዜ ተመልሰው ቢመጡም እሚዘልቁት አልሆነም። ተመልሰው ወደ ሀገራቸው ገቡ። ተሰደው የነበሩትን ንጉሠ ነገሥት መቀበል፤ ነገር ግን ተሰደው የሄዱትን ሊቀ ጳጳስ አልቀበልም ማለት፤ ለውጭ ተመልካች

የሚገባ ነገር አልነበረም። ነገር ግን ኢትዮጵያ አልተመለሰችበትም። ከዳር አደረሰችው። ኢትዮጵያዊ ሊቀ ጳጳስ ኂሳም ፓትርያርክ ተሾመ። በዚህም ረገድ አንድ መልካም ውጤት ተገኘ።[11]

ሌሎች እሥረኞች ሲመለሱ ዘርዓይ ደረሰ ሲመለስ አልቻለም። ምንም በሥራው ኢትዮጵያዊ ቢሆን በትውልዱ ኤርትራዊ መሆኑ ችግር ሳይፈጥር አልቀረም። ቢሆንም እሱ አጥብቆ እንደተከራከረላት ኢትዮጵያም አጥብቃ መከራከር ነበረባት። ይህንን አለማድረግም በታሪክ ፊት ያሳፍራታል።

የሻምበል አብዲሣ አጋ ሁኔታ ደግሞ ሌላው አሳዛኝ ታሪክ ነው። ጦርነቱ ሲያልቅ ወደ ካናዳ ተወሰዱ። ዜግነታቸውን እንዲለውጡ ተጠየቁ። በዚህ ጊዜ ተመልሰው ወደ ጣልያን አገር ተልከው እሥር ቤት ገቡ። በፍርድ ቤት ክስ ቀረበባቸው። ወንጀሉ በጦርነቱ ጊዜ 32 ገበሬዎች ገድለሀል የሚል ሆነ። ፊልድ ማርሻል ቫይካውንት አሌክሳንደር ለፍርድ ቤቱ አንድ ቴሌግራም አስተላለፉላቸው። ቴሌግራሙም ከጠላት አምልጠው ሽፍትነት እንደገቡ ከአስረዳ በኋላ "...ፋሽስትና ናዚሲስት የሚሠሩትን ተቃውሞ ለዓለም ነፃነት፤ ለኢትዮጵያ ክብር ተጋደለ። የመኮንኑ መሰቃየት ለእኛም ሆነ ለዓለም መንግሥታት የሚያሣዝን ጥልቅ ሐዘን ነው" የሚል ነበር። ፍርድ ቤቱ ቴሌግራሙ እንደ ደረሰው የሠላሳ ሁለት ዓመቱን እሥራት ወደ 18,000 ብር ለወጠላቸው። በአክፋፈልም ረገድም እንግሊዞች 32% ሬዱአቸው። የኢትዮጵያ መንግሥትና ሕዝብ 41% ከፈለላቸው።[12]

ይህ ሁኔታ አርበኛውን አጥብቆ አስመረረው። ብዙ ስሞታ ተነገረ። አቶ ሕይወት ጎደሩ ስለጠላት ዘመን የጻፉትን መጽሐፍ "ያቺ ቀን ተረግች" አሉት። ቀኛዝማች ታደሰ ዘወልዴ "ቀሪን ገረመው" አሉት። አቶ ዮፍታሔ ንጉሤ "እናት ኢትዮጵያ ሞኝ ነሽ ተላላ፣ የሞተልሽ ሳለ የገደለሽ በላ" ብለው ወዲያው ሞቱ። አቶ አበራ ጀምበሬ ስለበላይ ዘለቀ በጻፉት ታሪክ ቅልቅል ልብ ወለድ መጽሐፋቸው፤ "ብዕሬ አልቅሽ" በሚል ርዕስ ግጥም ደረደሩ። ነገር ግን ኢትዮጵያ ይህንን የመሰለ ሮሮ ለማድመጥ ጊዜ አልነበራትም። ዓለሙ ፋታ አሰሰጣትም፤ ወዘወዛት እንጂ። መስሚያ ጆሮ ማመዛዘኛ አእምሮ አጣች። ከዚህም የተነሣ አሁን ከአለችበት ማጥ የዘፈቃትን ረጅም ጉዞ ቀጠለች።

ማጣቀሻ ዕሑፎች

1. ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፣ *ሕይወቴና የኢትዮጵያ አርምሞ፣ 2ኛ መጽሐፍ*፣ ገጽ 232-338።
2. ስለ መሬት ሥልት ጥንታዊ ታሪክ እና የአዲሱ ዘመን የመሬት አስተዳደር ባጭሩ። በመሬት ይዞታ ሚኒስቴር የተደረገ ጥናት።
3. ጎጃር 23 ቀን 1935 ዓ.ም በተነገረ ሌላ አዋጅ።
4. ከበደ ተሰማ፣ *የታሪክ ማስታወሻ*፣ ገጽ 209።
5. ዘውገ ዘገየ፣ *አባ ኦስትር፣ የደኛዝማች በላይ ዘለቀ ታሪክ*፣ ገጽ 23-29።
6. በዚያ ዘመን አገረ ገዥው የማሕል ዳኛ ሆኖ በፍርድ ችሎት ይቀመጥ ነበርና።
7. *ታቦር ዋሚ፣ አባ ቦራ፣ የደኛዝማች ገረሱ ዱኪና የሌሎችም አርበኞች ታሪክ*፣ ገጽ 77-106።
8. የቡልጋና የሸንኮራ ትግል የሚለውን ምዕራፍ ይመልከቱ።
9. *ገሪማ ታፈረ፣ ጉንደሬ በጋሻው*፣ ገጽ 137-140።
10. *ታቦር ዋሚ*፣ ገጽ 52-53።
11. ዜና ባስልዩስ፣ ገጽ 35 እና 136።
12. መርሥዔ ሐዘን አበበ፣ *በኢጣልያ በረሃዎች*፣ ገጽ 64-73።

ምዕራፍ ስድሳ ሁለት
የሰላም ንግግር ከኢጣልያ ጋር

የሁለተኛው የዓለም ጦርነት በአውሮፓ ጀርመን ፖላንድን በመውረርዋ ነሐሴ 26 ቀን 1931 ዓ.ም /ሴፕተምበር 1 ቀን 1939/ ተጀምሮ፣ ሚያዝያ 26 ቀን 1937 ዓ.ም /ሜይ 5 ቀን 1945/ የበርሊን ከተማ ሲያዝ አለቀ። የሩቅ ምሥራቁ ጦርነቱ ግን ቀጠለ። ከዚህ እኛ የምንመለከተው ጦርነቱ በአውሮፓ ሲያልቅ ምን እንደተደረገ ነው።

ሙሶሊኒ ሚያዝያ 20 ቀን 1937 ዓ.ም /ኤፕሪል 28 ቀን 1945/ ሞተ። ሞቱም በማግሥቱ ለንደን ተሰማ። በዚሁ ቀን ማለትም ሚያዝያ 21 ቀን 1937 ዓ.ም /ኤፕሪል 29 ቀን 1945/ ሂትለር ራሱን ገደለ። ነገር ግን የጀርመን ጦር ጠቅላይ አዛዥ የነበረው ሂምለር፣ በስዊድን ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በኩል ከሚያዝያ 24 ቀን /ሜይ 2/ ቀን ጀምሮ ከምዕራባውያን ጋር የምሥጢር ግንኙነት አድርጉ ነበር። የሂምለር ሃሳብ በተለይ በምዕራብ ጦር ግንባር ላለው የጀርመን ሠራዊት የተኩስ አቁም ትዕዛዝ አስተላልፎ ትዕዛዝ ለመስጠት ሲሆን፣ በሁሉም ግንባር እጅ ከአልሰጠ እንደማይቀበሉት በሚስተር ቸርችል ሃሳብ ፕሬዚደንት ትሩማንና ማርሻል ስታሊን ተስማሙበት። ነገር ግን ሂምለር ስለተሠወረ ከስምምነት ላይ ሳይደርስ ቀረ። የጀርመንን እጅ መስጠት የሚያበስረው ስምምነት፣ ከያታል በተባለው በሌላ የጀርመን ጀነራል አማካይነት ሚያዝያ 29/ሜይ 7/ ቀን ተፈረመ። ተኩስም በማግስቱ ዕኩለ ሌሊት ጀምሮ ቆመ።[1]

በጦርነቱ ፍፃሜ ሶቭየት ራሺያ ብዙ አገሮችን ያዘ። እነ አስቶኒያ፣ ላትቪያ፣ ሊትዋንያን ጠቀለለ። ዩጐዝላቪያ፣ ሀንጋሪ፣ አልባኒያ፣ ቸኮዝሎቫኪያ፣ ፖላንድ፣ ሩሜንያና ቡልጋሪያ ኮሚኒስት አስተዳደር ውስጥ ገቡ። ከቅኝ ግዛት ሥር ይማቅቁ የነበሩ የአፍሪካና የእስያ አገሮች፣ ኮሚኒዝምን እንደ መድኀን አድርገው ተመለከቱ። በካፒታሊዝምና በኮሚኒዝም አስተዳደር በሚደርሰው ግጭት ሦስተኛው የዓለም ጦርነት እንዳይቀሰቀስ አሰጋ። በሁለተኛው የዓለም ጦርነት መፈጸም የተገኘው ሰላም ብዙም እንደማይቆይ ብዙ ምልክቶች ታዩ። ይህ የፖለቲካ ክስተት የምዕራብ አገሮችን አሰጋቸው። ዓለምን ከሌላ ጦርነት ለማዳን የሚቻልበትን መንገድ ቀየሱ።[2]

1ኛ. የጦር ወንጀለኞችን ጉዳይ የሚመረምሩና በአጥፊዎች ላይ ቅጣት የሚወስኑ የጦርና የሲቪል ፍርድ ቤቶች ተቋቋሙ። ነገር ግን እነዚህ ፍርድ ቤቶች በጣልያኖች ላይ፣ በተለይም በኢትዮጵያ የፈጸሙትን ወንጀል ከቁጥር ሳያገቡት ቀሩ።

2ኛ. በኢትዮጵያ እቤቱታ ተገንዞ በተቀበረው በዓለም መንግሥታት ጉባኤ ምትክ፣ የዓለም መንግሥታት ህብረትን አቋቋሙ። ኢትዮጵያ የድርጅቱን መመሥረቻ ደንብ ታህሣሥ 23 ቀን 1935 ዓ.ም ፈረመች። ሰኔ

18 ቀን 1937 ዓ.ም የድርጅቱን ቻርተር ፈርማ አባል ሆነች። ድርጅቱም ልዩ ልዩ ሥልጣን ይዞ ከጥቅምት 13 ቀን 1938 ዓ.ም ወና።[3]

3ኛ. በጦርነቱ የደቀቀችውን አውሮፓን በማርሻል ፕላን መልሶ አቋቋመ።

4ኛ. የቅኝ ግዛቶች ጉዳይ እየታየ ነፃነት የሚቀዳጁበት መንገድ በሕቡዕ አሠራር ተጀመረ።

እነዚህ ጽንሰ ሃሳቦች ከተሸከሙአቸው ጉዳዮች አንዱ፤ እርስበርሳቸው በተዋጉ አገሮች መካከል የሚደረገው ስምምነትና የሚፈጠረው የአሠራር ሥልት ሆነ። ከዚህም በስተቀር በወንጀለኝነት የሚጠየቁት ሀገሮችና የሚጠየቁበት ጉዳይ እንዲወሰን አስፈለገ። በ1937 /1945/ መጨረሻ አሸናፊዎች አገሮች ሞስኩ ከተማ ባደረጉት ስብሰባ፤ ተጠያቂዎቹ አገሮች ጃፓን በስተቀር ጀርመን፣ ኢጣሊያ፣ ሩማንያ፣ ሐንጋሪ፣ ፊንላንድ መሆናቸውን ወሰኑ። የሚከፍሉትም የጦር ካሣ ኢጣልያ 360፣ ቡልጋሪያ 70፣ ሀንጋሪ፣ ሩማንያና ፊንላንድ እያንዳንዳቸው 300 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር እንደሆነ ተወሰነባቸው። አንዱ ፍጥጫ በትሬኤስት ምክንያት ሆነ። ብዙም ችግር ሳይደርስ እንግሊዝና አሜሪካን ከዮጐዝላቪያ በጦር ኃይል ነጥቀው እጅ አደረጉ። ጀርመንን እንግሊዝ፣ አሜሪካ፣ ፈረንሣይና ራሺያ ተከፋፈሉአት። ድርሻቸው በይዞታቸው መጠን ሆነ።

ከስምምነት ላይ የተደረሰባቸውን ውል እንዲፈርመባቸው ከሚያስፈልጉ አገሮች አንድዋ ኢትዮጵያ ሆነች። ስምምነት እንዲደረግ የሚያስፈልገውም፤ ከወራሪዋ ከኢጣልያና በነዓ አውጭነት ከቆመችው ከእንግሊዝ ጋር ሆነ። መጀመሪያ የእንግሊዙ ስምምነት ጥር 22 ቀን 1934 ዓ.ም አዲስ አበባ ላይ ተፈርሞ እንደነበር ቀደም ብለን አስረድተናል። አሁን ደግሞ ስምምነቱ በወሰን ክልል ረገድ የነበረውን ቅርፅ እንመለከታለን።

በመጀመሪያ ደረጃ ስምምነቱ የባቡር ሐዲዱን በእንግሊዝ ጦር ሥር አድርጐታል። ከድሬዳዋ እስከ ሱማሌ የሚደርስ መጠኑ ያልታወቀ መሬት ለእንግሊዝ ጦር ማቋቋሚያ አድርጐአል። ይህ ሁኔታ በኢትዮጵያ ላይ ምን ያህል ችግር እንደፈጠረ ዛሬም መገመት ይቻላል። አንዱ መስተካከል የነበረበት ጉዳይ ይህ ሆነ።

ሁለተኛው ጉዳይ ከወራሪዋ ከኢጣሊያ ጋር ያለው ነው። ጥያቄዎቹ፡-

ሀ. ኢጣልያ በኢትዮጵያና በአልባኒያ ላይ ያላትን የይገባኛል ጥያቄ እንድታንሣ ተጠየቀች። ያለምንም ማንገራገር አነሳች።

ለ. በአፍሪካ አሕጉር የነበሩት የኢጣልያ ግዛቶች፤ ማለትም የሊቢያ፣ የኤርትራና የሶማሊያ ጉዳዮች ግን አነጋገሩ። በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የቅኝ ግዛት ማስወገጃ ጉባዔ ተጠባባቂነት/ትረስትሺፕ/ ሥር እንዲቆዩ ተወሰነ። እነዚህ ግዛቶች በእንግሊዝና በፈረንሣይ ይዞታ ሥር ቆዩ። የኢትዮጵያ ጥያቄ አድማጭ አጥቶ አንዳንድ አካባቢዎች በእንግሊዝ ይዞታ

ሥር እስከ አሥር ዓመት ያህል ሊቆዩ ቻሉ። በዚህ ላይ ደግሞ እንግሊዝ ታላቅዋ ሶማሊያ የሚለውን ሃሳብ አነሣስታ ሰሜን ሶማሊያንም ጨመረችበትና፤ አሁን ወደሚታየው ሁኔታ ያደረሱትን ጉዳዮች አስጀመረች። የኤርትራ ጉዳይ ከሁሉም የበለጠ አከራከረ። ኢትዮጵያ አጥብቃ ስለያዘች አሁን የታየው በጦርነትና በኃይል የመገንጠል ክስተት ተፈጠረ።[4]

ሐ. የጦር ካሣው ጉዳይ ሌላው አነጋጋሪ ጉዳይ ሆነ። የጣልያን ጠበ አጫሪነትዋና ወራሪነትዋ አላከራከረም።

መ. ኢጣልያ ከኢትዮጵያ ዘርፋ የወሰደቻቸውን የታሪክ ቅርሶች እንድትመልስ የሚለው ደግሞ ሌላ ጥያቄ ሆነ። አሁን አዲስ አበባ ባቡር ጣቢያ አደባባይ የሚገኘው የሞዓ አንበሳ ኃውልት ተመለሰ። የአክሱም ሐውልትም ቀሞ ከቆየበት ከሮም ከተማ በቅርቡ ሊመለስ ችሏል። ጥያቄው ኢጣልያ ኢትዮጵያን ለማልማት ክፍተኛ ወጭ አድርጋለች ወደሚል አመለካከት ዞረ። ኢጣልያ በኢትዮጵያ ላይ ያካሄደችው የልማትና የጥፋት ሥራ ሲመዛዘን፤ የጥፋቱ ወገን እንደ አመዘነ ቀደም ብለን ተመልክተናል። ነገር ግን ለአውሮፓ እንደዚያ አልታየውም። ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ አርባ ሚሊዮን ብር ካሰች። ኢትዮጵያ የተከራከረችው ስለ ሕግ ጭምር እንጂ ስለጥቅም ብቻ አልነበረምና ተቀበለች።



ሁለቱ ባላንጣዎች ቀጳሜዊ ኃይለሥላሴና ቤኒቶ ሙሶሊኒ።

የአውሮፓን የፖለቲካ ባሕርይ ጥቂት ለመመልከት ያህል፤ ኢጣልያ ከጦርነቱ በኋላ ምን እንደ ተደረገላት ማየት ያስፈልጋል። በኢትዮጵያ ላይ በአጥቂነት መነሳትዋን፤ በጦር ኃይል መውረርዋን፤ ሰላማዊውን የኢትዮጵያን ሕዝብ በዓለም ሕግ በተከለከለ የጋዝ መርዝ መፃጀትዋን ማንም አይክድም። ሁሉም ያምናል። ነገር ግን የሚደመጠው የኢትዮጵያ ጥያቄ አይደለም



ሁለቱ ባለንጣዎች ቀዳማዊ ኃይለሥላሴና ቤኒቶ ሙሶሊኒ።

የኢጣልያ እንጂ። ኢጣልያ ጦርነቱን በማስነሳት የመጀመሪያዋ ናት። ነገር ግን በጋለፊነት የተጠየቀችው ከጀርመን ጋር በመተባበርዋ ብቻ ነው። በአውሮፓ አድላዊ አመለካከት ጣልያን ኢትዮጵያን መቀየቀጥዋ ተገቢ ነው ማለት ነው። በፖትስደም የድል አድራጊዎቹ መንግሥታት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ጉባዔ ላይ የኢጣልያ ጉዳይ ተነሣ። ለድል አድራጊዎቹ መንግሥታት የጦር ጓደኛ እንደነበረች ሆኖ ተቆጠረች። ለዚህም ምክንያት የሆነው ስር ዊንስተን ቸርችል ለኢጣልያ መንግሥትና ሕዝብ በራዲዮ አስተላልፈው በነበረው መልእክት ተደናግጠው፣ ጥቂት የኢጣልያ ሹማምንት ሙሶሊኒን ከሥልጣኑ በማውረድ ኢጣልያን ከጀርመን ለመነጠል ጥቂት ሙከራ አድርገው ስለነበር ነው። በዚህ ውሣኔ መሠረት ኢጣልያ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አባል ሆነች። እሷም የቀድሞ ግዛትዋን ሊብያን፣ ኤርትራንና ሶማሊያን መልሣ ለመያዝ እንዲፈቀድላት፣ በነሐሴ 1938 ዓ.ም በፓሪስ ከተማ ለተደረገው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ጉባኤ ለማቅረብ በቃች።

ከዚህም የተነሣ ሁኔታዎች ተሰዋወጡ። በጎዳር ወር 1940 ዓ.ም ለንደን በተደረገው የእነዚያው መንግሥታት ጉባዔ ላይ ደግሞ የሕዝቦች ድምፅ እንዲጠየቅ ተወሰነ። ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ ኤርትራ ከኢትዮጵያ መዋሐድን፣ ሶማሊያ ነፃነትን መረጡ። በዚህ ዓይነት የኢትዮጵያ ምሥራቃዊ የወሰን ጉዳይ ጎዳር 26 ቀን 1927 ዓ.ም ሥርወ ነገር ተመልሶ ገባ። በኢትዮጵያና በሶማሊያ መካከል አለመግባባት እየተፈጠረ በተደጋጋሚ ግጭት ተነሣ። ከሁለቱም ወገን ብዙ ደም ፈሰሰ። በአድልዎ የተሰጣት ዕድል ለኢጣልያም አልጠቀማት። አጥቂ ሆነው ድንገት ቀደምዋት። እርስዋ በፖለቲካ እየዘቀጠች ሄዳ በሃምሣ ስምንት ዓመት ሃምሣ ሰባት መንግሥት እስከ ማቋቋም ደረሰች። ማፊያ እየተባለ በዓለም የታወቀ የወንበዴ ቡድን መፈንጫ ሆነች።

ማጣቀሻ ፅሑፎች

1. Winston Churchill, *The Second World War*, pp. 464-470.
2. Winston Churchill, *The Grand Alliance*, pp. 434-444.
3. Kimons Skordiales, *Kagnew*, p. 1.
4. Carlton Hayes, *Contemporary Europe Since 1870*, pp. 682-689.

ምዕራፍ ስድሣ ሰስት
ኢትዮጵያና ነፃነትዋ

ኢትዮጵያ በመንግሥታት ታሪክ ዘመን ሁሉ እንደኖረች አሳክራክረም። ወገንም ጠላትም የተቀበለው ሐቅ ነው። የሚያከራክረው ለምን ያህል ዘመን የሚለው ጥያቄ ብቻ ነው። አንድ መቶ ዓመት በሚለው የሻዕቢያ ቀልድና ሦስት ሺህ ዓመት በሚለው የደርግ ፌዝ መርካት የለብንም። ጉዳዩን በጥልቀ መመርመር ይገባናል።

ኢትዮጵያ ክርስቶስ ሊወለድ 2800 ዓመት ሲቀረው በተፃፈ ታሪክ ውስጥ ስምዋ እንደተጠቀሰ የሚያረጋግጥ ማስረጃ አንደ አለ ተመዝግቦል።[1] ክርስቶስ ሊወለድ 2500 ዓመት ሲቀረው ከግብጻውያን ጋር የንግድ ግንኙነት እንደነበራትም በታሪክ ተዘክሮአል። በመጽሐፍ ቅዱስም በተደጋጋሚ ተጠቅሳ ትገኛለች።

ከላይ የተጠቀሱት ሁኔታዎች ከውጭ አገር የተገኙ ናቸው። ወደ ሀገራችን የታሪክ ጽሑፎች ስንመለስ ይበልጥ ተጨባጭነት ያላቸው ማስረጃዎች እናገኛለን። በኢትዮጵያውያን ታሪክ ፀሐፊዎች ዘንድ የመጀመሪያው ንጉሥ ሰብስታህ ነው። የነገሠው ክርስቶስ ሊወለድ 2545 ዓመት ሲቀረው ነው። ከእሱ ወዲህ ያለውን ቀረቤታ እንመለከታለን።

መንግሥቶች	የነገሥታት ብዛት	ዘመን
1. ከሰብስታህ እስከ ጴኦሪ	22	560
2. ከጴኦሪ እስከ ቀዳማዊ ምኒልክ	52	1003
3. ከቀዳማዊ ምኒልክ እስከ ባዚን 8ኛ ዓመት የክርስቶስ ልደት	67	982
እስከ ክርስቶስ ልደት	141	2545
4. ከባዚን 9ኛ ዓመት እስከ ዛጉዬ...	93	920
5. ከዛጉዬ እስከ ይኩኖ አምላክ	11	333
6. ከይኩኖ አምላክ እስከ ሠርፀ ድንግል..	26	201
7. ከሠርፀ ድንግል እስከ ተክለ ጊዮርጊስ /ከ1553 እስከ 1777 ዓ.ም/..	18	224
8. ከተክለ ጊዮርጊስ እስከ ዳግማዊ ቴዎድሮስ	14	68
9. ከቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ልጅ ኢያሱን ጨምሮ...	7	121
10. የአብዮት ዘመን.....	4	20
ከክርስቶስ ልደት በኋላ	173	1987
ጠቅላላ ድምር.....	314	4532 ነው [2]

የመንግሥቶች ዓይነት የተለያየ መሆኑ አያስደንቅም። የወሰኑ በየጊዜው መስፋትና መጥበብም በአንድ ሀገር ላይ ብዙ ጊዜ የሚታይ ነገር ነው። የመናገሻ ከተማው ከቦታ ወደ ቦታው መዘዋወርም አያስገርምም። መታየት ያለበት የሀገሪቱ ሕልውና ፀንቶ መኖሩ ነው። ስለዚህ ኢትዮጵያ በመንግሥትነት መሥፈርትየኖረችበት ዘመን ከ4532 ቢበልጥ እንጂ አያንስም። አንድ ሕዝብ ተሰብስቦ ወዲያው በአንድ ሥርወ መንግሥት ሥር አይሰባሰብም። ረዘም ያለ ጊዜ ያስፈልገዋል። ስለዚህ ዛሬ በ1987 ዓ.ም ኢትዮጵያ ለ5000 ዘመን እንደኖረች ቢቆጠር ልዩነቱ ከ468 ዓመት ስለማይበልጥ ማጋነን አይሆንም።

በስም አጠራርዋ ጭምር የአግዓዝ ተፋሰስ በታሪክ ውስጥ ይታያል። መጽሐፍ ቅዱስ ስድሳ ሦስት ጊዜ ያህል ይጠቅሳታል። በነገሥታትዋም ስም ሲጠራት ንግሥት ሳባ፣ ንግሥት አዜብ ይላታል። ኩሽ የሚላትም ጊዜ አለ። ቅዱስ ዳዊት ግን ደጋግሞ ኢትዮጵያ ይላታል። ቁርአን ሕዝቦችዋን ሃበሻ ይላቸዋል። የእንግሊዝ ጸሐፍት አቢሲንያ ይሉአታል። መሶሊኒ ስምዋን ከአነጭራሹ ደምስሶ ምሥራቅ አፍሪካ ብሎአት ነበር። ኢትዮጵያ በኢትዮጵያዊነትዋ ኖራለች። ወደፊትም ትኖራለች።[3]

ታሪክዋን በዘመን አቆጣጠር፣ በስም አጠራር የጀመርነው ለዋዛ አይደለም። ኢትዮጵያ በኢትዮጵያዊነትዋ ታውቃ ነፃነትዋን ጠብቃ ከ5000 ዓመት ላላነሰ ጊዜ መኖርዋን ለማጠየቅ ነው። በዚህ ረጅም ዘመን ማዕከላዊ መንግሥቱ ከበረሃማው ኮሜርዌ ወደ ደጋው የወጣው፣ ከወራሪዎች ለመከላከል ጭምር ሳይሆን አልቀረም። የአሶር፣ የፋርስ፣ የግሪክ እና የሮም ተፅዕኖ ከብዶ ነበርና።[4] አክሱም፣ ላሊበላ፣ ፈጠጋር፣ ጉንደር፣ ደብረ ታቦር፣ መቀሌ፣ አዲስ አበባ ተዘዋውሮአል። ወሰንዋም እንደ ጊዜው ሁኔታ ሲጠብና ሲሰፋ ኖሮአል። የኢትዮጵያ ሕልውና ግን ታሪክ ከተመዘገበበት ጊዜ ጀምሮ እንደ ጸና ቆይቶአል።

በአገር ውስጥ አስተዳደር ረገድ የኢትዮጵያ ሁኔታ ጭንቅና መከራ የበዛበት እንደ ሆነ የሚያመለክቱ ብዙ የታሪክ አሻራዎች አሉ። የሀገሪቱ ማዕከል ከቦታ ወደ ቦታ መንቀራጠጥ በየጊዜው ለተነሱ መሪዎች ይጠቅም እንጂ ለሕዝብ የሚበጅ አልነበረም። የሀገር ዳር ድንበር የሚጠበቀው ሁል ጊዜም በጦርነት ነው። ሥልጣን ከአንድ ሰው ወደ ሌላ የሚዘዋወረው በፍልሚያ ነው። ይህ ሁሉ የሚገፋው በድሐው ሕዝብ ነው።

አሁን የታሪክ ቅርስ አድርገን የምንመለከታቸው የአክሱም ሐውልቶች የተሠሩት፣ የላሊበላ የአለት አብያተ ክርስቲያናት የተፈለፈሉት፣ የጉንደር ቤተ መንግሥቶች የታነጹት፣ በጊዜው የነበረውን ሕዝብ እየጠቀሙ አልነበረም። እየገዱ እያሰቃዩት እንጂ። እነዚህን ሁኔታዎች ለመለወጥ ብዙ ድካም ተደክሞአል።

ከባሕረ ሠላጤ ነገሥታት ጋር ለነበረው ፍጥጫ መከላከያ የሚረዳ ወዳጅ ማፍራት አስፈለገ። በንግሥት ሣባና በንጉሥ ሰለሞን መካከል እንደ ዘመኑ ሁኔታ የወዳጅነት ግንኙነት ተፈጠረ። እስከ መዋለድም ተደረሰ። ይህ ሀገርን ከውጭ ወራሪ ለማዳን የተደረገ ሙከራ፣ እሥራኤላውያንን ኢትዮጵያ ውስጥ አስገባቸው። በቀዳማዊ ምኒልክ መንገሥ ምክንያት ለሥልጣን አበቃቸው። በጥቁሮቹ ኢትዮጵያውያንና በነጮቹ እሥራኤልውያን መካከል የተፈጠረው የዘር ልዩነት ወጣቶችን እርስ በርስ በማጋባት የአስተዳደር ጥበብ ወረሰ። አበሻ ማለትም ድብልቅ ክልስልስ ሕዝብ ተነሣ። አረማዊ የነበረው እምነት በጽላተ ሙሴ ወደ ኢትዮጵያ መምጣት፣ በብሉይ ወደ አምልኮተ እግዚአብሔር ተሸጋገረ።[5] ወራሪ ጠላት ጽላተ ሙሴን እየተሸከመ በእግዚአብሔር በመተማመን የመከላከል ዘዴ ተገኘ።

ከቤተ እሥራኤል በመጣው አዲስ አስተዳደርና በቀድሞው ሥርዓት መካከል የተቀሰቀሰው ግጭት፣ ዮዲትን /ጉዲትን/ አስነሰቶ የመንግሥቱን ማዕከል ከአክሱም ወደ ላስታ አዛወረው። ሥርወ መንግሥቱንም ከንግሥት ሳባና ከሰሎሞን ዘር ወደ ዛጉዬ ወኖኖች አሸጋገረው። ይህ የሥልጣን ቅሚያ ከውጭ ተፅዕኖ ለማምለጥ ጭምር የተደረገ ሳይሆን አልቀረም። ስለዚህ ሀገርን የመከላከል ጉዳይም አለበት ሊባል ይበቃል። ቢሆንም ረዥም ጊዜ የወሰደ ዕልቂትና ጥፋት አስከተለ።

በዚያም ጊዜ የውጭ ወራሪዎች ኢትዮጵያን ለማጥቃት፣ ቢቻልም ለመያዝ ሞክረዋል። ሁሉም በኢትዮጵያውያን ድል እየተመቱ ወደየመጡበት ተመልሰዋል። ዋና ዋናዎቹን እንጠቅሳለን። ክርስቶስ ሊወለድ 336 ዓመት ሊቀረው ታላቁ እስክንድር መቄዶንያ በምትባለው የግሪክ አገር ተነሣ። ከግብፅ እስከ ህንድ ያለውን አገር ሁሉ ገዛ። ኢትዮጵያን ለመያዝ በአደረገው መከራ እሱ ራሱ በስለላ ሥራ ላይ እንደ ተሰማራ ተይዞ ከንግሥት ሕንደኬ አደባባይ ቀረበ። በንግሥት ሕንደኬ ሠራዊት ብዛትና በስለላ ጥበበዋ በመደነቅ የወረራ ሃሳቡን ትቶ በሰላም ተመለሰ።

አውግስጦስ ቄሣር የተባለው የሮም ገዥ ከአውሮፓ፣ ከአፍሪካና ከእስያም አህጉር ብዙ አገር አስገበረ። ኢትዮጵያንም ለማስገበር ፈልጐ አይሎስ ጋሎስ በሚባል የጦር አዛዥ አማካይነት፣ 10,000 እግረኛና 8,000 ፈረሰኛ ጦር ላከ። ኢትዮጵያውያን ሀገራቸውን እንዳይረግጥ ከጠረፋቸው ላይ በጦር አገዱት። ከዚያም ለብዙ ዓመታት ተዋግተው ሠራዊቱን ፈጅተው መለሱት። ኔሮ የሚባለው የሮም ንጉሥም ኢትዮጵያን ለመያዝ ፈለገ። ሰላዮቹና አማካሪዎቹ የሰጡትን ምክር ጥሶ በኃይሉ ተማምኖ፣ ከምቤሰስ በሚባል አዛዥ መሪነት ታላቅ ጦር ወደ ኢትዮጵያ ላከ። እሱንም ኢትዮጵያውያን ወግተው ድል በማድረግ መልሰውታል።[6]

ሃያ ዓመት ገደማ /ከ1516-1536 ዓ.ም/ የፈጀውና ብዙ ጥፋት ያደረሰው በግራኝ መሐመድ መሣሪያነት የተካሄደው የቱርክ ወረራ ነው።

ይህንን ጦርነት የሀገር ውስጥ የርስበርስ ውጊያ አድርገው የሚመለከቱ፣ የሃይማኖት ጦርነት አድርገው የሚያዩም አሉ። በእጅ አዙር የተካሄደ ወረራ መሆኑን ከአለማጤናቸው ነው እንጂ፣ ጦርነቱ የቱርክ ወረራ ነው።[7] ይህንን የቱርክን ወረራ ኢትዮጵያውያን ብቻቸውን ሊመልሱት አልቻሉም። የፖርቹጋሎችን ዕርዳታ መጠየቅ ነበረባቸው። ፖርቹጋሎችም ሰዕርዳታ ገብተው ቱርኮቹን አሸነፉና የኢትዮጵያን ነፃነት አረጋገጡ።[8] ነገር ግን ግራኝን በማሸነፍ ወረራ ከመለሱ በኋላ፣ እነሱ እራሳቸው ሥር ሰድደው አስቸገሩ። ከእነሱ የመላቀቁም ሥራ ቀላል አልነበረም። በአባቶቻችን የፖለቲካ ጥበብ ያለ ግጭት በሰላም ተፈጸመ። የሱስኒዮስ "ፋሲል ይንገሥ፣ ሃይማኖት ይመለስ" የሚለው አዋጅ የዚህ ሂደት መደምደሚያ ነበር።

ከዚህ ቀጥሎ ተከታታይ የወረራ መከራ በኢትዮጵያ ላይ የተካሄደው፣ ከአስራዘጠነኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ነው። ዘመኑ የቅኝ ግዛት የተስፋፋበት በመሆኑ አንዱ ሲመለስ ሌላው እየተተካ በኢትዮጵያ ላይ ተረባረቡባት። ከ1824 እስከ 1927 ዓ.ም ድረስ የነበረው ምዕተ ዓመት ያላቋረጠ የጦርነት አሳት የነደደበት ጊዜ ነበር። በዚህ አንድ መቶ ዓመት ውስጥ በድምሩ 32 ወራሪዎች በኢትዮጵያ ላይ ዘምተው ሁልጊዜም እየተሸነፉ ተመልሰዋል። ከእነዚህ ወራሪዎች 11 በምዕራብ፣ 4 በሰሜን፣ 15 በምሥራቅ፣ 2 በደቡብ የመጡ ነበሩ። ከወራሪዎቹ ቱርክ 10 ጊዜ፣ ጣልያን ደግሞ 8 ጊዜ ሙከራ አድርገዋል። ግብጾች፣ ሱዳኖች፣ እንግሊዝና ፊረንሣይም የተቻላቸውን አድርገዋል። ከእነዚህ ጦርነቶች ትልቁና ወሣኙ ኢጣልያ የተሸነፈችበት የአድዋው ነበር። ከዚህም በስተቀር የኢትዮጵያን የግዛት አንድነት ለማፍረስ፣ ሦስት ጊዜ በእንግሊዝና በጣልያን፣ አንድ ጊዜ ደግሞ በእንግሊዝ፣ በፊረንሣይና በጣልያን መንግሥታት መካከል ውል ተፈርሞአል።[9]

የ1928 ዓ.ምቱ የኢጣልያ ወረራ የተቀለቀሰው ኢትዮጵያ ከዚህ በላይ በተገለጹት 32 ዓለም አቀፍ ጦርነቶች ብዙ ችግር ከደረሰባት በኋላ ነው። በሀገር ውስጥ የተካሄደው የርስበርስ ውጊያ ደግሞ ብዙ ጉዳት አድርሶባታል።

ኢትዮጵያና ኢጣልያ ጦርነታቸው እንደምን እንደአካሄዱት ከታየ በኋላ፣ በተመራማሪ አእምሮ የሚነሳው ጥያቄ "ለመሆኑ ጦርነቱን ማስቀረት የሚቻልበት ዘዴ አልነበረምን?" የሚል ይሆናል። ነፃነትዋ እስከተጠበቀላትና የግዛት አንድነትዋ እስከተከበረላት ድረስ፣ በኢትዮጵያ በኩል ጦርነቱን የማስቀረት ከፍተኛ ፍላጐት ነበር።[10] ስለዚህ በኢጣልያ በኩል የነበረውን ሁኔታ መመልከት ግድ ይሆናል።

ኢጣልያ ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛት የመያዝ ሃሳብዋ ቁርጠኛ ነበር። ምክንያቶቹ ቀደም ብለው ተዘርዝረዋል። በኢጣልያ በኩል ጥናት የሚካሄደው "እንደምን?" በሚል ጥያቄ ላይ ብቻ ነበር። ይህ በጉልህ እየታወቀ፣ ጦርነቱ እንዲቀር በኢትዮጵያ በኩል ጥረት አለመደረጉን የእነሱ በኩል ተከራካሪዎች ያወግዛሉ። የኢትዮጵያ መንግሥት ኢጣልያ የንግድና የልማት ሥራዎች

እንድታካሂድ በ1920ዓ.ም /1928/ የተደረገውን ስምምነት ቢያከብር ኖሮ ጦርነት ይነሣ እንዳልነበረ ያስባሉ። የሆርና ላቫል የዕርቅ ሃሳብ በኢትዮጵያ በኩል ተቀባይነት አግኝቶ ቢሆን፣ ጦርነቱ ይቀም እንደነበረ አድርገው ያስባሉ።[11] እውነት ነው። ይህ መንገድ ኢጣልያ ኢትዮጵያን ያለጦርነት እጅ ታደርግበት ስለነበር፣ ያ ሁሉ የደም መፋሰስ አይደርስም ነበር። ምናልባት የኢጣልያ ቅኝ ገዥነት እንደ ጸና ይቀርም ነበር። እንደዚህ አለመሆኑ ኢጣልያውያንን ያጸጽታል። ነገር ግን የኢትዮጵያ ጥቅም አልነበረም። ኢትዮጵያ ነፃነትዋን ጠብቃ፣ ወሰንዋን አስከብራ የምትኖርበት ዕርቅ በዛ ውስጥ አልነበረም። ንጉሠ ነገሥቱ ይህንን እጅ አሰጥ እርቅ አለመቀበላቸው ያስመሰግናቸዋል። በወቅቱ ቀርበው በነበሩት አማራጮች፣ ጦርነቱን ለማስቀረት የሚቻልበት አንዳች ዘዴ እንደ አልነበረ እስማማለሁ።

በኢትዮጵያና በኢጣልያ መካከል የተካሄደውን ጦርነት ከዚህ በላይ ባሉት ምዕራፎች ሁሉ በዝርዝር ተመልክተናል። ከዚህ በመቀጠል ደግሞ ለአሁኑም ሆነ ለወደፊቱ ከታሪካችን መማር የሚገባንን እንመርምር። ስለዚህ ቀጣዩ ጥያቄ "ኢትዮጵያ ከዚህ ሁሉ ወራሪ ነፃነትዋን አስከብራ ለመኖር ያበቁአት ምን፣ ምን ናቸው?" የሚል ይሆናል። ይህንንም ጥያቄ መመርመር ትምህርት ይገኝበታል። ስለዚህ በነፃነት ለመኖር ያበቁአትን ነገሮች አንድ በአንድ እንመለከታቸዋለን።

1ኛ. እንደእኔ፡- ኢትዮጵያን በነፃነት ጠብቆ ያቆያት እግዚአብሔር ነው። ልብ ለአለው፣ ለዚህ ብዙ ማስረጃ አለ፤ ኢትዮጵያ በመጽሐፍ ቅዱስ በተደጋጋሚ ተጠቅሳለች። ቅዱስ ዳዊት "ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች" አለ። "እግዚአብሔር ይነሣ፣ ጠላቶቹም ይበተኑ።... ጢስ እንደሚበን እንደዚሁ ይብነኑ።... ጻድቃንም ደስ ይበላቸው። በእግዚአብሔርም ፊት ሐሤት ያድርጉ..." በአለበት መዝሙሩ፤ ደግሞም "...አንተም የዘንዶውን ራስ ቀጠቀጥህ። ለኢትዮጵያ ስዎችም ምግባቸውን ሰጠሀቸው..." አለ።[12] እስላሞችም ነቢዩ መሐመድ "አበሾችን አትንኩ ያለዚያ ትጠፋላችሁ" እንደ አሉ። እነዚህ ቃላት ለኢትዮጵያ በትክክል ተፈጽመውላታል። እግዚአብሔር ኢትዮጵያን የሚረዳት እርስዋን በማዳን ብቻ አይደለም። ጠላቶችዋን በማጥፋት ጭምር እንጂ። ኢትዮጵያን የነኩ ኃይሎች ጠፍተዋል። አንባቢ ሊገነዘበው ስለሚችል ማስረጃ ለማቅረብ አንሞክርም። ልበ ቢሶች ልብ አይሉትም እንጂ፣ አሁንም እየታየ ነው። ወደፊትም ይቀጥላል። ኢትዮጵያ በእምነት እስከ ጸናች ድረስ አይናወጽም። ቃለ መለኮት ነውና።

2ኛ. ኢትዮጵያ ነፃነትዋን አስከብራ የኖረችው በልጆችዋ ደም ነው። በዘመናችን አነጋገር "በትግል" ነው። ኢትዮጵያውያን ታላቁ ችግራቸው እርስበርሳቸው አለመስማማትና አለመተባበር ነው። ሆኖም የሚለያዩትና እርስበርሳቸው የሚጋጩት በሰላም ጊዜ ነው። የውጭ ወራሪ በመጣ ጊዜ የርስበርስ ጠባቸውን ወደ ጐን በመተው፤ የመጣባቸውን ጠላት ተባብረው

ይመልሳሉ። በተለይ የአማራው ነገድ የሀገርን ነፃነት በመጠበቅ ረገድ የከፈለውን መሥዋዕትነት መካድ ሞኝነት ነው። ይህ ነገር መልካም ነው። የርስበርስ ልዩነታቸውን በመሣሪያ ፍልሚያ ሳይሆን በሰላምና በመመካከር ለማቃለል የሚችሉበትን ሥርዓት ቢመሠርቱ ደግሞ እጅግ መልካም በሆነላቸው ነበር። እያደር በመቀጨጭ ፈንታ ይዳብሩ ነበር።

3ኛ. ኢትዮጵያን በነፃነት ለማኖር ከረዱት ነገሮች አንዱ ዘውድ ነው። በሰላም ጊዜ የዘውድ አገዛዝ ተፅዕኖ ከባድ ነው። ብዙዎቹን አስመርሮአል። አወራረሱም ከሥርዓት እየወጣ ብዙ ደም አፋስሶአል። ብዙ ጥፋት አድርሶአል። የውጭ ወራሪ በመጣ ጊዜ ግን ሕዝቡን አንድ በማድረግ ረገድ ያለው ችሎታ ፅኑዕ ነው። ነገሥታቱም ብዙ የሕይወት መስዋዕትነት ከፍለዋል። የኢትዮጵያን ነፃነት በመጠበቅ በኩል ዘውድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርጐአል። ዘላባጅ እንጂ እውነተኛ ታሪክ ይህንን እውነት ሊክድ አይችልም።[13]

4ኛ. ለኢትዮጵያ ነፃነት ደጀን ሆኖ ያገለገለው የመሬት አቀማመጥ ነው። ለምነትዋ ብዙ ጠላት አፍርቶባታል። በአንፃሩ ደግሞ የጅአግራፊ አቀማመጥ ለነፃነት በተደረገው ትግል በጐ አስተዋፅኦ አድርጓዋል። በሀገሪቱ በመላ ታላላቅ ተራሮችና ሸንተረሮች አሉ። በውስጣቸውም ውሃና ለም መሬቶች አቅፈው፣ የውጭ ወራሪ በወጣ ጊዜ ለመከላከል የተመቹ እጅግ ብዙ ናቸው። ተዋጊው ሠራዊት ስንቅና ውሃ በማጣት አይቸገርም። ሕዝብም እነዚህን በሮች በጥንቃቄ ይጠብቃቸዋል። ለምሣሌ እኔ በተወለድኩበት አካባቢ እያንዳንዱ ቤተሰብ ከአያት ከቅድመ አያት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣለት በር አለ። በጥንቃቄ መጠበቅ አለበት። ያለአግባብ በጠላት ከአስያዘ ቤተሰቡ ይዋረዳል ይናቃል። በንጉሠ ነገሥቱ ጊዜ የነበረው የኢትዮጵያ መዝሙር

ብርቱ ናቸውና ተራሮችሽ፣
አትፈሪም ከጠላቶችሽ፣

ይል የነበረው በከንቱ አልነበረም። እስከ አሁን የገለጽነው የደጋውን ነው። የቆላውን አገር ከወራሪ ለመከላከል ግን እጅግ አስቸጋሪ ነው። ኢትዮጵያ የባሕር በሮችዋን ያጣችው ከዚህ የተነሣ ነው።

5ኛ. አውሮፓውያን ኢትዮጵያ ነፃነትዋን ጠብቃ ለመኖር የቻለችው በአውሮፓውያን እርስበርስ መከፋፈል እንደሆነ አድርገው ይገምታሉ። በመጠኑ እውነትነት አለው። አንዱ በጠላትነት ሲነሣ፣ ሌላው በወዳጅነት ከኢትዮጵያ ጐን ይቆማል። ይህንን የሚያደርጉት የርስበርስ ሚዛናቸውን ለመጠበቅ በሚያደርጉት ጥንቃቄ እንጂ፣ ለኢትዮጵያ ደንታ ኖሮአቸው አይደለም። አብዛኞቹ የኢትዮጵያ ነገሥታት ይህንን ሁኔታ ተገንዝበው አውሮፓውያንን እርስበርሳቸው የፖለቲካ ጨዋታ እንዲጫወቱ በማድረግ፣ የኢትዮጵያን ነፃነትና ጥቅም አስጠብቀዋል። በተለይም ብልሁ ዳግማዊ አፄ ምኒልክ።

6ኛ. የኢትዮጵያን ነፃነት የረዱ አገሮች አሉ። ስለኢትዮጵያ ነፃነት ስናስብ፣ እነሱንም ማስታወስና ማመስገን ይገባናል። ፖርቱጊዞች በ16ኛው ክፍለ ዘመን ከተሰነዘረብን የኡቶማን መንግሥት ወረራ ስለአዳኑን እናመሰግናቸዋለን።[14] እንግሊዞች በ1927 እስከ 1930 ዓ.ም ክቆየው የጣልያን ወረራ ስለአላቀቁን ትውልድ የማይረሳው ምስጋና እናመሰግናቸዋለን። የቀድሞው የሶቪየት ሕብረት መሣሪያ በመሸጥ፣ ኪዩባና ደቡብ የመን ወታደር በመስጠት በ1969 እስከ 70 ዓ.ም ከተቃጣብን የሶማሊያ መንግሥት ወረራ ተከላክለውልናል። እነሱንም እናመሰግናቸዋለን።

ይህንን ምዕራፍ ከመደምደማችን በፊት "ለወደፊቱስ ምን ይሻላል?" በሚል ጥያቄ ላይ ጥቂት ማስተዋል ይበጃል። አንድነትና ብርታት የሚሉት ገራገር ፊሊጦች በቂ አይደሉም። እውነተኛ ነገሮች ላይ ማተኮር ያስፈልጋል። ኢትዮጵያ ጠላት የሚያበዙባት ፀጋዎች አሏት። ከእነዚህም ጠላት አፍሪ ፀጋዎች ዋና ዋናዎቹ ከዚህ የሚከተሉት ናቸው።

ሀ. ለም አፈር፣ ኢትዮጵያ አፈር አላት። አያያዛችንን በማበላሸት እያጠፋነው ነው እንጂ፣ በእህል፣ በእፅዋት፣ በዛፎች፣ በእንስሳትና በአራዊት ያለው ሀብት ቀላል አይደለም።

ለ. ለስላሳ አየር፣ ኢትዮጵያ መላውን ዓመት የሚቆይ ለስላሳ አየር አላት። ከቆላው አገር በስተቀር። ይህ ፀጋ ቀላል አይደለም። በርካታ አገሮች ይህን አልታደሉም።

ሐ. ውሃ፣ በዓለም ላይ ውሃ ታላቅ ሀብት ነው። ኢትዮጵያ ከዓመት ዓመት ጥሩ ውሃ በብዛት የሚያፈስሱ ታላላቅ ወንዞች አላት። የእነዚህ ውሃዎች አጠባበቅና አጠቃቀም የራሱ የሆነ ችግር አለው። በተለይም የዓባይ።

መ. ማዕድን፣ ማዕድን የሀብት ምንጭ ነው። ኢትዮጵያ ብዙ ማዕድናት አሉአት። አውጥቶ መጠቀም አልተቻለም። ያልተቻለውም በአውቀትና በአቅም ማነስ ምክንያት ነው። በእነዚህም ጠላት ከመግዛት ይልቅ የመጠቀምን ፈሊጥ መከተል ይሻላል።

ሠ. አቀማመጣችን፣ የኢትዮጵያ የጂአግራፊ አቀማመጥ በአውሮፓና በአፍሪካ፣ በመካከለኛውና በሩቅ ምሥራቅ መተላለፊያ ላይ ነች። ስለዚህም በየጊዜው የሚነሱ ገናን መንግሥታት ይተናኩሱአታል።

ረ. ቅኝ ግዛትን ተናንቃ በማሸነፍ ከ5000 ዓመት በነፃነት ኖራለች። ይህም ጥሩ ታሪክ የሌላቸውን አገሮች ያስቀናቸዋል። የኢትዮጵያ ታሪክ የአንድ መቶ ዓመት ነው እስከማለት የደረሱት ከዚህ የተነሣ ነው።

ሰ. ኢትዮጵያ ለጥቁሩ ሕዝብ መልካም አርአያ ናት። የአፍሪካ አገሮች ምክርዋን ማዳመጥ ጀምረዋል። የዘር ልዩነት በሽታ የተጠናወታቸው አገሮች ይህንን አይወዱም።

ሽ. በእምነት ምክንያት የሚቃረኑአት የውጭ ኃይሎች አሉ። ክርስቲያኖቹ ካቶሊኮችና ፕሮቴስታንቶችም አልተኙላትም። እስላሞችም እንደዚሁ።

ቀ. ሌላው ችግር የውጭ ጉዳይ ነው። አንድ ጊዜ ከአንዱ ሌላ ጊዜ ከሌላው መሆን አይጠቅምም። የሚሻለው በተቻለ መጠን ከሁሉም ወዳጅ መሆን፤ ይህ ባልተቻለ ጊዜ ገለልተኛ መሆን ነው።

ከዚህ በላይ ከሀ እስከ ሽ የተመለከተው የውጭ አገር ኃይሎች በኢትዮጵያ ላይ ያላቸውን አመለካከት የሚያሳይ ነው። በዚሁ ላይ ደግሞ የሀገር ውስጥ ችግር አለ። እነሱንም እንደ ውጭ አገሮቹ ጉዳዮች በየፈርጃቸው መመልከት ያስፈልጋል።

ትልቁ ችግር የመልካም መንግሥት እጦት ነው። ሀገርዋ መልካም፣ ሕዝብዋ ሠላም ፈላጊ፣ ሠላም ወዳድ ነው። ስለዚህ ገዥዎች ይሚሚቱባታል። በማዘን፣ በመራራት አይተዋትም። ሥልጣን ለመያዝ ብዙ ደም ያፈሳሉ። ከያዙ በኋላ በሥልጣን ላይ ለመቆየት፣ በሕዝብ ላይ ብዙ የጭካኔ ሥራ ይሠራሉ። ታሳላቅ ብዝበዛ ያካሂዳሉ። ሥራቸውን ስለሚያውቁ፣ በራሳቸው አይተማመኑም። ስለዚህ ምሥጢራቸውን ከውጭ አገር ስዎች ጋር ያደርጋሉ። ገንዘብም የሚያስቀምጡት በውጭ አገር ይሆናል። ይህ ሁኔታ ሕዝብን አስመርሮአል። ሀገሪቱን አራቁቶአል።

ሁለተኛው ችግር የሕዝብ አንድነት መቀነስ ነው። ኢትዮጵያ ብዙ ጐሣዎች፣ እንደ ዘመናችን አነጋገር ብሔረሰቦች ያሉባት አገር ናት። በ1945 ዓ.ም አካባቢ በትምህርት ሚኒስቴር የተካሄደ አንድ ጥናት የብሔረሰቦቹን ብዛት በቋንቋ ረገድ ተመልክቶ እስከ 115 አድርሶት ነበር። እንደ መመዘኛው ነው። በማንኛውም መመዘኛ ቢሆን ከ80 አያንስም። በዚህ ላይ ደግሞ የእምነት፣ የባሕልና የሥርዓት ልዩነቶች አሉ። እነዚህ ልዩነቶች ሥምረት ካላገኙና ተከባብረውና ተደጋግፈው የሚኖሩበት ሥርዓት ካልተፈጠረ፣ ኢትዮጵያ ጽንአት ልታገኝ አትችልም። ኢትዮጵያ ጽንአት ካላገኘች ጥቃት አይቀርላትም።

ስለዚህ፣ አዲሱ ትውልድ የአገሩን ነፃነትና አንድነት ለመጠበቅ፣ ሁለት አፎት ያለው ሠይፍ ጨብጦ መዋጋት ይኖርበታል። በአንድ ወገን በሀገር ውስጥ ከመጥፎ መንግሥታት፣ ከዘርና ከሃይማኖት ልዩነት። በሌላ ወገን ደግሞ ከውጭ ወራሪዎች። እዚህ ላይ መታወስ ያለበት ጣልያን እስከ ዛሬም ድረስ በመጥፎ ሥራዋ ተጸጽታ ኢትዮጵያን ይቅርታ አለመጠየቅዋ ነው።

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም በነፃነት ትኑር!
(እንደእኔ፣ በበኩሌ፦ አሜን!)

አባሪ 1

የንጉሠ ነገሥት መልአከ ፀሐይ አነጋገስ

ልጅ ኢያሱ በወደቁ ጊዜ ከልጆቻቸው አንዱ መድኃኒዓለም በተባለ ገዳም፣ አባ ይርዳው በተባሉ አበምኔት እንዲጠበቁ ተደርጎ ነበር። ይህ ልጅ የተወለደው ጨፋ በተባለው ሥፍራ ነሞሪ ከነበሩት ከወይዘሮ ፀሐይ ወርቅ ዳርጌ ሲሆን፤ ስሙም የኋላሸት ነበር።

የጣልያን ጦር ወደ ኢትዮጵያ ሲገባ አርበኞችን የሚያንቀሳቅስ አንድ መሪ ስላስፈለገ፣ ከፍ ሲል የተጠቀሰው በወቅቱ እድሜው 18 ዓመት የነበረው የኋላሸት ኢያሱ፣ በአለቃ ወልደሃዋርያ ዘውዴ አቀነባባሪነት ነሐሴ 29 ቀን 1929 ዓ.ም አሁድ ዕለት ወክፈሌ ሚካኤል ቤተክርስቲያን በተከናወነ ሥርዓት ነገሠ። እሱም ከነገሠ በኋላ በተራው፦

- ባላምባራስ አበበ አረጋይን "ራስ"፤
- ቀኝ አዝማች ኃይሉ ወልደመድህንን "ደጃዝማች"፤
- ፊታውራሪ ዘውዱ አባክራንን "ደጃዝማች"፤
- አለቃ ወልደሃዋርያ ዘውዴን "ፊታውራሪ"፤
- አቶ ወልደ ዮሐንስን "በጅሮንድ"፤
- ቀኛዝማች ክበረ ኃይለሥላሴን "ክንቲባ"፤
- አቶ ዝቅ አርጌን "ፊታውራሪ"፤
- አቶ ሞገስን "ፊታውራሪ"፤
- አቶ ገብረመስቀል ኃይሌን "ቀኛዝማች"፤
- አለቃ ሥዩም ተክሌን "ግራዝማች"፤
- ወጣት ምስካ ሥዩምን "ቀኛዝማች"፤ እንዲሁም ሌሎችንም ብዙ የጦር መሪዎችን በመሾም አርበኝነትን ሥርዓት አስይዞ አቋቋመ።

በዚህ ዓይነት አርበኛውን ካጠናከረ በኋላ በረከት፣ ስድስቶ ላይ መሽን የነበረውን የጣልያን ጦር ለመጨረስና ምሽጉን እጅ ለማድረግ ነሐሴ 27 ቀን 1930 ዓ.ም ትልቅ ጦርነት መራ። የጦርነቱ ዝግጅት የተቀነባበረው በምስጢር ነበር። ነገር ግን ምሥጢሩ ለጠላት ቀድሞ ደርሶ ኖሮ መከራው ሳይሳካ ቀረ። ብዙ ሰውም አለቀ።

ይህንንም ተከትሎ መልዓከ ፀሐይ ኢያሱ ምኒልክ መስከረም 19 ቀን 1931 ዓ.ም የሰው ብልሃትና የሰው ተንኮል አለበት በሚያሰኝ አጠያያቂ ሁኔታ ሞቱ። መሞታቸውም በወክፈሌ ሚካኤል ቤተክርስቲያን ወዲያውኑ ዜናው ደርሶ ሊነገር ችሏል።

አባሪ 2
የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች ማሕበር አመሠራረት

የጣልያን ወራሪ ጦር በሚያዝያ 27 ቀን 1928 ዓ.ም አዲስ አበባ ገብቶ ኢትዮጵያን መያዙን ለዓለም አስታወቀ። አርበኝነት ሳይውል ሳያድር በየቦታው ተጀመረ። በቡልጋ አርበኝነት የተጀመረው በየአካባቢው የጎበዝ አለቃ በመምረጥ፣ በአፄ ምኒልክ /ቀደም ሲል ማይጨው፣ ኋላ ላይ ደግሞ አዛውረው/ ኮረማሽ በተባለው ሥፍራ በሚገኝ ዋሻ ተቀምጦ የነበረውን ዳር ድንበር ማስከበሪያ የጦር መሣሪያ በመክፋፈል እና በእጅ የነበረውን እንደ ናስማሰር የመሳሰሉ ኋላ ቀር መሣሪያዎች በማንገብ፣ ጦር በመያዝና ጩቤ በመታጠቅ ነበር። እንዲሁም አንድ መሣሪያ ለሦስት ተጻጅቦ በመያዝ የጠላት ወታደርን ገድሎ መሣሪያውን በመቀማት ነበር።

የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች ማኅበር ጥር 2 ቀን 1931 ዓ.ም ተገለጸ፣ አንቂፊኝ በተባለ ቦታ ተመሰረተ። ሌሎች ደግሞ አንቀላፊት በምትባል ሌላ ሥፍራ ላይ እኛም ቀደም ብለን ጥቅምት 23 ቀን ማኅበር አቁቁመን ነበር የሚል ድምፅ በየካቲት ወር ቢያሰሙም፣ ጉዳዩ ለታሪክ ቅሚያ ተብሎ የተቀነባበረ ተንኮል እንጂ እውነተኛ መሠረት ስላልነበረው አልሠራም።

ጥር 2 ቀን የተመሠረተው ትክክለኛው የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች ማኅበር የተመሠረተበት

1ኛ ዓላማ፦

1.1 አርበኞች እርስበርሳቸው እየተረዳዱና እየተደጋገፉ፣ በየቆሙበት ግንባር የወራሪ ጣልያንን ጦር በአቅማቸው ሁሉ እንዲክላከሉ።

1.2 በአንዱ ላይ ጥቃት ቢደርስ በጋራ እንዲከላከሉ።

1.3 የሚገኙ ማስረጃዎችን እና መረጃዎችን በምስጢር እንዲላላኩ፣ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ

2ኛ ዓላማ፦

2.1 አርበኞችን እንዲመሩ በአርበኞች ስምምነት ትንሽ ቀደም ሲል የነገሡት መልአከ ፀሐይ ኢያሱ ምኒልክ የተባሉት የ18 ዓመቱ ወጣት ንጉሥ፣ መስከረም 19 ቀን 1931 ዓ.ም ድንገተኛና አስገራሚ በሆነ ሁኔታ ስለሞቱ አርበኛው እንዳይላላ ስጋት ስለተፈጠረ፣

2.2 የንጉሠ ነገሥት መልአከ ፀሐይን ሞት ተከትሎ፣ መሴ ቀስተኛ በተባለ አንድ የስዊስ ተወላጅ በሆነ ሰው በተቀሰቀሰ ዕርቅ ምክንያት፣ በጎንደር ወር 1931 ዓ.ም ሮርች በተባለ ቦታ የዕርቅ ነጥቦች በመቅረባቸው ምክንያት፣ ብዙ አርበኞች ወደ ግል ኑሯቸው በመመለሳቸው የአርበኛው ክንድ እንዳይላላ ስላሰጋ ነበር ማኅበሩ የተመሠረተው። ዕርቁም ሚያዝያ 7 ቀን 1931 ዓ.ም ፈረሰ። አርበኞችም ትግላቸውን በማሕበራቸው አማካኝነት አጠናክረው ቀጠሉ።

2.3 በአንዳንድ የአርበኛ መሪዎች መካከል በተነሱ ጥቃቅን ግጭቶች ምክንያት ጉዳት ስለደረሱ። ለምሳሌም፦ ፊታውራሪ ገበቅአርጌ እና ፊታውራሪ ሞገሤ መኩሪያ እርስበርሳቸው ተዋግተው ስለሞቱና ሠራዊታቸውም ስለተፈታ።

በፊታውራሪ ወልደሃዲቅ ዘውዴና በፊታውራሪ ደባልቄ ተክሌ የሚመሩ አርበኞች የቀረበላቸውን ዕርቅ ሊቀበሉ ከቻሉበት ቅድመ ሁኔታ ዋና ዋናዎቹ፦

3.1 ሞቃዲሾ፣ ደናኔ /ሶማሊያ ግዛት ውስጥ/ እንዲሁም በኤርትራ ናኩራ ወደ ተሰኙ ቦታዎች ተወስደው የታሰሩ ኢትዮጵያውያን ሁሉ እንዲፈቱ፣

3.2 ኢትዮጵያዊ ያለ ፍርድ እንዳይገደል፣

3.3 የኢትዮጵያውያን ጉዳይ በኢትዮጵያውያን ዳኞች ብቻ እንዲታይ፣

3.4 በምግብ እጦት ሲጎላቆል ለነበረው አርበኛ ጣልያን ልብስ እና ምግብ እንዲሰጥ የሚሉ ነበሩ።

በተለይ የታሰሩ ኢትዮጵያውያን እንዲፈቱ ተብሎ በተጠቀሰው ቅድመ ሁኔታ መሠረት ብዙዎች ሊፈቱ በቅተዋል።

አባሪ 3
የሙሶሊኒ አጭር የሕይወት ታሪክ

ቤኒቶ ሙሶሊኒ በኢትዮጵያም፣ በኢጣልያም ታሪክ ውስጥ ስመ ሲጠቀስ ይኖራል። በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የሚጠቀሰው በጨካኝነቱ ነው። በኢጣልያ ታሪክ ውስጥ ግን ኢትዮጵያን የኢጣልያ ቅኝ ግዛት ለማድረግ በአካሄደው የጦር ሥራና በፋሽስት ፓርቲ መሥራችነቱ ይታወሣል። መጥፎ ዕድሉ ሆኖ ሁለቱም በእሱ በራሱ ግብር ተበላሽበት።

ሙሶሊኒ አሌዘንድሮ ሙሶሊኒና ወይዘሮ ሮዛ ከተባሉ ባልና ሚስት ሐምሌ 22 ቀን 1875 ዓ.ም /ጁላይ 29 ቀን 1883/ ሻራኖ ዲ ኮስታ በተባለች ቦታ ተወለደ። ስሙም ቤኒቶ ተባለ። ዕድሜው ለትምህርት ሲደርስ በእናቱ ብርታት ትምህርት ቤት ገባ። በትምህርቱ ስልቹ ይሁን እንጂ ጉበዝ ነበር። ሩየንዛ በተባለችው ከተማ ወደ አለው ሣልሲያን መነኮሳት ወደሚያስተዳድሩት ትምህርት ቤት እንዲገባ የተደረገው፣ ጠባዩን ለማረም ይችላሉ በሚል አስተያየት ጭምር ነበር። ነገር ግን አልቻሉም። አባቱ አሌዛንድሮ የፖለቲካ ጠረን የሸተተው ነበርና፣ ልጁን ቤኒቶን በአረፍት ጊዜው ሮማኛ ከተባለው ከተማ ወስዶ የሥራ አጦችን ብዛት ስለአሳየው ቤኒቶ ልቡ ተነካ። የመምህርነት ትምህርት ተከታትሎ ቢመረቅም ይህ ስሜቱ አልቀዘቅዝ አለ።

የቤኒቶ ሙሶሊኒ የፖለቲካ ስሜት ዳበረ። ከትምህርት ቤት ወደ ሕዝብ ተሸጋገረ። በተለይም በየካቲት 1894 ዓ.ም /በፈብሪዋሪ 1902/ ኢሚልያ በተባለ አካባቢ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህርነት ከተቀጠረ በኋላ በሃይማኖትና በማኅበራዊ ጉዳይ ጭምር አተኮረ። በአደባባይ ይናገርና ከተቃዋሚዎች ጋር ይከራከር ጀመር። "...ጋሪባልዲ በሚያርፍባት ኢጣልያ ውስጥ ክመኖር ሞት ይሻላል..." አለ። ይህ ቃል ሠራተኞችን ቀሰቀሰ። ባለሥልጣኖቹን አስቆጣ። እሱም ከአስተማሪነት ሥራው ተባረረ።

በነሐሴ ወር 1895 ዓ.ም /1903/ ወደ ስዊስ አገር ተሰደደ። የተሰደደበትን ምክንያት ሲያስረዳ ደግሞ "...ኢጣልያን በደም ማጥለቅለቅ ከሚፈልጉ ሰዎች ጋር መተባበር አልፈልግም..." አለ። ስደት የሄደው ከብሔራዊ ውትድርና ሸሽቶ ነበርና። በተሰደደበትም አገር ከፖለቲካ ሥራ አልታገስ ስለአለ ተደጋግሞ ታሠረ። ሲያቅታቸው ስዊሶች ከአገራቸው አስወጥተው አባረሩት።

ወደ ሀገሩ ተመልሶ ካሪን በተባለ ቦታ እንደገና በአስተማሪነት ሥራ በ1897 ዓ.ም /1904/ በመስከረም ወር ተቀጠረ። ለአስተማሪነት ሥራ አክብሮትና አለመሰልቸትና በደመወዝ ማነስ፣ ሲጠጣና ሲያመነዝር ቂጥኝ ስለያዘው ራሱን ለመግደል እስከመሞከር ድረስ ተበሳጨ። በዘሉፕ ዩኒቨርስቲ አማካይነት ለሁለት መቶ ያህል ሰዎች የተሰጠውን ፈተና ስለአለፈ፣ ኦኒልያ በተባለ የግል ትምህርት ቤት በአስተማሪነት በየካቲት 1900 ዓ.ም /1908/

ተቀጠረ። በዚህ ሥራው ላይ እንዳለ ሁለት ጊዜ ታሠረ። አንዱ እሥራት የ3 ወር ነበር። ገበሬዎችን ከዘረፉ ሰዎች ጋር በመደገፍና አንዱን አሳሳሪ ሰው በማስፈራራት ነው። ሁለተኛው እሥራት ግን ባልተፈቀደ ጉባዔ ላይ ንግግር በማድረጉ ሲሆን፣ የተፈረደበትን 10 ሊሬ አልከፍልም ብሎ በፈቃዱ ለእሥር ቀን ነበር። እንደዚህ በመሳሰሉ የአካባቢ ጉዳዮች ላይ ተንጠልጥሎ ቡቡሔራዊ ጉዳይ ላይ አስክ ማተኮር ደረሰ።

በመጋቢት 1904 ዓ.ም /1912/ ሣልሣዊ ኢማኑኤልን ለመግደል የተደረገውን ሙከራ በመቃወም የኢጣልያ ብሔራዊ ምክር ቤት ተወካዮች ሲልክ፣ ሦስት የሶሺያሊስቱ ፓርቲ አባላት አብረው ወደ ቤተ መንግሥት ሄዱ። ሙሶሊኒ ተቃውሞ አስነሰቶ አባሪ የነበሩትን ሦስት የሶሺያሊስት ፓርቲ አባላት ከፓርቲው እንዲባረሩ አደረጉ። በውቅቱ የነበረው መንግሥት ትርኤስት ለአውስትሪያ ትሰጥ ያለውን ሃሳብ "የሀገር ሽያጭ" ብሎ ተቃወመው። የራሱን ፓርቲ ማቋቋም ያዘ። ስሙንም "ፋሺ" አለው። ይህ ቃል ጊዜያዊ ትርጉም ቡድን የሚል ነበር። ነገር ግን እየዋለ እያደረ ሮማውያን ጥንት በጦር ሜዳ ላይ ይይዙት በነበረ ዱላ ተመሰለ። ተከታዮችም ፋሺስት ተባሉ። ርእዮተ ዓለሙም ፋሽዝም ሆነ። በዚህ ተንቀሳቃሽ የፋሽስት ፓርቲ ተቋቋመ። በዚህ የስደትና የትግል ጊዜው ፈረንሣይኛና ጀርመንኛ ቋንቋ አጠና። እንግሊዝኛንም በመጠኑ።

የትግሉ ጽናት፣ የገንዘብ ማጣትም፣ ስደትም፣ የማስተማር ሥራ መሰልቸትም፣ መታሠር መፈታትም፣ ብቸኝነትም ተደማምረው ሚስት የማግባት ፍላጉት አሳደሩበት። ከብዙ ልጃገረዶች መካከል ወይዘሪት ራሼልን አጨ። ለመዳት፣ ወደዳት። ነገር ግን የእሱ አባትና የእርስዋ እናት ስለተቃወሙ፣ በጋብቻው አንስማማም ስለአሉ እንደገና ራሱን ለመግደል ሞከረ። ተፈቀደላቸው ተጋቡ። ልጆች ተወለዱ። ቤት ንብረት ሞቀ። ራሼል መልካም ሚስት ደግ እናት ሆነች። እሱ ግን ከሌሎች ጋለሞቶች ጋር ቀጠለ። ከብዙዎቹም እንድዋ ክለሬት ፔታኪ ሕይወትዋን እስከ መስጠት ድረስ ታማኝ ሆነችው።

መስከረም 17 ቀን 1904 ዓ.ም /1911/ ባደረገው ንግግር "...ኢጣልያ መዋጋት የማይችሉ የፈሪዎች አገር ናት..." ስለአለ፣ ክሱ ሮም በማዕከላዊ ፍርድ ቤት እንዲታይ ተደረገ። እሱም "...በነፃ ብትሰቁኝ ሥራዬን እቀጥላለሁ፣ ብትቀጡኝ ደግሞ ክብር ይሆንልኛል..." በማለት መከራከሩን ትቶ የፍርድ ቤቱን ውሣኔ እንደሚቀበል አስታወቀ። ዳኞቹም በቀረበበት የበጥባጭነት ወንጀል የአንድ ዓመት እሥራት ፈረዱበት፣ ነገር ግን በዚያው ዓመት በየካቲት ወር ተፈታ። የሶሺያሊስት አብዮት መሪ እንደሆነ ያህል ተቆጠረለት። "አቫንቲ" ማለትም ወደፊት የተባለው ጋዜጣ አዘጋጅ ሆነ። የፓርቲውንም የጋዜጣውንም ሥራ በትጋት አካሄደ። ደመወዙም በወር 500 ሌሬ ሆነለት።

በዚያ ዘመን ስተደረገው የምክር ቤት ምርጫ ለውድድር ቀረበ። ነገር ግን ከአንድ ቀን በስተቀር ስለራሱ አልተናገረም። ጓደኞቹን ረዳ። ሃምሣ ሦስት ባልደረቦቹ ሲመረጡ እሱ ሳይመረጥ ቀረ። በውጭ ሆኜ ብረዳ ይሻላል አለ። መቼም ሥልጣን አላገኝ ብሎ ነው። እንደ አለውም ማበጣበጡን ቀጠለ። እሱ ሥልጣን ካልያዘ ኢጣልያ ሰላም እንደማታገኝ እስኪታወቅለት ድረስ።

አቫንቲ በተባለው ጋዜጣ የጥቅምት 8 ቀን 1906/18 አክቶበር 1914/ እትም ሙሶሊኒ ለፓርቲው ተከታዮች ክባድ ማስጠንቀቂያ ሰጠ። የፓርቲው ፖሊሲ ምኞት የሚሰጥና ትዕግስትን እንጂ ማሰብን የማይጠይቅ እንደሆነ ገለጸ። መመሪያን ለማክበር በሚደረግ መከራ የሶሺያሊዝም መንፈስ ከመጥፋት እንደደረሰ አስጠነቀቀ። የሶሺያሊስት ፓርቲ ምክር ቤት በጉባዔ ቢጠይቀው መልስ አልሰጥ ስለአለ፣ ከአቫንቲ ጋዜጣ አዘጋጅነት ሥራው ተባረረ። ደመወዙን እንዲወስድ ቢጠየቅ እምቢ አለ።

ጎዳር 6 ቀን 1907 ዓ.ም /ኖቬምበር 1914/ ኢል ፖፖሉ ደ ኢታልያ፣ ማለትም የኢጣልያ ሕዝብ የሚል አዲስ ጋዜጣ አወጣ። በመጀመሪያ አትሙ "...መጠበቅ መዘግየትን ያስከትላል..." በማለት ፈጣን እርምጃ መውሰድ እንደሚያስፈልግ አስረዳ። አዲሱ ጋዜጣ በሕዝብ ዘንድ ተወዳጅነት እያገኘ ሄደ። በቀን እስከ 25,000 ቅጂ ይሸጥ ጀመር። የሶሺያሊስት ፓርቲ ሙሶሊኒ ጋዜጣውን ከውጭ አገር ቦሚገኝ ዕርዳታ ለማካሄዱ ማስረጃ ለማግኘት ልዩ ጥናት ቢያደርግም ማስረጃ ሳያገኝ ቀረ። ጎዳር 16 ቀን 1907 ዓ.ም /ኖቬምበር 25 ቀን 1914/ የሶሺያሊስት ፓርቲ ባደረገው ጉባዔ ሥራውን ማስረዳት አቅቶት ስብሰባው ከተደረገበት ትያትር ቤት ሸሽቶ ወጣ። ብቻውን ቀረ። ሰው ከዳው። እሱ ግን ተስፋ አልቆረጠም "...በዕርና ሽጉጥ በእጄ ላይ እስከአለ ድረስ ማንንም አልፈራም" አለ።

ቀደም ብሎ የጀመረውን አዲስ ፓርቲ የማቋቋም ሥራ ቀጠለ። ስሙንም ፋሺ ደ አስዮን ሬቮሊሲዮናርያ አሰው። በግንቦት 1907/1915/ ዓ.ም ኢጣልያ ከመጀመሪያው የዓለም ጦርነት ከምዕራባውያን ጐን በመሆን ገበታ ነበር። መሶሊኒ በሮምና ሚላን ከተሞች በየምክንያቱ ሰልፍ እያካሄደ አስቸግሮ ነበርና ለሁለት ጊዜ ለብሔራዊ ውትድርና ተጠራ። ማምለጥ ስለአልቻለ ደስተኛ መስሎ ገባ። የአሥር አለቅነት ማዕረግ አገኘ። የካቲት 15 ቀን 1909 ዓ.ም /ፌብሪዋሪ 23 ቀን 1917/ ከአንድ የጦር ልምምድ ላይ አንድ የእጅ ቦምብ ፈንድቶ ሌሎች አምስት ወታደሮች ሲሞቱ፣ እሱ አርባ አራት ቦታ ቆስሎ ዳነ። ሞቶ በሆነ ኖሮ ምንኛ ደግ ነበር! እሱ ግን "ወደ ትሪኤስት የሚወስደውን መንገድ በደሜ በማቅላቴ እደሰታለሁ" አለ። በዚህም ተጨማሪ ሞገስ አገኘ።

ጦርነቱ በሙሶሊኒ ላይ ሌላ ችግር ሳያስከትል አለቀ። ነገር ግን ኢጣልያ በጦርነቱ በቂ ተሳትፎ ስለአደረገች፣ በቪርሳይ ውል የፈለገቸውን በከፊል እንጂ አምዋልታ ሳታገኝ ቀረች። ዳልማትያና ፍዩም የተባሉትን

አውራጃዎች ልታገኝ አልቻለችም። የሙሶሊኒ ትንቢት ደረሰ። በጦርነቱ የሞቱት 652,000 ወታደሮች ደም በከንቱ እንደ ፈሰሰ ቆጠረው። ግንኙነቱንም ከጦርነቱ ከተመለሱ ወታደሮች ጋር አደረገ።

በኢጣልያ መንግሥት በኩል የነበረው ሁኔታ ለሙሶሊኒ ብጥብጥ ማካሄጃ ተስማሚ ነበር። በባለሥልጣኖች ዘንድ ጉቦኝነት፣ መደለል፣ ጥቅም ማጋበስ በዝቶ ነበር። ከወንጀል ብዛት የተነሣ በ1916 ዓ.ም ብቻ በገንዘብ ወይም በእሥራት የተቀጡ ሰዎች ብዛት እስከ 362,000 ደረሰ። ከጦር ግንባር ተመልሰው ሥራ የአጡ ሰዎች ቁጥር ከሚሊዮን አለፈ። ሙሶሊኒ እነዚህን ሁኔታዎች ምክንያት በማድረግ፣ መንግሥቱን በሕዝብ ዘንድ ለማስጠላት ታላቅ የፖለቲካ ዘመቻ አካሄደ። በሠራተኞች ዘንድ ድጋፍ አገኘ።

በአንድ ወገን መንግሥቱን እያዳከመ፣ በሌላ ወገን የራሱን የፖለቲካ ቡድን አጠናከረ። ለመጋቢት 10 ቀን 1911/1919/ ዓ.ም ጠቅላላ ስብሰባ ጠራ። ለስብሰባው የተጋበዙት የማንኛውም ፓርቲ አባል የሆኑ ሁሉ ነበሩ። የስብሰባው ዓላማ ኢጣልያን ሊያጠፋአት በመንቀሳቀስ ከአሉት ኃያላን ለማዳን እንደሆነ በጋዜጣ ተገለጸ። ስብሰባው በሚላን ከተማ በአንድ የንግድ ማኅበር መሥሪያ ቤት ክላይ በተጠቀሰው ቀን ተደረገ። በጠቅላላው 119 ሰዎች በስብሰባው ላይ ተገኙ። ከተገኙት ሰዎች አማጽያን ሶሺያሊስቶች፣ በጥባጮች፣ የሪፐብሊክ መንግሥት ማቋቋም የሚፈልጉ፣ የቀድሞ ወታደሮችና ሌሎችም ነበሩባቸው። ነገር ግን ታዋቂ ሰዎች አልነበሩም። ሙሶሊኒ ቀደም ብሎ ያዘጋጀው ቻርተር ይዘት ግልጽ አልነበረም። ዝልጉስጉስ ሆነ። ቢሆንም ያለ ተቃውሞ ጸደቀ። ሙሶሊኒ ፈነደቀ። ዋናው ነገር የፋሽስት ፓርቲ ሕልውና ማግኘቱ ነበር።

የፋሽስት ፓርቲ በፍጥነት ተስፋፋ። በአንድ ወር ውስጥ 82 ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች በኢጣልያ ዋና ዋና ከተሞች ተቋቋመ። በዚሁ ወቅት 14,000 አባላት ተመዘገቡ። በዚሁ ወቅት 107 ብጥብጦች ተካሄዱ። አብዛኞቹ የሶሺያሊስት ፓርቲን በመቃወም ነበር። ሚያዝያ 7 ቀን 1911 /1919/ ዓ.ም አቫንቲ የሚባለው የሶሺያሊስት ጋዜጣ መሥሪያ ቤት ተቃጠለ። ሠራተኞቹ ኢል ፖፖሉ የሚባለውን የፋሽስት ፓርቲ ጋዜጣ መሥሪያ ቤት ለማለቃጠል ተነሳስተዋል ተብሎ መሶሊኒ ገነነ። ዕርዳታ እንደ ውሃ ፈሰሰለት። ብጥብጡ በየመልኩ ቀጠለ። የፋሽስት ፓርቲ ተጠናከረ። በመላ ሀገሪቱ 149 ቅርንጫፎች አቋቋሞ 45,000 አባላት መዘገበ። በሥልጣን ላይ የነበረው ዩኒቲ መንግሥት ሥራውን ለቅቆ አዲስ ምርጫ ጠራ።

በጎዳር 1912 ዓ.ም /1919/ በተደረገው የብሔራዊ ምክር ቤት ምርጫ የፋሽስት አባላት መመረጣቸውን ሙሶሊኒ ተቃወመ። ምርጫው ለሥልጣን እንዲያበቃው አውቆ "በውስጡ ጥቂት ወንበሮች ከመያዝ ይልቅ፣ በምክር ቤቱ ዙሪያ ብዙ ሕዝብ አለልኝ ማንጫጫት የበለጠ ተደማጭነትን ያስገኛል" አለ። ተቃዋሚዎቹ አልቀበል አሉት። በመጨረሻ እሱም ራሱ ቡሚላን ከተማ

ለውድድር ተመዘገበ። ነገር ግን አንድም የፋሽስት አባል ሳይመረጥ ቀረ። ሙሶሊኒ የፈራው ውርደት ደረሰ። በዚህ ላይ ደግሞ ፋሽዝምን ይደግፉ የነበሩት ጳጳስ ሞተው የሚቃወሙት ሌላ ጳጳስ ተሾሙ። በሙሶሊኒና በባልደረባቹ ላይ የፖለቲካ ተፅዕኖ ተደረገባቸው። ሙሶሊኒ ግን ተስፋ አልቆረጠም። ከቶውንም በረታ። መላዋን ኢጣልያ በብጥብጥ አጥለቀለቃት። በ1912 ዓ.ም /1921/ ብቻ 1881 ብጥብጥ ተመዘገበ። ኢጣልያ ከማጥ ውስጥ ገባች። የሌሬ ዋጋ ቀነሰ። ኢንዱስትሪዎች በከሰል እጥረት ቆሙ። ጸበ ተወደደ።

የሶሺያሊስት ፓርቲ በጥር 1913 ዓ.ም /1921/ ሊቦርኖ በተባለች ከተማ ተሰበሰበ። ፓርቲው ወደ ኮሚኒስት ፓርቲነት እንዲለወጥ ሃሳብ ቀረበ። በአክራሪዎችና በለዘብተኞች መካከል አንድ ሣምንት ሙሉ ክርክር ከተካሄደ በኋላ በአሣር በመከራ አክራሪዎች ተረቱ። ነገር ግን ጦሱ ሳይበርድ ቀረ። ራሺያ ይህንን ሁኔታ ለመለወጥ በሚቀጥለው ሦስት ወር ውስጥ ስድሣ ሚሊዮን ሊሬ ኢጣልያ ውስጥ አፍስሳ ምንም ውጤት ሳታገኝ ቀረች። ካፒታሊስቶች ለሕልውናቸው ሲሉ የፋሽስት ፓርቲን ደገፉ። የፋሽስት ፓርቲ ናረ። አንድ መቶ ሺህ አባላት ከሶሺያሊስት ፓርቲ ዞሩ።

በሶሺያሊስት ፓርቲ ውስጥ ልዩነት እንደ ተፈጠረ ሲያይ፣ ሙሶሊኒ በሣልሣዊ ኢማኑኤል እናት አማካይነት ከንጉሡ ጋር የምሥጢር ግንኙነት ፈጠረ። ንጉሡን ላይነካ፣ ንጉሡም ሊደግፉት ተስማሙ። በአንድ ወገን ከንጉሡ ጋር ሲስማማ፣ በሌላ ወገን ተቀናቃኙን የሶሺያሊስት ፓርቲን ማውደሙን አጣደፈ። እስከ ግንቦት ወር ድረስ 120 የሠራተኛ ጽሕፈት ቤቶች ተቃጠሉ። ከ200 በላይ የሶሻሊስት ፓርቲ መሰብሰቢያ ቦታዎች ተመዘበሩ። በድምሩ 261 ሰዎች ሞቱ። ሌሎች 1267 ቆሰሉ። ጃዮሊቲ የተባለው ጠቅላይ ሚኒስትር አዲስ ምርጫ እንዲደረግ አዘዙ።

ግንቦት 7 ቀን 1913 ዓ.ም /1921/ በተደረገው ምርጫ ከ8535 ወንበሮች 35 ይዞ ምክር ቤት ገባ። ሙሶሊንም ራሱ ከሚላን ከተማ ተመረጠ። ቀድሞ ይቃወመው የነበረውን የካቶሊክ እምነት አክበረው። ከዚያም አልፎ "የካቶሊክ ቤተክርስቲያን ለኢጣልያኖች ጥቅምና ክብር የቆመች ናት" በማለት በምክር ቤቱ ውስጥ ተናገረ። ከንጉሡም ከጳጳሱም ተስማማ ማለት ነው።

በሰኔ ወር አዲሱ መንግሥት ክርክር ሲደረግባት የቆየችውን ደልማጥያ የተባለችውን የኢጣልያ ግዛት ለዩጐዝላቪያ ለቀቀ። ለሙሶሊኒ ተመቸው። ሀገሪቱን በብጥብጥ አቀጣጠላት። ንጉሡ የምክር ቤቱን አባላት አነጋግሮ፣ ቦናሚ የተባለው ሰው መንግሥት እንዲያቋቁም አዘዘው። ነገር ግን ለሙሶሊኒ በአዲሱ መንግሥት ውስጥ ቦታ ሳይሰጠው ቀረ። ደጋፊዎቹ ጥቂት እሱም ለመንግሥት ሥራ ባይተዋር ነበር። እሱ ግን ማበጣበጡን ቀጠለ። በሐምሌ ወር ሚርዛና በተባለች መንደር ብጥብጥ ተነስቶ ብዙ የሶሻሊስት

ፓርቲ ደጋፊዎች በፖሊስ ተገደሉ። ከፋሽስት ፓርቲ ግን አንድም ሳይሞት ስለቀረ፣ በሁለቱ ፓርቲዎች መካከል የነበረው ተቃርኖ ይበልጡን ተጋጋመ። ሙሶሊኒ ራሱ ተቃውሞ ተቀሰቀሰበት። ቢሆንም ተስፋ አልቆረጠም፤ ማበጣበጡን ቀጠለ። ብጥብጥ አካሄያጅ ቡድን አቋቋመ። ጥቁር ሸሚዝ አስበሳቸው። ሶሺያሊስቶችን እንዲያጠቁ አደረገ። የፋሽስት ፓርቲ በትረ መንግሥት ለመያዝ ብቁ መሆኑን በይፋ አስታወቀ። "...ቢወድዱ ይስጡን፣ ያለዚያም እኛው ራሳችን እንወስደዋለን" አለ። በምሥጢር ደግሞ ከንጉሡ እናት ጋር ጀምሮት የነበረውን ግንኙነት አጠበቀ። አዲስ በተቋቋመው መንግሥት ውስጥ የሚሪን፣ የገንዘብ፣ የእርሻና የቅኝ ግዛት ሚኒስትርነት ሥራዎችና፣ እንደዚሁም ሌሎች አራት የምክትል ሚኒስትርነት ቦታዎች ለፋሽስት ፓርቲ ተመደቡ። እሱ ግን አልቀበልም አለ። ንጉሡ ቢያስፈልጉት ጠፋ። በብዙ ልምምጥ ሲሰሰት የራሱን መንግሥት ከማቋቋም በስተቀር፣ በሌላ ፓርቲ መንግሥት ውስጥ ለማሳተፍ አለመፈለጉን ይፋ አደረገ። ብጥብጡ ቀጠለ። የአደጋ መከላከያ አዋጅ ማውጣት አስፈለገ። ነገር ግን ንጉሡ አዋጁን አልፈርምም አሉ። ዘውዱን ለማዳን ሙሶሊኒን ጠቅላይ ሚኒስትር አድርጉ መሾም ግድ ሆነበት። ሌላ አማራጭ ጠፋ። ሙሶሊኒ ሮም ከተማ መጥቶ መንግሥት እንዲያቋቁም የተፈቀደለት መሆኑን የሚያስታውቅ መግለጫ በንጉሡ ቃል ወጣ። ጥቅምት 20 ቀን 1915/1922/ ዓ.ም ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነ።

ለምክር ቤት የሥራ ፕሮግራም አቀረበ። የውጭ ጉዳይን በተመለከተ ኢጣልያ የገባችባቸውን ዓለም አቀፍ ግዴታዎች እንደሚያከብር አስታወቀ። የሀገር ውስጥ ጉዳይን በተመለከተ ሕዝብ የሚፈልገውን አስተዳደር እንደሚመሠርት፣ ሕግ እንደሚያከብር፣ ጸጥታና መረጋጋትን እንደሚያሰፍን፣ የልማት ሥራዎችን እንደሚያጠናክር ቃል ገባ። ምክር ቤቱም የሥራ ፕሮግራሙን አጸደቀለት። የሕዝብ አክብሮት አገኘ። ሌትና በተባለው ተራራ ላይ እሳተ ገሞራ ሊፈነዳ እሳት መርጨት ከጀመረ በኋላ፣ ሙሶሊኒ ጠቅላይ ሚኒስትር ሲሆን ተመልሶ መቀዝቀዙ ጭምር በምሥራች መልክ በጋዜጣ እስከ መውጣት ደረሰ።

አቅዋሙን ለማጠናከር በወሰደው እርምጃ የሮምን ከተማ ለማደስና ለማሰፋፋት ጥረት አደረገ። ዋናው ጉዳይ ከተማይቱን የማጽዳቱ ሥራ ሆነ። ገጠሩን እየተዘዋወረ ችግሮችን ለመረዳት ሞከረ። ዋናው ጉዳይ መልካም ወሬ የመንዛቱ ጉዳይ ነው። የፖለቲካ ኃይልን ከሕዝብ ፍላጐት ጋር ለማጣጣም ከጀለ። ነገር ግን አንድ ችግር ሲቃለል ሌላ እየተተካ አስቸገረ። ጉዳዮችን እያጠና ውሣኔ የሚሰጥ የፋሽስት ምክር ቤት አቋቋመ። ሥልጣን ሰጠው። እሱ ራሱ ሰብሳቢ ሆነ። የፋሽስት ፓርቲ ያሠለጠነና ያስታጠቀው አስካድርሲት ለተባለው ሠራዊት ሕጋዊ አቅዋም ሰጠው። ለደሀንነቱ ሥራ ኃላፊ አደረገው። ቀጥሎ የፋሽስት ፓርቲ አባል ያልሆኑትን ሚኒስትሮች

አንድ በአንድ ከሥልጣን አባረረ። በዚህ ሁሉ ሕዝብ ተባብረው። የነበሩት ጥቃቅን ተቃውሞዎች ሂደቱን የማገድ አቅም አሳጉኑም። ጉዞው ቀጠለ።

ነገር በአንዲህ እንዳለ በልዑል አልጋ ወራሽ ራስ ተፈሪ መኮንን የተመራ የኢትዮጵያ ልዑካን ቡድን ሮም ገባ። በሮም ቆይታውም በአዲሱ አምባ ገነን ከዱቼ ሙሶሊኒ ተገናኝቶ ተነጋገረ። በንግግሩ ላይ በኢትዮጵያ በኩል ስለ አስብ ጉዳይ ተነስቶ በዲፕሎማቲክ መሥመር ለአዲስ አበባ መልሶ እንደሚሰጥ ከኢጣልያ በኩል ቃል ተገባ። በተግባር እንደታየው የኢትዮጵያን ዓለም ማህበር መግባት ኢጣልያ ደገፈች።[1]

ቀጣዩ ትንቅንቅ ሕዝብ ከመረጠው ምክር ቤት ጋር ሆነ። በ1916 /1924/ ዓ.ም አዲስ የምርጫ ሕግ አወጣ። ሕጉም ቀደም ብሎ በተደረገው ምርጫ ከምክር ቤቱ ወንበሮች 6.5% ብቻ የነበረውን የፋሽስት ፓርቲ፣ በቀጣይ ምርጫ ወደ 66.7% ከፍ ከሚያደርግ ነበር። በአዲሱ ሕግ መሠረት በዚያው ዓመት መጋቢት 28 /ኤፕሪል 6/ አዲስ ምርጫ ተካሄደ። በምርጫው የፋሽስት ፓርቲ ከምክር ቤቱ ወንበሮች 65% ያዘ። የተፈለገው ነገር ተገኘ።

ምክር ቤቱ ሥራውን ቀጠለ። በዚያው ዓመት ግንቦት 22 ቀን ምክር ቤቱ በአደረገው ስብሰባ ላይ ጊያክሞ ማቲዮቲ የተባለው የሶሺያሊስት ፓርቲ አባል የሙሶሊኒን አሠራር ነቀፈ። የምክር ቤቱን አባላት እርስ በርሳቸው ያደባደበ ክርክር ተካሄደ። ከሙሶሊኒ ዛቻ ተሠንዘርበት ነበርና ማቲዮቲ ከምክር ቤት እንደወጣ ለጋዜጠኞች በሰጠው ቃል፣ ዛቻውን በተመለከተ "...አትስጉ..." ለሙሶሊኒ ዛቻ ቃል እንጂ፣ እንዳች አይደለም... አለ። ነገር ግን ለኔ 3 ቀን የደረሰበት ጠፋ። በማቲዮቲ መጥፋት በተነሳው የርስበርስ ጭቅጭቅ ደቦ የሕዝብ ደህንነት ሥራውን ለቀቀ። በዚህም ጠቡ አልበርድ አለ። በጋዜጣ ለተጠቀጣጠለው ውዝግብ ሙሶሊኒ ኃላፊነቱን ወሰደ። "እኔ ለጋዜጠኞች የመጻፍ ሥልጣን በመስጠቴ ነው" ቢልም ውዝግቡ አልበርድ አለ። የመንግሥት ግልበጣ አሰጋ። ለዚህም ሙሶሊኒ "ንጉሡ ከጠየቁኝ ሥልጣኔን በፈቃደኛነት እለቃለሁ" አለ። ብዙ የፋሽስት ፓርቲ ደጋፊዎች ደነገጡ። ነገር ግን ንጉሡ ሥልጣን ልቀቅ ብሎ ሙሶሊኒን ለመጠየቅ አልደፈረም። ሙሶሊኒም ልምምጡን በምሥጢር ቀጠለ።

ተቃዋሚዎቹ ሌላ መገልገያ ሲያጡ ወደ ግድያ ዞሩ። ሙሶሊኒን ለመግደል አራት ሙከራ አደረጉ። አንዱም አልተሳካ። መጋቢት 29 ቀን 1918 ፆሚያዝያ 7 ቀን 1926/ ዓ.ም አንዲት እንግሊዛዊት ሴት በሽጉጥ ጥይት አፍንጫውን ጨረፈችው። ይህ ሁኔታ ሥልጣኑን ለማጠናከር ይበልጡኑ ረዳው። በግንቦት 1919 /1927/ ዓ.ም የፖለቲካ እሥረኞች ብዛት 698 ደረሰ። በ1920/1928/ ዓ.ም የወጡት ድርጅቶች ፈርሰው የፋሽስት ዓላማዎችን ሊያራምዱ በሚችሉበት ሁኔታ ተሻሽለው ተቋቋመ። በዚህ ዓይነት መቀጠሉን ሲገነዘብ ምክር ቤቱ ሥልጣኑን ለፋሽስት ፓርቲ ለቀቀ። ድምድሙም በሕግ መምሪያ 216 ለ15፣ በሕግ መወሰኛ ደግሞ 161 ለ46

ነበር። በዚህ ውሣኔ መሰረት ሥልጣን ወደፋሽስት ምክር ቤት ተዛወረ። ሕዝብ የመረጠው ምክር ቤት ኅዳር 29 ቀን 1921 ዓ.ም /ዲሴምበር 8 ቀን 1928/ ከነጭራሹ ተዘጋ። ሂደቱን የንጉሡም ተቃውሞ ሊያግደው ሳይችል ቀርቶ ሙሶሊኒ ባለ ሙሉ ሥልጣን ሆነ። ከንቀቱ ጽንሰት የተነሣ ከንጉሡ ጋር ያለውን የሥልጣን ግንኙነት "በሁለት አልጋ የሚካሄድ ጋብቻ" አለው። ዱቼ የተባለው የክብር ስም ዋና መጠሪያው ሆነ።

ቀጣዩ ትግል ደግሞ ከሮም ካቶሊክ ቤተክህነት ጋር ሆነ። ሙሶሊኒ ስለሃይማኖት ደንታ አልነበረውም። የፖለቲካ ድጋፍ ለማግኘት ሲል ብቻ ከቤተክህነቱ ጋር የካቲት 4 ቀን 1921 ዓ.ም /ፌብሪዋሪ 11 ቀን 1929/ አንድ ስምምነት እሱ ራሱ ተፈራረመ። ውሉን የተፈራረመበትን የወርቅ ብዕር ከተሸለመ በኋላ ባደረገው ንግግር፣ ከእንግዲህ ቤተክርስቲያኒቱን እንደሚደግፍ አስታወቀ። ሁኔታው በሕዝብ ስሜት ላይ ተፅዕኖ አሳድሮ ስለነበር እንደ እፎይታ ተቆጠረ። ጳጳሱም "እግዚአብሔርን ለኢጣልያ፣ ኢጣልያንንም ለእግዚአብሔር ሰጠን" አሉ። ጳጳሱ እንዲህ ያሉት ኢጣልያን ሰፋሽዝም ማለትም ለሙሶሊኒ መስጠታቸውን ልባቸው እያወቀ ሳይሆን አልቀረም። ወጣም ወረደ ሙሶሊኒ በዚህም ሌላ ድል አገኘ።

በሀገር ላይ ያለውን ሥልጣን ሁሉ እንደዚህ ጠቅልሎ ከተሸከመ በኋላ፣ ሙሶሊኒ የአመራር ጉዞውን ቀጠለ። ጣልያኖች በሃሳብ ተንቀሳቀሱ። ለብዙ ዘመን አንገታቸውን ደፍተው በኖሩበት አገራቸው፣ አንገታቸውን ቀና አድርገው መራመድ ጀመሩ። ሙሶሊኒም ክብርና ኩራት ተሰማው። በሚላን ከተማ ባደረገው አንድ ንግግር ላይ "...ኢጣልያ ለሦስተኛ ጊዜ የሰው ልጅ ሥልጣኔ መዲና ሆናለች..." አለ። እውነትም ዓለም አደነቀው። ሚስተር ቸርችል "...ኢጣልያዊ ብሆን ኖሮ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ አከተልህ ነበር..." አሉት። መሐተማ ጋንዲ "የአዲሲቱ ኢጣልያ መድኅን" አደረጉት።

አስገራሚ ሥራዎች ተካሄዱ። የጣልያንን ሕዝብ ለማብዛት፣ ሕፃናት በብዛት እንዲወለዱ ከመንግሥት ድጋፍ ተሰጠ። በወንደላጤዎች ላይ ተጨማሪ ግብር ተጣለ። በድምሩ 1300 ልጆች የወለዱ 93 እናቶች በየአሉበት ተሰብስበው ሮምን በገና ወራት እንዲጉበኙ ተደረገ። ዱቼ አነጋገራቸው። በኅዳር 1926 /1933/ ዓ.ም በአንድ ወር ውስጥ በሮም ከተማ ብቻ 2,620 ጋብቻዎች ተፈጸመ። ሁሉም ከሙሶሊኒ ስጦታ ደረሳቸው። ለድሆች ነፃ ሕክምና፣ ምግብና ልብስ ተሰጠ። የልጆች የመዝናኛ ቦታዎች ተዘጋጁ። ለገበሬዎች ልዩ ድጋፍ ተሰጠ። ጫለስ ሲዘር አስቦት የነበረው የመስኖና የግድብ ሥራዎች እንደገና ተጠኑ። በገጠር አዳዲስ ከተሞች እንደ አንጉዳይ ፈለ። ወባ ከአገር ጠፋ። በግንቦትና በሰኔ ወር 1925/1933/፣ የመጀመሪያውን የዓለም ጦርነት ከአቆሙት ኃያላን መንግሥታት ጋር የሰላም ውል ሮም ላይ ተፈረመ። የአባሰ ዘር በሽታ ተቀነሰ።

ነገር ግን እነዚህ ሥራዎች ብዙም ሳይቆዩ መክሰም ጀመሩ። ጠንካራ መሠረት አልነበራቸውምና። አንዳንዶቹም በጅምር ቀሩ። ለልማት የተመደበው ገንዘብ ከባለ ሥልጣኖች ኪስ ገባ። የወሊድ መጠን በመጨመር ፋንታ ከ2.7% ወደ 2.3% ዝቅ አለ። ጠንካራ የነበረውን የመሬት ሥሪት ለማሻሻል ምንም ሙከራ ስለአልተደረገ የገበሬው ድካም መና እየቀረ ሄደ። ደመወዝ በሌሎች አገሮች ከነበረው ጋር የማይስተካከል ሆነ። የሥራ አጥ ቁጥር በረከተ። አሳፋሪ ውጤቶች እየተደበቁ፣ ደህና ደህናዎቹ በሕዝብ መገናኛ ይገለጹ ጀመር። ኢኮኖሚው ወደቀ። ሙሶሊኒ ወደ ግል ሕይወቱ አዘነበለ። ለስብሰባዎች እንደ ወትሮ በሰዓት መድረሱ፣ የመነጋገሪያ ጉዳዮች መዘጋጀታቸው፣ ስብሰባዎች በትክክል መካሄዳቸው ቀረ። ስብሰባዎች የባለ ሥልጣኖች መነታረኪያ ሆኑ። ቀሪ ሲበዛ ስም ይጠራ ጀመር። ሙሶሊኒ በዚህ ዓይነት ሊወጣው ከማይቻል የፖለቲካ ማጥ ውስጥ ሲገባ፣ የትኩረት ዓይኑን ወደ ኢትዮጵያ አዞረ።

ከሥልጣን ኮርቻ ላይ ለመቆናጠጥ ሲፍጨረጨር የኢትዮጵያን ጉዳይ በምሥጢር ሰባለሥልጣናትና ለታማኞቹ መግለጹ አልቀረም ነበርና ሙከራው ተቃናለት። ፕሮፓጋንዳውን አጠናከረ። የእድዋን ቂም፣ የኢጣልያንን ክብርና ጥቅም የሚነኮሩ ንግግሮች ተደረጉ። ጋዜጦች ታተሙ። በጉንደር የኢጣልያ ቆንሲል ላይ ጉዳት እንደደረሰ፣ በወልወል ግጭት ኢጣልያ እንደተጠቃች እየተደረገ ተነገረ። ንጉሡና መኳንንቶቻቸው፣ ጳጳሱ አባ ፓየስ 11ኛና ካህናት፣ ሕዝብ በጠቅላላ ደገፈው።

በኢትዮጵያ ላይ ታላቅ ዘመቻ መራ። የዘመቻውን ሂደት እርምጃ በእርምጃ እየተከታተለ፣ የተጣመመውን እያቃና፣ የጐደለውን እየሞላ ጦርነቱን አካሄደ። በወረራው ምክንያት በአውሮፓ የተነሣውን የፖለቲካ ውዝግብ አረገበ። ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛትነት ያዘ። ጦርነቱ ያከተመ ለሳም የተመሠረተ አስመሰለ። በሀገር ውስጥ ጉዳይ ተበላሽቶበት የነበረውን አቅሞሙን እንደገና መልሶ አጠናከረው። ሥልጣን ሞቀ፣ ክብር ደመቀ። ነገር ግን ራሼል "እንግዲህ ይበቃል" አለች። ሙሶሊኒ ይህቺን ምክር አላዳመጠም። በኑሮ ጉዳይ ላይ የአመለካከት ልዩነት በባልና ሚስቱ መካከል ተፈጠረ። ሙሶሊኒ ከራሼል ሲቃቃር ከቀድሞ ወዳጆቹ ሌሎች ጋለሞቶቹን አፈራረቀ። በመጨረሻም ከክላሬታ ፔታኪ ጋር ተጣበቀ። እርስዋም እስከ መገደል ታማኝ ሆነችለት።

በእስፔይን ሀገር ጀነራል ፍራንኮ ሐምሌ 11 ቀን 1928 ዓ.ም /ጁላይ 18 ቀን 1936/ ብጥብጥ አስነሳ። ብጥብጡ ወደ እርስበርስ ጦርነት ተሸጋገረ። ሙሶሊኒ ወዲያው 70,000 ወታደር ላከለት። የኢትዮጵያው እንደ አሰቀ በመቁጠር። በዚህ የተነሣ በአንድ ጊዜ ሁለት ጦርነት ማካሄድ ግድ ሆነበት። ከሂትለር ያለውን ግንኙነት አጠናከረ። ታዳጊ የፖለቲካ ኃይሎች ፋሽዝም፣ ናዝሲዝምና ኮሚኒዝም እንደ ሆኑ አድርጐ ገመተ።

ጃፓንንም ከመልካም ግምት አገባት። ሌላውን ዓለም ከቁም ነገር መቁጠሩን ተወ። ከእነዚሁ መንግሥታት ጋር በጎዳር 1930 /1937/ ዓ.ም ውል ተፈራረመ። ለይምሰል ያህል ከእንግሊዝ ጋር እንደዚሁ። በኢትዮጵያ ላይ ያለውን ገዥነት እንዲያውቅለት በሀገር ውስጥ የነበሩት አይሁዳውያን 47,000 ብቻ እንደሆኑ አሳወቀ። በጎብረተሰቡ ዘንድ ምንም ችግር ሳያጋጥም ዘርን በተመለከተ የጣልያኖችን ግንኙነት አርያን ከሚባለው የነጭ ዘር መሆኑን የሚገልጽና "...አይሁዳውያን ከኢጣልያኖች ጋር የደም ጥልቀት የላቸውም..." የሚል አዋጅ ሐምሌ 7 ቀን 1930 ዓ.ም /ጁላይ 14 ቀን 1938/ አወጣ። በዚህም ሂትለር በጀርመን የሚያካሂደውን አይሁዳውያንን የመጨረስ ተግባር ደገፈው። ሙሶሊኒ ጀርመንን፣ ሂትለር ጣልያንን በመጐብኘትና መግለጫ በማውጣት አንድነታቸውን አጠናከሩ።

አዲሱ የሞሶሊኒ ሕልም ከዚህ ተጀመረ። ኮርሲካ፣ ቲቺኖና ሌሎችም በአካባቢው ያሉ ጥቃቅን አገሮች ወደ ኢጣልያ የሚጠቃለሉበት መንገድ ተጠና። ቼኮዝሎቫኪያን በሰዎች የተፈጠረች እንጂ፣ ብሔርነት የሌላት አገር አድርጐ ገመተ። አልባኒያ፣ ግሪክ፣ የጐዝላቪያ፣ ሐንጋሪ፣ ሩማንያና ቡልጋሪያ የኢጣልያ እንዲሆኑ ታሰበ። እንደዚሁም የማልታ እና የኮርሲካ ደሴቶች ወደ ኢጣልያ እንዲጠቃለሉ ታቀደ። የምሥራቅ አፍሪካ ቅኝ ግዛትም ቱኒዝያን፣ ግብፅን፣ ሱዳንን፣ ሰሜን ሶማሊያንና ደሴቶቿን እንዲያካትት ተፈለገ።[1] ይህ ይዞታ በሜዲትራኒያንና በቀይ ባህር ላይ የሚያስገኘውን የበላይነት ማጤን ይገባል። ይህንን ዓላማ ይዞ ሰኔ 3 ቀን1932 ዓ.ም /ጁን 15 ቀን 1940/ ከሂትለር ጐን ለመቆም ወሰነ።

ሙሶሊኒ ከዚህ ውሣኔ ላይ የደረሰው በደንብ አስቦበት እንጂ በስሜት ተገፋፍቶ አልነበረም። ከዚህ ውሣኔ ላይ ያደረሱትን ነጥቦች መመልከት ይገባል። እነሱም፣

1ኛ. ኢጣልያ ከጀርመን ጋር ያላት ጉርብትና፣

2ኛ. ፋሽዝምና ናዝሲም ያላቸው የርዕዮተ ዓለም ዝምድና፣

3ኛ. በጊዜው የነበረው የኃይል ሚዛን በጀርመን እጅ መሆኑ፣

4ኛ. የአውቶሚክን ምሥጢር ለማግኘት መቃረቡ፣

5ኛ. ከጀርመን ጐን ቢሆን በሀገሮች ቅርምት ኢጣልያ የምታገኘው ጥቅም ነበሩ።

ስለዚህ ውሣኔው ከኢጣልያ ጥቅምና ከጊዜው ሁኔታ ጋር ሲታይ የሚነቀፍ አልነበረም። ነገር ግን በሙሶሊኒ ሕይወትና ሥልጣን፣ እንደዚሁም በፋሽስት ፓርቲና በኢጣልያ ላይ ታላቅ ለውጥ አመጣ። የእነዚህን ሁኔታዎች ግምጋሜ በኋላ እንመለስበታለን።



የፋሽስቱ መሪ ቤኒቶ ሙሶሊኒ።

አልባንያን መጋቢት 29 ቀን 1931 ዓ.ም /አፕሪል 7 ቀን 1939/ ያዘ። ጀርመን የአውሮፓ አገሮችን መውረር ስለጀመረ በመሸቀዳደም ሙሶሊኒ መስከረም 18 ቀን 1933 ዓ.ም /ሴፕቴምበር 1939/ ግሪክን ደገመ። አከታትሎም በርበራን ያዘ። ግብጽና ሱዳን ግዛት ውስጥ በጦር ኃይል ዕድገት ከመጨረሻው ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደረሰ።

ወይዘሮ ራሼል የፈራችው ደረሰ። ከጥቅምት ወር 1933 ዓ.ም ጀምሮ ሥሱስ ዞረ። ጦርነቶቹ በሙሉ በኢጣልያ ላይ ሚዛን ደፉ። በኢትዮጵያ ላይ ጦርነቱ ከመቸውም የበለጠ ጠነከረ። በኢትዮጵያ ላይ ወጭ የተደረገው በክንቱ እንደከሰረ ታወቀ። አሰፔይን የገባው ወታደር ከዚያው ቀልጦ ቀረ። ግሪክ የገባው ተባረረ። በዩጉዝላቪያ የተቀሰቀሰው ጦርነት የማይቻል ሆኖ ወደ አልባኒያም ተሻገረ። የኢጣልያ ወታደሮች ከሰሜን ሶማሊያና ከሱዳን ተባረሩ። ግብፅን ለማጥቃት ከሞከረው የኢጣልያ ጦር 113,000 በአንድ ጊዜ ተማረከ። በኢጣልያ ባለሥልጣኖች መካከል ሲካሄድ የቆየው አለመግባባት ጠነከረ። ሥልጣኑን ለማጠናከር ሲል እሱም ራሱ ባለሥልጣኖቹን እርስበርስ ሲያጋጭ ቆይቶ ነበርና ጠቡን ማብረድ አቃተው።

ኢትዮጵያ ነፃ ወጣች። ጀነራል ሎሬንሲኒ ሞቶ ኤርትራ ከእንግሊዝ እጅ ገባች። ሶማሊያም እንደዚሁ። ዱካ ደ አምስታ አምበላን፣ ጀነራል ናዚ ጐንደር ተማረኩ። የስዊዝ ካናል ተዘጋ። የሰሜን አፍሪካ ጦርነት አየገፋ ሄደ። የኢጣልያ ድርሻ ይሆናሉ ተብለው የነበሩትን ዩጉዝላቪያን፣ ሩማንያንና ሀንጋሪን ጀርመን ተሸቀዳድሞ ሲይዝ የጦር

ኃይሏ ቁጥር ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደረሰ። ሙሶሊኒ ከሂትለር ጋር ያለው ወዳጅነት ጠነከረ። ሂትለር ሙሶሊኒን ከሥልጣን ለማስወገድ ሲያሴሩ የነበሩትን ሁሉ ጨፈጨፈ። ሙሶሊኒ ከሂትለር ጋር ያለው ወዳጅነት ጠነከረ። ሂትለር ሙሶሊኒን ከሥልጣን ለማስወገድ ሲያሴሩ የነበሩትን ሁሉ ጨፈጨፈ። ሙሶሊኒ ከሂትለር ጋር ያለው ወዳጅነት ጠነከረ። ሂትለር ሙሶሊኒን ከሥልጣን ለማስወገድ ሲያሴሩ የነበሩትን ሁሉ ጨፈጨፈ።

ሙሶሊኒ ከክላሬታ ፒታኪ ጋር የሚሠራው ሥራ በፋሽስት ፓርቲ ጽህፈት ቤት ተመረመረ። ቤተሰቦችዋ በብዙ የመንግሥት ጉዳይ ጣልቃ ገብተው ተገኙ። ክላሬታ ዳግመኛ አጠገቡ እንዳትደርስ ተከለከለች። የራሼል መደሰት ሙሶሊኒን ሊያጽናናው አልቻለም። ተከዘ። የአንጀት በሽታ /አልሰር/ ያዘው። ሂትለር ይህንን ሲገነዘብ ኢጣልያን በኃይል ለመያዝ ከጀለ። ይህ ደግሞ የኢጣልያን ባለሥልጣኖች አስቆጣ።

ሁኔታዎች ሁሉ እንደዚህ ሲበላሹ በሙሶሊኒ ላይ ጠላቶቹ ገነነበት። በዱና ግራንዲ አነሳሽነት የፋሽስት ምክር ቤት እንደገና እንዲከፈት፣ ሕዝብ የመረጠው ምክር ቤት ተመልሶ እንዲጠራ፣ ንጉሡ ሥልጣናቸውን መልሰው እንዲይዙ ነገር ተጠነሰሰ። በብዙዎቹ የፋሽስት ባለሥልጣኖች ዘንድ ሃሳቡ ድጋፍ አገኘ። ሙሶሊኒ አንድም ፋሽስቶችን ለማስፈራራት፣ አንድም ንጉሡን ለመለማመጥ፣ አንድም ደግሞ ካልቀረልኝ ብሎ "ሥልጣን መልሶ ለንጉሡ ማስረከብ የምትሉትን አማራጭ እቀበላለሁ" አለ። በዚሁ ተወሰነ። የምክር ቤቱን ውሣኔ ለንጉሡ ማቅረብ መጥፎ ዕድሉ ሆነ።

ሁለቱም ሴቶች ሙሶሊኒ ሥልጣን ለንጉሡ መልሶ ማስረከቡን ተቃወሙ። የሙሶሊኒ ጥያቄ "ኋላ ምን ላድርግ?" ሆነ። ራሼል "ንጉሡ ከሀዲ ነው ይገድልሀል" አለችው። ማምለጫ ዘዴ ግን አላቀረበችም። ክላራ "አሞኛል ብለህ ብትተኛስ?" አለች። ሕመምም የሞት መጀመሪያ ነው። የተቃወሙት 19 የፋሽስት ባለሥልጣኖች እንዲያዙ የሰጠው ትዕዛዝ ውጤት ሳያስገኝ ቀረ። ስለዚህ ሙሶሊኒ የፋሽስት ምክር ቤት ያሳለፈውን ውሣኔ ለንጉሡ ከማቅረብ የሚያመልጥበት ዘዴ አጣ። በአንድ በኩልም ንጉሡ እንደማይጨክንበት አድርጐ ገመተ። ቀደም ብሎ የውስጥ ግንኙነት ነበረውና፣ ንጉሡን ከሥልጣን ሊያወርደው ይችል በነበረበት ጊዜ አልጨከነበትም ነበርና። ደግሞም ያለእሱ ኢጣልያ የምትቆም አልመሰለውም ነበርና።

የሚስቱንም፣ የሴት ልጁንም፣ የቁባቱንም ምክር ጥሶ ወደ ንጉሡ ዘንድ ሄደ። ንጉሡም በመልካም ተቀበለው። ሙሶሊኒ የፋሽስቱን ምክር ቤት ውሣኔ ከአቀረበ በኋላ፣ ምክር ቤቱ ሃሳብ የማቅረብ እንጂ ውሣኔ የመስጠት ሥልጣን እንደሌለው ገለጸ። ነገር ግን ንጉሡ ይህንን ክርክር አልተቀበለም። ምክንያቱም ሙሶሊኒ በሕዝብ የተመረጠውን ምክር ቤት የዘጋው፣ ሥልጣኑን ወደ ፋሽስት ምክር ቤት እንዲዛወር በማድረግ ነበርና። ደግሞም የንጉሡ ጥቅም ሥልጣኑን መልሶ በመረከብ ሙሶሊኒን



የፋሽስቱ መሪ ቤኒቶ ሙሶሊኒ።

ከሥልጣን ማባረር ነበርና፤ ንጉሡም "...አንተ የተጠላህ ሰው ነህ። ከእኔ በስተቀር ደጅ የለህም። እኔም ለሕይወትህ ጥበቃ አደርግልሀለሁ..." በማለት ንግግሩን ደምድሞ አሰናበተው። ሙሶሊኒ ወደ እሥር ቤት ጉዞውን ቀጠለ።

ሙሶሊኒ ምን እንደተወሰነበት አልተረዳም። ነገር ግን ከቤተ መንግሥቱ ሲወጣ ያልጠበቀው ነገር አጋጠመው። አንድ መኮንን ተጠጋው። እንዲጠብቀው ከንጉሡ መታዘዙን ነገረው። ሙሶሊኒ አሁንም አልገባውም። "አስፈላጊ አይደለም" የሚል መልስ ሰጥቶ ጉዞውን ቀጠለ። ነገር ግን መኪናው በአካባቢው አልነበረም። በዚህ ጊዜ ተደናገረው። መኮንኑም አስገድዶ ከአንድ የአሥረኞች መኪና ውስጥ አስገባው። ከመንገድ አሱን የሚያጅብ ሳይሆን ፋሽሊዝም ይውደም የሚል ሰልፈኛ አየ። ከዚያም ወደ ፖሊስ ጣቢያ ተወሰደ። በዚህ ዓይነት ሙሶሊኒ ሐምሌ 17 ቀን 1935 ዓ.ም /16 ቀን 1943/ እሥር ቤት ገባ።

ማርሻል ባዶልዩ በሙሶሊኒ ምትክ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆኖ ተሾመ። "የት መኖር ትፈልጋለህ?" የሚል ጥያቄ ቀርቦለት ሙሶሊኒ ሮካ ዴል ካሚናቴ የተባለውን ቦታ መረጠ። ነገር ግን ምርጫውን አላገኘም። ፖንዛ ወደ ተባለችው ደሴት ተወሰደ። ይህች ደሴት ብዙ ኢትዮጵያውያን አሥረኞች የሚለቀቁባት ነበረች። የፖንዛ እሥራት አስተማማኝ ባለመሆኑ ደግሞም ዱካውን ለማጥፋት ሲባል ማደሌና ወደ ተባለችው ሌላ ደሴት ተወሰደ። የታሠረበት ቦታ ከባሕር ወለል በላይ 6,500 ጫማ እንደሆነ ሲነገረው፤ ሙሶሊኒ ከከፍተኛው እሥር ቤት ገብቻለሁ ማለት ነዋ! ብሎ ተደነቀ።

የሙሶሊኒ መታሠር ለሂትለር እጹን እንደ መቆረጥ ያህል ሆነበት። አዲሶቹ መሪዎች የፖሊሲ ለውጥ ስለአደረጉ በጦርነቱ ሂደት ላይ አደገኛ ነገር ተፈጠረ። ስለዚህ ሂትለር ሙሶሊኒ የታሠረበትን ቦታ ያፈላልግ ጀመር። ሙሶሊኒ ተፈቅዶለት ነበርና አንድ ቀን ሲንሸራሸር አንድ የበጮች አረኛ ወደ እሱ ቀርቦ "ጀርመኖች ይፈልጉሀል። አሁን ሄጀ እነግራቸዋለሁ" ብሎት ከፊቱ በረረ። ሞሶሊኒ አላመነም። ከጥቂት ቀናት በኋላ አራት የጀርመን አይሮፕላኖች ተከታትለው በአቅራቢያው አረፉ። ወታደሮችም ከአይሮፕላኖች እየወረዱ በመሮጥ ሙሶሊኒ የነበረበትን ቤት ከበቡ። የኢጣልያ ፖሊሶች ለመተኮስ ተዘጋጅተው ሳሉ ሙሶሊኒ በመስኮት ይመለከት ነበርና። "አትተኩሱ! በመካከላቸው ኢጣልያዊ ፖሊስ አለ" ብሎ በታላቅ ድምፅ ጮኸ። ፖሊሶቹ ፈዘዙ። በአንድ አቶ እስከዚኒ በሚባል ሻምበል የሚመሩ የጀርመን ወታደሮች ሙሶሊኒ ከአለበት ቤት ገቡ። ወደ ጀርመን አገር ሲወስዱት እንደመጡ ነገሩት።

ሞሶሊኒ ሲፈታ ኢጣልያ ተበጠበጠች። ማርሻል ባዶልዮ ማረጋጋት አቃተው። የኢጣልያ ንጉሡና የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ተብሎ የነበረው ሣልሣዊ ኢማኑኤል አገር ጥሎ ጠፋ። ይህንን ሁኔታ ተገንዝቦ የነበረው ጀነራል ሶሌቲ ሙሶሊኒ ሮም ገብቶ አዲስ መንግሥት እንዲያቋቁም ፈለገ። ሙሶሊኒ በመካከላቸው ኢጣልያዊ መኮንን አለ በማለቱ ለወታደሮቹ እንዳይተኩሱ ትዕዛዝ የሰጠው አሱን አይቶ ነበር። ነገር ግን በሃሳብ ጭምር በመንገላታት ተዳክሞ ነበርና፤ የጀነራል ሶሊቲን እቅድ መቀበል አልቻለም። ከዚህም በስቀር ሂትለር ወደ አሱ እንዲሄድ አስተላልፎለት የነበረውን ቃል ማክበር ስለነበረበት፤ ወደ ጀርመን አገር መስከረም 2 ቀን 1936 ዓ.ም /ሴፕተምበር 12 ቀን 1943/ ሄደ። ሌሎች የጀርመን ወታደሮች ወይዘሮ ራሼልን ከኢጣልያ ወደ ጀርመን አገር በዚያው መስከረም 2 ቀን ወስደዋት ነበርና፤ ባልና ሚስቱ ሚዮኒክ ከተማ መስከረም 3 ቀን ተገናኙ።

ሚዮኒክ ከደረሰ በኋላ ሙሶሊኒ የሂትለርን ድንፋታ ማዳመጥ ነበረበት። ሂትለር ጣልያኖች ስለከዱት ጦርነቱን ብቻውን መቀጠል እንደአለበት ገልጾ፤ ወደ ሥልጣን እንዲመለስ ሞሶሊኒን ጠየቀው። አሻንጉሊት አድርጉ እንደ አሻው ሊጫወትብት። ሙሶሊኒ ወደ ሥልጣን የመመለስ ጉጉት አልነበረውም። የአሱ ወደ ሥልጣን መመለስ በኢጣልያ ውስጥ የርስበርስ ጦርነት እንደሚያስነሣ ገለጸ። ነገር ግን ሂትለር አልተቀበለውም። በግድ መመለስ እንደአለበት አስታወቀው። ሞሶሊኒ መልሶ በሂትለር ላይ ጮኸበት። ጀርመኖች ጣልያኖችን እንጂ፣ ጣልያኖች ጀርመኖችን እንዳልከዱ ነገረው። ከዚያም አልፎ ጀርመኖች የኢጣልያን ምድር ለቅቀው መውጣት እንደ አለባቸው በድፍረት አስታወቀው። ሆኖም ሂትለር አልተበገረለትም። እምቢ ከአለ ገድሎት በአይሮፕላን አደጋ እንደ ሞተ መግለጫ በማውጣት፤ በምትኩ ሌላ ሰው ሹሞ ኢጣልያንን ያስርጎራሄ እንደሚቀጣት ገለጸለት። አያደርግም አይባልም። በሌላ በኩል ደግሞ ሚስቱ ወይዘሮ ራሼልና ልጁ ወይዘሮ ኤዳ ወደ ሥልጣን መልሱን ብለው አጥብቀው ተቃወሙ። ወይዘሮ ራሼል ገና በደህና ቀን "እንግዲህ በቃ" ብላ ነበርና የፈራችው እንደ ደረሰ ገለጸች። ኤዳ ደግሞ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የኮንት ቺያኖ ሚስት ነበረችና ምክርዋ ከብዶት የነበረው ሙሶሊኒ በጉዳዩ በደንብ ከአሰበበት በኋላ ወደ ሥልጣን ለመመለስ ወሰነ። ወደ ሥልጣን የሚመለሰው ወድዶ ሳይሆን ለኢጣልያ ብሎ ነበርና "ኃላፊነቴን እስክ መጨረሻው መወጣት አለብኝ" አለ።

መስከረም 5 ቀን 1934 ዓ.ም /15 ቀን ሙሶሊኒ/ ድምጹን ለኢጣልያ ሕዝብ በጀርመን ሬዲዮ አሰማ። "ሶሺያሊስት መንግሥት

እንደሚያቋቁም አሰታወቀ። የፋሽስት ፓርቲ በሕዝብ እንደተጠላና እንደረከሰ ተረድቶ ነበርና። ድምጹ ከመቅጠኑ የተነሣ ድምጹን ለይተው የሚያውቁ ጣልያኖች የእሱ አልመሰላቸውም። ብዙዎቹም እንደገና ወደ ሥልጣን ባይወጣ ወደዱ። ፈቅዶ እንጂ ተገድዶ አልመሰላቸውም ነበርና።

ሙሶሊኒ ጥቂት ደጋፊዎቹን አስከትሎ ወደ አገሩ ተመለሰ። ነገር ግን ሮም መግባት አልቻለም። ጋርዳ ከተባለው ደሴት ምዕራብ በሆነች ሣሉ በተባለች ትንሽ ከተማ መንግሥት አቋቋመ። ሕዝቡን ለማስተባበር ሕመምተኛና ደካማ ሰውነቱ የሚፈቅድለትን ሁሉ አደረገ። አገር የመምራቱ ሥራ ከበደበት። በዚያ ላይ የጀርመኖች ተፅዕኖ ተጨመረበት። ሂትለር እሱን እንደ ሎሌ ኢጣልያን እንደ ቅኝ ግዛት ቆጠራት። ቡበዙ ሽህ የሚቆጠሩ የኢጣልያ ዜጐች እየተገደዱ ለጀርመኖች የጉልበት ሥራ ከመሥራት ደረሱ። ይህም ታላቅ ሀዘንና ሥቃይ ፈጠረ። አዲስ የሾማቸው ሚኒስትሮች የቀድሞዎቹ የፋሽስት ፓርቲ ባለሥልጣኖች በሀገር ላይ የክህደት ሥራ ስለፈፀሙ በወንጀል እንዲከሰሱ ሃሳብ አቀረቡ። የአዲሱን መንግሥት ሥልጣን ለማጠናከር፤ ተቃዋሚዎችን ማጥፋት አስፈላጊ መስሎ ታያቸው። እሱ ግን አዲስ ሥራ መሥራት እንጂ፤ ወደ ቀደሞው የፖለቲካ አዘቅት ተመልሶ መውረድ አልፈለገም። ደግሞም ሥራቸው የሀገርን የማዳን እንጂ፤ የማጥፋት መከራ መስሎ አልታይህ አለው። ደግሞም አማቹን ቺያኖን ከሞት የሚያደርስ፤ ከሚወዳት ልጁ ከኤዳ የሚያለያየው ሆነበት። ደግሞም ብዙዎቹ የፋሽሲት ፓርቲ ባለሥልጣኖች ከሀገር ስለወጡ ለፍርድ የሚቀርቡት ሰደስቱ ብቻ ሆኑ።

በጉዳዩ ብዙ ከአሰበበት በኋላ ጥያቄውን ማገድ ስለአልቻለ እንዲከሰሱ ፈቀደ። የፍርድ ቤት ሥራ ተካሄደ። ሞት ተፈረደባቸው። እሱም የፍርዱን ሂደት ለማገድ ስለአልፈለገ ጥር 3 ቀን 1936 ዓ.ም /ጀንዋሪ 11 ቀን 1945/ ቺያኖና ሌሎቹ አምስት ጓደኞቹ በጥይት ተደበደቡ። ወይዘሮ ኤዳ የባልዋን የክንት ቺያኖን የምሥጢር ማስታወሻዎች ይዛ ስዊዝ ሀገር በመግባት ለእንግሊዞች አስረከበች። የጠረጠሩ አመለጡ። ያልጠረጠሩ ተመነጠሩ። ይህ ሁኔታ ሙሶሊኒን እጅግ አሳዘነው። ወደ መንፈሳዊ ሕይወት ለመመለስ አሰቦ የአጥቢያውን ቄስ ቢያማክር "ቁረብ" አለው። ይህንን መቀበል አልቻለም። "ገና ጊዜ አለኝ" አለ። ጊዜ ሞቱ መቃረቡን አላወቀም።

እሱ በታሠረ ጊዜ ቁባቱ ወይዘሪት ክለራ ፒታኪ ሮም ከተማ ታሥራ ነበር። እሱ ሲፈታ እርስዋም ተፈታች። ገሥግሣ ከአሰበት ከሣሉ ከተማ ደረሰች። የእርስዋ መምጣት ለሙሶሊኒ ተጨማሪ ራስ ምታት ሆነበት። በመንግሥት ባለሥልጣኖች ዘንድ የተወደደች አልነበረችም።

ለክብሩ መልሶ ግንባታ አመች ሁኔታ አይፈጥርም። በዚያ ላይ ደግሞ በሁለቱ ሴቶች፣ ማለትም በሚስቱ በወይዘሮ ራሼልና በቁባቱ በወይዘሪት ክላራ ፔታኪ መካከል ታላቅ ጭቅጭቅ ተነሣ። ሙሶሊኒ ተዳከመ። "ቺያኖ ከሞተ ወዲህ እኔውም ራሴ ቀስ በቀስ በመሞት ላይ ነኝ" አለ።

አዲሱ መንግሥት በመጠኑ ተጠናከረ። የ600 ቀናት ዕድሜ አገኘ። ነገር ግን ወደ ሮም ሊያስገባው አልቻለም። የኢጣልያ ሕዝብ ጥላቻ ሊቀዘቅዝ በእንግሊዝ የሚካሄደው ጦርነት ተጋጋመ። ሰሜን አፍሪካን ጠቅልሎ ይዞ ወደ ሲሲሊ ደሴት ተሻገረ። ከዚያም የኢጣልያን መሬት ጫማ ረገጠ። ከዚያም እንደ ቅልጥም በተዘረጋው አገር ከደቡብ ወደ ሰሜን ወጣበት። የኢጣልያ ጦር መከላከል አልቻለም። ደግሞም ተከፋፈለ። የጀርመን ጦር ቀደም ብሎ በእንግሊዝ በተሠራ ጥበብ ወደ ኮርሲካ ሄዶ ስለነበር እንዳች ማድረግ አልተቻለም። በሙሶሊኒ መንግሥት ላይ ያመፀው ሠራዊት ከእንግሊዝ ጦር ጉን ቆመ።[2] ሮም ከተማ ወድዳ እስክትጠላ ድረስ በቦምብና በመድፍ ተደብድባ በእንግሊዝ ተያዘች። ሙሶሊኒ ያለ አንዳች ውል እጁን እንዲሰጥ ተጠየቀ። ከሁሉም ይበልጥ ያስገረመው እጁን እንዲሰጥ የተጠየቀው የገዛ ሀገሩ ተወላጅ በነበሩ ሽፍቶች በመሆኑ ነበር።

ሞሶሊኒ እጁን ለሽፍቶች ከመስጠት ሞትን መረጠ። በእጁ የነበሩትን የምሥጢር ወረቀቶች በጥንቃቄ መረጠ። ጥቂቱን በቦርሳው ከተቶ ያዘ። ሌላው በጀልባ ተወስዶ ከባሕር ውስጥ እንዲሰቀቅ አደረገ። ባለቤቱ ወይዘሮ ራሼል ወደ ሞንዛ እንደተሔድ አድርጐ ከሣሉ ከተማ ሚሳን ወደ ምትባል ሌላ ትንሽ ከተማ ሸሸ። ክላራ "ከአንተ አልለይም" ብላ ተከተለችው። የአሜሪካንና የእንግሊዝ ጦር በሎኛ የተባለውን ከተማ ያዘ። ራሺያኖች በርሲን ለመግባት መቃረባቸው ታወቀ። ቫልተሊና በተባለችው መንደር ውስጥ አብረውት ከነበሩ ጥቂት ሚኒስትሮችና የጦር ሹማምንት ጋር ስብሰባ አደረገ። ለመከላከል ሙከራ እንዲደረግ ቢያሳስብ ተቀባይ አጣ። በፋሽስት ፓርቲ መራራ ጥላቻ መፈጠሩ አሳዘነው። በካርዲናል ሹተር አማካይነት ከሽፍቶቹ ጋር ግንኙነት ፈጠረ። እነሱ ግን የልብ ልብ ተሰምቶአቸው ነበርና በሁለት ሰዓት ውስጥ እጁን እንዲሰጥ ጠየቁት። በድፍረታቸው ተደንቆ ጥያቄውን ሳይቀበል ቀረ።

ጥቂት ታማኞቹን አስከትሎ ከሞ ወደ ተባለች ሌላ ትንሽ መንደር ሸሸ። ወደ ስዊዝ አገር እንዲሰደድ ምክር ቢቀርብለት "በምንም ምክንያት ከኢጣልያ ውጭ አልሄድም" አለ። ሚያዝያ 19 ቀን 1937 ዓ.ም /ኤፕሪል 27 ቀን 1945/ ለሚስቱ ለወይዘሮ ራሼል የመጨረሻ ደብዳቤ ጻፈ። ብዙ እንደ በደላት ያውቅ ነበርና ይቅርታ ጠየቃት። "በርግጥ የማፈቅረው

አንቺን እንደ ሆነ እመኝ...ልጆቹን ይዘሽ ወደ ስዊዝ አገር ሂጂ።... ከጣልያኖች ይልቅ እነሱ ይራሩ ይሆናል..." አላት። ወረቀቱ ሲደርሳት ወይዘሮ ራሼል "ወደ ስዊዝ አገር ሂድ" አለችው። እሱ ግን "አላደርገውም! ተስፋ የለኝም። የመጣውን እቀበላለሁ። ...ሹፌሬም እንኪን ከዳኝ..." የሚል መልስ ላከላት።

ከዚያም ሚናጅ ወደምትባል ሌላ ትንሽ መንደር ሸሸ። ክላራ የስፔይንን ሰንደቅ ዓላማ በሚያውለበልብ አውቶሞቢል ደረሰችበት። እሱም አይቶአት ተደነቀ። "የምትከተይኝ ስሞት ነውን?" አላት። ራሼል ስዊስ አገር እንዳትገባ መከልከልዋን ሰምቶ አዘነ። አብረውት የነበሩት 12 ወታደሮች ብቻ ስለነበሩ መፈናፈን አልቻለም። ምድር ጠበበችው። ሙሶ ወደተባለች ሌላ ትንሽ መንደር ሸሸ። የሚዝዘው ከጀርመን ወታደሮች ጋር ነበር። በመንገድ ላይ ሽፍቶች አቆሙአቸው። ጀርመኖቹ ብቻ እንዲያልፉ ስምምነት ተደረገና ጉዞው ቀጠለ። ሞሶሊኒ የጀርመን ወታደር ልብስ ለብሶ የጀርመን ወታደር መስሎ አንድ ካሚዮን ላይ ተደብቆ ነበር። ደንጉ ከተባለች ትንሽ ከተማ ሲደርሱ ሽፍቶቹ ማጣራት ጀመሩ። ጣልያኖቹን ወዲያው ከመኪና አስወርደው ወሰዱአቸው። ሙሶሊኒን ግን ለጊዜው አላወቁትም ነበርና ከመኪናው ላይ ቆየ። ፍተሻው ሲያልቅ ሲል ከአሥራ ሁለት የጀርመን ወታደሮች ጋር አንድ የተወለወለ ቦት ጫማ ያደረገ ሰው ከነዳጅ በርሜሎች መካከል ተዘርሮ ታየ። በጫማው ሁኔታ የገነገነው ፈታሽ "ኢጣልያዊ ነህ?" ብሎ ቢጠይቀው "አዎን ነኝ" ብሎ መለሰ። ሙሶሊኒ መሆኑ ታወቀ። እሱም ክላራ ፔታኪም ተያዙ።

ሽፍቶቹ መልሰው ወደ ደንጉ ወሰዱት። የከተማዋ ባለሥልጣኖች ከአንግሊዞች ለመሠወር ከከተማይቱ በላይ ወደሚገኝ ተራራ አወጡት። ራሱን አሥረው ቀስለኛ አስመሰሉት። ፔታኪም ነርሱ ሆነች። ሁለቱንም አንድ ክፍል ውስጥ አስገቡአቸው። ኮሎኔል ቫላሪዮ የተባለ የሽፍቶች አለቃ በአንድ አሜሪካዊ መኮንን የተፈረመ ወረቀት በማቅረብ እሥረኞቹን እንዲሰጡት ጠየቀ። የከተማዋ ሹም እልሰጥም በማለት ተከራከረ። ነገር ግን ሙሶሊኒን ማዳን አልተቻለም። ሙሶሊኒ ከሽፍቶቹ እጅ ወደቀ።

በለደፍ እየጮሽመና እያዳፋ ወስዶ ከግንብ አስጠጋው። በሌለበት የሞት ፈርድ እንደተፈረደበት የሚገልጽ ጽሑፍ አነበበለት። ሙሶሊኒ አንድ ቀን ለፍርድ መቅረብ እንደማይቀርለት አውቆ፣ በአንድ በቆዳ በተጠረዘች ማስታወሻ ጽፎ ይዞ ይዞር ነበር። ከእጁ አይለያትም ነበር። በዚያም ቀን ይዘአት ነበር። ባለሰበው ሞት እንደተፈረደበት ሲሰማ ላይጨነቅ አለቀረም። "ምን አደረግሁህ?" ብሎ መኮንኑን ጠየቀው። በግል ቁም እንጂ በፍርድ እንደተወሰነበት አድርጉ አልቆጠረውም ማለት ነው።

በዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት እንጂ በሽፍቶች ያውም በሌለበት "እንዲፈረድበት" አልጠረጠረም ነበር። መኮንኑ መልስ ሳይሰጠው ሊገድለው ተዘጋጀ። ወይዘሪት ክላራ ፔታኪ ልታድነው ሞከረች። እሱን ከገደላችሁት እኔንም ግደሉኝ ብላ ጮኸች። ነገር ግን ልታድነው አልቻለችም። የግደያው ሥራ ቀጠለ።

ቫላሪዮ የተባለው ሽፍታ ጠመንጃውን በፍጥነት አነጣጥሮ ምላጩን ሳበ። ነገር ግን ጠመንጃው አልተተኮሰም። ከሽፈ። በጠመንጃ ሰደፍ ራሱን ሊከሰክሰው ሲዘጋጅ ያየ ሌላ ወታደር መትረየስ አቀረበለት። ቫለሪዮም በቶሎ ተቀብሎ በሙሶሊኒ ላይ አምስት ጥይት አፈሰሰበት። ወደቀ። ክላራ ፔታኪ ሮጣ ከሬሣው ላይ ወደቀች። ቫለሪዮ እርስዋንም ደገማት። ዱቺ ቢኒቶ ሙሶሊኒ ሚያዝያ 20 ቀን 1937 ዓ.ም /አፕሪል 28 ቀን 1945/ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ተገደለ።

የሙሶሊኒ አበሳ በዚህ አላበቃም። ሬሣው ከክላራ ፔታኪና አብረውት ከተገደሉ ሌሎች 21 ፋሽስቶች ጋር በካሚዮን ተጭኖ ወደ ሚላን ከተማ ተወሰደ። እዚያም ፔያሳ ሌሎሬቶ በተባለችው ትንሽ አደባባይ ካለ ቤንዚን ማደያ የዝቅዝቂት ተሰቅሎ መሣለቂያ ሆነ።[3]

ሞሶሊኒ ጨካኝ ሰው ነበር። በኢትዮጵያና በኢትዮጵያውያን የፈጸመው ግፍ እጅግ ከፍተኛ ነው። በጥይት በቦምብ ፈጃቸው። የመርዝ ጋዝ አዘነመባቸው። በኢትዮጵያ ላይ ጦርነት የቀሰቀሰውና የመራው እሱ ራሱ ነው። ስለዚህ በኢትዮጵያ ላይ ለተፈፀመው በደል በታሪክ ፊት ተጠያቂው እሱ ነው። ነገር ግን አውሮፓውያን ይህንን በደል ከበደል አልቆጠሩበትም። ለኢጣልያ ጥቅም እንደ ተፈጸመ አድርገው ቆጠሩት እንጂ። ሞሶሊኒ ብዙ ጣልያኖችንም ገድሎአል፣ አሥሮአል፣ አሰቃይቷአል። ነገር ግን ለኢጣልያ ታላላቅ ሥራዎች ሠርቷል። ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛትነት ላፍታም ቢሆን ሰጥቶአታል። በኢጣልያ ውስጥ ያንቀሳቀሳቸው የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ኑሮ ሥራዎች ቀላል አልነበሩም። ነገር ግን ያ ሁሉ ሥራ ከእሱው ጋር አብሮ ጠፋ። ኢጣልያ ከአዲስ ማጥ ውስጥ ገባች። በእሱ ስሕተት ብቻ አልነበረም። በዓለም የፖለቲካ ሁኔታና በተለይም በሂትለር እብደት ጭምር እንጂ። ቢሆንም ለሀገሩ እስከ መጨረሻ ህቅታው ድረስ ሠራ። ሂትለር በእስጨነቀው ጊዜ እንኪን የወገኖቹን ጥቃት ቸል ሳይል ተከራክረላቸው።

በአመራር ረገድ ሙሶሊኒ ክብር እንጂ፣ የግል ጥቅም ማጋበስ አልፈለገም። በአደባባይ ጪሂ ነው። ዓለሙም የሚያውቀው በዚህ ጠባዩ ነው። በግል ሰውነት ሲታይ ያስባል፣ ብዙ አማራጮችን የማየትና የሚያዋጣውን የመምረጥ ችሎታ ነበረው። ዬሕግ፣ የአምነት፣ የነሲና፣

የጥቅም ጉዳዮች ለእሱ ምንም አይደሉም። እሱ የሚከተለው የሚያዋጣውን ብቻ ነው። ከንጉሡም፣ ከጳጳሱም፣ ከመኳንንቱም፣ ከመነኳሳትም መስማማቱ ለዚህ ጉልህ ማስረጃ ነው። ብልጠት አበዛና በዚሁ በተጠቀመበት ዘዴ ተመልሶ ወደቀ። ነገር ግን የወደቀው በራሱ ስሕተት ብቻ አልነበረም። በሂትለርም ቄምር እንጂ።

የግል ሕይወቱ ውጣ ውረድ የሞላበት ነበር። ወደ ሥልጣን ኮርቻ ለመፈናጠጥ ባደረገው ጥረት ቤተሰቡ ብዙ መሥዋዕት ከፍሎአል። ለገንዘብ ግድ አልነበረውም። ከአቫንቲ ጋዜጠኝነት ሥራው በተባረረ ጊዜ ደመወዙ መከፈሉ እንደሚቀጥል ተነግሮት ነበር። እሱ ግን እምቢ አለ። ግንበኛ ሆኜ መኖር አያቅተኝም አለ። በሚስቱ በወይዘሮ ራሼል ብዙ በደል ፈጽሞባታል። እሱ ከሌሎች ጋለሞቶች ጋር ሲምነሸነሽ ራሼል በኑሮ ችግር ትጠበስ ነበር። ለምሣሌ ከሥልጣን በወረደ ጊዜ ከልዩ ልዩ የጦር ክፍል የተውጣጡ ወጣት መኰንኖች ለመፈተሽ ከቤቱ ሄዱ። አደጋ እንዳይደርስባቸው ሰግተው ተጠንቅቀው ነበር። ከቤቱ አካባቢ ሲደርሱ አለመጠን ጭር አለባቸው። በር ቢያንኳኩ አንዲት ያሸረጠች ሴት ወጣች። ራስዋን አስተዋውቃ ለመግባት ቢጠይቁ ፈቀደችላቸው። የሚፈተሽ ነገር አልነበረም። በቤቱ ውስጥ የነበሩት ዕቃዎች በማንኛውም ኢጣልያዊ ሹም ቤት የሚገኙ ዓይነት ነበሩ።

ክፍሎቹን እየተዘዋወሩ ሲገብኙ በአውሮፕላን አደጋ የሞተው ልጁ ይተኛበት ከነበረው ክፍል ደረሱ። የምዋቹ ፎቶግራፍ ተሰቅሎአል። ሻማ ተበርቶለታል። ከመኰንኖቹ አንዱ "ከዚህ ልጅ ጋር ሚላን አንድ ትምህርት ቤት ነበርን" አሉ። ሌላውም አየር ኃይል እንደሚያውቀው ተናገረ። አንዱ መኰንን ደግሞ "ታውቂዋለሽ?" ብሎ ራሼልን ጠየቃት። ገረዱ እንጂ የዱቼ ሚስት አለመሰለቻቸውም ነበርና። "እናቱ ነኝ እኮ!" ባለቻቸው ጊዜ ደነገጡ። አለቀሱም። እርስዋም "በቤት ውስጥ ያለው ይህ ነው" ብላ አንድ ጠርሙስ ወይን አቀረበችላቸው። መጠጡ ለገና መቆያ ጀነራል ፍራንኮ የላኩላት ነበር። እጅግ ተደነቁ። ዱቼ እንደገና ወደ ሥልጣን እንደሚመለስ ያላቸውን ተስፋ ገልጸውላት እያዘኑ ሄዱ። ራሼል ግን በደሉን ሁሉ ችላ ብላ ኖረች። ከሁሉም በላይ የሚያስገርመው የወይዘሪት ክላራ ፒታኬ ነው። እሱ ራሱ እስኪደነቅ ድረስ ታማኙ ሆነች። የጭንቁ ተካፋይ ሆነች። በመጨረሻም "እሱን ከገደላችሁት እኔንም ድገሙኝ" ብላ ሬሣው ላይ ተጠመጠመች። እንዳሰቸውም ተገደለች። አብራው በሚላን ከተማ የዝቅዝቁት ተሰቀለች። ይገርማል ከልብወለድ የረቀቀ ድርጊት!

አባሪ 4
የፋሽስት ፓርቲ አነሣስና አወዳደቅ

የ19ኛው ምዕተ ዓመት ሁለተኛው አጋማሽ በአውሮፓ አዳዲስ ርዕዮታት ዓለም የተጠነሰሱበት ዘመን ነበር። የኮሚኒዝም ፍልሥፍና የተቀመረው በዚህ ጊዜ ነው። ከዚያ ቀደም ብሎ በትምህርት መልክ ሲነገሩ፣ በፍልሥፍና መልክ ተራቅቆ ሲደረግባቸው የቆዩ የፖለቲካና የሕዝብ አስተዳደር ባሕረ ሃሳቦች ቅርጽ እያገኙ ሄዱ። ይህ ሁኔታ ኢጣልያንም መዳሰሱ አልቀረም። በዚህ ላይ ደግሞ የአድዋ ቁስል ተጨመረበት።

ሃያኛው ክፍለ ዘመን ሲብት ኢጣልያ በእነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ ነበረች። በዚህ ላይ ደግሞ የኢኮኖሚ ድቀት፣ የሥራ አጥ ብዛት፣ በየጊዜው የሚነሱና የሚወድቁ መንግሥታት ግልብጥብጦሽ ሕዝቡን እያስመረረ ሄደ። የፋሽዝም አፈጣጠርና አስተዳደግ በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሆነ። ዕምነትን የሚጋፋ፣ ባለሥልጣኖችን የሚደፍር፣ አዲስ ለውጥ የሚሻ ትውልድ ተነሣ። የነበሩት ፓርቲዎች ጥሙን የማያረኩለት ሆኑ። ለጭቁኑ በማለት የተንቀሳቀሰው የፋሽት ፓርቲም የማይጠቅም ወጣው። ስለዚህ አዲስ ፓርቲ ማቋቋም አስፈለገ። በዚህ ላይ ደግሞ የቤኒቶ አእምሮ ለሚብላላው አመለካከት በር ከፈተ።

ፋሽዝም እንደ ሌሎቹ ርዕዮተ ዓለሞች በፅንሰ ሃሳብ ደረጃ ምርምር ተደርጉበት የተነሣ አይደለም። ለምሣሌ ኮሚኒዝም በፍሬድሪክ ኤንግልስና በካርል ማርክስ ጥናትና ምርምር ከተደረገበት በኋላ ነው በሊኒንና ከእሱም በኋላ በእስታሊን የተንቀሳቀሰው። ፋሽዝም ግን መጀመሪያ እየተንቀሳቀሰ ነው ርዕዮተ ዓለሙን ለመቅረጽ የሞከረው።

ሂደቱን ብንመለከት ሙሶሊኒ ከሶሺያሊስት ፓርቲ ጋር በሥልጣን ፍለጋም፣ በአመለካከትም ተጋጨ። ሶሺያሊስቶች ከብልህነት ይልቅ የጀብደኝነት መሥመር ተከተሉ። ሙሶሊኒን በአንዳንድ ጉዳይ አለዝበው አብሮአቸው እንዲቆም በማድረግ ፈንታ ገፈተሩት። እሱም እንደነርሱ እልህ ያዘውና አዲስ ፓርቲ በማቋቋም የራሱን ፍላጐት በሥራ ላይ ማዋል ፈለገ። ከሁለት እንጨት ፍጭት እሳት እንዲወጣ የፋሽስት ፓርቲ ከዚህ የርስበርስ ግጭት ወጣ።

የሙሶሊኒን የሕይወት ታሪክ በሚመለከተው ምዕራፍ እንደ ተገለፀው፣ ሙሶሊኒ አዲስ ቡድን አሰባስቦ ስሙን "ፋሺ" አለው። የዚህ ቃል የመጀመሪያ ትርጉሙ "ቡድን" ከማለት እምብዛም የተለየ አልነበረም። የሙሶሊኒንም ሃሳብ ተከታዮችን አፍርቶ ለሥልጣን የሚያበቃ አንድ የሆነ ድርጅት ከመቋቋም የተለየ አልነበረም። በትግሉ ውስጥ እየነቃና መካርም እያገኘ ሄደ እንጂ፣ ለመጀመሪያው ጊዜ ሥልጣን ቢይዝ ምን ሊሠራ እንደሚፈልግ አያውቅም ነበር። ግልጽ ዓላማ አልነበረውም።

በ1904 ዓ.ም የተጠነሰሰው የፋሺ ቡድን እየተጠናከረ ሄደ። ተከታዮቹ ፋሽስቶች ተባሉ። በሀገር ጉዳይ ላይ እያተኮሩ ሄዱ። በወቅቱ የነበሩት የኢጣልያ መንግሥቶች ላይ አቃቂር ማውጣትን አዘወተሩ። ቀስበቀስም አድማጭ እያገኙ ሄዱ። የሕዝቡንም የልብ ትርታ ማድመጥ ጀመሩ። በዚያን ወቅት ለሕዝብ ቅርበት ነበራቸውና ፍላጐቱን ለማወቅ፣ የእነሱንም ሃሳብ ለማሳወቅ ቻሉ። ተፎካካሪአቸው ሶሺያሊዝም ሆነ። እሱን ለመቋቋም ሲባል በፓርቲነት መቋቋም አስፈለገ። ስለዚህ ፓርቲው መጋቢት 14 ቀን 1911 ዓ.ም /ማርች 23 ቀን 1919/ በይፋ ተቋቋመ። ፓርቲው የተቋቋመው በሚላን እንጂ በኢጣልያ ዋና ከተማ በሮም አልነበረም። የተመሰረተውም በሚላን ከተማ በአንድ የነጋዴያን ማህበር መሥሪያ ቤት በተሰበሰቡ 119 ሰዎች ነበር። ይሁን እንጂ በምሥረታው ጉባዔ ላይ የሃሳብ ልዩነት አላጋጠመውም። ነገርግን የሁሉን አስተያየት ለማስተናገድ በተደረገው ጥረት የመመሥረቻው ደንብ በጣም ልል ሆነ። ፓርቲው ፋሽዝም፣ አባላቱ ፋሽስት፣ ጽህፈት ቤቶቹ ፋሺ፣ መሪው ቢኒቶ ሙሶሊኒ ዱቼ /ጌታ/ ተባሉ።[1]

ከዚህ በኋላ ድጋፍ ሰጭ ሲቃውንት ተንቀሳቀሱ። ስሙን በተመለከተ በጥንት ዘመን ሮማውያን ለሚይዙት እንደ ፋስ መጥረቢያ ያለ መሳሪያ የሚያሠሩበት ጠንካራ ገመድ "ፋሺ" ይባል እንደነበሩ ድርሳናትን አገላብጠው አገኙ። ፋሽዝምም ሰዎችን ያስተባብራል የሚል ሃሳብ በመከተል ባሕላዊ ስሜትን እንዲቀሰቅስ አደረጉ። ቡድን ወይም ክበብ የሚለው የመጀመሪያው አስተሳሰብ በዚህ በአዲሱ ትርጓሜ ተተካ። ርዕዮተ ዓለሙን በተመለከተ ፋሽዝም የአዲስ ለውጥ አራማጅ፣ ለሀገር ጥቅም የሚሠራ፣ ድሆችን የሚታደግ እንደሚሆን አጠቃላይ ግንዛቤ ተገኘ። በወቅቱ የነበረው የኮሚኒዝም ርዕዮተ ዓለም ዓላማውን በሰላም በሥራ ላይ እንደሚያውል ሲቀሰቅስ፣ ፋሽዝም የሥርዓት ለውጥ ለማምጣት ኃይል አስፈላጊ እንደሚሆን አስታወቀ። ከዚህ ላይ እውነትን የመናገር ችሎታውን ማድነቅ ይገባል። በጦር ሜዳ፣ በባዕድ ሕዝብ ላይ የተፈፀመ በመሆኑ በኢትዮጵያ ላይ የፈፀመው ግፍ ካልተቆጠረበት በስተቀር፣ ፋሽዝም ከኮሚኒዝምና ከናዚስም የበለጠ የደም አፋሳሽነት ግብር አላሳየም። ነገር ግን ኮሚኒዝምና ናዚስም የገዛ ሕዝባቸውን በደም አጥለቅልቀው ስማቸው በክፉ አይነሳም። ፋሺዝም ግን መዘባበቻ ሆኖ ቀረ።

ሃሳቡና ግብሩ ተለያዩ። አዲስ የስርዓት ለውጥ የማምጣት ዓላማ ይዞ፣ ለዚህም የኃይል ሥራ አስፈላጊ መሆኑን አምኖ ተነሣ። ከምርጫም ውስጥ ገባ። በሚያዝያ 1913 ዓ.ም /1921/ በተደረገው ምርጫ ከ535 መንበሮች 35 /6.5%/ ብቻ አገኙ። ይቺን መቆናጠጫ እርካብ አድርጐ ወደ ሥልጣን ለመውጣት ተናፍቈረጨረ። አበጣበጠ፣ ደም አፋሰሰ። ስለዚህ አካሄዱ በልጆች ጨዋታ የውሬ፣የጭፍን የሚባለውን ዓይነት ሆነ። በሙሶሊኒ

ብርታትና በእርሱ ጠቅላይ ሚኒስትርነት ጥቅምት 20 ቀን 1915 ዓ.ም /30 ቀን 1922/ በትረ መንግሥት ቀማ።

በትረ መንግሥት በጨበጠም ጊዜ ማንኛውም አዲስ መንግሥት እንደሚያቀርበው ዓይነት የሥራ ፕሮግራም አቀረበ እንጂ፣ በርዕዮተ ዓለም ላይ የተመሠረተ የለውጥ ሥርዓት ለማምጣት አልሞከረም። ሙሶሊኒ ፋሽዝም ለሠራተኛው ወገን የቆመ በመሆኑ የመደብ ትግል ማካሄድና ካፒታሊዝምን መቃወም እንደሚገባው ከመግለጹ በቀር፣ በፓርቲ ደረጃ የተወሰደ እርምጃ አልነበረም። ሆኖም በድርጅት ረገድ ፋሽዝም ፈጣን ዕድገት አሳየ። ፓርቲው ከተቋቋመበት ከመጋቢት 1911 እስከ ጥቅምት ወር 1912/1919/ ዓ.ም ባለው ሰባት ወር ብቻ 149 ጽህፈት ቤቶች ከፈተ። በደምሩ 45000 አባላት አስባሰበ። ከዚያም በኋላ አቅዋሙን እያጠናከረ ሄደ።

ለውጥ አራማጅ መስሎ ሥልጣን ከያዘ በኋላ፣ ፋሽዝም ለውጥ ከማምጣት ይልቅ ሥልጣኑን ማጠናከርን አስቀድሞ፣ ንጉሡን ለመነቅነቅ አንዳች መከራ አላደረገም። እንዲያውም ባለምዋል ሆነ። ዐረ-ሐይማኖት አመለካከቱን ለወጠ፣ ከካቶሊክ ቤተ ክህነት ጋር ተስማማ። ከመኢንንቱ ክካህናቱ ተባበረ። እንደዚህ አድርጐ ከላይ ቤቶች ጋር ከተስማማ በኋላ ዓይኑን ወደ ታች ቤት አዞረ። ተቃዋሚዎችን ለመቆጣጠር ልዩ ጥረት አደረገ። ሃሳብን አስተያየትን በነፃ መስጠት ቀረ። ስብሰባና ሰልፍ ማድረግ ተከለከለ። ጋዜጠኞች ወደ ውጭ አገር ተሰደዱ። ዛቻና ማስፈራራት ዋና ሥራ ሆነ። ከ1918 ዓ.ም ጀምሮ ፋሺዝም ተቃናቃኝ የሌለበት ብቸኛ ፓርቲ ሆነ። ሙሶሊኒም ፈላጭ ቆራጭ ባለሥልጣን ሆነ።

ለፋሽስት ፓርቲና ለመሪው ለሙሶሊኒ ታማኝ ያልሆኑ ሠራተኞች ከሥራ የሚባረሩበት ደንብ ወጣ። ሙሶሊኒን መንካት በከፍተኛ ደረጃ የሚያስቀጣ ወንጀል ሆነ። ሕዝብ ጸጥ ሲል የፋሽዝም ትኩረት ወደ ምክር ቤት ዞረ። ለምክር ቤት የመወዳደርና የመመረጥ መብት ለፋሽስት አባላት ተሰጠ። በ1917 ዓ.ም ከምክር ቤት ወንበር ሁለት ሲሦው ከእነሱ እንዲሆን ተደረገ። ይህም የማይበቃ ሆኖ በ1919 ዓ.ም የመምረጥን መብት ሙሉ በሙሉ ለፋሽስት አባላት እንዲሆን የሚደነግግ አዋጅ ወጣ።

የዚህን ሕግ አወጣጥ ሥልት ማጤን ደግ ነው። የሕግ መምሪያው ምክር ቤት መቀመጫዎች 535 ነበሩ። የምርጫው ሕግ በተሻሻለበት ስብሰባ ላይ የተገኙት 231/43.2%/ ነበሩ። ምልዐተ ጉባዔ አልነበረም ማለት ነው። ለይሉኝ አይሉ ቢኒቶ ሙሶሊኒ ምልዐተ ጉባዔ አለመኖር ምንም አይደለም። ዋናው ነገር ከተሰበሰቡት አባላት 216/93.5%/ መደገፋቸው ብቻ ነው። የምርጫው ሕግ በዚህ ዓይነት ተለውጦ የመመረጥ መብት የፋሽስት ፓርቲ አባላት ብቻ ሆነ። የሕዝብ መብት በተወዳዳሪነት በቀረበው ግለሰብ ላይ "ይሁን አይሁን" ሆነ።

ይህንን ሕግ ለማስፈፀም በመላ ኢጣልያ አሥራ ሦስት የምርጫ መሥሪያ ቤቶች /ሴንዩሌትስ/ ተቋቋመ። የፓርቲውን ሥራ የሚያካሂድ ማዕከላዊ የፋሽስት ፓርቲ ምክር ቤት ተቋቋመ። የፓርቲ አባላት የሚመረጡት በዚህ ምክር ቤት ነበሩ። ለምሣሌ በ1929 /1933/ ዓ.ም ምርጫ፣ ለአባልነት ከአመለከቱት 600000 ግለሰቦች መካከል የተመረጡት 200000 ነበሩ። እነዚህም ለ10000 የፋሽስት መሥሪያ ቤቶች እንደየድርሻቸው ተከፋፈሉ። የምርጫው ጉዳይ በዚህ ዓይነት ተጉዞ ምክር ቤቱ በፋሽስት አባላት ተሞላ። ይህም ሆኖ የምክር ቤቱን ባሕርይ መቆጣጠር ስለአልተቻለ ከእነጭራሹ ተዘጋ። የፋሽስት ምክር ቤት ሙሉ ሥልጣን ያዘ። ነገር ግን እሱም የሚተዳደረው በሙሶሊኒ ሥልጣን ሆነ።

በሌላ በኩል አንዳንድ በጐ ውጤቶች ታዩ። ከታዩት በጐ ውጤቶች አንዱ ሮም የኢጣልያ ዋና ከተማ ከሆነችበት ከ1862 /1870/ ዓ.ም ጀምሮ ሲያጨቃጭቅ የቆየው የቤተመንግሥትና የቤተክህነት ክርክር በስምምነት ማለቁ ነበር። በስምምነቱ ከተጠቀሱት ጉዳዮች ጳጳሱ በሚሰጡት ሹመት መንግሥትን ሊያማክሩ፣ መንግሥት የጳጳሳቱን ደመወዝ ሊከፍል፣ ተሿሚዎቹ ለሀገሪቱ ለንጉሡና ለመንግሥቱ ታማኝነታቸውን በመሐላ እንዲያረጋግጡ፣ በመንግሥት ትምህርት ቤት የሃይማኖት ትምህርት ሊሰጥ፣ ቤተክርስቲያን ከፖለቲካ ጉዳይ ውስጥ ላትገባ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ነበሩ። በ1923 /1931/ ዓ.ም የካቶሊክ ክበቦች በመዘጋታቸው፣ በ1930 /1938/ ዓ.ም ደግሞ የዘር ልዩነት ሕግ በመውጣቱ ጳጳሱ ቅሬታ ቢሰማቸውም፣ ስምምነቱ እፎይታ አስገኘ።

በልማት ሥራዎችም ረገድ በፋሽስት አመራር አንዳንድ በጐ ውጤቶች ታዩ። ለድሆች ነፃ ሕክምና፣ ለገበሬዎች ድጋፍ የሚሰጥ ሥርዓት ተፈጠረ። ትምህርት ተስፋፋ። በ1913/1921/ ዓ.ም 3 ሚሊዮን የነበረው የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች ቁጥር በ1927/1935/ ዓ.ም ወደ 4.5 ሚሊዮን /50%/ ከፍ አለ። በመሠረተ ትምህርት መሥፋፋት በዚሁ በተጠቀሰት ሁለት ዘመናት የመሐይምናን ቁጥር ከ75% ወደ ዜሮ ወረደ። ነገር ግን መምህራኑ የፋሽስቱን ርዕዮተ ዓለም የተቃኘ ስለነበር፣ ትምህርት የፖለቲካ ሥራ ማካሄጃ መሣሪያ ሆነ። ከዚህም የተነሣ የወታደራዊ ሥልጠና ጠነከረ። የጦረኝነት መንፈስ ሠፈነ።

የዜግነት ስሜት ተጠናከረ። የቀድሞ የባህል ቅርሶች ተከበሩ። ብሔራዊ ታሪክ ክብር አገኘ። እንደ ዮልዮስ ቄሣር ለመሳሰሉ የቀድሞ መሪዎች ሐውልት ተቋቋመ። አዳዲስ መንገዶች ተሠሩ። ባቡር ተሻሻለ። ከሮም ከተማ በተጠረገው ቆሻሻ ከተሞላው ባሕር ላይ አሁን ፋዎንቺኖ እየተባለ የሚጠራው አይሮፕላን ማረፊያ ተሠራ።

በዚህ ላይ ደግሞ ንጉሡንና ጳጳሱን፣ መኳንንቱንና ካህናቱን፣ ሴቱንና ወንዱን፣ ልጁንና አዋቂውን መላዋን ኢጣልያን ያስደሰተ ሥራ ተከናወነ።

ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛትነት በመያዝ ፋሽዝም አበበ። ቀደም ብሎ በአንዳንድ የፖለቲካ ሰዎች አስተሳሰብ ይንከባለል የነበረው "ፋሽዝም ያሸንፋል እንጂ አይሸነፍም" የሚለው አመለካከት፣ በኢጣልያ ብቻ ሳይሆን በዓለም ጭምር ሠፈነ። ተቃውሞ አስተመ።

ሥልጣን ሲደረጅ ቀስ በቀስ ችግር ተፈጠረ። ባለሥልጣኖቹን ፍቅረ ንዋይ አደረባቸው። በተለይም ከኢትዮጵያ አስተዳደር ጋር ግንኙነት ባለው ሥራ የቆሙት፣ ለልዩ ልዩ ሥራ ከሚመደበው ገንዘብ አብዛኛው ከአንዳንዱም እስከ 81.4% ወደ እነሱ ኪስ መፍሰስ አመጣ።[2] ከዚህ ድርጊት ከሙሶሊኒ ከራሱ በስተቀር ሌሎች ነፃ አልነበሩም። ሙሶሊኒ ግን የፍቅረ ንዋይ ደዌ አልተጠናወተውም።

በባለሥልጣኖች መካከል የርስበርስ መናቆር ጠነከረ። የአመለካከት ልዩነት፣ የሥልጣንና የክብር ጥያቄ፣ የጥቅም ክፍፍሉሽ ሚዛን ዋናዎች የጠብ ምንጮች ሆኑ። በኢትዮጵያ ላይ በአለው እንደራሴና ሮማ በቅኝ ግዛት ጉዳይ ሚኒስትር መካከል የተካሄደውን ጭቅጭቅ ማጤን የነገሩን ክብደት ሊያስገነዝብ ይችላል።

ስብሰባዎች በሥነ ሥርዓት መካሄዳቸው ቀረ። ሙሶሊኒን ምቾትና የቤተሰብ ጣጣ አንቆ ያዘው። የመንግሥቱን ጉዳይ ትቶ ቁባቱን በማስታመም ከአንድ ወር በላይ ሥራ የፈታበትን ጊዜ በታሪኩ ውስጥ ተመልክቶአል። ተቆጣጣሪ ስለጠፋ የፓርቲው ውስጣዊ ሁኔታ እየተበላሸ ሄደ።

የፋሽስት ፓርቲ ተቃዋሚዎች በዚህ ሁኔታ በእጅጉ ተጠቀሙ። የፓርቲውን አቅዋም በሕዝብ ዘንድ ማስጠላት፣ ከውስጥም በልዩ ልዩ ዘዴ መቦርቦር ያዙ። በሉ በርቱ ባይ እንጂ፣ ተው ባይ ጠፋ። ንጉሡ ቀስ በቀስ ሥልጣኑን መልሶ ለመያዝ እጁን አስተዳደር ውስጥ ማስገባት ቀጠለ። ለምሣሌ ሂትለር ሮምን ሊጎበኝ ሲመጣ መስተንግዶው በርዕሰብሔር ደረጃ መካሄድ ስለነበረበት ንጉሡ አስተናጋጅ ሆነ። ጉብኝቱ መሶሊኒ እንደ አሰበው ሳይሆን ቀረ።

ቤተክህነትም ቀደም ከተፈረመው ስምምነት ሊገኝ ከሚችለው ፀጋ ከተቋደሰ በኋላ፣ በአንዳንድ ጉዳዮች ከመንግሥት ፖለቲካ ማፈንገጥ አመጣ። ለምሣሌ የዘር መድልዎን አዋጅ መቃወም። በዚያው ላይ ደግሞ የፋሽስት ፓርቲን ይደግፉ የነበሩት ጳጳስ አባ ፓየስ 12ኛ ሞተው፣ ፋሽዝምን የማይደግፉ ጳጳስ ተመርጠው ተሾሙ።

በኢትዮጵያ ጦርነቱ ከባድ ሆነ። ብዙ የተደከመባቸውና ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ የፈሰሰባቸው የልማት ሥራዎች ክንቱ ሆኑ። የፋሽስት ፓርቲ በሕዝብ እየተጠላ ሄደ። ፓርቲው እነዚህን ችግሮች ማቃለል ተሣነው። ከሙሶሊኒ አምባ ገነንነት መላቀቅም መቆጣጠርም አቃተው። የሙሶሊኒም የፖለቲካ ስሜት አውታሮች ደነዘዙ። የአእምሮው ጤንነት እስከሚያጠራጥር ድረስ ክፉን ከደግ መለየቱ ቀረ።

ኢጣልያ በዚህ ሁኔታ ላይ እንደአለች በአውሮፓ ጦርነት ተቀሰቀሰ። የሕዝቡን አንድነት የሚያሰባስብና ለሀገር ጥቅም ማስገኘት የሚችል አቅዋም መያዝ ግድ ሆነ። ከጦርነቱ ገለልተኛ መሆን የማይቻል ሆነ። ከእኔ ካልሆናችሁ ጠላቶቼ ናችሁ የሚለው የሂትለር ጥያቄ መደመጥ አስፈለገው። ከላይ በተጠቀሱትና በሌሎችም ጉዳዮች ተተብትቦ የታሠረውና የዛገው የፋሽስት ፓርቲ፤ ለችግሩ መፍትሔ ማግኘት ወይም ለጥያቄው መልስ መስጠት አቃተው። ስለዚህ በሙሶሊኒ ልዩ ውሣኔ ኢጣልያ ከጀርመን ጐን በመቆም ሰኔ 3 ቀን 1932 ዓ.ም ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ገባች። ከጦርነቱም ሊገኝ የሚቻለውን ያህል አገር ለመያዝ የፋሽስት ፓርቲ መከራ አደረገ። አልባንያንና ግሪክን ወረረ። ዩጐዝላቪያን ለመያዝ፤ የሜዲቴራኒያንን ባሕር ለመቆጣጠር ሞከረ። የአፍሪካን ቅኝ ግዛት ለማስፋፋት ጣረ። ይህ ሁሉ በፓርቲው ተሠራ ይባል እንጂ፤ በሙሶሊኒ ሃሳብና ጥረት ተደረገ።

ውሎ አድሮ ግን በሙሶሊኒ ላይ ጥፋት በዛ። ሐምሌ 1935 ዓ.ም /ጁላይ 26 ቀን 1943/ ከሥልጣን ወረደ። የፋሽስት ፓርቲም በዚያው ቀን አብሮት ከሥልጣን ወረደ። ከዚያ በኋላ እንኳን ለሥልጣን ሊበቃ፤ በፓርቲነት ሊቀጥል አልቻለም። ምንም ለፋሽስት ፓርቲ ፍቅር ቢኖረው ሙሶሊኒ በሂትለር አስገዳጅነት በሣሉ ከተማ አዲስ መንግሥት ያቋቋመው በፋሽስት ፓርቲ አልነበረም። በኢጣልያ ሶሻሊስት ፓርቲ /በሪፐብሊክ ሶሲያሌ ኢታልያና/ እንጂ። ከዚያም በኋላ በኢጣልያም ሆነ በማንኛውም ሌላ ሀገር ፋሽዝም በፓርቲነት አልተቋቋመም። በጭካኔ ምልክትነት የዓለም ኅብረተሰብ መዘባበቻ ሆኖ ቀረ።

ቀጣዩ ጥያቄ "ይህ ንቅናቄ እንደዚህ መሠረት የሌለው ሆኖ ሳለ፤ ጥንቱን እንደምን ለሥልጣን?" በቃ የሚል ይሆናል። የፋሽስት ፓርቲ ለሥልጣን የበቃው ራሱን በፓርቲነት በማጠናከር ሳይሆን፤ በሌሎች ላይ ችግር በመፍጠር እንደሆነ ተመልክተናል። ተከታዩ ጥያቄ "ችግር መፍጠሩንስ ቢሆን እንደምን ቻለው?" የሚል ነው። ለዚህ ጥያቄ የሀገሪቱን ጠቅላላ ሁኔታና በወቅቱ የነበረውን መንግሥት አቅዋም፤ እንዲሁም የሌሎች ፓርቲዎችን ባሕርይ አጠር ባለ ሁኔታ መቃኘት ያስፈልጋል።

ኢጣልያ አንድነትዋን መሥርታ ሮምን መናገሻ ከተማዋ ከአደረገችበት ከ1862/1870/ ዓ.ም ጀምሮ የምትተዳደረው በሊበራል ፓርቲ ነበር። ይህንን ፓርቲ የአድዋ ሽንፈት ቢያንገላታውም፤ ለዘብተኛ ከመሆኑ የተነሣ ተቃራኒ ኃይላትን እያስተባበረ፣ ተቃውሞን እየታገሰም ቆየ። የኮሚኒዝም እንቅስቃሴ እየተጠናከረ ሲሄድ ይህ ልል አስተዳደር ግራ እየተጋባ ሄደ። በእንደኛው የዓለም ጦርነት ከ1906 እስከ 1910 ዓ.ም /1914-1918/ ፤ መጀመሪያ ወደ ጀርመን በኋላ ደግሞ ወደ እንግሊዝ ወለም ዘለም በማለት ዳኑ። ነገር ግን ጦርነቱ ከአስከተለው ችግር ሊያመልጥ አልቻለም። ኢጣልያ በጦርነቱ በቂ ተሳትፎ ስለአልነበራት በቪርሳይ ውል ጥምዋን የሚያረካ ውጤት ሳታገኝ

ቀረች። ስድስት መቶ ሃምሣ ሁለት ሺህ ወታደሮችዋን አስፈጅታ። በዚህ የፖለቲካ ችግር ላይ የኢኮኖሚ ድቀት ደረሰ። ሥራ አጥ በዛ፣ ውንብድና ጠነከረ። ልዩ ልዩ ፓርቲዎች መንፈራገጥ ጀመሩ። ለዘብተኛ አስተዳደር የማይችላቸው ሆኑ። በጎዳር 1912 /1919/ ዓ.ም ጠቅላላ የምክር ቤት ምርጫ ተደረገ። ውጤቱ ጠንካራ መንግሥት ለማቋቋም ሳያስችል ስለቀረ፤ በሚያዝያ ወር 1913 /1921/ ዓ.ም ሌላ ጠቅላላ ምርጫ ተደገመ። እሱ ደግሞ የባሰ ሆነ። የሁለቱ ምርጫዎች ውጤት ከዚህ እንደሚከተለው ነበር።

	የ1912	%	የ1913	%
የምክር ቤት ወንበር	574	100	535	100
ሊበራል ፓርቲ	312	55	255	47
ሶሻያሊስት ፓርቲ	156	27	122	23
ሕዝባዊ/ፖፑላር/ ፓርቲ	101	17	107	20
ኮሚኒስቶች	-	-	16	3
ፋሽስቶች	-	-	35	7

በዚህ ዓይነት ገዥ የነበረው የሊበራል ፓርቲ የአባላት ቁጥር ቀነሰ። እነዚያውም ደግሞ እርስበርሳቸው የማይስማሙ ሆኑ።[3] አዳዲሶቹ ሶስት ፓርቲዎችም ራሳቸውን ችለው መንግሥት ማቋቋም አልቻሉም። የሕዝባዊ /ፓፑላር/ ፓርቲ አባላት የካቶሊክ እምነት ተከታዮች ሲሆኑ፤ ከሶሻያሊስቶቹ ብዙዎቹ ዝንባሌአቸው ወደ ኮሚኒስቶች ስለሆነ፤ ሁለቱ ፓርቲዎች በጥምር መሥራት አልቻሉም። ስለዚህ ፋሽስቶች በሙሶሊኒ የፖለቲካ ጥበብ በመጠቀም ጥቅምት 17 ቀን 1915 ዓ.ም /አክቶበር 27 ቀን 1922/ ሮም ከተማ በለልፍ በመግባት፤ በምርጫ በተገኘው የ7% የፖለቲካ አቅም ያለአንዳች ርዕዮተ ዓለም ሥልጣን ያዙ። የፋሽስት ፓርቲ መና የቀረው ግብሩ ብቻ ሳይሆን አነሳሱም ጭምር እንደዚህ መናኛ ስለነበር ሳይሆን አልቀረም።

ፋሽዝምን በተመለከተ የመጨረሻውና ዋናው ጥያቄ "ለመሆኑ ርዕዮተ ዓለሙ ምን ነበር?" የሚል ነው። ዋናው የፋሽዝም የፖለቲካ ጥበብ በአንድ በተወሰነ ርዕዮተ ዓለም አለመታሠር ነው። እንዳሻ ለመሆን፤ እንዳሻ ለማድረግ እንዲያመች። ሌሎቹ ፓርቲዎች በተለይም ኮሚኒዝም በጠነከረ ርዕዮተ ዓለም ላይ ተመሠርቶ በመንቀሳቀሱ፤ ፋሺዝምም ርዕዮተ ዓለም እንዲኖረው አስገድዶታል። በመሆኑም ሥልጣን በያዘ በአሥር ዓመት፤ ማለትም በ1921/1933/ ዓ.ም ሙሶሊኒ የፓርቲ መመሪያ አውጣ። እሱም፣

1ኛ. ሰብዓዊ አመለካከቶችን ሁሉ መጠራጠር፣

2ኛ. የሰውን የተፈጥሮ እኩልነት መካድ፣

3ኛ. ዓላማን ከግብ ለማድረስ በሂሰትም፣ በኃይልም መጠቀም፣

4ኛ. በምሑራን የሚመራ መንግሥት ማቋቋም፣

5ኛ. ሥራን በአንድ ወጥ አመራር ማካሄድ፣
6ኛ. የዘርን ንጽሕና መጠበቅና የበላይ ገዥነትን ማራመድ፣
7ኛ. ዓለም አቀፍ ህግጋትንና ሥርዓቶችን መዋጋት ነበሩ።

የእነዚህ መርዛማ ሰባት "ቃላት" ውጤት፣ የኢጣልያን ሕዝብ በአምልኮተ እግዚአብሔር ከጸኑ ሥርዓቶች ውጭ አደረገው። አምባገነኑ መሪ፣ ማለትም ሙሶሊኒ ምንጊዜም ትክክል ነው የሚል አስተሳሰብ ቀርጸ። የሰውን የተፈጥሮ እኩልነት ደመሰሰ። የዘር መበላለጥን አሰፈነ። እንኪን ወታደር ለመሆን ውጣቶቹን ለወታደርነት ሥራ ለማዘጋጀት አይችሉም በሚል አመለካከት፣ ሴቶቹን ከማንኛውም ሥራ ከአስተማሪነት ጭምር አገዳቸው። የኃይልና የውሸት ሥራን አነገሠ። የሕዝቡን የዕለት ኑሮ ከአዋቂዎች ነን ባዮች ቅዠት ውስጥ ከተተው። ሃይማኖትን፣ ትምህርትን፣ ልዩ ልዩ የመተዳደሪያ ሥራዎችን፣ ንግድና እርሻን ጭምር ከፖለቲካ መዘውር ውስጥ አስገባቸው። መንግሥቱን ከሌሎች መንግሥታት ጋር አፋጭቶ ከዓለም ማኅበር አስወጣው። በመጨረሻም ኢጣልያን ከውድቀት አደረሳት። ፋሺዝም በጀርመን፣ በጃፓን፣ በአርጀንቲናና በሌሎችም አገሮች ያላየው ባሕርይ ልዩነትም ተመሳሳይነትም አለው። እኛ ግን ወደዚያ አንሸጋገርም።[4]

ማጣቀሻ ፅሑፎች

1. Stanley Cooperman, *Mussolini Research Notes*, pp.25-32.
2. የኢትዮጵያ ገበሬዎች የመሬት ግምት አከፋፈል።
3. Carlton Hayes, *Contemporary Europe*, pp.569-571.
4. William Einstein, *Today's Isms*, pp. 100-126

አባሪ ሠሌዳ *
የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦርነት ያስከተለው የኢኮኖሚ ጉዳት
በኢትዮጵያ ላይ የደረሰ ጉዳት

1. በመንግሥት ላይ ለደረሰው ጉዳት ካሣ የተጠየቀበት[8]

1.1 ለጦር መሣሪያ የወጣ	268,131,550
1.2 ሳይገባ የቀረ ግብር	254,028,680
1.3 የተለያዩ ኪሣራዎች	1,325,300,000
የቁጥር 1 ድምር	1,847,460,200

2. በሕዝብ ላይ ለደረሰ ጉዳት ካሣ የተጠየቀበት[9]

2.1 ለተቃጠሉ 2000 ቤ/ክ/ኖች	20,000,000
2.2 ለተቃጠሉ ቤቶች	105,000,000
2.3 በጦርነቱ ለሞቱ 257 ሺህ ወታደሮች	275,000,000
2.4 ለሞቱ አርበኞች	78,500,000
2.5 ለሞቱ ሴቶችና ሕፃናት	17,800,000
2.6 የካቲት 12 ቀን 1929 ለሞቱ 30 ሺህ ሰዎች	30,000,000
2.7 ተማርከው ለተገደሉ 24 ሺህ አርበኞች	24,000,000
2.8 በአሥራት ለሞቱ 35 ሺህ ሰዎች	35,000,000
2.9 በስደትና በረሀብ ላለቁ 300ሺህ ሰዎች	300,000,000
2.10 ለ5 ሚሊዮን የቀንድ ከብት.	250,000,000
2.11 ለ7 ሚሊዮን በግና ፍየል	70,000,000
2.12 ለ1 ሚሊዮን ፈረስና በቅሎ	50,000,000
2.13 ለ700 ሺህ ግመሎች	70,000,000
የቁጥር 2 ድምር	1,325,300,000

3. በሕዝብ ላይ ከደረሰው ጉዳት ካሣ ሳይጠየቅ የቀረ[10]

3.1 በኢትዮጵያ ስደተኞች ከሀገር የወጣ	10,000,000
3.2 በኢጣልያኖች የተወሰደ	50,000,000
3.3 በእንግሊዞች የተወሰዱ	50,000,000
3.4 የጣልያን ወታደር የዘረፈው	37,500,000
3.5 ሕዝብ የተዘራረፈው	3,000,000
3.6 ለገበሬ ሊከፈል ተፈቅዶ ሳይከፈል የቀረ	2,175,300
3.7 ከ50 ሺህ እሥረኛ የባከነ የሥራ ጊዜ	18,250,000

3.8 ለ213000 የመንገድ ሠራተኞች ሳይከፈል	8,520,000
3.9 ለ920000 ባንዳ አገልግሎት የቀረ	92,000,000
3.10 ለ450000 ሥራ የፈታበት	82,125,000
3.11 ለ16000 ስደተኞች ሥራ የፈታበት	11,680,000
3.12 ለ30000አካለ ጕደሎ	82,125,000
3.13 የ3 ሚሊዮን አራዊት ዋጋ ድምር	60,000,000
3.14 የኢጣልያኖች ከሕዝብ የገፈፉት መሣሪያ	86,762,200
3.15 ከአዲስ አበባ እስከ ኮረም የተሠራውን መንገድ	30,000,000
በኢትዮጵያ ላይ ደየረሰ የቁ.3 ድምር	894,137,700
ጠቅላላ ድምር	4,066,897,900

የፀሐፊው አጭር የሕይወት ታሪክ እና ፎቷቸው

የእኔ የአቶ ተድላ ዘሙሐንስ ዘውዴ የሕይወት ታሪክ ባጭሩ ከዚህ እንደሚከተለው ነው።

1. የልደት ቦታ መገሬ ዛለ፣ ቡልጋ፣ ሸዋ።
2. የአምስት ዓመት አርበኛ። ባልደረብነት የፊታውራሪ ወልደፃድቅ ዘውዴ ሀብቴ።
   ትምህርት፣
   ሀ. በኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን እስከ ጸመ ድጓ /ከመምህር ጌታሁን/ ብፅዕ አቡነ ጢሞቲዎስ፣ ሊቀ ጳጳስ ዘሰ.ጳ።
   ለ. በዘመናዊ ትምህርት ቢ.ኤ ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ /አዲስ አበባ/ ዩኒቨርስቲ በኤክስቴንሽን።
3. በመንግሥት ሠራተኛነት 42 ዓመት ከ3 ወር፣ ከመስከረም 1942 እስከ ጎንደር 1984 ዓ.ም። በትምህርት ሚኒስቴር እስከ ዋና ዳሬክተርነት፣ በመንግሥት ሠራተኞች ማስተዳደሪያ ጠቅላይ መሥሪያ ቤት በምክትል ኮሚሽነርነት፣ በኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ዋና ሥራ አስኪያጅነት ማዕረግ።



አቶ ተድላ ዘሮሐንስ ዘውዴ

ዋቢ መጻሕፍት

የአማርኛ መጻሕፍት

የማስታወቂያና ቱሪዝም ሚኒስቴር፣ *የኢትዮጵያ የድል መታሰቢያ 25ኛ ዓመት፣ ከ1933 እስከ 1958 ዓ.ም*፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፣ 1958 ዓ.ም።

ታደለ ዘወልዴ /ቀኛዝማች/፣ *ቀሪን ገረመው፣ የአርበኞች ታሪክ*፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ 1960 ዓ.ም።

ታደለ ሜጫ፣ *ጥቁር አንበሳ በምዕራብ ኢትዮጵያ*፣ አሥመራ፣ ኩሪየራ ኤረትራዮ ማኅበር ማተሚያ ቤት፣ ኮ 1953 ዓ.ም።

ፊሊቀ ዳኜ /ፊታውራሪ/፣ *አምስቱ የመከራ ዓመትና ፍፃሜው አጭር ማስታወሻ*፣ ሁለተኛ እትም፣ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ ሐምሌ 1944 ዓ.ም።

ጳውሎስ ኞኞ፣ *የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦርነት*፣ አዲስ አበባ፣ ቦሌ ማተሚያ ቤት፣ መስከረም 1980 ዓ.ም።

ጳውሎስ ኞኞ፣ *አጤ ምኒልክ*፣ አዲስ አበባ፣ ቦሌ ማተሚያ ቤት፣ 1984 ዓ.ም።

ተክለፃድቅ መኩሪያ፣ *የኢትዮጵያ ታሪክ፣ ከአፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ*፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ 1961 ዓ.ም።

ሽፈራው መንገሻ፣ *የኢትዮጵያ የታሪክ ጉዞ*፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ 42ኛ ዘመን።

ሙሉ ለው ምትኩ /አዛዥ/፣ *የአርበኞች ትግል ከፋሽስት ጋር፣ ከሸዋ እስከ ሱዳን ጠረፍ*፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1937 ዓ.ም።

አክሊሉ ገብረ ኪሮስ /አፈ ሊቀ ሊቃውንት/፣ *ዜና ባስለዮስ፣ ሊቀ ጳጳሳት ኢትዮጵያዊ*፣ አዲስ አበባ፣ ትንሣዔ ዘጥዋዔ ማተሚያ ቤት፣ ሰኔ 10 ቀን 1950 ዓ.ም።

የኢሉባቡር ኢሠፓ ኮሚቴ፣ ስ10ኛው አብዮት በዓል የተዘጋጀ "የኢሉባቡር መድበለ ታሪክ"፣ ነሐሴ 1975 ዓ.ም።

እንዳለ ቢረሳው /ሊቀ ጠበብት/፣ "በኢጣልያ ጦሬ ከተማ ስለተገደሉ ሰዎች የተፃፈ ማስታወሻ" /የእጅ ጽሑፍ/፣ ጎንደር 1929 ዓ.ም።

አሐዱ ሣቡሬ፣ *ስታሪክ ማጎደር*፣ ኢትዮጵያን ሬቪው መጽሔት፣ ቅጽ 2፣ ቁጥር 2፣ አዲስ አበባ፣ የካቲት 1991 ዓ.ም።

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ /ንጉሠ ነገሥት/፣ ሕይወቱና የኢትዮጵያ እርምጃ፣ አንደኛ መጽሐፍ፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ 1965 ዓ.ም።



አቶ ተድላ ዘዮሐንስ ዘውዴ

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ /ንጉሠ ነገሥት/፣ *ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ፣ ሁለተኛ መጽሐፍ*፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ 1966 ዓ.ም።

መኮንን እንዳልካቸው /ራስ ቢትወደድ/፣ *መጽሐፍ የዓለምን ምሬት ማጣፈጫ ማር ነው*፣ አዲስ አበባ፣ ቅዱስ ጊዮርጊስ ማተሚያ ቤት፣ 1960 ዓ.ም።

የሮማ ብርሃን፣ አዲስ አበባ፣ የጥር 1932 ዓ.ም እትም።

የራስ ቲያትር የሕዝብ ግንኙነት ማስታወቂያ፣ *የፊልም ጥበብ በኢትዮጵያ*፣ አዲስ አበባ፣ ሴንተራል ማተሚያ ቤት፣ 1976 ዓ.ም።

ይልማ ማናዬ፣ *ገሞራው ዘርዓይ ደረስ*፣ አዲስ አበባ፣ ቅዱስ ጊዮርጊስ ማተሚያ ቤት፣ 1964 ዓ.ም።

ዘውገ ዘገየ፣ *ለባ ኦስትር፣ የደግናው የበላይ ዘለቀ ታሪክ*፣ አዲስ አበባ፣ ቦሌ ማተሚያ ቤት፣ ጎንደር 1983 ዓ.ም።

ሕይወት ጎዳሩ /ፊታውራሪ/፣ *ያቺ ቀን ተረሣች*፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1967 ዓ.ም።

ተክለ ማርያም /አባ/፣ *የምስክየ ሕዙናን ገዳም አመሠራረት*፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ በ41ኛው የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት።

ታደሰ ዘወልዴ /ቀኛዝማች/፣ *የአባላሸኝ ዘመን*፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ 1955 ዓ.ም።

ተክለ ዓድቅ መኩሪያ፣ *አፄ ምኒልክ እና የኢትዮጵያ አንድነት*፣ አዲስ አበባ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፣ 1983 ዓ.ም።

አያሌው እምሩ /ሊቀ ጠበብት/፣ *መኾ ተሰመደና ክተኩሳ ዝምድና*፣ አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባዔ ማተሚያ ቤት፣ 1953 ዓ.ም።

ፍካሬ መጽሔት፣ አንደኛ ዓመት ቅጽ 1፣ ቁጥር 1፣ የካቲት 1985 ዓ.ም።

ላጲስ ጌታቸው ደሌቦ፣ *የኢትዮጵያ ረድም የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ*፣ *ሰንደኛ መጽሐፍ*፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፣ 1983 ዓ.ም።

መድረክ መጽሔት፣ ቅጽ 1 ቁጥር 1፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፣ ሚያዝያ 1985 ዓ.ም።

ክፍሉ ጽዮን ማሞ፣ *የጦር ወንጀል ምንድነው?* ማስዳ መጽሔት፣ ቅጽ 1 ቁጥር 2፣ ጥር 1985 ዓ.ም ።

አደፍርስ አየለ፣ *ጦቢያ* መጽሔት፣ መስከረም 1985 ዓ.ም።

ተክለፃድቅ መኩሪያ፣ *የኢትዮጵያ ታሪክ*፣ *ኑብያ /ናፖታ-መርዌ/*፣ *አንደኛ መጽሐፍ*፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ የካቲት 1 ቀን 1965 ዓ.ም።

ይልማ ደሬሳ፣ *የኢትዮጵያ ታሪክ በአሥራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን*፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ ጎንደር 20 ቀን 1959 ዓ.ም።

ገብረሥላሴ ወልደ አረጋዊ /ፀሐፊ ትዕዛዝ/፣ *ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ*፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ፣ 1959 ዓ.ም።

ጥንታዊት ኢትዮጵያ አገራዊ የደግኖች ማኅበር፣ *ማኅበረ ሰማዕታት መዋዕያን*፣ *መሠረታዊ ደንብ*፣ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1956 ዓ.ም።

ጀርጅ ኤፍ ኤች በርክሌይ፣ ትርጉም ዳኜው ወልደ ሥላሴ፣ አዲስ አበባ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1979 ዓ.ም።

ቢ. ዴዝሞንድ፣ የኢትዮጵያ አርባ ኩንታል ወርቅ የት ደረሰ? ትርጉም፣ ታደሰ በየነ እርገጤ፣ ብራና ኤሌክትሮ አሳታሚ፣ አዲስ አበባ፣ 1985 ዓ.ም።

ሙራድ ከማል /ዶክተር/፣ የፖርቹጋሎች ጀግንነት፣ ትርጉም ዮናስ ቦጋለ፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ 1952 ዓ.ም።

ጆን ሐዛወይ ስፔንሰር፣ *ጥርስ የገባች ሰገር*፣ ትርጉም መንግሥቱ ኃይለማርያም አርአያ /ሌ.ኮ/፣ መዝገቡ ምትኬ ቢልልኝ፣ ጎንደር 1986 ዓ.ም።

ጋስፖሬኒ ገ.ማ /አባ/፣ የኢትዮጵያ ታሪክ፣ አሥመራ አርቲግራፊክ ማ.ቤት፣ ለ25ኛው ዓመት በዓል ለቀዳማዊ ኃይለሥላሴ አምላ የቀረበ።

ግርማ ዘውዴ፣ *ኢትዮጵያን*፣ ት.መ.ማ.ማ ድርጅት፣ የካቲት 1985 ዓ.ም

English Books

Araya Habtay. *The Role of Eritrean Askaris In the Italo-Ethiopian War.* H.S.I.U., A.A. 1970.

Bahru Zewde. *A History of Modern Ethiopia.* A.A.U. Press; 1992.

Campbell, John C. *Defence of the Middle East.* The Harold Praff House; New York, 1960.

Churchil, Winston S. *The Grand Alliance.*Houghton Mifflin Co.: London, 1950.

Cooperman, Stanley. *Mussolini.* Monarch Press Inc; New York.

Einstein, William. *Today's ISMS.* Prentice Hall Inc.; California, 1964.

Frusci, Luigi. *Sue Fronte Meridianale.* Cappelli, Lichinia (ed); Bologna, Italy.

Greenfield, Richard. *Ethiopia, A New Political History.* Frederick A. Praeger; New York, Washington D.C London, 1965.

Hayes, Carlton J.H. *Contemporary Europe since 1870.* The Macmillan Co; New York, 1958.

Mosely, Leonard. *Haile Selassie.* Wedenfled and Nicolson; London, 1964.

Pankhurst, Sylvia. *Ethiopia: A Cultural History.* Lolivela House; London, 1955.

Pankhurst, Sylvia.*Why Do we Destroy Ethiopian Ports?*

Petrides, Pierre. *The Boundary Question between Ethiopia and Somalia.* Peoples Publishing House; New Delhi, 1983.

Rubenson, Sven. *The Survival of Ethiopian Independence.* Kuraz Publishing Agency; Addis Ababa, 1991.

Sabacchi, Alberto. *Ethiopia under Mussolini, Fascism and the Colonial Experience.* Z Books Ltd.: London, 1985.

Skordiales, Kiman. Kagnew. *The Story of Ethiopian Fighters in Korea.* Radio Press: Tokyo, 1954.

Steer, George L. *Sealed and Delivered.* Hodder and Stovghton Ltd: London, 1942.

Vellari, Luigi. *The Ethiopian Crises.* Health and Co.; Boston.

ኢጣልያ በኢትዮጵያ ስሚሰው መጽሐፍ የምስክርነት ቃል የሰጡ

1. **ተካነ ባንቲ /መልአክ መዊ0/**
   በ1985 ዓ/ም ተጉስት፣ የድንባሮ /ማንባርሞ/ ማርያም አለቃ የደብረ መዊዕ ቅድስት ማርያምን ጽላት በቅስና ሥልጣን፣ ታቦትዋን ይዘው ማይጨው የዘመቱ፣
2. **በየነ ደምሴ /መምሬ/**
   በቅስና ሥልጣን የአራዳ ደብረ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ጽላት ይዘው ከባላምባራስ /ራስ/ አበበ አረጋይ ጋር ተቀላቅለው እስከ መጨረሻው ታቦቱን ይዘው በአርበኝነት የሠሩ አርበኞች።
3. **ሥዩም ያዕቆብ /አቶ/**
   ኤርትራዊ፣ የኢጣልያኖች ሃሳብ፣ በኢትዮጵያ ላይ ስመዝመት መሆኑን በተኩስ ልምምድ አስመስለው ለወገኖቹ በፊሊፕ ያስረዳውን ኤርትራዊ የሚያውቁ።
4. **ደምሴ አብዮ ሆይ ቄርሎስ /መምሬ፣ በጊላ ደግሞ አባ/**
   በጦርነቱ ጊዜ የባላምባራስ /ራስ/ አበበ አባ ነፍሱ፣ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ለራስ አበበ የላኩአቸውን መልእክቶች፣ ከኢጣልያ ጋር የሚደረገውን የመደለያ ዓርቅ ምሥጢር፣ እንደዚሁም የንጉሠ መልአክ ፀሐይን አሟሟት ለማጣራት የተደረገውን ሙከራ የሚያውቁ ቆስለው በመማረክ ሞቃድሾ የታሠሩ አርበኛ።
5. **ወልደ ፃድቅ ሽንቁጤ፣**
   በፊታውራሪ ወልደ ፃድቅ ዘውዴ ባልደረብነት የቡልጋ አርበኛ።
   ገልጌላ በተሰጠው የጦር ሥልጠና የተካፈሉ።
6. **መልአክ በቀለ ዘውዴ /ሻለቃ/**
   በዕርቅ ጊዜ ከቡልጋ ከአርበኞች ቡድን ጋር አዲስ አበባ የገባ።
7. **ንጋቱ ወልደ ዮሐንስ፣ ዘመዴነህ /አቶ/**
   ሰኔ 15 ቀን 1931 ዓ/ም ከደባ ጉጀ፣ ሸንኮራ፣ አልቂት ድኖ የ50 ዓመት መታሰቢያውን ሰኔ 15 ቀን 1981 ዓ/ም በማክበር የአልቂቱን ሁኔታ ያስረዳ።
8. **አባ ገብረ መስቀል /አቡነ ዮሐንስ ሲቀ ጳጳስ ዘትግራይ/**
   በቀጨኔ መድኃኔዓለም አለቅነታቸው ተጠርተው ኢጣልያኖች አዲስ አበባ ላይ ለመዋጋት የነበራቸውን ሃሳብ በምክር ያፈረሱ።
9. **እንቁ ኃይለ መስቀል /ኩሉኔል/**
   ደጃዝማች ፊቀረ ማርያም በወደቁበት በራምቡቲው ጦርነት የተካፈሉ፣ በኋላም የኬንያ ስደተኛ።
10. **ይላቅ ጌታነህ /የ50 አለቃ/**

ሸዋ፣ ሽንኮራ፣ ከራምቡቲ ጦርነት የተማረኩት አርበኞች በመርዝ መገደላቸውን ያየ።

11. **ኃይሌ ዳርጌ /ማራዝማች/**
የቀድሞ ስሙ የኂላእሸት ኃይሌ የነበረውን መልአከ ፀሐይ ኢያሱ፣ ምኒልክን ከአብሮ ገዳም ካወጡት የቡልጋ አርበኞች አንዱ።
እንደዚሁም መጽሐፍ የተማረከበትን ሁኔታ የሚያውቅ።

12. **ቀጸላ አባትዩ /አቶ/**
በዲቁና ሥልጣን መልአከ ፀሐይ ኢያሱን ጭንቁት ማርያም፣ ቡገሬ ዛለ፣ ቡልጋ፣ ሥጋ ወደሙ ያቀበለ።

13. **በቃሉ ተገኘ /አባ/**
ጐጃም፣ ገና ሐይቅ አራ ኪዳነ ምህረት አንድ የጣልያን የጦር አዛዥ በገባ ጊዜ ከመቅደሱ በር ወድቆ መሞቱን ዲያቆን ሆነው ያዩ።

14. **እሸቴ ባዩ /አቶ/**
ወደ ኬንያ የተሰደዱና በዚያ የደረሰውን ሁኔታ የሚያውቁ

15. **መኮንን ደነቀ /ጀነራል/**
ንጉሠ ነገሥቱ ወደ ስደት ሲሄዱ እስከ ድሬዳዋ ድረስ ያወረዱአቸውን መኪንንት በመቶ አለቅነት የተረከቡ ፖሊስ።

16. **ዓለመ ሥላሴ ገላ /አቶ/**
በሞቃድሶሾ አሥረኛ የነበሩና፣ በዚያ የነበረውን አበሳና ሥቃይ የቀመሱና ያዩ።

17. **ወልደ ጊዮርጊስ ኪሮኔ /መ.አለቃ/**
በፊታውራሪ ወልደ ዓድቅ ዘውዴ ባልደረብነት፣ የቡልጋ አርበኛ። ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ባቃጠለ በአንድ ላይ ፍርድ በተሰጠ ጊዜ የነበረ። የፊታውራሪ ዝቅ አርጋቸውንና የፊታውራሪ ሞገሴን አሟሟት የሚያውቅ አርበኛ።

18. **ጌታቸው በቀሰ ዘውዴ /አቶ/**
የመድፍ አፈሙዝ ከእንጨት ተፈልፍሎ መተኮሱን ያየ የቡልጋ አርበኛ።

19. **ኃይሌ ወልደ ዓድቅ /ፊታውራሪ/**
መልአከ ፀሐይ ኢያሱን ለማንገሥ በተደረገው ምክር ላይ የነበሩና ያነገሡ፣ በኂላም ለአካባቢው ሕዝብ አዋጅ የነገሩ የቡልጋ አርበኛ።

20. **ሠርጤ፣ ወልደ ዓድቅ /ሻለቃ/**
እነ ፊታውራሪ አጉናፍር መደዲማ ላይ በርስ በርስ ጠብ ያለቁበትን ምክንያትና የፈጃቸውን የሚያውቁ የቡልጋ አርበኛ።

21. **ልሣነ ወርቅ ተስፋዬ /አቶ/**
መልአከ ፀሐየ ኢያሱ በታመሙ ጊዜ ሠራዊቱ በሲቋ መኪስ አሱላ መመራቱን ያዩ የቡልጋ አርበኛ።

22. **ምሥካየ ሥዩም ተክሌ /ቀኛዝማች/**
ደጃዝማች ፍቅረ ማርያም አዲስ አበባን ያጠቁበትን ሁኔታና እንደዚሁም በአራን ቡቲ ጦርነት ላይ መሞታቸውን ለቡልጋ አርበኛ ነጋሮ ዲደታ ቡልጋ በአርበኝነት የሞተ።

23. **ሞላ ገዘሙ /አቶ/**
በአራንቡቲ ጦርነት ላይ የተካፈሉና ደጃዝማች ፍቅረ ሥላሴ ወደ ሣማ ለንበት ዋሻ እንደገቡ ለቤት አሽከሮቻቸው ሲነገር የሰሙ።

24. **መኮንን ወልደ ሚካኤል /አቶ/**
መልአከ ፀሐይ ኢያሱ ጀሎ አገር ማርያም በእጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ እጅ በድጋሚ ተቀብተው ነጉሠ ነገሥት መባላቸውን በደብተርነት ማኅሌት በመቆም ያዩ የቡልጋ አርበኛ።

25. **ቃለ ክርስቶስ ዓባይ /ኩሉኔል/**
የትግራይ አርበኞች ከማይጨው ጦርነት በኂላ እንደምን ወደ አገራቸው ወደ ትግራይ እንደተመለሱ የሚያውቁ።

26. **በቀለ ፀጋዬ /አቶ/**
ከእነ ፊቴውራሪ ወንድምነህ ጋር ተጉለት ተማርከው ለመረሸን ከቀረቡ በኂላ አዛዡ ኢጣልያዊ ከሞት ካዳናቸው በኂላ አምልጠው አርበኝነታቸውን የቀጠሉ።

27. **ወልደ ገብርኤል ወልደ ሚካኤል /አቶ/**
በደጃዝማችነት አውራሪስ ዱሉ ባልደረብነት የመንዝ አርበኛ። ደጃዝማቹ ጠሳት ከተባረረ በኂላ በብስጭት መሞታቸውን ያየ።


RED SEA
N
AFRICA
ERITREA
SUDAN
ARABIA
Dahlak Archipelago
Asmara
Massawa
Keren
Adigrat
Makele
GONDER
TIGRAY
Gondar
WELO
DJIBOUTI
GULF OF ADEN
GOJAM
Debre Markos
SHEWA
Addis Ababa
SOMALIA
Harar
WELEGA
Nekemte
ARSI
Asella
HARERGE
ILUBABOR
Mettu
Jimma
Ambo
Gedeo
KEFA
Arba Minch
GAMO GOFA
BALE
SOMALIA
SIDAMO
SUDAN
KENYA
0 100 200 300 Kilometers
0 50 100 150 Miles

የታሪክ ጥናት ተቀዳሚ ሚና የህብረተሰብን አላፊና ዘላቂ አሴቶችን መመርመርና በነዋሪ አሴቶቹ ላይ ማቆም ነው። ታሪክ በአንድ አገር ብሔራዊ ጉዳዮች ላይ ሁነኛ ሚና እንዲጫወት ከተፈለገ በትንሹ ሁለት ቅድመ ሁኔታዎችን ማሟላት አለበት። አንደኛ ለታሪክ ጥናት የማያወላውል መስጠትና ታማኝነት። ሁለተኛ የላቀ የህገር ፍቅርና አላማ። እነዚህ ፍጹም ባልተዋሃዱበት የሚጻፍ ታሪክ ሚዛን ያልጠበቀና ረብ የለሽ ከመሆን አይድንም።

እንዳለመታደል የኢትዮጵያ ዘመናዊ ሥነ-ታሪክ ገና ከጮርቃ እድሜው ላለፉት አራት አሰርት ዓመታት በተግራራ ርእዮች ከግራ ቀኝ በመ ንገላታቱ ዘመን የሚያሻግር ብሔራዊ ራእይ ለመያዝ አልቻለም። ቢብዙ ድካም የተሰሩ ጥናቶች ከአካዳሚያዊ ንፍቀ ክበብ ባለፈ ህዝባዊ ተደራሽነት ሊኖራቸው አልታደሉም። ምናልባት በበጎ ጎኑ አካዳሚያዊ የታሪክ ጥናትና ዘገባ ራሱን በገሃድ "የአሸናፊዎች ደንገጡር" ከመሆን ተከላከሏል ማለት ይቻል ይሆናል።

ከዚህ አካዳሚያዊ ቅጥር ውጭ ታሪክን በትርፍ ጊዜያቸው የሚመረምሩና የሚጽፉ በርካታ ዜጎች አሉን። "ዘልማዳውያን" በሚል የሸመጥ ፈርጅ ይታወቃሉ። እነዚህ ጸሐፍት ህዝብን ተደራሲ በማድረግ፣ በራሱ ቋንቋ በመቅረብና ለ"መንግሥታዊ" ታሪክ አማራጭ በማቅረብ ረገድ የማይናቅ ተግባር አከናውነዋል።

የዚህ የኢትዮጵያና የጣልያን ጦርነት በሚል ርዕስ የተጻፈ ታሪክ ደራሲ ተድላ ዘዮሐንስ ዘውዴ በዘመናቸው ያዩትንና የሰሙትን የአንድ ጀግና ትውልድ ታሪክ ከመዛግብትና ከሰዎች ምስክርነት ጋር በማወራረስ ከፍተኛ ዋጋ ያለው ስራ አቅርበዋል። እጅግ እንደደከመበት አያጠራጥርም።

በተለይም ደግሞ እንዲህ አይነት ብሔራዊ አንድምታ ያላቸው ርእሶች በአገር የታሪክ ባለሙያዎች "አይኬ" ሆነው በመቆየታቸው፤ ኢትዮጵያውያን የዝ ታሪካቸንን የወቅቱ ባለጋራችን ከነበረችው ከጣልያን ምሁራን የማንበብ አሳፋሪ ግዴታ ውስጥ ነበርን። ደራሲው እጅግ የተበታተነውንና ለፈውን የአርበኝነት ዘመን ተጋድሎ ከኢትዮጵያውያን ወገን ብሔራዊ ቅርጽ ሰጥተው አቅርበውልናል። በከፍተኛ ቀናኢነት የተጻፈ ቢሆንም ሚዛኑን የጠበቀ ነው።

ደራሲው ተድላ ዘዮሐንስ የቱንም ያህል ተመልካች ፈረንጅችና ባይተዋር ትውልዶች ሊያሳዩን ያልቻሉትን የጊዜውን መንፈስና ህይወት በየመሃሉ ብልጭ ያደርጉልናል፤ ያስገርሙናል ያዝናኑናል። ቋንቋቸው ባለዜማ ነው፤ ምናልባት ታላቁን ተከለጻድቅ መኩሪያን ያስታውሰናል። ባለውለታችን ናቸው ብዮ አምናለሁ።

መጽሐፉ ከዘመናዊ የታሪክ አጻጻፍ ረገድ በመረጃና ተጠየቅ፣ በዘገባ ስልትና ንድፈ ሃሳባዊ መሰረት እንከን የለሽ ነው ባይባልም፤ በኢትዮጵያና በጣልያን ጦርነት ድርሳን ውስጥ ግን የራሱን ድርሻ እንደሚይዝ አያጠራጥርም። ለታሪክ አጥኝዎች ጠቃሚ ምንጭ ነው የሚል እምነት አለኝ። ባለታሪኩ ህዝብ ደግሞ በህሊናው ሸንጎ ይዳኝቸዋል።

ቴዎድሮስ ኃይለማርያም ገድሉ
ፒኤችዲ ካንዳ [illegible] አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ETB 26 99

ማንኩሳ አሳታሚ

ዋጋ ብር 75.00

Cover Design: Jake 0923 157643

ኢንተርናሽናል ሊደርሺፕ ኢንስትቲዩት ሀትመት ሥራ